# ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም በሙሉ
# በእግዚአብሔር ትእዛዝ፣ አሳሳቢነትና ገላጭነት የተጻፈ
# ጸሐፊዉ ከእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ አንዱ
# ከቅዱስ ኪዳኗ አገር ከኢትዮጵያ የተገኘ።

ከእግዚአብሔር ቍጣና ጠረጋ በኋላ፤ በቅርቡ በሚገለጸዉ በእግዚአብሔር መንግሥት (ቤተሕዝቡ፣ ቤተምልክናዉ፣ ቤተክህነቱ ተዋሕደዉ በአንድ መንፈስ ቅዱስ በሚመራበት ሥርዓት) በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን የዓለም ገጽታንና አከላለልን በተወሰነ ደረጃ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ




ኅዳር፲፮፳፻፭(2005) ዓ.ም

ኢሜል: teklekidan979@yahoo.com

## ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተላለፈ ሦስተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት

## የጀርባ ሽፋን  ላይ የሚወጣ

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: የኢትዮጵያ ትንሣኤና መልካሙ ዘመን እንዴት ነዉ የሚመጣዉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እያንዳንዳችን በሚገባ ልናዉቀዉና ልናስተዉለዉ የሚገባን እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ መንገድና ጊዜ ማከናወን እንደሚችልና እንደ ፍጡሮቹ የዓመታት፣ የወራት፣ የቀናት ዝግጅት እንደማያስፈልገዉ ነዉ:: ምክንያቱም ሕይወት ያለዉም የሌለዉም ከእርሱ በወጣ ኃይል የተዋቀረ ስለሆነ ሁሉን ያዉቃል፤ ሁሉ በእርሱ ዕይታና ቁጥጥር ዉስጥ ነዉ:: ልክ እኛ ንፋስ ሥዕላችንን (ቴሌቪዥናችንን) በርቀት መቆጣጠሪያ (በሪሞት ኮንትሮል) ጣቢያዎችን (ቻናሎችን) በርቀት ሆነን እንደምንለዋዉጥና ከፈለግንም ማጥፋት እንዲሁም ድምፁን ከርቀት ሆነን መጨመርና መቀነስ እንደምንችል ሁሉ፤ ይኸዉም የርቀት መቆጣጠሪያዉ (የሪሞት ኮንትሮሉ) ዉስጣዊ አካሉ  ከንፋስ ሥዕሉ (ከቴሌቪዥኑ) ዉስጣዊ አካሉ ጋር የሚገናኝበት የተለየ ኃይል ስላለዉ የርቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዉ  ንፋስ ሥዕሉን በቀላሉ ማዘዝ ስለሚችል፤ እንደዚሁ ሁሉ ማንኛዉም ፍጥረት በእግዚአብሔር ኃይል ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜና መንገድ ማከናወን ይችላል:: በማንኛዉም ጊዜ ማንኛዉንም ትዕዛዝ በመስጠት የሚፈልገዉን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል::

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሆነ መልካሙ ዘመን የሚመጣዉ እርሱ እግዚአብሔር በወሰነዉ ቀን፣ ከቀናት በኋላ ይሁን ከወራት ወይንም ከዓመታት በኋላ  እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: እኛ በተነገረን መሰረት በእርግጠኝነት አሁን ባለነዉ ትዉልድ ነዉ በእግዚአብሔር መልእክታት ላይ የተገለጸዉ ሁሉ የሚፈጸመዉ:: ልክ የቀድሞዉ የአገሪቱ የቤተ ምልክናዉ(የቤተ መንግሥት) ተጠሪ የነበሩቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና የቤተ ክህነቱ ተጠሪ የነበሩት ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስ ባልታሰበና ባልተገመተ ጊዜና አጠራር በአንድ ላይ ተጠርተዉ እንደሄዱ ሁሉ፤ የዓመፃ ልጆችም ባላሰቡት ጊዜና አጠራር ከምድር ተጠርገዉና ዋጋ ከፍለዉ እንዲሁ ብን ብለዉ ይጠፋሉ፤ ከምድር ይጸዳሉ:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን መልክእትና የንስሐ ጥሪ «አንቀበልም» ብለዉ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የጸኑት ሰዎች፣ ልክ በኖኅ ዘመን የንስሐ ጥሪና እድል ተሰቷቸዉ በኖኅ ላይ ባላገጡትና  የእግዚአብሔርን ጥሪ ከቁም ነገር ባልቆጠሩት ላይ ድንገት ሳያስቡትና ሳይገምቱ የእግዚአብሔር ቁጣ መቶ እንደጠራረጋቸዉ ሁሉ፤ አሁንም የዓመፃ ስራ አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች በየአገሩ ያሉ ዓመፀኛ መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች፣ እንዲሁም በዓመፃ የጸኑ ሕዝቦች ሕሊናቸዉን አደንድነዋልና እንዲሁ ሳያስቡትና ሳይዘጋጁ በእግዚብሔር ቁጣ ይጠረጋሉ፤ ከምድር ይጸዳሉ:: ያ የሚጠረጉበትና የሚጸዱበት መንገድ የሚታወቀዉ በአንዱ አምላክ በፈጣሪ ነዉ::

ከእኛ የሚጠበቀዉ ራሳችንን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ብቻ ነዉ:: ስራዉን ሁሉ በበላይ የሚያከናዉነዉ እግዚአብሔር ስለሆነ የእርሱን ድንቅ ስራና ተአምር በናፍቆትና በጽናት መጠባበቅ ነዉ:: ወደ መጨረሻዉ ጠረጋና ጽዳት ጊዜ ስለደረስን

አንድ የተለየ ክስተት ሲፈጠር የሚመለከታቸዉ ኃይሎች በተጠንቀቅ እንደሚቆሙ፤ እኛም በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ምግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ሆነን በተጠንቀቅ መጠበቅ ነዉ ያለብን። በራሳችን ሥልጣን አንድ ቀን የመቆየትና የመኖር ዋስትና ስለሌለን ዛሬ ነገ ሳንል ሁል ጊዜ ዝግጅዎች ሆነን መገኘት አለብን።»

እነዚህን የመሳሰሉና የተለያዩ የሕይወት ጥያቄና መልስ፥ የተለያዩ ምስጢራትና ትንቢታዊ ሐተታዎችን፥ እንዲሁም ቀድሞ ሰለነበረዉ፣ ወደፊትም ስለሚሆነዉ፣ ከዛም ባለፈ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ስለሚኖረዉ ሕይወት የሚገልጽ፤ በእግዚአብሔር አሳሳቢነትና ትእዛዝ እንዲሁም ገላጭነት የተጻፈ ስለሆነ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ የዓለም ሕዝብ ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ ነዉ።

የእግዚአብሔርን ተአምርና ታላቅ ተስፋን እንዲሁም እጅግ በቅርቡ የሚመጣዉን የኢትዮጵያን ትንሣኤና መልካም ዘመን በሕሊና እርካታና ሰላም ሆኖ በናፍቆት የሚጠባበቀዉ ሰዉ።

**ማዉጫ** **ገጽ**


1. የፊት ለፊት ሽፋን ......................................................1
2. የኃላ ሽፋን ...................................................................2-3
3. ማዉጫ... ....................................................................4
4. ማስታወሻ ....................................................................5-6
5. መቅድም ......................................................................7-12
6. መግቢያ .......................................................................13-14
7. ክፍል አንድ ..................................................................15-54
8. ክፍል ሁለት .................................................................55-104
9. ክፈል ሦስት .................................................................105-136
10. ክፍል አራት .................................................................137-227
11. ክፍል አምስት ..............................................................228-315
12. ክፍል ስድስት...............................................................316-360
13. ክፍል ሰባት..................................................................361-410
14. ክፍል ስምንት...............................................................411-489
15. ክፍል ዘጠኝ..................................................................490-594
16. ክፍል አሥር..................................................................595-617

## ማስታወሻ

በመጀመሪያ በምሕረቱ ጎብኝቶኝ፤ በቸርነቱ ጠብቆኝ ኃጢአቴን ሳይመለከት፤ ስንፍናዬንና ድክመቴን ሳይቆጥር፤ በርኅራኄዉና በፍቅሩ ለንስሐ አብቅቶኝ በሕይወት ጎዳና እንድጓዝ አድርጎ በሕይወት አኑሮኝ ስለ እዉነት እንድመሰክር የፈቀደና ያስነሳኝን የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉን አምላክ ዛሬም ዘወትርም አመሰግነዋለሁ:: እንዲሁም በእናትነት ፍቅሯ ከሕፃንነት እድሜዬ እስከ አሁን ድረስ በረድኤቷና በጠብቆቷ ያልተለየችኝን ወደፊትም የማትለየኝን፤ እኔ ሳላዉቃት ያወቀችኝን ለሰዉ ዘሮች በሙሉ በአደራ እናትነት የተሰጠችዉን፤ የሕይወታችን ምስጢር ቁልፍ፤ የወደቁ ወዳጆቿን የምታነሳ፤ የተዳደፉትን የምታነጻ፤ ጸጋንና ክብር የምታሰጥ፤ እመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከወዳጇ ከመድኃኔዓለም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተመሰገነች ትሁን::

በመቀጠል በእግዚአብሔር ጥሪና አገልግሎት ዉስጥ እያለሁ የእግዚአብሔርን መልእክት በተመረጡት ሳይቀር ተቀባይነትን አቶ ሲዳፈንና ሲጣጣል ዉስጤ እጅግ አዝኖ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር በፈቀደዉ መንገድ ያገናኘኝ አባት ታናሽነቴንና ተራነቴን ሳይመለከቱ ማንነቴንም ለማወቅ ሳይፈልጉ ምክንያቱም መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ነዉና፤ የሰዉ ምስክርነትና የራስ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ሳያስፈልጋቸዉ ስለ እግዚአብሔር መልእክት የሚያጽናና እና የሚያበረታታ መልስ የሰጡኝን ከመጀመሪያዉ ግንኙነት ጀምሮ በጸሎት፣ በማጽናናት፣ በማበረታታት እስከ አሁን ድረስ ያልተለዩኝን፤ በእግዚአብሔርና በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አገልጋይነት በእንደራሴነትና በባለሟልነት ታጭተዉና ተቀብተዉ ያሉት፣ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን ርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌ(ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ) የሚሆኑትን እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ:: የታመኑላት እመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ለሰማያዊ ክብርና መንግሥት ከነቤተሰቦ ታብቃዎት እላለሁ:: እንዲሁም ከልጅነት እድሜ ጀምረዉ እየተጋደሉለት ያለዉ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ እምነትና ምግባር እንዲሁም ሥርዓትና ትዉፊት እስከ ምድራዊ ሕይወትዎ ፍጻሜ ዘመን ድረስ በታጋድሎዎ ያጽናዎ፤ ሰማያዊዉን የድል አክሊል እግዚአብሔር ያጎናጽፎዎ እላለሁ:: እኛም የአሁን ትዉልዶች ቅዱሱን ኪዳን ለመጠበቅ እግዚአብሔር ይርዳን፤ በሙሉ እዉነት እንድንመላለስ ያድርገን እላለሁ::

በማስከተል ደግሞ በእግዚአብሔር ጥሪና አገልግሎት ዉስጥ እያለሁ በሰዎች ዘንድ የተጎሳቆለ ኑሮና ሕይወት በሚመስለዉ ባልተለመደ የአኗኗር ሕይወት ዉስጥ ስመላለስ በትዕግስትና በጽናት ከጎኔ ሳትለይ እኔንም ልጆቻችንንም በፍቅር እስከ አሁን ድረስ እንክብካቤ እያደረገችልን ያለችዉን ዉድ ባለቤቴን እግዚአብሔር ይስጥሽ ለሰማያዊ ክብርና መንግሥት ያብቃሽ እላለሁ:: እንዲሁም ልጆቼንም እግዚአብሔር ያሳድጋችሁ፤ ለምድራዊዉም ለሰማያዊዉም ክብርና መንግሥት ያብቃችሁ እላለሁ::

ሌላዉ ለእያንዳንዱ አንባቢ የማስታዉሰዉና የማሳስበዉ በእግዚአብሔር መልእክት እንዳትሰናከሉ ከመጀመሪያ ጀምራችሁ በትዕግስት እስከመጨረሻዉ ድረስ አንብቡት:: ከዚያ በኋላ

የፈለጋችሁትንና የመረጣችሁን ክፍል ሆነ ምእራፍ ወይንም አንቀጽ ብታነቡ አትሰናከሉብትም፡፡ ምክንያቱም አጠቃላይ ፍሬ ሐሳቡን ከተረዳችሁ ከእግዚአብሔር እዉነት ጋር ትሰለፋላችሁና፡፡ ነገር ግን ምኑንም ሳታነቡ እየመረጣችሁ የምታነቡ ከሆነ ልትሰናከሉበት፣ ልትወድቁበት፣ በመጨረሻም ልትጠፉበት ትችላላችሁ፡፡ ለምድራዊ ነገር ቀናትና ወራት አይደለም ዓመታትና ዘመናችሁን ሁሉ ሰዉታችሁ በማንበብና በመመራመር ትኖሩ የለም ወይ? ታዲያ ለሥጋችሁም በረከት ለነፍሳችሁ ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጣችሁን የእግዚአብሔርን ቃልና መልእክታት፣ ዓመታትና ወራት አይደለም ሳምንታት የማይፈጁባችሁን በትዕግስትና በማስተዋል ብታነቡት ምን ትጎዳላችሁ? ምንስ ይቀርባችኋል? በመሆኑም ባለቀ ሰዓት ጸጸትና ቁጭት ዉስጥ ከመግባታችን በፊት በእግዚአብሔር ቃልና መልእክት ተጠቅመን ራሳችንንም ሌላዉን ወገናችንንም ከጥፋትና ከወድቀት፣ ከመደምሰስ እንጠብቀዉ፣ እንታደገዉ!

ከዚህ በተጨማሪ የደረሷችሁን የእግዚአብሔር መልእክታት በወረቀት አትማችሁ ብትይዙት፣ በዓለም እየታየ ያለዉና በስፋት የሚታየዉን ክስተት ብትከታተሉበት፣ ሌላዉንም ወገን ብታሳዉቁበት የተሻለ መሆኑን እመክራለሁ፡፡ ምክያቱም ልክ በቅርቡ ማለትም ከጥቅምት፲፰÷፳፻፭ (18/2/2005) ዓ.ም. ጀምሮ በአሜሪካን የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ባለበት በኒዎርክ ከተማ የእግዚአብሔር ቁጣ የሆነዉ ዐዉሎ ነፋስ የመብራት፣ የትራንስፓርት፣ የኢንተርኔት አጠቃቀምን እንዳበላሸ ሁሉ ለወደፊትም በከፋዉ መልኩ የተለያዩ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጫ የሆኑ ክስተቶች በሁሉም አገራት መከሰታቸዉ አይቀርምና እንደ አሁን በኢንተርኔት ሆነ በሌላ መንገድ መገናኝትና በኮምፒተር የማንጠቀምበት ወራት ሊመጣ ይችላልና፤ መልእክታቱን በእጃችን ብንይዛቸዉ ለሚከሰቱት ክስተቶች መፍትሔዉ ምን እንደሆነ እኛም አዉቀን ሌላዉንም ልናሳዉቅ እንችላለንና፡፡

ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ በማዉጫዉ ላይ በየክፍል ዉስጥ ያሉትን ፍሬ ነገሮች በአጭሩ ያላስቀመጥኩበት ዋና ምክንያት፤ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ትምህርት እዉቀት ያልተገኘና እርሱ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ የገለጸልኝን፣ ያስተማረኝን፣ የተናገረኝን፣ በሥጋዊና በመንፈሳዊ እዉቀቴ ደረጃ አሳስቦ ያጻፈኝን ብቻ ስለሆነ፤ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ አንብባችሁ ወደ ሙሉ እዉነት እንድትመጡ ለማስቻል ነዉ፡፡ አጠቃላይ የእግዚአብሔርን መልእክት ለመረዳትና ለማስተዋል እንዲሁም ራስን ለእዉነተኛ ንስሐ ለማብቃትና ለሙሉ እዉነት ለመሰለፍ፣ የዚህ ሁሉ ዉጤት የሚሆነዉን ምድራዊ በረከትና የማያልፈዉን የእግዚአብሔር መንግሥት ለመዉረስ፣ በትህትናና በትዕግስት ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻ ድረድ እናንበዉ፡፡ መረዳት ከተቸገርን ደግሞ ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርገንና የእኛ እዉቀት ምንም እንዳልሆነ ተረድተን፣ አምላክ ፈጣሪ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስለሆነ «አንተ እዉነተኛ አምላክ እዉነቱን ግለጽልኝ፣ ሐሰቱን አስወግድልኝ » እንበለዉ፡፡ ቅንነትና እዉነተኛነት በተሞላ ሕይወት ሆነን ከጠየቅነዉ እርሱ ርኅሩኅ፣ አፍቃሪ፣ ደግ አባት ነዉና ከእርሱ የሆነዉን እዉነት ይገልጽልና ሐሰቱን ደግሞ ያጋልጥልናል፡፡

በተረፈ ደካማና ኃጢአተኛ ታናሽ ልጃችሁና ወንድማችሁ ስለሆንኩ ሁላችሁም በጸሎታችሁ አስቡኝ፡፡

# መቅድም

በመጀመሪያ ሳይገባኝ አሁንም ለሦስትኛ ጊዜ መልእክቱን ለመጻፍ በመመረጤ የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉን እዉነተኛዉን አምላክ አልፋና ዖሜጋን አመሰግናለሁ::

የተከበራችሁ የአዳምና ሔዋን ዘሮች የሆናችሁ የዓለም ሕዝቦችና የቅዱሱ ኪዳን ባለቤቶች ኢትዮጵያዉን አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ፤ እግዚአብሔር በባለፉት መልእክታቱ የሚሆነዉንና ከእኛ የሚጠበቀዉን በግልጽ ተናግሮን ነበር:: ነገር ግን እጅግ ብዙዎቻችን ከላይ ከመሪ እስከ እታች ያለን ሰዎች አልሰማነዉም፤ ያዘዘዉንም ተግባራዊ አላደረግንም:: እርሱ እንደኛ አይደለምና አሁንም ለንስሐ የሚጋብዘንና የእርሱ ሕዝቦች ድንቅ ተአምሩንና ተስፋዉን በጽናት፣ በትጋት፣ በጾም፣ በጸሎት እንዲጠብቁ ይኸዉ ሦስተኛዉን መልእክት ከነሐሴ ፲፰÷፳፻፬ (18/12/2004) ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ኅዳር ፲፪፥፳፻፭ (12/03/2005) ዓ.ም ድረስ በተለያየ ቀንና ሰዓት ያሳሰበኝን፣ የገለጸልኝን፣ የተናገረኝን፣ ባጠቃላይ ያጻፈኝን አቅርቤላችኋለሁ::

እግዚአብሔር እንደሰዉ በሰዉ ላይ ተስፋ ያልቆረጠ፤ በመጀመሪያ መልእክቱ «እግዚአብሔር» ይላል ብሎ ቢያጽፍም የሚቀበለዉና የሚሰማዉ ሰዉ በማጣቱ፤ «እስቲ ትዉልዱ ዲያብሎስ የሚለዉንና የእርሱ አገልጋዮች የሚሉትን ስለሆነ የሚሰማዉ» በማለት፤ «የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ» ይላል በማለት ሁለተኛዉን መልእክት አስተላልፎ ነበር:: ነገር ግን ይህንንም ትዉልዱ አልተቀበለዉም:: ትዕግስቱ እጅግ የበዛ አምላክ አሁንም የትዉልዱን መጥፋት አልፈለገምና ቸርነቱንና ምሕረቱን በማብዛት ለሦስተኛ ጊዜ ትዉልዱ «እግዚአብሔር ይላል» ሲል ካልሰማና ካልተቀበለ፤ እንዲሁም «የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ» ይላል ሲል ካልሰማና ካልተቀበለ፤ አሁን የሚቀረዉ እንደ እርሱ ፍጡር የሆነዉ ሰዉ «የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ» ይላል ቢባል ምናልባት ይቀበለዉ እንደሆነ የመጨረሻ መጨረሻ ሙከራ ላድርግ በማለት እንዳጻፈዉ ይገመታል::

እንግዲህ «ነገር በሦስት ምስክር ይጸናል» እንዲሉ፤ ከመጨረሻ ቁጣ በፊት ሦስተኛዉን የመመለስና የንስሐ እድል የሰጠዉ ለዚህ ይመስለኛል:: ስለዚህ ሁላችንም በተሰጠን እድል ብንጠቀም ለሥጋችንም ለነፍሳችንም የሚበጀን ነዉ:: እንኳን ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር ቀርቶ፤ ምን እንደሚያረጉን ለማናዉቃቸዉ ፍጡር ሰዎች እጃችንን ሰተን እንማረክ የለም ወይ!? ፈቃዳቸዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም አብረናቸዉ እንሰለፍ የለም ወይ? ታዲያ ለሥጋችንም ለነፍሳችንም የሚያስፈልገንን መልካም ነገር እንደሚሰጠን እርግጠኛ ለሆነዉ ለእግዚአብሔር እጃችንን ብንሰጥና በንስሐ ራሳችንን በፊቱ አዋርደን ለእዉነተኛ ሕይወት ብንሰለፍ፤ ከኃጢአት በስተቀር ምን የሚቀርብንና የምናጣዉ መልካም ነገር አለ!? ወይስ ከምድር በተለያየ መንገድ እንደተጠረጉትና እየተጠረጉ እንዳሉት ዓመፀኞች ሰዎች ዳግም የንስሐ እድል ወደሌለበት ቦታ በእግዚአብሔር ቁጣ ተጠርገን እንድንሄድ ይሆን የተፈለገዉ? የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ሕሊና ያለዉ ሕያዉ ፍጥረት የሆነዉ ትልቁ ሰዉ የሚጎዳበትንና የሚጠቀምበትን መለየት እንዴት ተሳነዉ!?

ሌላዉ በድጋሜ ለመግለጽ የምፈልገዉ በእግዚአብሔር መልእክታት ሆነ በተለያየ ጊዜ በጽሑፍ መልእክት በገለጽኩት የእግዚአብሔር እዉነት ላይ፤ እግዚአብሔር ፈቃዱን ብቻ የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀብተዉ በእንዳራሴነት የኢትዮጵያን ሆነ የዓለምን ሕዝብ የሚያገለግሉና የሚጠብቁ ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) እና ርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌ(ፓትርያርክ) አጭቷል፤ አዘጋጅቷል:: በኢትዮጵያ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ የነበረና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ መፈጸምና ማስፈጸም ተስኗቸዉ ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ ማስጠንቀቂያና ምክር ቢሰጣቸዉም አልሰማ በማለታቸዉ ምክንያት ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሳይደርሱ በእግዚአብሔር ተተፍተዉ በቁጣዉ በሥጋ ሞት የተጠሩትን ጠቅላይ ሚኒስትርና ፓትርያርኩን ማሰቡ ብቻ በቂ ነዉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአገልግሎትና ለጠባቂነት ያዘጋጃቸዉ እንደራሴዎች እንዳሉ፤ በእግዚአብሔር መልእክታትና በእርሱ ፈቃድ በተጻፉ የጽሑፍ መልእክት ላይ በግልጽ የተገለጸና ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር እነሱም ሆኑ የዓለም መግሥታት ወንበሩን ለእዉነተኛ ለእግዚአብሔር አገልጋዮችና እንደራሴዎች እንዲያስረክቡና እነሱም ከወንበራቸዉ በእግዚአብሔር ቁጣ ከመቆረጣቸዉ በፊት በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ ተገልጾላቸዉ ነበር:: ኢትዮጵያዉያኑ መሪዎች የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቦች ስለነበሩ ከማንም በላይ ለእግዚአብሔር ቃልና መልእክት ቅድሚያ በመስጠት ሊሰሙና የተባሉትን ሊፈጽሙ ሲገባ ሕሊናቸዉን በማደንደናቸዉ ምክንያት ደንዳኖች የሚጠብቃቸዉን እዉነተኛ ፍርድ ከእግዚአብሔር ተቀብለዉ ወደ ሁለተኛዉ ቦታ ዳግም የንስሐ እድል ወደሌለበት ተጉዘዋል::

በየካቲት ፳፯÷፳፻፬ (27/06/2004) ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት የቤተምልክናዉ (የቤተመንግሥት) ተጠሪ ለነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመጨረሻ አስተያየትና ምክር እንዲሁም ለወደፊት የሚሆነዉንና የማይቀረዉን ግልጽ በሆነ ቋንቋ፤ ለሕዳሴዉ ግድብ አስተያየት እንድንሰጥበት በተዘጋጀልን የኢ-ጦማር(ኢሜል) አድራሻ <pm@erta.gov.et> የተገለጸላቸዉና ሁለቱ የእግዚአብሔር መልእክታት «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!» በሚል ርእስ የተጻፈዉ የመጀመሪያ መልእክት፣ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ የተጻፈዉን ሁለተኛዉን መልእክት፣ እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ ሁለት ደብዳቤዎች አባሪ ተደርጎ ተልኮላቸዉ ነበር:: እንዲሁም ቀደም ሲል በብዙ መቶ ለሚቆጠሩ ግለሰቦችና የተለያየ አካላት በግልባጭ አሳዉቄ ነበር:: ለምስክርነትና ለመፈራረጃ ጭምር ይሆን ዘንድና መልክቱ ታፍኖ እንዳይቀር ለመንግሥት አካላትና እንዲሁም ለመንግሥት የተለየ ቅርበት ይኖራቸዋል ብዬ ላሰብኩት ለ <feedback@erta.gov.et> እና <mccreporter@yahoo.com> ለመሳሰሉት ጭምር ከእግዚአብሔር መልእክታት ጋር አባሪ አድርጌ በግልባጭ ልኬላቸዉ ነበር:: ነገር ግን ማንም ከቁም ነገር አልቆጠረዉም፣ አልተመለከተዉም:: አቶ መለስ ዜናዊም ሕሊናቸዉን በማደንደን ስለጸኑ በአጭር ወራት ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና ልክ በስድስተኛዉ ወር በነሐሴ ፳፯÷፳፻፬ (27/12/2004) ዓ.ም የተመኩበት ኃይልና አንደበት ሳያድናቸዉ አካላቸዉ ወደ መቃብር ሊወርድ ችሏል:: ሕያዉ ነፍሳቸዉም ለእዉነተኛ ንስሐ ሳትበቃና ስለ እዉነት ሳትመሰክር በዓመፃ

ሕይወት ላይ እንዳለች አስቀድሞ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ለዘላለም ዋጋ ወደምትከፍልበት ቦታ ልትሄድ ችላለች።

የሚቀጥለዉ ተረኞች ደግሞ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ካልሰጡና ከእዉነት ጋር ካልተሰለፉ በስተቀር ከእነሱ ስር ያሉት ባለሥልጣናትና የዓለም መንግሥታት ናቸዉ። የሚመለከታችሁ ሰዎች ሁሉ! እግዚአብሔር በግልጽ በቁጣዉ የተለያዩ አገራት መሪዎችን ከወንበሩ እየቆረጠ እያያችሁ፤ አሁንም በሥጋና ደም ስሜት ተመርታችሁና ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ በማድረግ በእዉነተኛዉ በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊ የአገልግሎት ወንበር ላይ በዓመፃ ለመቀመጥ መሞከሩ በከፋዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ለመጠረግ መሆኑን እንድታዉቁ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም በቅርቡ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚዘረጋዉን የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትም ቤተሕዝቡ፣ ቤተ መንግሥቱ፣ ቤተክህነቱ በአንድ ላይ ተዋሕዶ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመራበት የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ሥርዓት፤ ማንም ይሁን ማን ማስቀረት አይደለም ለአንድ ቀን ማዘግየት የሚችል ፍጡር የለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ያላችሁ ቀሪዎቻችሁ ባለሥልጣናት በእግዚአብሔር ያልተመረጡትንና ያልተቀቡትን ለማስቀመጥ የምታደርጉትን የዓመፃ ተግባር ብታቆሙና የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምርጫ ብትጠባበቁ ለሥጋችሁም ለነፍሳችሁም የሚበጃችሁ መሆኑን ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

መንፈሳዊ ወንበር ጠባቂዎች! በሰዉ ሥርዓት የሚደረገዉ ምርጫ በዘመናችን ያፈራዉን መራራ ፍሬ በደንብ የተመለከትንና ያስተዋልን ይመስለኛል። ስለዚህ የሰዉ ሥርዓት ትተን በእግዚአብሔር ሥርዓት እርሱ እግዚአብሔር የመረጠዉና የቀባዉ አባት እንዲሰጠን ሁላችንም ራሳችንን በእዉነተኛ ንስሐ አጥርተን በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት ሆነን እንጠይቀዉ። የሥጋና የደም ስሜታችን መስፈርት ትተን ይኸዉም «ለርእሰ ሊቃነ ካህናት(ፓትርያርክ) ሊመረጥ የሚገባዉ ጳጳስ መሆን አለበት፣ ወይንም ቆብ የደፋ መነኩሴ መሆን አለበት» የሚለዉን የሰዉ ሥርዓት ትተን፤ እግዚአብሔር ሐዋርያትን ከተለያየ ተግባርና ሕይወት እንደጠራ ሁሉ አሁንም ከፈለገ ከምእምን ፣ ከፈለገ ከዲያቆን፣ ከፈለገ ከሕጋዊ ካህን፣ ከፈለገ ከመምህር፣ ከፈለገ ከገዳማዉያን፣ ከፈለገ ከመናንያን፣ ከፈለገ ከባሕታዉያን፣ ከፈለገ ከጳጳሳት ዉስጥ ሊመርጥ ይችላልና በእኛ እዉቀትና አስተሳሰብ አንገድበዉ። በዚህ አስተሳሳሰብና አቋም ምርጫዉን ለእግዚአብሔር ክፍት ካላደረግን፤ የሰዉ ምርጫ ይሆንና ከባለፉት ተመራጮች በከፋ መልኩ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚፈጽምና የሚያስፈጽም አባት ልንመርጥ እንችላለን። ስለዚህ በእግዚአብሔር ሥርዓት ሆነን መምረጥ ካልቻልን ደግሞ እግዚአብሔር ሰማያዊ ሥርዓቱን የሚዘረጋበት ጊዜ ሩቅ ስላልሆነ ያንን ጊዜ በትዕግስት መጠባበቅና ለሕዝብና ለምእመናን የሚበጀዉን፣ ለአገርና ለቤተክርስቲያን ለእዉነተኛና ለመልካም አሰራሩ የሚረዳዉን መዋቅር ብትዘረጉ፤ ሌባ፣ ቀማኛ፣ ወንበዴ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ዘማዊ፣ አመንዝራ፣ በምንፍቅናና በባዕድ አምላኮ የሚመላለሱ፣ በመተተኝነትና በመጽሐፍ ገላጭነት ሕይወት ያሉ፣ ባጠቃላይ የእዉነትና የቤተክርስቲያን እንቅፋት የሆኑ በተለያየ የኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡትን እንክርዳዶችን ከስንዴዉ ብትለዩና እዉነተኞችንና ቅኖችን በሚገባቸዉ ቦታ ብታስቀምጡ ነዉ የሚሻላችሁ። በፖለቲከኞች ተጽህኖ ስር ወድቃችሁ እንዳለፉት ፓትርያርክ የፖለቲካ ስራ አስፈጻሚ

የምትመርጡ ከሆነ ደግሞ የከፋዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ነዉ የሚመጣባችሁና በላያችሁ ላይ የሚነደዉ::

ስለ እዉነተኛ ንስሐ ደግሞ አንድ የምለዉ ነገር አለ:: ይኸወም በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ በምዕራፍ ፳(20) ላይ አንድ የተገለጸ መዋዕለ ዜና(ታሪክ) አለ:: ከታሪኩሙ የምንረዳዉ አክዓብ የተባለ የእስራኤል ንጉሥ ከሚስቱ ኤልዛቤል ጋር በመሆን ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ሲፈጽም ሲያስፈጽም ነበር:: አንድ ምስኪን ደሃ ናቡቴ በተባለ ሰዉ ላይም በኤልዛቤል የክፋት ሐሳብ አፍላቂነት የሐሰት ምስክር አዘጋጅተዉ በመወንጀል የጭከናና ግፍ ተግባር አስፈጽመዉበት ነበር::

ታዲያ ሁሉን የሚመለከት የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ የመልከ ጼዴቅ አምላክ፤ ነቢዩን ኤልያስን «ተነሥተህ በሰማርያ የሚኖረዉን የእስራኤል ንጉሥ አክዓብን ትገናኝ ዘንድ ዉረድ፤ እነሆ፣ ይወርሰዉ ዘንድ በወረደበት በናቡቴ የወይን ቦታ ዉስጥ አለ:: አንተም :- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ዉሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተም ደም ደግሞ ዉሾች ይልሱታል ብለህ ንገረዉ:: አክዓብም ኤልያስን :- <u>ጠላቴ ሆይ፣ አገኘሸኝን</u>? አለዉ:: እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰለት :- አግኝቼሃለሁ፤ <u>በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ለማድረግ ራስህን ሸጠሃልና:: እነሆ፣ ክፉ ነገር አመጣብሃለዉ፣ ፈጽሞም እጠርግሃለሁ፣ አክዓብም በእስራኤል ዘንድ የታሰረዉንና የተለቀቀዉን ወንድ ሁሉ አጠፋለሁ፤ በሥራህም አስቈጥተኸኛልና፣ እስራኤልንም አስተሃልና ቤትህን እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርባዓም ቤት እንደ አኪያም ልጅ እንደ ባኦስ ቤት አደርገዋለሁ::</u> ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ኤልዛቤል :- <u>በኢይዝራኤል ቅጥር አጠገብ ኤልዛቤል ዉሾች ይበሉአታል</u> ብሎ ተናገረ:: ከአክዓብም ወገን በከተማይቱ ዉስጥ የሞተዉን ዉሾች ይበሉታል፤ በሜዳዉም የሞተዉን የሰማይ ወፎች ይበሉታል:: በእግዚአብሔር ፊት ክፋት ለመስራት ራሱን እንደ ሸጠ፣ ሚስቱም ኤልዛቤል እንደነዳችዉ፣ እንደ አክዓብ ያለ ሰዉ አልነበረም:: <u>እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ፊት ያጠፋቸዉ አሞራዉያን እንደ ሠሩት ሁሉ፣ ጣዖታትን በመከተል እጅግ ርኩስ ነገር ሠራ::</u>

<u>አክዓብም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ ገላዉን ማቅ አለበሰ፣ ጾመም፣ በማቅ ላይም ተኛ፣ ቅስስ ብሎም ሄደ::</u> ደግሞም :- አክዓብ በፊቴ እንደ ተዋረደ አየህ? በፊቴ የተዋረደ ስለ ሆነ በልጁ ዘመን በቤቱ ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ እንጂ በእርሱ ዘመን ክፉ ነገር አላመጣም የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቴስብያዊዉ ወደ ኤልያስ መጣ ::» ይላል መጽሐ. ነገሥት ቀዳማዊ ፳(20)፣ ፲፯ እስከ ፳፱(17-29)

ከላይ የተጻፈዉና በእግዚአብሔር አሳሳቢነት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጸዉ መዋዕለ ዜና (ታሪክ) የሚያስተምረን በእዉነተኛ ንስሐ ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት የሚያዋርዱና ምሕረት የሚጠይቁ ዓመፀኛ ሰዎች፤ ርኅሩኅ አምላክ እግዚአብሔር በምሕረቱ እንደሚጎበኛቸዉና የወሰነባቸዉን ቅጣት እንደሚያነሳላቸዉ ነዉ:: ለእዚህም እድል ከበቁት ዉስጥ አንዱ ሕሊናዉን በመሸጥ እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ የሚወሰድ እንደ ጠፍ ከብት በሚስቱ ዝም ብሎ ይነዳ የነበረዉ ንጉሥ አክዓብ ነበር:: ይሁንና በንስሐ ሕይወት እስከ መጨረሻዉ ድረስ ስላልጸናና ተመልሶ በዓመፃና

በክህደት ተግባር ስለተሰለፈ፣ ራሱን በድጋሜ ለእግዚአብሔር ቁጣ ስላዘጋጀ፣ በተቃራኒ ወገን ጦር ተወግቶ ሊሞትና በእግዚአብሔር የተነገረዉ ትንቢት ሊፈጸምበት ችሏል። በንስሐ እድል ከነአካቴዉ መጠቀም ያልፈለገችዉ ደግሞ የክፋት፣ የተንኮል፣ የበቀል፣ የግፍ ሐሳብ አመንጪ ና ሐሳቧን ወደ ተግባር ታስለዉጥ የነበረችዉ ሚስቱ ኤልዛቤል ነበረች። ይህች ዓመፀኛ ሴት እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢዩ ኤልያስ በኩል እንዳስነገረዉ በመጽ. ነገሥት ካልዕ ምዕራፍ ፱(9)፣ ከቁጥር ፴ እስከ ፴፯(30-37) ድረስ በተጻፈዉ መሰረት በከፋ አሟሟት፣ በዉርደትና በስቃይ ልትሞትና መታሰቢያዋም ሊጠፋ ችሏል።

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ የእግዚአብሔርን እዉነት የሚያስተላልፉ ሰዎች በዲያብሎስ መንፈስ በሚመሩና የዲያብሎስን ፈቃድ በሚፈጽሙና በሚያስፈጽሙ ሰዎች ዘንድ ሁሌም እንደጠላት ነዉ የሚታዩትና የሚቆጠሩት። ምክንያቱም የጨለማዉን ስራቸዉን ስለሚገልጹባቸዉና ገበናቸዉንም ስለሚጋለጡባቸዉ ነዉ።

አሁንም ያለዉ አምላክ የእነ ነቢዩ ሙሴ፣ ሳሙኤል፣ ኤርምያስ፣ ዳንኤል፣ ሕዝቅኤል፣ ኤልያስ፣ ኢሳይያስ... ወዘተ አምላክ ስለሆነ፤ ሕሊናችሁን እየሸጣችሁ ያላችሁ በተለያየ ኃላፊነት ቦታ የተቀመጣችሁ ሆነ በተራ አገልጋይነት ዉስጥ ያላችሁ ሰዎች! ራሳችሁን በንስሐ በእግዚአብሔር ፊት አዋርዳችሁ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ እንድትሰለፉና ስለ እግዚአብሔር እዉነት እንድትመሰክሩ አሳስባችኋለሁ፤ እንዲሁም አስጠነቅቃችኋለሁ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተም ላይ ጭምር ይመጣባችኋልና። የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ሐሳብ አመንጪ ዎችና ወደተግባር የምትለዉጡና የምታስለዉጡ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ ተገልጦ ቢናገራችሁ የማትሰሙና ራሳችሁን ለእዉነተኛ ንስሐ የማታዘጋጁ ስለሆነ እጅግ እጅግ በቅርቡ ከላይ እስከ ታች ያላችሁ እንደ ዓመፃችሁ ደረጃ በእግዚአብሔር ቁጣ እንደምትጠረጉና ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራችሁ በምድርም በሰማይም ዋጋ እንደምትከፍሉና መታሰቢያችሁም ለዘላለም እንደሚጠፋ ልታዉቁ ይገባል።

ሌላዉ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መልእክታት የማሰራጨት የዉዴታን ግዴታን በተመለከተ አንድ የምለዉ ነገር አለ። ይኸዉም በመጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፭(25) ከቁጥር ፲፬ እስከ ፴(14-30) እና በሉቃስ ወንጌል በምእራፍ፲፱(19) ከቁጥር ፲፩ እስከ ፳፯(11-27) በግልጽ አምላካችን እንደተናገረዉ፤ እያንዳንዱ ሰዉ ለእርሱ የሚመጥነዉና የሚገባዉ መክሊት ተሰቶታል። በተሰጠዉ መክሊት መጠን ያተረፈ እንደ ትጋቱና ትርፉ ከእግዚአብሔር የሚያገኘዉ ዋጋ ከፍ ይላል። እንደ አቅሙ ያተረፈ በዚያኑ ያህል ዋጋ ተመስግኖ ይከፈለዋል። እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ሳያዉቅና በመጥፎ መልኩ መስሎት ኃላፊነቱን በሚገባ ያልተወጣ ሰዉ ደግሞ ያለዉ መክሊት መወሰድ ብቻ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ዓምፇልና እንዲሁም እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት እንዲነግሥ ስላልፈቀደ የከፋዉን ቅጣት ይቀበላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ምሕረቱ ሆነ ቸርነቱ የተየለሌ ቢሆንም ፍርዱ ደግሞ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ነዉ።

በመሆኑም ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ያልሆነዉን እያንዳንዱ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ የመመርመር ነጻ ፈቃድና የራሱን ዉሳኔ የማድረግ ምርጫ አለዉ፡፡ ከእግዚአብሔር አለመሆኑን ካረጋገጠ ደግሞ በእግዚአብሔር ስም የሚነገደዉን አለመቀበል ብቻ አይደለም ከሥጋና ከደም ስሜት ዉጭ በሆነ መንገድ፣ በእዉነተኛነትና በቅንነት ስሜት መቃወምና ማዉገዝ ጭምር ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ሕሊናዉ ወይንም መንፈስ ቅዱስ፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ከመሰከረበት ደግሞ ከሥጋና ደም ስሜት ራሱን በመለየት ስለ እዉነት ሊመሰክርና የእግዚአብሔርንም መልእክት እንደ ርግብ የዋህ እንደ እባብ ልባም ሆነ ለወገኖቹ ለአዳም ዘር ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡

ይህን ሐሳብ ያመጣሁት በእኔ በኩል የተላለፈዉ የእግዚአብሔር መልእክት «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» እና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ የተጻፉትን ሆነ፤ «በሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በኩል «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል የተጻፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት የደረሰዉ ሰዉ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲደርሰዉ ፈቅዶለታልና ከሥጋና ደም ስሜት ራሱን በመለየት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ሊመረምረዉና ከእግዚአብሔር መሆኑን ካስተዋለና ከተረዳ የሥጋና የደም ስሜቱ ቢቀበለዉም ባይቀበለዉም ለሌላዉ ወገን የማሳወቅ የዉዴታ ግዴታ አለበት፡፡ በራሱ አፍኖ ከያዘና ለሌላዉ ማድረስ ሲችል ካለደረሰ፤ «አንተ ክፉ ባሪያ» ተብሎ ሊወቀስና ሊከሰስ እንደሚችል ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ራሱ ሆነ ወገኑ እንዳይጠፋ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ፈልጎ ነዉ እግዚአብሔር በተለያየ ምክንያት መልእክቱ እንዲደርሰዉ ያደረገዉና፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛዉም ሰዉ የድርሻዉን ተወቶ ሌላዉ ቢቀበለዉም ባይቀበለዉም አንዳች አይጠየቅበትም፡፡ ይልቁኑ «አንተ በጥቂት ታምነሃልና ለበለጠዉ ዋጋና አገልግሎት ነዉ የምትታጨዉ» የሚል ምላሽ ነዉ ከአምላኩ የሚያገኘዉ፡፡

## መግቢያ

እግዚአብሔር ከየካቲት፳፻፫(2003) ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በእኔ በኩል መልእክቱን በተለያየ መንገድ «እግዚአብሔር» ይላል፣ እንዲሁም «የጨለማዉ ገዥ» ይላል በማለት ለትዉልዱ ያቀረበ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ በሚቀረዉ ምድራዊ ፍጡር በሆነዉ ሰዉ ስም «የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ሰዉ» ይላል በማለት ሦስተኛዉን መልእክቱን አስተላልፎልናል። ለእኔ የማላዉቃቸዉ እዉቀቶችና ምስጢራት እንዲሁም ትንቢቶች በመገለጹ ብቻ የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ ሁሌም አደንቃለሁ፤ እርሱንም አመሰግነዋለሁ። እንዲሁም አንድ ደብዳቤ ለማርቀቅ ይከብደኝ የነበረዉና ከምኞት ዉጭ አንዳች የሥነ ጽሑፍ ተሰጥኦ ያልነበረኝን ሰዉ፤ ሃያ ቀን ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ከሁለት መቶ ገጽ በላይ ያጻፈኝ፤ እንዲሁም ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ከአራት መቶ ገጽ በላይ ያጻፈኝ አምላክ ለወደፊትም በራሴ የማልችለዉንና የማልወጣዉን የእርሱን ስራ እንድወጣዉ እንደሚያደርግ በፍጹም አምናለሁ።

**በክፍል አንድ**: የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፤ በእግዚአብሔር አገልጋይ አማካይነት ስለ ሕይወታቸዉና አጠራራቸዉ ለተጠየቁት የሰጡን ምላሽ ይገልጻል። እንዲሁም በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ የተገለጹት በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም እንዴት እንደሚተገበሩ ያሳዉቀናል። በአራት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።።

**በክፍል ሁለት**: ከመጀመሪያ ሥነ ፍጥረት ጀምሮ ስለነበዉና እስከ ሕያዉነት ዘመንና ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ስለሚሆነዉ ሕይወትና የተለያዩ ምስጢራት፣ እዉቀቶች፣ እንዲሁም ትንቢቶች ተገልጸዉበታል። በሦስት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

**በክፍል ሦስት**: ተጨማሪ እዉቀቶችና ምስጢራት እንዲሁም የእግዚአብሔር እዉነት በተብራራ መልኩ ቀርቦበታል። በሦስት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

**ክፍል አራት**: የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነታ በተጨማሪ በሰፊዉ ተብራርቶ ቀርቦበታል። በሰባት ምዕራፍ ተከፋፍሏል።

**በክፍል አምስት**: በመጀመሪያዉ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የእግዚአብሔር መልእክትና በሁለተኛዉ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፉት ትንቢቶችና እዉነታዎች ማብራሪያ ተሰቶበታል። በዘጠኝ ምዕራፍ ተከፋፍሏል።

**ክፍል ስድስት**: በዓለምና በኢትዮጵያ ስላለዉ እዉነታ በተወሰነ መልኩ ተገልጿል። በአምስት ምዕራፍ ተከፋፍሏል።

**በክፍል ሰባት**፡ ከእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ጋር የተያያዘና በኢትዮጵያና በዓለም ዉስጥ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ያለዉን አከላለል፣ እንዲሁም ሌሎች እዉነታዎችን ይዟል። በአምስት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

**በክፍል ስምንት**፡ በኢትዮጵያ ዉስጥ ስላለዉ እዉነታ በዝርዝር ቀርቦበታል። በአምስት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

**በክፍል ዘጠኝ**፡ በ፳፻፬(2004) ዓ.ም የተከሰቱ የተለያዩ ጉዳዮችና በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ቀሪ እዉነታዎች ቀርቦበታል። በአሥር ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

**በክፍል አሥር**፡ በየካቲት ፳፯÷፳፻፬ (27/06/2004) ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተጻፈ አስተያየትና ምክር እንዲሁም ትንቢታዊ መልእክት የያዘዉ መልእክት፤ በሰኔ ፲፭÷፳፻፬ (15/10/2004) ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋሕዶ ስም በሕዋ ሰሌዳ (በድረ ገጽ) በተለያየ ብሎግ «መንፈሳዊ» መልእክት ለሚያስተላልፉ የተሰጠ ምክርና ማስጠንቀቂያ መልእክት፤ እንዲሁም ከነሐሴ አንድ ጀምሮ ተጽፎ ነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ (15/12/2004) ዓ.ም ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተላለፈ መልእክት የያዘ ነዉ። በሦስት ምዕራፍም ተከፋፍሏል።

## ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ በሙሉ

# ክፍል አንድ

## ምዕራፍ አንድ

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፤ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የንስሐ እድሜና ጤና ሰቶን ለዚህች ቀን ስላደረሰን ስሙ የተመሰገነ ይሁን እያልኩ ወደ መጀመሪያ ጥያቄዬ እገባለሁ:: ወደዚህ አገልግሎትና ጥሪ እንዴት እንደገቡና የሕይወት ታሪኮዎን በአጭሩ ቢገልጹልን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ስለሁሉም ነገር ሁሉ የእርሱ በእርሱ ለእርሱ የሆነ አምላክ አልፋና ዖሜጋ የሆነዉ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከአደራ እናታችን ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ስሙ የተመሰገነ ይሁን እያልኩ ወደ ምላሹ እገባለሁ::

ወደዚህ ሕይወት ልገባ የቻልኩት በልማድ አጠራር ባጋጣሚ፤ በትክክለኛዉ አጠራር ደግሞ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነዉ:: ይኸዉም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ ኅዳር ወይንም ታሕሳስ ወር ላይ ይመስለኛል አንድ ጓደኛዬን ስፈልግ፣ ዩኒቨርስቲ ዉስጥ ባለዉ መሰብሰቢያና መማሪያ ክፍል ዉስጥ መንፈሳዊ መርሐግብር እየተከታተለ መሆኑን ሌሎች ተማሪዎች ስለነገሩኝ፤ እኔም ቀደም ሲል በግቢ ዉስጥ መንፈሳዊ መርሐግብር እንዳለ አላዉቅም ነበርና ጋደኛዬን ለመፈለግ ወደዛ አመራሁ:: በወቅቱም አንድ በጋብቻ የምዛመደዉ ወንድም ሲያስተምር ደረስኩና እኔም መርሐግብሩን ተሳትፌ ይሰብክ የነበረዉ ወንድም ከመካነ አእምሮ( ከዩንቨርስቲ) መመረቁንና በመንግሥት ስራ ላይ መሰማራቱን እንጂ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ እንደሚሳተፍ ቀደም ሲል የማለዉቅ ሲሆን፤ ከመርሐግብሩ በኋላ ሰባኪዉን ወንድም ሰላም ካልኩ በኋላ ከግቢዉ ተጠሪ ተማሪ ጋር አስተዋወቀኝ:: ከዚያም አንድ ብዬ መንፈሳዊ ሕይወት ጀመርኩ:: በግቢዉ ዉስጥ እና በአጥቢያዉ በሚገኝ ቤተክርስቲያን ዉስጥ በሚካሄዱት መርሐ ግብሮች ላይ መሳተፍ ጀመርኩ::

በመጀመሪያ የወሰድኩት እርምጃ እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት ዉስጥ የተማርኩ ስለነበረና ዝሙቱ፣ ስካሩ፣ ዘፈኑ፣ ዳንኪራዉ ...ወዘተ እንደ ትልቅ ስራ የሚቆጠርበትና እኔም ለአጭር ወራት ቢሆንም ከእነዚህ ሕይወት ያልራኩ ስለነበረ ራሴን ከዚህ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ለየዉ:: ከጓደኞቼ ጋር ያለኝን ግንኙነት ገደብኩ:: የማመልከዉን አምላክና ሃይማኖት በሚገባ ማወቅና ማስተዋል ጀመርኩ:: ከዚያም የዓብይ ጾም መግቢያ ላይ የግቢዉ ተጠሪ ተማሪ በመንፈሳዊ መርሐ ግብር ላይ «የዓብይ ጾም ሰኞ ስለሚጀምር፣ የቁርሳችንን ዳቦ ለእኔ ቢጤዎች እንሰጣለን፤ ስም ዝርስራችሁን ጻፉና ለሚመለከተዉ አካል እናስተላልፋለን» በማለት ትእዛዝ ሲሰጥ፤ እኔ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ እንኳን እስከ ስድስት ሰዓት መጾም ቀርቶ ረቡዕና አርብ ጾሙን የተዉኩና የፍስክ መብል እበላ ስለነበረ፤ ለጊዜዉ በዉስጤ በማጉረምረም «ሁላችን የምንጾም መሰለዉ እንዴ?» በማለት ቅር እየተሰኘዉ ስሜን

አስተላለፍኩ:: አንድ ሦስት ቀን እንደጾምኩ ግን ሕይወቴ እየተለወጠና እየተሰበረ መጣ :: «ለካስ ጾም እንደዚህ ጥቅም አለዉ እንዴ!» እያልኩ በትጋት መጾም ጀመርኩ:: አእምሮዬ ብሩህ እየሆነ መጣ፤ ያሳለፍኩትን የኃጢአት ሕይወት እየኮነንኩና እግዚአብሔርንም በትክክለኛዉ መንገድ አለማምለኬን እያጸጸተኝ በራሴ ፈቃድ ጾሙን ወደ ዘጠኝ ሰዓት አደረስኩት:: በመጨረሻዉ በሕማማት ጊዜ በራሴ ፈቃድ ወደ አስራ አንድ ሰዓት አሻሻልኩት:: ስላለፈዉ ሕይወቴም ማንባትና በነገረ መስቀሉ ፍቅር መቃጠል ጀመርኩ::

በስብከት ጊዜም መምህራን «ሰዉ ቅዱስ ቁርባን ካልተቀበለ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም» ሲሉ በመስማቴ፤ ዋና ዓላማዬ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ ነበርና በትንሣኤ በዓል የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀበልኩ:: ከበዓል መልስ ለግቢዉ ተጠሪ ተማሪ መቁረቤን ነገርኩት:: እርሱም የንስሐ አባት እንደያዝኩና እንዳልያዝኩ ጠየቀኝ:: እኔም እንዳልያዝኩና መያዝ እንዳለበት እንዳላወኩ ነገርኩት:: እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ በማዉጣት የንስሐ አባት አስፈላጊነት ካስረዳኝ በኋላ ቤተክርስቲያን ወስዶኝ ከአንድ ካህን አገናኝቶኝ በሥርዓቱ ለመመላለስና ለመቁረብ ችያለሁ:: በዚያዉ ሕይወት እያለሁ በክረምት ወራት ለመንፈሳዊ ትምህርት ሥልጠና በግቢዉ ጉባኤ ተመርጬ ወደ አንድ ቦታ ሄድኩ:: በዚያም መሰረታዊ የሃይማኖት ትምህርትና የኢትዮጵያና የዓለም አብያተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም የቤተክርስቲያን ሥርዓት ለአንድ ወር ተኩል ያህል በተወሰነ ደረጃ ተማርኩ:: ለእኔ ግን ከትምህርቶቹ በላይ በዚያ ቦታ መንፈሳዊ ሕይወቴ እጅግ ሊለወጥና ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም፣ ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ኢትዮጵያ የተለየ ፍቅርና ዉስጤ ደግሞ ስለ እዉነት ሊቃጠልና መንፈሳዊ ቅናት ሊያድርብኝ ችሏል:: በዚያም ምክንያት እየተማርኩ እያለሁና የምስክር ወረቀት ከወሰድኩ በኋላ፤ ምንም እንኳን በቤተክርስቲያናችን ልማድ አንድ አስተማሪ ካልተጋበዘ በስተቀር «ላስተምር፣ ልመስክር» የማይል ቢሆንም፤ እኔ ማንነቴን ወደማያዉቁኝ አብያተ ክርስቲያናት ወደተለያዩ ከተማዎች ሄጄ ማንነቴን ከገለጽኩላቸዉ በኋላ ለመመስከር ብፈልግም በአንድ ቤተክርስቲያን ብቻ ፍቃድ አግኝቼ ዉስጤ ስለሚቃጠልበት መመስከር ችያለሁ:: በሌሎች ግን እድሉ ሳይሰጠኝ የቀረና በሁለት ቤተክርስቲያን ደግሞ በአስመሳይ አማኞችና አገልጋዮች ከድብደባ እግዚአብሔር በቸርነቱና በጥበቃዉ አትርፎኛል::

ባጋጠሙኝ የተለያዩ ቀላል ፈተናዎች ዉስጤ ተሰምቶኝ ነበርና ለሳምንት ያህል በቤት ዉስጥ ሱባዔ ያዝኩ:: ከዚያም ዉስጤ ይቃጠልበት የነበረዉ ስሜት በርዶልኝ ትምህርት በሚጀመርበት በመስከረም ወር ወደምማርበት ኮሌጅ በመመለስ ትምህርቴን ቀጠልኩ:: ይሁንና በተረጋጋ ሕሊና መቀጠል ባለመቻሌና እንዲሁም ከንቱነቴን በማስተዋሌ፣ ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ ያስተዋልኩት ነፍሴ ብቻ በምትረዳዉ የተለያዩ ምስጢራት ሲገለጹልኝ «ለምን አልመንን » በማለት ትምህርቴን በማቋረጥ ራሴን ለምነና ሕይወት አዘጋጀሁ:: ከዚያም አቅምና ጽናት እስከማገኝ ድረስ በመጀመሪያ ራሴን ለዚያ ሕይወት ለማለማመድ ወደ አንድ ገዳም አመራሁ:: ነገር ግን አበምኔቱ (የገዳሙ አስተዳዳሪ) «ለጊዜዉ ባጀት ስለሌለን ባጀት በሚኖርበት ጊዜ እንነግርሃለን» ስላሉኝ ወደቤተሰቤ በመመለስ የእግዚአብሔርን ጥሪ መጠባበቅ ጀመርኩ:: ይሁንና እስከ ሁለት ዓመት ድረስ አንዳች ጥሪ

ስላልመጣልኝ ወዳቋረትኩት ትምህርት ተመልሼ ትምህርቴን ጨረስኩ፤ ተመረኩ፤ ወደ ስራ ዓለም ተሰማራሁ።

ከዚያም ብር ለመድኩ፤ የብቸኝነት ሕይወቱን ዉሳኔ በመሻር «ለምን ትዳር አልይዝም» አልኩ። ምንም እንኳን ከጾምና ከጸሎት ባልለይም በመንፈሳዊ ሕይወቴ ዛልኩ። ለትዳር ያሰብኳት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በጓደኝነት የያዝኳት እህት መንፈሳዊ ሕይወቴን ሳጠብቅ በቅዱስ ጳዎሎስ መልእክት ላይ «በብቸኝነት ሕይወት የሆነ ሰዉ እግዚአብሔርን በሙሉ ሕይወቱ ማገልገል» ይችላል የሚለዉን በማንበብ «ለምን እግዚአብሔርን በሙሉ ሕይወቴ አላገለግለዉም?» በማለት የምወዳትን የምትወደኝን ጋደኛ የራሷን ምርጫ እንድታደርግና እንድታገባ፣ ሕይወቷንም በቅዱስ ቁርባን ወስና እንድትኖር፣ እኔም እንደማላገባ በደብዳቤ ገልጨላት ተለያይተን ነበርና፤ እርሷም የተወሰነ ዓመት ጠብቃኝ ባል ልታገባ ችላለች። የኮሌጅ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ በነበርኩ ጊዜ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የመንግሥት ሥርዓቱ እግዚአብሔር መፍራት የሌለበትና አሕዛባዊ ሕይወት የነገሠበት ስለነበረ፤ ብዙ የሴት ጋደኛ ሆነ ብዙ የወንድ ጓደኛ መያዝ እንደ ታላቅ ጀብዱ ነገር ስለሚታይና ኃጢአቱና ነዉሩ እንደ ክብር ስለሚቆጠር፤ እኔም ለአጭር ወራት ቢሆንም የተለየ ግንኙነት ባይኖረኝም ሁለት ሦስት የሴት ጓደኛ ይዤ ነበር።

ታዲያ ስራ ይዤ ትዳር በማስብበት ወቅት ሁለተኛዋ ጋደኛዬ የነበረችዉን በማሰብ ትዳር አለመያዟን አረጋግጬ በጋደኝነት የቀጠልኩ ቢሆንም ብዙ ሳንቆይ መግባባት አልቻልንምና ከእርሷ በመጣ እንለያይ ጥያቄ ተለያየን። ከዚያም ወደግል ስራ ተሰማርቼ ስሰራ የቆየሁ ቢሆንም፤ ሕይወቱ ከባድ የሆነና ለሕሊናዬ ያልተመቸኝና ስሜቴም የተጎዳበት ስለነበረ ተዉኩት። ከዚያም ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በማዘንበል ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ስል እዉነት በማዘን ጠጉሬንና ጢሜንም በማሳደግ የኢትዮጵያን ትንሣኤ መጠባበቅ ጀምርኩ። በዚህ ሕይወት ዉስጥ እያለሁ ሰዉ በራሱ ሥልጣንና ጽናት እንደሚፈልገዉ መኖር እንደማይችል በመዉደቅና በመነሳት ተማርኩ። ከዚያም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ራሴ ፈቃድና ምኞት መሄድ እንደማይገባኝ አስተዋልኩ፣ ለስራም ወደ ክፍለ ሀገር ወጣሁ፣ በዚያም እግዚአብሔር ያዘጋጀልኝን ሔዋኔን አገኘዉ፣ ትዳርም መሰረትኩ፣ ልጆችም ወለድኩ። ትምህርቴንም በማሻሻል እንደገና ተመረኩ። ከዚያም በቂ ጊዜ ማግኘት ስችል የቀደመ ሕይወቴን ማሰብና «ለምን ከዚህ በፊት በሰማኒያዎቹ ዓመተ ምሕረት እነዚያ ምስጢራት እግዚአብሔር ገለጸልኝ? እንዲሁ በዉስጤ እንዲኖሩ ነዉ ወይ?» በማለት እጠይቅና ስለማዉቀዉም እዉነት ማዘንና መቃጠል፣ እንደቀድሞ በበዓላት ጊዜ ወደ ተለያዩ ገዳማት መሄድ ጀመርኩ። ከዚያም በአንድ ቤተክርስቲያን ግቢ ዉስጥ በፍልሰታ ጾም ሱባዔ ገባዉ። ለሦስት ዓመት የተለየዉትን ቅዱስ ቁርባን ከእነቤተሰቤ ተቀበልኩ። ከሱባዔ እንደወጣሁ አንድ ወንድም «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ የተጻፈ መልእክት ሰጠኝ። እኔም ከአሥር ዓመት በፊት እጠባበቀዉ የነበረ ስለሆነ በአንድ ቀን ንባብ የጨረስኩት ሲሆን ጸሐፊዉም እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ ጠባቂነትና አገልጋይነት የመረጣቸዉና የቀባቸዉ በኢትዮጵያዉያን ዘንድ የኢትዮጵያን ትንሣዔ የሚጠባበቁ «ቴዎድሮስ» በማለት የሚጠባበቁት በእግዚአብሔር ተቀብተዉ የሚነግሡት ንጉሥ መሆናቸዉን አወኩ። በሳምንት ዉስጥ ደግሞ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምጽ መልካቸዉን፣ ስማቸዉን፣ ሌላ ሥልጣናቸዉንም

ጭምር እግዚአብሔር ገለጸልኝ፡፡ ከሳምንት በኋላ ደግሞ በመስከረም አንድ ፳፻፫ዓ.ም(1/01/2003) ዘመን መለወጫ ላይ ዓለም በዘፈንና በዳንኪራ ሲቀበለዉ፣ እኩለ ሌሊት ላይ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ የመጀመሪያዉን «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ የተጻፈዉን የእግዚአብሔር መልአክት መጻፍ ጀመርኩ፡፡

ለእኔ የመጀመሪያ ክስተት ስለነበረ ኀዘንተኛ ሆንኩ፣ በተለያየ ቀንና ሰዓት ወደ ሕሊናዬ የሚመጣዉ ድምፅ ተከትዬ በወረቀት ላይ ከዚያ በመቀመሪያ(በኮምፒተር) ላይ መጻፍ ጀመርኩ፡፡ መስከረም ፳፮÷፳፻፫ (26/01/2003) ዓ.ም የጽሑፉን ስራ ሙሉ በሙሉ ከጨረስኩ በኋላ፣ ያ በእምነት ብቻ የማዉቀዉን አምላክ «ምን ላድርገዉ?» በማለት ጠየኩት፡፡ እርሱም «እነ እገሌን ተገናኝ» አለኝ፡፡ እኔም ይወክላቸዋል ብዬ ወደ ገመትኩት ሰዉ በመሄድ ያለዉን ሁኔታ በእንባ ጭምር በማስረዳት መልእክቱን ሰጠሁ፡፡ በመስከረም፳፱÷፳፻፫ (29/01/2003) ዓ.ም. የቅድስት አርሴማ ዓመታዊ በዓል ሲከበር በቅዳሴ ሰዓት ላይ በተለመደዉ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ በቀጣይ ለኢትዮጵያ(ለምስራቅ አፍሪካ) ምን እንደምሆን ተነገረኝ፡፡ እኔ ግን ደስታ ሳይሆን ሁለተኛ ኀዘን ነዉ የሆነብን፡፡ ምክንያቱም ሳይገባኝ የእግዚአብሔር መልእክት አስተላላፊ የሆንኩት ራሱ የከበደኝና ኀዘንተኛ ያረገኝ ሲሆን፣ ያ ስሜቴ እያለ ለዚያ ወንበር ብቃት ሆነ እዉቀት ሳይኖረኝ መታጨቴ ኀዘኔን አበዛዉ እንጂ አላስደሰተኝም፣ አላስፈነደቀኝም፣ ይልቁኑ መሪር እንባ እንዳነባ ነዉ ያደረገኝ፡፡

እግዚአብሔር ለራሱ ዓላማ ላስነሳቸዉ አካላት ተወካይ ከሰጠዉ በኋላ በእነሱ በኩል ነዉ ታትሞ የሚሰራጨዉ በሚል እምነት ስከታተልና ስጠባበቅ ከሦስት ሳምንት በኋላ ተወካዩ አንብቦት መጨረሱን ገልጾልኝ፣ አንዳንድ ጥያቄዎችን ከጠየቀኝና እኔም ከመለስኩለት በኋላ ያልጠበኩት ምላሽ ነበር የሰጠኝ፡፡ ይኸዉም ፓለቲካዊ ይዘት እንዳለዉና ከቤተክርስቲያን እዉቀት ዉጭ እንደሆነና እንደማይቀበለዉ በግልጽና በድፍረት ነገረኝ፡፡ በወቅቱ ከማዘን ዉጭ ምንም ሳልል በጸሎት አስበኝ በማለት ተለየሁት፡፡ ታዲያ እናትና ልጅ የሚያጋጥመኝን ምልሻ ቀደም ብለዉ ያዉቁታልና ስሜቴ እጅግ እንዳይጎዳ በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡትን በአካልም፣ በስምም፣ በዝናም የማላዉቃቸዉን በአድራሻቸዉ እንድገናኝ አስደርገዉ የእግዚአብሔርን መልእክት ላኩላቸዉ፡፡ እሳቸዉም መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነዉና እዉቀታቸዉን ሳያመልኩና ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ሳያደርጉ የእኔን ማንነት ለማወቅ ሳይፈልጉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ መርምረዉት፣ ምንም እንኳን አንዳንድ የማይታወቁ እዉቀቶችና ምስጢራት ቢኖሩበትም ያ ሰዎች ስላላወቁትና ስላላስተዋሉት እንጂ የነበረና ያለ እዉነታ መሆኑን አዉቀዉና ከእግዚአብሔር መሆኑን አረጋግጠዉ የተቀበሉት መሆኑን በአጭር ቀናት ዉስጥ ምላሽ ሰጡኝ፡፡ እኔም ከኀዘኔ በተወሰነ ደረጃ ተጽናናሁ፡፡ ነገር ግን የተመረጡት አካላት ተወካይ «አልቀበለዉም» በማለቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባሁኝ፡፡ ይኸዉም «ፍጹም ያንተ መልእክት የሆነዉን አንተ የመረጥካቸዉ አካላት ተወካይ አልቀበለዉም ብሏል፣ ስለዚህ አንድ ግለሰብ አይደለም ዓለም እስኪቀበለዉ ድረስ በዓለም ላይ ቅሬታዬንና ተቃዉሞዬን ለመግለጽ ከእንግዲህ በትዉልዱ ጎስቋላ ገጽና መልክ በሚስለዉ መልክና ሕይወት ነዉ የምመላለሰዉ» በማለቴ ነዉ እስከ አሁን ድረስ ማንም በሥጋዊ ዓይኑ ሲመለከተኝ

ጎስቋላ ወይንም ራሱን የጣለ ወይንም እብድ ወይንም ንክ ወይንም ፈላስፋ በሚያስመስለዉ ገጽታ የምመላለሰዉ::

እዚህ ላይ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡት ካህኑ እጨጌዉን ወይንም ፓትርያርክ የሚሆኑትን ያወኳቸዉ፣ ልክ በአካልም በስምም በሌላም መልኩ የማላዉቃቸዉ በሥጋዊዉ ወንበር ላይ የሚቀመጡትን ካህኑ ርእሰ ነገሥት (ንጉሠ ነገሥት) ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ በእግዚአብሔር ድምፅ ባወኳቸዉ መንገድ ነዉ:: ሁለቱን በመንፈስ ቅዱስ ነዉ ያወካቸዉ እንጂ በአካል በመተዋወቅ አይደለም:: በሚገለጡበት ወቅትም በተገለጸልኝና በተነገረኝ መሰረት ማንነታቸዉን፣ ስማቸዉን፣ ሥልጣናቸዉን መለየትና ማረጋገጥ እችላለሁ:: ለዚህ ነዉ ዓለም እስከ አሁን ድረስ እዉቅና ባይሰጣቸዉም እግዚአብሔር ስለመረጣቸዉና ስለቀባቸዉ እንዲሁም በቅድስት ድንግል ማርያም ሆነ በቅዱሳን መላእክትና በጻድቃን እዉቅና ስለተሰጣቸዉ እኔም እዉቅና ሰጥቼ በመልእክታቴ ላይ «ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴና ባለሟል ካህኑ እጨጌ፣ ካህኑ ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት)» በማለት መልእክታቴን የማሳዉቀቻዉ:: እንዲሁም በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ሁሉ በግልጽና በተጠያቂነት ሥርዓት ስለሚከናወን አጠቃላይ እንቅስቃሴዬን ጭምር እንዲያዉቁት በማሰብ ነዉ::

ታዲያ የእግዚአብሔር መልእክት ተቀባይነቱን በእንደራሴዉ በኩል ከተገለጸልኝ በኋላ ለሌላዉ ለሕጋዊ ተወካይ የእግዚአብሔርን መልእክት በደብዳቤ ያቀረብኩ ሲሆን፤ እስከ አሁን ድረስ አንዳች ምላሽ አልተሰጠኝም:: ይሁንና የወገኖቼ ኢትዮጵያዉያን ሆነ የዓለም ሕዝብ ጥፋት አላስቻለኝምና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሳልጠብቅ በራሴዉ መንገድና ወጭ በመጽሐፍ መልክ አሳትሜ ከየካቲት፭÷፪፻፫ (5/06/2003) ዓ.ም ጀምሮ በየቤተክርስቲያኑ ማሳረጨት የቻልኩ ቢሆንም፤ አንድ ቀን ወደ አንድ ቤተክርስቲያን ሄጄ በማሰራጨት ላይ እያለዉ መድረኩን በሚመሩ አስመሳይ አገልጋዮች ተቃዉሞ ስለገጠመኝና የማስደብደብ ሙከራ ቢያደርጉም በሰማዕቷ እርዳታ አንድ ከእነሱ በሚሻል ተራ አስከባሪ አማካይነት እየተገፈተርኩና እየተሰደብኩ ተባረርኩ:: ከዚያም ወደ አንድ ቤተክርስቲያን በመሄድ በተለመደዉ አሰራሬ ከቤተክርስቲያን ቅጥር ዉጭ አንዳች ድምፅ ሳላሰማ መጻሕፍቱን በእጆቼ ከፍ አድርጌ ለሁለት ሰዎች እንዳሰራጨዉ ለጊዜ ማሳለፊያ የመጣ የሚመስል አስመሳይ አማኝ፤ ስለ መጽሐፉ ይዘት አንዳች ሳይጠይቅና ሳያነብ ሁከት አስነስቶ ባካባቢዉ የነበሩትን የፖሊስ ተጠሪዎችን በማስመጣት ወደ ቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪና ሰባኬ ወንጌል ወደተባለዉ እንድቀርብ ተደረገ:: እነሱም ስለ እኔ ሆነ ስለመጽሐፉ አንዳች ሳይጠይቁኝ መንግሥት እዉነተኛ ተቃዋሚዎቹን ለመበቀል ባወጣዉ ሕግ ሽፋን በአሸባሪነት ወንጀል እንድከሰስ የክርስቶስን መስቀል ያህልና ቅዱስ ወንጌል ይዘዉ በሐሰት «በቤተክርስቲያን ዉስጥ ዓለም ታልፋለች እያለ ሁከትና ሽብር ሲነዛና ረብሻ ሲፈጥር ነዉ የያዝነዉ» በማለት የሐሰት ምስክር ቢጤዎቻቸዉን አዘጋጅተዉ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ::

በፖሊሶቹም አስፈላጊዉ ምርመራ የተደረገብኝ ሲሆን አንዳች ጥፋት ስላላገኙብኝ ይልቁኑ መስቀልና ወንጌል ከያዙት ተሸለዉ «ጴጥሮስ እንኳ ጆሮ ቆርጧልና አይሰማህ» በማለት በነጻ

አሰናብተዉኛል:: በወቅቱ የማይረሳኝ ስለቤተሰቤ ስጠየቅ ገና በሕፃንነት እድሜ ያሉት ልጆቼ ትዝ ብለዉኝ ያለቀስኩት መሪር እንባ ነዉ:: ከዚያ የወሰንኩት በኅዳር፲፪÷፳፻፫ (12/03/2003) ዓ.ም የቅዱስ ሚካኤል በዓል ዕለት  በቅዳሴ ሰዓት የጌታን ስነ ስቅለት እየተመለከትኩ ምርር ብዬ በማልቀስ እግዚአብሔርን «ራሴን ለዓለም አዋርጄ በመልእክትህ ገልጫለሁ፤ ሌላ ምን ላድርግ?» ብዬ ስጠይቀዉ፤ «ራቁትህን ሂድ» የሚል ምላሽ ነበር የተሰጠኝና በዚያን ወቅትም በደስታ አነባዉ:: ምክንያቱም በሥጋ ሞት እንደማላከብረዉ ስለተረዳዉ በዚሁ መልኩ እዳከብረዉ ፈቃዱ ስለሆነ በደስታና በጉጉት ነበር ራቁቴን የምሄድበትን በናፍቆት ስጠባበቅ የነበረዉ:: ይሁንና «የእግዚአብሔር አገልጋዮች» የተባሉ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪና «የወንጌል ሰባኪ» የተባሉ፤ «የእግዚአብሔርን መልእክት አለመቀበል ብቻ አይደለም ለማስወንጀል የዉሸት መረጃ የሚያዘጋጁ ከሆነ፣ ዓለማዉያንማ እንዴት ይቀበሉታል? ይሰሙታል?» በማለት ወደ ልቤ ተመልሼ፤ ቀደም ሲል መልእክቱን ካደረስኩ በኋላ ራቁቴን ለመሄድ የወሰንኩትን የራሴን አካሄድ ትቼ፤ እርሱ እግዚአብሔር ነፍሴ በምትሰማዉ ድምፅ ብቻ መልእክቱን «እንዲህ አድርግ» እስከሚለኝ ድረስ  ለመጠበቅ ወሰንኩ:: እንዲሁም «ራቁትህን ሂድ» ላለኝ ደግሞ «እግዚአብሔር ሆይ! ፈቃድ ከሆነ በኀዘን ዉስጥ ላለችዉ ባለቤቴና ሕፃናት ልጆቼ እንዲሁም የእኔ ሁኔታ ስላስጨነቃቸዉና ስላሳሰባቸዉ ቤተሰቦቼና ወዳጆቼ ስትል ይህን ጽዋ ከእኔ አሳልፍ» በማለት ጥያቄዬን አቀረብኩ :: እንዲሁም «ግድ መፈጸም አለብህ ካልከኝ ደግሞ፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ ራቁትህን ሂድ ስትለኝ ነዉ የምፈጸመዉ» በማለት እንደ ራሴ ሥጋና ደም ሐሳብ የምሄድበትን አካሄድ አቆምኩ::

ከመስከረም፳፻፫(2003) ዓ.ም እስከ ሚያዚያ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ፋሲካ ድረስ ወድቄበት ከነበረዉ መሬት በመነሳት አልጋዬ ላይ ወጣሁ:: የእግዚአብሔርን ቀንና ጥሪን መጠባበቅ ጀምርኩ:: መስከረም አንድ ፳፻፬ (1/01/2004) ዓ.ም ሲመጣ እንደ አምናዉ የሚመጣልኝ ድምፅ ይኖር ይሆን እያልኩ ስጠብቅ አንዳች ነገር ሳይመጣ ቀርቶ፤ መስከረም አጋማሽ ላይ ግን እንደ ተለመደዉ ነፍሴ ብቻ የምትሰማዉ ድምፅ መቶልኝ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ የተጻፈዉን ሁለተኛ ዉን የእግዚብሔርን መልእክት፣ አንብቤዉ ሆነ ሰምቼዉ በማለዉቀዉ አጻጻፍ እስከ ታሕሳስ ፳፻፬ዓ.ም (2004) መጀመሪያ ድረስ እንድጽፍ አደረገኝ:: ታዲያ ገና መልእክቱን እየጻፍኩ እያለ በመስከረም ወር ማለቂያ ላይ ምንም ሳልጠይቅ መልእክቱን አምና «አንቀበልም» ላሉኝ በቀጥታ እንድሰጥና ለእንደራሴዎቹና ለአንድ ወንድም ደግሞ በግልባጭ እንዳሳዉቅ ተነገረኝ:: በጥቅምት፳፯÷፳፻፬ (27/02/2004) ዓ.ም ደግሞ በጸሎት ላይ ምርር ብዬ የሲቃ ለቅሶ ሳለቅስ ርኅሩኅ የሆነዉ አምላክ፤ የመጀመሪያዉንና ሁለተኛዉን መልእክት እንዳሰራጭ ሙሉ ፈቃድ ሰጠኝ:: ከዚያች ቀን ጀምሮ የተለየ መጽናናት አግኝቼ     ሁለተኛዉን መልእክት ቀን ከሌሊት  በመጻፍ ለታሕሳስ ፲፮÷፳፻፬ (16/04/2004) ዓ.ም ስርጭት አደረስኩ::

ከዚያም ከተለያዩ ጽሑፎችና ከመገናኛ ብዙኃን በማገኘዉ አድራሻ እስከ አሁን ድረስ  በኢ-ጦማር (በኢሜል) አድራሻቸዉ ቁጥራቸዉ በሺዎች ለሚቆጠሩ ለተለያዩ ግለሰቦችና አካላት እየላኩ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ በሚያዚያ ወር ፳፻፬ (2004) ዓ.ም «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል

ርእስ በርእሰ ነገሥት«በሣልሳዊ ተዎድሮስ» በመባል ለዘመናት ሲነገርና ሲጠበቅ በነበሩት የእግዚአብሔር እንደራሴና ባለሟል የተላለፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት ቀደም ሲል በእኔ በኩል የተጻፈዉን መልእክት ላስተላለፍኩላቸዉ ሰዎች ሁሉ እንዲደርሳቸዉ አድርጌያለሁ:: ከዚህ ሌላ ደግሞ ስለ ሕዳሴዉ ግድብ ለጠቅላይ ሚንስትሩ አስተያየት እንድንሰጥ በተከፈተልን ልዩ አድራሻ(ኢሜል) አማካይነት የካቲት፳፯÷፳፻፬ (27/06/2004) ዓ.ም በሦስት ገጽ መልእክት አስተያየቴንና ምክሬን ገልጨላቸዉ ነበር:: እንዲሁም እሳቸዉም ሆኑ ሌሎች የዓለም መንግሥታት በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡና የሚያዋጣቸዉም ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ወንበሩን እግዚአብሔር ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ለንጉሠ ነገሥቱና ለካህኑ እጨጌ አሳልፈዉ እንዲሰጡና በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር በመስጠት በእርሱ ሥርዓት እንዲመላለሱ ተገልጾላቸዉ ነበር:: ይሁንና አልሰማ በማለታቸዉ ከሦስት ወር በኋላ በእግዚአብሔር ቁጣ አልጋ ላይ ሊወድቁና የቁም ስቃያቸዉን አይተዉ እዉነተኛ ንስሐ ሳይገቡ ከነዓመፃቸዉና ከነትዕቢታቸዉ ይህችን ምድር በሥጋ ሊለዩ ችለዋል:: በነፍሳቸዉ ደግሞ ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ተላብሰዉ እንደ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ተግባራቸዉና ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ እንደ አለመወጣታቸዉ ደረጃ ፍዳቸዉን ለሕያዉነት ዘመን ወደሚቀበሉበት ሁለተኛ መቀጫ ቦታ ተጉዘዋል::

እኔ የሚያሳዝነኝ በሥጋ መለየታቸዉ ሳይሆን ምክንያቱም ሁላችንም ከሥጋችን በተለያየ ጥሪ መለየታችን አይቀርምና፤ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡና በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ እንዲሁም በእግዚአብሔር እዉነታና በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያመፁትና ያሳመፁትን ፣የካዱትና ያስካዱትን እንዲሁም ርኩሰት የፈጸሙትንና ያስፈጸሙትን በግልጽ አምነዉ ምሕረትን ጠይቀዉ ባለመሄዳቸዉና ራሳቸዉን ለከፋዉ ቅጣት አሳልፈዉ በመስጠታቸዉ ነዉ:: ሌላዉ አስገራሚዉ ደግሞ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናት ሆኑ ካድሬዎቻቸዉ እንዲሁም ደጋፊዎቻቸዉ እነሱም ዋጋ እንደሚከፍሉ ባለማስተዋልና ሕሊናቸዉን በማደንደን «እጃችንን አንሰጥም፤ በንስሐ ራሳችንን አናዋርድም» በማለት በዓመፃቸዉ መጽናታቸዉ ነዉ::

ይህም የሚያሳየዉ ዓመፃቸዉና ትዕቢታቸዉ ከፈርኦንና ከሠራዊቱ የባሰ መሆኑን ነዉ:: ምክንያቱም ፈርኦን የግብፃዉያን በኩር ከራሱ ልጅ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቁጣ ሲረግፉ እጁን ለእግዚአብሔር ሰቶ የታዘዘዉን ሊፈጽም ችሎ ነበርና:: የአሁኖቹ ግን ዋና መሪያቸዉ ባልታሰበና ባልተገመተ ጊዜ ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበሩ ተቆርጦ ሲሄዱ ዐይናቸዉ እያየ ሕሊናቸዉን እስከ አሁን ድረስ አደንድነዉ የተባሉትን ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆናቸዉ ነዉ:: እስከ አሁን ድረስ በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ እንደ ጸኑ ነዉ:: ይህም ለከፋ ምድራዊና ሰማያዊ ቅጣት ራሳቸዉን እያዘጋጁ እንደሆነ ይሰማኛል:: ምናልባት አሁንም የሚሰማ አካል ካለ ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ወንበሩን ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን እዉነተኛ እንደራሴዎችና ባለሟሎች እንዲለቁ አሳስባቸዋለዉ፤ አስጠነቅቃቸዋለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ከማንም በላይ ያዉቃልና ነዉ በእግዚአብሔር አሰራር ዉስጥ ቅድመ ሁኔታና ድርድር የሌለዉ:: የእግዚአብሔር እንደራሴዎች እግዚአብሔር በእነሱ ላይ አድሮ ስለሚሰራና ስለሚፈርድ የእርሱ ፈቃድ

ብቻ ነዉ የሚጸናዉ እንጂ እንደ ዲያብሎስ እንደራሴዎች መሪዎችና ባለሚሎች ባለሥልጣናት እንዲሁም ዉዶች ካድሬዎች የሥጋና የደም ስሜታቸዉ አይደለም።

በሰኔ፲፭÷፳፻፬ (15/10/2004) ዓ.ም ለተለያዩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም «መንፈሳዊ አገልግሎት ነዉ የምንሰጠዉ» በማለት በሕዋ ሰሌዳ(ድረ ገጽ) ላይ መልእክት ለሚያስተላልፉ ሰዎች ምክርና ማስጠንቀቂያ የደረሳቸዉ ሲሆን፤ በግልጽ የተገለጸላቸዉ ደግሞ በሥጋዊ ወንበር ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት ሰዎች የሚቀራቸዉ እንደ ንጉሥ ሳኦልና ግብረ አበሮቹ እንዲሁም እንደ ካህኑ ኤሊና ልጆቹ ዋጋ ከፍለዉ ማለፍ ብቻ እንደ ሆነና ሥጋዊዉ ሆነ መንፈሳዊዉ ወንበር እንድ ንጉሥ ዳዊት ለተመረጡትና ለተቀቡት ለርእሰ ነገሥቱ (ንጉሠ ነገሥቱ) እና እንደ ነብዩ ሳሙኤል ለተመረጡትና ለተቀቡት ለካህኑ እጨጌዉ ተላልፎ መሰጠቱን ነዉ። ታዲያ ይኸዉ በሁለት ወር ዉስጥ ሁለቱም በወንበር ላይ የተቀመጡት መሪዎች ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ ከነዓመፃቸዉ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና ወደ ሁለተኛዉ ዓለም ሊጓዙ ችለዋል። ከእንግዲህም ግብረአበሮቻቸዉ ዋጋ ከፍለዉ ማለፍ ነዉ የሚቀራቸዉ።

ከዚህ በተጨማሪ ነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ (15/12/2004) ዓ.ም ከዚህ በፊት የእግዚአብሔር መልእክታት ለተላኩላቸዉ ሰዎች ሆነ አካላት ለሁሉም በሰኔ፲፭÷፳፻፬ (በ15/10/2004) ዓ.ም የተጻፈዉን መልእክትና ተጨማሪ መልእክት ተልኮላቸዋል። በአዲሱ መልእክትም ለዓለም መንግሥታት የእግዚአብሔርን መልእክት እንዲያደርሱና እጃቸዉን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ እንዲያደርጉ፤ «እግዚአብሔርንም አናዉቅም፤ መልእክቱን አንቀበልም» ካሉ ደግሞ ዋጋ ከፍለዉ ከነዓመፃቸዉና ክህደታቸዉ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ወደ ሲኦል እንደሚጠሩና ፍዳቸዉንም ለሕያዉነት ዘመን እንደሚቀበሉ እንዲገልጹላቸዉ ማሳሰቢያ ሰጥቻለሁ። ታዲያ ይህ ሁሉ ጥረቴ የዓለም ሕዝብን ሆነ ኢትዮጵያዉያንን ከጥፋትና ከጠረጋ ለማትረፍ ቢሆንም ትዉልዱ በዲያብሎስ ሥርዓት ዉስጥ ስለሚመላለስ ሕሊናዉ በተለያዩ ጉዳዮችና ወሬዎች ስለደነዘዘ እንዲሁም በፖለቲካ ሕሊናዉ ስለተመረዘና ስለተበከለ ተስፋዉንም ምድርን ስላደረገና በእዉቀቱ፣ በኃይሉ፣ በሥልጣኑ፣ በሀብቱ ስለተመካ፤ እዉቀታቸዉና ሊቅነታቸዉ ጣዖት ስለሆነባቸዉ ለእግዚአብሔር መልእክትና ቃል ቦታ አልሰጡትም። ይልቁና ንስሐ ከመግባት ይልቅ በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት እየጨመሩ ራሳቸዉን ሙሉ በሙሉ ለማስደምሰስ እያዘጋጁ ነዉ። በደላቸዉና ዓመፃቸዉ በኖኅና በሎጥ ዘመን ከነበሩ ሰዎች የባሰ ስለሆነ እንግዲህ የሚቀራቸዉ የምርጫቸዉን ምድራዊ ሆነ ሰማያዉ ቅጣት መቀበል ነዉ። ያኔ ማንነታቸዉንና ምንነታቸዉን በሚገባ ያስተዉላሉ።

የሕይወት ታሪኬን ጠቅለል አድርጌ ለማቅረብ እግዚአብሔርን በማወቅና በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ በማምለክ የተመላለስኩበት ዘመን ከአሥር ዓመት እንደማይበልጥ እገምታለሁ። ሌላዉ ዘመኔ እግዚአብሔርን ባለማወቅና እንዲሁም እንደ ሥጋና ደሜ ስሜት የተመላለስኩበት ስለሆነ ምንም እንኳ እድሜዬ በኅልማሳነት ቢቆጠርም እኔ ግን ትክክለኛ እድሜ አድርጌ የምወስደዉ በንስሐ በቅዱሳን ቁርባን ሕይወት ዉስጥ የተለመላለስኩበትን ጊዜ ነዉ። ይህም ከአሥር ዓመት እንደማይበልጥ እገምታለሁ። ኖሬያለሁ የምለዉ አካሄዴን ከእግዚአብሔር ጋር ባደረኳቸዉ ዓመታት ነዉ እንጂ

በሕፃንነት ሆነ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ያሳለፍኳቸዉ እንዲሁም እንደ ሥጋና ደም ስሜት የተመላለስኩባቸዉ ዘመናት እንደ ዘመን አልቆጥራቸዉም:: እንግዲህ ለጥያቄያችሁ ያለኝ መልስ ይህን ይመስላል::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: መንፈሳዊ አጀማመሮን እንደገለጹልን መንፈሳዊ ሕይወት ከጀመሩ ገና አሥር ወር ሳይሞላዎት ነዉ ዉስጦትን ለምንና አዘጋጅተዉ በመጀመሪያ ለእዚያ ሕይወት ራሶትን ለማለማመድ ወደ ገዳም የሄዱትና ሳይሰካሎት ወደ ቤተሰቦ የተመለሱት:: በአሥር ወር ዉስጥ ለመመነን መወሰነ እጅግ አልፈጠነም ወይ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:__ እንደ መንፈሳዊ አካሄድ እጅግ ፈጥኗል:: እኔ ከምንና ሐሳብ በፊት በሦስት ወር መንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ ነዉ ካለትዳር በብቸኝነት ሕይወት ለመኖርና እግዚአብሔርን በብቸኝነት ሕይወት ለማገልገል የወሰንኩት:: እኔ መንፈሳዊዉን ሕይወት ተመልክቼ የነበረዉ እንደ ሥጋዊዉ ሕይወት እንደ ጥረቴና ዉሳኔዬ የምፈልግበት ደረጃ ላይ ለመድስ ነበር:: ገና በልጅነቴ ለመሆን የምፈልገዉ የነበረዉ በራሴ አስተሳሰብ ትልቅ ደረጃ ላይ እንደደረሱትና ለእኔ የመጨረሻ ደረጃ አድርጌ ለምቆጥረዉ ስራ ነበር:: በትምህርትም ቢሆን ነገሮችን በደንብ ማገንዘብ ከቻልኩ ጀምሮ ለአንደኛ ደረጃ ነበር የማጠናዉና የምጥረዉ:: ከዚያም የሚመጣልኝን ዉጤትና ደረጃ በጸጋ እቀበለዋለሁ:: በከፍተኛ ትምህርት ተቋምም ኤ ለማግኘት ነበር የምጥረዉና የማጠናዉ፤ ከዚያም የመጣልኝን ዉጤት በጸጋ እቀበለዋለሁ:: የማያረካኝ ዉጤት ቢመጣብኝ እንኳ የራሴን ጥረት ስላደረኩ አይቆጨኝም፤ እልህም አልገባም ነበር::

በመንፈሳዊ ሕይወቱም ልክ እንደ ዓለማዊዉ ሐሳብ የመጨረሻዉን የብቃት ደረጃ ለመድረስ ካለኝ ፍላጎትና ዉሳኔ አንጻር ነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳላስተዉል፣ እንደ ራስ ፍላጎትና ምኞት ነገሮች እንደማይሆኑ ሳልገነዘብ፣ ከዚያም ባለፈ ሌት ተቀን በእኛ መንፈሳዊ ሕይወት በተቃራኒ ጎን የሚሰለፈዉን ዲያብሎስ(ሰይጣናት) አርቄዉ በመመልከቴ፣ የብቃት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከጀማሪነት ወደ ማዕከላዊነት ለመሸጋጋር እንኳ ብዙ ዓመታትን እንደሚፈጅ ባለመረዳቴ፣ ብቃት(ፍጹምነት) ላይም ለመድረስ የእግዚአብሔር እርዳታና ጸጋ እንደሚያስፈልግ ባለመገንዘቤ፣ ባጠቃላይ እንደ ሥጋና ደም ስሜቴ እንጂ እንደ እግዚአብሔር ጥሪና ፈቃድ ባለመመላለሴና በራሴ ሥልጣንና ጥረት ፍላጎቴንና ምኞቴን የማሳካ መስሎኝ ስለታየኝ ነዉ በራሴ ወስኜ በራሴ መንገድ መጓዝ የጀመርኩት:: ፍጥነት የተሞላዉ ዉሳኔ የተከሰተዉም ከዚሁ ፈጣንና ችኩል ጠባዬ የተነሳ ነዉ:: በሂደት ግን እንኳን እኔ ሌላዉም በራሱ ሥልጣን መስራትና መናገር ቀርቶ ማሰብ እንደማይችልና ሁሉ በእግዚአብሔር እርዳታና ቸርነት እንደሚሆን አስተዉያለሁ:: ከሰዉ የሚጠበቀዉ ቀና ማሰብ፣ መልካም መስራት፣ እዉነተኛ መሆን ነዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና መሪነት ነዉ ልንኖር የሚገባዉ እንጂ ተለዋዋጭና ጽናት በሌለዉ የሥጋና የደም ስሜታችን ፍላጎትና ምኞት የምንጓዝ ከሆነ ልንወድቅ፣ ልንሳቀል፣ መንገዳችንንም ልንስት እንችላለን:: ለእዚህም ነዉ ብዙ ሰዎች በሥጋና ደም ስሜታቸዉ እየተጓዙ ከሕይወት መንገድ የወጡትና በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሱትና ሌላዉም እንዲመላለስ የሚያደርጉት::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: እነዚህ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚባሉት ምንድናቸዉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚባሉት ባጠቃላይ እግዚአብሔር የማይወዳቸዉ ለፍርድ የሚዳርጉን የተለያዩ ኃጢአቶች ናቸዉ:: ዓመፃ የሚባሉት በተግባር ሆነ በንግግር እንዲሁም በሐሳብ ሊፈጸሙ የሚችሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ቃል የሚቃረኑ በዲያብሎስ መንፈስ የሚወደዱ ናቸዉ:: ለምሳሌ አስርቱን ትእዛዛት አለመጠበቅ ዓመፃ ነዉ:: ደረጃቸዉም ይለያያል:: ይኸዉም አንድ ትእዛዝ የጣሰና ሁለት ትእዛዝ የጣሰ የዓመፃ ደረጃቸዉና የሚቀጡበት ቅጣት እንዲሁ ይለያያል:: ሌላዉ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት የመሳሰሉትን ማሰብ ሆነ መናገር እንዲሁም ወደተግባር መለወጥ ዓመፃ ነዉ:: ነገር ግን የቅጣቱ ደረጃ በተግባር የተፈጸመዉ በንግግር ከተፈጸመዉ ይበልጣል:: በንግግር ደረጃ የተፈጸመዉ በሐሳብ ከተፈጸመዉ ይበልጣል:: ይህም የሚያሳየን በተግባር ሆነ በንግግር እንዲሁም በሐሳብ የሚፈጸም ኃጢአት ንስሐ ካልተገባበትና በሕሊናችንም ክፉዉን ሐሳብ ካልተቃወምነዉ እንጠየቅበታለን ማለት ነዉ:: ለዚህም ነዉ ክፉ ምኞት የሚያስጠይቅ ስለሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ፤ ወደ ሴት አይቶ የተመኘ እንደ አመነዘረ እንደሚቆጠር በግልጽ ያስተማረዉ:: ምንም እንኳ በተግባር ዝሙት የፈጸም የሚቀጣዉ ወይንም የሚጠየቅበት ደረጃና በሐሳብ በዝሙት የወደቀ የሚቀጣዉና የሚጠየቅበት ደረጃ ቢለያይም የተግባሩም፣ የንግግሩም፣ የሐሳቡም ኃጢአት ጭምር ያስጠይቃል::

ክህደት ደግሞ የእግዚአብሔር እዉነት ላይ በተቃራኒ አቋም መሰለፍ ነዉ:: እዉነተኛዉን አምላክ ክዶ ሰዉ በፈጠረዉ አምላክ የሚታመን ሰዉ እዉነተኛዉን አምላክ ክዷል ማለት ነዉ፤ በዚህም ክህደቱ ይጠየቅበታል:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን ህልዉና የካደ ሰዉ በግልጽ ክህደትን ፈጽሟል ማለት ነዉ:: ርኩሰት በተመለከተ በተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ መመላለስ ነዉ:: ሰዎች ከእዉነተኛ አምልኮ ወተዉ በአረማዊነት ሆነ በአሕዛብነት ሕይወት የሚፈጸሙት የተለያዩ አምልኮዎች በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቁና የሚያስፈርዱ ርኩሰት ናቸዉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: አሁን የተሰማሩበት ሙያ በልጅነት ለመሆን ይመኙት ከነበረዉ ጋር አንድ ዓይነት ነዉ ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: የልጅነት ምኞቴ የሥጋና የደም ስሜቴ ነበር እንጂ ስጦታዬ አለመሆኑን ትልቅ ከሆንኩ በኋላ አስተዉያለሁ:: የልጅነቴ ምኞቶች በእኔ አስተሳሰብ ሐኪም መሆን የመጨረሻ ደረጃ አድርጌ እቆጥር ነበርና ሐኪም ለመሆን ነበር የምመኘዉ:: ነገር ግን የሚጠበቅብኝም ነጥብ ማግኘት ባለመቻሌ ለዚህ ሙያ ልበቃ አልቻልኩም:: እግዚአብሔር ባወቀዉ ደግሞ ስጦታዬ ከቁጥር ጋር ነበርና በስጦታዬ ሙያ ልመረቅ ችያለሁ:: አሁን ላይ ሆኜ ሳስበዉ የልጅነቴ ምኞት የሥጋና የደም ስሜት እንጂ ስጦታዬ አለመሆኑንና በዚያ ሙያ ላይ ብሰማራ ኖሮ የሚሳካልኝ እንደማይሆን እገምታለሁ:: ያ ብቻ አይደለም አሁን የተሰማራሁበት ሙያ ምንም እንኳን በራሴ በምፈልገዉ ደረጃ የሚጠበቅብኝን ባለመጣቴና በሚያሰራኝ አካል ግን በሚፈለግብኝ ደረጃ የተወጣሁና እንዲሁም ለኑሮዬ ጥሩ ገቢ ያስገኘልኝ ቢሆንም፤ ለሕሊናዬ ግን የምፈልገዉን እርካታ

አልሰጠኝም፡፡ ምክንያቱም እንደምፈልገዉ ዉጤት ማምጣት ባለመቻሌና ብቻዬንም ማምጣት ስለማልችል ነዉ፡፡ ለእኔ እርካታ እየሰጠኝ ያለዉ የእግዚአብሔርን መልእክት ለወገኖቼ ለኢትዮጵያዉያን ሆነ ለዓለም ሕዝብ ማስተላለፍ መቻሌ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ እንደምፈልገዉና እንደምመኘዉ ዉጤት ባለመጣም ለሕሊናዬ ማድረግ ያለብኝን በራሴ በኩል እንደተወጣዉ ስለምቆጥር እርካታ አለኝ፡፡ ለወደፊትም በእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ ብሰለፍ እርካታዬ የበለጠ እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__: *የሕፃንነትና የልጅነት አስተዳደጎዎ ምን ይመስል ነበር?*

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: እኔ በመደብ ላይ ተቀምጬ፣ በጠፍር አልጋ ላይ ተኝቼ፣ በኩራዝና በፋኖስ ጭቃ ቤት ዉስጥ በገብስ እንጀራና በወንዝ ዉኃ ነዉ ያደኩት፡፡ ከስምንተኛ ክፍል በኋላ ደግሞ ቅንና ለሰዉ በሚኖረዉ ወንድሜ አማካይነት በአንድ ግቢ ተገድቤ ከብዙ ወንድሞች ጋር ነዉ በኅበረት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የኖርኩት፡፡ ከዚያም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዉስጥ የገባሁት፡፡

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__: *ከታናናሽና ከታላላቅ ወንድምና እህቶት ጋር የነበሮት የሕፃንነትና የልጅነት ሕይወትዎ፣ ግንኙነትዎ እንዴት እንደ ነበር፣ እንዲሁም ከወላጆችዎ ጋር የነበሮት ሕይወትና ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበረ ቢገልጹልን?*

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: እኔ በአንድ ወላጅ እንደ እናትም እንደአባትም ሆነዉ እንዳሳደጉኝና እንዲሁም በብቸኝነት እንዳደኩ ነዉ የሚሰማኝ፡፡ እንዲሁም በሕፃንነቴና በልጅነት እድሜዬ ከወንድምና እህቶቼ ጋር «እንዲህ እጫወት ነበር፤ እንዲህ አደርግ ነበር» የምለዉ የለም፡፡ አስተዳደጌ በብቸኛነት ስለነበረ ይመስለኛል አሁን ከሰዉ ጋር ያለኝ ግንኙነት የተወሰነና የተገደበ የሆነዉ፡፡

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__: *የትዳር አጀማመሮና ሕይዎትዎ እንዴት እንደነበረና አሁን ምን እንደሚመስል ቢገልጹልን?*

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከወጣትነት እድሜ ጀምሮ በራሴ መስፈርትና ምርጫ የትዳር አጋር ስፈልግ ነበር፡፡ ይሁንና የእኔ ምርጫ በተለያየ ምክንያት ሳይሳካልኝ ቀርቶ በሠላሶዎቹ እድሜ መጀመሪያ ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ የትዳር ጓደኛ ላገኝና በወራቶች እድሜ ዉስጥ ለጋብቻ ወስነን ዓመት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ልንጋባ ችለናል፡፡ በወቅቱ የእኔ መስፈርት የነበረዉ እግዚአብሔርን መፍራት ያለባት የቤተክርስቲያን ልጅ መሆኗንና ዉስጤም ሕሊናዬ የተቀበላት መሆኑ ብቻ ነበር፡፡ ከዚያ ዉጭ ስለ ቤተሰቧ ሆነ ስለ ዘሯና ጎሷ(ብሔሯ) እንዲሁም ስለትምህርትና የስራ ደረጃዋ ቦታ አልሰጠሁኝም፡፡ እርሷም የቤተክርስቲያን ሰዉ መሆኔንና ቤተሰብ ላስተዳድርና ልመራ መቻሌን እንዲሁም ሕሊናዋ ስለተቀበለዉ እንጂ፤ ሀብት ንብረትን፣

ዘርን፣ ጎጥን(ብሔርን) አንዳች እንደመስፈርት ሳትቆጥር በኢትዮጵያዊነቴ ብቻ ነዉ ልትቀበለኝና ለትዳር ፈቃደኝነቷን የገለጸችልኝ፡፡

እሷነቷን ከተቀበልኩና ለትዳር ከወሰን በኋላ ነዉ ስለ ቤተሰቧ በተወሰነ ደረጃ ለማወቅ የቻልኩት፡፡ እሷም በትዳር ወቅት ነዉ ስለቤተሰቦቼ በደንብ ያወቀችዉ፡፡ የእግዚአብሔር ምርጫና ፈቃድ ስለነበረ በኋላም የእኔም ቤተሰብ ሆነ የእርሷ ቤተሰብ ተመሳሳይነት ያላቸዉና ወላጆቻችንም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች ሆነዉ የታዩት፡፡ እንዲሁም ቤተሰቡም ሁሉም በአምልኮተ እግዚአብሔር ዉስጥ የሚመላለሱ እግዚአብሔርን መፍራት ያለባቸዉ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔር ባርኮትና በረከት ሳይለየን ልጅ ወለድን፤ የራሳችን ቤት ኖረን፤ ኑሮዋችንም ተሻሻለ፤ ሕይወታችንም በጋብቻችን ጊዜ በቅዱስ ቁርባን እንደተዋሕድንና አንድ እንደሆን ሁሉ አሁንም በሥጋዉና በደሙ ተወስነን እግዚአብሔርንም በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እያመለክን እንደ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት እየተመላለስንና እየኖርን እንገኛ ለን፡፡ » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሁለት

«**ጠያቂዉ አገልጋይ**: ቀጣይ ጥያቄዬ በእርሶ በኩል ሆነ «በሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በኩል በተላለፈዉ የእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ ጥንት ስለነበረዉ፣ አሁን እያለ ስላለሁ፣ ወደፊትም ስለሚሆነዉ፣ እንዲሁም በፍርድ ቀንና ከፍርድ ቀን በኋላ ከዚያም አልፎ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ስለሚሆነዉ ሳይቀር እግዚአብሔር ግልጽ ባለ ቋንቋ እንዲቀርብ አድርጓል:: ታዲያ ትዉልዱ ሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንዴት ማስተዋልና ለሕዝቡም ለመግለጽ፣ ለማስረዳት ተሳናቸዉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በእርግጥ እግዚአብሔር ያላደረገልን ነገር የለም:: የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ በሥጋ ማርያም ተገልጾ አስተምሮናል፣ ምን ማድረግ እንዳለብን፣ ምን ማድረግ እንደሌለብን፣ ተስፋችን ምን እንደሆነ ሁሉን ራሱ በሥጋ ተገልጾ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ ሁሉን ገልጾልናል:: ታዲያ የመጀመሪያ የእርሱ ተቃራኒና ተቃዋሚ የሆኑት ሰዎች የእግዚአብሔር አገልጋይ የተባሉት ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት ነበሩ:: ምክንያቱም አገልግሎታቸዉ ለገቢ ማግኛ፣ ለመከበር፣ የበላይ አዛዥ ናዛዥ ለመሆን እንጂ ራሳቸዉን በእግዚአብሔርና በሕዝብ ፊት ዝቅ አድርገዉ በእዉነትና በመንፈስ እያመለኩ ሕዝቡንና ምእመኑን ለማገልገል አልነበረም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የሰዎች ዉጫዊ ሕይወታቸዉን ብቻ አይደለም የዉስጣቸዉንም ጭምር ስለሚያዉቅ አስመሳይ አገልጋዮች መሆናቸዉን መስክሮባቸዋል፤ ለእዉነተኛ አገልጋዮች አርአያ ለመሆን ሁሉን የጽድቅ ስራ እየሰራ አሳይቷቸዋል፤ ራሱንም ዝቅ አድርጎ በትህትና አገልግሏቸዋል፤ ስለ እዉነትም ካለ አንዳች  ፍርሃት ሆነ ማስመሰል መስክሯል:: ስለ እዉነትም ራሱን ክዶ ከመሰደብ፣ ከመገረፍ፣ ከመዋረድ፣ ከመሰቀልና፣ በሥጋ ከመሞት ጭምር የተለያየ መከራን በመቀበል ምሳሌ ሆኗቸዋል::

ታዲያ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን እርሱ ፈጣሪ አምላክ እግዚአብሔር ለአርአያ የፈጸመዉን መፈጸም ሲጠበቅባቸዉ በተቃራኒ መሰለፋቸዉ ነዉ እጅግ የሚያሳዝነዉና የሚያስተዛዝበዉ:: በተለይ በመንፈሳዊ ሆነ በሥጋዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ምእመኑንና ሕዝቡን እናገለግላለን የሚሉ አገልጋዮች ከሁሉ በላይ በሕይወታቸዉ አርአያ በመሆን ነገረ መስቀሉ በሕሊናቸዉ ታትሞና ተስሎ ሊታያቸዉና ያ ምስኪን አባት ትዝ እያላቸዉ በእዉነትና በመንፈስ እያመለኩና እያገለገሉ መኖር ሲጠበቅባቸዉ፤ እነሱ ግን አምላክን ያህል ራቁቱን በመስቀል ላይ ሰቅለዉ ራሳቸዉን ያገለግላሉ፣ እንዲሁም ያስመልካሉ፣ ያስገንናሉ:: ታዲያ ምእመኑ ሆነ ሕዝቡ እነሱን እየተመለከተ እንዴት ለሕናዉና ለአምላኩ ይታመን? ሕሊናዉን እንዲሸጥ እያደረጉና በኃያላቸዉና በጦራቸዉ እንዲሁም በስለላ ድርጅታቸዉ እያስጨነቁት እንዴት ራሱን ሊክድና ስለ እዉነት ሊመሰክር ይችላል? ተስፋዉን ምድር እንዲያደርግ ሌት ተቀን እየሰበኩት፤ እንዴት ወደማንነቱ ተመልሶ ተስፋዉን ሰማያዊ አድርጎ ይኑር? ሕሊናዉን በፖለቲካ መርዘዉና በክለዉ፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን አስፋፍተዉ፣ ራስ ወዳድነትንና ስግብግበነትን ፈጥረዉ፣ ሕዝቡ እንዴት እርስ በእርስ ሊፋቀርና ሊተሳሰብ ይችላል? ባጠቃላይ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊዉ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ እግዚአብሔርን መፍራት በሌለበት

ሕይወት የሚመላለሱ አስመሳይ የሕዝብና የምእመናን አገልጋዮች፤ መልካም ፍሬ እንዴት ያፍሩ? እንዴትስ መልካም ፍሬ ይሰብስቡ? ለዚህም ነዉ የዓመፃ ልጆችና የዓመፃ ሰዎች በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ስለተቀመጡ መልካም ፍሬ ማፍራት ባለመቻላቸዉና በተለያዩ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ በመመላለስ ላይ በመሆናቸዉ ምክንያት የእግዚአብሔርን መልእክት ለመቀበልና ለሕዝቡም ለማስተላለፍ ፈቃደኛ ያልሆኑት።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ታዲያ አሁን ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: አሁን መደረግ ያለበት በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ያሉ ሰዎች በእዉነተኛ ንስሐ በመመለስና ይህንንም በይፋ በማሳወቅ ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ወንበሩን እግዚአብሔር ላዘጋጃቸዉ እንደራሴዎቹና ባለሚሎቹ መልቀቅ ነዉ። በቅንነትና በእዉነት እያገለገሉ ያሉ ሰዎች ካሉ እግዚአብሔር ያዉቃቸዋልና ለሙሉ አገልግሎት ሊያበቃቸዉ ይችላል። ከእዚያ ዉጭ በዓመፃና በክህደት እንዲሁም በአምልኮ ምንዝርና ያሉ ሰዎች በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ በእዉነተኛ ሕይወት ሆነዉ የበደሉትን አምላክና ሕዝብ ይካሱ። «አይ እኛ የእግዚአብሔርን መልእክት አንቀበልም፤ ወንበሩንም ለእንደራሴዎቹና ለባለሚሎቹ አንለቅም» የሚሉ ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔር ሊያደርግ የወሰነዉን ማንም ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ አይችልምና በቁጣዉ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ ይቆርጣቸዋል፤ በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍላቸዋል፤ በመጨረሻም ፍዳቸዉን ይቀበላሉ። በእግዚአብሔር ቀንና ቁጣ፤ ተራ፣ አቅመ ቢስ፣ ልምሾ፣ መሆናቸዉን ይረዳሉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ቀደም ብለዉ እንደነገሩን በጥቅምት፳፯÷፳፻፬ (27/02/2004) ዓ.ም የመጀመሪያዉንም ሁለተኛዉንም የእግዚአብሔር መልእክት እንዲያሰራጩ ከእግዚአብሔር እንደተፈቀደሎት ነዉ። ታዲያ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ የታተመዉን መጽሐፍ አሰራጩት ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ለማሰራጭት ሙከራ አድርጌያለዉ ብል የሚቀል ይመስለኛል። ምክንያቱም በየአብያተክርስቲያኑ አካባቢ ለማሰራጨት ብሞክርም፤ ትዉልዱ ዝነኞችንና ታዋቂዎችን ብቻ የሚፈልግና የሚሰማ ስለሆነ በመጽሐፉ ላይ ጸሐፊዉ ተብሎ የተገለጸዉ ስም ደግሞ «ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ» የሚል ነዉና በትዉልዱ አልተፈለገም፤ ተቀባይነትን ባለማግኘቱም አሁንም መጻሕፍቱ በእስር ላይ ይገኛሉ። ይህ ስም በትዉልዱ እንደ ስም ሊቆጠር አልቻለም። ምክንያቱም ወይን ሊቅ ወይንም መልአክ ወይንም ምሁር ወይን የክህንት ሥልጣን ወይንም ዲፕሎማ ወይንም ድግሪ ተብሎ እንዲገለጽ ነዉ ትዉልዱ የሚፈልገዉ እንጂ፤ «መጽሐፉ ምን ይዟል?» ብሎ አይጠይቅም፤ ለማንበብም ፈቃደኛ አይደለም። በመጽሐፍ ስርጭቱ ተስፋ የቆረጥኩበት ደግሞ፤ በየካቲት፲፮÷፳፻፬(16/06/2004) ዓ.ም በእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት፤ የእመቤታችን ልጆች ይድረሳቸዉ ብዬ በሺህ የሚቆጠር መጽሐፍ ይዤ ብገኝም ሁለት ሰዉ ነዉ የመጽሐፉን የዉጭዉን ገጽታ በመመልከት ለመዉሰድ ፈቃደኛ የሆነዉና ያንንም እኔ ዘንድ መቶ ጸሐፊዉ ማን

እንደሆነ ጠይቀዉኝ እኔም በክፍል አንድ በምዕራፍ ስድስት በገጽ 28 ላይ የጸሐፊዉ ማንነትን በማስነበብ ነዉ:: ይኸዉም

«ይላል ሳይገባዉ ለዚህ መልዕክት አስተላላፊነት የተመረጠዉ ተራና ወራዳ ኃጢአተኛ ሰዉ» በማለት ነዉ ራሱን የገለጸዉ ብዬ ያስራዳዋቸዉና፤ «ይህም የእግዚአብሔር መልእክት ስለሆነ ራሱን በማዋረድ ነዉ እግዚአብሔር እንዲከብርና እንዲገን ፈልጎ ስሙን እንኳ መግለጽ ያልፈለገዉ:: ለንግድ ነዉ እንዳይባል ደግሞ በአሁን ሰዓት እንኳን በዚህ ዋጋ ለመሸጥ አይደለም ለማሳተም እንኳ አይቻልም:: አሁን ለእናንተ እንዲደርስ የተደረገበት ዋጋ እንኳ በመጽሐፉ ላይ ከተገለጸዉ ዋጋ በታች በማተሚያዉ ዋጋ ነዉ፤ ደግሞ መጽሐፉ እዉነተኛ ባይሆን እንኳ የምትከስሩት አሥር ብር ብቻ ነዉ እንጂ በሕይወታችሁ ላይ አንዳች የሚቀነስ ሆነ የሚጨመር አይደለም:: ነገር ግን አሥር ብር አዉጥታችሁ ከአሥር ሺህ ብር በላይ የሚገመት ቁም ነገር ልታገኙበት ትችላላችሁ:: እንኳን በእግዚአብሔር ስም የመጣ አይደለም፤ ሌላ አንዳች ለሥጋችን ሆነ ለነፍሳችን ጥቅም የማይሰጡ ጽሑፎችን ገዝተን እናነብ የለም ወይ? አሁንም የገንዘብ ጉዳይ አይደለም! በነጻ ልሰጣችሁ እችላለሁ፤ ነገር ግን ሰዉ ዋጋ ላልከፈለበት ነገር ትኩረት ስለማይሰጥ፤ ስላልከፈላችሁበት በቁም ነገር ላታነቡት ወይንም ላታዩት ትችላላችሁ በሚል እምነት ነዉ ዋጋ እንድትከፍሉበት የተደረገዉ:: ዋጋ ከከፈላችሁበት ግን ቢያንስ ትንሽም ብትሆን የራሳችሁን ገንዘብ አዉጥታችሁበታልና ምንድነዉ? ብላችሁ መጽሐፉን ማንበባችሁ አይቀርም:: አንብባችሁት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዉጭ ከሆነ ደግሞ ማቃጠል ትችላላችሁ» በማለት ስናገራቸዉ፤ «ለማንኛም» በማለት ሁለቱ ሰዎች መጽሐፉን ሊወስዱ ችለዋል:: አንድ አባት ደግሞ የኢትዮጵያን ትንሣኤ የሚጠባበቁ ነበሩና የመጽሐፉን ርእስና አረንጋዴ ቢጫ ቀይ መደብ መሆኑን ብቻ በመመልከት መጽሐፉን ቢፈልጉም፤ መጽሐፉን ለሚያዞሩት ወንድሞች «ገንዘብ እንደጎደላቸዉና ባነሰ ዋጋ እንዲሸጡላቸዉ» ሲጠይቋቸዉ፤ እኔ በአቅራቢያዉ ነበርኩና እኔን አገናኟቸዉ:: እኔንም ሲጠይቁኝ ጉዳዩ የገንዘብ እንዳልሆነና እስከዚያ ድረስ እሳቸዉ ብቻ መጽሐፉን በፍላጎት ለመዉሰድ እንደቻሉ ገልጬላቸዉ፤ ለእሳቸዉም ሆነ ለሌሎች የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለሚጠባበቁ ይሆን ዘንድ ስድስት መጽሐፍ በነጻ ሰጥቻቸዋለሁ::

ከበዓሉ በኋላ እመቤታችንን፤ «እንግዲህ ከአንቺ በላይ ለአዳምና ለሔዋን ዘሮች የሚያስብና የሚቆረቆር የለም:: ይኸዉ በቤትሽ መጥቼ ከሦስት ሰዉ በስተቀር መጽሐፉን የፈለገና የወሰደ የለም» በማለት የተሰማኝን ቅሬታ ገልጬ፤ ምናልባት በመጽሐፍ አከፋፋዮች ዘንድ ከታተመበት ዋጋ በታች ቀንሼ ከወሰዱ በማለት ወደ መጽሐፍ አከፋፋይ ሄድኩኝ:: እነሱም «መንፈሳዊ መጽሐፍ አናከፋፍልም» አሉኝ:: ከዚያም ወደ መንፈሳዊ መጽሐፍ አከፋፋይ ሄድኩ፤ እነሱም «ማንነቱ የማይታወቅ ሰዉ የጻፈዉን አናከፋፍልም» አሉኝ:: አንዱ ብቻ «ላንበዉና ከዛ በኋላ አከፋፍላለዉ» አለኝ:: እኔም አንድ መጽሐፍ ሰጠሁት:: ካነበበም በኋላ «የመጽሐፉ ይዘት ጥሩ ቢሆንም ሰዎች የሚገሰጹበትና ኃጢአታቸዉ ሲገለጽ ደስ አይላቸዉም፤ ለማንኛዉም ዋጋ ስንት ነዉ ብሎ ጠየቀኝ?» እኔም እንኳን ትርፍ አይደለም የድካም ዋጋ እንዳልተጨመረበት ገልጬ በኪሳራ ከታተመበት ዋጋ በታች መዉሰድ እንደሚችል ተስማምተን ዋና አላማዬ ለአማኙ እንዲደርስ መሆኑን ገለጽኩለት:: እሱም «ሃምሳ ፍሬ ልዉሰድና ልሞክር» ብሎኝ እኔም ሃምሳ ፍሬ ሰጠሁት:: ከሳምንት በኋላ እንዴት

እንደሆነለት ጠየኩት:: እሱም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች እያዩት « ይህ ማን እንደጻፈዉ የማይታወቅ እኛ ማንነቱን ለማናዉቀዉ ለኪስ ማደለቢያ እንዲሆ እንጋዘም አሉኝ» በማለት መለሰልኝ:: እኔም ከዚያን ቀን ጀምሮ በመጽሐፉ ላይ ራሴ ፍርድ ሰጥቼ እንዲታሰር አደረኩት:: አሁንም በእስር ላይ ይገኛል:: በኢትዮጵያ ቀን ከእሰሩ ይፈታል:: አሁን ያቀለለዉና ያላገጠበት እንዲሁም ያጣጣለዉና የናቀዉ ትዉልድ ያኔ እንደሚፈልገዉ እገምታለሁ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ **(15/12/2004)** ዓ.ም ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ መልእክት ሲያስተላለፉ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መሞታቸዉን አልሰሙም ነበር ወይ? በዚያን ዕለት ነበር መሞታቸዉ በመገናኛ ብዙኃን የተገለጸዉና:: እንዲሁም በመልእክቱ ዉስጥ:

«ከሥጋዊ መሪ ከርእስ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) በባዕዳን አጠራር ደግሞ ከፕሬዘዳንት(ከጠቅላይ ሚኒስትር) እስከ ቀበሌ ተጠሪ(ተሿሚ) ድረስ እንዲሁም ከመንፈሳዊ መሪ ከርእሰ ሊቃነ ካህናት(እጨጌ) በባዕዳን አጠራር ደግሞ ከርእሰ ሊቃና ጳጳሳት (ፓትርያርክ) ጀምሮ እስከ ገጠር አብያተ ክርስቲያን ተጠሪ(ኃላፊ) ጭምር እግዚአብሔር ያዘጋጀ ስለሆነ፣ ከዲያብሎስ ሥርዓት መሪዎችና አራማጆች ጋር አንዳች አንድነትና ኅብረት መፍጠር የለብንም:: እነዚህ የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች በሕሊናቸዉ የነገሠዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ሌት ተቀን ለእርሱ ፈቃድ የተሰለፉ ናቸዉ እንጂ ለእግዚአብሔር እዉነት ቦታ የላቸዉም:: በእግዚአብሔር መልእክቶችና በእኔ የተለያዩ ደብዳቤዎች ዉስጥ እንደተገለጸዉ የባለጊዜነት ዘመናቸዉ በአራት ነጥብ የተደመደመበትና የሚቀራቸዉም የዘሩትን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የጥላቻና የበቀል ፣ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፣ የክፋትና የተንኮል ፍሬያቸዉም እንደ ኮሶ የሚመር ቢሆንም ጠጥተዉ ማለፍ ብቻ ነዉ:: እግዚአብሔር በዚህ ምድር ዉስጥ ጭምር ፍርዱ ምን ያህል ፍትሐዊና እጅግ ጥብቅ መሆኑን ያሳያቸዋል:: ስለዚህ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀዉ ራሳችንን ለእዉነተኛ ንስሐና እምነት ማብቃትና ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበት የኢትዮጵያዉያን ሥርዓትና የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንን መጠበቅ ነዉ::» ተብሎ ተገልጾ ነበርና::

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ **15/12/2004** ዓ.ም የተሰራጫዉ መልእክት የተጻፈዉ ነሐሴ አንድ ፳፻፬ **(1/12/2004)** ዓ.ም የእመቤታችን ፍልሰታ ጾም እንደተጀመረ ነዉ:: ታዲያ ወደፊ የሚሆነዉን ሁሉ የሚያዉቅ አምላክ፤ ነሐሴ ሦስት ፳፻፬ **(3/12/2004)** ዓ.ም መልእክቱን ለማስተላለፍ ተዘጋጅቼና ሙከራም አድርጌ የነበረዉን እንዳይሳካ አደረገዉ:: እኔም እግዚአብሔር አለመፍቀዱን አስተዉዬ ሱባዔ እስከሚያልቅ ድረስ አቆየሁት:: በዚህ መሃል እጨጌ አባ ጳዉሎስ መሞታቸዉ ተነገረ:: ሱባዔዉ እንዳለቀ ነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ **(15/12/2004)** ዓ.ም፤ ነሐሴ አንድ የተጻፈዉን በኢሜል ለማሰራጨት ከቤት ስወጣ ከጎረቤት የአቶ መለስ ዜናዊ መሞት ሰማዉኝ:: ምንም እንኳ መሞታቸዉን ባዉቅም እግዚአብሔር አስቀድሞ አሳስቦኝ ያጻፈኝን ማሻሻያ ሳላደርግ ነዉ እንዳለ ያሰራጨሁት::» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ምዕራፍ ሦስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በአሁን ሰዓት በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ የተለያዩ ባህሎች፣ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ የተለያየ አኗኗር ነዉ ያለዉና የሚታየዉ:: ታዲያ እነዚህን ወደ አንድነት ለማምጣት እንዴት ይቻላል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ ለማለት የምፈልገዉ በሰዉ የማይቻል በእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል:: ለመሆኑ የዓለም ሕዝብ የማን ፍጥረት ነዉ? የአንዱ አምላክና ፈጣሪ የእግዚአብሔር አይደለምን? ዘሩስ የአዳምና ሔዋን አይደለምን? ልጠበብ ቢል እንኳ ከኖኅ ልጆች ከካም፣ ከሴም፣ ከያፌት ሊያልፍ ይችላልን? ከእነሱስ የተወለዱት የወንድማማች ልጆች የሆኑ አንድ ቤተሰብ አይደሉምን? አንድ የነበረዉ የሰዉ ልጆች መግባቢያ ቋንቋ የተለያየዉ ሰዎች በዓመፃቸዉ፣ በክህደታቸዉ፣ በርኩሰት ሕይወታቸዉና ተግባራቸዉ ምክንያት የኃጢአት ዋጋ ሆኖ በባቢሎን ሰዎች ላይ የተከሰተ አይደለምን? ባህልስ በአኗኗር ሂደት ዉስጥ ሰዎች የፈጠሩት አይደለምን? ሃይማኖትስ ቢሆን አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የነበረ ፈጣሪ አንድ አምላክ አይደለምን? እግዚአብሔር በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) በአዳምና በሔዋን ሥራዓት ኃብቻ የመሰረተዉ፤ ከዚያም በኖኅ ቀስተ ደመና በመልከ ጸዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት ገንብቶ ያሳደገዉ፤ በመካከለኛዉ የሕግ ዘመን በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ የአብርሃምንና የመልከጸዴቅ ዘሮችን አዋሕዶ ከዚህ ምሉዕ ትዉልድ ከተገኘችዉ ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በሥጋ በመገለጽ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ያጸናዉና ምሉዕ ያደረገዉ ያ አንዱን ሃይማኖት አይደለምን? ታዲያ እኛ ልንቀበለዉና ልናምንበት የሚገባዉ ከአዳም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ተያይዞ የመጣዉን በግለሰቦች ያልተመሰረተዉን የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት መሆን አይገባምን?

ትዉልዱ እኮ እዉነታዉን የሚገልጽለት እዉነተኛ አገልጋይ አጣ እንጂ እንኳን ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሃይማኖት(እምነት) መቀበል አይደለም፤ ይኸዉ «አንተ የተፈጠርከዉ በእግዚአብሔር ሳይሆን በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ:: ስለዚህ ሕያዉ ፍጥረት ሳትሆን እንስሳ ነህ:: እንደ እንስሳ ትወለዳለህ፣ ታድጋለህ፣ ትሞታለህ፣ ሕይወትህ በዚህ ይደመደማል፤ እግዚአብሔር የሚባል የለም የገዥ መደቦች ለመጨቆኛ የፈጠሩት ማስፈራሪያ ነዉ:: ... ወዘተ» ሲባል አምኖ የተቀበለና በግልጽ «እግዚአብሔር የለም» ብሎ የዲያብሎስ እምነትና ሥርዓት የሆነዉን የሶሻሊስት ሥርዓት ያወጀና የተቀበለ ከዚያም የአብዮታዊ ዲሞክራሲና የካፒታሊስት እምነት የተቀበለና በግልጽ ዓመፃና ክህደት የፈጸመ ነዉ:: እንዲሁም በባህል ሽፋን በአደባባይና በየወንዛወንዙ ጣዖትና ባዕድ አምልኮ የሆነዉን ርኩሰት የፈጸመና ያስፈጸመ ነዉ:: ታዲያ በሥጋዉም በነፍሱም የሚጠቀምበትን ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሃይማኖትና ሥርዓት እንዴት አይቀበል!? እጅግ ይቀበላል:: ምክንያቱም ሕያዉ ነፍሳችን በግንባራችን ፊት ለፊት አንጎል ዉስጥ ያለችዉ በተለምዶ ሕሊና ወይንም አእምሮ በጥንት አጠራር ልቦና የምትባለዉ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረችዉና እግዚአብሔርን የመምሰል ብቃት ያላት ነፍሳችን ለዓይን ቅጽበት እንኳ ከእግዚአብሔር ህልዉናና ጠብቆት ስለማትለይ እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነች እግዚአብሔር

በእዉነት ስለሚያጸናት፤ ለእኛ አእምሮ የሚከብደዉን ትዉልዱ ሁሉ በአንድ እዉነት ዉስጥ ሊሰባሰብ ይችላል።

ይህች ነፍስ የእግዚአብሔርን እዉነት ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነች ግን እንኳን በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ እዉቀት ዉስጥ የሌሉት ቀርቶ ምሁር፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ ሳይንቲስት፣ ሊቃዉንት ተብለዉ እንኳ የእግዚአብሔርን ህልዉና በመካድ ማፈሪያና ያበደ አእምሮ እንዳላቸዉ በግልጽ «እኛ የተገኘነዉ ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉና እንስሳት ነን፤ ሞተን፣ በስብሰን፣ እንቀራለን እንጂ ሕያዋን አይደለን» በማለት ይኸዉ ባደባባይና በብዙኃን መገናኛ በግልጽ እስከ አሁን ድረስ ምስክርነትን በይፋ ሲሰጡ ተመልክተናል፤ አድምጠናል። ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነቶች ከሃዲያንና ዓማፅያን «የእግዚአብሔርን እዉነት አንቀበልም» ቢሉ ብዙም አንገረምም፤ አንደነቅም። ነገር ግን ዳግም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ይህን የክህደት ትምህርት እንዲሰጡ እድሉና ቦታዉ አይሰጣቸዉም። ነገር ግን ወደ ልባቸዉ ከተመለሱና በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ከሰጡና እዉነትን ከተቀበሉ ምሉዕ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። በተቀረ ግን በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሆነ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንደ ዳግም የክህደትና የዓመፃ ትምህርታቸዉ ቦታ አይኖረዉም። እዉቀቱም ሆነ ጥበቡ ሰዎች ከጉስቁልና ሕይወት የሚለዩበትና ለኑሮዋቸዉ የሚጠቅም እንዲሆን ይደረጋል እንጂ እግዚአብሔር የሚካድበትና ለሰዉ ዘሮች መጥፊያና ማጥፊያ የሚሆን መሳሪያ አይሰራበትም።

ከላይ እንደተገለጸዉ በኃጢአታችን ምክንያት የመጣዉን የቋንቋ መለያየት በጽድቅ ስራ ወደ አንድነት የሚያመጣን መንገድ እንፈጥራለን እንጂ እንደ ዲያብሎስ አገልጋዮች የቋንቋ ልዩነት በመፍጠር አንዱን ጎሳ በአንዱ ጎሳ፣ አንዱን ብሔር በአንዱ ብሔር ላይ አነሳስተዉ የራሳቸዉን መሰሪ ተግባርና በቀል እንደፈጸሙት የዓመፃና የጭከና ተግባር አይፈጸምም። ሕዝቡ እንደ እግዚአብሔር ፍጥረትነቱና ልጅነቱ እንዲሁም እንደ አዳም ዘርነቱና እንደ ኖኅ ልጆች ዉሕድነቱ እንዲኖር ይደረጋል እንጂ፤ በቀለም፣ በሃማኖት፣ በቋንቋ፣ በርዕዮተ ዓለም ልዩነት እንዲፈጠር ተደርጎ እርስ በእርስ ሕዝቡ እንዲጣላ፣ እንዲከፋፈል፣ እንዲለያይ አይደረግም። ጥላቻና በቀል አይዘራም፤ ዘረኝነትንና ጎጠኝነት አይስፋፋም፤ ክፋትና ተንኮል እንዲሁም ዓመፃና ክህደት አይነግሥም፤ ርኩሰትም አይፈጸምም። ባጠቃለይ ሕዝቡ ሕሊናዉ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዲመራና እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ በምድራዊ ሕይወቱ ዘመንም ተባርኮና በበረከት ተትረፍርፎ በነፍሱም በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ ሆኖ የሚኖርበት ብርሃናዊ ሥርዓት ነዉ የሚፈጠረዉ።

ባህልን በተመለከተ የእግዚአብሔርን እዉነት የሚቃረንና የዲያብሎስ ፍሬ የሆኑት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንድ እንዲታዩ እድሉ አይሰጣቸዉም። ለምሳሌ በእግዚአብሔር የለሽ ሥርዓትና እንዲሁም ከንቱ በሆነ ሥጋዊ መጠበብ በተመላለሱ ገዢዎች ዘመን ትዉልዱ እንደ ትክክለኛ ተግባርና ጥበብ እንዲታይ የተደረገዉ በየጥንቆላ፣ በየሚርቱ፣ በየርኩሰት ቦታ ለሰይጣናት የሚቀርበዉ ማጓራት፣ መጮህ፣ መንቀጥቀጥ፣ መዝለል፣ መራቆት፣ መዳራት፣ መንዘፍዘፍ፣ ባጠቃላይ ከሰዉነት ባሕርይ አዉጥቶ ወደ አጋንትነት የሚለወጥበትና የዲያብሎስ ምሱ(ግብሩ) የሚቀርብበት አሁን በዘመናዊ መልክ እየተቀነባበረ ትዉልዱ ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ ነፍሱ

እንድታብድ ያስደረገዉ ዳንኪራና ዘፈን በእግዚአብሔር ምስጋናና ሽብሸባ እንዲሁም ስለ እዉነትና ስለ አገር፣ ስለ ክበረ በዓል የሚዘመርበት ሆኖ እንዲተካ ይደረጋል። እንዲሁም ሌሎች ለሥጋዊ ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን አንዳች ጥቅም የሌላቸዉና ከባዕድ አምልኮ ጋር የተያያዙ ባህሎችና ልማዶች ካሉ ወደሚጠቅሙ ሥጋዊና መንፈሳዊ ባህሎችና ልማድ እንዲለወጡ ይደረጋል እንጂ እግዚአብሔርን የማያምኑና የማያመልኩ የአሕዛብና የአረማዉያን ባህል(ልማድ) የሚጸናበትና የሚስፋፋበት መንገድ አይኖርም።

ባህላዊ እምነትና ባዕድ አምልኮ በተመለከተ በዚሁ ተግባራቸዉ የጸኑትና ዋና ተዋናይ የሆኑት በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከምድር እንደሚጸዱ ይገመታል። ምናልባት የተወሰነ ቅንነት ተገኝቶባቸዉ የሚተርፉ ካሉ ደግሞ ለእዉነተኛ ንስሐ እንዲበቁ ይደረጋል። «በዓመፃችንና በርኩሰት ሕይወታችንና ተግባራችን እንጸናለን» የሚሉትን ደግሞ እንደ አሕዛብና አረማዉያን መሪዎች «ዲሞክራሲ መብታችሁ ነዉ፤ እንደፈለጋችሁ ሁኑ» በማለት ዲያብሎሳዊ ቋንቋ በመጠቀም በርኩሰት ተግባራቸዉ እንዲጸኑ አይደረግም፤ ወደ እዉነት የሚመጡበት መንገድ ይፈለጋል። በዚያዉ በርኩሰት እምነታቸዉና በዓመፃቸዉ ከጸኑ ግን ከሰይጣናት የሚለዩት ሥጋ በመልበሳቸዉ ነዉ እንጂ በተግባራቸዉ ስላልሆነ ሰይጣናትን በጸሎትና በጾም እንዲሁም በንስሐና በእዉነተኛ ሕይወት እንደምንቀጣቸዉና እንደምናቃጥላቸዉ ሁሉ፤ እነዚህ በሥጋ የተገለጹትን የዲያብሎስ አገልጋዮችን ወደ ዋናዉ መቀጫ ሲኦል በሥጋ ሞት እስከሚጠሩ ድረስ ነጻነታቸዉ ወደሚገደብበትና ስለ ርኩሰትና ዓመፃ ተግባራቸዉ ዋጋ ወደሚከፍሉበት እንዲሁም ወደልባቸዉ የሚመለሱ ከሆነ ለእዉነተኛ ንስሐ ወደሚበቁበት ቦታ ይገባሉ እንጂ ዳግም የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በጥንቆላ፣ በአስማት፣ በመተት፣ በሟርት፣ በጨሌ፣ በወንዛወንዝና በተራራ፣ በእንጨት አምልኮ ባጠቃላይ በባዕድና በጣዖት አምልኮ እንዲመላለሱ እድሉ አይሰጣቸዉም። በቅድስት አገራችን ኢትዮጵያና በእግዚአብሔር ሕዝቦች አገር ዳግም ርኩሰት በአደባባይ አይፈጸምም።

ጠያቂዉ አገልጋይ፣ ከላይ በግልጽ ያቀረቡትን ትዉልዱ የሚቀበለዉ ይመስሎታል ወይ? ምክንያቱም እንደ ሰዉ ሰዉኛ ካየነዉ እንኳን በባዶ እጅ ቀርቶ ታላላቅ የተባሉ ኃያላን መንግሥታት ሆኑ «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» የሚሉት በተለያየ መሳሪያና ደኅንነት ድርጅት የተደራጁት እንኳ የራሳቸዉን ዓለማ እንደሚፈልጉት ማሳካት አልተቻላቸዉም። ታዲያ እንዴት አድርጋችሁ ነዉ የእግዚአብሔርን ዓላማ ተግባራዊ የምታደርጉት? ትዉልዱ ነጋ ጠባ በዘፈንና በዳንኪራ ሕይወት ነዉ ያለዉ። ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ በዘረጋዉ ሥርዓት «እንደፈለጋችሁ የፈለጋችሁትን እምነት ማራመድ ትችላላችሁ፤ ከፈለጋችሁ በዛፉ ሆነ በሰይጣን ማምለክ ትችላላችሁ፤ የፈለጋችሁትን ባዕድ አምልኮ መፈጸም ትችላላችሁ፤ በፈለጋችሁት ሕይወት በግብረሰዶም ጭምር መኖር ትችላላችሁ፤ ይህ ሁሉ ዲሞክራሲ መብታችሁ ነዉ» በማለት አዉጀዋል። ታዲያ በዚህ ፖለቲካ ሕሊናዉ የተበከለና የተመረዘ ትዉልድ እንዴት የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ይቀበላል?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡ አሁንም በድጋሚ የምለዉ «ለእግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም» የሚለዉን እዉነት ለሚያምን ሰዉ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር እግዚአብሔር

በፈቀደዉ መንገድ ያደርገዋል፤ ይፈጽመዋል:: እኛ ለአግልግሎት ወደ ወንበር የምንወጣዉ በመሳሪያ ኃይል ወይንም በሰዉ ድጋፍ ወይንም በብልጣብልጥነት ወይንም በመፈንቅለ መንግሥት ወይንም በጦርነት .. ወዘተ በመሳሰሉት መንገድ ሳይሆን እግዚአብሔር እርሱ በፈቀደዉ መንገድ ነዉ:: ስለዚህ እኛ ግለሰቦችን ወይንም ቡድኖችን ወይንም ድርጅቶችን ለማስደሰትና የእነሱን ፈቃድ ለመፈጸም አይደለም እግዚአብሔር በባዶ እጃችንን ወደ ወንበር የሚያመጣን:: **ነፍስ ከሥጋችን ተለይታ ወደ እርሱ እስከምንሄድ ድረስ የእርሱን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ የተጠራነዉ::** በመሆኑም እርሱ የሚያሳስበንና የሚያሰራንን ብቻ ነዉ እንጂ የራሳችንን የሥጋና ደም ስሜት ወይንም የሌሎችን የሥጋና ደም ስሜት አይደለም የምንፈጽመዉና የምናስፈጽመዉ:: በዓለም የሚታየዉ ግን መንግሥታት በበላይ መሪያቸዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ እርሱ የሚያሳስባቸዉንና የራሳቸዉን ሥጋና ደም ስሜት እንዲሁም የግለሰቦችንና የቡድኖችን፣ የድርጅቶችን ዓለማ ነዉ የሚያስፈጽሙት:: የሚያፈሩትም ፍሬ በግልጽ የዓመፃ፣ የክህደት፣ ርኩሰት ፍሬ ነዉ:: መጨረሻቸዉም ነፍሳቸዉ ከቅርፊት ሥጋቸዉ በተለያየ መንገድ ተለይታ ለሕያዉነት ዘመን እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ወደሚቀጡበት ሲኦልና በኋላም ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ነዉ ከነግብረአበሮቻቸዉ የሚገቡት::

እኛ ደግሞ ተስፋችን ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ስለሆነ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖረን እድሜ አንጻር ይህ ምድራዊ ዘመናችን የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ የማይሞላ ስለሆነ፤ በዚህች አጭር ዘመን ዉስጥ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትንና ለሰማያዊ ሕያዉ መንግሥት የሚያበቃንን ሕይወት በመያዝ መልካም ፍሬ ለማፍራት ነዉ ሌት ተቀን የምንተጋዉ  እንጂ ዲያብሎስ ደስ የሚሰኝበትንና የሚፈልገዉን ፍሬ አናፈራም፤ አናስፈራም:: የእኛ ኃይል እንደ ሥጋዉያኑ የጦር መሳሪያ ወይንም የሰዉ ድጋፍ ሳይሆን፤ ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ የሆነ፣ የፈለገዉን በፈለገዉ ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ ማድረግ የሚችል፣ ከፈለገ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ የሚታየዉንም የማይታየዉንም ከመኖር ወደ አለመኖር በሚያሳልፍ፣ ከፈለገም አሁን ከሚታየዉ በእልፍ አእላፋት ወትእልፊት እጥፍ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት በሚችለዉ ኃያሉ ገናና አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ:: ስለዚህ ይህ አምላክ የዓመፃ ልጆችን ከፈለገ በቅጽበት ዉስጥ አይቀጡ አቀጣጥ ቀጧቸዉ፣ እንደ አቧራ አብኗቸዉ፣ እንደ እንፋሎት አትኗቸዉ ከዚህ ምድር ሊያጸዳቸዉ ይችላል:: የንስሐ ልብ ያላቸዉን ደግሞ ለእዉነተኛ ንስሐና ለሙሉ እዉነታ አብቅቷቸዉ ለፈቃዱ እንዲሰለፉ ሊያደርግ ይችላል:: በመሆኑም ከእኛ የሚጠበቀዉ ፈቃዱን ለመፈጸምና ለማስፈጸም መዘጋጀት እንጂ ሌላዉ የእርሱ ስራና ድርሻ ነዉ::

ስለዘፈኑና ዳንኪራዉ ደግሞ ትዉልዱ እንደ ትክክለኛ ተግባርና እንደ ጥበብ እንዲቆጥረዉ በመንግሥታቱ ስለተደረገና ብዙኃን መገናኛም (ማስ ሚዲያ) በእነሱ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነና ለፈቃዳቸዉ ማስፈጸሚያ ስላዋሉት ነዉ እንጂ፤ የዲያብሎስ ፍሬ መሆኑን ቢነገራቸዉ ወዲያዉ ነዉ አቁመዉ አምላካቸዉን በበለጠ ሁኔታ ለማምለክና ለማመስገን እንዲሁም ስለተለያዩ እዉነታዎችና ስለ አገር  ለመዘመር የሚተጉት:: ምክንያቱን በዚህ ሕይወት ዉስጥ ያሉትን አንዳንድ ሰዎች ብንመለከት እንኳን ባለ ብዙ ሀብት ባለቤት አይደለም መንፈሳዉያን የተባሉ ባለ ብዙ ሀብትና ንብረት ባለቤት የሆኑ ሰዎች ያልፈጸሙን ትልልቅ የእርዳታ ተግባር ፈጽመዋል:: በመቶ ሺህ ቤትባ በሚሊዮን

የሚቆጥር ገንዘብ አዉጥተዉ «ይህ ዘሬ ነዉ፣ ጎጤ ነዉ፣ ዘመዴ ነዉ፣ ቤተሰቤ ነዉ... ወዘተ » በማለት ልዩነት ሳያደርጉ «ይህ ኢትዮጵያዊ ወገኔ ነዉ፣ ገንዘብ እንዳይሞት የሚያደርገዉ ከሆነ እኔ እከፍላለሁ፤ እነዚህ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ወገኔ ናቸዉ እርዳታ ሊደረግላቸዉ ይገባል» በማለት ስግብግብነትና ስስት ሳያጠቃቸዉ ወገናቸዉን ሲረዱና ሲታደጉ ተመልክተናል፤ ሰምተናል:: እንዲሁም ለችግረኛ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻቸዉ ጊዜያቸዉንና ገንዘባቸዉን በመሰዋት እርዳታና አገልግሎት የሚሰጡ ዘፋኞችና ዳንኪርተኞች አሉ::

በተቃራኒ ደግሞ ብዙዎች ሀብትና ንብረት ያላቸዉ የስም አማኞች ስግብግብነትና ስስት ተሞልተዉ እንኳን ወገናቸዉን ሊረዱ ቀርቶ ያላቸዉ ሀብትና ንብረት አላረካ እያላቸዉ የምስኪኑን ሐቅ የሚከለክሉ፣ ደሀዉን የሚያስጨንቁና የሚበዘብዙ አሉ:: እንዲሁም ብዙዎች ሰዎች በተለያየ የሃይማኖት ኃላፊነት ተቀምጠዉ፣ መስቀልንና ወንጌልን ይዘዉ፣ የእምነት ተቋማትንና የቤተክርስቲያንን ገንዘብና ሀብት የሚዘርፉ ሌባ፣ ቀማኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ወንበዴ፣ ዘማዊ፣ ሴሰኛ ሰዎች አሉ:: ይህም የሚያሳየን ባለማወቅ በተለያየ ኃጢአትና ዓመፃ ተግባር ላይ የተሰማሩ አንዳንድ ሰዎች የሕይወትን መንገድና ምስጢር ቢያስተዉሉ ከማንም በላይ የጽድቅ ስራ ብቻ አይደለም የትሩፋት ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ ነዉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ የሕይወትን መንገድ ማወቅ ብቻ አይደለም በተለያየ ኃላፊነት ላይ ተቀምጠዉ በእዉነትና በታማኝነት ማገልገል ተስኗቸዉ የተለያዩ አካላትንንና ግለሰቦችን ያሰናከሉ አስመሳይ አገልጋዮች እንዳሉ ነዉ::

ሌላዉ የራሴን የቀደመ አመለካከቴን ብገልጽላችሁ፤ በመዋዕለ ዜናዬ እንደገለጽኩላችሁ እኔም በዘፈኑና በዳንኪራዉ ሕይወት አሳልፌያለሁ:: እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ እያለሁም ዘመናዊዉን ዘፈንና ዳንኪራ ብቻ በመቃወም የሀገር ባህል ዘፈንና ጭፈራ ሕሊናዬን በራሴ በማሳመን እቀበለዉ ነበር:: ይሁንና ለተለየ አገልግሎት እግዚአብሔር ሲጠራኝ ነፍሳት በዘፈንና በዳንኪራ ከሕፃናት እስከ አዋቂ ድረስ ያሉት እያበዱ መሆናቸዉን ስለገለጸልኝና በእነሱ የሚዝናኑትም ባበደች ነፍስ እየተዝናኑ መሆኑን እንዳስተዉል ስላደረገኝ፤ የራሴን የዉሸት እዉነት ትቼ ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት በመምጣት ስለሚያሳብዱት ሆነ ስለሚያብዱት ነፍሳትም ማዘን ጀምሬያለሁ:: አሁን ዳንኪራዉንና ዘፈኑን በቴሌቭዥን ስመለከት ከመዝናናት ይልቅ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍስ በዉሸት እዉነት ተታላ በምን መልኩ እያበደች እንደሆነና ሰብአዊ ባሕርያዋን እንዴት አድርጋ ወደ ሌላ ባሕርይ እየለወጠች መሆኑን ነዉ በትዝብትና በኀዘን የምመለከተዉ::

መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎች በዲያብሎስ ዲሞክራሲ ፍልስፍና ትዉልዱ የፈለገዉን እንዲፈጽም የፈቀዱሉት ሕሊናዉን ለማደንዘዝና የራሳቸዉን መሰሪ ዓላማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንጂ፤ ለሥልጣናቸዉ አስጊና ተቀናቃኝ ከሆነ እንኳን እነዚህን ቀርቶ መብላትና መጠጣት እንዲሁም መናገርና መጻፍ እንደሚከለክሉና እንደ አስፈላጊነቱም በእስርና በግድያ እንደሚበቀሉ ዓለም ያዉቀዋል:: ይህም ለሥልጣናቸዉ አስጊ ያልሆነዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም ፈቃደኞች መሆናቸዉንና ለሥልጣናቸዉ ስጋት የሚፈጥርባቸዉን ማንኛዉንም የቅድስናና የእዉነት ተግባር ግን የሚቃወሙ፣ የሚያግዱ፣ ሲፈልጉም «ሁከትን ሽብር ፈጣሪ» የሚል

ስያሜ በመስጠት የተንኮልና የበቀል ተግባር ላይ እንደሚሰማሩና ለማስመሰልና ለመሸንገል ብቻ ተግባራዊ የማያደርጉትን በወረቀት ላይ የተለያዩ ነጻነቶችን እንደሚያሰፍሩ ትዉልዱ ስለሚያዉቅ ለመሰሪነታቸዉና አስመሳይነታቸዉ ብዙ ምስክር መስጠት አይስፈልግም፡፡

ባጠቃላይ ከእግዚአብሔር የሆኑ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይሰለፋሉ፤ ከዲያብሎስ የሆኑና እንዲሁም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ለመቀበል ሊቸገሩ ይችላል፡፡ እኛ ግን ለተጠራንበት ዓለማ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብን ሳናደርግ «እንደ እባብ ልባም፣ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ» ተብሏልና በቅንነት፣ በእዉነት፣ በትዕግስት፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በጽናት፣ በቆራጥነት፣ በመልካም ተግባርና ሕይወት ዉስጥ ሆነን የእግዚብሔርን ፈቃድ በአራቱም ማእዘን እንፈጽማለን እናስፈጽማለን እንጂ፤ በሰዉ ለመወደድ ወይንም ድጋፍ ለማግኘት ስንል እግዚአብሔር የማይፈቅደዉን ተግባር አንፈጽምም፤ አናስፈጽምም፡፡ በእርሱ ቁጥጥርና መሪነት ዉስጥ ሆነን ነዉ ለተልኮ የምንሰለፈዉ እንጂ ለራሳችን ቅርፊት ሥጋ ሆነ ለግለሰቦች ቅርፊት ሥጋ የሚመች የዓመፃ ስራ አንፈጽምም፣ አናስፈጽምም፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፣ በግልጽ እንደነገሩን በዳንኪራና ዘፈን ሕይወት ዉስጥ ማሳለፊዎችን ገልጸዉልናል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ከመጀመሮ በፊት ሆነ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ ከገቡ በኋላ እንዲሁም ከመስከረም ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ከእግዚአብሔር ልዩ ጥሪ በኋላ ምክንያቱም መመልከትና መስማት ባይፈልጉ እንኳ ቴሌቪዥን ማየቶት፣ ሬድዮን መስማቶት አይቀርምና፤ ይመለከቱትና ያዳምጡት የነበረዉ ዘፈንና ዳንኪራ ምን ዓይነት እንደነበረና ለሕሊናዎ የተለየ ስሜት ይሰጦት የነበረዉ ዘፈን ምን ዓይነት እንደነበረ ቢገልጹልን?

<u>***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***</u>: ለአጭር ጊዜ ቢሆንም በተለያየ ሕይወትና የኃጢአት ተግባር ዉስጥ መመላለሴ እዉነትን የበለጠ እንድፈልጋትና ሐሰትን ደግሞ በከፋ መልኩ እንድጠላት አስችሎኛል፡፡ ምክንያቱም በተለያየ ሕይወት ዉስጥ ባላሳልፍ ኖሮ ኃጢአቱ ሊናፍቀኝ፣ ነዉሩን እንደ ክብር ዉርደቱን እንደ ታላቅነት ልመለከተዉ እችል ነበርና፡፡ ለዘፈኑ ድምፅ የለኝም እንጂ መዝፈኔ አይቀርም ነበር፡፡ ለዳንኪራዉና ለጭፈራዉ ግን ከልጅነቴ ጀምሮ በራሴ በምለማመደዉ ጥረት እንደ ዳንኪርተኞቹና ጨፋሪዎቹ ባልሆንም ከአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ያሉትን የተለያዩ ዳንኪራኒ ጭፈራዎችን እችል ነበር፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ከጀመሪኩ በኋላ ደግሞ ዘመናዊ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን በመተዉ በራሴ የዉሸት እዉነት ባህላዊ ዘፈኖችንና ጭፈራዎችን እቀበላቸዉ ነበር፡፡ ከ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ጀምሮ ዘመናዊ ሆነ ባህላዊ ዘፈኖች ሆኑ ዳንኪራዎች የጨለማዉ ገዥ ምሱ(ግብሩ) መሆናቸዉን እንዳዉቅና እንዳስተዉለዉ ስለተደረገ ሁሉንም መተዉ ችያለሁ፡፡

ከድሮ ጀምሮ ዘፈን ስሰማ ምን እንደሚሉ ጆሮዬ አስተዉሎ አይሰማዉም ነበር፡፡ ጆሮዬ ይሰማ የነበረዉ ዜማዉን ብቻ ነበር፡፡ የድምጻቸዉ ቅላጼ አሳዛኝና እንደ ትዝታ ዓይነት ከሆነ ይስበኝ ነበር፡፡ ብቃት ኖሮት ሊያስለቅሰኝ የሚችል የሚያሳዝን ቅላጼ ቢኖር ከሁሉ በበለጠ ለማዳመጥ እመርጠዉ ነበር፡፡ በአሁን አእምሮዬ ስገመግመዉ ከድሮ ጀምሮ ነፍሴ የራሷ መኖሪያ ምድር ዉስጥ እንዳልነበረች

ታዉቅ ነበር ማለት ነዉ:: ምክንያቱም ብዙ ሰዉ ዘፈንን የሚፈልገዉ ሊዝናናበትና ሊደሰትበት እንጂ ሊያዝንበት አይደለምና:: እኔ ግን የሚያሳዝነኝ ዘፈን ነበር ለመስማት ጆሮዬ ክፍት የነበረዉ:: ከዚያ ዉጭ ደግሞ ስለ አገር የሚዘፈነዉ እንጉርጉሮ፣ ሽለላ ጆሮዬ በደንብ ተከፍቶ ይሰማቸዋል:: አሁንም ጭምር ዘረኝነት፣ ጎጠኝነት፣ መከፋፈል በሌለበት በአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ስር ስለ አገርና ስለ ሕዝቧ፣ ስለ መልካም ምድሯ፣ ስለተለያዩ ተፈጥሮዎቿ፣ ስለተለያዩ ቅርሶቿ ሲዘፈን ጆሮዬ ተከፍቶ ይሰማል::

እዚህ ላይ ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ በፊት ዘፈን ስሰማ ከቅላጼዉ ድምጽ ዉጭ በዘፈን ዉስጥ የሚባለዉ ነገር ጆሮዬ ተከፍቶ አይሰማዉም፣ ልብ አይለዉም ነበር:: አሁን ግን ጆሮዬ በደንብ ተከፍቶ የሚሰማዉ ሲሆን፤ በዉስጡም ያ ቅርፊት ሥጋ ልባሽና ያቺ ቅርፊት ሥጋ ለባሽ ሲመለኩ፣ ሲመሰገኑ፣ ሲገኑ፣ ሲደነቁ ነዉ የሚሰማዉ:: ታዲያ የሚታየዉ ዳንኪራና መራቆት ብቻ አይደለም መልእክቱ ጭምር ፍጹም የዲያብሎስ ፍሬና ዉጤት መሆኑን በሚገባ ያሳዉቀናል::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ለጆሮ ይስቦት የነበረ የዘፋኞች ቅላጼ ድምፅ እንደምሳሌ ሊገልጹልን የሚችሉት ካለ ቢገልጹልን?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: በእኔ በኩል ለጆሮዬ ይስቡኝ የነበረ አሳዛኝ የድምፅ ቅላጼዎች የነበሩት እንደምሳሌ የሁለት ዘፋኞችን እገልጻለሁ:: እነዚህም ሙሉቀን መለሰና አብተዉ ከበደ ናቸዉ:: እነዚህና ሌሎችም ዘፋኞች ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት መተዉ አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እያመለኩ በቅዱስ ያሬድ ዜማ እንደ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት ዝማሬ ቢያቀርቡ ጸሎቴና ምኞቴ ነዉ::

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>*** የፓለቲካ አመለካከትዎ እንዴት እንደነበረ፣ በየትኛዉ ፓለቲካ ድርጅት ታቅፈዉ እንደነበረ፣ የማን ፓለቲካ ይደግፉና ይቃወሙ እንደነበር ቢገልጹልን?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: ስለ ፓለቲካ መማርና ማወቅ ከጀመርኩ ጀምሮ ስለ ፓለቲካ ጥሩ አመለካከት አልነበረኝም:: ምክንያቱም በፓለቲካ ዉስጥ ስለ ጥላቻና ስለበቀል እንዲሁም ስለ ክህደትና ዓመፃ እንደ መልካም ነገር ተቆጥሮ ስለሚሰበክና፤ በተቃራኒ ደግሞ ስለ ፍቅርና አንድነት እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና መፍራት መሰበከ ይቅርና የእግዚአብሔርን ህልዉና የሚያስክድ ስለነበረ ነዉ:: ጆሮ ሰጥቼ የተከታተልኩት ደግሞ በምርጫ 97 ነበር:: ከምርጫ በኋላ በተፈጠረዉ የተለያየ ክስተትና እርስ በእርስ መጣላት እንዲሁም መጠላለፍ ፓለቲካን የበለጠ እንድጠላዉ አድርጎኛል:: እንኳን የፓለቲካ አባል ልሆን ቀርቶ የሙያ ማኅበርና መንፈሳዊ ማኅበር አባል አይደለሁም:: ምክንያቱም የአንድ ፓለቲካ ሆነ ማኅበር አባል ከሆንኩ የሕሊና ነጻነቴ ይገፋል የሚል እምነት ስላለኝ ነዉ:: ይኸዉም የአንድ ድርጅት ሆነ ማኅበር አባል ሆንኩ ማለት የድርጅቱን አቋም ባምንበትም ባላምንበትም እንደ አመንኩ አደርጌ አቋሙን ማራመድ አለብኝና፤ እንዲሁም ሕሊናዬ የማይቀበለዉ ዉሳኔ ከተሰጠም ሕሊናዬን አሳምኜ መደገፍ አለብኝ:: ያ ካልሆነ ደግሞ ለሕሊናዬ ስል ከፓለቲካዉ ሆነ ከተለያየ ማኅበር ማግለል አለብኝ::

እስከ አሁን ድረስ በራሴ እምነት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የቆመና የእርሱን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተሰለፈ ድርጅት ሆነ ማኅበር አለ ብዬ ስላላመንኩ የማንም የፓለቲካ ሆነ ማኅበር አባል አይደለሁም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆኑትን ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ እግዚአብሔርን ማምለክና ማፍቀር፣ እዉነተኛ የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት እንዲሁም ስለ አንዲት እዉነተኛ ሰንደቅ ዓለማ ... ወዘተ የሚሰብክ፣ ስለ እዉነት የሚቆረቆር፣ ስለ እዉነትኛ እኩልነትና ነጻነት እንዲሁም ሰብአዊ መብትና ክብር ... ወዘተ የሚቆም ድርጅትን ሆነ ማኅበርን እደግፋለሁ:: ግፍና ጭካኝ፣ አድሎና በደል የሚፈጽም፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን፣ መከፋፈልንና ልዩነትን የሚሰብክ፣ ክፋትና ተንኮል፣ ጥላቻንና በቀልን የሚዘራ፣ ጣዖትና ባዕድ አምለኮን ርኩሰትን የሚያስፋፋ፣ በትዕቢትና እብሪት ሕይወት የሚመላለስ፣ በተናገረዉ ቃል ሆኖ የማይገኝ አስመሳይን፣ ባጠቃላይ ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን የሚፈጽምን የሚያስፈጽምን እቃወማለሁ:: ድጋፌን ሆነ ተቃዉሞዬን እገልጽ የነበረዉና እየገለጽኩ ያለሁት በዉስጤ ነዉ:: መልካም ለሚያስቡትና ለሚሰሩት እንዲሁም ስለ እዉነት ለሚመሰክሩትን ስለሚሟገቱት እግዚአብሔር እንዲረዳቸዉና አሸናፊነት እንዲጎናጸፉ፤ በተቃራኒ ደግሞ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት እየፈጸሙ ላሉት ልቦና እንዲሰጣቸዉና ለእዉነተኛ ሕይወትና አገልግሎት እንዲያሰልፈቸዉ፤ የንስሐ ልብ የሌላቸዉን ደንዳናዎችን ደግሞ ከባለ ጊዜነት እንዲሽራቸዉና የክፋት፣ የተንኮል፣ የቂም በቀል፣ የትዕቢት፣ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የሐሰት ንግግራቸዉንና ተግባራቸዉን እንዲያስወግድና እዉነትን ብቻ እንዲያነግሥ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ነዉ::

__ጠያቂዉ አገልጋይ:__ ሌላዉ መጠየቅ የምፈልገዉ የትምህርት ደረጃዎንና የተሰማሩበት የስራ መስክ፣ ለእዚህ መንፈሳዊ እዉቀት ያደረሶትን መምህራን ቢገልጹልን? እንዲሁም ለወደፊት ምን እንደሚሆኑ ከእግዚአብሔር በግልጽ ተነግሮታልና ሥልጣኖትንና የስራ ድርሻዎ ምን እንደሚሆን ከወዲሁ ቢያሳዉቁን? ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ፣ በእምነት ከማምለክ በተጨማሪ እንዴት በተጨባጭ ከማግኘት ባልተናነሰ መልኩ ሊያገኙትና ለመልእክት አስተላላፊነት ሊመረጡ ቻሉ? የወደፊት ዓላማዎትንና ራእዮን ቢገልጹልን? ከዚህ በተጨማሪ ፓለቲካዊ እዉቀት አሎት ወይ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: በእርግጥ ለእግዚብሔር አገልግሎትና መልእክት አስተላላፊነት የሚያበቃ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ እዉቀት የሌለኝ ሲሆን፤ ለጊዜዉ ሥጋዊ እዉቀቴንና የስራ ድርሻዬን መግለጽ ልተወዉና ስለ መንፈሳዊ እዉቀቴ ልግለጽ:: ገና የሰባትን የስምንት ዓመት እድሜ ላይ ሆኜ ከተማርኩት ዉዳሴ ማርያም፣ መልክዐ ማርያምና መልክዐ ኢየሱስ ዉጭ አንዳች ትምህርት የሌለኝና እነሱም ቢሆን ከአስራ አንድና አስራ ሁለት እድሜዬ በኋላ መድገም(መጸለይ) ስላቆምኩ ተረስተዉኝ አሁን በመጽሐፍ ብቻ የምጸልይ ነኝ:: በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ የሌለሁ አንድ ተራ ምእመን ነኝ:: ስለዚህ ለዚህ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና መልእክተኛነት ያበቃኝ ወይንም ያደረሰኝ መምህር የለኝም ማለት ነዉ:: የእኔ መምህሬ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ምስጢራትን ሆነ የተለያዩ እዉቀቶችን የገለጸልኝና ያሳወቀኝ እርሱ አንዱ እግዚአብሔር ነዉ::

ለወደፊት የሚኖረኝ ሥልጣን የሌለኝና የስራ ድርሻዬ የኢትዮጵያ(የምስራቅ አፍሪካ) የእግዚአብሔርን ሕዝቦች አገልጋይ ወይንም ባሪያ ወይንም አሽከር መሆን ነዉ። ያ የማይታየዉና የማይመረመረዉ እግዚአብሔርን ያገኘሁት ለማግኘት ፈልጌ ሳይሆን በፊትም ሆነ አሁንም እግዚአብሔርን በእምነት ብቻ እንዳዉቀዉ ነዉ የምፈልገዉ እንጂ በምልክትና በተአምራት እንዳዉቀዉ አልፈልግም። የእኔ ፍላጎትና ጸሎት እኔ ራሴን በአምላክ ፊት ዝቅ አደርጌና አዋርጄ በእዉነትና በመንፈስ አምልኬዉ በምሕረቱና በቸርነቱ ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ እንዲያበቃኝ ሲሆን፤ የእግዚአብሔር ሐሳብና የሰዉ ሐሳብ እንዲሁም የእግዚአብሔር ፈቃድና የሰዉ ፈቃድ የማይገናኝ ስለሆነ፤ እርሱ እግዚአብሔር ደግሞ ሳይገባኝ ምስጢራቱንና እዉነታዉን ገልጾልኝ ለመልእክት አስተላላፊነት መረጠኝ። ስለዚህ ከእኔ የሚጠበቀዉ «አድርግ» የሚለኝን ማድረግና «አታድርግ» የሚለኝን ደግሞ አለማድረግ ነዉ። ከዚያ ዉጭ በሥጋና ደም ስሜቱ ተመርቼ አንዳች ለራሴ ሆነ ለሰዉ ስል የማደርገዉ ነገር የለም። እንደ ማንኛዉ ሰዉ ተራና ኃጢአተኛ ሰዉ ነኝና ቤተሰቤን በአግባቡና በሥርዓቱ እያስተዳደርኩ የተጠራሁበትን የእግዚአብሔር አገልግሎት በቅንነትና በእዉነት እንዲሁም ራስን በመካድና ስለ እዉነት በመመስከር እርሱ ባለቤቱ ከዚህች ጎስቋላ ዓለም እስከሚለየኝ ድረስ በትዕግስትና በጽነት መኖር ነዉ የሚጠበቅብኝ።

የወደፊት ዓላማዬምና ራእዬ በምድራዊ ዘመኔ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ መፈጸምና ማስፈጸም፤ የተመለከት የተመለኩትን ሥልጣንና ክብር፣ የግል ብልጽግናና ዝና እንዲሁም ሌት ተቀን የምንተጋለትንና የምናስመልከዉን ቅርፊት ገላችንን ጭምር ከንቱ በማድረግ፤ ያ ሁሉን በአምላካዊ ሥልጣኑ ማድረግ ሲችል ራሱን ዝቅ አድርጎና አዋርዶ ለሰዉ ልጆች ፍቅሩን በመስቀል ላይ የገለጸዉን አልፋና ዖሜጋ የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ማስገነንና በእዉነትና በመንፈስ ማስመለክ፤ ትእዛዙና ሕጉ እንዲጠበቅ ማድረግ፤ እንዲሁም በሰማያት ከብራና ገና መኖር ስትችል ለአደራ ልጆቿ ለሰዉ ዘሮች ስትል ኀዘንተኛ መሆንን የመረጠች ሁል ጊዜ ለሰዉ ልጆች ጥብቅና የምትቆመዉን እመ አምላክ ድንግል ማርያምን እንደ አምላኳና ልጇ በአራቱም ማዕዘን ማስገነንና ማስመስገን ነዉ። እንዲሁም ለዘጠናዎቹ ነጥብ የሚያበቃ የጽድቅ ተግባር በመፈጸም ለማይልፈዉ ለሰማያዊ መንግሥት ራሴን ሆነ ሌላዉን ማብቃት ነዉ።

ፓለቲካ በተመለከተ ከሚባለዉና ከሚጻፈዉ ዉጭ ምንም የማዉቀዉ ነገር የለም። ምንም እንኳን እጅግ ጥቂቶች ፓለቲካን የሕዝብን ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትሐዊና መልካም አስተዳደር ለማምጣት የሚደራጁበት ቢሆንም፤ እስከ አሁን ድረስ ተሳክቶላቸዉ ወደ ወንበር አልመጡም ማለት ይቻላል። ምክንያቱም እጅግ ብዙዎቹ ፓለቲካ የሚለዉን በዉሸት እዉነት ስለተኩትና የራሳቸዉን የግልና ስዉር ዓላማ የሚፈጽሙበትና የሚያስፈጽሙበት፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ እየተመሩ እዉነተኛ ነጻነትን፣ እኩልነትን ፣ ፍትሐዊና መልካም አስተዳደር የሚያጠፉበትና የሚያስወግዱበት ነዉ። እንዲሁም የዲያብሎስን ፈቃድ በአራቱም ማእዘን የሚያስፈጽሙበት ዋና መሳሪያ ነዉ።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ታዲያ እርሶ ታላቅ፣ ምሁር፣ ሊቅ፣ ቅዱስ፣ ብፁዕ፣ እንዲሁም ፓለቲከኛ ካልሆኑ እንዴት ተራና ኃጢአተኛ ሰዉ ሆነዉ የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋይ ሊሆኑ ይችላሉ?

**<u>መላሽ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እንደ ሰዉ ሰዉኛ ቢሆን ራስን ካልካቡና ካላገነኑ እንዲሁም ራስን እንደ አዋቂና ቅዱስ አድርገዉ ካላቀረቡ በስተቀር ራስን ዝቅ በማድረግና በማዋረድ የተለያየ ወንበር ላይ መቀመጥ እንደማይቻል ካለፉት ዜና መዋዕልና ታሪኮች እንዲሁም በዚህች በአጭር እድሜያችን ተመልክተናል፡፡ በእግዚአብሔር አሰራርና መንግሥት ዉስጥ ራሱን የሚያመጻድቅና የሚያገን እንዲሁም ታላቅና አዋቂ አድርጎ የሚቀርብ ሰዉ ቦታ የለዉም፡፡ እግዚአብሔር የዉጭዉን ሳይሆን ለሰዉ የማይታወቀዉን የዉስጡን ነዉ የሚመለከተዉ፡፡ እግዚአብሔርን፣ ንግግር በማጣፈጥና በማስመሰል ማንም ፍጡር አያታልለዉም፡፡ ለማንኛዉም አገልግሎት የራሱን ሰዎች ሲያሰልፍ የሚመርጠዉና የሚያጨዉ በሰዉ ምርጫ ሳይሆን በራሱ መስፈርትና ምርጫ ነዉ፡፡ የእግዚአብሔር ምርጫና የሰዉ ምርጫ የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት እንዳለዉ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ሁሉ ያዉቃሉ፡፡ ምርጫችንን ባለማወቃችን ይኸዉ በግፈኞች፣ በጨካኞች፣ በዘረኞች፣ በጎጠኞች፣ በትዕቢተኞች፣ በተንኮለኞች፣ በሌቦች፣ ጥላቻና በቀል በሞላባቸዉ፣ እግዚአብሔር መፍራት አንዳች በሌላቸዉ ዓመፀኞችና ከሃዲያን ለዘመናት መከራችንና ፍዳችንን አይተናል፤ አሁንም እያየን ነዉ፡፡፡

እዚህ ላይ በግልጽ በድጋሜ ለመግለጽ የምፈልገዉ እንደ ምድራዊ ሥርዓት ለመምህርነት የሚያበቃ እዉቀት ሆነ ሌላ ተሰጥኦ ስለሌለኝ፤ አሁንም ሆነ ለወደፊት የእኔ የስራ ድርሻ ማንም ሰዉ የተማረዉም፣ ያልተማረዉም ሊያደርገዉ የሚችለዉ የምስክርነት ተግባር ብቻ ማከናወን ነዉ፡፡ ለመምህርነት ሆነ ለአስተማሪነት እዉቀቱና ለዚያ የሚሆን ተሰጥኦና ጸጋ ያላቸዉ ብዙ አገልጋዮች ስላሉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የእኔ ስራ ግን ከእግዚአብሔር የሆነዉን ምስክርነት መስጠት ብቻ ነዉ እንጂ የታሪክ ሆነ የምርምር እንዲሁም የሥጋዊ ሆነ የመንፈሳዊ ምሁርና ሊቅ አይደለሁም፡፡

ማን ያዉቃል! እግዚአብሔር በእዉቀታቸዉ፣ በሊቅነታቸዉ፣ በማንነታቸዉ ራሳቸዉን የሚያመጻድቁትንና የሚያስታብዩትን ለማሰፈር፤ ከምንም ምንም ዉስጥ የሌሉትን እያስነሳ ምስክርነትን ቢያሰጥ? ስንት አንደበተ ርቱዕ ተናጋሪ እያለ ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ቆራጥነት የተላበሰዉን ኮልታፋን ሙሴ አስነስቶ ለታላቅ ነብይነትና ለመሪነት የመረጠና ያስነሳ አምላክ፤ ስንት ምሁራን ታላላቅ የተባሉ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት እያሉ ምንም የማያዉቁትን ነገር ግን ቅንነትንና እዉነተኛነትን የተላበሱትን ሐዋርያት፤ ማንነታቸዉን ሳይመለከት ከአሳ አጥማጅነት የመረጠ አምላክ፤ ከትምህርት ትምህርት ከአገልግሎት አገልግሎት ዉስጥ የሌሉትን ሰማዕቱን ቅዱስ ጊዮርጊስን፣ ሰማዕቷን ቅድስት አርሴማን ያስነሳና ያስመሰከረ አምላክ፤ ማን ያዉቃል አሁንም ያልታሰቡና ያልተጠበቁ ቅንነትና እዉነተኛት እንዲሁም ትጋትና ቆራጥነት የተላበሱ ሰዎችን አስነስቶ በሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ቢያስቀምጥ!?

እግዚአብሔርን፤ «ምራን፣ ንገሥብን ፣ አስተዳድረን፣ መግበን፣ ግዛን» ማለት ሲገባን ፍጡሩን ሰዉ «ምራን፣ ንገሥብን ፣ አስተዳድረን፣ ግዛን» በማለታችን ይኸዉ ለዘመናት በዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚዎች በሥጋም በነፍስም ለመከራና ለስቃይ ሕይወት ተዳርገን በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ሞት በሆነዉ ሕይወት ዉስጥ ልንመላለስ ችለናል፡፡ «ምሩን፣ ንገሡብን፣ ግዙን፣ አስተዳድሩን፣ መግቡን» ያልናቸዉ ሰዎች ደግሞ ራሳቸዉንና መሰሎቻቸዉን ብቻ ለተንደላቀቀና ለተለየ ክብረትና ግነት ሕይወት አዘጋጅተዉ ሕዝቡን ግን ለረኃብ፣ ለስደት፣ ለችግር፣ ለእስር፣ ለሞት፣ ለበሽታ፣ ባጠቃላይ ለተለያዩ ጉስቁልናና መከራ ሕይወት ዳርገዉታል፡፡ ይህ የሚያሳየን ምርጫችን የሥጋና ደም ስሜት በመሆኑ አንዳች በሥጋችን ሆነ በነፍሳችን እንዳልተጠቀምን ነዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አራት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ወደ እግዚአብሔር አገልግሎትና ጥሪ ማለትም ከ፳፻፫ ዓ.ም (2003) ወዲህና ከዚያ በፊት ያሉት አቋምና አስተሳሰብ አንድ አይነት ነዉ ወይ? ወይስ ተለዉጧል?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: የማንኛዉም ሰዉ አስተሳሰብና አቋም በትምህርት፣ በእድሜ እድገት፣ በስራ፣ በማኅበራ ሕይወት፣ በልምድ፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ተጋድሎ፣ ባጠቃላይ በምድራዊ ሕይወቱ በሚከሰቱ ነገሮች አስተሳሰቡ እየበሰለ፣ ነገሮችን እያስተዋለና እየተረዳ ይሄዳል:: ቀድሞ እንደ ትክክል የሚቆጥራቸዉ ስህተት ሆነዉ ሊያገኛቸዉ ይችላል:: እንዲሁም እንደ ስህተት ሆነዉ ታይተዉት የነበሩት እንደ ትክክል ሆነዉ ሊያገኛቸዉ ይችላል:: ታዲያ እንደ ማስተዋሉና መረዳቱ አንድ ሰዉ ቀድሞ የነበረዉን አስተሳሰብና አቋም ለዉጦ ወደ ትክክለኛዉ እዉነታ ሲመጣ «ለምን የቀድሞ አቋሙንና አስተሳሰቡን ለወጠ?» ማለት የለብንም:: ነገር ግን ከመልካምነት ወደ መጥፎነት፣ ከእዉነተኛነት ወደ ሐሰተኛነት፣ ከቅንነት ወደ ጠማማነት ከተለወጠ፤ መሪዉ ያደረገዉ መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን ርኩስ መንፈስን ስለሆነ አቋሙንና አስተሳሰቡን እንዲያስተካክል ልናደርገዉና ልንመክረዉ ይገባል:: «እንቢ» ካለ ደግሞ ልንገስጸዉና እንደ አስፈላጊነቱም አግባብ ባለዉ ሕግና ሥርዓት ልንጠይቀዉ ይገባል::

እኔም እንደማንኛዉም ሰዉ ከተለያዩ ትምህርቶችና ልምዶች በየዓመቱ አይደለም በየወራቱ አሁን ድረስ በተለያየ መንገድ በማስተዉለዉና በምረዳዉ ነገር ራሴን እያስተካከልኩና ለወደፊትም ድክመቴንና ስህተቴን የማስተካክልና ወደ ፍጹም ሕይወት ለመጠጋት ነዉ እለት እለት የምዘጋጀዉ:: ፍጹም የሆነዉ እግዚአብሔርና በሰማዊ መንግሥት ዉስጥ ያሉ ቅዱሳንና ጻድቃን ብቻ ናቸዉ ተጨማሪ ማስተካከያና ማረሚያ የማያስፈልጋቸዉ እንጂ፤ እኛ ሥጋ ለባሽ ሰዎች ሁል ጊዜ ሕይወታችን ለመልካም ለዉጥ ሊዘጋጅ ይገባዋል::

አንዳንድ የተስተካከሉና የተለወጡ አስተሳሰቦቼና አቋሞቼን ብገልጽ፤ ቀደም ሲል ማንኛዉንም ሰዉ እንደ ራሴ በመቁጠር በተናገረዉ ቃል ሆኖ ይገኛል፤ የማያደርገዉን «እንዲህ አድርጉ» ብሎ አይናገርም በሚል እምነት በተለይ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የተሰማሩት ሰዎች በተናገሩት ቃል ሆነዉ የሚገኙ ይመስለኝ ነበር:: በተጨባጭ ባየሁትና በሰማዉት አብዛኛዎች ከዋና አባቶች ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ያሉት ለማስመሰልና በሰዉ ዘንድ እዉነተኛ መስለዉ ለመቅረብ ነዉ እንጂ «አትስረቁ» እያሉ እነሱ ግን ዋና ሌባ ሆነዉ አግኝቻቸዋለሁ:: «አትዘሙቱ» እያሉ ዋና ዘሚች ሆነዉ አግኝቻቸዋሉ:: « ቂም በቀል ከእናንተ አስወግዱ» እያሉ እነሱ ግን ዋና ቂም በቀለኛ ሆነዉ አግኝቻቸዋለሁ:: ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን እያወገዙ እነሱ ግን ዋና ዘረኛና ጎጠኛ ሆነዉ አግኝቻቸዋለሁ:: «አትዋሹ» እያሉ ዋና ቀጣፍ ሰዉን ከሰዉ የሚያጣሉና የሚከፋፍሉ መሰሪ ሆነዉ አግኝቻቸዋለሁ:: «እግዚአብሔር ብቻ ያናገረኝን ነዉ የማስተምራችሁ» እያሉ የሥጋና የደም ስሜታቸዉን እንዲሁም በዲያብሎስ መንፈስ ዉስጥ ሆነዉ ሲያስተምሩ አግኝቻቸዋለሁ:: «ስለ እዉነት ራሳችንን ክደን እንመስክር፤ እናገልግል» እያሉ እነሱ ግን «ኑሮ ተመሳስሎ፤ ከራስ በላይ

ንፋስ» በሚለዉ በአሕዛብ ሕይወት ሲመላለሱ አስተዉያለሁ። ባጠቃላይ «በአንድ አፍ ሁለት ምላስ» እንደሚባዉ ሆነዉ ነዉ ብዙዎቹን ያገኘዋቸዉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስሜቶቼ በጣም ተጎድተዉ ነበር። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ወንበር ላይና አገልጋሎት ላይ ተቀምጠዉና ተሰማርተዉ ያልጠበኩትን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭና በተቃራኒ ሕይወት ዉስጥ በመኖራቸዉና በስሙ በመነገዳቸዉ ነዉ። በሂደት ግን ምንም እንኳ በማልጠብቃቸዉ ድርጊቶች የተለየ የቁጭትና የኀዘን ስሜት ቢሰማኝም፣ እንደ በፊቱ በዉስጤ መብገንገንና መናደድ ትቼ፣ በምመለከተዉ፣ በምሰማዉ፣ በማነበዉ መጥፎና መሰሪ ነገር «እግዚአብሔር ያስተካክለዉ፣ እርሱ እዉነተኛ ፍርድ ይስጠ» በማለት ሁሉንም ለእርሱ አሳልፌ መስጠት ጀመርኩ።

ቀድሞ «የተለያየ መንፈሳዊ ጸጋ የተሰጣቸዉ ሰዎች ናቸዉ» ብዬ የማስባቸዉ ሰዎች ፍጹም እግዚአብሔር የሚያሰራቸዉን ብቻ ነዉ የሚሰሩትና እርሱ የሚያናግራዉን ብቻ ነዉ የሚናገሩት በማለት አስብ ነበር። እንዲሁም እንክርዳድ የተደባለቀበት ትምህርታቸዉን ሳይቀር ፍጹም ትክክል አድርጌ እቆጥርና ራሴንም ለተግባራዊነቱ አሰለፍ ነበር። አሁን ግን ራሳቸዉን ባዶ አድርገዉ ለመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ብቻ ካላዋሉ በስተቀር፣ አታላዩ (ሸዋጁ) መንፈስ መንፈሳዊነታቸዉን ተጠቅሞ አንበታቸዉን አንደበቱ ሕይወታቸዉን ሕይወት አደርጎ በመጠቀም ያልተገባ ተግባርና ኃጢአት እንደሚያስፈጽማቸዉ፣ እንዲሁም የሥጋና የደም ስሜት ትምህርት እንደሚያሰጣቸዉ፣ ከዚያም ባለፈ ለእርሱ የሚመችና ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚያርቅና የሚለይ የማስመሰል ትምህርት እንደሚያሰጣቸዉ አስተዉያለሁ። በዚህም ምክንያት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ አገልግሎት የማይሰጠዉን ሰዉ አገልግሎቱንና ትምህርቱን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እየመረመርኩ በስዴዉ እጠቀማለሁ፣ እንክርዳዱን እንደ እንክርዳድነቱ እመለከተዋለዉ እንጂ የተባለዉን ሁሉ አልቀበለዉም።

ሰይጣናትን ደግሞ ማንነታቸዉን በግልጽ ባልመለከትም በግልጽ ከማየት ባልተናነሰ መልኩ በእኔ ላይ ሆነ በሌላዉ ላይ በሚፈጽሙት የተለያየ ፈተናና ከሰዎች ሕሊናና አካል በተለያየ ምክንያት ሲወጡ አዉቃቸዋለሁ። እነሱ በረቂቅነት እኔ ደግሞ በግዙፍ አካል በዚህች ዓለም ወስጥ እየኖርን እንዳለ በደንብ እንተዋወቃለን። ነገር ግን የመጨረሻ እልኸኞች ናቸዉና «ታዉቀናል» ብለዉ ተስፋ የማይቆርጡና የማይርቁ፣ ማንኛዉንም ሰዉ እንደሚፈትኑ ወደ ሕሊናዬ ሆነ አካሌ በመግባት የሚፈታተኑኝ ናቸዉ። እግዚአብሔርንም በግልጽ ባልመለከተዉም በግልጽ ከመመልከት ባልተናነሰ መልኩ እርሱ በፈቀደልኝ መጠን አዉቄዋለሁ። ለዐይን ቅጽበት ያህል ከፍጥረቱ እንደማይለይ አስተዉያለሁ። ካለ እርሱ እዉቅናና ፈቃድ በዚህች ምድር ሆነ በሌላ ቦታ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን እንደማይቻል በሚገባ ተረድቻለሁ። የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ ማከናወን እንደሚችል አንዳች የሚሳነዉ ነገር እንደሌለ በሚገባ አዉቄያለሁ።

የመጀመሪያዉንና ሁለተኛዉን የእግዚአብሔር መልእክት ስጽፍ ወደ ሕሊናዬ የሚመጣዉ ነፍሴ ብቻ የምትሰማዉ የእግዚአብሔር ድምፅ ነገሮችን ሲገልጽልኝና ሲያሳስበኝ ወዲያዉ ወረቀት ላይ ካላሰፈርኩት ልክ ወተት ሲገነፍል እንደዳይፈስ መፍትሔ እንደምንሰጠዉ ሁሉ እኔም ሕሊናዬ

ስለሚወጥረኝ ወዲያዉ ነበር በወረቀት ላይ የማሰፍረዉና በኋላ ደግሞ በመቀመሪያ(በኮምፒተር) እጽፍ የነበረዉ፡፡ ይህን ሦስተኛዉን የእግዚአብሔር መልእክት ግን የተለያዩ መገለጾች ሆነ ማሳሰቢያዎች ወደ ሕሊናዬ ሲመጡ በመቀመሪያ (በኮምፒተር) እየጻፍኩ እያለ ከሆነ በዚያዉ እጽፈዋለሁ፡፡ ነገር ግን በስራ ላይ ወይንም ከሰዉ ጋር እየተነጋገርኩ ወይንም መኪና ዉስጥ ወይንም በእግሬ እየድኩ ባጠቃላይ በተለያየ ሁኔታ ዉስጥ ሆኜ ያ ድምፅ ከመጣ እንደበፊቱ ወዲያዉ በወረቀት ላይ ለማስፈር ሳልቸኩል የተለያዩ ጉዳዮችና እዉቀቶች ቢሆኑ እንኳ በመቀመሪያ(በኮምፒተር) ለመጻፍ አመቺ በሆነ ሰዓት ነዉ እጽፋቸዉ የነበረዉ፡፡ በዚህ ሦስተኛዉ መልእክት ጊዜ ነፍሴ ብቻ የምትሰማዉ ድምፅ በአብዛኛዉ ጊዜ ይመጣ የነበረዉ ከእንቅልፌ ነቅቼ በጸሎት ጊዜና ከጸሎት በኃላ ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ ደግሞ በስራ ላይ ሆነ በተለያየ ሁኔታ ላይ እያለሁም ይመጣ ነበር፡፡

በመጀመሪያዉ መልእክት ጊዜ ሰዉ ሁሉ እንደ እኔ በየዋሃት የእግዚአብሔርን መልእክት የሚቀበል መስሎኝ መልእክቱን ቶሎ ለማድረስ ዐይኔ እስከሚቀላና እስከሚያብጥ ድረስ ነበር ሕሊናዬ እስከሚደክም ድረስ ቀን ከሌሊት እጽፍ የነበረዉ፡፡ በሁለተኛዉ መልእክት ጊዜ ደግሞ የመጀመሪያዉ መልእክት አንድ መፍትሔ ላይ ሳይደርስና በሚፈለገዉ መጠን ለሕዝብ ሳይሰራጭ እንድጽፍ ስለተደረገ በተረጋጋ ሁኔታ ነበር ስጽፍ የነበረዉ፡፡ ነገር ግን ጥቅምት፳፯÷፳፻፬ዓ.ም (27/02/2004) የመጀመሪያዉን ሆነ ሁለተኛዉን እንዲሁም የታተመዉን መጽሐፍ ማሰራጨት እንደምችል ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ ሲነገረኝ እንደ መጀመሪያዉ መልእክት አጻጻፍ ባይሆንም በምችለዉ ሁሉ ቀን ከሌሊት በመጻፍ ለታሕሳስ ፲፮÷፳፻፬ዓ.ም (16/04/2004) ለስርጭት ላደርስ ችያለሁ፡፡ ይህን ሦስተኛዉን መልእክት ስጽፍ እንደ ቀደሙት ሁለት መልእክታት ቶሎ የጽሑፌን ስራ ጨርሼ ለማሰራጨት ሳልቸኩል፤ ነገር ግን በምችለዉ አቅም ሁሉ አስፈላጊዉን ትጋት በማሳየት ልጽፍ ችያለሁ፡፡ እንደበፊቱ ለማሰራጨት ያልቸኮልኩትም ምክንያት ትዉልዱ ለእግዚአብሔር መልእክት ሆነ ቃል፤ ጊዜዉን ለመስጠት አይፈልግምና፤ እንዲሁም በተለያየ መንገድ ሕሊናዉ እንዲደነዝዝ ስለተደረገ እንኳን ፍጡሩን ሰዉ ቀርቶ ራሱ እግዚአብሔር ተገልጦ ቢናገረዉ የሚቀበለዉ አይደለምና ነዉ፡፡ አሁንም ቢሆን ትዉልዱ ባይቀበለኝም ዳተኛነትና ስንፍና ሳይታይብኝ በምችለዉ ሁሉ ቀንም ይሁን ሌሊት እንዲሁም ንጋት ላይ ከሌሎች የስራ ድርሻዎቼ ጋር ጉን ለጎን በመወጣት በሦስት ወር ዉስጥ ከአምስት መቶ ገጽ በላይ ጽፌ ለስርጭት ላደርስ ችያለሁ፡፡

ትዉልዱ ያላስተዋለዉ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በተለዩ አገልጋዮቹና መልእክተኞቹ የሚያስተላልፈዉን ቃል «አልሰማም፣ አልቀበለዉም፣ አልፈልገዉም፣ ተግባራዊ አላደርግም» የሚል ሰዉ፤ እግዚአብሔርን «አልሰማም፣ አልቀበለዉም፣ አልፈልገዉ፣ ተግባራዊ አላደርግም» እንዳለ እንደሚቆጠርና ፍርዱም ከብሉይ ዘመን ሆነ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ከምድር በሥጋ ሞት ከተጠሩት ሰዎች በላይ እንደሚሆንበት ነዉ፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ በዘመኑ የነበሩ ሰዎች፣ ትምህርቱ በተለያየ ተአምርና ፈዉስ ቢደገፍም ሊሰሙትና ሊቀበሉት ባለመቻላቸዉ ምክንያት፤ በፍርድ ቀን የሰዶምና የጎሞራ ሰዎች ፍርዱ እንደሚቀልላቸዉና በእነሱ ላይ ደግሞ በባሰ መልኩ ፍርዱ እንደሚብስባቸዉ ነበር ያሳሰባቸዉና ያስጠነቀቃቸዉ፡፡ እነሱ የተመለከቱት ተአምርና ፈዉስ እንዲሁም የተሰጠዉ ትምህርት እነዚያ የዱሮ ዓመፀኛ ሰዎች

የመመልከትና የመስማት እድል ቢያጋጥማቸዉ ኖሮ ለዚያ መጠረግ እንደማይዳረጉና መኖሪያቸዉም እስከ አሁን ድረስ እንደሚኖር ጭምር ነበር የልባቸዉን ደንዳናነት ለመግለጽ የተናገራቸዉ።

«በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸዉን ከተሞዎች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸዉ ጀምረ እንዲህም አለ ፦ ወዮልሽ ኮራዚ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ በእናንተ የተደረገዉ ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰዉ አመድም ነስንሰዉ ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበረና። ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገዉ ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና። ነገር ግን እላችኋለሁ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል።» ሉቃስ፲፩(11)፥፳ እስከ ፳፬ (20-24)። አሁንም በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ድንቅ ስራ በተለያየ መልኩ በዓለም እየታየና የተለያዩ እዉቀቶችና ምስጢራት እየተገለጹ የማይቀበል ትዉልድ ካለፉት ዓመፀኛ ሰዎች በላይ ፍርዱ እንደሚብስባቸዉና የሚታበዩበትም እንደሚጠፉ ነዉ።

እስከ ጥቅምት፳፯፥፳፻፬ (27/02/2004) ዓ.ም ድረስ የእግዚአብሔርን መልእክት እንዳሰራጭ ስላልተፈቀደልኝና ታፍኖ ስለቆየ እንዲሁም በዉስጤ ብቻ ስለምብገነገን እግዚአብሔር አንድ መፍትሔ እንዲሰጠዉና ለእኔም አዝኖልኝ ስለመልእክቱ አንድ ነገር እንዲለኝ በመፈለግ ራሴን እንደ በድን አድርጌ ነበር የምቆጥረዉና የምሰይመዉ የነበረዉ። ምክንያቱም አንዳች ማድረግ አልቻልኩምና። ጥቅምት፳፯፥፳፻፬ዓ.ም (27/2004) ዓ.ም ሁሉንም እንዳስተላልፍ ሙሉ ፈቃድ ከተሰጠኝ በኋላ ግን በብሩህ ተስፋ ዉስጥ መመላለስ ቻልኩ። ምክንያቱም በራሴ ማድረግ ያለብኝን ማድረግ ችያለሁና፤ ሌላዉ ደግሞ እግዚአብሔር ራሴን ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የማዝነዉ ኀዘን ከሁለት ዓመት በኋላ ከመስከረም ፳፻፭(2005) ጀምሮ በተለየ ሁኔታ ቀንሶልኛል። ይኸዉም ቀድሞ የአዳምና የሔዋን ዘሮች ሁሉ እንደ ራሴ በመመልከት በእግዚአብሔር መልእክት ደንገጥ የሚሉና ለመልእክቱ ቦታ ሰተዉ ለተግባራዊነቱ ይሰለፋሉ በሚል እምነት፤ እግዚአብሔርን «እኔ ዋና ኃጢአተኛዉን ለንስሐ ያበቃኸኝና ለፈቃድህ ያሰለፍከኝ አምላክ፣ ዓለም ባለማወቅና ባማስተዋል ስለሆነ በኃጢአት ዉስጥ እየተመላለሰ ያለዉ፤ መልእክትህ ለአዳም ዘር ሳይደርስ የመጨረሻ ቁጣህን አታምጣ» በማለት ነበር በኀዘን ዉስጥ ሆኜ ጸሎቴን አቀርብ የነበረዉ። አሁን ግን እንኳ በዓለም ሕይወት የሚመላለሰዉ ቀርቶ «በመንፈሳዊ አገልግሎትና ሕይወት ነዉ የሚመላለሰዉ» የሚባለዉ ሰዉ ሳይቀር የእግዚአብሔርን መልእክት በሥጋና ደም ስሜቱ በመመርመርና ነጥብ በማትሞላዉ እዉቀቱ በመገምገም ለእርሱ የሥጋና ደም ስሜት ካልተመቸዉ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት የማይቀበልና የሚንቅ፣ ከዚያም ባለፈ የሚቃወምና የሚተች በመሆኑ በእግዚአብሔር የተለያየ ቁጣ ካልሆነ በስተቀር ትዉልዱ የእግዚአብሔርን መልእክት የማይቀበልና ለተግባራዊነቱ የማይሰለፍ መሆኑን ስላስተዋልኩ፤ ኀዘኑ ቀሎልኝ በምመለከተዉ ሆነ በምሰማዉ እንዲሁም በማነበዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ባጠቃላይ የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ ጽሑፍ፣ ትዕይንት ሕሊናዬ የመቋቋም ኃይል ስለተጎናጸፈች እንደ ቀድሞዉ የተለየ ኀዘን አይሰማኝም።

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ዓመፀኛና እብሪተኛ ላይ በሚወስደዉ ቅጣት ሆነ እርምኛ እንደ ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ነፍሳት « ፍርዶችህ እዉነትና ጽድቅ ናቸዉ:: ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግናለን፤ አሕዛብም ተቈጡ፣ ቍጣህም መጣ፣ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፣ ለባሪያዎችህም ለነብያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸዉን ትሰጥ ዘንድ፣ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ» ራእየ ዮሐ. 11፡17እስከ18 በማለት ነዉ ለእያንዳንዱ እንደ ዓመፃዉ ደረጃ ዋጋ የሚያስከፍለዉንና እንደ ጽድቁ ዋጋ የሚከፍለዉን አምላክ ምስጋናዬንና ጸሎቴን የማቀርበዉ እንጂ፤ እንደ ቀድሞ «እንዲህ አድርግልን» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር መሟገትን አቁሜያለሁ:: ምክንያቱን ከምፈልገዉ በላይ ማድረግ የምፈልገዉን እንዳደርግ በነጻነት ተፈቅዶልኝ አድርጌያለሁና:: የተለየ ጸሎቴንም ማቅረብ ለጊዜዉ ትቻለዉ:: ምክንያቱም «እኔም የሚሰማኝና የሚቀበለኝ ሰዉ አጥቻለሁና ኀዘንተኛ ነኝ» የሚለዉን ምላሽ ስለሰጠኝና ስለሚሰጠኝ ዳግም የእግዚአብሔርን ኀዘንተኛ መሆንን ላለመስማት «ሁለተኛ የተለየ ጥያቄ አላቀርብም፣ የምስጋና ጸሎት ነዉ የማቀርብለት» ብዬ ለራሴ ተናግሬያለሁ:: ቢበዛ «ይህን ሦስተኛዉን መልእክትን ሳላሰራጭ የመጨረሻዉን ቁጣ አታምጣ» የሚለዉን ባቀርብ ነዉ:: በትዉልዱ አሁንም ተስፋ ሳይልቆርጥ ማድረግ ያለብኝን እያደረኩ ነዉ:: ለወደፊትም እግዚአብሔር በመራኝና ባሳሰበኝ ሁሉ ማዳረግ ያለብኝን አደርጋለሁ::

ወደ ግል ሕይወቴ ስመጣ ደግሞ በፊት ስለወደፊቱ በራሴ ስሌት ነበር ለመሄድ አቅድ የነበረዉና ራሴንም ላላስፈላጊ ሐሳብና ጭንቀት የምዳርግ የነበረዉ:: አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ከራሴ ስሌት ወጥቼ ስለ ወደፊቱ እርሱ እግዚአብሔር በሚፈቅደዉ ሕይወትና መንገድ ብቻ ለመጓዝ፣ እለት እለት ደግሞ ከኔ የሚጠበቀዉን ድርሻ መወጣትና ማከናወን ብቻ እንዳለብኝ አስተዉዬ፤ ካለ አንዳች ጭንቀትና የተለየ ሐሳብ ሕይወቴን እየመራሁ እገኛለሁ:: ቀድሞ እድሜዬን በሥጋዬ ዕድገት አሰላዉ ነበር:: አሁን ግን በነፍሴ ሕያዉነት ዘመን ስለማሰላዉ እስከ አለሁበት ጊዜ ያለፈዉ ዘመኔን እንደ ዐይን ጥቅሻ እድሜ ነዉ የምመለከተዉ:: ምክንያቱም ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሆን ነገር የለምና ለወደፊቱ ደግሞ ለሕያዉነት ዘመን እንደምኖር በሚገባ ስላወኩና ስለስተዋልኩ፣ ሕያዉ ለሚያደርገኝ ተግባር ነዉ የምተጋዉና ምድራዊ ሕይወቴን እግዚአብሔር በሰጠኝ ኃላፊነት በአግባቡ ተወጥቼ፣ የሚፈለግብኝን ፍሬ አፍርቼ ወደ ሁለተኛዉ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታ ለመሄድ ነዉ በናፍቆት ከተገለጥኩበት ሥጋ የምለይበትን ጊዜ የምጠባበቀዉ::

እዚህ ላይ በተጨማሪ ለመግለጽ የምፈልገዉ የዓለም ሥልጣን ሆነ ሀብት ሁሉ የእኔ ቢሆን በበድን ሕይወት ነዉ የማያቸዉ እንጂ አንዳች የተለየ ነገር በሕይወቴ ለዉጥ አያመጣም:: ምድራዊ ተግባሬም የሚሆነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምና ማስፈጸም ብቻ እንጂ «ይህ ዘሬ ነዉ፣ ይህ ጎጤ ነዉ፣ ይህ ዘመዴ ነዉ፣ ይህ ቤተሰቤ ነዉ፣ ይህ ወንድሜ ነዉ፣ ይህች እህቴ ናት፣ ይህ አባቴ ነዉ፣ ይህች እናቴ ነች፣ እነዚህ ልጆቼ ናቸዉ፣ ይህ ጓደኛዬ ነዉ::» ብዬ እግዚአብሔር የማይፈቅደዉንና የማይወደዉን ተግባር ስለማንም ሰዉ ስል አልፈጽምም:: እግዚአብሔር ደግሞ በዚህች አጭር ዘመኔ የሰዉን ማንነት በደንብ አሳዉቆኛል:: ይኸዉም ምንም እንኳን ወላጅ አባትና

እናት እጅግ ብዙዎቹ ለልጆቻቸዉ መስዋዕት የሚሆኑ፣ ከራሳቸዉ በላይ ለልጆቻቸዉ የሚኖሩ፤ እንዲሁም ከቤተሰብና ከዘመድ በላይ የሚሆኑ ነገር ግን ቤተሰብ ሆነ ዘመድ ያልሆኑ እጅግ እጅግ ጥቂት ሰዎች ቢኖሩም፤ ከዚህ በተጨማሪ እንደ እዉነተኛ ወላጅ የሚሆኑ ወንድም ሆነ እህት እንዲሁም ቤተሰብ ሆነ ዘመድ ሊኖሩ ቢችሉም፣ እንደ አጠቃላይ ግን ከእዉነተኛ ወላጅ ዉጭ እጅግ እጅግ ብዙዎች፤ ሰዉን የሚፈልጉት ከፍቅር አንጻር ሳይሆን ከጥቅም አንጻር ብቻ መሆኑን በሚገባ ላስተዉል ችያለሁ::

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__: በእግዚአብሔር መልእክቶች ዉስጥ የተገለጹት የእርሶን ሰብእና መግለጽ ይችላሉ ማለት እንችላለን?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንዳስተዋልኩት በሰዎች ዉስጥ ሁለት ሰብእና እናዳለና ተዋሕደዉ እንዳሉ ለማስተዋል ችያለሁ:: የመጀመሪያ ሰብእና ዉስጣዊዉ የሆነዉ በዉጭ ባሉ ሰዎች የማይታወቅ መልካምም ይሁን መጥፎ ሊሆን የሚችል ሲሆን፤ ሁለተኛዉ ሰብእና ደግም ዉጫዊ፣ በዉጭ ባሉ ሰዎች ጭምር የሚታወቅ ነዉ:: ስለዚህ አንድ ሰዉ በዉጭ በሚያሳየዉ ጠባይና ሕይወቱ የዉስጡን ይወክላል ማለት አይቻልም:: ከዉጭ ሲታይ እዉነተኛና ትሁት የሚመስል ዉስጣዊ ማንነቱ ሲያይልበት ሐሰተኛ፣ አስመሳይና፣ ትዕቢተኛ ፣ ጨካኝ ሊሆን ይችላል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ዉጫዊ ማንነቱ ከዉስጣዊ ማንነቱ ጋር አንድ ዓይነት ሆኖ ሊገኝ ይችላል:: ከዚህ የምንረዳዉ አንድ ሰዉን እንደ ዉጫዊ ማንነቱ ዉስጣዊዉም አንድ ዓይነት ነዉ ማለት እንደማይቻልና እንዲሁም ዉጫዊዉና ዉስጣዊ ማንነቱ ተመሳሳይ አይደለም ማለት አንችልም:: ምክንያቱም ተመሳሳይ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፤ ተቃራኒ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ:: እኛ ሰዎች የሰዎችን ዉስጣዊ ማንነት ስለማናዉቅ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሚመለከተዉ በዉስጣዊ ማንነቱ ነዉ:: በዚህ ምክንያት ማንም ሊያታልለዉ ሆነ ሊሸነግለዉ አይችልም:: እኛ ሰዎች ግን በአንደበት ልናታልልና ልንሸነገል እንችላለን:: ዞሮ ዞሮ ከልብ ሞልቶ የተረፈዉ በተግባር ሆነ በንግግር እንዲሁም በጽሑፍ መገለጹ አይቀርምና የሰዎችን ዉስጣዊ ማንነት ከተግባራቸዉ፣ ከንግግራቸዉ፣ ከጽሑፋቸዉ ልናዉቅና ልናስተዉል እንችላላን::

***ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ*** በጽሑፉ ዉስጥ ያለዉ አብዛኛዉ ዉስጣዊ ማንነቴን ነዉ የሚገልጸዉ:: ዉጫዊ ማንነቴ በአብዛኛዉ ከሰዉ ጋር አብሮ የሚያኖረኝ፤ ለሰዉ ስሜት በጣም የምጠነቀቅ፤ አንዳንዴም በይሉኝታ ራሴን የምጎዳ፤ ሌላዉ ከሚጎዳ የራሴን መጎዳት የማስቀድም፤ እዉነት ስተገፋና ስትዳፈን በዉስጤ ነዉ የምብገነገነዉና ቅሬታዬን የማቀርበዉ እንዲሁም ለእግዚአብሔር አሳልፌ የሚሰጠዉ እንጂ ከማንም ጋር የማልጋፈጥ ነኝ:: በዚህ ጠባዬ ምክንያት ከክፉዉ ሆነ ከደጉ፣ ከጠማማዉ ሆነ ከቀናዉ፣ ከእዉነተኛዉ ሆነ ከሐሰተኛዉ፣ ከሀብታሙ ሆነ ከደሀዉ፣ ባጠቃላይ ከማንም ሰዉ ጋር መኖር የምችል ነኝ:: ነገር ግን ስሜቴ ከሚጎዳበት መራቅና ብቸኝነትን የምመርጥ፤ እንዲሁም ሕሊናዬ የማይቀበለዉንና የማላምንበትን ማንም ይሁን ማን ለሰዉ ብዬ የማላደርግና የማልተባበር ሰዉ ነኝ:: የራሴ የምለዉን ሰዉ ጉድለቱን ሆነ ጥፋቱን ለመናገር ወደ ኋላ የማልልም ነኝ:: ይህን ማለቴ ደግሞ ለሕሊናዬና ለአምላኬ ሳልታመን ኃጢአት ሳልፈጽሞ ቀርቶ

ሳይሆን፤ አጠቃላይ ጠባዬን ለመግልጽ ነዉ። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ስለፈጸምኩት ኃጢአት ደግሞ በእዉነተኛ ጸጸትና ንስሐ ከሰማያዊ መዝገብ ላይ በቅዱስ ቁርባን አማካይነት ስላስደመሰስኩትና ስለ ሌላ ሳይሆን ስለ ሕሊናዬና ስለ አምላኬ ብቻ በማንኛዉም ነገር ታማኝ ሆኜ በመኖር ላይ እገኛለሁ።

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: አሁን በእግዚአብሔር አገልግሎትና ጥሪ ዉስጥ እያሉ ከሰዎች ጋር ያሎት ግንኙነት እንዴት ነዉ?

***<u>የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: ከማኛዉም ሰዉ ጋር የቀድሞ ሆነ የአሁን ግንኙነቴ ያዉ ነዉ። ነገር ግን አሁን ማንም ሰዉ በተግባሬ ብቻ አይደለም በንግግሬ እንዳይሰናከልብኝ ከፍተኛ ጥንቃቄ አደርጋለሁ። በተቀረ ግን ከቤተሰቤ ሆነ ከቅርብ ወገኖቼ እንዲሁም ከስራ ባልደረቦቼና ከሌሎችም ጋር ያለኝ ግንኙነት እንደ ቀድሞዉ እንደ ተራነቴ ነዉ እንጂ ራሴን የተለየሁ አድርጌ አይደለም የምቀርበዉ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ግንኙነትም እንደቀድሞ ሲሆን፤ ነገር ግን አሁን የበለጠ አፈቅረዋለሁ፤ አከብረዋለሁ፤ እግዛለታለሁ፤ አመልከዋለሁ፤ በተግባርም፣ በንግግርም፣ በሐሳብም ጭምር ከኃጢአት ለመጠበቅና እርሱ ደስ የሚሰኝበትን ተግባር፣ ንግግር፣ ሐሳብ ለመፈጸም እጅጉን እተጋለሁ።

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: ቀድሞ ይጸልዩት የነበረዉና ከእግዚአብሔር ጥሪ በኋላ የሚጸልዩት ጸሎት ልዩነት አለዉ ወይ?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: የምጸልየዉ ጸሎት ልዩነት የለዉም። ነገር ቀድሞ እምጸልየዉ ላይ እየጨመርኩ የምጸልየዉ አለ። ለምሳሌ የኢትዮጵያዉያን የቃል ኪዳን ጸሎት፣ የኢትዮጵያዉያን የሃይማኖት ጸሎት፣ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን የሚቀርቡ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎት፣ የመከራ ጊዜና የቅዱሱ ኪዳን እንዲሁም የሰንደቅ ዓለማ መዝሙርን በየዕለቱ በተጨማሪ አደርሳለሁ። ቀድሞ «እግዚአብሔር ሆይ! ዓለም ሁሉ ነገር መስቀልህን ይወቅ ማወቅ ብቻ አይደለም ያስተዉል፣ ማወቅና ማስተዋል ብቻ አይደለም እያወቅን እያስተዋልን የድፍረት በደል እንዳንፈጽም አንተን መፍራት በልቦናችን ዉስጥ አኑርልን።» በማለት እጸለይ የነበረዉ ላይ «እግዚአብሔር ሆይ! አንተን መፍራት በልቦናችን ዉስጥ አኑረህም የድፍረት ድፍት በደል እንፈጽማለንና ዓለም ሁሉ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይዉንና ጎስቋላ ሕይወቱንና ኑሮዉን እንዲያስተዉል አድርግ። ያኔ ሥርዓት እንይዝላሀለን፣ ልክ እንገባልሃለን፣ እንኳን በአንተ ቦታ ላይ ተቀምጠን ራሳችንን ማስገነንና ማስመለክ ቀርቶ የሚገባን ክብር ቢኖር እንኳ እንንቀዋለን፤ አንተን ብቻ ለማስገነንና ለማስመለክ እንተጋለን» በማለት አክዬበታለሁ። አሁን ደግሞ «ነገር መስቀሉን እያወቅንና እያስተዋልን እንዲሁም አንተን መፍራት በዉስጣችን ተቀምጦልን ከዚያም በላይ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርያችንንና ጎስቋላ ሕይወታችንና ኑሮዋችንን እያስተዋልን አሁንም ከዓመፃና ከክህደት እንዲሁም ከርኩሰት ሕይወት መለየት አልቻልንምና ተራና አቅመ ቢስ ልምሾ መሆናችንን አሳያን፤ ያኔ እጃችንን እንሰጣለን፣ ለፈቃድህም እንሰለፋለን» በማለት አክዬበታለሁ።

እንዲሁም «በአራቱም ማእዘን የተዘረጋዉን የዲያብሎስ ሥርዓት ደምስሰህልን ያንተን ሰማያዊ ሥርዓት ዘርጋልን፣ ንጉሣችን አንተ እግዚአብሔር፤ ንግሥታችን እመቤታችን ድንግል ማርያም፤ ባለሥልጣኖቻችን ቅዱሳን መላእክት፤ አስተዳዳሪዎቻችንንና አለቆቻችን ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ይሁኑ» እያልኩ ጨምሬበታለሁ:: ከዚህ በተጨማሪ «በአራቱም ማእዘን የአዳምና ሔዋን ዘሮችን የሚፈታተኑትንና የሚያጠቁትን በብዙ ትእለፊት(በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስትን (ሰይጣናትን) ኃይላቸዉን ልምሾ አድርግልን፤ ጨካኞችን ደግሞ አንተም ጨክነህባቸዉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኃይላቸዉን ልምሾ ከማድረግ በተጨማሪ ዳግም የአዳምና ሔዋንን ዘሮች መፈታተንና መጉዳት አይደለም በራሳቸዉ ህልዉና መኖር በማይችሉበት ደረጃ ቅጣቸዉ፤ የተበላሹ ይሁኑ፤ ምክንያቱም ተመልሰዉ የአዳምና የሔዋንን ዘሮች ለማጥቃትና ለመጎዳት እንዳይመለሱ:: እኛን ሕፃን አዋቂ ሳይሉ በበሽታ ያበላሹን የለም ወይ!?:: ከሰዉ ዘሮች ተለይተዉ በራሳቸዉ ሕይወት ብቻ የሚኖሩትን ርኩሳን መናፍስት ወደ ሰዉ ዘሮች እንዳይመጡ ይገደቡ:: እንደሌሎቹ ርኩሳን መናፍስት ወደ ሰዎች መተዉ ለማጥቃት የሚያስቡ ከሆነ እንዳሰቡ ኃይላቸዉ ልምሾ ከመሆን ባለፈ የተበላሹ ይሁኑ:: እንኳን የአዳምና ሔዋንን ዘሮች ለመፈታተንና ለማጥቃት አይደለም በራሳቸዉ ህልዉና መኖር እንዳይችሉ አድረግ:: እንዲሁም ዋና አዛዣቸዉን ዲያብሎስ ልምሾና የተበላሸ ከማድረግ በተጨማሪ ፍዳዉን እንዲቀበል አድርገህ ለብቻዉ አይቀጡ አቀጣጥ ቅጣዉ:: ባጠቃላይ «ዲያብሎስና ሠራዊቱ ሰይጣናት ለ7504 ዓመት በሰዉ ዘሮች ሕሊናና አካል ላይ ነግሠዉ መከራና ፍዳችንን እያሳዩንና ከአንተ ጋር እያጣሉን ስለሆነ ኃይላቸዉ ልምሾ ይሁን፣ እንኳን እኛን ለማጥቃት አይደለም በራሳቸዉ ህልዉና መኖር በማይችሉበት ደረጃ ይበላሹ፣ ዋናዉ አዛዣቸዉና መሪያቸዉ ዲያብሎስም ታስሮ ፍዳዉን ይቀበል» እያልኩ መጸለይ ጀምሬያለሁ::::

ከዚህም ጋርም «ከእኛ ከአዳም ዘሮች አንዳች ነገር ሳትጠብቅ ስለ እናትህ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ስለ ቅዱሳን መላእክት፣ ስለ ነቢያት፣ ስለ ሐዋርያት፣ ስለ ሰማዕታት፣ ስለ ጻድቃን፣ እንዲሁም በዚህ ምድር ዉስጥ በእዉነትና በመንፈስ ስለሚያመልኩ እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች ስትል፣ ስለ ቅዱሱ ኪዳንህ ስትል እንዲያዉ በምሕረትህ ጎብኝተኸን በአራቱም ማእዘን ያንተ ፈቃድ ብቻ ይፈጸም» በማለት ጨምሬበታለሁ:: እንዲሁም አቅሜና ስሜቴ እስከምን ያህል ድረስ እንደሆነ ስላስተዋልኩ «እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔን ልክስክሱን ክፋት ክርፋት የሞላብኝን ከነቤተሰቤ ለሰይጣናት ፈተና አሳልፈህ አትስጠን:: አንችለዉም እርሱ የክፋት፣ የተንኮል፣ የጭከና፣ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጥበበኛ ነዉ፤ እኛ ደግሞ ተራና ወራዳ ኃጢአተኛ መሆናችንን አምነን እጃችንን ለአንተ ሰተናል:: ስለዚህ ሰይጣናት ሆኑ የእነርሱ አገልጋዮች በእኛ ላይ አንዳች ሥልጣን አይኑራቸዉ፤ አንተ ሳትፈቅድ አንዲቱን ጠጉራችንን መንካት ሆነ ማስነካት አይችሉምና» በማለት ለሰይጣናት ፈተና ተላልፌ እንዳልሰጥ አጥብቄ እየጠየኩት ነዉ:: ምክንያቱም አቅም የሌለኝና ስሜቴ በቀላሉ የሚጎዳ ነዉና::

ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ደግሞ «ንዒ አቤኪ» ከሚለዉ በተጨማሪ «እንቋ ስምሽን ወስጄ ገንዘብ አደረኩኝ እመቤቴ ማርያም እናቴ እማምዬ ነሽ አልኩኝ፤ እንቋ ስምሽን ወስጄ ገንዘብ አደረኩኝ እመቤቴ ማርያም ተስፋዬ መጽናኛዬ ነሽ አልኩኝ፤ እንቋ ስምሽን ወስጄ ገንዘብ አደረኩኝ

እመቤቴ ማርያም አምባ መጠጊያዬ ነሽ አልኩኝ» በማለት ያከልኩበትና፤ እንዲሁም «እመቤቴ ማርያም ሆይ! ዓለም ሁሉ የሕይወት ምስጢር ቁልፍነትሽን እንዲያዉቅና እንዲያስተዉል አድርጊ» የሚለዉን የጨመርኩ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ «ለአዳምን ሔዋን ዘሮች ከአንቺ ባላይ የሚያዝንና የሚያስብ ስለሌለ፤ እኛ የአዳም ዘሮች ደግሞ ክብር የማይወድልን፣ ምርጫችንን መለየት ያቃተን፣ በሽንት ቤት ሰገራ ዉስጥ ሆነን መጋትንና መሽተትን እንጂ የምንፈልገዉ ከከፋዉና ከከረፋዉ እንዲሁም ከሸተተዉ ሕይወት ራሳችንን መለየት የማንፈልግ ስለሆነ፤ አንቺ በእናትነትሽ ፍቅርና ርኅራኄሽ እንደ እኛ ጠማማነትን ዓመፀኛነት ሳትመለከቺንና ሳትጸየፊን በመጫኛም ቢሆን ከሽንት ቤት ዉስጥ አዉጥተሽንና ዉኃ በጎማም ቢሆን ረጭተሽብንና አጽድተሽን ጥሩ ጠረኝ ያለዉ ቅባት ቀብተሽን ወደ ፈጣሪ አምላካችን አቅርቢን» በማለት አክዬበታለዉ።

ከዚህ በተጨማሪም ራሴን የበለጠ በእግዚአብሔር ፊት ለማዋረድና ተራነቴንና ወራዳነቴን ለመግለጽ ስል በፊት ራሴን ከምጠራበት ጸያፍ ስያሜ በተጨማሪ በሕሊናዬ የመጡልኝን ጸያፍ ስያሜዎችን ሁሉ በማከል ራሴን እጠራለሁ። ከዚህ በፊትም በመጀመሪያዉ የእግዚአብሐር መልእክት ላይ የገለጽኩት ጸያፍ ስያሜዎች ሙሉዉን ሳይሆን የተወሰነዉን ነዉ። ምክንያቱም ለሰዉ ሕሊና ይከብዳሉ በሚል ስሜት። አሁንም የጨመርኳቸዉ ጸያፍ ስሞች ለሰዉ ሕሊና ይከብዳሉ ብዬ ስለገመትኩ አልገልጻቸዉም። ለወደፊትም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የበለጠዉን ኃይል ለመጎናጸፍና ጸጋን ለማግኘት ጸሎቴን እየጨመርኩና ራሴንም እያዋረድኩ ነዉ የምሄደዉ እንጂ የምቀንስበት ሆነ ራሴን ከፍ ከፍ የማደርግበት፣ የማመጻድቅበት ምክንያት የለም። ዋናዉ ግቤ ለሰማያዊ አክሊልና መንግሥት ለመብቃት ነዉ።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ለእግዚአብሔር አገልግሎት በተለየ ሁኔታ ከተጠሩ በኋላ ቀድሞ ከሚመገቡትና ከሚጠጡት መብልና መጠጥ የለዉጡት ወይንም የተዉት አለ ወይ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በቀድሞ መንፈሳዊ ሕይወቴ ሆነ ከሁለት ዓመት ወዲህ ለእግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት ከተጠራሁ በኋላ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከሚፈቅድልኝ ዉጭ የተመገብኩት ሆነ የጠጣሁት የለም። አሁንም በዚያዉ ሕይወት ነዉ ያለሁት፤ ያኔ የምበላዉና የምጠጣዉን እበላለሁ፣ እጠጣለሁ። በጾም ወቅት የሚከለከለዉን ያኔም አልበላም፣ አሁንም አልበላም። በቤተክርስቲያኒቱ የታወጁትን ሰባቱን አጿማት እንደ አቅሜ በፊትም እጾም ነበር፣ አሁንም እጾማለሁ። ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ከፍልሰታ ጾም ዉጭ ሌሎቹን እንደ አቅሜ እስከ ስድስት ሰዓት ነበር የምጾመዉ። ከአራት ዓመት ወዲህ ደግሞ የዐብይ ጾምን እንደ ፍልሰታ ጾም እስከ ቅዳሴ ማብቂያ ድረስ መጾም ጀምሬያለሁ። ወደፊትም እንደ ቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ እምነትና ምግባር እንዲሁም ሥርዓትና ትዉፊት መሰረት ነዉ የምኖረዉ።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: የእግዚአብሔርን መልእክታት ሲጽፉ ከጎኖት በሐሳብ፣ በጽሑፍ፣ በእዉቀት የሚረዳምና የሚያማክሮት ሰዎች ነበሩ ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ትእዛዝ ስራ ዉስጥ የሰዉ ምክር ሆነ እዉቀት አያስፈልግም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ፍጹም ነዉ:: የሰዉ እዉቀት ሆነ አስተሳሰብ ሙሉ አይደለም:: እኔ የምጽፋቸዉ ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን የጻፍኳቸዉ መንፈስ ቅዱስ በሥጋዊ ጆሮ በማይደመጠዉ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ የሚገልጽልኝንና የሚያሳስበኝን ምስጢርና እዉቀት እንዲሁም እርሱ እንዲጻፍና እንዲገለጥ የሚፈልገዉን ብቻ ነዉ እንጂ ሥጋና ደም ስሜቴ ያፈለቀዉን አይደለም:: ስለዚህ የእኔ መሪና ደጋፊ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነበር:: በመቀመሪያም(በኮምፒተር) ስጽፍ የመጀመሪያዉን መልእክት በጸሐፊ ያስጀመርኩ ሲሆን ወዲያዉ ፊደላቶቹን ከተለማመድኩ በኋላ ግን ራሴዉ ልጽፍና ሁለተኛዉንም ይህን ሦስተኛዉንም ብቻዬን ነዉ የጻፍኩት:: ጉዳዩንም የሚያዉቀዉ እግዚአብሔርና እርሱ እንዲያዉቁ የፈቀደላቸዉ ቅዱሳንና ጻድቃን እንዲሁም ሳይገባኝ ለመልእክቱ ጸሐፊነት የተመረጥኩት እኔ ነን:: የመጨረሻ ጽሑፌም የሚቆመዉና ለስርጭት የሚበቃዉ ያ በተለየ ሁኔታ ወደ ነፍሴ የሚመጣዉ ድምፅ ሲቆም ነዉ እንጂ በቀን ለአንድ ደቂቃ ቢሆን እንኳ ያ ድምፅ ሲመጣልኝ ወይንም ሲያሳስበኝ ወዲያ በሕሊናዬ አኑሬዉ ሲመቻችልኝ በመቀመሪያ እጽፈዋለሁ:: እንዲህ እያለ ነዉ በመጨረሻም ከመጽሔት፣ ከመጻሕፍት፣ ከማስታወቂያ ሰሌዳ፣ ከተለያዩ ድረ ገጽ፣ ከፌስ ቡክ፣ በወረቀት ላይ ከሰፈረ፣ ባጠቃላይ ከተለያየ ቦታ ባገኘሁት አድራሻ የሃይማኖት፣ የቀለም፣ የዘር፣ የጎሳ፣ የቋንቋ ልዩነት ሳላደርግ «ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረት ነዉ፤ የአዳምና የሔዋን ዘሮች አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ እህቶቼ፣ ወንድሞቼ ናቸዉ::» በሚል አስተሳሰብና እምነት ነዉ ስልክላቸዉ የነበረዉ፤ አሁንም የምልክላቸዉ:: ማንበብ አለማንበብ፣ መቀበል አለመቀበል፣ ለሌላዉ ወገን ማድረስ አለማድረስ ደግሞ የእነርሱ ድርሻ ነዉ:: የእኔ ድርሻ በምችለዉና እግዚአብሔር ባሳሰበኝ መንገድ ሁሉ ለአዳም ዘር ማድረስ ነዉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: በእግዚአብሔር ጥሪና አገልግሎትና ዉስጥ ማስመሰል፣ መሸንገል የለም:: እዉነቱን እዉነት፣ ሐሰቱን ሐሰት፣ እምነቱን እምነት፣ ክህደቱን ክህደት፣ ብርሃኑን ብርሃን፣ ጨለማዉን ጨለማ እንጂ «ተመሳስሎ ኑሮና ከራስ በላይ ንፋስ» የሚለዉ የአሕዛብ ፍልስፍና አይሰራም:: ዓለም ደግሞ እየተመራበት ያለዉ በዚህ አሕዛባዊ ወይንም እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች መመሪያና አስተሳሰብ ስለሆነ፤ ከዓለም የተለያየ ፈተናና ችግር እንዲሁም ተቃዉሞና ጥቃት ሊደርስቦት እንደሚችል ይታወቃል:: እንደገለጹልን የቤተሰብ አስተዳደሪና የልጆች አባት ኖት:: ታዲያ በእርሶ ላይ አንድ ችግር ሆነ ጉዳት ቢመጣ ከእርሶ ባለፈ ቤተሰቦ ሊቸገሩና ሊጎዱ አይችልም ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: መታወቅ ያለበት አንድ ሰዉ ራሱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ካሰለፈ ስለ እዉነት ራሱን መካድና መጥላት እንዲሁም ከቤተሰቡ፣ ከልጆቹ፣ ከዘመዶቹ፣ ከጋደኞቹ፣ ከስራዉ፣ ከሥልጣኑ፣ ከክብሩ፣ ከጥቅሙ፣ ከዝናዉ፣ ባጠቃላይ የእኔ ናቸዉ፣ ለእኔ ይሆኑኛል፣ ለእኔ ይጠቅሙኛል... ወዘተ ከሚላቸዉ በላይ እግዚአብሔን ማፍቀርና ለእግዚአብሔር ቅድሚ መስጠት ይጠበቅበታል:: ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ጥሪ ብቁ ሊሆን አይችልም:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሊጠብቅ ሆነ

ሊያገለግል ብቃት አይኖረዉም:: ምክንያቱም ከእግዚአብሔር በላይ ራሱን ከወደደና ለራሱ ሥጋና ደም ስሜት ቅድሚያ ከሰጠ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ መፈጸምና ማስፈጸም ይሳነዋል:: ተስፋዉን ምድር አደርጎ ስለሚመላለስ በማስመሰልና በሽንገላ ይመላለሳል፤ አንድ ፈተና ወይንም ችግር ቢያጋጥመዉ በጎቹን ለአዉሬ ትቶ ነዉ የሚሸሸዉ እንጂ ራሱን መስዋዕት አይደርግም::

እኔም እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለ እዉነት ራሴን በመካድና በመጥላት ነዉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ጥሪ ራሴን ያዘጋጀሁት:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ የሚመጣብኝን ማንኛዉም ፈተናና ችግር እርሱን አምባ መጠጊያ ኃይል አድርጌ እወጠዋለሁ በሚል እምነት ነዉ ከሁሉ በላይ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሴን አሳልፌ ያለሁት:: ምንም እንኳን በእኔ ላይና በቤተሰቤ ላይ ቀርቶ በማንም የአዳምና ሔዋን ዘር ላይ በደል፣ ግፍ፣ ጥቃት፣ በቀል፣ አድሎ፣ ግድያ፣ ስቃይ፣ ማሳደድ፣ መከራ፣ ፈተና ... ወዘተ እንዲደርስ አልፈልግም:: ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምክንያት በእኔም ሆነ በቤተሰቤ እንዲሁም በሌላዉም የተለያዩ መከራና ፈተና ቢመጣ ደግሞ በጸጋና በአኮቴት መቀበል እንዳለብን አምናለሁ:: በመሆኑም በተለይ ከራሴ በላይ በባለቤቴና በልጆች ላይ የሚፈጠረዉ ተጽህኖና ኀዘን እንዲሁም ችግርና ፈተና ከባድ ቢሆንም «ከእኔ በላይ አምላካቸዉና እዉነተኛ አባታቸዉ ያስብላቸዋል፣ መከታና ጋሻ ይሆናቸዋል» ብዬ ስለማምን፤ በእኔ ላይ አንድ ነገር ቢፈጠር እንኳ ምንም እንደማይሆኑ ይሰማኛል:: ሌላዉ መታወቅ ያለበት እግዚአብሔር ሳይፈቅድ ማንም የእግዚአብሔር አገልጋዮቹንና መልእክተኞቹን አንዳች ሊያደርጋቸዉ አይችልም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ ዐይን ብሌን ስለሚመለከታቸዉ፤ በሚደርስባቸዉ ፈተናና መከራ ሰማያዊ የድል አክሊልና ዋጋ እንዲያገኙበት ፈልጎ ለዓመፃ ልጆች አሳልፎ ካልሰጣቸዉ በስተቀር፤ ሁሉ ፍጥረት በእግዚአብሔር ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ በዓመፀኞችና ግፈኞች ላይ ከዐይን ቅጽበት ባነሰ ጊዜ ዉስጥ እርምጃ ሊወስድባቸዉና እንዳልነበሩ ሊያደርጋቸዉ ይችላልና::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ከእግዚአብሔር ጥሪ በኋላ እንደ ቀድሞዉ የተለያየ ብዙኃን መገናኛ (ማስ ሚዲያ) ይከታተላሉ ወይ? የሚከታተሉ ከሆነስ በሚመለከቱት፣ በሚሰሙት፣ በሚያነቡት ምን ይሰማዎታል? ምን ታዘቡ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ከእግዚአብሔር ጥሪ በፊት የተለያዩ ብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያ) አልከታተልም ማለት ይቻላል:: በአጋጣሚዎች ቴሌቪዥን እመለከት እንዲሁም ጋዜጣ አነብ ይሆናል እንጂ ስራዬ ብዬ የምከታተለዉ ዜና ሆነ ዝግጅት የለም:: አሁን ግን ከበፊቱ በተሻለ ዜናዎችንንና አንዳንድ ዉይይቶችን እከታተላለሁ፤ ጋዜጣ፣ መጽሔት በተወሰነ ደረጃ አነባለሁ:: እንዲሁም ቀደም ሲል አንዳች የማልጠቀምበት ኢንተርኔት በመጠቀመ በተለያየ ሕዋ ሰሌዳ(ድረ ገጽ) በተለያየ ብሎጎች ከኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን በተወሰነ ደረጃ እከታተላለሁ::

ቀድሞ የምመለከትበትና የማነብበት ዐይን አሁን ከምመለከትበትና ከማነብበት ዐይን ጋር አንድ ዓይነት ቢሆንም ማስተዋሌና መረዳቴ ግን ከፍተኛ ልዩነት አለዉ:: ይኸዉም ቀድሞ በቴሌቪዥን

የሚቀርበዉን ዘፈንና ዳንኪራ ስመለከት ነፍሴ ምንም የማይመስላትና የምትዝናናበት የነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን ዐይነ ሕሊናዬ በደንብ ስለተከፈተልኝ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍስ በሥጋ ተገልጻ በምን መልኩ እያበደችና ከሰዉነት ባሕርይ ወታ አንድነቷን ከርኩሳን መናፍስት ጋር እያደረገች መሆኑን ነዉ እምረዳዉ። በዚህም ምክንያት ከመዝናናት ይልቅ በማየዉ ነገር አዝናለሁ። ዲያብሎስ ሙሉ በሙሉ ትዉልዱን እንደተቆጣጠረዉ በማስተዋሌ ደግሞ የዲያብሎስ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ከዓለም ተደምስሶ የእግዚአብሐር ሥርዓት ብቻ በአራቱም ማእዘን እንዲዘረጋ እግዚአብሐርን እለት እለት እየጠየኩት እገኛለሁ።

በተለያየ ቻናል የሚቀርበዉ የዉጭ ፊልምና ዘፈን እንዲሁም ዳንኪራ በዓለም ላይ አእምሮ ሕጻናትና አእምሮ ቀላሎች እንደነገሡ እንዲሁም ትዉልዱን ሁሉ አእምሮ ሕፃንና አእምሮ ቀላል እንዳደረጉት፣ ከዛም ባለፈ ርኩሰት በዓለም ላይ በከፋ መልኩ መንገሡና ነዉሩ እንደ ክብርና ታላቅነት መቆጠሩ፣ ኃጢአቱ እንደ ጽድቅ መታየቱ፣ ዉርደቱና ጉስቁልናዉ እንደ ተጋድሎ መታየቱን በሚገባ ላስተዉል ችያለዉ። ከሚነበቡት ደግሞ ብዙዎቹ «ተመሳስለህ ኑር፣ ሕሊናህ ባይቀበለዉም ለመኖር ሕሊናህን ሽጥ፣ ስዉር ዓላማህን በወርቃማ አባባልና አቀራረብ ሸፍነህ አቅርብ... ወዘተ» በሚለዉ የአሕዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት መንፈስ መሪነት የሚጻፉና፤ እጅግ ጥቂቶቹ ደግሞ ያለዉን እዉነት ካለማስመሰልና ካለሽንገላ የሚያቀርቡ፤ አንዳንዶች ደግሞ  የሥጋና የደም ስሜታቸዉን የሚያቀርቡ፤ እጅግ ዉስኖች ደግሞ የእግዚአብሔርን እዉነት ብቻ ለይተዉ የሚያቀርቡ፤ ባጠቃላይ የተደበላለቀና አንድነት የሌለዉ ነዉ።

በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ቢሆን የእያንዳንዱ አቀራረብ ይዘትና ጥራት ይለያይ ይሆናል እንጂ ሁሉም ለእግዚአብሔር እዉነት ነበር የሚቆሙት። እንዲሁም ሁሉም መልካም ፍሬ የሚፈራበትን መንገድ ነበር የሚጠቁሙት። ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም ምድራዊ በረከት የሚገኝበት ሰላምን፣ ፍቅርን፣ አንድትን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ ቅንነትን፣ መልካምነትን፣ እዉተኛነትን፣ ባጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን ነበር የሚቀርብበትና ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊ ክብርና መንግሥት የሚያበቃ እዉነት ነበር የሚገለጽበት። ይሁንና ሥርዓቱ በበላይ በጨለማዉ ገዥ ስለሚመራ የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ሊቀርብበት አልቻለም።

ወደ ትዝብቱ ስመጣ በሚታየዉ፣ በሚደመጠዉ፣ በሚነበበዉ፣ አንዳንድ ሰዎች ምን ያህል ከሕሊናቸዉ በተቃራኒ መሰላፋቸዉና እንኳን የማይታየዉንና የማይዳሰሰዉን እግዚአብሔርን አይደለም የሚታየዉን ሰዉ አንዳች የማያፍሩና የማይፈሩ፣ ሕሊናቸዉን የሚሸጡ፣ እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚወሰዱ፣ እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብለዉ የሚነዱ ሰዎችን ላስተዉል ችያለሁ። በተቃራኒ ደግሞ እጅግ በጣት የሚቆጠሩ ለሕሊናቸዉ የታመኑ ቆራጥ ሰዎች መኖራቸዉን ተገንዝቤያለሁ። እንዲሁም እጅግ እጅግ በጣት የሚቆጠሩ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የታመኑ እዉነተኛ ሰዎች መኖራቸዉን ተረድቻለሁ። ባጠቃላይ ዓለም በተደበላለቀ ኑሮና ሕይወት አቋምና አስተሳሰብ እንዳለች በሚገባ ላስተዉልና ልገነዘብ ችያለሁ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: «እግዚአብሔር ሙሉ ሥልጣን እሰጥኃለዉ ጠይቅ?» ቢሎት ምን ዓይነት ሥልጣን እንዲኖሮት ነዉ የሚፈልጉት?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ይህን እድል እግዚአብሔር ቢሰጠኝ የምጠይቀዉ የአዳምና ሔዋን ዘሮች በሙሉ ቀን ከሌሊት የሚፈታተኑት እንዲሁም ጥቃት የሚፈጽሙትን ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናትን) ኃይላቸዉን ልምሾ ማድረግ፣ እንዲሁም ጨካኞቹን ሰይጣናት ደግሞ ልክ እነሱ ሽባ በሽተኛ እንድንሆን አድርገዉ እንደሚያበላሹን ሁሉ፤ እነሱን ማበላሸትና እንኳን ተመልሰዉ የአዳምን ዘር መፈታተንና ማጥቃት እንዲሁም ጉዳት ማድረስ አይደለም፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በራሳቸዉ ህልዉና ሊኖሩ በማይችሉበት ደረጃ ማበላሸት ነዉ። ምክንያቱም ለ7504 ዓመት በሰዉ ዘሮች ላይ ነግሠዉ ትዉልዱን ከአምላኩ እንዲጣላ አስደርገዋል፤ በዚህም ምክንያት ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ዳርገዋቸዋል፤ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉም በችግር፣ በመከራ፣ በስቃይ፣ በጉስቁልና ሕይወት እንዲኖሩ፤ እርሰ በእርስ እንዲጣሉ፤ እንዲገዳደሉ፣ እንዲጨካከኑ አስደርገዋልና ነዉ። ከፍርድ ቀን በኋላ ነጻነታቸዉ ሙሉ በሙሉ ተገድበዉ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ፍዳቸዉን ስለሚቀበሉ ነዉ እስከ ፍርድ ቀን ያልኩትም።» **በማለት ያልኖረበት ጊዜ የሌለ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር የሁሉ ፈጣሪና ጌታ የሆነዉ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ክፍል ሁለት

### ምዕራፍ አንድ

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ፈቃዶት ከሆነ በተለይ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ለተጻፉት የእግዚአብሔር መልእክት በተመለከተ ጸሐፊዉ እርሶ ስለሆኑ አንዳንድ ጥያቄዎችን ብናቀርብና ማብራሪያ ቢሰጡኝ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እዚህ ላይ አንድ ነገር ለመናገር እፈልጋለሁ:: ይኸዉም የእግዚአብሔር መልእክት የሚመለከተዉ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ሁሉ ጭምር እንጂ አንድ ግለሰብን ብቻ አይደለም:: ምክንያቱም ጸሐፊዉ አንድ ግለሰብ ቢሆንም ገላጨና አሳሳቢዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ሁሉ እግዚአብሔር በፈቀደላቸዉ መጠን መልእክቱን ሊያስተዉሉና ሊረዱ ይችላሉ:: ነቢያት እግዚአብሔር የገለጸላቸዉንና የተናገራቸዉን አንዳች ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ ጽፈዋል:: ነገር ግን ካልተፈቀደላቸዉ በቀር የጻፉትን ሆነ የተገለጸላቸዉን አያስተዉሉትም፤ አይረዱትም:: እንዲሁም ማንም ሰዉ መንፈስ ቅዱስ ካልገለጸለት በስተቀር በራሱ አንብቦ ትንቢቶቹን ሆነ ምስጢራቱን ሊያስተዉልና ሊረዳ አይችልም:: እርሱ እግዚአብሔር የፈቀደለት ሰዉ ብቻ ነዉ ትንቢቱንም ሆነ ምስጢራቱን እንዲሁም ራእዩን ሊያስተዉልና ሊረዳ የሚችለዉ:: ብዙዉን ጊዜ ትንቢቶቹ ከተፈጸሙ በኋላ ነዉ ትዉልዱ የሚያስተዉለዉ::

ጸሐፊዎቹ እነሱ በሚያዉቁት እዉቀት ደረጃና እንዲሁም እግዚአብሔር በሚገልጽላቸዉ እዉቀት ደረጃ ስለሆነ የሚጽፉት፤ በእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ በተለያየ አገላለጽ የተለያዩ እዉቀቶችና ምስጢራት ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ነገር ግን አይጋጩም:: እንደ ምሳሌ ባቀርብላችሁ አራቱን ወንጌላት የተጻፉት በአራት የተለያየ እዉቀትና ብቃት እንዲሁም ጠባይ ባላቸዉ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ባለሟሎች አማካይነት ነዉ:: መሪያቸዉ አንድ መንፈስ ቅዱስ ቢሆንም መልእክቱን ሲጽፉ ደግሞ በራሳቸዉ አገላለጽና እዉቀት ደረጃ ነዉ እንጂ በአንድ ዓይነት አገላለጽና አቀራረብ እንዲያቀርቡ አልተደረገም:: ፍቁረ እግዚእ የተባለዉ ቅዱስ ዮሐንስ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ምስጢረ መለኮትንና ምስጢረ ጥምቀትን፣ እንዲሁም ምስጢረ ቁርባንን እንዲያስተዉል ተደርጎ በተለየ ሁኔታ እግዚአብሔር አሳስቦት በወንጌሉ ሊጽፍ ችሏል:: እንዲሁም ስለእመቤታችን ክብርና የተለየ ጸጋ፣ የአደራ እናትነት እንዲያስተዉል ተደርጎ ዉኃዉ ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠበትን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምርና በመስቀሉ ስር ለአዳም ዘር በአደራ እናትንትና የአዳም ዘር በልጅነት እንደተሰጣት በተለየ ሁኔታ አቅርቧል:: ወንጌላዊዉም ማቴዎስ ከብሉይ ዘመን ትዉልዶች ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ያለዉን በዝርዝር በመግለጽ ወንጌሉን ጀምሯል:: ወንጌላዊዉ ማርቆስም በእዉቀቱ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ያሳሰበዉን ጽፎልናል:: ወንጌላዊዉ ሉቃስም ከቅዱስ ገብርኤል ብስራት ጀምሮ ያለዉን እንደ እዉቀቱና ብቃቱ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ያሳሰበዉን ጽፎልናል::

የሰዎች የእዉቀት ደረጃ መለያየቱን እንደምሳሌ ለማቅረብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱን የገለጸበትን የደብረ ታቦር ሁኔታን እንደመመልከታቸዉና እንደመስማታቸዉ እንዲሁም እንደ እዉቀት ደረጃቸዉና ብቃታቸዉ ሦስቱ ወንጌላዉያን በተለያየ አገላለጽ አቀርበዋል። ነገር ግን ሁሉም ብርሃነ መለኮቱ መገለጹን ነዉ ያሰፈሩት። ታዲያ ቅንነትና እዉነተኛነት ያልተላበሰ ሕሊና በእግዚአብሔር ቃሎችና መልእክታት ሊሰናከል ይችላል። ይኸዉም እንዴት እንደተጻፈ ስለማይረዳና ስለማያስተዉል ራሱ እግዚአብሔር እንደጻፈዉ በመቁጠር «የሁሉም አጻጻፍና አገላለጥ እንዲሁም አቆጣጠር አንድ ዓይነት መሆን አለበት» በማለት ነዉ። እግዚአብሔር፤ ነቢያት ሆኑ ሐዋርያት እንደ እዉቀታቸዉና መረዳታቸዉ እንዲጽፉ ያደረገዉ፣ ፈቃደኛ የሆነለትንና ለእርሱ ፈቃድ የሚመቸዉን ማንኛዉንም ሰዉ የእዉቀትና የተለየ ተሰጥኦን መለያ መስፈር ሳያበጅለትና አንድ ዓይነት መሆን አለበት ሳይል፤ እያንዳንዱ የተመረጠ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የሆነዉን እዉቀት ሆነ ምስጢር እንዲሁም ትንቢት በተለያየ ጊዜ እንደሚያቀርብ ትዉልዱ እንዲያስተዉል ነዉ። ያማ ባይሆን ከብሉይ ዘመን ጀምሮ ሁሉም አንድ ዓይነት አገላለጽና አቀራረብ እንዲኖረዉ ራሱ እግዚአብሔር እየጻፈ ለትዉልዱ ያስተላልፍ ነበር።

ከራሴ እዉቀት እንደ ምሳሌ ባቀርብ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ የተጻፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት በምጽፍበት ወቅት በብሉይ ዘመን እስራኤላዉያን በግብጽ በስደትና በባርነት የቆዩበት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ የሚለዉን ነዉ። እንዲሁም አራት መቶ የሚለዉን ነዉ። አሁን ደግሞ ሁለት መቶ አስራ አምስት ዓመት እንደሆነና አራት መቶ ቤት የተባለዉ ከአብርሃንም ዘመን ጀምሮ ሲቆጠር መሆኑን ሲያስተምሩና ሲጽፉ ሰመቻለሁ፣ አንብቤያለሁ። ነገር ግን አራት መቶ ሠላሳ ይባል፣ አራት መቶ ይባል፣ ሁለት መቶ አስራ አምስት ይባል፣ ነቢያት ሆኑ ሐዋርያት እንዲሁም ጻድቃን እንደዚህ የመሳሰሉ እዉቀቶችን ሲናገሩ ሆነ ሲጽፉ እነሱ በሚያዉቁት እዉቀት ደረጃ ነዉ። ትክክለኛዉን የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ። ለድኅነት ይህ እዉቀት ግድ አስፈላጊ ከሆነ ግን እግዚአብሔር መልእክቱን ለሚጽፉት አገልጋዮቹ «የዚህ ያህል ዘመን ነዉ» ብሎ ትክክለኛዉን ዘመን እንዲጽፉ ያደርጋል። እዉቀት ብቻ ከሆነ ደግሞ እዉቀት ድኅነት አይሆንምና ጸሐፊዉ እንደ እዉቀቱ ነዉ አሳስቦት የሚያጽፈዉ። መምህራንና ሊቃዉንት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በገለጸላቸዉ ደረጃ «ይህ የተባለዉ ለዚህ ነዉ፣ ያ የተባለዉ በዚህ ምክንያት ነዉ» ብለዉ ማሰረዳትና መግለጽ ይጠበቅባቸዋል እንጂ፤ እንደ ትምህረተ ሃይማኖት ቆጥረዉ ክፍፍልና መለያየት ማምጣት እንዲሁም እንድ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ለማስታረቅ መሄድ የለባቸዉም። ምክንያቱም ቀድሞም አልተጣሉምና። ቢጣሉ ኖሮ አጻፊዉ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ እንዲስተካከሉ ያደርግ ነበር።

እዚህ ላይ ዋናዉ ልናስተዉልና ልንረዳ የሚገባዉ በብሉይ ዘመን ሆነ በሐዲስ ዘመን የተጻፉት የእግዚአብሔር ቃሎችና መልእክታት እርሱ እግዚአብሔር እንዲጻፉ የፈቀደዉና የገለጸላቸዉ እንዲሁም በሚጽፉበት ጊዜ ያሳሰባቸዉን ነዉ። እንኳን በዚያ ዘመን አንድ ወጥ ትምህርት በማይሰጥበት ቀርቶ አሁን ዘመናዊ ትምህርት በስፋት በሚሰጥበት ዘመን እንኳ ስለ አንድ ነገር ጸሐፊዎች ተመሳሳይና አንድ አይነት የሆነ ጽሑፍ አያቀርቡም። እንደ እዉቀታቸዉ ደረጃና

ብቃታቸዉ ይለያያል፡፡ ምናልባት በአንድ አስተሳሰብ የሚመሩ ከሆነ አቀራረቡና አገላለጹ ቢለያይም ጽሑፋቸዉ ግን አይቃረንም፤ አይጋጭም፡፡ የእግዚአብሔር ቃልና መልእክት ደግሞ ገላጩና አሳሳቢዉ እንዲሁም አጻፊዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ አቀራረቡና አገላለጡ ቢለያይ እንኳ ፈጽሞ አይጋጭም፤ አይቃረንም፡፡

ሌላዉ ምሳሌ ደግሞ በመስከረም፳፻፫(2003) ዓ.ም «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ የተጻፈዉን የመጀመሪያዉን የእግዚአብሔር መልእክት በምጽፍበት ወቅት የነበረኝ የቃላት ሆነ የፊደል እዉቀት ደረጃ ሁለተኛዉን መልእክት «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ከተጻፈዉ ያንሳል፤ እንዲሁም ይህ ሦስተኛዉ መልእክት «ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ» በሚል እየተጻፈ ያለዉ ከባለፉት የቃላት ሆነ የፊደል እንዲሁም እዉቀት የተሻለ ነዉ፡፡ ለወደፊትም የምጽፋቸዉ ካሉ በእዉቀትና በምስጢር ደረጃ ሳይሆን በቃላትና በፊደላት እንዲሁም በሥርዓተ ነጥብ ካለፉት የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ ሕሊናዬ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ዉስጥ ሆኜ የምጽፈዉ ጽሑፍና በነጻ ሕሊናዬ እየተመራዉ የምጽፈዉ ጽሑፍ ደረጃዉ ሊለያይና ሊበላለጥ ይችላል፡፡ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ዉስጥ ስሆን መጻፍ የሌለበት እዉቀት ሆነ ምስጢር ቢኖር እንዳልጽፈዉ ስለሚያደርግና ብጽፈዉ እንኳ እንዳወጣዉ ስለምታዘዝ ነዉ፡፡ በራሴ ነጻ ሕሊና ፈቃድ ግን መጻፍ ስላለበትና ስለሌለበት ብዙ ላልጠነቀቅ እችላለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሰዉ ሊታረምና ሊስተካከል የሚችል እዉቀት ሊሆን ይችላል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነትና አሳሳቢነት እንዲሁም በትእዛዝ የሚጻፍን እዉቀት ሆነ ምስጢር እንዲሁም ትንቢት ማንም ሰዉ ሊያረመዉና ሊያስተካክለዉ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ እዉቀት ሙሉና ማስተካከያና እርማት የማይሰጥበት ነዉ፡፡ ነገር ግን የተሻሉ ቃላትንና አገላለጽ መጠቀም እንዲሁም የበለጠ ማብራራት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከግእዙ ጋር የሚጣጣሙ ፊደላትን መጠቀም ይቻላል፡፡ ዋና ፍሬ ሐሳቡን ሆነ መልእክቱን ግን እንኳን ሌላ ሰዉ ይቅርና መልእክቱን የጻፈዉ ግለሰብ እንኳ ሊያሻሽለዉና ሊለዉጠዉ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከእግዚብሔር የሆነዉን ከእግዚአብሔር በላይ ሆኖ ሊያርመዉና ሊያሻሽለዉ የሚችል ፍጡር የለምና፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የፈቀደለት ሰዉ እግዚአብሔር በገለጸለትና እንዲያዉቀዉ በሚፈልገዉ ደረጃ ሊተረጉምና ሊያስረዳ እንዲሁም ሊያብራራ ይችላል፡፡

ወደ አጻጻፌ ስመጣ የመጀመሪያዉን መልእክት ስጽፍ ስለፊደል ብዙ አልጠነቀቅም፣ ምክንያቱም ልዩነታቸዉንና ጥቅማቸዉን ብዙም አላዉቅም ነበርና፡፡ በሂደት ግን ስለ ፊደል ልዩነት በተወሰነ ደረጃ ሳዉቅ ራሴ የጻፍኳቸዉ የተሳሳቱ ፊደሎች እንኳ ይቀፉኛል፡፡ ምክንያቱም በትክክለኛዉ እዉቀት ሲመዘኑ ትርጉም አልባ ስለሚሆኑ ነዉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲያጽፈኝ የእዉቀቴን ደረጃ መስፈርት አድርጎ ስላልሆነ እኔም ሆንኩ ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች የመሃይመነቱን አጻጻፍ ሊቀበሉት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ማንም አይበልጥምና፡፡ እግዚአብሔር የመረጠዉን ማንም ሊያጣጣል ሆነ ሊንቅ አይቻለዉምና፡፡ ይሁንና ያንን አላዋቂ ግን በሂደት ወደ ሙሉ እዉቀት ለማብቃት ግን እያንዳንዱ ሰዉ እንደ አቅሙ የሚቻለዉን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ አላዋቂዉም ሰዉ ድክመቱንና አላዋቂነቱን በሚገባ ተረድቶ ራሱን ለሙሉ እዉቀት ማዘጋጀት ይጠበቅበታል እንጂ

እግዚአብሔር ስላጻፈኝ ሌላ እዉቀት ሆነ ትምህርት አያስፈልገኝም ማለት የለበትም። በቁጥር በኩልም በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ የኢትጵያን ቁጥር ሙሉ በሙሉ አልተጠቀምኩም። ምክንያቱም ስጽፍ የለመድኩት የአረብን ቁጥር ስለሆነና ለራስ ቅርስና ማንነት ብዙ ትኩረት ባለመስጠቴና ለመጻፍም ስለሚቀለኝ ነዉ። እንዲሁም ዘመናዊዉ የትምህርት አሰጣጥ ማንነቴን ወይንም ኢትዮጵያዊነቴን እንዳጣና የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዉያን ለሆነዉ እዉቀት ሆነ የማንነት መገለጫ ብዙም ስሜት እንዳይኖረኝ አድርጓል። በሂደት ግን ወደ ራስ ማንነቴ ስመጣ ለራሴ ቅርስ ትኩረት መስጠትና ቁጥሮቹንም በደንብ ለማወቅ ቻልኩ። ብዙዎች የኢትዮጵያን ቁጥር ስለማያዉቁ ነዉ በሁለተኛዉ መልእክት ላይ በቅንፍ ዉስጥ የአረብኛዉን ቁጥር የጻፍኩት።

ሌላዉ እንደ ምሳሌ የማቀርበዉ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ስጽፍ ስለ ቅዱሱ ኪዳን አንዳች እዉቀት አልነበረኝም። ያ ማለት ደግሞ ከእኔ እዉቀት ወጭ ነዉ እንጂ ቅዱሱ ኪዳን በእግዚአብሔር ሆነ በሌሎች አገልጋዮች የሚታወቅ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፤ አሁን ደግሞ ለትዉልዱ በግልጽና በይፋ የቀረበ ነዉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር እያንዳንዱን ምስጢር ሆነ እዉቀት እንደትዉልዱ የመራዳትና የእዉቀት ደረጃ እንዲሁም ቅንና እዉነተኛ ልቦና መሰረት ነዉ የሚገልጽዉና እርሱ በፈቀደ ወቅትና ጊዜ ዉስጥ ነዉ ለኢትዮጵያዉያን ሆነ ለዓለም ሕዝብ በሚገባቸዉ መልክ እንዲገለጽ የሚያደርገዉ። በዚሁ መሰረት በመጀመሪያዉ መልእክት መጨረሻ ላይ እኔም እንዳዉቀዉ ተደርጎ በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ በተወሰነ ደረጃ እንድመሰክር የተደረገዉ። በመጀመሪያዉ መልእክት ላይ ስለ ኢትዮጵያ እና ስለ ኢትዮጵያዊነት አንዳች እንዳልቀባጥር መንፈስ ቅዱስ የተቆጣጠረኝና አንዳች ስለ ኢትዮጵያዊነት እንዳልጽፍ ያደረገዉ፤ በዚያን ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ እና ስለ ኢትዮጵያዊነት የነበረኝ እዉቀት ያልተሟላና ጎዶሎ ቢበዛ የሦስት ሺህ ዓመት ታሪክ እንጂ የ7500 ታሪክ አንዳች እዉቀት ያልነበረኝ በመሆኑ ነዉ። እንዲሁም በእግዚአብሔር፣ በእዉነተኛ አገልጋዮቹና ባለሟሎቹ ዘንድ በተሟላ መልኩ መገለጹን ስለሚያዉቅ ነዉ በመጀመሪያዉ መልእክቱ አንዳች እንዳላነሳ ያደረገዉና ወደ ሙሉ እዉቀት ያመጣኝ።

እዚህ ላይ ሕሊናዉ ቅንነትና እዉነተኛነት የጎደለዉና ጠማማነት የሞላዉ ሰዉ በእግዚአብሔር ቃልና መልእክት ይሰናከላል እንጂ ሕይወትን አያተርፍበትም። ምክንያቱም በሚያነብበት ወቅት ሕሊናዉ ንቁ የሚሆነዉ ከጽሑፎቹ ዉስጥ ተቃራኒ ወይንም ለእርሱ የሚስማማ ጥቅስ ነዉ የሚፈልገዉ እንጂ፤ በእግዚአብሔር ቃል ሊታነጽበትና ሊማርበት አይደለም። በዚህ ሕይወት ዉስጥ በብዛት የሚገኙት ደግሞ በተለያየ እምነት መሰል ድርጅቶች ዉስጥ በአገልግሎት ሆነ በአማኝነት ዉስጥ የሚመላለሱ ናቸዉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ አንድ ምሳሌ ባቀርብ፡ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ፪(2)÷ ቁጥር ፵፰(48 )ላይ «ልጄ ሆይ÷ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን አለችሁ።» ይላል።

ከዚህ ጽሑፍ የምንረዳዉ ጸሐፊዉ ቅዱስ ሉቃስ እመቤታችን ለልጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረችዉን ቃል በቃል ነዉ የጻፈዉ እንጂ «ቅንነትና እዉነተኛነት የጎደለዉ ጠማማ ትዉልድ ሊነሳ ስለሚችልና ቃላትና ሐረግ  እንዲሁም ዐረፍተ ነገር እየመረጠ በእግዚአብሔር ቃል ሊሰናከልና

ሊወድቅ ይችላል» በማለት የእመቤታችንን አባባል አላሻሻለዉም። ይኸዉም አረጋዊዉ ቅዱስ ዮሴፍ በራሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አሳዳጊ እንጂ አባት እንዳልሆነ ይታወቃል፤ ቅንነትና እዉነተኛነት የሞላዉ ሕሊና ይህን በደንብ ያስተዉላል። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ካለአባት ነዉና ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰዉ የሆነዉ። ነገር ግን ከእናቱ ድንግል ማርያም ጋር ሆኖ እንደ አባት ስላሳደገዉ የአባትነት ክብር ተሰቶት «አባት» ተብሎ ተጠራ። በርኩሳን መናፍስት መንፈስ የሚመራ ጠማማ ሕሊና ያለዉ ሰዉ ግን «ይኸዉ በመጽሐፍ ቅዱስ በምእራፍ፪÷ በቁጥር ፵፰ ላይ በግልጽ አባት ተብሎ ተጠርቷል፤ ለዚያዉም በእናቱ ማርያም» በማለት ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባዉና «ኢየሱስ ክርስቶስ የዮሴፍ ልጅ ነዉ» ሊልና በጽሑፉ ተሰናክሎ ሌላዉንም ሊያሰናክል ይችላል። ለዚህም ነዉ ሰዎች መሪያቸዉን የዲያብሎስን መንፈስ አድርገዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ቃል በማዉጣትና መመሪያ በማድረግ በብዙ ሺህ «እምነቶች» በየጊዜዉ እየተፈጠሩ ያሉትና የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች ለዲያብሎስ እየተገበሩ የሚታየዉ።

እንደዚህ የመሳሰሉ ሌሎች ምሳሌዎችን ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ቅንነት ላለዉ ሰዉ እንዳይሰናከል አንዷ ፍሬ ሐሳብ ሊበቃዉ ይችላል። ቅንነት ለሌለዉና የሚሰናከልበትን ለሚፈልግ ደግሞ መጽሐፍ ያክል መረጃ ቢቀርብለት ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም። ምክንያቱም እዉነትን ሳይሆን የሚፈልገዉ የራሱን ስሜት ብቻ ስለሚያዳምጥና በራሱ የዉሸት እዉነት ለመኖር የወሰነ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ማስተዋልንና ማወቅን አያገኝም። እንግዲህ በቅንነትና በእዉነት የእግዚአብሔርን ምስጢርና መልእክት ለመረዳትና ለማስተዋል ለሚቀርብልኝ ጥያቄ እግዚአብሔር ባሳወቀኝና በገለጸልኝ መጠን አብራራለሁኝ። አንዳንዶቹን ትንቢቶችና ምስጢራት በምጽፋቸዉ ጊዜ የተረዳዋቸዉ እንዳሉ ሁሉ አንዳንዶቹን ደግሞ ከጻፍኳቸዉ በኋላ ከተወሰነ ቀናትና ወራት በኋላ ሲሆን፤ አንዳንዶቹን ደግሞ ትንቢቶቹና አባባሎቹ ተፈጽመዉ ሲገኙ ነዉ በደንብ ያስተዋልኳቸዉ።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: እንግዲህ ፈቃዶት መሆኑን ስለተረዳን የመጀመሪያ ጥያቄዬ በመጀመሪያዉ ሆነ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ብዙ ቦታ ላይ በሰዉ ልጆች ላይ ስለተከሰቱት ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይና፣ ስለ ጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ምንነታቸዉንና ምክንያታቸዉን ቢያብራሩልን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ለዚህ ጥያቄ ምልሻ ከመጀመሪያዉ ሥነ ፍጥረት በመጀመር እገልጽላችኋለሁ። ወደ ዝርዝር ጉዳይ ከመግባቴ በፊት በቀጣይ የምገልጻቸዉ የእግዚአብሔር እዉነታዎችን፣ የተለያዩ እዉቀቶችንና ምስጢራትን በደንብ እንድትረዷቸዉ በእኔም ሆነ በሌሎች የእግዚአብሔር አገልጋዮች ዘንድ ቀደም ሲል የማይታወቁ ቃላቶችን በማብራራት እጀምራለሁ።

**አማናዊ ባሕርይ**: የሚባለዉ የነበረ፣ ያለ፣ ለወደፊትም የሚኖር፣ የሌለበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር የእግዚአብሔር ባሕርይ ነዉ።

**አማናዊ ሕዋ**: የሚባለዉ ምንም ፍጥረት ከመፈጠሩ በፊት የነበረ፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉና እግዚአብሔርም እንደ አማናዊ ባሕርይዉ የሚኖርበት ቦታ ነዉ። በአሁን ሰዓት በዉስጡ አራት አማናዊ ያልሆኑ ምሳሌያዊ ቦታዎች አሉ። እነሱም ሰማያት፣ ዓለም(ምድርንና ገነትን የያዘች)፣ ሲኦል እና ማረፊያ ቦታ ናቸዉ። በፍረድ ቀን ዓለም፣ ሲኦል ማረፊያ ቦታ ከመኖር ወደ አለመኖር ሲያልፉ በምትካቸዉ ገሃነመ እሳት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ይዘጋጃል።

**አማናዊ ፍጥረት**: የሚባለዉ ከነበረ፣ ካለ፣ ሕያዉ ሆኖ ከሚኖር ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተገኘ፤ ከመኖር ወደ አለመኖር የማያልፍ ሕያዉ ፍጥረት ነዉ። አማናዊ ፍጥረት የምትባለዉ የመናፍስትና የሰዎች ነፍስ ብቻ ናት። እነዚህ ነፍሳት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የሰረጹ(የወጡ) ስለሆነ እግዚአብሔርን መምሰል ብቃት ያላቸዉና እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነዉ መኖር የሚችሉ ፍጥረታት ናቸዉ።

**ብርሃናዊ ባሕርይ**: የሚባለዉ እግዚአብሔር ለሕያዉ ፍጥረቶቹ ባሕርይዉን ወስኖ የሚገለጽበት ረቂቅ አካሉ ሲሆን፤ እስከ አሁን ድረስና እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ይህን የራሱን ባሕርይ ጸጋ ለአንድ ነፍስ ብቻ ነዉ የሰጠዉ።

**ምሳሌያዊ ባሕርይ ፍጥረት**: የሚባለዉ ቀድሞ ያልነበረ፣ በሕያዉነት ዘመን ዉስጥ እግዚአብሔር በኃይሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣዉ፣ በፈለገ ጊዜም ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፈዉ የሚችል ፍጥረት ነዉ። ይህ ምሳሌያዊ ባሕርይ ረቂቅ ስለሆነ በሥጋ የተገለጸ ሰዉ(ነፍስ) ሊመለከተዉ የማይችል ነዉ።

**ምስሌያዊ ፍጥረት**: የሚባለዉ አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ሁለት ሕያዋን ነፍሳት በገነት ዉስጥ «አታድርጉ» የተባሉትን ትእዛዝ በመጣስ በማመጻቸዉ ምክንያት በዚህች ምድር ዉስጥ ከምሳሌያዊ ባሕርይ ፍጥረት ቀጥሎ የተፈጠረ ነዉ። እነዚህ ፍጥረታት እንደ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቀድሞ ያልነበሩ፣ በሕያዉነት ዘመን ዉስጥ እግዚአብሔር በኃይሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸዉ፣ በፈለገ ጊዜም ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፋቸዉ የሚችል በሥጋዊ ዐይናችን የምናያቸዉ ማንኛ ዉም ፍጥረታት ናቸዉ።

**አማናዊ ብርሃን**: የሚባለዉ እርሱ እግዚአብሔር በብርሃናዊ ባሕርይዉ የሚያበራዉ ብርሃን ነዉ። ይህም ያለዉ በሰማያትና በገነት ዉስጥ ብቻ ነዉ።

**ምሳሌያዊ ብርሃን**: የሚባለዉ ከምሳሌያዊ ባሕርይና ከምሳሌያዊ ፍጥረት የሚገኝ ብርሃን ነዉ። በማረፊያ ቦታ የሚገኘዉ ብርሃን ከረቂቁ ምሳሌያዊ ባሕርይ ሲሆን፤ በምድር ዉስጥ የሚገኘዉ ደግሞ በሥጋዊ ዐይናችን ከምንመለከታቸዉ ከፀሐይ፣ ከጨረቃ እንዲሁም ከሰዉ ሰራሽ ቁሳቁሶች ወይንም ኃይሎች ነዉ። ለምሳሌ ከኩራዝ፣ ከሻማ፣ ከአምቦል ከመሳሰሉት ነዉ።

***ምሳሌያዊ ጨለማ***: የሚባለዉ ከምሳሌያዊ ባሕርይ የሚገኝ በሲኦልና በምድር ዉስጥ የሚታይ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ረቂቅ ጨለማ ነገር ነዉ::

***ምሳሌያዊ ሕዋ***: የሚባለዉ ከምሳሌያዊ ባሕርይ የተዘጋጀ ይህ በዐይናችን የማናየዉና ምን እንደሆነ የማናዉቀዉ ክፍት ቦታ ሁሉ ነዉ::

***አማናዊ ድምፅ***: የሚባለዉ በእያንዳንዱ ሕያዉ ፍጥረት በሕሊናዉ(በነፍሱ) የሚታሰበዉ ነዉ:: ምክንያቱም እንደታሰበ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ እግዚአብሔር በፈቀደለት ፍጥረት ያ የታሰበዉ ነገር በድምፅ መልክ ይሰማልና ነዉ::

***ምሳሌያዊ ድምፅ***: የሚባለዉ በምሳሌያዊ ባሕርይ ሆነ በምሳሌያዊ ፍጥረት የተገለጹ ፍጥረታት በአንደበታቸዉ የሚነገርና የሚወጣ በተገለጹት ረቂቅ ጆሮና በሥጋዊ ጆሮ የሚደመጥ ድምፅ ነዉ::

***እግዚአብሔር፣ ፈጣሪ፣ አዶናይ፣ ኤልሻዳይ፣ ያህዌህ***: የምንለዉ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፤ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር፤ መጀመሪያና መጨረሻዉ (አልፋና ዖሜጋ) የሆነዉ አምላክ፤ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ ቦታ «አማናዊ ሕዋ» በመባል በሚታወቀዉ ዉስጥ እንደ ረቂቅነቱ ባሕርይ ብቻዉን ይኖር ነበር:: በሕያዉነት አኗኗር ዘመን ዉስጥ በእኛ ሕሊና ሊታወቅ ቀርቶ ሊታሰብ በማይቻልበት ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ክብሩ ብቻዉን እንደቀረ አዉቆ የባሕርይዉ ተካፋይ የክብሩ ወራሽ የሚሆን ሕያዉ ፍጥረት ለመፍጠር ወሰነ:: በዚህም ምክንያት የዛሬ ፯፻፭ (7505) ዓመት ገዳማ የመጀመሪዉን ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ ሰማያትን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ:: ከዚያም እልፍ አእላፋ ወትልፊት( የትሪሊዮን ትሪሊዮን) የሆኑ መናፍስት ከባሕርይዉ አስርጾ(አዉጥቶ) ካለመኖር ወደመኖር አመጣቸዉ:: ረቂቅ አካላቸዉ በሌላ ረቂቅ አካል በሆነዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ እንዲገደብና እንዲገለጹ አደረገ:: እያንዳንዱም የራሱ መልክ፣ አካል፣ ስም እንዲኖረዉ አደረገ:: በመጨረሻም በሰማያት ዉስጥ አንዲገቡ ተደረገ:: እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረዉ አማናዊ ባሕርይዉ ብቻ በአማናዊዉ ሕዋ ዉስጥ መኖሩን ቀጠለ::

*ታዲያ ራሳቸዉን በሰማያት ዉስጥ ያገኙት እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መናፍስት ካለመኖር ወደመኖር ያመጣቸዉንና በዚያ መልክ፣ አካል፣ ስም እንዲገለጹ ያደረገዉን ፈጣሪያቸዉን ሲፈልጉና ማንነቱን ለማወቅ ሲመኙ፤ ለሁሉ የበላይ አለቃ እንዲሆን የተፈጠረዉ «ሳጥናኤል» በመባል የሚታወቀዉ መናፍስት፤ እርሱ የተገለጸበት አካል ከሌሎቹ ገዝፎ ስለታየዉና ከሁሉ በላይ እንደሆነ ተሰምቶት «እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ፣ እኔን አምልኩ» አለ:: ይሁንና እጅግ እጅግ እጅግ የበዙት መናፍስት ሕያዉ ነፍሳቸዉ(ሕሊናቸዉ) እርሱ እንደነሱ እንደሆነና እርሱ እንዳልፈጠራቸዉ ስለመሰከረባቸዉ አልተቀበሉትም:: አንዳንዶቹ መናፍስት ቅዱስ ሚካኤል በመባል የሚታወቀዉ ደግሞ አለመቀበል ብቻ አይደለም በግልጽ ተቃዉሞ በማሰማትና ማንም መናፍስተ እርሱን እንዳይቀበልና እንዳያመልክ ትዕዛዝ ሰጠ:: ቅዱስ ገብርኤል በመባል የሚታወቀዉም መናፍስት አለመቀበል ብቻ አይደለም እርሱ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣቸዉ አምላክ በግልጽ እስከሚገለጽ ድረስ ባሉበት እንዲጸኑና በትዕግስት እንዲጠብቁ ትእዛዝ ሰጠ:: እንዲሁም ሌሎች መናፈስት እነሱን*

ተከትለዉ ሳጥናኤልን እንደማይቀበሉና እንደነሱ ፍጡር መሆኑን መሰከሩበት፡፡ ከጸኑት አንጻር አንድ መቶኛ እንኳ የማይሞሉት እልፍ አእላፋት( በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩት መናፍስት ደግሞ «ሳጥናኤል ነዉ አምላካችን» በማለት ተቀበሉት እንዲሁም እልፍ አእላፋት(በቢሊዮኖች) የሚቆጠሩት ደግሞ በጥርጣሬ «ሊሆንም ላይሆንም ይችላል» በማለት በሁለት አቋም ዉስጥ ተገኙ፡፡ በዚህን ጊዜ ሁከትና ሽብር በሰማያት ዉስጥ ተፈጠረ፡፡ በምሳሌያዊ ባሕርይ በተገለጸዉ አንደበታቸዉ የሚነገረዉን ንግግራቸዉን ብቻ አይደለም በዉስጥ ነፍሳቸዉ(ሕሊናቸዉ) እየታሰበ ያለዉን ሐሳባቸዉን ጭምር የሚያዳምጠዉ ፈጣሪ አምላክ ለመጀመሪያ ጊዜ ረቂቅ ባሕርይዉን ወስኖ ሊረዱት(ሊያዉቁት) በሚችሉት መልክ በብርሃናዊ ባሕርይ በመገለጽ በመሃከላቸዉ ተገኘ፡፡

ከዚያም ለአለቅነት ተመርጦ የነበረዉን «ሳጥናኤል» በመባል የሚታወቀዉን መናፍስት ጽጋዉን ገፎ ዲያብሎስ የሚል ስያሜ ሰጠዉ፡፡ እርሱን የተቀበሉትን እልፉ አእላፋት(በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ መናፍስትን እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ጸጋቸዉን ገፎ ርኩሳን መናፍስት ተባሉ፡፡ በሁለት አቋም በጥርጥር ዉስጥ የነበሩትንም እልፉ አእላፋት(በቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ መናፍስት እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ጸጋቸዉን ገፎ የዲያብሎስ ተከታዮች ተጠራጣሪ ርኩሳን መናፍስት ተባሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለተኛዋ ምሳሌያዊ ቦታ ዓለም ተፈጠረች፡፡ ልክ በአንድ መስክ ብዙ እንስሳትን አሰማርተን ከመሃከላቸዉ አንድ ወይፈን ወይንም በሬ ሌሎቹን ቢያዉክና ቢረብሽ ወዲያዉ ከመሃከላቸዉ እሱንና እርሱን ተከትለዉ የሚያዉኩትን ከሌሎቹ እንደምንለይና ለብቻቸዉ እንደምናደርግ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም ሁከት ፈጣሪዎቹንና ረባሾቹን መናፍስት ከሰማያት ዉስጥ በማዉጣት በዓለም ዉስጥ ምድር የተባለች ትንሽ ቦታ ተፈጥራ በድቅድቅ ጨለማ እንድትሞላ ተደርጎ ዲያብሎስና ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ወደ እዚህች ምድር ተጣሉ፡፡

በእምነታቸዉ የጸኑት እልፉ አእላፋት ወትእልፊት (የትሪሊዮን ትሪሊዮን) መናፍስት ደግሞ ቅዱሳን መናፍስት ተብለዉ ባሳዩት ጽናትና ሳጥናኤልን በተቃወሙት ብቃት ደረጃ ማዕረግና ክብር ተሰቷቸዉ በሰማያት ዉስጥ ኖሮዋቸዉን ቀጠሉ፡፡ እግዚአብሔርም በዚያ በተገለጸላቸዉ ብርሃናዊ ባሕርይ ባሕርይዉን ወስኖ በእዉነትና በመንፈስ መመለክ ጀመረ፡፡ ቅዱስ ሚካኤልም ባሳየዉ ቆራጥነትና ጽናት በሳጥናኤል ምትክ ለሁሉ አለቃ እንዲሆን ተሾመ፡፡ ቅዱስ ገብርኤልም ባሳየዉ ቆራጥነትና ጽናት ሁለተኛ አለቃ ሆኖ ተሾመ፡፡ ሌሎቹም እንዳሳዩት ቆራጥነትና ጽናት የሥልጣን ማዕረግ ተሰቷቸዉ እንደ ባለሟልነታቸዉ ደረጃ በሰማያት ዉስጥ እግዚአብሔርን እያመለኩ መኖራቸዉን ቀጠሉ፡፡

እግዚአብሔር ወደ ምድር በተጣሉት ርኩሳን መናፍስት ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት ለመፍጠር ወስኖ በዓለም ዉስጥ ከምድር ጎን ገነትን አዘጋጀ፡፡ ከዚያም እንደ መጀመሪያዎቹ መናፍስት ዓመፃና ክህደት እንዳይፈጸምበት፤ በመጀመሪያ ፍጥረታት(በአዳምና ሔዋን) አማካይነት ከእርሱ ባሕርይ የሚሰርጹት ነፍሳት በሁለቱ ነፍሳት ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት ካለመኖር ወደመኖር እንዲመጡ ለማድረግ አስቦ ሁለት ነፍሳት ከባሕርይዉ በማስረጽ ካለመኖር ወደመኖር አምጥቷቸዉ በገነት ዉስጥ አኖራቸዉ፡፡ እንደ ቀድሞ መናፍስት ካለመኖር ወደ መኖር

ያመጣቸዉን ፈጣሪ በነጻ ሕሊናቸዉ በመፈለግ እንዳይቸገሩና የዓመፃና የክህደት ሐሳብ እንዳይመጣባቸዉ በማሰብ በግልጽ በብርሃናዊ ባሕርይዉ በመገለጽ የገነት ዉስጥ አኗኗራቸዉን በግልጽ አስረዳቸዉ:: ሌሎች ነፍሳት ቁጥራቸዉ ወደምድር ከተጣሉት ርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆን ድረስ በእነሱ በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት በሂደት በገነት ዉስጥ እንደሚገለጹ፤ የሁሉም ወላጆች እንደሚሆኑ፤ እንዲሁም ቁጥራቸዉ ከርኩሳን መናፍስት እኩል በሚሆንበት ጊዜ ወደ ሰማያት ዉስጥ እንደሚገቡና በቅዱሳን መላእክት አኗኗር እንደሚኖሩ፤ በገነት ዉስጥ ስራቸዉም እርሱን በእዉነትና በመንፈስ እያመለኩና እያመሰገኑ መኖር ብቻ እንደሆነ፤ በእነሱ ምሳሌያዊ ባሕርይ አማካይነት ካለመኖር ወደ መኖር የሚመጡትን ነፍሳት አባትና እናት በመሆን በኃላፊነትና በአስተማሪነት እንደ እግዚአብሔር ልጅነታቸዉ መጠበቅ እንዳለባቸዉ፤ የመጨረሻ ተስፋቸዉን መንግሥተ ሰማያት በተስፋ እንዲጠባበቁና አምልኳቸዉን ባግባቡ እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ አዘዛቸዉ:: በመጨረሻም ለመገዛታቸዉና በእዉነትን በመንፈስ ማምለካቸዉ የሚገለጽበትን ከሌሎች ፍጥረታት በተለይ ሁኔታ አንዲት ዕፀ በለስ ፈጥሮ እርሷን እንዳይበሉ፣ ከበሉ ግን የሞት ሞት እንደሚሞቱ፣ ከገነትም እንደሚወጡ ገልጾላቸዉ ተለያቸዉ:: እነሱም በተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) የገነት ኑሯዋቸዉን መኖር ቀጠሉ:: በዚያም ስራቸዉ የነበረዉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መኖር እንጂ ለተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ ሆነ ለነፍሳቸዉ አንዳች የሚሰሩት ነገር አልነበረም:: የሚመገቡት ሆነ የሚጠጡት ፍጥረታት ሁሉ ከምሳሌያዊ ባሕርያቸዉ ጋር ልክ እንደ አየር የሚዋሃድ እንጂ እንደዚህ ምድራዊ ሕይወት ምሳሌያዊ ፍጥረት አልነበረም:: ሁሉም ረቂቅ ነገሮች ነበሩ::

ወደ እዚህች ምድር ዉስጥ ተጥለዉ በድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ እየተቀጡ ያሉት ዲያብሎስና ሰይጣናት በእነሱ ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት ከጎናቸዉ ባለችዉ ገነት ዉስጥ መፈጠሩን ተረድተዉ በቅናት ይቃጠሉ ነበር:: የመጀመሪያ የገነት ፍጥረት የነበሩት ሁለቱ ነፍሳት የእምነታቸዉ ጽናትና አቋም ይታይ ዘንድ ግድ ነበርና ዲያብሎስም በተገለጸበት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ፈቃድ አግኝቶ ወደ ገነት ገባ:: በዚያም በመጀመሪያ ያገኛት ነፍስ በምድራዊ ስሟ ሔዋን በመባል የምትታወቀዉን ሲሆን፤ ስለ ገነት አኗኗራቸዉ ጠየቃት:: እርሷም እንደነሱ በምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) የተገለጸ ነበርና አንዳች ጥርጣሬ ሳያድርባት እግዚአብሔር ያላቸዉን በሙሉ ነገረችዉ:: እርሱም ክፋትና ተንኮል የሞላበት ነበርና ከእግዚአብሔር በላይ አዋቂ መስሎ በመታየት «ይህች አትብሉ የተባላችሁትን ብትበሉ እንደሱ እንደምትሆኑና ልክ እርሱ እንደተገለጸበት ብርሃናዊ ባሕርይ እንደምትገለጹ አዉቆ ነዉ እዳትበሉ ያላችሁ እንጂ ሞት የሚባል አያገኛችሁም፤ ይህን የነገርኳችሁ በግልጽ ሁሉን ስለነገርሽኝ ነዉ» በማለት በምኞት እንድትቃጠል አድርጎ ወደ ምድር ተመለሰ::

እርሷም ከእነሱ በላይ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾ የተናገራቸዉን ተግባራዊ ማድረግ ሲጠበቅባት በተቃራኒዉ እንደነሱ በምሳሌያዊ ባሕርይ የተገለጸዉን ፍጡሩን በመስማትና በማመን በምኞት ተሸንፋ ያ ያልተፈቀደላቸዉን ከምሳሌያዊ ባሕርይ የተፈጠረዉን ፍሬ በመብላት በምድራዊ ስሙ አዳም በመባል ለሚታወቀዉ ዲያብሎስ ያላትን ሁሉ በመንገር ለመብል ጋበዘችዉ:: እርሱም በመጀመሪያ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾና ካለመኖር ወደመኖር አምጥቷቸዉ በገነት ያኖራቸዉን

አምላክ ትእዛዝ መጠበቅ ትቶ፤ እርሱም በምኞት ተሸንፎ «አትብሉ» የተባሉትን ፍሬ በመብላት በጋራ ዓመፃና ክህደት ፈጸሙ።

በዚህ ጊዜ ጸጋቸዉ ተገፈፈ፤ ባዶነት ተሰማቸዉ፤ ኀዘን መጣባቸዉ፤ ተጨነቁ፤ ሰጉ። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተግባራቸዉንና ሐሳባቸዉን ሲከታተልና ሲሰማ የነበረዉ ፈጣሪያቸዉ እግዚአብሔር መጀመሪ በሚያዉቁት ብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾ ለምን ያዘዛቸዉን እንዳልጠበቁ ጠየቃቸዉ። አዳም በመባል የሚታወቀዉ የመጀመሪያዉ የገነት ፍጡር ነፍስ ሔዋን በመባል የምትታወቀዉ ነፍስ እንዳሳሳተችዉ ገለጸ። ሔዋን በመባል የምትታወቀዉ ነፍስ ደግሞ አንድ የማታዉቀዉ እንደሷ በምሳሌያዊ ባሕርይ የተገለጸ ዲያብሎስ በመባል የሚታወቀዉ እንዳሳሳታት ገለጸች። ይሁንና ሁለቱም ነፍሳት የመቀበልም ያለመቀበልም ነጻ ፈቃድና ነጻ ሕሊና ስላላቸዉ በነጻ ፈቃዳቸዉ ተጠቅመዉና በምኞት ተሸንፈዉ ዓመፃና ክህደት ስለፈጸሙ እንደ ርኩሳን መናፍስት ጸጋቸዉ ተገፎና ዓመፃቸዉ ከርኩሳት መናፍስት በላይ ስለሆነ፤ ይኸዉም ርኩሳን መናፍስት በሰማያት ዉስጥ ሲያምፁ ምንም እንኳን ከእነሱ በላይ የሁሉ ፈጣሪ እንዳለ ሕሊናቸዉ እየመሰከረባቸዉ ቢሆንም፤ በግልጽ እግዚአብሔርን አልተመለከቱም፤ በግልጽ «እንዲህ አታድርጉ፣ እንዲህ አድርጉ» አልተባሉምና። አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ነፍሳት ግን በግልጽ እግዚአብሔር በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾና ተናግሯቸዉ ሕሊናቸዉም ማድረግ እንደሌለባቸዉ እየመሰከረባቸዉ ሕሊናቸዉን በማደንደን «አትብሉ» የተባሉትን በድፍረት በመብላታቸዉ ነዉ።

በአዳምና ሔዋን የገነት ዓመፃ ምክንያት ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ የነበረችዉና የሰይጣናት መቀጫ ብቻ የነበረችዉ ምድር ለሁለተኞቹ ዓማፅያን ጭምር መቀጫ እንድትሆን አሁን በምድር የሚታዩትም የማይታዩትም ምሳሌያዊ ባሕርይና ምስሌያዊ ፍጥረታት ካለመኖር ወደ መኖር ሊመጡ ችለዋል። ለምሳሌ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ አየር፣ ንፋስ፣ ዉኃ፣ መሬት፣ እፀዋት፣ አዝርዕት፣ አእዋፋት፣ እንስሳት … ወዘተ በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ፍጥረታት ጭምር ነዉ። እነዚህ ፍጥረታት ተፈጥረዉ ካለቁ በኋላ ፀሐይና ጨረቃ ከተፈጠሩ በኋላ ባለዉ የቀን አቆጣጠር በእለተ አርብ፤ ከተፈጠረዉ መሬት ይህች ሕያዉ ነፍሳችን የምትገለጽበትና የምትወሰንበት ሥጋ ተፈጠረ። ከዚያም በገነት በምሳሌያዊ ባሕርይ (ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ በሌለዉ ረቂቅ አካል) ተገልጸዉ የነበሩት ሁለቱ ነፍሳት ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ በተላበሰዉ በሥጋ እንዲገለጹ በማድረግ፤ በገነት ተገልጸዉበት የነበረዉን ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ወደ አለመኖር አሳለፈዉ። እንዲሁም እግዚአብሔርን ብቻ እያመሰገኑ የሚኖሩበትን የገነት ኑሮ ስላቃለሉና ያልተገባቸዉን ምኞት ስላሰቡ፣ ምኞታቸዉንም ለመፈጸም ያልተፈቀደላቸዉን መብል ስለበሉ በዚህች ምድር ዉስጥ ወተዉ፣ ወርደዉ፣ በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲኖሩ ተፈረደባቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ ያፍቃሪያቸዉንና የጠባቂያቸዉን አምላክ ቃል አቃለዉ የፍጡሩን ቃል በመስማት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለጣሱ፤ በገነት ዉስጥ ቃሉን ሰምተዉ የዓመፃ ተባባሪ በሆኑለት በዲያብሎስና በሠራዊቱ ሰይጣናት ሴት ተቀን በዚህ ምድር ዉስጥ እንደሚቀጡና እንደሚቀጠቀጡ ተነገራቸዉ።

በመጨረሻም በክብር የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች የሆኑት ነፍሳትን በምሳሌያዊ ባሕርይ ገንኙነት ብቻ ካለምንም ድካምና ልፋት እንዲሁም ምጥ በሁለቱ ነፍሳት አማካይነት ብቻ ካለመኖር ወደመኖር እንዲመጡ የወሰነዉን እቅድ ሽሮ፤ እነሱና የእነሱ ልጆች የልጅ ልጆች ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ሰይጣናት እኩል እስከሚሆኑ ድረስ በምሳሌያዊ ፍጥረት( በሥጋዊ ዐይን በሚታየዉ አካል) ግንኙነት አማካይነት እንዲዋለዱ፤ በሥጋ ሞት ነፍሳቸዉ ከሥጋቸዉ ስትለይ ደግሞ እንደ ሰይጣናት ጸጋ የተለየዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ተላብሰዉ ከዓለም ጎን ከተፈጠረችዉ ሦስተኛ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ ሲኦል ዉስጥ እንደሚገቡና በዚያም እንደ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ ቅጣታቸዉን እንደሚቀበሉ ነግሯቸዉ ተለያቸዉ።

አዳምና ሔዋንም በዚህች ምድር ዉስጥ በሥጋ ተገልጸዉ ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይና በጎስቋላ ኑሮና ሕይወት መኖራቸዉን ቀጠሉ። ሌት ተቀን በዲያብሎስ እየተፈተኑና እየተቀጠቀጡ ኑሮዋቸዉን መኖር ጀመሩ። ከዚያም ወደ ልባቸዉ በመመለስ ስለ ዓመፃና ክህደት ተግባራቸዉ መጸጸትና ማንባት ጀመሩ። አምላካቸዉንም ይቅርታ እንዲያደደርግላቸዉ ተማጸኑት። እርሱ ርኅሩኅ አምላክ በሕያዉ ፍጥረቱ የማይጨክን፤ በእዉነተኛ ንስሐ በጸጸት ስለተመለሱና ከእነሱ የሚወለዱት ልጆች ባላወቁትና ባልፈጸሙት ዓመፃና ክህደት በመጀመሪያ ወላጆቻቸዉ ዓመፃና ክህደት ምክንያት በእነሱ ላይ ጭምር የሞት ሞት ፍርድ ስለተወሰነባቸዉ፤ በነዚህ ሁለት ምክንያት በእርሱ እቅድ መሰረት ከባሕርይዉ የሚሰርጹት ነፍሳት ቁጥራቸዉ ከርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆን ድረስ ያሉትን ነፍሳት ለቅጽበት ካለመኖር ወደመኖር በማምጣት በዚያች ቅጽበት ዉስጥ በነጻ ሕሊናቸዉ ያሳዩትንና ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸዉን ፈጣሪ የመፈለግና በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ ብቃታቸዉን ተመለከተ።

በዚያን ጊዜም አዛዛኝ ዕይታ ነዉ የተመለከተዉ። ይኸዉም እጅግ ብዙ ነፍሳት እልፍ አእላፋት (በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ ነፍሳት እርሱ በሚፈልገዉ ደረጃ አላገኛቸዉም፤ ቀለዉ ነዉ የተገኙት። ጥቂቶች ደግሞ በሰማያት ዉስጥ ቀደም ብሎ እንዳመፁት መናፍስት ያልተገባ ሐሳብ ሲያስቡ ነዉ የተመለከተዉ። የተወሰኑ ደግሞ በሚፈልገዉ ደረጃ ነዉ ያገኛቸዉ፤ ጥቂቶች ደግሞ ከሚጠብቀዉ ደረጃ በላይ ነዉ የተመለከተዉ። አንዲት ነፍስ ደግሞ እጅግ ከሚጠብቀዉ በላይ ሆኗ ነዉ ያገኛት። የእያንዳንዱን ነፍሳት ደረጃ ከተመለከተ በኋላ ስለዓመፃዉና ክህደቱ እጅግ ሲያዝን ለነበረዉ አዳም በብርሃናዊ ድምፅ ብቻ በመገለጽ «እጅግ የበቃችዉ ነፍስ ስትወለድ ወደቀደመዉ መኖሪያ ቦታ ገነት ዉስጥ አስገባሃለሁ» በማለት ቃል ኪዳን ገብቶለት አጽናናዉ። የተመለከታቸዉን ነፍሳት ልክ እኛ ነፍሳችን ሕያዉ የሆነች የማታንቀላፋ ቢሆንም በእግዚአብሔር መንፈስና በርኩስ መንፈስ ኃይል ተሸንፈን ስናቀላፋ ነፍሳችን አንዳች ነገር እንደማታዉቅ፤ እንዲሁም ነፍስ በማኅፀን ዉስጥ እያለች ሕያዉ ብትሆንም አንዳች የምታስተዉለዉና የምታዉቀዉ ነገር እንደሌለ ሁሉ፤ እነዚያ ነፍሳትም በወንድና ሴት ጾታ ግንኙነት አማካይነት ሰዉ እስከሚሆኑ ድረስ በብርሃናዊ ባሕርይ ተሸፍነዉ በእግዚአብሔር ዘንድ አንዳች ሳያስተዉሉና ሳያዉቁ ይኖራሉ። ሰዉ በሚሆኑበት ጊዜ የሚወለዱትም በአዳምና ሔዋን ንስሐ ጊዜ በታዩበት ደረጃ ነዉ። ነገር ግን በሥጋ ከተገለጹ በኋላ በሚያሳዩት የእምነትና የምግባር ደረጃ ነዉ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚበቁት እንጂ ቀድሞ የታዩበት ደረጃ

በዚያ ደረጃ ከመወለድ ዉጪ ከምድራዊ ሕይወታቸዉ ቀጥሎ ለሚኖራቸዉ ሕይወት ደረጃ የተለየ ነጥብ አይጨምርላቸዉም።

ከላይ የተገለጸዉ ግልጽ እንዲሆንላችሁ በቁጥር አስቀምጠዋለሁ። በአዳምና ሔዋን ንስሐ ጊዜ የታዩት ነፍሳት ቀለዉ የተገኙት ከ40-59 ነጥብ ያገኙ ሲሆን፤ ሰዉ ሆነዉ ሲገለጹ ከ40-49 ነጥብ ያቀኙት አእምሮ ቀላል ሆነዉ ነዉ የሚወለዱት፤ ከ50-59 ያሉት ደግሞ አእምሮ ሕፃናት ሆነዉ ነዉ የሚወለዱት። ከ20-39 ነጥብ ያገኙት ደግሞ የክፉ ትንቢት ፈጻሚ ሆነዉ ይወለዳሉ። ከ60-89 ነጥብ ያገኙት ደግሞ አእምሮ አዋቂ ሆነዉ ይወለዳሉ። ከ90-99 ነጥብ ያገኙ አእምሮ ጽኑአን ሆነዉ ይወለዳሉ። 100 ነጥብ ያገኘችሁ የሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነችዉ እመቤታችን ድንግል ማርያም ተወልዳ የአምላክ እናት ለመሆን በቅታለች። እግዚአብሔርም ለአዳም ቃል ኪዳን በገባለት መሰረት እርሷ ሰዉ ሆና ስትወለድና ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ፤ ቀድሞ በሰማያት ባሳየዉ ብቃት መሰረት በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ባለሟልነትንና ክብርን ያገኘዉ ቅዱስ ገብርኤል፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለዉን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ጸንሳ እንደምትወልድ በተነገራት ጊዜ «ለእግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም» በማለት ባመነች ቅጽበት እርሱ በሰማያት በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾ በእልፍ አእላፋት ወትእልፊት ቅዱሳን መላእክት የሚመለከዉ፣ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ደግሞ እንደ አማናዊ ባሕርይዉ ያለዉ፣ ከእርሱ በወጣ ኃይል የተፈጠሩትን ፍጥረታት በሙሉ የሚቆጣጠረዉ፣ አልፋና ያሜጋ የሆነዉ፣ የሁሉ ፈጣሪና ገዥ አምላክ፤ ካለበት ሳይጎል፣ ከፍጥረታቱ ሳይለይ፣ ባሕርይዉን ብቻ ወስኖ ምድራዊ ዘመኗ ጭምር ነፍሷን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ ካደረሰችዉ ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ ተወለደ።

ከዚያም እንደ ሰዉ ጥቂት በጥቂቱ አደገ። ገና በሕፃንነቱ ከእናቱ ድንግል ማርያም፣ ከአሳዳጊዉ ዮሴፍና እንዲሁም ከሰሎሜ ጋር ወደ ግብፅ ተሰደደ። ከዚያም ወደተወለደበት አገር ተመለሰ። በተወለደዉ ሥጋ እድሜዉ ሠላሳ ዓመት ሲሞላዉ እዉነትን ለዓለም ገለጸ፣ አስተማረ፣ የተለያዩ ተአምራትንና ፈወስን አደረገ፣ ምስኪኖችን አጽናና፣ አስመሳዮችን ገሰጸ፣ ባጠቃላይ የሰዉ ዘሮች ሊያደርጉት የሚገባቸዉንና የማይገባቸዉን በሚገባ አሳወቃቸዉ። በመጨረሻም ሞተዉ እንደማይቀሩና ሕያዋን መሆናቸዉን፣ በሥጋ ሞተዉ እንደሚነሱ፣ በዓለም የሚመጣባቸዉን የተለያየ ፈተናና መከራ በጽናት፣ በቆራጥነት፣ በትዕግስት፣ በአኮቴት መቀበል እንዳለባቸዉ ለማሳየት፤ የተለያዩ መከራንና ስቃይን እስከ መሰቀል ድረስ ተቀብሎ ሁሉ ተደርገዉበት አሳያቸዉም። ሞተዉ እንደማይቀሩ ትንሳኤ እንዳላቸዉ በግልጽ በሦስተኛዉ ቀን ከሙታን መካከል ተነሥቶ አሳያቸዉ። በመጨረሻም በእርሱ አምነዉ፣ እንደ እርሱ ፈቃድ ተመላልሰዉ፣ ቃሉን ጠብቀዉ የሚገኙ አማኞች ሆኑ አገልጋዮች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገቡ ለማሳየት ወደ ሰማይ ዐርጎ አሳያቸዉ። ፈቃዱን ለሚፈጽሙ ኃይል የሚጎናጸፉበትን ጸጋ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በበዓለ አምሳ አደላቸዉ።

እርሱ ሰዉ የሆነ አምላክ ለአዳም ቃል ኪዳን በገባለት መሰረት በዕለተ አርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነፍስ ከሥጋዉ እንደተለየች በቀጥታ የሄደዉ አዳምና ሔዋን በገነት ዓመፃን ፈጽመዉ ወደ እዚህች ምድር በገቡበት ወቅት የሰዎች ነፍስ ከሥጋዋ ስትለይ እንደ መናፍስት ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ተላብሳ ወደምትኖርበትና እንደ ምድራዊ ዓመፃና ክህደቷ እንዲሁም ርኩሰቷ ተግባር ዋጋ ወደ ምትከፍለበት ቦታ ከዓለም ጎን ወዳለችዉ ሲኦል ነዉ። እዚያ ያሉትን ነፍሳት በሙሉ አዉጥቷቸዉ ወደ ገነትና ማረፊያ ቦታ ነዉ ያስገባቸዉ። ማረፊያ ቦታ ከዓለምና ከሲኦል ጎን የተፈጠረችዉ በዚያን ጊዜ ነዉ። ወደ ገነት ያስገባቸዉ በምድራዊ ዘመናቸዉ በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) በነጻ ሕሊናቸዉ ተመርተዉ ቀና ያሰቡ፣ መልካም የሰሩ፣ ኃጢአት ሲፈጽሙ በሕናቸዉ የተጸጸቱ፣ እንዲሁም በኪዳነ ኦሪት(በሕገ ኦሪት) ተመርተዉ ሕጉን የጠበቁ፣ በኃጢአት ሲወድቁም የኃጢአት ስርየት የተደረገላቸዉና የተጸጸቱ፣ በሕፃንነትና በልጅነት እድሜ በሥጋ ሞት ተጠርተዉ ወደ ሲኦል የገቡና በሲኦል ዉስጥ እያሉ በእዉነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን የፈለጉና ያመለኩ፣ ባጠቃላይ ለገነት የሚያበቃ ሕይወት የያዙት ነፍሳት(ሰዎች) ብቻ ናቸዉ። እነዚህ በፍርድ ቀን በማረፊያ ቦታ የሚከናወነዉን የመጨረሻ ፍርድ ተመልክተዉ ወደ መንግሥተ ሰማያት በቀጥታ የሚገቡ የጸደቁ ነፍሳት ናቸዉ።

ወደ አራተኛዋ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ ማረፊያ ቦታ የገቡት ደግሞ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የተመላለሱና በኪዳነ ልቦና ተመርተዉ ስለ ኃጢአታቸዉ የሕሊና ጸጸት ያላደረጉ፤ እንዲሁም በኪዳነ ኦሪት ተመርተዉ ሕጉን ያልጠበቁና በኃጢአት ሲወድቁም የኃጢአት ሥርየት ያልተደረገላቸዉና ያልተጸጸቱ ነፍሳት(ሰዎች) ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ በሕፃንነትና በልጅነት እድሜያቸዉ በሥጋ ሞት ተጠርተዉ በሲኦል ዉስጥ ለገነት የሚያበቃ ሕይወት ያልያዙ ነፍሳት ናቸዉ። እነዚህ በማረፊያ ቦታ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በሚያሳዩት የእዉነትና የመንፈስ አምልኮ ብቃትና እግዚአብሔርን የመፈለግ ሕይወት ብቃት መሰረት በፍርድ ቀን ለመጨረሻ ፍርድ ቀርበዉ ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ሕይወት የያዙ ወደ መንግሥት ሰማያት የሚገቡ ሲሆን፤ ለዚያ ሕይወት ያልበቁ ደግሞ እንደ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ተግባራቸዉ ደረጃ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ የሚገቡና እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ የመጨረሻ ቅጣት የሚቀበሉ ናቸዉ።

ክርስቶስ በሲኦል ያሉትን ነፍሳት ነጻ አዉጥቶ ወደ ገነትና ማረፊያ ቦታ ባስገባቸዉ ጊዜ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት በዚያች ሰዓት በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰዉና ኃጢአተኝነቱን አምኖ የተናዘዘዉ እንዲሁም ከልቡ በመጸጸት የመስቀል ፍርዱም እንደሚገባዉ ያመነዉ፤ ነገር ግን አምላኩን ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ ምሕረት የጠየቀዉ ፈያተዊ ዘየማን በመባል የሚታወቀዉ ሰዉ፤ የመጀመሪያዉ ገነት ገቢ ሊሆን በቅቷል። በተቃራኒዉ ደግሞ ከክርስቶስ እግር ስር የተማረዉ፣ የተለያዩ ተአምራትና ፈዉስ የተመለከተዉ፣ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት የተለያየ ጸጋ ተሰቶት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረዉና በመጨረሻ ሰዓት ቀድሞም ልቦናዉ ከጥቅምና ከገንዘብ ጋር ብቻ የሆነዉ፤ የዚህች ምድር ብልጽግናና የገንዘብ ፍቅር ያሸነፈዉ፤ እንዲሁም የዉስጡ ክፋትና ተንኮል አይሎበት ለገንዘብ ሲል አምላኩን ለተቃዋሚዎቹ አሳልፎ የሰጠዉ

የአስቆሮቱ ይሁዳ፤ ነፍሳት ከሲኦል ወተዉ ወደገነትና ወደ ማረፊያ ቦታ ሲገቡ እርሱ ደግሞ በምሕረት ዘመን ዳግም የንስሐ እድል ወደሌለበት የመጀመሪያዉ ሲኦል ዉስጥ በመግባት መከራና ስቃይ ተቀባይ ሆኗል፡፡ ራሱንም ለገሃነመ እሳት ፍርድ ያጨ የመጀመሪዉ ሰዉ(ነፍስ) ሆኗል፡፡ ለዚህም ነዉ «ባልተወለደ ይሻለዉ ነበር» የተባለዉ፡፡

ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ነፍሳት ወደ ገነት፣ ወደ ማረፊያ ቦታና ወደ ሲኦል ነዉ የሚገቡት፡፡ ወደ ገነት የሚገቡት በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አምላክነቱ ብቻ የሚያመልኩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ፣ ነብይ፣ አንድ ኢየሱስ ነዉ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ ከእርሱ ጋር የሚስተካከሉና አንድ የሆኑ አካላት የሉም፣ ፍጡር ነዉ.... ወዘተ» የማይሉ ናቸዉ፡፡ እንዲሁም ሕይወታቸዉንም በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባርና በእዉነተኛነት የሚመሩ፤ በኃጢአት ሲወድቁም በእዉነተኛ ንስሐ የሚመለሱና ምሳሌ ያልሆነዉን ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚሆነዉን መለኮት የተዋሐደዉን ቅዱስ ሥጋና ደም የተቀበሉ ናቸዉ፡፡ ወደ ሲኦል የሚገቡት ደግሞ በዓመፃ፣ በክህደት፣ እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እንዳሉ በሥጋ ሞት የተጠሩና እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐና ሕይወት ዉስጥ ሳይመላለሱ መንፈሳዊዉን አገልግሎት እንደ ስራ መስክ ቆጥዉ በድፍረት መለኮት የተዋሐደዉን ቅዱስ ቁርባን የተቀበሉ  ነፍሳት ጭምር ናቸዉ፡፡ ወደ ማረፊያ ቦታ የሚገቡት ደግሞ በምድራዊ ሕይወታቸዉ ዘመን በመሰላቸዉ መንገድ የተመላለሱ፤ ነገር ግን ቅንነት ያላቸዉ፣ ኃጢአት ሲፈጽሙ የሕሊና ጸጸት ያደረጉ ሰዎች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በማረፊያ ቦታ በሚኖራቸዉ እግዚአብሔርን የመፈለግና በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ ብቃት በፍርድ ቀን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግባት እድል አላቸዉ፡፡ ሌሎች ወደማረፊያ ቦታ የሚገቡት የምድራዊ እምነትና ምግባር ሕይወታቸዉ ያልታየ ሕፃናትና ልጆች እንዲሁም አእምሮዋቸዉን በአግባቡ ማዘዝ የማይችሉ አእምሮ ሕሙማን ናቸዉ፡፡ እነዚህ በማረፊያ ቦታ በሚያሳዩት በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ ብቃታቸዉ ታይቶ የሚፈለገዉ ብቃት ደረጃ ላይ ከደረሱ በፍርድ ቀን ወደ መንግሥት ሰማያት የመግባት እድል አላቸዉ፡፡

ስለዚህ ከእኛ ከሰዎች የሚጠበቀዉ በእእምሮ ቀላል ሆነ በአእምሮ ሕፃናት እንዲሁም በአእምሮ አዋቂዎች ወይንም በአእምሮ ጽኑአን ደረጃ ሆነን ልንወለድ እንችላለን፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ የምንችለዉ በምድራዊ ሕይወት ዘመናችን በምናገኘዉ የእምነትና ምግባር ነጥብ ስለሆነ እያንዳንዱ ሰዉ ቢያንስ 60 ከ 100 ነጥብ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በሰማያት ዉስጥ ሆነ በገነት ዉስጥ የሚኖረን ክብርና የቅድስና ማዕረግ እንደ ምድራዊ ነጥባችን ስለሚለያይ በእምነትና በምግባር የምናሳየዉ ሕይወት ለ90 ቤቶች ነጥብ ለማግኘት መትጋት ነዉ ያለብን እንጂ በነፍሳችን ልንደክም አይገባም፡፡ ከ60 ነጥብ በታች የምናመጣ ሰዎች ደግሞ በሲኦልና በገሃነመ እሳት የሚደርስብን ቅጣት እንደ ነጥባችን  ዝቅተኛነት ደረጃ የሚለያይና ነጥባችን ዝቅ ባለ መጠን የሚደርስብን ስቃይና መከራ ስለሚበረታብም፤ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወትና በእዉነተኛ ንስሐ ልንመላለስ ይገባል፡፡ የእያንዳንዱ ሰዉ የጽድቅ ስራ ቢያንስ ቢያንስ 60 ቤቶች ዉስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

ከ40 ነጥብ በታች የሚያሳዩ ትዕቢት(የፈርኦን ወንድምና እህቶች)፣ ክፋትና ተንኮል(የይሁዳ ወንድምና እህቶች)፣ ዓመፃ(የአርዮስ ወንድምና እህቶች) ካሉ፤ እንደ እኔ ባይፈጠሩ ወይንም ባይወለዱ ይሻላቸዉ ነበር:: ምክንያቱም ትዕቢታቸዉ፣ ክፋታቸዉና ተንኮላቸዉ፣ እንዲሁም ዓመፀኝነታቸዉ ሕሊናቸዉን ስለሚያደነድንና እንኳን ፍጡሮቹን የእግዚአብሔር አገልጋዮችንና መልእክተኞችን ሊሰሙ ቀርቶ እርሱ እግዚአብሔር ተገልጾ ቢናገራቸዉ፣ ተአምራትና ፈዉስ ቢያደርግ፣ የተለየ ጸጋ ቢሰጣቸዉ እንኳ የማይሰሙና የሚላቸዉንም የማይፈጽሙ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ የሚንቀሳቀሱና የሚመሩ ደንዳኖች በመሆናቸዉ ነዉ:: እነሱ ሙሉ በሙሉ በሲኦል ነጻነታቸዉ ተገድቦ ፍዳቸዉን እስከሚቀበሉ ድረስ የዓመፃ፣ የክህደትና የርኩሰት ተግባር ለመፈጸም ወደኋላ የማይሉ ስለሆነ በምድራዊ ሕግና ሥርዓት የሚገደቡ ይሆናል:: ከሕግና ከሥርዓት በላይ እንሁን ካሉ ደግሞ በዚህች ምድር ጭምር ስለ ዓመፀኝነታቸዉ፣ ስለ ክህደታቸዉ፣ ስለ ርኩሰታቸዉ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ነጻነታቸዉ ይገደባል፤ ዋጋም ይከፍሉበታል:: እንዲሁም አእምሮ ሕፃንና አእምሮ ቀላል በመሆን የዓመፃ ፈለግ የሚከተሉ ሌሎች የዓመፃ፣ የክህደትና የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች ካሉም  እንደ እነሱ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በሚዘጋጀዉ የጽድቅና የቅድስና ሕግና ሥርዓት ይገደባሉ፤ ይዳኛሉ::

**ወደ ጥያቄያችሁ ምላሽ ስገባ** ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸዉ በገነት ዉስጥ ሆነን ቢሆን ኑሮ ጨለማና ብርሃን አይፈራረቁብንም ነበር፤ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ብርሃናዊ ባሕርይ ነበር የሚያበራልን:: እንዲሁም ለመኖር መዉጣት መዉረድ አይጠበቅብንም ነበር:: መብላችን ሆነ መጠጣችን እንደ አየር ሳንደክምና ሳንለፋ የምናገኘዉና ተዋሕዶን ነበር የሚኖረዉ:: ከፀሐይ፣ ከዝናብ፣ ከሙቀት፣ ከቅዝቃዜ፣ ከብርድ፣ ከመሳሰሉት ለመከላከል መጠለያ ሆነ የምንለብሰዉ አያስፈልገንም ነበር:: በምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ስለምንገለጥና እነዚህ ነገሮችም በገነት ስለሌሉ አንዳች መጠለያ ሆነ ተጨማሪ ልብስ አያስፈልገንም ነበር:: እንዲሁም ለሕይወታች ህልዉና ጥገኛ የምንሆንባቸዉ እንስሳት ሆኑ እፀዋት አይስፈልጉንም ነበር:: ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ ተጨማሪ መገልገያ ቁሳቁሶች ሆነ ሕይወት ያላቸዉ ፍጥረታት አያስፈልገንም ነበር:: ምሳሌያዊ ፍጥረት በሆነዉ በሥጋዊ ዐይናችን በሚታየዉና በእጃችን  በሚዳስሰዉ አካል(ሥጋ) ስለማንገለጽ እንደ መናፍስት ወደፈለግነዉ ቦታ መንቀሳቀስ እንችል ነበር:: በዚህ ሥጋ በመገለጻችን ምክንያት የተከሰቱብን ያደፉና የጎደፉ ባሕርያት ዐይነምድር፣ ሽንት፣ ሽታ፣ ላበት፣ ንፍጥ፣ አክታ የመሳሰሉት አይከሰቱብንም ነበር:: የምንመገባቸዉ ሆነ የምንጠጣቸዉ ሁሉ ምሳሌያዊ ባሕርይ ስለነበሩ ከተገለጽንበት ምሳሌያዊ ባሕርይ ጋር ይዋሐዱ ነበር:: እንዲሁም በገነት ዉስጥ ሰይጣናት ስለማይኖሩ ወደ ነፍሳችንና አካላችን ስለማይገቡና ስለማይወጡ ማፋሸክ(ማዛጋት)፣ ማስነጠስ፣ ማሳል፣ ማሳከክ፣ መንጠራራት፣ መፍሳት አይታይብንም ነበር:: እንደ መናፍስት በማይሞት አካል ስለምንገለጽ፤ በምንገለጽበት አካል ምክንያት ሞት የሚባል ነገር በሕይወታችን አይጋጥመንም ነበር:: እንዲሁም ከመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት ካለመኖር ወደ መኖር ስለምንመጣ ሁላችንም በአንድ ቤተሰብ ስሜት ነዉ የምንኖረዉ እንጂ ልጆቼ፣ ወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ አባቴ፣ እናቴ፣ አጎቴ፣ አክስቴ፣ ዘመዴ፣ ዘሬ፣ ጎጤ፣ ነገዴ በማለት አንከፋፈልም ነበር:: ሕያዉ ነፍሳችን በርኩሳን መናፍስት ስለማትፈተን ማንቀላፋት ሆነ መድከም የሚባል አይታይብንም ነበር:: ስራችን ሁሉ እግዚአብሔርን ማምለክና

ማመስገን ነበር እንጂ ስለ አንዳች ነገር አንለፋም፣ አንወጣም፣ አንወርድም ነበር፡፡ ሁል ጊዜ ነፍሳችን የረካችና ደስተኛ ስለምትሆን አንዳች ምኞት ሆነ የተለየ ፍላጎት አያድርብንም ነበር፡፡ አንዳች ጉስቁልና ባሕርይ ሆነ ሕይወት ስለማይከሰትብን ማዘን ሆነ ማንባት አይኖርብንም ነበር፡፡ ባጠቃላይ ከአኗኗራችን ዉጭ እንደ ቅዱሳን መላእክት በቅድስናና በንጽህና እንዲሁም በእዉነተኛ ደስታ ሕይወት ብቻ ነበር የምንመላለሰዉ፡፡

ይሁንና ይህን የክብር ሕይወትና ኑሮ የቀደሙት ወላጆቻችን አቃለዉ በዓመፃ ስለተገኙ እነሱም ሆኑ እኛ ልጆቻቸዉ ለዚህ ለምድራዊ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም ለተጎሳቆለ ሕይወትና ኑሮ ተዳርገናል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ የሚከሰትብን ከምድራዊ ዘመን በኋላ ከሚኖረን የሕያዉነት እድሜ አንጻር በዐይን ቅጽበት እድሜያችን ዉስጥ ስለሆነ በትዕግስት፣ በጽናትና በአኮቴት ተቀብለን ፈጣሪ አምላካችንን በእዉነትና በመንፈስ በማምለክ ሕይወታችንንም በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ እንዲሁም በእዉነተኛ ሕይወት በመኖር ከሥጋ ሞት በኋላ ያለዉን የገነት እንዲሁም ከፍርድ ቀን በኋላ የሚኖረዉን ሰማያዊ ሕይወት በናፍቆት ልንጠባበቅ ይገባል፡፡ ባጠቃላይ ምድራዊ ዘመናችን የምንጠራበት፣ የምንነጥርበት፣ የምንነጣበት፣ እንዲሁም በወላጆቻችን በአዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ዓመፃ ምክንያት በዐይን ቅጽበት እድሜያችን የምንቀጣበት እንጂ እንኖርበታለን የምንለዉ አይደለም፡፡ ምድራዊ ቆይታችን ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቤታችንና ሕይወታችን የምንሸጋገርበት ድልድይ ብቻ ነዉ፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ እርሶ እንደገለጹልን በፀሐይና በበረዶ መቃጠላችን፣ በብርድና በቅዝቃዜ መኮራመታችን፣ የበላነዉ ወደ እዳሪ የጠጣነዉ ወደ ሽንትና ላበት መለወጡ፣ ኑሮን ለማሸነፍ መዉጣት መዉረዳችን፣ በዚህች ምድር ዉስጥ ለመኖርና ለመቆየት ግድ መብላትና መጠጣት ያስፈለገን፣ በድካምና በእንቅልፍ ሕይወት ዉስጥ መገኘታችን፣ በሥጋ መታመምና መሞታችን፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ቦታ ለመንቀሳቀስ ተጨማሪ ቁሳቁስ ሆነ ሌላ ፍጥረት መፈለጋችን፣ በርኩሳን መናፍስት ሁል ጊዜ ስለምንፈተንና ስለምንቀጣ ወደ ሕሊናችን የሚገቡት በአፋችን በኩል በማፋሸክ( በማዛጋት) እንዲሁም በአፍንጫችን በኩል በማስነጠስ የሚወጡት እና ከመተንፈሻ አካላችንና ከሆዳችን የሚገቡት በአፋችን በኩል በማሳልና በማግሳት የሚወጡት፣ በሆዳችን ዉስጥና በሽንት ፊኛችን ዉስጥ የሚገቡት በፈስ መልክና እንዲሁም ከዐይነ ምድራችንና ከሽንታችን ጋር የሚወጡት፣ በራሳችን ፈቃድና ምርጫ እርስ በእርስ የምንጣላዉና በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በጥል፣ በጦርነት ፣ በግድያ፣ በስርቆት፣ በጣዖትና በባዕድ አምልኮ፣ በመተት፣ በአስማት፣ በጥንቆላ፣ በሟርት፣ በስካር፣ በዝሙት፣ በአመንዝራነት፣ በዳንኪራ፣ በዘፈን፣ በዘረኝነት፣ በጎጠኝነት፣ በትዕቢት፣ ባጠቃላይ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት፤ እንኳን ለነፍሳችን ለሥጋችን በማይጠቅመን ሕይወት መመላለሳችን እንዲሁም ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይና በጉስቁልና ኑሮና ሕይወት ዉስጥ ለመኖር የተዳረግነዉና የተገደድነዉ በገነት ኑሮ ዉስጥ አዳምና ሔዋን በፈጸሙት ዓመፃና ክህደት ምክንያትና ከገነት ወተዉ ወደ እዚህች ምድር ሰይጣናት ብቻ ይኖሩበትና ይቀጡበት ወደነበረበት ሲገቡ በገነት ተገልጸዉበት የነበረዉ ረቂቅ አካል ተወግዶ ይህን ግዙፍ ሥጋ ለብሰዉ እንዲገለጹ ስለተደረገ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ታዲያ ይህ ምድራዊ ሕይወታችን ሕይወት ሆነና ነዉ እርስ በእርስ

የምንጣላዉና የምንከፋፈለዉ? በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በትዕቢት፣ በዓመፃ፣ በርኩሰት፣ በዝሙት፣ በግድያ፣ በስርቆት፣ በጥል ሕይወት የምንመላለሰዉ? ተስፋችንን ምድር አድርገን በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት የምንመላለሰዉ? አምላክን ያህል በመስቀል ላይ ራቁቱን ሰቅለን ሰይጣናትን ለማስደሰት ሌት ተቀን በዘፈንና በዳንኪራ ሕይወት የምንመላለሰዉ? ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ቃል «አንጠብቅም» በማለት የዐይን ቅጽበት እድሜ የማትሞላዉን ዘመናችንን በዓመፃ፣ በክህደት፣ በአምልኮ ምንዝርና ሕይወት የምንመላለሰዉና ራሳችንን ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ የምናዘጋጀዉ?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: እኔም ምርጫችን ይህን ዓይነቱ የሞት ሕይወት ማድረጋችን ነዉ የሚያሳዝነኝና ኀዘንተኛ እንድሆን ያስገደደኝ:: በተለይ እግዚአብሔር አምላክ በአምላካዊ ሥልጣኑ የፈለገዉን ማድረግ ሲችል አፍቅሮንና ወዶን ባሕርይዉን ዝቅ በማድረግና በማዋረድ ያልተገባዉን ሥጋ ከእመቤታችን ከቅድስተ ቅዱሳን ከንጽህይተ ንጹሃን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በተዋሕዶ በዚህች ምድር እንደ ሰዉ ተወልዶ፣ አድጎ፣ የተለያየ ጸዋትዎ መከራ በፍጥረቱ ተቀብሎ፣ እስከ መስቀል ድረስ ወዶንና አፍቅሮን፣ ማድረግ ያለብንና የሌለብን በግልጽ አስተምሮን፣ ታላቅ ተስፋችንን ነግሮን፤ ይኸዉ ሁለት ሺህ ዘመን ይህል እንኳ ቆይቶ ትዉልዱ አልተቀበለዉም፤ አላመነበትም:: «አመን» የሚሉትም አስመሳይ አገልጋይና አማኝ ሆነዉ ዕለት ዕለት እርሱን በሚያስቆጣ ተግባርና ንግግር ዉስጥ ይገኛሉ፤ በዓመፃና በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ ይመላለሳሉ:: ታዲያ እግዚአብሔር ምን ያላደረገልን ነገር አለ!? ምንስ ያልሆነልን ነገር አለ!? ስለ ዓመፃችን፣ ክህደታችን፣ ርኩሰታችን ከገሃነመ እሳት በላይ እጅግ የከፋ ቅጣት ቢቀጣን አያንሰንምን!? እጅግ ያንሰናል::

በተለይ ደግሞ ቃሉን እያወቅን በትልቅ ኃላፊነት፣ በእረኛነት ወንበር ላይ ተቀምጠን የእግዚአብሔርን ሕዝቦችና ልጆችን በአግባቡ ያልጠበቅን፤ ወንበሩን ያመለክንና ያስመልክን፣ በእግዚአብሔር ቦታ ላይ ሆነን መከበርንና መግነንን የፈለግን፣ ትዉልዱን ያሰናከልንና በእግዚአብሔር ስም የነገድን፣ በእግዚአብሔር ላይ ያላገጥን ሰዎች፤ አዎን! እጅግ የከፋዉ ቅጣት ይጠብቀናል፤ ይገባናልም:: ምክንያቱም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጥነዉ እንደ እግዚአብሔር ሆነን ሕዝቡን በቅንነት፣ በእዉነት ለማገልገልና ራሳችንን ክደን ስለ እዉነት እንድንመሰክር፣ እግዚአብሔርንም ከፍ ከፍ ለማድረግና በእዉነትና በመንፈስ ለማስመለክ ነዉ እንጂ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ጥላቻንና በቀልን፣ መከፋፈልንና መለያየትን ለመዝራት፣ ጣዖትንና ባዕድ አምልኮትን ለማስፋፋት፣ ባጠቃላይ ርኩሰትን፣ ዓመፃን፣ ክህደትን ለማንገሥ አልነበረም::

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: ቀደም ሲል በገለጹልን የተለያዩ ምስጢራትና እዉቀቶች፤ በእኛ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን የማይታወቁ አሉ:: ታዲያ የቤተክርስቲያኗ አባቶች ሆኑ ምእመናን ሊቀበሏቸዉ ይችላልን?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:*__ *እዚህ ላይ ለመግለጽ የምፈልገዉ ምስጢራቱን ሆነ እዉቀቶቹን የገለጽኩት እኔ ሳልሆን እርሱ እግዚአብሔር አምላክ ነዉ። ይህም እኔም ሆንኩ ሌላዉ ሰዉ ያለዉን ሙሉ እዉነታ እንዲያዉቅ ለማስቻል ፈልጎ ነዉ እግዚአብሔር ሁሉም ነገር በግልጽ እንዲገለጽ ያደረገዉ። እኔ እንደማንኛችሁም ነኝ። የእግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ ስለሆነ ብቻ ነዉ ልክ በቧንቧ ዉስጥ ዉኃ እንደሚያልፍና ወደሚፈለገዉ ቦታ እንደሚደርስና ቧንቧዉ ማስተላለፊያ ነዉ እንጂ የዉኃዉ ምንጭና መገኛ እንዳልሆነ ሁሉ፤ እኔም ሳይገባኝ እንደ ቧንቧዉ መተላለፊያ ሆኜ ነዉ  የተገኘሁት። እኔም እንደናንተ የማላዉቃቸዉና ከማንም ሰዉ ያልሰሟዋቸዉ ምስጢራትና እዉቀቶች አሉብት። ለዚህም እግዚብሔርን ጠይቄዋለሁ። ይኸዉም «እግዚአብሔር ሆይ! ከመጽሐፍ ቅዱስ ሆነ ከመምህራን የተማርኩት አዳምና ሔዋን በዚህ ምድር ዉስጥ በዐይናችን የምናያቸዉና የማናያቸዉ ፍጥረታት ከተፈጠሩላቸዉ በኋላ ነዉ በዕለተ አርብ እንደተፈጠሩ የተጻፈዉና መምህራንም የሚያስተምሩት፤ አሁን ለእኔ የገለጽክልኝና የተናገርከኝ ደግሞ ይህች ምድር በሰማያት ዉስጥ ላመጹት ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) መቀጫ ይሆን ዘንድ በድቅድቅ ጨለማ ተሞልታ እንደነበርና አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ሁለቱ ነፍሳት በገነት ዉስጥ ዓመፃና ክህደት ሲፈጽሙ እንዲቀጡበት አሁን በዚህች ምድር ዉስጥ የሚታዩት ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ መሬት፣ አየር፣ ዉኃ፣ እፀዋት፣ አዝርዕት፣ እንስሳት፣ የመሳሰሉት ከተፈጠሩ በኋላ አዳምና ሔዋን በረቂቁ ዓለም በገነት ዉስጥ በረቂቅ አካል(በምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጸዉ የነበረበትን አካል አስወግደህ በግዙፉ ዓለም ዉስጥ የሚቀጡበትና ያ በነጻነት ከቦታ ወደ ቦታ እንደ መናፍስት የሚንቀሳቀሱበትን አቅም ለመገደብ ይህን ሥጋ ከአፈር አበጅተህ በገነት ዉስጥ የነበሩት ሁለቱ ነፍሳት እንዲዋሐዱት አድረገህ በዚህች ምድር ዉስጥ እንዲገኙ እንዳደረክ ነዉ። ታዲያ እነዚህ እዉቀቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተገለጸዉ እዉቀት ጋር አይጋጬም፣ አይለያዩም ወይ?» በማለት ነበር።*

*ታዲያ የጠሰጠኝ ምላሽ «ለሙሴም ያን ምስጢርና እዉቀት የገለጽኩለት እኔ ነኝ። ትዉልዱ ሊረዳዉና ሊቀበለዉ የሚችለዉ እንዲሁም ሙሴ ራሱ ሊራዳዉና ሊቀበለዉ በሚችል መልኩ ነዉ የገነትን ኑሮ በግልጽ ያልገለጽኩለትና የዚህችን ምድር አፈጣጠር እንዲሁም ለአዳምና ሔዋን ሁሉ ነገር ከተፈጠረላቸዉ በኋላ በዕለተ አርብ ከአፈር ያበጀዉትን ይህን ሥጋችሁን ነፍሳቸዉ ተዋሕዳ መገለጿን ብቻ እንዲያሳዉቅ ያደረኩት። አሁን ግን ትዉልዱ የተማረና የሚመረምር እንዲሁም የሚጠይቅ አእምሮዉ የሰፋ ስለሆነ፤ ሙሉ እዉነታ ቢገለጽለት ሊቀበለዉ ስለሚችል ነዉ የገነቱን ሕይወትና ምድራዊ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቀለ ባሕርያችሁንና ጎስቋላ ኑሯዋችሁንና ሕይወታችሁን እንድታዉቁ ያደረኩት እንጂ አንዳች የሚጋጭና የተለያየ ነገር የለበትም።*

*አንተን ራስህን ልጠይቅህ! እኔ ሕያዉ ለሆነ ፍጥረቴና እንደፈቃዴ ለሚኖር እንዴት ያደፈና የጎደፈ፣ የጎሰቀለ ባሕርይ በሆኑት በዐይነ ምድር፣ በሽንት፣ በንፍጥ፣ በአቅታና በሽታ እንዲገለጽ አደርጋለሁ? እንዲሁም በጎስቋላ ሕይወትና ኑሮ በሆኑት በፀሐይና በሙቀት እንድትቃጠሉ፣ በብርድና በቅዝቃዜ እንድትኮራመቱ አደርጋለሁ? እንዴት ለመኖር በእንስሳትና በእፀዋት፣ በአዝርዕት ጥገኛ አንድትሆኑ አድርጌ እፈጥራችኋለሁ? እንዴት ከዝናብ፣ ከፀሐይ፣ ከብርድ ለመከላከል መጠለያ እንዲያስፈልጋችሁ አድርጌ እፈጥራችኋለሁ? እንዴት የሚቆስል፣ የሚደማ፣ ጉዳት የሚደርስበት፣*

የሚፈርስ፣ የሚሞት ሥጋ እንድትገለጡበት አድርጌ እፈጥራችኋለሁ? እንዴት የሚያለቅስና የሚያነባ ሕያዉ ፍጥረት እፈጥራለሁ? ይህ የእኔ ባሕርይ አይደለም፡፡ እነዚህ ሁሉ የተከሰቱባችሁ አዳምና ሔዋን በመባል የምታዉቋቸዉ ሁለቱ ነፍሳት በገነት ዉስጥ በግልጽ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጩ ካለመኖር ወደመኖር እንዳመጣዋቸዉ እያወቁ ከዚያም በላይ በግልጽ ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን ተነግሯቸዉና ለተገዥነታቸዉ ምልክት እንዲሆን በገነት ዉስጥ ከተፈጠሩት እጅግ ብዙ ምሳሌያዊ ባሕርይ ፍጥረቶች አንዲት ምሳሌያዊ ባሕርይ የሆነች ፍሬ እንዳይበሉ፣ ከበሉ ግን የሞት ሞት እንደሚሞቱ ገልጬላቸዉና አስጠንቅቂያቸዉ፣ ሕሊናቸዉን በማደንደን በድፍረትና በምኞት ተቃጥለዉ እንደ እኔ የሚሆኑ መስሏቸዉ፣ በእነሱ ረቂቅ አካል የተገለጸዉን የዲያብሎስን የማስመሰልና የተንኮል ቃል ሰምተዉ ያልተፈቀደላቸዉን ፍሬ በመብላታቸዉና ትእዛዜን ባለመጠበቃቸዉ ነዉ፡፡

ዓመፃቸዉም ከርኩሳን መናፍስት ስለበለጠ፣ ምክንያቱም ሰይጣናት ካለመኖር ወደ መኖር መተዉ በሰማያት ዉስጥ ራሳቸዉን አገኙ እንጂ እኔ በግልጽ ተገልጬ ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣዋቸዉ አልገለጽኩላቸዉም ነበር፡፡ ነገር ግን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸዉ አምላክ እንዳለ ሕሊናቸዉ እየመሰከረባቸዉ ሕሊናቸዉን በማደንደን ዓመፃ ስለፈጸሙ ጸጋቸዉ ተገፎ በዚህች ምድር በጉስቁልና ባሕርይ ብቻ እንዲቀጡ ተደርጓል፡፡ አዳምና ሔዋን ግን በግልጽ ማንነቴን እያወቁ፣ ገና አንድ ነፍስ እንኳ ከእኔ ባሕርይ ሰርጻ(ወታ) በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት በገነት ሳትገለጽ ስላመጹብኝ ከጉስቁልና ባሕርይ በተጨማሪ ይህን ሥጋ በመልበስ ባደፈና በጎደፈ እንዲሁም በጎሰቆል ባሕርይ እንዲገለጹ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ስለ ዓመፃቸዉ እጅግ ስለተጸጸቱና ይቅርታ ስለጠየቁ እንዲሁም እናንተ ልጆቻቸዉ ባላወቃችሁትና ባልፈጸማችሁት ዓመፃ በወላጆቻችሁ ዓመፃ ምክንያት የሞት ሞት ስለተፈረደባችሁ፣ በዚህች ምድር ዉስጥ ተገልጻችሁ በምትኖሩት ከሥጋ ሞት በኋላ ከምትኖሩት እድሜ አንጻር የዐይን ቅጽበት ጊዜ በማይሆነዉ ዘመናችሁ በምታሳዩት መልካም ምግባርና በእዉነትና በመንፈስ በምትፈጽሙት አምልኮ ዳግም የገነትና ለመጀመሪያ ዓላማ ለተፈጠራችሁበት መንግሥተ ሰማያት እንድትበቁ እድል የተሰጣችሁ፡፡» በማለት ስለመለሰልኝ ነዉ፣ እኔም ይህ እዉቀት እንጂ ሃይማኖት አለመሆኑን ስለተረዳሁና ስላስተዋልኩ ደግሞም ከእግዚአብሔር በላይ የሆነ አዋቂ ሆነ ምሁር ስለሌለ፣ እግዚአብሔር የገለጸልኝንና የተናገረኝን አንዳች ሳልቀንስ ሆነ ሳላሻሽል እንዳለ በመልእክታቱ ዉስጥ ያሰፈርኩት፡፡

በመሆኑም መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ የሆኑ አገልጋዮችና መምህራን እንዲሁም ምእመናን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ እንደሚቀበሉት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በተለያየ ዘመን እንኳን መንፈሳዊ እዉቀት አይደለም ለዓለማዊ ኑሮዋችን እንኳ የተለያዩ እዉቀቶችን እየገለጸ ከጉስቁልና ሕይወት የምንለይበትን የተለያዩ የጥበብ(የቴክኖሎጂ) ዉጤቶች ይኸዉ በዓለም ላይ ተገልጸዉ እየተጠቀምንባቸዉ ነዉ፡፡ ማንኛዉም እዉቀት ሆነ ጥበብ እንዲሁም ምስጢራት ካለእግዚአብሔር ፈቃድ አይገለጽም፡፡ ሰዎች ግን ያንን እዉቀትና ጥበብ የሰዉ ዘሮችን ከጉስቁልና ሕይወት ለማላቀቅ ሊጠቀሙበት ሲገባ፣ ይኸዉ ሕዝብና ሕዝብን የሚያጫርሱበትን የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች ሰርተዉ እርስ በእርስ እያገዳደሉት ይገኛል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን (ማስ

ሚዲያ) እግዚአብሔር ለሚደሰትበት መልካም ተግባርና ትምህርት እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቃልና ምስጋና ለማስተላለፍ ሊጠቀሙበት ሲገባ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ክህደትን፣ ዓመፃን፣ ርኩሰትን፣ ጥልንና ጥላቻን የሚያስተላልፉበት መሳሪያ ሆኗል፡፡ እግዚአብሔር የገለጸዉን እዉቀትና ጥበብ ለመልካም ነገር ያላልዋለዉ አካልና ግለሰብ ይጠየቅበታል እንጂ እግዚአብሔር የገለጸዉን እዉቀትና ጥበብ አንቃወምም፤ ይልቁኑ እርሱ ለሚፈቅደዉና ለሚወደዉ አገልግሎት ላይ እናዉለዋለን፡፡

እንደ ምሳሌ አንዳንድ ቀደም ሲል በተሳሳተ እዉቀት የነበሩና እግዚአብሔር እርሱ በፈቀደ ጊዜ የገለጸዉን ሙሉ እዉነት ብንመለከት፤ ከዛሬ ፭፻ (500) ዓመት በፊት መሬት ጠፍጣፋ እንደሆነች ተደርጎ ነበር የሚታመነዉ፡፡ «ጠፍጣፋ አይደለችም» የሚል ግለሰብ ሆነ አካል ካለ ደግሞ እንደ ከሃዲ ነበር የሚቆጠረዉ፡፡ ከዚያ ወዲህ ግን በተጨባጭ ክብ ሞላላ ሉል እንደምትመስል ተረጋግጧል፡፡ እኛም በሥጋዊ ዐይናችን ክብ መሆኗን ሳንመለከት በመሳሪያ ተመልክተዉ ባረጋገጡት ሰዎች አምነን ተቀብለነዋል፡፡ ይህም በአሁን ሰዓት ስለ መሬት ገጽታ ያለን እዉቀት ሙሉ እዉነታ ነዉ ፡፡ እንዲሁም ከመቶ ዓመታት በፊት በዚህች ምድር ዉስጥ ያሉ የተለያዩ ፕላኔቶች በግልጽ አይታወቁም ነበር፤ ምክንያቱም በሥጋዊ ዐይናችን ስለማናያቸዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን በአሁን ሰዓት የተለያዩ ፕላኔቶች እንዳሉ በተጨባጭ በመሳሪያ ተረጋግጧል፡፡ ለወደፊት ደግሞ እግዚአብሔር ገልጾ የሚያሳዉቀንን አናዉቅም፡፡ እኛ ግን በእዉቀታችንና ጥበባችን ልንመካ አይገባም፡፡

ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት «ነፍሳችን ዘላለማዊነት ናት አትሞትም» በማለታቸዉ እንደ ዓመፀኛ ተቆጥረዉ የተገደሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ የእዉቀትና የጥበብ ባለቤት እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ፡፡ አሁን እንደምናየዉ እግዚአብሔር የለሹ ትዉልድ ራሱ እግዚአብሔር በገለጸለት እዉቀትና ጥበብ ተመክቶና ታብዮ እግዚአብሔርን እየተገዳደረና ህልዉናዉን እያስካደ ይገኛል፡፡ የተፈጠረችለትን ምድር ትቶ ባልተገባዉ ፕላኔቶች ላይ ለመኖር እስከማቀድ ደርሷል፡፡ ልክ እንደ ባቢሎን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ለመፍጠር ቆርጦ ተነስቷን፡፡ ይህም ራሱን ለጥፋትና ለመደምሰስ እያዘጋጀ መሆኑን ነዉ የሚያሳየ፡፡ ታዲያ እኛ ሰዎች እነዚህን ፕላኔቶች እዚህ ሆነን ማየት ባለመቻላችን የሉም፣ ዉሸት ነዉ ማለት እንችላለን? አንችልም፡፡ እንዲሁም መሬት ድሮ ጠፍጣፋ ተደርጋ ትታመን ነበርና ከዚህ እዉቀትና አስተሳሰብ አንለይም፣ በድሮ በተሳሳተዉ እዉቀትና አስተሳሰብ እንጸናለን ማለት አለብን? የለብንም፡፡ እግዚአብሔር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ነዉ አስፈላጊዉን እዉቀት ሆነ ጥበብ እንዲሁም ምስጢራትን የሚገልጽልን፡፡

በሃይማኖት ደረጃ ግን እኔም ሆንኩ ሌላ ሰዉ እግዚአብሔር የመሰረተዉን ሃይማኖት መለወጥ፣ ማሻሻል አይችልም፡፡ አዳምና ሔዋን ከገነት ወተዉ ወደ እዚህች ምድር በሥጋ እንዲገለጹ ካደረገ ጀምሮና የመጀመሪያዉ ቅዱሱ ኪዳን በጋብቻ ተመስርቶ በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) የጸናዉ ከዚያም በኖኅ ቀስተ ደመና በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት ተገንብቶ ያደገዉን፤ በመካከለኛዉ የሕግ ዘመን በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ የአብርሃምንና የኢትዮጵያዊዉ መልከ ጼዴቅ ዘሮችን አዋሕዶ ከዚህ ምሉዕ ትዉልድ ከተገኘችዉ ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በሥጋ በመገለጽ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ያጸናዉና ምሉዕ ያደረገዉን ኪዳነ መንፈስ

ቅዱስን፤ ባጠቃላይ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናትን የያዘዉን የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ማንም ፍጡር ሊበርዘዉ፣ ሊከልሰዉ፣ ሊያሻሽለዉ፣ ሊጨምርበት፣ ሊቀንስበት አይችልም:: ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነዉ በኪዳነ ልቦና ሆነ በኪዳነ ኦሪት በመጨረሻም በሥጋ ማርያም ተገልጾ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ( በኪዳነ ወንጌል) ያጸናዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን እዉቀቶች እየበዙ፣ ምስጢራት እየተገለጹ፣ እየተስፋፉ፣ እየተመሰጠሩ ሊመጡ ይችላሉ:: እነሱንም ቢሆን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ተመርምረዉ ነዉ ልንቀበላቸዉ የሚገባዉ እንጂ ርኩሳን መናፍስትም እኛን ለማሳሳት ሁል ጊዜ እየተራቀቁ ስለሚመጡ ጥንቃቄ ማድረግ ግድ ያስፈልጋል::

በዘመናችን ሰይጣናት(ዲያብሎስ) በእግዚአብሔር ስም ሆነ በቃሉ የሚነግዱና የሚያስመስሉ እጅግ ብዙ የ«ሃይማኖት» ድርጅቶችንና ቡድኖችን አቋቁሞ ለዓመፃና ለክህደት ሕይወት አሰልፏቸዉ:: ይኸዉ ፍጽም እግዚአብሔር አልፋና ዖሜጋ የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ፣ ፍጡር ነዉ፣ ነብይ ነዉ፣ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ የሉም... ወዘተ» በማስባል እያስካደና እያሰደበ ይገኛል:: እንዲሁም በእዉነተኛዉ በእግዚአብሔር ቤትና እምነት ዉስጥም ይኸዉ የክህደትና የመናፍቅነት መንፈስ መልኩን ቀይሮና ተመሳስሎ በተሐድሶ መናፍቃን ስም እምነታችንና ሥርዓታችንን በመለወጥ ላይ ይገኛል:: በመሆኑም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚንቀሳቀቁትን በተለያየ አገልግሎት ዉስጥ ያሉ አስመሳይ አገልጋዮችንና አማኞችን ፈቃደኛ ከሆኑ ወደ ትክክለኛ መንገድ ማምጣት፤ ምክንያቱም መልካም የሰሩ መስሏቸዉ በዚህ ዓመፃ ተግባር ላይ የተሰለፉ ሊኖሩ ይችላሉና:: በዓላማ ለጥፋት የሚንቀሳቀሱትን ግን የጥፋትና የዓመፃ ሰዎች ስለሆኑ እንደ እንክርዳድነታቸዉ ሊለዩና ሊወገዙ ይገባል::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ:**</u> ይህ እዉቀቱን፣ ኃይሉን፣ ሥልጣኑን፣ ክብሩን፣ ቅርፊት ሥጋዉን (ገላዉን) የሚያመልክና የሚያስመልክ ትዉልድ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚቀበል ይመስሎታል?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:**</u> የእግዚአብሔር መልእክትና ቃል ትዉልዱ ቢቀበለዉም ባይቀበለዉም ከብሉይ ዘመን ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይተላለፋል:: ዓላማዉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ እንዲሁም እንዲበረቱና እንዲጽናኑ፣ ተስፋቸዉንም ለማለምለም አስቦ ነዉ እግዚአብሔር አገልጋዮቹንና መልእክተኞቹን በተለያየ ዘመን እያስነሳ ለሕዝቡ ቃሉንና መልእክቱን የሚያስተላልፈዉ:: መልእክታቱንና ቃሉን የሚሰሙ ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ የማይሰሙና ሰምተዉ ቃሉንም የማይጠብቁ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍሉበታል:: የእግዚአብሔር እዉነት የበለጠ እየተገለጸ የማይቀበልና እንደ ቃሉ ሆኖ የማይኖር ሰዉ ምንም ከማያዉቁትና የመስማቱንም እድል ካላገኙት ሰዎች ይልቅ እጅግ በከፋ መልኩ ነዉ በሲኦልና በገሃነመ እሳት ዉስጥ መከራና ስቃይ እንዲሁም ቅጣት የሚጠብቀዉ:: ምክንያቱም ሕሊናዉን በማደንደን ነዉና በዓመፃና በክህደት ሕይወቱ የጸናዉ::

የሕይወትን መንገድ ሳያዉቁና ሳይሰሙ በዓመፃና በክህደት ሕይወት ዉስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር ፍርድ ባያመልጡም፤ ፍርዱ ግን ይቀልላቸዋል:: ብዙ ስቃይና

መከራ አያገኛቸዉም፡፡ ከፍርድ የማያመልጡበት ምክንያት ማንኛዉም የአዳም ዘር ነፍሱ በእግዚአብሔር አርአያ ስለተፈጠረችና እግዚአብሔርን የመምሰል ጸጋ ስለተሰጣት እዉነተኛ ፈጣሪዋንና አባቷን በነጻ ሕሊናዉ የመፈለግና በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ የዉዴታ ግዴታ አለባት፡፡ ሕሊናዋ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣት ፈጣሪ እንዳለና ልታመልከዉ እንደሚገባ ሁል ጊዜ ይመሰክርባታልና ነዉ ማንኛዉ ሰዉ ነፍስ ማወቅ ከጀመረ ጀምሮ አምላኩን በእዉነትና በመንፈስ ማምለክ እንዲሁም ሕጉና ትእዛዙን ማክበርና መጠበቅ ያለበት፡፡ ከዚህ ሕይወት ከተለየ ግን ርኩሳን መናፍስት ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጣጠሩት ፈቃዳቸዉን ያስፈጽሙታል፤ በኃጢአት ይጥሉታል፤ በዓመፃና በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እንዲጸና አድርገዉ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ይዳርጉታል፡፡ ምክንያቱም ሰይጣናት የሰዉ ዘሮች በእነሱ ምትክ እንደተፈጠሩ ስለሚያዉቁ ኃይለኛ ቅናትና ምቀኝነት ስላለባቸዉ ለአንድ ነፍስ እንኳ ራርተዉ ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲበቃ ፈተናቸዉን የሚያርቁለት ሰዉ የለም፡፡ ይልቁና ራሱን ወደ እግዚአብሔር ያቀረበና ለሰማያዊ ሕይወት የሚተጋን ሰዉ በበለጠ ሁኔታ በመፈታተን ለመጣልና ለማሰናከል ይተጉበታል፡፡

ሌላዉ ደግሞ ትዉልዱ ስለ እዉነት ራሱን የካደና ስለ እዉነት የሚመሰክር፣ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮቱን የሚፈጽም፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚመላለስና በሕይወቱም የሚሰብክ፣ በሥጋዊዉም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት እዉነተኛ እረኛ ካገኘ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት እንደሚቀበልና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚመላለስ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም በኃጢአት ሕይወት የሚመላለሰዉ ሰዉ መንገዱ ጠፍቶት፣ የሕይወት ምስጢር ሳይገለጽለት ቀርቶ ነዉ እንጂ የኃጢአት ሕይወት አስደስቶት አይደለም፡፡ እንዲሁም በተለያየ የክህደትና የምንፍቅና እምነት ዉስጥ የሚመላለሱት ሰዎች ደግሞ፤ እምነታቸዉ የሕይወት መንገድና ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃቸዉ መስሏቸዉ ነዉ እንጂ የሞት መንገድ መሆኑን ቢያዉቁና ቢያስተዉሉ አንድ ቀን አይቆዩበትም ነበር፡፡ ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀዉ ካለማስመሰልና ካለማታለል የእግዚአብሔርን እዉነት በቅንነትና በእዉነት ለትዉልዱ መግለጽ፣ በሕይወታችን አርአያ መሆን፣ እንደ አገልጋይነታችን ራሳችንን ዝቅ አድርገን በትህትና ሕዝቡንና ምእመኑን ማገልገል፣ ከምግባር አልባ ሕይወት ሙሉ በሙሉ መለየት ነዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሁለት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ፡</u>** የእግዚአብሔር ምስጢርና እዉቀት እንዴትና በምን መልኩ ተገልጸሎት መልእክታቱን እንደ ጻፉ ለማወቅ የሚፈልጉ አሉና ፈቃዶት ከሆን ቢገልጹልን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡</u>** ቀደም ሲል በትንቢት ሆነ በራእይ እንዲሁም እግዚአብሔር እያሳሰባቸዉ የተጻፉት እዉቀቶች ሆኑ መልእክቶች እንዲሁም ወንጌል ከማንበብና በትምህርት ሆነ በስብከት ሲሰጥ ከመስማት ዉጭ እንዴት እየተገለጸላቸዉና እንደጻፉት አላዉቅም ነበር። ለራሴም ጠይቄ አላዉቅም። በእምነት ብቻ ተቀብየዉ አምኜበታለሁ። በመስከረም ወር ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ግን ከራእይ ዉጭ ያሉት ጽሑፎች በምን መልኩ እግዚአብሔር እየተናገራቸዉና እየገለጸላቸዉ እንዲሁም እያሳሰባቸዉ እንደጻፉት አስተዉያለሁ። ራእይ ግን እስከ አሁን ድረስ ስላልተገለጸልኝ እንዲሁም እንዲገለጽልኝም አልፈልግም፤ በምን መልኩ ተገልጾላቸዉ እንደጻፉት አሳስተዋልኩም። ራእይ እንዲገለጽልኝ ያልፈለኩበት ምክንያት ራእይ ካየሁ እግዚአብሔርን በተጨባጭ ነገር እንዳመንኩት ስለሚሰማኝና እግዚአብሔርን በተአምራትና በተጨባጭ ምልክት እንዳምነዉ ስለማልፈልግ ነዉ እንጂ ጸጋዉን በመናቅ ወይንም በማቃለል አይደለም። ነፍሳቸዉን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሱ ጻድቃን እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አይነቶቹ ይህን ጸጋ እንደሚያገኙ የታወቀ ነዉ።

እግዚአብሔር እርሱ በሚፈቅደዉና ለመሳሪያነት የሚጠቀምበት ሰዉ በእዉቀቱና ሕይወቱ ደረጃ በሚመጥነዉ መልክ ነዉ ሊገለጽለትና ሊናገረዉ እንዲሁም ሊታየዉ የሚችለዉ። የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች የራሳቸዉ የሆነ ጠባይ አላቸዉ። ጠባያቸዉና ብቃታቸዉ የተለያየ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ የእያንዳንዱ ጠባይና ሕይወት ተወዶላቸዋል። ለምሳሌ ሐዋርያትን ብንወስድ ከአስቆሮቱ ይሁዳ በስተቀርም ሁሉም የሚወደድ ጠባይና ቅንነት የሞላዉ ሕሊና ነዉ ያላቸዉ። አጠቃላይ ሕይወታቸዉና ጠባያቸዉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ቢሆንም የየራሳቸዉ ጠንካራ ይሁን ደካማ አቋምና ብቃት ነበራቸዉ። ቅዱስ ጴጥሮስን ብንወስድ ቶሎ መጠየቅንና መመለስን የሚወድ ነበር። ቅዱስ ዮሐንስን ብንዉስድ ደግሞ ረጋ ያለ የማይቸኩል ነበር። ቅዱስ ቶማስን ብንወስድ የሚባለዉንና የሚያየዉን ሁሉ ወዲያ የማይቀበል በራሱ ጊዜ ወደ ሙሉ እዉነታ የሚመጣ ነበር። ቅዱስ ናትኤልን ብንመለከት የዋህና ቅን ነበረ። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ምንም ይሉኝታና ፍርሃት የሌለበት፤ ፊሊጥ የማያዉቅ በቀጥታ እግዚአብሔር የሚያናግረዉን የሚናገር ቆራጥ ነበር። ቅዱስ ጳዉሎስ ደግሞ የብሉይ ኪዳን እዉቀት ያካበተና ፈሊጠኛ የነበረ፣ ባለዉ እዉቀትም አስፋፍቶና አመስጥሮ ብዙ መልእክታትን የጻፈ ለእግዚአብሔር ምርጥ ሆኖ የተገኘ ነበረ። ነቢዩ ሙሴ ስለ ወገኖቹ የሚቀናና የሚቆረቆር ለእግዚአብሔርም የታመነ ትሁት ነበረ። ነብዩ ኤልያስ ስለ እግዚአብሔር ሕግ መፍረስና ትእዛዝ አለመጠበቅ የሚቀናና የሚቃጠል ነበር። ጻድቁ ኖኅና ጻድቁ አብርሃም በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ሞገስ የነበራቸዉ አባቶች ነበሩ። ጻድቁ ኢዮብ ከሁሉ የላቀ ትዕግስት ነበረዉ። ካህኑ ንጉሥ መልከ ጼዴቅ ፍጹም እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰ ነበረ። ባጠቃላይ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣

መምህራን፣ የእግዚአብሔር መልእክተኞችና አገልጋዮች የራሳቸዉ ጠባይ፣ አቋም፣ ጽናት፣ ቅድስና፣ ብቃት፣ ትጋት፣ እዉቀት ያላቸዉ ቢሆንም ሁሉም ዓላማቸዉና ግባቸዉ የእግዚአብሔር ቃል እንዲጠበቅና ሰዎች ሁሉ እንደ ፈቃዱ ተመላልሰዉ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ ነዉ:: እንዲሁም እነሱም በቅንነት፣ በእዉነት ፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በቆራጥነት፣ በጽናት፣ በትዕግስት፣ በትህትና በፍቅር በመመላለስ አገልግሎታቸዉንና ምስክርነታቸዉን እንደፈጸሙ፤ እርሱ እግዚአብሔር በፈቀደዉ መልክ ነፍስ ከሥጋቸዉ ተልይታ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ገብተዋል:: የእነሱን ፈለግ የተከተሉና የሚከተሉ እንደእነሱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ::

**ወደ ጥያቄዉ መልስ ስመጣ** በእኔ በኩል የእግዚአብሔር ምስጢርና እዉነት የተገለጸልኝና የተማርኩት እንዲሁም በምን መልኩ እያሳሰበኝ ስጽፍ እንደነበር እግዚአብሔር በፈቀደዉ መጠን አሳዉቃችኋለሁ:: እያንዳንዳችን አፈጣጠራችን አንድ አይነት የሆነ፤ በሥጋ የተገለጽንበት አካል ብቻ በመልክ፣ በቁመና የሚለያይ እንጂ ነፍሳችን በግንባራችን ፊት ለፊት አንጎላችን ዉስጥ ያለችዉና በተለምዶ አእምሮ(ሕሊና) የምንላት ይህ ሥጋችን በድን እንዳይሆንና እንዳይፈርስ ሕይወትን የምትሰጠዉና ከእርሷ በወጣ ኃይል ተዋሕዳ የምትገኘዉ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች የሁላችንም ነፍስ በመልክ፣ በአካል፣ አንድ ዓይነት የሆነች፤ የማታድግ፣ የማታረጅ፣ የማትሞት፣ የዕፆታ ልዩነት የሌላት፣ እግዚአብሔር በፈቀደላት መጠን የምታስተዉልና የምትረዳ ታላቅ ፍጥረት ነች:: ከእግዚአብሔር ባሕርይ የሰረጸች(የወጣች) ስለሆነ እንደ ሌሎች ምሳሌያዊ ባሕርይና ምሳሌያዊ ፍጥረታት እንዲሁም ምሳሌያዉ ሕዋ፣ ምሳሌያዊ ብርሃን፣ ምሳሌያዊ ጨለማ ከመኖር ወደ አለመኖር የማታልፍ እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ የሆነች ናት:: በመሆኑም እግዚአብሔር ለዐይን ቅጽበት እንኳ የማይለያት፤ የምትሰራዉ፣ የምትናገረዉ፣ የምታስበዉ ሁሉ በባሕርይዉ መዝገብ ላይ የሚሰፍሩ ናቸዉ:: ነፍስ ካወቅንና ራሳችን ማመዛዘንና ማገናዘብ ከቻልንበት ጊዜ ጀምሮ ያለዉን የኃጢአት ሆነ የጽድቅ ስራ በባሕርይዉ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል:: የኃጢአት ተግባርና ንግግር እንዲሁም ሐሳብ ከባሕርይዉ መዝገብ የሚያጠፋቸዉና በፍርድ ቀን የማያስጠይቁን የሚሆኑት በእዉነተኛ ንስሐ ስንመለስና ስለ ኃጢአታችንም ስንጸጸት ብቻ ነዉ:: ከዚያ ዉጭ በፍርድ ቀን ሆነ በምድራዊ ሕይወት ዘመናችን ጭምር የሚያስጠይቁንና ዋጋም የሚያስከፍሉን ናቸዉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ የጽድቅ ስራችንና እዉነተኛ እምነትና አምልኳችን በምድራዊ ሆነ በሰማያዊ ሕይወታችን ጭምር ዋጋ የምናገኝበት ነዉ::

ታዲያ ይህች እግዚአብሔርን መምሰል የታላበሰች ነፍስ ፈቃደኛ ከሆነች እግዚአብሔር ቃል በቃል ሊናገራትና ሊያናግራት ይችላል:: እኛ በዚህ ምሳሌያዊ ፍጥረት በሆነዉ በሥጋችን ተገልጸን ምሳሌያዊ ፍጥረትና ምሳሌያዊ ባሕርይ በሞላት ዓለም(ምድር) ዉስጥ አንዱ አንዱን ሊሰማ የሚችለዉ በዚህ በተገለጽንበት ሥጋ አንደበት የሚነገረዉን ወይንም በምልክት የሚገለጸዉን ነዉ:: ተናጋሪዋ ግን ረቂቋ በአንጎላችን ዉስጥ ያለችዉ ነፍሳችን ናት:: ይህ የምንሰማዉ ድምፅ ምሳሌያዊ ድምፅ ነዉ እንጂ አማናዊዉ ድምፅ በአንደበታችን ከመገለጹ በፊት በነፍሳችን(በሕሊናችን) የታሰበዉና የተነገረዉ ነዉ:: ያ የምናስበዉ ሐሳብ በእግዚአብሔር ሆነ እግዚአብሔር በፈቀደላቸዉ ፍጥረታት ይሰማል፤ ይደመጣል:: ምክንያቱም ከሕሊናችን ተንጸባርቋልና:: ሰዎች ግን እንዳይሰሙት

በሥጋቸዉ ተገድበዋል። ሐሳባችን በእግዚአብሔርና እርሱ በፈቀደላቸዉ ቅዱሳን ዘንድ ብቻ አይደለም የሚሰማዉና የሚደመጠዉ፤ ለዐይን ቅጽበት እንኳ ከሕሊናችንና ከአካላችን በማይለዩትና በረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) በተገለጹት፣ የእያንዳንዳችንን ሕይወት ለመፈታተንና ለማጎሳቆል በዲያብሎስ በተመደቡት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ጭምር ነዉ። ስለዚህ እኛ የሰዉ ዘሮች ከኃጢአት መጠበቅ ያለብን ከሐሳብ ጀምሮ መሆን አለበት። ምክንያቱም በሐሳባችን የመጣዉ ኃጢአት በንግግር ወይንም በተግባር ይገለጻል፤ ይፈጸማልና ነዉ። እንዲሁም ርኩሳን መናፍስት ያን ሐሳባችን እዛዉ ነፍሳችን (ሕሊናችን) አጠገብ ሆነዉ ስለሚሰሙ ያሰብነዉን እንድንፈጽም ይፈታተኑናል፤ ይገፋፉናል። ከዚህ በተጨማሪ እዛዉ ሆነዉ ሥጋዊ ጆሮ በማያዳምጠዉ ረቂቅ ድምፅ ነፍሳችንን ይናገሯታል፤ ያሳስቧታል። ነፍሳችንም ፈቃደኛ ከሆነችላቸዉ ያን የተናገሯትን ወይንም ያሳሰቧትን በተግባር ወይንም በንግግር ወይንም በጽሑፍ ትገልጸዋለች። በነጻ ፈቃዷ ተጠቅማም ንግግራቸዉን ሆነ የሚያሳስቧትን ልትቃወምና እንዲሁም በተግባር ሆነ በንግግር ወይንም በጽሑፍ ላለመግለጽ ትችላለች። የእግዚብሔርን ሆነ የርኩሳን መናፍስት ድምፅ ሰምታ ለመቀበል ሆነ ላለመቀበል ሙሉ ነጻነት አላት። ዋጋም የምታገኘዉ ሆነ የምትከፍለዉ እንደ ምርጫዋና ዉሳኔዋ ነዉ እንጂ እንደ ፍላጎቷ አይደለም። የምትጠየቀዉም በተግባር ሆነ በንግግር እንዲሁም በጽሑፍ የዓመፃ ሐሳቧን እንደገለጸችዉ መጠን ነዉ።

ከራሷ ሆነ ከርኩሳን መናፍስት የመነጨዉን ክፉ ሐሳብ በነጻ ፈቃዷ ተጠቅማ መቃወምና ወደ መልካም ሐሳብ መምጣት ይጠበቅባታል። ያለበለዚያ ሐሳቧ ተሳክቶላት ያንን ያመፃ ሆነ የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ሐሳብ ወደ ተግባር ባትፈጽመዉ እንኳ እንደ ተግባሩ ባይሆንም ትጠየቅበታለች፤ ዋጋም ትከፍልበታለች። ምክንያቱም ቢመቻችላት ኖሮ ወደ ተግባር ትፈጽመዉ ነበርና ነዉ። ይህም የሚያሳየን የእግዚአብሔር ፍርድና ቁጥጥር ምን ያህል ጥብቅ እንደሆነ ነዉ። ምክንያቱም በራሱ አርአያ ነፍስን ስለፈጠራትና ከባሕርይዉ ስላሰረጻት እንደሱ እንድታስብና እንድትፈጽም እንዲሆም እንድትፈርድና እርሱን እንድትመስል ይፈልጋልና ነዉ።

ወደ እኔ የእግዚአብሔር ድምፅ አገላለጽ ስንመጣ። ያ ረቂቁን በሥጋዊ ጆሮ የማይደመጥ ነገር ግን ሁል ጊዜ ከእኛ የማይለየዉ ድምፅ በግልጽ በተለየ ሁኔታ የተረዳዉትና ያስተዋልኩት ለመስከረም ፩÷፳፻፫ (1/01/2003) ዓ.ም አጥቢያ እኩለ ሌሊት ስድስት ሰዓት ላይ ነዉ። ያ ነፍሴ ብቻ የምታዳምጠዉ ድምፅ ተከትዬ እርሱ የገለጸልኝንና ያሳወቀኝን እንዲሁም በእኔ እዉቀት የማዉቃቸዉን በሚያሳስበኝ ድምፅ ተከትዬ ብእሬን በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመርኩ። ያ የተለየ ድምፅ ሲቆም አቆማለሁ። በእንደዚህ ዓይነት ቀንም፣ ሌሊትም፣ ስራ እየሰራሁም፣ ከሰዉ ጋር ሆኜም፣ እረፍት ላይ ሆኜም በተለያየ ቀናትና ሰዓት ወደ ሕሊናዬ (ነፍሴ) የሚመጣዉን ማሳሰቢያ ሁሉ እስከ መስከረም ሃያ ስድስት ፳፻፫ ዓ.ም ድረስ በወረቀት ላይና በመቀመሪያ(በኮምፒተር) ላይ ጻፍኩ።

የመጀመሪያዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ የሆነዉ ሰማያትና የተወሰኑ መናፍስት በሰማያት ሲያምፁ የተፈጠረችዉ ሁለተኛዋ ምሳሌያዊ ቦታ የሆነችዉ ዓለምና በዓለም ዉስጥ ያሉት ይህች

የምንኖርባት ምድርና ከምድር ጎን ያለችዉ ገነት እንዲሁም አዳምና ሔዋን በገነት ሲያምፁ የተፈጠረችዉ ሦስተኛዋ ምሳሌያዊ ቦታ የሆነችዉና ከዓለም ዉጭ ያለችዉ ሲኦል፤ እንዲሁም ክርስቶስ ነፍሳትን ከሲኦል ሲያወጣ የተፈጠረችዉ ከሲኦልና ከዓለም ጎን ያለችዉ ማረፊያ ቦታ የተገለጹልኝ፤ ልክ በአስኳላዉ(በዓለማዊ ትምህርት) የዓለም ካርታ ተስለዉ የትኛዉ ሀገር ኬትኛዉ አገር እንደሚዋሰንና የት እንዳሉ ሲገለጽልን በሥጋዊ ዐይናችን እያየን እንደምንረዳዉና እንደምናዉቀዉ ሁሉ፤ ነፍሴ ብቻ ይህንኑ ቦታ እንደ ካርታዉ በሥዕል መልክ ነዉ የተገለጸላት:: ያ ብቻ አይደለም በፍርድ ቀን ካለመኖር ወደ መኖር የምትመጣዉ አምስተኛዋ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ የምትሆነዉ ገሃነመ እሳትና ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ የምትዘጋጀዉ ዓመፀኛ መናፍስትና ነፍሳት በብርሃናዊ ባሕርይ ተሸፍነዉ በአንድ ቦታ በበድን ሕይወት የሚኖሩበት ቦታ በሥዕላዊ አገላለጽ የተማርኩት:: ከዚህ በተጨማሪ ከነዚህ ዓለማት ዉጭ ያለዉ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ እግዚአብሔር እንደ አማናዊ ባሕርይዉ የሚኖርበት አማናዊ ሕዋ በሕሊናዬ እንዳስተዉለዉና እንዳዉቀዉ ተደረገ:: የማይደረስበትና የማይታወቅ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ በመሆኑ እጅጉን አደነኩ:: ሳይገባኝ እነዚህ ሁሉ ስለተገለጹልኝ ባዶነትና ኀዘን ተሰማኝ::

ሰማያት፣ ዓለም፣ ሲኦልና ማረፊያ ቦታ፣ ሁሉም የሚነካኩበት ቦታ አላቸዉ:: በዚያች በተነካኩበት ቦታ ብቻ ነዉ ነፍሳት ሆኑ መናፍስት የሚተላለፉበትና ከአንዱ ወደ አንዱ ዓለም የሚገቡበት:: እነዚህ ዓለማት በብርሃናዊ ብርሃን የተከበቡ ሲሆን፤ ማንም ፍጥረት ወደ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሊገባ ሆነ ሊያልፍበት አይችልም:: ልክ የእሳት ራት እሳት ዉስጥ ስትገባ እንደምትኮማተር፤ ፍጥረት ወደእዚያ ቢገባ ይህ እድል ነዉ የሚያጋጥመዉ:: በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሊገባ ሆነ ሊያልፍ የሚችለዉ በብርሃናዊ ባሕርይ የተገለጸ ፍጥረት ብቻ ነዉ:: ይህም የሚሆነዉ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ነፍሳችን የመጨረሻዉ ቅድስናና ብቃት ደረጀ ላይ ስትደርስና እንደ አማናዊ ፍጥረትነቷ ስትገለጽ ብቻ ነዉ ወደእዚያ ዉስጥ መግባት የምትችለዉ እንጂ ምሳሌያዊ ባሕርይ ሆነ ምሳሌያዊ ፍጥረት ተላብሳ ወደዚያ መግባት አትችልም::

ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ መግባት የሚችሉት፤ በፍርድ ቀን የመጨረሻ ፍርድ የሚጠባበቁት ሰዎች«ርኩሳን ነፍሳት» ተብለዉ በሲኦል ያሉ፤ በምድራዊ ዘመናቸዉ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃ ሕይወትና ብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱና ምንም እንኳን የሕይወትን መንገድ ባያገኙም በተወሰነ ቅንነታቸዉና መልካም ስራቸዉ ምክንያት በማረፊያ ቦታ ላይ የሚገኙ፤ ነገር ግን በዚያ ቆይታቸዉ በእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃ እምነትና ሕይወት መያዝ የልቻሉ፤ እንዲሁም በገነት፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሲኦል፣ በምድርና በሰማያት ዉስጥ ያሉ የሰዎች ነፍስ ቁጥር በምድር ዉስጥ ካሉት ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ቁጥር ጋር እኩል በሚሆንበት ሰዓትና ይህች ምድር ሆነች ዓለም ከመኖር ወደ አለመኖር ስታልፍ በመቅሰፍት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ የሚጠሩት ሰዎች ነፍስ፤ ባጠቃላይ ለሰማያዊ መንግሥት የማይበቁ ሰዎች(ርኩሳን ነፍሳት)፤ በዚህች ምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት ጋር የመጨረሻ ፍርድ በማረፊያ ቦታ ተቀብለዉና ረቂቅ የማይጠፋ እሳትና ረቂቅ የማይሞቱ ትሎች ወደሞሉበት ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ተጥለዉ ለሕያዉነት ዘመን ፍዳቸዉን ከተቀበሉ በኋላና በተቃራኒዉ ደግሞ በዚህች ዓለም ዉስጥ ከምድር ጎን

በገነት ዉስጥ ያሉት  ጻድቃን ሰዎች (የጸደቁ ነፍሳት)ና በማረፊያ ቦታ ላይ ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ሕይወትና ብቃት የያዙ ነፍሳት፣ እንዲሁም በፍርድ ቀን በምሕረት ሞት ከዚህች ምድር ወደ ማረፊያ ቦታ የሚገቡ ሰዎች(ነፍሳት) የእግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን የመጨረሻ ፍርድ ተመልክተዉ ወደ ሰማያት ከገቡና ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ የሆኑት ሲኦል፣ ማረፊያ ቦታ፣ እንዲሁም ዓለም ከመኖር ወደ አለመኖር አልፈዉ በአማናዊ ሕዋ ከተተኩ በኋላ ለሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ በሰማያት ዉስጥ በቅዱሳን መላእክት ሥርዓት እግዚአብሔር ካመለኩና የመጨረሻዉን ቅድስናና ጸጋ ከተላበሱ በኋላ ነዉ፡፡

በእኛ ሕሊና ደረጃ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኃላ ማለት ሕያዉ ዘመን ማለት ነዉ፡፡ ምክንያቱም ከዛሬ እግዚአብሔር ያልኖረበት ጊዜ የለምና እስካልኖረበት መጀመሪያ ከሌለዉ መጀመሪያ ድረስ ዘመኑን ማወቅ አይደለም መገመት እንኳን ስለማንችል ነዉ፡፡ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኃላ ማለት በእኛ ሕሊና ሊደረስበት ቀርቶ ሊታሰብ የማይችል ከነጌቲቭ የትየለሌ(አኒፊኒት) (-∞)እስከ አሁን ድረስ ያለዉ ዘመን ያትየለሌ(ኢንፊኒቲ) ስለሆነ፤ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኃላ ማለት በእኛ አቆጣጠር የትየለሌ(ኢንፊኒት) ነዉ፡፡ ከዚህ ዘመን በኃላ ነዉ በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንደ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ተግባራቸዉ ደረጃ ፍዳቸዉን የሚቀበሉት ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳት ነፍሳት የሚነጹት፡፡ በመጨረሻም የተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋል፤ እነሱም የራሳቸዉን ህልዉና አተዉ በብርሃናዊ ባሕርይ ተሸፍነዉ በበድን ሕይወት አንዳች ሳያዉቁና ሳያስተዉሉ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ በነጥብ ቦታ ላይ ለሕያዉነት ዘመን ይኖራሉ፡፡ ገሃነመ እሳትም ምሳሌያዊ ባሕርይ ናትና ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ዉስጧ ካሉት ፍጥረታት ጋር ከመኖር ወደ መኖር ታልፋለች፡፡ ቦታዉም በአማናዊ ሕዋ ይተካል፡፡

ከዚሁ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኃላም በሰማያት ዉስጥ ያሉት ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት የተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ ከመኖር ወደ አለመኖር አልፎ እንደ አማናዊ ባሕርያቸዉ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጸዉ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ከአማናዊዉ አስገኛቸዉና አባታቸዉ እግዚአብሔር በመባል ከሚታወቀዉ አልፋና ዖሜጋ ጋር ሕያዉ ሆነዉ በመጨረሻዉ ቅድስናና ብቃት ሕይወት ይኖራሉ፡፡ ሰማያትም ምሳሌያዊ ባሕርይ ናትና ዉስጧ ከሚኖሩት ምሳሌያዊ ባሕርይ ጋር ከመኖር ወደ አለመኖር ታልፋለች፤ በቦታዉም በአማናዊ ሕዋ ይተካል፡፡ በመጨረሻም መጀመሪና መጨረሻ የሌለዉ አማናዊ ሕዋ ቦታና ዓመፀኞች መናፍስትና ነፍሳት በበድን ሕይወት የሚኖሩበት ቦታ ብቻ ይቀራል፡፡ በወላጆቻችን ግንኙነት አማካይነት በሚፈጠረዉ ፅንስ ነፍሳችን ከሥጋችን ተዋሕዳ ሕያዉ የሆነች ፍጥረት ብትሆንም፤ ልክ በእናታችን ማኅፀን ዉስጥ ሆነን አንዳች የምንናዉቀዉና የምናስተዉለዉ ነገር እንደሌ ሁሉ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኃላ እነዚህ ዓመፀኛ መናፍስትና ነፍሳት አንዳች ነገር ሳያስተዉሉና ሳያዉቁ ነዉ በበድን ሕይወት በብርሃናዊ ባሕርይ ተሸፍነዉ በአንድ ቦታ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ የሚኖሩት፡፡

ለወደፊት የሚፈጸሙ ትንቢቶችና አሁን ከላይ በዝርዝር ለወደፊት የሚሆኑትን የጻፍኳቸዉ ቃል በቃል እግዚአብሔር በሥጋዊ ጆሮ በማይደመጥ ድምፅ አማካይነት ለነፍሴ የተናገራትንና

የገለጸላትን ነዉ። ስለ ጥንቱ እኔ ስለማላዉቀዉ ነገር ደግሞ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ እየተተረከልኝ(እየተነገረኝ) ነዉ የጻፍኩት። ስለማዉቃቸዉ እዉቀቶች ደግሞ እንዲሁ በነፍሴ ብቻ በሚሰማዉ ድምፅ ማሳሰቢያ እየተሰጠኝ ነዉ። ይህ ሁሉ የሆነዉ ሕሊናዬ እያወቀ በተለያየ ሰዓትና ቀን ነዉ። ታዲያ እግዚአብሔርን የማዉቀዉ በዚሁ በሥጋዊ ጆሮ በማይሰማ ድምፅ እንጂ ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሆነ አልተመለከተኩትም። እንዲህ ነዉ ብዬ እግዚአብሔርን ልገልጽ ሆነ እኔም በተጨባጭ ላዉቀዉ አይቻለኝም። ነገር ግን ለዐይን ቅጽበት እንኳ ከሕያዉ ፍጥረታቱ እንደማይለይና ከረቂቃኑ ፍጥረታት ጀምሮ እስከ ግዙፍ ፍጥረታት ድረስ ከእርሱ በወጣ ኃይል የተፈጠሩና ካለመኖር ወደ መኖር የመጡ ስለሆነ፤ በእርሱ ዕይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆኑ ካለ እርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊደረግ እንደማይችል በሚገባ ላስተዉልና ልረዳ ችያለሁ። ለዚህም ነዉ ቅርፊት ሥጋ ለባሾችን ሳልፈራና እንዲሁም ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ከንቱ የሆነ ሥጋዊ መጠበብ ሳለደርግ የእግዚአብሔርን መልእክታት እርሱ ባሰሰበኝና በመራኝ መንገድ ሁሉ ለአዳም ዘር የማስተላልፈዉ። እንዲሁም ከሰዎች ሕሊናና እዉቀት በላይ የሆነዉን ትዉልዱ ቢቀበለዉም ባይቀበለዉም፣ ቢያምነዉም ባያምነዉም በግልጽ ያሰፈርኩት።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ለመግለጽ እወዳለሁ። ይህች ምድር በዓለም ዉስጥ ያለች፤ ከማረፊያ ቦታ ሆነ ከሲኦል እንዲሁም ከሰማያት ጋር የተነካካችበት ቦታ ያለ ሲሆን፤ የሰዎች ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይና ረቂቅ አካል እንደ መናፍስት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ለብሳ እንደ እምነቷና ምግባሯ ወደ ሰማያት፣ ወደ ማረፊያ ቦታ፣ እንዲሁም ወደ ሲኦል የምትገባዉ በዚሁ ምድር ከሌላዉ ዓለም ጋር በተነካካችበት ቦታ ነዉ። ወደ ገነት የሚገቡት ደግሞ ገነት ከዚህች ምድር ጎን በዓለም ዉስጥ ስለሆነች በቀጥታ ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሰዉ ነዉ። በፍርድ ቀን ደግሞ ዓለም ከማረፊያ ቦታ ጋር በተነካካችበት ቦታ ነዉ ወደ ማረፊያ ቦታ የሚገቡትና እንዲሁም ማረፊያ ቦታ ከሰማያት ጋር በተነካካችበት ቦታ ነዉ የመጨረሻን ፍርድ ተመልክተዉ ወደ ሰማያት ዉስጥ የሚገቡት። እነዚህ ቦታዎች በሥዕል መልክ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪዉ መልእክት ሽፋን (ልባስ) ላይ በምን መልኩ እንደተቀመጡ መመልከት ይቻላል።

የዓለም ፍጻሜ የሚሆነዉ የእኛ የሰዉ ዘሮች ነፍስ በሰማያት፣ በገነት፣ በሲኦል፣ በማረፊያ ቦታና ምድር ዉስጥ ያለዉ ቁጥር ብዛት፤ በዚህች ምድር ዉስጥ ካሉት እልፍ አእላፋት(በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ቁጥር ብዛት ጋር እኩል ሲሆን ነዉ። በዚያን ጊዜ አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ሰዎች በምሕረት ሞት ነፍሳቸዉ ረቂቅ አካል ተላብሳ ወደማረፊያ ቦታ ፈጣሪዋን ኢየሱስ ክርስቶስን ይህች ዓለም ከማረፊያ ቦታ ጋር በምትነካካበት አቅጣጫ እየተመለከቱት በደስታ ሲሆን፤ በዓመፃና በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት እየተመላለሱ ያሉ ሰዎች ደግሞ በመቅሰፍት ሞት በፍርድ ቀን የምትዘጋጀዉን ገሃነመ እሳትን እያዩ ነዉ ለመጨረሻ ፍርድ ወደ ማረፊያ ቦታ በረቂቅ አካል የሚሄዱት። በዚህች ምድር ዉስጥ ለዘመናት በዓመፃ ያሉት ሰይጣናትም(ርኩሳን መናፈስትም) በጭንቀትና በስጋት ሆነዉ ነዉ የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ለመቀበል ወደማረፊያ ቦታ የሚገኙት። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጨረሻ

ፍርድ በእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መናፍስት(መላእክት)ና በቅዱሳን ነፍሳት ታጅቦ በክብርና በኃይል ለሁሉም የሚገለጸዉና የመጨረሻ ፍርዱን የሚሰጠዉ ከዚህች ዓለም ዉጭ ባለችዉ ማረፊያ ቦታ ነዉ እንጂ ዳግም ወደ ምድር(መሬት) መቶ አይደለም:: ስለዚህ «ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ አገር፣ በእዚህ ከተማ ተገለጸ፣ መጣ... ወዘተ» የሚል ሰዉ፤ እርሱ በሽዋጁ(አታላዩ) ዲያብሎስ መንፈስ የተታለለና ለጨለማዉ ገዥ አገልግሎት የተሰለፈ ሰዉ ነዉ እንጂ፤ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ አይደለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉ እንደ ፀሐይ ተገልጾ የሚታየዉ በዓለም ፍጻሜ በፍርድ ቀን ይህች ዓለም(ምድር) ከማረፊያ ቦታ በተነካካችበት አቅጣጫ ነዉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ:**</u> «ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ በእግዚአብሔር ድምፅ እየተመራሁ ጻፍኩ» ላሉት ድምፁ ምን እንደሚመስል በምሳሌ ቢያስረዱን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:**</u> ሁላችንም አላወቅነዉም፣ አላስተዋልነዉ እንጂ የእግዚአብሔር ድምፅ ተለይቶን አያዉቅም:: እኔም በተለየ ሁኔታ ያወኩትና ያስተዋልኩት ከመስከረም ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ጀምሮ ነዉ:: ከዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ የተለያየ ምስጢራት ተገልጸዉልኝ ነበር:: ነገር ግን ያ የገለጸልኝ እግዚአብሔር መሆኑን ባዉቅም በምን መልኩ እንደሆነ ግን በደንብ አላወኩም፣ አላስተዋልኩም ነበር:: እንዲሁም ለምናኔ ሕይወት እንደወሰንኩኝ ለወደፊት ለኢትዮጵያ ምን እንደምሆን ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ ተነግሮኝ ነበር:: ነገር ግን የእግዚአብሔርና የዲያብሎስ ድምፅ የመለየቱ ብቃት አልነበረኝምና «ሰይጣን ከዓላማዬ ሊያስቀረኝ ፈልጎ ለመፈታተን ይሆናል» በማለት በጥርጣሬ ነዉ የሰማሁት እንጂ፤ እስከ መስከረም፳፱÷፳፻፫ (29/01/2003) ዓ.ም ድረስ አልተቀበልኩትም፤ ለሰዉም «እንዲህ ተብያለሁ» ብዬ ተናግሬ አላዉቅም ነበር:: መስከረም ፳፱÷፳፻፫ (29/2003) ዓ.ም ከመስከረም አንድ ፳፻፫ (1/01/2003) ዓ.ም ጀምሮ እንዳዉቀዉና እንዳስተዉለዉ በተደረገዉ ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ፤ የቅድስት አርሴማ ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ ቤተክርስቲያን ተገኝቼ ቅዳሴ እያስቀደስኩ እያለ ነዉ ያ የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ የተነገረኝ፤ የእግዚአብሔር ድምፅ መሆኑን ያወኩትና ሙሉ በሙሉ አምኜ የተቀበልኩት::

እግዚአብሔር አምላክ ሕያዉ ፍጥረቱ ከሆነችዉ ሕሊና(ነፍስ) ለዐይን ቅጽበት ያህል እንኳ አይለይም:: ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሕያዉ ፍጥረት በነጻ ሕሊናዉ የማሰብ ሥልጣን ቢኖረዉም፤ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ዉስጥ ነዉ:: እግዚአብሔር ከፈለገ ከራሳችን ፈቃድ ዉጭ ሊያናግረንና ሊያስመሰክረን ይችላል:: ይህም የሚያሳየን በራሳችን ሥልጣን ብቻ ልናስብ፣ ልንናገር፣ ልንሰራ እንደማንችል ነዉ:: እግዚአብሔር ፈቃዱ ስለሆነ ብቻ ነዉ እንደፈለግነዉ ልናስብ፣ ልንናገር፣ ልንሰራ የቻልነዉ እንጂ ይህን ነጻነት ሊገድበዉ ይችላል::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** ያ በሥጋዊ ጆሮ በማንኛዉም ሰዉ ሊሰማ የማይችለዉ የእግዚአብሔር ድምፅ ነፍሳችን ብቻ የምትሰማዉ የተለየ ጸጋ ሲሰጣት ብቻ ነዉ:: ለምሳሌ ሁለት ሰዎች አጠገብ ላጠገብ ተቀምጠዉ አንደኛዉ አንደኛዉን ምን ድምፅ ሳያሰማ በሕሊናዉ(በአእምሮዉ) «ዳቦ ስጠኝ?» ቢለዉ፤ ተናገሪዉ ሰዉ ከሕሊናዉ ያንን ጥያቄ ድምፅ ባይኖረዉም አዉጥቶታል:: ነገር

ግን አጠገቡ ያለዉ ሰዉ ያንን አማናዊ ድምፅ የመስማት ጸጋ ስላልተሰጠዉ አይሰማዉ እንጂ፤ ጸጋዉ ቢሰጠዉ ምን እንደተባለ ሰምቶ ያንን የጠየቀዉን ዳቦ ሊያቀርብለት ይችል ነበር፡፡ እኔም የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዳዉቅና እንዳስተዉል እንዲሁም እንድሰማዉ ሳይገባኝ የተለየ ጸጋ ስለተሰጠኝ ነዉ ልሰማዉና ቃል በቃል ሲናገረኝና ሲያስታዉሰኝ እጽፍ የነበረዉ፡፡ ሰዉ የተለየ ጸጋ ከተሰጠዉ ሌላ ሰዉ እያሰበ ያለዉን ሊያዳምጥ ይችላል፡፡ እንኳን ሰዉ ሰይጣናትም ተፈቅዶላቸዉ ይኸዉ እያንዳንዳችን እያሰብን ያለነዉን ሕሊናችን(ነፍሳችን) ጋር ሆነዉ ያዳምጣሉ፡፡ ስለዚህ ሰዉ ከኃጢአት ሊጠበቅ የሚገባዉ ከሐሳቡ መሆን አለበት ማለት ነዉ፡፡ ሰይጣናት ዋና ከሳሾቻችን ስለሆኑ እንኳን በምንሰራዉና በምንናገረዉ አይደለም በምናስበዉ ሐሳብ ጭምር ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ የክፋት፣ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የስድብ፣ የጥላቻና የጥል ሐሳብ ቢመጣብን እንኳ በሕሊናችን ልንቃወመዉና በዉስጣችንም እግዚአብሔርን ይቅርታ ልንጠይቀዉ ይጠበቅብናል፡፡ ያኔ ሰይጣናት አፍረዉና ተበሳጭተዉ ተናደዉ ከእኛ ይርቃሉ፤ እኛ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጸጋን(ኃይልን) እንላበሳለን፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>** በዝርዝር በገለጹልን መሰረት የተረዳሁት የተለያዩ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች የራሳቸዉ የሆነ ጠባይ፣ ብቃት፣ ትጋት፣ ጽናት፣ እዉቀት፣ ቅድስና እንዳላቸዉና እንደ ማንነታቸዉ እግዚአብሔር እንደሚጠቀምባቸዉ ላስተዉል ችያለሁ፡፡ ለዚህም ነዉ በእርሶ በኩል በተጻፋት የእግዚአብሔር መልእክቶች ዉስጥ የመንፈስ ቅዱስ መልእክታትና ዉጤቶች ናቸዉ ተብለዉ የተገለጹት «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ዉስጥ የተገለጹት እዉነታዎች፣ ምስጢራት፣ ትንቢቶች፣ እዉቀቶች ሆኑ በአንደኛዉ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ የተጻፋት በተለየ ስለ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናትና ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵዊነት በዝርዝር የተገለጸበት «ኢትዮጵያዊዉ በማንነቱ ፍለጋ» «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ» «ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ ምስጢሮች የተገለጹበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት ቁጥር አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት» በሚል የተገለጹት፤ እንዲሁም በአንደኛዉ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ እንደራሴ አማካይነት የተጻፋት በተለየ አሁን እየሆነ ስላለዉና ወደፊትም በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ላይ ስለሚሆነዉና ስለሚከሰተዉ ክስተት ገልጽ ባለ ቋንቋ የቀረበበት «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን መልእክት አንድ እስከ አምስት» በሚል በተገለጹት የእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ አገላለጣቸዉ፣ አቀራረባቸዉ፣ አጻጻፈቸዉ የተለያየ የሆነዉና ነገር ግን በሦስቱም ጸሐፊዎች የተገለጸዉ እዉነታ፣ ምስጢራት፣ ትንቢቶች፣ እዉቀቶች ዓላማቸዉና ግባቸዉ አንድ የሆነ፤ የእግዚአብሔርን እዉነታ የገለጸና ትዉልዱንም ለንስሐ የሚጠራና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚነትና አስፈጻሚነት የሚያበቃ፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ምስጢር አገሩ የሆነችዉንና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስራት አገር የሆነችዉ የቅዱሱ ኪዳን ባለቤትና ባለአደራ የሆነችዉ ኢትዮጵያ ትንሣኤዋን የሚያበስርና ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሆነ ከዓለም በእግዚአብሔር ቁጣ በሆኑት በተለያዩ መቅሰፍቶችና ቅጣቶች ከምድር እንደሚጸዱ ወይንም እንደሚጠረጉ ወይንም እንደሚቆረጡ ወይንም እንደሚወገዱ ወይንም እንደሚደመሰሱ ነዉ የሚገልጸዉና ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ፍቅር የተላበሱ ደግሞ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ እንደሚደርሱና ለእግዚአብሔር መንግሥትም ታጭተዉ

ለሰማያዊ መንግሥት የሚበቁ በምድራዊ ሕይወታቸዉም ተባርከዉ በበረከት፣ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት፣ በብልጽግና፣ በጤና ፣ ባጠቃላይ በመልካም ሕይወት እንደሚኖሩና ብሩህ ተስፋ እንዳላቸዉ የሚገልጽ ነዉ:: ታዲያ በነዚህ መልእክታት ትዉልዱ እንዳይሰናከል ምን ምክር ይሰጣሉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በመጀመሪያ ለመግለጽ የምፈልገዉ አለ:: ይኸዉም እኔ ከሁለቱ እግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች ጋር ልደመርና ልቆጠር አይገባኝም:: ምክንያቱም እኔ ገና ትላንት ነዉ ለእግዚአብሔር አገልጋይነትና መልእክተኛነት የተጠራሁት፤ እንዲሁም አንዳች ቅድስና ሆነ ብቃት፣ እዉቀትና ትጋት የሌለኝ ኃጢአተኛና መሃይም፣ ደካም ሰዉ ነኝ:: እነዚያ አባቶች ግን ዘመናቸዉን በአገልግሎትና በተለያየ ፈተናና መከራ ዉስጥ ያለፉ፣ ተፈትነዉ እንደ ወርቅ ጠርተዉ ራሳቸዉን ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሱ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ራሳቸዉን አሳልፈዉ የሰጡ፣ የእናት አገራቸዉ የኢትዮጵያና የቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታቸዉ ፍቅር በዉስጣቸዉ እለት እለት እየተቀጣጠለ የሚኖርና ስለ እዉነት ኀዘንተኛ የሆኑ፣ ነገረ መስቀሉ በሕሊናቸዉ ዉስጥ የሚደማ፣ የአደራ እናታቸዉ የእመ አምላክ መሪሪ ኀዘን በሕሊናቸዉ ዉስጥ የሚያነባ፣ ባጠቃላይ ለአሥራዎቹና ከአንድ ከፍል ዘመን አጋማሽ በላይ በተጋድሎ ዉስጥ ያሉ ስለ እዉነት ራሳቸዉን የካዱና ስለእዉነት ማንን ሳይፈሩ የሚመሰክሩ ናቸዉ:: ስለዚህ እንደ እኔ ዓይነቱ ሰዉ እንኳን ከእነሱ እኩል ሊጠራና ሊቆጠር ቀርቶ እነሱ ባሉበት ቦታ እንኳ መቀመጥ የማይገባዉ ነዉ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ራሳቸዉን የሚያመጻድቁትንና የሚያስታብዩትን እንዲሁም እዉቀታቸዉንና ክብራቸዉን የሚያመልኩትንና የሚያስመልኩትን ለማሳፈር ሲል፤ ከእዉቀት እዉቀት፣ ከቅድስና ቅድስና፣ ከአገልግሎት አገልግሎት፣ ከትጋት ትጋት ዉስጥ የሌለበትን አንድ ተራ ምስኪን ሰዉ መጠቀም እንደሚችል ለማሳየትና የእግዚአብሔር ምርጫና የዓለም ምርጫ የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት እንዳላቸዉና እንደማይገናኝ ለትዉልዱ ለመግለጽ ፈልጎ ነዉ እኔን ለአገልግሎትና ለመልእክተኛነት የመረጠኝ::

**ወደ ጥያቄዉ መልስ ስገባ** በአሁን ዘመን ሰዉ እዉቀቱ፣ ኃይሉ፣ ሥልጣኑ፣ ገላዉ፣ ክብሩ፣ ሀብቱ፣ ጣዖት ስለሆነበት ለእግዚአብሔር መልእክትና ቃል ቦታ አይሰጥም:: «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ» የሚለዉም፤ የእግዚአብሔርን እዉቀትና ሙሉ እዉነታ ነጥብ በማትሞላዉ በራሱ እዉቀት ገድቦና በራሱ የዉሸት እዉነት በመመራትና የሥጋና ደም ስሜቱን ለመፈጸም ለማስፈጸም ስለሚፈልግ፤ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ለመቀበልና ለመፈጸም ፈቃደኛ አይደለም:: ተስፋዉን ምድር ያደረገ ትዉልድ ደግሞ እግዚአብሔር ሆነ እምነት የዉሸት አድርጎ ስለቆጠረዉና ሕሊናዉ በፖለቲካ ስለተበከለና ስለተመረዘ ሌት ተቀን የሚተጋዉ የቅርፊት ሥጋዉን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ስለሆነ ለእግዚአብሔር ቃል ቦታ የለዉም:: ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ፍቅር የተላበሱ አገልጋዮችና ምእመናን እንዲሁም ሕዝቦች ስላሉ፤ እነሱ የእግዚአብሔርን መልእክትና ቃል ተቀብለዉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚሰለፉ ተስፋ እናደርጋለን:: ከንቱ በሆነዉ በምድራዊ ነገር ለሚመኩ ደግሞ እግዚአብሔር ልቦና እንዲሰጣቸዉ እንጸልያለን::

ባጠቃላይ በእግዚአብሔር መልእክታት እጅግ ብዙዎቹ ተሰናክለዋል፣ ንቀዉታል፣ አጣጥለዉታል፣ ከዚያም ባለፈ ሌሎች እንዳይጠቀሙበት አፍነዉ ይዘዉታል። እንኳን ተራዉ ሰዉና ምእመን ቀርቶ በእዉነተኛዉ እምነት ዉስጥ ሆነዉ በተለያየ አገልግሎት የተሰማሩት ሰዎች ሳይቀር በራሳቸዉ ነጥብ በማትሞላ እዉቀታቸዉ ገምግመዉ እንደ ተራና የቅዠታም ጽሑፍ አድርገዉ ቆጥረዋል። ነገር ግን ሁሉ ተፈጽሞ ሲመለከቱ በአቋማቸዉና በድርጊታቸዉ ያፍራሉ። ለዚህም የሚደርሱት የተወሰነ ቅንነትና እዉነተኛነት የተገኘባቸዉ ናቸዉ እንጂ በእግዚአብሔር እዉነት ላይ ያላገጡና የናቁ ግን ከዓመፃ ልጆች ጋር እግዚአብሔር በተለያየ ቁጣዉ ከምድር ያጸዳቸዋል (ይጠርጋቸዋል)። የእግዚአብሔር ቁጣ ማለት አንድ አይነት ሳይሆን የተለያየ ነዉ። ለምሳሌ የመቅሰፍት በሽታ፣ ረኃብ፣ ጦርነት ፣ ድርቅ፣ ሽብርና ሁከት፣ ጎርፍ፣ እሳተ ጎሞራ፣ አዉሎ ንፋስ፣ ሰደድ እሳት፣ ፍንዳታ፣ ግጭት፣ አደጋ፣ የማይታወቁ የተለያዩ መቅሳፍቶች... ወዘተ የመሳሰሉተ ናቸዉ።

ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ እግዚአብሔር ብዙ አገልጋዮችና መልእክተኞች አሉት። ነገር ግን በእርሱ ተቀብተዉና ተመርጠዉ ለእንደራሴነትና ለባለሟልነት ታጭተዉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡ አገልጋዮቹ በምድር የመጨረሻ ወሳኞችና እንደ እግዚአብሔር ሆነዉ የሚዳኙ፣ የሚወስኑ ናቸዉ። ስለዚህ ከእያንዳንዱ አገልጋይና ምእመን የሚጠበቀዉ በሥጋና ደም ስሜት ባልሆነ መልኩ የሚሰማዉንና የሚያምንበት ቅን ሐሳብ፣ መልካም ተግባር፣ እዉነተኛ ሕይወት ለእንደራሴዎቹ ማቅረብና ማሳመን ነዉ እንጂ «እኛ ከእናተ በላይ አዋቂ ነን፤ ይህ ግድ መፈጸም አለበት» በማለት ብንታበይ በተዘዋዋሪ «እኛ ከእግዚአብሔር በላይ ነን» ማለታችን እንደሆነ ልናዉቅና ልናስተዉል ይገባል። ምክንያቱም በየትኛዉም የቅድስና ደረጃ ላይ እንገኝ፣ ጸጋዉ ተሰቶን ከቅዱሳን መላእክት ጋር በሰማያዊ ሥርዓት ላይ እየተሳተፍን ወደ ምድር እንመለስ፣ እግዚአብሔር በራሱ መስፈርት እነዚህን እንደራሴዎች ከእኛ አልቆ ስለመረጠና ፈቃዱን ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንደ ልቡ ሆነዉ ስለተገኙለት ነዉ ቀብቶ በእዉነተኛዉ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ በርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) ደረጃ እና በርእሰ ሊቃነ ካህናት(እጨጌነት) (ፓትርያርክነት) የሚያስቀምጣቸዉ። እንዲሁም ከተለያዩ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና አማኞች የሚቀርቡ ሐሳቦችን ሆነ ተግባሮችን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እየመረመሩ እንክርዳዱን ከስንዴዉ የመለየት ብቃት እግዚአብሔር ስለሚሰጣቸዉ ነዉ። በእኛ መልካም የሚመስለን ሐሳብና ተግባር በእግዚአብሔር ዘንድ መጥፎና ዓመፃ ሊሆን ይችላልና።

በዓለም ዉስጥ የተለያዩ መንግሥታት ለዲያብሎስ እንደ ልቡ መሆን ስለቻሉ፤ እንዲሁም ፈቃዱን ስለሚፈጽሙና ስለሚያስፈጽሙ ነዉ የራሱን አገልጋዮች ወደ ወንበር እያመጣ ለዘመናት የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሲያስጨንቅ፣ ግፍና በደል፣ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ሲያስፈጽም የኖረዉና አሁንም ያንኑ ፈቃዱን በየአገሩ ባሉ መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ እንዲሁም ካድሬዎች እያስፈጸመ ያለዉ። አሁን ግን የባለጊዜነቱ ዘመን ስለተደመደመበት ወንበሩ ለእዉነተኛ ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ተላልፎ ይሰጣል። በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ይፈጸማል። እዉነት ባለ ጊዜ ትሆናለች፤ ሐሳት ደግሞ ትደመሰሳለች።

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: እግዚብሔር ለእኛ ለአዳም ዘር ከጥፋትና ከዉድቀት እንዲሁም ከመደምሰስ ለማዳን ከጥንት ከብሉይ ዘመን አንስቶ እስከ አሁን ድረስ መልእክቱን በአገልጋዮቹ አማካይነት አስተላልፎልናል:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ዓለም እዉነታ ለይተን እንድናዉቅ፣ እየሆነዉ ስላለዉና ወደፊት ስለሚሆነዉ ጭምር በግልጽ በመልእክቱ አስተላልፎልናል:: በዋናነትም ለአገልግሎትና ለመልእክተኛነት የመረጠዉ ደግሞ ኢትዮጵያዉያንን ነዉ:: ነገር ግን ኢትዮጵያዉያን ሆኑ የዓለም ሕዝቦች አልተቀበሉትም:: ስንቱን የዓለም እዉቀት ልብወለዱን ሳይቀር የሚያነበዉና ጊዜዉን ለምድራዊ እዉቀት ሆነ ትዕይንት የሚሰዋዉ፤ ለብዙ ዓመታት መስዋዕትነት ከፍሎ በመማር፣ በማጥናት፣ በመመራመር ዘመኑን የሚያሳልፈዉ የአሁን ትዉልድ፤ ስለምን ይሆን እንኳን ዓመታት አይደለም ወራት የማይፈጁበትን የእግዚአብሔር መልእክታት ለማንበብና የተባለዉን ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነዉ? እንዲሁም ኢትዮጵያ ከሌላዉ ዓለም አገራት ተለይታ የታየችዉና ስለምን ይሆን የእግዚአብሔር ልዩ አገልጋዮችና መልእክተኞች ኢትዮጵያዉያን ሆነዉ የተገኙት?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:__ እኔም የሚያሳዝነኝና የሚያስገርመኝ በምድራዊ ሕይወታችን ቢሳካልንም ባይሳካልም፣ ብንጠቀምበትም ብንጎዳበትም በዚህች ምድራዊ ቆይታችን ዘመን ለሥጋችን የተለያዩ እዉቀቶች ከሕፃንነት ጀምሮ በአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም በኮሌጅና በዩንቨርስቲ ደረጃ በትጋትና በንቃት እንማራለን፤ እናስተምራለን:: ከዚያም ባለፈ እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፈጻሜ ድረስ በመማርና በመመራመር ዘመናችንን እናሳልፋለን:: ነገር ግን ይህ ሁሉ ድካማችንና ልፋታችን ለሥጋችን ቢጠቅመንም በሥጋ ሞት ይደመደማል:: ለሕያዉ ነፍሳችን ግን ምናልባት በምድራዊ ዘመን ቆይታዋ የጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲቀልላት ሊያደርግ ቢችልም፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት ግን አያበቃትም:: ለሕያዉነት ኑሮዋ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆና ካልተገኘች በስተቀር አንዳች ነገር አያደርግላትም:: ታዲያ ለዚህ ምድራዊ ለዐይን ቅጽበት እድሜያችን እንደምንተጋ ሁሉ ዋና ገንዘባችን ለሆነችዉ ለሕያዉ ነፍሳችን (ሕይወታችን) አንዳች ትኩረት አለመስጠታችንና የምትጠቀምበትን አለመፈለጋችን ምን ያህል ማንነታችንና ታላቅ ተስፋችንን አለማወቃችንን ነዉ የሚያሳየዉ::

ለነፍሳችን ጊዜ መስጠት ጊዜ እንዳባከን አድርገን ስለምንቆጥርና ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ህልዉና በመጠራጠር የገነትና የመንግሥተ ሰማያት ኑሮ፣ እንዲሁም የሲኦልና የገሃነመ እሳት ፍርድ እንደሌለ አድርገን ስለምናስብ ነዉ ይህች ወደ እዉነተኛ ሕይወትና ኑሮ መሸጋገሪያ ዘመናችንን በአግባቡ መኖር ተስኖን ራሳችንን እንደ እንስሳ በመቁጠር «እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን» በማለት የከሃዲያን አስተሳሰብ ይዘን በራሳችን ላይ የሞት ሞት ፍርድ እየፈረድን ያለነዉና፤ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰችዉን ሕያዉ ነፍሳችንን ንቀን ለአፈርና ለምስጥ አስረክበን ለምንሄደዉ ሥጋችን ብቻ ራሳችንን ሰዉተን የምንኖረዉ:: በዚህች ምድር(መሬት) ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖረን ሕያዉነት እድሜ አንጻር የዐይን ቅጽበት እድሜ በማትሞላ ዘመናችን እንደፈለግነዉ ሆነን፣ ሁሉ የእኛ ሆኖ ብንኖር ምን ዋጋ አለዉ? ምክንያቱም አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ካላደረግንና እንደ ቃሉ ሆነን ካልተገኘን ነፍሳችን ከሥጋችን በሥጋ ሞት ስትለይ

ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሳ እስከ ፍርድ ቀን በድቅድቅ ጨለማ ሲኦል ዉስጥ በስቃይና በጭንቀት ስለምትኖር፤ እንዲሁም ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ እንደ ዓመፃዋ ደረጃ እሳቱ በማይጠፋ ትሎቹ በማይሞቱበት ገሃነመ እሳት ዉስጥ ፍዳዋን እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ስለምትቀበል ነዉ።

አንድ ጨለማ ክፍል ዉስጥ እንኳን ለዘመናት መታሰር አይደልም ለአንድ ዓመት መታሰር ምን ያህል ነዉ የሚያስጨንቀን? በዚህ ግዙፍ ሥጋችን(ምሳሌያዊ ፍጥረት) በተገለጽነዉ ምሳሌያዊ ፍጥረት በሆኑት አይጦች፣ እንሽላሊቶች፣ ትኋኖች፣ የተለያዩ ትሎች ጋር እንኳን ለሕያዉነት ዘመን አይደለም ለአንድ ቀን በአንድ ክፍል ዉስጥ አብረን ማደርና መኖር ምን ያህል እንደሚያሰቅቅና እንደሚያስጨንቅ ለማስተዋል አይከብደንም። በገሃነመ እሳት ዉስጥ ደግሞ በረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ስለምንገለጽ ረቂቅ እሳት ለሕያዉነት ዘመን ከማይጠፋ እንዲሁም ረቂቅ ትሎች ለሕያዉነት ዘመን ከማይሞቱ ትሎች ጋር ስለምንኖር እንደ ምድራዊ ዓመፃ፣ ክህደት፣ እንዲሁም ርኩሰት ደረጃ ስቃያችንን እንደምንቀበልና ስለ ዓመፃችንና ማላገጣችን ዋጋ እንደምንከፍልበት እያወቅን፤ በዐይን ቅጽበት እድሜያችን በዓመፃ፣ በክህደት፣ እንዲሁም በርኩሰት ሕይወታችን መጽናታችን ነዉ ዉስጤን የሚያንገበግበኝና የሚያሳዝነኝ። ብቻ ብዙ ብዙ ነገር አለ «ሆድ ይፍጀዉ» ብሎ ማለፍ ሳይሻል አይቀርም።

ወደ ኢትዮጵያ መመረጥ ስንመጣ ይህች አገር የእግዚአብሔር ምስጢር አገሩና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስራት አገር ናት። አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረዉ ወደ እዚህች ምድር ሲገቡ የተገለጹበት ሥጋ ከዚህች ምድር አፈር ነዉ የተበጀዉ። እንዲሁም የመጀመሪያ መኖሪያ አገራቸዉ ይህችዉ «ዔደን ገነት» የተባለች የአባይ ወንዝ የሚናሳባት አገር ናት። ሕዝቦቿም በኪዳነ ልቦና እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ ሲያመልኩ የነበረ፤ ከዚያም በኪዳነ ኦሪት አምልኳቸዉን ሲፈጽሙ የነበረ፤ በመጨረሻም እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ በመሰረተዉ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ በተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንተዉ ያለ፤ ባጠቃላይ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተጠብቆባት ያለች ብቸኛ አገር ስለሆነችና ለዘመናት የተለያዩ ፈተናዎችንና ጥቃቶችን ተቋቁማ አምላኳን አጥብቃ በመያዟ ምክንያት ነዉ ለዓለም ብርሃንነት የተመረጠችዉና ለእዉነተኛ አገልግሎት ልጆቿ የታጨት።

በአሁን ዘመንም ስለ እዉነት የሚያነቡና የሚጸልዩ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭዉ ዓለም በገዳም፣ በዋሻ፣ በበረሃ፣ በገጠር፣ በከተማ፣ በየአብያተክርስቲያኑ ወድቀዉ ያሉ የኢትዮጵያን ትንሣኤ የሚጠባበቁ እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ ምርጦች አሉ። የዓመፃ ልጆች በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራቸዉ ከተቆረጡና ከምድር ከጸዱ(ከተጠረጉ) በኋላ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለመጠበቅና ለማገልገል ወደ ወንበር ይመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ሥርዓት ይዘረጋሉ፤ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ በአራቱም ማእዘን ያስፈጽማሉ፤ ይፈጽማሉ። እግዚአብሔርም ኢትዮጵያን ሆነ ዓለምን በበረከትና በምሕረት ይጎበኛል። ኢትዮጵያም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ ትጸናለች። ማንም ምንም ሊያደርጋት አይችልም። ሊያጠፏት የተነሱና የሚነሱ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ። በእርሷም ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ ላይ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ

እየተመራ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በነጻነት ይኖራሉ፣ ለፈቃዱም ይሰለፋሉ:: በምድራዊ ዘመናቸዉም ተባርከዉ ለሰማያዊ ሕያዉ መንግሥት ይበቃሉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: እግዚአብሔር የማይችለዉና የማያዉቀዉ ነገር እንደሌላ ይታወቃል:: እንዲሁም ርኅሩኅና መሐሪ መሆኑ ይታወቃል:: ታዲያ በሰማያት ዉስጥ መናፍስትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ሲፈጥር በዓመፃቸዉ ወደ እዚህች ምድር የጣላቸዉ ርኩሳን መናፍስት፣ ኃጢአት ወይንም ዓመፃ እንዳይፈጽሙ አድርጎ ለምን አልፈጠራቸዉም? እንዲሁም እንደሚያምጹ እያወቀ ለምን ፈጠራቸዉ? ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ስህተታቸዉ ብቻ ለዚህ ለከፋ ጉስቁልና ሕይወት ዳረጋቸዉ? በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚህ ከሰማያት ወደ ምድር በተጣሉት ርኩሳን መናፍስት ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት ለመፍጠር አቅዶ ሁለቱን ነፍሳት ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በዓለም ዉስጥ ባዘጋጃት ገነት ዉስጥ ማስገባት ለምን አስፈለገዉ? እንዲሁም አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ሁለቱ ነፍሳት በአንድ ጊዜ ስህተታቸዉ አሁን ለምናየዉ ለእዚህ ምድራዉ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይና ጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ዳረጋቸዉ? እንዲሁም ከምድራዊ ዘመን በኃላም በሲኦል ከዚያም በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንዲፈረድባቸዉ ለምን አደረገ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እናንተም እንዳላችሁ እግዚአብሔር አንዳች የማይሳነዉ ሁሉን ማድረግ የሚችል ኃያልና ሁሉን አዋቂ አምላክ ነዉ:: ነገር ግን በእርሱ ደረጃ ብቻ የሚታወቅ እንጂ በእኛ እንኳን ማወቅ አይደለም መገመት የማንችላቸዉ ብዙ ነገሮች አሉ:: እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ: እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ይችላል ምንም የሚሳነዉ ነገር የለም ብለናል:: ታዲያ እግዚአብሔር ራሱን በራሱ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ ይችላል ወይ? ምላሻችሁ ምንድ ነዉ? «አይችልም» ካላችሁ ለእግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም ሁሉን ማድረግ ይችላል ብለናል:: «ይችላል» ብንል ደግሞ ህልዉናዉን የሚያጣ አምላክ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቶች መልስ የሌላቸዉ ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ::

«እግዚአብሔር መናፍስት እንዳያምጹ ማድረግ አይችልም ነበር ወይ? እንዲሁም እንደሚያምጹ አያዉቅም ነበር ወይ?» ላላችሁት ጥያቄ ያለዉ መልስ: እግዚአብሔር በሕያዉነት ዘመኑ ቀደም ሲል አንዳች ፍጥረት የሚባል ያልፈጠረ ብቻዉን በረቂቅ ባሕርይዉ መጀመሪያና መጨረሻ በሌላዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ መጀመሪያ ከሌለዉ ጊዜ ጀምሮ ብቻዉን ይኖር ነበር:: ባሕርይዉና ክብሩ ለብቻዉ መቅረቱን በሕያዉነት ዘመኑ አዉቆና የባሕርይዉና የክብሩ ተከፋይ ስሙን አመስጋኝ ፍጥረት ለመፍጠር ወስኖ ከባሕርይዉ ፍጹም እርሱን የመሰሉ ሕያዋን እልፍ አእላፍ ወትእልፊት(የትሪሊዮን ትሪሊዮን) መናፍስት ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ አማናዊ ባሕርያቸዉ በምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) እንዲገደብና እንዲገለጽ በማድረግ በመጀመሪያዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ በሆነዉ በሰማያት ዉስጥ ራሳቸዉን እንዲያገኙ አደረገ:: ነጻ ፈቃድና ምርጫ እንዲኖራቸዉ አደርጎ ስለፈጠራቸዉ ያ ነጻ ፈቃዳቸዉና ምርጫቸዉ ይታይ ዘንድ ማንነቱን በግልጽ ሳይገልጽላቸዉ በነጻ ሕሊናቸዉ እርሱን እንዲፈልጉና በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልኩት ነበር ፍላጎቱና አጠባበቁ:: ይሁንና ለሁሉ አለቃ እንዲሆን ያሰበዉ «ሳጥናኤል» በመባል የሚታወቀዉ የአሁኑ ዲያብሎስ እርሱ

የተገለጸበት ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ከሌሎቹ መናፍስት በላይ የሆነ መስሎ ስለታየዉና ቀድሞ ያልነበረችዉን ትዕቢት ለመጀመሪያ ጊዜ በማሰብ ቀድሞ አለመኖሩን ሕሊናዉ እየመሰከረበት፣ እንዲሁም የፈጠረዉ አምላክ በሕሊናዉ(በነፍሱ) ቃል በቃል ፈጣሪዉ እንዳለ እየነገረዉ ሕሊናዉን በማደንደን፣ አብሯቸዉ የተገኙትን መናፈስት ሁሉ «እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ እኔን አምልኩ» በማለት ሲያዛቸዉ፣ እጅግ ከቁጥር በላይ የሆኑት እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መናፍስት በነጻ ፈቃዳቸዉና ምርጫቸዉ እንዲሁም ፈጣሪያቸዉ እግዚአብሔር፣ እርሱ ሳጥናኤን እንዳልፈጠራቸዉና እንዳይቀበሉት በሕሊናቸዉ ቃል በቃል ሲናገራቸዉና ሳጥናኤልም በእነሱ አካል መገለጹንና እንደነሱ መሆኑን ተመልክተዉና በሕሊናቸዉ የተነገራቸዉን የፈጣሪ ቃል ሰምተዉና አምነዉ ሳጥናኤልን የተቃወሙትና «እንቀበልም» ያሉት ሲሆን፣ ከጸኑት አንጻር እጅግ እጅግ ጥቂቶቹ አንድ መቶኛ እንኳ የማይሞሉት እንደነሱ መሆኑንና የተለየ አለመሆኑን እየተመለከቱ እንዲሁም በሕሊናቸዉ ፈጣሪያቸዉ እየተናገራቸዉ ሕሊናቸዉን በማደንደን ሳጥናኤልን ስለተቀበሉትና ስላመኑት እንዲሁም ጥቂቶቹ ደግሞ መሃል ሰፋሪ ሆነዉ መቃወምና አለመቀበል ሲገባቸዉ «ምናልባት ቢሆንስ» በማለት በጥርጣሬና በዝምታ ስለተቀበሉት ነዉ እግዚአብሔር ወዲያ ባሕርይዉን ወስኖ በሚገባቸዉ መልክ በመካከላቸዉ በብርሃናዊ ባሕርይዉ በመገለጽ ለእያንዳንዳቸዉ እንደ እምነታቸዉና ጽናታቸዉ እንዲሁም ዓመፃቸዉና ጥርጣሬያቸዉ ዋጋ የከፈለዉ::

ልክ ለምሳሌ በቤታችን ዉስጥ ያልተጠበቀና የልታሰበ ቃጠሎ ቢነሳ ወዲያዉ የምንወስደዉ እርምጃ በሕሊናችን የመጣልንን ዉሳኔ እንደሆነ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ያልጠበቀዉ ክስተት በሰማያት ዉስጥ ሲፈጠር ወዲያዉ የወሰነዉ ዓመፃኞቹንና ተጠራጣሪዎቹን መናፍስት ስለ ዓመፃና ጥርጣሬያቸዉ ዋጋ የሚከፍሉበትን ቦታ ማዘጋጀት ነበር:: በዚሁ መሰረት ከሰማያት ቀጥላ ለዓመፀኞቹ መቀጫ ቦታ ሁለተኛዋ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ ዓለምን በመፍጠር በዉስጧ ደግሞ ምድርን በማዘጋጀትና ድቅድቅ ጨለማን በመሙላት ዓመፀኞቹንና ተጠራጣሪ የነበሩትን መናፍስት ጸጋቸዉን ገፎ በጉስቁልና ሕይወት እንዲኖሩ «ርኩሳን መናፍስት» ብሎ ወደ ምድር ጣላቸዉ::

ከዚያም ልክ እኛ ልጆቻችን ቢሞቱ ሌላ ልጅ እንደምንፈልግና የመተካት አቅሙና ብቃቱ እስካለን ድረስ እንደምንተካ፣ እርሱም ወደ ምድር በተጣሉት መናፍስት ምትክ ሌሎች ሕያዋን ነፍሳት ካለመኖር ወደመኖር ለማምጣት ወስኖ በዓለም ዉስጥ ከምድር ጎን ገነትን አዘጋጀ:: ከዚያም በሰማያት ዉስጥ ያሉት መናፍስት በአንጼ ተፈጥረዉ ራሳቸዉን ስላገኙ በዓመፃ ስለወደቁ እንደዚያ ዓይነት ክስተት እንዳይፈጠር በሁለት ነፍሳት አማካይነት ከእርሱ ባሕርይ የሚሰርጹት(የሚወጡት) ሕያዋን ነፍሳት ካለመኖር ወደመኖር እንዲመጡ ለማድረግ ፈልጎ አዳምና ሔዋን በመባል በምድራዊ ስማቸዉ የምናዉቃቸዉን ሁለቱን ነፍሳት ከባሕርይ በማስረጽ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸዉ አማናዊ ባሕርያቸዉ በምሳሌያዊ ባሕርይ እንዲገደብና እንዲገለጽ በማድረግ በገነት ዉስጥ ለተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ የሚያስፈልጋቸዉን ምሳሌያዊ ባሕርይ ፍጥረታት ፈጥሮ አኖራቸዉ:: ከዚያም እንደ ቀደሙት መናፍስት ዓመፃ እንዳይፈጽሙ ለተገኘነታቸዉ ማረጋገጫ በገነት ዉስጥ የተፈጠረላቸዉን ሁሉ እንዲጠቀሙና እንዲበሉ ነገር ግን አንዲት ፍሬ እንዳይበሉ፣ እንዲሁም በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት ነፍሳት በእነሱ አማካይነት ካለመኖር ወደመኖር እንደሚመጡና

የሁሉም ወላጆችና ኃላፊዎች እንደሚሆኑ፣ ከዚያም ቁጥራቸዉ በዓመፃቸዉ ምክንያት ወደ ምድር ከተጣሉት ርኩሳን መናፍስት ጋር እኩል በሚሆንበት ጊዜ ወደ ሰማያት ዉስጥ እንደሚገቡና በቅዱሳን መላእክት ሥርዓት እንደሚኖሩ በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾ ነገሯቸዉ ነበር። እነሱ ግን ገና አንድ ነፍስ ካለመኖር ወደመኖር ሳትመጣ እምነታቸዉና ጽናቸዉ ይታይ ዘንድና በነጻ ፈቃዳቸዉና ምርጫቸዉ የሚወስኑት ዉሳኔና አቋም ይታይ ዘንድ ግድ አስፈላጊ ነበርና፤ በምትኩ ሌላ ፍጥረት መፈጠሩን የተረዳዉ ዲያብሎስ ተፈቅዶለት ከምድር ወደ ገነት በመግባትና የገነት ኑሮዋቸዉን በመጠየቅ ያልተፈቀደላቸዉን ፍሬ እንዲበሉና ከበሉ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር እንደሚሆኑ በመግለጽ የመብላት ምኞት አነሳሳባቸዉ። ሔዋንም በመጀመሪያ በምኞት ተሸንፋ ያልተፈቀደላትን ፍሬ በላች፤ በመቀጠልም ያልተፈቀደላቸዉን ፍሬ አዳምን በመጋብዝ አበላችዉ።

ያኔ ነዉ የእግዚአብሔር ጸጋ የተለያቸዉና እግዚአብሔርም ለሁለተኞቹ ዓማፂያን መቀጫ ትሆን ዘንድ ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ የነበረችዉን ምድር አሁን በዐይናችን የምናያቸዉን ሆነ የማናያቸዉን ፍጥረታት ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ሁለቱ ነፍሳት እንዲቀጡበትና እንዲገለጹበት ይህን የለበስነዉን ሥጋ ከአፈር አበጅቶ በገነት ተገልጸዉበት የነበረዉን ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ደግሞ ወደ አለመኖር በማሳለፍ የተፈጠረዉን ሥጋ እንዲዋሐዱ በማድረግ በመሬት ላይ እንዲገለጹ ያደረገዉና ዓመፃቸዉም ከርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ዓመፃ በላይ በመሆኑ ከጉስቁልና ባሕርይ በተጨማሪ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ እንዲላበሱና በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲኖሩ ያደረገዉ።

ከላይ የተገለጹት ሁሉ መናፍስት በሰማያት ዉስጥ ባያምጹ ኖሮ ዓለምና ገነት አይፈጠሩም ነበር፤ እንዲሁም ምድርና ሰዎችም አይፈጠሩም ነበር። ከዚያም አዳምና ሔዋን በገነት ዉስጥ ባያምጹ ኖሮ እኛ በዚህች ምድር ላደፈና ለጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም ለጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ አንዳረግም ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ ወደ ገነት ገብቶ አዳምና ሔዋንን ባያሳስትና ሁለተኛ ዓመፃ ባይፈጽም ኖሮ በገነት የአዳምና ሔዋን ዘሮች ቁጥር ምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል በሚሆንበት ሰዓት እነሱ ወደ ሰማያት ሲገቡ፤ እርሱም ከሠራዊቶቹ ሰይጣናት ጋር የቅጣት ዘመናቸዉ በዓለም ዉስጥ አጥሮላቸዉ በእግዚአብሔር ህልዉና ተሸፍነዉ የራሳቸዉን ህልዉና አተዉ በበድን ሕይወት ዉስጥ አንዳች ሳያዉቁና ሳያስተዉሉ ይኖሩ ነበር። ዓለምም ወደአለመኖር አልፋ በአማናዊ ሕዋ ተተክታ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሰማይትና በዉስጧ የሚኖሩት ቅዱሳን መናፍስትና ነፍሳት ብቻ ይቀሩ ነበር። እንዲሁም ሲኦል፣ ገሃነመ እሳት የሚባሉ ሌላ መቀጫ ቦታ አይፈጠሩም ነበር።

ሲኦል የተፈጠረችዉ አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረዉ በዚህች ምድር በሥጋ እንዲገለጡ በመደረጉና የሞት ሞት ስለተፈረደባቸዉ፤ በሥጋ ሞት ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይ እንዲኖሩባትና እንደ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ እንዲቀጡበት ነዉ። እንዲሁም ሰይጣናት ሆኑ ሰዎች በምድር ላይ ዓመፃቸዉ፣ ክህደታቸዉ፣ ርኩሰታቸዉ ባይከፋ ኖሮ ገሃነመ እሳት አይዘጋጅም ነበር። ይሁንና ሰይጣናት ሆኑ የሰዉ ዘሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እግዚአብሔርን ከማስደሰትና ስለ ዓመፃቸዉም ከመጸጸት

ይልቅ በበደል ላይ በደል፣ በዓመፃ ላይ ዓመፃ በመፈጸማቸዉና በኃጢአታቸዉም ባለመጸጸታቸዉ ምክንያት የባሰዉ መቅጫ ቦታ ገሃነመ እሳት እንዲዘጋጅ እግዚአብሔርን ስላስገደዱት ነዉ ገሃነመ እሳት የሚፈጠረዉ።

ባጠቃላይ እግዚብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍሳቸዉ ባልጠበቀዉና ባላሰበዉ በተቃራኒ አቋም ስለተገኘችና በዓመፃዋም ስለጸናች ነዉ ቅጣቷ ሊያይልባት የቻለዉ። እግዚአብሔር በእዉነት ስለሚጸጸቱትና ንስሐ ለሚገቡት ስለ ዓመፃቸዉ ዋጋ እንዲከፍሉ አድርጎ ፍጹም ይቅርታና ምሕረት የሚያደርግ አምላክ ነዉ። ለዚህም ነዉ ሊሆን የማይችለዉ፣ ነገር ግን የሆነዉ፤ ሁሉን በአምላካዊ ሥልጣኑ ማድረግ ሲችልና ማንም «ለምን እንዲህ አደረክ?» ብሎ የማይጠይቀዉና የማይከራከዉ ሆኖ ሳለ፤ ያ በእኛ አንደበት ሊገለጽ የማይችለዉን መለኮታዊ ባሕርይዉንና ክብሩን እንዲሁም ኃይሉን ዝቅ አድርጎና አዋርዶ ይህን ጎስቋላ ሥጋችንን ገንዘቡ አድርጎ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በምድር በመገለጽ፣ ምን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን በግልጽ አስተምሮንና ለእኛ አርአያ ለመሆን ሁሉን መልካም ተግባር ፈጽሞና በመጨረሻም ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ እዉነት ራሳችንን በመካድ እንድንመሰክርና እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነን በመገኘት ራሳችንን ለሰማያዊ መንግሥት እንድናበቃ የተለያየ ጸዋትዎ መከራ በመቀበልና እንዲሁም የድኅነትን መንገድ ለማቅለልና ሕያዉ ሆነን ከእርሱ ጋር እንድንኖር ለማስቻል ቅዱስ ሥጋዉን ክቡር ደሙን ሰዉቶ በመስጠት እንድንበላዉና እንድንጠጣዉ ያደረገዉ። የሚሳዝነዉ ግን ቀላሉን የድኅነት መንገድ «አንፈልግም፣ ሕያዉ እንድንሆን አድርጎ ለሰማያዊ መንግሥት የሚያበቃንን ሥጋህንና ደምህን አንበላም፣ አንጠጣም፣ ስለ ዓመፃችን ሆነ ስለ ክህደታችን እንዲሁም ስለ ርኩሰት ተግባራችን ንስሐ አንገባም፣ ካንተ የሆነዉን እዉነት አንቀበልም፤» በማለት በዓመፃችን ጸንተን ራሳችንን ለከፋዉ ቅጣት አዘጋጅተናል።

ታዲያ እግዚአብሔር ምን ያላደረገልን ነገር ኖሮ ነዉ እንደ ጨካኝ ልናየዉ የምንችለዉ? እኛስ ምን ጎደለብን ብለን ነዉ ከዲያብሎስ ጋር አንድነት ፈጥረን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ ተግባርና እምነት ላይ የምንሰማራዉና የምንገኘዉ? ምንስ ተስፋ አድርገን ነዉ በዓመፃ፣ በክህደተ፣ በርኩሰት ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት የምንመላለሰዉ? ምንስ እንዲደረግልን ፈልገን ነዉ ንስሐ አንገባም፣ የእግዚአብሔርን እዉነት አንቀበልም የምንለዉ? ማንስ ያድነናል ስለ ዓመፃችን ዋጋ ስነከፍል? በምንስ አቅማችን ነዉ የእግዚአብሔርን የተለያየ ቁጣ የምንቋቋመዉ? ምንስ ቢደረግልን ነዉ እጃችንን ለእግዚአብሔር የምንሰጠዉና ለፈቃዱ የምንሰለፈዉ? እንግዲህ «እንዲህ አልተደረገልንም» የምንለዉ ነገር እንደሌለና እኛም ለመጠየቅ አቅሙና ክብረ ሕሊና (ሞራል) እንደሌለን ልናስተዉል ይገባል። ምክንያቱም ሊደረግልን ከሚገባዉ እጅግ በላይ እግዚአብሔር አድርጎልናል። ከእኛ ነዉ እንጂ ከእርሱ አንዳች የጎደለ ነገር የለም። በመሆኑም በሚያመዛዝነዉና በሚያገናዝበዉ ሕሊናችን ተመርተን በእዉነተኛ ንስሐ ለእግዚአብሔር እጃችንን ልንሰጥና በሙሉ እዉነት ልንመላለስና ልንኖር ይገባል። በተቀረ ግን የእግዚአብሔርን የከፋ ቅጣት በምድርም በሰማይም መቀበላችን አይቀርም። እግዚአብሔር እጅግ አፍቃሪና ርኅሩኅ ነዉ። በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ በሚጸኑት እብሪተኞችና ትዕቢተኞች ላይ

ደግሞ ፍርዱ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ነዉ።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡**

## ምዕራፍ ሦስት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ በማቴዎስ ወንጌል በምእራፍ 28 ከቁጥር 16እስከ20 ድረስ «አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸዉ ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፣ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ነበሩ:: ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸዉ:- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ:: <u>እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያተመቃችኋቸዉ፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸዉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸዉ፤</u> እኔ እስከ ዓለም ፈጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::» በማለት ተናግሯል:: ይህም የሚያሳየዉ ማንኛዉንም የአዳም ዘር ለእግዚአብሔር መንግሥት ለማብቃትና ራስም ለመብቃት በመጀመሪያ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ (በሥላሴ) ስም መጠመቅና በእግዚአብሔር የታዘዙትን ትእዛዛት መጠበቅ እንዳለበት ነዉ በግልጽ የሚያሳየዉ:: ስለዚህና እንዲሁም ለሕሊናችን የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነትን ለመረዳት የሚከብደዉን ቢገልጹልን:

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር ያልተገለጹትን ምስጢራትንና እዉነታዎች የሚገልጸዉ  መገለጽ ባለበት ወቅትና ዘመን ነዉ:: በዚሁ መሰረት የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ ባሕርይዉንና ማንነቱን  ወስኖና ሰዉሮ ለአዳም ቃል በገባለት መሰረት ይኸዉም «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለዉ» ባለዉ መሰረት፤ የእርሱ በምድር በድንግል ማርያም ሥጋ መገለጥ ዘመን ሲደርስ ሰዉ ሆነ:: ከዚያም እንደማንኛዉ ሰዉ ከኃጢአት በስተቀት ሁሉን ፈጽሞ በምድር ተመላለሰ:: በምድር በተገለጸበት ሠላሳ ዓመት ሲሞላዉ ለዓለም እዉነትን መግለጥ ጀመረ:: እንዳይሰናከሉበትና ቀጣይ ትዉልድ የእርሱን ማንነት እንዲያዉቁ እርሱና እግዚአብሔር አንድ መሆናቸዉንም ጭምር አስተማረ:: የተለያዩ ተአምራትንና ፈዉስ በአምላካዊ ሥልጣኑ አከናወነ:: በመጨረሻም የተለያዩ መከራዎችን ተቀብሎ በመስቀል ላይ ተሰቀለ:: ከዚያም በሥጋዉ ሞቶ በሦስተኛዉ ቀን ተነሳ :: ወደሰማይ ከማረጉ በፊትም ወሳኝ የሆነዉን ትእዛዝ ከላይ የተገለጸዉን ሰጠ::

ለዚህም ነዉ እኛ በእርሱ የምናምን ምእመናን በቅድስት ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሰረት ወንድ በአርባ ቀኑ፣ ሴት በሰማኒያ ቀኗ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ለመወለድና እዉነተኛ ልጅነታችንን ለማረጋገጥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የምንጠመቀዉ:: ምክንያቱም ከእርሱ በመንፈስ ዳግም ካልተወለድን በስተቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማንገባ በግልጽ አስተምሯልና::

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነትን እንኳን እኛ ሥጋ ለባሽ ሰዎች ቀርቶ ቅዱሳን መላእክት እንኳ ሊገልጹትና ሊያዉቁት አይችልም:: ነገር ግን እኛም ሆን እነሱ በእምነት እናምናለን፤ እንቀበላለን:: ምስጢረ ሥላሴ የተባለበትም አንዱ ምክንያት የአንድነቱና የሦስተነቱ ምስጢር ከሕሊናችን በላይ ስለሆነና በግልጽ ማወቅና መመልከት ስለማንችል ነዉ:: ይሁንና የቀደሙት አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ አንድነቱንና ሦስትነቱን እኛ በምንረዳዉ መልክ በተለያየ ምሳሌ አቅርበዉልናል:: ያም ቢሆን ሙሉ ሆኖ ሊገልጽልን እንደማይችል ይታወቃል:: ምክንያቱም

በዐይናችን የምናየዉ ፍጥረት እግዚአብሔርን ሊገለጽ አይችልምና። አንዱን የቅዱሳን አባቶቻችን ምሳሌ ባቀርብላችሁ፡ ፀሐይ የራሷ ክበብ አላት እንዲሁም ከእርሷ የማይለይ ብርሃንና ሙቀት አላት። ሦስቱም በአንዴ እኩል የነበሩና የማይቀዳደሙ እንዲሁም የማይለያዩ ነገር ግን የራሳቸዉ መለያ ያላቸዉ ነዉ። ይኸዉም ክበብ፣ ሙቀት፣ ብርሃን ነዉ። በዚሁ መሰረት ክበቡ እንደ አብ፤ ሙቀቱ እንደ መንፈስ ቅዱስ፤ ብርሃኑ እንደ ወልድ(ኢየሱስ ክርስቶስ) ተመስሎ ቀርቧል። ይህም ለሕሊናችን እንዲገባን ተብሎ ነዉ እንጂ ምሳሌዉ ሙሉ ሊሆን አይችልም።

በብሉይ ዘመን እግዚአብሔር «አዶናይ፣ ያሕዌህ፣ አልፋና ያሜጋ፣ ኤልሻዳይ፣ የሠራዊት ጌታ፣ አምላክ ... ወዘተ» በመባል የሚታወቅና ሦስትነቱና አንድነቱ በግልጽ የማይታወቅ በአንድ አምላክነቱ ብቻ የሚታወቅና የሚመለክ ነበር። በሐዲስ ዘመን ነዉ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ከተገለጸ በኋላ አንድነቱንና ሦስትነቱን የገለጸዉ። እንዲሁም በመፍጠር፣ በሥልጣን፣ በክብር፣ በፈቃድ፣ በአገዛዝ፣ በህልዉና፣ ባጠቃላይ በመለኮታዊ ባሕርይ አንድ መሆናቸዉንና በዚህም ምክንያት አንድ አምላክ መሆኑን የገለጸዉ ። ታዲያ የአንድነቱንና ሦስትነቱን ምስጢር ልናዉቅና ልንረዳ የምንችለዉ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔርነቱ ብቻ ስናምንበትና ስናመልከዉ ነዉ እንጂ «አማላጅ፣ ነብይ ፣ ፍጡር፣ አንድ ኢየሱስ ብቻ» በሚለዉ ደረጃ የምናምነዉ ከሆነ ስለ እርሱ ሆነ ስለ አብና መንፈስ ቅዱስ አንዳች እዉነታ አናዉቅም፤ አይገለጽልንም። ለዚህም ነዉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ ሲያስተምር በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ10 ቁጥር22 ላይ እንዲሁም ማቴዎስ 11 ቁጥር 27 ላይ «ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰቶኛል፣ <u>ወልድንም ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር ያሚያዉቅ የለም፤</u> <u>አብንም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያዉቅ የለም አለ</u>።» በማለት ገላጫ እርሱ መሆኑን በገልጽ የተናገረዉ።

እዚህ ላይ ጌታችን በገልጽ እንደተናገዉ ስለ አብ ሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ መግለጽ የሚችለዉ እርሱ ወልድ የተባለዉ እንደሆነና እርሱ ካልገለጸልን በስተቀር ስለ አብ ሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ አንዳች ማወቅ  እንደማንችል ነዉ። ስለዚህ እርሱ በገለጸልን መሰረት አብ ሆነ መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር በመለኮት አንድ የሆኑ የማይበልጡት ወይንም የማያንሱት በመለኮት አንድ የሆኑ ናቸዉ ። የአብና የመንፈስ ቅዱስ ህልዉና እና አምላክነት የምንክድ ከሆነ እርሱን ወልድን ክደናልና እምነታችን የተሳሳተ የክህደት መሆኑን ይመሰክርብናል። በመሆኑም በመለኮት አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ ፈጣሪ ነዉ የምንላቸዉ እንጂ በስም፣ በአካል፣ በግብር ስለተለያዩ ሦስት አምላክ አንልም። የወልድ ፈቃድ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነዉ። የአብ ፈቃድ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነዉ። የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የአብና የወልድ ፈቃድ ነዉ። በፈቃድ ሆነ በመለኮት አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ አንድ እግዚአብሔር አንደ ፈጣሪ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እየተባለ የሚመለክ ጌታ ነዉ እኛ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የምናምነዉና የምናመልከዉ። ከኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነት አምልኮና እምነት ዉጭ የሆነ እምነት ሆነ አምልኮ የሞት ሕይወትና የክህደት እምነት እንደሆነ ነዉ የምንመሰክረዉ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ:** ከዚህ ጋር በተያያዘ ለድኅነታችን ወሳኝ ስለሆነዉ ቅዱስ ቁርባን ቢገልጹልን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:** የክርስቶስ ሥጋና ደም ልክ እንደ ጥምቀቱ ለሕያዉነት ሕይወታችንና ለሰማያዊ መንግሥት ወሳኝ የሆነ ትእዛዝ ነዉ:: በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 6 ከቁጥር 53እስከ59 እንደተገለጸዉ «ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸዉ እዉነት እዉነት እላችኋለሁ፣ የሰዉን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም:: ***ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለዉ፤*** እኔም በመጨረሻዉ ቀን አስነሳዋለሁ:: ***ሥጋዬ እዉነተኛ መብል ደሜም እዉነተኛ መጠጥ ነዉና::*** ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ:: ሕያዉ አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሳ ሕያዉ እንደምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሳ ሕያዉ ይሆናል:: ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነዉ አባቶቻችሁ መና በልተዉ እንደ ሞቱ አይደለም ይህን የሚበላ ለዘላለም ይኖራል::» በማለት ነዉ በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ ሆኖ ለመኖር የሚፈልግ ሰዉ አማናዊ የሆነዉን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መብላትና መጠጣት እንዳለበት በግልጽ ያስተማረዉ::

እንዲሁም ማንም ሰዉ በኃጢአት ቢወድቅና ከክርስቶስ ሥጋና ደም ቢለይ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሶ ዳግም የክርስቶስን ሥጋና ደም ካልበላና ካልጠጣ በስተቀር በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ ሕያዉ ሆኖ እንደማይኖር ነዉ የሚያስተምረን:: ስለዚህ ማንኛዉም አማኝ እንደ ክርስቶስ ሕያዉ ለመሆን ከፈለገና ምርጫዉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ካደረገ በምድራዊ ሕይወቱ ዘመኑ ሁሉ በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ ተወስኖ መኖር እንዳለበት ነዉ ቃሉ በግልጽ የሚያስረዳንና በኃጢአት የወደቀና ከቅዱስ ቁርባን የተለየ ሰዉ ደግሞ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሶ ቅዱስ ቁርባን መቀበል እንዳለበት የሚገልጽልን::

**ጠያቂዉ አገልጋይ:** እዚህ ላይ ሰዉ በዉኃ ሲጠመቅ እንዴት ዉኃዉ ሰዉ ከእግዚአብሔር እንዲወለድና ልጅነትን ያስገኝለታል? እንዲሁም ቁርባን እንዴት ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ተለዉጦ ሕይወት ይሆነናል? እንዴት ኃጢአታችንን ከእግዚአብሐር ባሕርይ መዝገብ ላይ ይደመስስልናል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:** እምነት፤ እኛ በሥጋዊ ዐይናችን እንደምናያቸዉ ምሳሌያዉ ፍጥረታት በማየት የምናረጋግጠዉ አይደለም:: እስከ አሁን ድረስ በተለያየ ሃይማኖት ዉስጥ የሚመላለሱ ሰዎች ነፍስ እንዳላቸዉ ቢያምኑም፤ የት ቦታ ላይ እንደሆነች ግን በእርግጠኝነት አያዉቁም:: አንዳንዶች በደም ዉስጥ ናት ይላሉ፤ አንዳንዶች የት ዉስጥ እንዳለች አይታወቅም፣ እዚህ ናት፣ እዚያ ናት ማለት አይቻለም ይላሉ:: አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ታላቋን ፍጥረት እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰችዉን ሕያዉ ነፍስ እንድናዉቅና እንድናስተዉል ፈቅዶ ይኸዉም ሕያዉ ነፍሳችን በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረች በረቂቅ አካል ደረጃ በግንባራችን ፊት ለፊት በአንጎላችን ዉስጥ እንደሆነችና «ሕሊና ወይንም አእምሮ» የምትባለዉ ራሷ መሆኑን ገለጸልን:: ከዚህ በተጨማሪ ከእርሷ በሚወጣ ኃይል ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጠፍራችን ድረስ ተዋሕዳ

ያለች፣ ለዚህ ለሚታየዉ ግዙፉ ሥጋችን(አካላችን) ሕይወትን የምትሰጠዉ እርሷ እንደሆነችና እርሷ ስትለየዉ በድን ቅርፊት እንደሚሆን እንድናስተዉልና እንድናዉቅ አስቻለን። ታዲያ ይህችን ሕያዉ ነፍስ በሥጋዊ ዐይናችን ማየት ባለመቻላችንና ሌሎችም አይተዉ ማረጋገጥ ስላልቻሉ ነፍስ የለንም ማለት ይቻላልን? ፈጽሞ አይቻልም።

እንደዚሁ ሁሉ በጥምቀት ከእግዚአብሔር እንደምንወለድና ቅዱስ ቁርባን በምንቀበልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት አድርገን አንድነት እንደምንፈጥር እንዲሁም ኃጢአታችን ከባሕርይዉ መዝገብ ላይ እንደሚጠፋልን፣ እንደሚደመሰስልን በሥጋዊ ዐይናችን ማየትና ማወቅ አንችልም። በእምነት ግን እንችላለን። ይኸዉም ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ባሕርይ የወጣች(የሰረጸች) ናት። በመሆኑም እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ የሆነች ከመኖር ወደ አለመኖር የማታልፍ ሕያዊት ናት። ይህ ባሕርይዋ የእግዚአብሔር ሕያዉ ፍጥረትና ልጅ አሰኝቷታል። ነገር ግን በአዳምና ሔዋን ኃጢአት (ዓመፃና ክህደት) ምክንያት ሕያዉ ፍጥረትነቷን ባታጣም ልጅነቷን ግን አታለች። ይህ ልጅነቷ የተመለሰዉ እርሱ ፈጣሪዋ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣት አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ባሕርይዉን ዝቅ አድርጎ ሰዉ ሆኖ በምድር በተገለጸበት ዘመን ነዉ።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸዉ የሰዉ ዘሮች ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ለመወለድና ወደ ቀደመዉ የልጅነት ክብር ለመመለስ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ወይንም በሥላሴ ስም ሊጠመቁ ግድ ነዉ። ይህ ጥምቀት የሚከናወነዉ ድግሞ በዉኃ ነዉ። በመሆኑም አንድ ሰዉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በዉኃ ሲጠመቅ ወደ ቀደመዉ ክብሩ አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ ወደነበረዉ የልጅነት ማዕረግ ይመለሳል። እስከ ምድራዊ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ልጅነቱን ከጠበቀ «የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ ለእግዚአብሔር ሕያዉ መንግሥት ይበቃል። እንደ ቅዱሳን መላእክት ተቆጥሮ እንደ እግዚአብሔር ፍጥረትነቱና ልጅነቱ ሕያዉ ሆኖ ይኖራል። ቅዱስ ቁርባንም ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንዲኖረንና እግዚአብሔር እንዲያድርብን የሚያደርገዉና በኃጢአት ስንወድቅም እዉነተኛ ንስሐ ገብተን ስለ ኃጢአታችን በምንጸጸትበት ቅዱስ ቁርባን በመንቀበልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የሚደመሰስልን፣ በቅዳሴ ጊዜ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ዉእቱ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በካህኑ ጸሎት አማካይነት ህብስቱና ወይኑ ፍጹም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል። የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ደግሞ መለኮት ወይንም እግዚአብሔር የተዋሐደዉ ስለሆነ በመንቀበልበት ወቅት መለኮት ወይንም እግዚአብሔር ያድርብናል ማለት ነዉ። እንዲሁም በኃጢአት ወድቀን በእዉነተኛ ንስሐና ጸጸት ቀኖናችንን ጨርሰን ቅዱስ ቁርባን በመንቀበልበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲዋሐደንና እንዲያድርብ ስለምናደርግ፤ እግዚአብሔር ደግሞ በባሕርይዉ ንጹህና ቅዱስ ስለሆነ የቀደመዉ ኃጢአታችን ሁሉ ከባሕርይዉ መዝገብ ላይ ይጠፋልናል፣ ይደመሰስልናል። እዉነተኛ ንስሐ ለገባንበት ኃጢአት ዳግም አንጠየቅበትም። እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ሕይወታችንን በንስሐ እየመረመርን በምንቀበል ጊዜ ሁሉ በተግባር፣ በንግግር፣ በሐሳብ የፈጸምናቸዉ ኃጢአቶች ከባሕርይዉ መዝገብ ላይ ስለሚደመሰስልን በፍርድ ቀን አንዳች የምንጠየቅበት ነገር የለም። እንዲሁም ነፍስ ከሥጋችን ስትለይ በቀጥታ እንደ መናፍስት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ወይንም በሥጋዊ ዐይናች የማይታይ አካል ለብሳ ወደ ገነት ነዉ የምትገባዉ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ:** እዚህ ላይ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን በተለያየ ኃጢአት ሕይወት ዉስጥ በዝሙት፣ በሴሰኝነት፣ በዘፋኝነትና በዳንኪራ፣ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ፣ በስርቆት፣ በጥልና በግድያ፣ በጥላቻና በበቀል፣ በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በዓመፃ ሕይወት ዉስጥ እያሉና እየተመላለሱ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉና የሚያቀብሉ ሰዎች፤ ቅዱስ ቁርባኑ ሕይወት ይሆናቸዋል ወይ? እንዲሁም አንዳንድ ምእመናን በተለያየ የኃጢአት ሕይወት ዉስጥ ተመላልሰዉ በዚያዉ የዓመፃ ሕይወታቸዉ እንደ ጸኑ ስለ ኃጢአታቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ሳይጸጸቱ በመጨረሻ ሊሞቱ ወይንም በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ በተለያየ በሽታ ሲያዙ «ለማንኛዉም ሥጋና ደሙን ይቀበሉ» ተብሎ ስለቆረቡ ብቻ ቅዱስ ቁርባኑ ሕይወት ሆኖ ለሰማያዊ መንግሥት ያበቃቸዋል ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ ሊታወቅ የሚገባዉ በዚህች ምድር ዉስጥ ማንም ንጹህና ቅዱስ አይደለም:: ምክንያቱም እልፋ አእላፋት (በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ስላሉና ሁል ጊዜ የሰዉ ልጆችን ስለሚፈታተኑ እንዲሁም ነፍሳችን የጎሰቆለ ባሕርይ በተላበሰዉ ሥጋችን ስለተገለጸች ከተግባር ኃጢአት ብንከለከል ከንግግር ኃጢአት አንከለከልም፤ እንዲሁም ከተግባርና ከንግግር ኃጢአት ብንከለከል ከሐሳብ ኃጢአት አንከለከልም፤ ከሦስቱ ኃጢአት ብንከለከል እንኳ ከርኩሳን መናፍስት ፈተና ልንለይና ፍጹም እንደ ቅዱሳን መላእክት ልንሆን አንችልም:: ይሁንና ሥጋችን ሆነ ሰይጣናት የሚያመጡብንን ፈተና በተሰጡን መሳሪያዎች በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ እንዲሁም በቃሉ ልናሸንፍና ራሳችንን በመግዛት እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰችዉ ነፍሳችን በሥጋችን ላይ የበላይነትን ተጎናጽፋ በተግባርም፣ በንግግርም፣ በሐሳብም ጭምር ከኃጢአት ልትከለከል ትችላለች:: ለዚህም ብቃት ሙሉ ፈቃድና ነጻነት አላት:: ነገር ግን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን የምንመላለስ ከሆነ እንኳን ከንግግርና ከሐሳብ ኃጢአት ልንከለከል ቀርቶ ከተግባር ኃጢአትም መለየት አንችልም::

ከላይ የተገለጹት የርኩሳን መናፍስት ፍሬ የሆኑት የኃጢአት ተግባራትና የሕሊና ዓመፆች ነፍሳችን እንኳን በተግባርና በንግግር እንድትፈጽም አይደለም በሐሳቧ እንድትቀበለዉ አልተፈቀደላትም:: ሰይጣናት እንኳ ቢናገሯትና ቢያሳስቧት ገና ከሐሳብ ደረጃ መቃወምና ወደ ተግባር ላለመለወጥ መወሰን ነዉ ያለባት እንጂ በተለያየ ኃጢአት ሕይወት እየተመላለሰች ቅዱስ ቁርባን በድፍረት ብትቀበል ፍዳ ነዉ የሚሆንባት እንጂ ሕይወት አይሆናትም:: በተለይ በአገልግሎት ዉስጥ ሆነዉ በማስመሰልና አገልግሎቱንም እንደ ገቢ ማግኛ ቆጥረዉ በድፍረት ቅዱስ ቁርባኑን እየተቀበሉ የሚያቀብሉ አስመሳይ አገልጋዮች ከማንም በላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያገኙና የእግዚአብሔር ቁጣ በተለያየ መንገድ የሚገለጽባቸዉ ነዉ:: አስመሳይ ምእመናንም እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ በምድር ሆነ በሲኦል እንደ አስመሳዮቹ አገልጋዮች መከራና ስቃይ ይቀበሉበታል እንጂ ለማስመሰል የሚቀበሉት ቅዱስ ቁርባን ሕይወት አይሆናቸዉም:: ሕይወት የሚሆናቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ በጸጸት ሲመለሱና በአገልግሎት ዉስጥ የተሰማሩትም ያሰናከሉትን ምእመን በግልጽ ይቅርታ ጠይቀዉ የዓመፃ ተግባራቸዉን በግልጽ አምነዉ በእዉነተኛ ጸጸትና ንስሐ ከተመለሱ ነዉ የቀደም ኃጢአታቸዉ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ ተደምስሶ ለሰማያዊ መንግሥት የሚበቁት እንጂ፤ እያስመሰሉ የሚያገለግሉ ከሆነ በእግዚአብሔር ላይ አላግጠዋልና የንስሐ ሕሊና ሳያገኙ እግዚአብሔርም

አላግጦባቸዉ ወደ እዉነተኛ መቀጫ ቦታ ሲኦል ይሄዳሉ እንጂ ለእግዚአብሔር መንግሥት አይበቁም።

ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ እዉነተኛ ንስሐ ምን እንደሆነ ነዉ። ሰዉ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ይበድላል፣ ይሳሳታል፣ ያጠፋል። ነገር ግን ኃጢአቱን ሆነ በደሉን ሕሊናዉ ይመሰክርበታልና ወይንም እግዚብሔር በሥጋዊ ጆሮ በማይሰማዉ ድምፅ ይወቅሰዋልና በዚያን ጊዜ ከሕሊናዉ ሊጸጸትና ኃጢአቱንም አምኖ ዳግም በዚያ ኃጢአት ላለመመላለስ ወስኖ እግዚአብሔርንም «ይቅር በለኝ» ብሎ ነፍሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆና አንድነትና ኅብረት እንዲኖራት አድርጎ ቅዱስ ቁርባኑን ሲቀበል ነዉ ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚደመሰስለትና ፍጹም ምሕረትን አግኝቶ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚበቃዉ እንጂ በብልጣብልጥነትና ምንም አማራጭ ስለሌለን «ለማንኛዉም» በሚል አስተሳሰብ የምንቀበለዉ ቅዱስ ቁርባን ሕይወት አይሆነንም፤ ኃጢአታችንንም ከሰማያዊ መዝገብ ላይ አያስፍቅልንም፤ አያስደመስስልንም።

እዚህ ላይ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራኒዮ አደባባይ ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ወቅት በግራና በቀኙ የተሰቀሉ የወንበዴዎቹን ሕይወትና በነጻ ሕሊናቸዉና ፈቃዳቸዉ የወሰኑትን ዉሳኔ መመልከት ያስፈልጋል። እነዚህ ሁለት ወንበዴዎች በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በነጻ ፈቃዳቸዉና ምርጫቸዉ የዉንብድና ሕይወት መርጠዉ ተመላልሰዋል። በመጨረሻም ስለ ዓመፃቸዉ በሥጋ እንዲሞቱ የመስቀል ፍርድ ተፈርዶባቸዋል። ፍርዳቸዉንም ተቀብለዉ በክርስቶስ ግራና ቀኝ ተሰቅለዋል። በግራ በኩል የተሰቀለዉ ወንበዴ በዚያች ወቅት የተለያዩ ተአምራቶችና ምልክቶች ሲፈጸሙ አይቷል፣ ሰምቷል፣ ይሁንና ወደ ልቡ(ወደ ሕሊናዉ) ተመልሶ ስለ ዓመፃዉና ስለ ኃጢአቱ መጸጸትና ከእግዚአብሔርም ምሕረትን ለመጠየቅ ፈቃደኛ አልሆነም። ይልቁኑ በክርስቶስ ላይ ይዘብትበትና ያላግጥበት ነበር። በተቃራኒዉ ደግሞ በቀኝ በኩል የተሰቀለዉ «ፈያታዊ ዘየማን» በመባል የሚታወቀዉ ወንበዴ የምድራዊ ሕይወቱ የፈጸመዉን የዓመፃና የኃጢአት ተግባሩን አምኖ፣ ፍርዱም እንደሚገባዉ ተቀብሎ፣ ነገር ግን በዚያች በመጨረሻ ሰዓት እዉነተኛ ጸጸት አድርጎና ንስሐ ገብቶ ነፍሱን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅና ምሕረት ሊጠይቅ ችሏል። ያ ብቻ አይደለም በዚያች ወቅት ሟች ፈራሽ በስባሽ አለማሆኑንና ትንሣኤ እንዳለዉ በማመን አምላኩን « ጌታ ሆይ በመንግሥት በመጣህ ጊዜ አስበኝ፤ በደሌን አምኛለሁ፤ ተጸጽቻለሁ፤ ያንተንም እዉነተኛት መስክሬያለሁ፤ አምኜብሃለሁ» በማለት በእዉነተኛ ንስሐና ጸጸት አምላኩን ይቅርታ ስለጠየቀ ምሕረትን አግኝቶ ለእግዚአብሔር ሕያዉ መንግሥት ሊበቃና የመጀመሪዉ ገነት ገቢ ሊሆን ችሏል። ይህም የሚያሳየን በእዉነተኛ ንስሐ የሚመለስ ሰዉ በየትኛዉም የእድሜ ዘመኑ ይቅርታን እንደሚያገኝና ኃጢአቱም ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ እንደሚደመሰስለት፣ በመጨረሻም ለእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚበቃ ነዉ።

ታዲያ ከማንኛዉም የአዳም ዘር የሚጠበቀዉ እዉነተኛ ንስሐና ጸጸት እንጂ አጉል ብልጣብልጥነትና የማስመሰል ሕይወት ወይንም «ለማንኛዉም» የሚል የጥርጥር ሕይወት አይደለም። በመሆኑም ሁላችንም ኃጢአተኞች መሆናችንን አምነን ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ

አድርገን ስለ ዓመፃችን በእዉነተኛ ንስሐ ተጸጽተን ወደ ቅዱስ ቁርባኑ መቅረብ ይኖርብናል እንጂ፤ ራሳችንን በማመጻደቅና እንዲሁም በማስመሰል ሕይወት አይደለም:: ያኔ ነዉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የፈጸምነዉ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚደመሰስልንና በፍርድ ቀንም የማያስጠይቀን የሚሆነዉ:: ከዚያ ዉጭ በአቋራጭ መንገድና በብልጣብልጥነት ሕይወት ኃጢአታችንን ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ሊናስደመስስና ራሳችንንም ለእግዚአብሔር መንግሥት ልናበቃ አንችልም::

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__: ሳንጸልይና ሳንጾም ነፍሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛትና ለሰማያዊ መንግሥቱ መብቃት አንችልም ወይ?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩላችሁ ይህች ምድር የሰይጣናት መኖሪያ ስለሆነች ሕይወታችን በነዚህ ርኩሳን መናፍስት ፈተና የተሞላች ናት:: ለዐይን ቅጽበት እንኳ ከሕሊናችን(ከነፍሳችን)ና ከአካላችን አይለዩም:: ስለዚህ የሚያመጡብንን ፈተና ለማሸነፍና ነፍሳችንም ኃይል እንድትጎናጸፍ ከእግዚብሔር የተሰጣት ትልቁ መከላከያ ጸሎት፣ ጾምና ስግደት ናቸዉ:: በምንጸልይበት ጊዜ ልክ አንድ በብረምጣድ ላይ የሚቆላ ባቄላ እሳት ከታች ሲነድበት እንደሚለበለብና እንደሚቃጠል ሁሉ ሰይጣናትም እንዲሁ ይለበለባሉ፣ ይቃጠላሉና ኃይላቸዉ ይደክማል፤ በተቃራኒ ደግሞ የእኛ ነፍስ ትበረታለች፤ ኃይልን ትጎናጸፋለች:: እንዲሁም በምንጾም ወቅት ልክ በበረትድስት ዉስጥ ሥጋ በእሳት ስንቀቅል ሥጋዉ እንደሚቀቀልና ሙክክ እንደሚል ሁሉ፤ በጾም ወቅትም ሰይጣናት እንደዚህ ይቀቀላሉ፤ ኃይላቸዉ ልምሾ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪ በምንሰግድበት ጊዜ ልክ በመዶሻ አንድን ነገር ስንፈልጥ ብትንትኑና ፍርክስክሱ እንደሚወጣ እንዲሁም በስለታም ሰይፍ አንድ ሥጋ ሲቆረጥ በቀላሉ እንደሚቆራረጥ ሁሉ፤ ስንሰግድ ሰይጣናት እንደዚሁ ብትንትናቸዉና ፍርክስክሳቸዉ ይወጣል:: ታዲያ የተገለጹበት አካል እንደኛ ግዙፍ አካል ያልሆነ ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) ስለሆነ የሚደርስባቸዉን መቃጠል፣ መቀቀል፣ መፈረካከስና መቆራረጥ ህልዉናቸዉን አያጠፋዉም:: ነገር ግን ኃይላቸዉን ልምሾ ያደርጋል፤ ስቃይና መከራ ያደርስባቸዋል:: እንደዛም ሆኖ ተስፋ ባለመቁረጥ ይኸዉም «አንድ ቀን አዳክመን በኃጢአት እንጥለዋለን፣ እናሰናክለዉለን፣ እናስፈርድበታለን፣ ባጠቃላይ ከእግዚአብሔር መንግሥት እንለየዋለን፣ በምድርም እናጎሳቁለዋለን» በማለት እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ይፈታተኑናል እንጂ ተስፋ ቆርጠዉ ከእኛ አይርቁም:: የመጨረሻ እልኸኞችና እስከ ሥጋ ሞታችን ቀን ድረስ «አንድ ቀን ድል እናደርጋቸዋለን፣ በኃጢአት እንጥላቸዋለን፣ እናስፈርድባቸዋልን» በማለት ተስፋ ሳይቆርጡ የሚፈታተኑንና በኃጢአት ከወደቅንላቸዉም የሚቀጠቅጡን፣ የሚያጎሳቁሉን፣ መከራና ፍዳ የሚያሳዩን የመጨረሻ ጨካኝና አረመኔ ፍጡሮች ናቸዉ::

ስለዚህ በነፍሳች ላይ እንዳይሰለጥኑና ኃይል እንዳያገኙ ሕይወታችንን በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በእግዚአብሔር ቃል ልንመራ ይገባል:: ያ ካልሆነ ግን ነፍሳችን ኃይሏ እየተዳከመ ስለሚሄድ ሰይጣናት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረዋት ፈቃዳቸዉን ሊያስፈጽሚትና እንዲሁም በምድራዊ ሕይወታችን ዘመን ሊያጎሳቁሉን፣ ሊቀጠቅጡን፣ በመጨረሻም ከነ ኃጢአታችን በዓመፃ ሕይወት

ዉስጥ እንዳለን ለሞት ሊዳርጉንና በነፍሳችን ደግሞ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ሊያበቁን ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በምድራዊ ሕይወታችን ዘመን እኛን ለመፈታተንና ለማጎሳቆል ወደ ኋላ የማይሉ አንዳች ርኅራኄና ተስፋ መቁረጥ  የሌለባቸዉ ስለሆነ፤ እኛም ሁል ጊዜ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በቃሉ ልንተጋ ይገባል እንጂ አሁን እንደሚታየዉ «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንደለቅ፣ እንዝፈን፣ እንዝናና፣ እንደ ፍላጎታችን እንሁን... ወዘተ» በሚል በአሕዛብ ወይንም በአረማዉያን ወይን «እግዚአብሔር የለም በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ በኢቮልሽን አማካይነት ነዉ ሰዉ የሆነዉ» እንደሚሉት ከሃዲያንና ዓማፅያን ሰዎች ሕይወት ከተመላለስን፤ ሕይወታችን የእብደትና የመከራ እንዲሁም የስቃይ ነዉ የሚሆነዉ እንጂ የረካችና ደስተኛ፣ ሰላም የሞላባት ነፍስ ሊኖረን አይችልም፡፡ ይልቁኑ የተቅበዘበዘች፣ ሰላም የሌላት፣ ባዶነት የሚሰማት ነፍስ ነዉ የሚኖረን፡፡

ከዚህ ጋር አያይዤ የምገልጸዉ ነገር ቢኖር ከላይ ከተገለጹት ጋር አብሮ የሚሄዱ የምጽዋት፣ የትምህርት፣ የምስጋና ተግባሮች አሉ፡፡ ምጽዋት እያንዳንዱ ሰዉ በአቅሙ ለሌላዉ አቅም ለሌለዉና እርዳታ ለሚያስፈልገዉ ወገኑ እርዳታና ድጋፍ የሚያደርግበት ሲሆን፤ እያንዳንዱ ሰዉ ከስግብግብነትና ከስስት ሕይወት ራሱን ለይቶ ወገኑን የመርዳት የዉዴታ ግዴታ ተግባሩ ነዉ፡፡ ከዚህ ጋርም ከጊዜዉ፣ ከሀብቱ፣ ከእዉቀቱ፣  ለእግዚአብሔር  አገልግሎት መስጠት የዉዴታ ግዴታ አለበት፡፡ ትምህርት በተመለከተ ቢያንስ እያንዳንዱ ሰዉ ማንን እንደሚያመልክና ራሱ ሆነ ፈጣሪዉ ማን እንደሆነ አዉቆ ከልማድ ሕይወት ተለይቶ አምላኩንም በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ መኖር ይጠበቅበታል፡፡ ምስጋናም በተመለከተ እያንዳንዱ ሰዉ እግዚአብሔር መፍራት ባለበት ሕይወት ዉስጥ ሆኖ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣዉን አምላክ እንዲሁም ፍቅሩን እስከ መስቀል ድረስ የገለጸለትን አምላክ ማመስገን ይጠበቅበታል፡፡

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: በአዳምና ሔዋን እዉነተኛ ንስሐ ጊዜ የታዩት ነፍሳት ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል እስከሚሆን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በወንድና በሴት ጾታ ግንኙነት አማካይነት ካለመኖር ወደ መኖር በመምጣት በምድር በሥጋ ይገለጻሉ፤ ከዚያም በሥጋ ይሞታሉ፡፡ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ የሚከሰተዉና የሚጠብቃትን ሕይወት ቢገልጹልን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ ከሥጋና ደም እዉቀት ዉጭ የሆነን ነገር መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር ሊገልጽ የሚችል ማንም የለም፡፡ በትምህርት የሚገኝ እዉቀትም ቢሆን ሙሉ አይደለም፡፡ ሰዉ በተረዳዉና በመሰለዉ መልክ ሊገልጽና ሊያስተምር ይችላል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ገለጻና ማስተማር ግን ፍጹም የሆነ የማይቀነስበትና የማይጨመርበት ነዉ፡፡ ስለዚህ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ይግለጽልን እያልኩ እንደሚከተለዉ የጥያቄዉን መልስ እሰጣለሁ፡፡

ነፍሳችን በባሕርያዋ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች፣ የማትሞት፣ ከሕያዉ እግዚአብሔር ባሕርይ ዉስጥ የተገኘች ሕያዉ የሆነች ፍጥረት ናት፡፡ ሊትገለጽ የምትችለዉና የምትገደበዉ ሕያዉ ባልሆነ ፍጥረት፤ ማለትም ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያልፍ በሚችል ቀድሞ ባልነበረ ወደፊትም

ላይኖር በሚችል ግዙፍ አካል(ምሳሌያዊ ፍጥረት) እና ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ነዉ። ነፍሳችን ከሕያዉ እግዚአብሔር ባሐርይ ሰርጻ(ወጣ) በዚህ ምድር በሴት ማኅፀን ዉስጥ በግዙፉ ሥጋ የምትገለጸዉ በወንድና በሴት ጾታዊ ግንኙነት አማካይነት ብቻ ነዉ። ጽንስ ተያዘ ማለት ነፍስ አማናዊ ረቂቅ ባሕርይዋ በምሳሌያዊዉ ፍጥረት (በሥጋ) ተገለጸች ወይንም ተገደበች ማለት ነዉ። ከዚያም እግዚአብሔር ባዘጋጀላት ሥርዓት በሥጋዋ የማኅፀን እድገቷን ጨርሳ በመወለድ በምድር ዉስጥ በግልጽ ትታያለች። ከዚያም በሥጋ ታድጋለች፣ አእምሮዋም እግዚብሔር በፈቀደላት መጠንና እርሷም በምትጥረዉ ጥረት እየተከፈተላትና ነገሮችን እያወቀች፣ እያስተዋለች ትሄዳለች። በመጨረሻም እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ በምድር ከተገለጸችበትና ከተገደበችበት ሥጋ ትለያለች። ያንን መለየት ደግሞ እኛ ሰዎች «ሞት» እንለዋለን።

ነፍሳችን በዚህ ሥጋ ከተገለጸች በኋላ በምድራዊ ሕይወት ዘመኗ በምትይዘዉ መልካምነት ሆነ መጥፎነት፣ ቀናነት ሆነ ጠማማነት፣ ደግነት ሆነ ክፋት፣ መታዘዝ ሆነ ዓመፀኛነት፣ ባጠቃላይ በነጻ ፈቃዷና ምርጫዋ በምድር ላይ የያዘችዉን ጠበይ እንደያዘች ምድራዊ ዘመኗን ስትፈጽምና ከሥጋዋ «ሞት» በተባለ መሳሪያ ስትለይ፣ በምድር የተገለጸችበት ሥጋ ወደ ተፈጠረበት መሬት ሲመለስ፣ እርሷ ግን እንደ መናፍስት ረቂቁን አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሳ ትገለጻለች፤ ትገደብበታለችም። ወዲያዉ በምድር ዉስጥ የምታስታዉሰዉም የማታስታዉሰዉም ሁሉ ይታወሳታል። ነፍስ ነገሮችን ማገናዘብና ክፉና ደግ መለየት ከቻለችበት ምድራዊ ዘመኗ ጀምሮ የፈጸመችዉ መልካም ሆነ መጥፎ፣ የጽድቅ ሆነ የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ ሐሳብ ጭምር፤ ልክ እኛ አንድ የምናዉቀዉን ጥያቄ በሕሊናችን አስታዉሰን እንደምንመልስ ሁሉ፤ መንፈስ ቅዱስም አንድ በአንድ በሕሊናዋ ያስታዉሳታል። ምድራዊ ሕይወቷን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገችና ስለ ኃጢአቷ የተጸጸተች እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐና በእዉነተኛ ሕይወት ሆና ቅዱስ ቁርባን የተቀበለች ነፍስ፤ ኃጢአቷ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ ስለሚደመሰስ መንፈስ ቅዱስ አንዳች አያስታዉሳትም። ነገር ግን ምድራዊ ሕይወቷ ከእግዚአብሔር ጋር ያላደረገች፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልተመላለሰች፣ ስለ ኃጢአቷም ያልተጸጸተችና በእዉነተኛ ንስሐና ሕይወት ወደ ሥጋና ደሙ ያልቀረበች ነፍስ፤ ኃጢአቷን መንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በሕሊናዋ ያስታዉሳቷል። በዚያም ምክንያት ትጨነቃለች፤ «የመጨረሻዉ ፍርድ ምን ይሆን?» እያለች ትሰጋለች፤ «ምነዉ በዚያች ለዐይን ቅጽበት ለማትሞላ ምድራዊ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተመላልሼ በሕጉና በሥርዓቱ ኖሬ ቢሆን!» እያለች የማይጠቅም ጸጸት ታደርጋለች፤ ትብገነገናለች። ከራሷም አልፎ በምድር ላሉ ወገኖቿ «ምናለ ይህን የመከራና የስቃይ ሕይወት ቢነግሯቸዉ» ትላለች። ባጠቃላይ እንደ ምድራዊ ዓመፃ ደረጃ ትሰቃያለች፤ ፍዳዋን ትቀበላለች። ከዚህ በተጨማሪ በሕዝብ ሆነ በምእመናን አገልግሎትና ጠባቂነት በተለያየ ወንበር ላይ ኖራ መልካም ፍሬ ሳታፈራ በሥጋ ሞት ተጠርታ ከሆነ ደግሞ፤ ከግሏ ኃጢአት በተጨማሪ በአግባቡ ላልጠበቀቻቸዉና ላላገለገለቻቸዉ ሕዝቦችና ምእመናን ለእያንዳንዱ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬ ትጠየቅባቸዋለች። በዚህም መከራዋና ስቃያ እጅግ የከፋና ልትቋቋመዉ የማትችል «ምነዉ ባልተፈጠርኩ፤ በወንበር ላይ ባልተቀመጥኩ፤» የምትልበት ደረጃ ትደርሳለች።

በዚህ ሕይወት በድቅድቅ ጨለማ በሲኦል ዉስጥ ትቆይና በዓለም ፍጻሜ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከእልፍ አእላፋት መላእክትና ከቅዱሳን ነፍሳት ጋር ለመጨረሻ ፍርድ ወደማረፊያ ቦታ ሲመጣ ከሲኦል ትወጣና የመጨረሻ ፍርድ የሆነዉን «እናንተ ዓመፀኞች ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀ ገሃነመ እሳት ከግብር አባታችሁ ጋር ግቡ »ብሎ ይወስንባታል፡፡ ዓመፀኞቹ ነፍሳትም በዚያም በተገለጹበት ረቂቅ አካል፤ በማይጠፋዉ በረቂቁ እሳትና በረቂቃኑ በማይሞቱት ትሎች ዉስጥ እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ እንደ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ የመጨረሻ ፍዳቸዉን ይቀበላሉ፤ ሲቀጡም ይኖራሉ፡፡

አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉና ስለ ኃጢአታቸዉም እዉነተኛ ንስሐ የገቡ ሰዎች ደግሞ ልክ ነፍሳቸዉ ከሥጋቸዉ እንደተለየች በቅዱሳን መላእክት ታጅባ ቀድሞ አዳምና ሔዋን በገነት ተገልጠዉበት የነበረዉን ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሳ ወደ ገነት ትገባለች፡፡ በዚያም ከጻድቃን ጋር በመሆን አምላኳን በእዉነትና በመንፈስ እያመለከች እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በቅድስናና በደስታ በገነት አኗኗር ትኖራለች፡፡ በዓለም ፍጻሜ ደግሞ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጨረሻ ፍርድ ከእልፍ አእላፈት ቅዱሳን መላእክት ጋር ወደ ማረፊያ ቦታ ሲመጣ የመጨረሻዉን ፍርድ « እናንተ የሥላሴን ፈቃድ ፈጽማችሁ የተገኛችሁ ብሩካን! ዓለም ሳትፈጠር በፊት ወደተዘጋጀላችሁ፤ ርኩሳን የሆኑት መናፍስት ወዳቃለሉት ሰማያዊ መንግሥቴ ግቡ፤ እንደ ቅዱሳን መናፍስት(መላእክት) ሆናችሁ ኑሩ» ብሎ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በመሰላቸዉ መንገድ ተመላልሰዉ የኖሩና ኃጢአት ሲፈጽሙም የሕሊና ጸጸት ያደረጉ፤ ቅንነትና መልካምነት የተገኘባቸዉ፣ ነገር ግን በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ያልተመላለሱ ሰዎች ደግሞ፤ ነፍስ ከሥጋቸዉ እንደተለየች ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሰዉ ወደ ማረፊያ ቦታ ይገባሉ፡፡ በዚያም በሚያሳዩት የእዉነትና የመንፈስ አምልኮ ብቃት ለሰማያዊ መንግሥት የሚያበቃ ሆኖ ከተገኘ በፍርድ ቀን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማረፊያ ቦታ ሲገለጽ የመጨረሻ ፍርድ አግኝተዉ በገነት ከነበሩት ጋር አብረዉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ፡፡ ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ሕይወት ያልያዙት ደግሞ እንደ ዓመፃ ደረጃቸዉ ከሲኦል ዉስጥ ከነበሩት ርኩሳን ነፍሳት(ሰዎች) ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላሉ፡፡

በምድራዊ ዘመናቸዉ የእምነትና የምግባር ባጠቃላይ የጽድቅ ሆነ የዓመፃ ደረጃቸዉ ያልታዩ ሕፃናትና በሥጋቸዉ የአእምሮ እመምተኛ የሆኑና በምድራዊ ዘመናቸዉ የሚሰሩትንና የሚያደርጉትን የማያዉቁ ሰዎች ደግሞ፤ ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይ በቀጥታ ረቂቅ አካል ተላብሰዉ ወደ ማረፊያ ቦታ ነዉ የሚገቡት፡፡ ነፍሳቸዉ እንደማንኛዉ ሰዉ ሕያዉ ነፍስ ናትና በማረፊያ ቦታ በሚያሳዩት የእዉነትና የመንፈስ አምልኮ ብቃት በፍርድ ቀን ወደ መንግሥተ ሰማያት ሆነ ወደ ገሃነመ እሳት የመግባት እድል የሚያጋጥማቸዉ ነዉ፡፡ በነጻ ሕሊናቸዉ አምላካቸዉን ፈልገዉ በእዉነትና በመንፈስ ካመለኩት በፍርድ ቀን የመጨረሻ ፍርድ አግኝተዉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ ሲሆን፤ በተቃራኒዉ ደግሞ ልክ እኛ በምድራዊ ዘመናችን በራሳችን ሥጋና ደም ስሜት ተመርተን እንደ

አሕዛብ መደዴ ኑሮ እንደምንኖረዉ እነሱም አምላካቸዉን በሕሊናቸዉ ፈልገዉ እዉነትኛ አምልኮ መፈጸም ካልቻሉ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላሉ።

በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ እንደ ጻድቁ ሄኖክ፣ ነቢዩ ኤልያስ፣ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ፣ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነፍሳቸዉን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሱ ሰዎች ከተገኙ ደግሞ፤ ሥጋዊ ሞት ደርሶባቸዉ ሆነ ሳይደርስባቸዉ ነፍስ ከሥጋቸዉ እንደተለየች በቀጥታ እግዚአብሔር በአምላካዊ ሥልጣኑ የፍርድ ቀንን ሳይጠብቅ የቅዱሳን መላእክት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) እንዲለብሱ አደርጎ ወደ ሰማያት ዉስጥ ያስገባቸዋል። በፍርድ ቀንም አምላካቸዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመሆን አጅበዉ በማረፊያ ቦታ በታላቅ ክብር ይገኛሉ።

የሰዉ ዘሮች በምድር፣ በገነት፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሲኦል፣ በሰማያት ዉስጥ ያሉት ነፍሳት ቁጥር፤ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን ነፍሳት ቁጥር እኩል በሚሆንበት ዘመን በዚህች ምድር ዉስጥ የሚኖሩ ሰዎች አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለሱ ሰዎች በምሕረት ሞት ነፍስ ከሥጋቸዉ ተለይታ ወደ ማረፊያ ቦታ በመሄድ በረቂቅ አካል የመጨረሻዉን የእግዚአብሔርን ፍርድ አግኝተዉ በገነት ከነበሩት ጻድቃን ነፍሳት ጋር በመሆን ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ። በተቃራኒ ደግሞ በዚያ ዘመን በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሱ ሰዎች፤ በመቅሰፍት ሞት ነፍስ ከሥጋቸዉ ትለይና ወደ ማረፍያ ቦታ በረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) እንድትገለጽ ተደርጋ በምድር ከሚኖሩት ርኩሳን መናፈስት ጋር የመጨረሻዉን ፍርድ ተቀብለዉ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ተጥለዉ ፍዳቸዉን አብረዉ ይቀበላሉ።» **በማለት እዉነተኛና ፍትሐዊ ፍርድ የሚሰጠዉ፣ ፍቅሩና ምሕረቱ ደግሞ የትየለሌ የሆነዉ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ክፍል ሦስት

### ምዕራፍ አንድ

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ ማንም በራሱ ስልጣን መስራት ሆነ መናገር እንዲሁም ማሰብ እንደማይችል የተገለጸ ነገር አለ፡፡ ታዲያ በራሳችን ነጻ ፈቃድ ማምለክ ሆነ ከኃጢአት መከልከል ካልቻልን ለምን እንኮነናለን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ነጻ ፈቃድና ነጻ ምርጫ ሲሰጠን የራሳችን ነጻ ፈቃድ ሆነ ሥልጣን የተወሰነ ገደብ አለበት፡፡ ለምሳሌ ማንም በአየር ላይ ለመንሳፈፍ ቢፈልግ እንዳይንሳፈፍ አፈጣጠሩ ይገድበዋል፡፡ ነገር ግን በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ በፈጠረዉ ሌላ መሳሪያ አማካይነት ሊንሳፈፍ ይችላል፡፡ ማንም የሰዉን ሐሳብ ለመስማት ቢፈልግ የተለየ ጸጋ ከእግዚአብሔር ካልተሰጠዉ በስተቀር በአፈጣጠሩ እንዳይሰማ ተደርጎ ተገድቧል፡፡ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ በሚፈጥረዉ መሳሪያም እንዲሰማ እዉቀትና ጥበብ እስከ አሁን ድረስ አልተሰጠዉም፡፡ የሚሰራዉን ሆነ የሚናገረዉን እንዲሁም የሚያሰበዉን ሰይጣናት እንዳይመለከቱት፣ እንዳይሰሙት፣ እንዳያዉቁት፣ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዳያዉቀዉና እንዳይሰማዉ ማድረግ እንዳይችል ተደርጎ ነዉ በዚህ ሥጋዉ በምድር እንዲገለጽ የተደረገዉ፡፡ በዚህም ምክንያት በሰዉ ዘንድ ምስጢር ብሎ የያዘዉና የጠበቀዉ ነገር እንኳን በእግዚአብሔርና እርሱ በፈቀደላቸዉ ቅዱሳን ዘንድ ቀርቶ በተፈቀደላቸዉ ሰይጣናት ዘንድ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ካልፈቀደና ካላዘዘ በስተቀር ቅዱሳን ሆኑ ሰይጣናት የማንንም የዉስጥ ሐሳብ ሆነ ምስጢር ማዉጣት አይችሉም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰዉ ረቂቁን እግዚአብሔር ሆነ በምሳሌያዊ ባሕርይ(በረቂቅ አካል) የተገለጹትን ሰይጣናትን እንዳይመለከት ተደርጎ ስለተፈጠረ፤ እግዚአብሔርን ሆነ ሰይጣናትን በዚህ ሥጋ እያለ እንደ እዉነተኛ ባሕርያቸዉ (ረቂቅነታቸዉ) ሊመለከት አይችልም፡፡ ነገር ግን ከተፈቀደለት እግዚአብሔር በሚፈቅደዉ መልክና ሁኔታ ሊያዉቅ ይችላል፡፡ እንደዚህ የመሳሰሉ ብዙ ገደብ አለበት፡፡ ነጻ ፈቃድና ምርጫ የተሰጠዉ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍሱ ነገሮችን በሚገባ እንድታመዛዝንና እዉነትን ፈልጋ በእዉነት እንድትኖር፣ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣትን ፈጣሪ በእዉነትና በመንፈስ እንድታመልክ ነዉ፡፡ ከዚህ ፈቃድ በተቃራኒ በርኩስ መንፈስ ተመርታ ለክፋት፣ ለተንኮል፣ ለምቀኝነት፣ ለትዕቢት፣ ለዓመፃ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት፣ ባጠቃላይ ለኃጢአት ሕይወት ከተሰለፈች ደግሞ የተፈቀደላትን ሕይወት አቃላና በሕሊናዋ የሚናገራትን የእግዚአብሔርን ድምፅ «አልሰማ» በማለት ለዓመፃ የተሰለፈች ስለሆነ፤ እንደ ምርጫዋ ዋጋ ትከፍልበታለች፡፡ በተቃራኒዉ ለመልካም ሕይወት ራሷን ካዘጋጀች ደግሞ እንደ ነጻ ምርጫዋ ዋጋ ትቀበላለች፡፡

ከዚህ ዉጪ በዚህች ምድር ዉስጥ የሞሉት ርኩሳን መናፍስት ከሕፃን እስከ አዋቂ እንዲሁም ከጻድቅ እስከ ኃጢአተኛዉ ሰዉ ድረስ እንደ እያንዳንዱ ሰዉ የነፍሳቸዉ ብቃት ደረጃ ማለትም እንደ እድሜያቸዉና እዉቀታቸዉ ደረጃ ለዐይን ጥቅሻ ያህል እንኳ ከሕሊናቸዉና ከአካላቸዉ ሳይለዩ ፈተና ያመጣሉ፡፡ ለዚህም ነዉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በምድር በተመላለሰበት

ወቅት «<u>ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ</u>» በማለት ለእያንዳንዱ ሰዉ ቃሉን ያስተላለፈዉ:: ምክንያቱም ካልጸለይንና ካልጾምን የዲያብሎስን ፈተና ማለፍ ስለማንችልና በኃጢአት ስለምንወድቅ ነዉ:: እንዲሁም ራሳችንን በጽድቅ ስራችን የምናመጻድቅና የምናስታብይ ከሆነም ራሳችንን በፈቃደኝነት ለዲይብሎስ ፈተና የሰጠን ስለሆነ በተለያየ መንገድ እንወድቃለን፤ እንዋረዳለን:: ለዚህም ነዉ ማንም ሰዉ በራሱ ታብዮና ተመጻድቆ የሚመላለስ ከሆነ በራሱ ሥልጣን ኃጢአትን ላለማሰብ፣ ላለመናገር፣ በተግባርም ላለመፈጸም የማይችለዉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በትዕቢተኛና ራሱን በሚያመጻድቅ ሰዉ ላይ ስለማያድርና ኃይል የሚሆነዉን ጸጋ ስለማያድል፤ ትዕቢተኛና ራሱን የሚያመጻድቅ ሰዉ በተለያየ መልክ በኃጢአት ይወድቃል፤ አቅመ ቢስ ተራ መሆኑን ይረዳል:: ነገር ግን ከዉድቀቱ ተምሮ ራሱን ሳያስታብይና ሳያመጻድቅ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከኖረ ደግሞ እግዚአብሔር በቸርነቱ ስለሚጠብቀዉ ከኃጢአት ተግባር ሆነ ንግግር እንዲሁም ሐሳብ ይከለከላል ማለት ነዉ::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ከዚህ ጋር የተያየዘ አንድ ጥያቄ አለኝ:: ይኸዉም ሰዎች አንዳንድ ሱሶች እንደሚጎዷቸዉና ክብራቸዉንም እንደሚቀንስ እያወቁ ለምን በተለያየ ሱሶችና አደንዛዥ ዕፆች ይጠመዳሉ:

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በተለያየ መልኩ እንደተገለጸዉ ይህች ምድር የእኛ እዉነተኛ መኖሪያ ሳትሆን በአዳምና ሔዋን የገነት ዓመፃ ምክንያት የገባንባትና እንዲሁም ጠርተን፣ ነጥረን፣ ነተን፣ ወደ እዉነተኛ መኖሪያችን ቦታ ገነትና መንግሥተ ሰማያት ዉስጥ የምንሸጋግርባት ድልድይ ናት:: ከእኛም የሚጠበቀዉ ከድልድዩ እንዳንወድቅና ገደል ዉስጥ ግብተን እንዳንከሰከስ በትክክለኛዉ መስመር መሄድ ብቻ ነዉ:: ከድልድዩ ሊጥሉንና ከእዉነተኛ መንገድ ለይተዉ ከዚህች ምድር ወደባሱት ቦታዎች ወደ ሲኦልና ገሃነመ እሳት ዉስጥ ለማስገባት ሌት ተቀን የሚጥሩ እልፍ አእላፋት (በብዙ ቢሊዮኖች) የሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስት በዚህች ምድር ዉስጥ አሉ:: ዋናዉ ስራቸዉም ክፉዎችና ምቀኞች ስለሆኑ እኛን በተለያየ ኃጢአትና ሱሶች በመጣል የእነሱ ባሪያ እንድንሆንና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወተን በተለያየ ዓመፃ ሕይወት ዉስጥ እንድንመላለስ ነዉ::

እኛን ባሪያቸዉ ከሚያደርጉን አንዱ በተለያየ ሱስ እንድንጠመድና ነፍሳችንን (ሕሊናችንን) በማስጨነቅና በመፈታተን ያንን ምሳቸዉን(ግብራቸዉን) እንድናቀርብላቸዉ በማድረግ የእነሱ ተገዥ ያደርጉናል:: በሥጋችንም በነፍሳችንም ያጎሳቁሉናል:: በመሆኑም እያንዳንዳችን ርኩሳን መናፍስት የተለያየ ፈተናና ማስጨነቅ በሕሊናችን እንደሚያመጡ አዉቀን ስሜታችንን መቆጣጠርና ራሳችንን ልንገዛ ይገባል:: ስሜታችንን ልንቆጣጠርና ራሳችንን ልንገዛ የምንችለዉ ደግሞ እነዚህ ሌት ተቀን ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ በሰዉ ሕሊናና አካል ዉስጥ እየገቡ የሚፈታተኑንን ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናትን)፤ በጸሎት፣ በጾም፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ በእዉነተኛ ሕይወት ስናዳክማቸዉና ከእግዚአብሔር ጸጋ ስናገኝ ብቻ ነዉ እንጂ እንደ አሕዛብ(አረማዉያን) መደዴ ኑሮ የምንኖርና «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንጨፍር፣ እንዝፈን፣ እንደለቅ፣ እንዝናና፣...ወዘተ) እያልን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን ከተመላለስን፤ የሚያመጡብንን ፈተናና ማስጨነቅ መቋቋም ስለሚያቅተን ወዲያዉ ነዉ

ያስለመድናቸዉን ምስ(ግብር) የሆነዉን ሲጃራ ሆነ ጫት፣ ወይንም ሺሻና አደንዛዥ ዕፅ ወይንም አስካሪ መጠጥና ሌሎች ለእነሱ ግብር የሆኑትን በተለያየ መልኩ የምናቀርበዉ::

ጠያቂዉ አገልጋይ: ነፍሳችን የተገለጸችበት ሥጋ መልክና ደም ግባት የነፍሳችንን ደረጃ ሊያሳይና የታላቅነታችንና የታናሽነታችን እንዲሁም የብቃትና የደካማነታችን መለያ ሊሆን ይችላል ወይ?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ: በተለያየ ቦታ ላይ ስለነፍሳችን በሚገባ ተገልጿል:: ይህች ነፍስ ማንም ፍጡር ሊፈጥራት ሆነ ካለመኖር ወደ መኖር ሊያመጣት አይችልም:: ከእግዚአብሔር ባሕርይ የምትገኝና በአካል፣ በመልክ፣ በጾታ አንድ አይነት ናት:: ሰዉ ሆና በምድር ስትወለድም በአዳምና ሔዋን ንስሐ ጊዜ በታየችበት የእምነት ብቃት ደረጃ ነዉ የምትወለደዉ:: ለእግዚአብሔር መንግሥት ሆነ ለምድራዊ ሕይወቷ በታየችበት ብቃት ደረጃ ከመወለድ ዉጭ በምድራዊ ሕይወት ዘመኗ በምታሳየዉ እምነትና ምግባር ነዉ በምድርም በሰማይም ዋጋ የምትቀበለዉ:: በዓመፃ ሕይወትም ከተመላለሰች ዋጋ የምትከፍለዉ:: እያንዳንዱ ወላጅ ለወላጅነት የሚሰጡት ነፍሳት ወይንም ሊወልዳቸዉ የሚችለዉ በምድራዊ ሕይወቱ ዘመን በሚያሳየዉ የሕይወት ብቃት ነዉ:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላስ ሰዉ እንደሚያሳየዉ የሕይወት ብቃት የበቁ(አእምሮ ጽኑአን) ወይንም ምርጥ ነፍሳት(አእምሮ አዋቂዎች) የሆኑ ሕፃናትን ሊወልድ ይችላል:: በተቃራኒ ደግሞ እግዚአብሔር ደስ በማይሰኝበት ሕይወት የሚመላሱ አእምሮ ሕፃናትን ወይንም አእምሮ ቀላሎችን፣ ከባሰም ትዕቢትን፣ ክፋትን፣ ዓመፃን ሊወልዱ ይችላሉ:: ስለዚህ እያንዳንዱ ሰዉ አእምሮ ጸኑአንና አእምሮ አዋቂዎችን ለመዉለድ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና በመልካም ሕይወት ሊመላለስ ይገባዋል::

**ወደ ጥያቄዉ መልስ ስገባ:** ይህ በሥጋዊ ዐይናችን የምንመለከተዉ መልካችን ሆነ ደም ግባታችች የነፍሳችን ማንነት ሆነ ታላቅነት፣ ታናሽት፣ ብቃት፣ ደካማናት የማይገልጽ ነዉ:: ከወላጅ፣ ከዘር፣ ከነገድ ሊወረስ የሚችል፤ በተለያየ መልክ ማለትም ጥቁር፣ነጭ፣ ቀይ፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ፣ መልከ ቀና፣ መልከ ጥፉ፣ ሰልካካ፣ ጎራዳ፣ ወፍራም፣ ቀጭን ፣ ረጅም፣ አጭር፣ አካለ ሙሉ፣ አካለ ጎዶሎ፣... ወዘተ ሆኖ ሊገለጽ ይችላል:: መልከ መልካም ሆኖ እግዚአብሔር የሚወደዉን ስራ የሚሰራ መልአክ የሚመስል ሰዉ እንዳለ ሁሉ፤ መልከ መልካም ሆነ እግዚአብሔር የማይወደዉን ስራ የሚሰራ ጨለማ ሰይጣን የሚመስል ሰዉ አለ:: እንዲሁም መልከመልካም ሳይሆን እግዚብሔር የሚወደዉን ስራ የሚሰራ መልአክ የሚመስል ሰዉ እንዳለ ሁሉ፤ መልከ መልካም ሳይሆን እግዚአብሔር የማይወደዉን ስራ የሚሰራ ጨለማ ሰይጣን የሚመስል አለ:: ይህም የሚያሳየን የተገለጽንበት መልክና ደም ግባት እዉነተኛና ዉስጣዊ ማንነታችንን የማይገልጽ ነዉ:: መልካም ፍሬ ልናፈራ የምንችለዉ በዉስጣዊ እዉነተኛ ማንነታችን እንጂ በዉጪ በሚታየዉ ማንነታችን አይደለም:: እንዲሁም መራራ ፍሬ ልናፈራ የምንችለዉ በዉስጣዊ ማንነታችን ነዉ እንጂ በዉጫዊ ማንነታችን አይደለም:: ባጠቃላይ ማንም በመልኩ የበላይ ወይን የበታች፣ ወይንም ታላቅ ወይንም ታናሽ አይደለም:: እያንዳንዱ በሚያሳየዉ እምነትና ምግባር ነዉ ታላቅ ሆነ ታናሽ የሚሆነዉ:: እንደ

እግዚአብሔር ፈቃድ በቅንነት፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛነት የሚመላለስ ሰዉ ምንም ይሁን ምን እርሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብርና ሞገስ ያለዉ ታላቅ ሰዉ ነዉ። በተቃራኒዉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይመላሰስ በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት፣ በዓመፃ ሕይወት የሚመላለስ ምንም ይሁን ምን እርሱ ታናሽና በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀና የተጠላ ነዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች ማንም ይሁን ማን በራሱ ሥልጣን ምንም ሊያደርጋቸዉና ሊጎዳቸዉ እንደማይችል ተገልጿል። ታዲያ ነቢያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ለምን የተለያየ መከራና ስቃይ ሊደርስባቸዉና ግፍ ሊፈጸምባቸዉ ቻለ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን ወደ እግዚአብሔር የምንጠራበት መንገድ የተለያየ ነዉ። እንደ ማንኛዉም ሰዉ በእርግና(እርጅና) ሆነ በሕመም ነፍስ ከሥጋችን ተለይታ ወደ ተዘጋጀላት ቦታ ልትሄድ ትችላለች። እግዚአብሔር ከፈቀደላት ደግሞ እንደ ጻድቁ ሄኖክ፣ እንደ ነቢዩ ኤልያስ፣ እንደ ሐዋርያዉ ቅዱስ ዮሐንስ የሥጋ ሞትን ሳትመለከት በምሕረት ሞት ወደተዘጋጀላት ቦታ ልትሄድ ትችላለች። በሌላ መልኩ ደግሞ ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑና እንደነሱ በቆራጥነትና በጽናት ሕይወት እንዲኖሩ፣ እንዲሁም የሚደርስባቸዉን የተለያየ መከራና ስቃይ በመፍራት ስለ እዉነት ከመመስከርና በእዉነት ከመኖር ወደ ኋላ እንዳይሉ፣ ከዚህ በተጨማሪ ለሚከፍሉት መስዋዕትነት ታላቅ የድልና የክብር አክሊል እንደሚጠብቃቸዉ ትዉልዱ እንዲያዉቅ ተብሎ በተለያየ መከራና ስቃይ በሰማዕትነት አምላካቸዉን አክብረዉ ወደ ተዘጋጀላቸዉ ልዩ መኖሪያ ቦታ የሚሄዱ አሉ። ይህም የሚያሳየን በእያንዳንዱ ጥሪ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ነዉ በዚያ መልኩ እንዲጠሩ ያደረገዉ እንጂ በተለያየ መከራና ስቃይ በሰማዕትነት የተጠሩ ሰዎች ያ መከራ እንዳይደርስባቸዉ እግዚአብሔር ማድረግ ይችል ነበር። ይኸዉም እነዚያ ዓመፃኛና ግፍ ፈጻሚዎች ከመጀመሪያዉ የእርሱን አገልጋዮችና መልእክተኞች ለመጉዳት እንዳያስቡ ሊያደርግ ይችላል። ቢያስቡ እንኳ በተለያየ መንገድ ሐሳባቸዉ እንዳይሳካ ሊያደርግ ይችላል። ሐሳባቸዉ ተሳክቶላቸዉ ጥቃቱን ለመፈጸም ቢሄዱ እንኳ ኃይላቸዉን ልምሾ አድርጎ እነሱን በተለያየ መቅሰፍት ሊያጠፋቸዉ ይችላል። ጥቃቱ ተሳክቶላቸዉ ቢፈጽሙ እንኳ እንደነ አናንያና፣ እንደ ነቢዩ ዳንኤል፣ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንዳች ጉዳት እንዳይደርስባቸዉ ሊያደርግ ይችላል። በዚህም ምክንያት ነዉ እርሱ እግዚአብሔር ሳይፈቅድ በአገልጋዮቹና በመልእክተኞቹ ላይ ማንም ሰዉ በራሱ ሥልጣን ጉዳትና ጥቃት እንዲሁም ግፍ ሊፈጽም የማይችለዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከዚህ ጋር በተያያዘ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በማሳሰቢያ በገጽ <u>8</u> ላይ «እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰዉ በሚሊዮኖች አይደለም በቢሊዮን የሚቆጠሩትን በእግዚአብሔር ኃይል ድል ሊያደርጋቸዉ ይችላል። ምክንያቱም ሁሉን የሚያደርገዉ እግዚአብሔር ነዉና፤ ለእግዚአብሔር ደግሞ ሁሉ ቀላልና ተራ ነገር ነዉ።» ይላል። እንዴት አንድ ሰዉ በሚሊዮኖች ሆነ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩትን ድል ሊያደርግ ይችላል?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: በመጀመሪያ አንደ ነገር ማወቅ ይኖርብናል። ይኸዉም በዐይን የሚታየዉም የማይታየዉም ከግዙፉ እስከ ረቂቁ ነገር ከእግዚአብሔር በወጣ ኃይል የተዋቀረና ይህም ኃይል በእርሱ ዕይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ እርሱ እግዚአብሔር ሳያዉቀዉና ሳይፈቅደዉ በዚህ ዓለም ሆነ በሌላዉ ዓለም አንዳች የሚሆን ነገር የለም። ሁሉ በእርሱ ዕይታና ቁጥጥር ዉስጥ ነዉ። ስለዚህ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በአንድ ላይ ተሰልፎ ከቁጥር የማይገቡት የእግዚአብሔር አገልጋዮቹንና መልእክተኞቹን ለማጥቃትና ለመጉዳት ቢነሱ ጠባቸዉ ከእግዚአብሔር ጋር ነዉና፤ የሚዋጋቸዉና ድል የሚያደርጋቸዉ እግዚአብሔር ነዉ እንጂ እነዚያ አገልጋዮችና መልእክተኞች አይደሉም። እግዚአብሔር ደግሞ ከፈለገ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ አእላፋት(በሚሊዮን) የሚቆጠሩትን አይደለም በትእልፊት (በቢሊዮን) የሚቆጠሩትን በአንዴ ሊያረግፋቸዉና ሊጠርጋቸዉ፣ እንደ አቧራ ሊያበናቸዉ፣ እንደ እንፋሎት ሊያተናቸዉ፣ እንደ ዱቄት ሊፈጫቸዉና ሊያደቃቸዉ፣ እንደ ኖኅና እንደ ሎጥ ዘመን ሊደመስሳቸዉ ይችላል። ለዚህ ነዉ እርሱ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰዉ፤ እግዚአብሔር እንዲፈጽም የሚያደርገዉን፣ ማንም ምንም ሊያደርግ የማይችለዉ። እንኳን የእግዚአብሔርን መልካም ነገር የሚፈጽም አይደለም የእግዚአብሔር ቁጣ ሆነዉ ለመቅጫ የሚነሱ ሰዎችን፤ የእግዚአብሔር ቁጣ እስከሚበርድ ድረስ ማንም ምንም ሊያደርጋቸዉ አይችልም። ምክንያቱም በእርሱ የተፈቀደላቸዉ ስለሆነ እነዚያ መቀጣት ያለባቸዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች ዋጋ የሚከፍሉት በሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድርም ጭምር ስለሆነ ነዉ። ለዚህም እንደ ምሳሌ ብንመለከት በብሉይ ዘመን እስራኤላዉያን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ርቀዉ ቃሉንም ባለመስማት በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት በጸኑ ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የእግዚአብሔር ቁጣ ሆኖ መሪዎቹን ከወንበር ቆርጧቸዋል። የተለያየ መከራና ስቃይ አድርሶባቸዋል። ሕዝቡም ለስደትና ለምርኮ ተዳርገዋል።

ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔር ባወቀዉና በፈቀደዉ ምክንያት ጨካኞችና ግፈኞች ሰዎች፤ ልክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ሄሮድስ ምንም የማያዉቀትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ሕፃናት እንደገደለ፤ ምንም በማያዉቁት ላይ መከራና ስቃይ ሊያደርሱባቸዉ ይችላል። ታዲያ በእግዚአብሔር እዉቅና የተፈጸመ ስለሆነ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር ከፈለገ ጨካኙን፤ የጭከና ተግባር ከማከናወኑ በፊት በሥጋ ሞት ሊጠራዉና ከምድር ሊያስወግደዉ ይችል ነበር። እዚህ ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲባል እግዚአብሔር የወደደዉ ተግባር ነዉ ማለት ሳይሆን፤ በዚያ ሕይወት ይታለፍ ዘንድ ግድ ስለሆነ ድርጊቱ በእግዚአብሔር ዘንድ እየታወቀ ቢሆንም ተፈጻሚ ሊሆን ችሏል ለማለት ነዉ እንጂ እያንዳንዱ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ ለሚፈጽመዉ ግፍና መከራ በዚያኑ ልክ በምድርም በሰማያም ዋጋ ይከፍልበታል። ለእግዚአብሔር ቁጣነት የሚመረጡትም ሰዎች፤ በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጎልማሳነት ዘመናቸዉ በሚያሳዩት ትዕቢት፣ ክፋትና ተንኮል፣ ዓመፃ፣ ጭከና፣ እንዲሁም አእምሮ ቀላልነትና አእምሮ ሕፃንነት ምክንያት ነዉ እንጂ እግዚአብሔር ወስኖባቸዉ አይደለም። ለዚህም ነዉ እንደ ስራቸዉ የሚፈረድባቸዉ። እንኳን በፍጡሮቹ ሰዎች አይደለም ራሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ እርሱ ባወቀዉና በፈቀደዉ መልክ በክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች የተለያየ መከራና ግፍ ተፈጽሞበታል። ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎችም የተመረጡት ከላይ በተገለጸዉ መስፈርት ምክንያት ነዉ እንጂ እግዚአብሔር ወስኖባቸዉ አይደለም።

እያንዳንዱ ሰዉ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ መልካም ሆነ መጥፎ ተግባር የመስራት ነጻነት አለዉ:: በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ በሚፈጽመዉ ስራና እምነት ነዉ የሚፈረድለትና የሚፈረድበት እንጂ ሲፈጠር ማንም ሰዉ አልተፈረደለትም፤ አልትፈረደበትም:: በምድር ላይ ከተገለጸ በኃላ በሚያሳየዉ የመልካም ሆነ የመጥፎ ብቃት ደረጃ ነዉ ለገነት ሆነ ለሲኦል እንዲሁም ለመንግሥተ ሰማያት ሆነ ለገሃነመ እሳት የሚታጨዉና የሚዳረገዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችዉ ዉስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በቶሎ እንደሚመጣና ቀኑ መቅረቡ ይገልጻል:: ነገር ግን ይኸዉ ሁለት ሺህ ዓመት ቆይቶ እንኳ አልመጣም:: የእኛ አቆጣጠርና የእግዚአብሔር አቆጣጠር ይለያያል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በእርግጥ የእኛና የእግዚአብሔር አቆጣጠር አይገናኝም:: እኛ ፀሐይንና ጨረቃን ተከትለን ነዉ ቀናቶች፣ ወራቶች፣ ዓመታትን፣ ዘመናትን የምንከፋፍለዉ:: በእግዚብሔር ዘንድ ለእኛ ብዙ ዘመን የሚመስለን የዐይን ጥቅሻ ጊዜ እንኳ አይሆንም:: ምክንያቱም ያልኖረበት ዘመን የለምና እኛ ያሳለፍነዉ ዘመን ለዚያ ዘመን ቢካፍል አልቦ(ዜሮ) ይመጣልና ነዉ፤ እንኳን በመቶዎች የሚቆጠር ዘመን ቀርቶ በሺዎች የሚቆጠር ዘመን በእርሱ ዘንድ እንደ አንድ ቀን አይሆንም:: ከዚህ አንጻር በቶሎ የሚለዉ በእኛ ዘመን ብዙ ዘመን አድርገን ብንቆጥረዉም በእርሱ ዘንድ ግን የዐይን ቅጽበት ጊዜ ያህል ነዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሕይወታችን ዝግጁ ሆነንና ታምነን እንድንገኝ ስለሚፈልግ፤ ማንኛዉም የሚፈጸም ድርጊት በግልጽ አያሳዉቀንም:: ልክ ሞታችንን እንደማናዉቅና ሁል ጊዜ ሕይወታችንን በንስሐ እየመረመርን በቅዱስ ቁርባን ተወስነን መኖር እንዳለብን ሁሉ፤ ስለ ዓለም እልፈትና ስለ ቀኑ በእርግጠኝነት የምናዉቀዉ ነገር የለም:: ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን በመፍራትና በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ዉስጥ እንድንመላለስና በዝግጅት ሕይወት እንድንኖር ፈልጎ ነዉ በቶሎ እንደሚመጣ የተናገረዉና ያናገረዉ::

አንዳንድ ምእመናን ሆኑ አገልጋዮች፤ በዘመናችንም እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ትንሣኤ በቅርቡ እንደሚመጣ በተለያዩ አገልጋዮችና ምእመናን ሲያናግር፤ በቀናት ወይንም በወራት ወይንም በዓመታት ዉስጥ ወዲያዉ እንደሚመጣ አድርገዉ በማሰብ ከጠበቁት ወራት ወይንም ዓመት በላይ ሲሆንባቸዉ በመልእክቱ ተሰናክለዋል:: እንዲሁም አንዳንዶች እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስምልኩ ስለሆነ፤ እንዲሁም ሁሉም እንደነሱ በባዶ ሕይወት የሚመላለስ እየመሰላቸዉ «እግዚአብሔር በአሁን ዘመን መልእክቱን የሚያስተላልፈበት ሰዉ የለም» በማለት የእግዚአብሔርን ስራ የሚገድቡና እግዚአብሔርንም ነጥብ በማትሞላ እዉቀታቸዉ ወደ ራሳቸዉ ሐሳብ ለማምጣት የሚዳፈሩ አሉ:: እግዚአብሔር ከዓመታት በኃላ ወይንም ከዘመናት በኃላ የሚያከናዉነዉን አስቀድሞ በመልእክተኞቹ ያናግራል:: ነገር ግን ዘመኑንና ቀኑን በግልጽ አያናግርም:: ቢበዛ ምልክቶችን ያናግራል:: በመሆኑም ከእኛ የሚጠበቀዉ የእግዚአብሔርን መልእክት ሆነ ቃል በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ መመርመር ነዉ እንጂ በእዉቀታችንና በጥበባችን የምንመረምር ከሆነ እንሰናከልበታል:: እንደ ዓመፃችን ደረጃም ልንወድቅበትና ልንጠረግበት እንችላለን:: አይሁድ ካህናት፣ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰናከሉትና የወደቁበት ከዚያም በእግዚአብሔር ቁጣ የተጠረጉበት ተአምሩን፣ ፈዉሱን፣ ትምህርቱን በእዉነትና በመንፈስ መመርመር ሲገባቸዉ በእዉቀታቸዉና በሊቅነታቸዉ በመመርመራቸዉና በመታበያቸዉ ነዉ፡፡ እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን የእግዚአብሔር እዉነተተኛ አገልጋዮችና መልእክተኞች በሕልም ወይንም በራእይ ወይንም በድምፅ የሚገለጽላቸዉ መቼ እንደሚፈጸም በግልጽ ቀኑ እስካልተነገራቸዉ ድረስ ሕልሙ ሆነ ራእዩ እንዲሁም በድምፅ የተነገራቸዉ መቼ በተግባር እንደሚፈጸም አያዉቁም፡፡ ራእዩን እንዳዩና ድምፁን እንደሰሙ ካዩበትና ከሰሙበት ጊዜ በኋላ ባለዉ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆን ስለሚያምኑ፤ ያ እግዚአብሔር የገለጸላቸዉንና የተናገራቸዉን ለሕዝብ እንዲያቀርቡ ከታዘዙ ያዩትን የተባሉትን ወዲያ ለሕዝቡ ያቀርባሉ፡፡ ጊዜዉ እስካልተገለጸላቸዉና እስካልተነገራቸዉ ድረስ በቶሎ እንደሚሆን ነዉ መግለጽ ያለባቸዉ፡፡ ምክንያቱም ከተገለጸላቸዉና ከተነገራቸዉ በኋላ ራእዩ ሆነ ድምፁ ወደተግባር ሊለወጥ ስለሚችል እያንዳንዱ ሰዉ ዛሬ ነገ ሳይል በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስና በእዉነተኛ ሕይወት መኖር አለበትና፡፡ እንደ ጻድቁ ዮሴፍ፣ እንደ ነቢዩ ኤርምያስ፣ እንደ ነብዩ ዮናስ በግልጽ ቀኑ የተነገረዉ እዉነተኛ አገልጋይና መልእክተኛ ካለ ደግሞ የሥጋና የደም ስሜቱና እዉቀቱን ሳይጨምር በግልጽ ሊያሳዉቅና ሊናገር ይችላል፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሁለት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን «እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ወይንም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወይንም ቅዱሳን መላእክት ወይንም ቅዱሳንና ጻድቃን ተገለጹልን፣ እንዲህ አሉን» የሚሉ ሰዎች አሉ:: በምን መልኩ ነዉ የሚገለጹላቸዉ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እዚህ ላይ ሁለት ተቃራኒ መንፈሶች በዚህች ምድር ዉስጥ እንዳሉ እያንዳንዳችን ማወቅና ማስተዋል ይኖርብናል:: ዲያብሎስ ከነ ሠራዊቱ ሰይጣናት፣ ከእግዚአብሔር እንደሆነ በመምሰል ሊፈታተነንና ሊያታልለን፣ እንዲሁም ከመንገዳችን ሊያወጣን እንደሚችል መገንዘብ ይገባናል:: ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ያልሆነዉን እያንዳንዳችን የመለየት ጸጋ የተሰጠን እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ እንድናመልከዉና እያንዳንዱን መገለጥ ሆነ መልእክት፣ እንዲሁም አገልግሎት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ በመመርመር ነዉ:: እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን የምናመልክና የምንመረምር ከሆነ ልንሰናከልና ልንወድቅ እንችላለን:: በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ የምንመላለስና የምንመራ ከሆነ ግን ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ያልሆነዉ መለየት አንቸገርም:: ለዚህ ብቃት ካልደረስን ደግሞ የሚያጋጥመንን ወይንም ያጋጠመንን የተለየ ጸጋ ላለዉ እዉነተኛ አገልጋይና ምእመን በመግለጽ ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ያልሆነዉን እንዲለዩልን ማማከር ይበጃል:: ምክንያቱም ዲያብሎስ የእምነታችንን ብቃትና የየእለት ሕይወታችን ብቻ አይደለም እያሰብነዉ ያለዉንና የዉስጥ አቋማችንን በሚገባ ስለሚያዉቅ እንደ ሐሳባችንንና አቋማችን የተለያየ ፈተና ሊያመጣብን ይችላል:: ለዚህም ነዉ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን በሚያሳዩት መንፈሳዊ ትጋትና ብቃት እግዚአብሔር እንደ ደረጃቸዉ ጸጋዉን አድሏቸዉ እንደሚጠቀምባቸዉ ሁሉ፤ በሥጋና ደም ስሜት ሲመላለሱ ደግሞ ሰይጣናት ተጠቅመዉባቸዉ ከእግዚአብሔር እዉነት ተቃራኒ እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ ያደርጋቸዋል:: በመሆኑም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል::

እግዚአብሔር ሆነ እመቤታችን እንዲሁም ቅዱሳን መላእክት ሆኑ ጻድቃን ለፈቀዱላቸዉና ለወደዱት ሰዉ በሚገባቸዉ መልክ ሊገለጡላቸዉ ይችላል:: እያንዳንዱ ሰዉ ፈቃደኛ ከሆነና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካሟላ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በነፍሱ( በሕሊናዉ) እንደ ረቂቅነቱ ሊገለጽለት(ሥጋዊ ጆሮ በማያዳምጠዉ) ድምፅ ሊናገረዉ ይችላል:: ከዚያ ዉጭ ለማንኛዉም ሰዉ እግዚአብሔር በነፍሱ(በሕሊናዉ) የመገለጫዉ አንዱ መንገድ በሕሊና ወቀሳና መልካም ለሚያደርገዉ ደግሞ የተለየ ጸጋ በማደል ነዉ:: ከዚህ ዉጭ እንደ ግለሰቡ ብቃትና መረዳት በራእይ ወይንም በህልም ወይንም በግልጥ በሚገባዉ መልኩ ሊገለጡለት ይችላሉ:: ዋናዉ «ከእግዚአብሔር ነዉ፣ አይደለም» ለሚለዉ ከላይ በገለጽኩት መሰረት መመርመር ወይንም ማስመርመር ነዉ የሚጠበቅብን::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: አንዳንድ መምህራንና ምእመናን እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ሞተን እንደምንቀርና በፍርድ ቀን ግን ይህ የተገለጽንበት ሥጋና አጥንት ከያለበት ተሰብስቦ ነፍሳችን

እንደምትዋሐደዉና ወደ መንግሥተ ሰማያት ወይንም ወደ ሲኦል እንደምንገባ ያስተምራሉ፤ ያምናሉ:: ታዲያ ይህ የሚበሰብሰዉና ያደፈና የጎደፈ እንዲሁም የጎሰቆለ ባሕርይ የተላበሰዉ ሥጋችንና አጥንታችን እንደ ጾታ ልዩነታችን ወደ መንግሥተ ሰማያትና ወደ ገሃነመ እሳት ይገባል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን ነቢያት ሆኑ መምህራን እንዲሁም የተለያዩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በዘመናቸዉ በሚረዱትና ትዉልዱም በሚገባዉ መልክ ነዉ ሊጽፉ ሆነ ሊያስተምሩ የሚችሉት:: አሁን ባለነዉ ትዉልድ የጥንቱን ሆነ የኋላ ዘመናትን እዉቀት ሆነ ትምህርት ልንገመግምና «ይህ በዚህ መልኩ ነበር መጻፍ ያለበት፤ ይህ በዚህ መልኩ ነበር ትምህርት መሰጠት ያለበት» ማለት አንችልም:: ምክንያቱም በዘመኑ ለነበረዉ ትዉልድ የሚገባዉና የሚመጥነዉ ነበር:: ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በተገለጸበት ዘመን በትንሣኤ የሚያምኑ ሰዎች ትንሣኤ ምን እንደሆነ በግልጽ አላስተዋሉትም:: በሥጋ የሞተ ሰዉ እንደ ገና ሊነሳ የሚችል አይመስላቸዉ ነበር:: እንዲሁም ከሥጋ ሞት በኋላ ስላለዉ ሕይወትና ከፍርድ ቀን በኋላ ስለሚኖረዉ ሕይወት በሚገባ አላስተዋሉም ነበር:: አንዳንዶቹ ይህ ምድራዊ የጋብቻ ሥርዓት ሁሉ በሰማይም የሚቀጥል አድርገዉ የሚያስቡ ሁሉ ነበሩ:: ክርስቶስ ግን ለዚህ የተሳሳተ እምነትና አስተሳሰብ  በሰማያት ዉስጥ መጋባት ሆነ በምድር ላይ በተገለጽንበት ግዙፍ ሥጋና አካል እንደማንገለጽ ይልቁኑ እንደ ቅዱሳን መላእክት በረቂቅ አካልና በሰማያዊ ሥርዓት ብቻ ሕያዉ ሆነን እንደምንኖር ነዉ በግልጽ የተናገራቸዉና ያስተማራቸዉ::

ስለዚህ በመጻሕፍት ሆነ በመምህራን እኛ ልንረዳዉና በሚገባን መልኩ ሕያዋን እንደሆን፣ ሞተን እንደማንቀር ለማስተማር ነፍሳችን ተመልሳ ሥጋችንና አጥንታችንን ተዋሕዳ እንደምትነሳና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሆነ ወደ ሲኦልና ገሃነመ እሳት እንደምትገባ ቢገልጹና ቢያስተምሩ ትክክል አይደለም ማለት አንችልም:: አንድ አንደኛ ደረጃ ያለ ተማሪ ከሁለተኛ ደረጃ ካለ ተማሪ በሥጋዊ እዉቀትና በማስተዋል እንደሚያንስ፣ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ያለ ተማሪ ከከፍተኛ ተቋም ተማሪ በሥጋዊ እዉቀት እንደሚያንስና እንደ ደረጃቸዉ ሊገባቸዉና ሊረዱት የሚችሉት ትምህርት እንደሚሰጣቸዉና በሚገባቸዉና በሚመጥናቸዉ ምሳሌ እንደሚቀርብ ሁሉ፤ በመንፈሳዊ እዉቀት ደረጃም አንድ ስለ ትንሣኤ የማያዉቅና የማያምንን ሰዉ «ከሥጋ ሞት በኋላ በረቂቅ አካል ነዉ የምትገለጠዉ፣ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በገነት ወይንም በሲኦል ዉስጥ ትቆይና በፍርድ ቀን ደግሞ የቅዱሳን መላእክትን ረቂቅ አካል ተላብሰህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ:: በሲኦል ከነበርክ ደግሞ እንደ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ረቂቅ አካል ለብሰህ(ተገልጠህበት) ወደ ገሃነመ እሳት ትገባለህ» ቢባል ራሱን በሥጋ የተገለጸ ብቻ አድርጎ ስለሚያስብና በግንባሩ ፊት ለፊት ሆና አንጎል ዉስጥ በረቂቅ አካል ያለችዉን ሕያዉ ነፍሱን(ሕሊናዉን) ማስተዋልና ማወቅ ስለሚከብደዉና ስለሚረቅበት፤ የሚያዉቅበትና የሚያስተዉልበት ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በሚያዉቀውና በሚረዳዉ በራሱ አካል በሥጋዉና በአጥንቱ ምሳሌ እየተመሰለለት ቢማር በሂደት ወደ ሙሉ እዉቀትና እምነት እንዲመጣ ስለሚረዳዉ ይሆናል «ሥጋችን ተመልሶ ከአጥንታችን ጋር በመዋሐድ »ይነሳል ተብሎ ትምህርት የሚሰጠዉ::

ያለዉ እዉነታ ግን እኛ ማለት ነፍሳችን(ሕሊናችን) ናት፡፡ ይህ ሥጋችን በምድር ተገልጸንበት የምንታይበትና የምንመላለስበት ነዉ እንጂ ሕያዉና አማናዊ ፍጥረት አይደለም፡፡ ነፍሳችን ብቻ ናት ከነበረ ካለ ሕያዉ ሆኖ ከሚኖር አምላክ ዘንድ ሰርጻ(ወጣ) ሕያዉ ሆና በተለያየ መልኩ የምትኖረዉ፡፡ ከምድራዊ ዘመኗ በኋላ በምሳሌያዊ ባሕርይ(በረቂቅ አካል) ነዉ የምትገለጸዉ እንጂ ዳግም ግዙፍ አካል( ምሳሌያዊ ፍጥረት) ለብሳ አትገለጽም፡፡ ምክንያቱም ከዚህች ምድር ዉጪ ያለዉ ዓለም ሁሉ ረቂቅ ነዉ፡፡ በዚህ ሥጋዊ ዐይናችን የሚታይና በሥጋዊ እጃችን የሚዳሰስ ነገር የለበትም፡፡ ነፍሳችን እንደ መናፍስት በረቂቅነት ነዉ ሕያዉ ሆና በተዘጋጀላት ቦታ የምትኖረዉ፡፡ ነፍሳችን በምድርም ቢሆን የጾታ ልዩነት የላትም፡፡ የተገለጸችበት ሥጋ አካል ብቻ ነዉ የጾታ ልዩነት ያለዉ፡፡ ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ እንደ ቅዱሳን መናፍስትና እንደ ርኩሳን መናፍስት የጾታ ልዩነት እንደሌላቸዉ ሁሉ በረቂቅ አካል ነዉ ካለ ጾታ ልዩነት የምትገለጸዉ፡፡ ስለዚህ ይህ በምድር የተገለጽንበት ማች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ፣ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ የተላበሰዉ ሥጋችን ዳግም አንገለጥበትም ማለት ነዉ፡፡

ለዚህ እንደ ምሳሌ የማቀርብላችሁ አንድ የመኪና አካል በተለያየ መልክና ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ነገር ግን ትንሽም ይሁን ግዙፍ መኪና የሚያንቀሳቅሰዉ ዋናዋ ሞተር ነዉ፡፡ ሞተር ከሌለ የመኪናዉ አካል ምን ቢያምር፣ ምን ግዙፍ ቢሆን ፣ ምን የሚመች ቢሆን ለመጓጓዣ አገልግሎት አይሰጥም፤ ያዉ እንደ ቆርቆሮነቱ ነዉ የሚታየዉ፡፡ መኪና ነዉ አያስብለዉም፡፡ እነደዚሁ ሁሉ ለዚህ ለተገለጽንበት ሥጋ ሕይወት የምትሰጠዉ በግንባራችን ፊት ለፊት አንጎላችን ዉስጥ ያለችዉ ረቂቋ ሕያዉ ነፍሳችን ናት፡፡ እርሷ ስትለየዉ ይህ ሥጋ ሰዉ መሆኑ ይቀርና ሬሳ ወይንም አስከሬን ነዉ የሚሆነዉ እንጂ ዳግም በምድር ላይ የተለየ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ አንድ አካሉ የተበላሸ መኪና ሞተሩ ደህና ከሆነ ሌላ አካል ተበጅቶለት አገልግሎት መስጠት እንደሚችል ሁሉ፤ ነፍሳችንም የማትሞትና ከመኖር ወደ አለመኖር የማታልፍ ስለሆነ እግዚአብሔር በሚያዘጋጅላት በሌላ ረቂቅ አካል ተገልጻ በተዘጋጀላት ቦታ ትኖራለች፡፡ አንድ ሞተር በሚዘጋጅለት አካል (ቦዲይ) ቅርጹ ሆነ መልኩ የተለያየ ቢሆን እንኳ ዋናዉ አንቀሳቃሽ ሞተር አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዉጭ መኪኖቹ በሚታየዉ አካላቸዉ የተለያዩ ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ እንደዚሁ ሁሉ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ሁሉ ነፍሳቸዉ አንድ ዓይነት ብትሆንም የተገለጹበት አካል ጥቁር ወይንም ነጭ ወይንም ቀይ ወይንም ጠይም ወይንም የቀይ ዳማ መልክ ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡ እንዲሁም ቁመናቸዉ አጭር ወይንም ረጅም ቀጭን ወይንም ወፍራም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በዓለም ላይ የሚታየዉ የሰዎች መለያየት በተገለጽንበት አፈር ዉስጥ ገብቶ በሚበሰብሰዉና ወደ አፈርነት በሚለወጠዉ ቅርፊት በሆነዉ ሥጋችን እንጂ በሕያዉ ነፍሳችን እድሜያችን ሳይቀር አንድ የሆነ በአዳም ንስሐ ጊዜ የሁላችንም ነፍስ የታየችና ካለመኖር ወደ መኖር የመጣች ናት፡፡ እድሜያችንም ከዚያ ወዲህ የሚቆጠረዉ በሥጋችንም በምድር ተገልጸን በምንመላለስበት ወቅት ነዉ እንጂ ለወደፊት የማንኖርበት ጊዜ ስለሌለ እድሜያችን ከሥጋ ሞት በኋላ አይቆጠርም፡፡ እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነን ነዉ የምንኖረዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ አንዳንድ መምህራንና ምእመናን የእግዚአብሔርን መንግሥት በቀላሉ የሚገባበት መንገድ እንዳለና እዉነተኛ ንስሐ ቢገባም ባይገባም፣ ቅዱስ ቁርባን ቢቀበሉም ባይቀበሉም፣

*መልካም ምግባር ቢይዙም ባይዙም ወደ ገነትና ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ የሚያስተምሩና የሚናገሩ አሉ። እዚህ ላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ሌላ ሰፊ አቋራጭ መንገድ አለ ወይ?*

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>:** ዓለም መንገዱን የሳተዉና ለሥጋና ደም ስሜቱ የሚገዛዉ፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ፈቃድ የሚወጣዉ በአስመሳይ አገልጋዮችና በሐሰተኛ ምስክሮች አማካይነት ነዉ። እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ ስለ ሕይወት መንገድ ጠባብነት በግልጽ በማቴዎስ ወንጌል በምእራፍ 7 ከቁጥር 13 እስከ 14 «**<u>በጠበበዉ ደጅ ግቡ</u>** ወደ ጥፋት የሚወስደዉ ደጁ ሰፊ ነዉ...» ይላል። እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 13: ከቁጥር 24 እስከ 30 «**<u>በጠበበዉ በር ለመግባት ተጋደሉ</u>**፤ እላችኋለሁና፣ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም። (ምክንያቱም ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ቅድሚያ በመስጠት ለእግዚአብሔር ፈቃድ አይሰለፉምና።) ባለቤቱ ተነስቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ እናንተ በዉጭ ቆማችሁ :- ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ለታንኳኩ ትጀምራላችሁ፤ እርሱም መልሶ :- ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላዉቃችሁም ይላችኋል። ( ምክንያቱም እንደ ቃሌ ሆናችሁ የማትገኙ አስመሳይ አገልጋይና አማኝ ስለሆናችሁ።) **<u>በዚያን ጊዜም በፊትህ በላን ጠጣንም በአዳባባያችንም አስተማርህ ልትሉ ትጀምራላችሁ፤</u>** እርሱም :- እላችኋለሁ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላዉቃችሁም፤ ሁላችሁም ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ይላችኋል። **<u>አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ፣ እናንተ ግን ወደ ዉጭ ተጥላችሁ ስትቀሩ፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።</u>** ከምሥራቅና ከምዕራብም ከሰሜንና ከደቡብም ይመጣሉ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ። እነሆም፣ ከኋለኞች ፊተኞች የሚሆኑ አሉ፣ ከፊተኞች ኋለኞች የሚሆኑ አሉ።» ይላል*

ይህ የሚያሳየን ደግሞ ማንም ይሁን ማን በዓመፃ፣ በክህደትና በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ የሚመላለስ፤ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሰና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልተመላለሰ በስተቀር በአቋራጭ ወይንም በብልጣብልጥነት ለሥጋ በሚመች በሰፊ መንገድ ዉስጥ የሚመላለስ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም ማለት ነዉ። ለምሳሌ በፕሮቴስታንቱና በመሰሎቻቸዉ የእምነት ተቋሞች ብዙዎችን ለመሳብ የሚጠቀሙበት መንገድ አንዱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስገባ ሰፊ መንገድ እንዳለ ነዉ። «በጠበበዉ መንገድ ዉስጥ ለመግባት ተጋደሉ» የሚለዉን፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት ለመብቃት ታላቅ ተጋድሎ እንደሚጠብቀን የሚገልጸዉን የእግዚአብሔር ቃል በተቃራኒ ተሰልፈዉ ለሰማያዊ መንግሥት የተለየ ተጋድሎ እንደማያስፈልግና «ኢየሱስ ጌታ ነዉ» ተብሎ ከታመነ፤ ትእዛዝ ተጠበቀ አልተጠበቀ፣ ምግባር ተያዘ አልተያዘ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚወረስ ነዉ የሚያስተምሩትና የሚመሰክሩት። ይህ ታዲያ አታላዩ(ሸዋጁ) የዲያብሎስ መንፈስ በክርስትናና በኢየሱስ ስም ሽፋን ራሱን ሰዉሮ ትዉልዱን ወደ ሞትና ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ እየወሰደዉ ያለዉ። ምክንያቱም እዉነተኛ ንስሐና መለኮት የተዋሐደዉ ሥጋና ደም በእነሱ ዘነድ አይታወቅም። ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ምጽዋዕት የመሳሰሉት የተለየ ጸጋና ኃይል የምናገኝባቸዉ በእነሱ ዘንድ ቦታ የላቸዉም። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ «ቃሌ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል» ያለዉን ቃል አቃለዉና ንቀዉ «ትእዛዝ ተጠበቀ አልተጠበቀ በጸጋ ስለዳን

መንግሥቱን እንወርሳለን» እያሉ ራሳቸዉን በማታለልና በዉሸት እዉነት ራሳቸዉን በማጽናናት ትዉልዱን ወደ ሞትና መቀመቅ እየመሩት ይገኛሉ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት የሚወረሰዉ እንደ ቃሉ ሆኖ በመገኘት ነዉ እንጂ ለሥጋና ደም ስሜታችን በሚመች ሥርዓትና ሕይወት በመመላለስ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም በምድር ከተገለጸ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብን፣ ምን ማድረግ እንደሌለብን በግልጽ አስተምሮናል፡፡ በዚሁ መሰረት እያንዳንዱ የአዳምና ሔዋን ዘር ለእግዚአብሔር መንግሥት ለመብቃት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅና የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነትን ማመን ግድ ይሆንበታል፡፡ ከዚያም ለሕያዉነት ሕይወት የሚያበቃንና ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንድንፈጥር የሚያደርገንን ቅዱስ ቁርባን መለኮት የተዋሐደዉን «ምሳሌያዊ ያልሆነ እዉነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደሙ ነዉ» ብሎ በማመን መቀበል ግድ ይሆንበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሕግ ማክበርና እንደ ትእዛዙ መኖር ይጠበቅበታል፡፡ ሰዉ ሥጋ ለባሽ ነዉና በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ ደግሞ ተጸጽቶ በእዉነተኛ ንስሐ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን በመቀበል ኃጢአቱን ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ማስደምሰስ ይኖበታል፡፡ ባጠቃላይ ምድራዊ ሕይወቱን በንስሐ እየመረመረ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለስ ሰዉ ነዉ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ የሚችለዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ አቋራጭ ወይንም ሰፊ መንገድ ወይንም በብልጣብልጥነት የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ አይቻልም፡፡

ነፍስ በዚህ ምድር ዉስጥ ራሷን ከእግዚአብሔር ጋር በንስሐ አስታርቃና አንድነት ሳትፈጥር በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት፣ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እያለች በሥጋ ሞት ከተጠራች በምንም መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ አትችልም፡፡ በመሆኑም በየትኛዉም አገልግሎት ላይ ያለ አገልጋይ ሆነ ምእመን ከእግዚአብሔር እዉነት ዉጭ «ወደ እግዚአብሐር መንግሥት የሚያስገባ ሌላ አቋራጭ መንገድ አለ» በማለት፤ «ይህን ካመጣችሁ፣ ወይንም እንደዚህ ካደረጋችሁ፣ ንስሐ ባትገቡም፣ ትእዛዙንና ሕጉን ባትጠብቁም፣ ቅዱስ ቁርባን ባትቀበሉም ኃጢአታችሁ ስለሚደመሰስ ገነትና መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ» የሚል ካለ፤ እርሱ በሰዉ ነፍስ የሚጫወት ለሥጋዉና ለጥቅሙ ያደረ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚመላለስ አስመሳይ አገልጋይና አማኝ ነዉ፡፡ እዉነተኛ አገልጋይና ምእመን ማንንም ሳይሸነግል እያንዳንዱ ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን ራሱን ክዶ የሚናገርና ስለ እዉነት የሚመሰክር ነዉ እንጂ ለሥልጣኑ፣ ለክብሩ፣ ለጥቅሙ፣ ለዝናዉ ሲል ምእመናን የሚሸነግልና የሚያስመስል አይደለም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በሕሊናዬ የሚጉላላና ግልጽ ያልሆነ አንድ ጥያቄ አቀርባለሁ፡፡ ይኸዉም በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ በተለያየ ቦታ ላይ አዳምና ሔዋን በዚህች ምድር ዉስጥ ባደፈና በጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲኖሩ ከተፈረደባቸዉ በኋላ በእዉነተኛ ንስሐ በተመለሱ፣ እንዲሁም ስለ ዓመፃቸዉና ክህደታቸዉ እጅግ በተጸጸቱና እግዚአብሔርንም ይቅርታ በጠየቁ ወቅት፣ የሰዉ ዘሮች ነፍሳት ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆን ድረስ እግዚአብሔር ለቅጽበት ያህል ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸዉ በዚያ

ቅጽበት በነጻ ሕሊናቸዉ ያሳዩትን የእምነትና እርሱን ፈጣሪያቸዉንና አምላካቸዉን የመፈለግ ብቃት አንደተመለከተና እጅግ ከበቃችዉ ነፍስ ከእመቤታችን ነፍስ ጀምሮ ሌሎች የበቁ ነፍሳት(አእምሮ ጽኑአን)፣ ምርጥ ነፍሳት(አእምሮ አዋቂዎች)፣ አእምሮ ሕፃናት(ራሳቸዉን በሚገባ መግዛት ያልቻሉ)፣ አእምሮ ቀላሎች (የሚያረካ ሕሊና ያልያዙ)፣ ትዕቢትና ክፋት እንዲሁም ዓመፃ (ያልተገባ ሕሊና የያዙ) ነፍሳት እንደታዩና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና እቅድ ሰዉ ሆነዉ እንደሚወለዱ ተገልጿል:: እዚህ ላይ እነዚህ ነፍሳት ሰዉ ሆነዉ እስከሚወለዱና በምድር እስከሚገለጹ ድረስ የሚያዉቁት ነገር አለ ወይ? እንዲሁም ምንም የማያዉቁ ከሆነ በምን መልኩ ነዉ እንዳያዉቁ የተደረገዉ::

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በዚህች ምድር ዉስጥ ባደፈና በጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲኖሩ አልፈረደባቸዉም:: በራሳቸዉ ነጻ ፈቃድና ምርጫ ነዉ ምድራዊ የመከራና የስቃይ ሕይወት ያመጡት:: የእግዚአብሔር ምርጫና ፈቃድ በገነት አንዳች ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም ጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ በማይታይባት ዉስጥ እንዲኖሩና በሁለቱ ነፍሳት በምሳሌያዉ ባሕርይ(በረቂቅ አካል) ግንኙነት አማካይነት በእቅዱ የነበሩት ነፍሳት ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ቁጥር ጋር እኩል እስከሚሆንበት ድረስ ከባሕርይዉ እየወጡ (እየሰረጹ) በገነት እንዲገለጹና ቁጥራቸዉ በምድር ካሉት ርኩሳን መናፍስት እኩል በሚሆንበት ጊዜ እያንዳንዱ ነፍስ እንደ ቅዱሳን መላእክት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ለብሰዉ(ተገልጸዉበት) ወደ ሰማያት ዉስጥ እንዲገቡ፣ እንዲሁም በሰማያዊ ሥርዓት እንዲመላለሱና ሕያዉ ሆነዉ በተቀደሰና በደስታ ሕይወት ብቻ እንዲኖሩ ነበር:: ይሁንና ገና አንድ ነፍስ ካለመኖር ወደ መኖር በገነት ዉስጥ ሳትመጣ አዳምና ሔዋን «አታድርጉ» የተባሉትን ሕሊናቸዉን በማደንደን በድፍረት በማድረጋቸዉና እግዚአብሔርንም በማስቆጣታቸዉ ምክንያት ነዉ ከገነት ተባረዉ አሁን በለበስነዉ ሥጋ በምድር እንዲገለጹ የተደረገዉ::

እነሱ ግን በሰሩት ስህተትና ዓመፃ እጅግ በመጸጸት በእዉነተኛ ንስሐ በመመለስ እርሱን እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ ሆነዉ ይቅርታ ጠየቁት:: እርሱም በባሕርይዉ ርኅሩኅና ይቅር ባይ ስለሆነ ይቅርታ አድርጎላቸዉ ወደ ቀደመ ግዛታቸዉ ገነትና ለመጀመሪያ ለተፈጠሩበት ዓላማ ለመንግሥተ ሰማያት እንደሚያበቃቸዉ ቃል ገባላቸዉ:: ሰዉ ሆነዉ እንዲወለዱ ወይንም በምድር በሥጋ እንዲገለጹ የሚደረጉት ነፍሳት እንዲታዩ ያደረገዉ የአዳምና የሔዋን እዉነተኛ ንስሐ ነዉ:: በዚሁ መሰረት ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) እኩል እስከሚሆን ድረስ ነፍሳትን ለዐይን ጥቅሻ ያህል ከባሕርይዉ በማዉጣት(በማስረጽ) ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በዚያች ቅጽበት በነጻ ሕሊናቸዉ ያሳዩት የእምነትና እግዚአብሔርን የመፈለግ ብቃት በባሕርይዉ ካየና ደረጃ ከሰጣቸዉ በኋላ ወዲያዉ ነዉ ሁሉም ነፍሳት ልክ በርኩሳን መናፍስት መንፈስ ኃይል ወይንም በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ተሸንፈን እንደምናቀላፋና በባሕርይዋ እንደ እግዚአብሔር የማታንቀላፋዉ ሕያዉ ነፍሳችን በእንቅልፍ ጊዜ አንዳች እንደማታስተዉልና አንዳች እንደማናዉቅ ሁሉ፤ እነዚያ ነፍሳት ደረጃቸዉ ከታየ በኋላ ወዲያዉ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል በመሸነፋቸዉና አንዳች እንዳያዉቁና እንዳያስተዉሉ ስለተደረገ፤ ሰዉ ሆነዉ እስከሚጸነሱና እስከሚወለዱ ድረስ

እንዳች የሚያዉቁት ሆነ የሚያስተዉሉት ነገር የለም፡፡ ከተወለዱም በኋላ ቢሆን የማንኛዉም ሕፃን ነፍስ እንደ ማንኛዉ አዋቂ ነፍስ አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ የሕያዉነትና የማወቅ ብቃት ቢኖራትም፤ እርሱ እግዚአብሔር በሚፈቅድላት መጠን ብቻ ነዉ ነገሮችን እያወቀችና እያስተዋለች በሥጋዋ የምታድገዉ እንጂ በአንዴ የምታዉቀዉና የምታስተዉለዉ ነገር የለም፡፡ ተጠያቂ የምትሆነዉ ደግሞ ነገሮችን በሚገባ ማወቅና ማስተዋል ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ በነጻ ሕሊናዋ በምታሳየዉና በምትፈጽመዉ ተግባር፣ ንግግር፣ እንዲሁም ሐሳብ ነዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል**፡፡

### ምዕራፍ ሦስት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በዚህች ምድር፣ በገነት፣ በሲኦል፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሰማያት ዉስጥ ያለዉ አኗኗርና አምልኮ ቢገልጹልን?

**<u>የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: የእኛ የሰዉ ዘሮችና የሰይጣናት ምድራዊ አኗኗራችን: ሁላችንም እንደምናዉቀዉ የእኛ የአዳም ዘሮች ምድራዊ አኗኗራችን ባደፈና በጎሰቆለ ባሕርይና በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ዉስጥ ነዉ:: አምልኳችንም እግዚአብሔር በግልጽ እየታየንና እያወቅነዉ ሳይሆን እንደ ረቂቅነቱ በእዉነትና በመንፈስ ነዉ:: የርኩሳን መናፍስት አኗኗር ደግሞ በረቂቅ አካል በረቂቅ ዓለም ዉስጥ በጉስቁልና ባሕርይና በስቃይ ሕይወት ዉስጥ ነዉ:: በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ ምክንያት እግዚአብሔርን የማምለክና የማወቅ ብቃት ስለሌላቸዉ መሪያቸዉን ዲያብሎስን እያመለኩትና እየተገዙለት ነዉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቆዩት::

በገነት ያለዉ አኗኗር ደግሞ ለገነት የሚያበቃ ሕይወት የያዙት ነፍሳት ከዚህ ሥጋቸዉ በተለያየ መልክ ሲለዩ የሚገለጹት አካል ቀድሞ አዳምና ሔዋን በገነት ተገልጸዉበት የነበረዉን ረቂቅ አካል ለብሰዉ ነዉ:: በገነት እግዚአብሔር በግልጽ ስለማይታይና ስለማይታወቅ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በእዉነትና በመንፈስ ነዉ የሚያመልኩት:: አኗኗራቸዉም በረቂቅ ዓለም ዉስጥ አዳምና ሔዋን በዓመፃ ከመዉደቃቸዉ በፊት በኖሩበት አኗኗር ነዉ::

በሲኦል ቦታ ያለዉ አኗኗር ሁሉም ነፍሳት ከሥጋቸዉ እንደተለዩ እንደ ርኩሳን መናፍስት ረቂቅ አካል ስለሚለብሱ፤ በተገለጹበት አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) እንደ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ በጉስቁልና ሕይወት በስቃይ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ይቆያሉ:: በምድር ዉስጥ እንዳሉት ርኩሳን መናፍስት በዓመፃቸዉ በመጽናታቸዉና በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ባለመመላለሳቸዉና እግዚአብሔርንም በእዉነትና በመንፈስ ባለማምለካቸዉ ምክንያት ወደዚያ ስለገቡ፤ በሲኦል ዉስጥ እግዚአብሔርን የማወቅና የማምለክ ብቃት የላቸዉም:: በዚህም ምክንያት በፍርድ ቀን ሁሉም ከሌሎች ዓመፀኛ ነፍሳትና ርኩሳን መናፍስት ጋር የመጨረሻዉን ፍርድ በማረፊያ ቦታ ተቀብለዉ በቀጥታ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ነዉ የሚጣሉትና በዚያም እንደ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ ፍዳቸዉን የሚቀበሉት::

በማረፊያ ቦታ ያለዉ ሕያወት ደግሞ: ሁሉም ነፍሳት በረቂቅ አካል ስለሚገለጹ በረቂቅ ዓለም ዉስጥ ነዉ የሚኖሩት:: ፈቃደኛ የሆኑ ነፍሳት እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ በማምለክ ራሳቸዉን ለሰማያዊ ሕይወት ማዘጋጀት ይችላሉ:: እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በእንደሚያሳዩት የእምነትና እግዚአብሔርን የመፈለግ ብቃት ለሰማያዊ መንግሥት ሊበቁ፤ የሚፈለገዉ ብቃት ደረጃ ላይ ካልደረሱ ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: እንዲሁም በማረፊያ ቦታ ቆይታቸዉ እንደ ራሳቸዉ ስሜት ብቻ የሚኖሩ ነፍሳት ደግሞ ምንም እንኳን ሌላዉን የሚያሳምጹበት አቅምና ኃይል ባይኖራቸዉም፤ በራሳቸዉ ስሜት በሚፈጽሙት ዓመፃ ምክንያት በተገለጹበት ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) በጉስቁልና ሕይወት እንደ ዓመፃ ሐሳባቸዉ ደረጃ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ

ይሰቃያሉ። በፍርድ ቀንም ከሌሎች ዓመፀኛ ነፍሳት ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ተጥለዉ የመጨረሻዉን ቅጣት ይቀበላሉ።

በሰማያት ዉስጥ ያለዉ አኗኗር ሁሉም በረቂቅ አካል ስለተገለጹ በረቂቅ ዓለም ዉስጥ ነዉ የሚኖሩት። በሰማያት ብቻ ነዉ እግዚአብሔር ባሕርይዉን ወስኖ በብርሃናዊ ባሕርይዉ በመገለጽ በእልፍ አእላፋት ወትእልፊት (የትሪሊዮን ትሪሊዮን) ቅዱሳት መናፍስት(ቅዱሳት መላእክት)ና እጅግ ብቃት ላይ በደረሱ በቅዱሳን ነፍሳት በሚገባቸዉ መልክ ተገልጾ የሚመለከዉ። በዚያም ያለዉ ሕይወት ከማንኛዉ ቦታ በተለየ መልኩ በቅድስናና በእዉነተኛ ደስታ ሕይወት የሚኖርበት ነዉ። ሁሉም ሰዉ ይህን ሕይወት ነዉ ሊመኝና ሊናፍቅ የሚገባዉ እንጂ እዉነተኛ ደስታ የማይገኝባትን ዓለም መዉደድና በዉስጧ በኃጢአት ሕይወት መጠመድ የለበትም።

በፍርድ ቀን በምትዘጋጀዉ ገሃነመ እሳት ዉስጥ የሚኖረዉ አኗኗር ከሌሎች ቦታዎች በከፋ መልኩ ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ዋጋ የሚከፍሉበት ነዉ። በዉስጡ የማይጠፋ ረቂቅ እሳት የሞላበትና የማይሞቱ ረቂቅ ትሎች የሚገኙበት እንዲሆን ተደርጎ ነዉ የሚዘጋጀዉና ዓመፀኞቹ መናፍስትና ነፍሳት እንድ ምድራዊ ዓመፃቸዉ ደረጃ በተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ(ረቂቅ አካል) የረቂቁ እሳትና የረቂቃኖቹ ትሎች ጥቃት የሚደርስባቸዉ። በምድር እጅግ ዓመፃ የፈጸመ መናፍስትና ነፍስ በገሃነመ እሳትም ዉስጥ ልቋቋመዉ የማይችለዉ ስቃይ ነዉ በማይጠፋዉ እሳትና በማይሞቱት ትሎች የሚደርስባት። እንዲሁም ጥቂት ዓመፃ የፈጸመ መናፍስትና የፈጸመች ነፍስ ልትቋቋመዉ የምትችለዉ ጥቂት ስቃይ ነዉ የሚያጋጥማት። እነዚህ መናፍስትና ነፍሳት ለዚህ ስቃይና መከራ ሕይወት የሚዳረጉት ሁለቱም እግዚአብሔርን የመምሰል ብቃት እያላቸዉና ጸጋዉ ተሰቷዉ ሕሊናቸዉን በማደንደንና ከሕሊናቸዉ ፈቃድ በተቃራኒ ነጻ ፈቃዳቸዉንና ምርጫቸዉን በመጠቀም በዓመፃና በክህደት ስለቆሙ ነዉ። እንዲሁም የነፍሳቸዉ ባሕርይ እጅግ የላቀችና ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተገኘች ሆና ሳለ እነሱ ግን ለዓመፃ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት ሕይወት ስላሰለፏትና ከዉድቀታቸዉም በእዉነተኛ ንስሐ ለመመለስና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እንዲሁም በእዉነተኛ ሕይወት ለመመላለስ ፈቃደኛ ባመሆናቸዉ ነዉ ፍርዱ ሊብስባቸዉ የሚችለዉ። ማስተዋል ላለዉ ሰዉ ለሕያዉነት ዘመን ሁል ጊዜ በማይጠፋ እሳት መለብለብና በማይሞቱ ትሎች መነከስ ቀርቶ ለደቂቃዎች እንኳ በታፈነ እምቅ አየር ዉስጥ መቆየትና በዝንብ መነከስ፣ በቅማልና በትኋን መበላት ምን ያህል አስጨናቂ እንደሆነ ይታወቃል። እግዚአብሔን መመሰል የተላበሰች ነፍስ ስለ ትዕቢቷ፣ ስለ ዓመፃዋ፣ ስለ ክህደቷ፣ ስለ ርኩሰቷ መከራንና ስቃይን የምትቀበለዉ፤ ልክ በዚህ ምድር ዉስጥ በተገለጸችበት ሥጋ ላይ የሚደርስ ጉዳት ሁሉ እንደሚያሰቃያት፣ በገሃነመ እሳትም በተገለጸችበት ረቂቅ አካሏ ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ነዉ እንድትሰቃይ የሚያደርጋት። ታዲያ ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ በራሷ ላይ ያመጣችሁ ራሷ ፈቅዳና ወዳ ነዉ። ማንም አላስገደዳትም፤ በነጻ ፈቃዷና ምርጫዋ እግዚአብሔር ማምለክና እንደ ፈቃዱ መኖር፣ በመጨረሻም በእርሱ ሰማያዊ መንግሥት ዉስጥ ሕያዉ ሆኗ መኖር ባለመፈለጓ ነዉ ለዚያ ሕይወት ራሷን የዳረገችዉና የምትዳርገዉ።

ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ የሚኖረዉ ሕይወት ደግም፤ ይኸዉም በፍርድ ቀን ጻድቃን ነፍሳት ወደ ሰማያት ዉስጥ ከገቡና ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ከተጣሉ በኋላ፤ በእኛ አቆጣጠር ከሕያዉነት ዘመን (ከእልፍ አእላፍ ወትእልፊት ምእልፊት) ወይንም የትሪሊዮን ትሪሊዮን ትሪሊዮን) በሕሊናችን ልንደርስበትና ልንገምተዉ ከምንችለዉ ዘመን በኋላ የእግዚአብሔር ቸርነትና ምሕረት በዝታ ለሕያዉነት ዘመን በቅድስናና በደስታ በሰማያት ዉስጥ የሚኖሩት ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት የመጨረሻዉን ጸጋ ብርሃናዊ ባሕርይ እንዲላበሱ ተደርጎ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ እንደ አማናዊ ባሕርያቸዉ ከአማናዊዉ አባታቸዉና ፈጣሪያቸዉ እግዚአብሔር ጋር የመጨረሻዉን ቅድስናና ደስታ አግኝተዉ ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ።

በተቃራኒ ደግሞ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ለሕያዉነት ዘመን በስቃይና በመከራ የሚኖሩት ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት (የተኮነኑ ሰዎች) የተገለጹበት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ከመኖር ወደ አለመኖር አልፎ እግዚአብሔር በአምላካዊ ሥልጣኑ አንጽቷቸዉ ሁሉም በነጥብ ቦታ በብርሃናዊ ባሕርይዉ እንዲሸፈኑ በማድረግ የራሳቸዉን ህልዉና አሳጥቷቸዉ በበድን ሕይወት አንዳች ሳያዉቁና ሳያስተዉሉ ለሕያዉነት ዘመን በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ይኖራሉ። ልክ አንድ ሕፃን በእናቱ ማኅፀን ዉስጥ እያለ ሕያዉ ፍጥረት ቢሆንም አንዳች የሚያዉቀውና የሚያስተዉለዉ ነገር እንደሌለ ሁሉ እንዚህ ርኩሳን መናፍስትና ዓመፀኛ ነፍሳት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ አንዳች የሚያዉቁት ሆነ የሚያስተዉሉት ነገር አይኖርም። ሕያዋን ፍጥረታት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የወጡ(የሰረጹ) ስለሆኑና እንደ ምሳሌያዊ ባሕርይና ምስሌያዊ ፍጥረት ከመኖር ወደ አለመኖር ማለፍ ስለማይችሉ ብቻ ነዉ የራሳቸዉን ህልዉና እንዳያዉቁና እንዳያስተዉሉ ተደርጎ በብርሃናዊ ባሕርይ በአንድ ቦታ እንዲሸፈኑ ተደርጎ እንዲኖሩ የሚደረገዉ።

ከላይ እንደተገለጸዉ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ የሚኖረዉ ቦታ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ አማናዊ ሕዋና ዓመፀኞች መናፍስትና ነፍሳት በነጥብ ቦታ የራሳቸዉን ህልዉና አተዉ የሚኖሩበት ነጥብ ቦታ ብቻ ነዉ። ምሳሌያዊ ፍጥረት(በሥጋዊ ዐይናችን የምናየዉ ነገር ሁሉ) በዓለም ፍጻሜ ዘመን ከመኖር ወደ አለመኖር እንደሚያልፍ ሁሉ፣ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላም ፍጥረት የሚባለዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ(በሥጋዊ ዐይናችን የማናያቸዉ ነገሮች ሁሉ) ሙሉ በሙሉ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ። አማናዊ ፍጥረት የሆኑት መናፍስትና ነፍሳት እንደ አማናዊ ባሕርያቸዉ ብቻ እና አማናዊ ፈጣሪያቸዉ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፤ የማያኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸዉ በራሳቸዉ ህልዉና እንዲኖሩ ያደረገዉ፣ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ፣ ሁሉ የእርሱ በእርሱ ለእርሱ የሆነ አምላክ ብቻ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ እንደ አማናዊ ባሕርይዉ ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ። ይህ ነዉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ቃል የሚመላለሱና የሚኖሩ ሰዎች የመጨረሻ እድላቸዉና ክብራቸዉ። ይህን ያስተዋለ! በዉኑ በዚህች ምድር ዉስጥ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ለመመላለስና ለመኖር ይፈልጋልን!? ይመኛልን!? በኃጢአት የወደቀ ሰዉ ለንስሐና ለይቅርታ የአንድ ቀን ቀጠሮ ይስጣልን!? ብቻ የዉስጤን ለመግልጽ አንደበትና ቃላት ስለሚያጥረኝ ዝም ማለቱን መርጫለሁ።

***ጠያቂዉ አገልጋይ***: የዲያብሎስ(የሰይጣናት) ከፍተኛ አገልጋዮችና ከፍተኛ ባለሟሎች የሆኑት ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ መጽሐፍ ገላጮች፣ ሟርተኞች፣ የመሳሰሉት ስለ ወደፊቱ ሆነ ስላለፈዉ ነገር ማወቅና መናገር ይችላሉ ወይ? የሚችሉ ከሆነ ያንን እዉቀት እንዴት ነዉ ሊያገኙ የሚችሉት?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: መታወቅ ያለበት ነገር እግዚአብሔር ከፈለገ እንኳን በአርአያዉ የፈጠራቸዉን ሕያዉ ፍጥረታት የሆኑ ሰዎችን አይደለም ሕያዋን ያልሆኑትን ደማዊት ነፍስ ያላቸዉን እንስሳትና ሕይወት የሌላቸዉን ግዑዝ ፍጥረታትን ማናገር ይችላል:: ለዚህም ነዉ በብሉይ ዘመን የበለዐምን አህያ ያነገረዉ፤ እንዲሁም በሐዲስ ዘመን ግብዞቹን ጸሕፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናትን ለማሳፈር ድንጋዮች ድምፅ አሰምተዉ እንዲያመሰግኑት ያስደረገዉ:: ሌላዉ መታወቅ ያለበት አዳምና ሔዋን በገነት እያሉ እግዚአብሔር የነገራቸዉን ቃልና ምስጢር መጠበቅ ሲገባቸዉ፤ ዲያብሎስ ለመፈተን ወደ እነሱ በሄደ ወቅትና አኗኗራቸዉን በጠየቃቸዉ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገራቸዉን ቃልና ምስጢር እንዳለ ዘክዝከዉ በመናገራቸዉና አትብሉ የተባሉትን ፍሬ በመብላታቸዉ ምክንያት ወደ እዚህች ጎስቋላ፣ የሰይጣናት መኖሪያና መቀጫ ምድር ዉስጥ ሲገቡ እነሱም ሆኑ ልጆቻቸዉ ገበናቸዉ ሁሉ በሰይጣናት እንዲታወቅ ፈርዶባቸዋል:: በዚህም ምክንያት ሰይጣናት ሰዎች የሰሩትንና የተናገሩትን ብቻ አይደለም እያሰቡ ያሉትን ጭምር ያዉቃሉ:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር ለማንም ሰዉ መናገር ሆነ መግለጽ አይችሉም::

ስለወደፊቱ የሚያዉቀዉ ደግሞ አንዱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻና እርሱ እንዲያዉቁ የፈቀደላቸዉ ቅዱሳንና እንዲሁም የመረጣቸዉ ሰዎች ብቻ ናቸዉ:: ሰይጣናት ሆኑ የእነሱ ባሪያዎች የሆኑት ጠንቋዮችና መጽሐፍ ገላጮች ስለወደፊቱ ሊያዉቁ የሚችሉት እንደማንኛዉም ሰዉ ያለዉን ተጨባጭ ሁኔታ በመመልከት የወደፊቱን ከመገመት ዉጭ በእርግጠኝነት የሚሆነዉን አያዉቁም:: ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር በሕልም ወይንም በራእይ ወይንም በድምፅ ለባለሟሎቹና ለእዉነተኛ አገልጋዮቹ ለወደፊቱ የሚሆነዉን ሲገልጽላቸዉ በመጀመሪያ ተመልካቾቹና አዳማጮቹ እነዚያ የእግዚአብሔር ምርጦች የሆኑ ሰዎች ቢሆኑም፤ በሕሊናቸዉ ያ የሚታየዉና የሚደመጠዉ ከተገለጸና ከተንጸባረቀ በኋላ ሰይጣናት ከሰዉ ዘሮች ሕሊናና አካል ለዐይን ቅጽበት ያህል ስለማይለዩ ያ የተገለጸዉንና የተደመጠዉን ሊያዉቁ ይችላሉ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ካልፈቀደላቸዉ በስተቀር ለማንም መግለጽ ሆነ ማሳወቅ አይችሉም::

በመሆኑም ጠንቋዮች ሆኑ መጽሐፍ ገላጮች እንዲሁም ሟርተኞች ስላለፈዉ ሆነ ስለወደፊቱ አንዳች ማወቅ አይችሉም:: ነገር ግን የሰይጣናት ሙሉ በሙሉ ማደሪያ የሆኑ ጠንቋዮች ሆኑ ማርተኞች፣ ልክ እግዚአብሔር ሲፈቅድ በአገልጋዮቹ አማካይነት በጸሎትን በጠበል በሰዎች ላይ ያደሩ ሰይጣናት በእሳት ሰንሰለት ሲታሰሩ የተደረገዉንና ያደረጉትን እንደሚገልጹ ሁሉ፤ የሰይጣን አገልጋዮች የሆኑትም ሰይጣን ከተፈቀደለት ብቻ በእነሱ ላይ አድሮ ያለፈዉን ሊናገር ይችላል:: ይህ የሚያሳየን የሰይጣን አገልጋዮች ያለፈዉን በመናገራቸዉ ከእግዚአብሔር እንደሆኑ የማያስቆጥርን ሰይጣናት እኛን ወደ እነሱ አገልግሎት ለማምጣትና ከእግዚአብሔር ጋር ለማጣላት የሚያመጡት

ፈተና መሆኑን ነዉ:: ስለዚህ የጠንቋዮች ሆነ የአስማተኞችን እንዲሁም የመተተኞችንና የመጽሐፍ ገላጮችን ተግባር ሆነ ንግግር የሰይጣናት መሆኑን አዉቀን ከዚህ ዓመፃ ተግባርና ሕይወት ሙሉ በሙሉ መለየት ይኖርብናል:: እምነታችንም በተአምራትና ምልክት መሆን የለበትም:: እግዚአብሔር የሚወደዉ በእዉነትና በመንፈስ ሲመለክ ብቻ ነዉ:: ተአምራትና ምልክት እኛን ለማጽናት ነዉ የሚጠቅመን እንጂ ሕይወት ሆኖን ለሰማያዊ መንግሥትና ለሕያዉነት ሕይወትና ድኅነት አያበቃንም::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: እንደሚታወቀዉ በዓለም ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሃይማኖቶችና እምነቶች አሉ:: ከሁሉ በላይ ደግሞ በክርስትና ስም የሚጠሩ እጅግ ይበዛሉ:: አንድ አምላክ ካለና ክርስትናን የመሰረተዉ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ከሆነ ለምን የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች በዓለማችን ሊፈጠሩ ቻሉ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: ማንም ሰዉ ሊያዉቀዉ የሚገባዉ ይህች በግንባራችን ፊት ለፊት በአንጎላችን ዉስጥ ያለችዉ በተለምዶ ሕሊና ወይንም አእምሮ የምንላት ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ባሕርይ የወጣች(የሰረጸች) ሕያዉ ፍጥረት ስለሆነች፤ በምድራዊ ዘመኗ ራሷን ስታዉቅና ማመዛዘንና ማገናዘብ ስትጀምር ከእርሷ በላይ የሆነዉን ያስገኛትን(የፈጠራትን) አምላክ ወይንም ኃይል ትፈልጋለች:: ከመጀመሪያዉ የወለዷት ወላጆች ሃይማኖት ወይንም እምነት ካላቸዉ አምልኮታቸዉን በዚያዉ ትቀጥላለች:: እያንዳንዱ ሰዉ ነገሮችን ማመዛዘንና ማገናዘብ ሲጀምር የሚያመልከዉን አምላክ ሆነ ሌላ ባዕድ አምልኮ፣ እግዚአብሔር በሰጠዉ ነጻ ሕሊናና ፈቃድ መመርመርና ወደ እዉነት የመምጣት ኃላፊነትና የዉዴታ ግዴታ አለበት:: ምክንያቱም ወደ እዉነት የሚመራዉ መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ እዉነትን ለሚፈልጉ ሕያዋን ፍጥረታት ወደ እዉነት ይመራቸዋልና:: በተቃራኒ ደግሞ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ የሚመሩትን የዲያብሎስ መንፈስ ወደ ክህደትና ዓመፃ እንዲሁም ርኩሰት ሕይወት ይመራቸዋል::

በዓለም ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ሊፈጠሩ የቻሉት በዚሁ ሰዎች በነጻ ሕሊናቸዉ በሚፈቅዱለት የመንፈስ ቅዱስ ተቃራኒ በሆነዉ በዲያብሎስ መንፈስ አማካይነት ነዉ:: እጅግ ብዙ ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጡት ለሥጋና ለደም ስሜታቸዉ በመሆኑ የዲያብሎስ መንፈስ እንደሚፈልገዉ ይመራቸዋል፤ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ተገዢና ባሪያ ያደርጋቸዋል:: በመጨረሻም ለሞትና ለከፋዉ ፍርድ ያቀርባቸዋል:: እጅግ ጥቂቶች ደግሞ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ በመታመን ከአዳምና ከሔዋን ተከትለዉ በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ በእዉነትና በመንፈስ አምላካቸዉን ያመልኩ ነበር:: አምልኮዋቸዉንም በተለያየ መንገድ ይገልጹ ነበር:: ኃጢአት ሲፈጽሙም በሕሊና ጸጸትና በተለያየ መንገድ አምላካቸዉን ምሕረትና ይቅርታ ይጠይቁ ነበር:: ከዚያም አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩ 4000 ሺህ ዘመን ገደማ፤ እግዚአብሔር በእዉነትና በመንፈስ በኪዳነ ልቦና አምልኮትን መፈጸል ላልቻሉትና ልባቸዉ ወደ ተለያየ ጣዖት አምልኮ ላመዘኑና የሚታይ ነገር ለፈለጉ ሰዎች ሲል በኪዳነ ልቦና ይጠበቁ የነበሩትን ትእዛዛት በኪዳነ ኦሪትን(በሕገ

አራት) አማካይነት በሚታይና በሚዳሰስ ጽላት ላይ ጽፎ ሰጣቸዉ፡፡ በዚህም ትዉልዱ አምላኩን በእዉነትና በሥርዓት ሊያመልከዉ አልቻለም፡፡

በመጨረሻም የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ ማለትም አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩ 5500 ዘመን በኋላ እዉነተኛዉ አምላክ ባሕርይዉን ወስኖ ፍጹም ሰዉና ፍጹም አምላክ ሆኖ በዓለም በመገለጽ ማንነቱን ለትዉልዱ አሳወቀ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸዉና ምን ማደረግ እንደሌለባቸዉ አስተማረ፡፡ እዉነተኛ አምላክነቱን የሚገልጹ ተአምራትንና ፈዉስ በማድረግ፣ እንዲሁም ፍቅሩንና ምሕረቱን ለማሳየት የተለያዩ ፈተናዎችንና መከራዎችን እስከ መስቀል ድረስ በመቀበል፣ ከዚያም ማንም በሥጋዉ ሞቶ እንደማይቀር ሕያዉ ፍጥረት መሆኑን እንዲያዉቅና እንዲያምን በሥጋዉ ሞቶ በሦስተኛዉ ቀን በመነሳት ትንሣኤን አሳይቶ፤ በመጨረሻም እያንዳንዱ ሰዉ ከሥጋ ሞት በኋላ መኖሪያዉ ወደ ሌላ ዓለም ዉስጥ መሆኑን እንዲያዉቅና እንዲያምን ወደ ሰማይ በማረግ አሳይቶናል፡፡ በመዋዕለ ሥጋዌዉም ክርስትናን በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ወይንም በኪዳና ምሕረት(በሕገ ወንጌል) መስርቶ ለትዉልዱ የድኅነትን የሕይወት መንገድ አዘጋጅቷል፡፡

ታዲያ እግዚአብሔር ለሕያዉ ፍጥረታቱ ሰዎች ፍቅሩንና የቸርነቱን ስራ እስከ እዚህ ድረስ ቢገልጽም ሕያዋን ፍጥረታቱ ግን የእርሱን ስራ ሊያስተዉሉና ሊረዱ እንዲሁም በሚፈልገዉ አምልኮ ዉስጥ ሊመላለሱ አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ሃይማኖቶችና እምነቶች በዓለም ላይ ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር ትዉልዱ ወደ እዉነተኛ አምልኮ እንዲመለስና በእዉነትና በመንፈስ አምልከዉት በማያልፈዉ መንግሥቱ ዉስጥ ሕያዉ ሆነዉ እንዲኖሩ ለማድረግ አስቀድሞ በሥጋ በምድር ዉስጥ ሰዉ ሆኖ ሲገለጽ በተናገረዉ ሊቀርና ሊሻሻል በማይችለዉ ቃል ኪዳን፣ ይኸዉም በዮሐንስ ወንጌል በምዕረፍ 10 ቁጥር 16 ላይ «<u>ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፣አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛዉም አንድ</u>» ብላል፡፡

እንዲሁም በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 27 ቁጥር 24 ላይ «<u>ባሪያዬም ዳዊት ንጉሥ ይሆናቸዋል፤ ለሁሉም አንድ እረኛ ይሆንላቸዋል በፍርዴም ይሄዳሉ ትእዛዜንም ይጠብቃሉ ያደርጉማል፡፡ማደሪያዬም በላያቸዉ ላይ ይሆናል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛ ል፡፡</u>»

ከዚህ በተጨማሪ በኢሳይያስ ትንቢት ምዕራፍ24÷ ከቁጥር 1እስከ7 «እነሆ ÷ እግዚአብሔር ምድርን ባዶ ያደርጋታል÷ ባድማም ያደርጋታል÷ ይገለብጣትማል÷ በእርስዋም የተቀመጡትን ይበትናል፡፡ እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ÷ እንደ ባሪያዉም እንዲሁ ጌታዉ÷ እንደ ባሪያይቱም እንዲሁ እመቤትዋ÷ እንደሚገዛም እንዲሁ የሚሸጠዉ÷ እንደ አበዳሪዉም እንዲሁ ተበዳሪዉ ÷ እንደ ዕዳ አስከፋዩም እንዲሁ ዕዳ ከፋዩ ይሆናል፡፡

ምድር መፈታትን ትፈታለች፥ ፈጽማም ትበላሻለች፤ እግዚአብሔር ይህን ቃል ተናግሮአልና። ምድርም አለቀሰች ረገፈችም ዓለም ደከመች ረገፈችም፤ የምድርም ሕዝብ ታላላቆች ደከሙ። ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች፥ ሕጉን ተላልፈዋልና፥ ሥርዓቱንም ለዉጠዋልና፥ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና። ስለዚህ መርገም ምድርን ትበላለች በእርሷም የተቀመጡ ይቀጣሉ ስለዚህ የምድር ሰዎች ይቃጠላሉ ጥቂት ሰዎችም ይቀራሉ።»

« በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸዉማለች፥ ለዘላለም ትቆማለች። ደንጋዩም እጅ ሳይነካዉ ከተራራ ተፈንቅሎ ብረቱንና ናሱን ሸክላዉንም ብሩን ወርቁን ሲፈጨዉ እንዳየህ፥ እንዲሁ ከዚህ በኋላ የሚሆነዉን ታላቁ አምላክ ለንጉሡ አስታዉቆታል ሕልሙም እዉነተኛ ፍቺዉም የታመነ ነዉ።» ዳን.2: 44-45

« በልብዋ ፡- ንግሥት ሆኜ እቀመጣለሁ ባልቴትም አልሆንም ኀዘንንም ከቶ አላይም ስላለች፥ ስላለች በአንድ ቀን ሞትና ኀዘን ራብም የሆኑ መቅሰፍቶችዋ ይመጣሉ በእሳትም ትቃጠላለች፤ የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነዉና።» ዮሐንስ ራእይ 18: 7-8

«ሰባተኛዉም መልአክ ነፋ በሰማይም -የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ። በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኖቻቸዉ የተቀመጡ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በግንባራቸዉ ተደፍተዉ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፡- ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግናሃለን አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸዉን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።» ዮሐንስ ራእይ 12: 15እስከ18

«የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመዉንም እባብ ዘንዶዉን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለዉን ያዘዉ፥ ሺህ ዓመትም አሰረዉ፥ ወደ ጥልቅም ጣለዉ አሕዛብንም ወደፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።» ዮሐንስ ራእይ 20: 1 እስከ 3

«በዘመኑም ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፥ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፥ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ። ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ ሄደዉ -ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንዉጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በጎዳናዉም እንሄዳለን ይላሉ። በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፥ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል ሰይፋቸዉንም ማረሻ፥ ጦራቸዉንም

***ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፤ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም፡፡»*** ኢሳይያስ. 2፥2-4

«እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና የቀደሙትም አይታሰቡም ወደ ልብም አይገቡም፡፡ ነገር ግን በፈጠርሁት ደስ ይበላችሁ ለዘላለምም ሐሤት አድርጉ እነሆ ኢየሩሳሌምን ለሐሤት ሕዝብዋንም ለደስታ እፈጥራለሁና፡፡ እኔም በኢየሩሳሌም ሐሤት አደርጋለሁ በሕዝቤም ደስ ይለኛል ከዚያም ወዲያ የልቅሶ ድምፅና የዋይታ ድምፅ አይሰማባትም፡፡ ከዚያም ወዲያ ጥቂት ዘመን ብቻ የሚኖር ሕፃን ወይም ዕድሜዉን ያልፈጸመ ሽማግሌ አይገኝም ጐልማሳዉ የመቶ ዓመት ሆኖት ይሞታልና ኃጢአተኛዉም የመቶ ዓመት ሆኖት የተረገመ ይሆናልና፡፡ ቤቶችንም ይሠራሉ ይቀመጡባቸዉማል ወይኑንም ይተክላሉ ፍሬዉንም ይበላሉ፡፡ ሌላ እንዲቀመጥበት አይሠሩም ሌላም እንዲበላዉ አይተክሉም የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ ይሆናልና እኔም የመረጥኋቸዉ በእጃቸዉ ሥራ ረጅም ዘመን ደስ ይላቸዋልና፡፡ እነርሱ ከነልጆቻቸዉ የእግዚአብሔር ቡሩካን ዘር ናቸዉና በከንቱ አይደክሙም ለጥፋትም አይወልዱም፡፡ እንዲህም ይሆናል ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ፡፡ **ተኵላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል የእባብም መብል ትቢያ ይሆናል**፡፡ በተቀደሰዉ ተራራዬ ሁሉ አይጐዱም አያጠፉምም ይላል እግዚአብሔር፡፡» ኢሳይያስ. 65፥17እስከ25

«በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈዉ ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፣ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፡፡ በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸዉም አሳልፈዉ ይሰጣጣሉ እርስ በእርሳቸዉም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነብያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ በዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል፡፡ **ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፣ በዚያን ጊዜ መጨረሻዉ ይመጣል**፡፡» *ማቴዎስ*24፥9እስከ14

«በፊተኛዉ ትንሣኤ ዕድል ያለዉ ብፁዕና ቅዱስ ነዉ፤ ሁለተኛዉ ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለዉም፥ ዳሩ ግን **የእግዚአብሔና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ**፡፡»ዮሐንስ ራእይ 20፥ 6

ከላይ የተገለጹት ትንቢታት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚሆንበት ሰዓቱ ደርሷልና ባለማወቅ እርሱ ከመሰረተዉ የሕይወት መንገድ ዉጭ ያሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመፍራትና በማምለክ ያሉ ከእዉነተኛዉ በረት ዉጭ የሆኑትን በጎቹን ወደ እዉነተኛ በረት ዉስጥ ያስገባቸዋል፡፡ እነርሱም ድምፁን ስለሚሰሙ ለመግባት አይቸገሩም፡፡ ከዚያ ዉጭ የሆኑት ሐሰተኛ አምላኮችንና ሃይማኖቶችን እንዲሁም እምነቶችን ሊያጋልጣቸዉና ሊያጠፉቸዉ በመወሰኑ ምክንያት፤ ይኸዉ ትዉልዱ ወደ ሙሉ እዉነት እንዲመጣ በተለያዩ አገልጋዮቹና መልእክተኞቹ አማካይነት የተደበቁና ትዉልዱ ያላስተዋላቸዉ እዉነታዎችና ምስጢራት እንዲሁም እየሆነ ያለዉንና ወደፊትም የሚሆነዉን በግልጽ እንዲታወቅ አደረገ፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር በምድር የሚዘረጋዉ መንግሥቱ ማለትም ቤተሕዝቡ፥

ቤተክህነቱ፥ ቤተምልክናዉ ተዋሕዶ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበት ሥርዓት፤ ቅዱሱን ኪዳን ከዓለም መፈጠር መጀመሪያ ጀምረዉ እስከ አሁን ድረስ በጠበቁ በኢትዮጵያዉያንና በተመረጠችዉ አገር ኢትዮጵያ ተዘርግቶ እስከ ለዓለም ፍጻሜ ድረስ ኢትዮጵያዉያንና ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር እንደራሴነት እንዲያገለግሉና እንድታገለግል ተመረጠች:: በዚህም ኢትዮጵያዉያን በተለየ ሁኔታ ልንደሰትና ራሳችንንም በእዉነተኛ ንሰሐ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ልናበቃ ይገባል::

**ወደ ጥያቄዉ መላሽ ስገባ:** በዓለም ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ቢኖሩም እጅግ ብዙዎቹ ሰዎች በሥጋና ደም ስሜታቸዉ በመመራትና ዲያብሎስ ሕሊናቸዉን በመጠቀም የፈጠራቸዉና ለእግዚአብሔር ሕያዉ መንግሥት አንዳች የማያበቁ ናቸዉ:: ማንኛዉም ሰዉ ቀና ካሰበ፣ መልካም ከሰራ፣ ለሕሊናዉ ከታመነ፣ እምነት ይኑረዉ አይኑረዉ እግዚአብሔር አንዳች አድሎ ሳያደርግ የሕሊና ሰላምና እርካታ ይሰጠዋል:: እንዲሁም በምድራዊ ሕይወቱ የተለያየ በረከትና ጸጋ ይሰጠዋል:: ነገር ግን በነጻ ሕሊናዉና ፈቃድ ተመርቶ ሙሉ  እዉነትን ካልፈለገና እራሱንም ለሰማያዊ መንግሥት ለማብቃት ካለዘጋጀ በስተቀር እግዚአብሔር ነጻነቱን ተጋፍቶ በግድ በእዉነተኛ አምልኮ ዉስጥ እንዲገባና እንዲመላለስ አያደርገዉም:: ምክንቱም እግዚአብሔር በባሕርይዉ እያንዳንዱ ሰዉ በዚህች የዐይን ቅጽበት እድሜ በማትሞላዉ ምድራዊ ዘመኑ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ እዉነትን እንዲፈልግና በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልከዉ ነዉ የሚፈልገዉ::

በብሉይ ዘመን ያሉ የተለያዩ እምነቶች ስንመለከት የመጀመሪያዉ የሰዉ ዘሮቸ እምነት የአዳምና የሔዋን እምነት ነዉ:: ይህም በነጻ ሕሊናቸዉ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ በእዉነትና በመንፈስ የሚያመልኩት ነዉ:: በሥጋ በዚህች ምድር ላይ ከተገለጹም በኋላ በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) እየተመሩ ሲፈጽሙት የነበረዉ አምልኮትና እምነት ነዉ:: ይህ እምነትና አምልኮ በኢትዮጵያዉያን ዘንድ እስከ ኪዳነ ኦሪት(ሕገ ኦሪት) ድረስ ሲቀጥል ቆይቶ፤ እግዚአብሔር በታላቁ ነቢይ በሙሴ አማካይነት ለእስራኤላዉያን ኪዳና ኦሪትን(ሕገ ኦሪትን) ሲሰጥ ኢትዮጵያዉያንም ኪዳነ ኦሪትን በንግሥታቸዉ ማክዳ (አዜብ)(ሳባ)  አማካይነት እንዲቀበሉና በኪዳነ ልቦና የሚፈጽሙትን አምልኮና ሥርዓት በኪዳነ ኦሪት እንዲታደስ አድርገዉ በኪዳነ ኦሪት አምልኮና ሥርዓት እስከ ክርስቶስ መወለድና እርገት ድረስ ሲፈጽሙ ቆይተዉዋል:: ከዚያም እርሱ የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የሆነዉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በሥጋ ማርያም ተገልጾ ሁሉን ፈጽሞ ወደ ሰማይ ባረገበት ዘመን በ34 ዓ.ም የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬ ባለሟልና ተጠሪ የሆነዉ ጃንደረባዉ አበሜሌክ(ባኮስ) የተለመደዉን የአምልኮ ሥርዓት ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም በሄደበት ወቅት እግዚአብሔር ሐዋርያዉን ፊሊጶስን በመላክ እንዲገናኘዉ አድርጎ ክርስትናን ተቀብሎ በአገሩ በማስፋፋት በኪዳነ ኦሪት ሲፈጸም የነበረዉ አምልኮና ሥርዓት በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ታድሶና ተደምድሞ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት (ክርስትና) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመስፋፋት እስከ አሁን ድረስ አምልኮቱና ሥርዓቱ ተጠብቆ ይገኛል::

ይህም የሚያሳየን በአዳምና ሔዋን ይመለክ የነበረዉ፣ ከዚያም በተለያየ ዘመን በአበዉ አባቶችና በእመዉ እናቶች ሲመለክ የነበረዉ፣ በዉኃ ጥፋት ዘመንም በኖኅና በቤተሰቡ ሲመለክ

የነበረዉ፣ በመልከ ጼዴቅና በአብርሃም ይመለክ የነበረዉ፣ በካህኑ ዮቶርና በነብዩ ሙሴ ከነቤተሰባቸዉ ይመለክ የነበረዉ፣ በንጉሥ ዳዊትና በልጁ በጠቢቡ ሰለሞን እንዲሁም በንግሥት ማክዳ (አዜብ)(ሳባ) በሕዝባቸዉ ጭምር ይመለክ የነበረዉ፣ በነቢያትና በመምህራን ይመለክ የነበረዉ፣ ያዉ እርሱ ነዉ ከእመቤታችን ከቅድስተ ቅዱሳን ከንጽህይተ ንጹሃን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በመወለድ በምድር ተገልጾ ክርስትናን የመሰረተዉና ትዉልዱም አምላክነቱን አምኖ ትእዛዙን በመፈጸም እንደ ቃሉ ሆነዉ እንዲገኙ ያስተማረዉ:: በዚሁም መሰረት ሐዋርያትና ደቀመዛሙርቱ አምነዉበት ለዓለም ምስክርነትን ሊሰጡና ክርስትናን በአራቱም ማዕዘን ሊያስፋፉ ችለዋል:: አበዉ ሐዋርያትም የእነሱን ፈለግ ተከትለዉ ክርስትናን አስፋፍተዋል:: ከዚያም ሰማዕታት በታላቅ ተጋድሎ ክርስትናን አስጠብቀዋል::

በኋላም በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ክርስቲያኖች ነጻነትን አግኝተዉ በ325 ዓ.ም ገደማ በክርስቶስ ላይ የክህደት ትምህርት ያመጣዉንና «ወልድ ፍጡር ነዉ» ያለዉን አርዮስን፣ እዉነተኛ መምህራንና ሊቃዉንት በማዉገዝ የሃይማኖት ጸሎት በማዘጋጀት ክርስቶስ የመሰረተዉን ሃይማኖትና እምነት አስጠብቀዋል:: ከዚያም በ381 ዓ.ም ገደማ «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሳል» የሚል ትምህርት ያመጣዉን መቅዶንዮስን በማዉገዝ የመጀመሪያዉን ሃይማኖትና እምነት አስጠብቀዋል:: በ431 ዓ.ም ገደማ «እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መባል የለባትም» ያለዉን በጵጵስና ደረጃ ላይ የነበረዉ ንስጥሮስን በማዉገዝ የመጀመሪያዉን ሃይማኖትና እምነት አስጠብቀዋል:: በ451 ዓ.ም የሥጋና የደም ስሜታቸዉ ያየለባቸዉ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት መሪዎች የበላይ ለመሆንና የራሳቸዉን ጥቅም ብቻ በማስቀደም እንዲሁም እንደ አሁን ዘመን እንደሚታየዉ እርስ በእርስ በመጠላለፍ፣ አንድ ሃይማኖት አንድ እምነት አንድ ቤተክርስቲያን የነበረዉን «አምላክ ሰዉ ሆነ ሰዉ አምላክ ሆነ፤ በተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ» የሚለዉን ሃይማኖትና እምነት ወደ ሁለት ባሕርይ በመለወጥና የተለያየ መከራና ፈተና የተቀበለዉን፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉን፣ በሥጋዉ የሞተዉን፣ በሦስተኛ ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሳዉን፣ በኋላም ወደ ሰማይ ያረገዉን እግዚአብሔር፤ ትዉልዱ እንዲጠራጠረዉ የሚያደርገዉን የሁለት ባሕርይ እምነት ሊፈጠር ቻለ:: ነገር ግን «ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል በአንድ አካል ከሁለት ባሕርይ በአንድ ባሕርይ ነዉ ተገልጾ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ የሆነዉ» በሚለዉ የመጀመሪያ እምነት የኢትዮጵያ፣ የግብፅ፣ የአርመን ፣የሶርያ፣ የሕንድ አብያተ ክርስቲያናት ይዘዉ ሲቀጥሉና የመጀመሪዉን ሃይማኖትና እምነት ሲጠብቁ፤ ሌሎቹ «በሁለት ባሕርይ» በሚለዉ እምነትና አስተሳሰብ እንዲሁም በሂደት ደግሞ ቀደም ሲል እዉነተኛ መምህራንና ሊቃዉንት «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ነዉ የሰረጸዉ» ብለዉ ያስተማሩትን ትምህርት በመለወጥ «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ነዉ የሰረጸዉ» በማለት ክፍፍሉን አሰፉት::

በመጨረሻም በ1054 ዓ.ም ገደማ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር የበላይነትን ለመያዝ በሥጋና ደም ስሜት ትግል ፈጥረዉ «ኦርቶዶክስና ካቶሊክ» በሚል ስያሜ እርስ በእርሳቸዉ እንደገና ተከፋፈሉ:: በ1521 ዓ.ም ገደማ አሁንም በሥጋና ደም ስሜት ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ወንበር የበላይነትና ለግል ጥቅም ሲባል ከካቶሊክ ሃይማኖት የመጀመሪያዉ ተቃዋሚ «መንፈሳዊ» ዓማፂ

ቡድን «ፕሮቴስታንት» በመባል የሚታወቀዉ ድርጅት ተመሰረተ:: በነዚህ «መንፈሳዊ» ዓማፂያን ድርጅት እምነት እርሱ ፍጹም እግዚአብሔር አምላክ የሆነዉ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ» ተብሎ ተካደ፣ ተሰደበ:: የእመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት ተሽሮ ለሕሊና የሚዘገንንና የሚከብድ የማጥላላት ዘመቻ ተደረገባት:: ቅዱሳንና ጻድቃን ተቃለሉ፣ ተሰደቡ:: በመንፈሳዊ ሽፋን ለሥጋ የሚመች የአምልኮ ሥርዓት ተስፋፋ:: ባጠቃላይ አሁን በሺዎች ለሚቆጠሩ የፕሮቴስታን ድርጅቶች መፈጠር መሰረት ተጣለ::

ከላይ ባጭሩ እንደተገለጸዉ የክርስትና ሃይማኖትና እምነት ሊለያይ የቻለዉ ግለሰቦችና ቡድኖች በሥጋና ደም ስሜታቸዉ በመመራት በዚህ ስሜታቸዉ ደግሞ የዲያብሎስ መንፈስ በመግባትና በመቆጣጠር ወደ ጥርጥርና ክህደት ስላስገባቸዉ ነዉ:: እንዲሁም ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ወንበር የበላይነትና ለግል ጥቅም ሲሉ ሃይማኖትንና እምነትን ሽፋን አድርገዉ የራሳቸዉን የግልና የቡድን ዓለማ ለማሳካት ሲሉ ነዉ ክፍፍልንና መለያየትን ያመጡት:: በዚህ ክፍፍልና መለያየት ምክንያት ደግሞ ከእነሱ በበለጠ ሁኔታ በሥጋና በደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱ ትዉልዶች በመፈጠራቸዉ ምክንያት የዲያብሎስ መንፈስ ይህንኑ ስሜታቸዉን በመጠቀም ከ18ተኛዉ ክፍለ ዘመን ወዲህ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ወንበር እንዲለያዩ በማድረግ ዲያብሎስ ሥጋዊዉን ወንበር ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠርና ለእርሱ ሙሉ አገልግሎት በማዋል አሁን ላለዉ የመጨረሻ ክህደትና ዓመፃ እንዲሁም ርኩሰት ሕይወትና ተግባር አዉሎታል:: በዚህም ምክንያት በሥጋዊዉ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ እንደ ልቡ የሚሆኑትን ፖለቲከኞችን በማዘጋጀትና በመመልመል ፈቃዱን በአራቱም ማዕዘን እያስፈጸመ ይገኛል::

አሁን ግን እግዚአብሔር ስለተመረጡት ሲል ይህ የባለጊዜነት ዘመኑን ሊሽረዉ የወሰነና ሥጋዊዉን ወንበርና መንፈሳዊዉን ወንበር ተዋሕዶ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ይሆናል:: ለዚህ ዉሳኔዉና ተግባሩ እንቅፋት የሚሆኑትንና በእዉነተኛ ንስሐ አልመለስ የሚሉትን፣ ሕሊናቸዉን ያደነደኑ የዓመፃ ልጆችንና የእነሱን ተባባሪዎችን ከምድር በተለያየ ቁጣዉ የሚያጸዳቸዉ (የሚጠርጋቸዉ) ይሆናል:: ከዚያም ቤተሕዝቡን፣ ቤተክህነቱን፣ ቤተ መንግሥቱን በአንድ ላይ በማዋሐድ በመንፈስ ቅዱስ እንዲመራ ያደርጋል:: ስለዚህ ለምድራዊዉ ሆነ ለሰማያዊዉ የእግዚአብሔር መንግሥት ለመብቃት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀዉ ራሳችንን ለእዉነተኛ ንስሐ ማብቃትና በእዉነተኛ ሕይወት መመላለስ ብቻ ነዉ:: ከዚያ ዉጭ የራሳችንን ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ብናደርግና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስቀረት ወይንም ለማዘግየት ብንሞክር አይቀጡ አቀጣት ተቀተን፣ ተዋርደን፣ ፍዳችንን ተቀብለን ነዉ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ የምንሄደዉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የወሰነዉንና ያቀደዉን ማንም ሊሽርና ሊለዉጥ እንዲሁም ሊያስቀር አይችልምና:: በመሆኑም አቅማችንንና ተራነታችንን አዉቀን እጃችንን ለእግዚአብሔር መስጠትና ለፈቃዱ መሰለፍ ነዉ የሚጠበቅብን እንጂ ከእርሱ ፈቃድ በተቃራኒ ብንቆምና ብንላተም የምንጎዳዉ እኛዉ ነን::

ከክርስትና እምነት ዉጭ ያሉ ሃይማኖቶችና እምነቶች በብሉይ ዘመን በተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች የተፈጠሩ፤ አሁን ባለነዉ ዘመንም በተለይ በእስያ አህጉር ዉስጥ ባሉ ሕዝቦች ዘንድ

የሚታመኑና አምልኮ የሚፈጸምባቸዉ ሲሆኑ፤ ከዚህ በተጨማሪ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ አገራትና ሕዝቦች በተለያየ መልክ የሚፈጸሙ የባዕድና የጣዖት አምልኮ አሉ። በሐዲስ ዘመን ከእነዚህ ለየት ብሎ በሃይማኖትና በእምነት ደረጃ የተፈጠረዉና በተለይ በመካከለኛዉ ምስራቅ አገራት በአገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ እያገለገለ ያለዉ የእስልምና እምነት ነዉ። ይህ እምነት ምንም እንኳን በአንድ አምላክ የሚታመንበት ቢሆንም ያ አንድ አምላክ የተባለዉ እዉነተኛ አምላክ ግን በግልጽ ተክዶበታል። ይህ እምነት የተመሰረተዉና የተስፋፋዉ በአንድ ግለሰብና በእርሱ ተከታዮች እንዲሁም የተለያዩ ቡድኖች አማካይነት በስብከት፣ በጦርነት፣ በሰይፍ፣ በመሳሰሉት መንገድ በፈቃደኛነትና በግዳጅ ነዉ። እዉነተኛዉ ክርስቶስ የመሰረተዉ እምነትና ሃይማኖት መስፋፋት ከእስልምና እምነት መስፋፋት መንገድ የሚለየዉ፣ የቀደመዉ ክርስትና ሃይማኖት የተሰፋፋዉ ከመስራቹ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ በሐዋርያት፣ በሰማዕታት፣ በመምህራን፣ በጻድቃን አማካይነት በስብከትና በትምህርት እንዲሁም የተለያየ መከራና ስቃይ በመቀበልና መስዋዕት በመሆን ነዉ እንጂ በማስገደድና በሰይፍ፣ እንዲሁም በጦርነት አልነበረም።

የእስልምና ሃይማኖትና እምነት መስራች የሆነዉ በ570 ዓ.ም ገደማ የተወለደዉና ተከታዮቹ «ነብያችን» የሚሉት በመሃመድ አማካይነት ሲሆን፤ እምነቱም ከተለያዩ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን እምነቶችና አስተምህሮዎች በመዉሰድና በዘመኑ የነበሩት ትዉልዶች ሊቀበሉት በሚችል መንገድ የተቀነባበረ ነዉ። የተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ እንዲጠፉና እንዲወገዱ ያደረገዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም፤ ለሰማያዊ መንግሥት የሚያበቃዉን መሰረታዊ እምነት የሆነዉን የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን ስለማይቀበል፤ በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ዳግም በመንፈስ የመወለድ ጸጋ የሚገኝበትን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅን ስለማይቀበልና ለሕያዉነት ሕይወት የሚያበቃዉንና ኃጢአት መደምሰሻ የሆነዉን መለኮት የተዋሐደዉን የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት የማይቀበል ስለሆነ በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች አማኞቹ ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥትና ገነት ሳይበቁ ቀርተዋል። ምንም እንኳን በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በመልካም ምግባር የሚመላሱ አማኞች በዉስጡ ቢኖሩም፤ ዋናዉ የሕይወት መንገድና ራሱ ሕይወት የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኔዓለምን ከእግዚአብሔርነቱ ባሕርይና ሥልጣን እንዲሁም ክብርና ቅድስና ዝቅ አድርገዉ «አምላክ ሳይሆን የአላህ መልክተኛ ነብይ ነዉ» በማለት በግልጽ ስለካዱትና አምላክነቱን አምነዉ ባለመቀበላቸዉ ምክንያት ከሕይወት መንገድና ከሕያዉነት ሕይወት ሊርቁ ችለዋል። አላስተዋሉትም እንጂ «አላህ» ወይንም የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉ እግዚአብሔር ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ። በመሆኑም አሁን ያለዉ ትዉልድ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመዉረስና ሕያዉ ሆኖ ለመኖር የቀደሙት ወላጆቹ ባለማወቅና ባለማስተዋል እርሱን እዉነተኛ ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደካዱት አስተዉሎና አዉቆ፣ ነገር ግን ባለማወቅና ባለማስተዋል ስለሆነ ፍርዱ እንደሚቀልላቸዉና በመልካም ምግባርና ፈጣሪን በማፍቀርና በመፍራት ያለፉ ደግሞ በማረፊያ ቦታ እድሉን መጠቀም ከቻሉ የመዳን እድል ሊኖራቸዉ እንደሚችል ተገንዝቦ፣ አሁን ግን እግዚአብሔር ሙሉ እዉነታዉ ለዓለም እንዲገለጽ ስላደረገ አሁን ያለዉ ትዉልድ በዚያዉ ክህደቱ ከጸና የከፋ ቅጣት እንደሚጠብቀዉ ተረድቶ፤ እርሱ «አላህ» የተባለዉ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ ከሰማያት ሳይጎል፣ ከአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሳይጎል፣ ዓለምን ከመግቦቱና ከቁጥጥሩ ሳይለይ፣ ባሕርይዉን ብቻ ወስኖ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ የተወለደዉና በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት የተወሰነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሊያምኑና እዉነትን ሊከተሉ ይገባቸዋል:: ምክንያቱም እያወቀና ሳይዉቅ በዓመፃ ሆነ በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት የሚመላለስ ሰዉ፤ የሚፈረድበት ፍርድ እንደዚያዉ ይለያያል:: አዉቆ የሚያምጽ፣ የሚክድ፣ የሚረክስ ሰዉ እጅግ ሊቋቋመዉ የማይችለዉ የቅጣት ፍርድ ነዉ የሚፈረድበት:: ባለማወቅ የሚያምጽ፣ የሚክድ፣ የሚረክስ፣ ከእዉነተኛዉ ከእግዚአብሔር ፍርድ ባያመልጥም ፍርዱና ቅጣቱ ይቀልለታል::

እዚህ ላይ እያንዳንዱን የእምነቱን ተከታይ የምመክረዉ መጾሙ፣ መጸለዩ፣ መስገዱ፣ ማመስገኑ፣ ምጽዋት ማድረጉ፣ ለሃይማኖት መቅናቱ፣ ፈጣሪን መዉደዱ፣ መልካም ምግባር መያዙ የሚደገፍና የሚበረታታ ሲሆን፤ አምልኮቱን ግን በእዉነትና በመንፈስ እንዲሁም በእዉነተኛ አምልኮ ዉስጥ ሊፈጸም ይገባዋል:: ምክንያቱም በምድር በምናሳየዉ ከባዕድና ከጣዖት አምልኮ ዉጭ በሚፈጸም አምልኮና መልካም ምግባር እግዚአብሔር ምንም አድሎና መለያየት ሳያደርግ የሕሊና ሰላም፣ እርካታ፣ በረከት የሚሰጥ ቢሆንም፤ የተለየ ሰማያዊ ጸጋን የሚያድለዉና ለሰማያዊ መንግሥቱ ሊያበቃን የሚችለዉ ደግሞ በእዉነተኛ እምነት ዉስጥ ሆነን በመንፈጽመዉ የእዉነትና የመንፈስ እምልኮ እንዲሁም በምንፈጽዉ መልካም ምግባርና ሕይወት ነዉ:: ስለዚህ በነጻ ሕሊናችንንና ፈቃዳችን ተጠቅመን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታን ልንቀበልና ልንኖርበት ይገባል:: ራሳችንንም ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ ልናድን ይገባል እንጂ የሥጋና የደም ስሜታችንን ልንከተል አይገባም::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: እዚህ ላይ በዓለም ዉስጥ በክርስትናና በኢየሱስ ስም በሺዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች አሉ:: ኢየሱስ ሆነ ክርስትና አንድ አንደሆነ እየታወቀ እንዴት ብዙ ኢየሱሶች ሊመለኩና የተለያየ የክርስትና እምነት ሊፈጠር ቻለ? እነዚህ ሁሉ «በመጽሐፍ ቅዱስ ነዉ የምናምነዉ» ይላሉ :: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ አንድ ሃይማኖት አንድ ጥምቀት አንድ ጌታ አንድ ቤተክርስቲያን ብቻ እንዳለ ነዉ የሚገልጸዉ:: ታዲያ እነዚህ በሺዎች የሚቆጠሩ መንገዶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያስገባሉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በሁላችንም ዘንድ መታወቅ ያለበት ራሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም በምድር ላይ ተገልጾ በተመላለሰበት ዘመን በወቅቱ ለነበሩት ተከታዮቹና ሕዝቦች፣ ብዙ ሐሰተኛ መምህራን፣ ሐሰተኛ ነብያት በስሙ እንደሚመጡና ብዙዎቹንም እንደሚያስቱ አስቀድሞ ስለገለጸልን፤ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በእርሱ ስም መፈጠራቸዉና ብዙዎችም ተሰናክለዉ በዚያ እምነት ዉስጥ መግባታቸዉ ብዙም አያስደንቀንም:: ለተለያየ እምነት መፈጠር ምክንያት የሆነዉ ደግሞ በሥጋና ደም ስሜታችን ስለምንመራ ነዉ እንጂ በነፍሳችን ስሜት በመንፈስ ቅዱስ ብንመራ እንኳን ብዙ እምነቶችና አምላኮች አይደለም ሁለት እምነትና ሁለት አምላክ አይኖርም ነበር:: አሁን እንደሚታየዉ በክርስትና ስም በዓለም ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠር በኢትዮጵያ ደግሞ በአስራና በመቶ የሚቆጠር የእምነት ድርጅት ተፈጥረዋል:: ይህም የሚያሳየዉ የዲያብሎስ መንፈስ ሥጋዊዉን ወንበር ተቆጣጥሮ ፈቃዱን ከማስፈጸሙ በተጨማሪ በመንፈሳዊ ወንበር ደግሞ

በሃይማኖት ሽፋን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ የሕይወትን መንገድና እዉነተኛዉን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ለማጥፋትና ለመደምሰስ ቆርጦ መነሳቱን እንዲሁም በመንፈሳዊ መድረክም ብዙ እንደ ልቡ የሆኑ አገልጋዮች እንዳገኘ ነዉ።

የሚያሳዝነዉ ደግሞ ሁሉም «በመጽሐፍ ቅዱስ ነዉ የምንመራዉ፤ የምናመልከዉም አምላክ አንድ አምላክ ነዉ» በማለት ነዉ አንዱን መጽሐፍ ቅዱስና አንዱን አምላክ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ እንዲሁም በዲያብሎስ መንፈስ ተመርተዉ የተለያየ እምነትና አስተምሮ የፈጠሩትና ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ማርኪያ በማድረግ ራሳቸዉን ለሞት ሞት እያዘጋጁ ያሉት። ምክንያቱም ሕሊናቸዉ አንድ አምላክ አንድ እምነት እንዳለ እየመሰከረባቸዉ፤ ሕሊናቸዉን በማደንደን ነዉ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲፈልጉ «አማለጅ ነዉ፣ ፍጡር ነዉ፣ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባል የለም ራሱ ወልድ(ኢየሱስ) ነዉ በብሉይ ዘመን ሆነ በአዲስ ዘመን መልኩን እየለዋወጠ የመጣዉ፣ እንደ ማንኛዉም ሰዉ ተራ ሰዉ ነዉ...ወዘተ» እያሉ የካዱትና እለት እለት እየሰደቡት፣ እያላገጡበት ያለዉ። አስገራሚዉ ደግሞ «አማላጅ» እያሉ በሚሰድቡትና በሚያላግጡት የተለያዩ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች በሆኑት በጴንጤ ቆስጤ፣ በወንጌላዉያን፣ በሜቶዲስት፣ በካልቪን፣ በሉተራን፣ በመጥምቃዉያን፣ በብርሃነ ወንጌል፣ በቃለ ሕይወት፣ በመሰረት ሕይወት፣ በመቅረዝ፣ በእርገት፣ በአሸናፊዎች፣ በምስጋና፣ በሙሉ ወንጌል፣ በመካነ ኢየሱስ፣ በሬማ፣ በመሰረተ ክርስቶስ፣ የብልጽግና ወንጌል አማኞች፣ የሰላም ወንጌል አማኞች፣ የመማጸኛ ከተማ አማኞች፣ የምስጋና ወንጌል አማኞች፣ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን... ወዘተ የመሳሰሉት የፕሮቴስታንት ክፍልፋይ ድርጅቶችና በአንግሊካን፣ በሰባተኛ ቀን አድቬንትስቶች... በመሳሰሉት ሆነ አንድ ኢየሱስ እያሉ የአብና የመንፈስ ቅዱስን ህልዉና በካዱ «የሐዋርያት ቤተክርስቲያን» በተባሉ፣ እንዲሁም «ኢየሱስ የያሕዌህ የመጀመሪያ ፍጡር ነዉ፤ እኛም የዮሐ ምስክሮች ነን» በማለት ፍጹም ተቃራኒ በሆነ በተለያየ እምነት ዉስጥ ሆነዉ፣ በእነዚህ ተቃራኒ እምነት ባላቸዉ ድርጅቶች ሁሉ የዲያብሎስ መንፈስ የሚፈጥረዉ «ልሳን» የተባለ ትዕይንትና ክስተት ሲታይና «አገልጋይ» የተባለ ሆነ «አማኝ» የተባለ ሲንዘፈዘፍና ሲያጓራ እንዲሁም ሃሌ ሉያ ሬዲማይሳንታራሪያ እያሉ አንዳች ትርጉም የሌለዉን ቋንቋ ሲለፈልፉ እየሰሙ፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተቆጥሮ መታየቱና እንዲሁም አንድም ሰዉ «ተቃራኒ እምነትና አስተምሮ እያለን እንዴት ይህ ምልክት በሁላችን ላይ ይታያል?» በማለት አለመጠየቁ፤ ምን ያህል ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) የእያንዳንዱን የእምነት አገልጋይና አማኝ ሕሊና እንደተቆጣጠሩትና አንዳች እንዳያስተዉልና እንዳይመረምር ሕሊናዉን ዘግተዉ እንዳደነደኑት ነዉ የሚያሳየን። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በ«መዝሙር» ሽፋን ሲዘፍኑበትና ሲጨፍሩበት አንዳች ሕሊናቸዉ የማይከብዳቸዉና የሰይጣናት ምስ(ግብር) የሆነዉን ዘፈንና ዳንኪራ የእግዚአብሔር ስም በሚጠራበት ቦታ ሲቀርብ አንድም ሰዉ «ይህ የአጋንንት ስራ እንዴት በእዉነተኛ አምልኮ ስፍራ በመዝሙር ሽፋን ይቀርባል?» ብሎ የሚጠይቅ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ሽፋን ስለሚከናወን አንድም ሰዉ አምልኮቱ ለዲያብሎስ እንደሆነ አልጠረጠረም። እግዚአብሔርን ያመለከ ለኢየሱስ የዘመረና ያመሰገነ ነዉ የሚመስለዉ። እዉነታዉ ግን ዲያብሎስ ማንነቱን ሰዉሮ በ«ኢየሱስ» ስም እያመለኩትና እያመሰገኑት ነዉ።

እዚህ ላይ በሌላዉ ዓለም ዉስጥ ካሉት የፕሮቴስታንትና መሰል እምነት ተከታዮች ይልቅ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ኢትዮጵያዉያን በዚህ መሰሉ እምነት ዉስጥ መመላለሳቸዉና «ሕይወት ነዉ» ብለዉ መኖራቸዉ እጅግ ያሳዝናል፣ ያስገርማል:: ምክንያቱም ሌላዉ ዓለም መንገዱ ጠፍቶበትና ከወላጆቹ የወረሰዉ እምነት በመሆኑ በዚህ ዓመፃ «እምነት» ዉስጥ ቢመላለስ ብዙም አያስደንቅም:: የሚያሳዝነዉና የሚያስደንቀዉ ግን ከብሉይ ዘመን ጀምሮ በኪዳነ ልቦናና በኪዳነ ኦሪት እንዲሁም ክርስትና በዓለም ሲሰበክ በመጀመሪያ የተቀበለችና ኪዳነ ልቦናና ኪዳነ ኦሪት በመንፈስ ቅዱስ ታድሰዉ ቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ያገኘበትን በኪዳነ ምሕረት እያተመራች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔርነቱ (እንደ አምላክነቱ) ብቻ የምታመልክና እግዚአብሔርንም በአንድነትና በሦስትነት የምታምን፣ የምታመልክ፣ የምታመሰግን ተዋሕዶ ሃይማኖትን አቃለዉና ንቀዉ እንዲሁም ጠልተዉ በዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ በሆነዉ በዲያብሎስ በበላይ በሚመራዉ «እምነት» ዉስጥ መመላለሳቸዉና ተዋሕዶ ሃይማኖትን በመቃወም ነፍሳትን ከሕይወት መንገድ እያወጡ ለሰይጣናት በመገበራቸዉ ነዉ:: እንግዲህ እግዚአብሔር፣ የዲያብሎስን የዘመናት የረቀቀ ጥፋቱንና ጥቃቱን እያጋለጠ ስለሆነ እዉነት በምትነግሥበት ጊዜ ባለማወቅና በየዋህነት እዉነተኛዉን ኢየሱስ ያገኙ መስሏቸዉ በዚህ ዓመፃ እምነት ዉስጥ ያሉ ሰዎች እመቤታችን የመረጠቻቸዉ ካሉ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ በመድረስ ወደ እዉነተኛ ሃይማኖታቸዉና እምነታቸዉ ይመለሳሉ:: በዲያብሎስ አገልጋይነትና አማኝነት ያሉ ደግሞ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ እንደ ዓመፃ ልጆች በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጸዳሉ(ይጠረጋሉ)::

እዚህ ላይ «የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ሃይማኖትና እምነት ተከታዮች ነን» ለሚሉት መልእክት አለኝ:: ይኸዉም ለክርስትና ሃይማኖት መከፋፈል፣ መዳከም፣ መቀጨጭ ምክንያት የሆናችሁ እናተ ናችሁና የዘራችሁትን የዓመፅ ፍሬ ከማጨዳችሁ በፊት እስከ አምስተኛዉ ክፍል ዘመን አጋማሽ ድረስ(451 ዓ.ም) ድረስ ምንም ሳትከፈልና ሳትለወጥ፣ ሳትሻሻል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሰረታት ሐዋርያት እንዳስፋፏት፣ አበዉ ሐዋርያት እንደጠበቋት፣ ሰማዕታት እንደተጋደሉላት፣ መምህራንና ሊቃዉንት እንደመሰከሩለት ሆና ወደተገኘችዉ ወደ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ሃይማኖት ተመለሱ:: እንደ እምነቷና ሥርዓቷ ኑሩ:: ያለፈዉ የመከፋፈል፣ የመለያየት፣ የመንፈሳዊና ሥጋዊ ወንበር የበላይነት ለማግኘት ሲባል የተፈጸመዉ የዓመፃና የክህደት ዘመን ይብቃ እላለሁ:: እግዚአብሔር ቅዱሱን ኪዳን ጠብቀዉ ባሉ ኢትዮጵያዉያን አገልጋዮቹና ባለሟሎቹ እንዲሁም መልእክተኞቹና እንደራሴዎቹ አማካይነት ሙሉ እዉነትን ለዓለም አሳዉቋል:: ይህም የሚያሳየዉ እግዚአብሔር በወደደዉና በፈቀደዉ የሕይወት መንገድ የተመላለሱና ለእግዚአብሔር እዉነተኛ አገልግሎት ተሰልፈዉ የተገኙት ኢትዮጵያዉያን መሆናቸዉን ነዉ:: ስለዚህ በዓመፀኞች ላይ የሚመጣዉ የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተም ላይ ሳይመጣ እጃችሁን ለእግዚአብሔር በመስጠት በኢትዮጵያ ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ሃይማኖት ስር በአንድነት ተሰለፉ እላለሁ::

ሌላዉ ከክርስትናና ከእስልምና እምነት ዉጭ ያላችሁ ቡዲዝም፣ ሂንዱዚም የመሳሰላችሁት በተለየ ሁኔታ አሁን ከላይ ያልተገለጻችሁት የተለያዩ ግለሰቦች በተመሰረቱ እምነቶች ዉስጥ የምትመላለሱ ሰዎች ሁሉ! እናንተም ከእግዚአብሔር ቁጣ ለመዳን ዛሬ ነገ ሳትሉ እጃችሁን

ለእግዚአብሔር በመስጠት በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ወስጥ በመመላለስ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆናችሁ ተገኙ። ጥቅሙ ለእናንተዉ ነዉ። ምክንያቱም በሥጋዊ ወንበር ላይ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ያሉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት እምነትና ተግባር የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ የጨለማዉ ገዢ አገልጋዮች ሆኑ ተከታዮች እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡና በእዉነተኛ ንሰሐ ተመልሰዉ እዉነትን ካልተቀበሉ በስተቀር በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጠረጋሉ፤ መታሰቢያቸዉም ለዘላለም ይጠፋልና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከላይ እንደገለጹት በዓለም ላይ በክርስትና ሆነ በእስልምና እምነት ሥጋዊዉና መንፈሳዊ ወንበር ተለያይተዉና ተከፋፍለዉ ሕዝቡን ለሁለት ጌታ ከፍለዉ ማስተዳደርና መምራት የተጀመረዉ የተለያዩ ፈላስፋዎች ከተነሱና ዘመናዊ ስልጣኔ በተጀመረበት ከ18ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ገልጸዉልናል። የኢትዮጵያስ መቼ ነዉ መከፋፈልና መለያየት የተጀመረዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በኢትዮጵያ ሕዝቡን ለእግዚአብሔርና ለዲያብሎስ ከፋፍሎ ማስተዳደርና መምራት የተጀመረዉ ከዉጭዉ ዓለም ቀጥሎ በ20ኛዉ ክፍል ዘመን አጋማሽ ገደማ ጀምሮ ሲሆን፤ በግልጽ ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱና ቤተ መንግሥቱ ተለያይተዉ እንደ ዉጭዉ ዓለም የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት እምነትና ተግባር የነገሠዉ ደግሞ ከመስከረም ፪÷፲፱፻፷፯ (2/1/1967) ዓ.ም ጀምሮ ነዉ። ለዚህ ነዉ እግዚአብሔር «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ መልእክቱ በክፍል ሦስት በገጽ 66 ላይ «አሁንም ለሠላሳ ሰባት(37) ዓመት የዓመፃ ልጆች ተነስተዉ ክህደትንና መናፍቅነትን ቢያስፋፉ፤ መድረኮችንና ብዙኃን መገናኛን (ማስሚዲያን) ለዘፈንና ለዳንኪራ ለወሬ ቢያዉሉም፤ ሰዎች ወደ እዉነት እንዳይመጡ በተለያየ መንገድ ሐሰት እንድትነግሥ ቢያደርጉም፤ በሰዎች መካከል ጥላቻና መከፋፈል ቢዘሩም፤ እዉነትን ሊያጠፉ ሆነ ሊያሸንፉ አይችሉም። እዉነት ትነግሥና የሐሰት ተግባራቸዉ ገበና ትገልጣለች፤ ባዶ ቀፎ መሆናቸዉን ታሳዉቃለች፤ መንገዳቸዉ ሁሉ የሞት መንገድ ጨለማን የለበሰ የዲያብሎስ ፍሬ መሆኑን ታሳዉቃቸዋለች» ይላል።

ይህ ዘመን እንግዲህ የሚያልቀዉ መስከረም 2/2005 ዓ.ም ነዉ። ከዚያም የሚቀረዉ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ አገልጋዮች ከወንበራቸዉ ከተቆረጡና ስለ ዓመፃቸዉም ዋጋ ከከፈሉ በኋላ ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በመንፈስ ቅዱስ ተዋሕዶ በአንድነት ይመራል። ሕዝቡም ለአንድ ጌታ ለእግዚአብሔር ብቻ ይገዛል። የዲያብሎስ ገዥነት ይሻራል።

እዚህ ላይ አንድ የእግዚአብሔር እዉነታን አቀርባለሁ። ሥጋዊዉንና መንፈሳዊ ወንበር ለያይተዉ ሕዝቡን ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ሲፈልጉ ለዲያብሎስ እንዲገዛ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ያደረጉ ሆነ በድፍረትና በግልጽ የፈጸሙ ሰዎች በተለያየ ጊዜ ዋጋ ከፍለዉ አልፈዋል፤እያለፉም ነዉ፤ ያልፋሉ እንጂ ከእግዚአብሔር የሆነዉን የቅዱሱ ኪዳን መንግሥት ማንም ሊያጠፋዉና ሊያስቀረዉ አይችልም። ለ37 ዓመት ያህል ዘመን የዲያብሎስ ሥርዓት ባለ ጊዜ እንዲሆን እግዚአብሔር

የፈቀደዉም፤ ቀደም ሲል ሆነ በ37 ዓመት ዉስጥ ትዉልዱ ባሳየዉ የዓመፅና የክህደት ሕይወት ዋጋ እንዲከፍልበትና የዲያብሎስ ሥርዓት ምን ያህል የከፋና የከረፋ መሆኑን እንዲያዉቅና ዳግም እንዳይመኘዉና እንዳይናፍቀዉ ለማስተማር ነዉ:: እንዲሁም ትዉልዱ ወደ ልቡ እንዲመለስና በእዉነተኛ የብርሃን ሥርዓት ለመመላለስ እራሱ ፈቅዶና ወዶ እንዲወስን ነዉ:: አሁን ግን ትዉልዱ ሁሉን አይቶ እጁን ለእግዚአብሔር እንደሰጠ ይገመታል:: በመሆኑም እግዚአብሔር ስለ ቅዱሱ ኪዳን ሲል ራሱ የእርሱን መንግሥት መስርቶልና እዉነተኛ አገልጋዮቹንና እንደራሴዎቹን በእዉነተኛ ወንበር ላይ አስቀምጦ ሕዝቡን ራሱ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ እዉነተኛ ፍርድም ይሰጣል:: በረከቱንም ያትረፈርፍልናል፣ ፍቅርን ያላብሰል፣ ባጠቃላይ በምሕረት ይጎበኘናል:: እንዲሁም ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ ያድነናል፤ በምድርም እንባረካለን፣ ለሰማያዊ ሕያዉ መንግሥቱም እንበቃለን::

የሰዉ ሥርዓት ለመመስረት የተነሱት የቀደሙት ሆኑ የአሁኖቹ መሪዎች ያላስተዋሉትና ያልተገነዘቡት፤ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ የነፍስ የምድራዊ ሕይወት ዘመኗ ማብቃቱን እንደሚያሳይ ሁሉ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን አስተዳደር ለይቶ ሕዝቡ በአንድ በኩል በሥጋዉያን እንዲተዳደር በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈሳዉያን እንዲተዳደር ሲደረግ በነፍሱ እንደገደሉትና በድን እንዲሆን እንደፈረዱበት ነዉ:: ማንም ሰዉ ከመንፈሳዊ ሕይወቱ ተለይቶ በዓለማዊ ሕይወት ብቻ ከተመላለሰ ለእርሱ በሕይወት የተመላለሰ ይመስለዋል እንጂ በደመ ነፍስ ነዉ የሚመላለሰዉ:: እንዲሁም በነፍሱ ደግሞ የሞተ በድን ነዉ ማለት ነዉ:: ምክንያቱም እኛ ሰዎች የተፈጠርነዉ እንደ እንስሳ እንድንበላ፣ እንድንጠጣ፣ የተወሰነ ዘመን በምድር ላይ ታይተን እንድንጠፋ ሳይሆን፤ እጅግ እጅግ አጭር በሆነችዉ በምድራዊ ዘመናችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተመላልሰን፣ ለሥጋችንም ማድረግ ያለብንን አድርገን፣ እንዲሁም ነፍሳችንን ለእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግሥት ማብቃትና የነፍሳችን በላይነት ማስጠበቅ ነዉ ያለብን:: በእግዚአብሔር እንደማያምኑትና ራሳቸዉን ከእንስሳት ጋር እንዳስተካከሉት አረማዉያንና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች ከሃዲያን «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንጨፍር፣ እንደለቅ...» ወዘተ እያሉ ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ የሚመላለሱ ሰዎች፤ በእዉነተኛ ነፍሳቸዉ ባሕርይ ሳይሆን እየኖሩት ያለዉ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ በደመ ነፍስ ነዉ:: ይህ እንደ እንስሳ ቢያስቆጥራቸዉም ነፍሳቸዉ ሕያዉ ናትና ከሥጋዋ ስትለይ እንደ ርኩሳን መናፍስት ተቆጥረዉ በሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ እንደ ነፍሳዊ ባሕርያቸዉ ዋጋ ይከፍሉበታል፤ ፍዳቸዉንም ይቀበላሉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ልቦና፣ ሕሊና፣ አእምሮ ስለሚባሉትና ልዩነታቸዉን ቢገልጹልን ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ስለ እነዚህ ማንነትና አንድነት እንዲሁም ልዩነት የምገልጽላችሁ በተለመደዉ በእግዚአብሔር እዉነት ነዉ እንጂ በተማርኩት ወይንም በሚነገረዉ መልክ አይደለም:: ሰዉ የሚባለዉ ከእግዚአብሔር ሕያዉ ባሕርይ የሰረጸች (የወጣች)እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍስ ከተገለጸችበት ሥጋ ጋር ተዋሕዳ ያለችዉ ነዉ:: ይህች ሕያዉ ነፍስ በረቂቅ አካል ደረጃ የምትገኘዉ ከግንባራችን ፊት ለፊት በአንጎል ዉስጥ ነዉ:: ከእርሷ በወጣ ኃይል ከራስ ጠጉር እስከ ጥፍር ድረስ ይህን የተገለጽንበትን አካል ተዋሕዳ

ያለችና ለሥጋችን(አካላችን) ሕይወትን የምትሰጠዉ እርሷ ናት። እርሷ ስትለየዉ ይህ አካል(ሥጋ) ወዲያዉ በድን ይሆናል። ምክንያቱም ሕይወትን ሰታ ታንቀሳቅሰዉ የነበረችዉ እርሷ ነበረችና። እርሷ ግን የሕይወት ባለቤት እንድትሆን ተደርጋ ስለተፈጠረች አትሞትም፤ በድን አትሆንም፣ ከመኖር ወደ አለመኖር አታልፍም። በሌላ ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጻ ሕያዉ ሆና እግዚአብሔር ባዘጋጀላት ቦታ ትኖራለች።

ቀደም ብሎ ሕሊና ወይንም አእምሮ የሚለዉ ቃላት ከመፈጠሩ በፊት ይህች ሕያዉ ነፍስ ልቦና ተብላ ነበር የምትጠራዉ። አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕሊና ወይንም አእምሮ የሚሉት ቃላት ሲፈጠሩ ደግሞ ሕሊና ወይንም አእምሮ ተብላ ተጠርታለች። ስለዚህ ልቦና፣ ሕሊና፣ አእምሮ የነፍሳችን ሌላ ስሞች ናቸዉ ማለት ነዉ። በልማድ ግን እኛ ልቦና የምንለዉ ለዚህ ለአካላችን(ሥጋችን) ወሳኝ አካል የሆነዉና የደም ዝዉዉር የሚካሄድበትን ልብ ነዉ። ይህ ልብ ግን ከሌሎች አካላት በተለየ መልኩ በግንባራችን ፊት ለፊት አንጎላችን ዉስጥ ካለችዉ ረቂቋና ሕያዉ ከሆነችዉ ነፍሳችን ጋር ግንኙነት ያለዉና ነፍሳችን ስትለየዉ ደግሞ ከሥጋችን ጋር ያለዉን ግንኙነት ወዲያዉ የሚያቋርጥ ከአካላችን(ከሥጋችን) ወሳኝ የሆነ አካል ነዉ እንጂ የምናስብበት፣ የምናገናዝብበት አካል አይደለም። የምናስበዉ፣ የምናገናዝበዉ፣ የምንመራዉ በግንባራችን ፊት ለፊት በአንጎላችን ዉሰጥ ባለችዉ ሕያዉ ነፍሳችን ነዉ። እኛ ማለት ደግሞ ነፍሳችን ናት። ይህ ሥጋችን በምድር የተገለጽንበት፤ ሰዉ ያስባለን ነዉ እንጂ ነፍሳችን እንደ መናፍስት(መላእክት) እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ረቂቅ ሕያዉ ፍጥረት ናት። ልክ አንድ ሞተር የተለያየ አካል ተሰርቶለት የተለያየ ስያሜና መልክ ቢሰጠዉ ያዉ አንዱ ሞተር እንጂ የተለየ ሞተር እንዳልሆነ ሁሉ፤ የሰዉ ዘሮችም የተለያየ ስምና መልክ ቢይዙም እያንዳንዱ አንድ ዓይነት የሆነች በመልክ፣ በገጽ፣ የማትለያይ ሕያዉ ነፍስ ባለቤት ነዉ። ሞተሩ የተገለጸበት አካል(ቦዲይ) ቢወገድ መኪና ወይንም ባቡር ወይንም አይሮፕላን ተብሎ አገልግሎት እንደማይሰጥ ሁሉ፤ ነፍስም ከተገለጸችበት ሥጋ ስትለይ እንደ ረቂቅነቷና ሕያዉነቷ ነዉ የምትታወቀዉ እንጂ እንደ ሥጋና ደም ለባሽ ሰዉነቷ አይደለም። መኪና መኪና ያሰኘዉ ሞተር ስላለዉና አገልግሎት ስለሚሰጥና ሞተር ከሌለዉ እንደማንኛዉም ቁሳቁስ የሚቆጠር እንጂ መኪና እንደማይባል ሁሉ፤ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ይህ ሥጋ ክብሩ ይቀራል፣ ሰዉ አይባልም፣ ወደ አፈርነትም ይለወጣል። ይህም የሚያሳየን የእኛ የሰዉ ዘሮች እዉነተኛ ገንዘብ ሕያዉ ነፍሳችን እንጂ ይህ ወደ አፈርነት የሚለወጠዉ፣ ሥጋችንና አፅማችን አይደለም።» **በማለት የአዶናይ፣ የኤልሻዳይ፣ የያህዌህ፣ የአልፋና ዖሜጋ፣ የሁሉ ፈጣሪ፣ የአንዱ አምላክ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ክፍል አራት

### ምዕራፍ አንድ

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: የተለያየ ሰዎች የተለያየ አቋምና ብቃት አላቸዉ:: አንዳንድ ሰዎች ሌሎች እንደነሱ ግድ መሆን አለባቸዉ በማለት ከእነርሱ የደከሙትን ወይንም እንደነርሱ ብቃት የማያሳዩትን ይተቻሉ፣ ይንቃሉ፣ ያንቋሽሻሉ፣ ራሳቸዉንም ያመጻድቃሉ:: ለዚህ አስተሳሰብ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

*<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>*: እዚህ ላይ በእግዚአብሔር ምሳሌ ሕያዉ ሆኖ የተፈጠረዉን ሰዉ ምንም ይሁን ምን መጥላት ሆነ ማንቋሸሽ ማንም ሰዉ አይችልም:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጅ ነዉና:: ማንም ሰዉ የሚሰራዉን ኃጢአት ተግባር ሆነ ንግግር እንዲሁም የክፋትና የተንኮል ሐሳቡን ነዉ መጥላትና መቃወም ያለብን እንጂ ራሱን ግለሰቡን መሆን የለበትም:: ምክንያቱም እኛ ሰዎች በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ስለተፈጠርን እግዚአብሔር የሚጠላዉ የዓመፃ ስራችንን ነዉ እንጂ እኛን አይደለምና:: ለዚህም ነዉ ከበደላችንና ከኃጢአታችን በእዉነተኛ ንስሐ ይቅርታን ስንጠይቀዉ ይቅር ብሎን ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ የሚያበቃን:: እኛም የእርሱን ባሕርይ ተላብሰናልና የበደለንን ሆነ በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ የዓመፃ ስራ ሲሰራ ቆይቶ ወደ ሕሊናዉ( ወደ ልቡ) ሲመለስ፣ ኃጢአቱን አምኖ ይቅርታን ሲጠይቅ ልባዊ ይቅርታን መስጠት ነዉ ያለብን:: ሰዉየዉን በሰራዉ ስራ ስራዉን ሳይሆን እሱነቱን የምንጠላ ከሆነ ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ አልተላበስንም ማለት ነዉ:: ይኸዉም የማይገባንን ባሕርይና ጠባይ ስለተላበስን፤ በዚህም ምክንያት ያ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የበደለን ሰዉ ይቅርታን ሲጠይቀን ከልባችን ይቅር የማንል እንሆናለን ማለት ነዉ:: ይህን ባሕርይና ጠባይ ተላብሰን ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት ልንበቃ አንችልም:: ምክንያቱም ቂመኛና በቀለኛ ነፍስ ለእግዚአብሔር መንግሥት አትበቃምና::

**ወደ ጥያቄዉ መልስ ስመጣ** በዚህች ምድር ዉስጥ ያለን ሰዎች አይደለም ቅዱሳን መላእክት ሆኑ በገነት ያሉት ጻድቃን የነፍሳቸዉ ብቃት ትለያያለች:: ይኸዉም መላእክት ሳጥናኤል በሰማያት ዉስጥ ሲያምፅ ባሳዩት ተቃዉሞና የእምነት ጽናት ሲሆን፤ ጻድቃን ደግሞ በምድራዊ ሕይወታቸዉ ዘመን ባሳዩት ተጋድሎና ጽናት ነዉ:: ስለዚህ በዚህ ምድር በሕይወተ ሥጋ ያለን ሰዎች ደግሞ በብቃት ሆነ በእዉቀት እንዲሁም በጽናት ሆነ በትጋት እንለያያለን:: አንድ የሚያደርገን ግን እግዚብሔር ደስ በሚሰኝበት በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት መመላለስ ነዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን በምናሳየዉ የትሩፋት ሆነ የጽድቅ ስራ ልንለያይ እንችላለን:: በገዳም ዉስጥ ያለ ሰዉ በዓለም ዉስጥ ያለ ሰዉ ሁሉ እንደሱ እንዲጾም፣ እንዲጸልይ፣ እንዲያመሰግን መጠበቅ የለበትም:: በቤተክርስቲያን መደበኛ አገልጋይ የሆነዉ ሰዉ ሌላ መደበኛ አገልጋይ ያልሆነ አገልጋይና ምእመን እንደሱ አገልግሎት እንዲሰጥና እንዲሁም የምስጋና ሆነ የጸሎት ሥርዓት ላይ እንዲሳተፍ መጠበቅ የለበትም:: እንዲሁም በተለያየ የስራ መስክ የተሰማረ ሰዉ፤ አንድ ሙሉ ጊዜዉን

ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚያሳልፈዉን አገልጋይ እንደ እኔ በዓለም በተለያየ ስራ ይሰማራ ማለት የለበትም፡፡ አንድ የተሟላ እዉቀት ያለዉ ሰዉ ከእርሱ አነስ ያለ እዉቀት ያለዉ ሰዉ እንደሱ እየተነተነና እያመሰጠረ እንዲያስተምር መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ የተለየ ጸጋ የተሰጠዉ ሰዉ ሌላዉ ሰዉ ልክ እንደሱ በተለየ ጸጋ እንዲገለጥ መጠበቅ የለበትም፡፡

ጥሩ አድርጎ የሚሰብክ ሆነ የሚያስተርምር አገልጋይን «ለምን ባማረ ድምጽ አይዘምርም?» ማለት የለብንም፡፡ እንዲሁም ባማረ ድምጽ የሚዘምረዉን «ለምን ጥሩ አድርጎ አያስተምርም፣ አይሰብክም?» ማለት የለብንም፡፡ ጥሩ የመናገር አንደበት ያለዉ ሰዉ ሌላ ሰዉ እንደሱ አንደበተ ርቱዕ ሆኖ እንዲናገር መጠበቅ የለበትም፡፡ እያንዳንዱ እንደ ተሰጠዉ ጸጋ ነዉ ማገልገል ያለበትና የአገልግሎቱን መድረክ እንደ ተሰጥኦ ማሰለፍ ነዉ የሚጠበቅብን፡፡ አንድ ራሱን ፍጹምነት(ብቃት) ደረጃ ላይ ያደረሰ ሰዉ ሌላዉም ሰዉ በተለያየ ሕይወት ተፈትኖ ለዚያ ብቃት እንደሚደርስ ዘንግቶ፤ ሁሉም ሰዉ ፍጹም(ብቁ) መሆን አለበት ብሎ መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ የተለየ ትህትና ያለዉ ሰዉ ሌላዉም ሰዉ እርሱ በሚገልጸዉ ትህትና መልክ እንዲገለጽ መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ የረጋ ሰዉ ሌላዉም እንደሱ ረጋ ያለ ጭምት እንዲሆን መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ ተጫዋችና ተናጋሪ ሰዉ ሌላዉም እንደሱ እንዲጫወትና እንዲናገር መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ ለጋስ ሰዉ ሌላዉ እንደሱ እንዲለግስ መጠበቅ የለበትም፡፡

አንድ ሁሉን ታጋሽ፣ የሚፈጸመዉን አድሎና በደል ታግሶ ፈጣሪዉ ፍርድ እንዲሰጥ ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሚሰጥ ሰዉ፤ ሌላ ሰዉ ስለ እዉነት እንዲፈረድለት ወደ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ወደተቀመጡ የእግዚአብሔርና የሕዝብ አገልጋይ ወደሆኑት አካላት የተፈጸመዉን አድሎና በደል እንዲሁም ዓመፃና ርኩሰት ቢያቀርብና ቢያስፈርድ፤ «ለምን እንደ እኔ ሁሉን አትተዉም?» ማለት የለበትም፡፡ በየዋህነትና በቅንነት የእግዚአብሔርን መልእክትና ቃል ሰምቶ ወዲያ ራሱን ለእዉነተኛ ንስሐና ሕይወት ራሱን የሚያበቃ የዋህና ቅን ሰዉ ሌላዉ ሰዉም «ወዲያዉ የእግዚአብሔር መልእክትና ቃል ሰምቶ ራሱን መለወጥና ለእዉነተኛ ንስሐና ሕይወት መብቃት አለበት» ማለት የለበትም፡፡ ነገሮችን ሁሉ በየዋህነትና በቅንነት የሚመለከትና የሚቀበል ሰዉ ሌላዉ በማጥናትና በመመርመር በሂደት ሲቀበል «እንደ እኔ ወዲያዉ ለምን ተቀብለህ ተግባራዊ አላደረክም?» ማለት የለበትም፡፡ ስለ ሰዎች ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባርና ንግግር እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ በዓመፀኞች ላይ የሚያመጣዉን ቁጣ «እግዚአብሔር ሆይ! በኃጢአታችን ምክንያት የመጣዉን ቁጣህን አርቅ፣ በምሕረትህ ጎብኘን፣ ይቅር በለን፡፡» በማለት የሚጸልየዉ የተለየ ጸጋ የተሰጠዉ ሰዉ፤ ሌላዉ ሰዉ ቅዱሳን መላእክትንና ቅዱሳን ነፍሳን ተከትሎ «እግዚአብሔር ሆይ ፍርድ እዉነተኛና አድሎ የሌለበት ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉ የምትፈርድ ነህ» በማለት የእግዚአብሔርን ዳኝነትና ፍትሐዊነት የሚመሰክረዉንና በእግዚአብሔር ፍርድ የሚደሰትን ሰዉ፤ «ለምን እንደ እኔ ዓይነት ጸሎትና አቋም አታሳይም?» ማለት የለበትም፡፡

ራሱን በሚገባ የገዛና መደረግ ያለበትንና የሌለበትን በሚገባ አዉቆ አግባብ ባለዉ ሕይወት የሚመላለስ ሰዉ፤ በምድር ዉስጥ የሚኖሩ የተለያየ ጠባይና ሕይወት የያዙ ሰዎች እንዳሉ ዘንግቶና

እንዲሁም አእምሮ ቀላሎች፣ አእምሮ ሕፃናት፣ እነ ትዕቢት(የፈርኦን ወንድምና እህቶች)፣ እነ ክፋት(የይሁዳ ወንድምና እህቶች)፣ እነ ዓመፃ(የአርዮስ ወንድምና እህቶች)፣ ለጊዜያዊ ስልጣንና ጥቅም ሲሉ ሕሊናቸዉን የሚሸጡና ሕሊናቸዉንም አደንድነዉ የማይገባ ስራ የሚሰሩ ሰዎች እንዳሉ ዘንግቶና ሁሉ እንደሱ መስሎት «እያንዳንዱ የሚገዛበትና የሚዳኝበት አግባብ ያለዉ ሕግና ሥርዓት እንዲሁም አኗኗር አያስፈልግም» ማለት የለበትም፡፡ ማንም ሰዉ «ሁሉም ሰዉ አንድ ዓይነት ጠባይና ጽናት እንዲሁም አገልግሎትና ትጋት ይኑረዉ፤ እንዲሁም እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ እንደፈለገዉ ይኑር» ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡

አንድ በወጣትነት እድሜ ያለ «በጎልማሳነትና በአዛዉንትነት እድሜ ያለን ሰዉ እንደኔ ያስብ፣ እንደኔ ይስራ፣ ባጠቃላይ እንደ እኔ ይሁን» ብሎ መጠበቅ የለበትም፡፡ እንዲሁም አንድ ጎልማሳ ወይንም አዛዉንት «ወጣቱ እንደ እኔ ያስብ፣ እንደ እኔ ይሁን» ብሎ መጠበቅ የለበትም፡፡ አንድ ልጅ እርሱም በዚያ ሕይወት ማለፉን ዘንግቶ «ሕፃናት ለምን እንደ እኔ አይሆኑም? የሚጎዳቸዉንና የማይጎዳቸዉን አይለዩም? ባጠቃላይ እኔ የማሳየዉን ብቃት ለምን አያሳዩም?» ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡ በእያንዳንዱ የተለያየ እድሜ ዉስጥ ያለ ሰዉ የሚጠበቅበት ቅን ማሰብ፣ መልካም መስራት፣ እዉነተኛ መሆን ነዉ እንጂ እድሜያችን እየጨመረና እየበሰልን ስንሄድ ቀድሞ እንደ ትክክል እንቆጥራቸዉና ጥብቅና እንቆምላቸዉ የነበሩ ነገሮች ስህተት እንደሆኑ እየተገለጹልን ይሄዳሉ፡፡ በትምህርት እየበሰልን ስንሄድ ነገሮንች በደንብ ማወቅና ማመዛዘን እንችላለን፡፡ በማኅበራዊ ሕይወት ዉስጥ ስናልፍ ብዙ የሕይወት ተሞክሮዎች እናገኛለን፡፡ ባጠቃላይ እንደ እድሜያችን ደረጃ የአስተሳሰባችንና የብቃታችን ደረጃ ስለሚለያይ በሁሉም እድሜ ክልል ያለ ሰዉ ሁሉ አንድ አቋምና አስተሳሰብ መያዝ አለበት ማለት የለብንም፡፡

አንድ በትዳር ሕይወት ዉስጥ ያልተመላለሰና ያልኖረና ከመደበኛዉ ስራ ዉጭ ሙሉ ጊዜዉን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ያዋለ ሰዉ፤ ትዳርና ቤተሰብ ያለዉ ሰዉ ልክ እንደሱ ሙሉ ጊዜዉን በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ማሰለፍ አለበት ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች የሆኑትን ቤተሰብ በአግባቡና በሥርዓቱ ማሳደግ እንዲሁም እግዚአብሔር መፍራት ባለበት ሕይወት መምራትና የቤተሰብ አስተዳደርን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ራሱ ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት ነዉና፡፡ አንድ በተለያየ ስራ የተሰማራና ጊዜዉን ለቤተሰቡም፣ ለመንፈሳዊዉም፣ ለማኅበራዊዉም ሰዉቶ የሚያገለግልን ሰዉ «ለምን ለቤተሰብህ ብቻ አትሆንም?» ማለት የለብንም፡፡ ይልቁኑ ራሱን ለሰዉ መስዋዕት እያደረገ ስለሆነ ልንደግፈዉ፣ ልንረዳዉ፣ ልናበረታታዉ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ለሁሉ የሚኖርና በሰማይም የሚያገኘዉ ዋጋ ከፍ ያለ ነዉና፡፡ ራሳቸዉን የገዙና ጸጋዉ የበዛላቸዉ ባለትዳሮች በአንድ አቋም ተስማምተዉና ፈቅደዉ በሰባቱም አጿማት ሆነ በሌሎች በፈቃድ ጾም ወቅት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መከልከል የቻሉ አገልጋይና ምእመን፤ ሌላዉ እንደ ተሰጥኦዉ የተወሰኑትን አጿማት ብቻ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲከለከል፤ «ለምን እንደኛ በሁሉም አጿማት ወቅት ሆነ በፈቃድ ጾም ወቅት ከግብረ ሥጋ አትከለከሉም?» ማለት የለባቸዉም፡፡ ራስን ከዝሙትና ከአመንዝራነት መጠበቁ ራሱ ትልቅ ጾም ነዉና፡፡ አንድ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ብቻ የተሰማራ፣ እስከ ዘጠኝ ሰዓት፣ እስከ አስራ አንድ ሰዓት፣ እንዲሁም እስከ ምሽት ወይንም ለቀናተ የሚጾም ሰዉ፤

ሌላ አገልጋይ ሆነ በዓለም በተለያየ የስራ መስክ የተሰማራ ሰዉ «እንደኔ ይጹም» ማለት የለበትም። የበለጠ የሚጾምና የሚጸልይ ሰዉ የበለጠ ጸጋና መንፈሳዊ ኃይል እንደሚያገኝ የታወቀ ቢሆንም፤ እያንዳንዱ እንደተሰጠዉ ጸጋና እንደሚሰራዉ ስራ የአጿጿም ሰዓቱ ሊለያይ ይችላል። ነገር ግን በጾም ወቅት እያንዳንዱ ከጥሉላት መብል መከልከል ይጠበቅበታል።

አንድ በሚናገረዉ ቃል ሆኖ የሚገኝ ለሕሊናዉና ለአምላኩ የሚታመን ሰዉ፤ «ሌላዉም ሰዉ ሁሉ በሚናገረዉ ቃል ሆኖ የሚገኝ ነዉ» በማለት ሁሉንም ተናጋሪ ማመን የለበትም። የተነገረዉ በተግባር ሲፈጸምና ተናጋሪዉም በተናገረዉ ቃል ሆኖ በመገኘት ሕይወቱ ምስክርነትን ሲሰጥ ብቻ ነዉ ማመን ያለበት። ምክንያቱም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ ብዙዎች እዉነተኛ አገልጋይ ለመምሰልና የዋሃንን ለማታለል እንዲሁም የራሳቸዉን ስዉር ተግባር ለመፈጸም ሲሉ የማያደርጉትንና የማይፈጽሙት ብዙ ንግግር ያደርጋሉ። ይህም ተግባራቸዉ ፍጹም ተቃራኒ የሆነና አስመሳይ መሆናቸዉን ይመሰክርባቸዋል።

አንድ ራሱ ላይ እንዲደረግ የማይፈልገዉን በሰዉ ላይ የማያደርግ፣ በሌላ ሰዉ እንዲደረግለት የሚፈልገዉን እርሱም ለሌላዉ ሰዉ የሚያደርግ፣ እንዲሁም አንዳች ቅጣት ሆነ እርምጃ እንዳይደርስበትና እንዳይወሰድበት አግባብነት ያላቸዉን ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ ሥርዓቶች፣ ደንቦች፣ የሚጠብቅ ጠንቃቃ ሰዉ፤ ሌላዉ በሕገ ወጥነት፣ በሥርዓት አልበኝነት፣ በመመሪያ ጣሽነትና ደንብን ባለማክበር ፍትሐዊ ዋጋ እንዲከፍል ወይንም ፍትሐዊ ፍርድ ተወስኖበት እንዲቀጣ ቢደረግ፤ «ለምን ይቀጣል? ለምን እርምጃ ይወሰድበታል?» ማለት የለበትም። ምክንያቱም ሰዉ የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ሕሊና ያለዉ ታላቅ ፍጡር ነዉና ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ አግባብነት ያላቸዉን ሕጎችና ደንቦችን እንዲሁም መመሪያዎችንና ሥርዓቶን መጠበቅ ይጠበቅበታል። ይህ ዓይነቱ ሰዉ እንደ ሥጋና ደሙ ስሜት ብቻ በመንቀሳቀስ ሕጎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪዎችን፣ ሥርዓቶችን ከጣስ ግን ተመጣጠኝና ሊማርበት የሚያስችለዉ ፍትሐዊ ቅጣት ሲቀጣ፤ «ልክ ነዉ በጥፋቴና በስንፍናዬ ነዉ የጠቀጣሁት» ማለትና ለቀጣይ ያንን ጥፋት ላለመድገም መወሰን ነዉ ያለበት እንጂ የራሱን የዉሸት እዉነት ፈጥሮ «እንዲህ ተደረኩ፤ እንዲህ ተደረገብኝ... ወዘተ» ቢል፤ ይህ ለግል ሕይወቱ ሆነ ለሕያዉ ነፍሱ አንዳች አይጠቅመዉም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ቅጣት ሆነ እርምጃ ትምህርት ሰጪ እስከሆነ ድረስ ሰዉ በማወቅም፣ ባለማወቅም፣ በስንፍናም፣ በጥመትም፣ በየዋህነትም ሊሳሳትና ሊያጠፋ ይችላል። ዋናዉ ግን ከስህተት ወይንም ከጥፋት ትምህርት ወስዶ ዳግም ያንን ስህተትና ጥፋት አለመድገም ነዉ ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ።

አንድ ለሚሰራዉና ለሚናገረዉ ስራና ንግግር የሚጠነቀቅና በነፍሱ ፈቃድ የሚመላለስ በሥጋዉና በደሙ ስሜት ላይ የበላይነትን የተጎናጸፈ፣ ራሱን በሚገባ የገዛ ሰዉ፤ አንድ እንደ ሥጋና ደሙ ስሜት የሚመላለስ፣ የሥጋና የደሙ ስሜት በነፍሱ ላይ የበላይነትን የተጎናጸፈና ራሱን በሚገባ ያልገዛ ሰዉ፤ የሚያስገምተዉና ከእርሱ የማይጠበቅ ተግባር ሆነ ንግግር ሲሰራና ሲናገር «ለምን እንደ እኔ በነፍሱ ፈቃድ ብቻ አይመላለስም?» ማለትና መኮነን የለበትም። ነገር ግን ተገቢ ያልሆነዉን ተግባርና ንግግር እንክርዳድ መሆኑንና አእምሮ ካለዉ ሰዉ የማይጠበቅ መሆኑን ማሳወቅና ተግባሩን

ሆነ ንግግሩን ወደ እዉነት መምራት ነዉ የሚጠበቅበት:: ምክንያቱም ብዙዎች በሥጋና ደም ስሜት ተመርተዉ የሚፈጽሙት ተግባርና ንግግር እንደ ትክክለኛ ተግባርና ንግግር አድርገዉ ነዉ የሚቆጥሩት:: ለዚህም ነዉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር እዉነታ ተቃራኒ የሆነዉን እንደ ትክክለኛ ነገር ቆጥረዉ በግልጽ በየመድረኩ የሚሰሩትና የሚናገሩት:: ይህም የሚያሳየን ብዙዎች በራሳቸዉ የዉሸት እዉነት በሆነዉ በሞት ሕይወት ዉስጥ እየተመላለሱ መሆናቸዉን ነዉ::

አንድ ርኅሩኅ ሰዉ ሁሉም እንደሱ መስሎትና የተለያየ ጠባይና አቋም ያላቸዉ ሰዎች መኖራቸዉን ሳያስተዉል «በተለያየ ጥፋት ተግባር ዉስጥ የተሰማሩ ሰዎች ሁሉ ምሕረትና ይቅርታ ይደረግላቸዉ» ማለት የለበትም:: ምክንያቱም አንዳንዶች ዋጋ ካልከፈሉበት በስተቀር ከጥፋታቸዉ አይማሩምና:: እንዲሁም እነ ትዕቢት፣ እነ ክፋትና ተንኮል፣ እነ ዓመፃ፣ ስለ ጥፋታቸዉና ዓመፃቸዉ እንደ ጥፋታቸዉ ደረጃ ካልተቀጡና ዋጋ ካልከፈሉ በስተቀር ለበለጠ ጥፋትና ጥቃት ራሳቸዉን ያዘጋጃሉ፤ ያሰልፋሉ:: እዉነተኛና ፍትሐዊ ፍረድ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነዉና እሱን መምሰል የተላበሰች ነፍስም እዉነተኛና ፍትሐዊ ፍርድ መፍረድ ይጠበቅባታል እንጂ ስለ ግለሰብ ሆነ ስለ ቡድን እንዲሁም ስለድርጅት ወይንም ስለ መንግሥት ሲባል ኢ- ፍትሐዊ ፍርድና የሐሰት ፍርድ ማንም ቢሆን መፍረድ የለበትም:: ምክንያቱም በእዉነተኛዉ ፈራጅ እግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃል፤ ዋጋም ያስከፍላልና::

አንድ የተለየ ጸጋና ኃይል አግኝቶ ከተለያዩ ሱሶችና የማይገቡ ጠባያት ቶሎ መለየት የቻለና አካሄዱን ፍጹም ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሰዉ፤ ሰዎች የተለያየ ጽናትና አቋም እንዳላቸዉና እንደ ትጋታቸዉና ጥረታቸዉ ጸጋንና ኃይልን እንደሚጎናጸፉ ሳያስተዉል ቀርቶ፤ «ለምን እንደ እኔ በአንዴ ከሱሳቸዉ ሆነ ከማይገባ ጠባይ ለመለየት ወስነዉና ከዚህ ከሞት ሕይወት በአንዴ ተለይተዉ አካሄዳቸዉን ፍጹም ከእግዚአብሔር ጋር አያደርጉም?» ማለት የለበትም:: ነገር ግን ለሌሎች ምሳሌ መሆንንና ደካሞችን ማበረታታትና መደገፍ ይጠበቅበታል::

አንድ የአገልግሎት ድርሻዉን ለመወጣት ካለምንም ይሉኝታ ባለማወቅም ይሁን በማወቅ እንዲሁም በአእምሮ ሕፃንነት ይሁን በእእምሮ ቀላልነት ወይንም በዓመፃና በትዕቢት ሕይወት ካለቦታዉና ካለወንበሩ የተቀመጠን ሰዉ ቢያስነሳና ወደ ተገባዉ ቦታ ቢያስቀምጥ፣ እንዲሁም ሥርዓትና ደንብ ባለማክበር ከሕግ በላይ ልሁን የሚለዉን ሰዉ ወደ ፍርድ ቢያቀርበዉና እንደ ዓመፃዉ ደረጃ ዋጋ ቢያስከፍለዉ «ለምን አስነሳኸኝ? እንዲሁም ለምን አስቀጣኸኝ?» በማለት ሊቀየመዉና ቅር ሊሰኝበት አይገባም:: ምክንያቱም የስራ ድርሻዉን በአግባቡ ተወጣ እንጂ ማንንም ለመጥቀም ወይንም ለመጉዳት አይደለም ያደረገዉና:: ያንን የስራ ድርሻዉን በአግባቡ ባይወጣ ደግሞ ራሱ ተጠያቂ ይሆናል፣ እንደ ጥፋቱም ሊቀጣ ይችላልና::

ከአንድ ዘር ወይንም ከአንድ ነገድ ወይንም ከአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ወይንም ከአንድ ጎሳ(ብሔር) ወይንም ሃይማኖት ዉስጥ ጥሩ ይሁን መጥፎ ተግባር በሚሰራ ሰዉ፤ ሌሎቹን በዚያ ጥሩነት

ወይንም መጥፎነት ይወክላል ማለት አይቻልም:: ጥሩነት ሆነ መጥፎነት ከእያንዳንዱ ሰዉ ከነጻ ሕሊናዉ በፈቃዱና በምርጫዉ የሚወጣና በተግባርም የሚታይ ነዉ እንጂ በቀለም፣ በዘር፣ በነገድ፣ በቋንቋ ተናጋሪነት፣ በጎሳ(በብሔር) ፣ በስመ ሃይማኖት የሚተላለፍ አይደለም:: ሊተላለፍ የሚችለዉ ቢበዛ የሥጋ ባሕርይና መልክ እንጂ ነፍስ(ሕሊና) ከእግዚአብሔር ባሕርይ የምትወጣ(የምትሰርጽ) ስለሆነ መልካም ሆነ መጥፎ ለመሆን የራሷ ነጻ ፈቃድና ምርጫ አላት:: በመሆኑም በአንድ ወይንም በተወሰነ ሰዉ ጥሩነትና መጥፎነት ሌሎቹም ወገኖች «እንዲህ ናቸዉ» ብሎ ማሰብና መፈረጅ አግባብ አይደለም:: እንኳን በቀለም፣ በዘር፣ በነገድ፣ በጎሳ(ብሔር) አይደለም፤ በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ እንኳ ልጆች የተለያየ ጠባይና አቋም፣ እንዲሁም ብቃትና ተሰጥኦ ነዉ ያላቸዉ::

አንድ የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛለትን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እየተመራ የሚያገለግል ሰዉ፤ በእግዚአብሔር አሳሳቢነትና ገላጭነት ቀደም ባሉ የምስጋና ሆነ የጸሎት እንዲሁም የእዉቀት መጻሕፍትን አስፋፍቶና አሟልቶ ቢጽፍ «ለምን ከነባሩ ጽሑፍ ላይ ጨመርክ?» ማለት የለብንም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በተለያየ ዘመን እንደ ትዉልዱ እዉቀትና ብቃት አእምሮን እያሰፋ፣ ምስጢራትን እየገለጸ ስለሚሄድ፤ የእግዚአብሔርን እዉነት እስካልተቃረነና የሥጋና የደም ስሜት እስካልተጨመረበት ድረስ አንድ ምስጋና ሆነ ጸሎት እንዲሁም እዉቀት ቢስፋፋና ግልጥልጥ ቢደረግ የበለጠ ዉጤት የሚያመጣና ለፍሬም የሚያበቃ ነዉ:: ለዚህም ነዉ በአንዳንድ የምስጋና ሆነ የጸሎት እንዲሁም የእዉቀት መጻሕፍት ዉስጥ በተለያየ ዘመን የተነሱ አባቶች የራሳቸዉን ምስጋናና ጸሎት እንዲሁም እዉቀት የጨመሩት:: ዋናዉ በስንዴ ዉስጥ እንክርዳድ ከተጨመረ ያንን እንክርዳድ አለመቀበልና ከስንዴዉ በመለየት በስዴዉ ብቻ መጠቀም ነዉ:: ስንዴዉ የበለጠ እንዲበዛና ጣፋጭ እንዲሆን የሚያደርገዉን ደግሞ በደንብ ልንጠቀምበት ይገባል እንጂ የጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት ሕይወት ይዘን «ከእኛ በላይ እዉቀት፣ ከእኛ በላይ ሊቅነት፣ ከእኛ በላይ ቅድስና ... ወዘተ የለም» በማለት ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር መላተምና መጋጨት የለብንም:: ምክንያቱም የመጀመሪያ ተጎጂ እንሆናለን:: እግዚአብሔር እንዲገለጽ ያደረገዉን እዉነት ሆነ ምስጢራት እንዲሁም እዉቀት ማንም ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያጠፋዉ አይችልምና::

እያንዳንዱ ሰዉ ደረጃዉ ቢለያይ መልካም ጠባይ እንዲኖረዉና እንደ ተሰጠዉ ጸጋ እንዲያገለግል፣ እንዲኖር ነዉ የሚጠበቀዉ እንጂ፤ የሁሉም ሰዉ ብቃት አንድ ዓይነት ቢሆንማ ኖሮ ሁሉም ሰዉ በትምህርቱ ከክፍል አንደኛ ነበር የሚወጣዉ:: ነገር ግን እያንዳንዱ ሰዉ ወደ ተከተይ ደረጃ ለማለፍ ቢያንስ ማለፊያ ነጥብ ማምጣት ይጠበቅበታል:: ይህን እንዳያመጣ የሚከለክለዉ እንዳች ነገር የለምና:: ያን ካላመጣ ደግሞ ስለ ስንፍናዉ ሆነ ስለ ድክመቱ ዋጋ በመክፈል በቀጣይ የሚያገኘዉን መልካም እድል ያጣል ማለት ነዉ:: ስለዚህ ማንኛችንም ለመልካም ነገር የተሰለፍን እግዚአብሔር የሚወደዉን ተግባር እንደ ስጦታችን ማከናወን፣ እንደምንወጣዉ አቅም የጽድቅና የትሩፋት ስራ መስራት፣ ከኃጢአት ደግሞ ሙሉ በሙሉ መከልከል ነዉ የሚጠበቅብን እንጂ «ሁሉም ሰዉ እንደ እኔ ይሁን» ማለት አንችልም:: እንዲሁም በስራችንና በአገልግሎታችን የምንመጻደቅ ከሆነ ክርስትናዉ ያልገባን መሆኑን የሚመሰክርብንና ከእግዚአብሔርም ዋጋ የሚያሳጣን ይሆናል:: ደካማ ከገጠመን ልናበረታታዉ፣ ልንመክረዉ፣ ልንገስጸዉ፣ ልንጸልይለት ይገባል እንጂ ስለ

ድክመቱ መኮነንና እንደ በደለኛ መቁጠር የለብንም:: በዓመፃ ሕይወት ያለዉንም ወደ እግዚአብሔር እዉነት እንዲመጣ ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ልንመሰክርለትና ወደ ንስሐ ልናመጣዉ ይገባል እንጂ ከምድር መጥፋት፣ መደምሰስ አለበት ማለት የለብንም:: ምክንያቱም የማዳንም የማጥፋትም ሥልጣኑ የእግዚአብሔር ስለሆነ፤ ከእኛ የሚጠበቀዉ መልካም ማሰብና መስራ ነዉ:: ከዚያ ዉጪ እኛ «ይዳኑ» ስላልን ብቻ እግዚአብሔር አያድንም:: እኛ «ይጥፉ፣ ይደምሰሱ» ስላልን ብቻ አይደመሰሱም:: እርሱ እዉነተኛ ፍትሐዊ ፈርድ ነዉ የሚሰጠዉ:: ከእኛ የሚጠበቀዉን ነዉ እኛ ማድረግ የሚጠበቅብን እንጂ በእግዚአብሔር የማዳን ሆነ የማጥፋት ጣልቃ መግባት አንችልም::

ለዚህም ነዉ «ጠላታችሁን ዉደዱ» በማለት ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ ያስተማረን:: ምክንያቱም እኛ«ጠላት» ያልነዉ ሰዉ በራሳችን መስፈርት ወስደን ነዉ እንጂ በትክክል ጠላታችን ላይሆን ስለሚችልና ይልቁኑ ለእኛ ሕይወት በማሰብ በሚያደርገዉ መልካምና እዉነተኛ አገልግሎት ተቃራኒ ስያሜ ሰተነዉ ሊሆን ይችላል:: ለዚህ ምስክሩ የአዳምን ዘር ለማዳን ባሕርይዉን ወስኖ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በምድር የተገለጸዉና ሊያድናቸዉ የመጣዉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶሰ፤ ስለ እዉነት በመመስከሩና በእዉነት በማገልገሉ ምክንያት እንደ ጠላት ተቆጥሮ ሊወነጀልና ሊሰቀል የቻለዉ:: በመሆኑም የእኛ የሰዉ ልጆች ጠላት በእርግጠኝነት የምናዉቀዉ ዲያብሎስና በዚህች ምድር ዉስጥ ያሉት የእርሱ ሠራዊት እልፍ አእላፈት(በብዙ ቢሊዮን) የሚቆጠሩት ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ብቻ ናቸዉ እንጂ የሰዉ ዘሮች አይደሉም:: ብዙ ሰዎች የዓመፃ ስራቸዉን እንደ ትክክለኛ ስራ አድርገዉ በመቁጠር ነዉ የሚሰሩት፣ የሚናገሩት እንጂ በእርግጠኛነት የተሳሳተ መሆኑን አዉቀዉ አይደለም:: ነገር ግን ለሕሊናቸዉ ባለመገዛት እግዚአብሔር በሕሊናቸዉ ስህተቱን እየነገራቸዉ ሕሊናቸዉን በማደንደን በዓመፃዉ ስራ ስለሚጸኑ ነዉ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር ላይ የተሰለፉትን እዉነተኛ ፍርድ የሚፈርድባቸዉ:: ስለዚህ እያንዳንዱም ሰዉ በስራም ሆነ በሌላ አገልግሎት የተሰጠዉን ኃላፊነትና ተግባር እንደሚጠበቅበት መወጣት ይኖርበታል:: መወጣት ካልቻለ ደግሞ ሊወጣ የሚችለዉን የስራ ድርሻ መፈለግ ይኖርበታል እንጂ በተቀመጠበት ወንበር ሆነ የስራ ድርሻ ዳተኛና ስራዉን የሚበድል መሆን የለበትም:: እያንዳንዱ ከሆነለት ከሚጠበቅበት በላይ በመስራት ከእግዚአብሔርም ከሰዉም መርቃት ቢያገኝና የተለየ ሽልማት ቢጎናጸፍ መልካም ነዉ:: ካልሆነለት ግን ቢያንስ ቢያንስ የሚጠበቅበትን ዝቅተኛ አገልግሎት መፈጸም ይጠበቅበታል::

አንድ አእምሮዉ ተክፍቶለት ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ እዉቀትና ምስጢር በቀላሉ የሚረዳ ሰዉ፤ ሰዎች የተለያየ ተሰጥኦ እንዳላቸዉ ማስተዋል ተስኖት እንደሱ መረዳትና ማስተዋል የተሳነቸዉን ሰዎች «እነዚህ ምን የማይገባቸዉ ናቸዉ?» ማለት የለበትም:: ምክንያቱም እያንዳንዱ በተሰጠዉ እዉቀትና ሙያ በስኬት ከሰራና ፍሬ ካፈራ እርሱ በተሳካለት እዉቀት ሆነ ሙያ ምሁር፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር ነዉ::

አንድ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሰባቱን አጿማት መጾም አቅቶት የቻለዉን ጾም የሚጾም፤ እግዚአብሔርን «እኔ ደካማ በመሆኔ ነዉ ሁሉንም አጿማት መጾም ያልቻልኩት፣ በዚህም ተጎጂዉ እኔ ነኝ፣ ምክንያቱም የሆነላቸዉ ባሕታዉያንና ገዳማዉያን ዘመናቸዉን ከላመና ከጣማ መብል ተለይተዉ ከፍተኛዉን ጸጋና ኃይል ተላብሰዉ ነፍሳቸዉን ለታላቅ ክብር ሲያበቁ፤ እኔ ግን ከላመዉና ከጣመዉ መብል ሳልለይ እንኳ በጾም ወቅት ከጥሉላት መብል መከልከል አልቻልኩም። ስለዚህ አንተዉ ኃይልን ሰተሽኝ የተሟላ ጾም እንድጾም አድርገኝ» ብሎ ሰንፍናዉን በማመኝ ፈጣሪዉን ኃይል መጠየቅ ነዉ ያለበት እንጂ፤ «ጾም አይስፈልግም፤ በዚህ ቀን በዚህ ወር ጹሙ አልተባልንም፤ የገናና የሰኔ ጾም የቄሶች ነዉ...» ወዘተ ማለት የለበትም። ምክንያቱም አብልጦ የጾም ሰይጣንን ስለሚያዳክም የበለጠዉን ኃይል(ጸጋ) ይጎናጸፋል። አሳንሶ የጾመ ሰይጣናትን በሚገባ ስለማያዳክማቸዉ በፈተና ሊወድቅና የሥጋና ደም ስሜቱ አይሎበት ራሱን መግዛት ይሳነዋል። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ጸጋ ለማግኘትና ኃይልን ለመጎናጸፍ እያንዳንዱ አገልጋይ ሆነ ምእመን ቢያንስ ቢያንስ የሚጠበቅበትን ዝቅተኛ ጾም ሊጾም ይገባዋል። ከቻለ ደግሞ አብልጦ ቢጾም ተጠቃሚ ነዉ የሚሆነዉ እንጂ አይጎዳበትም።

አንድ ተናግሮ ማሳመን የሚችል ሰዉ እንደሱ መናገር የማይችለዉ ሰዉ በእዉቀት ሆነ በብቃት ከእርሱ ያነሰ አድርጎ መቁጠር የለበትም። ምክንያቱም ያ ሰዉ የመናገር ጸጋ ቢሰጠዉ በመቶ እጥፍ ሊበልጠዉ ይችላልና። አንድ ሰዉ መናገር ባለመቻሉ ደግሞ የእዉቀት ሆነ የብቃት ጉድለት አይደለም። ነገር ግን ያ የማይናገር ሰዉ በሕይወቱ ሊናገርና ሊያሳምን እንዲሁም ብቃቱንም ማሳየት ይጠበቅበታል። ብዙዎች ይናገራሉ እንጂ የሚናገሩትን በሕይወታቸዉ አይገልጹም። ከዚህ ደግሞ በተግባር የማይፈጽሙትን አለመናገር ይሻላል። ምክንያቱም በሰዎች ዘንድ መቅለልንና መገመትን ያመጣል።

አንድ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ የተሰማራና በሌሊት አገልግሎት የሚተጋ ሰዉ እርሱ በሌሊት ቤተክርስቲያን ሄዶ በማመስገኑ፤ በስራ ድካም ያረፉ(ያንቀላፉ) ሰዎች እንዲሁም ሕፃናትና ሕመምተኞች መኖራቸዉን ዘንግቶ «ሌሎቹም በተኙበት የምስጋና ተካፋይ መሆን አለባቸዉ» ብሎ ድምፅ ማጉያዉ በእኩለ ሌሊት ወደ ዉጭ ይለቀቅ ማለት የለበትም። ሁሉ በአግባቡና በጊዜ ሲሆን ነዉ ጥቅም የሚሰጠዉና ፍሬ የሚያፈራዉ። በስብከት ሆነ በቅዳሴ ሰዓት እንዲሁም ድምፅ መረበሽ በማያስፈልግበት በተለየ ዝግጅት ላይ፣ ምንም እንኳ በተንቀሳቃሽ ስልክ(በሞባይል) ድምፅ መጥሪያዉን መዝሙር ማድረግ መልካም ቢሆንም ያለጊዜዉና ያለቦታዉ ስልኩ ቢጠራ ረብሻ ነዉ እንጂ መዝሙር አይሆንም። እንዲሁም እልልታና ጭብጨባ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ማቅረብ መልካም ቢሆንም፤ ትምህርት እየተሰጠና እየተሰበከ ካለጊዜዉ እልል ቢባል ወይንም ቢጨበጨብ ረብሻ ነዉ እንጂ ምስጋና አይደለም። ሁሉ በአግባቡ ሲሆን ነዉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት የሚሆነዉ እንጂ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን በመመላለስና ሕሊናችንን በማደንደን ከረበሽንና ካወክን ከበረከት ይልቅ መርገም ነዉ የሚጠብቀን።

እዚህ ላይ አንድ ለማንሳት የምፈልገዉ በመንፈሳዊ መድረክ ላይ ምንም እንኳን ሕሊናን አሸንፎ ለእልልታና ለጭብጨባ የሚዳርግ የእግዚአብሔር ድንቅ ተአምርና ስራ ቢኖርም፤ አንዳንዶች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚያስተምሩ ሆኑ የሚሰብኩ፤ ልክ እንደ ፖለቲከኞች አንድ ዐረፍተ ነገር ሆነ ቃል ሲናገሩ እንዲጨበጭብላቸዉና እልል እንዲባልላቸዉ እንደሚፈልጉ፤ እነሱም አንድ ዐረፍተ ነገር እንደተናገሩ እንዲጨበጨብላቸዉና እልል እንዲባልላቸዉ የሚፈልጉ አሉ። እንዲሁም መናፍቃን የሚናገሩት ሲጠፋባቸዉ «ሃሌ ሉያ» እያሉ አሜን እንደሚያስብሉ፤ በእዉነተኛዉ መድረክም ይህን የመናፍቃን ልማድ ለማለማመድ የተሰለፉ አስመሳይ አገልጋዮችም አሉ።

አንድ ማንነቱ በማይታወቅበት አድራሻ መተቸትና መቃወም ያለበትን በግልጽ የሚተችና የሚቃወም ሰዉ፤ ሌላዉ በሚታወቅት ማንነት እንደ እባብ ልባም እንደ ርግብ የዋህ ሆኖ ሲተችና ሲቃወም «ለምን እንደ እኔ በግልጽ አትተችም፣ አትቃወምም?» ማለት የለበትም። ይህች ዓለም በተኩላዎች ስለተሞላች ተኩላዉን ዓለም ድል ማድረግ የሚቻለዉ ቅንነትንና እዉነተኛነትን ብቻ በመያዝ ሳይሆን ልባምነትንና የዋህነትን አጣምሮ በመያዝ ጭምር ነዉ። ለዚህም ነዉ ራሱ እግዚአብሔር፤ «በአገልግሎታችሁ ዉስጥ እንደ እባብ ልባምና እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ» ብሎ በግልጽ የመከረዉና ያዘዘዉ።

አንድ እርሱ ያላለፈበትን ሕይወት ወይንም ተግባር ሲያዳናቅና ሲያገን እንዲሁም ሲገረም የተገኘን ሰዉ «ለምን ይህን ያዳንቃል፣ ምን ያስገርመዋል፣ ለምን ያገናል?» ማለት የለብንም። ምክንያቱም ምናልባት እኛ ስላለፍንበት ምንም ላይመስለን ቢችልም፤ አስቀድሞ በዚያ ሕይወት ሆነ ተግባር ከማለፋችን በፊት ስንደነቅበት፣ ስንገረምበትን፣ ስናገን ነበርና። ሌላዉ እኛ ባለፍንበት ሕይወት ሆነ ተግባር ሌሎች ሲያልፉ መታረም ያላባቸዉን እንደራሳችን በመመልከት እንዲታረሙ ማድረግ፣ አይቶ ማለፍ የሚገባዉን አይቶ ማለፍ፣ አክብሮት ልንሰጠዉ የሚገባዉን አክብሮት መስጠት፣ ትኩረት መስጠት የሚገባዉን ትኩረት መስጠት፣ እገዛና ድጋፊ የሚያስፈልገዉን እገዛ መስጠት፣ እርዳታ የሚያስፈልገዉን እርዳታ መስጠት፣ የተለየ ቦታ መሰጠጥ የሚያስፈልገዉን የተለየ ቦታ መስጠት፣ መገሰጽ የሚገባዉን መገሰጽ፣ መቀጣት የሚገባዉን አግባብነት ያለዉን ቅጣት መቅጣት ይገባል።

አንድ ከልምድ ወይንም ከእዉቀቱ የተነሳ በልዩ ብቃት የሚሰራ ሰዉ፤ ገና ጀማሪዉን ሰዉ ሊተችና «እንደ እኔ የማይሰራ ነዉ» ማለት የለበትም። ምክንያቱም እርሱም ሲጀምር በዚያ ድክመት ዉስጥ አልፎ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እንደ እርሱ በብቃት እንዲሰራ መንገዱን ሊያሳየዉና ሊያበረታታዉ ይገባል። አንድ ሰራተኛ የተወሰነ ጊዜ ሰርቶ የሚጠበቅበትን መስራት ካልቻለ ግን ሌላ የሚመጥነዉን ወይንም ስጦታዉን መፈለግ ይጠበቅበታል እንጂ ተስፋ መቁረጥና ራሱን እንደ ደካማ መቁጠር የለበትም። ምክንያቱም የራሱን ስጦታ በሚያገኝበት ጊዜ ከሌሎቹ ልቆ ይገኛልና። አንድ የቀለም ትምህርት ያልሆነለት ሰዉ በቴክኒክ ስራ የተዋጣለት ብቁ ሊሆን ይችላል። አንድ በቀለም ትምህርት የተዋጣለት ሰዉ በቴክኒክ ስራ ደካማ ሊሆን ይችላል። ከሁለቱም ያልሆ ደግሞ በጉልበት ስራ የተዋጣለት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰዉ ተሰጥኦዉን መፈለግ

ይጠበቅበታል እንጂ ቢያንስ ካለ አንድ ተሰጥኦ ወደዚህች ምድር ካለመኖር ወደ መኖር የሚመጣ ሰዉ የለም። ተሰጥኦዉንም ለመልካም ነገር ላይ ነዉ ማዋል ያለበት እንጂ ለመጥፎ ነገር ካዋለዉ በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍልበታል(ይቀጣበታል)። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰዉ በተሰጥኦዉ፤ ለሰዉ ልጆች የሚጠቅም ተግባር ነዉ መፈጸም ያለበት እንጂ ለጥፋትና ለዉድቀት የሚያበቃ ተግባር ሆነ መሳሪያ መስራት የለበትም። ምክንያቱም ስጦታዉን በሰጠዉ አምላክ ዘንድ ይጠየቅበታልና፤ መልካም ከሰራበት ደግሞ ዋጋ ያገኝበታልና፤ ተጨማሪ ተሰጥኦ ሊሰጠዉ ይችላልና።

አንድ የሚፈለገዉን የእዉቀት ደረጃና የሚፈለገዉን መስፈርት ያሟላ ነገር ግን ለመድረክ የሚሆን ተሰጥኦ የሌለዉ ሰዉ፤ የመድረክ ተሰጥኦ ያላቸዉ ሰዎች የሚፈለገዉን ዝግጅት ሆነ የተለያየ መርሐግብር በተለያየ መድረክና በብዙኃን መገናኛ(በማስ ሚዲያ) ሲያቀርቡ «እኔ እንዴት አላቀርብም» ሊልና ቅሬታ ሊሰማዉ አይገባም። ነገር ግን ተሰጦኦና ብቃት እያለዉ በአድሎና በዘመድ አዝማድ እንዲሁም በጥቅማጥቅም ምክንያት ተጽህኖ ከተደረገበት ግን በአሳማኝ ማስረጃ ለሚመለከተዉ አካል ማቅረብና ማስፈረድ (ማስወሰን) ይጠበቅበታል። ተሰጥኦ ከሌለዉ ደግሞ ራሱን ለተሰጠበት የስራ መስክ ማሰለፍ ይኖርበታል።

አንድ ያምንበት የነበረዉ እምነት ወይንም ይከተለዉ የነበረዉ ባህል ከአንድ ሚስት በላይ ፈቅዶለት ሕጋዊ ሚስቶች የነበሩት ሰዉ፤ ወደ እዉነትኛዉ የሕይወት መንገድ ሲመጣ፣ በእዉነተኛ ዉ ሕይወት ዉስጥ የሚፈቀደዉ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ስለሆነ «ሕጋዊ ሚስቶችህም ቢሆኑ መፍታትና አንዷን ብቻ በመያዝ ሌላዉን ቤተሰብህን መበተን አለብህ» ማለት የለብንም። ምክንያቱም ባለማወቅና እምነቱ ወይም ባህሉ በሚፈቅድለት መሰረት የፈጸመዉ ስህተት ስለነበረ፤ ነገር ግን አንድ ሚስት ብቻ ማግባት ሲገባዉ ከዚያ በላይ በማግባቱ በራሱ ጊዜ በራሱ ላይ ሸክም እንዳመጣ አስረድቶ እያንዳንዱን ካለ አንዳች አድሎና መለያየት በእኩል እያፈቀረ ለሁሉም የሚገባቸዉን ማድረግ እንዳለበት ማሳወቅ፣ እንዲሁም ያላገባዉን ወንድ ደግሞ በቀደም የስህተት እምነትና ባህል ዉስጥ እንዳይመላለስ ማስተማርና የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ብቻ መሆኑን ማሳወቅ፣ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት አንድ ሚስት ብቻ አግብቶ እንዲኖር ማስረዳት፣ ከዚያ ዉጭ የሚመላለስ ከሆነ ግን በቅዱሱ ኪዳን ላይ እንዳመፀ ተቆጥሮ በምድርም በሰማይም እንደሚጠየቅበትና ዋጋ እንደሚከፍልበት ማስረዳት ይጠበቅብናል። አንድ ሰዉ እርሱ በቀደመዉ ዘመን በወላጆቹ ምርጫ ትዳር በመያዙ፤ አሁን ደግሞ እያንዳንዱ ሰዉ በራሱ መርጦና ፈቅዶ ቢያገባ «ለምን እንደ ጥንቱ ወላጅ ብቻ የመረጠልህን ወይንም የመረጠልሽን ብቻ ማግባት አለባችሁ» ማለት የለበትም።

አንድ ሕፃን(ልጅ» በረቂቃ ርኩሳን መናፍስት ፈተናና ማስጨነቅ ወይንም በግል ፍላጎቱ አለመሟላት ምክንያት ቀን ይሁን ምሽት ላይ በማልቀስ አስቸግሮን ቆይቶ፤ ወይንም ተኝቶ ከእንቅልፉ ከተነሳ በኋላ ያደረገዉን ሁሉ ረስቶ «አባዬ፣ እማዬ» በማለት ሲቀርበን አንድም የሚያስታዉሰዉና የሚያስተዉለዉ ነገር ስለሌለ፤ አንድም ልጃችን ስለሆነ ያለፈዉን ያስቸገረንን ሁሉ እኛም ረስተን በፍቅር እንደምናቀርበዉ፤ በሥጋቸዉ አዋቂዎች ሆነዉ እእምሮዋቸዉ ሕፃናት የሆኑ ሰዎች በድርጊት ወይንም በንግግር አስቀይመዉን በኋላ ሁሉን ረስተዉ በፍቅር ሲቀርቡን ከቻልን እንደ ልጆቻችን

ምንም እንዳልተፈጠረ ቆጥረን በፍቅር መቀበል፤ ያን ካልቻልን ደግሞ ያጠፋዉን ስህተት በግልጽ በመናገርና ምክንያቱን መጠየቅ፣ በግልጽ በመወያየትና በመወቃቀስ፣ «ይቅር ለእግዚአብሔር» በማለት የዲያብሎስን የክፋትና የጥላቻ እንዲሁም የተንኮልና የበቀል ሕይወት ማስቀረት ነዉ ያለበን እንጂ «ለምን እንዲህ አደረገብኝ? ለምን እንዲህ ተናገረ?... ወዘተ» በማለት ለበቀልና ለጥል ከተነሳሳንና ይቅርባይነት ዉስጣችን ከሌለ የሕፃናትን(የልጆችን) ልብ አልያዝንምና ለእግዚአብሔር መንግሥት አንበቃም።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ሁለት

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: *የእዉነተኛ ደስታ መገለጫ የሆነዉ የሕሊና ሰላምና እርካታ በምን መንገድና ሕይወት ነዉ የሚገኘዉ?*

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: እዉነተኛ የሕሊና ሰላምና እርካታ የሚገኘዉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነዉ:: ይህም የሚገኘዉ አንዳች በአዳም ዘሮች ልዩነትና አድሎ ሳይደረግ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ ለሕሊና በመታመን ሲሚመላለስ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚታደል ነዉ እንጂ በገንዘብ፣ በሥልጣን፣ በእዉቀት፣ በክብር፣ በዝና የሚገኝ አይደለም:: ያማ ቢሆን ስንቱ ባለሀብት፣ ባለሥልጣን፣ ባለክብር፣ ባለዝና ሕሊናዉ የረካና ሰላም ያለዉ ይሆን ነበር:: እንዲሁም እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር፣ በቅንነት፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት የሚመላለስ ምስኪን የሕሊና ሰላምና እርካታ ባጣ ነበር:: ይሁንና እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰዉ ዉስጣዊዉን ሆነ ዉጫዊዉን ሕይወት ስለሚያዉቅ እዉነተኛዉን ሰላምና እርካታ የሚሰጠዉ እንደ ደረጃቸዉ ለእያንዳንዱ ቅን ሐሳቢና መልካም ሰሪ፣ እንዲሁም ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታማኝ ሆኖ ለሚመላለስ ሰዉ ነዉ::

በዓለም ላይ የሚታየዉ የማስመሰል ሰላምና እርካታ ግን ጊዜያዊና የዉሸት ነዉ:: ሰዎች በባዶነት ሕይወትና በተቅበዘበዘ ጠባይ እየተመላለሱ «ደስተኛ ነኝ፣ ሰላም ያለኝ ነኝ» እያሉ ራሳቸዉንና አድናቂዎቻቸዉን ያታልላሉ:: ለዚህም ነዉ ባዶነት የተሞላዉና ሰላምና እርካታ ያጣዉ ሕይወታቸዉ ለተለያዩ ሱሶችና አደንዛዥ ዕፅ የሚዳርጋቸዉ:: ይህ ሰላምና እርካታ የሚነሳዉ የርኩሳን መናፍስት(የሰይጣናት መንፈስ)፣ እነዚህ የተለያዩ ምሶቹና ሌሎቹ ግብሮቹ ሲቀርቡለት የሱስ ባሪያ አድርጎ ለማስቀረት ሲል በዚያ በሚያስጨንቃቸዉና ሰላምና እርካታ በሚያሳጣቸዉ ሰዓት የተለዩ ሱሶቹና ግብሮቹ ሲቀርቡለት ከሕሊናቸዉና ከአካላቸዉ ለተወሰነ ደቂቃና ሰዓት ይርቅላቸዋል:: ነገር ግን ወዲያ ተመልሶ ደግሞ ያስጨንቃቸዋል፤ ሰላምና እርካታ ያሳጣቸዋል:: በዚህ መልኩ ተስፋ ቢስ ሕይወት እንዲኖሩ አድርጎ ገንዘቡ ገንዘብ ሳይሆንላቸዉ፣ ሥልጣኑ ሥልጣን ሳይሆንላቸዉ፣ ክብሩ ክብር ሳይሆንላቸዉ፣ ዝናዉ ዝና ሳይንላቸዉ ባዶነት በተሞላ ሕይወት የእርሱ ባሪያ ሆነዉ እንዲኖሩ አድርጎ ለሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት የመከራና ስቃይ ሕይወት ይዳርጋቸዋል::

በተቃራኒ ደግሞ የዲያብሎስ መንፈስ የእግዚአብሔርን ሰዎች ሰላምና እርካታ ለመንሳት እንዲሁም ለማስጨነቅ ወደ ሕሊናቸዉና አካላቸዉ ሲገባ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በመልካም ምግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት አማካይነት የሚቋቋሙብትንና የሚያሸንፉብትን ኃይል ስለሚላበሱ አንዳች ነገር ሊያደርጋቸዉ አይችልም:: የሕሊና ሰላማቸዉና እርካታ እንደተጠበቀ ይቆያል:: እንዲሁም የእግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚያገኙት ጸጋና ኃይል ርኩሳን መናፍስትን ስለሚያቃጥላቸዉና ስለሚያዳክማቸዉ፤ ሰይጣናት በምድራዊ ሕይወታቸዉ ከሚገጥማቸዉ ጉስቁልና የስቃይ ሕይወት በተጨማሪ የእነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ምድራዊ ሕይወት ስቃያቸዉንና መከራቸዉን የሚያበዛባቸዉ ስለሆነ፣ ሰይጣናት የእነዚህ ሰዎች መጥፋት ነዉ ፍላጎታቸዉና በዓመፃ

ሰዎች ላይ እያደሩ የተለያየ ጥቃትና ጥፋት ለማምጣት የሚቻላቸዉን የክፋትና የተንኮል ተግባር በተለያዩ አገልጋዮቻቸዉ ላይ በማደር የሚያስፈጽሙት፡፡ ለዚህም ነዉ በዓለም ላይ ለዘመናት የእግዚአብሔር ሰዎች የተለያየ ጥቃትና በደል ሲፈጸምባቸዉ የኖረዉና በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ቦታ አግኝተዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ መፈጸምና ማስፈጸም ያልቻሉት፡፡

ባጠቃላይ ከላይ እንደተገለጸዉ እዉነተኛ ሰላምና እርካታ የሚገኝበት መንገድ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባርና በእዉነተኛ ሕይወት ነዉ፡፡ የደስተኛነት ሕይወት መገለጫዉም ባልተቅበዘበዘና ባልተጨናነቀ ሕይወት በመመላለስና እርካታና ሰላም በሞላዉ ሕሊና መኖር ነዉ፡፡ በዚህ ሕይወት የሚመላለስ ሰዉ በምኞት አይቃጠልም፣ ባገኘዉ ነገር እየረካ የበለጠዉን ለመስራት የሚተጋ ነዉ፡፡ አንዳች በሕይወቱ ተስፋ አይቆርጥም፡፡ ምክንያቱም ታላቅ ተስፋዉን ሰማያዊ ሕይወት እያሰበ በሰይጣናት ሆነ በሰዎች አማካይነት የሚመጣበት ፈተናና መከራ በትዕግስትና በጽናት ስለሚወጣዉ ነዉ፡፡

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ በመንፈሳዊ ሆነ በሥጋዊ ሕይወትና አገልግሎት ዉስጥ እያለን ሕይወታችን ሆነ አገልግሎታችን ምን መሆን አለበት?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__፡ ማንኛዉን ሰዉ በማንኛዉም ሕይወት ዉስጥ ሆነ አገልግሎት ዉስጥ ያለ ሰዉ ቅንና እዉነተኛ መሆን አለበት፡፡ በተለይ በመንፈሳዊ ሆነ በሥጋዊ አገልግሎት ዉስጥ ያለ ሰዉ ለሌሎች አርአያ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም በተናገረዉ ቃል ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ ባጠቃላይ መሪያችንን መንፈስ ቅዱስ አድርገን እንደ ርግብ የዋህ እንደ እባብ ልባም ሆነን፣ ትህትናንና ፍቅርን ተላብሰን፣ በቅንነትና በእዉነት ልንኖርና ልናገለግል ይገባል፡፡ በዚህ ሕይወት ነዉ መልካም ስራ ልንሰራና ጣፋጭ ፍሬ ልናፈራ የምንችለዉ እንጂ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን የምንመላለስ ከሆነ በዚህ ስሜታችን መንፈስ ቅዱስ ስለማይመራንና የዲያብሎስ መንፈስ ስለሚቆጣጠረን የምናወራዉ ሌላ ተግባራችን ሌላ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የምንፈልገዉ ፍሬ መልካም የምናፈረዉ ፍሬ ደግሞ መራራ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕይወታችን ሆነ አገልግሎታችን ማስመሰልና ሽንገላ የሞላበት ይሆናል፡፡ ለዚህ ነዉ በፖለቲካዉ ሕይወት ዉስጥ መልካም ለመስራት፤ እኩልነትን፣ ነጻነትን፣ ፍትሕና ፍትሐዊነትን፣ መልካም አስተዳደርን ለማምጣትና ለመፈጸም ተነሳስተዉ ወንበሩ ላይ ሲቀመጡ ደግሞ ተቃራኒዉን የሚፈጽሙት፡፡ ምክንያቱም መሪያቸዉ ያደረጉት የሥጋና የደም ስሜታቸዉን ስለሆነ፣ ይህን ስሜት ደግሞ ርኩሳን መናፍስት እንደፈለጉት ስለሚጠቀሙበት ፈቃዳቸዉን ይፈጽሙበታል፣ ያስፈጽሙበታል፡፡ እግዚአብሔር ለዓይን ቅጽበት ያህል ከሕሊናችን ወይንም ከነፍሳችን እንደማይለየንና ጠብቆቱን፣ መግቦቱን እንደሚያደርግልን ሁሉ፤ ርኩሳን መናፍስትም(ሰይጣናትም) እኛን ለመፈታተን ከሕሊናችንና ከአካላችን ለዓይን ቅጽበት ያህል አይለዩንም፡፡ ሌላዉ ቀርቶ በሕሊናችን እያሰብነዉ ያለዉን ስለሚያዳምጡ በሐሳባችን ገብተዉ ሕሊናችን በሚቀበለዉ መልኩ ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን ያስፈጽሙናል፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ ቀና የምናስብና እዉነተኞች ከሆን ሕይወታችንንም በትህትናና በፍቅር የምንመራ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ስለሚያድርብን የርኩሳን መናፍስት መንፈስ ቦታ አያገኝም፤ እኛንም ለማሸነፍ ኃይል አይኖረዉም፡፡

በመልካም ሕይወታችንና በእዉነተኛ አገልግሎታችን ቅናት የሚያድረበትና ሁል ጊዜ ለጥፋት የሚሰለፈዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ በቀጥታ ራሱና በሥጋ በተገለጹ አገልጋዮቹ ሰዎች አማካይነት ፈተና ስለሚያመጣብን ሁል ጊዜ በትጋት ልንጸልይና በጸሎታችንም እግዚአብሔርን «ደካሞች ነንና ወደፈተና አታግባን» ልንለዉ ይገባል እንጂ በመንፈሳዊነት ሕይወት ጀብደኝነት የለም፤ አያስፈልግምም:: ለዚህም ነዉ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶት በመዋዕለ ሥጋዊዉ መከራ እንደሚደርስበት፣ እንደሚሰቀል እያወቀና ለሐዋርያቱም አስቀድሞ ነግሯቸዉ ሳለ፤ በሥጋ ተገልጾ ፍጹመ ሰዉ ፍጹም አምላክ የሆነዉ ለእኛ አርአያ ሊሆን ነዉና፤ በመጨረሻዉ ሰዓት ያ የመከራና የስቅላት ጽዋ እንደማያልፍ ግድ የሚፈጽመዉ መሆኑ እያወቀ፤ «አባት ሆይ ፈቃድህ ከሆነ ይህችን ጽዋ ከኔ አሳልፍ ነፍሴ ተጨነቀች» በማለት የጸልየዉ:: እርሱ እንዲህ ካስተማረን እኛማ ፍጡሮቹ «ይህን ጽዋ ከእኔ አሳልፍ ነፍሴ ተጨነቀች» ማለት ብቻ ሳይሆን ያለብን፤ «ከነጭራሹኑ ፈተና አታምጣብን»ማለት ነዉ የሚጠበቅብን:: በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 4፣ 8እስከ13 ላይ እንደተገለጸዉ ዲያብሎስ ከቅዱሳት መጽሐፍት ጥቅስ ጠቅሶ «ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፣ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸዉ ያነሡሃል ተብሎ ተጽፋአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፣ ከዚህ ወደ ታች ራስህን ወርዉር አለዉ:: ኢየሱስም መልሶ:- ጌታን አምላክህን አትፈታተን ተብሎአል አለዉ:: ዲያብሎስም ፈተናዉን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜዉ ከእርሱ ተለየ» ይላል:: ከዚህ የምንረዳዉ ሁሉ እንደሚደረግልንና ጥበቃም እንደሚደረግልን ብናዉቅም ራሳችንን ግን በራሳችን ፍላጎት ለፈተና አሳልፈን መስጠት እንደሌለብን ነዉ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን ያዉቃል፤ ነገር ግን የዲያብሎስን ፍላጎት አልፈጸመም፤ ይልቁኑ እርሱም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅስ በመጥቀስ ነዉ ያሳፈረዉ::

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ግድ መከራ መቀበል ካለብን ደግሞ የእርሱን አርአያ ተከትለን የሚመጣብንን ማንኛዉንም ፈተናና መከራ በጸጋና በአኰቴት ልንቀበል ይገባል እንጂ «ተመሳስሎ ኖሮ» በሚለዉ የአሕዛብ መመሪያ ተመርተን ከእግዚአብሔር እዉነት ወደ ኋላ ማለት የለብንም:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር አማኝና አገልጋይ ለመሆን ስለ እዉነት ራሳችንን በመካድና በመጥላት ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ልንመሰክር ይገባል:: ለዚህ ነዉ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ መምህራን፣ ጻድቃን የመሳሰሉት የአምላካቸዉን ፈለግ ተከትለዉ የተለያዩ መከራዎችን በመቀበል በድል አክሊል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገቡት:: እንዲሁም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእኔ ይልቅ ቤተሰቡን፣ ልጆቹን፣ ሚስቱን፣ ዘመዱን፣ ጓደኛዉን፣ ስራዉን፣ ሥልጣኑን፣ ክብሩን፣ ዝናዉን፣ ጥቅሙን ... የሚወድ፤ ለእኔ ሊሆን አይገባም» በማለት ከእግዚአብሔር በላይ ማንንም ማስቀደም እንደሌለብን በግልጽ የተናገረዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: እግዚአብሔር በግልጽ ሐሰተኛ ነብያትን «ሐሰተኛ ነብያት ናቸዉ» ይላል፤ ሐሰተኛ ወንጌላዉያንን «ሐሰተኛ ወንጌላዉያን ናቸዉ» ይላል፤ ሐሰተኛ ሰባኪያንን «ሐሰተኛ ሰባኪያን ናቸዉ» ይላል፤ ሐሰተኛ መምህራንን «ሐሰተኛ መምህራን ናቸዉ» ይላል፤ ሐሰተኛ አገልጋዮችን «ሐሰተኛ አገልጋይ ናቸዉ» ይላል፤ ሐሰተኛ እምነትን «ሐሰተኛ እምነት ነዉ» ይላል፤ ባጠቃላይ በግልጽ «ሐሰቱን ሐሰት፤ እዉነቱን እዉነት ነዉ» ይላል:: የእግዚአብሔር አገልጋዮች ደግሞ እንደ

እግዚአብሔር በግልጽ «ሐሰቱን ሐሰት፤ እዉነቱን እዉነት ነዉ» አይሉም:: የእርሱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እስከ ሆኑ ድረስ ለምን የአምላካቸዉን ፈለግ አይከተሉም?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: እግዚአብሔር በባሕርይዉ ሁሉን አዋቂና ፍጹም ነዉ:: ስለዚህ «ሐሰተኛዉን ሐሰተኛ ነዉ፤ እዉነተኛዉን እዉነተኛ ነዉ» ቢል ፈጽም ትክክልና እዉነት ነዉ:: ወደ ሰዎች ስንመጣ ግን ብዙዎቻችን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን ስለምንመላለስና ለሥጋችን ፈቃድ ስለምናደላ ልንሳሳትና እርግጠኞች ሳንሆን እንችላለን:: ለዚህም ነዉ የእግዚአብሔር እዉነተኛ ነቢያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን የተለያየ ስያሜ እየተሰጣቸዉ ለተለያየ መከራና ስቃይ የተዳረጉት:: እዉነተኞች ሳሉ ሐሰተኞች ተብለዋል፤ ከእግዚአብሔር ሆነዉ ሳለ ከዲያብሎስ ተብለዋል:: እንኳን እነሱ ራሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም በምድር ላይ ተገልጾ በሚያስተምርበትና የተለያዩ ፈዉስና ተአምራት ሲያደረግ «ሐሰተኛ ነዉ፤ ከእግዚአብሔር አይደለም ...ወዘተ» በማለት ለሕሊናችን ብዙ የሚዘገንን ስያሜ ተሰቶት ነበረ:: ለዚያዉም «የእግዚአብሔር አገልጋይና የሕዝብ እረኛ ነን» በሚሉ ጭምር:: በመሆኑም ፍጹም በመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመራ ሰዉ ካልሆነ በስተቀር «እዉነተኛዉን እዉነተኛ፣ ሐሰተኛዉን ሐሰተኛ » ለማለት ብቃት የለዉም:: በዘመናችንም «እዉነተኛ አገልጋይና የምእመናንና የሕዝብ አገልጋይና እረኛ ነን» የሚሉት ናቸዉ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችንና መልእክተኞችን እያሳደዱ ያሉት፤ የተለያየ ስያሜ እየሰጡ የተለያየ መከራና ስቃይ እንዲሁም ግፍና በቀል የሚፈጽሙባቸዉ::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት እዉነተኛ አገልጋዮችም ቢሆኑ በተኩላዉ ዓለም ዉስጥ ስላሉ ተኩላዉን ዓለም ለማሸነፍ « እንደ እባብ ልባም፣ እንደ ርግብ የዋህ» ሁኑ ብሎ አምላካችን በመዋዕለ ሥጋዌዉ ስላስተማረና ስላዘዘ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሙሉ እዉነት በልባምነትና በየዋህነት፣ በእዉነትና በቅንነት፣ በትህትናና በፍቅር መግለጽና ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል:: ሐሰተኞችንም ሐሰተኝነታቸዉን የሚያሳይና የሚገልጽ እዉነተኛ ማስረጃና መረጃ በማቅረብ ማጋለጥና ባለማወቅ በክህደት ሆነ በመንፍቅና እንዲሁም በዓመፃ እምነትና ሕይወት የሚመላለሱት ወገኖችን ደግሞ ወደ እዉነተኛ እምነትና ሕይወት ማምጣት ነዉ የሚጠበቅባቸዉ እንጂ፤ «ተመሳስለህና ሕሊናህን ሸጠህ አገልግል፣ ኑር» የሚለዉ የአሕዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች የሚያራምዱትን የማስመሰልና የሸንገላ ንግግርና ተግባር መከተል የለባቸዉም:: ምክንያቱም ነቢያት ሆኑ መምህራን እንዲሁም ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣ ከከሃድያንና ከአረማዉያን እንዲሁም ከአስመሳይ አገልጋዮች ፈተናና ጥቃት፣ መከራና ስቃይ ለመዳን የማስመሰል ትምህርትና የሸንገላ ሕይወት ማሰየትና ራሳቸዉን ከተለያየ ፈተናና ጥቃት መጠበቅ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች ስለሆኑ እግዚአብሔር የሚያናግራቸዉንና የሚያሰራቸዉን ነበር የሚናገሩትና የሚሰሩት የነበረዉ:: ለዚህም ነዉ ሕሊናቸዉን ባለመሸጣቸዉና ስለ እዉነት ካለማስመሰልና ካለሸንገላ በመመስከራቸዉ ለተለያየ መከራና ስቃይ የተዳረጉትና በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የድል አክሊልና የቅድስና ማዕረግ ያገኙት:: በእነሱ ቦታ የተተኩት አገልጋዮችም የእነሱን ፈለግ ተከትለዉ ሊያገለግሉ ይገባል እንጂ ከሃዲያን መንግሥታትን ሆነ ሐሰተኛ መምህራንን በመፍራት «ጨለማዉን ብርሃን ነዉ፣ የሞቱን መንገድ የሕይወት መንገድ ነዉ፣ ክህደቱን እምነት ነዉ፣

ዓመፃዉን መታዘዝ ነዉ፣ ሐሰቱን እዉነት ነዉ፣ ሰፊዉን ጠባብ ነዉ፣ ርኩሰቱን ቅድስና ነዉ... ወዘተ» የሚሉ ከሆነ እነሱ እዉነተኛ አገልጋዮች ሳይሆኑ ሐሰተኞች፣ አስመሳዮች፣ ቅጥረኞች ናቸዉ ማለት ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የሰዎች የእዉቀትና የትጋት እንዲሁም ብቃት የተለያየ እንደሆነ ይታወቃል:: አንድ ሰዉ በትምህርት ደረጃዉ ጥሩ ዉጤት ካላመጣና ጥሩ ደረጃ ላይ ካልደረሰ ሰነፍ ነዉ ማለት ይቻላል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት እያንዳንዱ ሰዉ የራሱ የሆነ የተለየ ተሰጥኦ አለዉ:: ትልቁ በተሰጥኦ ዉስጥ ሆኖ መገኘት ነዉ:: አንዳንድ ሰዉ በትምህርቱ ደካማ ሊሆን ይችላል፤ በሌላ በኩል በተለየ ሙያ ደግሞ የተዋጣለት ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ በአንዱ ያልተሳካለት ሰዉ በዚያ ደካማ ቢሆን ሰነፍ ነዉ ማለት አንችልም:: ምክንያቱም በሌላዉ በራሱ ተሰጥኦ ጠንካራ ሆኖ ተገኝቷልና:: በመሆኑም አንድ ሰዉ ለተሰለፈለት እዉቀትና ተግባር የራሱን የመጨረሻዉን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል እንጂ ሁሉም የመጨረሻዉን አንደኛ ማዕረግ ማግኘት አለበት ማለት የለብንም:: ነገር ግን ከእያንዳንዱ በትምህርቱ ሆነ በስራዉ የሚጠበቅበትን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለበት:: ያ ካልሆነለት ግን ስጦታዉን መፈለግና በተሰጥኦ ብቃቱን ማሳየት ይጠበቅበታል:: በተሰማራበት የስራ መስክ ስኬታማ የሆነ ሰዉ ሙያዉ ምንም ይሁን ምን እርሱ በሙያዉ ሊቅና አዋቂ እንዲሁም ምሁር ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ») በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል አራት የጸሐፊዉ መልእክት በገጽ 70 ላይ «የእግዚአሔርን ፈቃድ ባለማስተዋልና ባለማወቅ በኃጢአት ስራ የምንመላለስ ሰዎች፤ ያለፈዉ የዓመጻ ዘመናችን ይብቃን:: ነዉሩን እንደ ክብር፣ ኃጢአቱን እንደ ታላቅ ስራ፣ መታዘዙን እንደ ዉርደት፣ ትዕቢቱንና ዓመጻዉን እንደ ጀግንነት፣ ርኩሰቱን እንደ ቅድስና ቆጥረን የተመላለስንበት ሕይወት ይብቃን:: <u>እድሜ ሰቶን ለመልካሙ ዘመን ከደረስን ይህ እየፈጸምነዉ ያለዉ የኃጢአት ተግባር በእዉነተኛ ሕሊናችን ስንመለከተዉ «በዉኑ እኛ ሰዎች ነበርን ወይ እንዲህ የሰይጣናትን ተግባር የምንፈጽመዉ? » ብለን ራሳችንን የምንታዘብ እንሆናለን::</u>

አሁን ግን ኃጢአቱ ጽድቅ፣ መልካም፣ ታላቅ መስሎን እንፈጽማለን:: ስለዚህ <u>እግዚአብሔር በቁጣዉ ገስጾን ሳይቀጣን በፊት ከኃጢአት ተግባርና ንግግር ተለይተን ስላለፈዉ በደላችን ንስሐ እንግባ</u>:: <u>እዉነትን ያልተቀበልን ደግሞ እዉነትን ተቀብለን ለሰማያዊ መንግሥት በሚያበቃን ሃይማኖት ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመሆን እንመላለስ</u>::» ይላል፤ ታዲያ ወደ ሕሊናችን ለመመለስ ግድ መልካም ዘመን ያስፈልገናል ወይ? እንዲሁም እኛ ሰዎች ሁለት ሕሊና ነዉ የያዝነዉ ማለት ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: መልካም ለመስራት ሆነ ለመናገር እንዲሁም ለማሰብ ዘመንና ወቅት አልተለየም:: የሰዉ ዘር ሁሉ በነጻ ሕሊናዉ የማመዛዘንና የማገናዘብ ሥልጣን

ስለተሰጠዉና ሕያዉ ነፍሱ እግዚአብሔርን መምሰል ስለተላበሰች ሁል ጊዜ መልካም መስራት፣ እዉነትን መናገር፣ ቀና ማሰብ ይጠበቅበታል። ከላይ ለማለት የተፈለገዉ አሁን ያለነዉ ትዉልዶች በተለያየ መንገድ ማለትም በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን (ማስ ሚዲያ)፣ በትምህርት፣ በፖለቲካ ሕሊናችን ስለተበከለና «የትኛዉ ነዉ የእግዚአብሔር ፈቃድና የሚወደደዉ? የትኛዉ ነዉ የዲያብሎስ ፈቃድና በሰይጣናት መንፈስ የሚከናወን?... ወዘተ» የሚለዉን በሚገባ አለየንም። ለዚህም ነዉ በትዕቢት ሕይወት ስንመላለስና እብሪተኛ ስንሆን ልክ እንደ ታላቅና ጀግና ሰዉ ታይተን በሰዎች ዘንድ የምንገነዉና የምንደነቀዉ። ነገር ገን በእዉነተኛ ሕሊና ዉስጥ መሪያችን መንፈስ ቅዱስ ሲሆንልን ትዕቢተኛነቱና እብሪተኛነቱ ከሰይጣናት ጋር እኩል የሚያስቀጥረንና  የሚያስፈርድብን የደካሞችና የሰነፎች ጠባይና ሕይወት መለያ ነዉ።

እንዲሁም በዉሸት፣ በተንኮል፣ በክፋት፣ በበቀል ተግባርና ሕይወት ስንመላለስ፤ በብልጠት ሕይወት የተመላለስንና ታላቅ ተግበር የፈጸምን ጀብደኛ አድርገን ራሳችንን እንቆጥራለን፤ እናስቆጥራለን። ነገር ግን በእዉነተኛ ሕሊናችን ስንመለከተዉ የዲያብሎስ አገልጋይ ወይንም መሳሪያ ሆነን የሰይጣናት ፈቃድ እየፈጸምንና እያስፈጸምን ነዉ። ለዚህም ነዉ ብዙዎች በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ አስመሳይ አገልጋዮች የራሳቸዉን የዉሸት እዉነት ፈጥረዉ የዲያብሎስ ፍሬ የሆኑትን ሰዎችን መከፋፈላቸዉና ጥላቻ መፍጠራቸዉን፣ ለበቀልና ለበደል ማነሳሳታቸዉን፣ የሥልጣን እድሜያቸዉን የሚያስረዝምላቸዉ የጥበብ ስራ አድርገዉ  የሚቆጥሩት።

ሌላዉ ደግሞ በየጥንቆላ፣ በየዛሩ፣ በየሚርቱ፣ በየአስማቱ፣ በየመተቱ፣ በመሳሰሉት ፍጹም የዲያብሎስ ስራ በነገሠባቸዉ ቦታ ላይ የሚቀርበዉ ማጓራት፣ መጮህ፣ መንቀጥቀጥ፣ መንዘፍዘፍ፣ መፈራገጥ፣ ጎንበስ ቀና ማለት፣ እንጣጥ እንጣጥ ማለት፣ መዳራት፣ መተሻሸት፣... ወዘተ ተግባር አሁን ደግሞ በዘመናዉ መልክ ተሻሽሎና በተለያዩ ማጀቢያዎች ታጅቦ በተለያዩ መድረኮችና በብዙኃን መገናኛ እንደ ታላቅ ጥበብና ስራ ተቆጥሮ በዳንኪራና በዘፈን መልክ ሲቀርብልን እንመሰጣለን፣ እናደንቃለን፣ እናገናለን። ነገር ግን በእዉነተኛ ሕሊናችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነን በምንመለከትበት ሰዓት እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍሳችን በሥጋ ተገልጣ እያበደች መሆኑንና አጋንንት ደግሞ ነፍሳችንን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረዋት እየተዝናኑባት መሆኑን እናስተዉላለን።

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆችና አስካሪ መጠጦች ስንሰክር የተለየ ደስታ ያገኘን እየመሰለን ያልተገቡና ርኩሰት ተግባሮችን እንፈጽማለን። ነገር ግን በእነዚህ አደንዛዥ ዕፆችና አስካሪ መጠጦች አማካይነት ርኩሳን መናፍስት ነፍሳችንን በማዳከም ኃይልን ካሳጡ በኋላ ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጣጠሩን የፈለጉትን ተግባር ያስፈጽሙናል። ለዚህ ነዉ ለሕሊናችን የሚዘገንንና እንኳን በተግባር ለመፈጸም አይደለም ለማሰብ የሚከብዱ ተግባሮች በአደንዛዥ ዕፆችና በአስካሪ መጠጦች የሰከሩ ሰዎች የሚፈጽሙት። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ሰይጣናት ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጧጠሯቸዉ የሚያሳስቧቸዉን ሁሉ ወደተግባር ይለዉጣሉ፤ ያስለዉጣሉ። ወደ እዉነተኛ ሕሊናቸዉ ሲመለሱ ግን ያ ድርጊታቸዉ ሁሉ ስህተት መሆኑን ያዉቃሉ። በዚህ ምክንያት ሕሊናቸዉ የተረበሸና ሰላም ያጣ

ይሆናል፡፡ ሰይጣናት ፍላጎታቸዉ እነዚህን ሰዎች በምድርም አጎሳቁለዉ ሰላምና እርካታ የሌላቸዉ አድርገዉ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ማዘጋጀትና ከገቡበት ሱስ እንዳይወጡ የሚቻላቸዉን ጥረት ሁሉ ማድረግ ነዉ፡፡

ወደ አለባበሳችንና ወደ አገላለጻችን ስንመጣ ደግሞ ቀደም ያሉት ወላጆቻችን እግዚአብሔርን በመፍራት ይመላለሱ ስለነበረ እንኳን በተግባር በሚፈጸሙ ኃጢአት በዝሙቱ ሊመላለሱ ቀርቶ የማይሆን አለባበስ አይለብሱም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሕሊናቸዉ ስለማይፈቅድላቸዉና ነዉሩንና ክብሩን በሚገባ መለየት ስለቻሉ ነዉ፡፡ አሁን ያለነዉ ትዉልዶች ግን አዉሮፓዊነት ሆነ አሜሪካዊነት መሆን የታላቅነትና የቅድስና ደረጃ እየመሰለን ነዉር የሆነዉንና እግዚአብሔርም በግልጽ «ይህ አይነት አለባበስ በእኔ ዘንድ ጥል ነዉ» እያለን ሕሊናችንን በማደንደን የከበረዉን ገላችንን ገላልጠን ስንሄድ አንዳች አናፍርም፤ በተወጣጠረ ሱሪ አካላችንን እያሳየን ወንዱን ለዝሙትና ለሴሰኛነት ስናሰለፍ አንዳች አይሰማንም፤ ይልቁኑ ታላቅ ጀብዱ ያደረግን ነዉ የሚመስለን፡፡ ሴቱም ሆነ ወንዱ ጠጉራችን ተንጨባሮ ስንሄድ የሥልጣኔና የዘመናዊነት ብቃት ይመስለናል፡፡ ወደ እዉነተኛ ሕሊናችን ብንመለስ እያደረግን ያለዉ ሁሉ ነዉር መሆኑንና የከበረ ገላችንንም እያራከስነዉ እንዲሁም እያስመለክነዉ መሆኑን እናስተዉልና ገላችንን በሥርዓቱ እናከብረዉ ነበር፡፡ እንዲሁም መንጨባረሩም የእብደት ምልክት አድርገን በአገባቡ እንሰራዉና እንስተካከለዉ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በግልጽ በኦሪት ዘዳግም22 ቁጥር5 ላይ« ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤**<u>ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነዉ</u>**፡፡» ይላል፤ በዚህ ምክንያት ቃሉን ጠብቀን «በእኔ ዘንድ የተጠላ ነዉ» ያለዉን አለባበስ ትተን እግዚአብሔር በሚወደዉ የጨዋና ሥርዓት ባለዉ አለባበስ እንገለጥ ነበር፡፡

ወደ ጋብቻ ሕይወትም ስንመጣ በሕሊናችን የዝሙት መንፈስ ስለነገሠ ከጋብቻ ዉጭ ከተለያዩ ሴቶች ጋር ዝሙት መፈጸም ታላቅ ተግባርና ጀብደኝነት አድርገን እንቆጥራለን፡፡ እንዲሁም በጋብቻ ላይ መማገጥና ማመንዘር እንደ እርፍና(ብልጠት) ተግባር እንቆጥረዋለን፡፡ ወደ ሕሊናችን ስንመለስ ግን እንኳን በግልጽ ዝሙትን መፈጸምና ማመንዘር ቀርቶ ሴትን ዓይቶ ለዝሙት መመኘት ራሱ የሚያስጠይቅ በመሆኑ በደል አድርገን ስለምንቆጥር ስለሐሳባችን እንኳ በሕሊናችን እንጸጸታለን፡፡ የዝሙትና የአመንዝራነት ሕይወት የኃጢአት ሕይወት መሆኑን ስለምናዉቅ ራሳችንንና ክብራችንን እስከ ምድራዊ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ እንጠብቃለን እንጂ አንልከሰከስም፡፡ ባጠቃላይ ሲታይ አንዷ ሕሊናችን(ነፍሳችን) ናት በተለያየ ወቅት ጠባያዋንና አቋሟን የምትለዋዉጠዉና በነጻ ፈቃዷ ለመልካምም ይሁን ለመጥፎ ሕይወት የምትሰለፈዉ እንጂ ሁለት ሕሊና(ነፍስ) የለንም፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**፡ ሰዎች ሲጃራ፣ ጫት፣ አደንዛዥ ዕፆች... የመሳሰሉት አካላቸዉን እንደሚጎዷቸዉ እንዲሁም ገንዘባቸዉን እንደሚያባክን እያወቁ ስለ ምን ያጨሳሉ? ይቅማሉ? ይጠቀማሉ?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: እነዚህ የሚያጨሱና የሚቀሙ ሰዎች ሲጀምሩት የተለያየ ምክንያት ሊኖራቸዉ ይችላል። አንዳንዶች እንደ ሥልጣኔና እንደ ታላቅ ተግባር በመቁጠር፤ አንዳንዶች ሲጨንቃቸዉና ሕሊናቸዉ ሲረበሽ ከዚያ የሚገላግላቸዉ እየመሰላቸዉ፤ አንዳንዶች ሲበሳጩና የሕሊና ሰላማቸዉን ሲያጡ፤ ባጠቃላይ ሰዎች የሕሊና እርካታና ሰላም እንዲሁም እረፍት ሲያጡ ነዉ ለተለያዩ ሱሶች የሚዳረጉት። ታዲያ በዚህ ሱስ ዉስጥ ዋናዉ ተዋናዮች ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ናቸዉ። ምክንያቱም በአዳምና ሔዋን ዘሮች ላይ ሁሉ ለመፈታተን ወደ እያንዳንዱ ሰዉ ሕሊና ዉስጥ ይገባሉ፤ ይወጣሉ። ራሱን የገዛ ሰዉ እነዚህ ፈተናዎችን ስለሚቋቋም ወደ ሕሊናዉ የሚመጣዉን ክፉ ሐሳብ ይቃወመዋል፤ ወደ ተግባርም አይለዉጠዉም፤ በጽናትና በትዕግስት ያልፈዋል። ሰይጣናትም በዚህ ያፍራሉ፣ ይበሳጫሉ። እግዚአብሔር ደግሞ ለትዕግስተኞቹና በጽናት ፈተናዉን ለሚያልፉ ኃይልንና ጸጋን ያጎናጽፋል። ራሳቸዉን በሚገባ ያልገዙ ሰዎች ግን ይህ በርኩሳን መናፍስት ወደ ሕሊናቸዉ የሚመጣዉን የማስጨነቅ ሆነ የክፋት ሐሳብ የተለያየ የሱስ ምሱን በማቅረብና የክፋት ሐሳቡንም ወደ ተግባር በመለወጥ የእርሱ ባሪያና ተገዥ ይሆናሉ። ሰይጣናትም በዚህ ይደሰታሉ፤ ለበለጠዉ ጥፋትና ጥቃት ይዘጋጃሉ። እግዚአብሔር ደግሞ በእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ያዝንባቸዋል፣ ጸጋዉ ከእነሱ ይርቃል።

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: ርኩሳን መናፍስት ሁሉንም ሰዉ የሚፈታተኑ ከሆነ ወደ እያንዳንዱ ሰዉ ሕሊና በመግባት ሰላምና እርካታ ሲነሱና እንዲሁም ሲያስጨንቁ ምን ማድረግ አለብን?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: ይህች ምድር በመጀመሪያ የርኩሳን መናፍስት መኖሪያ የነበረችና አዳምና ሔዋን በገነት አትብሉ የተባሉት በመብላታቸዉና ዓመፃን በመፈጸማቸዉ ምክንያት ስለሆነ ወደዚህች ጉስቁልና ሕይወት ወደ ሞላባት ምድር ዉስጥ የገቡት፤ እኛም በእነሱ ምክንያት ለመጥራት፣ ለመንጠር፣ ለመንጣት፣ እንዲሁም ለመቀጣት ጭምር ስለሆነ በዚህች ምድር የምንገለጠዉ፤ ከምድራዊ ዘመናችን በኋላ ከሚኖረን ዘመን አንጻር የዚህች ምድር የፈተና ዘመናችን እጅግ እጅግ አነስተኛ የሆነ ከዐይን ቅጽበት እድሜ የማይበልጥ ስለሆነ፤ ርኩሳን መናፍስት የሚያመጡብንን የተለያየ ፈተና በተሰጡን መከላከያና ኃይል ማግኛ መሳሪያዎች በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በመልካም ተግባር፣ በቅን ሐሳብ፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ በጠበል፣ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ፣ በቅዱስ ቁርባን ድል ልናደርጋቸዉና እነሱንም ልንቀጣቸዉ፣ ልናቃጥላቸዉ እንችላለን። ሰይጣናት ሕሊናችንን ሰላምና እርካታ ለመንሳት ሆነ ለማስጨነቅ የሚፈቀድላቸዉ ለደቂቃዎች ቢበዛ ደግሞ ለሰዓታት ከዛም ከበለጠ ለቀናት ብቻ ስለሆነ ያንቺን ጊዜ በእረፍት ወይንም በእንቅልፈ ወይንም በተለያዩ መልካም መዝናኛ ወይንም በተለየ ስራ ማሳለፍ ይኖርብናል፤ እንዲሁም መላ ሰዉነታችንን በመታጠብ ያንቺን ደቂቃ ወይንም ሰዓት ማለፍ ይኖርብል እንጂ በፈተናቸዉና በማስጨነቃቸዉ ተሸንፈን ለተለያዩ ጎጂ ሱሶች የምንጋለጥ ከሆነ ሕሊናችንን በመቆጣጠር ባሪያቸዉ አድርገዉን ከእግዚአብሔር ልጅነትና መንግሥት ሊለዩን ይችላሉ።

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተላለፈዉ ላይ በተለያዩ ክፍሎች ዉስጥ ማንኛዉም በሽታ ምንጩ ርኩሳት

መናፍስት መሆናቸዉን ይገልጻል:: በዘመናዊዉ ሕክምና «ቫይረስ፣ ባክቴሪያ፣ ጀርም፣ ካንሰር፣ አላርጂክ፣ አስም፣ ኤድስ፣ ጋንግሪን፣ ደም ብዛት፣ ስኳር፣ ደም ግፊት፣ ጉንፍን ፣... ወዘተ» ተብለዉ የተለያዩ ስያሜዎች ስለሚሰጧቸዉ፤ ትዉልዱ የእግዚአብሔርን ሆነ የሰይጣናትን ህልዉና በመካድ ተስፋዉም ሥጋዉያን ላይ አድርጎ ይኖራል:: ለዚህ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የእዉቀት ሆነ የጥበብ ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነዉ:: ሰዎች ግን የእግዚአብሔር መሳሪያ በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ስለዚህ ለመልካም ተግባር የሚዉል እዉቀት ሆነ ጥበብ እግዚአብሔር የፈቀደዉና ሰዎችም ከጉስቁልና ሕይወት እንዲገላገሉ ቢያምኑትም ባያምኑትም ስለ ቸርነቱና ስለ ፍቅሩ ሲል እዉቀቱንና ጥበቡን ለሰዉ ዘሮች ይገልጻል:: እዉቀቱና ጥበቡን በአግባቡ ከተጠቀሙበት ማንም ሰዉ አይጠየቅበትም:: በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ደግሞ ያ ለመጥፎ ነገር ያዋለዉ ሰዉ ይጠየቅበታል፤ ዋጋም ይከፍልበታል::

**ወደ ጥያቄዉ አስተያየት ስመጣ** ዓለም በክህደት ሕይወት ዉስጥ ስለሚመላለስና «የሰዉ ዘሮች የተገኙት በዝግምተኛ ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ» በማለት ማፈሪያና ያበደ አእምሮ መያዙን በራሱ ላይ ቢያስመሰክርም፤ ለየዋሁ ሕዝብ ሲል እግዚአብሔር የተለያዩ የሕክምና እዉቀቶችንና ጥበቦችን ለዓለም ገልጿል:: ዓለም ግን በራሱ መጠበብና እዉቀት የፈጠረና ያገኘ መስሎት ራሱን ያመጻድቃል፤ ከዚያም ባለፈ ይታበያል:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል የሚታወቀዉ ሕክምናዉ ሆነ መድኃኒቱ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ ነዉ ሊፈዉስ ሆነ ሊያድን የሚችለዉ:: በተቀረ ግን የፈለገዉ ዓይነት ሕክምና ሆነ መድኃኒት ይደረግ ሕክምናዉ ሕክምና መድኃኒቱ መድኃኒት እንዲሆንና በሽተኛዉ እንዲድን እግዚአብሔር ካልፈቀደ በስተቀር ማንም ሰዉ ከበሽታዉ ሆነ ከሞት አይድንም:: ዓለም ያላስተዋለሁ የእግዚአብሔር እዉነታ ይህ ነዉ:: በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ እንደተገለጸዉ የበሽታዎች ምንጭ ሰይጣናት ናቸዉ:: ከቫይረስ በላይ እጅግ የረቀቁ ስለሆነ በተለያየ መልክ በአካላችን ዉስጥ እየተገለጹ ጉዳትና ጥቃት ያደርሱብናል:: ሲፈልጉ በዐይንና በማጉያ መነጽር በሚታይ አካል፣ ሲፈልጉ በዐይን ሆነ በተለየ መሳሪያ መታየት በማይቻልበት በረቂቅ አካል ተገልጸዉ ጉዳትና ጥቃት ያደርሱብናል::

ታዲያ እግዚአብሔር እንደ እኛ ክፋትና ክህደት ሳይመለከት ኃይላቸዉ የሚደክምበትንና በተለየ ሁኔታ የተገለጹበት አካል የሚሞትበትን የመድኃኒት እዉቀት ለተገባቸዉ ሰዎች በመግለጽ እንድንጠቀምበት አድርጎ ይፈዉሰናል:: እንዲሁም ለሚያምኑበት ደግሞ በጠበል፣ በእምነት፣ በጸሎት፣ በጾም፣ በቅዱስ ቁርባን አማካይነት ይፈዉሰናል:: እነዚህ ርኩሳን መናፍስት የማይሞቱ ሕያዋን ፍጥረታት በመሆናቸዉ፤ በተለየ ሁኔታ በተገለጹበት አካል ልክ እኛ ሰዎች ሕያዋን ብንሆንም የተገለጽንበት ሥጋ ሟች እንደሆነ ሁሉ እነሱም ከተገለጹበት ረቅቅ አካል በተጨማሪ በተለየ መልኩ ተገልጸዉ ጥቃትና ጉዳት የሚያድርሱበት አካል እንደ ሥጋችን በመድኃኒት ሊሞት ቢችልም እንደገና ራሳቸዉን በሌላ በተለየ አካል እየገለጹ ጥቃትና ጉዳት ሊያደርሱብን ይችላሉ:: ለዚህም ነዉ በአንድ ወቅት ለአንድ በሽታ ይሰራ የነበረ መድኃኒት ተመልሶ የመግደል አቅም የማይኖረዉና «በሽታዉ

መድኃኒቱን ስለተለማመደዉ ነዉ መዳን ያልቻለዉ» እየተባለ በሐኪሞች የሚነገረዉ፡፡ እዉነታዉ ግን እነዚህ ርኩሳን መናፍስት በሌላ በተለየ አካል ስለተገጡ ነዉ የተገለጡበት አካል በቀድሞ መድኃኒት ሊሞት ያልቻለዉ፡፡ በአሁን ዘመን መድኃኒት አልተገኘለትም የተባለዉ ኤድስ ቫይረስ ርኩሳን መናፍስት በረቂቅ አካል ተገልጸዉ የሚያደርሱት ጥቃትና ጉዳት ሲሆን፤ ይህም የእግዚአብሔር ቁጣ ሆኖ በዝሙትና በግብረ ሰዶም ፈጻሚዎች ላይ የተገለጠ ስለሆነ ለዚህ ፈዉስ የሚሆን መድኃኒት እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም፡፡ «የእድሜ ማራዘሚ» የሚባለዉም እግዚአብሔር በቸርነቱ እምነታቸዉን እያየ እርሱ እስከሚጠራቸዉ ጊዜ እድሜ ስለሰጣቸዉ ነዉ እንጂ ማንኛዉም መድኃኒት ቢሆን እግዚአብሔር የቆረጣትን እድሜ ሊቀጥል ሆነ ሊጨምር አይችልም፡፡ ያማ ቢሆን ስንቱ መድኃኒት መግዛትና መጠቀም የሚችል እድሜዉን አስረዝሞ በኖረ! ስንቱ አቅም የሌለዉ እድሜዉ ባጠረ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ግን እንደ እኛ ጠማማነትና ዓመፃ ሳይሆን እንደ ቸርነቱና ምሕረቱ ለጤናችን ሆነ ለችግራችን የሚሆን የተለያየ እዉቀትንና ጥበብን እየገለጸ እንድንጠቀምበት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ምስጋና ማቅረብ ያለብን ለእዉቀትና ለጥበብ ባለቤት ለእግዚአብሔር ነዉ እንጂ ለሥጋ ለባሹ ለእግዚአብሔር መሳሪያ ሆኖ ላገለገለዉ ሰዉ አይደለም፡፡ መመስገንም መግነንም የሚገባዉ ለእርሱ ለመሐሪዉና ለይቅርባዩ አምላክ ነዉ፡፡ መሳሪያ ሆኖ ላገለገለዉ ደግሞ በእግዚአብሔር ስም መመረቅና የድካሙንና የልፋቱን ዋጋ መክፈል ነዉ የሚገባዉ፡፡ እኛ የሰዉ ዘሮች አቅማችንን ማወቅ ያለብን፣ ከተፈቀደላቸዉ ለበሽታና ለሞት የሚዳርጉን ትንሿ የወባ ትንኞች ሳይሆኑ በእነሱ ላይ በማደር ጉዳትና ጥቃት የሚፈጽሙት ረቂቃኑ ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ናቸዉ፡፡ እነዚህ ርኩሳን መናፍስት እንኳን ትንኞች ላይ አይደለም ትልቁ ሕያዉ ፍጥረት በሆነዉ የሰዉ ዘር ላይ በማደር የተለያየ ፈተናና ጥቃት ይፈጽሙብና፡፡ ለእዚህ ምስክሩ ሰይጣናት በእግዚአብሐር ኃይል ታስረዉ ሲለፈልፉ ለሥጋችን ሕይወት ሰቷ የምታንቀሳቅሰዉ ነፍሳችን ብቻ ብትሆንም፤ ሰይጣናት በዚያን ወቅት በነፍሳችን ቦታ ተተክተዉ ሥጋችንን እንደልባቸዉ ያዙታል፣ ያደረጉትን ሁሉ አንዳች ሳይቀባጥሩ የራሳችንን አንደበት አንደበት አድርገዉ ይናገራሉ፣ ባለቤቱ የማያዉቀዉንና የረሳዉን ድርጊት አንድ በአንድ እየዘረዘሩ ይናገራሉ፣ ማንነታቸዉን ይገልጻሉ፣ የሕመሙ ምክንያትና ምንጭ እነሱ መሆናቸዉን ያሳዉቃሉ፣ በእግዚአብሔር ኃይል ታስረዉ እየተቃጠሉ እንደሚለፈልፉ ይመሰክራሉ፣ ተራና አቅመ ቢስነታቸዉን አምነዉ እንደሚለቁና እንደሚለዩ በበሽተኛዉ ላይ አድረዉ ይገዘታሉ፣ ይምላሉ፣ በመጨረሻም በሽተኛዉ በእግዚአብሔር ኃይል ከበሽታዉና ከታሰረበት ይፈወሳል፤ ሰይጣናትም ሲሰናበቱ ወደ ሕሊናዉ ይመለሳል፡፡ ታዲያ በትልቁ ሕያዉ ፍጥረት ሰዉ ላይ የሚያድሩ ከሆነ በሌሎች ሕይወት ባላቸዉ ላይ እንዴት አድርገዉ በማደር የአዳምን ዘር አያጠቁ!? እጅግ ያጠቃሉ፡፡ የእኛ የሰዉ ዘሮች ከእግዚአብሔር ጸጋ መለየት ለእዚህ ጎስቋላ ሕይወት ዳርጎናል፡፡

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ አንዳንድ አገልጋዮችን አማኞች «ሰይጣናት እኛ ጋር ድርሽ አይሉም» ይላሉ፡፡ በእግዚአብሔር የማያምኑ ደግሞ «ሰይጣናት ሰዉ የፈጠራቸዉ ምናባዊ ፍጥረታት ናቸዉ እንጂ ሰይጣን የሚባል ነገር የለም፡፡ ሰዎች ለጭንቀታቸዉ የሰጡት ስያሜ ነዉ፡፡» የሚሉ አሉ፡፡ ለዚህ ምላሾት ምንድነዉ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ሰይጣናት(አጋንንት)(ርኩሳን መናፍስት) እንኳን የሰዉ ዘሮችን ይቅርና እርሱ እግዚአብሔር ሰዉ ሆኖ በምድር በተለገለጠበት ዘመን በዘመነ ሥጋዌ በስዉር አይደለም በግልጽ ፈትነዉታል፡፡ ነገር ግን በፈተናዉ ሊያሸንፉት አልቻሉም፡፡ ይልቁኑ ኃይላቸዉ ልምሾ ሆኖ ነዉ የተመለሱት፡፡ እኛ ደከማዎቹን ፍጥረታትንማ የበለጠ በስዉርና በግልጽ ሊፈትኑን ይችላሉ፡፡ ከሕፃን እስከ አዋቂ ከጻድቅ እስከ ኃጢአተኛ ሰዉ ድረስ ወደ ሕሊናና ወደተለያየ የሰዉነት አካል ዉስጥ በመግባት ሊፈትኑ ይችላሉ፡፡ የማይችሉት በራሳቸዉ ሥልጣን እዉነተኛ አገልጋዮችንና አማኞችን መጉዳትና በላያቸዉ ላይ ማደር ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማይመላለሱት ዓመፀኞች፣ ከሃዲዎች፣ ርኩሰት ፈጻሚዎች ላይ መፈታተን ብቻ አይደለም መጉዳትና ማደር ይችላሉ፡፡

«ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) የሉም» ለሚሉት በተጨባጭ ማንነታቸዉ እንዲዉቁ እንደሚከተለዉ እገልጽላቸዋለሁ፡፡ እነዚህ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) በተለያየ ምክንያት ወደ ሕሊናቸዉ ዉስጥ የገቡት በአፋችሁ በኩል «ሃሃ» በማስባል ሆነ በዝምታ እያስፋሽኳችሁ በአፋችሁ በኩል ይወጣሉ፡፡ «እጥሽ» እያስባሉ በአፍንጫችሁ በኩል በማስነጠስ ይወጣሉ፡፡ ወደ መተንፈሻ አካላችሁ ዉስጥ የገቡት ደግሞ በአፋችሁ በኩል «ኡኡ»በማለት በማሳል ይወጣሉ፡፡ ወደ መገጣጠሚያ አካላችሁ የሚገቡት ደግሙ በማንጠራራት ይወጣሉ፡፡ ወደ ሆድ እቃችሁ የሚገቡት ደግሞ በፊንጢጣ በኩል በፈስ መልክ ይወጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በእንባ መልክ ይወጣሉ፤ ምንም ምልክት ሳይሳዩ ዝም ብለዉ ይወጣሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ከዓይነምደርና ከሽንት፣ ከአክታ፣ ከንፍጥ ጋር አብረዉ ይወጣሉ፡፡ ስለዚህ «ሰይጣናት የሉም እግዚአብሔር የለም» የሚሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ህልዉና ብቻ ሳይሆነ በብዙ ትእልፊት(በብዙ ቢሊዮን) የሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍሰት በዚህች ምድር ዉስጥ መኖራቸዉን አስተዉለዉ ራሳቸዉን በንስሐ እየመረመሩና በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ እየተጓዙ የዓይን ቅጽበት ምድራዊ ዘመናቸዉን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ይኖርባቸዋል እንጂ በምድራዊ ዘመናቸዉም በጉስቁልና ሕይወት፣ ነፍስ ከሥጋቸዉ ከተለየች በኋላ ደግሞ በከፋዉ ጉስቁልና ሕይወት ለሕያዉነት ዘመን መኖር የለባቸዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሦስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በቅዱሳት መጻሕፍት ሆነ በአዋልድ መጻሐፍት ዉስጥ « እስከ ሦስት፣ ሰባት፣ አስር፣ ሺህ፣... ወዘተ ትዉልድ እምርላችኋለዉ» የሚል ቃል ኪዳን አለ:: ታዲያ እንደዚህ ዓይነት ቃል ኪዳን ካለ እኛ በቀደሙት ሆነ በአሁን ወላጆቻችን ምክንያት ምሕረት አግኝተን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባ ከሆነ፤ ስለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሆነ ሥርዓት መጠበቅ አለመጠበቅ ለምን እንጨናነቃለን? እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን እንደፈለግነዉ ለምን አንኖርም? ስለ እነሱ ሲባል ኃጢአታችን ይቅር የሚባል ከሆነ ስለምን ስለ ኃጢአታችንንና በደላችን እንጸጸታለን? ንስሐ እንገባለን? እንደ አረማዉያንና አሕዛብ እንደፈለግነዉ ለምን አንኖርም? ዋናዉ የመጨረሻ ግባችን በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ ለሕያዉነት መኖር እስከ ሆነ ድረስ በወላጆቻችን ጽድቅ ስራ ለመንግሥቱ እንደምንበቃና ኃጢአታችን ሁሉ ይቅር እንደሚባል ቃል ከተገባ «ይህን አድርጉ፣ ይህን አታድርጉ» ለምን እንባላለን? ስለመዳኛችን ዋስትና ከተሰጠን ለምን እንደልባችን አንሆንም?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፍርዱ እዉነተኛና ፍትሐዊ እንዲሁም እጅግ ጥብቅ ነዉ:: እንኳ እርሱ እግዚአብሔር ይቅርና እዉነተኛ አገልጋዮቹ ነቢያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣ እንዲሁም ካህናት ፍርዳቸዉ እንደ እግዚአብሔር ነዉ:: ምክንያቱም በእነሱ ላይ አድሮ የሚዳኘዉና የሚፈርደዉ እርሱ ነዉና:: እግዚአብሔር በባሕርይዉ አድሎና ሽንገላ የለዉም:: ቃሉም የማይለዋወጥና የማያልፍ ነዉ:: በመሆኑም ቃል ኪዳኑ ሆነ የተስፋዉ ቃል የተጠበቀ ነዉ:: «ቃላት ይገላል ትርጓሜ ያድናል» እንደተባለዉ፤ እግዚአብሔር የተናገረዉን በራሳችን አስተሳሰብ ለራሳችን እንዲመች ካደረግን እንሰናከልበታለን፣ እንወድቅበታለን፣ እንጠፋበታለን ማለት ነዉ:: በመሆኑም በተለያዩ መጻሕፍት ላይ ያለዉን መረዳት ያለብን እንደ መንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ነዉ እንጂ እንደ ሥጋና ደም ስሜት መሆን የለበትም::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስገባ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ለሚመላለሱ ሰዎች የምሕረት ቃል ኪዳኑ በዘመናት ወይንም በዓመታት የተገደበ አይደለም:: እግዚአብሔር ቀድሞ በገነት ዉስጥ ለአዳምና ሔዋን ቃል ኪዳን የገባላቸዉ፤ የታዘዙትን ቀላል ትእዛዝ እስከ መጨረሻ ከጠበቁ እነሱና ልጆቻቸዉ ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስ( ሰይጣናት) ቁጥር እኩል እስከሚሆን ድረስ በገነት ዉስጥ በገነት ሥርዓት በተቀደሰና በደስታ ሕይወት ብቻ ሕያዉ ሆነዉ እንዲሚኖሩና፤ ቁጥራቸዉ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት (በሰማያት) ዉስጥ እንደ ቅዱሳን መናፍስት(መላእክት) በሰማያዊ ሥርዓት ሕያዉ ሆነዉ እንደሚኖሩ ነበር:: ነገር ግን ገና አንድ ልጅ እንኳ ካለመኖር ወደ መኖር ሳይመጣ የታዘዙትን ትእዛዝ ሳይጠብቁ ቀረ:: በዚህም ምክንያት የማይሻረዉ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ራሳቸዉ ፈቅደዉና ወደዉ አፈረሱት:: ራሳቸዉን ለከፋ ቅጣትና ለጉስቁልና ዳረጉ:: በመጨረሻም የሞት ሞትን ሞቱ:: ይኸዉም በምድር በሥጋቸዉ፣ በሲኦል በነፍሳቸዉ አይቀጡ አቀጣት ጠቀጡ፣ ተዋረዱ፣ ስለ ቃል ኪዳን ማፍረሳቸዉ የከፋ ዋጋ ከፈሉ::

ይሁንና ወደ ሕሊናቸዉ በመመለስ ስለ ዓመፃቸዉ እጅግ ተጸጸቱ፣ አነቡ፣ እዉነተኛ ንስሐ ገቡ:: ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ፈቃደኛነታቸዉን ለአምላካቸዉ ገለጹ:: እግዚአብሔርም እዉነተኛ ንስሐቸዉን ተቀብሎ በምድር ዋጋ ቢከፍሉም፣ በነፍሳቸዉ ግን ቃል ኪዳኑ እንደሚጠበቅላቸዉ ማረጋገጫ ተሰጣቸዉ:: ወደ መጀመሪያ መኖሪያቸዉ ገነትና ወደ መጨረሻ ተስፋቸዉ መንግሥተ ሰማያት ዉስጥ እንደሚያስገባቸዉና ቃል ኪዳኑ እንዳልፈረሰ ገለጸላቸዉ:: በምድር ዉስጥ በኪዳነ ልቦና(በሕገ ልቦና) አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ በማምለካቻቸዉና ትእዛዙን በመጠበቃቸዉ ምክንያት በእዉነተኛ ንስሐቸዉ ገነት ሊመለሱና ለሰማያዊ መንግሥት ሊታጩ ችለዋል::

አሁንም ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚሰራዉና ተፈጻሚ የሚሆነዉ እንደ ቃሉ ሆነን ስንገኝ ብቻ ነዉ እንጂ በቀደሙት ሆነ በአሁን ወላጆቻንን ጽድቅ ስራ ብቻ ለእግዚአብሔር መንግሥት አንበቃልም:: እንኳን እኛ እዉነተኛ ንስሐ ያልገባንና ቅዱስ ቁርባን ያልተቀበልን ዓመፀኞች ቀርቶ፣ ወላጆቻችን የመጀመሪያ አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገዉ በመጨረሻ ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከወጡና በእዉነተኛ ንስሐ ቅዱስ ቁርባን ካልተቀበሉ በስተቀር የቀድም ጽድቅ ስራቸዉ እንኳን ለእኛ ሊተርፍ ቀርቶ ለእነርሱም ፍርዱን ከማቅለል ዉጭ ለራሳቸዉም አይሆናቸዉም:: ስለዚህ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ቃል ኪዳን የገባላቸዉ ሌሎች በእነሱ ጽድቅ ስራ ብቻ እንዲድኑና በኃጢአት እንዲኖሩ እንዲሁም እንዲመላለሱ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ሰዉ የእነሱን ሕይወት ተከትሎና እነሱ የፈጸሙትን ተጋድሎ እንዲፈጽም፣ በሕይወቱም እነሱን እንዲመስል ነዉ::

በብሉይ ዘመን ሆነ በሐዲስ ዘመን እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ወይንም ትእዛዙን ያልጠበቁትንና ያፈረሱትን ፈርዶባቸዋል:: ለምሳሌ በግብፅ በባርነት ዉስጥ የነበሩትን እስራኤላዉያን ስለ አባቶቻቸዉ ስለ አብርሃም ስለ ይስሐቅ ስለ ያዕቆብ ሲል ወደ ከነዓን ሊመልሳቸዉ ወዶ በታላቁ ነቢይ በሙሴ መሪነት ከግብፅ ነጻ ቢያወጣቸዉም፤ ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቃቸዉና እንደ ፈቃዱ ባለመመላለሳቸዉ ምክንያት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ከወጡ ታላላቆች ሰዎች ኢያሱና ካሌብ ብቻ ናቸዉ እንደ ቃሉ ሆነዉ በመገኘታቸዉ ወደ ከነዓን ምድር የገቡት:: ሌሎቹ በዓመፃቸዉ፣ በክህደታቸዉ፣ በርኩሰታቸዉ ምክንያት በመንገድ ላይ ረግፈዉ ቀርተዋል:: እግዚአብሔር ለንጉሥ ዳዊት ሆነ ለንጉሥ ሰለሞን መንግሥታቸዉን እስከ መጨረሻ ድረስ እንደሚያጸናላቸዉ ቃል የገባላቸዉ ቢሆንም በንጉሥ ሰለሞን ዘመን ቃል ኪዳኑ ስለፈረሰና ስላልጠበቀ፣ እንደ ትእዛዙ ሆኖ ስላልተገኘ፣ እንዲሁም በሁለተኛዉ ትዉልድ በሮብዓም በከፋ መልኩ ዓመፃ ስለተፈጸመ መንግሥቱ ለሁለት ሊከፈልና በኋላም ዓመፃቸዉ በመክፋቱ ምክንያት ሕዝቡ ለምርኮና ለባርነት ተዳርገዋል:: በአዲስ ዘመንም እንደ ክርስትናዉ ሆነዉ ያልተገኙ መንግሥታት፣ ቡድኖች፣ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች፣ በተለያየ መንገድ ቅጣት ሊደርስባቸዉና እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ዋጋ ሊከፍሉ ችለዋል፤ በእዉነተኛ ንስሐ እስካልተመለሱና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስካልተመላለሱ ድረስ አሁንም፣ ወደፊትም ስለ ዓመፃቸዉ፣ ስለ ክህደታቸዉና ስለ ርኩሰታቸዉ ዋጋ ይከፍላሉ:: አሁን ያለነዉ ትዉልድም እንደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሆነን ካልተገኘን በምድርም በሰማይም ፍዳችንን እንቀበላለን፤ ዋጋም እንከፍላለን እንጂ በአንዱ ጽድቅ እኛ በብልጣብልጥነትና በአቋጭ መንገድ በኃጢአትና በበደል፣ በግፍ እየተመላለስን የእግዚአብሔርን መንግሥት አንወርስም:: እዉነተኛ የቅዱሳንና የጻድቃን ወዳጆች

ከሆንና በስማቸዉ የማንነግድ፣ የማናላግጥ ከሆነ ለእዉነተኛ ንስሐና ለቅዱስ ቁርባን እንድንበቃ አድርገዉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ያበቁናል። በስማቸዉ ብቻ የምንነግድና በዓመፃ ሕይወት የምንመላለስ ከሆነ እኛም እንዳላገጥን ተላግጦብን ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ነዉ የምንበቃዉ እንጂ እግዚአብሔርን ሆነ ቅዱሳንን እንዲሁም ጻድቃንን ልናታልል አንችልም።

እግዚአብሔር በኦሪት ዘጸአት ምእራፍ 20 ቀጥር 5 ላይ «በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትዉልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ፣ **ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትዉልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ** እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ» ይላል። ታዲያ ይህ የሚያሳየን የእግዚአብሔር ቁጣ እጅግ ዉሱን እንደሆነ ነገር ግን ምሕረቱ እጅግ እጅግ ብዙ መሆኑን ነዉ እንጂ፤ አባት በዓመፃ ሕይወት ቢመላለስ ልጅ ደግሞ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ቢኖር ስለ አባቱ ዓመፃ የሚኮነንና የሚቀጣ አይደልም። እንዲሁም እስከ አንደኛዉ ሁለተኛዉ ሦስተኛዉ አራተኛዉ ትዉልድ በዓመፃ ሕይወት ቢመላለሱና አምስተኛዉ ትዉልድም በዓመፃዉ ቢቀጥል እስከ ሦስትና አራት ትዉልድ ስለተባላ አምስተኛዉ በምሕረት ይታያል ማለት አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ አባት እግዚአብሔርን አስደስቶ በምሕረት ለእግዚአብሔር መንግሥት በመብቃቱ ልጅ ደግሞ በአባቱ ተቃራኒ ሕይወት በኃጢአት ቢኖር እግዚአብሔር «እስከ ሺህ ትዉልድ ምሕረት አድርጋለሁ» ስላለ ስለ አባቱ ሲባል ምሕረትን ያገኛል ማለት አይደለም። እንዲሁም እስከ ሺህ ትዉልድ ድረስ ትዉልዱ እግዚአብሔር በሚደሰትበት ሕይወት በመመላለሱ ምክንያት ምሕረት አግኝቶ አንድ ሺህ አንደኛዉ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ቢመላለስ እስከ ሺህ ትዉልድ ምሕረት አደርጋለዉ ነዉና ያለዉ፣ ከዚያ በላይ ያለ ትዉልድ ምሕረት አይደረግለትም ለማለት አይደለም። ሺህ ቁጥር በንስሐ ለሚመለስ ትዉልድ እግዚአብሔር ምሕረቱ ገደብ እንደሌለዉና እንዲሁም ቁጣዉ በሚቆጠር ትዉልድ ላይ ብቻ ሊገለጽ እንደሚችል ነዉ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚጸናዉ የእርሱም ቃል ኪዳን በአግባቡ ከተጠበቀና እያንዳንዱ አማኝ ሆነ አገልጋይ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነዉ እንጂ ማንም ኃጢአተኛ ስለ ዓመፃዉ ሳይጸጸትና ንስሐ ሳይገባ እንዲሁም ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ኃጢአቱን የሚያስደመስስለትን መለኮት የተዋሐደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ሳይቀበል በምንም ሁኔታ ለእግዚአብሔር መንግሥት አይበቃም። ከሲኦልና ከገሃነመ እሳት ፍርድ አያመልጥም።

እዚህ ላይ አንድ ለማስታወስ የምፈልገዉ አንዳንድ ማስተዋል የጎደላቸዉና ለጨለማዉ ገዥ መንፈስ ተገዥ የሆኑ እንዲሁም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱ ሰዎች የሚሉትን የዓመፃና የክህደት ንግግርና ስብከትን ነዉ። ይኸዉም አልፋና ዖሜጋ የሆነዉ የሁሉ ፈጣሪና አምላክ የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ» እያሉ እያላገጡበትና እየሰደቡት፤ ማንኛዉም ለሰዉ የሚያስብ ሕያዉ ፍጥረት ሊያደርገዉ የሚችለዉን ቀላሉን የማማለድ ተግባር «ቅዱሳን ሆኑ ጻድቃን አያማልዱም» በማለት ያ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስካደና ያሰደበ የሰይጣናት መንፈስ ቅዱሳንና ጻድቃንንም አሰደቧል፣ አስክዷል። የእግዚአብሔር እዉነታ ግን ቅዱሳንና ጻድቃን ቀላሉን ማማለድ ቀርቶ ከባዱን የእግዚአብሔርን ፍርድ መፍረድ ሙሉ ሥልጣን አላቸዉ። ይኸዉም የሚወስኑት ሆነ የሚፈርዱት እንደ እግዚአብሔር አድሎ የሌለዉ እዉነተኛና ፍትሐዊ ነዉ። ምክንያቱም እርሱ

እግዚአብሔር የሚያሳስባቸዉን ነዉና የሚወስኑትና የሚፈርዱት፡፡ ለዚህ እንደ ማስረጃ ለማቅረብ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 1 ከቁጥር 8እስከ23 ላይ ቅዱስ ገብርኤል ለጻድቁና ለካህኑ ዘካርያስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መላኩና ባለቤቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ እንደምታረግዝና ልጅ እንደምትወልድ በተናገረዉ ጊዜ፣ እንደ ካህንነቱና ታላቅ ኃላፊነቱ የቀደሙት የአባቶቹንና እናቶቹን የአብርሃምና የሳራን ሕይወት አስቦና የእግዚአብሔርንም ሁሉን አድራጊነት አምኖ «ለእግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም» በማለት የመላኩን ቃል መቀበል ሲገባዉ፣ የእግዚአብሔርን የማይሻሻልና የማይለወጥ ቃል ዘንግቶ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ በማሰብ «ይህ እንዴት ይሆናል?» ብሎ የእርሱን ሆነ የባለቤቱን ማርጀት በመግለጹና የእግዚአብሔርን መልእክት በመጠራጠሩ ምክንያት፣ ቅዱስ ገብርኤል በራሱ ሥልጣን ምልክት ይሆነዉ ዘነድ መጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እስከሚወለድ ድረስ ካህኑ ዘካርያስ ዲዳ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ታዲያ ይህን ዉሳኔና ፍርድ ሲወስን እግዚአብሔርን አላማከረም ወይንም አልጠየቀም፡፡ ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥርና መሪነት ዉስጥ ስለሆነ ያ ዉሳኔ ሆነ ፍርድ የመንፈስ ቅዱስ ነዉ እንጂ የቅዱስ ገብርኤል ብቻ አልነበረም፡፡ ይህም የሚያሳየን ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር ሆነዉ የመፍረድ ብቃት የተሰጣቸዉ ስለሆነ በዉሳኔያቸዉና በፍርዳቸዉም አንዳች አይጠየቁበትም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለሐዋሪያት ተጠሪነትና ኃላፊነት የተመረጠዉ ቅዱስ ጴጥሮስ በአገልግሎት ዉስጥ እያለ በሐዋርያት ስራ በምእራፍ 5 ከቁጥር 1እስከ11 እንደተገለጸዉ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉ ከሐዋርያት ማኅበር ጋር ለመቀላቀል የፈለጉ፣ ነገር ግን በብልጣብልጥነት ሕይወት እዛም እዚህም እያጣቀሱና ከዓለምም ከመንፈሳዊነትም በማታለል ለመኖር የወሰኑ፣ ሰዉን እንደሚያታልሉ እግዚአብሔርንም ለማታለል የሞከሩትን፤ ይኸዉም ንብረታቸዉን ሸጠዉ ለማኅበሩ ለማስረከብ በፈቃዳቸዉ ወስነዉ ሳለ የሸጡትን ገንዘብ ግማሹን በመደበቅ በግማሹ ብቻ እንደሸጡ አስመስለዉ ለሐዋርያዉ ቅዱስ ጴጥሮስ በመግለጻቸዉ ምክንያት እርሱ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ዉስጥ ያለና መሪዉም መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ በነፍሱ ዐይን ድርጊታቸዉን በመመልከቱና በነፍሱ ጆሮ የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማት ምን እንደተደረገ ስላወቀ እንደ ኃላፊነቱ፣ ሌሎችም ይህን የዓመፃና የማታለል ተግባር እንዳይፈጽሙ በግሳጼ ብቻ በእግዚአብሔር መቅሰፍት ሞት ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ዓለም እንዲሄዱ አድርጓል፡፡ ታዲያ ይህን ሲወስንና ሲፈርድ እግዚአብሔርን አላማከረም፣ አልጠየቀም፡፡ ይህም የሚያሳየን የጻድቃን ዉሳኔ ሆነ ፍርድ እንደ እግዚአብሔር ዉሳኔና ፍርድ መሆኑን ነዉ፡፡ እግዚአብሔርም «እነዚህ ሁለት ከማኅበሩ ጋር ሊቀላቀሉ የፈለጉት አታላይና አጭበርባሪ ቢሆኑም ለምን ገሰጽካቸዉ? እኔም የሞት ፍርድ እንድወስንባቸዉ ለምን አስደረክ? ጠላታችሁን ዉደዱ እያልኩ አንተ እንዴት ስለ ዓመፃቸዉ ጥቀጣቸዋለህ» በማለት ቅዱስ ጴጥሮስን አልጠየቀዉም ወይንም ስህተት ፈጽመሃል አላለዉም፡፡ ምክንያቱም ቅዱስ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነትና አሳሳቢነት ነዉና ያንን ዉሳኔ የወሰነዉ፡፡ ባጠቃላይ ቅዱሳን ሆኑ ጻድቃን ማማለድ ብቻ አይደለም እንደ እግዚአብሔር ሊወስኑና ሊፈርዱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም በእነርሱ ላይ አድሮ የሚወስነዉና የሚፈርደዉ እርሱ እግዚአብሔር ነዉና፡፡

በብሉይ ዘመን የነበረዉን ነቢዩ ኤልያስን ብንመለከት በመጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ 17÷ከቁጥር 1እስከ2 እግዚአብሔርን፤ ዓመፀኞች ለእርሱን ፈቃድ እስከሚሰለፉና ከዓመፃ ተግባር እስከሚለዩ ድረስ ዝናብ እንዳያዘንብ ጠይቆ ለሦስት ዓመት እንዳይዘንብ አስደርጓል። እንዲሁም በትዕቢትና በእብሪት እርሱን ይዘዉ ለንጉሡ ሊያቀርቡ የነበሩትን ወታደሮች ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲበላቸዉ አስደርጓል። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ልመና ቅርብ የሆነ  ስለ እርሱ በመቅናት ለሚጠይቁት ጥያቄ ፈጥኖ ምላሽ የሚሰጣቸዉ ነዉ።

ከዚህ በተጨማሪ በሐዋርያት ስራ በምዕራፍ 13 ከቁጥር8እስከ12 ላይ « ጠንቋዩ ግን ኤልማስ፣ ስሙ እንዲሁ ይተረጎማልና፣ አገረ ገዥዉን ከማመን ሊያጣምም ፈልጎ ተቃወማቸዉ። ጳዉሎስ የተባለዉ ሳዉል ግን መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ትኩር ብሎ ሲመለከተዉ ፡- አንተ ተንኮል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፣ የዲያብሎስ ልጅ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፣ የቀናዉን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍም? አሁንም፣ እነሆ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፣ ዕዉርም ትሆናለህ እስከ ጊዜዉም ፀሐይን አታይም አለዉ። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት፣ በእጁም የሚመራዉን እየዞረ ፈለገ። በዚያን ጊዜ አገረ ገዡ የተደረገዉን ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ» ይላል።

ታዲያ ከላይ የተገለጸዉ በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት የተጻፈዉ ድርጊት የሚያሳዉቀን የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች፤ የታወሩትን ማብራት፣ በሽተኞችን መፈወስ ብቻ ሳይሆን ተንኮለኞችና ክፉዎችን «የዲያብሎስ ልጆች» የተባሉትን፣ የእግዚአብሔርን እዉነት የሚቃወሙና የሚያጣምሙትን ጭምር ማሳወር ሆነ በሌላ መቅሰፍት ሊቀጧቸዉ እንደሚችሉ ነዉ።

በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ በምዕራፍ 11፡ ከቁጥር 4እስከ6 ላይ « እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለት ወይራዎችና ሁለት መቅረዞች ናቸዉ። ማንምም ሊጎዳቸዉ ቢወድ እሳት ከአፋቸዉ ይወጣል ጠላቶቻቸዉንም ይበላል፤ ማንም ሊጎዳቸዉ ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል። እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸዉ፣ ዉኃዎችን ወደ ደም ሊለዉጡ በሚፈልጉትም ጊዜ ሁሉ በመቅሰፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸዉ» ይላል። ይህም በግልጽ የሚያሳየን እንደ ነቢዩ አልያስና ጻድቁ ሄኖክ ዓይነት የሆኑ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ ስለሚያድር ማንኛዉንም መቅሰፍት በዓመፀኞች ላይ ማምጣትና መቅጣት እንደሚችሉ ነዉ። እግዚአብሔር ለመረጣቸዉና ለባለሚሎቹ የዚህን ያህል ሥልጣን ሰቷቸዋል። ምክንያቱም እርሱ የሚያሳስባቸዉን ነዉ የሚያስቡት፣ እስር የሚያናግራቸዉን ነዉ  የሚናገሩት፣ የሚያሰራቸዉን ነዉ የሚሰሩትና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ አንዳንድ መምህራንና ምእመናን ወላጆች በሚፈጽሙት የተለያየ ባዕድ አምልኮ ምክንያት የሚዋሐዷቸዉና ወዳጅ ያደረጓቸዉ በተለያየ ስም የሚጠሩ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ከወላጆች ወደ ልጅ ይተላለፋሉ የሚሉ አሉ። ልጅ ምንም በማያዉቀዉ ነገር እንዴት

የወላጆቹ ወይንም የአያት ቅድመ አያቶቹ ጌታና አዛዥ የነበሩት ርኩሳን መናፍስት ሊያድሩባቸዉና ባሪያ ሊያደርጓዉ ይችላል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ማንኛዉም ልጅ ሲወለድ ነጻ ሕሊናዉን ይዞ ነዉ የሚወለደዉ:: ነገር ግን ወላጆች የሚያምኑባቸዉና ባዕድ አምልኮ የሚፈጽሙላቸዉ፣ የተለያየ ግብር የሚያቀርቡላቸዉ፣ በተለያየ ስም የሚጠሩ አጋንንት፤ ያ ቤተሰብ ፈቃደኛ ሆኖ ስላቀረባቸዉ በቤተሰቡ ላይ ሊነግሡና ፈቃዳቸዉን ሊያስፈጽሙ ይችላሉ:: ይሁንና ያ የራሱን ነጻ ሕሊና ይዞ የተወለደዉ(የተወለደችዉ) ልጅ ሕሊናቸዉ ማመዛዘንና ማገናዘብ በሚችልበት ጊዜ ያን ባዕድና ጣዖት አምልኮ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ በመመርመር፤ የአጋንንት ስራና የእነርሱ ባሪያ መሆን እንደሆነ አስተዉሎ ከዚያ ሕይወት ራሱን መለየትና እዉነተኛዉን አምላክ መፈለግ ይጠበቅበታል:: ከዚያም እዉነትን ተቀብሎ እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖርና በተሰጡት መሳሪያዎች በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ በቅዱስ ቁርባን ፣ እንዲሁም በእምነቱና በጠበሉ በወላጆቹ ምክንያት የተላለፈበትን ርኩሳን መናፍስት ማራቅና ኃይላቸዉን ልምሾ በማድረግ በተቃራኒዉ እነርሱን ሊቀጣቸዉና ሊያቃጥላቸዉ ይችላል:: ይህን ነጻ ፈቃድና ሥልጣን እግዚአብሔር ለማንኛዉም ሰዉ ሰቷል:: ይህን ነጻ ፈቃድ ባለመጠቀም ዝም ብሎ በወላጆቹ ባዕድና ጣዖት አምልኮ የሚመላለስ ከሆነ እርሱም በሥጋ ሞት ከዚህች ምድር ሲለይ እነዚያ አጋንነት ወደ ልጆቹ በመተላለፍ ያንኑ ርኩሰት ተግባር ሊያስፈጽሙ ይችላሉ:: ልጆቹ ነጻ ፈቃዳቸዉን ተጠቅመዉ ከዚያ ሕይወት ራሳቸዉን ከለዩ ደግሞ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሰለፍ ይችላሉ:: እያንዳንዱ ልጅ እንደምርጫዉና ዉሳኔዉ ራሱን ከርኩሳን መናፍስት ነጻ ማድረግ ይችላል:: የእነርሱ ባሪያ ሆኖ ለመኖር ከፈለገም እግዚአብሔር አስገድዶ ከዚያ ሕይወት አያወጣዉም:: ነገር ግን በምድርም ሆነ በሰማይ ስለ ዓመፃዉና ክህደቱ እንዲሁም ርኩሰት ተግባሩ ዋጋ ያስከፍለዋል፤ ፍዳዉንም ያሳየዋል::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፤የቅድስናና የብቃት እንዲሁም እግዚአብሔር መምሰል መለያዉ ምንድነዉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፤ እያንዳንዳችን እግዚአብሔር «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ፤ እኔ ፍጹም ነኝና ፍጹማን ሁኑ፤» ባለዉ መሰረት ነፍሳችን የእግዚአብሔርን ባሕርይ መምሰል የተላበሰች፣ በምድራዊ ዘመናችን በምናሳየዉ ሕይወትና ብቃት የቅድስናና የብቃት ደረጃችን ሊለያይ ቢችልም ሁሉም የሰዉ ዘር ከክፋት፣ ከትዕቢት፣ ከእብሪት፣ ከምቀኝነት፣ ከተንኮል፣ ከዓመፃ፣ ከክፉ ቅናት፣ ከጥላቻና ከበቀል፣ ከዘረኝነትና ከጎጠኝንት፣ ከራስ ወዳድነትና ከስግብግብነት፣ ከዘፋኝነትና ከዳንኪርተኛነት ፣ ከተለያዩ ጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ ከዝሙት፣ ከስርቆት፣ ከግድያ፣ ከመዋሸትና ከማጭበርበር፣ ከሴሰኝነት፣ ከግብረሰዶም፣ ከጥንቆላ፣ ከመተተት፣ ከሟርት፣ ከአስማት፣ ከመጽሐፍ ገላጭነት... ወዘተ ሕይወት መለያት አለብን:: ከነዚህ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰትና የሥጋና የደም ስሜት በምንለየዉ ደረጃና ብቃት ነዉ ከ60 እስከ 99 ነጥብ አግኝተን ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃት የምንችለዉ:: 70 ነጥብ ያገኘዉ 65 ነጥብ ካገኘዉ ሰዉ በደረጃ የሚበልጥ ሲሆን፤ 80 ነጥብ ካገኘዉ ሰዉ ደግሞ በነጥብ ያንሳል፤ ነገር ግን ሦስቱም ከ60 ነጥብ በላይ ስላገኙ ለእግዚአብሔር መንግሥት ይበቃሉ:: በዚያም የሚያገኙት ክብር፣

ደስታ እንደ ነጥባቸዉ ደረጃ ይለያያል:: ታዲያ ከ60 ነጥብ በላይ አግኝቶ ለእግዚአብሔር መንግሥት ለመብቃት ደግሞ ነፍሳችን የሰይጣናትን መንፈስ ኃይል የምታሸንፍበትና ራሷን በመግዛት በሥጋዋ ላይ የበላይት የምትጎናጸፍበትን ጸጋ(ኃይል) ለማግኘት መጸለይ፣ መጾም፣ መስገድ፣ ማመስገን ፣ ወገኗን መርዳትና ማገዝ፣ ቃሉን መስማትና በተግባር ማዋል፣ በንስሐ ሕይወት እየተመላለሰች በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ መወሰን፣ እንደተሰጣት ጸጋ ስለ እዉነት መቆርቆርና ማንባት፣ በአምልኮዋና በአገልግሎቷ በእግዚአብሔርና በሕዝብ ፊት ራሳን ዝቅ አድርጋ በትህትና፣ በፍቅር፣ በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በትጋት፣ በጽናት፣ በትዕግስት፣ በይቅርባይነት መኖር ይጠበቅባታል:: እነዚህን ሕይወት ከተላበሰች በኋላ ደግሞ በራሷ ፈቃድ የትሩፋትና የተጋድሎ ስራ በመስራት ራሷን ብቃት ደረጃ ላይ ማድረስ ትችላለች:: በተለያየ ዓመጻና ትዕቢት እንዲሁም አምላኮ ምንዝርና ሕይወት እየተመላለሱ የትሩፋትና የተጋድሎ ስራ ልስራ ቢባል ፍሬ ማፍራት አይቻልም:: ይልቁኑ ያ ትሩፋትና ተጋድሎ ስራ የሚመስለን የበለጠ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም በትዕቢተኛና በዓመፀኛ ሕሊና የሚያድረስ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ዓመፃዉንና ክህደቱን እንደ ትልቅ ስራ እንድንቆጥረዉ አድርጎ ለእርሱ ፈቃድ ፈጻሚነትና አስፈጻሚነት ሊያዉለን ይችላል:: ለዚህም ነዉ ብዙዎች የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት እምነትና አገልግሎት እንደ ትክክለኛ እምነትና አገልግሎት ቆጥረዉ የሚኖሩበትና ራሳቸዉን ለከፋዉ ቅጣት እያዘጋጁ ያሉት:: ነገር ግን ቅድሚያ መያዝ ያለባቸዉን ትክክለኛ መንፈሳዊ ሕይወት በተሟላ መልኩ ቢይዙ ኖሮ እግዚአብሔር አድሮባቸዉ እንደ ነቢያት ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣ መምህራን ታላቅ ስራ ያሰራቸዉ ነበር:: በትሩፋታቸዉና በተጋድሏቸዉም ለታላቅ ክብርና ጸጋ ይበቁ ነበር::

ከላይ እንዳየነዉ የቅድስናና የብቃት መለያዉ ሲጠቃለል በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት መኖር ነዉ:: እያንዳንዱም ሰዉ በሚያሳየዉ ቅን ሐሳብ፣ መልካም ተግባር፣ እዉነተኛ ሕይወት የተለያየ ደረጃና ብቃት ሊኖረዉ ይችላል:: እያንዳንዱ ቢያንስ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃ 60 ነጥብ የሚያስገኝለትን ሕይወት ሊይዝ ይገባዋል:: ከሆነለት ደግሞ በዘጠናዎቹ ነጥብ የሚያስገኝለትን ሕይወትና ብቃት ሊይዝ ይገባዋል::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፤ አንዳንድ ሰዎች ሰዉን ገጹንና ቁመናዉን ብቻ ተመልክተዉ « ይህ ሰዉ ስመለከተዉ እናደዳለዉ፣ ያስጠላኛል፣ ባጠገቤ ባያለፍ እመርጣለዉ፣ ሳየዉ ደም ፍላቴ ይመጣብኛል፣ ብሰድበዉና ብጣላዉ እመርጣለሁ... ወዘተ» የሚሉ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ሰዎች መልአክ ሆነዉ ነዉ በዐይናቸዉ ብቻ በማየት የሰዎችን ማንነት መለየት የቻሉት? ወይስ የተለየ ጸጋ ተሰቷቸዉ ነዉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፤ በመጀመሪያ በዚህ አስተሳሰብና አመለካከት ያለ ሰዉ የሚሳዉቀን የእግዚአብሔርን ጸጋ ሳይሆን የዲያብሎስ መንፈስ የጨለማዉ ጸጋ እንደተጠጋዉ ነዉ:: በሰዎች ሕሊና ዉስጥ ለዐይን ቅጽበት ከፈተና የማይለየዉ ርኩስ መንፈስ በነፍስ ፈቃድ ላይ ሲሰለጥንና ሲነግሥ፣ ነፍስን እንደፈለገዉ ማዘዝ ሲችል ነዉ ይህ ዓይነት ስሜት በሰዎች ላይ የሚንጸባረቀዉ እንጂ እንኳን ማንነቱና ምንነቱን የማናዉቀዉን ሰዉ ከመሬት ተነስተን መልኩን

ብቻ በማየት «ይህ ሰዉ አስጠላኝ፣ መንፈሴ አይወደዉም፣ ሳየዉና ሲያየኝ ደም ፊላቴ ይመጣብኛል፣ እንደዉ ባካባቢዬ ባላየዉ እመርጣለዉ፣... ወዘተ» በማለት ልንጠላዉና ክፉ ልናስብበት ቀርቶ በተግባሩ መሰሪ የሆነዉን ሰዉ እንኳ ተግባሩን ነዉ ልንጠላዉና ልንጸየፊዉ የሚገባዉ እንጂ፤ ለመሰሪ ተግባሩ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለስ ስለቀደመዉ የዓመፃ ተግባሩ ልንጠላዉና ልንርቀዉ አይገባም፡፡ ነገር ግን እሱነቱን የምንጠላ ከሆነ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለስም ላንወደዉና ላናቀርበዉ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ የእዉነተኛ ክርስትና ሕይወት መገለጫ አይደለም፡፡

የሰዉ መልክ ወይንም ቁመና የሰዉን መልካምንና መጥፎነትን አይገልጸዉም፡፡ የሰዉ ማንነቱ የሚገለጸዉ በስራዉና በሚያፈራዉ መልካም ይሁን መጥፎ ፍሬ ነዉ፡፡ እንኳን በመልክ፣ በንግግር እንኳ ሰዉን የማንለይበት ዘመን ላይ ነን፡፡ ምክንያቱም እጅግ ብዙዎች በዓለማዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ እያሉ የሚናገሩት ሌላ የሚሰሩት ደግሞ ሌላ፣ የሚዘሩት ሌላ የሚያፈሩት ሌላ ሆኖ ነዉ የታየዉና የተገኘዉ፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን ተግባር ብቻ አይደለም ንግግር ጭምር በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ልንመረምር ይገባል እንጂ ሰዉን እንኳን በማየት በመስማት እንኳ «እንዲህ ነዉ» ማለት ይከብዳል፡፡ በሕሊናችን የነገሠዉን የጥላቻና የበቀል መንፈስ ደግሞ በእግዚአብሐር መሳሪያ ልናርቀዉና የአዳምና ሔዋን ዘሮችን ሁሉ ልንወድና ልናፈቅር ይገባል፡፡ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ ያሉትን ተግባራቸዉን ነዉ መጥላትና መቃወም ያለብን እንጂ ማንነታዉን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ነፍሳችን እግዚአብሔር መምሰል የተላበሰች ስለሆነ እግዚአብሔር ደግሞ ዘመናችንን ሁሉ በኃጢአት ተመላልሰን ወደ ልባችን ስንመለስና እዉነትን ስናስተዉል በእዉነተኛ ንስሐ ተጸጽተን ወደ እርሱ ስንመለስ የቀደመዉን የዓመፃ ተግባራችንን እያስታወሰ «ይቅር አልላችሁም፣ ተጸይፌያችኋለዉ፣ ለመንግሥቴ አትበቁም» አይለንም፡፡ ነፍስ ከሥጋ እስከምትለይ ድረስ በትዕግስት ይጠብቀናል፤ በዓመፃችን ጸንተን ከዚህች ምድር በሥጋ ሞት ከተለየን በኋላ ነዉ «እናንተ ርጉማን ዓመፀኞች፣ የዲያብሎስ አገልጋዮችና ልጆች» ብሎ የዓመፃ ዋጋችንን የሚከፍለን፡፡ እስከዚያች ድረስ ግን በእዉነተኛ ንስሐ እንድንመለስና እንደ ልጅነታችን እንድንኖር እድሉን ይሰጠናል፡፡ በዓመፃችን ምክንያት በምድር ዋጋ ቢያስከፍለን እንኳ በእዉነተኛ ንስሐ እስከተመለስን ድረስ በሰማያት ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ ያበቃናል፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፤ አንድ ሰዉ ስለ ሰራዉ መልካም ተግባር እንዲሁም ማድረግ ያለበትን በአግባቡ ማድረግ ስለቻለ፣ ከተለያየ አካላት ወይንም ግለሰብ ሽልማትና ስጦት ቢያገኝ ተገቢ ነዉ ወይ? ያ ግለሰብን መቀበል ይገባዋል ወይ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፤ ማንኛዉም ሰዉ መልካም የሚሰራዉ ሆነ ማድረግ ያለበትን ማድረጉ ወይንም ማገልገል ያለበትን በትክክል ማገልገሉ ለመሸለምና ስጦታን ለማግኘት መሆን የለበትም፡፡ ለሕሊናዉና ለአምላኩ ብቻ በመታመንና «ከእግዚአብሔር ዋጋ አገኝበታለሁ» በማለት መሆን አለበት፡፡ ይህ ከሆነ እንደዚህ አስተሳሰብና አቋም ያለዉ ሰዉ ተሸለማ አልተሸለመ፣ ስጦታ ተሰጠዉ አልተሰጠዉ ከመልካም ተግባሩና ከትጋት አገልግሎቱ የሚለየዉ ነገር የለም፡፡ እንዲሁም ሽልማት ሆነ ስጦታ ቢሰጠዉ ለበለጠ መልካም ተግባርና ለትጋት አገልግሎት

ያሰልፈዋል እንጂ ከሌላ አካል ወይንም ግለሰብ ሽልማትና ስጦታ እንዲጠብቅ አያደርገዉም። በአብዛኛዉ የሚታየዉና በዓለም ያለዉ እዉነታ ግን ሰዎች የተለየ ሽልማት ለማግኘትና እንዲሁም ከተለያዩ አካላት ሆነ ግለሰቦች ስጦታ ለማግኘት ሲሉ ብቻ መልካም ይሰራሉ፣ በትጋት ያገለግላሉ። ይህ አስተሳሰብና አቋም ደግሞ ሽልማት ሆነ ስጦታ የማይሰጠዉን ሰዉ መልካም ላያደርጉና በትጋትና በቅንነት ላያገለግሉት ያስችላል። ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በመጀመሪያ ይህን አስተሳሰብና አቋም ሊለዉጡ ይገባል። ሽልማት ሆነ ስጦታ አገኙ አላገኙ ሁሉንም በቅንነትና በትጋት ማገልገል መቻል አለባቸዉ። ሽልማቱና ስጦታዉ ይህን አስተሳሰባቸዉንና አቋማቸዉን የሚለዉጥ ከሆነ ግን ሽልማት ሆነ ስጦታ ላለመቀበል መወሰን አለባቸዉ። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን ታላቁን ሽልማትና ስጦታን ያስቀርባቸዋልና። እንዲሁም ሽልማትና ስጦታ ያላመጣላቸዉን አካልና ግለሰብ በአግባቡና በቅንነት፣ በትጋት ባለማገልገላቸዉ ምክንያትም ይጠየቁበታልና። ባጠቃላይ ሽልማትና ስጦታ መስጠት አለመስጠት ችግር የሌለዉ ቢሆንም፤ የሚያመጣዉ ዉጤት ነዉ ጥቅም ወይንም ጉዳት ያለዉ። ያን የመለየትና የማወቅ ደግሞ እያንዳንዱ በነጻ ሕሊናዉ ማመዛዘንና ማገናዘብ ይችላል።

የሰዎች አስተሳሰብና አቋም የተለያየ መሆኑን የምናዉቀዉ በተለያየ ግብዣ ሆነ ዝግጅት ላይ ብዙ ሰዎች ስጦታን ይጠብቃሉ። ስጦታን ያመጣላቸዉን ሰዉ በተለየ ሁኔታ የሚመለከቱ ሲሆን፤ ስጦታ ያላመጣላቸዉን ደግሞ ጊዜዉን፣ ገንዘቡን ሰዉቶ መምጣቱ ታላቅ ስጦታና የፍቅር መግለጫ መሆኑን በመዘንጋት አክብሮትና የተለየ ቦታ አይሰጡትም። ነገር ግን ይህ አስተሳሰብና አመለካከት ትክክል ያልሆነ ነዉ። ምክንያቱም ያ የተጠራ ሰዉ የደስታ ተካፋይ እንዲሆን እስከሆነ ድረስ የተጠራዉ፣ ጠሪዉ ከዚያ ሰዉ አንዳች ስጦታ ሆነ ሌላ ነገር መጠበቅ የለበትም። ግለሰቡ አቅሙ ፈቅዶለት ወዶ የሚያደርገዉ ሽልማት ሆነ ስጦታ ካለ ደግሞ በመመረቅና በማመስገን ከመቀበል ዉጭ ከሌሎች ሽልማት ሆነ ስጦታ ካላመጡት ሰዎች በማነጻጸር እንደተለየ አድርገዉ መመልከት የለባቸዉም። ምክንያቱም ያንን ሽልማት ወይንም ስጦታ ያመጣዉ ሰዉ አቅሙ ስለፈቀደለት ወይንም የተለየ ፍቅሩን ለመግለጽ ወይንም የራሴን አስተዋጽኦ ላድርግ ወይንም ከዚህ በፊት የተደረገለትን ዉለታ ለመመለስ ይሆናል። ባጠቃላይ ሰዉ በይሉኝታ ወይንም ዉለታ በመጠበቅ ወይንም ለራስ ስዉር ዓላማ ለማስለፍና ለመደለያ ሽልማትን ሆነ ስጦታን መስጠት የለበትም። ተቀባዩም ለቡድን ሆነ ለግለሰብ ስዉር ዓላማና ለመደለያ የሚሰጥ ሽልማትን ሆነ ስጦታን መቀበል የለበትም። ምክንያቱም የአሕዛብ ሕይወት በትዉልዱ ስለነገሠ ሰዉ ማድረግ ያለበትን ሳይሆን የሚያደርገዉ፤ በማንኪያ ሰቶ በጭልፋ ለመቀበል ወይንም በሁለት ጣት ሰቶ በአሥር ጣት ለመቀበል ነዉና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ ለሕሊናና ለአምላክ መታመን ልዩነት አለዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ ሰዉ ፍጹም ቢሆን ኖሮ ሁለቱም በአንድ ይጠሩ ነበር። ነገር ግን ሰዉ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ ስለሚያስብ፣ ስለሚናገር፣ ስለሚሰራ ሁለቱ ሊለያዩ ችለዋል። ያ ብቻ አይደለም እየራሳቸዉ ለሦስት ሊከፈሉ ችለዋል። በሕሊናዉ ፈቃድ ብቻ የሚመራ ሰዉ አንደኛዉ ላማነበት ነገር ለሕሊናዉ ታማኝ ሆኖ ይኖራል። ሁለተኛዉ ሕሊናዉ

የማይቀበለዉን ለመኖር ሲል እየፈጸመ ሊኖር ይችላል:: ሦስተኛዉ ከሕሊናዉ ተቃራኒ በመፈጸም ይኖራል:: እነዚህን ሳብራራ ለሕሊናዉ ታማኝ ሆኖ የሚኖር ሰዉ የሚያምንበት ትክክል ይሁን ስህተት ባመነበት ነገር ጸንቶ እስከመጨረሻ የሚኖር ሕሊናዉን የማይሸጥ ሰዉ ነዉ:: አቋሙን እንኳ የሚለዉጠዉና የሚያሻሽለዉ ስላመነበትና የቀድሞዉ አቋሙ ስህተት መሆኑን ሲያስተዉል ነዉ:: ሁለተኛዉ ሕሊናዉ ያላመነዉ እየፈጸመና እያስፈጸመ የሚኖር ሰዉ፤ ለመኖር ሲል ትክክለኛ ተግባር አለመሆኑን ሕሊናዉ እየመሰከረበት ነገር ግን ሕሊናዉን በማሳመን ለክብሩ፣ ለጥቅሙ፣ ለዝናዉ፣ ለሽልማት... ወዘተ ለመሳሰሉት ሲል ትክክል ያልሆነዉን ትክክል ነዉ እያለ የሚኖር ሰዉ ነዉ:: ከሕሊናዉ ተቃራኒ የሆነ ሰዉ ደግሞ ሕሊናዉ የሚፈጽመዉን ድርጊት እየተቃወመዉ ሕሊናዉን በማደንደን በትዕቢትና በእብሪት፣ በዓመፃ የሚፈጽም ሰዉ ነዉ:: እነዚህ ሦስት ባሕርይ(ጠባይ) ፖለቲከኞች ተላብሰዋቸዋል:: አንዳንዶቹ ዓለማቸዉ ትክክል ይሁን ስህተት ለእነሱ ትክክል መስሎ ስለታያቸዉ ባመኑበት ቆራጥ ሆነዉ ዓላቸዉን ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ:: አንዳንዶቹ ሕሊናቸዉ ባይቀበለዉ ራሳቸዉን አሳምነዉ ለሚያገኙት የሥልጣን ይሁን የተለያየ ጥቅማጥቅም ሲሉ የዓላማዉ ተባባሪና ፈጻሚ እንዲሁም አስፈጻሚ ይሆናሉ:: አንዳንዶቹ ደግም ሕሊናቸዉ እየተቃወማቸዉ ከሕሊናቸዉ በተቃራኒ በመሰለፍ ሕሊናቸዉን አደንድነዉ «በሉ» የተባሉት ይላሉ:: «ፈጽሙ» የተባሉትን ማንኛዉንም ነገር ይፈጽማሉ:: በመሪነት ደረጃ ላይ ያሉት ዋና ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች በአንደኛዉ ምድብ ዉስጥ ሲካተቱ፤ ከእነርሱ ስር ያሉ ባለስልጣናት ደግሞ በሁለተኛዉ ምድብ ዉስጥ ይገባሉ:: ካድሬዎችና ከላይ ከመሪዎችና ከባለሥልጣናት የሚተላለፈዉን የበቀል፣ የክፋት፣ የተንኮል ስራ አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች ደግሞ በሦስተኛዉ ምድብ ወይስ ይመደባሉ::

ለአምላክ መታመን የሚለዉም እንደ ሕሊና በሦስት የሚከፈል ሲሆን፤ አንደኛዉ እምነቱ ትክክል ይሁን ስህተት ላመነበት እምነት ራሱን ሰዉቶና ታማኝ ሆኖ የሚገኝ ነዉ:: ሁለተኛዉ ደግሞ በዚያ እምነት ዉስጥ በመገኘቱ በሚያገኘዉ የሥልጣን ይሁን ክብር እንዲሁም የተለያዩ ሥጋዊ ትቅማጥቅሞች ምክንያት ለአምላክ የታመነ መስሉ የሚኖር አስመሳይ አገልጋይና አማኝ ነዉ:: ሦስተኛዉ ደግሞ እያመለከ ያለዉ ፍጹም የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ መሆኑን እያወቀ በድፍረት ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚፈጽም ነዉ:: እነዚህ ለማብራራት የመጀመሪያዉ ሰዉ ለነፍሱ ፈቃድ ቅድሚያ በመስጠት እምነቱን ወይንም ሃይማኖቱን እንድ ትክክለኛ የሕይወት መስመር ቆጥሮ በእምነቱ የሚታዘዘዉን ትእዛዝ አክብሮ የሚኖርና እንደ እምነቱ ሆኖ የሚገኝ ነዉ:: ሁለተኛዉ ሰዉ ደግሞ የሚያምንበት ሃይማኖት ሆነ እምነት ትክክል ይሁን ስህተት ግድ ሳይሰጠዉ ለሥጋዊ ክብርና ጥቅም ቅድሚያ ሰቶ እንደ ሥጋና ደሙ ስሜት የሚያገለግልና የሚያምን ነዉ:: የተሻለ ጥቅም የሚያገኝበት ሌላ መንገድ ካገኘ በዚያም ለመመላሰስ ወደ ኋላ የማይል ነዉ:: ነገር ግን ሁሉን በእምነትና በአምላክ ስም ነዉ የሚያከናዉነዉ:: ሦስተኛዉ ደግሞ የሚፈጽመዉ ተግባር የሚናገረዉ ንግግር ፍጹም ኢ-ሃይማኖታዉ ሆኖ ሳለ ለራሱም ሆነ ለሌላዉ እንደ ትክክለኛ ተግባርና ንግግር እንደፈጸመ በማቅረብ በተለያየ ባዕድና ጣዖት አምልኮ የሚመላለስ በሰዉ ላይ የተለያየ ግፍና ጭከና ተግባር የሚፈጽም ፍጹም የዲያብሎስ አገልጋይ ነዉ:: ከላይ በተገለጹት ዉስጥ በመጀመሪያዉ ምድብ ዉስጥ በተለያየ ሃይማኖት ወስጥ ከወላጆቻቸዉ በወረሱት ሃይማኖት ዉስጥ የሚመላለሱ ሰዎች የሚመደቡበት ሲሆን፤ በሁለተኛዉ ዉስጥ ደግሞ ቀድሞ እምነት ይኑራቸዉ አይኑራቸዉ ወይንም

ለተለያየ ጥቅም ማግኛ ሲሉ በተለያየ እምነት ወይንም ሃይማኖት ዉስጥ የሚመላለሱት ሰዎች ይመደባሉ። በሦስተኛዉ ምድብ ደግሞ በሃይማኖትና እምነት ሽፋን የራሳቸዉን የሥጋና የደም ስሜት ለማርካትን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ዓለማቸዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ይመደቡበታል።

መሆን ያለበት እያንዳንዱ ሰዉ ለሕሊናዉና ለአምላኩ በአንድ ላይ መታመን ነዉ። ሁለቱ በአንድ ላይ ተዋሕደዉ የሚገኙበት ሰዉ አንድ ሕሊናዉ የማያምንበትና የማይቀበለዉን አይፈጽምም፤ አያስፈጽምም። እንዲሁም ለእዉነተኛዉ አምላክ የታመነ ስለሆነ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የተሰለፈና ሁሉን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እየመረመረ ከእዉነት ጋር ብቻ ተሰልፎ የሚኖር ነዉ። ሁለቱንም አጣምሮ ስለያዘ በተሳሳተ መስመር ዉስጥ ቢሆን እንኳ ለሥጋዊ ሥልጣን ሆነ ክብር እንዲሁም ለተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ሲል ሕሊናዉን የማይሸጥና ለአምላኩ የሚታመን ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለመቀበልና በእዉነተኛዉ የሕይወት መስመር ለመጓዝ አይከብደዉም። አሁን በዓለም  የሚታየዉ  እዉነታ ግን እያንዳንዱ ሰዉ ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ የሚኖርበትን የሕይወት መንገድ መፈለግ ሳይሆን እያንዳንዱ ሰዉ የራሱን የዉሸት እዉነት ፈጥሮ ሰዎች በዚያ የዉሸት እዉነት መንገድ ዉስጥ እንዲመላለሱ ማድረግ ነዉ ። ስል እዉነት ራሱን ክዶ የሚመሰክርና በእዉነትም የሚኖር ሰዉ ከሌላዉ ሰዉ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር የለም ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ ሰዎች ለሥጋቸዉ የሚመች ሥርዓት ነዉ የመሰረቱ እንጂ ለሕያዉ ነፍሳቸዉ የሚሆን አይደለምና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ ሰዉ ለሕሊናዉና ለአምላኩ ከታመነ ሕግና ሥርዓት ያስፈልገዋል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ ለሕሊናዉና ለአምላኩ የታመነ ፍጹም ሰዉ የለም እንጂ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረና እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍስ ያለችዉ ሰዉ ሕግና ሥርዓት ባለስፈለገዉና «ይህን አድርግ፣ ይህን አታድርግ» ባልተባለ ነበር። በዚህች ምድር አምስት ዓይነት ሰዎች ስላሉ እነዚህም አእምሮ ጽኑአን(የበቁ ነፍሳት) የተባሉ፣ አእምሮ አዋቂዎች(ምርጥ ነፍሳት) የተባሉ፣ አእምሮ ሕፃናት(ራሳቸዉን በደንብ ያልገዙ ልክስክስ ባሕርይ የያዙ) የተባሉ፣ አእምሮ ቀላል(የረከሰ ጠባይ የያዙ) የተባሉ፣ ትዕቢት ክህደት ዓመፃ(የፈርኦን የይሁዳ የአርዮስ ወንድምና እህቶች) የተባሉ ናቸዉ።

ለአእምሮ ጽኑአን ሕግና ሥርዓት ባያስፈልጋቸዉም በምድር ዉስጥ ካሉት ሕዝቦች ብዛት አንጻር አንድ መቶኛ (አንድ ፐርሰንት) ስለማይሞሉ ግድ ለሌሎች በሚያስፈልገዉ አስፈላጊ ሕግና ሥርዓት ዉስጥ ሊኖሩ ይገባል። ለአእምሮ አዋቂዎች ሆነ ለሌሎች ሕግና ሥርዓት ግድ ያስፈልጋል። ምክንያቱም አእምሮ አዋቂዎች በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት እንዲሁም ለተለያዩ ጥቅሞች በመሸነፍ ሕግና ሥርዓት ሊተላለፉ ይችላሉና። አእምሮ ሕፃናት በሥጋቸዉ አዋቂ ቢሆኑም በአእምሮዋቸዉ ሕፃናት የሆኑ ልክስክስ በሆነ ጠባያቸዉ ምክንያት ሕግና ሥርዓት ሊተላለፉ ይችላሉ። አእምሮ ቀላሎች በረከሰ ጠባያቸዉ ምክንያት በበለጠ ሁኔታ ሕግና ሥርዓት ሊጥሱ

ይችላሉ፡፡ ትዕቢት፣ ክፋት፣ ዓመፃ የተባሉ የፈርኦን የይሁዳ የአርዮስ ወንድምና እህቶች ደግሞ በከፋ መልኩ ሕግና ሥርዓት ሊጥሱ ይችላል፡፡ በመሆኑም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተዘጋጀ የቅድስናና የጽድቅ ሕገ መንግሥትና ሰማያዊ ሥርዓት የተላበሰ ሥርዓት በዚህች ምድር ለሰዉ ዘሮች ግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰዉ በእኩልነትና በነጻነት የሚዳኝበት የፍትሕ ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡ «ከሕግ በላይ ልሁን፤ ከሥርዓት ወጥቼ እንደፈለኩ ልሁን፤» የሚል ሰዉ ማንም ይሁን ማን እንደ ዓመፃዉ ደረጃ ዋጋ የሚከፍልበት(የሚቀጣበት) ሕግና ሥርዓት ከሌለ እያንዳንዱ ሰዉ የተለያየ ጽናትና ጠባይ እዲሁም አስተሳሰብና ሕይወት ስለያዘ ሕገወጥነትና ሥርዓተ አልበኝነት ይነግሣል፡፡ ይህም ሰዎች እንደ እንስሳት በሥጋና በደም ስሜታቸዉ ብቻ እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም እልፍ አእላፋት ርኩሳን መናፍስት በሞሉባት ምድር ዉስጥ እያንዳንዱ ሰዉ አግባብነት ባለዉ ሕይወትና ኑሮ እንዲኖር የሚገደብበትና ገደቡን ካለፈ ዋጋ የሚከፍልበት(የሚቀጣበት) እዉነተኛ ሕግና ሥርዓት ያስፈልገዋል፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አራት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: የእግዚአብሔር እንደራሴዎችና ባለሚሎች እንዲሁም እዉነተኛ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ታላቅ የክብር ስም እያላቸዉና ለወደፊትም ምን እንደሚሆኑ እያወቁ ራሳቸዉን ግን «አገልጋይ(ባሪያ) ነን» እያሉ ነዉ ለሕዝቡና ለምእመኑ አገልግሎት የሚሰጡት:: ለምን እንዳላቸዉ የክበር ስምና እንደሚኖራቸዉ የስም አጠራር ራሳቸዉን አይጠሩም?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ከእግዚአብሔር የሆኑ እዉነተኛ እንደራሴዎችና አገልጋዮች ለራሳቸዉ ክብርና ዝና የሚቆሙ፣ ራሳቸዉን የሚክቡ፣ ከፍ ከፍ የሚያደርጉ አይደሉም:: የአምላካቸዉን ክብርና ዝና የሚያስቀድሙ፣ ስለ እዉነት የሚመሰክሩና የሚኖሩ ናቸዉ:: ምንም እንኳ በዓለም እያሉ የተለያየ ስያሜ ቢያገኙም ለምሳሌ ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) ንጉሥ፣ ፕሬዝደንት(ርእሰ ብሔር)፣ ጠቅላይ ምሉክ(ጠቅላይ ሚኒስተር)፣ ሚኒስትር፣ ኃላፊ፣ አስተዳዳር፣ ተጠሪ ... ወዘተ የሚል ስያሜ ቢኖራቸዉ እንኳ፤ እዉነተኛ ተጠሪነታቸዉ ለአምላክ ስለሆነ፤ ራሳቸዉን እንደ ሕዝብ አገልጋይነታቸዉ(ባሪያነታቸዉ) ነዉ የሚመለከቱትና የሚቆጥሩት:: እንዲሁም ርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌ(ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት) (ፓትርያርክ)፣ ሊቀካህናት(ሊቀጳጳስ)፣ ካህን(ጳጳስ)፣ ኃላፊ፣ አስተዳዳሪ ፣ ተጠሪ... ወዘተ የሚል ስያሜ ቢኖራቸዉም፤ እዉነተኛ ተጠሪነታቸዉ ለአምላክ ስለሆነ፤ ራሳቸዉን እንደ ምእመን አገልጋይነታቸዉ(ባሪያነታቸዉ) ነዉ የሚመለከቱትና የሚቆጥሩት:: በዚህም ምክንያት እንደ አገልጋይነታቸዉ እስከ እለተ ሞታቸዉ (በሥጋ ሞት) እስከሚጠሩ ድረስ በእዉነት፣ በቅንነት ፣ በታማኝነት አገልግለዉ ወደ ፈጣሪያቸዉ ከሄዱ እንደ አገልግሎታቸዉ ደረጃ እዉነተኛዉን ማዕረግ ከእግዚአብሔር አግኝተዉ ከሰማያዉያኑ ቅዱሳን መላእክት ወይንም ከጻድቃን ጋር እንደ ብቃታቸዉና ፍሬያቸዉ ደረጃ ተቀላቅለዉ በእዉነተኞቹ በእግዚአብሔር ባለሚሎች ዘንድ ይጠራሉ:: እስከ እለተ ሞታቸዉ ድረስ ካልታመኑና በእዉነትና በቅንነት ካለገለገሉ ደግሞ፤ በዓለም ሳሉ ያገኙት ከፍተኛ ማዕረግና ስያሜ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቃቸዉና ፍርዱን ከተራዉ ሰዉ በላይ የሚያስብስባቸዉ ነዉ:: ከዚህ አንጻር በታማኝነት ስለ እዉነት ራሱን ክዶ በእዉነትና በቅንነት፣ በትጋት ማገልገል የማይችል ሰዉ እንኳን ለከባድ ኃላፊነት ቀርቶ ለቀላል ኃላፊነት ባይሾም ይሻለዋል:: ምክንያቱም እንደተሰጠዉ ኃላፊነት ቢያንስ ዝቅተኛዉን ፍሬ ሊያፈራና በሕይወቱ ደግሞ እግዚአብሔርን መምሰል ተላብሶ በትህትና በፍቅር፣ በእዉነት፣ በትጋት፣ በቆራትነት ሊያገለግል ይገባዋልና::

አሁን በዓለም ያለዉ እዉነታ ግን ሰዎች በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ለተለያየ ኃላፊነት የሚወጡት ሥጋዊ ጥቅምና ክብር እንዲሁን ዝናና መግነንን ለማግኘትና የራሳቸዉን የሥጋና የደም ስሜታና ፈቃድ ለማርካትና ለመፈጸም ነዉ እንጂ፤ የእግዚአብሔር ተጠሪ ሆነዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ሕዝቡንና ምእመኑ በትህትና፣ በፍቅር፣ በእዉነት፣ በትጋት፣ በቅንነት፣ በታማኝነት ለማገልገል አይደለም:: ለዚህም ነዉ በሁለቱም ወንበር የተቀመጡ ከላይ እስከታች ያሉ ኃላፊዎች በአምባገነንነት ሕይወት የሚመላለሱትና ራሳቸዉን አድራጊ፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ እድርገዉ በመቁጠር፤ ሲፈልጉ የሚችሩ፣ ሲፈልጉ የሚነሱ አድርገዉ ራሳቸዉን በመቁጠር የሕዝብና

የምእመናን አገልጋይ(ባሪያ) መሆናቸዉን ክደዉና ዘንግተዉ ሕዝቡንና ምእመኑን እየበደሉት፣ እያማረሩት ያለዉ፡፡ የአገልግሎት የማዕረግ ስሙንም የሚፈልጉት ሊነግዱበት፣ የራሳቸዉን ፈቃድ ሊፈጽሙበትና ሊያስፈጽሙበት ነዉ እንጂ፤ በእግዚአብሔር እንጠየቅበታል በማለት እረኝነታቸዉንና ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ የሚወጡበት አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት በተወሰነ ማዕረግ መጠራት ስለማያረካቸዉ አንድ ሉክ ወረቀት የሚፈጅ ስያሜ እየተደጋገመ እንዲጠራ የሚፈልጉ፣ ራሳቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ ናቸዉ፡፡ ይህም የሚያሳየን እነዚህ አምባገነንና አስመሳይ አገልጋዮች የዲያብሎስ ተጠሪና ፈቃዱን የሚፈጽሙ፣ የሚያስፈጽሙ ናቸዉ እንጂ የእግዚአብሔር ተጠሪ፣ ፈቃዱን ፈጻሚና አስፈጻሚ አይደሉም፡፡

የአምባገነንና የአስመሳይ አገልጋዮች ሕይወታቸዉና ተግባራቸዉ በእዉነተኛ በእግዚአብሔር እንደራሴዎችና አገልጋዮች ስለሚታወቅ ነዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ የሕዝብና የምእመናን አገልጋይ እንጂ ሌላ ምንም እንዳልሆኑ ራሳቸዉን በመቁጠር «አገልጋያችሁ(ባሪያችሁ)» እያሉ ለሕዝቡና ለምእመኑ ራሳቸዉን የሚያስተዋዉቁትና የሚሰይሙት፡፡ እነዚህ እዉነተኛ የእግዚአብሔር እንደራሴዎችና አገልጋዮች ያላቸዉንና የሚኖራቸዉን የአገልግሎት ማዕረግ ስያሜ ሳያዉቁ ቀርቶ አይደለም፤ ከምንም ምንም ጸጋ የሌላቸዉ ዓመፀኛ መሪዎችና አገልጋዮች ስንትና ስንት ስያሜ ይዘዉ ሲጠሩ፤ እነሱ ግን እግዚአብሔር የሰጣቸዉን የአገልግሎትና የክብር ማዕረግ ከቁም ነገር ሳይቆጥሩት እንደ ተራ ሰዉ አገልጋይ(ባሪያ) እያሉ ለራሳቸዉ ስያሜ የሚሰጡት፡፡ ምክንያቱም ዋና ዓላማቸዉና ግባቸዉ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽመዉና አስፈጽመዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ መሄድና ማንም ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያጠፋዉ የማይችለዉን እዉነተኛዉን ሰማያዊ ማዕረግና አክሊል ለማግኘት ነዉ፡፡

<u>ጠያቂ አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ማለት ነዉ? አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት «ክርስቶስ ወደዚህች ምድር መቶ መንግሥት ይመሰርታል» ከሚሉ የተለያዩ እምነት ድርጅቶች ጋር ያያይዙታል፡፡ ከዚህ ጋር የተገናኘ ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት እግዚአብሔር ወደዚህች ምድር መቶ የሚዘረጋዉና እርሱ ምድራዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የሚፈልጋቸዉን በዙፋኑ ዙሪያ አድርጎ እንዲያስተዳድሩ የሚያደርገዉ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከአዳምና ሔዋን መፈጠር ጀምሮ የነበረ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ ላይ ተዋሕደዉ (እንደ ሥጋና ነፍስ እንዲሁም መንፈስ ተዋሕደዉ) በአንድ መንፈስ ቅዱስ ወይንም በአንድ እግዚአብሔር በበላይነት ሲመሩና የእርሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ሲፈጸም የሚታይ ሕይወትና ሥርዓት ነዉ እንጂ፤ ክርስቶስ ዳግም መቶ የሚመሰርተዉ መንግሥት አይደለም፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር እንደ ፍጡሩ ሰዉ ዘዉድ ጭኖ የሚነግሥ አይደለም፡፡ እያንዱን ፈቃደኛ በሆነ ሰዉ ላይ እግዚአብሔር በሕይወቱና በሕሊናዉ ላይ ነግሦ ፈቃዱን ሊያስፈጽምና ሙሉ በሙሉ ሊያድርበት ይችላል፡፡ እንዲሁም ፈቃደኛ የሆነ ትዉልድ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት ዉስጥ መመላለስና መኖር ይችላል፡፡ ይኸዉም አምላኩንና ፈጣሪዉን የባላይ ንጉሥ አድርጎ እርሱ

የሚያሰራዉን ስራ በመስራት ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ ላይ ተዋሕዶ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሰለፍ፣ በምድርም በረከትን በሰማያም ሕያዉ ሕይወትን ይዞ መኖር ይቻላል።

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: በገነት ሆነ በሰማያት ዉስጥ የሚኖሩት ቅዱሳንና ጻድቃን ናቸዉ። እንዲሁም በሁለቱም ቦታዎች የሚኖሩ ሕያዉ ፍጥረታት በምሳሌያዊ ባሕርይ ነዉ የተገለጹት። ታዲያ በሁለቱም ቦታ የሚገኘዉ ደስታና የሕሊና ሰላም እዲሁም እርካታ አንድ ዓይነት ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እንደተባለዉ በሁለቱም ቦታዎች (ዓለማት) ሕያዋን ፍጥረታት የሚገለጹት በረቂቅ አካም በምሳሌያዊ ባሕርይ ነዉ። እንዲሁም በሰማያት ያሉት ቅዱሳን ሲሆኑ በገነት ያሉት ደግሞ ጻድቃን ናቸዉ። በዚህም ምክንያት የሚኖራቸዉ ደስታ፣ የሕሊና ሰላም፣ እርካታ እንደ ማዕረጋቸዉ ይለያያል። ይኸዉም ቅዱሳን መላእክት በሰማያት ዉስጥ ሳጥናኤል ባስነሳዉ የዓመፃና ክህደት ድርጊት እንደመቃወማቸዉና ጽናታቸዉ ደረጃ ከ60 እስከ 100 ነጥብ ያገኙ ሲሆን፤ በዚሁ መሰረት 100 ነጥብ ያገኘዉ ቅዱስ ሚካኤል የሁሉ አለቃና ከሁሉ የሚበልጥ ክብርና ደስታ እንዲሁም እርካታ አለዉ። የሕሊና ሰላም ግን ሁሉም በእኩልነት አላቸዉ። በገነት የሚኖሩት ጻድቃንም እንደ ምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ የጽድቅና አገልግሎት ብቃት ደረጃ ነዉ ከ60 እስከ 89 ነጥብ አግኝተዉ፣ በዚያዉ ነጥባቸዉ ልክ ደስታና ርካታ አግኝተዉ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሚቆዩት። የሕሊና ሰላም ግን ሁሉም በእኩልነት አላቸዉ። በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ነፍሳቸዉን እንደ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስና ወንጌላዊዉ ቅዱስ ዮሐንስ እንዲሁም እንደ ጻድቁ ሄኖክና እንደ ነብዩ ኤልያስ ያሉ፣ ባጠቃላይ ራሳቸዉን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ እንዳደረሱት ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ቅዱሳን ነፍሳት ከ90 እስከ 99 ነጥብ ያገኙ ጻድቃን ደግሞ፤ እግዚአብሔር በአምላካዊ ሥልጣኑ ነፍስ ከሥጋቸዉ እንደተለየች ቅዱሳን መላእክት የተገለጹበትን ረቂቅ አካል ምሳሌያዊ ባሕርይ እንዲገለጹበት በማድረግ እንደ ነጥባቸዉ ማዕረግ ወደ ሰማያት ዉስጥ በማስገባት ከቅዱሳን መላእክት ጋር ይደምራቸዋል። በፍርድ ቀን ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት ጋር በመሆን እንደ ማዕረጋቸዉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጅበዉ በክብር በማረፊያ ቦታ ላይ ይገኛሉ።

በገነት ዉስጥ በምሳሌያዊ ባሕርይ(በረቂቅ አካል) የተገለጹት ጻድቃን ለገነት የሚያበቃዉን ዝቅተኛ ነጥብ 60 እስከ ከፍተኛዉ 89 ነጥብ ያገኙት ጻድቃን በፍርድ ቀን ወደ ሰማያት ሲገቡ በሰባት እጥፍ የሚበልጠዉን ቅዱሳን መላእክት የተገለጹበትን ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ነዉ የሚገለጹበትና የሚገኙት ደስታና ርካታ እንደ ጽድቅ ደረጃቸዉ(ነጥባቸዉ) ቢለያይም በሰባት እጥፍ ያህል ከገነት በላይ የሚሆን ደስታና ርካታን በሰማያት ያገኛሉ። በምድር ያሉ ጻድቃን ከገነት ከሚኖሩት ጻድቃን ገር የሚያገኙት ርካታም ሲነጻጸር እንደ ነጥባቸዉ ደረጃ ቢለያይም፤ የሁሉም በሰባት ነጥብ አንሶ ነዉ የሚገኘዉ። በምድር የሚያገኙት ርካታ(ድስታ) በገነት በሰባት እጥፍ ሆኖ ነዉ የሚጠብቃቸዉ። በፍርድ ቅን ወደ ሰማያት ሲገቡ ደግሞ በሰባት እጥፍ እንደገና የሚጨምር ይሆናል። ይህም የሚያሳየን በምድር ሆነ በገነት እንዲሁም በሰማያት ዉስጥ የሚኖረዉ ደስታና

እርካታ የሚለያይና የሚያገኙት እርካታና ደስታ እንዲሁም ክብር እንደ ነጥባቸዉ እንደሚለያይ ነዉ። ነገር ግን የሕሊና ሰላም ሁሉም በእኩልት ስላላቸዉ በገነትና በሰማያት ዉስጥ ቅናት ሆነ ሌላ የተለየ ምኞት በዉስጣቸዉ አያድርም። በምድርም ቢሆን በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር የሚመላለሱ ሰዎች በየትኛዉ እምነት ሆነ የሕይወት መስመር ዉስጥ ይኑሩ የሕሊናቸዉ ሰላም በእኩል የተጠበቀ ነዉ። የሚያገኙት ርካታና ደስታ ግን እንደ ቅን ሐሳባቸዉና መልካም ተግባራቸዉ ደረጃ ይለያያል።

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት)( አጋንንት) ለምድነዉ ማደሪያቸዉን ቆሻሻ በሆነ ነገር ላይ የሚያደርጉት? እንደ እኛ ሰዎች ሕያዋን የሆኑ፣ እንደ ቅዱሳን መላእክት የነበሩ አይደለም ወይ?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: ቅዱሳን መላእክት ሆኑ ርኩሳን መናፍስት እንዲሁም ሰዎች ነፍሳቸዉ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ታላቅ ፍጥረት ናት። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጸጋና ጥበቃ ስትለይ በተቃራኒ መልክ ትገለጻለች። ለዚህም ነዉ ርኩሳን መናፍስት ከእግዚአብሔር ጸጋ የተለዩና እንዲሁም በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ ስለጸኑ ኑሮዋቸዉ በረከሰና በሸተተ ቦታና ሕይወት ላይ የሆነዉ። ለምሳሌ ብንመለከት ከሰዉና ከእንስሳ አካል ዉጭ ባሉ ቆሻሻ ቦታ ዉስጥ ከመኖር በተጨማሪ በዐይነ ምድር፣ በሽንት፣ በፋንዲያ፣ በእበት፣ በኩስ፣ በበጠጥ፣ በንፍጥ፣ በአክታ በመሳሰሉት ዉስጥ ያድራሉ። ባሕርያቸዉም የሚሸት ሆኗል። ለዚህም ነዉ ወደ ሕሊናችን የሚገቡት ርኩሳን መናፍስት በአፍንጫችን በኩል በማስነጠስ ሲወጡ የተለየ መጥፎ ጠረን ያላቸዉ። እንዲሁም በሆዳችን ዉስጥ የሚገቡት በፊንጢጣችን በኩል በፈስ መልኩ ሲወጣ መጥፎ ሽታ ያላቸዉ።

እንኳን ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ቀርቶ የሰዉ ዘሮች ከእግዚአብሔር ጸጋ ራሳቸዉን ሲያርቁና ርኩሳን መናፍስትን ወደ ሕሊናቸዉና አካላቸዉ ሲያቀርቡ የርኩሳን መናፍስት ባሕርይ ይላበሳሉ። ቀላሉን ምሳሌ ብንመለከት እንኳ ሲጃራ መጥፎ የሚገማ ሽታ እንዳለዉ ይታወቃል፤ ነገርን ሰዎች ያጨሱታል። እንዲሁም በላበት ሆነ በተለያየ ምክንያት አካላችን ሲሸት ከመታጠብና ንጽህናችን ከመጠበቅ ይልቅ በዚያ መጥፎ ጠረን ዉስጥ እንሆናለን። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍስ ያለችዉ ሰዎች፤ በየገንዳዉና በቆሻሻዉ ቦታ ላይ ማደሪያቸዉና የጫት ገራባ መፈለጊያቸዉ አድርገዉታል። ይህም የሚያሳየን ሰይጣናት ብቻ ሳይሆኑ የሰዉ ልጆችም እግዚአብሔር መምሰል የተላበሰችዉ ነፍሳቸዉ የሰይጣናት ማደሪያ ስትሆን የእነርሱን ባሕርይ ትላበሳለች። ሙሉ በሙሉ የእነርሱን ባሕርይ ስትላበሰ ደግሞ የተለያዩ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር ትፈጽማለች።

በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ የምፈልገዉ አንዳንድ ርኩሳን መናፍስት ገላችንን የምንታጠብበትን ዉኃ መቋቋም ስለሚያቅተቸዉ በተለያየ መንገድ ከገቡበት ሕሊናችን ሆነ አካላችን ወዲያዉ ይወጣሉ። ለዚህም ነዉ መላ አካላችንን ስንታጠብ የሚቀለንና ያ በተለያየ መንገድ ከብዶን የነበረ የሕሊና ሆነ የአካል ድካም የሚወገድልን። ስለዚህ እኛ ሰዎች ነፍሳችን እግዚአብሔርን መምሰል

የተላበሰች ታላቅ ፍጥረት መሆኗን ተገንዝበን በአግባቡ ልንጠብቃትና እንደ ሰዉ ባሕርይ ልንኖር ይገባል እንጂ ወደ ሰይጣናት ባሕርይ መለወጥ የለብንም:: ያንን የምናደርግ ከሆነ የሚጠብቀን ቅጣት ከሰይጣናት በላይ ነዉ:: ምክንያቱም ወደ መንግሥት ሰማያት የመግባት እድል ያላት ሕያዉ ነፍሳችንን አቅለን በመገኘታችንና በዓመፃና በክህደት ሕይወት እንደ ሰይጣናት በመጽናታችን ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ ሰዎች የዉስጣቸዉ ሐሳብና ምኞች ሌላ ሰዉ አዉቆ እንዲፈጽምላቸዉ ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ያ የሚጠብቁት ሰዉ የዉሳጣቸዉን ፍላጎትና ስሜት መፈጸም ካልቻለ ይቀየሙታል:: የዉስጥን ሐሳብና ምኞች አዉቆ ሰዉ የሚፈልገዉን ማድረግ ይቻላል ወይ? ይህን ማድረግ ያልቻለን ሰዉ መቀየሙ ትክክል ነዉ ወይ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: የዉስጥን ሐሳብና ፍላጎት በአንደበታችን ወይንም በምልክት ካልገለጽን በስተቀር እንደ እኛዉ ዓይነት ሰዉ የዉስጣችንን ሊያዉቅና የምንፈልገዉን ማደረግ ሊሳነዉ ይችላል:: ምናልባት ሐሳባችንና ፍላጎታችንን ሊገምት ይችላል እንጂ በሥጋና ደም ስሜት የሰዉን ሐሳብና ፍላጎት በእርግጠኛነት ማወቅ አይቻልም:: እግዚአብሔርና እርሱ የፈቀደላቸዉ ፍጡሮቹ ብቻ ናቸዉ የዉስጣችንን ሐሳብና ፍላጎት የሚያዉቁት:: በመሆኑም እያንዳንዱ ሰዉ በግልጽ ፍላጎቱንና ሐሳቡን በመገለጽ ሊደረግለት የሚገባዉንና የሚፈልገዉን ለሚመለከተዉ ግለሰብ ሆነ አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል እንጂ «እንዴት የዉስጤን ፍላጎትና ሐሳብ አዉቆ ፍላጎቴን አያሟላም? አታሟላም?» ብሎ መቀየም አግባብነት የለዉም:: ቅሬታ ያለበት ሰዉ በግልጽ ቅሬታዉን ቅሬታ ላሰደረበት ሰዉ መግለጽና ምክንያቱም መጠየቅ ነዉ ያለበት እንጂ፤ ያ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ቅሬታ ያሳደረዉ ሰዉ ማስቀየሙን እንኳ ላያዉቅ ይችላል:: ባጠቃላይ ለማንኛዉም ማኅበራዊ ጉዳይና ኑሮ እያንዳንዱ ሰዉ በግልጽ መነጋገርና መወያየት ይገባዋል እንጂ እንደ ግል የዉስጥ አስተሳሰብ በዉስጣችን የምንቀየምና የምንብገነገን ከሆነ አንዳች ጥቅም የለዉም:: ይልቁኑ ራሳችንን ለጥላቻና ለበቀል በማዘጋጀት ለዲያብሎስ መንፈስ ማደሪያ እንሆናለን፤ የዓመፃ ስራን በመፈጸም ከእግዚአብሔር ልንጣላ እንችላለን::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የሰዎች ጠባይ በየቀኑ አይደለም በየሰዓቱና በየደቂቃዉ የሚለዋወጥበት ምክንያት ምንድነዉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት ይህች ምድር በብዙ ትእልፊት(በብዙ ቢሊዮን) የሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስት የተሞላችና ዋና ተግባራቸዉም እኛን የሰዉ ዘሮችን በተግባር ሆነ በንግግር እንዲሁም በሐሳብ ጭምር ኃጢአት እንድንፈጽም በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ማጣላትና ለገሃነመ እሳት መዳረግ ነዉ:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጸጋ የራቃቸዉ ስለሆነ ዉስጣቸዉ በክፋትና በተንኮል እንዲሁም በምቀኝነት የተሞላ ነዉ:: እንኳን እነሱ በኃጢአቱ ምክንያት የእግዚአብሔር ጸጋ የራቃቸዉ ሰዎች ሳይቀር በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት የተሞሉ ናቸዉ:: ታዲያ እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ወደ ሕሊናችንና አካላችን በመግባት ይፈትኑናል:: ራሳችንን በሚገባ መግዛት ካልቻልን ፈተናዉን መቋቋም አቅቶን የማይገባ ጠባይ ልናሳይ እንችላለን::

ለዚህም ነዉ እያንዳንዱ ሰዉ ራሱን በሚገባ ለመግዛት ሕይወቱን በጾምና በጸሎት መምራት ያለበትና በሐሳቡ፣ በንግግሩ፣ በተግባሩ እግዚአብሔርን በማምለክና በማፍቀር እንዲሁም በማክበርና በመፍራት መመላለስ የሚገባዉ:: ያኔ ከእግዚአብሔር ጸጋን(ኃይልን) ስለሚላበስ ተለዋዋጭ ጠባይ አያሳይም:: የሚመጣበትን ፈተና ሁሉ በመቋቋም አእምሮዉ በትክክለኛ አስተሳሰብና ተግባር እንዲጸና ማድረግ ይችላል::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸዉን የወደዱና የጠቀሙ እየመሰላቸዉ «እኔ እያለዉ ልጄ ስራ አይሰራም፥ አትሰራም» የሚሉ አሉ:: እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸዉን በሥርዓቱ ተቆጣጥሮ ማሳደግ ተስኗቸዉ አንዳንድ ነዉር የሆኑትን ለምሳሌ ንፍጥን መማቅ፥ ጣትን እየላሱ መብላት፥ ሰዉ ፊት አፍንጫን መጎርጎረና መትፋት፥ ሰዉ ፊት ተንፈራግጦና ተበለቃቅጦ መቀመጥ፥ ሰዉ ላይ ማሳል፥ በሰዉ ላይ መጮኽ፥ በሰዉ ፊት መፍሳት ... ወዘተ የመሳሰሉትን ነዉሮች ትዉልዱ እንደ ትክክለኛ ተግባር ቆጥሮ ይፈጽመዋል፤ እንደ ነዉርም አይመለከተዉም:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: በተለያየ ቦታ እንደጠቀስኩት የእግዚአብሔር ሕያዉ ፍጥረትና ልጆች የሆኑትን ሕፃናትን፤ እግዚአብሔርን በመወከል በአግባቡና በሥርዓቱ ማሳደግ የእያንዳንዱ ወላጅ ድርሻ ነዉ:: በአግባቡና በሥርዓቱ ያላሳደገ ወላጅ ከማንም በላይ የመጀመሪያዉ ተጎጂ እርሱ ነዉ:: በአግባቡና በሥርዓቱ ካሳደገ የመጀመሪያዉ ተጠቃሚ እርሱ ነዉ:: አንዳንድ ወላጆች ከአስተሳሰብና ካመለካከት ጉድለት የተነሳ ስራንና ሙያን እንደ ዉርደት ይመለከቱታል:: እዉነታዉ ግን የተለያየ ስራና ሙያ ባለቤት የሆነ ሰዉ የከበረ ነዉ እንጂ የተዋረደ አይደለም:: ይልቁና ስራ የማይችልና ሙያ የሌለዉ ነዉ ዉርደትን የሚላበሰዉ፤ በኑሮዉም የሚቸገረዉ:: ስለዚህ ልጆችን ስራ አለማለማመድና ሙያ እንዳይኖራቸዉ ማድረግ እነሱን መጎዳት ነዉ እንጂ መጥቀም አለመሆኑን እያንዳንዱ ወላጅ ሊያስተዉለዉ ይገባል:: በየትኛዉም የሀብት ደረጃ ላይ ያለ ወላጅ እርሱ ወቶ ወርዶ እንዳገኘ ሁሉ ልጆቹም ሰርተዉ እንዲያገኙ ማድረግ ነዉ ያለበት እንጂ ስንፍናን ካስተማረ ለልጆቹ ወድቀትን እየተመኘ ነዉ ማለት ነዉ:: ምክንያቱም ሀብት ወቶ ወርዶ እንደሚገኝ ልጆች ካለወቁ የገንዘብ አባካኝ ነዉ የሚሆኑት እንጂ ለራሳቸዉ ሆነ ለሌዉ ቅርስ ማስቀመጥን አይፈልጉም:: የእዉነተኛ ሀብት ምንጩን ካወቁ ግን ገንዘብን በአግባቡ በመጠቀም ለወገናቸዉና ለአገራቸዉ የሚተርፉ የስራ ሰዉ ይሆናሉ::

በዓለም ያለዉ እዉነታ ግን በስርቆት ሆነ በአቋራጭ መንገድ የተገኘ እንዲሁም በእዉነተኛ ላብ በተሰበሰበ ሀብት ላይ ያለፋዉና ያልደከመዉ ሰዉ ለተለያየ ቅንጦትና ለኃጢአት ተግባር የሚጠቀምበት፤ በወገኑ ላይም ታላቅ በመምሰል የሚመጻደቅበት፥ ሁሉን እንደፈለገዉ ማድረግ የሚችል አድርጎ የሚታበይበት ሆኖ ታይቷል:: አሁን ያለዉ ትዉልድ ግን ራሱን ከስግብግብነትና ከራስ ወዳድነት ለይቶ እንዲሁም ስንፍናን አርቆ ለእርሱ እንሚያስብ ለሌላዉ ወገኑም በማሳብ ሊኖርና «እኔ ብቻ ይድላኝ፤ ይመቸኝ፤ ከሁሉ በላይ ልሁን» የሚለዉን የአሕዛብ ሕይወት አስወግዶ ለራሴም

ለሌዉ ወገኔም ልኑር የሚለዉን አስተሳሰብ ተላብሶ ችግረኛና ተረጅ እንዳይኖር የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡

ወላጆች ልጆችን ገና በሕፃንነት እድሜያቸዉ ነዉር የሆነዉን ሳያስተምሯቸዉ በመቅረት፥ እንዲሁም ልቅ አድርገዉ በማሳደጋቸዉ፥ ከዚህ በተጨማሪም ራሳቸዉም በዚህ ነዉር ዉስጥ በመመላለሳቸዉ ምክንያት፣ ለሰዎች ስሜት ደንታ ቢስ በመሆንና እንደ እንስሳ በሥጋና ደም ስሜት ብቻ በመመላለስ ያልተገባ ድርጊት በልቅነት እንፈጽማለን፡፡ ልጆች ግን ቢያንስ ነገሮችን ማመዛዘንና ማገናዘብ ደረጃ ላይ ሲደርሱና የዉጭዉን ኅብረተሰብ አኗኗር በመመልከት ራሳቸዉን ከነዉር ተግባር ሊገቱ ይገባል፡፡ ይህን ያልተገባ ድርጊት ሲፈጽሙ የሚመክራቸዉንና የሚቆጣቸዉን ወላጅ ሆነ ወዳጅ ሊሰሙና ራሳቸዉን በመቆጣጠር ሊመላለሱ ይገባል እንጂ «ለምን እንዲህ እባላለሁ» ማለት የለባቸዉም፡፡ ለሌላዉ ወገን መቆርቆርና ማሰብ ከዚህ ከቀላሉ ድርጊት ይጀመራል፡፡ ሕሊናችንን አደንድነን ባልተገባ ድርጊት ዉስጥ የምንኖር ከሆነ፣ ምን ያህል ራሳችንን መቆጣጠር ያልቻል መሆናችንን ያሳያል፤ ለሌዉ ወገን ስሜት ደንታ ቢስ የሆን፣ እንኳን ለሌለዉ ወገን መቆርቆርና ጥብቅና ልንቆም ቀርቶ ለራሳችንም የማንሆን መሆኑን ነዉ ድርጊታችን የሚመሰክርብን፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ ሰዎች በተለያየ መንገድ ይሞታሉ፡፡ ለምሳሌ ትን ብሏቸዉ፣ በተለያየ በሽታ፣ በአደጋ፣ ተገለዉ፣ ተደብድበዉ፣ በድንገት፣ ደህና ተኝተዉ፣ በድንጋጤ፣ ተሰቃይተዉ፣ ... ወዘተ፡፡ ታዲያ አንድ ሰዉ ቀኑ ሳይደርስና እግዚአብሔር ሳይጠራዉ በተለያየ መንገድ ሊሞት ይችላል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ በሁላችን ዘንድ መታወቅ ያለበት እንኳን በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠርን ሕያዋን ፍጥረታት ይቅርና ሌሎች ሕይወት ያላቸዉ ፍጥረታት እንኳ እግዚአብሔር ካልፈቀደ በስተቀር ማንም ምንም ሊያደርጋቸዉ አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሳይጠራዉ የሚሞት ሰዉ አይኖርም፡፡ አጠራሩ ግን በተለያየ መንገድና ዘመን ሊሆን ይችላል፡፡ እድሜን መቀጠል ሆነ ማሳጠር የሚችለዉ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ፡፡ በእዚህም ምክንያት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀዉ ሁል ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ብቻ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር፤ ስንወለድ የሚንጠራበትን እድሜና ሕይወት አልወሰነብንም፡፡ በነጻ ሕሊናችን ተመርተን በምንመርጠዉ የሕይወት መስመር እንድንኖር ፈቃዱ ነዉ፡፡ ነገር ግን ለመንግሥቱ የሚያበቃን የእርሱን የሕይወት መንገድ ተከትለን ስንኖር ብቻ ነዉ፡፡ በምድራዊ ሕይወታችን በሚከሰቱ የተለያየ ክስተት የእርሱ ፈቃድ ሆኖ ከሕፃንነት እስከ እርግና(እርጅና) ዘመን ባለዉ እድሜያችን ነፍስ ከሥጋችን ልተለይና ወደ ሁለተኛዉ መኖሪያ ወይንም መቀጫ ቦታ ልትሄድ ትችላለች፡፡ በመሆኑም ትንታ ሆነ በሽታ፣ እንዲሁም ሰዉና አደጋ በራሳቸዉ ሥልጣን እኛን ሊገሉ አይችሉም፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ብቻ ነዉ ሞት በእኛ ላይ ሊመጣና ነፍስ ከሥጋችን ልትለይ የምትችለዉ፡፡ ፈቃዱ ነዉ የሚለዉ ደግሞ በእኛ ላይ የሚፈጸምብን ግድያ ሆነ ስቃይ እግዚአብሔር ይወደዋል ማለት ሳይሆን፤ በዚያ ዓይነት አሟሟት እንድንሞት እግዚአብሔር ፈቅዷል ማለት ነዉ፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ሰዎች በተለያየ መንገድ የደረሰባቸዉን ጥቃት ሆነ ጉዳት ለመርሳት ቢልጉ ለመርሳት የሚቸገሩ አሉ፡፡ ሕሊና በነጻነት የምትፈልገዉን ለመርሳት ሆነ ላለመርሳት አትችልም ወይ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ሕሊናችን ነጻ ፈቃድ አላት ሲባል ነጻነቷ በተወሰነ ደረጃ ተገድቦ ነዉ ያለዉ እንጂ እንደፍላጎቷና ምኞቷ ሁሉ መሆን ሆነ ማድረግ አይቻላትም፡፡ ከእርሷ የሚጠበቀዉ ለቅን ሐሳብ፣ ለመልካም ተግባር፣ ለእዉነተኛ ሕይወት መሰለፍ ብቻ ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ ሌላዉን ኃይል የሚያጎናጽፋት እግዚአብሔር ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ሕሊናችን (ነፍሳችን) ነገሮችን ማወቅና እንዲሁም ማመዛዘንና ማገናዘብ ከጀመረች ጊዜ አንስቶ አንዳንድ ድርጎቶችን ልትረሳም ልታስታዉስም ትችላለች፡፡ በመሆኑም የተለያየ ጉዳት ያደረሰባትን ግለሰብ ሆነ አካል ለመርሳት ፈልጋ ልትረሳ የማትችለዉ፤ ልክ አንድ አደጋ በአጋጣሚ ሲደርስ ያንን ድርጊት የተመለከተ ሰዉ ተመሳሳይ በሆነ ወሬ ወይንም ተመሳሳይ በሆነ ገጠመኝ ሊያስታዉሰዉ እንደሚችል ሁሉ፤ ሕሊናችን(ነፍሳችን) የደረሰባትን ጉዳት ሆነ ጥቃት የሚያስታዉሳት ገጠመኝ ሆነ ድርጊት ስትመለከት ወይንም ስትሰማ ልታስታዉሰዉ ትችላለች፡፡ ከእርሷ የሚጠበቀዉ ግን ከዉስጧ ያለዉን ጥላቻና በቀል ማስወገድ ነዉ፡፡ ያ ከሆነ የምታጠቃበት ሆነ የምትበቀልበት አጋጣሚ ብታገኝ ለጥል ሆነ ለበቀል አትነሳሳም፡፡ ነገረ ግን በዉስጧ ጥላቻና በቀል ካለ አጋጣሚዉን ተጠቅማ ለጥል ሆነ ለበቀል ልትነሳሳ ትችላለች፡፡ የሚያስጠይቃትም ይህ ድርጊቷ ነዉ እንጂ በሕሊናዋ ልትረሳ እየፈለገች የደረሰባትን ጉዳትና ጥቃት መርሳት ባልመቻሏ አይደለም፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ብዙዉን ጊዜ ሕዝቡ የባለጊዜዎችን የማጥላያና የማወደሻ ቅስቀሳን ተከትሎ እንዲጠላ የሚደረገዉን ግለሰብ ሆነ ቡድንን በጭፍን ይጠጣል፡፡ በተቃራኒ ደግሞ እንዲወደስ የሚደገዉን በደፈናዉ ያወድሳል፣ ያገናል፡፡ ይህ አግባብ ነዉ ወይ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በአመለካከትና በአስተሳሰብ በኩል በዓለም የሚታየዉ ዋንኛዉ ችግር ይህ ነዉ፡፡ በተለይ በፓለቲካዉ ሕይወት ስንመለከት ባለጊዜ የሆኑ ግለሰቦች ሆነ ቡድኖች ብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያ) በእነርሱ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ የሚፈልጉትን ቅዱስ፣ የማይፈልጉትን ርኩስ አድርገዉ ነዉ የሚያቀርቡት፡፡ ያ ብቻ አይደለም አንዱን በአንዱ ላይ በጥላቻ እያነሳሱ በቀልና ግፍ የሚያስፈጽሙት፡፡ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ምድር በተደጋጋሚ የታየ ስለሆነ ለዚህ ምሳሌ ማቅረቡ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በየእለቱ የሚንመለከተዉ ነዉ፡፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ እንደ ጀግና፣ ቅዱስ፣ ሰማዕት፣ ታላቅ፣ ታሪክ ሰሪ ተድረገዉ ሲታዩና ሲወደሱ፤ እዉነተኞችና ቅኖች ደግሞ እንደ ዓመፀኛና ከሃዲ ተቆጥረዋል፡፡

ከእያንዳንዱ ሰዉ የሚጠበቀዉ ግን በጭፍን ጥላቻ ሆነ በጭፍን ደጋፊነት ዉስጥ መመላለስ የለበትም፡፡ የእያንዳንዱን ተግባርና ንግግር በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እየመረመረ እንክርዳዱ ስንዴ መስሎ ለመታየት ቢፈልግ እንኳ እንደ እንክርዳድነቱ ነዉ መመልከት ያለበት እንጂ «እኛ ስንዴ ነን»

ብሎ የሚያወራዉን መቀበል የለበትም። በሌላ በኩል «ስንዴዉን እንክርዳድ ነዉ» ቢሉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ሲመረምረዉ ስንዴ ሆኖ ካገኘዉ ደግሞ እነሱ «እንክርዳድ ነዉ» ስላሉ ብቻ እንደ እንክርዳድ መቁጠር የለበትም። በዓለም የሚታየዉ ግን ተገላቢጦሹ አስተሳሰብና ሕይወት ነዉ። ምክንያቱም ለሕሊናዉና ለአምላኩ ያልታመነ ትዉልድ እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ ስንሚወሰድና እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብሎ ስለሚነዳ ነዉ። በዚህም ምክንያት ባለጊዜዎች ጨለማዉን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ መራራዉን ጣፋጭ፣ ጣፋጩን መራራ እያደረጉ በማቅረብ፤ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ተግባራቸዉን በቀላሉ መፈጸምና ማስፈጸም ችለዋል። ለሕሊናዉና ለአምላኩ የሚታመን ትዉልድ ግን ከእዉነት ጋር ብቻ ስለሚጸና የጨለማና የመራራ ተግባራቸዉን ይቃወማል፣ ያወግዛል፣ ያጋልጣል እንጂ እንደ ቦይ ዉኃ ዝም ብሎ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ አይወሰድም፤ እንደ ጠፍ ከብት አይነዳም።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በዚህ ምድር ዉስጥ የሰዉ ልጆችን ከእግዚአብሔር የሚለዩት ዋንኛ ነገሮች ምንድናቸዉ ይላሉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በእኔ እምነት **የመጀመሪያዉ ለሰዉ ልጆች የሕይወት እንቅፋት የሆነዉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሁለተኛ ጌታ» የተባለዉ ገንዘብ ነዉ።** እያንዳንዱ ሰዉ ቀን ከሌሊት የሚያስበዉ ስለገንዘብ ነዉ። ገንዘብ ለማግኘት ደግሞ ከቀላል ወንጀል እስከ ከፍተኛ ወንጀል ከመፈጸም አይመለስም። ገንዘብ ያለዉም በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት እርካታን አቶ ቀን ከሌሊት በገንዘብ ላይ ገንዘብ የሚጨምርበትን ነዉ የሚያስበዉ እንጂ «እኔ ለእኔም ሆነ ለቤተሰቤ በቂ ገንዘብ አለኝ፤ እስቲ ችግረኞችንና ድሆችን ለመርዳት ልስራ» አይልም። ይልቁኑ አንድ ምስኪን ወደ ገደል እንዳይገባ የደገፈችዉ አንድ ጉቶ ብትኖረዉ፤ እርሷን ቆርጦ ከመጠቀም ወደ ኋላ የማይመለስና ያ ምስኪንም ወደ ገደል ገብቶ ቢከሰከስ ሆነ ቢሞት አንዳች ስሜት አይሰጠዉም። ይህ የሚያሳየን ደግም ዲያብሎስ በአራቱም ማዕዘን የዘረጋዉ የጨለማ ሥርዓት ራስ ወዳድነትንና ስግብግብነትን የፈጠረ፣ እጅግ እጅግ ጥቂቶቹ ብዙዎችን አስጨንቀዉና ጨቁነዉ ያሉ መሆናቸዉን ነዉ። ለዚህም ነዉ ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለረኃብ፣ ለስደት፣ ለእስር፣ ለሞት፣ ለስቃይ፣ ለመከራ፣ ለችግር ተዳርገዉ ያሉትና ብዙዎቹ የዲያብሎስ አገልጋዮች ደግሞ እጅግ ከብረዉና ገነዉ ያሉት።

የገንዘብ ጠንቅ ስንመለከት አባትና ልጅ፣ ወንድምና ወንድም፣ እህትና እህት፣ ጓደኛና ጓደኛ፣ ዘመድና ዘመድ፣ ባዳና ባዳ፣ ወገንና ወገን ፣ ባጠቃላይ የሰዉ ዘሮች እርስ በእርስ የሚጣሉበትና የሚገዳደሉበት የዲያብሎስ ዋና መሳሪያና ሌት ተቀን የሚመለክ ነዉ። በመሆነም ገንዘብ ልንገለገልበት እንጂ ሊናመልከዉና ልናስመልከዉ አይገባም። እግዚአብሔር በሰጠን ሀብትና ንብት መርካት አለብን እንጂ ሌት ተቀን ገንዘብ ለማግኘት ብቻ የምንሯሯጥ ከሆነ ለራሳችንም ሳንረካ ለሥጋችንም ሆነ ለነፍሳችን ሳይጠቅመን በምኞት እንደተቃጠልን፣ እንደተጨነቅን ነው ወደ ሁሉተኛ መኖሪያ ወይንም መቀጫ ቦታ የምንጓዘዉ።

***ሁለተኛዉ አሰናካይ ደግሞ ዝሙት ነዉ***:: ነፍስ በሥጋ ላይ የበላይነት ካልተጎናጸፈች በስተቀር የሥጋና የደም ስሜታችን የሚመራን ከሆነ ማንም ሰዉ ከዝሙት ሊርቅ አይችልም:: ምክንያቱም ትዳር የሌለዉ ሕሊናዉ በዝሙት መንፈስ ስለሚሸነፍ ወይን በተግባር ወይን በንግግር ወይን በሐሳብ መዘሞቱ አይቀርም:: በትዳር ዉስጥ ያለ ደግሞ ነፍሱ በሥጋና ደም ስሜቱ ላይ የበላይነት ካልተጎናጸፈች በስተቀር ካማረችዉ ሴት ጋር ሁሉ ማመንዘርን ይፈልጋል:: ያ ብቻ አይደለም «ለእግዚአብሔር ራሴን ጃንደረባ አድርጌያለሁ» ያለዉ መነኩሴ እንኳ ራሱን በጾም፣ በስግደት፣ በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ካላተጋና ነፍሱ ሙሉ በሙሉ በሥጋዉ ላይ የበላይነትን ካልተጎናጸፈች በዝሙት ይወድቃል:: ስለዚህ ያላገቡ ሰዎች የራሳቸዉ ትንሽም ትሁን ብዙ መተዳደሪያ ገቢ ካላቸዉ ስጦታቸዉን (ሔዋናቸዉን) ፈልገዉ ማግባት ይጠበቅባቸዋል:: በትዳር ያሉት ደግሞ ራሳቸዉን ከዝሙት መንፈስ ጠብቀዉ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ መኖር አለባቸዉ:: ለእግዚአብሔር ራሳቸዉን ጃንደረባ ያደረጉ መነኮሳት ደግሞ ከማንም በላይ በመንፈሳዊ ተጋድሎ ሕይወት ዉስጥ መመላለስና መጽናት አለባቸዉ እንጂ ሥጋን በሚመች ሕይወት ዉስጥ ከተለመላለሱ ነፍሳቸዉ ኃይልን አታ መዉደቃቸዉና መልከስከሳቸዉ አይቀርም::

***ሦስተኛዉ ፈታኝ ደግሞ ምኞት ነዉ***:: ይኸዉም የሥልጣን፣ የክብር፣ የዝና፣ የግል ብልጽግና የመሳሰሉት ነዉ:: ሰዎች ይህን ምኞታቸዉን ለማሳካት ሕሊናን ከመሸጥና እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ ዝም ብሎ ከመሄድ ጀምሮ ከቀላል እስከ ከባድ ወንጀል ከመፈጸም አይመለሱም:: ስለዚህ አንድ ሰዉ እንደ አቅሙና እንደ ሕሊናዉ እየኖረ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ለሟሟላት እስካልተመላለሰና በምኞች ብቻ የሚከንፍ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላዉን ተግባር ሊፈጽም ይችላል:: በመሆኑም እያንዳንዳችን ለጊዜያዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ የተለያየ ጥቅማ ጥቅም ብለን ሕሊናችንን መሸጥ ሆነ እግዚአብሔር የማይፈቅደዉን መፈጸም የለብንም::

ከእነዚህ ዉጭ ያሉት ነገሮች በሥጋ ድካምና በሥጋና ደም ስሜታችን ተመርተን ራሳችንን ለሰይጣናት ፈተና አሳልፈን የምንሰጥና የምንወድቅባቸዉ ናቸዉ:: በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት ሆነ ከሌሎች ፈተና አምጪ ኃጢአት ለመጠበቅ ራሳችንን በጸሎት፣ በጾም፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ልንገዛና ነፍሳችንን በሥጋችን ላይ ያላትን የበላይነት ማስጠበቅ ይኖርብናል:: ያኔ እንደ ነፍሳችን ፈቃድ ስለምንመላለስ ለገንዘብ ሆነ ለዝሙት እንዲሁም ለተለያዩ ምኞቶችና ኃጢአት ተግባር ራሳችንን አሳልፈን አንሰጥም:: እንኳን በተግባርና በንግግር ኃጢአት መፈጸም ይቅርና በሐሳባችን እንኳ አንፈጽምም:: ሰይጣናት ኃጢአት ለማስፈጸም ቢፈታተኑን እንኳ ተቃዉመን እናሳፍራቸዋለን እንጂ በኃጢአት አንወድቅላቸዉም::

<u>***ጠያቂዉ አገልጋይ***</u>: አንዳንድ ሰዎች በዉጭዉ ዓለም በነጻነት እየኖሩ «ይህ ነጫጭባ» እያሉ በንቀትና በጥላቻ ይጠራሉ:: አንዳንድ ሰዎች ደግሞ «እነዚህ ዜጎች» በማለት በጥላቻና በበቀል አስተሳሰብ ይመለከታሉ:: አንዳንድ ሰዎች ደግሞ «ይህ ዘር፣ ይህ ነገድ፣ ይህ ቋንቋ ተናጋሪ፣ይህ ጎሳ(ብሔር)፣ ይህ ወገን ፣ ይህ ቤተሰብ» እያሉ በጥላቻና በበቀል አስተሳሰብና ተግባር ላይ ይሰለፋሉ፣ ይኖራሉ:: ይህን አስተሳሰብ እንዴት ይመለከቱታል?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ሁላችንም ማወቅ ያለብን ባለፉት ዘመናት ሆነ አሁን ባለነዉ ዘመን የተለያዩ መንግሥታት፣ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች የተለያየ ግፍ፣ በደል፣ አድሎ፣ በቀል ... ወዘተን ፈጽመዉ ይሆናል:: ነገር ግን ሊወክሉት የሚችለዉ መንግሥታቸዉን ወይንም ድርጅታቸዉን ወይንም ቡድናቸዉን ወይንም አንድ ራሳቸዉን እንጂ ሕዝብን፣ ዜጋን፣ ዘርን፣ ነገድን፣ የተለየ ቋንቋ ተናጋሪን፣ ጎሳን፣ ቤተሰብን አይወክሉም:: አሁን በትዉልዱ የሚታየዉ የጥላቻና የበቀል አስተሳሰብና ተግባር የዋናዉ ጠላታችን ዲያብሎስና የሠራዊቱ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) መንፈስ በሕሊናችን መንገሡና እኛም እንደነሱ ለግፍ፣ ለጭከና፣ ለአድሎ፣ ለበቀል እያነሳሳንና በተግባርም እየፈጸምን መሆኑን ነዉ:: በእግዚአብሔር እዉነታ ስንመለከት ይህ አስተሳሰብና አቋም ራስን እንደ ሰይጣናት የሚያስቆጥርና ጥፋትና ዉድቀት የሚያመጣብን ነዉ:: እግዚአብሔር እያንዳንዱን ግፈኛና ዓመፀኛን መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ እንዲሁም ግለሰብን እንደ እኛ ሳይቸኩል እርሱ በፈቀደዉ ጊዜ ይበቀላቸዋል፤ ስለ ግፋቸዉ፣ ስለ ጭከናቸዉ፣ ስለ አድላዊነታቸዉ፣ ስለ በቀላቸዉ፣ ባጠቃላይ ስለ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰትና ጭከና ተግባራቸዉ በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍላቸዋል(ይቀጣቸዋል):: ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀዉ እዉነተኛ ሆኖ መገኘትና ስለ እዉነት መመስከር፣ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ባጠቃላይ የጨለማ ስራቸዉን ለሕዝብ መግለጥና ሕዝቡም የእነሱን የዓመፃ ተግባር እንዳይፈጽምና ከእነሱ ጋርም በዓመፃቸዉ ተባባሪ እንዳይሆን ማሳሰብና መምክር ነዉ::

ለምሳሌ ፋሽስት የነበረዉ የጣሊያን መንግሥት ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት በፊት በእኛ በኢትዮጵያዉያን ላይ ግፍና በደል ፈጽሞብን ነበር:: ነገር ግን እነዚያ ግፈኞች የሚወክሉት በወቅቱ የነበረዉን መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ እንዲሁም በዚያ ግፍና በደል ዉስጥ የተሰማሩትን ግለሰቦችን ነዉ እንጂ የጣሊያንን ሕዝብ አይደለም:: እንዲሁም በኢትዮጵያ ዉስጥ መንግሥታት፣ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች ግፍና በደል እንዲሁም አድሎ ፈጽመዉ ይሆናል:: ነገር ግን የሚወክሉት በዘመኑና በወቅቱ የነበረዉን መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ በዓመፃና በግፍ ስራ ላይ የተሰማሩትን እያንዳንዱን ግለሰብን ነዉ እንጂ ነገድን፣ ቋንቋን፣ ዘርን፣ ጎሳን፣ ወገንን፣ ዘመድን፣ ቤተሰብን አይወክሉም:: » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ምዕራፍ አምስት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በሕይወት ዘመኖ ከተመለከቱትና ካጋጠሞት የተለየ ቦታ የሚሰጧቸዉ ሰዎች አሉ ወይ? እንዲሁም የተለየ አድናቆት የሚቸሯቸዉ ሰዎች አሉ ወይ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እንግዲህ የተጠየኩት በሕይወት ዘመኔ ከተመለከትኩትና ካጋጠሙኝ ነዉ እንጂ፤ እንዳጠቃላይ ብጠየቅ ኖሮ ምላሼ የነበረዉ: እኔ ልዩ ቦታ የምሰጣዋቸዉና አድኖቆቴን የምገልጽላቸዉ ሰዎች፤ እንደ ማንኛዉ ሰዉ በሥጋ ተገልጸዉ በእዉነትና በመንፈስ አምላካቸዉን በማመን፣ በተጨባጭ ያላዩትንና ያልዳሰሱትን አምላክ ተማምነዉና በመንግሥቱም ሕያዉ ሆነዉ እንደሚኖሩ አምነዉ፣ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዉ የመሰከሩና የመጣባቸዉን የተለያየ ፈተናና መከራ በጽናትና በቆራጥነት ተወተዉ፣ እስከ ምድራዊ ሕይወታቸዉ ፍጻሜ ድረስ ለአምላካቸዉ ታምነዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ የሄዱ፤ ጽድቃቸዉና ቅድስናቸዉ የተረጋገጠላቸዉ ነቢያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታትና ጻድቃንን ነበር::

አሁንም የተለያ ቦታ የምሰጣቸዉና አድናቆቴን የምገልጽላቸዉ «እገሌ እገሌ» ብዬ አልጠቅስም:: ነገር ግን እንደ ቀደሙት የእግዚአብሔር ምርጦች ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸዉን ክደዉ እየመሰከሩ ያሉትን ሲሆን፤ የተለየ ምስጋና የማቀርብላቸዉ ደግሞ እስከ ምድራዊ ሕይወት ፍጻሜያቸዉ ድረስ ለእግዚአብሔር ታማኝነታቸዉን ጠብቀዉና በእዉነትኛ አቋማቸዉ ጸንተዉ ወደ እቅፉ ከሄዱ በኋላ ነዉ:: ምክንያቱም ብዙዎች መልካም ሕይወትና ምስክርነት ይጀምሩና በኋላ ደግሞ የሥጋና የደም ስሜታቸዉን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ እንዲሁም ከዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚዎች ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ ሲሰሩ ታይተዋል፣ ተደምጠዋል:: ከዚህ አንጻር እያንዳንዳችን ልንታመን የምንችለዉ እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ለእግዚአብሔር በእዉነት ስንገዛና እንደ ቃሉ ሆነን ስንገኝ ነዉ::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: እዚህ ላይ አንዳንዶች በመንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ ሳይመላለሱና መንፈሳዊ አገልጋይ ሳይሆኑ ለሕሊናቸዉ ታምነዉ በደለኞችን፣ ግፈኞችን፣ አስመሳዮችን፣ ባጠቃላይ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ተመላልሰዉ በሕዝብ ላይ አድሎና በደል የሚፈጽሙትን መሪዎች ፣ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎችን የሚተቹና የሚቃወሙ አሉ:: በምስክርነታቸዉም የተለያየ መከራ፣ እስራት፣ ግድያ ሁሉ የሚፈጸምባቸዉ አሉ:: ስለነዚህ ምን አስተያየት አሎት?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ለሕሊናዉ የሚታመን ሰዉ ለአምላኩ መታመን አያቅተዉም:: ነገር ግን እንደ አምላኩ ፈቃድ ብቻ የማይመላለስ ከሆነ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) በሥጋና ደም ስሜቱ በመግባት ሊጠቀሙበትና ፈቃዳቸዉን ሊያስፈጹሙትና መስመሩን ሊያስቱት ይችላሉ:: ለዚህም ነዉ ብዙዎች ለሕሊናቸዉ ይታመኑን በሰዎች ላይ የሚደርሰዉ በደልና ግፍ እንዲሁም አድሎ አብገንግኗቸዉ ድርጊቱን ይቃወማሉ፣ ያወግዛሉ:: ነገር ግን እድሉን አግኝተዉ ወደ ወንበር ሲመጡ ያንኑ በደልና ግፍ እንዲሁም አድሎና መድሎ በሌላ መልክና ይልቁኑ በበለጠ ሁኔታ ይፈጽማሉ፣ ያስፈጽማሉ:: አንደበታቸዉና ተግባራቸዉ የማይገናኝ ይሆናል:: ቃል የገቡትን

ሁሉ ያፈርሳሉ:: ከዛም ባለፈ የሁሉ ፈጣሪና አስገኝ ነገሥታትን(መሪዎችን) የሚያፈራርቀዉን፣ የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜና መንገድ ማከናወን የሚችለዉን አምላክ ይክዳሉ፣ ያስክዳሉ:: እንዲሁም በሃይማኖታቸዉና በቤተክርስቲያናቸዉ ላይ ለጥፋት ይሰለፋሉ:: ሕሊናቸዉንም በማደንደን ለከፋ ዓመፃ ራሳቸዉን ያሰልፋሉ:: ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ በጋራ የሚታመኑ ቢሆን ኖሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድና መልካም የሆነዉን ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ስለሚነሱ ሰይጣናት ቦታ አግኝተዉ የዓመፃ ተግባር አያስፈጽሟቸዉም ነበር::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** ለሕሊናቸዉ በእዉነት የሚታመኑ ቆራጥ ሰዎች ወደ ሙሉ እዉነታ እንዲመጡ ቢደረግ፤ በመንፈሳዊ አገልግሎትና ሕይወት ዉስጥ ካሉት ሰዎች በላይ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት እንደሚመላለሱና በቆራጥነትና በጽናት ስለ እዉነት እንደሚመሰክሩ እገምታለሁ:: ምክንያቱም የእግዚአብሐርን መንግሥት ተስፋ ሳያደርጉና ከሥጋ ሞት በኋላ ያለዉን የእዉነት ሕይወትና የሕያዉነት ዘመን እድሜያቸዉን ሳያዉቁና ሳያስተዉሉ ነዉ በነጻ ሕሊናቸዉ ብቻ በመመራት «የፈቀደዉ መከራና ስቃይ ይምጣብኝ እንጂ በአገር ላይ ክህደትና ዓመፃ ሲፈጸምና በሕዝብ ላይ በደልና ግፍ ሲፈጸም ዝም አልልም፤ ድርጊቱን እቃወማለሁ፣ የተንኮልና የበቀል እንዲሁም የዓመፃ ተግባራቸዉን ለዓለም እገልጣለሁ... ወዘተ» በማለት መከራዉን፣ ስቃዩን፣ እስራቱ፣ ግድያዉን፣ ባጠቃላይ ሊያጋጥማቸዉ የሚችለዉን ችግር በጸጋ ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነዉ ሕይወታቸዉን ለሕዝብና ለአገር አሳልፈዉ የሰጡት:: እነዚህ ሰዎች፤ ሰማያዊ ተስፋቸዉን ቢያዉቁና ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በመመስከራቸዉ ታላቅ ሰማያዊ ዋጋ እንደሚያገኙና በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ ሕያዉ ሆነዉ እንደ እግዚአብሔር እንደሚኖሩ ቢያስተዉሉና ቢያምኑ እጅግ የበለጠዉን ተጋድሎ እንደሚፈጽሙ ምንም ጥርጥር የለዉም::

እነዚህ ለሕሊናቸዉ በእዉነት የሚታመኑ ቆራጥ ሰዎችን ስመለከትና በተቃራኒ ደግሞ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ ተሰማርተዉ «ኑሮ በመመሳሰል፣ ከራስ በላይ ንፋስ» የሚሉትን የአሕዛብ ሕይወት የያዙ፣ ስለ እዉነት መመስከርና በዚያም ምክንያት የሚመጣባቸዉን ማንኛዉንም ፈተና ለመወጣት ቆራጥ ያልሆኑ፣ ከነፈሰዉ ጋር አብረዉ የሚነፍሱ፣ እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ወሰዷቸዉ አቅጣጫ የሚሄዱ፣ እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብለዉ የሚነዱ፣ ለሕሊናቸዉም ለአምላካቸዉም ያልታመኑ አስመሳይ አገልጋዮችን ስመለከት፤ በአስመሳይ አገልጋዮች እጅግ አፍራለሁ:: «ምናለ የአገልግሎቱን ቦታ ሆነ ወንበር ለቀዉ ተራ ምእመን ቢሆኑ ፍርዱ ይቀልላቸዉ ነበር» እላለሁ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፤ ብዙ ሰዎች «ለሆዴ ወይንም ለሥጋዬ ነዉ የምኖረዉ» ይላሉ:: በእዉኑ ለሆድና ለሥጋችን ነዉ ወይ የተፈጠርነዉ? እኛ ማለት ይህ የተገለጽንበት ሥጋችን ነዉ ማለት ነዉን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፤ ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ ለሚመላለሱ፣ ሕያዉ ነፍስ እያላቸዉ ራሳቸዉን እንደ እንስሳ ቆጥረዉ «እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ የእኛ ሕይወት በዚህ ይደመደማል» የሚሉ፣ አሕዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች ይህን

ቢሉ አያስገርምም፤ አያስደንቅም፡፡ ምክንያቱም የሚኖሩት ለሆዳቸዉና ለሥጋቸዉ ነዉና፡፡ ሆዳቸዉ ከሞላና ከጠገበ ከዚያ ባለፈ ስለሌላ አያስቡብ፡፡ እንዲሁም ይህ ሆዳቸዉና ሥጋቸዉ ለእነሱ የመጨረሻ ታላቅ ነዉና ከማምለክና ከማስመለክ አይመለሱም፡፡ ሊያስገርምና ሊያሳዝን የሚገባዉ «እኔ በእግዚአብሔር ነዉ የማምነዉ፣ ነፍሴ አትሞትም ሕያዉ ናት፣ ትንሣኤ አለኝ... ወዘተ» የሚለዉ ሰዉ «የምኖረዉ ለሆዴና ለሥጋዬ ነዉ» ሲልና ለሆዱ ሲል ሕሊናዉን ሲሸጥ፣ እንዲሁም ቅርፊት ሥጋዉን ሲያመልክና ሲያስመልክ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የእዚህ የቅርፊት ሥጋችን ክብር የታወቀ ነዉ፤ መጨረሻዉ የአፈርና የምስጥ መብል እንደሚሆን፣ እንዲሁም እስከዛ ድረስም ጽዳታችንን ካልጠበቅን የሚሸት፣ ለዚሁ ምስክሩ የብብታችንና ካልሲያችንን ስናወጣ የሚታየዉ መጥፎ ጠረን ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን በልተን ወዲያ የምናራብ፣ ያ ጣፍጦን የበላነዉ መብል መጥፎ ጠረን ይዞ ወደ እዳሪ(ዐይነ ምድር) የሚለወጥ፣ ያ ጣፍጦን የጠጣነዉ መጥፎ ጠረን ይዞ ወደ ሽንት የሚለወጥ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብዙ በበላን ብዙ በጠጣን ጊዜ ወደ ብዙ እዳሪና ሽንት ነዉ የሚለወጠዉ እንጂ ለሆዳችን ሆነ ለሥጋችን የተለየ ነገር አይሰጠንም፡፡ በተቃራኒዉ እዉነተኛ ገንዘባችን የሆነችዉ ነፍሳችን ብዙ የእግዚአብሔርን ቃል ስተመገብ፤ ማስተዋል፣ እዉቀት፣ ሕይወት ታገኛለች፡፡

ታዲያ ይህ ሁሉ የሚያሳየን እኛ የተፈጠርነዉ ለመብልና ለመጠጥ ሳይሆን፤ ቀድሞ በገነት ለክብርና ለታላቅነት ሲሆን፤ በአዳምና ሔዋን ዓመፃ ምክንያት ደግሞ ስለ መብል ነዉና ያመፁት፣ ስለሆዳቸዉ እንዲቀጡ በዚህ በሚራበዉና በሚጠማዉ ሥጋ ሊገለጡ ችለዋል፡፡ ነገር ግን በእዉነተኛ ንስሐ ስለተመለሱና እኛም ልጆቻቸዉ ባልፈጸምነዉ ዓመፃ ፍርዱ በእኛ ላይ ስለጸና እኛም ልጆቻቸዉ አሳዝነነዉ፣ ይህ የቅጣት ዘመን እጅግ እጅግ አጭር ሆኖልን ከምድራዊ ዘመን በኋላ ከምንኖረዉ የሕያዉነት እድሜ አንጻር የዐይን ጥቅሻ እድሜ በማንኖርበት ምድራዊ ዘመን ብቻ በዚህ ባደፈና በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይና እንዲሁም በጎሰቆለ ሕይወትና ኑሮ ልንመላለስ ችለናል፡፡ ይህም የሚያሳየን እኛ ለሆድ ሳይሆን የተፈጠርነዉ የሆዳችንን ፈቃድ አሸንፈን ለሕሊናችንና ለአምላካችን ታምነን እንድንኖር ነዉ እንጂ፤ እንደ አሕዛብ ሆዳችንን አምላካችን ካደረግነዉና ስለ ሆዳችን ስንል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከወጣን ከአዳምና ሔዋን በላይ የከፋ የሲኦልና በኋላም የገሃነመ እሳት ፍርድ ነዉ የሚጠብቀን፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ የተለያየ ተግባር ስንሰራ፣ ስንናገር፣ ስናስብ፣ እንዲሁም ስናነብና ስንጸልይ ሐሳባችን ይሰረቃል፡፡ አንዳንዴ ራሳችንን እስከምንታዘብ ድረስ ተግባራችን የማይሆን ይሆናል፤ እንዲሁም ምን እንደ ጸለይን ሳናስተዉል እንጨርሳለን፡፡ ይህ ለምን ይመስሎታል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ በግልጽ እንደሚታወቀዉ ይህች ምድር በብዙ ትእልፊት(በብዙ ቢሊዮን) በሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስት የተሞላች ናት፡፡ እነዚህ ርስኩሳን መናፍስት ደግሞ ዉስጣቸዉ ክፋትና ተንኮል እንዲሁም ቅናትና ምቀኝነት የሞላባቸዉ ስለሆነ ዋና ተግባራቸዉ የሰዉ ዘሮችን መፈታተንና ከሆነላቸዉ ደግሞ አጎሳቁለዉና ኃጢአት አስፈጽመዉ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ መዳረግ ነዉ፡፡ የእነሱ እርካታ ይህ ነዉ፡፡ በመሆኑም ሕፃን ፣ አዋቂ፣ ጻድቅ፣ ኃጥእ ሳይሉ ሌት ተቀን የአዳምን ዘር ይፈታተናሉ፤ ከሆነላቸዉም ይጥላሉ፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ** ሐሳባችን የሚሰረቀዉ በርኩሳን መናፍስት ምክንያት ነዉ፡፡ ይኸዉም ከሕሊናች(ከአእምሮዋችን) ለዐይን ቅጽበት ስለማይለዩ እኛ ራሳችንን በመግዛትና በመቆጣጠት የበላይነት ካልተጎናጸፍን በስተቀር ስራችንን በትጋትና በብቃት ለማከናወን እንቸገራለን፡፡ በጸሎትና በምስጋና ጊዜም ሕሊናችን ተሰብስቦ የምንጸልይና የምናመሰግን ከሆነ ልክ መሃል ለመሃል እሳት የተፋፋመበት ቦታ ላይ ያለ ነገረ በጣም እንደሚቃጠል፤ እነሱም የዚያን የመቃጠል ስሜት ስለሚደርስባቸዉ ከቻሉ ከናካቴዉ ጸሎት እንዳይደረግ አእምሮን ይዘጋሉ፡፡ ያንን ማድረግ ከተሳናቸዉ ደግሞ መጠነኛ ልብለባ ብቻ እንዲደርስባቸዉ የሰዉን ሓሳብ በመስረቅ የተመስጦ ጸሎትና ምስጋንን እንዳይደርስ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀዉ በምንችለዉ አቅም ሁሉ ሕሊናችንን አሰባስበን መስራትና መጸለይ ነዉ፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ እየበዛልን ሲሄድ ርኩሳን መናፍስት በሕሊናችን የሚያመጡትን ከቀላል እስከ ከባድ ፈተና በቀላሉ ድል እያደረግንና የበለጠዉን ኃይል እየተጎናጸፍን እንሄዳለን፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**፡ ዲያብሎስ፤ ለሥጋዊዉም ሆነ «መንፈሳዊ አገልግሎት» ለሚመስለዉ ጭምር ለተለየ አገልግሎት የሚመርጣቸዉ ሰዎች የተለየ ተሰጥኦ ያላቸዉን ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት በዓለም ላይ በተለያየ የመሪነት ሆነ የኃላፊነት ቦታ የተቀመጡት ሰዎች ተናግሮ ማስመን የሚችሉ፣ አንደበተ ርቱዕ፣ የተማሩ፣ ቆራጦች ... ወዘተ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርም እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ለአገልግሎት ይጠቀምባቸዋል፡፡ በሁለቱ ያለዉ ልዩነት ምንድነዉ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**፤ በእርግጥ ዲያብሎስ ለተለየ አገልግሎት የሚጠቀምባቸዉ ሰዎች ፈቃዱን ሊፈጽሙለት የሚችሉ እንደልቡ የሆኑትን ሰዎች ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት አንደበታቸዉን አንደበት አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፡፡ አእምሮዋቸዉን አእምሮ አድርጎ በመጠቀም ከቀላል እስከ ከባድ የጭከና ተግባር ያስፈጽማቸዋል፤ እንዲሁም ሕይወታቸዉን ሕይወት አድርጎ ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ እንዲቆሙና እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ጥሩ ተናጋሪዎችን ይመርጣል፤ ፈቃዱን በቆራጥነት እንዲፈጽሙለት ቆራጥና ጨካኞችን ያዘጋጃል፤ ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ የሚኖሩትን ይመለምላል፡፡

ወደ እግዚአብሔር ምርጫ ስንመጣ እግዚአብሔር ሰዎች የማያዩትን የዉስጥ ቅንነት፣ እዉነተኛነት ፣ መልካምነትን ብቻ ነዉ የሚያየዉ፡፡ እንዲሁም ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ መልካምነት ባለበት ሕይወት ላይ አድሮ ራሱ ይናገራል፣ ያስተምራል፣ ይገስጻል፣ ይፈርዳል፡፡ ይህም የሚያሳየን የእግዚአብሔርና የዲያብሎስ ምርጫ የማይገናኝ መሆኑን ነዉ፡፡ ዲያብሎስ ዉስጣዊ ቅንነት፣ እዉነተኛነት፣ መልካምነት ያለዉን ሰዉ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም ለሕሊናዉና ለአምላኩ የታመነ ስለሆነ፡፡ እርሱ የሚፈልገዉ ቅን መስሎ፣ መልካምና እዉነተኛ መስሎ የሚታየዉን አስመሳይ ሰዉን ነዉ፡፡ ምክንያቱም አስመሳይ ሰዉ አንደበቱ የሚናገረዉና ዉስጡ ተቃራኒ ስለሆነ ሕዝቡን እየሸነገለና እያታለለ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ያስፈጽማልና፡፡ ለዚህም ነዉ በዓለም ላይ ያሉ መሪዎችና ባለሥልጣናት ለሰዉ ሕሊና ተስማሚና ተቀባይነት ያለዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ሐሳብ ፈጥረዉ በሰላ አንደበታቸዉ እያሳመኑ የእግዚአብሔርን መቅሰፍትና ቁጣ የሚያመጣዉን

ግብረ ሰዶምን ሳይቀር «የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲ መብታቸዉ ነዉ» እያሉ በመብትና በዲሞክራሲ ሽፋን ርኩሰቱን ያነገሡት:: ሌሎቹንም የዓመፃ ተግባር በዚህ መልኩ እያሳመኑ ነዉ ለዘመናት ሕዝቡን ሲያሳምፁና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሲያወጡ የነበረዉ፤ አሁንም ያለዉ:: ከላይ እንደተመለከትነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ቅኖች፣ እዉነተኞች፣ መልካሞች በተናገሩት ቃል ሆነዉ የሚገኙ፤ የማያስመስሉ፣ ትህትና፣ ፍቅር፣ የዋህነት፣ ልባምነት፣ ባጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የተላበሱ፤ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆኑ ናቸዉ:: በምድራዊ ቆይታቸዉም እግዚአብሐርም ሕዝብም የሚደሰትበትን ተግባር ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ፣ ሰዎች ከጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ የሚለዩበትን የተለያዩ ግንባታዎችን የሚሰሩና የሚያሰሩ ናቸዉ::

የዲያብሎስ አገልጋዮች ደግሞ ሕይወታቸዉ ሆነ ተግባራቸዉ እንዲሁም ንግግራቸዉ የማስመሰልና ወደ ተግባር የማይለወጥ የዲያብሎስን ፈቃድ የሆነ፤ ይህን ፈቃዱን ለመፈጸም ደግሞ ከዓመፃ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት ተግባራቸዉ ጎን ለጎን ለሰዉ ልጆች የሚጠቅሙ ተግባራት የሚሰሩ ናቸዉ:: ምክንያቱም ቁሳዉያን ስለሆኑ፤ በቁስ በሚያምኑና ተስፋቸዉ ምድር አድርገዉ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ የተለያዩ ልማቶች ሆነ ግንባታዎች ያከናዉናሉ:: እንዲሁም ለዲያብሎስን እንደ ልቡ ሆነዉ የሚጋልባቸዉና አንደበታቸዉን አንደበት አድርጎ የሚናገርበት፣ አእምሮዋቸዉን አእምሮ አድርጎ የዓመፅ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ሐሳብ የሚያሳስባቸዉ እንደ ልቡ የሆኑ ስለሆነ ሕዝብ ከሕዝብ የሚጫረስበትንና የሚገዳደልበትን መሳሪያም የሚሰሩና የሚያሰሩ ናቸዉ::

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***፤ በእግዚአብሔር አምልኮ ዉስጥ አምልኮታችን የሚገለጽበት የተለየ መለያ ያስፈልገናል ወይ? እንዲሁም ጸሳይ፣ ጺሚ፣ ሰጋጅ ... ወዘተ መሆናችን እንዲታወቅ መለያ ምልክት ሊኖረን ይገባል ወይ?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***፤ በእግዚአብሐር አምልኮ ዉስጥ የራሱ የሆነ ሥርዓትና ልማድ አለ:: አግባብነት ያለዉን ሥርዓትና ልማድ መጠበቅ ይኖርብናል:: ነገር ግን ያንን ሥርዓትና ልማድ መጠበቅ የማንችልበት አጋጣሚ ቢፈጠር እግዚአብሔር መንፈስ ነዉና በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ልናመልከዉ ይገባል እንጂ ከአምልኳችን መለየት የለብንም:: ለምሳሌ ለስራ የተላክንበት ቦታ ቤተክርስቲያን ባይኖር «ቤተክርስቲያን ስለሌለ አምልኮቱን የት እፈጽማለሁ» በማለት ራሳችንን ከአምልኮት መለየት የለብንም:: ባለንበት ቦታ ሆነን መጸለይና ማመስገን፣ መስገድ እንችላለን:: እንዲሁም ጸሎታችንን በየትኛዉም ስፍራ ሆነን ማቅረብ እንችላለን:: ከሥርዓትና ከልማድ ብንመለከት ደግሞ እኛ የኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልጆች የሆን በቅዳሴ ጊዜ ሆነ በአግልገሎት ዉስጥ እያለን ነጠላችንን መስቀለኛ አጣፍተን ነዉ የምናስቀድሰዉና የምናገለግለዉ:: ነገር ግን ነጠላ የማይኖረን አጋጣሚ ቢፈጠር «ነጠላ ስለሌለኝ ቤተክርስቲያን ሄጄ አላስቀድስም፣ አላመስግንም፣ አላገለግልም» ማለት የለብንም::

ሌላዉ የምናቀርበዉ ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ምስጋና ለታይታና «ጻላይ፣ ጿሚ፣ ሰጋጅ፣ አመስጋኝ» ለመባል ከሆነ ዋጋችን ከምድራዉያን ተቀብለናልና ከረቂቁ በእዉነትና በመንፈስ አምልኮ ከሚፈጸምለት አምላክ ዘንድ ዋጋ አናገኝበትም:: ምክንያቱም የጸለይነዉ፣ የጾምነዉ፣ የሰገድነዉ፣ ያመሰገነዉ ሰዎች እኛን «ጻላይ፣ ጿሚ፣ ሰጋጅ፣ አመስጋኝ ናቸዉ» እንዲሉን ስለሆነ ነዉ:: በመሆኑም እግዚአብሔር ጻላይ፣ ጿሚ፣ ሰጋጅ፣ አመስጋኝ እንድንመስል ከእኛ የሚፈልገዉ አንዳች ምልክት የለም:: በአገልግሎት ዉስጥ የሚታየዉ አለባበስ ሥርዓት ነዉ እንጂ ጻላይ፣ ጿሚ፣ ሰጋጅ፣ አመስጋኝ መሆናችንን የሚገልጽ አይደለም:: ከላይ ከሃይማኖት ተጠሪዉ ከርእስ ሊቃነ ካህናት እስከ ዲያቆን ድረስ ያለዉ አለባበስ ከአምልኮ ሥርዓት ጋር የሚሄድ ነዉ እንጂ፤ ራስችንን ለእግዚአብሔር ጃንደረባ ያደረግን መሆናችንን ከምናሳዉቅበት ቆብ ዉጭ ማንኛዉም አገልጋይ ከአገልግሎቱ ዉጭ በተለየ ወይንም እንደ ምእመን አለባበስ ቢገለጽ እንደ ሕግና ሥርዓት አፍራሽ አይቆጠርም::

***__ጠያቂዉ አገልጋይ__***፤ በመንፈሳዊ ሆነ በሥጋዊ ሕይወትና አገልግሎት ዉስጥ ብዙ ሰዎች በትጋትና በቅንነት፣ በመልካም ስነ ምግባር ሕያወታቸዉንና አገልግሎታቸዉን ይጀምሩና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ባልተገባ ሕይወትና ከእዛም ባለፈ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ላይ ይሰለፋሉ:: ይህ የተለያየ ባሕርይና ጠባይ ሊለዋወጥባቸዉ እንዴት ቻለ?

***__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__***፤ ይህች ምድር እዉነተኛ መኖሪያ ቦታ ሳትሆን ለእዉነተኛዋ መኖሪያ ቦታ መሸጋገሪያ ድልድይ፣ የምንጠራባት፣ የምንነጥረባት፣ የምንነጣባት ናት:: ጠርተን፣ ነጥረን፣ ነተን እንደ ብቃት ደረጃችን ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቤታችን ገነትና መንግሥተ ሰማያት ለመግባት በተለያዩ ፈተናዎች ማለፍ ግድ ነዉ:: ምክንያቱም ነጻ ሕሊናና እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ፍጥረት የሆነችዉ ነፍስ ስለተሰጠችን፤ በነጻ ሕሊናችን ተመርተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመመላለስ የምችልበት ብቃት ስላለን የሚመጡብንን ፈተና በድል ተወተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ቃል ሆነን በመገኘት ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቤታችንን መሄድ ይጠበቅብናል::

***ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ*** ብዙዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ሲቀርባቸዉ ለመልካም ተግባር፣ ለቅን ሐሳብ፣ ለእዉነተኛ ሕይወት ይነሳሳሉ:: በዚያን ጊዜ ትጋትንና መልካምነትን እንዲሁም እዉነተኛነትን ያሳያሉ:: ነገር ግን ማንነታቸዉና አቋማቸዉ እንዲለይ የሰይጣና መንፈስ ሲቀርባቸዉ ያንን ለደቂቃ ወይንም ለሰዓት ቢበዛ ለቀናት መታገስና መጽናት ተስኗቸዉና ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ቅድሚያ በመስጠት የማይገባ ባሕርይና ጠባይ ያሳያሉ:: ከእዛም ባለፈ በተለያየ ኃጢአት ይወድቃሉ:: በዚህም ምክንያት መጥራት፣ መንጠር፣ መንጣት አቅቷቸዉ ራሳቸዉን ለሞት ሞት ይዳርጋሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ በመዉደቅ በመነሳት ጠርተዉ፣ ነጥረዉ፣ ነተዉ ለታላቅ አገልግሎትና ለእግዚአብሔር መንግሥት ይበቃሉ:: አንዳንዶች ሕሊናቸዉን በማሳመን ለሥጋና ለደም ስሜታቸዉ የሚመቻቸዉን ሰፊ መንገድ ይፈልጋሉ፣ ወይንም ይመሰርታሉ:: በዚህ ምክንያት ራሳቸዉን ለከፋዉ ቅጣት ይዳርጋሉ:: ስለዚህ ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ የተለያዩ የሰይጣናት ይሁን የሰዉ ፈተና ሲመጣበት እንደ ቀድሞዉ ብቃትና ትጋት ለማሳየት ቢከብደዉ እንኳ እስከ መጨረሻዉ ድረስ

መጽናትና የሚቻለዉን ተግባር ሁሉ መፈጸም ነዉ። በዚህ መልኩ ፈተናዉን ካለፈ ከእግዚአብሔር የተለየ ኃይል(ጸጋ) ስለሚጎናጸፍ የበለጠ ፍሬ የሚያፈራና ለበለጠ ክብርና ለእግዚአብሔር መንግሥት ይበቃል። ልክ ሁሉም ተማሪ ቢማርም የእያንዳንዱን ማንነትና ችሎታ እንዲሁም ብቃት ለማወቅና ለመለየት እንደተማሩት መጠን ፈተና እንደሚሰጣቸዉና ተግተዉ የተማሩና ያጠኑ ፈተናዉን እንደሚያልፉና እንደብቃታቸዉ ደረጃ ነጥባቸዉ እንደሚለያይ ሁሉ፤ በዚህች የዐይን ቅጽበት እድሜያችን ማንነታችንና ብቃታችን ይታይ ዘንድ እንደ አቅማችን የተለያዩ ፈተናዎች ሊመጡብን ይችላል። በመሆኑም እስከመጨረሻ ልንጸና ይገባል፤ የወደቅን ደግሞ ወዲያዉ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰን ለበለጠ አገልግሎት ሆነ ሕይወት ልንሰለፍ ይገባል እንጂ ተስፋ የምንቆርጥ ከሆነ ሰይጣናት የበለጠ ይበቀሉናል፤ እንዲሁም ለከፋዉ ለእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት ይዳርጉናል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ የእግዚአብሔር ምሕረትን ይቅርታ አግኝቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት በቀላሉ የሚወረስበት አቋራጭ መንገድ አለ ወይ? ይህን ያልኩበት አንዳንድ አገልጋዮችና አማኞች « ንስሐ ብትገቡም ባትገቡም፣ትእዛዙን ብትጠብቁም ባትጠብቁም፣ ምግባር ቢኖራችሁም ባይኖራችሁም፣ ሥጋና ደሙን ብትቀበሉም ባትቀበሉም ይህን ካመጣችሁ፣ እዚህ ቦታ ከሄዳችሁ፣ እንዲህ ካደረጋችሁ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባታቸዉ የተረጋገጠ ይሆናል። ስለዚህ ስለመኮነን አንዳች አታስቡ፤ ድናችኋል፣ ተምራችኋል» የሚሉ አሉና ነዉ።

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ካቀረበልን ጀምሮ የአዳም ዘሮች ሁሉ ተምረናል፤ ድነናል። ይህ ድኅነትና ምሕረት የሚጸናዉና ለሕያዉ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃን ስናምንበትና እንደ ቃሉ ሆነን ስንገኝ ብቻ ነዉ እንጂ በአንደበታችን ብቻ «ድነናል፣ ተምረናል» ስላልን አይደለም። ማመንና እንደቃሉ ሆኖ መገኘት የሚገለጸዉ ደግሞ እምነትና ምግባርን አንድ ላይ አዋሕደን ስንገኝ ብቻ ነዉ። አንዳንድ ዉስጣቸዉ ባዶነት የሚሰማቸዉና ኃጢአትን በእግዚአብሔር ቃል ሽፋን አድርገዉ ለመፈጸም ሲሉ ብዙ ሰዎች የራሳቸዉን አቋራጭ መንገድ ይፈጥራሉ። እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ሲሳናቸዉ በእግዚአብሔር፣ በእመቤታችን፣ በቅዱሳን ስም እየነገዱ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ለመኖር ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ደግሞ የሕይወት መንገድ እጅግ ጠባብ መሆኗን ነዉ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 12 ቁጥር 29 ላይ የገለጸልን። በመሆኑም እግዚአብሔርን በብልጣብልጥነት አታለን ከንስሐና ከቅዱስ ሥጋዉና ደሙ ዉጭ በሆነ ሕይወት በምንም መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ አንችልም። ብዙዎች እንዲህ እያሉ የሚያስተምሩና ሰዎችን ከምግባር የሚለዩ አስመሳይ አገልጋዮች ዞር ብለዉ «ስለዳን፣ ስለተማርን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለምንወርስ፣ ይህን ኃጢአት ብንፈጽም ችግር የለዉም» እያሉ በዝሙቱ፣ በስርቆቱ፣ በመተቱ፣ በጥንቆላዉ፣ በክፋትና ተንኮል ሕይወት የሚሰለፉ ናቸዉ።

እግዚአብሔር ቅዱሳንና ጻድቃን ክብርና ሞገስ ከእርሱ ማግኘታቸዉን እንዲሁም ቅድስናቸዉ እንዲታወቅና እንዲታሰቡ ለማድረግ በሚታሰቡበት ቦታ ድንቃድንቅ ተአምራትን፣ ፈዉስን ሊያደርግ ይችላል። በቅዱሳንና በጻድቃን ምልጃና ተራዳኢነት የሚያምንና የሚያከብራቸዉ ሰዉ በረከትንና ጸጋን

ያገኛል። እዉነተኛ ባለሟላቸዉን ደግሞ ለንስሐ ለቅዱስ ቁርባን ያበቁታል። በመጨረሻም የእግዚአብሔር መንግሥት ይወርሳል። በተቃራኒዉ በቅዱሳንና በጻድቃን ስም የሚነገድ፣ በኃጢአት ሕይወት የሚመላለስና የሚልከሰከስ ሰዉ የንስሐ ሕሊና አያገኝም። ምክንያቱም ሕሊናዉን በማደንደን ነዉና ኃጢአት የፈጸመዉ። የንስሐ ሕሊና ሊያገኙ የሚችሉት ባለማወቅ ኃጢአት የፈጸሙና በሥጋ ድካምና በሰይጣን ፈተና ተሸንፈዉ በኃጢአት የወደቁ ብቻ ናቸዉ እንጂ ለራሱ አቋራጭ መንገድ ፈጥሮ «አንዴ ድኛለሁ፣ ተምሬላሁ» ብሎ በኃጢአት የሚጸናና የሚመላለስ ሰዉ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሰና ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን ካልተቀበለ በስተቀርበ በምንም መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ስድስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በእርሶም ሆነ በሌሎች የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች እንዲሁም እንራሴዎች በኩል በተላለፉ የእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ «ትጠረጋላችሁ፣ ትቆረጣላችሁ፣ ትደመሰሳለችሁት፣ ትጠፋላችሁ፣ ትደቃላችሁ፣ ትፈጫላችሁ፣ ትወድማላችሁ... ወዘተ» የሚሉ ቃላቶች አሉ:: እንዲሁም በአንዳንድ አዋልድ የጸሎት ሆነ የምስጋና መጻሕፍት ላይ ኃጢአተኞች፣ ዓመፀኞን እንዲጠፉ የሚገልጽበት ቦታ አለ:: እነዚህ አባባሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸዉ ወይ? ምክንያቱም «ጠላታችሁን ዉደዱ» እየተባለ እነዚህ ቃላቶች መጠቀም አግባብ ነዉ ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በግልጽ ማወቅ ያለብን እያንዳንዱ ቃላት፣ ሐረግ፣ ዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ምዕራፍ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ዉስጥ የተገለጹት ምክንያት አላቸዉ::

ለምሳሌ መጽሐፈ ነገሥት ም.16፥ቁ.1እስከ4 «የእግዚአብሔር ቃል በባኦስ ላይ እንዲህ ብሎ ወደ አናኒ ልጅ ወደ ኢዩ መጣ:: ከመሬት አስነሥቼ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ አለቃ አድርጌሃለሁ፤ አንተ ግን በኢዮርብዓም መንገድ ሄደሃል፣ በኃጢአታቸዉም ያስቈጡኝ ዘንድ ሕዝቤን እስራኤልን አስተሃቸዋል:: ስለዚህም፣ **እነሆ ባኦስንና ቤቱን ፈጽሜ እጠርጋለሁ**፤ ቤትህንም እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም ቤት አደርጋለሁ:: **ከባኦስም ወገን በከተማይቱ ዉስጥ የሚሞተዉን ዉሾች ይበሉታል፤ በሜዳዉም የሚሞተዉን የሰማይ ወፎች ይበሉታል**::»ይላል:: ይህ በዓመፀኞች ላይ የመጣባቸዉን የእግዚአብሔርን ቁጣ ያሳየናል:: አሁንም ወደፊትም በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ዋና ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ በዚህና ከዚህ በላይም እንዲሁም ባነሰ መልኩ ሊመጣባቸዉ ይችላል::

1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 2 ከቁጥር 9እስከ10 « እርሱ የቅዱሳኑን እግር ይጠብቃል ኃጥአን ግን ዝም ብለዉ በጨለማ ይቀመጣሉ፤ ሰዉ በኃይሉ አይበረታምና:: **ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ**፤ በሰማይም ያንጎዳጕድባቸዋል፤ እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል፤ ለንጉሡም ኃይል ይሰጣል፤ የመሲሑንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል::»ይላል::

መዝሙረ ዳዊት መዝ9 ቁ.5 « አሕዛብን ገሠጽህ ዝንጉዎችንም አጠፋህ **ስማቸዉንም ለዘላለም ደመሰስህ::** ጠላቶች በጦር ለዘላለም ጠፉ ከተሞቻቸዉንም አፈረስህ **ዝክራቸዉም በአንድነት ጠፋ**::»

መዝ11(12) ቁጥር 3 **«የሽንገላ ከንፈሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል**::»

መዝ.17 ቁ.42-44 «የጠላቶቼን ጀርባ ሰተኸኝ የሚጠሉኝንም አጠፋሃቸዉ:: ጮኹ የሚረዳቸዉም አልነበረም፤ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ አልሰማቸዉም:: **እንደ ትቢያ በነፋስ ፊት እፈጫቸዋለሁ**:: **እንደ አደባባይም ጭቃ እረግጣቸዋለሁ**::»

*መዝ19(20) ቁ. 8እስከ13* « እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታግኛቸዉ ቀኝህም የሚጠሉህን ታግኛ ቸዉ:: በተቍጣህም ጊዜ እንደ እሳት እቶን አድርጋቸዉ:: **<u>እግዚአብሔር በቍጣዉ ያጠፋቸዋል እሳትም ትበላቸዋለች</u>**:: ፍሬአቸዉ ከምድር ዘራቸዉንም ከሰዉ ልጆች ታጠፋለህ:: ክፋትን በአንተ ላይ ዘርግተዋልና የማይቻላቸዉንም ምክር አሰቡ:: ወደ ኋላቸዉ ትመልሳቸዋለህ፤ ፍላጻን በፊታቸዉ ላይ ታዘጋጃለህ:: አቤቱ በኃይልህ ከፍ ከፍ በል፤ ጽናትህንም እናመሰግናለን እንዘምርማለን::»

*መዝ.144(145) ቁጥር 20* «<u>ኃጢአተኞችንም ሁሉ ያጠፋል</u>»

*መዝ 142(143) ቁ.12* «በምሕረትህ <u>ጠላቶቼን ደምስሳቸዉ</u>፣ እኔ ባሪያህ ነኝና ነፍሴን <u>የሚያስጨንቁአትን ሁሉ አጥፋቸዉ</u>:: »ይላል::

*መዝ.82(83) ÷12እስከ18* <u>«የእግዚአብሔርን መሠዊያ እንወርሳለን የሚሉትን:: አምላኬ ሆይ እንደ ትቢያ በነፋስ ፊትም እንደ ገለባ አድርጋቸዉ</u>:: እሳት ዱሩን እንደሚያቃጥል ነበልባልም ተራሮችን አንደሚያነድድ እንዲሁ <u>በቍጣህ አሳዳቸዉ</u>÷ <u>በመቅሰፍትህም አስደንግጣቸዉ</u>:: ፊታቸዉን እፍረት ሙላዉ÷ አቤቱ ስምህንም ይፈልጋሉ:: <u>ይፈሩ ለዘላለሙም ይታወኩ ይጐስቍሉ ይጥፉም</u>:: ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ በምድርም ሁሉ ላይም አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንህ ይወቁ::»

*መዝ.69(70)÷22እስከ28* «ማዕዳቸዉ በፊታቸዉ ለወጥመድ ለፍዳ ለዕንቅፋት ትሁንባቸዉ ዓይኖቻቸዉ እንዳያዩ ይጨልሙ ጀርባቸዉም ዘወትር ይጕበጥ:: <u>መአትህን በላያቸዉ አፍስስ የቍጣህ መቅሠፍትም ያግኛቸዉ</u> ማደሪያቸዉ በረሃ ትሁን÷ በድንኳኖቻቸዉም የሚቀመጥ አይገኝ::አንተ የቀሰፍኸዉን እነርሱ አሳድደዋልና በቍስሌም ላይ ጥዝጣዜ ጨመሩብኝ:: በኃጢአታቸዉ ላይ ኃጢአትን ጨምርባቸዉ በጽድቅህም አይግቡ:: <u>ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ</u>::»

*መዝ.59 ÷ 5እስከ13* «አንተም አቤቱ የኃያላን አምላክ የእስራኤል አምላክ አሕዛብን ሁሉ ትጐበኛቸዉ ዘንድ ተነሥ <u>ዓመፅ የሚያደርጉትን ሁሉ አትማራቸዉ</u>::ማታ ይመለሱ እንደ ዉሾችም ይራቡ በከተማም ይዞሩ::እነሆ በአፋቸዉ አሰምተዉ ይናገራሉ ሰይፍም በከንፈሮቻቸዉ አለ ማን ይሰማል? ይላሉ::

አንተ ግን አቤቱ ትሥቅባቸዋለህ አሕዛብንም ሁሉ ትንቃቸዋለህ:: እግዚአብሔር መጠጊያዬ ነዉና ኃይሌን ወደ አንተ አስጠጋለሁ:: የአምላኬ ቸርነቱ ይገናኘኛል አምላኬ በጠላቶቼ ላይ ያሳየኛል:: ሕግህን እንዳይረሱ አትግደላቸዉ አቤቱ ጋሻዬ <u>በኃይልህ በትናቸዉ አዉርዳቸዉም</u>::

ስለ አፋቸዉ ኃጢአት ስለ ከንፈራቸዉም ቃል መርገምንና ሐሰትን ስለሚናገሩ <u>በትዕቢታቸዉ ይጠመዱ</u>:: <u>በቍጣ አጥፋቸዉ</u> እንዳይኖሩም አጥፋቸዉ የያዕቆብም አምላክ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንዲገዛ ይወቁ::»

*መዝ. 109 ÷ 15* « ***መታሰቢያቸዉ ከምድር ይጥፋ***::» ይላል

ትንቢተ ኢሳይያስ 17 ÷ 12እስከ14 «እንደ ባሕር ሞገድ ድምፅ ለሚተምሙ ለወገኖች ብዛት እንደ ኃይለኛም ዉኃ ጩኸት ለሚጮኹ **አሕዛብ ወዮላቸዉ!** አሕዛብ እንደ ብዙ ወኃ ጩኸት ይጮኻሉ እርሱ ግን ይገሥጻቸዋል እነርሱም እየሸሹ ይርቃሉ **በተራራም ላይ እንዳለ እብቅ በነፋስ ፊት ዐዉሎ ነፋስ እንደ ሚያዞረዉም ትቢያ ይበተናሉ**:: በመሸ ጊዜ እነሆ ድንጋጤ አለ ከማለዳም በፊት አይገኙም:: የዘረፉን ሰዎች እድል ፈንታ የበዘበዙንም ዕጣ ይህ ነዉ::»

ትንቢተ ኢሳይያስ 28÷16እስከ19 «ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ የተፈተነዉን÷ የከበረዉን÷ መሠረቱ የጸናዉን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም:: ለገመድ ፍርድን ለቱንቢም ጽድቅን አደርጋለሁ፤ በረዶዉም የሐሰትን መሸሸጊያ ይጠርጋል÷ ዉኆችም መሰሪያዉን ያሰጥማሉ:: ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል÷ ከሲኦልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይጸናም፤ **የሚትረፈረፍ መቅሠፍት ባለፈ ጊዜ ትረገጡበታላችሁ**::»

ትንቢተ ኢሳይያስ 30÷11እስከ14 «ስለዚህ የእስራኤል ቅዱስ እንዲህ ይላል ይህችን ቃል አቃልላችኋልና በግፍና በጠማምነት ታምናችኋልና በእርሱም ተደግፋችኋልና ስለዚህ ይህ በደል አዘብዝቦ ለመፍረስ እንደ ቀረበ አፈራረሱም ፈጥኖ ድንገት እንደሚመጣ እንደረጅም ቅጥር ይሆንባችኋል:: **የሸክለኛ ማድጋ እንደሚሰበር ይሰብረዋል ሳይራራም ያደቅቀዋል** ከስባሪዉም እሳት ከማንደጃ የሚወስዱበት ወይም ዉኃ ከጉድጓድ የሚቀዱበት ገል አይገኝም::»

ኢሳ.51÷ 7እስከ8 «ጽድቅን የምታዉቁ ሕጌም በልባችሁ ያለ ሕዝብ ሆይ÷ **ስሙኝ የሰዉን ተግዳሮት አትፍሩ**÷ በስድባቸዉም አትደንግጡ:: **እንደ ልብስ ብል ይበላቸዋል**÷ እንደ በግ ጠጉር **ትል ይበላቸዋል**፤ ጽድቄ ግን ለዘላለም ማዳኔም ለትዉልድ ሁሉ ይሆናል::»

ኢሳይያስ 65 ÷ 6እስከ7 **«ኃጢአታችሁንና የአባቶቻችሁን ኃጢአት በአንድ ላይ ወደ ብብታቸዉ ፍዳ አድርጌ እመልሳለሁ እንጂ ዝም አልልም**÷ ይላል እግዚአብሔር በተራሮችም ላይ ስላጠኑ በኮረብቶችም ላይ ስለ ሰደቡኝ ስለዚህ አስቀድመዉ የሠሩትን ሥራቸዉን በብብታቸዉ እሰፍራለሁ::»

ኢሳይያስ 66 ÷ 15እስከ17 **«እነሆ እግዚአብሔር መዓቱን በቍጣ ዘለፋዉንም በእሳት ነበልባል ይመልስ ዘንድ ከእሳት ጋር ይመጣል**÷ ሰረገሎቹም እንደ ዐዉሎ ነፋስ ይሆናሉ:: **እግዚአብሔርም በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ በእሳትና በሰይፉ ይፈርዳል**፤ **በእግዚአብሔርም ተወግተዉ የሞቱት ይበዛሉ**:: በመካከላቸዉ ያለዉን አንዱን ተከትለዉ ወደ ገነቱ ይገቡ ዘንድ ሰዉነታቸዉን የሚቀድሱና የሚያነጹ÷ የእሪያንም ሥጋ አስጸያፊ ነገርንም አይጥንም የሚበሉ **በአንድነት ይጠፋሉ**÷ ይላል እግዚአብሔር::»

ኢሳይያስ5፥ከ11እስከ26 «ስካርን ለመከተል በጥዋት ለሚማልዱ፣ የወይን ጠጅም እስኪያቃጥላቸዉ እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸዉ! መሰንቆና በገና ከበሮና እምቢልታም የወይን ጠጅም በግብዣቸዉ አለ፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ግን አልተመለከቱም፣ እጁም ያደረገችዉን አላስተዋሉም።

ስለዚህ ሕዝቤ ወደ ምርኮ ሄዱ፣ ጌታን አላወቁትምና፤ ከበርቴዎቻቸዉም ተራቡ፣ ሕዝባቸዉም ተጠሙ። ሲኦልም ሆድዋን አስፍታለች፣ አፍዋንም ያለ ልክ ከፍታለች፣ ከበርቴዎቻቸዉና አዛዉንቶቻቸዉ ባለጠጎቻቸዉም ደስተኞቻቸዉም ወደ እርስዋ ይወርዳሉ። ሰዉም ይጎሰቍላል፣ ሰዉም ይዋረዳል፣ የትዕቢተኞችም ዓይን ትዋረዳለች፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ግን በፍርድ ከፍ ከፍ ብሎአል፣ ቅዱሱም አምላክ በጽድቅ ተቀድሶአል። የበግ ጠቦቶች በማሰማርያቸዉ ዉስጥ ይሰማራሉ፣ እንግዶችም የሰቡትም ባድማ ይበላሉ።

በደልን በምናምንቴ ገመድ፣ ኃጢአትንም በሰረገላ ማሰሪያ ወደ ራሳቸዉ ለሚስቡ ፡- እናይ ዘንድ ይቸኩሉ፣ ሥራዉንም ያፋጥን፤ እናዉቃትም ዘንድ የእስራኤል ቅዱስ ምክር ትቅረብ፣ ትምጣ ለሚሉ ወዮላቸዉ!

ክፉዉን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ፣ ጨለማዉን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ጣፋጩን መራራ መራራዉንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸዉ!

በዓይናቸዉ ጥበበኞች በነፍሳቸዉም አስተዋይ ለሆኑ ወዮላቸዉ!

የወይን ጠጅ ለመጠጣት ኃያላን የሚያሰክረዉንም ለማደባለቅ ጨካኞች ለሆኑ በደለኛዉን ስለ ጉቦ ጻድቅ ለሚያደርጉ፣ የጻድቁን ጽድቅ ለሚያስወግዱ ወዮላቸዉ!

ስለዚህ የእሳት ወላፈን ቃርሚያን እንደሚበላ፣ እንዲሁ የእነርሱ ሥር የበሰበሰ ይሆናል ቡቃያቸዉም እንደ ትቢያ ይበናል፤ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔርን ሕግ ጥለዋልና። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ ላይ ነድዶአል እጁንም በላያቸዉ ዘረግቶ መትቶአቸዋል። ተራሮችም ተንቀጠቀጡ፣ ሬሳቸዉም በአደባባይ መካከል እንደ ጕድፍ ሆኖአል። በዚህም ሁሉ እንኳ ቍጣዉ አልተመለሰችም፣ ነገር ግን እጁ ገና ተዘርግታ ትኖራለች።» ይላል

ትንቢተ ኤርምያስ 23 ከቁጥር 19እስከ20 « እነሆ፣የእግዚአብሔር ዐዉሎ ንፋስ፣ እርሱም ቍጣዉ፣ የሚያገለባብጥ ዐዉሎ ነፋስ ወጥቶአል፤ የዓመፀኞችን ራስ ይገለባብጣል። የእግዚአብሔር ቍጣ የልቡን አሳብ ሠርቶ እስኪፈጽም ድረስ አይመለስም በኋለኛዉ ዘመን ፈጽማችሁ ታስታዉሱታላችሁ።» ይላል

ሕዝቅኤል 27 ፥ 34እስከ36 «ነገሥታትን ባለ ጠጎች አድርገሻል። አሁን ግን በጥልቅ ዉኃ ዉስጥ በባሕር ተሰብረሻል ንግድሽና ጉባኤሽ ሁሉ በመካከልሽ ወድቀዋል። በደሴቶች የሚኖሩ ሁሉ

ተደንቀዉብሻል ነገሥታቶቻቸዉም እጅግ ፈርተዋል ፊታቸዉም ተለዉጦአል። የአሕዛብ ነጋዴዎች አፍዋጩብሽ <u>አንቺ ለድንጋጤ ሆነሻል እስከ</u> <u>ዘላለምም አትገኚም</u>።»

ሕዝቅኤል 30 ፥ 10እስ12 «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የግብፅን ብዛት በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ አሸራለሁ። እርሱና የአሕዛብ ጨከኞች <u>ሕዝቡ ምድሪቱን ለማጥፋት ይመጣሉ</u> ሰይፋቸዉንም በግብጽ ላይ ይመዝዛሉ <u>ምድሪቱንም በተገደሉት ይሞላሉ</u>። <u>ወንዞችንም ምድረ በዳ አደርጋለሁ</u> ምድሪቱንም በክፉ ሰዎች እጅ እሸጣለሁ <u>ምድሪቱንና ሙላዋንም በእንግዶች እጅ ባድማ አደርጋለሁ</u> እኔ እግዚአብሔር ተናግሬያለሁ።» ይላል

ትንቢተ አሞጽ 9፥ 1እስከ4 «ጌታን በመሠዊያዉ አጠገብ ቆሞ አየሁት እርሱም እንዲህ አለ ፦ መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ ጉልላቶቹን ምታ፥ በራሳቸዉም ሁሉ ላይ ሰባብራቸዉ <u>እኔም ከእነርሱ የቀሩትን በሰይፍ እገድላለሁ የሚሸሽ አያመልጥም</u>፥ የሚያመልጥም አይድንም። ወደ ሲኦል ቢወርድ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች ወደ ሰማይም ቢወጡ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ በቀርሜሎስም ራስ ዉስጥ ቢሸሸጉ ፈልጌ ከዚያ አወጣቸዋለሁ በጥልቅ ባሕር ዉስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ ከዚያ እባቡን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይነድፋቸዋል በጠላቶቻቸዉም ፊት ተማርከዉ ቢሄዱ ከዚያ ሰይፍን አዝዛለሁ ፥ እርሱም ይገድላቸዋል <u>ዓይኔንም በእነርሱ ላይ ለክፋት እንጂ ለመልካም አላደርግም</u>።» ይላል

በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 10፡ ቁጥር 15 ላይ ለትዕቢተኞችና ለእብሪተኞች እንዲሁም ለዓመፀኞች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «<u>ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ</u>»ብሏል። በዚሁ ወንጌል በምእራፍ 11 ቁጥር 42 «<u>ፍርድንና እግዚአብሔርን መዉደድ ስለምትተላለፉ ወዮላችሁ</u>» በማለት ጌታችን አስመሳይ አገልጋዮችን አስጠንቅቋል፡ በምእራፍ 20፡ ቁጥር 18 « በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ <u>ይቀጠቀጣል፤ የሚወድቅበት ሁሉ ግን ይፈጨዋል አለ</u>።» ይላል። ይህም በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ የሚሰናከል ሰዉ ይወድቅበታል፣ ይቀጠቀጥበታል፣ በመጨረሻም ይፈጭበታል ማለት ነዉ። ምዕራፍ 21 ቁጥር 24 «<u>የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች</u>።»

በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 3 ከቁጥር7እስከ9 « ስለዚህ ከእርሱ ሊጠመቁ ለወጡት ሕዝብ እንዲህ ይላቸዉ ነበር፦ <u>እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣዉ ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ?</u> እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ በልባችሁ ፦ አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ፤ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና፤ አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ <u>እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል</u>።» ይላል።

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 3 ቁጥር 10 «<u>መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቍረጣል ወደ እሳትም ይጣላል</u>» ቁጥር 12 « አዉድማዉን ፈጽሞ ያጠራል ስንዴዉንም በጎተራ ይከታል <u>ገለባዉን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል</u>።» ምዕራፍ 24 ቁጥር 50 «ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል

ከሁለት ይሰነጥቀዋል እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል» ይላል።

የቅዱስ ጳዉሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕራፍ 1 ፣ ቁጥር 18 «እዉነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸዉና በዓመፃቸዉ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ በሰማይ ይገለጣልና፤» ይላል

በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 14 ቁጥር 8 « ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ወደቀች እያለ ተከተለዉ።» ቁጥር 9እስከ11 « ለአዉሬዉና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩም ወይም በእጁ ምልክትን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቍጣዉ ወይን ጠጅ ይጠጣል በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሣቀያሉ። የሥቃያቸዉም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል ለአዉሬዉና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸዉም ይላል።» በምዕራፍ16 ቁጥር 4 «ሦስተኛዉም ጽዋዉን በወንዞችና በዉኃ ምንጮች ዉስጥ አፈሰሰ እነርሱም ደም ሆኑ። የዉኃዉም መልአክ ፡-ያለህና የነበርህ ጌታ ሆይ ቅዱስ ሆይ እንዲህ ስለ ፈረድህ ጻድቅ ነህ፤ የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል፤ የሚገባቸዉ ነዉና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። ከመሠዊያዉም ፡- አዎን ሁሉን የመትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ፍርዶችህ እዉነትና ጽድቅ ናቸዉ ብሎ ሲናገር ሰማሁ።» ምዕራፍ 18 ቁጥር 8 « ስለዚህ በአንድ ቀን ሞትና ኀዘን ራብም የሆኑ መቅሰፍቶች ይመጣሉ፤ በእሳትም ትቃጠላለች፤ የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነዉና።

ዮሐንስ ራእይ 21፣ቁጥር 8 «ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኛዎችም የአስማተኞችም ጣዖትን የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸዉ በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነዉ፤ ይኸዉም ሁለተኛ ሞት ነዉ።» ይላል።

ባጠቃላይ ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቃሉ፣ ይደመሰሳሉ፣ ይወድማሉ፣ ይጠራጋሉ፣ ከወንበራቸዉ ይቆረጣሉ፣ ከምድር ይጸዳሉ፤ ተራ፣ ወረዳ፣ ዓመፃኛ፣ ልምሾ መሆናቸዉ ይመሰከርባቸዋል፤ ይዋረዳሉ፣ ይቀጣሉ፣ ለሕያዉነት ዘመን በስቃይና በመከራ ሕይወት በሲኦልና በገሃነመ እሳት ዉስጥ ይኖራሉ፤ ፍዳቸዉን ይቀበላሉ።

እነዚህና ሌሎች ብዙ እነዚህ መሰሎች የሚያሳዩን የእግዚአብሔር ቅጣት ክብደታቸዉን ነዉ። አንዳንድ አባባሎች ቃል በቃል በተገለጸዉ መልኩ ይፈጸማሉ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ከወንበር መቆረጥ ማለት በሰይፍ ወይን በሌላ መሳሪያ መቆረጥ ማለት አይደለም። ከባለጊዜነትና ከሥልጣን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበሩ መወገድ ማለት ነዉ።

ከላይ በተወሰነ መልኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ያቀረብኩት በብሉይ ዘመን ሆነ በአዲስ ዘመን ያለዉ አምላክ አንድ ዓይነት ነዉ። ዘመናቱ ብቻ ነዉ የተለያዩት። ይኸዉም በአዲስ ዘመን የሕይወት መንገድ ቀሎልን ለእግዚአብሔር መንግሥት በቀላሉ ለመግባት እንችላለን። ነገር ግን በብሉይ ዘመን ሆነ በአዲስ ዘመን ኃጢአት የተከለከለና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ የሚመላለሱና

እግዚአብሔርን የሚገዳደሩ ከዛም ባለፈ የሚክዱና የሚያስክዱ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በምድርም ጭምር ዋጋ ከፍለዉ እንደሚጠረጉና እንደሚቀጡ ነዉ:: ታዲያ «ጠላታችሁን ዉደዱ» የተባልነዉ በብሉይ ዘመን በነብዩ ሙሴ አማካይነት ዘመኑ የጨለማና የሰዎች ንቃተ ሕሊና ያልሰለጠነና ያልሰፋ በመሆኑ «ጠላትህን ጥላ የሚል» አስተሳሰብ ስለነበረ ያንን ለመሻርና ለማሻሻል ነዉ:: ምክንያቱም ስለ ጠላት መለየት የእኛ መስፈርትና የእግዚአብሔር መስፈርት የተለየ ስለሆነ ነዉ:: ይኸዉም ለእኛ ጠላት የሚመስለን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችንና ፍላጎታችን ማሸከርከር የማንችለዉን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም በምናስቀዉ ቀልድ አልስቅ የሚለን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም ለማታለል ስንፈልግ አልታለልም የሚልና ሌላዉም እንዳይታለል የሚያስጠነቅቅ ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም ከእኛ ዓመፃ ዓላማ ጋር አልሰለፍ የሚል ሊሆን ይችላል:: ወይንም ለዓመፃ ስራችን «ሕሊናዬን አልሸጥም ለሕሊናዬና ለአምላኬ ነዉ የምታመነዉ» የሚለዉን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም ከስህተታችን እንድንታረም የሚመክረንና ከጥፋት የሚመልሰንን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም በእዉነትና በቅንነት ስለ ዓመፃችንና ስለ ክህደታችን እንዲሁም ስለ አምልኮ ምንዝርነታችን እየገሰጸን ወደ ሕይወት የሚመልሰንን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: ወይንም በትህትናና በፍቅር ሆኖ እያንዳንዱን ካለአድሎና በደል በእኩልነት የሚያገለግለዉን እዉነተኛ ሰዉን ሊሆን ይችላል:: ወይንም ስለ እዉነት ራሱን ክዶ የሚመሰክርና በእዉነት የሚያገለግልን የእግዚአብሔርን ሰዉ ሊሆን ይችላል:: በዓለም ላይ የሚታየዉም ይኸዉ እዉነታ ነዉ:: ባጠቃላይ እንኳን እንደ ጠላት ሊቆጠር ቀርቶ አንዳች ቅሬታ እንኳ ሊኖረን የማይገባዉን ሰዉ እንደ ጠላት ልንቆጥርና ልንጠላዉ ስለምንችል ነዉ በአዲስ ዘመን «ጠላታችሁን ዉደዱ» የተባለዉ:: ከእኛ የሚጠበቀዉ «ጠላታችን» ለምንለዉም መልካም ማድረግና ክፉዉን በክፉ አለመመለስ ነዉ:: እንዲህ ስናደርግ እግዚአብሔር ከእርሱ ፈቃድ ተቃራኒ የተሰለፈንና የእዉነት ተቃዋሚዉና እዉነተኛ ጠላት እርሱ የመለየት ብቃት አለዉና የራሱን እዉነተኛ ፍርድ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በምድርም ጭምር ይሰጣል፣ ይቀጣል፣ ያዋርዳል:: በእግዚአብሔር እዉነተኛ ፍርድ ደግሞ ከእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደ ቅዱሳኑ «እዉነተኛ ፈራጅ ነህ» ብሎ ያመሰግናል እንጂ እንደ ዓመፀኞቹና ከሃዲዎች እንዲሁም ርኩሰት ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች አያጉረመርምም:: የእግዚአብሔርን እዉነተኛና ፍትሐዊ ፍርድንም አይቃወምም::

ሌላዉ ይህን ያቀረብኩት በተወሰኑ በጸሎት፣ በምስጋና፣ በድርሳናት ዉስጥ የሥጋና ደም ስሜት አልተጨመሩም፤ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ የሆኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተጻፉት ላይ የራሳቸዉን እንክርዳድ አልጨመሩም ለማለት ፈልጌ ሳይሆን በትንሹ እዉቀታችን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉቀት ለመቃወምና ለመተቸት አንነሳ፣ ራሳችንን ለሙሉ እዉነትና እዉቀት እናብቃ ለማለት ፈልጌ ነዉ:: በኢትዮጵያ ትንሣኤ በመልካሙ ዘመን እዉነተኛ የበጎች እረኞች በእዉነተኛ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ሕዝቡንና ምእመኑን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ስለሚያገለግሉ፤ በስንዴ ዉስጥ የተዘረዉ የሥጋና የደም ስሜት የተገለጸበት እንክርዳድ ከስንዴዉ ስለሚለይና ንጹህ ስንዴ ብቻ ስለሚቀርብ፤ እስከዛዉ ድረስ እኛም እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን «ይህ ስህተት ነዉ፣ ይህ ይዉጣ፣ ይህ ይሻር፣ ይህ ትክክል ነዉ.... ወዘተ» እያልን እንዳንሰናከልና እንዳናሰናክል ራሳችንን መጠበቅ አለብን:: እንዲሁም ሕሊናችንን ለሙሉ እዉነት እያዘጋጀን በቅንነትና በእዉነት እየተመላለስን ያንን

ጊዜ በእምነታችንና በሥርዓታችን ጸንተን በመገኘት የሚመጣብንን ፈተና በትዕግስትና በቆራጥት ማሸነፍ ነዉ የሚገባን።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነዉ ተብሏል «ቀኝ ጉንጫችሁን ሲመቷችሁ ግራ ጉንጫችሁን ስጡ» ብሏል። ታዲያ ከላይ የተገለጹት ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ የእግዚአብሔር ቃል እርስ በእርሱ አይጋጭም ወይ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ሆነ በሌሎች አዋልድ መጻሕፍት ዉስጥ እያንዳንዱ ቃላት፣ ዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ምዕራፍ፣ ክፍል፣ የተጻፈበት ምክንያት አለዉ። ስለ አንድ ጉዳይ የተነገረዉ ወይንም የተጻፈዉ ስለዚያ ጉዳይ ለመግለጽ ነዉ እንጂ በዚያ ሽፋን ሌላዉን ጉዳይ ለራሳችን እንዲሆን አድርገን እንድንጠቀምበት አይደለም። እግዚአብሔር ፍርዱ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ እንደሆነ ሁሉ፤ ምሕረቱና ቸርነቱ ደግሞ ገደብ የሌለዉ የትየለሌ ነዉ። እግዚአብሔር የፍቅር፣ የሰላም፣ የእዉነት አምላክ ነዉ። በእነዚህ ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚፈጽመዉን ደግም በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍለዋል (ይቀጠዋል)። ስለ ምሕረቱና ቸርነቱ ደግሞ በእዉነተኛ ንስሐ የሚመለሰዉን እንደ ምድራዊ ዓመፃዉ ደረጃ በምድር ዋጋ ቢያስከፍለዉ(ቢቀጣዉ) እንኳ ይቅርታ አድርጎለት ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ ያበቃዋል። በምድራዊ ሕይወቱ ዘመንም ይባርከዋል። ከላይ የተገለጹት ተግባራዊ የሚሆነዉ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ሳይሆን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋቸዉ ሞልቶ እየፈሰሰ ባለና በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እርሱ አልመለስ ባሉትና በዓመፃ ላይ ዓመፃ እየፈጸሙ ያስቆጡት ላይ ነዉ። ምክንያቱም እንደ ሰይጣናት ሕሊናቸዉን አደንድነዉ በትዕቢትና በዓመፃ ሕይወት ስለጸኑ በሥጋ የተገለጹ ሰዎች ቢሆኑም ምድባቸዉ ግን ከርኩሳን መናፍስት ጋር ነዉ።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስመጣ እግዚአብሔር ዓለምን ያሸነፈዉ በፍቅርና በእዉነት ነዉ። ይኸዉም በሥጋ ማርያም ተገልጾ አሳዳጆችን ማጥፋት ሲችል እንደ አቅመ ቢስ ተሰዶ ነዉ ድል ያደረጋቸዉ። ተሳዳቢዎችን፣ ግፈኞችን፣ ጨካኞችን ወዲያዉ ሊያጠፋቸዉ ሲችል፤ ባለጊዜ ነበሩና ትዕግስትን ሊያስተምረን ምንም ማድረግ እንደማይችል ራሱን ቆጥሮ በትዕግስት፣ በጽናት የተለያየ ጸዋትዎ መከራ ተቀብሏል። እንዲሁም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነዉ ሞትን ድል አድርጎ በመሸነፍ ዓለም ያሸነፈዉና በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ዓለምን የሚያሸንፉበትን ኃይል ያጎናጸፈዉ። ከዚህ አንጻር እኛ እሱን በምናምንና በምናመልክ አማኞችና አገልጋዮች ላይ የተለያየ ፈተና ከዓለምና ከባለጊዜ ሰዎች ቢመጣብን እዉነትን ከመያዝና ስለ እዉነት ከመመስከር ዉጭ እነሱ በእኛ ላይ የሚያደርሱትን የክፋትና የበቀል ተግባር እኛም እንደነሱ መመለስ እንደሌለብን ነዉ። ምክንያቱም የዓመፃ ጽዋቸዉ ሲሞላ እግዚአብሔር በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በመቶ እጥፍ ስለሚበቀላቸዉ ነዉ።

ከእኛ የሚጠበቀዉ ልቦና እንዲሰጣቸዉ መጸለይና በእዉነተኛ አቋማችን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነን መገኘት ነዉ። ከዚያ ዉጭ ማንም ሰዉ ከሕግ በላይ አይደለምና እዉነተኛ ፈራጆች ቢኖሩም ባይኖሩም ለመፈራረጃም ጭምር ለሚመለከተዉ የሕግ አካል መገፋታችንን፣ መበደላችንን፣

ግፍ መፈጸሙን ማቅረብ እንችላለን፡፡ ፈራጁ ከባለጊዜዎች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ባይፈርድልን እንኳ እዉነተኛዉ ዳኛ እግዚአብሔር ይፈርዳልና «እኔ ግፍ ተፈጽሞብኛልና ግፍ ልፈጽም፤ እኔ ተበድያለሁና ልበድል፤ እኔ አድሎና መድሎ ተፈጽሞብኛልና እኔም አድሎና መድሎ ልፈጽም» የምንል ከሆነ፤ ይህ የአሕዛብ በእግዚአብሔር የማያምኑ ሕይወት ነዉና ይህ ደግሞ የሚመሰክርብን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል እንዳልጠበቅን ነዉ፡፡ ምክንያቱም በእርሱ በእዉነተኛዉ ፈራጃ አምላክ ስራ ገብተናልና፡፡ እነደዛ ካደረግን ደግሞ ስለእኛ ብሎ አይፈርድልንም፤ ይልቁኑ በራሳችን ስለተመካንና ስለታበይን፣ ስለመንፈጽመዉ ግፍና በደል እንጠየቅበታለን፤ ዋጋም እንከፍልበታለን፡፡

እዚህ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 10 ከቁጥር ከ24እስከ42 ያለዉን ብንመለከት ይኸዉም፡

«ደቀ መዝሙር ከመምህሩ ባሪያም ከጌታዉ አይበልጥም፡፡ ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ ባሪያም እንደ ጌታዉ መሆኑ ይበቃዋል፡፡ ባለቤቱን ብዔል ዜቡል ካሉት ቤተ ሰዎቹንማ እንዴት አብዝተዉ አይሉአቸዉ!

<u>እንግዲህ አትፍሩአቸዉ</u> <u>የማይገለጥ የተከደነ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና</u>፡፡ በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ፡፡ <u>ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸዉን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለዉን ፍሩ</u>፡፡ ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም፡፡ የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል፡፡ እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ፡፡ <u>ስለዚህ በሰዉ ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለዉ በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ በሰዉ ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለዉ በአባቴ ፊት እክድዋለሁ</u>፡፡

<u>በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን አንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም</u>፡፡ ሰዉን ከአባቱ ሴት ልጅንም ከእናትዋ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰዉም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል፡፡ <u>ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባዉም ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባዉም መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባዉም</u>፡፡ ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል፡፡

እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል፡፡ ነቢይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፡፡ ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ዉኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እዉነት እላችኋለሁ ዋጋዉ አይጠፋበትም፡፡» ይላል

ከላይ የተገለጸዉን ብንመለከት ማንም ሰዉ ስለ እዉነት ማንንም ሳይፈራ እንደ አባብ ልባም እንደ ርግብ የዋህ ሆኖ ሊመሰክርና በእዉነት ሊያገለግል ይገባዋል፡፡ በዚያ ምክንያት ደግም እግዚአብሔር ሳይፈቅድ አንዳች ፈተናና መከራ ሊደርስበት አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ፈተናና መከራ ቢመጣበት እንኳ ሊጎዳ የሚችለዉ ቢበዛ በሥጋዉ እንጂ ሕያዉ ነፍሱን ማንም ምን ሊያደርጋት አይችልም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ስለ እግዚአብሔር እዉነት ሲባል ሕዝብ ከሕዝብ፣ ቤተሰብ ከቤተስብ ሊለያይ እንደሚችል ነዉ፡፡ ምክንያቱም በዲያብሎስ መንፈስ የሚመራና በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሰዉ ምንም አንድነትና ኅብረት የላቸዉም፡፡ ምናልባት በሥጋዊ ኑሮዋቸዉ አንድነት ሊኖራቸዉ ቢችልም በመንፈሳዊ ሕይወታቸዉና አገልግሎታቸዉ ግን ለአንድ ዓላማ ሊሰለፉ አይችሉም፡፡ የሁለቱም ዓላማና ግብ ፍጹም ተቃራኒ ነዉ፡፡ ነገር ግን ከሥጋና ከደም ስሜታቸዉ ወተዉ ሁሉም ለእግዚአብሔር እዉነት ከተሰለፉ እንኳን ቤተሰብ ይቅርና አገርና ዓለም ለአንድ ዓላማና ግብ ሊሰለፉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የሁሉም መሪ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ስለሚሆን፤ ፈቃዱን ብቻ ያስፈጽማቸዋልና ነዉ፡፡ ስለዚህ ከእያንዳንዱ መጽሐፍ ክፍል የተነገረበትና የተጻፈበትን ምክንያት ሳንረዳና ሳናስተዉል ቀርተን ቃላትና ዐረፍተ ነገር ለራሳችን እንዲስማማ አድርገን ከተጠቀምና እንሰናከልበታለን፣ እንደወድቅበታል፣ እንጠረግበታልን፡፡ ለዚህም ነዉ አንዳንድ «መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ» የሚሉ የእምነት ድርጅቶች ለሥጋና ለደም ስሜታቸዉ ማርኪያ የሚሆን በሺዎች የሚቆጠሩ የእምነት ድርጅቶችን ፈጥረዉ እንደ ሥጋ ፈቃዳቸዉ እየተመላለሱ ያሉት፡፡ እንዲሁም እጅግ ብዙዎቹም የራሳቸዉን የዉሸት እዉነት ፈጥረዉ አገራቸዉ በግፈኞች ስትወረርና ግፍና በደል ሲፈጸም «እኛ አገራችን በሰማይ ነዉ» በማለት የወረራዉና የግፉ ተባባሪ በመሆን በአገራቸዉ ላይ ክህደት የፈጸሙትና ያስፈጸሙት፡፡ ለአገሩ ታማኝ ያልሆነና የአገር ፍቅር የሌለዉ ሰዉ ያለየዉን ዓለም «አፈቅራለሁ፣ ታማኝ እሆንለታለዉ» ቢል ማስመሰያና መሸንገያ ነዉ እንጂ በዚህች በአጭር ዘመናችን ለአገራችንና ለሕዝቡ ታማኝ መሆን ካልቻልንና የአገርና የወገን ፍቅር ከሌለን፣ እንደ እንስሳ በደመ ነፍስ ነዉ የምንመላለሰዉ እንጂ እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች አይደለንም፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፤ እግዚአብሔር ዓመፀኞችንና ግፈኞችን እንዲበቀል መጸለይና ማሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነዉ ወይ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፤ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት እኛ «እነዚህን ሰዎች ተበቀል» ስላልነዉ እግዚአብሔር በቀል አይፈጽምም፡፡ ምክንያቱም እንዲበቀላቸዉ የምንፈልገዉ ሰዎች ዓመፀኛና ግፈኛ ያልናቸዉ በራሳችን መስፈርት ነዉ እንጂ በእርሱ መስፈርት አይደለምና፡፡ ይኸዉም ብዙ እዉነተኛ ሰዎች «ዓመፀኛ» ተብለዉ ሲወነጀሉ ጥንትም ታይቷል፤ አሁንም እየተመለከትን ነዉ፡፡ ሌላዉ ደግሞ እግዚአብሔር የሚበቀለዉ የዓመፀኞች፣ የዓመፃና የግፍ ጽዋ ሞልቶ ሲፈስ ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 6 ቁጥር 9እስከ11 ላይ «አምስተኛ ዉ ማኅተብ በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያዉ በታች አየሁ፡፡ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ፡- <u>**ቅዱስና እዉነተኛ ጌታ ሆይ እስከ መቼ**</u>

ድረስ አትፈርድም ደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ፡፡ ለእያንዳንዳቸዉም ነጭ ልብስ ተሰጣቸዉ፣ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸዉ የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸዉና የወንድሞቻቸዉ ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፣ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸዉ፡፡» ይላል፡፡

ከዚህ የምንረዳዉ እንኳን በትክክል ዓመፀኛዉን፣ ግፈኛዉን መለየት የማንችል ሰዎች ቀርቶ ነፍሳቸዉን ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሱና በሰማዕትነት አምላካቸዉን ያከበሩ ቅዱሳን እንኳ እግዚአብሔር ዓመፀኞችንና ግፈኞችን እንዲበቀላቸዉና እንዲፈርድባቸዉ ሲጠይቁ፣ የዓመፀኞች ጽዋቸዉ ሲሞላ እንደሚፈጸመ ነዉ የተመለሰላቸዉና እነሱ ግን በታላቅ ክብር እንዲያርፉ የተደረገዉ፡፡

መዝ78(79)፥ ከ4እስከ6 «ለጎረቤቶቻችንም ስድብ ሆንን፣በዙሪያችንም ላሉ ሣቅና ዘበት፡፡ አቤቱ፣ እስከመቼ ለዘላለም ትቈጣለህ? ቅንዓትህም እንደ እሳት ይነድዳል? ስምህን በማይጠሩ መንግሥታት ላይ፣ በማያዉቅህም አሕዛብ ላይ መዓትህን አፍስስ፤» ይላል፡፡

ሌላዉ ደግሞ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች በምድር ላይ እያሉ ዓመፀኞችንና ግፈኞችን እንደ እግዚአብሔር ሆነዉ እንዲበቀሏቸዉ ሙሉ ሥልጣን ሊሰጣቸዉ ይችላል፡፡ ይኸዉም በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 17፡ 1እስከ2 ላይ እንደተገለጸዉ «ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህ ትተዋልና፣ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፣ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና፤ እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ አለ፡፡» በማለት ለአምላኩ ቀናኢ የሆነዉ ነብዩ ኤልያስ ለሦስት ዓመት ዝናብ እንዳይዘንብና ዓመፀኞች እንዲቀጡ አስደርጓል፡፡

እንዲሁም እሱን ለመያዝ ወደ እርሱ የተላኩትንና በትዕቢትና በእብሪት ሊይዙት የመጡትን የንጉሡን መልእክተኞች ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲበላቸዉ አስደርጓል፡፡ እግዚአብሔርም ኤልያስ ፈቃዱን የሚፈጽምና የሚያስፈጽም ስለሆነ የጠየቀዉን ሁሉ ወዲያዉ ፈጽሞለታል፡፡ በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 11 ቁጥር 4እስከ7 ድረስ « እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለት ወይራዎችና ሁለት መቅረዞች ናቸዉ፡፡ ማንም ሊጎዳቸዉ ቢወድ እሳት ከአፋቸዉ ይወጣል ጠላቶቻቸዉንም ይበላል፤ማንም ሊጎዳቸዉ ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል፡፡ እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸዉ፥ ዉኃዎችንም ወደ ደም ሊለዉጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸዉ፡፡» ይላል፡፡

ከዚህ የምንገነዘብ የእግዚአብሔር ልዩ አገልጋዮችና መልእክተኞች በእግዚአብሔር እዉነት ላይ በሚቃወሙትና በሚያምጹት ላይ የተለያየ መቅሰፍት ማምጣት እንደሚችሉና እነሱን ሊያጠቃ ሆነ ጉዳት ለማድረስ የሚሞክር ሰዉን ወዲያዉ ሊቀስፉ እንደሚችሉ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ሙሉ ማደሪያ ለሆኑ ለተለዩ አገልጋዮቹ እስከዚህ ድረስ ኃይልንና ሥልጣን አጎናጽፏቸዋል፡፡ እንደአጠቃላይ ግን ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀዉ እግዚአብሔር በራሱ መለኪያና ጊዜ በቀልን እንዲፈጽም ለእርሱ መተዉ ነዉ ያለብን እንጂ፤ ባለጊዜ ነኝ በሚል ስሜት እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን በራሳችን በቀልና

ግፍ የምንፈጽም ከሆነ እግዚአብሔር ደግሞ በመቶ እጥፍ እኛንም ይበቀለናል።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ሰባት

« <u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) እንዴት ሕፃናትንና አዋቂዎችን እኩል ይፈታተናሉ? ሕፃናት በምን አቅማቸዉ ነዉ ፈተናዉን ሊቋቋሙት የሚችሉት?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: መታወቅ ያለበት የሕፃናት ነፍስ ሆነ የአዋቂዎች ነፍስ አንድ ዓይነት የሆነች የማትለያይና የማትበላለጥ፣ የማታድቅ፣ የማትወፍር፣ የማታረጅ፣ የማትሞት፣ የወደፊት ዘመን እድሜዋ የማይቆጠር፣ ለወደፊት የማትኖርበት ዘመን የሌለ ነዉ:: በመሆኑም የሕፃናት ነፍስ ሆነ የአዋቂዎች ነፍስ የሰይጣናትን ፈተና በእኩል መቋቋም ይችላሉ:: ልዩነቱ ሕፃናት አእምሯቸዉ ተከፍቶ እንደ አዋቂዎች የማመዛዘንና የማገናዘብ ብቃት ስለሌላዉ በቀላሉ ራሳቸዉን መግዛት ስለማይችሉ የሰይጣናትን ፈተና መቋቋም ተስኗቸዉ የዉስጥ ስሜታቸዉንና ጭንቀታቸዉን በለቅሶና በመነጫነጭ ይገልጹታል:: እንኳን ሕፃናት ይቅርና በሥጋቸዉ አዋቂዎች ሆነዉ ራሳቸዉን በሚገባ ያልገዙና አእምሮ ሕፃናት የሆኑ ሰዎች ጭምር የርኩሳን መናፍስትን የደቂቃዎች ቢበዛ የቀናት ፈተናን መቋቋምና ስሜታቸዉን መቆጣጠረ ተስኗቸዉ ሲነጫነጩና በሆነዉ ባልሆነዉ ሲጣሉ ይታያል:: የሰይጣናት ፈተና በቀጥታ የሚመጣዉ በዋንኛነት በሕሊችን(በነፍሳችን) ሲሆን፤ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በአካላችን(በሥጋችን) ላይ ነዉ:: ሕፃናት ራሳቸዉን ካለመግዛትና ነገሮች ካለማመዛዘን ከሚመጣባቸዉ ፈተና ዉጭ እንደ አዋቂዎች በተለያዩ የኃጢአት ተግባር በርኩሳን መናፍስት አይፈተኑም:: አዋቂዎች ግን እንደ እድሜ ደረጃቸዉ፣ እንደሚያመዛዝንና እንደሚያገናዝብ አእምሮ ብቃታቸዉ ደረጃ በተግባር፣ በንግግር፣ በሐሳብ ጭምር ሊፈተኑ ይችላሉ:: ነጻ የሕሊና ፈቃዳቸዉንም ተጠቅመዉ በፈተናዉ ባለመዉደቅ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ መሰለፍ ይችላሉ:: በዓለም የሚመጣባቸዉን ፈተና በሚገባ ሲወጡ ነዉ በትንሹ ዘመናቸዉ በመታመናቸዉ ምክንያት የማያልፈዉን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚወርሱትና እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነዉ የሚኖሩት:: በተቃራኒ ደግሞ በዐይን ቅጽበት ምድራዊ ዘመናቸዉ ካልታመኑና በሰይጣናት ፈተና ከወደቁ በሕያዉነት ዘመናቸዉ አይታመኑምና ለእግዚአብሔር መንግሥት አይበቁም::

በአዳምና ሔዋን የገነት ዓመፃ ምክንያት በሁሉም የሰዉ ዘሮች ላይ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ ስለሚከሰት ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ ባደፈና በጎሰቆለ ባሕርይ ዉስጥ ይመላለሳሉ:: ከዚያ ዉጭ ግን ይህች ዓለም(ምድር) የፈተና ቦታ ናትና በተለያየ ቀንና ሰዓት ለተወሰነ ደቂቃ ቢበዛ ለተወሰነ ሰዓት እጅግ ቢበዛ ለቀናት ርኩሳን መናፍስት ነፍሳችንን(ሕሊናችንን) እንደ አቅማችን ደረጃ ሊፈታተኑና ሊያስጨንቁ ይችላሉ:: ነገር ግን ያቺን ፈተና በትዕግስትና በጽናት ልንወጣ ነዉ የሚገባን እንጂ ለደቂቃዎች መፈተንና መጨነቅ ብለን የማይገባ ስራ ልንሰራ ሆነ ንግግር ልንናገር አይገባም:: ሰይጣናት ለብዙ ቀናት ሆነ ለወራት ወይንም ለዓመታት ሊፈትኑንና ሊያስጨንቁት የሚችሉት በተለያየ የኃጢአትና የርኩሰት ሕይወት ስንመላለስና በዓመፃችን ጸንተን ስንገኝ ነዉ እንጂ ከተፈቀደላቸዉ የደቂቃ ቢበዛ የሰዓታት እጅግ ቢበዛ የጥቂት ቀናት ፈተናና ማስጨነቅ ዉጭ ማንንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊፈትኑና ሊያስጨንቁ አይችሉም:: ሰይጣናት የደቂቃና የሰዓታት ቢበዛ

የቀናት ፈቃድ ያገኙትም፣ እኛ እንዳንታበይና ራሳችንን እንዳናመጻድቅ፣ ሁሉ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጠብቆትና ቸርነት እንድናስተዉል፣ እንዲሁም በእዉነትና በቅንነት ሕይወት ብቻ እንድንመላለስ ፈልጎ ነዉ:: በዚህች እጅግ አጭር በሆነችዉ የሕይወት ዘመናችን ለሕሊናችንና ለአምላካችን ታማኝ ሆነን መኖር ይጠበቅብናል እንጂ እንደሥጋና ደም ስሜታችን የምንመላለስ ከሆነ የሰይጣናት መጫወቻ ነዉ የምንሆነዉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፤ አንዳንድ ወላጆች ሕፃናትን ማጾም «ኢ-ሰብአዊነት ነዉ» የሚሉ አሉ:: ሕፃናት መጾም የለባቸዉም ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፤ ቅድስት ቤተክርስቲን የቀደሙት ወላጆቻችን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ የጸሎት ሆነ የጾም፣ የምስጋና የመሳሰሉትን ሥርዓት አዘጋጅተዉልና:: እኛ በሥርዓቱ የምንጠቀም ደግሞ የትኛዉ ለትኛዉ ነዉ ሳንል ለሁሉም አንድ ዓይነት ትእዛዝ እንሰጣለን:: በገዳም ያለዉ በዓለም ያለዉ ተራዉ ምእመን እንደሱ እንዲጾምና እንዲጸልይ ይፈልጋል:: አንዳንድ አስመሳይ አገልጋዮች እነሱ የማይፈጽሙትን እዉነተኛና ብቃት ያላቸዉ አገልጋይ ለመምሰል በምእመኑ ላይ ሸክም ያበዙበታል:: ታዲያ ይህ ግለሰቦች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ እየተመሩ በምእመኑ ላይ የሚያመጡት ተጨማሪ ትእዛዝ በእዉነተኛ አገልጋዮች ዘንድ እየተጣራ ትክክለኛ መስመር ሊይዝ ይገባዋል:: አንዱ ሲፈልግ «በዚህ መጽሐፍ ላይ ቡና አጠጡ ይላልና ቡና የጠጣ ሰዉ ከአስርቱ ትእዛዝ አንዱን እንደሻረ ተቆጥሮ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም» ይላል:: አንዱ ተነስቶ «ሸኮናዉ ያልተሰነጠቀ እንስሳ ሥጋ የበላ ሰዉ ርኩስ ነዉና የእግዚአብሔር መንግሥት አይወርስም» ይላል:: አንዱ ተነስቶ «እዚህ ቦታ ያልሄደ ሰዉ ለእግዚአብሔርን መንግሥት አይበቃም፤ የሄደ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ካለምንም ምግባር ይወርሳል»ይላል:: አንዱ ተነስቶ «የእመቤታችን ሠላሳ ሦስቱን በዓላት ያላከበረና ስራ የሰራ ሰዉ ተዉግዟልና ገሃነመ እሳት ነዉ የሚገባዉ» ይላል:: አንዱ ተነስቶ « በልደታ፣ በባሕታ፣ በዮሐንስ፣ በአቦ፣ በኢየሱስ፣ በሥላሴ ፣ በኪሮስ፣ በሐና፣ በሚካኤል፣ በእግዚአብሔር አብ፣ በአረጋዊ፣ በቁርቆስ፣በኪዳነ ምሕረት፣ በስጢፋኖስ፣ በገብርኤል፣በማርያም፣ በዑራኤል፣ በጊዮርጊስ፣ በተክለሃይማኖት፣ በመርቆሪዮስ፣ በሀብተማርያም፣ በመድኃኔ ዓለም፣ በአማኑኤል፣ በባልወልድ፣ በቀዳሚት ስራ የሰራ ሰዉ ተወግዟል፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም» ይላል:: አንዱ ተነስቶ «በቅዳሴ ሰዓት በቤተክርስቲያን ወስጥ የሚንቀሳቀስ ይቀሰፋል፣ ይሰየፋል» ይላል:: አንዱ ተነስቶ «ወር አበባ የታያት ሴት ርኩስ ናት፤ ወደመቃብር የሄዱ ርኩሶች ናቸዉ፤ የወለደች ሴት ርኩስ ናት... ወዘተ» ይላል:: አንዱ ተነሥቶ «ያልተገረዘ ሰዉ ሊጠመቅና የእግዚአብሔ ልጅ ሊሆን አይችልም» ይላል:: አንዱ ተነሥቶ «ጠጉሩን ያልተላጨ ክርስትና መነሳትና ከእግዚአብሔር ልጅነት ማግኘት የለበትም» ይላል:: እንደዚህ የመሳሰሉ የተለያዩ ሰዎች የሚሰጡት ትምህርት አለ:: ታዲያ እዉነተኛ መምህራንና ሊቃዉንት እንዲሁም ካህናት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እየመረመሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንዲይዝ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስጋባ** በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ሕፃናት ከሰባት ዓመታቸዉ ጀምረዉ እንዲጾሙ ያዛል። ይህ ደግሞ ሥርዓት ነዉ እንጂ ዶግማ አይደለም። በሰባት ዓመቱ ጾም ያልጀመረ ሕፃን ሕግ አፍራሽ ኃጢአተኛ ነዉ ማለት አይደለም። ነገር ግን ዓለም የሚመራዉ በዉሸት እዉነት ወይንም በጨለማዉ ገዥ መንፈስ ስለሆነ እያንዳንዱን የሚመዝነዉና የሚገመግመዉ እንዲሁም የሚያሰላዉ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ ነዉ እንጂ እንደ ነፍሱ ፈቃድ በእዉነትና በመንፈስ ቅድስ አይደለም። እርሱነቱን ወይንም ሕያዉ ነፍሱን ክዶ ራሱን «እንስሳ ነኝ፣ ማቾ ፈረሽ በስባሽ ነኝ እንጂ ሕያዉ ፍጥረት አይደለሁም» ስላለ፤ ሕፃናት እንዲጾሙ በመደረጉ ቢቃወምና ትችት ቢያቀርብ አያስገርምም። እንኳን ሕፃናት «አዋቂዎች ለምን እንዲጾሙ ይደረጋል? ይጎዳሉ፣ የምግብ እጥረት ያጋጥማቸዋል» ቢል አያስደንቅም። ነገር ግን እምነት አለኝ የሚል ሰዉ «ለምን ሕፃናት ሆኑ አዋቂዎች ይጾማሉ?» ቢል ይህ ሊያስገርምና ሊያስደንቅ ይችላል። ምክንያቱም እምነት እያለዉ የጾምን ጥቅም የማያዉቅ ሰዉ ሆዱ አምላኩ የሆነ ሰዉ ነዉ እንጂ እዉነተኛ አምላክ እንዳለዉ አጠራጣሪ ነዉ። ወላጆቻችን ራሳችንን እንድንገዛ ገና ከሕፃንነት እድሜያችን ነዉ ያስተማሩን። ይኸዉም እንቁላሉ፣ ሥጋዉ፣ ቅቤዉ እያማረን በረቡዕና በአርብ እንዲሁም በዐብይ ጾምና በፍልሰታ ጾም እንዳንበላቸዉ በማድረግ ነዉ። በተለይ በፍልሰታ ጾም እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እንድንጾም አድርገዉ ገና በሕፃንነታችን በጾም የሚገኘዉን ኃይል(ጸጋ) እንድንላበስ አድረገዉናል። እንዲሁም ሰይጣናትን ገና ከሕፃንነት እድሜያችን ጀምሮ እንድንቀጣቸዉና እንድናቃጥላቸዉ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት ራሳችንን በመግዛት ነፍሳችን በሥጋችን ላይ የበላይነት እንድትቆናጸፍ ስላደረጉን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የምንመችና ትእዛዙን ለመጠበቅ የማንቸገር ሆነናል።

አሁን ያለነዉ ትዉልዶች ግን እንኳን ልጆቻችን እንዲጾሙና ከልጅነታቸዉ ጀምረዉ ራስን መግዛት እንዲለማመዱ ማስደረግ አይደለም ራሳችን ለሥጋችን የሚመች ሥርዓት የምንፈልጋና የምናፈላልግ እንዲሁም ራሳችንም ለመመስረት ቆርጠን የተነሳን ለሥጋችን ያደርንና «ለሆዴ ነዉ የምኖረዉ» እንዳሉት አሕዛብ ሆነናል። በዚህ ምክንያት ትዉልዱ እንኳን ራሱን ሊገዛ ቀርቶ እንደ ቦይ ወኃ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ የሚሄድና በተለያየ ሱስ ተጠምዶ ሰይጣናት የሚፈነጩበትና የሚጋልቡት ሆኗል። የዚህ ችግር ዉጤት ደግሞ የመጀመሪያዉ ዋጋ ከፋይ(ተቀጪ ) ወላጆች ሆነዋል። ምክንያቱም እንደ ዉጭዉ ዓለም ልጆቻቸዉ ልቅ፣ ጋጠወጥ ሆነዉ እንዲያድጉ ስላደረጉና እንደ እንስሳ «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንጨፍር፣ እንዝናና፣ እንወለዳለን ፣ እናድጋለን ፣ እንሞታለን ... ወዘተ» እንዲሉ አድርገዉ ስላሳደጓቸዉ እንኳን እግዚአብሔርንና ታላላቆችን መፍራትና ማክበር ይቅርና ወላጆች እንኳ ሳይከበሩ ልጆች በሚፈጽሙት የተለያየ ወንጀል በየእርስቤቱ የሚንከራተቱና ልጆቻቸዉም አልባሌ ቦታ በመዋል በተለያየ ያልተገባ ሕይወት ላይ ሊገኙ ችለዋል። ይህ ችግር ደግሞ ከወላጆች አልፎ ለቤተሰብ ከዚያም ለጎረቤት ከዚያፍ ለሰፈር ከዚያም ለአገርና ለዓለም ሸክም ሆኗል። ይህ ሁሉ ችግር የመጣዉ ልጆችን ገና ከሕፃንነታቸዉ ጅምሮ የእግዚአብሔርን ቃልና እግዚአብሔርን መፍራትና ማፍቀር ባለማስተማራችንና የተለያዩ ጸጋዎች የሚገኝበትን ጸሎት፣ ጾም፣ ምስጋና ስላላለማመድናቸዉና እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ እንዲመላለሱ ስላደረግን ነዉ።

በአግባቡ ልጆችን ባለማሳደጋችን ምክንያት ልጆቻችን ሆኑ እኛ ወላጆች በምድርም በሰማይም ዋጋ እንከፍልበታለን( እንቀጣበታለን) ማለት ነዉ:: ስለዚህ ሕፃናት እንደ አቅማቸዉና እድሜያቸዉ ደረጃ በልጅነታቸዉ ጾምን ቢጀምሩ ተጠቃሚ ይሆናሉ እንጂ አይጎዱም:: በጾም ምክንያት የመጀመሪያ ተጎጂ ሰይጣናት ናቸዉ:: ምክንያቱም በእኛ ሆድ ተጠቅመዉ ተመጋቢዎቹ እነሱ ናቸዉ:: ነገር ግን ነፍሳችን ከሥጋችን ጋር ተዋሕዳለችን በምድር ለመቆየት ይህ ሥጋ የሚራብና የሚጠማ ስለሆነ በእርሱ አማካይነት ነፍሳችን ተመጋቢ ናት:: በጾም ወቅት ግን ሰይጣናት ስለሚቀጡና ስለሚቃጠሉ ነፍሳችን በመጾሟ የበለጠ ኃይል ትጎናጸፋለች እንጂ አንዳች አትጎዳም:: ጾሙንም ቢሆን እያንዳንዱ እንደ ተሰጠዉ ጸጋ ነዉ መጾም ያለበት እንጂ አንድ ሰዉ «ባሕታዉያንና ገዳማዉያን ከዓመት እስከ ዓመት እንደሚጾሙ፤ እኔም ልጹም» ካለ የተለያ ጸጋ እስካላገኘ ድረስ አይቻለዉም:: ነገር ግን እምነቱ እንደሚያዘዉ መጾም ይጠበቅበታል::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፤ አንዳንድ የአብነት ተማሪዎች ወደ አገልግሎት ከመጡ በኋላ ከክርስትና ሕይወት ዉጭ በሆነ ተግባርና ሕይወት ይመላለሳሉ:: በቤተክርስቲያን ትምህርት ዉስጥ ለመተተኛ ነት፣ ለጥንቆላ፣ ለአስማት፣ ለመጽሐፍ ገላጭነት፣ ለመሳሰሉት እዉቀት የሚያበቃ ትምህርት ይሰጣል ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፤ በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት ነገር፤ እያንዳንዱ ሰዉ ለሚፈጽመዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ራሱን ነዉ የሚወክለዉ እንጂ ተቋምን ወይንም አገርን አይደለም:: ሰዉ በግሉ የተለያየ ኃጢአትን ሊፈጽም ይችላል:: ነገር ግን የሚጠየቀዉ በኃላፊነትና በአገልግሎት ላይ ሆኖ ከፈጸመ፤ አንድ ስለ ግል ኃጢአቱ፤ ሁለተኛ ደግም ሌሎች እዉነተኛ አገልጋዮችንንና ምእመናን በማሰናከሉ ነዉ:: በምድርም ይሁን በሰማይ የሚደርስበት ቅጣት ከፍ ያለ ይሆናል::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስገባ በቅድስት ቤተክርስቲያ ትምህርት ዉስጥ ከክርስትና ሕይወት ጋር የሚጋጭና የሚቃረን ትምህርት አይሰጥም:: አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን የሥጋ ፈቃዳቸዉን አሸንፈዉ የነፍሳቸዉን የበላይነት በማስጠበቅ በምድርም የሚባረኩበትንና በሰማይም የማያልፈዉን መንግሥት የሚወርሱበት ትምህርት ነዉ የሚሰጠዉ:: ለዚህም ነዉ አንዳንድ መምህራንና ሊቃዉንት ለሥጋቸዉ ጥቅም ሳይሯሯጡ ከዛም ባለፈ አንዳች ለአገልግሎታቸዉ ዋጋ ሳይጠብቁ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ዘመናቸዉን ሁሉ በማስተማርና በማገልገል የሚያሳልፉትና ትልቁን ዋጋ ከእግዚአብሔር በመጠበቅ በሥጋ ሞት እስከሚጠሩ ድረስ በቅንነትና በእዉነት፣ በትህትን፣ በፍቅር፣ በትጋት፣ በትዕግስት ሕይወት ጸንተዉ የሚኖሩት:: ታዲያ በስንዴ ዉስጥ እንክርዳድ እንደማይታጣ ሁሉ በእነዚህ በእዉነተኛ መምህራንና ሊቃውንት ስም የሚነግዱ አስመሳይ መምህራንና ሊቆች ይኖራሉ:: ተስፋቸዉ ምድራዊ ነዉና ሌት ተቀን ሐሳባቸዉ ገንዘብ ላይ ነዉ:: በዚህም ምክንያት ሰይጣናዊ ትምህርት ሊሰጡ ይችላሉ:: ለእዉነተኛ ትምህርት ብሎ የሄደዉን ተማሪ መስመሩን ሊያስቱት ይችላሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ የሰይጣናትን ትምህርት እንደ ጥበብ ቆጥረዉ የተለየየ የዓመፃና የርኩሰት ተግባር ሊፈጽሙበትና ሊያስፈጽሙበት ይችላል:: በመሆኑም ማንም ሰዉ እነዚህን ሰዎች ማጋለጥና

ስለ ዓመፃቸዉ ዋጋ እንዲከፍሉ (እንዲቀጡበት) ማድረግ ነዉ የሚጠበቅበት እንጂ ሊቀበላቸዉ ሆነ የአገልግሎት ቦታ ሊሰጣቸዉ አይገባም። በእነሱ ምክንያትም እዉነተኛ መምህራንን፣ ሊቃዉንትን፣ መዘምራንን፣ ካህናትን፣ ዲያቆራትን፣ ባጠቃላይ እዉነተኛ አገልጋዮችን ሊጠላ ሆነ ሊርቃቸዉ አይገባም።

እዉነተኛ መምህራን ሆኑ ሊቃዉንት ማንኛዉንም ተማሪ ከመጀመሪያዉ እግዚአብሔርን ማፍቀርና መፍራት እንዲይዝና በወንጌል እንዲታነጽ አድርገዉ ነዉ ማስተማር የሚጠበቅባቸዉ እንጂ፤ እንደ ሰዉ አዋቂ ሆነ ሊቅ ሆኖ መልካም ምግባርና የተቀደሰ ሕይወት ከሌለዉ ለነፍሱ አንዳች የሚጠቅመዉ ነገር የለም። ምናልባት በሥጋዉ ጥቅም ሊያገኝበት ይችል ይሆናል። ይህ ደግም ለዐይን ቅጽበት እድሜዉ የሚጠቅመዉ ነዉ እንጂ ለሕያዉነት ሕይወት አይጠቅመዉም። ይልቁና እያወቀ አጥፊ ከሆነ ከተራዉ ምእመን በላይ እጅግ የባሰ ፍርድ ነዉ የሚጠብቀዉ። የአብነት ተማሪዎቹ ደግሞ ከመምህራኖቻቸዉ መማር ያለባቸዉ እዉቀትን ብቻ ሳይሆን ትህትናቸዉን፣ ትጋታቸዉን፣ ፍቅራቸዉን፣ ትዕግስታቸዉን፣ ጽናታቸዉን፣ ቅንነታቸዉን፣ እዉነተኛነታቸዉን፣ ባጠቃላይ መልካም ስነ ምግባራቸዉንና የቅድስና ሕይወታቸዉን ጭምር መሆን አለበት። ያኔ ነዉ እነሱም የማስተማርና የመስበክ ደረጃ ላይ ሆነ የተለያየ አገልግሎት ላይ ሲሰማሩ መልካም ፍሬ ሊያፈሩ የሚችሉትና በምድርም ተባርከዉ በሰማይም ከብረዉ ሊኖሩ የሚችሉት። እዉቀትን ብቻ ይዘዉ ከወጡና ከምግባር ከተለዩ ግን እንኳን ለሌላዉ ሊተርፉና መልካም ፍሬ ሊያፈሩ ቀርቶ ለራሳቸዉም አይሆኑም። ምክንያቱም እዉቀቱን ለገቢ ማግኛ ብቻ ይጠቀሙበታል እንጂ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ አይገኙበትም።

አንዳንድ የዘመኑ «ሰባኪ ነን፣ ዘማሪ ነን» የሚሉ በቂ እዉቀትና ትምህርት ሳይኖራቸዉ ለገቢ ማግኛ ብቻ ተሰልፈዉ የእግዚአብሔርን ቃል ለሽያጭ የሚያዉሉት መንፈሳዊነቱ ስለሌላቸዉና ሌት ተቀን ሐሳባቸዉ ከገንዘብ ጋር ስለሆነ ነዉ። ለዚህም ነዉ ትምህርታቸዉ ሆነ ስብከታቸዉ እንክርዳድ የተደባለቀበት፤ መዝሙራቸዉም ዘፈንና ዳንኪራ የመሰለዉ። የእግዚአብሔር ቃል የሚሸጥ ቢሆን ኖሮ እዉቀት ያካበቱት መምህራንና ሊቃዉንት እንዲሁም ልዩ ድምፅ ያላቸዉ መዘምራን በየቀኑ የስብከትና የመዝሙር ካሴት እያወጡ ባለ ብዙ መቶ ሺህና ሚሊየነር በሆኑ ነበር። ነገር ግን ተግባራቸዉ እግዚአብሔርንና ምእመናን ማገልገል እንጂ ራሳቸዉን ማበልጸግና ለግላቸዉ ትርፍ ማካበት አይደለም። የልፋታቸዉንና የድካማቸዉን እንዲሁም የአገልግሎታቸዉን ክፍያ የሚጠብቁት ከአምላካቸዉ በመሆኑ ብዙም ይከፈላቸዉ ትንሽ ይከፈላቸዉ ለእዉቀታቸዉ ሳይሰስቱ ሙሉ ጊዜያቸዉንና ሕይወታቸዉን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚያዉሉት። የምድራዊ ሕይወታቸዉ የተሟላ ይሁን ያልተሟለ ቅድሚያ ለነፍሳቸዉ ነዉ የሚሰጡት። አስመሳይ አገልጋዮች ደግሞ ቅድሚ የሚሰጡት ለሥጋዊ ጥቅምና ለምድራዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ዝና ለመሳሰሉት ነው።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፤ ማንኛዉም ሰዉ ርኩሳን መናፍስትን ማቅረብ ሆነ ማራቅ ይችላል ወይ?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__፤ ርኩሳን መናፍስት ወደ ሕሊናችን ወይንም ነፍሳችን ሊቀርቡ የሚችሉት ክፋትና ተንኮል ስናስብ፣ ለጥላቻና ለበቀል ስንነሳሳ፣ ለትዕቢትን ለዓመፃ ሕይወት ራሳችንን ስናሰልፍ፣ ራሳችንን ለተለያየ ሐሳብና ጭንቀት ስንዳርግ፣ ለዝሙት የሚያነሳሳ ጡትንና እምብርትን፣ ቂጥና ታፋ፣ ዳሌና ባት የመሳሰሉትን ገላልጦ በሚያሳይ አለባበስ ስንገለጽ፤ በተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምላኮ ስንመላለስ፤ የተለያዩ የኃጢአት ተግባር ስንፈጽምና ስንመለከት፣ እንዲሁም ስንናገርና ስናስብ ነዉ። ለሕሊችን ወይንም ከነፍሳችን ልናርቃቸዉና ኃይላቸዉን ልምሾ ልናደርግ የምንችለዉ ደግሞ ቀና ስናስብ፣ መልካም ስንሰራ፣ እዉነተኛ ስንሆን ነዉ።

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__፤ በጾም ወቅት መምህራን ሆኑ ካህናት ምእመኑን፤ «ከዚህ ኃጢአት ተከልከሉ፣ የተጣላችሁ ታረቁ፣… ወዘተ» እያሉ ያስተምራሉ። ከጾም ዉጭ ኃጢአት እንዲፈጸም ሆነ ሰዉ ከሰዉ ጋር እንዲጣላ ይፈቀዳል ማለት ነዉ?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__፤ ኃጢአት በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እንድንፈጽመዉ አይፈቀድም። የጾም ዓላማም ከኃጢአት እንድንጠበቅ ከእግዚአብሔር ኃይልን(ጸጋን) የምናገኝበትና ሰይጣናትን ድል የምናደርግበት ነዉ። ታዲያ ሥጋ ለባሽ ሰዉ ፍጹም አይደለምና በተለያየ ምክንያት በኃጢአት ቢወድቅ እንዲሁም እንኳን ሰዉና ሰዉ እግርና እግር ይጋጫልና ከሰዉ ጋር የተቀያየመ ሰዉ ያስቀየመዉን ይቅርታ እንዲጠይቅ፤ ቅር የተሰኘዉም ሰዉ አንዳች ቂምና በቀል በዉስጡ ሳይሳድር በልቡ ይቅር እንዲል ለማሳሰብ ነዉ እንጂ፤ በጾም ወቅት ከጥሉላት መብል መከልከልና ለተወሰነ ሰዓት ካለመብልና ካለመጠጥ ቆይቶ ያንን መብልና መጠጥ ደግሞ ለችግረኛ እንዲያበላና እንዲያጠጣ ነዉ የሚጠበቅበት። የተለያዩ ኃጢአቶችን ግን እያንዳንዱ ሰዉ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ እንዲጾም ነዉ የሚታዘዘዉ።

__*ጠያቂዉ አገልጋይ*__፤ በአንዳንድ ቤተክርስቲያን ዉስጥና ዙሪያ ሰዎች «ይህን በሽታ የሚያርቅ፣ በሰይጣናት እንዳትፈተኑና እንዳትጠቁ የሚያደርግ፣ ሰይጣንን የሚያርቅ ልዩ ጽፈት(ድግምት) ያለበት ክታብ ግዙና አንገታችሁ ላይ አንጠልጥሉ፣ በሰዉነታችሁም ዉስጥ ቅበሩ» የሚሉ አሉ። ከእዉነተኛዉ ማኅተምና ከመስቀል በላይ ሰይጣናትን የሚያርቅና የሚጠብቅ በሰዎች የሚዘጋጅ ልዩ መከላከያ መሳሪያ ወይንም በአንገት ላይ የሚጠለቅ፣ በክንድ ላይ የሚታሰር፣ በሰዉነት ዉስጥ የሚቀበር ጽሑፍ አለ ወይ?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: እዚህ ላይ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ሆነ በሌላ ቦታ እንኳን ገቢያቸዉን በሚያሻሽጡ ሰዎች ቀርቶ «አገልጋይ ነን» ብለዉ የማይገባ ትምህርት ሆነ ተግባር የሚፈጽሙ ሰዎች፤ ቤተክርስቲያንን ሊወክሉ አይችሉም። ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ናትና እርሱን በመምሰል የሚያገለግሉና የሚኖሩ ናቸዉ ቤተክርስቲያንን ሊወክሉ የሚችሉት እንጂ ለሥጋዊ ጥቅም ብቻ ሌት ተቀን የሚሯሯጡ ሰዎች ምንም ይሁኑ ምን ቤተክርስቲያንን ሊወክሉ አይችሉም። በተቀደሰዉ ቤት ሆነ በእግዚአብሔር ቃል ሲነገድ እኔም ብዙ የተመለከትኳቸዉና የሰማዋቸዉ አሉ።

እንደምሳሌ ባቀርብ ጠንቋይንና መተተኛን እንደ አዋቂና ጥበበኛ ቆጥረዉ ወደ እነሱ የሚሄዱ ቀራቢ ሰዎችና «አገልጋይ» ነን የሚሉ አስመሳይ አገልጋዮች አሉ።

አንድ ወቅት ክፍለ ሀገር በስራ ላይ እያለሁ ራሴን ሲከብደኝና ሲጨንቀኝ ወደ አንዱ ቤተክርስቲያን ሄጄ ለሦስት ቀን ስጠበል ያጋጠመን አሳዛኝ ተግባር፣ አጥማቂዉ ባለመስቀል ካህን እዛ የሚያጠምቃቸዉን ሰዎች አንድ ሁለት ቀን ካጠመቁ በኋላ «ምንሽን ነዉ የሚያምሽ?» እያሉ ከጠየቁ በኋላ ከመስቀልና ከጠበል አስበልጠዉ «አንድ ለዚህ በሽታ ጽፈት  የሚያዉቅ ሰዉ አለ። ከፈለግሽ የዚህን ያህል ብር የምትከፍይ ከሆነ ከሰዉየዉ(ከመጽሐፍ ገላጭ)(ከመተተኛዉ) ጋር አገናኝሻለዉ» እያሉ የዋሃን ምእመናን ሲያሰናክሉ ተመልክቻለሁ። እኔም መናገር የማልችል ዝምተኛ ሰዉ ነኝኛ በዉስጤ ብቻ በመብገንገን አሳልፌዋለሁ። እንዳልናገራቸዉ አጥማቂ ካህን መነኩሴ ተብለዉ ነዉ ሌሎቹን እያጠመቁ ያሉት። ይህን የመሳሰሉ ብዙ የዓመፃ ስራ በተቀደሰዉ ቦታ ይፈጸማል።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ቤትና ቃል ለገንዘብ ማግኛ እያዋሉት ነዉ እንጂ ከመስቀል፣ ከዉዳሴ ማርያም ጸሎት፣ ከጠበል፣ ከሥጋና ደሙ በላይ መተተኞች ወይንም መጽሐፍ ገላጮች በተለያየ ቋንቋ በብራና፣ በወረቀት እየጻፉና በቆዳ እየጠቀለሉ እንዲሁም ጠንቋዮች እየጠነቆሉ የሰይጣናትን ፈተና ማራቅና ማዳን አይችሉም። ይልቁና ሌሎች አጋንንት እንዲዋሐዱንና መጫወቻቸዉ እንድንሆን  ነዉ የሚያስደርጉት። እነሱም የዲያብሎስ አገልጋዮች ናቸዉ እንጂ እዉነተኛ አገልጋዮች አይደሉም። ምናልባት  እኛን ለማታለልና ለማሳመን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሆነ ከአዋልድ መጻሕፍት ሊጠቃቅሱልን ይችላሉ። ሲፈልጉ እንደ ይሁዳ «ይህ ሽቶ ተሽጦ ለድሆች ለምን አይሰጥም» ብሎ እንደተናገረዉ ወርቃማ ቃላቶንችንና ንግግሮችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ከዛም ባለፈ ተቀባይነት ለማግኘት የእግዚአብሔርን፣ የእመቤታችን፣ የቅዱሳን ስም ሊጠሩ ይችላሉ።

ከዚህ ጋር በቅርቡ የገጠመኝ አንድ ዘመናዊ ትምህርት የተማረች ከዩንቨርስቲ የተመረቀችና በስራ ላይ ያለች እንዲሁም ወደ ቤተክርስቲያን የምትመላለስ አንዲት እህት በአንገቷ ላይ በቆዳ የተሸፈነ ዉስጡ ጽፈት ያለበት እንደ መስቀል አንግታ ተመልክቼ ምን እንደሆነ ስጠይቃት፤ «ሰይጣናትን የሚያርቅ የሰኔ ጎልጎታ ነዉ» አለችኝ። እኔም ኬት እንዳገኘችሁ ጠየኳት። እርሷም አንድ ሰዉ እንደሰጣት መለሰችልኝ። እኔም የይሁዳን ወርቃማ ንግግር ትዝ ብሎኝ «የቤተክርስቲያን መጽሐፍ ከሆነ ይጸለይበታል እንጂ በቆዳ ተሸፍኖ እንደ መስቀል አይነገትም» በማለት ቆዳዉን በምላጭ ፈተን አየነዉ። ከነገረችን መጽሐፍ ጋር አንዳች ግንኙነት ያሌለ «በመግቢያዉ ላይ ለማታለያ በግእዝ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ያለበት በዉስጡ ግን አስማተ ሞገስ የሚልና እንደመስተፋቅር ጽፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ታዲያ ወዲያዉ የመጣልኝ ይህች የተማረች እንዲህ ከሳተች ምኑንም የማያዉቁ ሰዎች ጠንቋዩን፣ መተተኛዉን፣ መጽሐፍ ገላጩን፣ አስማተኛዉን «ይህ አዋቂ፣ ጠቢብ ... ወዘተ ነዉ» እያሉ ቢሄዱ ብዙም ላያስደንቅ ይችላል አልኩኝ። ምክንያቱም እዉቀታቸዉ አነስተኛና በዘልማድ ሕይወት የሚመላለሱ፣ ከድሮ ጀምሮ እንደ ትዉፊት እነዚህ የዲያብሎስ አገልጋዮችን እንደ አዋቂና ጠቢብ እየታዩ ስለሆነ ነዉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የዛሬ አስር ዓመት ገደማ አንድ እህት ልጇ አእምሮዉ ይታመምና የተለያየ ቦታ ብትሞክርም አልድን ይላታል:: አንድ ባለመስቀል ካህን አምስት ሺህ ብር ከከፈለች አንድ የታወቀ «የቤተክርስቲያን» ሰዉ እንደሚያድንላት ይነግሯታል:: እርሷም ልጄ ይዳን እንጂ ችግር የለዉም ትላቸዋለች:: ለሰዉየዉም አንዱ ሆቴል አልጋ ይያዝለትን የተለያዩ መጻሕፍትን እያነበበ ለማዳን ጥረት ያደርጋል:: እኔን ያንን ሕመምተኛ ወንድም ለመጠየቅ ወደዚያ ስፍራ እሄዳለዉ:: የሰዉየዉን የማስመሰል ተግባር በመቃዋም ለታማሚዉ ቤተሰቦች እናገራለሁ:: ያ አስመሳይ በቤተክርስቲያን ስም የሚነግደዉ ሰዉ «እንዲህ የሚናገራችሁ ጀማሪ ክርስቲያን ስለሆነ ነዉ፤ የሰለሞንን ጥበብ ስለማያዉቅ ነዉ» በማለት አስተሳሰቤንና ዉሳኔዬን አናናቀዉ ፤አጥላላዉ:: ነገር ግን አምስት ሺህ ብሩን ቀስ በቀስ ከተቀበለ በኋላ «ለዚህ ፍቱን መድኃኒት የሚገኘዉ ሱዳን ነዉና ለትራንስፓርት የሚሆን ብር አምጡ» ብሎ በመቀበል በዚያዉ ሊጠፋ ችሏል:: ያ የገናኙት «ካህን ነኝ» ባዩ ባልታወቀ ምክንያት ቀኑን ሙሉ ደህና ዉለዉ ሌሊቱን ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ ወደተዘጋጀላቸዉ ቦታ በሥጋ ሞት ሊጠሩ ችለዋል:: በፈጣሪ ሲጠየቁ ምን ይመልሱ ይሆን? «አንተ የሰጠኸን ጥበበኞችና አዋቂዎች ናቸዉና ለምን አንጠቀምባቸዉም ይሉ ይሆን? የዋህ ምእመናንን በማሰናከላቸዉ ጭምር የባሰ ፍዳ አይቀበሉ ይሆን!? አሁን ያለነዉ ትዉልዶች ግን የአታላዮችና የአጭበርባሪ ዉጤቶችን አለመቀበል ብቻ አይደለም የዲያብሎስ አገልጋዮችንና የጥቅም ተጋሪ የሆኑ አስመሳይ አገልጋዮችን ጭምር ማጋለጥና በሕግም መጠየቅ ይጠበቅብናል:: ከእዉነተኛ አገልጋዮች ዉጭ የምንታዘዘዉን ማመንና መቀበል የለብንም:: እያንዳንዷን ድርጊት ሆነ ንግግር በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ መመርመር አለብን እንጂ በቃላትና በአፍ ማጣፈጥ መታለል የለብንም::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፤ አንዳንድ የሃይማኖት አገልጋይ መስለዉ «ይህ በሽታ መተት ተደርጎባችሁ ነዉ:: ይህን ያህል ከከፈላችሁ እኔ እፈታላችኋለዉ ወይንም አስፈታላችኋለዉ... ወዘተ» የሚሉ አሉ:: በዉኑ የእግዚአብሔር ጸጋ በገንዘብ ይለወጣል ወይ? እንዲሁም በዚህ መልኩ በሽታን ማዳን ይችላሉ ወይ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__፤ እጅግ ብዙዎቻችንን ከእዉቀት ማጣት የተነሳ እንስታለን፣ እናስታለን:: በትንቢተ ሆሴህ4:6እስከ8 እንደተገለጸዉ « ***ሕዝቤ እዉቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል***፤ አንተም እዉቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆን እጠላሃለሁ፤ የአምላክህን ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ:: እንደ ብዛታቸዉ መጠን ኃጢአት ሠሩብኝ፤ እኔም ክብራቸዉን ወደ ነዉር እለዉጣለሁ::»ይላል:: አስመሳይና አጭበርባሪ ሰዎች ቆብ ደፍተዉ፣ ካባ ለብሰዉ፣ ጥምጣም አድርገዉ፣ መስቀል ይዘዉ፣ የቤተክርስቲያን ሰዉ መስለዉ የዋሁን ምእመን ያሳሳታሉ፤ ያሰናክላሉ፣ ያጭበረብራሉ:: ምእመኑ ማወቅ ያለበትን እዉቀት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ አምላካችን «ሐሰተኞቹን፣ አታላዮቹን፣ አጭበርባሪዎቹን ከፍሬያቸዉ ታዉቋቸዋላችሁ» ብሎናልና «የእግዚአብሔርን ጸጋ በገንዘብ ልሸጥ» የሚል ሰዉ ገና ከንግግሩ ሐሰተኛ፣ አጭበርባሪ መሆኑን እናዉቅ ነበር:: እንዲሁም እንደማያድንና እንማይፈዉስ፣ የተተበተበም ካለ እንደማይፈታ እርግጠኛ እንሆን ነበር:: ነገር ግን ንግግሩን አጣፍጦ የሚመጣን ሰዉ አምነን እየተቀበልን እኛም ተሰናክለን ሰዎችንም እናሰናክላን::

እዚህ ላይ የዘልማድ አገልጋዮችን የዓመፃ አገልግሎት የሚያሳይ አንድ ገጠመኜን ልንገራችሁ አንድ እናት ልጇ በጠና ይታመምባታል በዘመናዊ ሕክምናዉ፣ በጠበሉም፣ በጠንቋዩም፣ በድግመተኛዉም ለማዳን ያልጣረችዉ ሙከራ የለም፡፡ በመጨረሻም ንስሐ አባቷን ታማክራለች፡፡ እሳቸዉም አንድ መጽሐፍ ገላጭ እንዳለ ይነግሯትና ያገናኟታል፡፡ አስፈላጊዉን ክፍያም ትፈጽማለች፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ገላጩም እንደ ጠንቋዩ፣ እንደ መተተኛዉ አታላይና አጭበርባሪ ስለነበረ ሊያድንላት አልቻለም፡፡ እኛ «ንስሐ አባት» ተብዬዉም መሞት አይቀርምና በድንገት ይሞታሉ፡፡ በመቶ ቤት ደሞዝተኛ የነበሩ ሲሆን በቤታቸዉ የተገኘዉ ኬት እንዳመጡት የማይታወቅ በብዙ አስራ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየን እኛ «ንስሐ አባት» ተብዬ በቤተክርስቲያን ተጠግተዉ አገልጋይ በመምሰል ዘመናቸዉን ሁሉ ገንዘብ በመስረቅም፣ በማታለልም ሲሰበስቡ የኖሩ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ የሚያሳዝነዉ ደግሞ ያ የዓመፃ ገንዘብ ለአንድ ነገር ሳያዉሉት መሄዳቸዉና በነፍሳቸዉ ደግሞ ለከፋዉ ቅጣት መዳረጋቸዉ ነዉ፡፡ እንኳን ምእመን ይቅርና አንዳንድ የስም «የሃይማኖት አባት» የሚባሉትም ለሰይጣን አገልግሎት ተሳታፊና ተባባሪ መሆናቸዉን ልናስተዉልና ልናዉቅ ይገባናል፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ አንዳንድ ምእመናን መስቀል ሲሳለሙ የተለያየ አካላቸዉን ለምሳሌ ጡታቸዉንና እምብርታቸዉን ጭምር በመስቀል እንዲተሻሸላቸዉ የሚፈልጉ አሉ፡፡ ይህ ድርጊት ፈተናን የሚያመጣ አይመስሎትም?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ በአገልጋዮች ሆነ በምእመናን ዘንድ ያለ ችግር የእምነት ችግር ነዉ፡፡ እምነት ከሌለን ደግሞ መላ አካላችንን ብንተሻሽ ፈዉስ ልናገኝ አንችልም፡፡ እምነት ካለን ደግም በግንባራችን መስቀሉን ተሳልመን ቀርቶ እንዲሁ እግዚአብሔር እንዲያድነን ብንጠይቀዉ ሊፈዉሰን ይችላል፡፡ ግንባራችንን ተሳለምን ማለት መላአካላችን ተሳልሟል ማለት ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት እያንዳንዱን አካላችንን እያስቆጠርን ማሳለም የለብንም፡፡ አሳላሚዉም ካለይሉኝታ በእምነት መላ አካላችን መሳለሙን ሊገልጹልን ይገባል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጸችዉ ያቺ 12 ዓመት ሙሉ ደም ሲፈሳት የነበረች ሴት «የጌታን ልብሱን ብቻ ከነካዉ እድናለዉ» ብላ በእምነት ስለነካችዉ ነዉ በመላ አኳላ የተሰራጨዉ በሽታዋ ወዲያ ሊፈወስ የቻለዉ፡፡

በዚሁ አጋጣሚ አንድ እህት የደረሰባትን ገጠመኝ ልንገራችሁ፤ ሰዉየዉ አንቱ የተባሉ በገዳሙ የተለየ ቦታ የተሰጣቸዉ ናቸዉ፡፡ ታዲያ ያቺ እህት ለጠበል ስትሄድ አባት ናቸዉ በማለት ከተዋወቀች በኋላ መነኩሴ በመሆናቸዉ አንዳች ሳትጠረጥር «ሰዉነትሽን ቅባቅዱስ ልቀባሽ» ብለዉ ልብሷን አስወልቀዉ ጡታንና ሁሉመናዋል ቀቧቧት፡፡ ከዚያ በኋላ ሌት ተቀን አባ ነበር ጥሪዋ፡፡ እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ወደ ልቧ እንድትመለስ አድርጎ ሕይወቷ ሊስተካከል ችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየን ከሥርዓትና አግባብ ካለዉ አቀራረብ ዉጭ ከማንም ጋር ማንም ሰዉ ቢሆን መቅረብ እንደሌለበት ነዉ፡፡ ስንቶች «አባት፣ መነኩሴ» ናቸዉ ብለዉ ቀርበዉ ብዙ ጉድ የተሰሩና ዲቃላቸዉን የታቀፉ አሉ፡፡ ስለዚህ በሥጋ የተገለጸ ሰዉ መልአክ አይደለምና የትኛዉም ብቃት ደረጃ ላይ ይድረስ እያንዳንዱ ግንኙነትና አቀራረብ በአግባቡና በሥርዓቱ ብቻ በገደብ መሆን አለበት፡፡

ሌላ ከዚህ ጋር የማዉቀዉን የአስመሳይ አገልጋዮች የዓመፃ ሕይወት አንዱን እገልጻለሁ። ይኸዉም «ሰባኪ» ተብየዉ አንደበት ያለዉና የተማረም ነዉ። በዚህ አንደበቱና እዉቀቱ በጳጳሳትና በሌሎች በቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ዘንድ ሞገስ ያለዉና ስብከት እንዲሰጥ በተለያየ መድረክ የሚጋበዝ ነዉ። ስብከቱን የሰማ እንኳን በተግባር ይፈጽመዋል አይደለም በሐሳቡ ያስበዋል ብሎ አያስብም፤ አንዳችም አይጠረጥርም። በስብከቱ የሚያዉቀዉ አንድ ወንድም በደንብ ይቀራረባሉ፤ ጓደኛም ይሆናሉ። አንድ ግቢ ጉን ለጎን ባለ ክፍል ዉስጥ ተከራይተዉ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ጓደኛዉ ለስራ ወደ መስክ ይወጣል። ሩቅ ስለሆነ ተመልሶ አልመጣም። ታዲያ ይህ «ሰባኪ» ተብየዉ ከጓደኛዉ ሚስት ጋር እንደ ወንድምና እህት ተቀራርበዉ ነበርና ባለቤቷ አለመኖሩን ሲያረጋግጥ ሌሊት ላይ በር በማንኳኳን ዝሙት ለመፈጸም ይጠይቃታል። እርሷ ግን እግዚአብሔርን የምትፈራና እንደ ቃሉ ሆና የተገኘች ስለነበረ መክራዉ ወደ ክፍሉ እንዲመለስ ታደርጋለች። በማግስቱ ስለ «ሰባኪዉ» ሕይወት የምታዉቃቸዉን ሰዎች ስትጠይቅ የለየለት ዘማዊ መሆኑንና ከሰራተኛ ጋር ጭምር ዝሙት የሚፈጽም፣ እዉነተኛ ሰባኪ መስሏቸዉ የሚቀርቡትን ሴቶች የሚደፍር ነዉረኛ መሆኑን ይነግሯታል። እርሷም እንደሌሎቹ ሰምታ ዝም አለች እንጂ እላይ ወዳሉት አባቶች ገበናዉን አልገለጠችም። ዝሙት የተፈጸመባቸዉና ሙከራ የተደረገባቸዉ እህቶች የዓመፃ ተግባሩን ማጋለጥና ከክህነቱም ማሻር ሲጠበቅባቸዉ በይሉኝታና «ቤተክርስቲያናችን ትሰደባለች፣ በከሃድያንና በመናፍቃን ዘንድ መዘባበቻ ትሆናለች» በማለት ዝም በማለታቸዉ፤ ይኸዉ እስከ ዛሬ ድረስ የዓመፃና የርኩሰት ተግባሩን እየፈጸመ፤ በእግዚአብሔር መድረክ ላይ ደግሞ እዉነተኛ አገልጋይ መስሎ ያታያል። ያ ብቻ አይደለም እዉነተኞችን የሚወነጅልና የሚያጥላላ፣ ከዛም ባለፈ የሚያሳድድ በአባቶች ዘንድ ተደማጭነትና ተቀባይነት ያለዉ ሰዉ ነዉ። የእዚህን ሰዉ ሕይወት የያዙ ብዙ አስመሳይ አገልጋዮች በእዉነተኛዉ ቤት በተለያየ ቦታ ዉስጥ ተሰግስገዉ አሉ። እግዚአብሔር ግን ታግሶ ታግሶ አንድ ቀን ከቤቱ እንደሚጠርጋቸዉና እንደሚያጸዳቸዉ በእምነት ዉስጥ ላለ ሰዉ ይታወቀዋል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) አስገድደዉን ኃጢአት ሊያስፈጽሙን ይችላሉ ወይ? እንዲሁም ራሳችንን እንድናጠፋ ሊያስደርጉን ይችላሉ ወይ? በጠበል ቦታ ሆነ በጸሎት አጋንንት ሲለፈልፉ «እንዲህ አድርግን አጋጨን፤ እንድህ አድርገን ገደልን፤ እንዲህ አድርገን አጣላን... ወዘተ» ይላሉ። በእርግጥ ሰይጣናት ማጋጨት ሆነ መግደል እንዲሁም ማጣላት ይችላሉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ መታወቅ ያለበት የርኩሳን መናፍስት ሆነ የእኛ የሰዎች ሥልጣን የተገደበና እንኳን ሌላዉን አስገድደን ጉዳት ማድረስ ቀርቶ በራሳችን ታብየንና ተመጻድቀን የማንፈልገዉን ላለመስራት፣ ላለመናገር፣ ላለማሰብ አንችልም። ሁሉን ማድረግ የሚቻለዉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ። በመሆኑም ርኩሳን መናፍስት መፈታተንና በአእምሯችን(በሕሊናችን) ኃጢአት እንድንፈጽም ሊናገሩን ይችላሉ እንጂ አስገድደዉ ማሰፈጸም አይችሉም። ያን ድምፃቸዉን ደግሞ ነፍሳችን የመስማት ብቃት አላትና «አይ ይህ ሐሳብ የእኔ አይደለም፣ የዲያብሎስ ነዉ አልፈጽምም፤» ማለት ትችላለች። በተቃራኒ ደግሞ የእነሱ ፈቃድ ፈጻሚ ሆና ያን የእነሱን ድምፅ ተከትላ ኃጢአትን መፈጸም ትችላለች። ነገር ግን በነጻ ሕሊናዉ ፈቅዳና ተመርታ የፈጸመችዉ ስለሆነ የምትጠየቀዉ ራሷ ነች እንጂ ሰይጣናት አይደሉም። የእነርሱን ድምፅ

ተቃዉማ «አልፈጽመዉም» ብትል ደግሞ በራሷ ነጻ ፈቃድና ዉሳኔ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ዋጋ ታገኛለች፣ ኃይልንም ትጎናጸፋለች። እንኳን ረቂቃኑ ሰይጣናት አይደለም ግዙፎቹ ሰዎች ኃጢአት እንድንፈጽም ሊፈታተኑን ይችላሉ። ነገር ግን በነጻ ሕሊናችን ተመርተን መፈጸም አለመፈጸም የእኛ ድርሻ ነዉ። ከፈጸምን እኛዉ ነን የምንጠየቅበት፤ ካልፈጸምን ደግሞ እኛዉ ነን የምንጠቀመዉ።

ሰዎች በችግር ኑሮ ዉስጥ ሆነዉ ሆነ ሀብትና ንብረት እያላቸዉ ራሳቸዉን የሚገሉት (የሚያጠፉት) በሕሊናቸዉ ተስፋ እንዲቆርጡና ሁሉን ነገር አጨልሞ የሚናገራቸዉን የዲያብሎስ ድምፅ ሰምተዉ ነዉ። ያን ድምፅ ቢቃወሙትና ያችን ወቅት ቢያሳልፉት ኖሮ ራሳቸዉን ነበር የምታዘቡት። «እንዴት እንዲህ አስባለሁ» በማለት ይጸጸቱበት ነበር። ነገር ግን እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ስለሚመላለሱ ያቺን ጊዜ የመጣባቸዉን ፈተና በትዕግስትና በጽናት ማሳለፍ ሲገባቸዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደማያገኙበት ቦታ በራሳቸዉ ነጻ ፈቃድና ወሳኔ ይሄዳሉ። በእግዚአብሔር የመግደል ሆነ የማዳን ሥልጣን ዉስጥ በመግባት በራሳቸዉ ላይ ሆነ በሌላዉ ላይ ማድረግ የሌለባቸዉን የኃጢአት ተግባር በመፈጸማቸዉ ራሳቸዉን ለከፋዉ ቅጣት ይዳርጋሉ።

ሰይጣናት የመግደል ሆነ በራሳቸዉ ሥልጣን መጉዳት የሚችሉ ቢሆን ኖሮ «ኃጢአት አልፈጽምም» እያለ የሚያስቸግራቸዉንና በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በመልካም ምግባር፣ በእዉነተኛ አምልኮ ፍዳቸዉን የሚያሳያቸዉን ሰዉ እንቅ እያረጉ በገደሉት ነበር። ነገር ግን እንኳን መግደል አይደለም ጉዳትና ፈተና ለማድረስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈቃድ እስካለገኙ ድረስ በማንም ላይ ማድረስ አይችሉም። በየጠበሉ ሆነ በየአብያተክርስቲያናኑ እንዲሁም በጸሎት ቦታ አጋንንት (ሰይጣናት) «እንዲህ አደረግን፣ እንዲህ አስደረግን» እያሉ የሚለፈልፉት ያንን ግለሰብ ባሳሰቡት መሰረት ፈቃደኛ ሆኖ ፈቃዳቸዉን በመፈጸሙ ምክንያት ነዉ እንጂ፤ አለመቀበል ሆነ አለመፈጸም ሙሉ ነጻነት አለዉ። «የተለያየ አደጋና ግጭት ፈጸምን፣ አስፈጸምን» የሚሉትም ለምሳሌ መኪና በምናሽከረክርበት ወቅት ሐሳባችንን በመስረቅ ከሌላ ሐሳቡን ከሰረቁበት ሰዉ ጋር እንድንጋጫ በሚያደርጉን ጊዜ እንዲሁም በሌላ ሰዉ ሆነ ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ ያ የክፋት ሐሳባቸዉ ስለተሳካላቸዉ ራሳቸዉ እንደአስደረጉ ስለሚቆጥሩ ነዉ እንጂ በእያንዳንዱ ድርጊት የእግዚአብሔር ቁጥጥርና ጥበቃ አለ። ልክ እኛ ይህን የእግዚአብሔር ቁጥጥራ ጥበቃ ማስተዋል እንደተሳነን እንሱም ደግሞ ከእኛ በባሰ የእግዚአብሔር ጸጋ የተለያቸዉ ስለሆነ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ለዐይን ቅጽበት ያህል እንኳ እንደማይለይ አያስተዉሉም፤ አያዉቁም። የክፋት ሐሳባቸዉ ሲሳካላቸዉ በራሳቸዉ ሥልጣን የፈጸሙት ነዉ የሚመስላቸዉ። እዉነታዉ ግን እግዚአብሔር ሳያዉቀዉና ሳይፈቅዳ አንዳች ነገር አይፈጸምም። እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሥልጣኑ ሁሉን መሻርና እንዳይከናወን ማድረግ ይችላል። ከዚህ አንጻር እኛ ሰዎች ሆነ ሰይጣናት በሚከናወነዉ ድርጊት በራሳችን ሥልጣን የፈጸምን ፣ ያስፈጸምን ይመስለናል እንጂ እግዚአብሔር አዉቆትና ፈቅዶት ነዉ የተሳካዉና የተከናወነዉ።

በመሆኑም ከእኛ ከአዳምና ሔዋን ዘሮች የሚጠበቀዉ ተሰፋችንን በእግዚአብሔር ላይ አድርገን እንደ ፈቃዱ መኖርና ከእኛ የሚጠበቀዉን ሁሉ ማድረግ ነዉ እንጂ በራሳችን መጠበብ ሆነ መጨነቅ የምንፈጥረዉ ሆነ የምንፈጽመዉ እንዲሁም የምናስፈጥረዉ ሆነ የምናስፈጽመዉ ነገር የለም። ቢበዛ

የምንችለዉ መፈታተን ነዉ። መጉዳት ሆነ ማጥቃት የምንችለዉ እግዚአብሔር ከፈቀደ ብቻ ነዉ። በተቀረ ኃይላችን የተገደበና የተወሰነ ነዉ። እግዚአብሔር በዐይን ቅጽበት ዉስጥ የፈለገዉን ማድረግ ስለሚችል ሐሳባችንን ሆነ ተግባራችንን ከንቱ ማድረግ ይችላል።

እዚህ ላይ አንድ የራሴን ተሞክሮ ልንገራችሁ፤ እግዚአብሔር በራሴ ሥልጣን የምፈልገዉን ሆነ የማልፈልገዉን ማድረግ እንደማልችል በመዉደቅ በመነሳት አስተምሮኛል። በዚህ ምክንያት በጋብቻዬ ወቅት ለእግዚአብሔር ያቀረብኩት የመሃይምነት ጸሎቴ «እግዚአብሔር ሆይ ከጋብቻ በኋላ ዝሙት እፈጽም አልፈጽም እንደሆነ አንተ ነህ የምታዉቀዉ፤ ነገር ገን ዝሙት የምፈጽም ከሆነ ከወደድከኝ ከመፈጸሜ በፊት ገለኽኝ ለመንግሥት አብቃኝ፤ ካልወደድከኝ ደግሞ ከመፈጸሜ በፊት ገለኽኝ በሲኦል አስገባኝ፤ ፍርዱ ይቀልልኛል» በማለት ነበር። ምክንያቱም እንኳን በተግባርና በንግግር አይደለም በሐሳብ እንኳ እንዳላስበዉ ለማድረግ ነዉ። እግዚአብሔር ይመስገን ይኸዉ የመሃይምነቴን ጸሎት ሰምቶኝ እስከ አሁን ድረስ በሐሳብ እንኳ እንዳላስበዉና እንዳልመኘዉ አጽንቶኛል። ሌላዉ የመሃይማነቴ ጸሎት ደግሞ ሰይጣናት ራሴን በማመጻደቅ እንዳያስታብዩኝ በጸሎቴ ወቅት በጸሎት መጻሕፍት ዉስጥ ያሉኝን ለእኛ በሚገባን መልኩ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የተሳሉትን የቅዱሳን ሥዕል «እግዚአብሔር ሆይ የቅዱሳንህ እግር ለመሳም አብቃኝ» እያልኩ ነዉ በሥዕላቸዉ ያለዉን እግራቸዉን የምስመዉ። በዚህ ምክንያት ይኸዉ ራሴን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርጌ እንደ ተራነቴና ወራዳነቴ እኖራለሁ። ሰይጣናትም ክፍተት አግኝተዉ እስከ አሁን ድረስ ከሕይወት መስመር አላሶጡኝም፤ አላስታበዩኝም። ወደፊትም እንደማያስታብዩኝና ራሴንም እንደማላመጻድቅ በእግዚአብሔር እተማመናለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ ከሁለት ዓመት በፊት ከነሐሴ ፩፲፪ (ከ1/12/2002) ዓ.ም ፍልሰታ ጾም በፊት ስለ ምድራዊ ብልጽግና ብዬ ለሕሊናዬና ለአምላኬ ባለመታመን በማይገባ ሀብት ማግኛ ተግባር እንዳልሰለፍ አድሎና በደል ለሚፈጽመዉ መንግሥት ሆነ ለሌላ አካል ጭምር ታማኝ ሆኜ ለመስራት ወስኜ እንደ ዝሙቱ «እግዚአብሔር ሆይ በማንኛዉም ኃላፊነት ስራ ላይ እያለሁ ምንም ችግር ቢያጋጥመኝ አንተ የማትፈቅደዉን ተግባር እንዳልፈጽም አድርገኝ። የምፈጽም ከሆነ ደግሞ አንተ ታዉቃለህና ከወደድከኝ ከመፈጸሜ በፊት አስቀድመህ ገለኽኝ ለመንግሥት አብቃኝ። ካልወደድከኝ ደግሞ ፍርዱ እንዲቀልልኝ ከመፈጸሜ በፊት አስቀድመህ ገለኽኝ የገሃነመ እሳት ፍርድ ፍረድብኝ» በማለት በመጸለዬ ይኸዉም እስከ አሁን ድረስ አጽንቶኝ ለሕሊናዬና ለአምላኬ ታምኜ እገኛለሁ። ከምድራዊ ሕይወት እስከምለይ ድረስ እንደሚያጸናኝ እምነቴ ሙሉ ነዉ። ምክንያቱም እንዲህ ብዬ እየለመንኩት ለዛያ ለክፉ ጠላት ዲያብሎስ ፈተና አሳልፎ እንደማይሰጠኝ እተማመንበታለሁና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን በበዓለት፣ በሰንበታት ምንም ዓይነት ስራ መሰራት የለበትም ይላሉ። ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ ከበዓላትና ከሰንበት አከባባር በፊት መታወቅ ያለበት ነገር በዓላት ሆኑ ሰንበት ለሰዉ ልጆች የተፈጠሩ ናቸዉ እንጂ የሰዉ ልጆች ለእነሱ የተፈጠሩ

አይደለም። ለዚህ ነዉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ ዘመን ደቀመዛሙርቱ በሰንበት በመንገድ ሲያልፉ ርቧቸዉ እሸት ቀጥፈዉ በሚበሉበት ወቅት፤ በባዶ ሕይወት «የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት እናስጠብቃለን፣ እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች ነን» የሚሉት ጸሐፍት ፈሪሳዉያን በድርጊታቸዉ ከፍተኛ ተቃዉሙ ነበር ያሰሙት። ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ እንዳፈረሱና ኃጢአተኛ አድርገዉ ነበር የቆጠሯቸዉ። ነገር ግን የሰንበት ጌታዋና ለሰዉ ልጆች እረፍት ያዘጋጀት አምላክ አጠገባቸዉ ነበርና ተቃዉሟቸዉንና አስተሳሰባቸዉን እንዲሁም ሕይወታቸዉን አልተቀበለዉም። ይልቁኑ ከመስዋዕት ይልቅ በቅድሚያ ቅን ሐሳብንና መልካም ሕይወት እንደሚመርጥ ነዉ የተናገራቸዉ።

አሁንም ታዲያ በጸሐፍት ፈሪሳዊ ሕይወት የሚመላለሱ የስም አገልጋይና አማኞች አሉ። አንዳንዶቹ ባለማወቅ፣ በቅንነት ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ነጥብ የማትሞላዉ እዉቀታቸዉ ጣዖት ስለሆነችባቸዉ ከእነሱ እዉቀትና አስተሳሰብ ዉጭ ያለዉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ እንደጣሰ አድርገዉ የሚቆጥሩ ናቸዉ። አማኙ ግን የዘልማድ አገልጋዮች የሚሉትን እግዚአብሔርን በመፍራት ስለሚፈጽም ለመፈረድ ይከብዳል። ምክንያቱም «የትኛዉ ነዉ ለጽድቅና ኩነኔ የሚያበቃዉ፣ የትኛዉ ነዉ ሥርዓት፣ የትኛዉ ነዉ ልማድ፣ የትኛዉ ነዉ ወግ፣ የትኛዉ ነዉ ሕግ... ወዘተ» የሚለዉን ጠንቅቆ ስለማይለይና በአስመሳይና በልማድ አገልጋዮች «ይህን አድርጉ፣ ይህን አታድርጉ»ሲባሉ ከቅንነታቸዉና እግዚአብሔርን ከመፍራታቸዉ የተነሳ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመቁጠር ተግባራዊ ስለሚያደርጉ ነዉ። ይህን በማድረጋቸዉ ደግሞ የሚጎዱ ሳይሆን ተጠቃሚ ናቸዉ። በራሳቸዉ ላይ ሸክም ከማብዛትና ትብታብ ከመተብተብ በስተቀር የሚጎዱበት ነገር የለም። ነገር ግን አስመሳይና የልማድ አገልጋዮች እነሱ ይናገሩታል እንጂ አንዱንም አይጠብቁም፤ አይፈጽሙም። በዚህም በማስመሰል ሕይወታቸዉ ሆነ እንደተናገሩት ባለመኖራቸዉ ይጠየቁበታል፤ ዋጋም ይከፍሉበታል።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስገባ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት የተለያዩ በዓላትና ሰንበት አለ። እነዚህ ሁሉ ለሰዉ ልጆች የተዘጋጁ ናቸዉ እንጂ የሰዉ ልጆች ለእነሱ የተፈጠሩ አይደለም። በዚሁ መሰረት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮት የሚፈጸምባቸዉና የነፍስ ግብይት የሚካሄድባቸዉ ናቸዉ። ለምሳሌ ብንወስድ መስከረም አንድ የዘመን መለወጫና እዉነታኛዉ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ነዉ። በዚህም ምክንያት ዋና በዓል ስለሆነ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በዓሉ በድምቀት ይከበራል። እንዲሁም መስከረም አሥራ ሰባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በዓል የሚታሰብበት ስለሆነ እንዲሁ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በዓሉ በድምቀት ይከበራል። ጥር አሥራ አንድ የጌታችን ጥምቀት የሚታሰብበት በዓል ስለሆነ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በዓሉ በድምቀት ይከበራል። በየዓመቱ የጌታችን ስቅለትና ትንሳኤ በሚሆንት ቀን የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በዓሉ በድምቀት ይከበራል። ከዚህ በተጨማሪ የሰንበት ጌታ የሆነዉ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ በብሉይ ዘመን ይቀርብ የነበረዉን የእንስሳት መስዋዕት አስቀርቶ በአዲስ ኪዳን መስዋዕት በቅዱስ ሥጋዉና በደሙ እንደተካዉ ሁሉ የብሉይ ዘመን ሰንበት የነበረችዉን ቀዳሚት በአዲስ ዘመን «የጌታ

ቀን» በተባለችዉ ሳይሽራት በእሁድ ቀን ተክቷታል። በመሆኑም የአዲስ ዘመን ሰንበት በሆነችዉ እሁድ እለት የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በዓሉ በመንፈሳዊ አገልግሎትና ትምህርት ይከበራል። እዚህ ላይ ታዲያ በነዚህ በዓላት እለት የሆስፒታል፣ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ የስልክ ፣ የመብራት ኃይል፣ የትራንስፓርት፣ የመድኃኒት ቤቶች ፣ የጥበቃ፣... ወዘተ መስሪያ ቤቶች ተረኛ የሆኑ ሰራተኞች የሚጠበቅባቸዉን የስራ ድርሻ ይወጣሉ። ይህን በማድረጋቸዉ ደግሞ በዓልን እንደሻሩና እንዳላከበሩ አይቆጠርም። ምክንያቱም የሚጠበቅባቸዉን ግዳጅ ነዉና የተወጡት። ስለዚህ በበዓላትን ሆነ በሰንበትን አክብሩ ሲባል እጅና እግራችሁን አጣጥፋችሁ ተቀመጡ፣ አትሂዱ፣ አታገልግሉ፣ አትማሩ፣ አታንቡ፣ አትጻፉ፣ አትብሉ፣ አትጠጡ፣ የሚጠበቅባችሁን ግዴታ አትወጡ ማለት ሳይሆን በዚያን እለት ነፍሳችሁ በተለየ ሁኔታ የምታርፍበትን ለሕያውነት ሕይወት የሚሆናትን መብል የምትበላበትና የምትጠጣበት፣ የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶች የምትማረበት፣ የተለየ መንፈሳዊ አገልግሎት የምትሰጥበት፣ ለፈጣሪዋና ለአምላኳ ራሷን አስገዝታና ሰዉታ ምስጋናና ጸሎት በተለየ ሁኔታ የምታቀርብበት፣ ባጠቃላይ የሥጋዋን ሐሳብና ተግባር ትታ በነፍሷ ሐሳብና ተግባር የምትመላለስበት ዕለት ነዉ። ነፍስ ስራ ፈታ የምትቀመጥና የምትባዝን ከሆነ ለተለያዩ ሰይጣናት ፈተና የምትጋለጥና የምትቀጠቀጥ ነዉ የምትሆነዉ። በመሆኑም በሥጋ ስራ ስትጠመድ የሰይጣናትን ፈተናና ጥቃት እንደማታስተዉል ሁሉ በነፍስ ስራ ስትጠመድ ደቅሞ ሰይጣናትን የምታቃጥልና የምትቀጠቅጥ ስለምትሆን ከእግዚአብሔር የተለየ ኃይልን(ጸጋን) ትጎናጸፋለች።

ታዲያ ከላይ ባየነዉ መሰረት በዓላትና ሰንበትን አግባብ ባለዉ መንገድ ስናከብር ተጠቃሚዎቹ እኛ ነን እንጂ ለእግዚአብሔር አንዳች የምንጨምርለት ሆነ የምንቀንስበት ነገር የለም። እንደ አሕዛብ እግዚአብሔርን እንደማያመልኩት መደዴ ኑሮ የምንኖርና ከዓመት እስከ ዓመት ቀን ከሌሊት በሥጋ ስራ ብንመላለስ ነፍሳችን እንደባከነችና እንደተቅበዘበዘች ከምድሩም ከሰማዩም ሳትሆን ወደ ሁሉተኛዉ ቦታ፣ የንስሐ እድል ወደማታገኝበት፣ የባሰ የጉስቁልናና የመከራ ሕይወት ወዳለበት ነዉ የምትሄደዉ እንጂ ከዓመት እስከ ዓመት፣ ቀን ከሌሊት ለሥጋ ስራ ስለተሰለፈች አስተያየት የሚደረግላት አይደለም። ምናልባት በሥጋዊ ኖሮዋ የተሟላና የተደራጀ ሀብትና ንብረት ሊኖራት ይችላል። ነገር ግን ነፍስ ከሥጋዋ ስትለይ ያ ሀብትና ንብረት ለነፍሷ አንዳች የሚጠቅመዉ ነገር የለም። በመሆኑም በሥጋም በነፍስም ለመጠቀም እያንዳንዳችን ለሥጋችን እንደምናስብና እንደምንተጋ ሁሉ ለነፍሳችንም ልናስብና ልንተጋ ይገባል ማለት ነዉ።

ሌላዉ እዚህ ላይ እንደ ዐበይት በዓል ሊከበር ይገበዋል የምላቸዉ እለታት አሉ። እነሱም የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሞቷ፣ ትንሳኤዋ፣ ዕርገቷ የሚታሰብበት ነሐሴ አስራ ስድስት ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ በቅዱሱ ኪዳን የእዉቀትና የምስጢር መገለጫ መሰረት ምንም እንኳን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እዉነተኛ ልደቷ መስከረም አንድ ቢሆንም መስከረም አንድ ተደራራቢ በዓል ያለበት በመሆኑ በዕለቱ ከመታሰቡ በተጨማሪ ግንቦት አንድ በዋና በዓልነት ቢከበር የሚል ነዉ። ምክንያቱም ከዚህ በፊት መስከረም ሁለት በኢትዮጵያ ምድር ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ለመፈጸምና ለማስፈጸም የታወጀበት ቀን እንደ ዋና በዓል ስናከብር የቆየን ሲሆን፤ አሁን ደግሞ ዓመፃዉን፣ ክህደቱን፣ ርኩሰቱን የበለጠ ለመፈጸምና ለማስፈጸም አዋጅ የተነገረበትን ግንቦት

ሃያ እናከብር የለም ወይ? ታዲያ በነዚህ ለዓመፃ ተግባር በታወጁበት ዕለት ምትክ የኢትዮጵያን ትንሣኤ እጅግ በቅርቡ በምታመጣዉና በምታስመጣዉ በእመቤታችን መታሰቢያ እለት በአዋጅ በዋና በዓልነት ብናከብረዉ ያንሰናል እንጂ አይበዛብንም።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ ከላይ እንደገለጹልን አግባብነት ያለዉ በዓል እንዴት እንደሚከበር ተረድተናል። ነገር ግን በአንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን ዘንድ እስከ አሁን ድረስ «አርብ የተወቀጠ ቡና ካልሆነ በስተቀር በእለተ ሰንበት የተወቀጠ ቡና አልተጠጣም» የሚሉ አሉ። እንዲሁም «ዛሬ ልደታ ናት፣ ባሕታ ናት፣ አቡዬ ናቸዉ፣ ኢየሱስ ነዉ፣ ሥላሴ ናቸዉ፣ ኪሮስ ናቸዉ፣ ሐና ናት፣ ያሬድ ነዉ፣ ሚካኤል ነዉ፣ እግዚአብሔር አብ ነዉ፣ አረጋዊ ናቸዉ፣ ገብረክርስቶስ ነዉ፣ ኪዳነምሕረት ናት፣ ስጢፋኖስ ነዉ፣ ገብርኤል ነዉ፣ ማርያም ናት፣ ዑራኤል ነዉ፣ ጊዮርጎስ ነዉ፣ ተክለሃይማኖት ናቸዉ፣ መርቆርዮስ ነዉ፣ ኢየሱስ ሞዐ ናቸዉ፣ ሀብተማርያም ናቸዉ፣ መድኃኔዓለም ነዉ፣ አማኑኤል ነዉ፣ ባለወልድ ነዉ፣ ዮሐንስ ነዉ፣ማርቆስ ነዉ... ወዘተ» በማለት ስራም አልሰራም አላሰራም የሚሉ አሉ። ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል።

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በዓላት የተዘጋጁልን ስንፍና እንድንፈጽምና እንድናስፋፋ አይደለም። አባቶቻችን እያንዳንዱን ቀን በእግዚአብሔር፣ በእመቤታችን ፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች የሰየሙልን እንድናስባቸዉና የበረከታቸዉ ተሳታፊ እንድንሆን ነዉ እንጂ እጅና እግራችንን አጣጥፈን እንድንቀመጥ አይደለም። በአጥቢያችን ባለዉ የቅዱሱ ወይንም የቅድስቷ ወራዊ በዓል በሚሆንበት ዕለት በተለየ ሁኔታ በጸሎትና በምስጋና እንድናስባቸዉ፣ እንዲሁም ዓመታዊ በዓል በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ በተለየ ሁኔታ በድምቀት እንድናከብራቸዉና እንድናሰባቸዉ ነዉ እንጂ አንዳች ስራ እንዳንሰራባቸዉ አይደለም። አንዳንድ ምእመናንም «በሰንበት የተወቀጠ ቡና አልጠጣም» የሚሉት የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ እንደጣሱ የሚቆጠርባቸዉ ስለሚስላቸዉ እግዚአብሔርን በመፍራት ነዉ እንጂ አስቀድሞ የዘልማድ መምህር ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የሚያዉቅና የሚኖርበት መምህር አግኝተዉ ቢሆን ኖሮ የትኛዉ ተግባር እንደሚያስኮንንና እንደሚያጸድቅ ስለሚለዩ ከዘልማድ ሕይወት ይወጡ ነበር። አሁን ያለዉ ትዉልድ ግን ከዘልማድ ሕይወት ራሱን ሊለይና አምላኩን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ሊያመልክ እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ቃል ብቻ ሊኖር ይገባዋል። በዘልማድ ሕይወት ዉስጥ ያሉትን ደግሞ በትህትናና በፍቅር ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ማምጣት ይጠበቅበታል።

እዚህ ላይ አንድ ገጠመኜን እገልጽላችኋለሁ፤ አንድ የገጠር ቤተክርስቲያን አገልጋይ ተሟልቶላት አገልግሎት የሚሰጠዉ በዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ ነበር። በዚህም ምክንያት በዙሪያዉ ያሉ አማኞች ልጆቻቸዉን ክርስትና የሚያስነሱት በዓመት አንዴ ወይንም ሁለቴ በሚቀደስበት ጊዜ ነበር። በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ እድሜያቸዉ ከፍ ካለ በኋላ ክርስትና የሚነሱ አሉ። ታዲያ አንድ ቀን በዘልማድ የሚያገለግሉት አገልጋይ በዓመታዉ በዓል ላይ ተገኝተዉ፣ እንኳን ሥርዓት እምነቱን በደንብ የማያዉቀዉ ምእመን ልጁን ክርስትና ለማስነሳት ሲገባ ልጁ ጠጉሩን አልተላጨም ነበርና «አካኪ ዘራፍ እንዴት ከነጠጉረ ከእግዚአብሔር በጥምቀት ልጅነት ያገኛል?» በማለት

ሲከራከሩ፤ ለነፍስ የሚቆረቆሩ ሌላዉ አገልጋይ «በስንት ጊዜ ተሳክቶላቸዉ ፡-ወላጆቻችን ያወረሱን እምነት ነዉ በማለት ልጃቸዉን ክርስትና ለማስነሳትና የአማኙን ቁጥር በአንድ ለመጨመር የመጡትን በፍቅርና በደስታ መቀበል ሲገባ እንደ ሕግና ትእዛዝ አፍራሺ ቆጥረን ስለ ጠጉር መላጨት አለመላጨት ብለን ክርስትና አናነሳም ማለት ይገባል ወይ? አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን ይህን ነዉ ወይ? ከእግዚአብሔር ልጅነት ማስገኘት ይበልጣል ወይስ የሰዉ ሥርዓት ይበልጣል?» በማለት ሲናገሯቸዉ፤ እኛ አገልጋይ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ያ ልጅ ሊጠመቅና ሊቆርብ ችሏል፡፡ ብዙዎቻችን ለእግዚአብሐር ሕግና ትእዛዝ አንዳች ቦታ ሳንሰጥ ለሰዉ ሥርዓት ግን ከእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ በላይ ነዉ ቦታ ሰተን ጥብቅና የምንቆመዉ፡፡

ሌላዉ ማወቅ ያለብን እመቤታችንን ሆነ ቅዱሳን መላእክትን እንዲሁም ጻድቃንን መቃወምና መናቅ እንዲሁም ማጥላላት ማለት በተዝዋዋሪ እግዚአብሔርን መቃወም፣ መናቅና፣ እንዲሁም ማጥላላት ማለት ነዉ፡፡ ምክንያቱም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልትፈቀር፣ ልትከበር፣ ለትመሰገን፣ ለትገን የቻላችሁ በመጀመሪያ ራሷን ብቃት ደረጃ ላይ አድርሳ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን በመብቋቷና ቅዱስ ሥጋዋንና ክቡር ደሟን እግዚአብሔር ነስቶትና ተዋሕዶት ስለተገለጸበትና ለሰዉ ዘሮች ሁሉ ለሕያዉነት ሕይወት እንዲበቁ እርሱ አዳኛችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ሰዉቶ እንድንበላዉና እንድንጠጣዉ ስላደረገን የመዳኛ ምክንያታችን ስለሆነች ነዉ፡፡ ሁለተኛ በአዳምና ሔዋን ዓመፃ ምክንያት ጸጋችን ተገፎና ተዋርደን እዉነተኛ አባትና እናት አተን ስንኖር እግዚአብሔር በእርሷ ሥጋ በመገለጽ እርሱ በአዳም ምትክ አባት ሲሆነን፤ እርሷ ደግሞ በሔዋን ምትክ እናት ሆና ስለተሰጠችን ነዉ፡፡ ሦስተኛ ደግሞ እርሷ በሰማያት ገናና ተመስግና መኖር ስትችል በእኛ አደራ ልጆቿ ምክንያት ኀዘንተኛ መሆንን በመምረጧና ሁል ጊዜ ለእኛ ምሕረትን የምትለምን ዋስ ጠበቃችን የሕይወታችን ምስጢር ቁልፍ ስለሆነች ነዉ፡፡

ቅዱሳንም መላእክት ሆኑ ቅዱሳን ነፍሳት ሊከብሩና ሊመሰገኑ የቻሉት የእግዚአብሔር ባላሟሎችና ወዳጆች ስለሆኑ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸማቸዉና በማስፈጸማቸዉ ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስና ክብር ስላገኙ ነዉ፡፡ በመሆኑም የእመቤታችን ሆነ የቅዱሳን መከበር ሆነ መመስገን እንዲሁም መግነን በተዝዋዋሪ የእነርሱ አምላክና ፈጣሪ የጌታቸዉ መከበር፣ መመስገን፣ መግነን ነዉ፡፡ በተቃራኒ በእነርሱ ላይ በጥላቻና በመናቅ ላይ መሰለፍ ማለት እግዚአብሔርን መጥላትና መናቅ ነዉ፡፡ አንድነታችን ከቅዱሳን ጋር ሲሆን ብቻ ነዉ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት የሚኖረን፡፡ ከቅዱሳን ጋር አንድነት ከሌለን ከእግዚአብሔር ጋርም አንዳች አንድነት የለንም፤ እነሱ በሚኖሩበት በሰማያትና በገነት ዉስጥም የመግባትና ከእነርሱ ጋር በኅብረት እግዚአብሔርን የማመስገን እድልና ብቃት እንዲሁም ክብረ ሕሊና(ሞራል) የለንም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ እጅግ ጥቂት አገልጋዮችና አማኞች በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ዉስጥ በጫማ መሄድ እንደ ሕግና ሥርዓት አፍራሽነት የሚቆጥሩ አሉ፡፡ ለዚህ ምን ምላሽ አሎት?

*__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__*: በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችንንና ቤተክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት መሰረት በቤተክርስቲያን ዉስጥ ነዉ ጫማ አድርጎ መግባት ክልክልነት ያለዉ እንጂ በቅጽር ግቢ ዉስጥ አይደለም:: በድፍረት ጫማዉን አድርጎ ቤተክርስቲያን ዉስጥ የሚገባ እንደ ዓመፀኛ የሚቆጠር ሲሆን በቅጽር ግብ ዉስጥ በጫማዉ የሚሄድ እንደ ሕግ አፍራሽና ሥርዓት ጣሽ አይቆጠርም:: ሌላዉ ግን ሰዉ በፈቃዱ የትሩፋት ስራ ሊሰራ ይችላል:: ይኸዉም «በዚህ የተለየና የተቀደሰ ስፍራ ከነጫማዬ አልገባም» ማለት የሚችል ሲሆን፤ ሌላዉን ግን መኮነንና እንደ ሕግና ሥርዓት አፍራሽ መመልከት የለበትም:: እንኳን የቅድስት ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ አይደለም «ቅድስት ኢትዮጵያ ትንሣኤዋ ሳይመጣ በእግሬ አረግጣትም» በማለት በባዶ እግራቸዉ የሚሄዱ ሰዎች አሉ:: ይህ የራሳቸዉ ቃል ኪዳንና የትሩፈት ስራ ነዉ እንጂ ሌሎች እንዲያደርጉት የታዘዘ አይደለም::

*__ጠያቂዉ አገልጋይ__*: አንዳንድ «ለእግዚአብሔር ቃል ነዉ የምንቆረቆረዉ፣ ትክክለኛ ያልሆነን ተግባር እንቃወማለን» የሚሉ ሰዎች፤ «እነዚህ የኦርቶዶክስ አገልጋዮችና አማኞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉጭ የተለያዩ መልካመልክ እያዘጋጁ ባዕድ አምልኮ ይፈጽማሉ» በማለት ትችትና ሃይማኖታችንና ቤተክስቲያናችንን የማጥላላት ዘመቻ ያደርጋሉ:: በእዉኑ መልክዐ መልክ ከእግዚአብሔር እዉነታ ዉጭ ነዉ ወይ? እግዚአብሔርን ሆነ ቅዱሳንን በሰዉ መልክ መግለጹ አግባብነት አለዉ ወይ?

*__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__*: አንድ መታወቅ ያለበት እዉነት እኛ እግዚአብሔርን የምናዉቀዉ እንደ እግዚአብሔርነቱ ባሕርይ አይደለም:: እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ባሕርይ ሊያዉቀዉ ሆነ ሊመለከተዉ የሚችል ፍጡር የለም:: ለእያንዳንዱ ሕያዉ ፍጡር በሚገባዉ መልኩ ነዉ የሚገለጸዉና የሚታወቀዉ:: እኛ በምሕረት ዘመን ዉስጥ ያለን ሰዎች በብሉይ ዘመን ካሉ ሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን በተለየ ሁኔታ እናዉቀዋለን:: ይኸዉም እንደ እኛ ሰዎች፤ ሰዉ ሆኖ በምድር ላይ በመገለጹ ነዉ:: ከእመቤታች ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ የተገለጸዉ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነዉ:: መልኩን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ገልጾላቸዉና አሳስቧቸዉ እኛ በምነረዳዉና በሚገባን መልኩ በሥዕል አስቀምጠዉልና:: በዚያም ረቂቁንና ከእኛ ለዐይን ቅጽበት ያህል እንኳ የማይለየዉን አምላክ አቅርበን እንመለከተዋን:: በዚሁ ሊገባን በሚችለዉ መልክ ምስጋና እናቀርብለታለን:: እመቤታችን ሆነች ቅዱሳንም በሰማያትና በገነት ዉስጥ ያሉ ሁሉ በረቂቅ አካል በምሳሌያዊ ባሕርይ ተገልጸዉ ያሉ ቢሆኑም፤ እኛ የምናዉቃቸዉ እንደ ረቂቅነታቸዉ ሳይሆን ቅዱሳን መላእክትን ለሰዉ ልጆች በሚገባቸዉና በሚረዱበት መልኩ በተገለጹበት መልካቸዉ፣ እንዲሁም ቅዱሳን ሰዎችን በምድር በሥጋ በተገለጹበት ወቅት ባለቸዉ መልክ ነዉ:: ይህን መልካቸዉም በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነትና አሳሳቢነት በሚገባንና በምንረዳዉ መልክ ተሥለዉልን ለጸሎትን ለምስጋና እየተጠቀምንባቸዉ ነዉ:: የተለያየ መልክዐ መልክ ተደርሶላቸዉ በምልጃቸዉ እንዳይለዩንና አንድነታችንና ኅብረታችን ከእነርሱ ጋር መሆኑን የምንገልጽበት እንዲሁም በጸሎትና በምስጋና የምናስብበት ነዉ:: ለተቃዉሞና ለትችት የተጋለጡ ወገኖቻችንም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ በማሰብና በመመራመር ነዉ እንጂ፤ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ ለዚህ ዓመፃ ሐሳብና የማጥላላት ተግባር ላይ አይሰለፉም ነበር:: ወደ ልባቸዉ

ከተመለሱና መሪያቸዉን መንፈስ ቅዱስ ካደረጉ የእመቤታችንን ሆነ የቅዱሳንን ክብርና ፍቅር ያስተዉላሉ የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆነች ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ጻድቃን ሊከበሩና ሊፈቀሩ የቻሉት ለእግዚአብሔር እዉነት ስለቆሙና በእግዚአብሔር የማዳን አገልግሎት ላይ ስለተሰማሩ፣ በሕይወት ዘመናቸዉም እግዚአብሔርን አስደስተዉ በመገኘታቸዉ ነዉና። በተቃራኒዉ ክብር ሆነ ቦታ የሌላቸዉ ደግሞ በእግዚአብሔር እዉነት በተቃራኒ የተሰለፉ የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ የሆኑ ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት(ዓመፀኛ ሰዎች) ናቸዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ አገልጋዮችና አማኞች «የጽጌን ጾም የሚጾም እመቤታችን ድንግል ማርያምን የሚወድ ነዉ» ይላሉ። ይህን ጾም የማይጾም እመቤታችንን አይወድም ማለት ነዉን? እንዲሁም በአንዳንድ ቦታ እንደ አዋጅ ጾም ተቆጥሮ ከቅዳሜና ከእሁድ ቀናት ዉጭ ቅዳሴ ከሰዓት በኋላ ነዉ የሚቀደሰዉ፤ ይህስ ትክክለኛ ሥርዓት ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ሁላችንም ማወቅ ያለብን ማንም ሰዉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ሆኖ የበለጠ ሲጾም የበለጠዉን ኃይል ወይንም ሰይጣናትን ድል የሚያደርገበት ጸጋ ይላበሳል። ስለዚህ ከዓመት ዓመት ቢጾም ነፍሱ ትጠቀማለች እንጂ አትጎዳም። ነገር ግን ማንም ስለጾመ ብቻ «የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ወዳጅ ነዉ፣ ማንም የማይጾም የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ወዳጅ አይደለም» ማለት ግን አንችልም። ስለዚህ የጽጌን ጾም የማይጾም «የእመቤታችን ወዳጅ አይደለም» ማለት አይቻልም። እንዲሁም የሚጾመዉ «እኔ የእመቤታችን ወዳጅ ነኝ» ብሎ ራሱን ማመጻደቅ የለበትም። እንኳን የፈቃድ ጾም የሆነችዉን የጽጌ ጾም ቀርቶ በአዋጅ የታወጁትን የገናና የሰኔን ጾም የማይጾሙ ብዙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች አሉ። ይህም በአራት ምክንያት ሊሆን ይችላል። አንደኛዉ የጾምን ጥቅም ባለማወቅ፣ ሁለተኛዉ ቀደም ባለና በሰዎች ዘንድ በነበረ የተሳሳተ አሳተሳሰብና እዉቀት ይኸዉም «የገናና የሰኔ ጾም የቄሶች ነዉ» በማለት ሲሆን፤ ሦስተኛዉ ደግሞ በሥጋ ድካምና በስንፍና ነዉ። አራተኛዉ ምክንያት በተሐድሶና በመናፍቃን መንፈስ ሕሊናዉ የተበከለና የተመረዘ ሰዉ መሪዉ ሌላ ተቃራኒ መንፈስ ስለሆነ «እኔ በየሱስ ድኛለሁ፤ የሱስ ጾሞልኛል» በማለት በዓመፃ እምነት ምክንያት ነዉ። ሌላዉ መታወቅ ያለበት እግዚብሔርን ሆነ እመቤታችንን መዉደዳችን የሚገለጸዉ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስንጠብቅና እንደ ቃሉ ሆነን ስንገኝ ነዉ። ለዚህ ብቃት ለመድረስ ደግሞ ሰይጣናትን(ርኩሳን መናፍስትን) ድል አድርገኝ የነፍሳችን ፈቃድ ከሥጋችን ፈቃድ በላይ እንዲሆንና ራሳችንን በሚገባ ለመግዛት እንድንችል ጾም ዋና መሳሪያችን ነዉ።

ወደ ሥርዓቱ ስንመጣ የተደበላለቀበት ዘመን ዉስጥ፣ ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች እንደ ሥጋና ደም ስሜት በሚመላለሱበት ወቅት ዉስጥ ስላለንና አንዳንዶች አስመሳይ አገልጋዮች «አስተዳዳሪ፣ ጸሐፊ፣ ሰባኪ፣ አገልጋይ» ተብለዉ በአርብና በረቡዕ ፍስክ ምግብ ላይ የሚሰለፉ እንዳሉ ሁሉ፤ ያጠበቁ መስሏቸዉ ራሳቸዉ ለራሳቸዉ ሥርዓት ፈጥረዉ የሚመላለሱ አገልጋዮችም አሉ። ይህ የተደበላለቀ ሕይወትና ሥርዓት እጅግ በቅርቡ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ስለሚስተካከል ከእኛ የሚጠበቀዉ

እዉነተኛ ተጠሪዎች በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ እስከሚቀመጡ ድረስ በታወቀዉ እምነትና ሥርዓት ጸንቶ መገኘት ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ሰዓት በቅዳሴ መሃል ካህኑ እጁን በዉኃ ሲጣጠብ ስለ ቅዱስ ቁርባን አቀባባል የሚያስፈራ ንግግር በካህኑም በዲያቆኑ የሚባል አለ:: ይህ የሚያስፈራራ አባባል ሰዎች ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዲቀርቡ ሳይሆን የሚያደርገዉ እንዲርቁና እንዲፈሩ ነዉ:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ::

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ በመጀመሪያ ለማለት የምፈልገዉ ነገር አለ:: ይኸዉም በኢትዮጵያ ተዋሕዶ እምነትና ሥርዓት ዉስጥ የሚታይ፣ የሚደመጥ፣ የሚነበብ ነገር ካለምክንያት አልተደረገም:: በዚሁ መሰረት አሁን ላለነዉ ትዉልዶች ማስፈራሪያ የሚመስለን ንባብ ሆነ ንግግር በዘመኑ እንዲነበብና እንዲነገር የተደረገበት ምክንያት አለዉ:: ይኸዉም ሰዎች በድፍረት ሥጋዉና ደሙን ይቀበሉ ስለነበረና አንዳንዶቹ ሥጋና ደሙን እንደ ተራ ነገር ይቆጥሩት ስለነበረ፣ እንዲሁም «ቅዱስ ቁርባኑ ወደ እዉነተኛዉ  መለኮት ወደ ተዋሐደዉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አይለወጥም» እያሉ አማኙን ያሳስቱ ስለነበር ነዉ::

እግዚአብሔር ሰዉን ከሌሎች ሕይወት ካላቸዉ ሆነ ከሌላቸዉ አልቆ የፈጠረዉ ስለሆነ፤ ነገሮችን የማወቅና የማመዛዘን እንዲሁም የመፍረድና የመወሰን ነጻነትና ኃይል አጎናጽፎታል:: በዚሁ መሰረት አንዳንድ አገልጋዮች፤ አሁን ያለዉ ትዉልድና ይህ ንባብና ንግግር እንዲገባ በተደረገበት ዘመን የነበሩ ሰዎች  አንድ ዓይነት አለመሆናቸዉን አስተዉለዉ እንዲሁም ትዉልዱ እንኳን በድፍረት ወደ ቅዱስ ቁርባን ሊቀርብ ይቅርና በተሳሳተ አመለካከት «ከቆረብኩ ዐይኔ ይጠፋል፣ ሰይጣን ይጠጋኛል፣ ሳረጅ ነዉ የምቆርበዉ.... ወዘተ» እያሉ የራቁት መሆኑን ተገንዝበዉ ያንን ማስፈራሪያ የሚመስለዉን ንባብና ንግግር በመለወጥ «በኃጢአቱ የተጸጸተ ንስሐ የገባ ሰዉ ወደ ቅዱስ ቁርባን ይቅረብ፤ ሥጋዉን ያለበላ ደሙን ያልጠጣ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም፤ ሥጋዉን የበላ ደሙን የጠጣ ሕያዉ ሆኖ ይኖራል» በማለት ለአሁን ትዉልድ አሻሽለዉ አቅርበዋል:: ነገር ግን ሁሉም ለማለት በሚያስችል ደረጃ ያ የቀድሞዉን ንባብና ንግግር ነዉ እስከ አሁን ድረስ የሚያቀርቡትና የሚናገሩት:: ይህም ከሁለት ምክንያት ይሆናል፤ አንደኛዉ «ስለ ነፍሳት መዳን አንዳች ስሜት የሌላቸዉ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች፤ ይህን አሻሽዬ ብናገር እንደ ከሃዲና መናፍቅ እቆጠሩኛል» በሚል ሥጋት ሲሆን፤ ሌላዉ ድግሞ በዘልማድ የሚያገለግል ካህን እርሱ በተለያየ ኃጢአት ተግባር እየተሰለፈ በድፍረት ስለሚቀበለዉ ምእመኑ ወደ ቁርባን ቀረበ አልቀረበ፣ ሥጋና ደሙን ተቀበለ አልተቀበለ አንዳች ስሜት ስለማይሰጠዉ፣ እንዲሁም እያገለገለ ያለዉ እንደ ስራ መስክ ቆጥሮት ነዉ እንጂ ሰማያዊ አገልግሎት መሆኑን ስለማያስተዉል፣ ንባቡ ሆነ ንግግሩ ምእመናን ከሥጋና ደሙ እንደሚያርቅ አያስተዉልም::

እዉነተኛ አገልጋዮች ግን ከቅዱስ ሥጋዉና ከክቡር ደሙ ዉጭ ያለ ሕይወት የሞተ ሕይወት መሆኑን በሚገባ አስተዉለዉ ለነፍሳት በማዘንና እዉነተኛ እረኛ በመሆን ምእመኑ በእዉነተኛ ንስሐ

ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዲቀርቡ የሚያደርግ ንባብና ንግግር እንዲቀርብ ማስደረግና በሲኖዶስ ደረጃ እንዲወሰን፣ እንዲሁም ከአሁን ትዉልድ ጋር የማይሄድ ንባብ ሆነ ንግግር ካለ የሚመለከታቸዉ አካላት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ሆነዉ እንዲያጣሩ በማድረግ መቀነስ ያለበትን መቀነስ፣ መጨመር ያለበትን መጨመር፣ መስተካከል ያለበትን ማስተካከል፣ መታረም ያለበትም ማረም ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም የአገልግሎቱን ወንበር ለመከበሪያና ጥቅም ለማግኛ የምንጠቀምበትና ስለ ለነፍሳት ድኅነት ሆነ መልካም ሕይወት ስሜት የማይሰጠን ከሆነ፤ እኛ እንደ ዓለማዉያኑ ለሥጋችን ያደርን ነን እንጂ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች «በጎቼን አሰማሩ፣ ጠቦቶቼን ጠብቁ፣ ግልገሎቼን ተንከባከቡ » የተባልን አይደለንም ማለት ነዉ።

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ፤ በክፋትና በጥላቻ፣ እንዲሁም ባለማወቅን ባለማስተዋል እንኳን በአዋልድ መጻሕፍት ይቅርና በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የገባ እንክርዳድ አቀርባለሁ። የመጀመሪያዉ በክፋትና በጥላቻ ከገቡት ወስጥ አንዱ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 67(68) ቁጥር 31 ላይ «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለዉን፤ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ጥላቻና በቀል ያላቸዉ በጨለማዉ ገዥ መንፈስ የሚመሩ ሰዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ የሚለዉን ለዉጠዉታል። ሌላዉ ባለማወቅና ባለማስተዋል እንዲሁም በሥጋና ደም እዉቀት ምክንያትና ዋናዉን መንፈስ ቅዱስ መሪ ባለማድረጋቸዉ ምክንያት አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን ሊቃዉንት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 4 ላይ «አንቺ ሴት» የሚለዉን  የኀዘን፣ የፍቅር፣ የርኅራኄ፣ የእናትን አጠራር የሆነዉን «አንቺ ሴትዮ» በማለት  የሩቅና የባዕድ አጠራር አድርገዉ አቅርበዉታል። በግልጽ እንደሚታወቀዉ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ናት። ይህም እናትነቷ ቅዱስ ገብርኤል የእግዚአብሔር ልጅ የተባለዉን ኢየሱስን እንደምትወልድ በነገራት ጊዜ «ለእግዚአብሔር የሚሳዉ ነገር የለም» ብላ «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» ባለች ጊዜ ተረጋግጧል። እናትነቷ ደግሞ በምድርም ብቻ ሳይሆን በሰማያት ዉስጥም እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ እንደ እናትነቷ ነዉ የምትከበረዉና የምትመሰገነዉ። ለዚህም ነዉ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በግልጽ በክፍል ሁለትና ሦስት በተለያየ ምዕራፍ ዉስጥ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን «እናቴ፣ የአዳራ እናታችሁ፣ እመቤታችሁ» እያለ የጠራት። ይህም የሚያሳየን የአምላክ እናትነቷ አሁንም ያልተሻረ፣ ክብሯ እንደተጠበቀ መሆኑን ነዉ። ታዲያ «ሴትዮ» ብሎ መተርጎ እንደ ቅርበት የእናትነት ስሜት ሳይሆን የሚያሳየን የባዕድ ወይንም የሩቅ ስሜት ነዉ። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስና ክብር አግኝታ እንዲሁም ባሳየችሁ ሕይወት ብቃት ተመርጣ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን የበቃችሁን እመቤታችንን እርሱ አቅርቧትና እክብሯት እያለ እኛ ልናርቃትና እንደ ማትታወቅ ሴት «ሴትዮ» እንድትባል የምናደርግ ከሆነ በተዝዋዋሪ ከእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ በተቃራኒ አቋም ቆመናል ማለት ነዉ።

ከዚህ በተጨማሪ ከአረብኛ ወደ ግእዝ በተተረጎመዉ ስንክሳር ዉስጥ «ኢትዮጵያዉያን የራሳቸዉ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ እንዲኖራቸዉ ስለጠየቁ መቅሰፍት መጣባቸዉ» በማለት ግብፃዉያን ሥልጣናቸዉንና የበላይነታቸዉን ለማስጠበቅ የጨመሩትን፤ አሁንም ወደ ኢትዮጵያዉኛ(ዐማርኛ)

ቋንቋ ሲተረጎም በዚያዉ ስሜት ነዉ። ይህም የግለሰቦችና ለግል ጥቅማቸዉ በቆሙት ግብፃዉያን የገባ ስለሆነ ይህን የመሳሰሉ ከአዋልድ መጻሕፍት ዉስጥ እንክርዳዱን ከስንዴዉ መለየት ይኖርበታል። በመሆኑም እነዚህ የመሳሰሉትን ኢትዮጵያዉያን መምህራንና ሊቃዉንት መሪቸዉን መንፈስ ቅዱስ አደርገዉ በእዉነትን በመንፈስ ቅዱስ እየመረመሩ እንክርዳዱን ከማንኛዉ ቅዱሳት ሆነ አዋልድ መጻሕፍት እንዲሁም ከተለያዩ ከማንኛዉም የእዉቀትና የጸሎት መጻሕፍት ዉስጥ በማዉጣት ንጹሁን ስንዴዉ ብቻ ለትዉልዱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። መምህርነቱና ሊቃዉንትነቱ ለዚህ ለእዉነተኛ አገልግሎትና ንጹህን ስንዴ ለማቅረብ ካልዋለ ስም ብቻ ሆኖ የሚያስጠይቀን ይሆናል ማለት ነዉ።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን ቡናን መጠጣት እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ማፍረስ የሚቆጥሩና የተከለከለ ስለመሆኑ ከአዋልድ መጽሐፍት ማስረጃ የሚያቀርቡ አሉ። በእዉኑ ቡና የሚጠጣ ሰዉ እንድ ኃጢአተኛ ተቆጥሮ ለእግዚአብሔር መንግሥት አይበቃምን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ስለ ቡና መጠጣትና አለመጠጣት እኔም ብዙ ሲባል ሰምቻለዉ። አንዳንድ አገልጋዮች ከባዕድ አምልኮ ጋር የሚፈጸመዉን የዓመፃ ተግባር በመመልከትና የሱስ ጠንቀኝነቱን በማስተዋል ሰዎች በባዕድ አምልኮ እንዳይመላለሱና የሱስ ባሪያ እንዳይሆኑ እንዳይጠጡ የሚከለክሉ አሉ። አንዳንዶቹ በዘልማድ ሕይወት የሚያገለግሉ ደግሞ እንደ አሥርቱ ትእዛዛት ቆጥረዉ ቡና የሚጠጣ ሰዉን እንደ ሕግ አፍራሽነት የሚቆጥሩ አሉ። ለዚህም የሚሆናቸዉ የራሳቸዉ የሥጋና ደም እዉቀት እንደ ማስረጃ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ምእመናን ደግሞ የዋህ እግዚአብሔር መፍራት ያለባቸዉ፣ የእግዚብሔር መንግሥት ለመዉረስ «አድርግ» የተባሉትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸዉን ያዘጋጁ ስለሆነ፤ እንኳን ቡና ይቅርና «የሚጣፍጥ መብልና መጠጥ ከእግዚአብሔር መንግሥት ይለያል፤ ይህን አትብሉ፣ ይህን አጠጡ» ቢባል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ የማይበሉና የማይጠጡ ናቸዉ። እንዲሁም ሌላዉ እንዲድንላቸዉ ስለሚፈልጉ በየዋህነትና በቅንነት ሌሎችም እንዳይበሉና እንዳይጠጡ ሊናገሩ ይችላሉ። አስገራሚዉና አሳዛኙ ግን «የእግዚአብሔን ቃል እናዉቃለን» ብለዉ ለምእመናን ቡናን መጠጣት እንደ ትእዛዝና ሕግ ማፍረስ ተቆጥሮ ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚለዩ መሆኑን የሚያስተምሩ ሰዎች ናቸዉ። ይህን ትተዉ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ትዕቢት፣ ዓመፃ፣ ቂም በቀል፣ ጥልና ግድያ፣ ሴሰኝትነት፣ ዝሙት፣ ስርቆት ባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ ዘፋኝነትና ዳንኪርተኛነት ... ወዘተ የሚፈጽም ሰዉ እንደ ረከሰ ተቆጥሮ እንዲሁም እንደ ትእዛዝና ሕግ አፍራሽነት ታይቶ ለእግዚአብሔር መንግሥት እንደማይበቃ ስለ ምን አያስተምሩም? አይሰብኩም!?

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ** በእግዚአብሔር እዉነት ማንም ሰዉ ለማንም ሱስ ተገዥ መሆን የለበትም። ምክንያቱም ሰይጣን በዚያ ላይ አድሮ ተገዥ ያደርገናልና። ነገር ግን ራሱን የገዛ ሰዉ ለስሜቱ ቡና ሆነ መጠጥ ቢጠጣ እንደ ትእዛዝና ሕግ አፍራሽ አይቆጠርም። የሚጠየቅበት ጠጥቶ ከሰከረና የማይገባ ስራ ከሰራ ነዉ። እንዲሁም የሱስ ተገዥ ሆኖ ያንን ሱሱን ለማርካት የሚፈጽመዉ የዓመፃ ተግባር ነዉ። ስለዚህ ሰዉ ቢቻለዉ ሱስ ከሚያመጣ ከቡና ሆነ ከመጠጥ ቢከለከል

ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን በዚያ ሰበብ የማይገባ ሕይወት ዉስጥ እንዳይከተዉ ነዉ፡፡ በተቀረ ግን ራሱን የሚቆጣጠርና የሚገዛ ሰዉ ቡናና መጠጥ ስለጠጣ «ትእዛዝ አፍርሰሃል፣ ሕግ ሽረሃል» ተብሎ ሊገሰጽና እንደ ኃጢአተኛ ሊቆጠር አይገባም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ብዙዎች ባያስተዉሉትም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሊቃዉንት፣ መምህራን፣ አገልጋዮች፣ ከዓለማዉያን «ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ ሳይንቲስት... ወዘተ» ከሚባሉት በላይ እዉቀትና ክህሎት አላቸዉ፡፡ ይህም እዉቀታቸዉና ልዩ ስጦታቸዉ ከሚታወቅበት አንዱ ብዙ መጽሐፍትን ካለምንም ማመሳከሪያና ድጋፍ በቃላቸዉ ብቻ ይዘዉ ማስተማርና ማገልገል የሚችሉና እንዲሁም ቅኔ ብዙ ነገሮችን ሟሟላት የሚጠበቅበትን መጽሐፍት ሳያገላብጡ፣ ማስታወሻ ሳይመለከቱ፣ ሰዎች ግጥምን እንኳ ጊዜ ወስደዉ አንዱን በማዉጣት አንዱን በማስገባት በመቀነስ በመጨመር ነዉ የሚደርሱትና ለሕዝብ የሚያቀርቡት፤ ቅኔ ግን አቅራቢዎቹ ከታሪኩና ከዕለቱ ጋር የሚሄድ የዜማ ልክና በዕለቱ ሊቀርብ የሚገባዉ ቅኔ ዓይነት ጠብቀዉ «አቅርቡ» ሲባሉ አዲስ ቅኔ ከዚያ በፊት ማንም ያላቀረቡዉን ወዲያዉ ከአእምሮዋቸዉ አፍልቀዉ የሚያቀርቡ ናቸዉ፡፡ ነገር ግን በዓለማዊዉ እዉቀት ደግሞ ወደ ኋላ የቀረን ነን፡፡ ኢትዮጵያዊዉ ሰዉነት የተለየ ብቃት ካለዉ፤ ሰለጠኑ እንደሚባሉት አገራት የደረሱበትን የእዉቀትና የጥበብ ዉጤቶችን ማምጣትና ማሳየት ያልቻልነዉ ለምንድነዉ? በአእምሮ ደረጃ ከእነሱ በብዙ እጥፍ እንደምንበልጥ ይኸዉ ከላይ የገለጽኩት ብቃት ብቻ ምስክር ሊሆን ይችላልና፡፡

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር የእያንዳንዳችንን ልቦና ያዉቃል፡፡ እንኳን በዓለም ላይ ያለ የእዉቀትና የጥበብ ሥልጣኔ ላይ ደርሰን አይደለም አሁን በድህነትና በችግር ዉስጥ ሆነን እንኳ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባራችን ጸንተን ዕለት ዕለት እግዚአብሔርን በሚያስቆጣ ሕይወት ዉስጥ እንገኛለን፡፡ በዓለም ሥልጣኔ ላይ ብንደርስማ በዚህ ትዕቢታችንና እብሪታችን እንዲሁም ክፋትና ዓመፃችን ሕይወት እጅግ የከፋ ዓመፃና ክህደት እንደምንፈጽም እግዚአብሔር ስለሚያዉቅ ነዉ ለዓለም የፈቀደዉን እዉቀትን ጥበብ የገደበብን፡፡ ነገር ግን የዓመፃ ልጆች ከምድር ሲጸዱና ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቁጣ ሲጠረጉ ያኔ ወደ ትክክለኛዉ የእዉቀትና የጥበብ ስጦታ ላይ እንደምንደርስ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ምክንያቱም እዉቀቱና ጥበቡ የምንታበይበትና የምናምጽበት ሳይሆን እግዚአብሔርን የምናስመሰግንበት እንዲሁም ለሰዉ ዘሮች የሚጠቅምና ከጉስቁልና ሕይወት የሚለያቸዉ ይሆናል እንጂ፤ እንደ ዓለማዉያኑ ሕዝብና ሕዝብን የሚያጫርስ መሳሪያ አይሰራበትም፡፡ ትዕቢተኝነታችንንና ጨካኝነታችንን የሚያስመሰክረዉን ኒዉክለር፣ ባዉሎጂካል መሳሪያ የመሳሰሉትን የዓመፃ ፍሬዎች እንኳን መስራት ይቅርና በሕሊናም የምናስበዉ አይሆንም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንድ ግራ የገባኝ ነገር አለ፡፡ ይኸዉም ክርስትና የኦሪቱን እምነት እንደተካ እየታወቀ እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ሆነ በሌላ አገራት ዉስጥ የኦሪት እምነት አለ፡፡ የኦሪት መስራች የሆነዉ ራሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ በወንጌል አድሶት ክርስትናና

መመስረቱ እየታወቀ አንዳንድ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ በዚያዉ ኦሪታዊ እምነት እንዴት ሊጸኑ ቻሉ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በእዉነቱ እንደሆነ በአሁን ዘመን የኦሪት እምነት አለ ማለት አይቻልም:: ምክንያቱም ቢኖር ኖሮ ያኔ የነበረዉ የመስዋዕት ሥርዓትና አምልኮ በዚያዉ መልክ ይፈጸም ነበር:: ነገር ግን አሁንም ትዉልዱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ላለመቀበል ሕሊናዉን በማደንደን ጸንቶ ስለተገኘ የስም ኦሪታዊ ነዉ እንጂ እንደ ቀደሙት እንደ ብሉይ ዘመን ኦሪት እምነት ሕይወት አይመላለሱም:: «ያ የመጨረሻ እምነት ነዉ» የሚሉ ከሆነ ደግሞ እንደ እምነቱና ሥርዓቱ ሆነዉ መገኘት ነበረባቸዉ:: ይሁንና ይኸዉ ለሁሉት ሺህ ዓመት ያህል ሕሊናቸዉን በማደንድን ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁንና አሁንም «ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሳች ነዉ፤ እዉነተኛዉ መሲህ አይደለም፤ ክርስቶስ ገና ይወለዳል ... ወዘተ» እያሉ ራሳቸዉን ለከፋዉ ጥፋትና መዉደቅ እያዘጋጁ ነዉ:: ስለዚህ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ እርሱ የቀደሙ ወላጆቻቸዉ ራቁቱን በመስቀል ላይ የሰቀሉት ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የቅርብ ወገኖቻቸዉ ሐዋርያት እንደመሰከሩት የጌቶች ጌታ፣ የአማልእት አምላክ፣ የሁሉ ፈጣሪ አልፋና ዖሜጋ የሆነ፣ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ የመልከ ጼዴቅ አምላክ መሆኑን አዉቀዉ እንደ አምላክነቱ ቢያምኑበትና ቢያመልኩት ራሳቸዉን ከጥፋትና ከመደምሰስ ያድናሉ እንጂ አንዳች የሚጎዱበት ሆነ የሚቀርባቸዉ ነገር የለም:: አሁንም «አይ በዓመፃችን እንጸናለን፤ አናምንበትም» የሚሉ ከሆነ ደግሞ የሚመጣባችሁን የእግዚአብሔር ቁጣ በጸጋ መቀበል ነዉ:: ቅንነትና መልካምነት የተላበሱና እዉነትን የሚፈልጉ ወገኖቻችን ደግሞ በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ አምላክነቱን እንደሚያምኑና እንደሚያመልኩት ተስፋ እናደርጋለን::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ያሉ አንዳንድ መምህራንና አማኞች ሳይቀር «ይህች ምድር የዲያብሎስ ናትና ዲያብሎስ ነዉ የሚነግሥባት እንጂ እግዚአብሔር አይነግሥባትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህች ምድር ሊገለጥ አይችልም» የሚሉ አሉ:: ለዚህ ምን አስተያየት አሎት?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ይህን ምእመናኑ ቢሉት አንዳች አያስገርምም፣ አያሳዝንም:: ምክንያቱም የእነርሱ እዉቀት ደረጃ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምንነት በሚገባ ሊያዉቁና ሊያስተዉሉ አይችሉምና:: ጽድቅና ኩነኔ እንዲሁም ሲኦልና መንግሥተ ሰማያት መኖራቸዉን ያምናሉ:: ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃቸዉን ሕይወት ለመያዝ ይጥራሉ፣ ይተጋሉ:: የሚያስገርመዉና የሚያሳዝነዉ «መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ፤ አዋቂ፣ ምሁራን ነን» ብለዉ ይህም የሚሉ ለዲያብሎስ ሥርዓት ታማኝ የሆኑ ዲያብሎስ በዚህች ምደር እንዲነግሥና ፈቃዱ እንዲፈጸም የሚያስተምሩ ናቸዉ:: የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚፈልግ ግለሰብ ሆነ ቡድን እንዲሁም መንግሥት በእርሱ ዘንድ የእግዚአብሔር መንግሥት አለች:: ምክንያቱም በእያንዳንዱ ሕይወት እግዚአብሔር የሚነግሥና ፈቃዱ ብቻ የሚፈጸም ከሆነ ያ ግለሰብ ወይንም ቡድን ወይንም መንግሥት ራሱ የእግዚአብሔር መንግሥት መንበር የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኗል ማለት ነዉ::

በመንግሥት ደረጃ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽምና የሚያስፈጽም ከሆነ፤ ይኸዉም ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመራ ከሆነ ያ መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ የተሰባሰቡበት ስለሆነና የእግዚአብሔርም ፈቃድ በአራቱም ማእዘን ስለሚፈጸም ነዉ፡፡ እጅግ በቅርቡ በኢትዮጵያ የሚዘረጋዉ ሰማያዊ ሥርዓት የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወክል ነዉ፡፡ ምክንያቱም በእዉነተኛዉ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀብተዉ የሚቀመጡት የእርሱ የእግዚአብሔር ምርጥ ባለሟሎችና እንደራሴዎች ናቸዉና፡፡ ከስራቸዉ ከዋናዉ ቤተመንግሥትና ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ ቀበሌና ገጠር አብያተክርስቲያናት ድረስ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ ናቸዉ እንጂ የዲያብሎስን ወይንም የግለሰቦችን ወይንም የሥጋና የደም ስሜት ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ አይደሉም፡፡

ሌላዉ እዚህ ላይ ለመግለጽ የምፈልገዉ የተለያዩ መምህራን እንዳሉ ነዉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ እዉነተኛ መምህራን ሲሆኑ እነዚህም እዉቀታቸዉን የማያመልኩና የማያስመልኩ እንደ ፈሪሳዊዉ ኒቆዲሞስ ዓይነቶች ለእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት የሚሰለፉ ናቸዉ፡፡ ሁለተኛዉ ዓይነቶች ደግሞ እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ ለሚያዉቁት እዉቀትና ሥርዓት ቀናዒ የሆኑ፤ ነገር ግን ሙሉ እዉነትን ሲያዉቁ ደግሞ እዉቀታቸዉ ጣዖት የማይሆንባቸዉ ስለ ሙሉ እዉነት በቆራጥነት የሚመሰክሩና የሚያገለግሉ ናቸዉ፡፡ ሦስተኛዎቹ ደግሞ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን አይሁድ ካህናት እንደ ቀያፋና ሐና ዓይነቶች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ዓይነቶቹ እዉቀታቸዉ ጣዖት ስለሚሆንባቸዉ ከእነርሱ እዉቀት በላይ የሆነ ወይንም የተለየ ሁሉ የክህደት እዉቀት ነዉ፡፡ እንኳን እግዚአብሔር የላካቸዉን መልእክተኞቹንና አገልጋዮችን መስማትና መቀበል ይቅርና እርሱ የእዉቀት ባለቤት ምስጢራትን የሚገልጽ አምላክ ተገልጾ ቢናገራቸዉ፣ ቢያስረዳቸዉ የማይቀበሉ የሙሉ እዉነት እንቅፋቶችና የእግዚአብሔርን አገልጋዮችና መልእክተኞችን ከማሳደድ፣ ከመግደል፣ ከማስገደል፣ ከማስወንጀል፣ ከማሰደብ፣ የተለያየ ፈተናና ጥቃት ከማስፈጸም ወደ ኋላ የማይመለሱ ናቸዉ፡፡ አራተኛዉ መምህራን ደግሞ ሙሉ እዉቀት የሌላቸዉ በዘልማድ የሚያገለግሉ፣ ስህተቱን እንደ ትክክል ቆጥረዉ የሚያስተምሩ፣ ራሳቸዉም ሆነ ሌላዉ ፍሬ እንዳያፈራ የሚያደርጉ ባዶ ቀፎ የሆኑ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ የተለዩ «መምህራን» ነን የሚሉ ደግሞ የሕይወት መንገድ ጠፍቶባቸዉ በሚያዉቁትና በተረዱት እዉቀት የሚያስተምሩ፣ እንክርዳዱንና ስንዴዉን ቀይጠዉ የሚያቀርቡ፣ እንክርዳዱን ከሰንዴዉ የመለየት ብቃት የሌላቸዉ፣ መልካም ፍሬ የማያፈሩ፤ ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን የሚያስፋፉ ናቸዉ፡፡ ምናልባት እነዚህ ወደ ልባቸዉ ከተመለሱ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ወደ እዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ የሚመራቸዉ ሰዉ አተዉ ነዉ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚያገለግሉት፡፡

የተለያዩ መምህራንና እንዲሁም «መምህራን ነን» የሚሉ ሰዎችን አስተሳሰባቸዉን በቁጥር ድምር ምሳሌ አቀርብላችኋለዉ፡፡

አንዳንዶቹ 1(አንድ) ሲደመር 1(አንድ) ሁለት ብቻ ነዉ የሚሉ አሉ፡፡ እነዚህ ለነፍሳት የሚያዝኑ የሕይወትን መንገድ ትዉልዱ አዉቆ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሰለፍ የሚፈልጉ አንዳች የተለየ ክብርና ዝና የማይፈልጉ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆኑ ቅኖችና እዉነተኞች ስለ እዉነት ራሳቸዉን የካዱ አእምሮ ጽንዓን ናቸዉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «ለምን 1 ሲደመር 1 እኩል ይሆናል ሁለት በቀላሉ ይባላል? ለምን የሕይወትን መንገድ አናወሳስበዉም፣ ለምን $1 + 0.2 + 0.4/0.2 + \sqrt{4} - 5 + 0.1 - 0.5 - 1 + 2 \div 2 + 2^2$ እኩል ይሆናል ሁለት አንልም» የሚሉ ናቸዉ፤ ምንም እንኳን ዉጤቱ ትክክል ቢሆንም የሕይወትን መንገድ የሚያወሳስቡ፣ በማወሳሰባቸዉም ምክንያት ደግሞ እንደተለየ ተደርገዉ እንዲቆጠሩና ሰዎችም እዉቀታቸዉን እንዲያመልኩላቸዉ የሚፈልጉ፣ የተለየ ክብርና ዝና የሚፈልጉ፣ ለነፍሳት ድኅነት ብዙም ስሜት የሌላቸዉ ናቸዉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ 1+0.5 እኩል ይሆናል ሁለት የሚሉ ናቸዉ፡፡ ይህም «ስህተቶችንም እንደ ትክክል እንቁጠር፤ የሕይወት መንገድ ያልሆኑትም እንደ ሕይወት መንገድ ቆጥረን «ተመሳስለህና ሕሊናህን ሽጠህ ኑር የሚለዉን የአሕዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት የሚያራምዱትን እምነት እንከተል» የሚሉ ናቸዉ፡፡ እነዚህ የሥጋና የደም ስሜታቸዉ ያየለባቸዉ፣ ዋና ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ የሚኖሩ፣ ሰማያዊዉን ሕይወት በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጡ ናቸዉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «£ +ሞ እኩል ይሆናል ሁለት» የሚሉ፤ አንዳች ግንኙነት የሌላቸዉን እንደ እምነትና የሕይወት መንገድ የሚቆጥሩ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሙሉ በሙሉ ሥጋዉያን ሲሆኑ ተስፋቸዉ ምድር ብቻ የሆነ «እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ ሕይወታችን በዚህ ይደመደማልና እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንጨፍር፣ እንዝናና፣ ከራስ በላይ ንፋስ ... ወዘተ» የሚሉ ናቸዉ፡፡ አንዳደንዶች «ሀ+ ሀ እኩል ይሆናል ሁለት» የሚሉ የሕይወት መንገድ የጠፋባቸዉ «ሁሉም እምነቶችና መንገዶች ወደ ሕይወት መንገድ የሚያደርሱ ናቸዉ» ብለዉ የሚያምኑ ናቸዉ፡፡

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን ዋና ችግራቸዉ፣ ድክመታቸዉ፣ ስህተታቸዉ ምንድነዉ ይላሉ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: የኢትዮጵያ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ችግር ሆነ ድክመት እንዲሁም ስህተት የሌባቸዉም፡፡ ችግር፣ ድክመት፣ ስህተት ያለዉ በቤተክህነት የአስተዳደር ሥርዓትና ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ ገጠር አብያተክርስቲያን አጥቢያ ድረስ ያለ የመልካም አስተዳደር ችግርና ድክመት እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነት የሌለበት አሰራር ነዉ፡፡ በዚህ ችግርና ድክመት ምክንያት ሌባ፣ ቀማኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ሴሰኛ፣ ዘማዊ፣ ወንበዴዉ፣ አንደበቱን እያሳመረ የሚኖር ነገር ግን ሕይወቱ ባዶ የሆነ አስመሳይ አገልጋይ... ወዘተ በተለያየ የኃላፊነት ቦታ ላይ በመቀመጥ ቤተክርስቲያንን በድለዋል፤ እዉነተኞችን አሳደዋል፤ ደብደበዋል፣ አሳስረዋል፣ አስገድለዋል፣ አሰድበዋል፣ ወንጅለዋል፣ ምእመኑንም እጅግ አሳዝነዋል፡፡ እነዚህ አስመሳይ አገልጋዮች በተለያየ ኃላፊነት ከሊቀጳጳስ እስከ ዲያቆንና ምእመን ድረስ ያሉ ቅኖችንና እዉነተኛ አገልጋዮችን፤ በተለያየ መንገድ መልካም አገልግሎት እንዳይሰጡ እንቅፋትና ማሰናከያ ሆነዋል፡፡

በእዉነትና በቅንነት እንነጋገር ከተባለ በቤተክህነት ከላይ እስከ ታች ድረስ ከመንግሥታዊና ከተለያዩ ድርጅቶች አሰራር በበለጠና በላቀ ደረጃ መልካምና እዉነተኛ አስተዳደር ሊኖር ሲገባ፤ ይኸዉም መሪዉ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ምእመኑን ሆነ አገልጋዩን በትህትና፣ በፍቅር፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በትጋት፣ በእዉነት ፣ ራስን በመግዛትና ዝቅ አድርጎ በአክብሮት ማገልገል ሲገባ፤ እንኳን ከመንግሥታዊና ከተለያዩ ድርጅቶች የሚበልጥ መዋቅርና አስተዳደር ሊኖር ይቅርና እጅግ እጅግ ያነሰ የአስተዳደርና የአገልግሎት አሰራር ነዉ ያለዉ። በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ፣ በጥቅማጥቅም፣ በሽንግላ፣ በተንኮል፣ በክፋት፣ በምቀኝነት፣ በጥላቻና በቀል፣ በመጠላለፍ ... ወዘተ የተተበተበ ነዉ። አንዳንድ የተማረሩ አገልጋዮችና አማኞች፤ ከቁጥር ባይገቡም በቅንነትና በእዉነት የሚያገለግሉትን አገልጋዮችንና አማኞችን ዘንግተዉ «ቤተክህነቱ ሰይጣናት የተሰባሰቡበት ነዉ» እስከማለት ደርሰዋል። ይህም የሚያሳየን ምንም እንኳን ክህነታቸዉን አክብረዉ የሃይማኖታቸዉና የቤተክርስቲያን ፍቅር እያቃጠላቸዉ የተለያዩ ፈተናዎችንና ችግሮችን ተቋቁመዉ በቅንነትና በእዉነት እያገለገሉ ያሉ እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ አገልጋዮችና አማኞች እንዳሉ ቢታወቅም፤በዋናነት የነገሠዉ የጨለማ ስራ ስለሆነ የእነርሱ መልካም ተግባር ተሸፍናል። እዉነት ስትነግሥ ግን መልካም ስራቸዉና እዉነተኛ ሕይወታቸዉ ብርሃን ሆኖ ጨለማዉን የሚያርቅና የሚያስወግድ ይሆናል።

አሁንም እግዚአብሔር ቤቱን የሚያጠራበትና የሚያጸዳበት ወራት ስለደረሰ ዋናዉን መሪ እግዚአብሔር ከወንበር ቆርጦ ነጻነትን እንዳጎናጸፈ ሁሉ በአሁን ሰዓት በበላይ ሆነዉ የሚመሩት አካላትና አባቶች ለመልካም አስተዳደርና ለእዉነተኛ አገልግሎት እንቅፋት የነበሩትንና የሆኑትን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እየመረመሩና እየገመገሙ ከዓመፃ አገልግሎት መለየትን እዉነተኞችንና ቅኖችን ወደሚገባቸዉ እዉነተኛዉ ወንበርና አገልግሎት ማምጣት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በእዉነትና በቅንነት ሲያገለግሉ የነበሩትንንና እያገለገሉ ያሉትን ለበለጠ አገልግሎት ማሰለፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማደረግ ከተሳናቸዉ እንዲሁም «ይህን እናድርግ» ብለዉ ሲነሱ በተለያየ መንፈሳዊ ሆነ ሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች እንቅፋት ሆነዉ የዓመፃና የክህደቱን እንዲሁም የርኩሰቱን ተግባር እንዲጸናና በዚያዉ እንዲቀጥል ካደረጉ ግን ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክስርስቶስ ቤቱን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በመኮታዊ ቁጣዉ ከላይ እስከ ታች ድረሰ ያስተካክለዋል፤ ያጸዳዋል፤ ዓመፀኞችንም በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍላቸዋል(ይቀጣቸዋል)» **በማለት የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን፣ የቅዱሳን አምላክ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

# ክፍል አምስት

## ምዕራፍ አንድ

« ጠያቂዉ አገልጋይ፡ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሁለት በምዕራፍ ሁለት በገጽ 32-33 ላይ እግዚአብሔር በሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጡትን የዓለም መንግሥታት ቃል በቃል የገሰጻቸዉ ተለበጧል፡፡ ይኸዉም፡

«እናንተ በሥጋዊ ወንበር የተቀመጣችሁ ከዋና መሪ እስከታች ድረስ ያላችሁ፤ ለመሆኑ በኃላፊነት የተሰጣችሁ የስራ ድርሻችሁ ምን እንደሆነ አውቃችኋልን? የማንን ፈቃድ ነው የምትፈጽሙት? መሪያችሁስ መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ የዲያቢሎስ መንፈስ ነው? ሕዝቡ እኔን እንዲያውቅ፣ እኔን በፍጹም ሕይወት እንዲያመልከኝ፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከትዕቢት፣ ከዓመፃ፣ ከግፍ፣ ከጣዖትና ባዕድ አምልኮት፣ ከዝሙት፣ ከዘረኝነት፣ ከዘፋኝነት፣ ከዳንኪረተኛነት፣ ከግድያ፣ ከስርቆት፣ ከጥንቆላ፣ ከአስማት፣ ከመተት፣ ከሟርት፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት በአጠቃላይ የሰይጣናት ፍሬ ወደ ሞት ከሚወስዱትና እኔንም ከሚያስቆጣ ተግባራት እንዲለይ አድርጋችኋልን?

<u>እስቲ ራሳችሁን መርምሩ? እንኳን የምትመሯቸውን ሰዎች ከዚህ ከርኩስ መንፈስ ፍሬ ልትለዩ ቀርቶ እናንተ ራሳችሁ ከእነዚህ ተግባር ተለይታችኋልን ? እንግዲህ መሪያችሁ እኔ እንደሆንኩ ወይንም ዲያብሎስ አንደሆነ ራሳችሁ ፍረዱ!</u> እኔና ዲያብሎስ አንድነት የሌለን፤ የእኔ ፈቃድ የሆነው ከላይ ከተገለጸው የዓመፃ ፍሬ ውጭ የሆነ፣ ሰዎች ሁሉ በቅንነት፣ በመልካምነት፣ በትህትና፣ በትዕግስት፣ በፍቅር፣ በመረዳዳት፣ በመተሳሰብ፣ በቸርነት፣ በእውነት፣ በእምነት፣ በአጠቃላይ በቅድስና ሕይወት በመመላለስ እንዲኖሩ ብቻ ነው፡፡

እናንተ ግን መሪያችሁ ዲያብሎስን ስላደረጋችሁ፤ ከርኩሰት ፍሬ በተጨማሪ ሰዎችን በነገድ፣ በዘር፣ በቋንቋ እየለያያችሁ ጥላቻ የምትፈጥሩ፤ ሰዎች አንድ ሆነው በፍቅር እኔን እንዳያመልኩ የምታደርጉ፤ «ወገኔ፣ ዘመዴ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ፣ ቤተሰቤ ነው» እያላችሁ አድሎ በማድረግ ራስ ወዳድነትን የምትፈጥሩ፤ <u>ሰዎች በስግብግብነት ሕይወት እንዲኖሩ አድርጋችሁ ሕዝቡን በችግርና በረኃብ የምትቀጡ፤ የምታወሩት ሌላ የምትሰሩት ሌላ የሆነ፤ ንግግራችሁና ተግባራችሁ የማይገናኝ፤ አስመሳይ ሸንጋይ የሆናችሁ፤ እውነተኛውንና ሐሊናዬን አልሸጥም የሚለውን የምታሳድዱ፤ የምታስሩ፤ የምትገሉ፤ በሐሰት የምትወነጅሉ ናችሁ</u> ፡፡ ታድያ ይህን ሁሉ ስታደርጉ ዝም ብዬ የማያችሁ አይመስላችሁ፤ እናንተ ለረጅም ጊዜ እንኖራለን፣ የራሳችንን ሐሳብ እናጸናለን፣ ለትውልዳችን እናስተላልፋለን ትላላችሁ፡፡ <u>ነገር ግን ይህ ሐሳባችሁ ይሻራል፤ ይቆረጣል፤ ፍሬ ሊያፈራ ለሚችል ይሰጣል፡፡</u>

ለመሆኑ የምትሰሩትንና የምትናገሩትን ቀርቶ የምታስቡትን የማዉቅና ሁሉ ነገር በእኔ ቁጥጥር ውስጥ የሆነ፤ እንኳን አሁን ያላችሁበትን ቀርቶ አይደለም የወደፊቱን የማዉቅ አምላክ ነኝ

:: በተቀመጣችሁበት ወንበር ላይ ሁላችሁም እንዳላችሁ ዓይናችሁ እያየ በትል ተበልታችሁ እንድትሞቱ ማድረግ የሚያቅተኝ ይመስላችኋልን? <u>እንኳን እናንተ ዓመፀኞችን ቀርቶ በመጀመሪያ አካሄዳቸው ከእኔ ጋር አድርገው በኋላ የረሱኝን እንኳን ቀጥቻቸዋለሁ፤ አዋርጃቸዋለሁ፤ ሐሳባቸውንና ምኞታቸውን ቆርጫለሁ::</u>

ስለዚህ ማንኛችሁም ብትሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ በሥጋዊ ወንበር ላይ ስትቀመጡ የራሳችሁን ምኞትና ሐሳብ ለመፈጸም ሳይሆን የእኔን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ብቻ መሆን አለበት:: <u>ምክንያቱም የምትመሩትና የምታስተዳድሩት ሕዝብ ዲያብሎስ የፈጠረውና የሚመግበው አይደለም:: ፈጣሪዉም እኔ፤ መጋቢውም እኔ ነኝ::</u> <u>መገዛትና ማምለክ ያለበት እኔ ነው እንጂ ዲያብሎስን አይደለም::</u> እናንተ ግን እኔን አታወቁም፤ በበላይ ሆኖ የሚመራችሁንም ዲያብሎስን አታዉቁትም፤ አታስተውሉትም፤ ብቻ የሚያሳሰባችሁን ሐሳብ ወደ ተግባር ትለውጡለታላችሁ፤ ፈቃዱን ሁሉ እናንተም እየፈጸማችሁ ሌላውንም ታስፈጽማላችሁ:: እውነትን በቅን ሐሳብና በመልካም ሕይወት አልፈለጋችሁምና ሕሊናችሁ የእኔን ፈቃድና ሐሳብ ሆነ፤ የመሪያችሁ ዲያብሎስ ፈቃድና ሐሳብ ሊያስተውልና ሊያውቅ አልቻለም:: እንደ ሥጋ ሐሳባችሁና ምኞታችሁ ትፈጽማላችሁ፤ ታስፈጽማላችሁ::

ለመሆኑ ስንት አምላክ አለ? ስንት ፈጣሪ አለ? ስንት የሁሉ አስገኝ አለ? አንድ እኔ ብቻ አይደለ ያለሁት!? ፍጥረታትን ሁሉ ካላመኖር ወደ መኖር ያመጣሁ፤ ከፈለኩም ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የምችል እኔ ብቻ አይደለሁምን!? <u>እናንተ ግን ለራሳችሁ ብዙ አምላክ ፈጥራችሁ፤ ሰዎችም በብዙ አምላክ እንዲመሩ አደረጋችሁ::</u> <u>እውነትን አጥፍታችኋል፤ እኔ በእውነትና በእምነት እንዳልመለክ አድርጋችኋል::</u> አንድ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ሁሉ፤ «በፈጣሪ አምላክ አምናለሁ» የሚል ሰው ሁሉ በአንድ ሃይማኖት ሆኖ እኔን ማምለክ አልነበረበትምን !?

እናንተ ግን ተስፋችሁና ተግባራችሁ ምድራዊ፤ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚ ስለሆናችሁ፤ ለእናንተ ሁሉም ሃይማኖት ትክክል ነው፤ <u>«ሁሉም በፈለገው መንገድ አምላክን ማምለክ ይችላል» እያላችሁ በሸንገላ ቋንቋ ዕድሜያችሁን የምታራዝሙ መስሏችኋል::</u> እኔ እንደ ሰው አይደለሁም፤ አልቸኩልም፤ ግብታዊ ውሳኔም አልሰጥም፤ ሁሉን በጊዜው የማከናውንበት ወቅት ስላለኝ፤ ለዚህ ነው የዓመፃ ተግባራችሁን እያየሁ ዝም የምለውና የዓመፃዉ ፅዋ ሞልቶ ሲፈስ ርምጃ የምወስደው:: <u>አሁን ግን ይበቃችኋል፤ የምሰራበት ወቅት ደርሷልና ባለጊዜ አትሆኑም፤ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚነታችሁ ይሻራል፤ ቦታውን ፈቃዴን ለሚፈጽሙና ሊሚያሰፈጽው ትለቃላችሁ</u>::» ይላል::

ለዚህ ግሳጼና የእግዚአብሔር ዉሳኔ ምን አስተያየት አሎት?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር የሚሰማዉና የሚቀበለዉ አጣ እንጂ መንግሥታቱ እዉነትን አዉቀዉ በእዉነት እንዲኖሩ፣ እዉነተኛ እረኞች እንዲሆኑ ፈልጎ ነዉ መልእክቱን ከመጨረሻዉ ቁጣ በፊት ያስተላለፈዉ:: ነገር ግን እንኳን የዉጭ መንግሥታት ይቅርና የኢትዮጵያ መንግሥት የእግዚአብሔርን መልእክት ለመስማትና ሕይወታቸዉንና አቋማቸዉን

ማስተካከል አልቻሉም:: በመሆኑን ከእንግዲህ የሚቀራቸዉ የእግዚአብሔር ዉሳኔ በዓለም መንግሥታት ላይ ጭምር መጽናት ነዉ:: ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በእያንዳንድ የዓለም መንግሥት ዉሳኔዉ ተግባራዊ እየሆነ ሲሆን በቀጣይም በሁሉም መንግሥታት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በዚሁ ምዕራፍ በገጽ 33-34 ላይ በዓለም ላይ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ያሉት የሃይማኖት መሪዎች ተገስጸዋል:: ይኸዉም:

«እናንተ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ፤ ለመሆኑ በወንበሩ ላይ የተቀመጣችሁበትን ዓላማ አውቃችኋልን? በውኑ የምታመልኩትን አምላክ በእውነት ታመልኩታላችሁን? በእውነትስ ታገለግላላችሁን? ለመሆኑ እርሱ ማነው? እናንተስ ማናችሁ?

እስቲ ስለምትሰሩት ስራና ስለ መንፈሳዊ ሕይወታችሁ ልትነግሩኝ ትችላላችሁን? የእናንተን በባዶ ሕይወት የተሞላ ወሬ የሚሰማችሁ አምላክ ያለ ይመስላችኋልን? ምን እየፈጸማችሁ፣ ምን እያስፈጸማችሁ ነው ያላችሁት? ማንን ነው የምታታልሉት? በዚህች ዓለም፣ በሌላዉም ዓለም፣ አማናዊ ሕዋ ውስጥም፤ ሁሉን በበላይ የምገዛ፣ የምቆጣጠር፣ የሁሉ አስገኝ፣ አልፋና ያሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው፣ ፊተኛውና ኋላኛው እኔ ነኝ:: ከእኔ ውጭ ማን አለና ነው እናንተ በክህደት፣ በዓመፃ፣ በውሸት፣ በማስመሰል የምታመልኩትና የምታሰመልኩት? እንኳን እኔን ቀርቶ፤ በዚህች ምድር እንደፈለገ የሚያሽከረክራችሁን፤ ሕሊናችሁን ለእርሱ ማደሪያ አድርጋችሁ እኔን የሚያስቆጣ ተግባር የምትፈጽሙለትን ዲያብሎስን ታውቁታላችሁን?

እንግዲህ በሥጋዊ ወንበር ላይ ከተቀመጡት በላይ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቃችሁ እወቁ:: ምክንያቱም በእኔ ስም ነውና የነገዳችሁት:: <u>እስቲ ፍሬ አፍርተናል የምትሉት አንዳች ነገር ካለ ንገሩኝ? ሰዎችን ከክፋት ወደ ደግነት፣ ከጠማማነት ወደ ቀናነት ፣ ከዓመፃ ወደ ታዛዥነት ፣ ከክህደት ወደ ታማኝነት ፣ ከርኩሰት ወደ ቅድስና፣ ከራስ ወዳድነት ወደ ወገን(አዳምና ሔዋን ዘር) ወዳድነት፣ ከስስት ወደ ቸርነት፣ ከስግብግብነት ወደ መርካት፣ ከጠብ ወደ ዕርቅ፣ ከጥላቻ ወደ ፍቅር፣ ከጣዖትና ከባዕድ አምልኮ ወደ እውነኛ አምልኮ፣ ከሰይጣናዊ ሥራ (ጥንቆላ፣ አስማት፣ መተት ወዘተ..) ወደ መንፈሳዊ ሥራ፣ ከመለያየት ወደ አንድነት፣ ከመቅበዝበዝ ወደ መረጋጋት፣ ከልመና ወደ ሥራ፣ ከድንቁርና ወደ እውቀት፣ ከስንፍና ወደ ትጋት፣ ከኀዘን ወደ ደስታ፣ በአጠቃላይ ከዲያብሎስ ፍሬ ወደ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ለውጣችኋልን ?</u>

እሲቲ ራሳችሁ ፍረዱ! ወደ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ለውጣችሁ ለንስሐ አብቅታችሁ ያከበራችሁት ሰው አለን ? <u>እናንተ ግን እንደ ሥጋውያን መሪዎችና ሠራተኞች ክብርና ዝናን፣ ጥቅምንና ድሎትን ፣ ውዳሴንና ሽልማትን ፈለጋችሁ::</u> እኔን ረስታችኋል፤ ሕዝቡን ለነጣቂ ተኩላ ለዲያብሎስ አሳልፋችሁ ሰጥታችኋል፤ ከሕይወት ይልቅ ወደሞት ወስዳችኋል፤ እውነት እንዳትታወቅ በዘልማድ እንዲመላለሱ አድርጋችኋል፤ በክህደትና በዓመፃ ሕይወት ኖራችኋል፤ አንድ እግዚአብሔር እኔ ብቻ እንደሆንኩ ብታውቁም ማስተዋልና እኔን መፍራት በውስጣችሁ የሌለ ስለሆነ፤ «ሁሉም

ሃይማኖት (እምነት) ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባል» ብላችሁ ስለምታስቡ ለእናንተ ሁሉም እምነት ትክክል ነው፡፡ ሰዎች ወደ እውነተኛው ሃይማኖት እንዳይመለሱና ድኅነትን እንዳያገኙ ሆናችኋል፡፡ በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን፣ በቅድስና ሕይወት እንዳይመላለሱ እንቅፋትና ማሰናከያ ሆናችኋል፡፡ **<u>እውነተኞቹንና በሃይማኖት የጸኑትን ታሳድዳላችሁ፣ ታስገድላላችሁ፣ ታሳስራላችሁ፣ ትወነጅላላችሁ፡፡ ታድያ በሥጋዊ ወንበር ላይ ያሉት ከፍርድ የማያመልጡ ከሆነ፣ እናንተ ከነእርሱ በባሰ ሁኔታ እንዴት አይፈረድባችሁም! እጅግ ይፈረድባችኋል፡፡</u>** ለእውነተኛ ለበጎች እረኛ ቦታውን ትለቃላችሁ፡፡» ይላል ፡፡

ለዚህ ግሳጼና ዉሳኔ ምን አስተያየት አሎት?

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***፡ በዓለም ያሉ የአስመሳይ አገልጋዮች ሕይወትና ተግባር ይቅርና በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ያሉ ብዙ አስመሳይ አገልጋዮች ሕይወትና ተግባር በቅርበት ስለምናዉቅ ግሳጼዉ የሚያንስ እንጂ አይበዛም፡፡ በእግዚአብሔር ስም የሚነግድና የሚያስመስል ሰዉ እንደ ዓለማዉያኑ ለመመለስ ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም «አዉቃለሁ» ባይ ስለሆነና እንዲሁም ሕሊናዉን በማደንደን ስለሚያምፅ ነዉ ፡፡ ራሱ እግዚአብሔር ቤቱን ካላጸዳና በዓመፃ እምነት የሚመላለሱትንም በምሕረቱና በተአምራት እንዲሁም በቁጣዉ ወደ እዉነት ካልመለስ በስተቀር በሰዉ የሚሆን አንዳች ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራና ተአምር እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***፡ በክፍል ሦስት በገጽ 55-56 ላይ በኢትየጵያ በሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ ሰዎች ተገስጸዉበታል፡፡ እንዲሁም በዓለም መንግሥታት ላይ የተወሰነዉ ፍርድ ጸንቶባቸዋል፡፡ ይኸዉም፡

«እናንተ በሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ የማን ፈቃድ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ ነው? ለመሆኑ በእናንተ ኃይልና እውቀት በዚህ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ይመስላችኋልን? በውኑ የእናንተ መሳሪያና ወታደሮቻችሁ ከቀድሞው ሥርዓት መሪዎች መሳሪያና ወታደሮች በልጠው ድል ያደረጋችሁ ይመስላችኋልን? እውነቱ ግን ነገሥታትን የማፈራርቅ፣ የምሾም የምሽር፣ ከፍ ከፍ የማደረግ የማዋርድ እኔ ነኝ፡፡ ያለፈው መሪና ግብረ አበሮቹ የዓመፃና የግፍ ጽዋቸው ሞልቶ ስለፈሰሰ ነው እነሱን ሽሬ ወደ ወንበር ያመጣኋችሁ፡፡

እናንተም በተቀመጣችሁበት ወንበር ሕዝቡን በሚገባ መምራት፣ ከክህደት ወደ እምነት፣ ከጥላቻ ወደ መፈቃቀር፣ ከመለያየት ወደ አንድነት፣ ከርኩሰት ወደ ቅድስና፣ ከጣዖትና ባዕድ አምልኮ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከጠማማነት ወደ መልካምነት፣ ከክፋት ወደ ደግነት፣ ከተንኮል ወደ ቀናነት፣ ከሌብነት ወደ ጨዋነት፣ ከራስ ወዳድነት ወደ ወገን (ኢትዮጵያዉያንን ሁሉ) ወዳድነት፣ ገንዘብንና ስልጣንን ከማምለክ ወደ እኔን ማምለክ፣ በትዕቢትና ዓመፃ ሕይወት ከመመላለስ ወደ ትህትናና ታዛዥነት መመለስ ሲገባቸው ተቃራኒውን ፈጽማችኋል ፡፡

ይህም አልበቃ ብሏችሁ ሕዝቡን በጎሳ፣ በቋንቋ ከፋፍላችሁ እርስ በእርሱ እንዳይተማመን፣ ጥላቻንና መለያየትን ፈጥራችኋል፤ በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድናችሁ ሕዝቡን በረኃብና በችግር እየቀጣችሁ ራሳችሁን አበልጽጋችኋል፤ ኢትዮጵያዊነቱንም ገዝግዛችኋል፤ እውነተኛውን ሃይማኖት በክህደት እንዲሸፈን አድርጋችኋል፤ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የፈለጋችሁትን እያስቀመጣችሁ ሊመራችሁና ሊገስጻችሁ የሚገባውን እንደፈለጋችሁ እያሽከረከራችሁ የዓመፅ ስራ ተባባሪ አደረጋችሁ፤ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾችና እህትማማቾች እንዲለያዩ እንዲገነጠሉ አደረጋችሁ፤ ከዚያም አልፎ እርስ በእርስ በጦርነት እንዲፋጁ አደረጋችሁ፤ እናንተ ግን በተደላደለ ወንበር ላይ ተቀምጣችሁ ምስኪኑ ወገናችሁ ደሙ በከንቱ እንዲፈስ አደረጋችሁ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ በሀገሩ በነጻነት ተዟዙሮ እንዳይሰራ፣ እንዳይኖር «ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል ነው፣ ይህንን ቋንቋ ካልተናገርክ የስራ ድርሻ የለህም፡» እያላችሁ አድሎና በደል ፈጸማችሁ፤ በኢትዮጵያዊነቱ ያመነውንና ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወገኖቼ ናቸው ብሎ ያመነውን አሰራችሁ፣ ገደላችሁ፣ አሳደዳችሁ፣ ወነጀላችሁ፤ እረ የእናንተ ተግባር ምኑ ተነግሮ ያልቃል፡፡ በአጠቃላይ የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው ዲያብሎስ የሚያዛችሁን ተግባር ፈጸማችሁ፤ አስፈጸማችሁ ፡፡

እረ ለመሆኑ ኢትዮጵያን ታውቋታላችሁ ወይ? ያሳለፈችው ታሪክ ምንድን ነው? የቀደሙት አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ምን ሰርተው እንዳለፉ ታውቃላችሁ? ይህች ሀገር በማን እንድምትጠበቅ ታውቃላችሁ? ለእርሷ ጥብቅና የሚቆሙላት እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? አታውቁም፡፡ አውቃችሁስ ቢሆን ኖሮ በዚህ ተግባር አታልፉም ነበር፡፡ የክፉ ተግባር ፈጻሚ አትሆኑም ነበር፡፡

እረ ለመሆኑ በጎሳና በቋንቋ የከፋፈላችሁት ሀገር ከዛሬ መቶ ዓመት፣ አምስት መቶ ዓመት፣ አንድ ሺህ ዓመት፣ ሁለት ሺህ ዓመት፣ ... ወዘተ አሁን ሰው የሚኖርበት አካባቢ ሰው ይኖርበት ነበርን? ማን ነበር ያን ጊዜ? በደንና በአራዊት የተሞላ አልነበረምን? ታድያ ከየት አምጥታችሁ ነው «ይህ ያንተ ክልልና መንግሥት፣ ይህ ያንተ የጎጥ ወሰንና ድንበር ነው» ብላችሁ የከፋና የከረፋ ሐሳብ ፈጥራችሁ አንድ የሆነዉን የኢትዮጵያን ሕዝብ የከፋፈላችሁት? ይህስ ለመከፋፈያና የራሳችሁን መሰሪ ተግባር ለመፈጸም የተጠቀማችሁበት የቋንቋ ክፍፍል፣ ቋንቋዉ ራሱ የዛሬ አምስት መቶ፣ አነድ ሺህ፣ ሁለት ሺህ ዓመት ነበረ ወይ? ለመሆኑ የሰዎች ቋንቋ የተለያየበት ምክንያት ታዉቃላችዉ?

ካላወቃችሁ እንግዲህ እወቁት፤ ሰዎች በትዕቢት፣ በክፋት፣ በዓመፃ ተሞልተዉ እኔን ሲገዳደሩ ነዉ በኃጢአታችሁ ምክንያት ቋንቋቸዉን የደበላለኩና በአራቱም ማዕዘን የበታተንኳቸዉ፡፡ የጽድቅ ዋጋ እንዳልሆነ አወቃችሁን? አሁን ደግሞ በምሕረት ዘመን ሰዎች ወደ አንድ ቋንቋ እንዲመጡ፣ እንዲግባቡ ፣ እንዲዋሐዱ፣ አንድ እንዲሆኑ በማደርግበት ጊዜ እናንተ ደግሞ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚዎች ናችሁና የእኔን ተቃራኒ ተግባር ትፈጽማላችሁ!

<u>በዉኑ በዚህ የሚቀጥል ይመስላችኋልን? ይህን የተመረጠ ሕዝብ እየሸነገላችሁ፣ እያታለላችሁ፣ ሕሊናዉን እንዲሸጥ እያደረጋችሁ፣ ለጥቅምና ለሥልጣን ራሱን እንዲክድ</u>

እያደረጋችሁ የምትኖሩ ይመስላችኋልን? በቃ የእናንተም የዓመፃና የርኩሰት ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነዉ:: የዘራችሁትን የክፋት፣ የተንኮል፣ የዘረኝነት፣ የጥላቻ፣ የመለያየት፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያችሁን ታጭዳላችሁ:: ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ:: በቅንነትና በእዉነት ለሚመላለሱ፣ የኔን ፈቃድ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለድንግል ማርያም ምርጥ ባለሚሎች ሥጋዊዉንም፣ መንፈሳዊዉንም ወንበር አሳልፌ እሰጣለሁ:: የጽድቅ ፍሬ ያፈሩበታል:: በረኃብ፣ በችግር፣ በልመና፣ በጦርነት፣ በጉስቁልና በዓለም ዘንድ እንድትታወቅ ያደረጋችኋትን «ሀገረ እግዚአብሔር» የተባለች ምስጢር አገሬ፣ የቅድስት ድንግል ማርያም አስራት አገር፣ የቀደመ ክብሯ ይመለሳል:: ከራሷ አልፋ ለዓለም ብርሃን ትሆናለች:: ልጆቿን በአራቱም ማዕዘን ትሾማለች:: በጎቼን በመልካም ሕይወት ታኖራለች::

እናንተ ግን « ሕዝቡን በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በክልል ከፋፍለናል ከእንግዲህ በኋላ ወደ አንድነት እንምጣ ብሎ አገራዊ ራእይ ይዞ የሚነሳ አካል ቢመጣ ሕዝቡ እርስ በእርስ ስለሚተላለቅ ማንም አይቀበላቸዉም፤ ከተቀበሏቸዉ ደግሞ እንገነጠላለን፤ እናስገነጥላለን» ብላችዉ የዚህች አገር መጥፋት፣ የሕዝቡን መተላለቅ ስሜት ሳይሰጣችሁ፣ ተስፋችሁ ምድራዊ የሆነ፣ ተግባራችሁና ሐሳባችሁ ተንኮልና ክፋት የሞላዉ የዓመፃ ልጆች፤ እናንተ እንደምትመኙትና እንደምታስቡት ይህች አገር ለጥፋትና ለዉድቀት አትዳረግም:: በቅዱሳን ጸሎት የምትጠበቅ፣ በሰማያዊ ሠራዊት የተከበበች፣ ባለ አስራቷም ሁሌ በፊቴ የምትቆምላት ስለሆነ ሊያጠፏት የሚነሱ ሁሉ ይጠፋሉ ::» **ይላል::**

ለዚህ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የእግዚአብሔር ፍርድ እያየነዉ ስለሆነ ከእኛ የሚጠበቀዉ መጨረሻቸዉን በትዕግስትና በጽናት እንዲሁም በብሩህ ተስፋ መጠባበቅ ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በዚሁ ምዕራፍ በገጽ 56-58 ላይ በኢትዮጵያ ዉስጥ በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡትም በተጨማሪ ተገስጸዋል:: ይኸዉም:

«እናንተ በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ፤ ማንን እያገለገላችሁ ነዉ? ለመሆኑ የምታመልኩት ማንን ነዉ? ለመሆኑ ምእመናንን ታዉቃላችሁ? ክርስትና በምን መልክ ለአሁን ዘመን ተላልፋ እንደመጣች ታዉቃላችሁን? አታዉቁም:: ብታዉቁም አላስተዋላችሁም:: ብታስተዉሉም የሥጋ ምኞታችሁና ፍላጎታችሁ አሸንፏችሁ እኔን ባለመፍራት ሕሊናችሁን ሸጣችኋል፤ የድፍረት በደል ፈጽማችኋል:: በጎቼ እረኛ የሌላቸዉ ሆነዉ ተቅበዝብዘዋል፤ ትእዛዜንና ሕጌን ሽራችኋል፤ ምእመናን በትእዛዜና በሥርዓቴ እንዳይመላለሱ ማሰናከያና እንቅፋት ሆናችኋል:: የራሳችሁ በደልና ኃጢአት አልበቃ ብሏችሁ እዉነተኛ አገልጋዮችን አሰራችሁ፣ አሳደዳችሁ፣ ገደላችሁ፣ አንከራተታችሁ፣ ወነጀላችሁ::

ክርስትናን መስራች የሆንኩ አምላክ፤ አምላካዊ ባሕርዬን ዝቅ ያደረኩት፤ ከእናቴ ከእናታችሁ ከእመቤታችሁ ከድንግል ማርያም ሥጋ ተዋሕጄ ሰዉ ስሆን፣ ከመወለዴ ጀምሮ እስከ ዕርገቴ ድረስ

የዚህ ዓለም ክብርና ጥቅም ፈልጌአለሁን? ስወለድ እንደ ተራ ደሀ ሰዉ በከብቶች በረት ዉስጥ፣ ከዚያም እንደ አቅመ ቢስ ሄሮድስን ሸሽቼ ወደ ግብፅ ተሰደድኩ፣ እንደ ችግረኛ በረኃብና በጥም በረኃ ለበረኃ ተንከራተትኩ፣ ከኃጢአት በቀር ፍጡር የሚያደርገዉን አደረኩ፣ ዘመን የማይቆጠርልኝ ሥጋ በመልበሴ ዘመን ተቆጥሮልኝ ሠላሳ ዓመት ሲሞላኝ ማስተማር ጀመርኩ፣ የማስተምረዉን በተግባር እየፈጸምኩ አሳየሁ:: ትምህርቴና ተግባሬ ዓላማዉ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ፣ ከኃጢአት ተግባር ወደ ጽድቅ እንዲመለሱ፣ በቅድስና ሕይወት ተመላልሰዉ ከሞት በኋላ ያለዉን ሕይወት ተስፋ አድርገዉ ራሳቸዉን ለሰማያዊ መንግሥት እንዲያዘጋጁ ነበር::

በመጨረሻም ፈቃዴ ስለሆነ፤ ልክ እንደናንተዉ በእዉነተኛዉ የሙሴ ወንበር ላይ የተቀመጡት የአይሁድ ካህናት፣ ጸሓፍት ፈሪሳዉያን «የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን፤ ለሕጉና ለትእዛዙ ቀናዒ ነን፤ ለሥርዓቱና ለፍርዱ ጥብቅና እንቆማለን፤» የሚሉ፤ ነገር ግን በአንደበታቸዉ እንጂ በተግባር የማይፈጽሙ፤ ባዶ ቀፎ የሆኑ፤ ዉስጣቸዉ ተንኮልና ዓመፃ፣ ትዕቢትና ቅናት የሞላባቸዉ ፍጡሮቼ፤ እኔዉ አምላካቸዉንና ፈጣሪያቸዉን ካለ በደሌ እንደበደለኛ፣ ካለ ወንጀሌ እንደወንጀለኛ፣ ካለ ኃጢአቴ እንደ ኃጢአተኛ ወንጅለዉኝ፤ የሐሰት ምስክር አዘጋጅተዉ፣ እዉነተኛዉ ፈራጅ የሆንኩትን በእኔ ላይ የሞት ፍርድ አስፈረዱብኝ፤ ሰደቡኝ፣ ተፉብኝ፣ ገረፉኝ፣ ዘበቱኝብ፣ አንገላቱኝ፣ እንደ ዋና ወንጀለኛ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉኝ:: ታድያ ሁሉን ማድረግ ስችል በትዕግስትና በአኮቴት ነዉ ይህን ከሕሊናችሁ በላይ የሆነዉን መከራ የተቀበልኩት::

ታዲያ ይህን ሁሉ ያደረኩት የሰዉ ዘር ሁሉ እንዲድኑበት ክርስትናን ለመመስረት ነዉ:: እኔ የመሰረትኳት ክርስትና የተስፋፋችሁ በቀላሉ አልነበረም:: ሐዋርያቶቼና ደቀመዛሙርቴ የእኔን ፈለግ ተከትለዉ የዚህ ዓለም ሥልጣን፣ ጥቅም፣ ክብር፣ ዝና ሳያሸንፋቸዉ ስለ እዉነት ተደበደቡ፣ ተገረፉ፣ ተሰደዱ፣ ተቃጠሉ፣ ተሰቀሉ፣ ለአራዊት ተጣሉ፣ በአጠቃላይ የተለያየ መከራ ደረሰባቸዉ፤ እዉነትን ግን ለአበዉ ሐዋርያት አስተላለፉ::

አበዉ ሐዋርያትም እንዲሁ የተለያየ መከራ ተቀብለዉ ለሰማዕታት አስተላለፉ:: ሰማዕታትም የተለያየ ጸዋትዎ መከራ በመቀበል ለአበዉ ሊቃዉንት፣ ለመምህራን አስተላለፉ:: እስከ አምስተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ አንዲት ሃይማኖት የነበረችዉ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፤ ልክ እንደናንተዉ ለሥጋ ፈቃዳቸዉ ያደሩ፤ እንደ ሥጋዊ አስተሳሰባቸዉ ሕዝብን ለሚመሩ መሪዎች ሕሊናቸዉን የሸጡ፤ የሃይማኖት መሪዎች የተባሉ ባሕርዬን ለሁለት ከፈሉ:: እኔ እግዚአብሔር ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኛለሁ:: ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኜ ነዉ ሰዉ የሆንኩት:: ታዲያ ሁለት ባሕርይ ብሎ መፈላሰፉ ኬት መጣ? እነዚህ ለሁለት የከፈሏት በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ የተቀመጡ ልክ እንደ እናንተ ክርስትና ያለፈችበትን መከራ የዘነጉ፤ ለሥጋዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ ጥቅም ቦታ የሰጡ፤ በዘመድ አዝማድ የተተበተቡ ስለሆነ እንዴት ስለ እዉነት ይቁሙ!?

የሃይማኖት አባቶች ስለ እዉነት በአንድነት ቆመዉ ክርስትናን በአራቱም ማዕዘን ሊያስፋፉና ሰዎችን ከሞት ወደ ሕይወት መመለስ፤ ከክህደት ወደ እምነት ማምጣት ሲገባቸዉ እርስ በእርስ እየተከፋፈሉና እየተወጋገዙ ክርስትናን አዳከሟት፤ አቀጨጯት፡፡

በዚህ ምክንያት በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ማለቂያ ላይ በራሱ ምኞትና ሐሳብ ተነሳስቶ ለፈጣሪ የቀና መስሎት ሕሊናዉን ለዲያብሎስ ማደሪያ ያደረገ ሐሰተኛ ነብይ፤ ክህደትን አስፋፋ፤ ክርስትናን ለማጥፋት ዘመቻ አደረገ፡፡ እኔ አልፋና ያሜጋ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ የሆንኩትን «ኢየሱስ ነብይ ነዉ፤ እኔም ከፈጣሪ የተላኩ ነብይ ነኝ » አለ በድፍረት፡፡ በዚህ ክህደት ምክንያት ትዉልዱ ለአንድ ሺህ አራት መቶ ዘመን በላይ በሞት ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ፡፡

በአሥራ አንደኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሁለት ባሕርይ ብለዉ ከከፈሉኝ ወገኖች (ኦርቶዶክስ) ከተባሉት «መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ነዉ የሰረጸዉ » በማለት ተከፋፍለዉ ከኦርቶዶክስ ካቶሊክ ተፈጠረ፡፡ ወደ መጀመሪያዋ ሃይማኖት «አንድ አካል፤ አንድ ባሕርይ » ከምትለዉ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ነዉ የሚሰርጸዉ ብላ ከምታምነዉ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መመለስ ሲገባቸዉ ሌላ ፍልስፍና ፈጠሩ ፡፡

ታዲያ ይህ መከፋፈል በእዉነት ስለ እኔ በመቅናትና እዉነትን ለሕዝብ(ለምእመን) ለማሳወቅ ሳይሆን ለሥልጣን፣ ለክብር፣ ለጥቅም፣ ለዝና ነበር፡፡ ይህም ክፍፍል ክርስትናን አዳከማት፤ አቀጨጫት እንጂ የሰዉ ዘሮች ወደ እዉነት እንዲመጡ አላደረገም፡፡

የዚህች ክርስትና ፈተናዋ አልበቃ ብሎ በአሥራ ስድስተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ላይ የካቶሊክ ተከታይ የነበረዉ መነኩሴ ሐሰተኛ ወንጌላዊ፤ የሥጋ ፈቃዱና ምኞቱ አሸንፎት ዉስጡ ዓመፃ የሞላበት ነበርና ለፕሮቴስታንት የክህደት እምነት መሰረት ጣለ፡፡ እኔ የሁሉ ፈራጅ ዳኛ የሆንኩትን፣ ከኔ በላይ ማንም የሌለዉን፣ ፈጣሪ አምላክ የሆንኩትን «አማላጅ »ነዉ በማለት አስካደኝ፤ አሰደበኝ፡፡ ከዚያም አልፎ የእናቴን የእመቤታችሁን የድንግል ማርያምን ክብር አዋረደ፣ አቀለለ፡፡ የቅዱሳንን ምልጃና ክብር አዋረደ፣ አቀለለ፡፡ በዚህ ክህደትና መናፍቅነት ምክንያት ትዉልዱ ለአምስት መቶ ዘመን በላይ በሞት ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ፡፡

<u>እንግዲህ የክህደቱና የመናፍቅነቱ ዘመን ይበቃችኋል፡፡ ነጻ ሕሊና የምታመዛዝኑበትና የምታስቡበት ተሰቷችሁ ነበር፡፡ ነገር ግን በቅን ሐሳብና በመልካም ሕይወት ተመላልሳችሁ እዉነትን ስላልፈለጋችሁ ድኅነትን ከሚሰጠዉ እዉነተኛ ሃይማኖትና ቅድስት ቤተክርስቲያን ተለይታችኋል ፡፡ አሁን ግን በሐሰት የተሞላዉ የክህደትና የመናፍቅነት እምነት ተሽሮ እዉነት ትገለጻለች፡፡ የሐሰት መንፈሳዊ ወንበራችሁ ይሻራል፡፡ በእዉነተኛ ወንበር ይተካል፡፡ ሞትና የጨለማ መንገድ ይቀራል፡፡ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ሃይማኖት የሁሉ መሪ ትሆናለች፡፡</u>

<u>እናንተ በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ ሆናችሁ በቀጥተኛዋ ተዋሕዶ ሃይማኖት በቅድስት ቤተክርስትያን ስም የነገዳችሁ፤ ያስመሰላችሁ ከላይ እስከ ታች ያላችሁ አስመሳይ አገልጋዮች፤ በጎቼን</u>

በሚገባ አልጠበቃችሁም፤ አላገለገላችሁምና ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ:: በቅንነትና በእዉነት ለሚያገለግሉ ለምርጥ ባለሟሎቼ ለድንግል ማርያም ምርጥ ልጆች ወንበራችሁ ትሰጣለች:: እናንተም የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ::» **ይላል::**

ለዚህ ግሳጼና ዉሳኔ ምን ምላሽ አሎት:

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ: የእግዚአብሔር ፍርድ እያየነዉ ስለሆነ ከእኛ የሚጠበቀዉ የአስመሳይ አገልጋዮች መጨረሻቸዉን በትዕግስትና በጽናት እንዲሁም በብሩህ ተስፋ መጠባበቅ ነዉ::» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ምዕራፍ ሁለት

« <u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ ማሳሰቢያ በሚል ዉስጥ በገጽ 11 ላይ ዓለምን በነጥብ ደረጃ እንደሚያዩትና ምድራዊ እድሜዎም የዐይን ቅጽበት ያህል እንደማይሆን ነዉ የገለጹልን፡፡ ይህን ቢያብራሩልን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በመጀመሪያ ለማሳወቅ የምፈለገዉ እኔ እንደ ማንኛዉም የአዳም ዘር ሰዉ ነኝ፡፡ በአፈጣጠሬ ከማንም አልበልጥም፤ አላንስም፡፡ እያንዳንዱ ሰዉ በሕያዉ ነፍሱ አንድ አይነት የሆነ፤ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍስ ያለዉና በነጻ ፈቃዱና ምርጫዉ መመላለስና መኖር የሚችል ነዉ፡፡ ሰዎች የሚለያዩት በሥጋ በተገለጹበት አካላቸዉ፣ በመልካቸዉ፣ በቁመታቸዉ፣ በጾታቸዉ ሲሆን፤ ይህም ልክ የምንለብሰዉ ልብስ ቀለሙና መጠኑ የሚለያይ ከሆነ ያዉ ጨርቅ ጨርቅ ቢሆንም በሥጋዊ ዐይን በሚታየዉ ቀለምና መጠን እንደሚለያይ ሁሉ፤ የእያንዳንዱ ሰዉ የተገለጸበት ሥጋ ያዉ በመጨረሻ አፈር ዉስጥ የሚገባ በስባሽ ቢሆንም፤ በሥጋዊ ዐይናችን በምናይበት ወቅት በመልክና በመጠን ይለያያል፡፡ ይህም የሚሳየን እኛ ማለት የተገለጽንበት ሥጋ ሳይሆን በግንባራችን ፊት ለፊት በአንጎላችን ዉስጥ በረቂቅ አካል የምትገኘዉና ለዚህ ለተገለጽንበት ሥጋ ሕይወትን ሰታ እርሷም በሥጋችን ተገድባ የምትገኘዉ፤ የማትሞት፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የማታልፈዉ ሕያዉ ነፍሳችን ናት፡፡ ይህ ሥጋችን፤ ነፍሳችን ስትለየዉ በድን የሚሆነዉ ሕይወትን ከነፍሳችን ስለሚያገኝ ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ እንደ ምሳሌያዊ ፍጥረትነቱ የሚሆን፤ ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያልፍ የሚችል ነዉ፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ዓለምን በነጥብ ደረጃ ልመለከታት የቻልኩት በነፍሴ ባሕርይ እንጂ ይህ ሥጋዊ ዐይንማ ከዚህ ምድር ዉጭ አይደለም በዚህ ምድር ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ፍጥረታትና ዓለማትን ማየት አይችልም፡፡ ነፍሴ ከዚህ ምድር ዉጭ ያለዉን ዓለምና አማናዊ ሕዋን እግዚአብሔር በፈቀደላት መንገድ እንድትረዳና እንድታስተዉል ስላደረገ ነዉ ይህን ዓለም ከእርሱ ዉጭ ካለዉ ዓለም ጋር ሲነጻጸር ነጥብ እንደማይሞላ መሆኑን በሚገባ ያስተዋልኩትና የተረዳዉት፡፡ እድሜዬንም፤ ከዚህች ምድር በሥጋ ሞት ስንለይ ሁላችንም ትንሣኤን የምናምንም ሆነ የማናምንም ሰዎች ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተገኘች(የሰረጸች) ስለሆነችና ከመኖር ወደ አለመኖር ስለማታልፍ፣ ሕያዉ ስለሆነች፣ በምድር ከተገለጸችበት ሥጋ ስትለይ በረቂቅ አካል(በምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገድባ እንደ መናፍስት ሆና ስለምትገለጽና በተዘጋጀላት ቦታ ስለምትኖር፤ የማትኖርበት ጊዜ የለምና፣ የዚህች ምድር እድሜዋ የማትኖርበት ጊዜ ለሌለዉ ዘመን ሲካፈል ሆነ ሲነጻጸር የዐይን ጥቅሻ ጊዜ እንኳ ስለማይሆን ነዉ ምድራዊ እድሜያችን የዐይን ቅጽበት ጊዜ እንኳ አይሆንም በማለት የገለጽኩት፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አንድ በምዕራፍ ሁለት በገጽ 45 አንቀጽ ሁለት ላይ ዲያብሎስ ሲያላግጥብን፡

«እናንተ የአዳም ዘሮች ትዝብቴን ልንገራችሁ:: ይኸዉም የኛን ያህል ኃይልና ብቃት ሳይኖራችሁ ሁሉን እንደምታደርጉ እንደፈለጋችሁት መሆን እንደምትችሉ ትደነፋላችሁ፣ ተፈጥሮን እንቆጣጠራለን እያላችሁ ትታበያላችሁ፣ እንዲህ ይሆናል እያላችሁ መፈክር ታሰማላችሁ:: አንዳንዴ እኛ ሰይጣናት እርስ በእርስ ስንጫወት <u>«እነዚህ የአዳም ዘሮች በዚህ ግዙፉ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ በተላበሰዉ ሥጋ ተገደቡ እንጂ እንደኛ በረቂቅ አካል ተገልጸዉ ቢሆን ኖሮ በቅጽበት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ይችላሉና ፈጣሪን ከሰማያት ዉስጥ እናዉርድ»</u> <u>በማለት ሰማያዊ ጦርነት ያዉጁ ነበር እንላለን:: አንዳንዴ ደግሞ በበሽታ ስትያዙ፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ላይ ሆናችሁ ዐይናችሁ ክርትት ክርትት ሲል፤ በተቃራኒ ኃይል ተሸንፋችሁ ስትማረኩና ባለጊዜነታችሁ ተሽሮ የዘራችሁትን ስታጭዱ ኩምሽሽ ብላችሁ ስንመለከታችሁ «አይ የሰዉ ጥጋብና እብሪት! ያ የሚደነፋና የሚታበይ አንደበትና ሕይወት ወዴት ሄደ?» እንላለን::</u> » በማለት ለገለጸዉ ያሉትን አስተያየት ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር በዚህ መልኩ እዉነታዉ እንዲገለጽ ያደረገዉ፤ እኛ ሰዎች እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ ዲያብሎስንና የእርሱን አገልጋይና ፈቃድ ፈጻሚዎችን ስለምንሰማ ነዉ ዲያብሎስ እያላገጠብን እዉነታዉን እንድናዉቅ ያደረገዉ:: የተባለዉ ደግም እዉነት የሆነ በየዕለት ሕይወታችን የሚታይና ካለፉትና ከራሳችን ሕይወት መማር ያልቻልን መሆናችንን የሚገልጽ ነዉ::

ከዚህ ጋር አንድ ለመግለጽ የምፈልገዉ እኛ ሰዎች ለሁለት ሺህ ዘመን ያህል ስለ ነገረ መስቀሉ እየተነገረና እየተሰበከ እንኳ ምርጫችንን አላወቅንም፤ አቋማችንንም አላስተካከልንም:: ይኸዉም አሁንም «ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ግፍ፣ በደል፣ ጭከና ... ወዘተ የሚፈጽመዉ በርባን፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ ታላቅ ነዉ፣ ንጹህ ነዉ፣ ቅዱስ ነዉ፣ መልካም ደግ ርኅሩኅ ነዉ፣ እርሱ ይንገሥብን፤ እርሱ አባት ይሁነን፤ እርሱ ይምራን፤ እርሱ ያስተዳድረን፤ እርሱ ይመግባን» እያልን የዲያብሎስ እንደራሴ የሆኑት ሥጋዉያን መሪዎች፣ ባለሟሎች የሆኑት ባለሥልጣናት፣ ዉዶች የሆኑት ካድሬዎች እንዲነግሡብን፣ አባት እንዲሆኑን፣ እንዲመሩን፣ እንዲያስተዳድሩን፣ እንዲመግቡን በመምረጣችንና እርሱ እግዚአብሔር እንዳይነግሥብን፣ አባት እንዳይሆነን፣ እንዳይመራን፣ እንዳያስተዳድረን፣ እንዳይመግን በማድረጋችን ነዉ::

እግዚአብሔር አሁንም በእኛ ተስፋ ሳይቆርጥ ለተመረጡት ሲል ዓመፀኞችን፣ ከሃዲያንን፣ ርኩሰት ፈጻሚዎችንና አስፈጻሚዎችን፣ ትዕቢተኞችን፣ እብሪተኞች ፣ ክፋትና ተንኮል ጥላቻና በቀል የሞላባቸዉን፣ የዲያቢሎስ ስራ አስፈጻሚዎችን በምድር ጭምር ዋጋ እንዲከፍሉ እያደረገ በተለያየ መንገድ በቁጣዉ ወደተዘጋጀላቸዉ ቦታ ሲጠራና እርሱን መፍራት ያለባቸዉን አገልጋዮቹንና ባለሟሎቹን እንዲሁም እንደራሴዎቹን ወደ ወንበር አምጥቶ መልካም የሆነዉንና የእርሱን ፈቃድ ለማስፈጸም ሲነሳ ደግሞ፤ «ለምን እነዚህን ዓመፀኞች፣ ግፈኞች፣ ትዕቢተኞ፣ እብሪተኞች፣ አድሎና በደል ፈጻሚዎች፣ ርኩሰት ፈጻሚዎችንና አስፈጻሚዎች፣ዘረኞችንና ጎጠኞችን፣ ባጠቃላይ የዲያብሎስ አገልጋዮችንና ወኪሎችን በሥጋ ሞት ጠራሃቸዉ፤ ነጠከን፤ ጨከንክብን::» እያልን ከእነሱ የባሰ ጨካኝና ግፈኛ እንዲታዘዝብን እየተፈታተነዉ እንገኛለን::

ታዲያ እንደ ምርጫችን እግዚአብሔር ሲሰጠን እግዚአብሔርን ማማረር የለብንም፡፡ በጸጋና በአኮቴት የምርጫችንን መራራ ፍሬ መጠጣት ነዉ ያለብን፡፡ ምክንያቱም ክብር የማይወድልን ስለሆነና ምርጫችን ከእግዚአብሔር ይልቅ ዲያብሎስንና አገልጋዮቹን በማድረጋችን ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ግን እንደ እኛ ሳይሆን ስለተመረጡት ሲል ዓመፀኞችንና የእነርሱ ተከታዮችን በዚህ ምድር ዋጋ እንዲከፍሉ አድርጎ፤ መልካም ሕይወትን፣ የምንመራበትንና የምንተዳደርበት የጽድቅን የቅድስና ሕገ መንግሥት፣ እንዲሁም የብርሃን ሥርዓትን በቅርቡ ስለሚያዘጋጅልን፤ እኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዚህ እየተጽናናን በትዕግስት፣ በጽናት፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በእዉነተኛ ንስሐ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ልንጠባበቅ ይገባል፡፡

እዚህ ላይ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ ዲያብሎስ በእኛ ኢትዮጵያዉያን ላይ እንዴት አድርጎ እያለገጠብን መሆኑን የሚያሳየዉን በክፍል አንድ በምዕራፍ ሦስት በገጽ 57-59 ላይ ያለዉን አቀርባለሁ፡፡

«እናንተ ኢትዮጵያዉን በችግርና በመከራ ዉስጥ እያላችሁ እንኳ «እግዚአብሔርን» ብላችሁ ሙጭጭ ብላችኋል፡፡ ታዲያ እንደ አሜሪካን፣ ጃፓን፣ ቻይና፣ ህንድ፣አዉሮፓ፣ ኤሽያ፣ መካከለኛዉ ምስራቅ ..ወዘተ አገራት በሥጋችሁ ብትበለጽጉማ ለእኔ አንዳች ቀዳዳ እንዳማትከፍቱልኝና ርኅራኄ እንደማታሳዩኝ አዉቃለሁና፤ ለዚህም ነዉ በችግር እየገባዉና በምርጥ እንደራሴዎቼ አማካይነት ከሕይወት መንገድ እያወጣሁ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ያሰለፍኳችሁ፡፡ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሬ ዉስጥ እንደማዉላችሁ ተገንዝባችሁ ከወዲሁ እጃችሁን ብትሰጡኝና የተሟላ አምልኮቴን ብታቀርቡልኝ የተሻለ መሆኑን በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ ፡፡

የኔ ተስፋና ምኞት የእናንተን ዉድቀትና ጥፋት ማየት ነዉ፡፡ ምክንያቱም እስከአሁን ለእኔ ያስቸገራችሁና እጅ አንሰጥም ብላችሁ የምትጋደሉት እናንተና አገራችሁ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ለእኔ አስቸግረዉኝ ለእናንተ ጥብቅና የሚቆሙ ከእናንተዉ ወተዉ በቅድስና ሕይወት የሚመላለሱት ብቻ ሳይሆን ሰማያዉያን ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነብያትና ሐዋርያት ጭምር በመሆኑ ነዉ አቅመቢስነቴና ልምሾነቴ እየባሰ ኃይሌ እየተዳከመ ያለዉ፡፡ ከሁሉ በላይ ያማረረችኝና ፍዳዬን የምታሳየኝ፤ ስሟ እንኳ እንዲነሳ የማልፈልገዉ ያች የምትመኩባት የአደራ እናታችሁ «ቅድስት ድንግል ማርያም» የምትባለዉ ናት፡፡ ከግዛቴ ወዴት እንድሄድላት ነዉ የምትፈልገዉ? የአዳም ዘሮች ራሳቸዉ መተዉ «ንጉሣችን ሁን፤ ፈቃድህን እንፈጽምልሃለን» አሉኝ እንጂ፤ አንድ ሰዉ እንኳን አስገድጄ «ይህን አድርግ፤ ይህን አታድርግ» አላልኩም፡፡ ሁሉም በሥጋዊ ስሜቱ እነደእንስሳ እየሆነ ነዉ እንጂ ይኸዉ በ7503 ዘመን ቆይታዬ እስኪ «ሰይጣን መሳሪያ ደግኖብኝና አስገድዶኝ ነዉ ኃጢአት የሰራዉት» የሚል አንደሰዉ ከተገኘ ይመስክርብኝ?

እንዲያዉም እኔ የማላዉቀዉን የርኩሰት ድርጊት እየፈጸሙና እየተሳደቡ ተቸግሬያለሁ፡፡ ምክንያቱም በሚሰሩትና በሚናገሩት ሁሉ «ሰይጣን ነዉ እንዲህ ያስደረገኝ» እያሉ፤ በእኔ ስለሚያላክኩና ፍዳዬን ለማባስ እለት እለት ስለሚወነጅሉኝ ነዉ፡፡ ዞሮ ዞሮ እዉነታዉ በመጨረሻዉ

ፍርድ ቀን ይታወቃል። አሁን ግን እናንተ ለሰዉ ልጆች በኀዘንና በምልጃ ጥብቃን የምትቆሙ ሁሉ፤ እነዚህ የአዳም ዘርን ከኔ አምልኮትና ሥርዓት ለዩልኝ። እኔ በራሴ ግዛት በነጻነት መኖርና ራሴን በራሴ ማስተዳደር ነዉ የምፈልገዉ። የአዳም ዘርን ሁሉ ለማስተዳደር ይኸዉ ለዘመናት ስወጣ ስወርድ ኖሬያለሁ። እናንተ የአዳም ዘሮች፤ እባካችሁ አሁን እንኳ ትንሽ ልረፍበት፤ ራሳችሁን በራሳችሁ አስተዳድሩ፤ ከፈለጋችሁ ንጉሣችሁን እግዚአብሔርን፤ ንግሥስታችሁን እናቱን ድንግል ማርያምን፤ ባለሥልጣኖቻችሁን ቅዱሳን መላእክትን ጻድቃንን አድርጉ። ካለፍላጎቴና ካለስራዬ ለእኔ የሰጣችሁኝን ሹመትና ሥልጣን ከኔ አንሱልኝ።

«አይ ምርጫችን አንተን ነዉ፤ ካላንተ አይሆንልንም» የምትሉ ከሆነ ደግሞ፤ እኔ በምርጫ አምናለሁና፤ ድካም ቢሰማኝም ሌላ ብዙ የምሰራዉ ስራ ቢኖርም፤ «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» እንደምትሉ እኔም ለእናንተ ያልሆነ ጉልበትና ጊዜ አይኑር እያልኩ፤ በተጠናከረ መልኩ መከራና ችግር፣ ስቃይ፣ ረኃብ፣ በሽታ፣ ስደት፣ ጦርነት፣ ረብሻ፣ ጭንቀት፣ ብጥብጥ፣ ፍንዳታ፣ ጎርፍ፣ አዉሎ ንፋስ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ **<u>የኒዉክለር ጥፋት</u>**፣ ባጠቃላይ ልክ የሚያስገባችሁና ሥርዓት የሚያሲዛችሁን እንዲሁም ምርጫችሁን እንድታስተካክሉ የሚያደርገዉን መልካሙን ስጦታና አገልግሎቴን ለማቅረብና ለማስቀረብ በታላቅ ትዕቢት በፊታችሁ እቆማለሁ።

ታድያ እናንተ ቅዱሳንን፣ ድንግል ማርያምን ለማቅለልና ለመሳደብ እዉነተኛዉን እግዚአብሔር ለማስካድ በተለያየ የእምነት ድርጅቴ ስልጠና የወሰዳችሁ ሁሉ፤ የሰለጠናችሁበትን ዓለማ በሚገባ ተረድታችሁ ለታላቁ የዓመፃና ክህደት ተግባር እንድትሰለፉ ከወዲሁ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ። እኔጋ መገለባበጥና መመሳሰል የሚባል ነገር ስለማይሰራ ላዘጋጀዋችሁ ክብር እንድትበቁ ሕሊናችሁን ከመካድና ከመሸጥ ጀምሮ ደማችሁን እስከመገበር ድረስ ወደ ኋላ እንዳትሉ ከአደራ ጭምር ነዉ የማሳስባችሁ። ድል ለሰፊዉ የዲያብሎስ ባሪያና እንደራሴ መንግሥታት፣ ባለስልጣናት፣ ካድሬ ሁሉ። » ይላል ዓመጸኛዉና ትዕቢተኛዉ ጨካኙ አረመኔዉ የጨለማ ገዥ ዲያብሎስ ከባሪያዎቹ ሰይጣናት ጭምር።» ይላል።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: «የጨለማዉ ገዥና ተግባርና ንግግር» በሚል ከተጻፈዉ የሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ ያልነበረ አሁን የገባ ቃል አለ። ይኸዉም ከላይ የተገለጸዉ **<u>ኒዉክለር</u>** የሚለዉ ነዉ። ያኔ ለምን አልገባም? አሁን ለምን ሊጨመርበት ቻለ? ምክንያቱም በእግዚአብሔር መልእክት ላይ ማንም ሊቀንስ ሆነ ሊጨምር ወይንም ሊያሻሽል አይችልምና።

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በእዉነቱ ያኔ ያልገባበትን ምክንያት እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ። ያኔም ሊያጽፈኝ ይችል ነበር። አሁን እንድጨምርበት ያደረገዉ የዓመፃ ልጆች የዘሩትን ፍሬ ማጨጃቸዉ ስለደረሰ ሊሆን ይችላል። ተጨማሪ የጨመርኩት በበፊቱ መልእክት ላይ ሳይሆን አሁን በሦስተኛዉ መልእክት ላይ ነዉ። ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ እግዚአብሔር ያጻፈኝ በእኔ እዉቀት ደረጃ ስለሆነ የተሻሉ ቃላትና አገላለጽ እንዲሁም ትክክለኛ ሥርዓት ነጥብና ፊደል ቢገባ ጽሑፉን ያሳምረዋል እንጂ አገላለጡ ላይ ሆነ መልእክቱ ላይ ለዉጥ

አያመጣም:: መቀነስ ሆነ መለወጥ እንዲሁም ማሻሻል የማይቻለዉ «ይህ እከሌን ቅር ያሰኛልና ይወጣ፣ ይህ ደግሞ ተቀባይነት እንዲያገኝ በዚህ መልኩ ይሻሻል? ... ወዘተ» ቢባል ነዉ:: ምክንያቱም ማንም ይሁን ማን ከእግዚአብሔር አይበልጥምና በጸሐፊዉ እዉቀት አድርጎ እግዚአብሔር ያስተላለፈዉን መልእክት ፍጹም ከእግዚአብሔር የሆነ አገልጋይ ሆነ አማኝ ሊለዉጥ፣ ሊቀንስ፣ ሊያሻሻል አይችልም:: ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሊያስፋፋዉና ሊያብራራዉ እንዲሁም ሰዋስዉን፣ ሥርዓተ ነጥቡን፣ ፊደላቱን፣ ቃላቱን የበለጠ ሊያሳምረዉና ሊያስተካክለዉ ይችላል::

ለምሳሌ ከዚህ በፊት ነቢይ ተብሎ መጻፍ የሚገባዉን ነብይ ብዬ ነበር የጻፍኩት:: ምክንያቱም የእኔ እዉቀት ደረጃ ያ ነበርና:: እንዲሁም መጻሕፍት ተብሎ መጻፍ የነበረበትን መጽሐፍቶች ብዬ ነበር የጻፍኩት:: ሥዕል ተብሎ መጻፍ የነበረበት ስዕል ብዬ ነበር የጻፍኩት:: እግዚአብሔር ተብሎ መጻፍ የነበረበትን እግዚአብሄር ብዬ ነበረ የጻፍኩት:: ሥርዓት ተብሎ መጻፍ የነበረበትን ስርዐት ብዬ ነበር የጻፍኩት:: ዓመፃ ተብሎ መጻፍ የነበረበትን አመጻ፣ ዐመጻ ብዬ ነበር የጻፍኩት:: ሥጋ ተብሎ መጻፍ የነበረበትን ስጋ ብዬ ነበር የጻፍኩት:: መንግሥት ተብሎ መጻፍ የነበረበትን መንግስት ብዬ ነበር የጻፍኩት:: ባጠቃላይ ከግእዝ የተወሰዱትን ቃላት እንዳለ መጻፍ ሲገባኝ፤ ከእዉቀት ማነስ የተነሰ በፈለኩት አጻጻፍና ፊደል ነበር የገለጽኩት:: አሁን ደግሞ ትክክለኛዉን ፊደል ሳዉቅ በትክክለኛ ዉ ፊደል ለመጻፍ ሞክሬያለሁ::

የመጀመሪያዉን መልእክት በምጽፍበት ወቅት ሰንደቅ ዓላማ ተብሎ መጻፍ የነበረበትን ባንዲራ ብዬ ጽፌ ነበር:: ነገር ግን ትክክለኛዉን አጻጻፍ ሳዉቅ ሰንደቅ ዓላማ ብዬ አስተካክየዋለሁ:: እንዲህ የመሳሰሉትን እኔም ሆንኩ እዉቀቱ ያላቸዉ ሰዎች ሊያርሙት ይችላሉ:: ምክንያቱም የጻፈዉ ፍጡሩ እኔ ነኝ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም:: እግዚአብሔር ደግሞ በእኔ እዉቀት ደረጃ ነዉ ያጻፈኝ እንጂ ትክክለኛዉ አጻጻፍ የቱ እንደሆነ ሳያዉቀዉ ቀርቶ አይደለም:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር እዉነት ጋር የሚያገናኛቸዉ ነገር ስለሌለ ይኸዉም እዉቀት እንጂ ድንነት ስላልሆ ነዉ በእኔ በመሃይም እዉቀት ያጻፈዉ:: ለመጻፍ ተጨማሪ ጊዜ ቢኖረኝ ደግሞ ሰዋሰዉን የበለጠ ላሳምረዉና ላሳከዉ እችል ነበር:: እንዲሁም ፊደላትን እየለቀምኩ በደንብ አርማቸዉ ነበር:: በአረብኛ ቁጥር ብቻ የተገለጹትን በኢትዮጵያዉያንም ቁጥር ይገለጹ ነበር:: ነገር ግን አሁን የተፈለገዉ የእግዚአብሔር መልእክትና ሙሉ እዉነት ለትዉልዱ እንዲደርስ ነዉ እንጂ የአጻጻፍ ብቃትና ጥራት አይደለም:: የአጻጻፍ ግድፈት ሊኖር ይችላል:: ይህ ሥጋ ለባሽ ሰዎች ፍጹማን አለመሆናችንን የሚመሰክርብን ነዉ:: ለምሳሌ «ማ» ለመጻፍ ተፈልጎ «ሚ» ቢጻፍ ፍጹም ተቃራኒ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል:: ይኸዉም የማይችል የሚለዉ የሚችል ተብሎ በአጻጻፍ ግድፈት ሊገለጽ ይችላል:: ነገር ግን ከላይና ከታች የተገለጸዉ ፍሬ ሐሳብ የትኛዉ አባባል እንደሆነ ይገልጽልናል:: በዚሁ መሰረት በቅንነት የሚያነበዉ ሰዉ ያንን የአጻጻፍ ግድፈት ራሱ አርሞት በትክክለኛ አነባበብ ያነበዋል፤ እንዲሁም ማስተካከያ እንዲደረግበት ያስደርጋል:: እግዚአብሔር ራሱ ቢጽፈዉ ግን በቃለት ሆነ በሰዋስዉ እንዲሁም በፊደላት ሆነ በሥርዓተ ነጥብ፣ በቁጥር አንዳች እንከን አናገኝበትም:: መጻፍና ለትዉልዱ ማስተላለፍ የእኛ የሰዎች ድርሻ ሲሆን፤ ሙሉ እዉነታን፣ ትንቢት፣ ምስጢር፣ እዉቀት የመሳሰሉትን መግልጽና ማሳወቅ ደግሞ የእግዚአብሔር ድርሻ ነዉ::

በእግዚአብሔር መልእክት ላይ ዋናዉ የእኛ ትኩረት መሆን ያለበት በሰዋስዉ አስካክና ማማር፣ በቃላትና ፊደላት መረጣ፣ በሥርዓተ ነጥብና በቁጥር አጠባበቅ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ያዘዘዉን ተግባራዊ ለማድረግ ራስን ማዘጋጀትና ለሙሉ ለእግዚአብሔር እዉነት መብቃት ነዉ:: ምክንያቱም እነዚህን በቂ ችሎታና እዉቀት ያለዉ ሰዉ ሊሰራቸዉና ሊያሳምራቸዉ የሚችል ነዉ:: እንዲሁም ራሱ ጸሐፊዉ በቂ ጊዜ ሲያገኝ ሊሰራቸዉና ሊያሳምራቸዉ የሚችል ነዉ:: የእግዘኢብሔርን መልእክት ግን ማንም ሰዉ ሊጽፈዉና ለትዉልዱ ሊያስተላልፍ አይችልም:: ለእግዚአብሔር መልእክት አስተላላፊነት ሥጋዊ እዉቀትና ችሎታ እንደ መስፈት የማይታይና ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ ሆኖ መገኘት ነዉ ዋናዉና የመጀመሪያዉ መስፈርት:: ከዚያ በኋላ ነዉ የእዉቀትና የችሎታ መስፈርት የሚታየዉ:: አንድ ሰዉ የተሟላ እዉቀትና ችሎታ ሳይኖረዉ ሆነ የተሟላ እዉቀትና ችሎታ ኖሮት የእግዚአብሔርን መልእክት ለማስተላለፍ ሊመረጥ ይችላል:: አንድ ሰዉ ግን ምን ያህል እዉቀትን ችሎታ ቢኖረዉ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ ካልሆነ በስተቀር፤ እዉቀቱና ችሎታዉ ብቻ እንደ መሰፈርት ታይቶ ለእግዚአብሔር አገልጋይነትና መልእክታኛነት አይበቃም:: በተቃራኒ ደግሞ አንድ ሰዉ በቂ እዉቀትና ችሎታ ሳይኖረዉ ለእግዚአብሔር እንደልቡ ከሆነ ለአገልግሎትና ለመልእክተኛነት ሊመረጥ ይችላል:: ሌላዉ መታወቅ ያለበት የእግዚአብሔር መልእክተኞች የእግዚአብሔርን መልእክት ለትዉልዱ ለማድረስ ሲታዘዙ፤ ልክ አንድ በምጥ የተያዘች ሴት ምጧን እስከምትገላገል ድረስ እረፍት እንደሌላት ሁሉ፤ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞችም የእግዚአብሔርን መልእክት ጽፈዉ ለትዉልዱ እስከሚያደርሱ ድረስ በምጥ ስሜት ዉስጥ ነዉ የሚመላለሱት:: መልእክቱን ካደረሱ በኋላ ነዉ እረፍቱ እረፍት፣ እንቅልፉ እንቅልፉ፣ መብሉ መብል፣ መጠጡ መጠጥ፣ ልብሱ ልብስ የሚሆናቸዉ እንጂ ሌት ተቀን ሙሉ ሐሳባቸዉንና ጊዜያቸዉን ለእግዚአብሔር ስራ ነዉ የሚያዉሉት::

**ወደ ጥያቄዉ ስመጣ**፣ እስቲ የሰዉ ልጆችን የከፋ የጭከና ሐሳብና ተግባር በማስተዋል እንገምግመዉ! ወገን ወገኑን በአንዴ የሚጨርስበትን መሳሪያ ለመስራት ሲያስብና ያንንም ሐሳቡን ወደ ተግባር ለዉጦ ማጥፊያ መሳሪያ መስራቱ እንዲሁም ለጥፋቱም ወቅትና ጊዜ መጠበቁ ምን ይባላል!?:: ይህ ተግባራቸዉ በግልጽ የዲያብሎስ አገልጋይነታቸዉን አይመሰክርባቸዉምን!? በደንብ ይመሰክርባቸዋል:: የሚያሳዝነዉ ደግሞ የጥፋቱ ገፈት ቀማሽ የሚሆኑት ከማንም በላይ ራሳቸዉ ናቸዉ:: ምክንያቱም ይህ የዓመፃና የጭከና ተግባራቸዉ የራሳቸዉ እጅግ የከፋ ፍሬ ስለሆነ፤ ሰዉ ደግሞ የዘራዉን ፍሬ ማጨዱ ስለማይቀር፣ እጅግ የከፋና የመረረ ፍሬ ቢሆንም በነጻ ሕሊናቸዉ ተመርተዉ የፈጠሩት በመሆኑ ዋጋ ይከፍሉበታል (ይቀጡበታል)::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የኒዉክለር መዘዙ ለዓለም የሚተርፍ ነዉና የዚህ የሰዉ ዘሮችን ማጥፊያ መሳሪያ ባለቤት የሆኑ ሆነ ሌሎች አገራት ምን ማድረግ አለባቸዉ ብለዉ ይመክራሉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያም ቢሆን መንግሥታት፤ በዓለም እጅግ ብዙ ሕዝብ በጉስቁልናና በችግር፣ በድህነት ዉስጥ እያሉ እነሱን ከችግርና ከጉስቁልና ሕይወት የሚለዩበትን፣ ለሕዝብና ለአገር እድገት የሚጠቅሙ የተለያዩ ግንባታዎችን ማከናወንና የዓለም ሕዝብ

አንደ አዳም ዘርነቱ እንደቤተሰብ ተፋቅሮና ተሳስብ እንዲኖር የራሳቸዉን ጥረት ማድረግ ሲገባቸዉ፤ በተቃራኒዉ ሕዝብና ሕዝብ የሚጨራረስበትን መሳሪያ መስራታቸዉ ራሱ ወንጀለኛነታቸዉን ይመሰክርባቸዋል። ለዚያዉም ከባድ ወንጀል። ምክንያቱም አንድና መቶ ወይንም በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ የሚያጠፋ ብቻ ሳይሆን በሚሊዮንና በቢሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የሚያጠፋ መሳሪያ ነዉና። ዞሮ ዞሮ ስለ ዓመፃቸዉ ንስሐ ከገቡ እግዚአብሔር መሐሪ ነዉና በምሕረቱ ሊጎበኛቸዉ ይችላል። ስለዚህ ዛሬ ነገ ሳይሉ መሳሪያዉ ከምድረ ገጽ የሚወገድበትን ወይንም የሚመክንበትን መንገድ መፍጠር አለባቸዉ። ያ ብቻ አይደለም ጦርነትንና አምባገነንነትን እንዲሁም የትዕቢትና የእብሪት ሕይወትን አስወግደዉ ሕዝቡ በፍቅርና በሰላም በአንድነት እንዲኖር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ያ ብቻም አይደለም ለሰዉ ዘሮች ጥፋት የተዘጋጁ የጦር መሳሪያዎችን ሁሉ ከምድሪቱ ሊያጣፉና ለሕዝብ የሚጠቅሙ የተለያዩ ልማትና ግንባታ ስራዎች ማከናወን ይገባቸዋል። ምክንያቱም እያንዳንዱ አገር እንደ ዓመፃዉ ደረጃ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣበታልና።

ሌላዉ ማወቅ ያለብን የኒዉክለር መዘዙ የከፋ ቢሆንም፤ ምንም ይምጣ ምን የእግዚአብሔር ሕዝቦች አንዳች የሚሆኑት ነገር የለም። ልክ አንድ ሕፃን ገደል ዉስጥ ገብተዉ ከሞቱ ከብዙዎች ሰዎች ዉስጥ ተርፎ በሕይወት እንደሚገኝ፤ ወይንም ሰዉን የሚገል መርዝ ጠጥቶ ምንም እንደማይሆን ሰዉ፤ ወይንም እንደ አናንያ ፣ አዛሪያ፣ ሚሳኤል ታላቅ ነበልባል እሳት ዉስጥ ተጥለዉ ምንም እንዳልሆኑ ነገር ግን የጣሏቸዉ በእሳቱ እንደተበሉ ሁሉ፤ እንኳን ኒዉክለር አይደለም ሰማይና ምድር ቢደበላለቁና እንደ መጅና ወፍጮ ቢገናኙ በእግዚአብሔር የሚተማመኑና እንደፈቃዱ የሚመላለሱ፣ እንዲሁም ቅንነትና መልካምነት የተገኘባቸዉ እርሱ እንዲድኑ የሚፈቅዳቸዉ ሰዎች አንዳች የሚሆኑት ነገር የለም።

እግዚአብሔር በአምላካዊ ሥልጣኑ ማንኛዉንም ማድረግ የሚችል፣ እንኳን በሕይወተ ሥጋ ያለዉን አይደለም በሕይወተ ሥጋ የሞተዉን አስነስቶ በምድር ተመልሶ እንዲኖር የሚያደርግ ምንም የማይሳነዉ አምላክ ነዉ። በመሆኑም የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ቅዱሱ ኪዳን የሚመላለሱ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ቅዱሱ ኪዳን ሲል እግዚአብሔር ከማንኛዉም ጥፋትና ድምሰሳ ይጠብቀናልና አንዳች ስጋትና ጭንቀት ሊይዘን አይገባም። በቅዱሱ ኪዳን ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ የአምልኮ ምንዝርና የፈጸምን ሰዎች ግን በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰን እጃችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ካልሰጠንና እንደ ቅዱሱ ኪዳን ካልተመላለስን ከእግዚአብሔር ቁጣ ልናመልጥ አንችልም። እንዲሁም ከምድር ልንጠረግና ልንጸዳ እንችላለን። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቁጣና ከጠረጋዉ ለመዳን እዉነተኛ ንስሐ ያልገባን እዉነተኛ ንስሐ እንግባ፤ የእግዚአብሔርን እዉነት ያልተቀበልን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት እንቀበል፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጭ በሆነ ሕይወት ዉስጥ የምንመላለስ በእዉነተኛ ሕይወት እንመላለስ፣ ቀና እናስብ፣ መልካም እንስራ።

በዚሁ አጋጣሚ የዓለም መንግሥታት ምን ያህል ሕሊናቸዉን ያደረደኑ፣ ስለ ሕዝብ አንዳች የማያስቡ ጨካኞች መሆናቸዉን የሚሰክርባቸዉ ጥቂቶቹን እገልጽላችኋለሁ። በእኛ አቆጣጠር በ፳፻፫ (2003) ዓ.ም በእነሱ በ2012 መጀመሪያ ላይ በጃፓን የተከሰተዉ የኒዉክለር ስጋት እነሱንም

አሳስቧቸዉ፤ እንኳን የኒዉክለር ባለቤት ለመሆን አይደለም ከዓለም ላይ ኒዉክለርን ለማጥፋት መሽቀዳደም ነበረባቸዉ፡፡ ይሁንና ዉስጣቸዉ ትዕቢትና ዓመፃ ስለሞላባቸዉ የሕዝብ መጎዳትና መጥፋት እንዳች አላሰጋቸዉም፡፡ ምክንያቱም ዲያብሎስ በበላይ ሆኖ የሚመራቸዉ ስለሆነ ለሕዝብ የማያስቡና የማይቆረቆሩ ራሳቸዉንንም ሕዝቡንም ለመጨረሻዉ የእግዚአብሔር ቁጣ እያዘጋጁት ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየን የዲያብሎስ እንደራሴና አገልጋይ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

ማስተዋል አጡ እንጂ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንኳን መከላከል ይቅርና መቋቋም እንደማይችሉ ከጥቅምት፲፰÷፳፻፭ (18/2/2005) ዓ.ም ጀምሮ ለአጭር ቀናት፣ በአሜሪካ የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት መቀመጫ የሆነችዉ ኒዎርክ በሃሪኬን ሳንዲ ዐዉሎ ንፋስ ስትመታ ማንም ሊከላከለዉ ሆነ ሊቋቋመዉ አልቻለም፡፡ በአጭር ቀናት ዉስጥ ይህን ያህል ጥፋት ካመጣ፤ ቀናቱ ቢጨምርማ እንዴት ሊኮን ነበር? እንዲሁም ከዚህ በከፋ መልኩ የተለያዩ የእግዚአብሔር ቁጣዎች ቢመጡ ማን ሊከላከልና ሊቋቋም ይችላል? ትዉልዱ ማወቅ ያለበት እንኳን እንዲህ የገዘፈዉ ጥፋት አይደለም የአፈር ብናኝ እንኳ እግዚአብሔር ሳያዉቀዉና ሳይፈቅደዉ የሰዉ ዓይን ዉስጥ አይገባም፡፡ ስለዚህ የዓለም መንግሥታት ሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች አቅማቸዉ ልምሾና ተራ መሆኑን አዉቀዉና አስተዉለዉ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ቢሰጡና ለእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሰለፉ ያተርፋሉ እንጂ አይጎዱም፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ በእርግጥ ምክሮትን በቅንነትና በየዋህነት የሚቀበለዉ አገር ቢኖር መልካም ነበር፡፡ አሁን ካለዉ ተጨባጭ ነገር እንኳን እርሶን፣ አንድ ኃያል አገር ተነስቶ አሁን ያሉትን «እንተግብር» ቢል እንደ እብድና ወፈፌ ነዉ የሚታየዉ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ በኃይሉ፣ በሀብቱ፣ በሥልጣኑ፣ በደኅንነቱና በስለላ መዋቅሩ፣ በጦር መሳሪያዉ ... ወዘተ የሚመካ ነዉና፡፡ በእዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፡ በአገራችን በኢትዮጵያ አንድ የሚባል አባባል አለ፡፡ ይኸዉም «ምከረዉ ምከረዉ እምቢ ካለ መከራ ይምከረዉ» የሚል ነዉ፡፡ ከእኛ የሚጠበቀዉ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነትን ማሳወቅ ነዉ፡፡ የእግዚአብሔርን መልእክትና የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል አለመቀበል፣ እንዲሁም መተግበር አለመተግበር የእያንዳንዱ አገር(መንግሥት) ሆነ ድርጅት እንዲሁም ቡድንና ግለሰብ ነጻ ምርጫና ዉሳኔ ነዉ፡፡ ነገር ግን ማንም ይሁን ማን «እብድም» ይበል ወፈፌ እንደ ዓመፃዉና ትዕቢቱ እንዲሁም ደንዳናነቱ በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍልበታል (ይቀጣበታል)፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱን ኃይልና የሚመካበት ሁሉ ከጥፋትና ከመደምሰስ ያድነዉ አያድነዉ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻዉን ሰተዋል፡፡**

### ምዕራፍ ሦስት

« <u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ ስለ ሴቶች ከገጽ 173-174 ድረስ ይገልጻል፡፡ ይኸዉም፡

«አስረኛዉ ጥያቄያችሁ የሆነዉ የራሳችሁ ሰብዕና በተመለከተ « አንዳንድ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን እኛ ከወንዶች ያነስን፣ በአደባባይ መዉጣት እንደሌለብን፣ እንደወንዱ በነጻነት መንቀሳቀስና ኃላፊነት ቦታ ላይ መቀመጥ እንደሌለብን፣ ለመሪነትና ለአስተዳዳሪነት ብቃት የሌለን አድርገዉ ያስተምራሉ:: በዚህ በኩል ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?» በማለት ለጠየቃችሁት ጥያቄ ምላሼ የሚከተለዉ ነዉ::

<u>እናቶቼና እህቶቼ እናንተ በኃላፊነት ማስተዳደር ካልቻላችሁ፤ ታዲያ የትኛዉ ሰዉ ነዉ ኃላፊነት ሊሸከምና ሊያስተዳድር የሚችለዉ!? የትኛዉ ወንድ ነዉ ከማህፀን ጀምሮ ፅንሱ የተለያየ ድካምና ጠባይ ሲያመጣ ተቋቁሞና ታግሶ ዘጠኝ ወር ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ ድርሻዉን የሚወጣ? የትኛዉ ወንድ ነዉ የጭንቋን ሰዓት ተጨንቆ አምጦ የሚወልደዉ? የትኛዉ ወንድ ነዉ ጡቱን አጥብቶ ሽንቱንና ቅዘኑን ሳይጸየፍ አጥቦ፣ ተንከባክቦ፣ መግቦ የሚያሳድግ? የትኛዉ ወንድ ነዉ«ልጄ ተራብ፣ ተጠማ፣ ተጎዳ፣ ተጎሳቆለ?» ብሎ በስስትና በርኅራኄ ልጁን የሚንከባከብና ለቁም ነገር የሚያበቃ? የትኛዉ ወንድ ነዉ ስለልጆቹ ራሱን ጎድቶ «ልጄ ይብላ፤ ይመቸዉ::» ብሎ ስለልጆቹ ሁሉን ችሎና ታግሶ የሚኖር? የትኛዉ ወንድ ነዉ ልጁን በፍቅርና በርኅራኄ፣ በሥርዓት ተንከባክቦ፣ ወቶ፣ ወርዶ ለወግ ለማእረግ የሚያደርስ? እንግዲህ እናንተ ለኃላፊነት፣ ለአሰተዳዳሪነት፣ ለመሪነት አትበቁም ከተባለ በዓለም ዉስጥ ለኃላፊነት ሆነ ለመሪነት የሚበቃ ሰዉ የለም ማለት ነዉ::</u>

ሴቶች ሆናችሁ ወንዶች ያለን ልዩነት በሕያዉ ነፍሳችን ባሕርይ ሳይሆን፤ በተገለጽንበት ሥጋ ነዉ:: ይኸዉም ወንድና ሴት ጾታ ብቻ ነዉ እንጂ ነፍሳችን የጾታ ሆነ የሌላ ልዩነት አንዳች የላትም:: ስለዚህ አንዳች የማንበላለጥ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል:: ይልቁኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆናችሁ ከተገኛችሁ በቅድስና ብቃት ልትበልጡን ትችላላችሁ:: ይኸዉም በቅድስና ሕይወቷ ብቃት ደረጃ ላይ በመድረሷ ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ለመሆን የበቃችሁ ነፍስ፤ የአዳም ተስፋ፣ የደናግል መመኪያ፣ የጻድቃን እመቤት፣ የሰማዕታት አክሊል፣ የደካሞች ምርኩስ፣ የህሙማን ፈዉስ፣ የድኅነታችን ምልክት፣ የቅዱሳን ሞገስ፣ ብቻ ምሳሌ ተመስሎላት ተመስሎላት፣ ተመስግና ተመስግና የማትጠገብ እመ አምላክ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሴት ጾታ ነዉ በሥጋዋ የተገለጸችሁ:: ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኛ ወንዶች በአደባባይ መዉጣት፣ መስራት፣ መናገር፣ መማር፣ ማስተማር፣ መጸለይ፣ ማመስገን፣ ኃላፊ፣ አስተዳዳሪ ፣ መሪ መሆን እንችላለን:: ትልቁ ሁላችንም ጠንክረን መስራት፣ መማር፣ ስለ እዉነት መጽናት፣ መትጋት፣ እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ ነዉ የሚጠበቅብን:: ከዚያ ዉጭ ለእናንተ የሚፈቀድ ለእኛ የሚከለከል መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የለም:: በሌላ በኩል ለእኛ የሚፈቀድ ለእናንተ የሚከለከል መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የለም:: ሁላችንም እንደ እምነታችንና ምግባራችን ነዉ የሚፈረድልንና የሚፈረድብን:: በእግዚአብሔር ዘንድ በጾታችን ምክንያት አንዳች አድሎ አይደረግም::

ልጆቻችንንም በሥርዓት፣ በትጋት፣ በንቃት፣ በብቃት የማሳደጉ ደርሻ የወንዱም የሴቱም ነዉ:: እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲያድጉ አድርገን በሥርዓት ካሳደግን በምድርም የመጀመሪያዉ ጥሩ ዋጋ ተከፋዮች እኛዉ ወላጆች ነን:: ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ልጆች በኃላፊነት ተረክበን እንደ እዉነተኛ አባትነቱ እንዲያከብሩት፣ እንዲያመልኩት አድርገናልና ዋጋችን ከፍ ያለ ይሆናል:: በተቃራኒዉ በሥርዓት ካላሳደግን፣ ጋጠ ወጥ ካደረግናቸዉ፤ እግዚአብሔርንም ሰዉንም የማያፍሩ፣ የማያከብሩ ከሆነ የመጀመሪያዉ ዋጋ ከፋዮች እኛ ወላጆች ነን:: ከዚያም ጥፋታቸዉ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለመንደር፣ ለአገር ይተርፋል::

በዚሁ ላሳዉቃችሁ የምፈልገዉ ነገር ልጆችን አርግዛ የመዉለድ ድርሻ የሴቷ ብቻ እንጂ የወንዱ እንዳልሆነ ሁሉ በኑሮዋችንም ወንዱም የራሱ ድርሻ አለዉ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ በአምላክነቱ ባሕርይ ባወቀዉ ለሐዋርያነት የመረጣቸዉ አስራ ሁለቱም ደቀመዛሙርት ወንዶች ብቻ ናቸዉ:: በዚህም ምክንያት በክህነት አገልግሎት ዉስጥ የሚሳተፉት ለመቀደስና ለማቁረብ የተፈቀደላቸዉ ወንዶች ብቻ ናቸዉ:: ነገር ግን ከዚያ ዉጭ በጸሎቱ፣ በምስጋናዉ ወንዱም ሴቱም በጋራ ያገለግላል፤ ይገለገላል:: ታዲያ አንዳንድ ዘመን አመጣሽ እህቶቻችን የዓለሙ ዓመፃ አልበቃ ብሏቸዉ በፖለቲካ ኅሊናቸዉ ተመርዞ «ለምን ቄስ፣ ጳጳስ አንሆንም?» በማለት በየአደባባዩና አዳራሹ ሲናገሩ ይታያል፤ ይደመጣል:: በእዉኑ እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት ቀንተዉ ነዉን? ወይስ የሃይማኖቱን እዉነተኛ መድረክ ወደ የጨለማዉ ገዥ ፖለቲካ መድረክ ለመለወጥ ፈልገዉ ይሆን? እንኳን እግዚአብሔር ያልፈቀደዉ አይደለም ተፈቅዶለትና ብቃቱም ኖሮት «ለዚህ አገልግሎት ታጭተሃል» ቢባል እንኳ፤ « እኔ ያልተገባዉ ሰዉ ነኝ::» ብሎ በትህትና ለአገልግሎት ይሰለፋል እንጂ በትዕቢትና በዓመፃ ሕሊና እንዴት እግዚአብሔርን ማገልገል ይቻላል?! ታዲያ አንዳንዶች ለዓመፃ ስራቸዉ እንደማጣቀሻ የሚጠቀሙት የሕይወት መመሪያችን የሆነዉ መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳቸዉ በሚመች መልኩ አድርገዉ በማቅረብ ነዉ:: ለዚህ መፍትሔዉ ሕሊናችን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንድትመራ ማድረግ ነዉ:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነዉን፣ የሰዉ ወግና ልማድ የሆነዉን፣ ከሥጋና ደም ስሜት የሆነዉን፣ የክህደቱን፣ የመናፍቅነቱን ባጠቃላይ ስንዴዉንና እንክርደዱን ያሳዉቀናል::» በማለት ቀርቧል::

**ከዚህ የምንረዳዉ ሴቶች ታላቅ ኃላፊነት መሸከም የሚችሉ፤ ይህንንም ለዘመናት በተግባር ያስመከሩ፤ በብቃትም ከወንዶች ሊበልጡ እንደሚችሉ የሚያሳይና ትዉልዱ ግን ይህን ያላስተዋለ መሆኑን ነዉ የሚገልጸዉ:: በዚህ ላይ ምን ዓይነት አስተያየት ነዉ ያሎት?**

<u>መላኩ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር በግልጽ የሴቶች ማንነታቸዉና ተግባራቸዉ እንዲገለጽ ያደረገዉ ብዙዉን ጊዜ እኛ ወንዶች የበላይ አድርገን ራሳችንን የምንቆጥርና ከሴቶች የበለጠ እንደምንሰራ አድርገን ራሳችንን ስለምናመጻድቅ፣ የእነሱን ጥንካሬ የእኛን ድክመት እንድናዉቀዉ ፈልጎ ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ ወንዱም ሆነ ሴት ፍጹም እኩል መሆናቸዉና

በነፍሳቸዉ አንድ የሆኑ፣ በተገለጹበት ሥጋቸዉ ጾታና አካል ብቻ ልዩነት እንዳላቸዉ ነዉ የሚገልጸዉ:: ስለዚህ ሁላችንም ይህን አስተዉለን ለእናቶቻችን፣ ለእህቶቻችን፣ ለባልተቤታችን (ሚስታችን) ትኩረት እንድንሰጥና ልፋታቸዉንና ትጋታቸዉን ልናስተዉል እንዲሁም ዋጋም ልንከፍለዉ እንደሚገባ ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከዚህ ጋር በማያያዝ በአሁን ሰዓት በወንዱም ሆነ በሴቱ የሚታይ ከኢትዮጵያ ባህልና ሕይወት የማይሄድ አዉሮፓዊና አሜሪካዊ ባህልና ሕይወት አለ:: በዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ ባህል የአንድ ኅብረተሰብና ማኅረሰብ መገለጫዉና ማንነቱ የሚታወቅበት ነዉ:: ጠቃሚ ባህሎች እንዳሉ ሁሉ ጎጂ ባህሎችም አሉ:: በተለይ ከባዕድና ከጣዖት አምልኮና እምነት ጋር የተያያዙ ባህሎች ሙሉ በሙሉ ጎጂና በሥጋም በነፍስም የማይጠቅሙ ናቸዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን እንደ ኅብረተሰቡ አስተዳደግና አኗኗር የተለያዩ ባህሎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በሥጋም በነፍስም የምንጠቀምባቸዉን የበለጠ ጠብቀናቸዉ መሄድ ይገባል:: በሥጋ የሚጠቅሙና ነፍስን የሚጎዱትን ደግሞ ወደነፍስ ጥቅም ጭምር ልናመጣቸዉ ይገባል:: ምክንያቱም የእኛ ዋና ገንዘባችን ነፍሳችን ናት እንጂ የዚህ ሥጋ የመጨረሻ ክብሩ ወደ አፈር መግባትና ለምስጥ መብል እንደሚሆን የታወቀ ነዉ:: ስለዚህ ባህላችን ዋና ትኩረት ሊያደርግ የሚገባዉ ለነፍሳችን መሆን ይገባል፤ ከዚያም በሥጋችንም ልትጠቀምበት እንችላለን::

ከዚህ አንጻር ለነፍሳችን ሆነ ለሥጋችን የምንጠቀምባቸዉ መልካም ባህሎችን የማንም ይሁን የማን ልንጠቀምባቸዉ እንችላለን:: ለምሳሌ ታማኝነትና ትጋት የተሞላ የስራ ባህል ከአዉሮፓም ይሁን ከአሜሪካ፣ ከአረብም ይሁን ከአፍሪካ፣ ከኤሽያም ይሁን ከአዉስተራሊያ ልንጠቀም እንችላለን:: በተቃራኒዉ ደግሞ ጎጂ የሆኑ የአኗኗርና የአለባበስ ባህሎችን ደግሞ የማንም ይሁን የማን ልንቀበላቸዉና ልንኖርባቸዉ እንዲሁም ልንገለጥባቸዉ አይገባም:: ለምሳሌ በተለያየ ሱስ ሕይወት ዉስጥ መመላለስ የለብንም:: ምክንያቱም በሱሱ ምክንያት ለዲያብሎስ ግብር ወይንም ምስ የሆነዉ ሲጃራም ይሁን አሸሽ፣ ጫትም ይሁን ሺሻ፣ አድንዘዥ ዕፅ ይሁን የተለያየ የደም መስዋዕት፣ ሙሉ በሙሉ ርኩሳን መናፍስ( ሰይጣናት) ነፍሳችንን(ሕሊናችንን) ሲፈታተኑንና ሲያስጨንቁን የሚቀርብላቸዉ ስለሆነና ለዲያብሎስ ባሪያዎቹና ተገዥዎቹ መሆናችን የሚያስመሰክር በመሆኑ እንደ ማንኛዉም ሰዉ የዚያች ደቂቃዎች ፈተናና ማስጨነቅ መቋቋምና በተለያየ ነገር ማሳለፍ ነዉ ያለብን እንጂ የተለያዩ ምሶቹን እንደ ጠንቋዮችና አስማተኞች እንዲሁም መተተኞችና ሟርተኞች የምናቀርብለት ከሆነ በገልጽ እሱን እያመለክን መሆናችንን ያስመሰክርብናል:: ስለዚህ በተለያየ ሱስ ሕይወት ዉስጥ መመላለስ ባህል ሳይሆን የዲያቢሎስ ባሪያ መሆን ነዉ:: በመሆኑም በተለያየ ሱስ የተያዝን ሰዎች የርኩሳን መናፍስት ኃይል ለማዳከምና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመላበስ ሕይወታንን በጸሎት፣ በጾም፣ በእግዚአብሔር ቃል ልንመራና ራሳችንን ልንገዛ ይገባል:: የእግዚአብሔርን መሳሪያ መጠቀም ካልቻልን በሕሊናችን(በነፍሳችን) ላይ እንደ ፈለጉ ነግሠዉ የሚኖሩትን ሰይጣናት ልናሸንፋቸዉና ራሳንን ልንገዛ አንችልም::

በኢትዮጵያ ምድር በተለየ ሁኔታ የዉጭዎች(የባዕዳን) አለባበስና ሥርዓት አልበኝነት ጎልቶ የሚታይና ትዉልዱ ፍጹም ለዲያብሎስ መጠቀሚያ መሳሪያ እየሆነ ይገኛል። ምንም እንኳን ሥርዓት አልበኝነት፣ ወላጅንና ታላላቆችን አልማክበርና አለመታዘዝ በወንዱ ላይ የበለጠ የሚታይ ሲሆን፤ በሴቶች በኩል ያለዉ አለባበስ የእግዚብሔርን የከፋ ቁጣ የሚያስመጣ ነዉ። ዱሮ በቡና ቤቶችና በሽርሙጥና(በዝሙት አዳሪነት) የሞት ሕይወት ዉስጥ በሚመላለሱትና የወንዱን የዝሙት ስሜት ለማነሳሳትና ለመሳብ «ፍንዳታ»ና «ኦቨር አክት» በመባል በሚታወቁበ ዘመናይ ሴቶች ይለበስ የነበረዉ አለባበስ፤ በአሁን ሰዓት በትዳር ዉስጥ ያሉት ሆኑ ከትዳር ዉጭ ያሉት ከልጅ እስከ አዋቂ ያሉት እህቶቻችንና እናቶቻችን ሳይቀሩ የቀደመዉን የእናቶቻቸዉን የጨዋ አለባበስ ትተዉ እንደ ዘማዉያኑ ደረታቸዉንና ጡጣቸዉን እንዲሁም እንብርታቸዉንና ቂጣቸዉን፣ ታፋና ዳሌያቸዉን፣ ባታቸዉን የሚያሳይ የተራቆተ አለባበስና አካላቸዉን ወጣጥሮ በሚያሳይ ሱሬና ጥብቅብቅ ባለ ልብስ ነዉ የሚወጡት፤ የሚገቡት። በዚህም ምክንያት በየቡና ቤቱና በሴተኛ አዳሪ ቤቶች ዉስጥ የነገሠዉ የዝሙት መንፈስ በሁሉም ቦታ ነግሦ ወንዱ በተግባር ባይረክስ እንኳ በንግግርና በሐሳቡ በመርከስ በዝሙት ወድቋል። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ማርያም ተገልጾ፣«በሐሳቡ ዝሙትን ያሰበ እርሱ እንደ አመነዘረ እንደሚቆጣርና ለዚያ ፈተና የዳረገም እንዳስመነዘረ(እንዳሰናከለ) እንደሚቆጠር» በግልጽ ተናግሮናል። ይኸዉም « ወደ ሴት አይቶ የተመኘ አመንዝሯል፤«ማሰናከያ ለሚያመጣ ወዮለት!» በማለት አስተምሯል፤ አስጠንቅቋል።

እህቶቻችን አላወቁት ወይንም አላስተዋሉትም እንጂ በዚህ እግዚአብሔርን በማያምኑ አረማዉያን አለባበስ መታየታቸዉ የከበረዉን ገላቸዉን በዝሙት የሞት ሕይወት እንደሚተዳደሩት እህቶቻችን እያራከሱትና ለአላፊ ለአግዳሚዉ «ይህ ገላዬ ይህን ይመስላል፤ ክብር የሌለዉ የተራቆተ ነዉ፤ ማንም ሰዉ እንዲመለከተዉ የተፈቀደና የቀለለ ነዉ፤ .. ወዘተ» በማለት የከበረዉንና ለማንም ተገላልጦ መታየት የሌለበትን ገላቸዉን እያራከሱትና እያቀለሉት ነዉ።

እዚህ ላይ ሊመሰከርላቸዉ የሚገባዉ በእስልምና እምነት ዉስጥ ያሉ እናቶቻችንና እህቶቻችን፤ ምንም እንኳን የቀደመ ኢትዮጵያዊ አለባበሱን ቢያጠፉትም፤ የከበረ ገላቸዉን ግን አክብረዉ ያሉ፣ ለወንዶችም ማሰናከያ ያልሆኑ፣ በጨዋ አለባበስ ነዉ ተገልጠዉ የሚወጡት፣ የሚገቡት። ራሳቸዉን ከተለያዩ የዓመፃና የርኩሰት ሕይወት ለይተዉ በዚህ የጨዋ አለባበስ የተገለጹት ሴቶች፤ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ በገጽ 136 ላይ መልካምነታቸዉ ተመስክሮላቸዋል። ይኸዉም:

«ታዲያ ትዉልዱ የእግዚአብሔርን ቃል አስተዉሎ ቢሆን ኖሮ እንኳን በተቀሰደሰዉ ስፍራ ቀርቶ በዓለም ላይ በዚህ አለባበስ አይሄድም ነበር። አሁን ግን በዓለም ቀርቶ በእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር የዲያብሎስ ሥርዓትና የአሕዛብ ሥርዓት ስለነገሠ የከበረዉ ገላ ተገላልጦና ተወጣጥሮ፤ ተራክሶና ተዋርዶ በየቦታዉ ይታያል። እናንተ አሁን እኔጋ ስትመጡ ሁላችሁም ከአናታችሁ እስከ እግራችሁ ድረስ ገላችሁን በሚያስከብር አለባበስና ወንዶችን ለዝሙት በማያነሳሳ እግዚአብሔር

መፍራት ያለበት አለባበስ ነዉ የቀረባችሁት፡፡ ይህ ደግሞ ፈጣሪን ማክበርና መዉዳድ እንዲሁም ለሰዉ ማሰናከያ አለመሆንን መምረጣችሁን ያሳያል፡፡ አሁንም እንደገና የምላችሁ እናንተ የሚቀራችሁ አረባዊ አልባበሳችሁን ወደ ኢትዮጵያዊ አለባበስ መቀየር ብቻ ነዉ እንጂ አሁን የሚታየዉ አለባበሳችሁ የጨዋ አለባበስ ነዉ፡፡»ይላል

ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያዉያን የቀደሙት ሆነ የአሁን ወላጆቻችን ያወረሱንን የጨዋ አለባበስ፣ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት፣ ወንዶችን ለዝሙት የማያነሳሳ፣ ባጠቃላይ የቀደሙት ወላጆቻችንን ፈለግ ተከትለን፣ የከበረዉን ገላችንን አክብረን፣ ክብረ ንጽህናችንንም ጠብቀን ልንኖር ይገባል እንጂ፤ እንደ አሕዛብ (እግዚአብሔር የለሽ) ሥርዓት አለባበስ ልንመላለስና ራሳችንንም ለመከራ ሥጋና ለመከራ ነፍስ አሳልፈን መስጠት የለብንም፡፡

እዚህ ላይ ለትዉልዱ የማቀርበዉ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸዉም የእግዚአብሔር ቁጣ በእያንዳንዱ ላይ በሚነድበት ወራት ሰዉነታቸዉን ለዝሙት በሚያነሳሳ መልኩ ገላልጠዉና በተወጣጠረ ሱሬ የወንዱን የፍትወት ስሜት ሊያነሳሳ በሚችል አለባበስ የሚወጡ፣ የሚገቡ የስም ክርስቲያን ናቸዉ ከቁጣዉ የሚድኑት? ወይስ ራሳቸዉን ከዝሙት ለይተዉ፣ የከበረ ገላቸዉን አክብረዉ፣ ሥርዓት ባለዉና በጨዋነት በሚያስከብራቸዉ አለባባስ የሚወጡትና የሚገቡት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ሴቶች ናቸዉ? ለምላሹ ከተቸገርን የእግዚአብሔርን እዉነተኛና ፍትሐዊ ፍርድ እጅግ በቅርቡ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለ ዓመፃ አለባበሳችን ዋጋ ከመክፈላችን በፊት እግዚአብሔር መፍራት ያለበት፣ ጨዋነት የሚታየብነት፣ የከበረዉ ገላ ሳይራከስና ለዝሙት ማነሳሻ እንዲሁም ለማስመለኪያ ሳናደርገዉ እንመላለስ፡፡ በዝሙት ሕይወት ዉስጥ ያለነዉም ዛሬ ነገ ሳንል ራሳችንን ከዚህ የዓመፃ ሕይወት እንለይ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠያቂያቸዉ አካል ምላሻዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አራት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተላለፈዉ ሁለተኛ ዉ የእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ በክፍል ሦስት በምዕራፍ ሁለት ከገጽ 213-220 ላይ እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገዉ መልእክት አለ:: ይኸዉም:

« በዓለም ዉስጥ የተለያዩ አገራት መሪዎች በአገራቸዉ ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ሃይማኖቶች እምነትና እንዲሁም ባህላዊ አምልኮ የሚፈጽሙትን ጭምር የሚወክሉ ከእያንዳንዱ ሶስት ሶስት ሰዉ አዘጋጅተዉ ልዩ ስሙ ጻድቃኔ ወደ ተባለ ቦታ የላኩና ከ195 አገራት በላይ እያንዳንዱን የሚያምኑበትን እምነት የሚወክሉ ሰዎች ለሰባት ቀን ሱባኤ እንዲገቡ አድርገዋል:: ዋናዉ ዓላማቸዉም የዓለም መንግሥታት በመደበኛዉ ስብሰባቸዉ « እግዚአብሔር አለ ከተባለ ሊኖር የሚችለዉ አንድ እግዚአብሔርና አንድ ሃይማኖት መሆን ሲገባዉ፤ በዓለም ዉስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር አምላክና ሃይማኖቶች ስለተፈጠሩ፤ ሕዝቡም በዚህ ግራ ስለተጋባ እዉነተኛዉ አምላክና እምነት እንዲለይ የኦርቶዶክሱም፣ የተዋሕዶዉም፣ የካቶሊኩም፣ የፕሮቴስታንቱም ባጠቃላይ በክርስትና ስም የሚጠራዉ ሁሉ እንዲሁም የይሁዲዉም፣ የእስላሙም፣ የቡዲሂዝሙም፣ የሂንዱዝሙም፣ የተለያዩ የባህላዊዉም፣ የጨሌዉም፣ የጣዖታቱም፣ ባጠቃለይ ከእምነት ጋር የተያያዘዉ ሁሉ ሶስት ሶስት ሰዉ ወክለዉ በጋራ ሱባኤ በመግባት እዉነተኛዉን አምላክና እዉነተኛዉ እምነት እንዲገለጽላቸዉ እንዲጠይቁ፤ ያለበለዚያ ደግሞ «እኛ ለጥቅማችን፣ ለስልጣናችን፣ ለክብራችን፣ ለዝናችን ስንል ነዉ አምላክ እያልን ሕዝቡን የምናደናግረዉና የምናስፈራራዉ እንጂ አምላክ ፈጣሪ የሚባል ነገር የለም::» ብለዉ በግልጽ ለዓለም ሕዝብ እንዲያሳዉቁ» ተብሎ በመወሰኑ ምክንያት ነዉ ከሁሉም እምነት የተወጣጣ ቡድን ወደ ስፍራዉ የተላከዉ::

የሁሉም አገራትና እምነት ተወካዮች ምንም እንኳን አብዛኛዉ ተወካይ የላመዉንና የሚጥመዉን ምግብ የለመደ ቢሆንም፤ በሱባኤዉ ቦታ የሚፈቀደዉ ቆሎና በሶ ብቻ ስለነበረ፤ ካለፍላጎታቸዉና ምርጫቸዉ በፈቃዳቸዉ ነዉና የመጡት እየተሰቀቁና እያጉረመረሙም ቢሆን ለሰባት ቀን በሱባኤ ሊቆዩ ችለዋል:: በመጨረሻም በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ማእከል ተገኝተዉ የተገለጸላቸዉን በዝርዝር አቅርበዋል::

በመጀመሪያ እንዲያቀርቡ እድል የተሰጣቸዉ ከሰሜንና ከደቡብ አሜሪካ አገራት ተወክለዉ የሄዱት ሲሆን፤ እነሱም በጋራ በመሆን « በእዉነቱ ነፍሳችን የምትፈልገዉን መብልና መጠጥ ማግኘት አለመቻሏ ለጊዜዉ ቅር ብንሰኝም በመጨረሻ ግን የተሰበረ ልቦናና ከልብ የማናመልከዉ እዉነተኛ አምላካችን በደላችንና ኃጢአታችንን ሳይመለከት፤ « ልጆቼ በዚህች በተቀደሰች አገርና ቦታ ላይ ተገኝታችሁ እኔን አምላካችሁንና እዉነተኛ አባታችሁን ደጅ ልትጠኑና እዉነተኛዉ ሃይማኖት እንዲገለጽላችሁ በጋራ በመገኘታችሁ ይህን ፍላጎታችሁንና ድካማችሁን ተመልክቼ ነዉ እዉነተኛዉን

ሃይማኖት ልገልጽላችሁ ፈቃዴ ሆኖ ወደ እናንተ በተለየ ሁኔታ የመጣሁት:: እኔ በነጻነት የምገዛ አምላክ ነኝና እዉነቱን እነግራችኋለሁ እንጂ በዚያ እምነት ዉስጥ እንድትኖሩ አላስገድዳችሁም:: ነገር ግን እዉነቱን እየነገርኳችሁ ባትኖሩበትና እዉነትን ብትክዱ ከማንም በላይ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቃችሁ ልታዉቁ ይገባል:: ምክንያቱም ይህን እድል ብዙዎች አላገኙም:: እናንተ ግን ሳይገባችሁ እኔን ፈጣሪያችሁን በግልጽ አዉቃችኋል:: ቃሌንም ሰምታችኋል::

በዓለም ዉስጥ የተለያዩ ዓይነት እምነት መኖሩን ባዉቅም ያ እምነታቸዉ እንደሚያዛቸዉ የሚኖሩ ግን እጅግ ጥቂቶች ብቻ ናቸዉ:: ሁሉም ማለት ይቻላል ለይስሙላ ነዉ ሃይማኖት አለኝ እምነት አለኝ የሚለዉ እንጂ የያዘዉን እምነት እንኳ በአግባቡ አያዉቅም፤ የሚባለዉንም አይፈጽምም:: በዘልማድ ነዉ ትዉልዱ የሚመላለሰዉ:: <u>**በተለይ በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ እምነት ድርጅቶች ዉስጥ ያሉ የሃይማኖት አባቶችና አማኞች ከሁሉ በላይ የባሰዉ ፍርድ ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: ምክንያቱም በመስቀል ላያ የተከፈለላቸዉን ዋጋ እያወቁ ከንቱ በማድረጋቸዉና በስሙ በመነገዳቸዉ ጭምር ነዉ::**</u> እንደ ቃሉና ትዕዛዙ አይኖሩም:: ይልቁኑ በቃሉ ያስመስሉበታል፤ ይነግዱበታል፤ ያዘፍኑበታል ያስጨፍሩበታል፤ ብቻ የማያደረጉበት ነገር የለም:: በመሆኑም ከሌሎች እምነት ተከታዮች ይልቅ ብዙ ፍሬ ሲጠበቅባቸዉ፤ እንኳን መልካም ፍሬ ሊያፈሩ ቀርቶ ሌላዉን ላለማሰናከል እንኳ ጥናቃቄ አያደርጉም:: የሚያምነዉንም የማያምነዉንም ነዉ የሚያሰናክሉት:: ለዚህም ነዉ የባሰ ፍርድ ይጠብቃቸዋል ያልኩት::

ሌሎቹ በእስልምና፣ በቡዲሂዝም፣ ሂንዱዚም፣.. ወዘተ እምነት የሚመላለሱት ከወላጆቻቸዉ በወረሱት እምነት ሲሆን፤ ብዙዎቹ እምነቱ የሚያዛቸዉን ይፈጽማሉ:: ምንም እንኳን ለሰማያዊዉ ሕያዉ ሕይወት የሚያበቃ እምነት ባይኖራቸዉም፣ ከእዉነተኛዉ ፍረድ ባያመልጡም፤ ምክንያቱም በአራቱም ማዕዘን ስሜ ሲጠራ ይሰማሉና « በመስቀል ላይ ምን ዋጋ ተከፈለ?» ብለዉ መጠየቅ ሲገባቸዉ፤ ለመጠየቅ ሆነ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ነዉ:: ነገር ግን አምነዉ ከሚያምጹት አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ይልቅ ፍርዱ ይቀልላቸዋል:: ሌሎቹ በጨሌዉ ፣ በጣኦትና ባዕድ አምልኮ የሚመላለሱ፣ በየወንዛወንዙና ተራራ እንዲሁም ምናምንቴ ቦታ ላይ አምልኮትና ርኩሰትን የሚፈጽሙ፤ በግልጽ ዲያብሎስን እያመለኩ ስለሆነ እኔንም እጅግ ስላስቆጡኝ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ የሚጠብቃቸዉ ፍርድ ይጠብቃቸዋል::

ባጠቃላይ ከኔ ከእዉነተኛዉ አምላክ አምልኮትና ትዕዛዝ ሥርዓት ዉጭ የሚመላለሱ ሰዎች እንደ ምድራዊ የኃጢአት ተግባራቸዉ ደረጃ ፍርድ ይጠብቃቸዋል:: እጅግ የከፋ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት የፈጸሙና የሚፈጽሙ ሰዎች እጅግ ሊቋቋሙት የማይችሉት ቅጣት ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: አነስተኛ ኃጢአት የፈጸሙ ደግሞ እንደ ደረጃዉ አነስተኛ ሊቋቋሙት የሚችሉት ቅጣት ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ ነዉ የሚፈረድለትና የሚፈረድበት እንጂ በስም ክርስቲያን በመሆን ብቻ የሚድንና ከቅጣት የሚያመልጥ የለም:: በኔ ዘንድ አንዳች አድሎ የለም:: ፍትሐዊ ፍርድ ነዉ የምሰጠዉ:: እዉነትን እያወቀ በእዉነት የማይኖር ከሁሉ የባሰ

ቅጣት ነዉ የሚጠብቀዉ:: የሰዉ ዘሮች ሆኑ ሰይጣናት የሚቀጡበት ቦታ አንድ ገሃነመ እሳት፣ እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፊበት ቦታ አንድ ቢሆንም፤ የሚሰማቸዉ የቅጣቱ ስሜት ግን እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ይለያያል::

እናንተ ሕይወትንና ድኅነትን ፈልጋችሁ፣ እዉነትንም ለዓለም ሕዝብ ልታስተዋዉቁ እምነታችሁን ወክላችሁ ነዉ የመጣችሁት:: በአገሮቻችሁ የሚፈጸመዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እጅግ በመክፋቱ ንስሐ ካልገባችሁና እጃችሁን ለእኔ ለአምላካችሁ ካልሰጣችሁ እንደ ኖኅ ዘመን ያላሰባችሁት ጥፋት ይመጣባችኋል:: እናንተ ራሳችሁ «እምነት አለን፤ አገልጋይ ነን፤» ትላላችሁ እንጂ አንዳች መልካም ምግባር የላችሁም:: በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በዘፈን፣ በዳንኪራ፣ በጥንቆላ፣ በመተት፣ በአስማት፣ በስካር፣ በጥላቻ፣ በቂም በቀል፣ በግድያ፣ በስርቆት፣ በዘረኝነት፣ በጎጠኝነት፣ በዝሙት፣ በመዳራት፣ በሴሰኝነት ፣ በግብረ ሰዶም፣ በጣዖትና በባዕድ አምልኮ፣ ብቻ ምኑ ተዘርዝሮ ያልቃል ለነፍሳችሁ ቀርቶ ለሥጋችሁ አንዳች በማይጠቅም፤ በሚያጎሳቁላችሁና በሚጎዳችሁ ሕይወት ዉስጥ ትመላለሳላችሁ:: ምርጫችሁን በዉል ያልተረዳችሁ፤ የሚያመዛዝናና የሚያገናዝብ ሕሊና(ሕያዉ ነፍስ) እያላችሁ የምትሰሩትን የማታዉቁ፣ በደመ ነፍስ የምትመላለሱ፣ የምትወጡ፣ የምትወርዱ ናችሁ:: ደግሞ በዚህ ሕይወት ዉስጥ እየተመላለሳችሁ «የሃይማኖት አባት ነን:: የእግዚአብሔር እንደራሴ ነን:: የሕዝቡ እረኛ ጠባቂ ነን» ትላላችሁ:: እግዚአብሔር መምሰልን የተላበሰች ሕሊናችሁን (ነፍሳችሁን) ማፈሪያና ያበደ አእምሮ እንዳደረጋችኋት ልትረዱ ይገባችኋል::

በብሉይ ዘመንና በሐዲስ ዘመን የተፈጸመዉን ድርጊት ሆነ ትምህርት በሚገባ አንብባችሁ ተረዱ:: ለእናንተ የአዳም ዘር ምን ያልተደረገላችሁ ነገር አለ!? ምን ያልተከፈለላችሁ ዋጋ አለ!? እንደዉ ሌላዉን ባታስተዉሉ እንኳ ማደሪያ ቦታ ጠፍቶ በከብቶች በረት ዉስጥ የተወለደዉን፣ ከዚያም እንደ አቅመ ቢስ ሄሮድስን ሸሽቶ ከእናቱ ከድንግል ማርያምና ከአሳዳጊዉ ዮሴፍ ጋር በረሀ ለበረሀ የተንከራተተዉን፣ እንደ ሰዉ ጥቂት በጥቂቱ ያደገዉንና የሰዎችን አኗኗር የኖረዉን፣ በተወለደዉ ሥጋ ሠላሳ ዓመት ሲሞላዉ የእዉነትን ቃል ለዓለም የገለጸዉንና ያስተማረዉን፣ የተለያዩ በሽተኞችን የፈወሰዉና ያጽናናዉን፣ የለያዩ ተአምራትን ያደረገዉን፣ በመጨረሻም እዉነትን በመናገሩና በማስተማሩ ክፉ ቅናት ያደረባቸዉ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን፤ ሕጉና ትዕዛዙን እንጠብቃለን፤ እናስጠብቃለን::» የሚሉ አስመሳይ አገልጋዮች የነበሩ የአይሁድ ካህናት፣ ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን በሐሰት ወንጀለዉት የተገረፈዉን፣ የተሰደበዉን፣ የተተፋበትን፣ የተደበደበዉን፣ የተሰቃየዉን፣ የተዘበተበትን ፣ ራቁቱን ያደረጉትን ፣ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የሰቀሉትን ፣ ባለቀ ሰዓት ላይ እንኳ በመስቀል ላይ ሆኖ «ተጠማሁ እባካችሁ የምጠጣዉን ዉኃ ስጡኝ?» ሲል እንኳ፤ ስንት የሚጣፍጠዉን መብልና መጠጥ የሰጠ፤ ተጨክኖበት መራራ ሐሞት የቀረበለትን ፣ ባጠቃላይ የተለያዩ ጸዋትዎ መከራ የተቀበለዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ታዉቁታላችሁ ወይ? ማንነቱንስ አስተዉላችኋል ወይ? እስቲ ምን ያላደረገላችሁ ነገር አለ? ምን ያልሆነላችሁ አለ? ምን ያህል ፍቅሩን

**እንደገለጸላችሁ አስተዉላችኋልን? ምን ያህል እንደለመናችሁና እንደተለማመጣችሁ ተረድታችኋልን? ምን ያህል እንዳከበራችሁና እንደሳሳላችሁ ተገንዝባችኋልን?** ብቻ እንደ እናንተ እንባ ቢኖረኝ **አሁንም ባነባዉላችሁ** በወደድኩ!

*ያ ይህን ሁሉ ያደረገላችሁ፤ ሕይወት የሚሆናችሁን ሥጋዉን ቆርሶ ደሙስ አፍሶ ራሱን በመስቀል ላይ ሰዉቶ «ሥጋዬን ብሉ፤ ደሜንም ጠጡ፤ የዘላለም ሕይወትን ታገኛላችሁ፤ በሰማያዊ መንግሥትም ዉስጥ ሕያዉ ሆናችዉ ትኖራላችሁ።» ያለዉ እኔ አምላካችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝ።* ***እኔ ይህን ያህል እያፈቀርኳችሁና እየፈለኳችሁ እኔን የሚያፈቅረኝና የሚፈልገኝ ሰዉ አጣሁ።*** *ዝም ብዬ እንዳልምራችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ፍርዴ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ነዉ። ዝም ብም ብዬ እንዳልፈርድባችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ርኅራኄና ፍቅሬ እጅግ ያይላል።* ***እኔም እንደ ሌሎቹ ሕያዋን ፍጥረቶቼ ቅዱሳንና ጻድቃን በእናንተ ኀዘተኛ ነኝ።*** *ከፍርድ ቀን በኋላ ግን ማንም ሰዉ ሆነ ሰይጣናት በእዉነተኞች፣ በቅኖችና በየዋሃን ላይ አንዳች ጥቃት ሆነ ጉዳት አያደርሱም። የሚያስቆጣኝንም ተግባር አይፈጽሙም። እንደ ዐመጻቸዉ ደረጃ ነጻነታቸዉ ተገድቦ በአንድ ቦታ ፍዳቸዉን ይቀበላሉ። እናንተ ግን ካዳችሁኝ፣ አስካዳችሁኝ፣ ሰደባችሁኝ፣ አሰደባችሁኝ፣ አዋረዳችሁኝ። ይኸዉም ስትፈልጉ « ሐሳች ነዉ።» ስትፈልጉ «ተራ ሰዉ ነዉ።» ስትፈልጉ « ነብይ ነዉ።» ስትፈልጉ «አማላጅ ነዉ።» ስትፈልጉ « ፍጡር ነዉ።» ስትፈልጉ « አንድ ኢየሱስ ነዉ፤ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ የሉም።» .. ወዘተ እያላችሁ በሞትና በክህደት ሕይወት ትመላለሳላችሁ። ታዲያ ታላቅ ዋጋ የከፈልኩላችሁ አምላክ ስለ ዓመፃና ክህደት ሕይወታችሁ ከገሃነመ እሳት በላይ መቅጫ ቦታ አዘጋጅቼ ብቀጣችሁ አያንሳችሁምን!*

*ከእኔ ይልቅ፤ሌት ተቀን የሚፈታተናችሁንና የሚያሰቃያችሁን፣ የሚቀጠቅጣችሁንና የሚያጎሳቁላችሁን ዲያብሎስንና ጭፍሮቹን ሰይጣናትን መምረጣችሁና ፈቃዳቸዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም መትጋታችሁ ስለ ምን ይሆን!? ይህ ምድራዊ ሕይወታችሁ ሕይወት ሆነና ነዉ ሌት ተቀን በዓመፃና በርኩሰት ሕይወት የምትመላለሱት? እኔን በሚያስቆጣ ተግባርና ዲያብሎስን በሚያስደስት ሕይወት የምትኖሩት? ይህ ሕይወት ሆነና ነዉ እርስ በእርስ የምትጣሉትና በስግብግብነት ሕይወት የምትመላለሱት? በስስት ሕይወት የምትኖሩት? ይህ ምድራዊ ሕይወታችሁ ሕይወት ሆነና ነዉ በቀለም፣ በዘር፣ በነገድ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ተለያይታችሁና ተቧድናችሁ በዲያብሎስ ሥርዓት በመመራት በጦርነት ፣ በግድያ፣ በግፍ፣ በጭቆና፣ በአድሎና በበደል ሕይወት የምትኖሩት?*

***ማስተዋሉን አጣችሁ እንጂ በዚህች ምድር አጭር ዘመን ቆይታችሁ እንኳን በከፋና በከረፋ ሕይወት ዉስጥ ልትመላለሱ ቀርቶ አንዲት ቀን እንኳ ሊዋልባትና ሊታደርባት የማትመረጥ መኖሪያ ናት።*** *ነገር ግን ይህች ምድር ቀድሞ የእናንተ ያልሆነች የሰይጣናት መቀጫ ቦታ ብቻ የነበረች፤ በአዳምና በሔዋን ዓመፃ ምክንያት ከገነት ሲባረሩ ለእነሱ መኖሪያና መቀጫ በሚሆን መልኩ*

ተዘጋጅታ የገቡባት፣ እናንተም በመጀመሪያ ወላጆቻችሁ ዓመፃ ምክንያት እየተቀጣችሁበትና እየጠራችሁበት ያለች ቦታ ናት እንጂ የእናንተ እዉነተኛዉ መኖሪያ ቦታችሁ ገነትና ሰማያት ናቸዉ:: እናንተ ግን በአጭር ዘመን ቆይታችሁ እኔን በመፍራትና በማምለክ ተመላልሳችሁ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታችሁ ከመግባት ይልቅ ከቀድሞ ወላጆቻችሁ ብሳችሁ የበለጠ ዓመፃና ክህደትን በመፈጸም ራሳችሁን ለበለጠዉ መቀጫ ቦታ ሲኦልና ገሃነመ እሳት ትዳርጋላችሁ:: በዚያ ዳግም የንስሐ እድል የሌላችሁ መሆኑን አሁንም ደግሜ አሳዉቃችኋለሁ:: የእናንተ የንስሐ እድል በዚህች እጅግ እጅግ ለአጭር ዘመን በነጻነት በምትንቀሳቀሱባት ምድር ዉስጥ ብቻ ነዉ:: እኔ <u>በፍጥረቴ አንዳች አድሎ አላደርግም:: ሰይጣናትም በዓመፃቸውና በክህደታችዉ ምክንያት ነጻነታቸዉን ገድቤ በገሃነመ እሳት የምቀጣቸዉ ከሆነ እናንተ የአዳም ዘሮች የንስሐ እድል ተሰቷችሁና ታላቅ ዋጋ ተከፍሎላችሁ በዓመፃና በክህደት ሕይወታችሁ ከጸናችሁ እንዴት አብልጬ አልቀጣችሁ!? እጅግ እቀጣችኋለሁ::</u>

እንግዲህ ይህን ሁሉ የተናገርኳችሁ እዉነትን ፈልጋችሁ በመምጣታችሁና ራስችሁን ዝቅ አድርጋችሁ በደጄ በመዉደቃችሁ ነዉ እንጂ በየቦታዉ አገልጋዮቼና ምስክሮቼ ስለ እዉነት ሊያስተምሯችሁና ሊነግሯችሁ ይችሉ ነበር:: ታዲያ እዉነተኛዉን ሃይማኖት የሚወክሉት እነዚህ የኢትዮጵያ ቀጥተኛዉ ተዋህዶ ሃይማኖት «ወኪል ነን» ብለዉ ከእናንተ ጋር እዚህ ሱባኤ ቦታ የመጡት ሰዎች እንዳይመስሏችሁ:: እነሱን በደንብ አዉቃቸዋለሁ፣ እንደእናንተ በስሜ የሚነግዱ፣ ትዕዛዙንና ሕጉን ይናገራሉ እንጂ እንደ ቃሉ የማይኖሩ፣ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ፣ በኔ ቦታ ላይ ሆነዉ መመስገንና መከበርን የሚፈልጉ፣ አንዴ በቤተክርስቲያን አንዴ በዓመፃዉና በርኩሰቱ ቦታ እየተገኙ ቡራኬ የሚሰጡ፣ ለሃይማኖቷ ሆነ ለሥርዓቷ ደንታ የሌላቸዉ፣ ሌት ተቀን ለጥቅማቸዉ ብቻ የሚሯሯጡ፣ ጥቅምና ክብር ካገኙ የዓመፃና የክህደት ተግባር ከመፈጸምና ከማስፈጸም ወደ ኋላ የማይሉ፣ ባጠቃላይ በእዉነተኛዋና በብቸኛዋ የሕይወት መንገድ በቀጥተኛዋ(ኦርቶዶክስ) ተዋህዶ ሃይማኖት ዉስጥና በብቸኛይቱና እዉነተኛይቱ ቤተክስቲያን ዉስጥ ሆነዉ እንደ ቃሌ የማይኖሩ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ:: ወደዚህ ስፍራ ተመርጠዉ የተላኩት የተለየ ምድራዊ ጥቅም የሚገኝበት ስለመሰላቸዉና «የሃይማኖቱ ተጠሪና መሪ ነኝ፣ የክርስቶስ እንደራሴ ነኝ::» ብለዉ በዓመፃ በወንበር ላይ የተቀመጡት ዕጨጌ ወዳጅና በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ፣ በጥቅማ ጥቅም የተገናኙ ስለሆነ ነዉ እንጂ በቅድስና ሕይወታቸዉ ተመርጠዉ የተላኩ አይደሉም::

እነዚህ ተወካዮች የሚያገኑትና ከፍ ከፍ የሚያደርጉት እንዲሁም የሚያስመልኩትን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ከዚህ ሱባኤ እንደወጣችሁ በቤተ ክህነቱ አዳራሽ ዉስጥ በአራቱም አቅጣጫ ግድግዳ ላይ በሳንቲ ሜትር ርቀት ለቁጥር በሚታክት ብዛት የተለጠፈዉን የአንድ ሰዉ ሥዕል መመልከት ትችላላችሁ:: እኔ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆንኩ እናቴ ድንግል ማርያም እንዲሁም ቅዱሳኖቼ እንኳ አንድ ሺኛዉ ያህል እንኳ አልገነንም፣ ከፍ ከፍ አላልንም:: ከሥዕሉ ጋር መጠኑ አነስ ቢልም የገነነዉን የዲያብሎስ ዓርማ የሆነዉን ኮከብ በየቦታዉ ተንጠልጥሎ ማየት ትችላላችሁ:: በተጨማሪም ቦሌ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን መግቢያ በር ጋር የቆመዉን በሕይወተ ሥጋ እያለ «እኔ ቅዱስ ነኝ»

በማለት በአጫፋሪዎቹ አማካይነት ያስቀመዉን ሐዉልት መመልከት ትችላላችሁ:: የዲያብሎስ ሥርዓት የዘረጉት የተለያዩ የአገራት መሪዎች እንኳ ራሳቸውን በዚህ መልክ አላገነኑን፤ አላስመለኩም:: እነዚህ ተወካዮች ሌላዉ የሚታወቁበት ልዩ ተግባር ደግሞ «የሃይማኖት መሪ ነኝ» ብለዉ ከተቀመጡት ዘንድ ሞገስንና ሽልማትን፣ ስልጣንን ለማግኘት ሲሉ እዉነተኛ አገልጋዮችን የሚያሳድዱ፣ የሚወነጅሉ፣ የሚያንከራትቱ፣ የሚያሳስሩ፣ የሚያስደበድቡ፣ የሚያስገድሉ፣ ባጠቃላይ ለበላይ አለቆቻቸዉ ታማኝ ሆነዉ ሕሊቸዉን በመሸጥ የሚመላለሱ በመሆናቸዉ ነዉ እንጂ ስንት ጻድቃንና እዉነተኛ አገልጋዮች እያሉ እነዚህ እለት እለት በዓመፃቸዉ የሚያስቆጡኝ አስመሳይ አገልጋዮች ወደዚህ የተቀደሰ ስፍራ ባልተላኩ ነበር::

እዚህም እንደ ዓለም ስራቸዉ እናንተንም፣ እኔንም አታለዉ ተመሳስለዉና የተለየ የከበሬታ ወንበር አግኝተዉ ለመመለስ እንደእናንተ ደጅ ጠኝ መስለዉ ተገኝተዋል:: ይህን ሕይወት ከረሱት ብዙ ዓመታት አስቆጥረዋል:: አሁን ግን ግድ ስለሆነባቸዉ ነዉ እንደ እናንተ በሙብሉ እየተንገሸገሹ «መች ቶሎ ባለቀልን?» እያሉ ከሱባኤ የሚወጡበትን ቀን የሚጠብቁት:: ከትቢያ አንስቻቸዉና የቆሎ ተማሪነት ጊዜያቸዉን ዘንግተዉ አሁን ላሉበት ደረጃ ሲደርሱ ያ በረከትና ጸጋ ያገኙበት የነበረዉን ሕይወት ከናካቴዉ ረስተዉና አሁን ያሉትን ተማሪዎችና መምህራንን ማስታወስና አስፈላጊዉን ሊፈጽሙላቸዉ ሲገባ፤ እነሱ ግን እንኳን ይህንን ሊያደርጉ ቀርቶ አሁን ያሉበትን ወንበር በማምለክ በኔ ቦታ ተቀምጠዉ መመስገንና መመለክን ይፈልጋሉ:: እናንተ ግን መጀመሪያ ላይ ብታጉረመርሙም አሁን ግን ደስ ብሏችሁ «ለካስ በሱባኤ እንደዚህ የተሰበረ ሕይወት ይገኝበታል» በማለት ለወደፊትም ሱባኤ እንደምትገቡ ለራሳችሁ ቃል የገባችሁት::

ከእንግዲህ እናንተ መመልከት ያለባችሁ እነዚህን አስመሳይ አገልጋዮችን ከነፈሰዉ ጋራ የሚነፍሱትን፣ እንደ ቦይ ዉሃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚሄዱትን፣ ለሆዳቸዉ ብቻ ያደሩትን ሳይሆን፤ ጊዜያቸዉን ሰዉተዉ «ደከመኝ፣ ሰለቸኝ፣» ሳይሉ፤ «ተራብን ፣ ተጠማን ፣ ተቸገርን» ሳይሉ፤ በእዉነተኛ አምልኮ ሆነዉ ስለ እዉነት እየመሰከሩ፣ ምዕመኑን ከዘልማድ ሕይወት የሚያላቅቁትንና ለንስሐ ለሥጋ ወደሙ የሚያበቁትን፤ ለመልካም ተግባር የሚያሰልፉትን፤ እንዲሁም ዘመናቸዉን ሁሉ ከሰዉ እንዳች ሳይጠብቁ «ከእግዚአብሔር ነዉ ዋጋ የምናገኘዉ::» በማለት መምህራንንና ሊቃዉንትን የሚያፈሩ በየቦታዉ የተረሱና አስተዋሽ ያጡ እዉነተኛ አገልጋዮቼን ሊቃዉንትንና የብሉያቱና የሐዲሳቱን እንዲሁም የዜማዉ፣ የዝማሜዉ፣ የአቋቋም፣ የድጓ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ..ወዘተ መምህራንን፤ ካህናትን ፣ መነኮሳትን፣ ሰባኪያንን ፣ዲያቆናትን፣ እንዲሁም ዘመናቸዉን ሁሉ በየገዳሙና በየዋሻዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ በመኖር ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ ሌት ተቀን የሚጸልዩትንና የሚያነቡትን መናንያንና ባሕታዉያንን ነዉ::

በአስመሳይ አገልጋዮች ሳትሰናከሉ እዉነተኛ አገልጋዮቼ በሚያዟችሁ መሰረት በኢትዮጵያ በቀጥተኛዋ ተዋህዶ ሃይማኖት ስር ሆናችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም

በመጠመቅ፣ ሕይወት በሚሆናችሁ በሥጋዬና በደሜ ታተሙ:: በምድራዊ ሕይወት ዘመናችሁም በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር በመመላሰስ ሰማያዊ መንግስታችሁን በመናፈቅ ኑሩ:: ያኔ በምድርም በረከትን ታገኛላችሁ፤ በሕይወታችሁም በፍቅር፣ በሰላም፣ በእርካታ፣ በጤና መኖር ትችላላችሁ::» በማለት ነዉ ያላሰብነዉና ያልጠበቅነዉ ምላሽ የተሰጠን በማለት አቅርበዋል::

የሌሎቹም ክፍለ አህጉር ተወካዮች ተጠይቀዉ «አሁን ከተነገረዉ ጋር አንድ አይነት ምላሽ ነዉ የተሰጠን::» ብለዉ ሁሉም በአንድ ድምጽ መልሰዋል:: ነገር ግን የኢትዮጲያ ቀጥተኛ ተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮች «እኛ በእዉነቱ ሁል ጊዜ ከአምላካችን መልስ የምናገኝና የምንነገኝ ስለሆነ በዚህ ሱባኤ ላይ አንዳች የተባልነዉ ነገር የለም:: የሌሎቹ አገራትና የተለያየ እምነት ተወካዮች «በሱባኤዉ እንዲህ ተባለ::» ብለዉ በአንድ ድምጽ የተናገሩት ተመካክረዉ ነዉ እንጂ ለእኛ ለሃይማኖቱ ባለቤቶች ያልተገለጸዉ ለእነሱ እንዴት ይገለጽላቸዋል?» <u>በማለት ንስሐ ከመግባት ይልቅ ስለክብራቸዉና ለጥቅማቸዉ በመቆም ዓለም እዉነታዉን እንዲያዉቅ እግዚአብሔር የተናገረዉን የእዉነት ቃል እንደ ቀደሙት ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት አጣጣሉት::</u>

በመጨረሻም የተባበሩት መንግስታት የሦስቱን የኢትዮጵያን የተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮችን አስተያየት ሰምተዉ ድምጽም በድምጽ የመሻር ስልጣናቸዉ ተጠቅመዉ ከ195 አገራት ባላይ የተቀበሉትን እዉነተኛ የሕይወት መንገድ የሆነችዉን የኢትዮጵያ ተዋህዶን ሃይማኖት በራሳቸዉ በኢትዮጵያዉያን የተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮች ተቃዉሞ ስለገጠመዉ፤ «እናንተ ተወካዮች በብልጠት ተመካክራችሁ የሌለዉን እግዚአብሔር አለ በማለት ልታታልሉን ብትሞክሩም ይኸዉ አብረዋችሁ የነበሩት እናንተ «ትክክለኛ ሃይማኖት ነዉ::» ያላችሁትን የሚወክሉ «ዉሸት ነዉ አልተገለጸላቸዉም» በማለት ስላረጋገጡልን፤ ዓለም እግዚአብሔር እንደሌለ እንዲያዉቅና ተፈጥሮ በለገሰችዉ ዘመን ሁሉ በዘፈንና በዳንኪራ ራሱን እያስደሰተ ይኑር:: «ሲኦል፣ ገሃነመ እሳተ፣ ገነት፣ መንግስተ ሰማያት» የሚባለዉ ሁሉ ዉሸት መሆኑ ተረጋግጧል::» በማለት መግለጫ በመሰጠቱ በድንጋጤ ዉስጥ የነበርኩት እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ያላሰብኩት ዉሳኔ በመሰጠቱ እኔና ሠራዊቶቼ ሰይጣናት ደስታችንን ለአንድ ወር ያህል በመዝፈንና በመጨፈር ልናሳልፍ ችለናል::» **ይላል የጨለማዉ ጌታ ሰዎችን ስለ ክብራቸዉና ጥቅማቸዉ የሞት መንገድን የሚያስመርጥ ሐሰተኛዉና አታላዩ መንፈስ ዲያብሎስ::** » ይላል፤

**ከላይ በግልጽ እንደተገለጸዉ እግዚአብሔር ዓለም እዉነቱን እንዲያዉቅ ፈልጎ ነበር በዚህ መልክ መልእክቱን ያስተላለፈዉ:: ነገር ግን በመጨረሻ እንደተገለጸዉ ዓለም በተልካሻና በማይመስል የሐሰት ምስክት እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም:: የሚያሳዝነዉ ደግሞ የእዉነት ባለቤት የሆኑትና የእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ተወካይ የሆኑት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተወካዮች ናቸዉ ለጊዚያዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም ብለዉ ነዉ ዓለም እዉነቱን እንዳይቀበልና በአንድ እዉነት ዉስጥ እንዳይሆን የሐሰት ምስክርነት የሰጡት:: ይህንን መልእክት እንዴት ያዩታል?**

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እግዚአብሔር እዉነትን ለዓለም ለመግለጽ ያላደረገዉ አንዳች ነገር የለም፡፡ ራሱ በሥጋ ተገልጾ ከማስተማርና ከማገልገል በተጨማሪ ነቢያትን፣ መምህራንን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ መምህራንን፣ ጻድቃንን እያስነሳ ለዘመናት እዉነትን ለዓለም ገልጿል፤ አሁንም አገልጋዮቹን እያስነሳ እየገለጸ ነዉ፡፡ ነገር ግን ትዉልዱ የሥጋና የደም ስሜቱን እንጂ የነፍሱን(የሕሊናዉን) ስሜትና ድምፅ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆኑ፤ ራሱን ለመከራ ሥጋና ለመከራ ነፍስ አሳልፎ ሰጧል፡፡ እኔ ይህን መልእክት ጽጽፍ በተለየ ሁኔታ እያነባዉና እያለቀስኩ ነዉ የጻፍኩት፡፡ ምክንያቱም ያ ነፍሴ ብቻ የምትሰማዉ ድምፅ ከላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚያ ሱባዔ ላይ ላሉት የተናገራቸዉ ለእኔም መናገሩ ስለሆነ ነዉ፡፡ አሁንም ሳነበዉ አነባለሁ፡፡ ምክንያቱም «ብቻ እንደ እናንተ እንባ ቢኖረኝ <u>አሁንም ባነባዉላችሁ</u> <u>በወደድኩ!</u>» «**<u>እኔ ይህን ያህል እያፈቀርኳችሁና እየፈለኳችሁ እኔን የሚያፈቅረኝና የሚፈልገኝ ሰዉ አጣሁ፡፡</u>** ዝም ብዬ እንዳልምራችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ፍርዴ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ነዉ፡፡ ዝም ብም ብዬ እንዳልፈርድባችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ርኅራኄና ፍቅሬ እጅግ ያይላል፡፡ **<u>እኔም እንደ ሌሎቹ ሕያዋን ፍጥረታቴ ቅዱሳንና ጻድቃን በእናንተ ኀዘተኛ ነኝ፡፡</u>** » እያለ ሲናገረኝ ነፍሴ እንዴት ይህን አሳዛኝ አንጀት የሚበላ ንግግር ትቋቋመዉ!

አሁንም እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚያነበዉ ሰዉ እኔ የፈጠርኩት ገጸ ባሕርይ አድርጎና ንግግሩንም እኔ የፈጠርኩት አድርጎ በማሰብ ከቁም ነገር ላይቆጥረዉ ይችል ይሆናል፡፡ መሪዉ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ግን እርሱም እኔ የተሰማኝ ኀዘንና ስሜት እንደሚሰማዉ እገምታለሁ፡፡ ምክንያቱም ነገረ መስቀሉ በሕሊናዉ ተስሎ የክርስቶስ ደም ይፈስበታልና፡፡ እንዲሁም አምላኩ ራቁቱን ሆኖ በመከራና በዉኃ ጥም ዉስጥ እያለ ስንቱን የሚጣፍጥ ምግብና መጠጥ የፈጠረ አምላክ ተጨክኖበት መራራ ሐሞት(መርዝ) ሲቀርብለት እየተመለከተ የአምላኩ ፍቅርና የቸርነት ስራ በዓይነ ሕሊናዉ ድቅን ይልበታልና፡፡

በመጨረሻ የታየዉ ክስተት ደግሞ አሁን እየታየ ያለዉን እዉነታ ስለሚገልጽ ከማሳዘን ዉጭ ብዙም አያስደንቀንም፡፡ ምክንያቱም በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት ብዙዎቹ የሕይወት መንገድ የሆነችዉ ብቸኛ ሃይማኖት «አምላክ ሰዉ ሆነ ሰዉ አምላክ ሆነ» ብላ የምትሰብከዉና የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በግልጽ የምታስተምረዉ፤ እንዲሁም ከድኅነታችን ጋር ፈጽሞ የማትለየዉን የመዳኛችን ምክንያት የሆነችዉን እመቤትና ንግሥት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን አክብራና አፍቅራ የያዘችዉ፤ ከዚህ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ባለሟሎችንና ወዳጆችን ቅዱሳን መላእክትን፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን አክብራ የያዘችዉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መሆኗን ቢያዉቁም፤ ለጊዜያዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም ብለዉ የእግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነትና የሶሻሊስት እንዲሁም የካፒታሊስት እምነት ተከታይ የሆኑትንና ፍጹም የዲያብሎስ አገልጋይ የሆኑትን ፖለቲከኞችን ተከትለዉ ነፍስና ሥጋን ለይተዉ ቤተ ሕዝቡን ለዲያብሎስና ለእግዚአብሔር ከፋፍለዉ መስጠታቸዉና የዚህን ዲያብሎሳዊ ሥርዓት ተቀብለዉና ደግፈዉ ከዚያም ባለፈ ዋና አስፈጻሚ ሆነዉ በመገኘታቸዉ ነዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አምስት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በዚሁ ክፍል በምዕራፍ ሦስት ከገጽ 221-226 የተገለጸዉ:

«አንዳንድ ምእምናን ተሰብስበዉ ቅሬታቸዉን ለማቅረብ ወደ ሃይማኖት አባቶች በመቅረብ <u>«የተከበሩ የኔታ! እኛ ብዙዉን ጊዜ ስንማርና ስንሰበክ ጻድቃን ናችሁ፤ እዚህ በመምጣታችሁ ድናችኋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ እዚህ መታችሁ በማጨብጨባችሁና እልል በማለታችሁ መንግስተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ፤ አሜን ካላችሁም ገነት ትገባላችሁ፤ የተመሰገናችሁ ቅዱሳ ናችሁ::» እያሉ ደስ የሚል ስብከትና እኛም በቀጥታ መንግስተ ሰማያት ዉስጥ ያለን እስኪመስለን ድረስ ነዉ የምንሰማቸዉ የነበረዉ:: ባለፈዉ ሳምንት ግን አንድ የማናዉቃቸዉ አባት ሰባኪ ይሁኑ ተሳዳቢ አናዉቅም</u> « እናንተ ምእመናን ሆናችሁ አገልጋዮች እግዚአብሔር እንደ ሰዉ አይታለልም:: እንኳን የምትሰሩትንና የምትናገሩትን ቀርቶ ጠማማና ርኩሰት የሞላዉ አሳባችሁን በሰማያዊ መዝገቡ ላይ የሚመዘግበዉና ንስሐ ላልገባችሁበትና ላልተጸጸታችሁበት ኃጢአት ሁሉ እንደምትጠየቁ ልታዉቁ ይገባል:: ስለዚህ እናንተ ያማረ ለብሳችሁ ብትታዩም እርሱ ባለቤቱ ደግሞ ዉጫችሁን ሳይሆን ዉስጣችሁን ነዉ የሚመለከተዉ:: በመሆኑም ከማስመሰል ሕይወት ተለይታችሁ እዉነተኛ ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁን እየተናዘዛችሁና እየተጸጸታችሁበት የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀበሉ:: ከዚያ ዉጭ በብልጣብልጥነትና በአቋራጭ መንገድ የእግዚአብሔርን መንግስት እንወርሳለን ብላችሁ አታስቡ:: የምትማሩትን ሆነ የምትሰሙትን ቃል በሕይወታችሁ ለዉጣችሁ እንደ ቃሉ ሆኖ በመገኘት በመልካም ምግባርና ሕይወት ተመላለሱ:: ያኔ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ ታገኛላችሁ:: ጸጋዉ ይበዛላችኋል:: በመጨረሻም ለሰማያዊ መንግስት ትበቃላችሁ:: ከዚያ ዉጭ በዘልማድና ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ቤተክርስቲያን ስለተመላለሳችሁ ብቻ ለመንግስተ ሰማያት የምትበቁ እንዳይመስላችሁ::

ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደምትመጡ አዉቃችሁ እለት እለት ፊታችሁን እንደምትታጠቡ ሁሉ ለፈጸማችሁት የተግባር ሆነ የንግግር ኃጢአት ንስሐ ሁል ጊዜ ልትገቡና ስለ ክፋትና ርኩሰት አሳባችሁ በኀሊናችሁ ልትጸጸቱ ይገባችኋል:: ያለፈዉ የማስመሰል የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የዘፈን ፣ የዳንኪራ፣ የዝሙት፣ የመዳራት፣ የሴሰኝነት ፣ የጥል፣ የጥላቻ፣ የቂም በቀል፣ የግድያ፣ የስርቆት፣ የባዕድና የጣዖት አምልኮ፣ የክፋት፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት ..ወዘተ ዘመን ይበቃችኋል:: እስከ አሁን እግዚአብሔር የንስሐ እድሜ ሰቷችሁ ለዚህ ዘመን በቅታችኋል::» በማለት ባዶነት እንዲሰማንና ኃጢአተኞች እንደሆን አደርገዉ በመቁጠር «ንስሐ ግቡ» አሉን:: ከሁሉ የሚገርመዉ ደግሞ እስከዛሬ ማንም ያልተናገረንን «አትዝፈኑ፤ ዳኒኪርተኛ አትሁኑ» አሉን:: እኛን ከሚናገሩ ለምን ቀን ከሌሊት በቴሌቭዥና በሬዲዮን የሚያቀርቡትን አይናገሩም? ክልክል ቢሆን ኖሮ በተለያዩ ሚዲያ አይተላለፍም ነበር:: ደግሞ የባህላችን መገለጫ የምንዝናናበትና የምንጨፍርበት ነዉ:: ሌላዉ ደግሞ የተለያዩ ባህላዊ አምልኮ እኛም ሆነ ቤተሰቦቻችን ወቅት እየጠበቁ ያከብራሉ፤ አስፈላጊዉንም ግብር ያቀርባሉ:: ይህም አንዱ የማንነታችንና የባህላችን መገለጫ ነዉ:: እኛ ብዙዉን ጊዜ በቤተክርስቲያን

በዐላት ላይ ተገኝተን ታቦት እናከብራለን፤ አንዳንዴ እንቅልፍ ካላሸነፈን እሁድ እሁድ ቤተክርስቲያን መተን እንሳለማለን:: ታዲያ ምን ጎደለ ብለዉ ነዉ እንዲህ ባዶነት እንዲሰማን አድርገዉ የሚያስተምሩንና የዘልማድ ሰዎች አድርገዉ የሚቆጥሩን?

እንዲህ የሚናገሩን ከሆነ ደግሞ እንደልባችን የምንሆንበትን የጴንጤዎችን እምነት እንከተላለን:: እነሱ ሁል ጊዜ «ጌታን ከተቀበላችሁ ትድናላችሁ፤ ስለምግባር አታስቡ፤ «ዋናዉ የሱስ ጌታ ነዉ::» ብላችሁ ከመሰከራችሁ መንግስተ ሰማያት ሰተት ብላችሁ ትገባላችሁ::» እያሉ ያባብሉናል:: እኛ ደግሞ «ከቤተሰባችን የወረስነዉ እምነት ስላለ ወደ እናንተ አንመጣም::» እያልን እስከአሁን ድረስ ሃይማኖታችንን አለወጥንም:: አሁን የምታከብዱብን ከሆነ እኛ እንደልባችን የምንሆንበትን፣ መጾም የሌለበትን፣ በፈለጉት ጊዜ በፈለጉት የአለባበስ ስታይል ከፈለጉ በተወጣጠረ ሱሬ፣ ከፈለጉ ደረትና ጡት በተገላለጠ አለባበስ፣ ከፈለጉ በአጭር ቀሚስ፣ ከፈለጉ በታይት፣ ከፈለጉ በቁምጣ ወደ አዳራሽ እየሄዱ የሚዝናኑበትን፣ እንዲሁም በዘመናዊ መሳሪያ የሚዘፈንበትንና የሚጨፈርበትን መዝሙር እናዳምጣለን፤ ጭፈራዉንም እንመለከታላን፤ እኛም ሲያስፈልገን እንደ ብሔር ብሔረሳችን እንጨፍርበታለን፤ በመሬት ላይ እየተንከባሉና እየተንፈራገጡ የሚያሳዩትን ትዕይን በመመልከት በመንፈስ እንሞላለን:: » በማለት ቅሬታቸዉንና አቋማቸዉን አቅርበዋል::

ቅሬታቸዉን የሰሙት አንድ የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ « ምን ጉድ መጣ? ምን ተብለዉ ተሰብከዉ ይሆን እንዲህ በቁጣ የመጡት?» በማለት አሳብ ዉስጥ አስገብታችሁኝ ነበር:: አሁን ንግግራችሁን ስሰማ ተረጋጋዉ:: መቼስ እኛ ሰዎች ስንባል የሚያመሰግነንን፣ የሚክበንን፣ የሚሸነግለንን ሰዉ ነዉ የምንወደዉና ንግግሩን ለማዳመጥ የምንፈልገዉ እንጂ ካለማስመሰልና ካለይሉኝት የሚናገረንንና የሚያስተምረንን አንወደዉም:: ብናስተዉል ግን እዉነቱን የሚነግረንን እንዲሁም ስለ ኃጢአታችን የሚገስጸንን ነበር መስማትና ማዳመጥ የነበረብን:: ምክንያቱም እርሱ ነዉና እዉነተኛ የነፍስ እረኛ:: እኛ ያስተማሯችሁ አባት ገና በትምህርት ያልጠነከራችሁ መሆናችሁን ስለተረዱ ነዉ እንጂ ብትጠነክሩ ኖሮ ጥልቅ ትምህርት ያስተምሯችሁ ነበር:: የበለጠ ይገስጿችሁ ነበር:: እናንተ እንዳላችሁኝ ከሆነ የለዘበ ቀለል ያለ ትምህርት ነዉ ያስተማሯችሁ እንጂ እናንተን አንዳች የሚያስቆጣና የሚያሳዝን ነገር አልተናገሯችሁም:: ከኔ ጀምሮ ሁላችንም ኃጢአተኞች መሆናችንን ሁል ጊዜ ልናምን ይገባል እንጂ ራሳችንን አንዳንድ እምነት ድርጅቶች እንሚሉት « ጻድቅ ነን» እያሉ ራሳቸዉን እንደሚያመጻድቁት ሰዎች አስተሳሰብ ካለን ዋና ኃጢአተኞች መሆናችንን ልናዉቅ ይገባል:: እንኳን በባዶ ሕይወት ዉስጥ ሆነን ቀርቶ በቅድስናና በጽድቅ ሕይወት ዉስጥ ብንሆን እንኳን ራሳችንን ተራ ወራዳ ኃጢአተኞች ሰዉ አድርገን ነዉ ወደ አምላካችን መቅረብ ያለብን እንጂ ነገ የምንሆነዉን ስለማናዉቅ በጽድቅ ስራችን ልንመጻደቅ አይገባም:: ብዙዎች ራሳቸዉን በማመጻደቃቸዉና በማስታበያቸዉ ምክንያት ነዉ አይወድቁ አወዳደቅ የወደቁትና የተዋረዱት::

አንዳንድ አባቶችና ወንድሞች የሚያመሰግኗችሁ «ጻድቃን ናችሁ፤ እዚህ በመምጣታችሁ መንግስተ ሰማይት ትገባላችሁ፤ ቅዱሳን ናችሁ.. ወዘተ» እያሉ ደስ ደስ የሚል ትምህርት የሚሰጧችሁና እናንተም ደስ ብሏችሁ ንስሐ ከመግባት ይልቅ በኃጢአታችሁ እንድትጸኑ እያደረጉ መሆኑን ስላላስተዋሉና እናንተም ስለምታበሏቸዉ፣ ስለምታጠጧቸዉ፣ አባት አባት፣ መምህር መምህር፣ ቅዱስ ቅዱስ፣ ብጹዕ ብጹዕ .. ወዘተ» ስለምትሏቸዉ፤ በይሉኝታ ተጠፍረዉና ክብራቸዉንና ጥቅማቸዉን በማስቀደማቸዉ ምክንያት ነዉ።

እኚህ አባት ግን ዋሻ ዉስጥ የነበሩ የዚህን ዓለም ስልጣን፣ ክብር፣ ብልጽግና፣ ዝና የናቁ፤ ዘመናቸዉን ሁሉ በዋሻ ዉስጥ ያሳለፉ፤ ለአገራቸዉና ለሕዝቧ ሌት ተቀን የሚጸልዩና የሚያነቡ፤ አምላካቸዉንና እናቱን ድንግል ማርያምን «ይህች ቅድስት አገር ካልተማረችና እዉነት ካልነገሠባት በቀር በጫማ አልረግጣትም» በማለት እንደምታያቸዉ በባዶ እግራቸዉ የሚንቀሳቀሱ፤ እንዲሁም ለአስራዎቹ አመታት በጸጉራቸዉ ሆነ በጺማቸዉ ላይ ምላጭ ሆነ መቀስ ሳያሰርፉ በመቆየታቸዉ የተጎነጎነ ጸጉራቸዉና ጺማቸዉ እብድ ያስመሰላቸዉ፤ አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች ራሳቸዉን ለንስሐና ለተቀደሰ ሕይወት ማብቃት ሲገባቸዉ «በባዶ እግር በመሄድ አይጸደቅም። እንደ እብድ መንጨባረር ከእግዚአብሔር አይደለም» እያሉ የማይመለከታቸዉን ቢዘባርቁም፤ እርሳቸዉ ግን ለዚህ ለተጎሳቆለ ገጽታ የተዳረጉበትን ምክንያትና ዓላማቸዉን ያዉቃሉና የሚተቿቸዉን በዝምታ በማለፍ እስከአሁን ድረስ በዚህ አቋማቸዉ ጸንተዉ ያሉ፤ ከባዕታቸዉም «ምህረት እስካልተደረገ ድረስ አልወጣም» በማለት ብዙ ዘመናትን ያሳለፉ ሲሆን፤ አሁን እዚህ ሊመጡ የቻሉትም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም «ልጆቼ ምእመናን እረኛ እንደሌላቸዉ በጎች ተቅበዝብዘዉብኛልና ሰብስብልኝ፤ በእዉነት የሚያስተምር፣ በሕይወቱ አርአያ የሚሆን፣ በነገረ መስቀሉ ፍቅር የሚቃጠል፣ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ የሚመሰክር፣ ካለማስመሰልና ካለሽንገላ የሚያስተምር አገልጋይ እዉነተኛ እረኛ አጥቻለዉና ሂድና ሕዝቡን አስተምር፤ ወንጌልን ስበክ፤ ለንስሐ ለቅዱስ ቁርባን አብቃ። አንዳንድ «ሰባኪ ነን» እያሉ ምእመኑን የሚያደናግሩ እንደ መናፍቃኑ የመዝናኛ ጉባኤ እያዘጋጁለት ወደ ልቡ እንዳይመለስና ወደ ንስሐ እንዳይቀርብ አድርገዉታል። ስብከታቸዉም እንደ መናፍቃን የሆነ፤ መዝሙራቸዉም ዘፈን ዘፍን ያለ፤ ምስጋናቸዉም ጭፈራ የመሰለ፤ ባታላዩ መንፈስ የሚመሩ፤ «ሰባኪ ነን» የሚሉትም በትዕቢትና ዓመፃ ሕይወት የሚመላለሱ ተኩላዎች ስለሆኑ ምእመኑ በእነዚህ ተኩላዎች ከመበላታቸዉ በፊት እዉነተኛ የቤተክርስቲያኗን አስተምሮ የጠበቀ ትምህርት ስጥ።

በእረኝነት በወንበር ላይ የተቀመጡት ሲሆን ሲሆን ራሳቸዉ እየተንቀሳቀሱ ምእመኑን ሊያስተምሩትና ለንስሐ ሊያበቁት ሲገባ፤ ያም ካልሆነላቸዉ የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት፣ አስተምህሮና ትዉፊት መጠበቅ ሲገባ፤ ለጥፋት ሰዎች ከለላና ጠበቃ ሆነዉ የዓመፃና የክህደት ተግባር የሚያሰሩ ስለሆነ፤ አንተ በአራቱም ማዕዘን እየተንቀሳቀስክ ከፈቀዱልህ በየአብያተክርስቲያኑ

በዉስጥ፣ ከከለከሉህ ደግሞ እንደ ተገፊ በዉጭ ሆነህ አስተምር፤ ስበክ፡፡ እኔ አብሬህ ነኝ አትፍራ፡፡ እነሱ ልጄን ራቁቱን በመስቀል ላይ ሰቅለዉ እያላገጡበትና በቁስሉ ላይ እንጨት እየከተቱበት ነዉ፡፡ መስቀሉንም የያዙት ሊነግዱበታ፣ ለያስመስሉበት፣ ሊከበሩበት እንጂ መከራን ሊቀበሉበትና ስለ እዉነት ሊመሰክሩበት አይደለም፡፡  ቀኑ ሲደርስ ዋጋ ስለሚከፍሉበት አንተ ግን ምእመኑን በሚገባ አስተምር፤ ስለ እዉነት መስክር፡፡» በማለት ስለታዘዙ ነዉ ወደ ዓለም አልወጣም ብለዉ ተደፍተዉ ከሚኖሩበት ዋሻቸዉ መተዉ ለማስተማር የተገደዱት፡፡

እናንተ አሁን «ተሰደብን» የምትሉት እንኳን መሰደብ ቀርቶ ግሳጼ አልደረሰባችሁም፡፡ ቃሉን አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ በቅዱሳት መጽሐፍት ዉስጥ እንደተጻፈልን ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ ወንድሙን «ደንቆሮ» ብሎ የሚሰድብ «ገሃነመ እሳት ይገባዋል» ብሎ አስተምሮናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጆሮዋቸዉ እየሰማ ቃሉን በተግባር የማይፈጽሙትን ዐይናቸዉ እያየ ምንም እንዳላየ ኅሊናቸዉን የሚያደነድኑትን የወቅቱ የሃይማኖት መሪዎችንና «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን» የሚሉትን አስመሳይ አገልጋዮችን « እናንተ ደንቆሮዎችና እዉራን» በማለት ገስጿቸዋል፡፡ እንዲሁም «በዉጭ አምረዉ የምትታዩ በዉስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን የምትመስሉ፡፡» በማለት ገስጻቸዋል፡፡ እንዲሁም የአዳም ዘሮች ፍጥረቶቹና ልጆቹ መሆናቸዉን ቢያዉቅም፤ የዲያብሎስን ስራ በመስራታቸዉና በዓመጻቸዉና በክፋታቸዉ ፍጹም ሰይጣናትን በመምሰላቸዉ «የዲያብሎስ ልጆች» በማለት ገስጿቸዋል፡፡ ታላቅነቱ የተመሰከረለት  የሐዋሪያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ ሳይቀር የሥጋና ደም ስሜቱ አሸንፎት ለግል ጥቅሙና ለክብሩ ቅድሚያ በመስጠት ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግስት ራሱን መካድ ተስኖት፤ ጌታችን ለሰዉ ዘሮች ሁሉ ሊፈጽም ያሰበዉን መስዋዕትነት ለማከላከልና ወደ ኋላ ለመጎተት ሲያስብና ሲናገር «አንተ ሰይጣን» ተብሎ ተገስጿል፡፡

ስለዚህ በዚህ መልኩና ከዚህም በላይ  ብትገሰጹ  እንኳ ስድብ ሳይሆን ማንነታችሁን አዉቃችሁ ባዶነት ተስምቷችሁ በንስሐ ወደ አምላካችሁ እንድትቀርቡና ተወዳጆቹ ልጆች እንድትሆኑለት፤ እንዲሁም ራሳችሁን እንዳታመጻድቁና እንዳታስታብዩ፣ ስለ እዉነትም ራሳችሁን እንድትክዱ ቆራጦች ለማድረግ  ስለሚፈልጉ ነዉ እንጂ እናንተን ለማዋረድ ወይንም ክብራችሁን ለመንካት ፈልገዉ አይደለም፡፡ ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ፤ አካለ ስንኩልን ማለትም ዐይነስዉር፣ ደንቆሮ፣ ሽባ፣ ባጠቃላይ በተለያየ ምክንያት አካሉ የጎደለበትንና በበሽታ የተጎዳን ሰዉ በጉድለቱ ብትሰድቡትና ብታሾፉበት የሰደባችሁትና ያሾፋችሁበት በእርሱ ሳይሆን በፈጠረዉ አምላክ ላይ በመሆኑ ምድራዊ ፍርድ ብቻ አይደለም ሰማያዊዉ ፍርድ የሆነዉ ገሃነመ እሳት እንደሚፈረድብን በማስተዋል ልታዉቁ ይገባል፡፡ እንኳን በአፈጣጠሩ ምክንያት መስደብ ቀርቶ፤ አንድ የአዳም ዘርና የእግዚአብሔር ፍጥረትን ልጅ የሆነዉን ሰዉ ምንም እንኳ እንደማንኛዉ ሰዉ ሙሉ አካለ ቢኖረዉና ድሀና ችግረኛ ቢሆን  ስለ ድህነቱና ችግርተኛነቱ ብትሰድቡትና ብታዋርዱት የሚያስጠይቃችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል፡፡

ሌላዉ ደግሞ በኔና በመሰሎቼ አገልጋዮች እንዳትሰናከሉ:: እኛ እርስ በእርስ በመጣላታችን፤ በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ተቧድነን ሁለተኛዋ ባቢሎን በመሆናችን አትገረሙ:: ለስልጣን፣ ለጥቅም፣ ለዝና፣ ለሽልማት ስንሯሯጥ፤ እርስ በእርስ ስንጠላለፍ፤ ጉድጓድ ስንማማስ፤ ወጥመድ ስናጠምድ ብትመለከቱ እንዳትሰናከሉ:: ሐሰትን ስንናገር፣ ሕሊናችንን ስንሸጥ፣ በምናስተምረዉ ቃል ሆነን መገኘት ሲሳነን ፣ ስለ እዉነት ራሳችንን ክደን መመስከር ሲያቅተን እያያችሁ አትታዘቡን::

እናንተ፤ የተለያየዉን ፈተና ተቋቁመዉ ሌት ተቀን በቅንነትና በእዉነት እንዲሁም በመልካም ሕይወት በገጠርም፣ በከተማም፣ እናት ቤተክርስቲያንንና እናት አገራቸዉን የሚያገለግሉትን አገልጋዮችን ተመልከቱ:: ይህ እኛ የምንጣላበትንንና የምንወነጃጀልበትን ሥልጣንና ክብር፣ ጥቅምንና ድሎትን ንቀዉ በየዋሻዉና በየገዳማቱ ወድቀዉ ሌት ተቀን ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ የሚጸልዩትንና የሚያነቡትን ተመልከቱ:: እንዲሁም ከእኛ በላይ እዉቀት ይዘዉ ማንም ሳያስታዉሳቸዉና ቦታ ሳይሰጣቸዉ «የአባቶቻችን ትምህርት እንዳይፋለስ::» በማለት አቋቋሙን፣ ሰዐታቱን፣ ድጓዉን፣ ቅዳሴዉን ፣ ኪዳኑን፣ ብሉያቱንና ሐዲሳቱን፣ የተለያዩ እዉቀቶችንና ድርሳናትን ለቀጣይ ትዉልድ እንዲተላለፍ ድርሻችንን እንወጣ::» በማለት በየቦታዉ የአብነት ተማሪዎችን የሚያስተምሩትን ሊቃዉንትንና መምህራንን ተመልከቱ::

እኔም ሆንኩ አንዳንድ አባቶቼና ወንድሞቼ በላያችን ላይ ከላይ ሰላይ ስለተመደበብንና የማስተማሩንም እድል ስላልተሰጠን ለሕሊናችን በማህሌቱ፣ በሰዓታቱ፣ በኪዳኑ፣ በቅዳሴዉ እናገለግላለን እንጂ እናንተን የማስተማሩን እድል ቢሰጠን እንደኝህ አባት ባይሆንም እንደአቅማችን ካለማስመሰልና ካለሽንገላ እንደምናስተምራችሁ አምናለሁ:: ነገር ግን ቦታ ስላልተሰጠን ቢያንስ ቢያንስ ቤተክርስቲያን እንዳትዘጋ በተማርነዉ አምላካችንን እናመሰግናለን፣ የአብነቱን ትምህርት የሚማሩ ልጆች ካገኘን ደግሞ ለቀጣይ ትዉልድ አገልጋይ እንዳይጠፋ በምንችለዉ መንገድ እናስተምራለን በማለት ነዉ እንጂ የዘልማድ ሕይወትና አገልግሎት በመስጠታችን ደስተኞች አይደለንም:: አሁን ያለዉ ትዉልድ የአብነቱን ትምህርት ብዙም የሚፈልገዉ አይመስልም፤ ምክንያቱም መንፈሳዊዉን ትምህርትና አገልግሎት እንደ ዓለማዊ የስራ መስክ ቆጥሮት ለገቢ ማስገኛ ስለሚያዉለዉ ለአጭር ወራት ተምሮ በየአደባባዩ መታየትንና ራሳን መካብ ነዉ የሚፈልገዉ:: ለዚህም ነዉ ቃሉን እንደ ሸቀጥ የሚነግዱበትና በሕይወት ሳይኖሩ «መምህር፣ መምህር::» ብቻ በመባል የሚመላለሱት፤ መልካም ስነምግባር የሌላቸዉ፤ ምእመኑን የሚያሰናክሉና የሚያስመርሩ አስመሳይ አገልጋዮች የተፈጠሩት::

አሁን አሁንማ አንድፊቱኑ «በዋሻና በገዳም ተሰዉረን በኖርን ይሻላል» እስከማለት ደርሰናል:: እና ምእመናን፤ አሁን ለነፍሳችሁ የሚያስብ፣ የሚያዝን፣ የሚራራ እዉነተኛ እረኛ እንዳገኛችሁ ተረድታችሁ በእኝህ አባት ልትጠቀሙ ይገባል እንጂ «ለምን ጻድቃን ፣ ቅዱሳን

አይሉንም፡፡» በማለት ያሰማችሁት ቅሬታ አግባብ አለመሆኑን እነግራችኋለሁ፡፡ ስለዚህ በላያችን ላይ የተመደቡት ሰላዮች ወደ ላይ ሪፖሪት አድርገዉ እስከሚያስባርሯቸዉ፣ እንደአስፈላጊነቱም እስከሚያሳስሯቸዉና እሰከሚያስደበድቧቸዉ ድረስ ተጠቀሙባቸዉ፡፡ በዚህች ሳምንት ስብከታቸዉ እንኳ ብዙ ምእመናን ወደ ንስሐ ቀርበዋል፤ «ሥጋዉና ደሙን እንዴት አድረገን ነዉ የምንቀበለዉ?» በማለት ሲጠይቁ ተደምጠዋል፤ ከወላጆቻቸዉ የወረሱትን ጨሌ አምጥተዉ አቃጥለዋል፤ ከባዕድ አምልኮ እንደሚለዩ ቃል ገብተዋል፡፡ እናንተም በእዉነት በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ ሆናችዉ መኖር ከፈለጋችሁ እንደዚህ ዓይነት አባቶችና ወንድሞች ናቸዉ የሚጠቅሟችሁ፡፡ ሌሎቻችን በእግዚአብሔር፣ በእመቤታችን ድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ሰዎች ስም የምንነግድ የጻድቃንን ፈለግ የማንከተል፤ እንደ ቃሉ ሆነን የማንገኝ አስመሳዮች ነን፡፡» በማለት ምላሽ የሰጧቸዉ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ በመልሳቸዉ ስለተበሳጨዉ ከዛች እለት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ለመበቀል  በእሳቸዉ ላይ ጭምር ነገር እያሴርኩባቸዉ እገኛለሁ፡፡» **ይላል የእዉነት ተቃዋሚ ዲያብሎስ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን፡፡»**ይላል

**ከላይ የተገለጸዉ በምእመናን ሆነ በአገልጋዮች ዘንድ በቤተክርስቲያናችን ዉስጥ የሚታይ ነዉ፡፡ ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ?**

መላሹ **የእግዚብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ይህም ከላይ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ነዉ፡፡ በአሁን ሰዓት እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት የእመቤታችን ባለሟሎችና ወዳጆች ተገፍተዉና የትም ተጥለዉ፣ ተረስተዉ ነዉ ያሉት፡፡ በገዳምም ይሁን በዋሻ እንዲሁም በከተማም ይሁን በገጠር በእዉነተኛ አገልግሎት የተሰማሩ ሁሉ የእርሷ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟሎችና ወዳጆች ናቸዉ፡፡ በአብዛኛዉ በተለያየ ወንበር ላይና ኃላፊነት ተመድበዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር የሚፈጽሙ ደግሞ በስሟ የሚነግዱ አስመሳይ አገልጋዮችና የእርሷ ተቃዋሚ ናቸዉ እንጂ እዉነተኛ አገልጋዮች አይደሉም፡፡ ለዚህም ምስክሩ ጌታችን በወንጌል በግልጽ እንደነገረን «እዉነተኛ አገልጋዮቼን ከፍሬያቸዉ ታዉቋቸዋላችሁ» ነዉ ያለዉ፡፡ በዚህ መሰረት በሚናገሩት የእግዚአብሔር ቃል ሆነዉ የማይገኙ፤ ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ፤ ሸንጋዮችና አስመሳዮች ናቸዉ፡፡ ሁል ጊዜ ትጋታቸዉ ለሥጋዊ ጥቅም ነዉ እንጂ ለቤተክርስቲያኗ ሆነ ለምእመኑ አንዳች ስሜት የሌላቸዉ፤ ወንበሩን ሆነ ኃላፊነቱን የፈለጉት ለገንዘብና የራሳቸዉን ዓላማ ለማሳካት እንጂ ለእዉነተኛ አገልግሎት አይደለም፡፡ ለዚህ ነዉ ማንነታቸዉ ሲታወቅና ተቃዉሞ ሲቀርብባቸዉ በተለመደዉ የሽንገላና የማስመሰል ንግግራቸዉ በቀጥታና በአንዳንድ የሴት ወይዘሮና ቆብ ደፊዎች ወደ ፓትርያርኩና ወደ መሰሎቻቸዉ በመቅረብ ሌሌላ ሹመት የሚታጨትና በዓመፃቸዉ ጸንተዉ የሚገኙት፡፡

እነሱ ጥቅም ካገኙበት ተሐድሶዎች ሆኑ መናፍቃን የእግዚአብሔርን መድረክ የዳንኪራና የጭፈራ ቢያደርጉት አንዳች ስሜት አይሰጣቸዉም፤ ይልቁና ያበረታታሉ፣ ይደግፋሉ፡፡ የክህደትና የጥርጥር ትምህርት ቢሰጥ አንች አይቆረቁራቸዉም፤ ይልቁኑ የክብር ሹመት «መጋቢ

ሐዲስ» እያሉ ስንት አባቶች ለዓመታት ተምረዉ ያልተሰጣቸዉን ስም፣ ወዳሴ ማርያምን እንኳ ባግባቡ ለማያደርስ አስመሳይ አገልጋይ ይሰጣሉ፡፡ ምእመናን እምነታቸዉን አወቁ አላወቁ፣ ወንጌል ተሰበከላቸዉ አልተሰበከላቸዉ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠበቁ አልጠበቁ፣ በሥርዓቱ ሄዱ አልሄዱ፣ ንስሐ ገቡ አልገቡ፣ ቆረቡ አልቆረቡ አንዳች የነፍሳት መጥፋት አያሳስባቸዉም፡፡ ይልቁና በዓመፃቸዉ እንዲጸኑ « እናንተ ቅዱሳን፣ ጻድቃን ናችሁ፤ እዚህ ስለመጣችሁና ስላጨበጨባችሁ፣ እልል ስላላችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ትወርሳላችሁ» እያሉ ምእመናን የሚሸነግሉና ምእመኑ ምግባር እንዳይኖረዉና በዘልማድ ብቻ እንዲመላለስ ያደርጋሉ፡፡ ባጠቃላይ በሥጋቸዉም ሆነ በነፍሳቸዉ የከፋ መርገም የሚያመጣባቸዉን ተግባር በተለያየ መልኩ እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ እዉነተኛ አገልጋዮችን ደግሞ ያሳድዳሉ፣ ይወነጅላሉ፣ ያሳስራሉ፣ ያስደበድባሉ፣ ያሰድባሉ፣ ያስገድላሉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሽ ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ስድስት

« ጠያቂዉ አገልጋይ፡ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ አምስት በገጽ314-315 ላይ፡

«አንዳንድ አገርና ወገን ወዳድ እንዲሁም የዓለም ምሁራን አንድ ላይ ሆነዉ ለሚመለከተዉ የተባበሩት መንግስታት ተወካይ ቅሬታቸዉን አቀረቡ፡፡ ይኸዉም «የእኛ ፍላጎትና ምኞት ቴክኖሎጂዉ፣ እዉቀቱ፣ ጥበቡ፣ ፍልስፍናዉ ሁሉ የአዳምና የሔዋን ዘሮችን የሚጠቅም፤ ከጉስቁልና ኑሮና ሕይወት የሚለይ፤ ረሀብ፣ ችግር፣ ስቃይ፣ ህመም፣ ድንቁርና፣ እርዛት ባጠቃላይ ሰዎች ሁሉ እደሰዉነታቸዉ ብቻ ተከብረዉ፣ ተፈቅረዉ፣ በልተዉ፣ ጠጥተዉ፣ ተምረዉ፣ መጠለያና መጠጊያ አግኝተዉ፣ እንዲኖሩ ነዉ እንጂ ለብዙ ሰዎች ለችግር ማቃለያና ለመርጃ የሚጠቅመዉ በቢሊዮንና በትሪሊዮን የሚቆጠር ብር ፈሰስ እየተደረገ ለተለያዩ ጦር መሳሪያና ለሕዋ ምርምር መደረጉ አግባብነት የሌለዉና ለእነዚህ የሚወጣዉ ገንዘብ ለልማት ስራ ቢዉል ኖሮ በምድራችን ረሀብ፣ ችግር፣ ሰቆቃ የሚባለዉ ቀርቶ ስማቸዉ እንኳ አይታወቅም ነበር፡፡

የየአገራቱ መሪዎች ሆኑ ባለስልጣናት ለክብራቸዉ፣ ለጥቅማቸዉ፣ ለዝናቸዉ፣ ለታላቅነታቸዉ፣ ለስልጣናቸዉ የቆሙ አምባገነን ናቸዉ፡፡ የወገናቸዉ የአዳም ዘር ሰቆቃና ችግር አንዳች አይሰማቸዉም፡፡ እነሱ ከገነኑ፣ ከተመሰገኑ፣ ከበሉ፣ ከጠጡ፣ ከተዝናኑ፣ ከጨፈሩ፣ ከዘፈኑ፣ ከተመለኩ፣ ሁሉ በእነሱ ቁጥጥር ዉስጥ ከሆነላቸዉ ለሌላዉ ወገናቸዉ አንዳች ስሜት የሌላቸዉ ናቸዉ፡፡

ከዚያም አልፈዉ በእብሪትና በትዕቢት «ከእኛ በላይ ማንም የለም፣ ቀና ብትሉ ጣርና ጣሪያ ነዉ» እያሉ የሚደነፉ፤ ሕዝብን የሚያስጨንቁና ግፍ የሚፈጽሙ ናቸዉ፡፡ የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግሞ ወደ ተግባር የማይለዉጡትን ለመሸንገያና ጎሊናን ለማሸጫ ለመጠቀም « እኛ ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለብልጽግና የቆምን ነን» ይላሉ፤ ተግባራቸዉ ግን ጦረኝነትና ግፈኝነት፣ አድሎና በደል ነዉ፡፡ ስለዚህ አላስፈላጊ ለሆነዉ የተለያዩ ጦር መሳሪያና ለተለያዩ ፕላኔቶች ግኝት የሚወጣዉ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለሕዝብ አገልግሎት ለትምህርት፣ ለጤና ፣ ለመኖሪያ ቤት፣ ለመስኖ፣ ለትራንስፖርት፣ ለመብራት፣ ለስልክ.. ወዘተ ለመሳሰሉት አገልግሎት ላይ እንዲዉል እንጠይቃለን፡፡» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ምሁር ተጨማሪ አስተያየት አለኝ ብለዉ፤« እኛ የሰዉ ዘሮች የፈጠረን አምላክ ረስተን እኛ ሳናስተዉለዉ ለጨለማዉ ገዥ ለዲያብሎስ ባሪያዎች ሆነን ሌት ተቀን ፈቃዱ በሚፈጸምበት የጨለማ ሥርዓት ዉስጥ በመመላለሳችን ነዉ መንግሥታት ሆኑ ባለሥልጣናት እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን መልካም ተግባር መፈጸምና ማስፈጸም ተስኗቸዉ ሕዝቡን ለጦርነት የሚያነሳሱትና ሀብትና ንብረት በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ዉስጥ እንዲሆን አድርገዉ በረሀብና በችግር እየቀጡት ያለዉ፡፡

ታዲያ የሕዝብ እንባ አንድ ቀን እንደ ጎርፍ ሆና እንዳይጠራርጋቸዉ እሰጋለሁ። እንደኔ አስተያየት ለሁሉም መፍትሔ የሚሆነዉ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመራ መንግሥታት ሆኑ ባለሥልጣናት በምንም መልኩ ሕሊናቸዉን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሊያደርጉትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊፈጽሙና ሊያስፈጽሙ ስለማይችሉ ይህ አሁን በዓለም ላይ የሚታየዉ <u>የዲያብሎስ ሥርዓት ሊወገድና በምድራዊ ሕይታችንም የምንጠቀምበት ለሰማያዊ ሕይወታችንም በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ ሆነን የምንኖርበት ሰማያዊ ሥርዓት ልንዘረጋና ከላይ የተገለጹትና መልካም ተግባራትን ልንፈጽም ይገባል</u>። ነገር ግን አሁንም «በዲያብሎስ ሥርዓት እንመራ» ከተባለ ይህ ቅርፊት ሥጋዉን የሚያመልክና የሚያስመልክ እንዲሁም ተስፋዉን ምድራዊ ያደረገ ትዉልድ ከላይ የተገለጹትን መልካም ተግባሮች ለመተግበር እንደሚቸገር ለመግለጽ እወዳለሁ» በማለት አስተያየታቸዉንና ስጋታቸዉን ገልጸዋል።

የመንግሥታቱም ተወካይ « በእርግጥ አስተሳሰባችሁና አስተያየታችሁ ጥሩ ቢሆንም ለዚህ ምላሽ መስጠት የሚችሉት አምስቱ ኃያላን አገራት የተባሉት አሜሪካ እንግሊዝ ፈረንሳይ ሩሲያና ቻይና ናቸዉ። ዓለምን እንደፈለጉ እያሽከረከሩት ያሉት እነሱ ስለሆኑ አሁን ባለሁ ሁኔታ የሚሰማችሁና የሚቀበላችሁ ግለሰብ ሆነ አካል ያለ አይመስለኝም። <u>ምናልባት ለወደፊት የአዳም ዘር ሁሉ (የዓለም ሕዝብ ሁሉ) ወገኔ አባቴ እናቴ ወንድሜ እህቴ ልጆቼ ናቸዉ የሚል ትዉልድ የሚፈጠርበት አገር ካለ ያኔ ሐሳባችሁና ጥያቄያችሁ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል እንጂ አሁን ይህን አሳብ ብታቀርቡ የእብድ አስተሳሰብ አድርገዉ ነዉ የሚቆጥሩት</u>።» በማለት ስለመለሱላቸዉ ጥያቄያቸዉ ዋጋ ቢስ ሆኖ ቀርቷል። እኔም የጨለማዉ ገዥ «ማን ጀግና ደፋር ነዉ ይህን መልካም ተግባር ሊፈጽምና ሰማያዊ ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችል!» በማለት ታብያለሁ።» **ይላል የትዕቢት አባት ዲያብሎስ**። » ተብሎ ተገልጻል።

**ይህ የሚሳየን በዓለም ላይ ያሉ መንግሥታት ራሳቸዉን ከአምላክ በላይ አድርገዉ የሚቆጥሩና በጦራቸዉ፣ በደኅንነታቸዉ፣ በሀብታቸዉ፣ በሥልጣናቸዉ፣ በእዉቀታቸዉ የሚመኩ፤ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር እዉነት የሚያቀርብ ሰዉ ቢያጋጥማቸዉ እንደ እብድና ንክ አድርገዉ የሚቆጥሩ ትዕቢተኞችና ትምክህተኞች መሆናቸዉን ነዉ። በዚህ ላይ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?**

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ እግዚአብሔር ሊያሳዉቀን የፈለገዉ በተለያየ አገር ዉስጥ ስለ ወገኖቻቸዉ፣ ስለ ዓለም ሕዝብ የሚያስቡና የሚቆረቆሩ የተማሩ ክፍሎች ቢኖሩም፤ ሥልጣኑንና ኃይሉን የተቆጣጠሩት አምባገነን መሪዎችና ባለሥልጣናት ስለሆኑ በዓለም ላይ ያለዉን ችግርና ጉስቁልና መፍትሔ ለመስጠት እንዳልቻሉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያዉያን ምሁራን ደግሞ የዓለም ችግር የሚፈታዉ በራስ ሥጋና ደም ስሜት ሐሳብና ተግባር ሳይሆን እግዚአብሔርን በማስቀደምና እርሱን መፍራት ባለበት ሰማያዊ ሥርዓት ስንመላለስና የዲያብሎስ ሥርዓት ሲወገድ መሆኑን እንደሚያምኑ የገለጹበትና ዓለም ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት እንዲመጣ አስተያየታቸዉን የሰጡበት ነዉ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፡ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ ስድስት ከገጽ318-323 ላይ፡

**«አንዳንድ ኢትዮጵያዊነታቸዉን የካዱ ከተገንጣይ ቡድን ጋር አብረዉ የነበሩ ሰዎች ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ ያላቸዉን አድናቆታቸዉንና ሙገሳቸዉን ገለጹ፡፡** ይኸዉም «እኛ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ክህደት የፈጸምን ቢቻለን ኖሮ ከመንግሥታችን ጎን በመሰለፍ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ልናጠፋ የነበርነዉን፤ እርሶ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰዉ ስለሆኑ በወንጌል የተጻፈዉን «ጠላታችሁን ዉደዱ» የሚለዉን ቃል ተከትለዉና አክብረዉ ከካድሬዎቾ ዉጭ ላሉት ለሌሎች ኢትዮጵያዉያን ዜጎች ያልተሰጠዉን የሁለተኛ ድግሪ የመማር እድል ስለሰጡንና እንዲሁም «በኢትዮጵያዊነታችሁ ካለማናችሁ፣ በክህደታችሁ ከጸናችሁ፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያን በዘረኝነትና በጎጠኝነት ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሳችን ተባባሪ ከሆናችሁ፣ ከነፍጠኞቹና ከትምክተኞቹ መንጋጋ አዉጥተንላችሁ ነጻነቷን የተጎናጸፈችዉን እናት አገራችሁን ኤርትራን ነጻነቷን እስከ መጨረሻዉ ድረስ ከጠበቃችሁ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዉያን ያላገኙትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመማር እድል እንሰጣችኋለን፤ በኢትዮጵያዊነታችሁ ክህደት በምታሳዩት ብቃት ደግሞ እስከ ፒችዲ ድረስ እናስተምራችኋለን፡፡» በማለት ቃል ስለገቡልን ነዉ፡፡

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ ለዚህ አድናቆትና ሙገሳ ምላሽ ሲሰጡ « ዉድ የቁርጥ ቀን ልጆች! በጫካ እያለን ወንድምና እህቶቻችን ኤርትራዉያንንና ትግራዉያንን ለማስገንጠል ታላቅ መስዋዕትነት በመክፈላችሁና ኤርትራን ነጻ በማዉጣታችሁ እንዲሁም አዲሲቷ ኢትዮጵያ በብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋ ተከፋፍላ የተለያዩ የክልላት መንግስታት ተመስርተዉ ለወደፊት ደግሞ ራሳቸዉን ሲችሉ እንደ እናት አገራችሁ ኤርትራ ለመገነጣጠል ያኮበኮቡ የወደፊቱ ነጻ አገራት የአሁኖቹ እጩ አገራትን ለማየት ስላስቻላችሁን በቅድሚያ ታላቅ ምስጋናችንንና አድናቆታችንን እናቀርባለን፡፡ ታዲያ አንድ ያልገለጻችሁትን የታላቅነታችን መለያ የሆነዉን ታላቅ ተግባር አለ፡፡ ይኸዉም በአገር ዉስጥ ስንቶቹን በአገር ክህደት፣ በአሸባሪነት እየወነጀልን እንደምናስርና ፍዳቸዉን በማሳየት እንደምናሳድድ ስላልገለጻችሁ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ አስበልጠን ነዉ ለእናንተ ኢትዮጵያዊነተችሁን በግልጽ ለካዳችሁት ይህን የመሰለ እንክብካቤ በማድረጋችን «ቅዱስና ጻድቅ» የሚለዉን ስያሜ ልታበረክቱልኝ ይገባ ነበር፡፡

ሌላዉ የታላቅነታችን መለያ እኛ እንኳን እናንተን ለኤርትራ መገንጠልና ነጻነት ለጥንቷ ኢትዮጵያ መከፋፈልና ወደ ጥፋት ማምራት ታላቅ ዉለታ ያደረጋችሁትን ዉዶቻችንን ቀርቶ በዉጭ ኢትዮጵያዊነታቸዉን ክደዉ ዜግነታቸዉን የለወጡትን አይደለም ለኢትዮጵያ መጥፋት የሚተጉ ክህደትንና መናፍቅነትን የሚያስፋፉ ሰዎች ብራቸዉን ይዘዉ ይምጡልን እንጂ ከኢትዮጵያዉያን በላይ እንክብካቤ አድርገንላቸዉ፤ የፈለጉትን እንፈጽምላቸዋለን፡፡ በተቃራኒዉ ደግሞ ኢትዮጵያዉያን ዜጎችን እያጎሳቆልን ፍዳቸዉን እናሳያቸዋለን፡፡ በዚህ መልኩ ነዉ የዘመናት በቀለኝነታችንን እየፈጸምን ያለነዉ፡፡

ስለዚህ እናንተም የኛ አጋር ሆናችሁ ዓላማችንን ካሳካችሁ ከማንኛዉም «ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡» ብሎ ከሚናገር ሰዉ በላይ እንክብካቤ የምናደርግላችሁና በእነሱ ላይ እንደምናሰለጥናችሁ ቃል እንገባላችኋለን፡፡ ዋናዉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነታችሁ ላይ በፈጸማችሁት የክህደትና የዐመጻ አቋም መጽናት ነዉ የሚጠበቅባችሁ፡፡

እኛ ዘንድ «አንድነትና ዉህደት» የሚባል ነገር የለም፡፡ እንኳን ከሌሎች ጋር አንድነትና ዉህደት መፍጠር ቀርቶ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ የኢትዮጵያዊነት ብሔራቸዉን አስክደን «እኔ ብሔሬ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን እኔ ትግሬ ነኝ፡፡ እኔ አማራ ነኝ፡፡ እኔ ኦሮሞ ነኝ፡፡ እኔ አፋር ነኝ፡፡ እኔ ሱማሌ ነኝ፡፡ እኔ ሐረሪ ነኝ፡፡... ወዘተ» በማለት በሰማኒያ ብሔር ብሔረሰቦች ስለከፋፈልን የኢትዮጵያዊነት ስሜት በዉስጣችሁ ካለ ከወዲሁ እርማችሁን እንድታወጡ በዚሁ አጋጣሚ እናሳስባችኋለን፡፡» በማለት ምክርና ማስጠንቀቂ ጭምር ሰተዋቸዋል፡፡ እኔም የጨለማዉ ገዥ በምክሩ ሆነ በማስጠንቀቂያዉ የተደሰተኩ በመሆኑ ትክክለኛ እንደራሴ ማዘጋጀቴን ለራሴዉ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

አንዳንድ ከእናት አገራቸዉ ከኢትዮጵያ መገንጠል ላይ በምርጫ ያልተሰለፉና በወቅቱ ልጆች የነበሩ በአንድላይ በመሰባሰብ «እኛ «ኤርትራዉያን» የምንባልና «ኢትዮጵያዉያን» የሚባሉ ዜጎች በስብሰባ ላይ ሆነ በተለያዩ ቦታዎች ሲታዩ መለያ የላቸዉም፡፡ መልካቸዉ ሆነ ጠባያቸዉ ተመሳሳይ የሆነ አንድ አይነት ናቸዉ፡፡ ይህም ልዩነት የፈጠሩት የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች መሆኑን ይገልጣል፡፡ ትንቢተ ኤርምያስ ም.፲፫፥፳፫(13:23) **«በዉኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን፣ ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሊለዉጥ ይችላልን?»** ብሎ ለተናገረዉና ለጠየቀዉ፤ «እኛ ኤርትራዉያን ነን እንጂ ኢትዮጵያዉን አይደለንም» ያልን ሰዎች፤ መልሳችን «አዎን» መሆኑ ምን ያህል ከእግዚብሔር ፈቃድ ዉጭ መሆናችንን ያሳያል፡፡ ይኸዉም ለእግዚብሔር ጥያቄ « አዎን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያም መልኩን ሊለዉጥ ይችላል፡፡» በማለት የማይሆን ጠማማ መልስ እንደሰጠነዉ ይታመናል፡፡» በማለት ከተወያዩ በኋላ፤

«ስለዚህ ለምን ኢትዮጵያዊ ዜግነታችን ለወጥን? ማን ለወጠዉ?» በማለት ጥያቄያቸዉን ከኢትዮጵያ በመገንጠላቸዉ ለሚቆረቆሩ ለሃይማኖት አባቶች ያቀረቡ ሲሆን፤ የተሰጣቸዉም መልስ «ልጆቻችን! በእርግጥ ኢትዮጵያዊ መልካችሁ ባይለወጥም፤ ታላላቆቻችሁና ወላጆቻችሁ እኛም ጭምር ክህደትን ፈጽመናል፡፡ ሌላዉ ቢቀር የቃል ኪዳን አገር መሆኗን ከብዙ ሺህ ዓመት በፊት ነብየ እግዚአብሔር ዳዊት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የተባለዉን የዘነጋንና በሁለት ከሃዲና ዐመጸና ቡድኖች «ሻዕብያና ወያኔ » በሚባሉት ተጽህኖና የክህደት ተግባር ነዉ ለማንፈልገዉ ሕይወት የተዳረግነዉ፡፡

እነሱ ተስፋቸዉ ምድራዊ ስለሆነና በስልጣን ጥማት የተቃጠሉ፤ ጥላቻ፣ ቂምና በቀል ያረገዙ በመሆናቸዉ ፍጹም የዲያብሎስ እንደራሴ ሆነዉ ፈቃዱን ሲያስፈጽሙለት፤ እኛ ግን እነሱን ተከትለን ምርጫችንን ዲያብሎስ ማድረጋችንንና እግዚአብሔርን መካዳችን፣ በስሙ መነገዳችን ነዉ

የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ:: ለዚህ ለአገርና ሃይማኖት ክህደታችን ሁላችንም ዋጋ እየከፈልንበት ነዉ:: ለወደፊትም የባሰዉን ዋጋ እንደምንከፍል ልናስተዉል ይገባል:: ከአስር ዓመት በፊት እናንተ ወጣቶች እያላችሁ እነዚህ ሁለት ወንበዴዎች ለስልጣናቸዉ የበላይነትና ጥቅም ሲሉ ሕዝቡ እንዲነጣጠልና እንዲገነጣጠል ያደረጉት አንሶ እርስ በእርስ አገዳደሉት፤ ደሙ በከንቱ እንዲፈስ አስደረጉ፤ እነሱ ግን በተደላደለ ወንበር ላይ ቂብ ብለዉ ዙፋናቸዉን በሕዝብ ደም ላይ ዘርግተዉ በተንደላቀቀ ሕይወት ይወጣሉ፤ ይገባሉ:: አሁንም ሲፈልጉ ጦርነት ከማወጅና ሕዝቡን ወደ እሳት ከመማገድ የማይመለሱ ጨካኝ አረመኔ ለሕዝቡ አንዳች ርኅራኄ የሌላቸዉ የዲያብሎስ ምርጦችና ባለሟሎች ናቸዉ::

አሁን እናንተ እንሰደድ ብላችሁ ወደ እናት አገራችሁ ኢትዮጵያ ብተሰደዱ የወያኔ(የኢህአዴግ) መንግስት አይቀበላችሁም:: ምክንያቱም «እኛ ኢትዮጵያዉያን ነን» ስለምትሉ፤ እንደ አገር ክህደት ቆጥሮ ወይን ራሱ ይወነጅላችኋል ወይንም ለአባቱ ሻዕብያ አሳልፎ ይሰጣችኋል:: ባጠቃላይ «በኢትዮጵያ ዉስጥ ገብተዉ አንድነት ያመጣሉ፤ ለክልላዊ መንግስታቱ ህልዉና አደጋ ይሆናሉ፤ ኢትዮጵያዊነት ብሔር ይቀሰቅሳሉ፤» በሚል ስጋት አይቀበላችሁም:: ነገር ግን « እኛ ኤርትራዉያን ነን:: ኢትዮጵያዉያን አይደለንም:: የሻዕብያን ስርዐት ብቻ ተቃዉመን ነዉ የመጣነዉ፤» የምትሉ ከሆነ ለእናንተ አስቦ ሳይሆን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ሊቀበላችሁና ለራሱ ለጥፋት ዓላማ ሊያሰልፋችሁ ይችላል::

የእኛ ምክር ግን ሁለተኛ ክህደት ከመፈጸም እዚሁ ኤርትራ ዉስጥ ሆናችሁ በልቦናችሁ ኢትዮጵያዊነታችሁን አምናችሁ ስላለፈዉ ክህደታችሁ ንስሐ ገብታችሁ ፈጣሪያችሁን በእዉነትና በመንፈስ እያመለካችሁ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ብትጠባበቁ የተሻለ መሆኑን እንመክራችኋለን:: እኛ ቀደም ሲል የሻዕብያ መንግስት ኀሊናችንን የመረዘዉ «የገዥ መደቦች በደል ፈጸሙብን ፤ አድሎ አደረጉብን ፤» በማለት ሲሆን ወደ ልባችን ስንመለስ ግን አድሎና በደል የተፈጸመበት ሁሉም ዜጋ በአራቱም ማዕዘን ያለዉ ኢትዮጵያዊ ላይ ጭምር ሲሆን ፤ በሕዝብ ስም የሚነግዱት ደግሞ እንደ አሁን ዘመን ባለጊዜ እንደሆኑት የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸዉ እንጂ ብሔሮች ወይንም ጎሳዎች አለመሆኑን በሚገባ ተረድተናል:: ታዲያ ያኔም ቢሆን ወደ ክህደቱ ከመግባት እንደ ሃይማኖት አባትነታችን ማንንም ሳንወግን «እግዚአብሔር ሆይ! ከግፈኞች፣ ከጨካኞች፣ አድሎና በደል ከሚፈጽሙ ሰዎች ገላግለን፤ ያንተን ሰማያዊ መንግስት አቋቁምልን፤ ያንተን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ እንደራሴዎችህን በሥጋዊዉና በመንፈሳዊዉ ወንበር ላይ አስቀምጥልን::» በማለት መለመንና መጸለይ ሲገባን እንደ ሥጋዉያኑ ሃይማኖት የሆነዉ ኢትዮጵያዊነትን ክደናል፤ የዐመጻ ተባባሪና አስፈጻሚ ሆነናል::

አሁን ግን እኛ የተወሰን አባቶችና እናቶች እንዲሁም ወንድሞችና እህቶች ስለ ክህደትና ዐመጻ ተግባራችን ንስሐ ገብተን ከእናት አገራችን ከኢትዮጵያ ከድንግል ማርያም ጋር ለመዋሀድና ከሃይማኖታችን ተዋህዶ ጋር አንድነት ለመፍጠር እግዚአብሔርን በጸሎት እየጠየቅንና ምህላ እያደረግን እንገኛለን:: እናንተም በሁሉም ቦታ ጸሎታችሁንና ምህላችሁን አጠናቅሩ:: በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ትንሳኤን የሚጠባበቁ ወገኖቻችን በጸሎትና በምህላ ላይ እንዳሉ እናዉቃለን:: ሁለቱም ቡድኖች ሻዕብያና ወያኔ በቅርቡ የዘሩትን የዐመጻና የክህደት ፍሬያቸዉን እንደሚያጭዱና የኢትዮጵያ ትንሳኤ እንደሚመጣ በእዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ተነግሮናል::

መሪዎች ሆኑ ሕዝቡ ካለፉት ታሪክ ትምህርት መዉሰድ ሲገባቸዉና ከእዉነት ጋር መሰለፍ ሲጠበቅባቸዉ « እኛ ምርጫችን የዲያብሎስ እንደራሴዎችን ነዉ:: የምንፈጽመዉም የእነሱን ፈቃድ ነዉ» በማለታቸዉ፤ እንደምርጫቸዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰቱ ጽዋ ሲሞላ የእግዚአብሔርን ቁጣን መቀበላቸዉ ስለማይቀር እየንዳንዱ ሰዉ ንስሐ ገብቶ እጅኑ ለአምላኩ ቢሰጥ የሚያዋጣዉ መሆኑን በዚሁ ምክራችንን እንገልጻለን::» በማለት አሰናብተዋቸዋል:: እኔ የጨለማዉ ገዥ በምክራቸዉና በአቋማቸዉ ተቆጥቼ በደኅንነቶቼ አማካይነት ለበላይ ባለስልጣናት ሪፖርት አስደርጌ ይኸዉ እስከ አሁን ድረስ በእስር ይገኛሉ::» **ይላል የክፋት፣ የዘረኝነት ፣ የኅጠኝነት አባት የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ጋር በመሆን:: » በማለት ቀርባል::**

**ከላይ እግዚአብሔር እንድናዉቀዉና እንድናሰተዉለዉ ያደረገዉ አሁን ሕወሐት(ኢሕአዲግ) የሚባለዉ መንግሥት ሕዝቡን እያስተዳደረ ያለዉ በኢትዮጵያዊነት ሽፋን የኢትዮጵያን ሕዝብ በተለያየ መንገድ እየተበቀለና የራሱን መሰሪ ተግባር እየፈጸመ መሆኑን ነዉ:: ለዚህ ጉዳይ አንዳንድ ነገሮች ቢሉን?**

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እንደተባለዉ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በሌላቸዉ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ በተነሱ ቡድኖች ነዉ አሁን እየተመራን ያለነዉ:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት እነዚህ የተወሰኑ በበቀልና በጥላቻ የተሞሉ የዓመፃ ሰዎች የሚወክሉት አንድ ራሳቸዉንና በራሳቸዉ ዓላማ ዙሪያ አሰልፈዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር የሚያስፈጽሙባቸዉ ግለሰቦችና ቡድኖችን እንጂ የማንንም ዘር ሆነ ነገድ እንዲሁም ቋንቋ ተናጋሪዎችን አይወክሉም:: በመሆኑም በባለጊዜዎች ሰዎች ምክንያት ምስኪኑንና ምንም ዉስጥ የሌለዉን ሰዉ ከእነርሱ ጋር መደመር የለብንም:: እጅና ጓንት ሆነዉ እየሰሩ ያሉት የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸዉ እንጂ አንድ የተወሰነ ቋንቋ ተናጋሪ ብቻ አይደለም:: ስለ እዉነታዉ ይህን ካልኩ በኋላ ወያኔ(ሕወሓት)ና ሻዕቢያ የሚባሉት ሁለት የዓመፃ ቡድኖች የመጀመሪያ ዓለማቸዉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵዊነትን በመከፋፈል ማዳከምና በሂደትም አጥፍጦ የራሳቸዉን ታላቅ መንግሥት ለመመስረት ነበር:: ነገር ግን የየዋሁ ኢትዮጵያዊ አምላክ በእዉነተኛ ዳኝነቱ እርስ በእርስ እንዲጣሉና ዓይንህን ለአፈር እንዲባባሉ አስደረገ:: ይኸዉ እስከ አሁን ድረስ እርስ በእርስ እየተጠላለፉና እየተወነጃጀሉ ቀደም ሲል በእቅዳቸዉ የነበረዉን ዓላማ ሳያሳኩ ወደመጨረሻ መጠረጊያቸዉ ጊዜ ላይ ደረሱ:: ሊያጠፏት የነበረችዉ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ትንሣኤያቸዉ ለዓለም ሊታይና ብርሃን ሊሆን ጊዜዉ ደረሰ:: እርሷንና ሕዝቦቿን ሊያጠፉ የተሰለፉ አገራት ሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ቡድኖችና ግለሰቦች ለትንሣኤዋ ሳይበቁ በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ እንደጸኑ የመጨረሻ ዋጋ በምድርም በሰማይም የሚከፍሉበት ጊዜ ላይ ስለሆን ከእነሱ ጋር ባለማወቅ፣ በየዋህነትና በጥቅም ተደልለዉ

በዓመፃ ዉስጥ የሚገኙ ሰዎች ዛሬ ነገ ሳይሉ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱና በእዉነተኛ ሕይወት እንዲኖሩ በዚህ አጋጣሚ አሳስባቸዋለሁ፡፡

**ጠያቂዉ አገልጋይ**፡ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በክፍል አራት ዉስጥ በተለየ ሁኔታ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ በመሪዎቹና በባለሥልጣኖቹ እንዲሁም በካድሬዎቹ ላይ እያሳገጠ ይናገራል፡፡ በእርግጥ የ21ኛዉ ዓመታቸዉ የመጨረሻ ዋጋ የሚከፍሉበት እንዲሁም ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ከፈጸሙባትና ካስፈጸሙባት ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ከወንበራቸዉ የሚቆረጡበትና የሚጠረጉበት ዘመን ነዉ ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፡ እግዚአብሔር በዚህ መልኩ እንዲነገር ያደረገበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል፡፡ እኛ እርሱ የሚሰራበትን ጊዜ በእርግጠኝነት እንዲህ ነዉ ማለት አንችልም፤ በግልጽ «እንዲህ ነዉ፤ በዚህ ጊዜ ዉስጥ ይህ ይፈጸማል» ብሎ ጊዜዉን እስካልገለጸልን ድረስ ግምት ነዉ የሚሆንብን፡፡ እኔም እንደእናንተ ከጽሑፉ የተረዳዉት 21ኛዉ ዘመናቸዉ ዋጋ የሚከፍሉበትና ከምድርም የሚጸዱበት ጊዜ እንደሆነ ነዉ የምገምተዉ፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል መላሻቸዉን ሰተዋል**፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ:** በእርሶ በኩል በተላለፈዉ የመጀመሪያ ሆነ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ በግልጽ አሁን በኢትዮጵያ ያለዉ መንግሥት የሥርዓት ዘመኑ መደምደሙና ዓመቱን ጭምር የሚገልጽ ነዉ:: ለምሳሌ «የኢትዮጵያና የዓለም መጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የመጀመሪያዉ የእግዚብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ ሁለት በገጽ 66:

«:-በዚህች አገር እዉነትን ለማጥፋ «ጉዲት» የተባለች የዓመፅ ልጅ ለአርባ ዘመን(ዓመታት) ቤተክርስቲያንን ስታቃጥል፣ ክርስቲያኖችን ስታሳድድ፣ ስትገል ነበረ:: ነገር ግን እዉነትን አላጠፋችም:: እስከአሁን ድረስ ይህች እዉነተኛ ቤተክርስቲያን አለች፤ እስከ ዓለም ፍጻሜም ትኖራለች:: «ግራኝ አህመድ» የተባለ የዓመፅ ልጅ ለአስራ አምስት ዓመት ቤተክርስቲያንን ሲያቃጥል፣ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ፣ ሲገል ነበረ:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ሆነ ክርስቲያኖችን ሊያጠፋ አልቻለም:: አሁንም ለሠላሳ ሰባት(37) ዓመት የዓመፃ ልጆች ተነስተዉ ክህደትንና መናፍቅነትን ቢያስፋፉ፤ መድረኮችንና ብዙኃን መገናኛን (ማስ ሚዲያን) ለዘፈንና ለዳንኪራ፣ ለወሬ ቢያዉሉም፤ ሰዎች ወደ እዉነት እንዳይመጡ በተለያየ መንገድ ሐሰት እንድትነግሥ ቢያደርጉም፤ በሰዎች መካከል ጥላቻና መከፋፈል ቢዘሩም፤ እዉነትን ሊያጠፉ ሆነ ሊያሸንፉ አይችሉም:: እዉነት ትነግሥና የሐሰት ተግባራቸዉን ገበና ትገልጣለች:: ባዶ ቀፎ መሆናቸዉን ታሳዉቃቸዋለች፤ መንገዳቸዉ ሁሉ የሞት መንገድ ጨለማን የለበሰ የዲያብሎስ ፍሬ መሆኑን ታሳዉቃቸዋለች::» ይላል ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ የሚፈርድለትና የሚፈርድበት ብቸኛ እዉነተኛ ትክክለኛ ፈራጅ እግዚአብሔር::» በማለት ነዉ እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገረዉ::

ታዲያ ይህ መልእክት የተላለፈዉ በመስከረም ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ሲሆን፤ ከመስከረም፪÷፲፱፻፷፯ (2/1/ 1967 ዓ.ም የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትም ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ ተዋሕዶ እንደ ሥጋና ነፍስ እንዲሁም መንፈስ ተዋሕዶ የሚመራበት የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት በግልጽ ከፈረሰበት ጊዜ አንስቶ ሲቆጠር 36ኛዉ ዓመት ላይ ነዉ መልእክቱ የተጻፈዉ:: የዓመፃ ልጆች ባለጊዜነት እስከ 37ተኛዉ ዓመት እንደሆነና ከዚያም ከባለጊዜነት እንደሚሻሩና የጨለማዉ ስራቸዉ እንደሚገለጽ፣ እንዲሁም ገበናቸዉ እንደሚወጣ፣ በመጨረሻም የዲያብሎስ አገልጋይነታቸዉ እንደሚመሰከርባቸዉ ነዉ የሚገልጸዉ::

ከመስከረም አጋማሽ ፳፻፬ (2004) ዓ.ም እስከ ታህሳስ መጀመሪያ ፳፻፬ (2004) ድረስ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ በገጽ 157-158 ላይ  የእግዚአብሔር አገልጋይና ባለሟል በሆኑት ላይ እግዚአብሔር አድርጎ ለመረጣቸዉ ሰዎች ያናገረዉ ደግሞ

«:-አንዳንድ ምሳሌ ብንመለከት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ የሥርዓት ማብቂያቸዉ በደረሰ ወቅት እሳቸዉም ሆኑ ሌላዉ ሰዉ ባላሰበዉና ባልጠበቀዉ መንገድ

ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና እሳቸዉም፣ ባለሥልጣኖቻቸዉም የተለያየ መከራና ግድያ ሊደርስባቸዉ ችሏል። ከዚያም የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሥርዓት ማብቂያ ላይም ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ከወንበራቸዉ ተቆርጠዉ እሳቸዉም ለስደት፣ ባለስልጣኖቻቸዉም ለችግርና ለእስር ተዳርገዋል። አሁንም ባለተረኛዉ አቶ መለስ ዜናዊ የሥርዓታቸዉ ማብቂያ መዳረሱ ቢታወቅም በምን መልኩ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡና እሳቸውም ሆኑ ባለስልጣኖቻቸዉ ስለ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባራቸዉ ምን ዋጋ እንደሚከፍሉ ቸሩ መድኃኔዓለም አንድዬ ነዉ የሚያዉቀዉ።

እኛ ግን የአዳም ዘሮች ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉና ስለ ዓመፃ፣ ስለክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራቸዉ ንስሐ ገብተዉ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሰተዉ በሰዉ ሳይሆን በራሱ ጊዜ እንዲጠራቸዉ ነዉ ምኞታችንና ጸሎታችን። የማንንም ጥፋትና ዉድቀት አንመኝም። በዉድቀታቸዉና በጥፋታቸዉም አንደሰትም። ምክንያቱም አንድነታቸዉንና ኅብረታቸዉን ከአምላካቸዉ ጋር ካደረጉ ሁላችንም በእግዚአብሔር መንግስት እዉነተኛ አምላካችንን በመስቀል ላይ ዋጋ የከፈለልንን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ ሕያዉ ሆነን በመንግሥቱ መኖር ነዉ ፍላጎታችንና ልምናችን። በዚሁ አጋጣሚ ስለ ነፍሳቸዉ የሚያስብላቸዉ ሰዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ ማንም ይሁን ማን በዚህ ምድር የዘራዉን ፍሬ ማጨዱና መራራዉን ፍሬ መጠጣቱ ስለማይቀር፤ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱና መልካም ፍሬ ማፍራት ባለመቻለቸዉ ምክንያት መልካም ፍሬ ለሚያፈሩትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ለሥጋዊዉ ሆነ ለመንፈሳዊዉ ወንበር ለታጩት እዉነተኛ እንደራሴዎች ወንበሩን ቢለቁ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበዉንና የወሰነዉን ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ ስለማይችል መራራዉን ጽዋ ጠጥተዉ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ ቀርተዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደ ማይገኝበት ቦታ ከሄዱ ፍርዱ እጅግ ይብስባቸዋልና ነዉ።

ከዉጭዎቹ ምሳሌ ብንመለከት ደግሞ የኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሴንና የሊቢያዉ መሪ ሙሀመድ ጋዳፍ «ማንም አይነካቸዉም፤ ከወንበራቸዉም ማንም አይነቀንቃቸዉም» ሲባል፤ የተቆረጠባቸዉ ቀን ሲደርስ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና የዉርደት ሞት ሊሞቱ ችለዋል። የግብጹ መሪም ብንመለከት ባለሰቡበትና ባልጠበቁበት ቀን በተከበሩበትና በገነኑበት አገርና ሕዝብ፣ በራሳቸዉ ሕዝብ ተዋርደዉ ከወንበራቸዉ መቆረጣቸዉና የቁም ስቃያቸዉን እያዩ መሆኑን እናዉቃለን።

ታዲያ በዚህ አጋጣሚ ለሌሎች የዓለም መንግሥታት መሪዎች የሚነግራቸዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ «ነግ በእኔ» ብለዉ ከመዉደቃቸዉና ከመዋረዳቸዉ በፊት ለእግዚአብሔር እጃቸዉን እንዲሰጡና ወንበሩንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙትና ለሚያስፈጽሙት ለኢትዮጵያዉያኑ ለተመረጡትና ለተቀቡት እዉነተኛ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማሪያም ባለሟሎችና እንደራሴዎች አሳልፈዉ ቢሰጡ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን

እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዓለም መንግሥታት መዉደቅም መነሳትም ምክንያት የምትሆነዉን ኢትዮጵያን የሚጎበኝበት ወራት ደርሷልና በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ለሚቋቋመዉ የእግዚአብሔር መንግስት እጁን የማይሰጥ መንግሥት ሆነ ቡድን እንዲሁም ግለሰብ ዳግም የንስሐ እድሜ ሳያገኝ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጠረጋልና ነዉ። ጥቅሙ ለራሳቸዉ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር «አደርገዋለዉ።» ያለዉን የዓለም ሕዝብ በአንድ ላይ ቢሰለፍ ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ አይችልምና።» ይላል።

**ታዲያ ስለነዚህ ነገር ምን ይሉናል?**

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:</u>** ታዲያ ከላይ በግልጽ እንደተጻፈዉ የአቶ መለስ ዜናዊና ባለሥልጣኖቻቸዉ ሥርዓት የመደምደሙ ጊዜ መድረሱና ለነፍሳቸዉ የሚያስብላቸዉ ሰዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለርኩሰት ተግባራቸዉ እዉነተኛ ንስሐ እንዲገቡና መልካም ፍሬ ማፍራት ባለመቻላቸዉ ምክንያት መልካም ፍሬ ለሚያፈሩትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ለሥጋዊዉ ሆነ ለመንፈሳዊዉ ወንበር ለታጩት እዉነተኛ እንደራሴዎች ወንበሩን ቢለቁ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሆነ ተግልጾ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበዉንና የወሰነዉን ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ ስለማይችል መራራዉን ጽዋ ጠጥተዉ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ ቀርተዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደ ማይገኝበት ቦታ ከሄዱ ፍርዱ እጅግ ስለሚብስባቸዉ ነዉ። አቶ መለስ ዜናዊ የእግዚአብሔርን መልእክት ለመስማትና የተባሉትን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ምክንያት መራራዉን ጽዋ ጠጥተዉ የዐይን ቅጽበት ዘመናቸዉን በአግባቡ መኖርና የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ተስኗቸዉ ራሳቸዉን ለከፋ ቅጣት ዳርገዉ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ተጉዘዋል። የቀሩት ባለሥልጣናት ሆኑ ግብረአበሮቻቸዉ መራራዉ ጽዋ ስለማይቀርላቸዉ ዛሬ ነገ ሳይሉ እግዚአብሔር የተናገረዉን ተግባራዊ ቢያደርጉ የሚበጃቸዉ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ አሳዉቃቸዋለሁ። ከዚህ በተጨማሪም በዓለም ላይ የሚመጣዉ ቁጣ መንግሥታቱን መጥረጉ ስለማይቀር እነሱም ዛሬ ነገ ሳይሉ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ቢሰጡና በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱ፤ ወንበሩንም እግዚአብሔር ለመረጣቸዉ ባለሚሎቹና አገልጋዮቹ ቢለቁ የሚበጃቸዉ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ በድጋሜ አሳስባለሁ።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>** ሌላዉ ደግሞ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ ከገጽ 251-294 ያለዉን ፍሬ ሐሳብ አጠር አድርጌ ላቅርብና ወደምፈልገዉ ጥያቄ እገባለሁ። በዚሁ ምዕራፍ እግዚአብሔር ሊያሳዉቀን የፈለገዉ የኢሕአዴግ መንግሥትና አጋሮቹ እንዲሁም የሃይማኖቶች መሪዎች፣ አስመሳይ አገልጋዮች፣ እንደ ቦይ ወደወሰዷቸዉ አቅጣጫ የሚሄዱ ሰዎች ምን እንደሚመስሉ የሚገልጽና፤ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች እንዲሁም ባለሚሎችና እንደራሴዎች ምን እንደሚመስሉ፣ አቋማቸዉ ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነዉ። በዚያ በተዘጋጀዉ የተለየ መድረክ ላይ ከየክልሉ የመጡ ተወካዮች ንግግር ካቀረቡ በኋላ ከደቡብ ክልል ተወክለዉ የመጡ ተወካይ ያለዉን እዉነታ በገጽ 263 ላይ የቀረበዉ ንግግር የሚከተለዉ ነዉ።

« በማስከተልም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! እኛ እንኳን ደስ ያሎት ለማለት ይከብደናል። ምክንያቱም «ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለዴሞክራሲ የቆምን ነን» እያላችሁ፤ ይኸዉ ዱሮ በአንድነት ተጨፍልቀን እንድንኖር የተደረገብን ግፍና በደል በእናንተ ዘመን እንደገና መደገሙና ከአምሳ በላይ ብሔር ብሔረሰቦችን በአንድላይ ጨፍልቃችሁ በነፍጠኞች ቋንቋ እንድንነጋገር፣ እንድንግባባ፣ እንድንማርበት፣ እንድንሰራበት በመደረጉ ነዉ። ከኛ መሀል እንኳ አንዳንድ ብሔሮችን እየመረጣችሁ በራሳቸዉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲናገሩ፣ እንዲማሩበት፣ እንዲሰሩበት ታደርጋላችሁ፤ ብዙዎቻችንን ግን በመጨፍለቅ ታስተዳድሩናላችሁ።

«ኢትዮጵያዉያን ናችሁ፤ በአንድ ላይ ኑሩ።» የሚሉን ከሆነና «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር መኖሯን ከልቦት ካመኑና «ኢትዮጵያዉያን» የሚባሉ ዜጎች መኖራቸዉን ካስተዋሉ፤ ይህን <u>የተንኮልና የመሰሪነት እንዲሁም የበቀለኝነት አገዛዞትን ይተዉና በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ሳንከፋፈልና ሳንጠላላ እንዲሁም ሳንለያይ እንደ ኢትዮጵያዊነታችንና እንደ አዳም ዘርነታችን በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት እንድንኖር አድርጉ እንጂ በአንዱ ጎሳ ላይ አንዱን ጎሰ፤ በአንዱ ብሔር ላይ አንዱን ብሔር እያነሳሳችሁ በቋንቋ ሽፋን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ልክ እንደ ኤርትራ ለመገንጠልና ኢትዮጵያዊነት ዜግነትን ለማስካድ የምታደርጉትን የወደፊት ምኞታችሁንና እቅዳችሁን ለማሰካትና የትግራይ አገርና ትግራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የኦሮሚያን አገርና ኦሮሚያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የአማሪያን አገርና አማራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሱማሊያን2 አገርንና ሱማሌያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ አፋሪያን አገርንና አፋራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሐረሪያን አገርና ሐረሪያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ጋምቤሊያን አገርና ጋምቤሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ቤንሻንጉሊያን አገርና ቤንሻንጉሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሲዳሚያን አገርና ሲዳማዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሃዲዪያን አገርና  ሃዲያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ወላይቲያን አገርና ወላይታዉያን ዜጎችን ለመፍጠር.. ወዘተ ዜጎችን ፈጥረዉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለማጥፋት መነሳሳቶትን ያቁሙ።</u> <u>በአሁን ሰዐት የክፋትና የተንኮል ተግባራችሁን ሕዝቡ በደንብ አዉቋል</u>። ዝም ያላችሁም በጦራችሁና በደኅንነታችሁ  ኃይል ተመክታችሁ ስላስፈራራችሁት ነዉ እንጂ ከተፋችሁ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል። በፊትም ተንኮላችሁ ስላልገባዉ ነዉ እርሱ በእርሱ የተጣላዉና የተገዳደለዉ፣ የተከፋፈለዉ።

<u>ከጎኖትም የተሰለፉት እንሆዱ አምላካቸዉና የስልጣን ጥመኞች ለጥቅም፣ ለክብር፣ ለዝና ሲሉ ኅሊናቸዉን የሚሸጡት ናቸዉ። «በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳንባ ነዉ የሚተነፍሱ።»</u> የሚባሉት  ናቸዉ አብሮዎት ከልብ የሚያገለግሎት እንጂ ሕዝቡ ማንነታችሁን ስላወቀ ሁሉን ነገር ትቶ ለአምላኩ እጁን ከሰጠ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። አብሮት ያሉት የሚያጫፍሮትም ጊዜ እስከሚካዳዎት ነዉ እንጂ ወደ ልባቸዉ ሲመለሱና የማን እንደራሴ መሆኖትን ሲያስተዉሉ አንቅረዉ ነዉ የሚተፎት። <u>ስለዚህ እርሶም ቢሆን ወደልቦት ተመልሰዉ እጆትን ለፈጣሪ ቢሰጡና ወንበሩንም በእግዚአብሔር ለተመረጡትና ለተቀቡት ለእዉነተኛ እንደራሴዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና</u>

**ለሚያስፈጽሙ ቢለቁ ያተርፋሉ እንጂ አይጎዱም:: እንቢ ብለዉ እንደፈርኦን ጎሊናዎን ካደነደኑ ደግሞ ደንዳናዎች የገጠማቸንዉን ጽዋ እንደሚጎነጩ አንዳች አይጠራጠሩ::**

ከዛሬ ቀን ጀምሮ ስለኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት ለማዉራት ብቃቱና ሞራሉ ስለሌሎት ከእርሶና ከቢጤዎቾ ጋር ምንም አንድነትና ህብረት ፈጥረን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር አንሰራም፤ ተባባሪም አንሆንም:: እናንተ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፓሊሲ አራማጆች፤ በብሔር ብሔረሰቦች ስም የምትነግዱ፤ ጎሊናችሁን የምትገለባብጡና የምትሸጡ አስመሳይ አገልጋዮች፤ የዲያብሎስ ሥርዓት ፈጻሚና አስፈጻሚ ሆናችሁ ሕዝቡን መከራዉንና ፍዳዉን የምታሳዩ፤ እርስ በእርስ እያጣላችሁና እየከፋፈላችሁ የራሳችሁን መሰሪ ተግባር የምትፈጽሙ፤ ስለ ክፋትና ጭከና ተግባራችሁ ዋጋ እንደምትከፍሉበት ልታዉቁ ይገባል::

ጎሊናችሁ በክህደት ፍልስፍና የተሞላ፤ የማርክስ፣ የኤንግልስ፣ የሌኒን፣ የቻርልስ ዳርዊን የመሳሰሉት የክህደት እምነቶችን አምጥታችሁ « ዘሮቻችሁ  አዳምና  ሔዋን ሳይሆኑ ጦጣ መሰል እንስሳዎች ናቸዉ:: በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ ሰዉ የሆናችሁት:: አምላክ የሚባል ያመጡት እናንተን ለመጨቆኛ መሳሪያ እንዲሆናቸዉ የገዥ መደቦች ናቸዉ::» በማለት የምትናገሩና የምታስተምሩ አንዳች ሀፍረት የማይታይባችሁ ከሃዲዎች ናችሁ:: **እዉነተኛ ማንነታችንን ያስካዳችሁና አሁን ደግሞ በቋንቋ ለያይታችሁን እርስ በእርስ በጥላቻና በቂም በቀል እንድንመላለስ ያደረጋችሁ ዓመፀኞች ናችሁ:: አሁን ግን ልታፍሩ ይገባችኋል::**

እኛ የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆቹ የሆን ዘሮቻችንም ጦጣዎች መሰል እንስሳት ሳይሆኑ የከበሩ ሕያዋን ፍጥረቶች አዳምና ሔዋን ናቸዉ:: ነገዳችንም የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዉህድ ዘር የሆነዉ ኢትዮጵያዊ ነን:: ብሔራችንም ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነዉ:: **እናንተ ግን እዉነተኛ ማንነታቸንን እያጠፋችሁ «የማንነታችሁ መለያ የሆነዉ ቋንቋችሁ ነዉ» በማለት የራሳችሁን መሰሪ ፍላጎት ማሟያ አደረጋችሁን:: ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠችና አገራት እየተዋሀዱ ባለበት ዘመን እናንተ ትንሿን አገር በጎጥ ከፋፍላችሁ፣ ምንም እንደማናዉቅ ሰዎች አድርጋችሁ በመቁጠር « ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ:: ያ ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ:: ብሔር ብሔረሰቦች ዙፋን ላይ ስላስቀመጥናችሁ ለስልጣናችሁና ለክብራችሁ ዙፋኑን ላለመልቀቅ እስከ መጨረሻዉ ድረስ የሞት ሽረት ማድረግ አለባችሁ::» በማለት እንኳን የተማረ ፊደል የቆጠረ አይደለም ሀ ሁን እንኳ የማያዉቅ መሃይም ይህን አስተሳሰብ ፈጥሮ ኢትዮጵያዉያንን አያጃጅልም ነበር::** እናንተ ግን ተማርን የምትሉ ይህን ለመፍጠርና ወደ ተግባር ለመለወጥ ጎሊናችሁ ፈቃደኛ ሆነ:: ወደተግባርም ለወጠዉ:: ይህም አስገራሚ ፍጡሮች መሆናችሁን ነዉ የሚያሳየዉ::» በማለት በምሬት እየተናገሩ እያለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕግስታቸዉ አልቆ ወዲያዉ ወደ ልዩ እስርቤት ተይዘዉ እንዲሄዱ ትዕዛዝ ለሚመለከተዉ አካል በመስጠታቸዉ፤ ተወካይ ተናጋሪዉ ለሰዉ ርኅራኄ በሌላቸዉ ልዩ ኃይሎች እየተዳፉና እየተቀጠቀጡ ተወሰዱ::

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከተቀመጡበት በቁጣና በንዴት ተነስተዉ «የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮችና የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ተወካዮች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ተወካይ በስተቀር ሁላችሁም አርቆ አሳቢና አስተዋይ መሆናችሁን ንግግራችሁ ይገልጻል:: ለዚህም በታላቁ መሪያችንና ገዥያችን ስም አመሰግናችኋለሁ:: <u>እስከዛሬ ድረስ ጨርቁን ሰንደቅ ዓላማና አዲሲቷን ኢትዮጵያ በትዕግስት የጠበኩት በቅድሚያ መስተካከል ያለባቸዉ ነገሮች እንዲስተካከሉ በማሰብ ስለነበረ አሁን በምንፈልገዉ የኢኮኖሚ፣ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ ደረጃ ስለደረስን ከሚከጥለዉ ዓመት ጀምሮ (፳፻፭)(2005 ዓ.ም) እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ነጻ መንግሥትን መስርቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚለዉን ስም ከምድረ ገጽ ማጥፋት ይችላል::</u>

<u>እኔ ተልእኮዬንና ሩጫዬን ጨርሻለሁ::</u> እናንተ አጉል ተስፈኞች «የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይመጣል::» በማለት የምትጠባበቁ ከዛሬ ጀምሮ ተስፋችሁን ሙሉ በሙሉ ልትቆርጡ ይገባል:: ከፈለጋችሁ ወደ አዉሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤሽያና አረብ አገራት መሰደድ ትችላላችሁ:: <u>ከሚቀጥለዉ ዓመት ጀምሮ(፳፻፭ ) ዓ.ም «ኢትዮጵያ » የሚባል ስም በብሔር ብሔረሰቦች አገራት አይጠራም»</u> በማለት ንግግራቸዉን የቋጩ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥና የእሳቸዉ ደጋፊዎች በንግግራቸዉና በዉሳኔያቸዉ ደስታችንንና ጭፈራችንን በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ዳንኪራ ሳናጣጥም እንዲሁም አንዳንዶች የስብሰባዉ ተሳታፊዎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ከመደሰታቸዉ የተነሳ ራሳቸዉን እስከሚስቱ ሲዘሉና ሲፈነድቁ እንዳለ»ይላል::

ከላይ በተጻፈዉ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተልኮዋቸዉንና ሩጫቸዉን መጨረሳቸዉን የሚገልጽና በሚቀጥለዉ ዓመት ማለትም ፳፻፭ (2005) ዓ.ም የመጀመሪያ ዓላማቸዉ የነበረዉንና ዉስጣቸዉ ያለዉን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ማዳከምና ብሎም ማጥፋት ተግባራዊ እንዲሆን ለባለሥልጣኖቻቸዉ፣ ለካድሬዎቻቸዉና ለደጋፊዎቻቸዉ መልእክት አስተላልፈዋል:: ከዚህ በኋላ ነዉ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ከእግዚአብሔር ተልከዉ ከገጽ <u>267-293</u> ድረስ ባለዉ ላይ ከተሰብሳቢዎቹ ጋር የተነጋገሩትና የእግዚአብሔርን መልእክት ያስተላለፉት:: ለምሳሌ ከገጽ 267-271 ያለዉን ብንመለከት:

« <u>እናንተ « ሕዝቡን ከፋፍለናል፤ ለአንድ ዓላማ እንዳይቆሙ አድርገናል፤ ጥላቻንና በቀልን ዘርተናል፤ ኢትዮጵያዊነትንና የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ቀንሰናል፤ አጥፍተናል፤ ጎጣዊ አስተሳሰብን አንግሠናል፤ አንዱን በአንዱ ላይ አነሳስተናል፤ ካድሬዎቻችንን አብዝተናል፤ ትዉልዱ ኅሊናዉን እንዲሸጥና እንደ ቦይ ዉኃ እንዲነዳ አድርገናል፤ ማንነቱንም አስጠፍተናል፤ ሕዝቡ እርስ በእርስ እንዳይተማመን ደኅንነቶቻችንና ካድሬዎቻችንን በየቦታዉ ሰግስገናል፤ ጦራችንንም አጠናክረናል፤ ልዩ ኃይል አቋቁመና:: በመሆኑም ማንም ከወንበራችን አያወርደንም፤ ስልጣናችንን ለትዉልድ እናስተላልፋለን፤ የፈለግነዉን እንደፈለግን እናደርጋለን» በማለት ታብያችኋል::</u>

<u>ነገር ግን የየዋሁና የቅኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ ስለ ሕዝቦቹ ሲል የዘራችሁትን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የዘረኝነት፣ የኅጠኝነት ፍሬያችሁን በቅርቡ እንደ ሚያሳጭዳችሁና መራራዉን</u>

ፍሬያችሁን ከዓመፃ ተባባሪዎቻችሁ ጋር እንደምትጠጡ ልታዉቁ ይገባል:: የስልጣንና የባለጊዜነታችሁ ጊዜ በአራት ነጥብ ተደምድሞባችኋል:: ስንት «ኃያላን» የተባሉ «ማንም አይነካቸዉም፣ አይነቀንቃቸዉም» የተባሉ ሰዎችና መንግሥታት እንዳልነበሩ ሲሆኑና መታሰቢያቸዉ ከምድረ ገጽ ሲጠፋ አልተመለከታችሁምን? ከተለያዩ ታሪኮችና ዜና መዋዕሎች አላነበባችሁምን? በዘመናችሁ አልተፈጸመምን? እናንተ በእዉነት ማስተዋል የጎደላችሁ ናችሁ::

ቢያንስ በጦሩና በስለላዉ ተቋም ተመክቶ የነበረዉ የደረግ(ኢሠፓ) አወዳደቅ አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ ወደ ወንበር እንደመጣችሁ ሕዝቡን በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል ታጥቀችሁ ትነሱ ነበር እንጂ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ታጥቃችሁ አትነሱም ነበር:: እንዲሁም በራሳችሁ ትግልና ታላቅነት ደርግን ያስወገዳችሁ አድርጋችሁ ባለመቁጠር ራሳችሁን ዝቅ አድርገችሁ አምላካችሁን ታከብሩና ታገኑ ነበር እንጂ በጦራችሁ፣ በስለላ መዋቅራችሁ፣ በስልጣናችሁ፣ በኃይላችሁ ተመክታችሁና ታብያችሁ በሕዝብ ጫንቃ ላይ አትረማመዱም፣ በደልና ግፍ አትፈጽሙም ነበር:: ሕዝቡንም ለዓመፃ፣ ለክህደትና ለርኩሰት ሕይወት አታነሳሱም ነበር::

ከእንግዲህ ግን የዐመጻ፣ የክህደቱ፣ የርኩሰቱ ዘመናችሁ የማብቃቱን መርዶ ለእናንተ ልናረዳ ለሕዝቡ ደግሞ ልናበስር ነዉ ከያለንበት ከአምላካችን ታዘን የመጣነዉ:: በዚሁ አጋጣሚ ለሕዝቡ፣ ከእንግዲህ እግዚአብሔር በአራቱም ማዕዘን ከፍ ከፍ የሚልበትና የሚነግሥበት ዘመን መድረሱንና ፈቃዱ በአራቱም ማዕዘን የሚፈጸምበት ወቅት የደረሰ መሆኑን ለማሳወቅ እንፈልጋለን::

እናንተ «ስልጣናችንን ለትዉልድ እናስተላልፋለን፤ መታሰቢያችንን ለዘለዓለም እናጸናለን::» በማለት ሌት ተቀን በክፋት፣ በተንኮል፣ በዓመፃ፣ በክህደት የምትመላለሱ ሰዎች፤ እንኳን ለትዉልዳችሁ ስልጣናችሁን ልታስተላልፉ ቀርቶ በእናንተዉ ዘመን ተዋርዳችሁ ከወንበረችሁ ትቆረጣላችሁ:: መታሰቢያችሁም ለዘለዓለም ከምድር ይደመሰሳል:: እኛ እስከዛሬ ለአገሪቱና ለዓለም ሕዝብ ጭምር ስንጸልይ ስናነባ ነበር:: እግዚአብሔርም ልመናችንንና እንባችንን ተመልክቶ ስለተመረጡ ቅዱሳኖቹና ከሁሉ በላይ ስለ እመ አምላክ ድንግል ማርያም ሲል በንስሐ አልመለስ ብለዉ ጎሊናቸዉን ያደነደኑትን ዓመፀኞችንና ከሃድያንን ፣ ግፈኞችን ከምድሪቱ ሊያጸዳ በመወሰኑና እዉነተኛ ቅኖች የዋሃን አገልጋዮችን ወደ ወንበር ሊያመጣ የመጨረሻዉን ዉሳኔ ስለወሰነ ምስጋናችንን በዚሁ እያቀረብን የኢትዮጵያን ትንሣኤ በመጠባበቅ ላይ ነን:: እንግዲህ የተማመናችሁበት የጨለማዉ ገዥ «ጌታችን ገዢያችን መሪያችን» የምትሉት ዲያብሎስ ከጠረጋዉ እንደሚያድናችሁ በቅርቡ የምናየዉ ሲሆን፤ እኛ ግን እንደ ወገንነታችን የምንመክራችሁና የምንለምናችሁ በንስሐ እጃችሁን ለእግዚአብሔር እንድትሰጡና ከመጠረጋችሁ በፊት ወንበሩንም እግዚአብሔርና እመቤታችን ለመረጧቸዉና ለቀቧቸዉ ትለቁ ዘንድ ነዉ » በማለት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ተናግረዋል::

ከላይ በእግዚአብሔር መልእክት ላይ እንደተገለጸዉ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች የሥልጣንና የባለ ጊዜነት ዘመናቸዉ መደምደሙና ይህንንም የእግዚአብሔር መልእክተኞች መርዶዎን

ለባለጊዜዎች ሊያረዱ የምስራቹን ለሕዝቡ እንዲያበስሩ መታዘዛቸዉን ገልጸዉ እንዲሁም ከመጠረጋቸዉ በፊት በንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡና ወንበሩንም እግዚአብሔርና እመቤታችን ለመረጧቸዉና ለቀቧቸዉ እንዲለቁ ከልመና ጭምር ነበር የተናገሯቸዉ:: ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ማንም የሰማቸዉና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተግባራዊ ያደረገ ሰዉ የለም:: **ለዚህ ጉዳይ ምን የሚሉት ነገር አለ?**

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:</u>** በዚህ ሆነ በቀጣይ ጽሑፎች ዉስጥ እግዚአብሔር የማንንም ጥፋት፣ ዉድቀት ስለማይፈልግ ነዉ መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎቻቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ለእርሱ ፈቃድ እንዲሰለፉና ነፍሳቸዉን ከከፋዉ ጥፋትና መከራ እንዲያድኑ በግልጽ የሚሆነዉን አስቀድሞ የገለጸዉ:: ነገር ግን ትዉልዱ የሥጋና የደም ስሜቱን እንጂ የሕያዉ ነፍሱን ስሜት ስለማያዳምጥ፤ ይኸዉ ለንስሐ ሳይበቃ በእግዚአብሔር ቁጣ እየተጠረገና ወደፊትም እጁን ለእግዚአብሔር እስከሚሰጥና የተባለዉን እስከሚፈጽም ድረስ ቁጣዉ እየጠነከረበት ይሄዳል እንጂ እግዚአብሔር የተናገረዉን ማንም አያስቀረዉም፤ አያዘገየዉም::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>** በዚሁ ምዕራፍ በገጽ 278-279 ድረስ የተገለጸዉ

«ኢትዮጵያ እንኳን ዜጎቿን «ኢትዮጵያዉያን ነን» የሚሉትን ቀርቶ የዓለምን ሕዝብ ትመራለች ብንላችሁ «ኡኡ» ልትሉ ስለምትችሉ የንስሐ እድሜ ካገኛችሁ ተፈጽም እንደምታዩ እንነግራችኋለን:: በዓመፃችሁ ጸንታችሁ ከተጠረጋችሁ ደግሞ ቅኖችና የዋሃን ትዉልዶች እንደሚያዩት በእግዚአብሔር ስም እናረጋግጥላችኋለን:: እንደእናንት የእግዚአብሔርን ኃይል የምንጠራጠር አይምሰላችሁ:: እግዚአብሔር፤ ንጉሡ ሰናክሬም የተመካባቸዉንና የተማመነባቸዉን **185000 (አንድመቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ**» ሠራዊት በዓይን ቅጽበት ዉስጥ እንዳልነበሩ አድርጎ እንዳረገፋቸዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አላነበባችሁምን? ሲወራስ አላዳመጣችሁምን?

እግዚአብሔር አሁን በኛ ዘመን ኃጢአት እጅግ በነገሠበት ወቅት ደግሞ 185000 አይደለም **<u>1850000000</u>** (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ) ሠራዊት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ማርገፍ የሚያቅተዉ ይመስላችኋልን? **<u>እናንተ ሆናችሁ በዓለም ዉስጥ ያለዉ ትዉልድ ማንም ይሁን ማን በዓመፃዉ ከጸናና እጁን ለእግዚአብሔር አልሰጥ ካለ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዓመፀኛ ትዉልድ ረግፎ እንደ ኖኅና ቤተሰቡ ቅንነት፣ የዋህነት፣ እዉነተኛነት የተላበሱትን ሰዎች ብቻ የማያስቀር ይመስላችኋልን?</u>**

**<u>ስለዚህ «ሠራዊቴ፣ ደኅንነቴ፣ ጠባቂዬ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ኃያላን መንግስታት፣ የአዉሮፓ ህብረት፣ የአፍሪካ ህብረት .. ወዘተ» የሚባሉት እንኳን እናንተን ራሳቸዉንም ማዳን እንደማይችሉ በዚሁ ልንነገልጽላችሁ እንወዳለን</u>**:: ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድኑ የሚችሉት በእዉነተኛ ንስሐ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሲሰጡና በኢትዮጵያ በቅርቡ እግዚአብሔር ለሚዘረጋዉ መንግሥቱ ለሥጋዊዉም ለመንፈሳዊዉም ሥርዓት ተገዥ ሲሆኑ ብቻ ነዉ:: **<u>በተቀረ ግን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት</u>**

***ጽዋቸዉን እያንዳንዱ መንግሥት፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ እየጠጣ ነጻነቱ ተገድቦ ወደሚኖርበትና እንደ ዓመፃዉ ደረጃ ፍዳዉን ወደሚቀበልበት ቦታ መሄድ ነዉ የሚቀረዉ::*** ይህን ሁሉ የተናገርነዉ መቼስ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ ብለን በማሰብ ሳይሆን የእናንተ ልበደንዳናነት ቢታወቅም ባለማወቅ በቅንነትና በየዋህነት አብሯዋችሁ የተሰለፉ ሰዎች ካሉ ከዛሬ ጀምሮ ከእናንተ ጋር አንድነትና ህብረት መፍጠራቸዉን አቁመዉ ከእዉነትና ከአምላካቸዉ ጋር ብቻ አንድነትና ህብረት እንዲፈጥሩ፣ እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ ለማሳሰብ ነዉ:: » በማለት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ተናግረዋል::

***ከላይ በተገለጸዉ መልእክት ዓመፀኞቹ የስም ኢትዮጵያዉያን ብቻ አይደለም ዓመፀኞቹ የዓለም መንግሥታትና ሕዝቦች ጭምር በእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚጠረጉ ነዉ የሚገልጸዉ:: በዚህ ላይ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?***

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:*** ከቀደም ብዬ እንደገለጽኩላችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሆኑ የዓለም ሕዝቦች የእግዚአብሔር ሕያዉ ፍጥረታት ናቸዉ:: ፈቃደኞች ከሆኑ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን የሚችሉና ለእግዚአብሔር መንግሥትም መብቃትና እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነዉ መኖር የሚችሉ ስለሆነና ሁሉም የሰዉ ዘር የአዳምና ሔዋን ዘሮች በመሆናቸዉ ነዉ ለእነሱም የንስሐ እድል የተሰጣቸዉና የተባሉትንም እንዲፈጽሙ ያዘዘዉ:: ነገር ግን እነሱም ሆኑ ኢትዮጵያዉያን ሕሊናቸዉ በፖለቲካ ስለተበከለና ስለተመረዘ እንዲሁም «እኛ የተገኘነዉ ከጦጣ መሰል እንሰሳ ነዉ፤ ማች፣ ፈራሽ፣ በሰባሽ ነን እንጂ ሕያዋን አይደለንም::» በማለታቸዉ ለእግዚአብሔር መልእክትና ቃል ቦታ አልሰጡም፤ ለመስማትም ፈቃደኞች አይደሉም:: ምናልባት የእግዚአብሔር ቁጣ ልክ ሲያስገባቸዉ ያኔ እጃቸዉን ይሰጣሉ፣ ለመልእክቱና ለቃሉ ተገዥ ይሆናሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

***ጠያቂዉ አገልጋይ:*** በዚሁ ምዕራፍ በገጽ 282-283

«ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የጦር ሠራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የደኅንነት ኃይል፣ ልዩ የጥበቃ ኮማንዶዎች፣ ባጠቃላይ ጦር መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮችና ፖሊሶች በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ወዲያዉ መመሪያ የሰጡ ሲሆን፤ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ የእግዚአብሔር መላእክት፤ በጦር ኃይላቸዉ፣ በስልጣናቸዉ፣ በጉልበታቸዉ፣ በሀብታቸዉ ተመክተዉ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ላይ ጥቃት ሊፈጽሙ የተነሱትን ሁሉ ከነመሳሪያዎቻቸዉ እንዳልነበሩ አድርገዉ ሊያጠፉቸዉና ሊደመስሷቸዉ ሲመጡ፤ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ወዲያ የእግዚአብሔር ቁጣ ከመሪዎች ሆነ ከባለስልጣኖች እንዲሁም ከተሰበሰቡት ሰዎች እንዲርቅ በመለመናቸዉ፣ በነብዩ በዮናስ ዘመን ***በነነዌ ሰዎች ላይ እንደታየዉ ምልክት የመጣዉ የእሳት ነበልባል በዓመፀኛ ሰዉ አናት ላይ ወርዶ ከመሃል አናታቸዉ ያለችዉን ጠጉር በልታ ተመለሰች::***

በወቅቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የታየ ምልክት ስላልነበረ እናታቸዉ ጠጉራቸዉ የተበላች ባለሥልጣናትና አስመሳይ አገልጋዮች፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የተለየ ምልክት ባለመታየቱ «ይህ የእነዚህ አስማተኞች ተግባር ነዉ እንጂ የእግዚአብሔር ምልክት አይደለም። የጠቅላይ ሚኒስትራችን ጌታ ታላቅና ዋና ስለሆነ የታየዉን ምልክት አናምንም፤ አንቀበልም » በማለት ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅት ፀሐይ ስትጨልም፣ አለታት ሲሠነጣጠቁ፣ እንዲሁም በሦስተኛዉ ቀን ከሙታን በኃይሉ ሲነሳ ወደ ልባቸዉ እንዳልተመለሱና ከቁም ነገር እንዳደልቆጠሩት ይልቁኑ የተደረገዉን ምልክት ሁሉ «ሐሰት ነዉ» ለማስባል የፈጠራ ወሬዎችን እንዳዘጋጁት ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን ፣ አይሁድ ካህናትና አለቆች፣ እንዲሁም ሥጋዉያን መሪዎችና ባለስልጣናት፤ የአሁኖቹም እጃቸዉን ለእግዚአብሔርና ለእንደራሴዎቹ ከመስጠት ይልቅ እንደ ቀደሙት መሰሎቻቸዉ ኅሊናቸዉን አደንድነዉ በዓመጻና በክህደታቸዉ ጸኑ።» በማለት ተገልጿል

ከላይ በቀረበዉ መሰረት በተሰብሳቢዎቹና በዓመፀኞቹ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ መቶ ከእናታቸዉ ላይ ያለዉን ጠጉራቸዉን በልታ ተመልሳለች። በጠቅላይ ሚኒስትሩ እናት ላይ ግን ምንም ምልክት አልታየም። በዚህም ምክንያት የእናታቸዉ ጠጉር የተበላችባቸዉ ዓመፀኞች በእግዚብሔር ተአምርና ምልክት ሳያምኑ <u>«ይህ ድርጊት የእነዚህ አስማተኞች ስራ ነዉ እንጂ የእግዚብሔር አይደለም የጠቅላይ ሚኒስትራችን ጌታ ዋናና ታላቅ ነዉ »</u> በማለት ንስሐ ከመግባትና ለእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ከመሰለፍ ይልቅ በዓመፃቸዉ የጸኑት። **የዚህን ምክንያትና በዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?**

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>**:** ማንም ሰዉ እንደሚያዉቀዉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እናት ላይ ጠጉር የለም። ይኸዉም በተፈጥሮ ከራሰ በረኃነት የተነሳ ነዉ። ታዲያ በስብሰባዉ ላይ የተገኙት የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተወካዮች እንዲሁም የፓለቲካና የተለያዩ አገራት ተወካዮች ይህን በደንብ ያዉቃሉ። አስቀድሞ በተፈጥሮ ጠጉራቸዉ የተበላቸዉ ጠቅላይ ሚኒስትር «ጠጉራቸዉ አልተበላም» ብሎ የእግዚብሔርን መልእክትና ምልክት መካድና፤ የእሳቸዉ ጌታና በበላይ የሚመራቸዉ ማን እንደሆነ እየታወቀ «እኛ የእነዚህን አስማተኞች መልእክት ሆነ ምልክት አናምናም፤ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ጌታ ዋናና ታላቅ ነዉ» ማለታቸዉ በዙሪያቸዉ ተሰብስበዉ ከነበሩት ከአንድ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሊቀ ጳጳስና ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከተወከለ አንድ ግለሰብ ዉጭ ያሉ የተለያዩ የሃይማኖት ተወካዮች፣ የተለያዩ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች፣ እንዲሁም ደጋፊዎች፣ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ አገራት ተወካዮች፣ በሕሊናቸዉ የእግዚአብሔር እዉነት እየመሰከረባቸዉ፤ እነርሱ ግን ሕሊናቸዉን በማደንደን እንኳን ግምት ዉስጥ የሚያስገባቸዉን ምስክርነት መስጠት ይቅርና በሐሳባቸዉ እንኳ ሊያስቡ የማይገባዉን የቀለለና የማይመስል አስተሳሰብና አቋም እንደያዙ ነዉ የሚያስረዳዉ። እንዲሁም ለሥልጣናቸዉ፣ ለጥቅማቸዉ፣ ለክብራቸዉ፣ ለዝናቸዉ ሲሉ ሕሊናቸዉን በመሸጥ ለጨለማዉ ገዥና ለጨለማዉ ሥርዓት ታማኝ የሆኑ መሆናቸዉን ነዉ የሚያሳየን። ይህም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞትና ቀብር እንዲሁም እስከአሁን ድረስ እየታየ ያለዉ ይህንኑ ማንነታቸዉን ይመሰክርባቸዋል።

ሌላዉ ደግሞ እነዚህ አስመሳይ አገልጋዮች ከሥርዓቱ ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ እየሰሩ ያሉት ሰዎች፤ ከእግዚአብሔር መልእክትና ምልክት በላይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመክተዉና እንደ ታላቅ አድርገዉ ስላያቸዉና እንደ አምላክና አማልእክት ስለቆጠሯቸዉ፤ እግዚአብሔር ደግሞ ታላቅ መሆኑንና ሁሉ በእርሱ ጭብጥ ዉስጥ መሆናቸዉን ለማሳየት ይኸዉ ከሁሉ ለይቶ አቶ መለስን ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ዉስጥ በሥጋ ሞት ጠርቷቸዋል። የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ አሁንም ለእግዚአብሔር መልእክትና ምልክት መገዛትና መቀበል እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ወደ ተግባር መለወጥ ሲገባቸዉ በተቃራኒዉ በመሰለፍ አሁንም በእግዚአብሔር ተይዘዉ የተወሰዱትን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ መለስ ዜናዊን እንደ አምላክና አማልክት ቆጥረዉ እያመሰገኑ፣ እያገነኑ፣ እያመለኩ፣ እያስመለኩ፣ እየተለማመኑ ነዉ ያለዉ። ይህ ደግሞ በተሰጣቸዉ የንስሐ እድሜ መጠቀም ስላልቻሉ ለከፋዉ ቅጣትንና መከራ ራሳቸዉን እያዘጋጁ መሆኑን ነዉ የሚሰማን። በዚሁ አጋጣሚ አሁንም የአቶ መለስ አቅም እስከምን ያህል ድረስ እንደነበረ አስተዉለዉ እንዲሁም ይመራቸዉ የነበረዉን መንፈስ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ መሆኑን በደንብ አዉቀዉ ወደ ልባቸዉ እንዲመለሱ፣ ለእግዚአብሔር ጥሪና ፈቃድ እንዲሰለፉ ለቀሪዎቹ ባለሥልጣናትና ከጎናቸዉ ለተሰለፉት የተለያዩ አካላት እንዲሁም ግለሰቦች መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u> እነዚያ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ስለ እዉነት የመሰከሩትንና የጨለማዉን ሥርዓት የዓመፃ ተግባር ያጋለጡ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ተወካይና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጳጳስ ማን እንደሆኑ ይታወቃል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:</u> እንግዲህ በቅርቡ ትንቢቱን ሲፈጽሙ የሚታወቁ ይሆናል። ልክ ቀድሞ ዲይብሎስ በሰማያት ዓመፃና ሁከት ሲፈጥር ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል በጽናት በመቆም ያዲያብሎን የዓመፃና የክህደት ተግባር በቆራጥነት እንደተቃወሙና ከእዉነት ጋር እንደተሰለፉ ሁሉ፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች አሁን በዓለም የነገሠዉን የጨለማ ገዥ ሥርዓት ይቃወማሉ፣ ያጋልጣሉ፣ ሕዝቡም ከእዉነት ጋር ብቻ እንዲሰለፍ ይመክራሉ፣ ያሳስባሉ ተብሎ ይገመታል። ለወደፊትም የደቡብ ኢትዮጵያ ተወካይ በኢትዮጵያ ትንሣኤ የኢትዮጵያ(የምስራቅ አፍሪካ) ከንጉሡ ስር በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ እንደሚያገለግሉ፤ እንዲሁም ሊቀ ጳጳሱ ከርእስ ሊቃነ ካህናት(ፓትርያርክ) ስር የኢትዮጵያ(የምስራቅ አፍሪካ) ሊቀ ጳጳስ(ሊቀ ካህናት) ሆነዉ እንደሚያገለግሉ ይገመታል። ይገመታል ያልኩበት ስለ ሁሉ ነገር በእርግጠኝነት የሚያዉቀዉና ሊናገር የሚችለዉ እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነዉ። እንዲሁም ሰዎች እንዳይሰናከሉና የራሳቸዉን ሥጋዊና ደማዊ አካሄድና ምርጫ እንዳያደርጉ ለማሳሰብም ጭምር ነዉ። እስከ አሁን ማንነታቸዉ በግልጽ የሚታወቁት ለኢትዮጵያና ለዓለም በሙሉ በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ድንግል ማርያም ተጠሪና ባለሟል የሆኑትና የተቀቡት ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) «ሓልሳዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁትና እንዲሁም ርእሰ ሊቃነ ካህናት(ፓትርያርክ) የሚሆኑት ካህኑ እጨጌ ናቸዉ። እንዲሁም በአራቱም ማእዘን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰለፉ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟሎችና ምርጥ ልጆች ናቸዉ። እነዚህም እግዚአብሔር በወሰነዉ ቀን ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የሚገለጡ ናቸዉ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ:** ከገጽ **283-291** ድረስ የተጻፈዉና በጎዘንና በርጎራጌ ገጽ በተገለጹት በእግዚአብሔር አገልጋይና ባለሟል የተነገረዉ:

«**በዚያዉ ወቅት አንድ አዛዉንት በጎዘንና በርጎራጌ ገጽ ባዶ እግራቸዉን ሆነዉ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የአንበሳ ምልክትና አንድ ሴት እጇን ዘርግታ የሚታይ ሰንደቅ ዓላማ ለብሰዉ በድንገት በመድረኩ ላይ መጡ::** እሳቸዉም « ከአስር ዓመት በፊት የእግዚአብሔርን መልእክት በተለያየ መልኩ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ አቅርቤያለሁ:: መልእክቱንና ማሳሰቢያዉን የሰማ፣ ሰምቶም የተቀበለና የፈጸመ ይገኝ እንደሆነ የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ:: እኔ በዚህ ነገር ልመሰክር አልችልም:: ደግሞም በዚች በእግዚአብሔር የእዉነት ተልዕኮ ከእኔ ጋር በዓላማ የተባበረና በተግባር የተሰለፈ ይኖር እንደሆነ፣ ከኖረም እስከመጨረሻ የሚጸናዉ ማን እንደሆነ እስካሁን ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ የሚያዉቅ የለም::

ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን በሚመለከት እጅግ ብዙ የሆኑ ባዕዳን የሆኑ አስተሳሰቦች፣ አስተያየቶችና ትችቶች በቃልና በጽሑፍ በግልና በጉባዔ በመጽሔት ሆነ በድምጽ ማሠራጫ በየቦታዉና በየመድረኩ ሲገለጡ፣ ሲቀርቡና ሲሠነዘሩ ይሰማል፤ ይታያልም:: የኢትዮጵያ መሠረቷ፣ ግድግዳዋና ጣራዋ፣ ጉልላቷም ስለሆነዉ ስለ ቅዱስ ኪዳኗና በእርሱ ስለተገኘዉ የኢትዮጵያዊነት ግን የሚናገርና የሚጽፍ ቀርቶ የሚያስብ እንኳ ያለ አይመስልም:: ይህም የራስ የሆነዉን ከመናቅና ከማቃለል የተነሳ መሆኑ ለኢትዮጵያዊዉ ይታወቀዋል::

ነገሩ እንግዳ አይደለም:: የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ግድም በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች «የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለችና ... መንገዱን አዘጋጁ፤ ጥርጊያዉንም አቅኑ!» ደግሞ «እናንተ የእፉኝትና የእባብ ልጆች! ከሚመጣዉ ቁጣ፣ ጥፋትና መቅሰፍት እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ መልካም ፍሬ አደርጉ!... መልካም ፍሬ የማያፈራዉን ሁሉ ሊቆረጥ መጥረቢያዉ በዛፎች ላይ ተሠንዝሯልና... ንስሐ ግቡ!» እያለ የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ያዋጅ ነጋሪ ነበር::

ነገር ግን ይህን ሰባኪ የሚሰማዉ ማንም እንደማይኖር አስቀድሞ በመንፈስ የተገለጠለት ነብይ፣ ያዋጅ ነጋሪዉን ቃል :«በምድረ በዳ የሚጮህ ሰዉ ድምጽ» በሚል ቅጽል አብራርቶት ነበር::

ዛሬም ሰሚ ቢኖርም ባይኖርም የእግዚአብሔር መንግስት ለሆነችዉ ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አገልግሎቴን የማበረክተዉ እኔ ትሑት ኢትዮጵያዊ እግዚአብሔር እስከፈቀደዉ ድረስ ተልዕኮዬን ከመቀጠል ወደ ኋላ አልልም:: ለዚህም ይህ የቃል ኪዳን ምስክርነት የዛሬዉ ማረጋገጫ ይሆናል::

ኢትዮጵያዊዉ ባሁኑ ትዉልድ ሁኔታ እንዳይገረምና ተስፋ እንዳይቆርጥ እንዲህ የሚለዉ የእግዚአብሔር ቃል እዉነቱን እየገለጠ በበለጠ ያጽናናዋል:: «እናንተ ግብዞች ኢሳይያስ ስለናንተ «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነዉ፤ የሰዉም ሥርዐት የሆነ ትምህርት

እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል::» ብሎ በእዉነት ትንቢት ተናገረ::» ሲል መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ስለነበረዉ ትዉልድ የጠቀሰዉ የነቢዩ ቃል ነዉ::

ደግሞም:«ከሃዲና ዓመጸኛ፣ አመንዝራ የሆነ ትዉልድ ምልክትን ይሻል፤ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠዉም፤... የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ተነስተዉ ከዚህ ትዉልድ ጋር ይፋረዳሉ፤ ያሳፍሩታልም፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፤ እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ:: ንግስት አዜብ በፍርድ ቀን ተነስታ ከዚህ ትዉልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ::» ብሎ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱና በዘመኑ ስለነበረዉ ትዉልድ የተናገራቸዉ ቃላት ለዚህ ትዉልድ ብርቱ ማስጠንቀቂያዎች ናቸዉ::

ከላይ የተገለጸዉና ከዚህ ቀደም በቃልም በጽሑፍም ደጋግሜ ያሳሰብሁትን እንደገና እያስታወስኩ አሁንም በዚህ የቃል ኪዳን ምስክርነቱ መዝጊያ ላይ ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ምክሬን አበረክታለሁ፤ የማስጠንቀቂያ ቃሌንም እሰጣለሁ::

**ለእዉነተኞቹ ኢትዮጵያዉያን!**

በመጀመሪያ በዚህ መልእክት ዉስጥ የተመለከተዉን የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር ጠብቃችሁ የምትገኙ ኢትዮጵያዉያን ካላችሁ በዚህ አቋማችሁ በያላችሁበት ጸንታችሁ ቁሙ! **<u>ይህ ዛሬ በእናንተ ላይ የመጣዉ መከራ ከባድ በመሆኑ እግዚአብሔር መላእክትን ሊፈትን ተሠዉሯቸዉ ሣለ የነበረዉን ሁኔታ ይመስላል::</u>**

ይህን ዓይነቱ መከራ ለእነርሱና ለእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ወዳጆች፣ ይልቁንም ለራሱ ለባለቤቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ አልቀረም:: ለእኛም ትምህርትና መቀጣጫ ይሆነን ዘንድ ከጥንት ሲያያዝ የመጣዉ ዜና ታሪካችን ይህንን ሁሉ ያስታዉሰናል::

ከቀደሙት የተላለፈልን የመላእክቱ የፈተና ታሪክ እንደሚያስረዳዉ ሳጥናኤል በሚል ስም የመላዉ ነገደ መላእክት የበላይ አለቃ የነበረዉና ከዉድቀቱ በኋላ ዲያብሎስ የተባለዉ መልአክ ራሱ ተሳስቶ መልአክትንም ሊያስታቸዉ «የፈጠርኳችሁ እኔ ነኝ» አላቸዉ::

ይህን የሐሰት ነገሩን ካልተቀበሉት መካከል አንዱ ሊቀ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል: «አምላካችን እስኪገለጥ በያለንበት እንርጋ!» የሚል ያዋጅ ቃል አሰማ::

ያዋጁን ቃል የተቀበሉት፣ በፈጣሪያቸዉ ፊት የበለጠ ሞገስን አግኝተዉ በዘላለማዊዉ የእግዚአብሔር ጸጋ የከበሩ ቅዱሳን ሲሆኑ፣ ያዋጁን ቃል ተቃዉመዉ ሳጥናኤልን የተከተሉት ግን ከፈጣሪያቸዉ ፊት ተወግደዉ በዘላለም ፍዳ የሚሠቃዩ ርኩሳን ሆኑ::

ስለዚህ እናንተም የእግዚአብሔር የሆናችሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ለጊዜዉ ዛሬ በመንፈስ ነገ ደግሞ በገሃድ በምትገለጽበት ጊዜ የዓመፀኞቹና የከሃዲያን ክፉ ዕድል ሳይሆን የደጋጎቹና የታማኞቹ መላእክት መልካም ዕድል ደርሷችሁ ደስ ይላችሁ ዘንድ በቃል ኪዳናችሁ ጸንታችሁና የሚገባችሁን እየፈጸማችሁ አምላካችሁ የሚያደርገዉን ተአምርና ኃይል በትእግሥት ጠብቁ።

ቀጥሎ በዉጭ አካላችሁ ብቻ ሳይሆን በዉስጥ ሰዉነታችሁ «ኢትዮጵያዊ ነኝ» የሚል እንደ ዉኃ የጠራና እንደ እሳት የሚያቃጥል ስሜት ያላችሁ ኢትዮጵያዉያን የምትገኙ ከሆነ ያ «ኢትዮጵያዊነታችሁ ሰዉ ሠራሽ ወይንም ጊዜ ያመጣዉ «ኢትዮጵያዊነት» ሳይሆን ከእግዚአብሔር በቃል ኪዳን የተገኘዉ «የእዉነተኛዉ ኢትዮጵያዊነት» ምልክት ነዉና ደስ ይበላችሁ!

ለእናንተ ይህን እላለሁ - ቃል ኪዳኑን ባፈረሱት ላይ እንዲሁም ባገር ዉስጥና በዉጭ ባሉ ግብረአበሮቻቸዉ ላይ ከዚህ የባሰዉ የሚያስጨንቀዉ የቅጣት ቀን ሳይመጣ እግዚአብሔር ከዚያ ቀን እንዲሰዉራችሁ፣ ይህንንም የፈተናዉን ዘመን አሳልፎ ምሕረቱና ሰላሙ በዓለሙ ሁሉ ሳይቀር የሚሰፍኑባት መንግሥቱ ከምትገለጥበት ጊዜ እንዲያደርሳችሁ ራሳችሁን በቶሎ በንስሐ አጽድታችሁና አስተካክላችሁ በእዉነተኛዉ ኢትዮጵያዊነት ታደሱ። «ቅዱስ ሥጋዉን በልታችሁ፣ ክቡር ደሙንም ጠጥታችሁ» ለንጉሣችሁ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለንግሥት እናቱ ክብር መገለጥ የተዘጋጃችሁ ሁኑ።

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዉያን ጉዳይ የሚወሰነዉ ችግራቸዉም መፍትሔ የሚያገኘዉ በሰዉኛ ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ከእርሱ ጋር ባለችሁ ቃል ኪዳን ከመጽናት በስተቀር በሌላዉ አትድከሙ። ከቃል ኪዳን አምላካችሁ ሊለያችሁ የተነሣዉን ተቃዋሚ ኃይል መስማትና መከተል ትታችሁ የዘላለማዊ መሪያችሁ የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ አገራችሁ የድንግል ማርያም ቃል የሆነዉን የቅዱስን ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁን ብቻ በሃይማኖት ጠብቁ፤ መጠበቃችሁንም በይፋ አስታዉቁ። በይፋ የምታሳዉቁትም « ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» በሚለዉ የነብዩን ቃልና የኢየሱስ ክርስቶስ ዓርማ የሆነዉ «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» የሚለዉ ምልክት በሠፈረበት «ያረንጓዴ ቢጫና ቀይ »ሰንደቅ ዓላችሁ ዙሪያ ስትሰባሰቡ ነዉ።

በዚህ ጊዜ እዉነቱን በየሕሊናችሁ ታገኙታላችሁ። ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንዳላችሁ ይሰማችኋል፤ በእርሱ እዉነት ደስ ይላችኋል፤ እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ከሰዉም ጋር ሰላም ይሆንላችኋል፤ በሁሉ ዘንድ ስምምነት ታገኛላችሁ። የምትታወቁት በዚህ ኢትዮጵያዊነታችሁ ስለሆነ፣ ባገራችሁና በዓለም ላይ የናቋችሁና ያጠቋችሁ የጠሏችሁና ያዋረዷችሁ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ ተጸጽተዉ ይቀበሏችኋል፤ ያከብሯችኋል፤ ይወድዷችኋል፤ይፈሯችኋል። ከእግዚአብሔርም የጠበቃችሁትም ሁሉ ይሆናል።

በመጨረሻም ከቤተክነቱና ከቤተ ምልክናዉ፣ ከቤተ ሕዝቡም ወገን በዚህ ትዉልድ ክህደትና ዓመፅ ዉስጥ ተካፋዮች ለሆናችሁት ሁሉ፡ ይህን እላለሁ፡- ዛሬ በኢትዮጵያዉያን ላይ እየወረደ ያለዉ መከራ የመጣበት ምክንያት ምን እንደሆነ በየጊዘዉ ገልጫለሁ። ይኸዉም በእግዚአብሔርና

በኢትዮጵያ መካከል ጸንቶ በኖረዉ ከዚህ በላይ በተመለከተዉ በቅዱስ ኪዳን ላይ ይህ ትዉልድ ቀደም ብሎ የልብ ክህደቱን ከፈጸመ በኋላ በኃይል ዓመፅ በመነሣቱ መሆኑን የሚያስረዳ ነዉ።

ይኸዉ የትዉልዱ ሁኔታና አድራጎት በእግዚአብሔር ፊት ጽዋዉ የሞላ ታላቅ ኃጢአት ሆኖ ስለተገኘ ላገራችን መርገም ሆነ፤መርገሙም በግልጽ የሚታየዉን ቅጣት መቅሰፍት አመጣ። እግዚአብሔር ግን ለመከራዉና ለፈተናዉ ብቻ አጋልጦ አልተወንም፤ ፈጽመን ከመጥፋት አድኖን <u>ለንስሐ የሚያስፈልገዉን ጊዜ በቸርነቱ እያራዘመልን እንሆ ለሰላሳ ሰባት ዓመታት አቆይቶናል። ለሰላሳ ስምንተኛዉ ግን ዋስትና የለንም።</u>

ስለዚህ እየቀጠለ በሄደዉ የመከራ ዘመን ዉስጥ ከስሕተታችሁ በንስሐ ያልተመለሳችሁ ሁሉ፡ በዚህ ምክንያት በመጣዉ ኃጢአትና መርገም ተይዛችሁ እንዳትቀሩ የባሰዉ ጥፋት ከመድረሱ በፊት ንስሐ ገብታችሁ ሥጋዉና ደሙን በመቀበል ሳትዘገዩ ከፈጣሪያችሁ ጋር ታረቁ። ራሳችሁን በቅዱስ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ አስተካክላችሁ በተቀደሰዉ ሰንደቅ ዓላማችሁ ዙሪያ ተሰባሰቡ።

<u>ይህን ካላደረጋችሁ ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የከበራችሁበትን ኢትዮጵያዊነታችሁን ተገፍፋችሁ፣ ልትይዙት የተመኛችሁትንም ሳታገኙ፡ ሁሉንም አጥታችሁ በሥጋችሁም በነፍሳችሁም ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እወቁ።</u>

እንዲሁም እናንተ የዓለም መንግስታትና ድርጅቶች! ኢትዮጵያን በሚመለከት፡ ለዓለም ሕዝቦችና ለኃያላኑ መንግስታት፣ ለዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችም ስለተሰጠዉ ማስጠንቀቂያና ስለደረሰባቸዉ ጉዳት የቅርቡን ታሪክ እዚህ ላይ መጥቀስ አግባብ ይሆናል።

በአደባባይና በአዋጅ፣ በጽሑፍና በማኅተም፣ ለኢትዮጵያ የገቡትን ቃል ኪዳን እርስ በርሳቸዉ በመመሳጠር ክድዉና ሽረዉ የቅዱስ ኪዳን ታማኝ የሆነዉን ኢትዮጵያዊዉን ዘር በመደምሰስና የቀረ ሕዝቧን በመለያየት ይህችን የእግዚአብሔር አገር ለማጥፋትና መንግስቷን ለማፈራረስ ሴራ አድርገዉ ተነሥተዉ የነበሩትን ኢጣልያንን እንግሊዝንና ፈረንሳይን እንዲሁም የዓለም መንግስታት ማኅበር ይባል የነበረዉን ተባባሪያቸዉን ድርጅትና አባል አገሮቹን እዉነተኛዉ ዳኛ እግዚአብሔር በ፪ኛዉ የዓለም ጦርነት የብረት በትር እንዴት አድርጎ እንደቀጣ አይዘነጋም።

ዛሬም ይህንኑ የክፋት ዓለማቸዉን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዉያን ላይ ለመፈጸም በተንኮል ተነሣስተዉ በነበሩት ሶቬዬት ኅብረት ይባል በነበረዉ ከሃዲ መንግስት ዩጎዝላቪያንና ሱማልያን በመሳሰሉት ተባባሪዎቹ አገሮች እንዲሁም በመካከለኛዉ ምስራቅ በሚገኙ አንዳንድ የኢትዮጵያ ተጻራሪ መንግስታት ላይ እየደረሰ ያለዉ ቅጣት እነሆ ዓለም በሙሉ ይመለከተዋል።

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግስት በመሆኗ** ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት በፊት በነበረዉ ዓለም ላይ እንደደረሰዉና በዚያን ጊዜ እንደሆነዉ ሁሉ ዛሬም ለኢትዮጵያዊዉ ብቻ ሳይሆን ለያንዳንዱ ባዕድ ግለሰብ፣ ለያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም፣ ለያንዳንዱ ሕዝብና መንግስት፣ ለኃያላኑም ሆነ

ለንዑሳኑ፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለተባለዉና ለመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ጭምር፡ <u>የእርሷ የኢትዮጵያ ጉዳይ ለታላቅ ፈተና የቀረበ የእግዚአብሔር የዳኝነቱ ሚዛን ነዉ፡፡</u>

<u>**የዚህ ፈተና ዉጤትና የዳኝነቱ ፍጻሜ ግን በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመዉ የቃል ኪዳን መፍረስ የቀጣት ኩነኔ አድርጎ እንዳመጣዉ እንደ ሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት የፍርድ ወሳኔ እንዳይሆን ለሁሉም ማን በነገራቸዉ? እኔንማ እንዴት ይሰሙኛል?**</u>

የዚህ ዓለም ሰዎች የፍርድ ቃል ደርሶ እስኪፈጸምባቸዉ ድረስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት የሚነገረዉ ቃል ተናጋሪዉን ጭምር የሚቃወሙና የሚጠሉ፣ የሚንቁና የሚያቃልሉ መሆናቸዉን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ለነበረዉ ትዉልድ የጠቀሰዉ እንዲህ የሚለዉ የነቢዩ ቃል የሚገኝበት የሐዋርያዉ መልእክት ያስረዳል፡-

« እነሆ የተመረጠንና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ፤ በእርሱ የሚያምን አያፍርም» ብሎ ተጽፏልና፡፡ እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ልምታምኑ ነዉ፤ ለማያምኑ ግን «ግንበኞች ንቀዉ የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ፣ የማሰናከያም ዓለት ሆነ»፡፡ የማያምኑ ስለሆነ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፤ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸዉ፡፡»

ይህ ቃል ዛሬ በባዕዳኑም በኢትዮጵያዉያኑም ዘንድ ሲፈጸም ይታያል፡፡ ይልቁኑም ባሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለዉ «በእግዚአብሔር አምናለሁ» የሚለዉ ሳይቀር በአብዛኛዉ ሰዉ ወይም ሕዝብ ወይም መንግስት የዛሬዉ ኢትዮጵያዊዉ ትዉልድ ጭምር አምልኮቱ፣ ታዛዥነቱና ትዉክልቱ ወደ እግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ ወደ ምድራዊዉ ገንዘብና ሀብት፣ ወደ ሥጋዊዉ እዉቀትና ጥበብ፣ ወደ ዓለማዊዉ ኃይልና ሥልጣን ብቻ መሆኑን ማየት እጅግ ያሳዝናል፡፡

በዚህ አንጻር በእዉቀታቸዉ፣ በገንዘባቸዉና በኃይላቸዉ ተመክተዉ እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነዉን ሁሉ የሚንቁትንና የሚያቃልሉትን የዚህን ዓለም ሰዎች ሊያሳፍር በእነርሱ ዘንድ አላዋቂዎች፣ ደካሞችና ድሆች ተብለዉ የተናቁትንና የተጠሉትን ኢትዮጵያዉያንንና በሩቅ ባዕዳንን እያስነሳ በእርሱ መሣሪያነት እግዚአብሔር የሚሰራዉን ድንቅ ሥራ መመልከት ደግሞ ያጽናናል፡፡

ሌላዉ የሚያስገርመዉ ሁኔታ፡-

ባንድ በኩል በኢትዮጵያ ምክንያት ያ ታላቅ መለኮታዊ ፍርድ ያስከተለዉ ፪ኛዉ  የዓለም ጦርነት በመላዉ የሰዉ ዘር ላይ ያደረሰዉን እልቂት በዓይናቸዉ ያዩት በዚያ ዘመን የነበሩት የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ አዛዉንትና ታሪኳን የሚያዉቀዉ ወጣት ትዉልድ አቋም ሲሆን፤

በሌላዉ በኩል ደግሞ እነዚያ ከመለኮታዊዉ ዳኝነት የተነሣ የቅጣቱ በትር በብርቱ የገረፋቸዉ ሕዝቦችና የእነርሱ የዓለም መንግስታት ድርጅት አድራጎት ነዉ፡፡

እነዚህ ሁለቱም ወገኖች ዛሬ በኢትዮጵያና በመላዉ ዓለም እየተካሄደ ያለዉን አምላካዊ ፍትሕ እየተመለከቱ አሁንም እንደቀድሞዉ ቃል ኪዳናቸዉን በማፍረስ በዚያዉ ተመሳሳይ ድርጊት ተሰማርተዉ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የእግዚአብሔር የሆነዉን መንግስታዊ አቋሟን ለማፈራረስ፣ ልጆቿንም ለመደምሰስ በኅብረት ሙከራ ሲያደርጉ እነሆ ይታያል።

<u>ኢትዮጵያዊዉ ግን በቃል ኪዳኑ በመተማመን እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ብቻ ዘርግቶ በሚያቀርበዉ አቤቱታ ለሁሉም ለያንዳንዱም የማይቀረዉን፣ ለዚህ ሥራቸዉ ምላሽ የሚሆነዉን መለኮታዊ ፍርድ በትእግስት ይጠባበቃል።</u>

ከእግዚአብሔር ዳኝነት ማምለጥ የሚችል ማንም የለምና፤ ከዋይታዉ ለመዳን ይህን የተንኮል ዓላማ የተከተሉት ሁሉ ባገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ያሉ ግለሰቦች ጭምር ከክፋት መንገዳቸዉ በንስሐ ይመለሱ ዘንድ እማጸናለሁ፤» እንዳሉ የተቆጣጠሩት እንባቸዉ ርግፍ ርግፍ ሲል ወደ መጡበት አቅጣጫ ወደ ሕዝቡ ተመለሱ።

<u>ወዲያዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለሥልጣኖች እንዲሁም ካድሬዎች ሁሉም</u> « ምንድነዉ የዛሬዉ ቀን! የአንብሳዉ ዓርማ ሲገርመን፣ ደግሞ ሰምተነዉና አይተናዉ የማናዉቀዉን «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ብለዉ እንደ አንበሳዉ ዘዉድ የደፋች ሴት እጆቿን ዘርግታ ያሳዩን እንዴ! ስለ ታላቁ ዓርማችን ከኮብ አንድ ሰዉ እንኳ አይመሰክርልንምን? የብሔር ብሔረሰቦች አገር ስለ ሆናችዉ ስለ አዲሲቷ ኢትዮጵያ አንድም ሰዉ ታላቅ ምስክርነትን አይሰጥም አንዴ? ታላቁን አንቀጽ የብሔር ብሔረሰቦች መብትንና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የሚለዉን የያዘ የዓለም አገራት እንኳ ይህን አይነት አንቀጽ የሌላቸዉ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሶሶ ስለሆነዉ ሕገ መንግሥታችን የሚያዳንቅና የሚያገን ሰዉ ይጥፋ? ከሌላዉ ዓለም ሕዝብ በተለየ ሁኔታ የፖለቲካችን ማጠንጠኛ ለሆነዉ የግብር አባታችን ያዘጋጀልንን <u>«ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን ሲያሜዉን እንደ አቡነ ሰበሰማያት የሚደጋግምልን ሰዉ ይጥፋ?</u> ደግሞ ከአገራቸዉ አልፈዉ ስለ ዓለም እንዲህ መናገራቸዉ ምን ይባላል? አንድ ሰዉ እንኳ «<u>የዚህ ብሔር ነጻ አዉጭ ነኝ፤ የዚህ ጎሳ ተወካይ ነኝ» ብሎ የሚቀርብ ሰዉ ይጥፋ</u>? <u>እረ ዘንድሮ ስንቱን ጉድ አሳየን፤</u> <u>ምን አይነት ንክ ጭንቅላት ቢኖራቸዉ ነዉ ከጎሳቸዉና ከብሔራቸዉ ዉጭ የሚያስቡትና እንዲሁም ከአገራቸዉ አልፈዉ ለዓለም ሕዝብ የሚቆረቆሩት</u>? ወይስ ስለ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ስለ አዲሲቷ ኢትዮጵያ የማያዉቁ ከማርስ ወይንም ከጨረቃ የመጡ የጥንቷ ኢትዮጵያዉያን ይሆኑ እንዴ?» እያሉ እየሳቁና እያፌዙ እንዲሁም አንዳንዶቹ እርስ በእርስ እየተወያዩ ሳለ፡-» በማለት ቀርቧል።

**ከላይ በተገለጸዉ ጽሑፍ የሚሆነዉና የማይቀረዉን እንዲሁም ምን መደረግ እንዳለበት እግዚአብሔር በባለሟሉ ላይ አድሮ ተናግሯል ፡፡ በዚህ ላይ አስተያየቶትን ቢገልጹልን?**

<u>*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*</u>፡ እግዚአብሔር በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች ከብዙ ዓመታት በፊት መልእክቱን ቢያስተላለፍም ትዉልዱ ግን ሊቀበለዉና ሊሰማዉ አልፈለገም። በዚህ ምክንያት ለ <u>37</u> ዓመት የታገሰዉ አምላክ በ38ተኛዉ ዓመት የዓመፃ ልጆችን ከባለጊዜነት ሙሉ

በሙሉ እንደሚሸራቸዉና ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራቸዉ ዋጋ አስከፍሏቸዉ መንግሥቱን በኢትዮጵያ ምድር እንደ ቀድሞዉ ዘርግቶ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራና እዉነተኛዉ መለኮታዊ ፍርድ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ላይ እንደሚገለጽ ነዉ:: ስለዚህ የዓመፃ ልጆች ባለጊዜነት ከመስከረም፪÷፲፱፻፷፯ (2/1/1967) ዓ.ም ጀመሮ ሲቆጠር 38ተኛዉ ዓመት 2005 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ለዓመፃ ልጆች የክህደትና የርኩሰት እንዲሁም የዓመፃ ስራ አስፈጻሚዎች የባለጊዜነት ዘመን በ37ተኛዉ እንደሚጠናቀቅ ወይንም ከኢሕአዴግ ግንቦት፳÷፲፱፻፹፫ (20/9/1983) ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ለ20 ዓመት የተፈቀደላቸዉና ለ21ኛዉ ዓመት ግን ዋስትና እንደሌላቸዉና ዋጋ የሚከፍሉበት ዘመን መሆኑን ነዉ በግልጽ የሚያስረዳን::

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ራሱን ለንስሐ ለቅዱስ ቁርባን አብቅቶ የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራና ተአምር በትዕግስት መጠባበቅ ይኖርበታል እንጂ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ማድረግ የለበትም:: ከእግዚአብሔር የታዘዘዉን መፈጸምና ለተግባራዊነቱ መሰለፍ ነዉ ያለበት:: ዘንድሮ(፳፻፬) (**2004** ዓ.ም) ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ባለሥልጣናቱ፣ ካድሬዎቹ «**<u>እረ ዘንድሮ ስንቱን ጉድ አሳየን፤»</u>** እንዳሉት ሁሉ ብዙ ጉድ ስላዩ፤ አሁን እንኳ ደንገጥ ብለዉና ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደዉ ቢገኙ ከባሰዉ ጉድ ሊተርፉ እንደሚችሉ እገልጻለሁ:: ከዚህ በተጨማሪ አሁን ያለዉ የዘረኝነትና የጎጠኝነት የሞት ሕይወት ሙሉ ሙሉ ቀርቶ እያንዳንዱ ሰዉ ለኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ሁሉ የሚያስብና ከዚያም ባለፈ ስለ ዓለም ሕዝብ የሚቆረቆር፤ እንኳን ኢትዮጵያዉያንን አይደለም «የአዳም ዘር ሁሉ አባቴና እናቴ፣ ወንድምና እህቶቼ ናቸዉ » የሚል ትዉልድ እደሚፈጠርና የዘረኞችና የጎጠኞች የጨለማ ስራ ጠፍቶ የብርሃን ሕገ መንግሥት እንደሚመጣ ልናዉቅ ይገባል::

ነገር ግን ከዚያ በፊት መንግሥት የዘራዉን መራራ ፍሬ ማጨዱና መጠጣቱ ስለማይቀር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት «**<u>ከሚከጥለዉ ዓመት ጀምሮ(፳፻፭ )(ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ) እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ነጻ መንግሥትን መስርቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚለዉን ስም ከምድረ ገጽ ማጥፋት ይችላል:: እኔ ተልእኮዬንና ሩጫዬን ጨርሻለሁ::</u>**» እንዳሉት ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ትእዛዛቸውና ምኞታቸዉ ይፈጸም ይሆናል:: ይህም ጊዜ የመጨረሻዉ ዋጋ የሚከፍሉበት ሊሆን ይችላል:: ከዚያ በኋላ ግን የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይመጣል::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u>** ሌላዉ ከገጽ **291-294** ድረስ በቁጣና በብሩህ ተስፋ ገጽ በተገለጹት በእግዚአብሔርና በእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ(ሣልሳዊ ቴዎድሮስ) አማካይነት የተነገረዉ:

«**<u>አንድ ጎልማሳ ጃኬትና ሱሬ ያደረጉ ከመሃል በድንገት በቁጣና በብሩህ ተስፋ ገጽ ወደ መድረኩ ሲመጡ አይተዉ፤</u>** «አሁን እንኳ ለእኛ የሚቆምና የሚመሰክር ዘመናዊ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ የሚወክል በድንገት ወደ መድረኩ መቶ ይናገርልን እንጂ! » እያሉ የጎልማሳዉን ንግግር በጉጉት እየጠበቁ ሳለ:

ጉልማሳዉ ሰዉ «ዓለም እነ ጳዉሎስን እብዶች ብላለች፤ዓለም በልዑል ስም የመጡትን እነማንን ተቀበለች? ተሳለቀች፣ ገደለች፣ አሳደደች እንጂ ዓለም ለእግዚአብሔር ባለአእምሮ የሆነን ሰዉ ለእናንተ እብድ ነዉ ትላላች:: ስለዚህ የእግዚአብሔር መልእክተኞችን ሰምታ አታዉቅም:: በመሆኑም ብትሰሙ ስሙ ባትሰሙም አትስሙ ነጻ ኅሊናና ፈቃድ አላችሁ:: እናንተ እንደምትሉት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ቃል «የእብዶች ቃል ነዉ» ሰምታችሁ ሳቁ፣ ተሳለቁበት፣ ይምሽ፣ ይንጋ፣ አይምሰላችሁ በሳቅና በፌዝ የፈጃችሁት ጊዜ በሺህ እጥፍ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ::

እኛ እናንተ የምታላግጡባትና ልታጠፏት የተሰለፋችሁት የጥንቲቷ ኢትዮጵያ ዜጎቿና ልጆቿ ነን:: በሌላ ዓለማት ዉስጥ ያልነበርን ለአስራዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚከናወኑትን ድርጊትና ንግግሮች አብረናችሁ ሆነን የምንመለከትና የምንከታተል ነን:: **ስራችሁንና ንግግራችሁን ለአስራዎቹ ዓመታት የተመለከትንና ያዳመጥን ሲሆን በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት በመፈጸማችሁና በማስፈጸማችሁ ሕሊናችን የደማና የቆሰለ፤ እግዚአብሔር ስራዉን የሚሰራበትን ጊዜ በትዕግስት እየተጠባበቅን ያለን ሰዎች ነን ::**

የሰዉ ዘር ስሙ የሥላሴ ባሪያ፣ የድንግል ማርያም ያደራ ልጅ፣ የከበሩ መላእክት ወደጅ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ባዘዘኝና በተናገረኝ መሰረት የመጀመሪያዉን የእግዚአብሔር መልእክት ኅዳር፯፥፲፱፻፺ (7/3/1998) ዓ.ም፣ ሁለተኛዉን መልእክት ግንቦት፳፯፥፳፻ (27/9/2000) ዓ.ም፣ ሶስተኛዉን መልእክት መጋቢት፲፱፥፳፻፩ (19/7/ 2001) ዓ.ም ለአገራት መሪዎች ፣ ለተባበሩት መንግሥታት፣ ለተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ፣ ለተለያዩ ግለሰቦች፣ ባጠቃላይ ለአዳም ዘር እንዲተላለፍ መልእክቱን የላኩ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ከአገሬ ኢትዮጵያ መንግሥት ጀምሮ አንድም መንግሥት መልእክቱን ለሕዝቡ አላስተላለፈም:: ለዚህም ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ ጭምር አስጠንቅቄ ነበር:: ነገር ግን እነሱም በንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር መስጠትና ሕዝቡም በንስሐ እጁን ለአምላክ እንዲሰጥ ማድረግ ሲጠበቅባቸዉ ተቃራኒ ተግባርና የእብሪትና የትዕቢት ንግግር ይናገራሉ፤ መልእክቱንም ከቁም ነገር አልቆጠሩም:: ይህም የሚያሳየው ምን ያህል ልበ ደንዳኖች መሆናችሁንና እግዚአብሔርንም ምን ያህል እንደናቃችሁ ነዉ የሚያሳየዉ::

እኔ ጸሎቴና ምኞቴ « እናንተ የእግዚአብሔርን መልእክት አንፈልገዉም፣ አንቀበለዉም::» ብትሉ እንኳ ሕዝቡ መልእክቱን ሰምቶ ራሳኑ ከጥፋትና ዉድቀት እንዲያድን ነበረ:: መልእክቱ በሰዎች እንዳይዳረስ ደግሞ «ማንም ሰዉ መልእክቱን እያባዛ እንዳያስተላልፍ ለተላላኪዎቻችሁ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጣችሁ:: የደረሳቸዉም ሰዎች ቢሆን ሕሊናቸዉ በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በመጽሔቱ፣ በጋዜጣዉ፣ በመጽሐፍ፣ በኢንተርኔት .. ወዘተ በመሳሰሉት በሚታዩት፣ በሚደመጡት፣ በሚነበቡት ስለደነዘዘ ለእግዚአብሔር መልእክት አንዳች ቦታ አልሰጠም::

«የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን::» የሚሉት ሳይቀር አጣጥለዉታል፤ ንቀዉታል:: ለሁሉም እያንዳንዱ ዋጋ መክፈሉ አይቀርም:: አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመልእክቱ እንደተገለጸዉ በዓለም ላይ ያልታሰቡና ያልተጠበቁ ክስተቶች ሲከሰቱ እያየ አሁን ትዉልዱ ደንገጥ ማለት ጀምሯል:: ይህ ገና

ምልክት ነዉ እጅግ የከፋዉና የማይገመተዉ ክስተት በቅርቡ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ላይ ይመጣል:: እያንዳንዱ መንግስት፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ የዘራዉን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ፍሬዉን ያጭዳል፤ መራራ ጽዋዉንም ይጠጣል::

አሁንም መንግሥታት ባትሰሙኝም ሕዝቡ ግን እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ:: ይኸዉም «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል የተላለፈዉ የሦስት ጊዜ ጥራዝ መልእክትን አንብባችሁ፣ መጭዉን ጊዜ አዉቃችሁ፣ ራሳችሁን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅታችሁ እንድትገኙ:: እናንተ የየአገራት መሪዎችና ተወካዮች፣ ባለሥልጣናት፣ የተለያዩ ተቋማትን ወክላችሁ እዚህ የተገኛችሁ፣ ባጠቃላይ በተለያየ ወንበርና ኃላፊነት ላይ ያላችሁ፤ አሁንም እግዚአብሔር የመጨረሻ እድል ሰቷችኋል:: ስለሆነም ሳትወዱ በግድ ከወንበራችሁና ከኃላፊነታችሁ ተቆርጣችሁ ከመዋረዳችሁ በፊት ወንበሩን ለድንግል ማርያም ባለሟሎችና ምርጥ የአደራ ልጆች፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ልቀቁ::

እናንተም የተለያዩ አገራት(መንግሥታት) መሪዎች ከሕዝቦቻችሁ ጭምር እጃችሁን ለሠራዊት ጌታ፣ አገልጋዮቹን በተመረጠችዉና ሞገስ ባገኘችዉ አገር በኢትዮጵያ በዙፋን ላይ ለሚያነግሠዉ ስጡ:: ያኔ በረከተ ሥጋንና ድኅነተ ነፍስን ታገኛላችሁ:: ሃይማኖታችሁም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ብቻ አድርጉ:: «አይ! እኛ የዲያብሎስ ሥርዓትን ፣ ራሳችንን ያነገሥንበትንና ከፍ ከፍ ያደረግንበትን ይሻለናል» የምትሉ ከሆነ ምራጫዉ የራሳችሁ ነዉ:: ነገር ግን የሚመጣባችሁን የእግዚአብሔር ቁጣ በጸጋ መቀበልና ዳግም የንስሐ እድል ወደማታገኙበትና ነጻነታችሁ ተገድቦ እንደ ዓመፃችሁ ደረጃ ፍዳችሁን ወደምትቀበሉበት ሲኦል እንደምትሄዱ ልታዉቁ ይገባል:: ሕዝቡን ባለማሰወቃችሁ ምክንያት እንደምትጠየቁበትና የባሰዉ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚመጣባችሁ ላሳዉቃችሁ እወዳለሁ:: ለብዙ ዓመታት ጥፋት እንዳይመጣ የራሴን ጥረት ባደርግም የሚቀበለኝ በማጣቴ በእንባ ጭምር ነዉ የአሁኑን መልእክቴን ያደረስኳችሁ::» በማለት ወደ ወጡበት ቦታ ተለመለሱ::

አንዳንድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አባቶች « ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል፤ ኢትዮጵያም ሆነች ዓለም በአንድ ንጉሥና በአንድ የሃይማኖት አባት ትመራለች እየተባለ ለዘመናት ሲነገር የነበረዉ ጊዜ ደረሰ እንዴ?» በማለት ሲያሾኮሹኩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰምተዉ:

« እናንተ በዛሬዉ እለት በዚህ ቦታ የተገኛችሁ ከአገር ዉስጥም ከዉጭም የመጣችሁ ተጋባዥ እንግዶችና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ከሚቀጥለዉ ዓመት ጀምሮ ነጻ መንግሥታችሁን ታዉጃላችሁ ብዬ የተናገርኩት ያላሰብኩትን መዘዝ ስላመጣብኝ፤ በመስከረም ወር (፳፻፭) (2005 ዓ.ም) በሚከፈተዉ የተከበረዉ ምክር ቤት ላይ አሁን የተባሉትንና ሌሎች ጉዳዮችን በመወያየት አስፈላጊዉን እርምጃና ዉሳኔ የምናደርግ መሆኑን አሳዉቃለሁ::

አሁን ሁላችሁም በተረጋጋ ሁኔታ ወደመጣችሁበት እንድትመለሱና ሕዝቡን እንድታረጋጉ በጥብቅ አሳስባለሁ:: እስከዚያዉ ድረስ ደግሞ እድሜ ማራዘሚያ ኪኒን የሆነዉን ልዩ ቋንቋዬን

«ብሔር ብሔረሰብነታችን ለብዙኃነታችን፣ ለአንድነታችን፣ ለሕዳሴያችን» የሚለዉን እንደ አቡነ ዘበሰማያት በተለያዩ መድረኮች በማነብነብ ያንቺን የምናጠፋበትን ወይን የምንጠፋበትን ጊዜ መጠበቅ ይኖርብናል» በማለት ተናግረዋል፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን እነዚያ «የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነን» ባሉት ላይ በሕዝብ ፊት ቀጥተኛ እርምጃ ይወሰድባቸዋል እያልኩ በጉጉት ስጠባበቅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላሳሰብኩትና ያላዘዝኩትን ንግግር በማደረጉ እስከአሁን ድረስ ብስጭቱ ባይለቀኝም እድሜ ከተሰጣቸዉ በመስከረም ወር ላይ ግን የብቀላ እርምጃ እንዲወሰድ ከማሳሰብ እንደማልቦዝን እገልጽላችኋለሁ፡፡» ይላል የጨለማዉ ገዥ መንግሥታትን የሚያደነድንና የሚያሳምጽ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጭምር፡፡ » በማለት ቀርቧል

ከላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ ከ፲፱፻፺፰ (ከ1998) ዓ.ም ጀምሮ ለዓለም መንግሥታት፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጭመር የእግዚአብሔር መልእክታትንና ማስጠንቀቂያ ጭምር ቢያስተላልፉም ማንም ሊሰማቸዉና ሊቀበላቸዉ እንዳልቻለ ያሳዉቆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ዓመፀኞቹ መንግሥታት፣ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች ጭምር በእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚጠረጉና መታሰቢያቸዉም ለዘላለም እንደሚደመሰስ ይገልጻል፡፡ **ለዚህ ያሉትን አስተያየት ቢገልጹልን?**

__መላኩ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት እግዚአብሔር ለሰዉ ልጆች እንዲድኑ ያላደረገዉ አንዳች ነገር የለም፡፡ እስከመጨረሻዉ በመታገስ ይኸዉ እስከ አሁን ዘመን የመጨረሻ ቁጣዉን ሳያመጣ የንስሐ እድሜ ሰቶናል፡፡ ነገር ግን የእኛ የሰዉ ልጆች ዓመፃ፣ ክህደትና ርኩሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋና እየከረፋ እንጂ መሻሻል አይታይበትም፡፡ ይህም ወደ መጨረሻዉ መጥፋትና መደምሰስ የሚዳርገን ነዉ፡፡ አሁን ወደ መጨረሻዉ የጥፋትና የጠረጋ ዘመን ላይ መድረሳችን በእግዚአብሔር አገልጋዮችና ባለሟሎች እንዲሁም መልእክተኞች አማካይነት የተላለፈዉ የእግዚአብሔር ቃል እየተፈጸመና የኢትዮጵያ ትንሣኤ እየተቃረበ መምጣቱን አስተዉለናል፡፡ አሁንም ባለቀ ሰዓት ቢሆንም እግዚአብሔር መሐሪና ርኅሩኅ ስለሆነ ትዉልዱ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለስ ጥሪዬንና ልመናዬን አቀርባለሁ፡፡

__ጠያቂዉ አገልጋይ:__ እዚህ ላይ በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ

« __በመስከረም ወር በሚከፈተዉ የተከበረዉ ምክር ቤት ላይ አሁን የተባሉትንና ሌሎች ጉዳዮችን በመወያየት አስፈላጊዉን እርምጃና ዉሳኔ የምናደርግ መሆኑን አሳዉቃለሁ፡፡__

__ያንቺን የምናጠፋበትን ወይን የምንጠፋበትን ጊዜ መጠበቅ ይኖርብናል» በማለት ተናግረዋል__ ፡፡ እንዲሁም የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ «__እድሜ ከተሰጣቸዉ በመስከረም ወር ላይ ግን የብቀላ እርምጃ እንዲወሰድ ከማሳሰብ እንደማልቦዝን እገልጽላችኋለሁ__፡፡» ይላል፡፡

እዚህ ላይ የ፳፻፬ (2004) ዓ.ም የተወካዮች ምክር ቤት ከተዘጋ በኋላና በመስከረም እስከሚከፈት ድረስ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ የተለየ ክስተት እንደሚፈጠርና የጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕይወት መቆየት አጠራጣሪ እንደሆነ የዉይይቱ መድረክ ያሳያናል፡፡ እንዲሁም ፳፻፭ (2005) ዓ.ም በመስከረም

በሚከፈተዉ ተወካዮች ምክርቤት ስብሰባ የተለየ ክስተት እንደሚፈጠርና እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሐሳብና ምኞት በ፳፻፭ (2005) ዓ.ም ኢትዮጵያን የሚያጠፉበትና እነሱም የሚጠፉበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ነዉ የሚያሳየን:: እርሶ የተወካዮች ምክር ቤት እንደተዘጋና ከመስከረም ወር መከፈት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚጠረጉና አሁን በሞቱበት መልክ እንደሚሞቱ ያዉቁ ነበር?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር የሚያጽፈዉን ትንቢት ሆነ ምስጢር ጸሐፊዉ ሆነ ሌላዉ አንባቢ እርሱ እግዚአብሔር እስካልገለጸለት ድረስ ሊያዉቀዉ ሆነ ሊያስተዉለዉ አይችልም:: በዚሁ መሰረት እኔም የምጽፋቸዉ ምስጢራት ሆነ ትንቢቶች ስጽፋቸዉ የማዉቃቸዉና የማስተዉላቸዉ እንዳሉ ሁሉ በወቅቱ የማላዉቃቸዉና የማለስተዉላቸዉ ምስጢራትና ትንቢቶች አሉ:: አንዳንዶቹን በሂደት ሳነባቸዉ የምረዳቸዉና የማስተዉላቸዉ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ትንቢቱ ወይንም እግዚአብሔር በፈለገዉ መልክ እንዲገለጽ ያደረገዉ ንግግር ተፈጻሚ ሲሆን ነዉ የምረዳዉና የማስተዉለዉ::

አሁን ለቀረብልኝ ጥያቄ ያለኝ መልስ የዓመፃ ልጆች የባለጊዜነታቸዉ ዘመን ከመስከረም ፪፥ ፲፱፻፷፯ (2/1/1967) ዓ.ም ጀምሮ ለ37 ዓመት እንደሆነ፤ ከኢሕአዴግ ዘመን ከግንቦት፳፥ ፲፱፻፸፫ (20/9/1983) ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ለ20 ዓመት ባለጊዜ እንደሚሆኑና ለ21ኛዉ ዓመት እስከ ግንቦት፳፥፳፻፭ (20/9/2005) ዓ.ም ድረስ ወይንም እስከ መስከረም፪፥፳፻፮ (2/2/2006) ዓ.ም ድረስ ዋስትና የሌላቸዉና ከባለጊዜነታቸዉ እንደሚሻሩ፣ ከወንበራቸዉ በተለያየ መንገድ እንደሚቆጠሩ ብቻ ነዉ ያስተዋልኩትና የተረዳዉት አንጂ በዚህ መልኩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡ አላወኩም:: ነገር ግን መስከረም ፳፻፭ (2005) ዓ.ም ለተወካዮች ምክርቤት ስብሰባ እንደማይደርሱ ግን ገምቻለሁ:: «እድሜ ከተሰጣቸዉ» የተባለዉም ነጻ የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ሕሊና በተፈጥሮ እንደማንኛዉ ሰዉ ስለተሰጣቸዉ ያንን ነጻ ምርጫና ፈቃድ ተጠቅመዉ በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ቢሰጡና እንደታዘዙት ወንበሩን ለእግዚአብሔር እንደራሴዎች ቢለቁና የእግዚአብሔርን መልእክት ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም መንግሥታት ቢያስተላልፉ ኖሮ እግዚአብሔር በአምላካዊ ሥልጣኑ ስለ እዉነተኛ ንስሐቸዉ ሲል የተቆረጠባቸዉን እድሜ ያስረዝምላቸዉ፣ ለኢትዮጵያም ትንሣኤ ያደርሳቸዉ ነበር:: ይሁንና በእብሪታቸዉና በትዕቢታቸዉ፣ እንዲሁም በዓመፃቸዉ ስለጸኑ በተቆረጠላቸዉ ጊዜ ዉስጥ በሥጋ ሞት ወደ ሁለተኛዉ መኖሪያና መቀጫ ቦታ ሊጠሩ ችለዋል:: ተተኪዎቹ ሆኑ ሌሎቹም ባለስልጣናት በመጨረሻዉ በእግዚአብሔር ቁጣ ተጠርገዉ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ እንዳይቀሩ የታዘዙትን ተግባራዊ ቢያደርጉ የሚበጃቸዉ እንደሆነ በዚሁ አጋጣሚ አሳዉቃቸዋለሁ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ:</u> በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ በገጽ 156-157 የተገለጸዉ:

«አንዳንድ ምሳሌ ብንመለከት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ የስርዐት ማብቂያቸዉ በደረሰ ወቅት እሳቸዉም ሆነ ሌላዉ ሰዉ ባላሰበዉና ባልጠበቀዉ መንገድ ከወንበራቸዉ

ሊቆረጡና እሳቸዉም ባለሥልጣኖቻቸዉም የተለያየ መከራና ግድያ ሊደርስባቸዉ ችሏል፡፡ ከዚያም የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ሥርዓት ማብቂያ ላይም ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ከወንበራቸዉ ተቆርጠዉ እሳቸዉም ለስደት ባለሥልጣኖቻቸዉም ለችግርና ለእስር ተዳርገዋል፡፡ አሁንም ባለተረኛዉ አቶ መለስ ዜናዊ የሥርዓታቸዉ ማብቂያ መዳረሱ ቢታወቅም በምን መልኩ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡና እሳቸውም ሆኑ ባለሥልጣኖቻቸዉ ስለ ዓመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባራቸዉ ምን ዋጋ እንደሚከፍሉ ቸሩ መድኃኔዓለም አንድዬ ነዉ የሚያዉቀዉ፡፡

እኛ ግን የአዳም ዘሮች ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉና ስለ ዓመጻ፣ ስለክህደት፣ ስለርኩሰት ተግባራቸዉ ንስሐ ገብተዉ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሰተዉ በሰዉ ሳይሆን በራሱ ጊዜ እንዲጠራቸዉ ነዉ ምኞታችንና ጸሎታችን፡፡ የማንንም ጥፋትና ዉድቀት አንመኝም፡፡ በዉድቀታቸዉና በጥፋታቸዉም አንደሰትም፡፡ ምክንያቱም አንድነታቸዉንና ኅብረታቸዉን ከአምላካቸዉ ጋር ካደረጉ ሁላችንም በእግዚአብሔር መንግሥት እዉነተኛ አምላካችንን በመስቀል ላይ ዋጋ የከፈለልንን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ ሕያዉ ሆነን በመንግሥቱ መኖር ነዉ ፍላጎታችንና ልምናችን፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ስለ ነፍሳቸዉ የሚያስብላቸዉ ሰዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ ማንም ይሁን ማን በዚህ ምድር የዘራዉን ፍሬ ማጨዱና መራራዉን ፍሬ መጠጣቱ ስለማይቀር፤ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱና መልካም ፍሬ ማፍራት ባለመቻለቸዉ ምክንያት መልካም ፍሬ ለሚያፈሩትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ለሥጋዊዉ ሆነ ለመንፈሳዊዉ ወንበር ለታጩት እዉነተኛ እንደራሴዎች ወንበሩ ቢለቁ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበዉንና የወሰነዉን ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ ስለማይችል መራራዉን ጽዋ ጠጥተዉ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ ቀርተዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደ ማይገኝበት ቦታ ከሄዱ ፍርዱ እጅግ ይብስባቸዋልና ነዉ፡፡

ከዉጭዎቹ ምሳሌ ብንመለከት ደግሞ የኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሴንና የሊቢያዉ መሪ ሙሀመድ ጋዳፍ «ማንም አይነካቸዉም፤ ከወንበራቸዉም ማንም አይነቀንቃቸዉም» ሲባል፤ የተቆረጠባቸዉ ቀን ሲደርስ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና የዉርደት ሞት ሊሞቱ ችለዋል፡፡ የግብጹ መሪም ብንመለከት ባለሰቡበትና ባልጠበቁበት ቀን በተከበሩበትና በገነኑበት አገርና ሕዝብ፣ በራሳቸዉ ሕዝብ ተዋርደዉ ከወንበራቸዉ መቆረጣቸዉና የቁም ስቃያቸዉን እያዩ መሆኑን እናዉቃለን፡፡

ታዲያ በዚህ አጋጣሚ ሌሎች የዓለም መንግሥታት መሪዎች የሚነግራቸዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ «ነግ በእኔ» ብለዉ ከመዉደቃቸዉና ከመዋረዳቸዉ በፊት ለእግዚአብሔር እጃቸዉን እንዲሰጡና ወንበሩንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙትና ለሚያስፈጽሙት ለኢትዮጵያዉያኑ ለተመረጡትና ለተቀቡት እዉነተኛ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማሪያም ባለሟሎችና እንደራሴዎች አሳልፈዉ ቢሰጡ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን

እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ:: <u>ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዓለም መንግሥታት መዉደቅም መነሳትም ምክንያት የምትሆነዉን ኢትዮጵያን የሚጎበኝበት ወራት ደርሷልና በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ለሚቋቋመዉ የእግዚአብሔር መንግሥት እጁን የማይሰጥ መንግሥት ሆነ ቡድን እንዲሁም ግለሰብ ዳግም የንስሐ እድሜ ሳያገኝ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጠረጋልና ነዉ::</u> ጥቅሙ ለራሳቸዉ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር «አደርገዋለዉ::» ያለዉን የዓለም ሕዝብ በአንድላይ ቢሰለፍ ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ አይችልምና::»ይላል

**እዚህ ላይም በግልጽ አቶ መለስ ዜናዊ በምን መልኩ እንደሚጠሩ ነዉ ያልታወቀዉ እንጂ የሥርዓታቸዉ ዘመን ማብቂያ መዳረሱና በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡ በስተቀር ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡ በግልጽ ተቀምጧል:: እንዲሁም የዓለም መንግሥታትም በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡ ነዉ የሚገልጸዉ:: ለእዚህ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?**

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር እንዲህ ግልጽ ባላ ቋንቋ የሚሆነዉን አስቀድሞ የገለጸዉና የንስሐ እድል የሚሰጠዉ የማንንም ጥፋት ስለማይፈልግ ነዉ:: ነገር ግን ሕሊናዉን አደንድኖ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰቱ ተግባር የሚጸናዉን ግን ታግሶ ታግሶ በምድርም ፍዳዉን አይቶ በሁለተኛዉም ዓለም የባሰዉን መከራና ቅጣት እንዲቀበል ያደርገዋል:: ለእዚህም ነዉ ትዉልዱ ለከፋዉ ቅጣት ከመዳረጉ በፊት ብዙ የሚታገሰዉና የንስሐ እድል የሚሰጠዉ:: የንስሐ እድሉን መጠቀም የማይፈልግ ሰዉ ልክ እንደ ሰይጣናት ነዉ የሚቆጠረዉ፤ ይኸዉም ሰይጣናት እስከ አሁን ድረስ ሕሊናቸዉን በማደንደን ስለ ዓመፃና ክህደት ተግባራቸዉ ፈጣሪያቸዉን ይቅርታ አልጠየቁትም:: አቶ መለስ ዜናዊም የዓመታትና የወራት የንስሐ ጥሪ ቢቀርብላቸዉም «አልቀበለዉም» በማለታቸዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ለምስልም ለድምፅም ሳይሆኑ እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸዉን ሆነ ሕዝቡን ሳይሰናበቱና ይቅርታ ሳይጠይቁ ለሕያዉነት ዘመን ዋጋ ወደሚከፍሉበትና ዳግም የንስሐ እድል ወደ ሌለዉ ሁለተኛዉ የከፋ ቦታ ሄደዋል:: ቀሪዎቹም ባለሥልጣናት በዓመፃ አቋማቸዉ ከጸኑ ከእርሳቸዉ የባሰ ቁጣ ነዉ የሚጠብቃቸዉ እንጂ የባለጊዜነት ዘመናቸዉ በአራት ነጥብ ተደምድሞባቸዋል:: የሚቀረዉ ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ አምልኮ ምንዝርነታቸዉ በምድርም ጭምር ዋጋ መክፈል (መቀጣት) ነዉ:: እንዲሁም የዓለም መንግሥታትም የሚቀራቸዉ በምድርም ጭምር ዋጋ ከፍለዉ(ተቀጠዉ) ዳግም የንስሐ እድል ወደ ሌለዉ የስቃይ ቦታ ሲኦል መሄድ ነዉ:: ምክንያቱም ለዓመታትና ለወራት የንስሐ እድሜ ቢሰጣቸዉም ንስሐ ከመግባት ይልቅ በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት በመጨመር እግዚአብሔርን እጅግ አስቆጥተዉታልና:: » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ምዕራፍ ስምንት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**፡ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ ከገጽ 153-154 ላይ፡

*«አሁን ወዳለዉ የኢትዮጵያ መንግሥት እዉነታ ስንመጣ ደግሞ «ከዚህ በፊት እንዲህ አልተደረገላችሁም፤ እኛ ግን እንዲህ ሰራንላችሁ፤ እንዲህ አደረግንላችሁ፤ እንዲህ እናደርግላችኋለን.. ወዘተ» በማለት ራሳቸዉን ባያመጻድቁና በአጉል ተስፋ ሕዝቡን እየሞሉ ኅሊናዉን ባያደነዝዙ፤ እንዲሁም በአቅማቸዉ ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ አገልግለዉ ያለፉትን እየኮነኑ ራሳቸዉን ታላቅ ለማድረግ ኅሊናቸዉን ባይሸጡ፤ ይልቁኑ « እኛ መስራት ከሚጠበቅብን ያነሰ ነዉ የሰራነዉ። ብንሰራም መስራት ያለብንን ነዉ የሰራነዉ። ለወደፊት ደግሞ እግዚአብሔር ባሳሰበንና በረዳን መጠን የበለጠዉን እንሰራለን። » ቢሉና፤ « በሕዝብ ስም የተበደርነዉን፣ የተረዳነዉን፣ እንዲሁም ከሕዝብ የሰበሰብነዉን ሙሉ በሙሉ በአግባቡ በልማት ላይ ማዋል ተስኖን የተወሰኑ ግለሰቦች እንዲጠቀሙበትና በአቋራጭ መንገድ እንዲከብሩበት በማድረጋችን፤ በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድነን ሕዝቡን በረሀብና በችግር ባንቀጣዉ ኖሮ፤ አሁን ከተሰራዉ ግንባታ በላይ ብዙ ግንባታዎችን እናከናዉን ነበር።» በማለት ንስሐ ቢገቡ፤ ከዚህ በተጨማሪም « ግንባታዉንና ልማቱን ያከናወነዉና የምናከናዉነዉ፤ አስተሳሰባችንና መመሪያችን አገራዊ ራእይ ይዘን በኢትዮጵያዊነት ብሔር ሳይሆን በጎጣዊ ስሜት፣ ለወደፊት ኢትዮጵያ የምትባል አገር ተከፋፍላና ተበታትና ህልዉናዋን ስታጣ ክልል መንግስታት የራሳቸዉን ነጻ መንግስትነት ሲያዉጁ ተጠቃሚ በምንሆንበት ምልኩ አድሎና በቀል በተሞላበት አስተሳሰብ ስለሆነ፤ ይህንን በክፋትና በተንኮል የተሞላዉ አስተሳሰባችንን ትተን በአራቱም ማዕዘን ያሉት «ኢትዮጵያዉያን ወንድምና እህቶቻችን፣ እናትና አባቶቻችን ናቸዉ።» ብለን ከእንግዲህ ካለ አድሎና በቀል በእኩልነት እናገለግላለን።» በማለት የዘረኝነትንና ጎጠኝነት አስተሳሰባቸዉን ቢተዉ፤ ማንም ሰዉ ከተመቻቸለትና ገንዘብ እርዳታ ካገኘ ሊሰራቸዉ የሚችለዉን መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ግድቦች፣ የመብራትና የስልክ አዉታሮች፣ ፋብሪካዎች ፣ የትራንስፓርት ዘርፎች.. ወዘተ እና « ለፖለቲካ ዓላማችን ነዉ የሰራነዉ።» በማለት በራሳቸዉ ጎጣዊ አስተሳሰብ ባይመሩ ኖሮ፤ ለተሰሩት የትምህርት፣ የጤና፣ የህንጻ፣ የዉሃ.. ወዘተ ግንባታዎችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ለፓለቲካዊ ድጋፍና ለካድሬነት ምልመላ ባይጠቀሙበትና የራሳቸዉን ሰዉ ብቻ ባያበለጽጉበትና «ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ናቸዉ፤ የስራ እድል እንፍጠርላቸዉ፤ ራሳቸዉንም ቤተሰባቸዉንም ይርዱ፤ ለእናት አገራቸዉም የራሳቸዉን አስተዋጽኦ ያድርጉ።» በሚል አስተሳሰብ ተደራጅቶ ቢሆን ኖሮ ስለ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፤ ባጠቃላይ ለሥጋዊ ሕይወታችን ጥቅም ስለሚሰጡን ሁሉ የእግዚአብሔር ስም እንዲጠራ ባይፈልጉም፤ እግዚአብሔር ይስጣችሁ፤ አገራችሁንና ሕዝባችሁን በቅንነትና በእዉነት የምታገለግሉበትን ልቦና ያድላችሁ፤ ለንስሐና ለእግዚአብሔር መንግስት ያብቃችሁ ብለን እንመርቃቸዉ ነበር።*

እንዲሁም በጨለማዉ ገዥ ገላጭነትና አሳሳቢነት በፈጠሩት «ብሔር ብሔረሰቦች» ቋንቋ፤ ኢትዮጵያዉያንን በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ከፋፍለዉ እርስ በእርሱ በጥላቻና በንቀት እንዲተያዩ፣ እንዲከፋፈል፣ እንዲለያዩ፣ ራሳቸዉን የተለየ አድርገዉ እንዲቆጥሩ፣ እንዲገዳደሉ፣ እንዲበቃቀሉ፣ ቂምና በቀል እንዲያረግዙ፣ ለጥፋትና ለበቀል ጊዜ እንዲጠብቁ፣ እንዲጨካከኑ፣ አንዱ በአንዱ እንዲነሳሳ፣ ባጠቃላይ የበላይ መሪያቸዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ያሳሰባቸዉን የዓመጻና የክህደት ፍሬዎችን ባያፈሩ፤ በእግዚአብሔር እዉነት ፣ በኢትዮጵያዊነት ፣ በሰንደቅ ዓለማ ላይ ዓመጻና ክህደት ባይፈጽሙና ባያስፈጽሙ፤ ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ « ብሔር ብሔረሰቦች» በሚል ሽፋን በዘፈንና በዳንኪራ ባያሳብዷቸዉና የጨለማን ስራ ባያሰሯቸዉ፤ «በብሔር ብሔረሰብ» ስም የራሳቸዉን መሰሪ ተግባር ባይፈጽሙና በሕዝቡም ስም ባይነግዱ ኖሮ በየበረኃዉ፣ በየገጠሩ፣ በየጫካዉ የተረሱና ትኩረት ያልተሰጣቸዉ ወገኖቻችን ኢትዮጵያዉያን እንዲታወቁ በመደረጉና ራሳቸዉን የሚያመጻድቁና በዘራቸዉ፣ በጎጣቸዉ የሚመኩ ሰዎች ደግሞ  በበረኃ ሆነ በጫካ እንዲሁም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች እንደማንኛዉ ኢትዮጵያዊ እኩል መሆናቸዉን እንዲያዉቁ በመደረጉና ትኩረት ስለተሰጣቸዉ፤ እግዚአብሔር ለሙሉ እዉቀትና ለእዉነተኛ እረኛነት ያብቃችሁ በማለት እንመርቃቸዉ ነበር፡፡» ተብሎ ተገልጿል

**እዚህ ላይ ኢሕአዴግ የሰራቸዉ የተለያዩ መልካም ተግባሮች መኖራቸዉን ይገልጽና ነገር ግን እንክርዳድ የተደባለቀባቸዉ መሆኑን ያሳዉቃል፡፡ በመሆኑም እንክርዳድ ተግባራቸዉን እስካላመኑ ድረስ ስለተሰራዉ መልካም ተግባር የተለየ ምስጋና እንደማይገባቸዉ ነዉ የሚያስረዳን፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ስራቸዉ ሁሉ መልካም ቢሆን እንኳ መስራት ያለባቸዉን ነዉና የሰሩት፤ ቢበዛ ከማበረታታትና እግዚአብሔር ይስጥልን ብሎ ከመመረቅ ባለፈ የተለየ ግነትና ምስጋና የሚቀርብበት ምክንያት የለምና፡፡ አሁን የሚታየዉ ከአገር መሪ እስከ ተራዉ ካድሬ ድረስ ነጋ ጠባ « እንዲህ ሰራን፣ እንዲህ ነን፣ እንድህ እንዳርጋለን» በማለት ራሳቸዉን የሚያገኑና የሚያመጻድቁ እንዲሁም ራሳቸዉን የሚያስታብዩ ናቸዉ፡፡ ለእዚህ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?**

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ ምድራዉያን ወይንም ሥጋዉያን ሐሳባቸዉ፣ ምኞታቸዉ፣ ስራቸዉ፣ ተስፋቸዉ ሁሉ ምድር ስለሆነ ለሰሩት ነገር ምስጋናን፣ ግነትን፣ የተለየ ክብረት ቢፈልጉ ብዙ አይስደንቅም፡፡ በእነርሱ አስተሳሰብ የሚመሩ ተከታዮቻቸዉና ደጋፊዎቻቸዉ ነጋ ጠባ «ኢሕአዴግ እንዲህ ነዉ፣ መለስ እንዲህ ነዉ፣ እገሌ እንዲህ ነዉ... ወዘተ» እያሉ ቢያመሰግኗቸዉ፣ ቢያገናቸዉ፣ እንደ አማልክት ቢቆጥሯዉ ብዙም አያስገርምም፡፡ ምክንያቱም ለእነርሱ አምላክ ሆነዉ ስለታያቸዉና ነጋ ጠባ ለቅርፊት ሥጋቸዉ እንጂ ለሕያዉ ነፍሳቸዉ አንዳች ስሜትና ቦታ ስለሌላቸዉ ነዉ፡፡ እነዚህ መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎች የእነርሱ ሰዉ የፈለገዉን ግፍና በደል ቢፈጽም፣ የእነርሱ ጥቅምና ክብር ከተጠበቀ ስለሌላ ወገናቸዉ አንዳች የማያስቡ፣ ሆዳቸዉና ጥቅማቸዉ አምላካቸዉ የሆነ ነዉ፡፡ ነገ ጠባ ስለምድራዊ ምቾትና ድሎት ሕይወታቸዉ ነዉ የሚያስቡት እንጂ «እኔ ማነኝ? ለምንድ ነዉ ወደእዚህች ምድር የመጣሁት?

ተስፋዬ ምንድ ነዉ? ከእንሳሰት የምለይበት ትልቁ ሕይወት ምንድ ነዉ? ወገኖቼ እነማን ናቸዉ? ፈጣሪስ ማነዉ? ... ወዘተ» የሚለዉን የማይጠይቁ፤ ስራቸዉ እንደ እንስሳ መብላት፣ መጠጣት ብቻ የሆነ፤ እንዲሁም ከመዝናናት፣ ከመዝፈን፣ ከመደለቅ፣ ዉጭ ለተገፋና ለተጎሳቆለ ወገናቸዉ የማያስቡ፤ ከዚህ በተጨማሪ ሕያዋን መሆናቸዉን ዘንግተዉና ክደዉ እንደ አሕዛብ «እንወለዳለን፣ አናድጋለን፣ እንሞታለን» ብለዉ  ራሳቸዉን ደማዊት ነፍስ ብቻ ካለዉ ከተራዉ እንስሳ ጋር የቆጠሩ ናቸዉ:: ስለእዚህ በእዚህ ሕይወት ዉስጥ ከሚመላለሱ አእምሮ አዋቂዎች ሆኑ አእምሮ ሕፃናት፣ እንዲሁም አእምሮ ቀላሎች፣ በትዕቢት በክፋት በዓመፃ ሕይወት ከሚመላለሱ ከፈርኦን፣ ከይሁዳ፣ ከአርዮስ ወንድምና እህቶች ብዙ የምንጠብቀዉ ነገር የለም::

እኛ ግን ተስፋችንን ሰማያዊ አድርገንና ሰማያዊ ዋጋ ብቻ በመጠበቅ ለአገራችንና ለሕዝቡ ከእዛም ባለፈ ለዓለምና ለሕዝቡ መልካም ለመስራት፣ ቅን ለማሰብ፣ እዉነተኛ ለመሆን ነዉ መሰለፍ ያለብን:: ያኔ በረከተ ሥጋና በረከት ነፍስ እናገኛለን:: እዉነተኛዉን ሰላምና እርካታ እንጎናጸፋለን:: በእግዚአብሔር መንግሥትም በእዉነተኛዉ ደስታ ሕይወት ሕያዉ ሆነን እንኖራለን::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ሌላዉ በክፍል ሦስት በምዕራፍ ሦስት ከገጽ 299-304 ድረስ የቀረበዉ:

«የተለያዩ ሃይማኖት፣ የተለያዩ ባህላዊ እምነት፣ የተለያዩ ባዕድ አምልኮ፣ እንዲሁም በግልጽ ሰይጣናትን የሚያመልኩ ተወካዮች የአገሪቱን መንግሥት ለማሳመን **<u>በቤተመንግሥት በመገኘት ንግግር አቅርበዋል:: በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሪ የተወከሉት ቀሲስ(ቄስ) ሲሆኑ</u>**፤ እሳቸዉም « በመጀመሪያ ለዚህች የተቀደሰች ቀን ያደረሰን የተመሰገነ ይሁን:: **<u>ቅዱስ አባታችን በዚህ ታላቅ ክብረ በዓል ላይ መገኘት ያልቻሉት ትንሽ የጤና መታወክ ስላጋጠማቸዉ ነዉ::</u>** ስለሆነም የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በስልክ እንደተነገሮት «  መምጣት ባለመቻሌ ይቅርታ፤ ነገር ግን አንደበቱ አንደበቴ የሆነዉን ታላቁን አገልጋዬን ነዉ የላኩላችሁ ከእኔ የሆነዉን ሁሉ ይነግራችኋል» ብለዉ ስለሆነ እኔ ልመጣ የቻልኩት በዚያዉ መሰረት እንደምታዳምጡኝ አምናለሁ::

የተከበሩ የአዲሲቷ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር! ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም የኢህአዴግ አባላት እንደማዕረጋችሁ፣ ተጋባዥ እንግዶች በሙሉ፤  እኔ እዚህ የተለየ ቦታ ከተመረጡ ሰዎች ዘንድ ቀርቤ ንግግር እንዳቀርብ እድሉ ስለተሰጠኝ የእናንተ የምርጦቹ አምላክን አመሰግነዋለሁ:: መንግሥታችን ባጎናጸፈን ዴሞክራሲ መብትና ነጻነት እንዲሁም ዕድገትና የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት፣ የሃይማኖት እኩልነትና ልዑላዊነት፣ እዉነተኛ ፍትሕ ያጎናጸፈን በመሆኑ እንደ ዉዳሴ ከንቱ ካልተቆጠረብኝ «መንግሥታችን የመላእክት ስብስቦች የሞሉበት ነዉ» ብል ማጋነን አይሆንብኝም::

ይህን ካልኩ ዘንድ <u>ለየት ያሉ ነጻነትንና እኩልነትን ከሚገልጹ ታላላቅ ተግባሮች</u> አንዳንዶቹን ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: መንግሥታችን ለሃይማኖታችን ሙሉ ነጻነትን ሰቶ የተለያዩ አምልኮቶችን

በጋራ እንድናከብር በማድረጉ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ቀድሞ ነፍጠኞችና የገዥ መደቦች አምልኮታችንን በነጻነት እንዳይፈጸም አምላኮቻችንንም እንዳናከብር እንዳልተደረገ ሁሉ፤ በሃያ ዓመቱ የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የነጻነት ፣ የእኩልነት ዘመን ዉስጥ ለበዓላችንና ለአምላካችን ትልቅ እዉቅና ተሰቶ በየወንዛወንዙ አምልኮታችንን እንድንፈጽምና እኛም የሃይማኖት አባቶች መስቀላችንን ይዘን በተለይ በዋናዉ የቢሾፍቱ አምላክ በሚከበረዉና አምልኮት በሚፈጸምበት ቦታ ላይ በእሬቻ በዓል ላይ ቡራኬና ትምህርት እንድንሰጥ እድሉን ስላገኘን ነዉ፡፡

እኛም የመንግሥታችን ስራ አስፈጻሚና ፈጻሚ መሆናችንን በግልጽ መመስከራችን ይታወቃል፡፡ ይኸዉም « በቤተ ክርስቲያን ሆነ በዚህ በተቀደሰ በዓል ላይ መታችሁ አምልኮ መፈጸም ክልክልነት የለዉም፤ ክልክልነት ያለዉ በሕገመንግሥቱ የተገለጹትን ወንጀሎች መፈጸም ብቻ ነዉ እንጂ አምልኮታችሁን በተለያየ ምልኩ ብትገልጹ ችግር የለዉም፡፡ « ታቦትና ጣዖት አንድነት የላቸዉም፤ ባዕድ አምልኮና የክርስትና እምነት አንድነትና ህብረት የላቸዉም፤ ዲያብሎሳዊና እግዚአብሔራዊ መንፈስና ሥርዓት አንድነትና ህብረት የላቸዉም፤ .. ወዘተ» የሚለዉ አባባል በዲሞክራሲያዊ መንግሥታችን ስለቀረና ሁሉም እኩልና አንድ እንደሆኑ ስለተረጋገጠ በዚሁ እድለኞች ናችሁ፤ እኛም ነን፡፡ ስለዚህ በብሔር ብሔረሰቦች አምልኮ ሆነ ሌሎች ባህሎች በአንድ ላይ በኅብረት አምልኮትን ልንፈጽም ይገባል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እንደምርጫችንና ፍላጎታችን የሃይማኖት መሪዎቻችንን ሐዉልት እንድናቆምና ስዕላቸዉንም በመለጠፍና በማቆም እንድንለማመንባቸዉና እንድናገናቸዉ ሙሉ ነጻነት ስለተሰጠን ታላቁ መንግሥታችንን እናደንቃለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየብሔር ብሔረሰባችን ተከፋፍለንና ተቧድነን በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ተለያይተን በዘመድ አዝማድ ተተብትበን ሃይማኖታችንንና ቤተክርስቲያናችንን በነጻነት እንድናገለግል እንዲሁም አንዳንዶቻችንም ለደኅንነታችን መሳሪያ እንድንታጠቅ ስለተፈቀደልን ባለእድለኛነታችንን ያሳያል፡፡ በሽልማት አንጻርም ምእመኑ ለልዩ ሽልማት እንዲያዋጣ እየተደረገ ልዩ መኪና እንዲገዛ እየተደረገ ዓለምን ለናቁ ለእግዚአብሔር ራሳቸዉን ጃንደረባ ላደረጉ ቅዱሳንና ብጹዐን አባቶች እንዲሸለሙና የሀብት፣ የንብረት፣ የህንጻ፣ የንግድ ተቋማት ባለቤት እንዲሆኑ ስለተደረገና እንዲሁም እኛም በነጻነት ከፈለግን በተሐድሶ፣ ከፈለግን በጸጋና ቅባት፣ ከፈለግን በምንፍቅናና በክህደት ብንመላለስ፤ ቅዱስ አባታችን ከመንግሥታችን ሙሉ ስልጣን በተሰጣቸዉ ድምጽን በድምጽ መሻር መብታቸዉ ተጠቅመዉ ነጻነትን አጎናጽፈዉናል፡፡ ጠበቃም ይሆኑናል፡፡ ሲፈልጉም ይሾሙናል፡፡ ባጠቃላይ ለዚህ ሙሉ ነጻነትን ላጎናጸፈን ለመንግሥታችን የምስጋናም ምስጋና ሊገባዉ ይገባል፡፡» ሲሉ በአዳራሹ የተሰባሰቡት እድምተኞች ከአስር ደቂቃ በላይ በጭብጨባና በእልልታ አዳራሹን አናግተዉት ነበር፡፡

በመሀል መድረኩን የሚመሩት አስተናጋጅ «ሰዓት ስለሌለን አንዴ ጸጥ በሉ» በማለት ካሳሰቡ በኋላ ለቀጣይ የእስልምና ሃይማኖት መሪ ተወካይ ሰተዋል፡፡ ተወካዩም « እኛ ሙስሊሞች ለዘመናት

ተጨቁነን የኖርን፤ በአገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ የምንታይ፤ እኛ ባለንበት የነፍጠኞች ገዥ መደቦች ቤተክርስቲያን አቋቁመዉ ሲያስቸግሩን ነበር። እድሜ ለኢህአዴግ መንግስታችን ይኸዉ ሃይማኖታችንን በነጻነትና በእኩልነት እንድናከብር፣ በአካባቢያችን ቀድሞ ተሰርተዉ የነበሩትን አብያተክርስቲያናትን እንድናፈርስና በአካባቢያችን ያሉትን ክርስቲያኖችን እንድናሳድድ፣እንድንበቀል፣ ተጽህኖ እንድናደርስ፣ ባለስልጣናትና ካድሬዎቻችሁ ጥሩ አድርገዉ ስለሰበኩን፤ ይኸዉም በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በጽሑፍ፣ በስብሰባ፣ በመንደርና በሰፈር ዉስጥ «ነፍጠኞች ወይንም አማሮች ወይንም ክርስቲያኖች የሆኑት የገዥ መደቦች ሃይማኖታችሁን፣ ባህላችሁን፣ ቋንቋችሁን ያጠፉባችሁና ወንዶቻችሁን በመስለብ፣ ሴቶቻችሁን ጡታቸዉን በመቁረጥ ግፍና በደል የፈጸሙባችሁና የገደሏችሁ መሆኑን እንድታቁ። አሁንም ይህን ሥርዓት ለመመለስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ስላሉ ዝም እንደትሉ።» በማለት ጎሲናችንን ስለመረዙትና ለበቀል ስላነሳሱት የፈለጋችሁትን ፍሬ በማፍራት ወደ ተግባር ለዉጠን በማሳየት ምን ያህል ከጎናችሁ እንደቆምን አስመስክረናል። ለወዲፊቱም በበለጠ ሁኔታ በቀድሞ ሥርዓት ዉስጥ የተመላለሱትን እንደምኞታችሁና ፍላጎታችሁ ብዙ እናሳያችኋለን።

*መንግሥታችንም ይህንኑ ታማኝነታችንን አይቶ ትልቅ ዉለታ የዋለልንን በዚሁ ለመግለጽ እንወዳለን። ይኸዉም የቀድሞ ነገሥታት ክርስቲያኖች ብቻ ተደርጎ ይቆጠር የነበረዉን ማስተካከያ እንዲደረግበት አድርጎና እዉነቱን አዉጥቶ የመጀመሪያ እስልምና እምነት የተቀበለዉንና ብሔራዊ ሃይማኖት ያደረገዉን ንጉሥ አልነጃሺን እዉቅና ሰቶልን ከተለያዩ ከአረብና ከአፍሪካ አገራት የእምነቱ ተከታዮች መተዉ በተቀደሰዉ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ አምልኮታቸዉን እንዲፈጽሙ በማድረጉ ነዉ። ሌላዉ ቀደም ያሉት አባት እንደገለጹት የተለያየ አምልኮታችንን በጋራ እንድንፈጽም በመደረጉና ለአምላኮቻችንም እዉቅና በመሰጠቱ በድጋሜ ለታላቁ መንግሥታችን ምስጋና እናቀርባለን።» በማለት እንድተናገሩ የተለመደዉ ጭብጨባ ሲቀርብ፤ ተናጋሪዉ ሰዓት ያለቀ መስሏቸዉ «ለወደፊት ደግሞ ብዙ የምንመሰክረዉ አለ» በማለት ንግግራቸዉን አቁመዋል።*

*በማስከተል ደግሞ የካቶሊክ ሃይማኖት ተወካይ « ይህች እለት እኛም የተመረጠችና የተቀደሰች ናት እንላለን። ታላቁ መንግሥታችን ባጎናጸፈን ዴሞክራሲና ነጻነት መብትና እኩልነት ይኸዉ የኦርቶዶክስ ምእመናን « ይህ የኛ ቤተክርስቲያን አይደለም ወይ? ዜማዉስ የኛ አይደለም? ሥርዓቱ የኛ አይደለም? አገልጋዮቹስ የኛ አይደለሙ ወይ?» ብለዉ እስከሚቸገሩ ድረስ ቤተክርስቲያናችንንና አምልኮታችንን በማመሳሰል ብዙ ነፍሳትን በቀላሉ መማረክ ችለናል። ምእመኑንም ከኋለ ቀር አለባበስ ለይተነዉ በዘመናዊ ደስ ባለዉ አለባበስ እንዲመላለስና የጾምና የጸሎት ሸክም አቅለንለት እንደ ሥጋዊ ፍላጎቱና ምርጫዉ አምልኮቱን እንዲፈጽም አድርገናል። መንግሥትም የኦርቶዶክስ አማኞችን በቀላሉ ወደ በረታችን ዉስጥ ለማስገባት እንድንችል መንገዱን በደንብ ስላመቻቸልን ዛሬም ዘወትርም እናመሰግነዋለን።» በማለት ንግግራቸዉን*

እንዳቀረቡ፤ የተለመደዉ ጭብጨባ ስለቀጠለ ለቀጣይ ተናጋሪዎች ማኅፀናቸዉ ከአምስት መቶ አመት በፊት ለፈለፈለቻቸዉ ለልጆቻቸዉ ለፕሮቴስታን ክፍልፋይ ድርጅቶች ተወካይ ሰተዋል::

ተወካዩም « እኛ የመንግሥታችንን ታላቅነት ለመናገር አንደበት ያጥረናል:: ብቻ ዝም ብለን «እጹብ፣ እጹብ፣ እጹብ» ብንል የሚቀል ይመስለኛል:: ለኛ ያወጣልንን ፀሐይ ለሌላ አልወጣም ብንል ማጋነን አይሆንብንም:: ዱሮ በቁጥር ይታወቁ የነበሩት የእምነት ድርጅቶቻችን አሁን እንደ አሜሪካ አገር ለቁጥር የሚታክቱ ድርጅቶች ተፈጥረዋል:: ዱሮ ለመግባት እንቸገርባቸዉ የነበሩ ክልሎችና ብሔር ብሔረሰቦች ክፍት ሆነዉልን እንዲሁም ዋና መሪዎች ሆነዉልን በአራቱም ማእዘን በተለያዩ ስያሜዎች ገብተን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን እያዳከምንና ምእመኑንም ከእናታችን ከካቶሊክ በላይ ወደ እኛ እያፈለስን እንገኛለን:: ምክያቱም እንኳን ምእመኑ አይደለም አገልጋዮቹ ሳይቀር በጾምና በጸሎት ስለተመረሩ፣ እንቅልፋቸዉን አተዉ በማገልገላቸዉ ነፍሳቸዉ እረፍት በማጣቷ እረፍት ስለምትፈልግ፣ ጥሩ መዝናኛ የሚፈልጉ ምእመናን ደግሞ በፈለጋቸዉ አለባበስ ከፈለጉ ደረትና ጡታቸዉን ገላልጠዉ፣ ከፈለጉ በተወጣጠረ ሱሪ መላ አካላቸዉን እያሳዩ፣ በመዝሙር የሚዘፍኑበትንና የሚጨፍሩበትን አዳራሽ ስለተዘጋጀላቸዉ፤ እንዲሁም እኛ ጋር መተዉ የሱስን ከተቀበሉ ምግባር ኖራቸዉ አልኖራቸዉ ስለ መጽደቃቸዉ ዋስትና ስለምንሰጣቸዉ፣ ባጠቃላይ ጠባቡን መንገድ አስወግደንና ንደን ሳይጨናነቁና ሳይጋፉ በሰፊዉ መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ ስለምናደርግ ምርጫቸዉን እኛን ንጹሀንንና ቅዱሳንን ስለሚያደርጉ ነዉ:: እንዲሁም በቀንና በሌሊት መንፈሳችንን ስለምንልክላቸዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ እኛ ይገባሉ ብለን እንገምታለን:: ለዚህ ነጻነትና እኩልነት ብቃት ላበቃን መንግሥታችን አሌ ሉዣ እንላለን::» በማለት ሲናገሩ የተለመደዉ ጭብጨባ ቀርቶ ሁሉም ሳያስቡት የተናጋሪዉ መንፈስ አሸንፏቸዉ «የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ ኦ የሱስ፣ ኦ የሱስ፣ ኦ የሱስ» እያሉ ለብዙ ደቂቃዎች እንደለፈለፉ የተወሰኑት መሬት ላይ ተንፈራግጠዉ «መንፈስ ተሞላን» በማለት ምስክርነትን ሰተዋል::

በማስከተል የባህላዊ እምነት ተከታዮች ተወካይ፤ «መንግሥታችን የአማልክቶቻችን ጸጋና በረከት ይድረሰዉ» በማለት ከመረቁ በኋላ «እኛ ለዘመናት አምልኮታችንን በስዉር በሽራኩቻዉ ተደብቀን ተሸማቀን ነበር ስንፈጽም የነበረዉ:: እድሜ ለዴሞክራሳዊ መንግስታችን ይኸዉ በየአደባባዩና በየወንዛወንዙ በግልጽ እዉቅና ተሰቶን አምልኮታችንን እንፈጽማለን:: «ባዕድ አምልኮ» እየተባልን ከሌሎች ሃይማኖቶችና አምላኮች ዝቅ ይሉ የነበረዉ አማልእክቶቻችን ይኸዉ አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ እየተከበሩና እየተመሰገኑ ናቸዉ:: ይኸም ባለ ጊዜ የመሆን እድል እንዳጋጠመንና የኛ መንፈስ የበላይነትን የተጎናጸፈ መሆኑን ያሳያል:: ሕዝቡም ከፈለገ በቤቱ በጨሌዉ ፣ በቦረንትቻዉ፣ በአርሲዋ እመቤት፣ በወሎ መጀን ፣ በታዬ ከራማ፣ በጠንቋዩ ፣ በአስማተኛዉ፣ በመተተኛዉ መንፈስ እየተለማመነ አምልኮቱን በነጻነትና እኩልነት በመፈጸም ላይ በመሆኑ ትልቋን ፀሐይ ለኛ በተለየ

ሁኔታ እንዳወጣችሁልን ነዉ የምናምነዉ። ለዚህም እንደ አማልክቶቻችን እግራችሁ ስር ወድቀን ብናመሰግናችሁ ደስ ይለናል» በማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩና በባለስልጣኖቹ እግር ስር ወደቁ።

<u>ወዲያ በቅናት የተቃጠለዉ የቀጥተኛዉ አዉሬ መንፈስ ተወካይ</u> « እናንተ ያለቦታዉ የወደቃችሁ ተነሱ» በማለት የባህላዊ እምነት ተወካዮችን እንዲነሱ ካዘዘ በኋላ <u>« በመጀመሪያ የጨለማዉ ገዥ ጌታችንን ዲያብሎስን እንድናመሰግን ሁላችሁም ተነሱ» በማለት ሲናገር ተሰብሳቢዎቹ የዲያብሎስ ስም በመጠራቱ ተደናግጠዉ ባሉበት ፈዘዙ። ወዲያዉ ተወካዩ « በእርግጥ እስከአሁን ድረስ በሥጋ የተገለጡ ወኪሎቻችንን ሲሆኑ ያዳመጣችሁት፤ ሁሉም የእኛን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ምስክርነትን ስለሰጡና ለመንግሥታችንም ታላቅ ምስጋናንና አድናቆትን ስላቀረባችሁ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስማችን እናመሰግናችኋለን።</u>

<u>ለወደፊት ደግሞ «ጎሊናችንን አንሸጥም፣ ከነፈነሰዉ ጋር አንነፍስም፤»</u> በማለት የኛ ተቀዋሚ በሆነዉ መንፈስ የሚመሩና «የምናመልከዉ አምላክ አንድ አምላክ ነዉ። እርሱም አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ የፍጥረታት ጌታና ፈጣሪ የሆነ ሁሉ በእርሱ ለእርሱ የተፈጠረ በአንድነትና በሦስትነት የሚመለክ አንድነቱንና ሦስትነቱንም የገለጸዉ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ በሆነዉ በመስቀል ላይ በተሰቀለዉ አምላክ በጌቶች ጌታ በነገሥታት ንጉሥ በሆነዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነዉ።» <u>በማለት የኛን የተለያዩ አማልክቶችን የሚቃወሙና የሱስን የማይቀበሉትን ምእመናንና አገልጋዮችን በግድም ይሁን በዉድ እንደ አሁኑ አይነት የምስክርነት አደባባይ አዘጋጅታችሁ አሁን የተሰጠዉን ምስክርነት እነሱም እንዲሰጡ አድርጉ።</u> ይህ ካልሆነ ግን በአጭር ጊዜ ዉስጥ በሥጋዊዉም ሆነ በመንፈሳዊዉም ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ስልጣናችሁ እንደሚሻርና ለሌላ ለተሻለ ብቃት ላላቸዉ ምርጥ ባለሟሎቼ ወንበሩን አሳልፌ እንደምሰጥ በታላቁ የግበር አባታችሁ ዲያብሎስ ስም እምላለሁ» ብዬ እኔ የጨለማዉ ገዥ ተሰወርኩ።

<u>በመቀጠል የአገሪቱ መሪ</u> «በእርግጥ ይህች ቀን የተመረጠች ብዙ ድንቃድንቅ ያልተጠበቁ ንግግሮችና ተአምራቶች የታዩበት ነዉ። ትንሽ የሚከብደዉ በመጨረሻ የታዘዝነዉን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ቢሆንም በአምስቱ ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የሽግግር ዓመት ዉስጥ ጉን ለጎን ተግባራዊ ለማድረግ እንድንችል እዚህ የተገኛችሁ ባለስልጣናትና የኢህአዴግ አባላት እንዲሁም አጋር ድርጅቶች፤የተለያዩ የሃይማኖትና እምነት ተወካዮች በጋራ መሰለፍ ይጠበቅባችኋል። ምክንያቱም ለህልዉናችን የመሪያችንን ፈቃድ ግድ መፈጸም አለብን። <u>ያለበለዚያ ከወንበራችን እንቆረጣለን። እንደመሰሳለን። መታሰቢያችንም ለዘለዓለም ይጠፋል። በመሆኑም እንደ በፊቱ ንግግሬ «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» የምል አይደለም። ተግባራዊ ለማድረግ የሞት ሽረት ልናደርግ እንደሚገባ ከልመና ጋር ነዉ የምማጸናችሁ።»</u> በማለት የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ የተለያዩ ባህላዊ እምነት ተከታዮች ተወካይ ዉይይቱ በምርቃት እንዲዘጋ በማድረግ በቤት ስራ ተለያይተዋል። እኔም የጨለማዉ ገዥ ትዕዛዜ ተግባራዊ እንደሚሆንና እንደማይሆን መጨረሻቸዉን እየተጠባበኩ ነዉ።»

***ይላል የጨለማዉ ገዥ አታላዩ በሰዉ ኀሊና በመንገሥ የዓመጻና የክህደት ስራ የሚያሰራዉ ሸዋጁ መንፈስ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ጋር በመሆን።»*** በማለት ቀርቧል

ከላይ የተገለጸዉ የእያንዳንዱን ሃይማኖትና የባህል እምነት ወክለዉ ያሉ ሰዎች፤ አሁን ካለዉ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት አራማጅ ከሆነዉ ከኢሕአዴግ መንግሥት ጋር ምን ያህል እጅና ጓንት ሆነዉ እየሰሩ እንዳለ የሚገልጽና ሕሊናቸዉን እንዴት አድርገዉ እንደሚሸጡ የሚያሳይ ነዉ። ይህም ድርጊታቸዉ የዲያብሎስ አገልጋይ መሆናቸዉን እንደሚመሰክርባቸዉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ በትዕቢትና በእብሪት ይደነፉ የነበሩት የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይላቸዉ እንደሚሰበርና ልምሾ እንደሚሆን ያሳየናል። እንዲሁም መታሰቢያቸዉ ለዘላለም እንዳይጠፋ፣ ከወንበራቸዉ እንዳይቆረጡና እንዳይደመሰሱ ከንቱ የሆነዉን ሥጋዊ መጠበብ አድርገዉ ትዉልዱ ሕሊናዉን እንዲሸጥ ባለሥልጣኖቻቸዉን፣ ካድሬዎቻቸዉን፣ ደጋፊዎቸዉን፣ እንዲሁም የተለያየ ሃይማኖት ተወካዮችን ከልመና ጋር እንዳሳሰቡ ነዉ። ይህ ማሳሰቢያቸዉ ተደርጎም፣ ተሰምቶም በማይታወቅ መልኩ ከዋናዉ ቤተመንግሥት ጀምሮ ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ በሞታቸዉ ሰበብ ትዉልዱ ሕሊናዉን እንዲሸጥ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ከሁሉም ሃይማኖቶች ዉስጥ ወደ ቤተመንግሥት ለማሳመን ከገቡት ዉስጥ የፕሮቴስታንቱ ተወካይ መንፈሳቸዉ ሁሉንም በዝረራ ያሸነፈና ተሰብሳቢዎቹ ቢፈልጉትም ባፈልጉትም ሳያስቡት በአንደበታቸዉ መንፈሱ እንዲሉ ያዘዘዉን ፈጽመዋል። በዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ወደ ምላሼ ከመግባቴ በፊት አንድ የምለዉ ነገር አለ። ይኸዉም እኔ በግሌ ማንም መንግሥት ሆነ ድርጅት እንዲሁም ቡድንና ግለሰብ አንዳች በደል ሆነ ግፍ አልፈጸመብኝም። በማንም ላይ አንዳች ጥላቻ ሆነ በቀል የለኝም። የዲያብሎስን ስራ ብቻ የምቃወምና ስራዉንና የእርሱን ፈቃድ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎችን የማጋልጥ ነኝ እንጂ የሥጋና የደም ስሜቴን አይደለም የምናገረዉ፣ የምጽፈዉ። የሥጋና ደሜ ስሜቴ የሚመራኝ ቢሆን ኖሮ፤ «ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በመናገሬ ሆነ በመጻፌ በእኔ ላይ ሆነ በቤተሰቤ ላይ ችግር ሊመጣብኝ ይችላል፤ ልታሰር፣ ልገደል እችላለሁ፤ ተቃዉሞ ሊመጣብኝና ጥቃት ሊደርስብኝ ይችላል፤» በሚል ስጋትና ፍርሃት እንዲሁም «ጥሩ ስራና ገቢ አለኝ፤ በሕይወቴና በኑሮዬ የተመቸኝና የተረጋጋዉ ደስተኛ ነኝ፤... ወዘተ» በሚል የራስ ወዳድነት ስሜት ተገድቤ እኖር ነበር እንጂ ለተለያየ ፈተናና መከራ የሚዳርገኝን የእግዚአብሔርን መልእክት በመጻፍ አላስተላልፍም ነበር።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ጥሪና አገልግሎት ላይ መሸነጋገልና ማስመሰል የለም። እንዲሁም ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተሰለፈ ቀርቶ አማኝ የተባለ ሳይቀር ራሱን እንዲክድና እንዲጠላ እርሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ በምድር በተመላለሰበት ወቅት በግልጽ አስተምሮናል፤ ነገሮናል። አሁን ያለዉ መንግሥት እንኳን በዚህ መልኩ ገበናቸዉ ተጋልጦና ፍጹም የዲያብሎስ አገልጋዮች መሆናቸዉ ተመስክሮባቸዉ አይደለም፤ «ሕሊናዬን እልሸጥም» የሚለዉንና እንዲሁም ስለ እዉነት የሚናገረዉን፣ የሚጽፈዉን ሰዉ የሐሰት መረጃ በማቀነባበርና ሐሰተኞች የሆኑ ሕሊናቸዉን

የሸጡ ዳኞች በወንበር ላይ እያስቀመጡ ስንቱን ኢትዮጵያዊ በእስር፣ በድብደባ፣ በግድያ፣ በማሳደድ፣ በማስቃየት፣ በማፈናቀል፣ ባጠቃላይ በተለያየ መንገድ በመበቀል ዉስጥ እንዳሉ ዓለም ያዉቀዋል:: እኔም የዲያብሎስ እንደራሴ በተባሉ መሪዎች፣ ባለሚል በተባሉ ባለሥልጣናት፣ ዉዶች በተባሉ ካድሬዎች፣ እንዲሁም በደጋፊዎቻቸዉና በሥርዓቱ ተጠቃሚ ሰዎች እንደምጠላ፣ ተቃዉሞና ጥቃት እንደሚደርስብኝ፣ ከዚያም ባለፈ ለእስር ሆነ ለግድያ እንደሚፈልጉኝ ባዉቅም፤ ስለ እግዚአብሔር እዉነትና ስለ ቅዱሱ ኪዳን ራሴን በመካድና በመጥላት ነዉ በምንሰፈሰፍላቸዉና በማፈቅራቸዉ ቤተሰቤ ላይና ምኑንም በማያዉቁት ሕፃናት ልጆቼ ላይ ፈርጄ ለእግዚአብሔር የእዉነት አገልግሎት የተሰለፍኩት:: ስለ እዉነት  አገልግሎቴ የሚመጣብኝን ማንኛዉንም ፈተናና መከራ በጸጋና በአኮቴት ለመቀበል ነዉ ራሴን ያዘጋጀዉት:: ምክንያቱም ማንኛዉም ሰዉ ተፈቅዶለት ቢጎዳኝ፤ ሊጎዳዉ የሚችለዉ ይህን የተገለጽኩበትን ለአፈርና ለምስጥ አስረክቤ የምሄደዉን ቅርፊት ሥጋ ነዉ እንጂ ሕያዉ የሆነች ነፍሴን አንዳች ሊያደርጋት አይችልም:: በሥጋዬ ላይም ቢሆን እርሱ እግዚአብሔር ካልፈቀደላቸዉ በስተቀር አንዲቷን ጠጉሬን እንኳ መንካት አይችሉም::

**ወደ ጥያቄዉ መልሽ** ስገባ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰዉ የሚያዉቀዉና የሚገመግመዉ በአንደበቱ አስመስሎ በሚናገረዉና በባዶ ሕይወት ራሱን አመጻድቆ በሚቀርበዉ አይደለም:: ለእዚህም ነዉ በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ የዉስጣቸዉ ገበናን ለዓለም የገለጸዉና ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ትዉልዱ እንዲያዉቃቸዉ ያደረገዉ:: እንደ ሰዉ ማስመሰልማ ስንቱ ዓመፀኛና ከሃዲ እንዲሁም ርኩሰት ፈጻሚና አስፈጻሚ ታላቅ፣ ቅዱስ፣ ጀግና፣ ሰማዕት፣ እዉነተኛ፣ ቅን ተብለዋል:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተገምግመዉ ርኩሳንና ዓመፀኞች መሆናቸዉ ተመስክሮባቸዋል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ስለ እዉነት በመመስከራቸዉና በመኖራቸዉ «ዓመፀኛ፣ ከሃዲ፣ ሐሰተኛ፣ ኃጢአተኛ» የተባሉ፤ በእግዚአብሔር ዘንደ ተገምግመዉ ታላቅ፣ ቅዱስ፣ ሰማዕት፣ ጻድቅ መሆናቸዉ ታዉቋል::

የሁሉም ሃይማኖት ተወካዮች ለሆዳቸዉና ለጥቅማቸዉ ያደሩ መሆኑን ታይቷል:: በተለይ የፓርትያርኩ ተወካይ አቶ መለስ እንኳ በግልጽ «ኢሕአዴግ የመላእክት ስብሰብ አይደለንም» እያሉ፤ ተወካዩ ግን ሕሊናዉን የሸጠ ነበርና በተለመደዉ የማስመሰልና የሽንገላ ንግግር «መንግሥታችን የመላእክት ስብስቦች የሞሉበት ነዉ» ብል ማጋነን አይሆንብኝም::» በማለት ንግግራቸዉን የጀመሩት:: ይህም የሚያሳየዉ በባዶነትና በማስመሰል ሕይወት የሚመላለሱት አስመሳይ አገልጋዮች እያወደሱና እያስመሰሉ ነዉ የሌብነት፣ የግፍ፣ የዓመፃ፣ የርኩሰት ተግባር እየፈጸሙ ያሉት:: ለዚህም ነዉ የፓትርያርኩ ቀኝ እጅ ሆነዉ ከታች እስከ ላይ ያሉ አስመሳይ አገልጋዮች እዉነተኛ አገልጋዮችንና አማኞችን ለማስፈራራትና ተጽህኖ ለማሳደር በተንቀሳቃሽ ስልካቸዉ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከፕሬዘዳንቱ፣ ከሚኒስትሮች፣ ከተለያዩ ባለሥልጣን፣ ከደኅንነት ኃላፊዎች ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳላቸዉ በማስመሰል ጉራቸዉን የሚነዙትና ስልክ እያስደወሉ «ልጆችህን አርፈህ ብታሳደግ ይሻልሃል:: በእኛ ስራ ጣልቃ ብትገባ፣ ገበናችንን ብታጋልጥ፣ ለስራችን እንቅፋት ብትሆን እርምጃ እናስወስድበሃለን» እያሉ በማስፈራራት የቅድስት ቤተክርስቲያን ገንዘብና ሀብት የሚዘርፉትና የሚያዘርፉት:: ደኅንነት የተባለዉም የሚሰጠዉን ፍርፋሪ(ጉርሻ) በልቶ ከዓመፀኞቹ(ከሌባዎቹና

ከልክስክሶቹ) ጋር ተቀናጅቶ እዉነተኛ አገልጋዮችንና ምእመናን ይወነጅላል፣ ያሳድዳል፣ ያስደበድባልያ፣ ያሰድባል፣ ያሳስራል፣ ከባሰም ያስገድላል። በዚህ መልኩ ነዉ የማፊያ ቡድኖችና የመንግሥት ተጠሪዎች በእዉነተኞች ላይ ግፍና በደል የሚፈጽሙት።

ሌላዉ የፕሮቴስታንቱ ተወካይ <u>«እኛ የመንግሥታችንን ታላቅነት ለመናገር አንደበት ያጥረናል። ብቻ ዝም ብለን «እጹብ፣ እጹብ፣ እጹብ» ብንል የሚቀል ይመስለኛል። ለኛ ያወጣልንን ፀሐይ ለሌላ አልወጣም ብንል ማጋነን አይሆንብንም። »</u> ማለታቸዉ የአቶ መለስ ወይንም የሕወሓት ወይንም የኢሕአዴግ መንግሥት በተለየ ሁኔታ ባለጊዜ እዳደረጋቸዉና በዉጭዉ የነገሠዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ የበላይነት እየተጎናጸፈ መሆኑን ነዉ። ወደ ቤተመንግሥት ከገቡት የተለያየ ሃይማኖት ተወካይ የፕሮቴስታንት ተወካዩ ሁሉንም እንደዘረሩ ይኸዉም የኢትዮጵያ ተጠሪ መንግሥት ሆነዋል። ይህም እግዚአብሔር አምላክ በስሙ የሚነግዱትን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ስም የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ላይ ዓመፃና ክህደት የፈጸሙትን አስመሳይ አገልጋዮችንና አማኞችን ለማሳፈር ሲል ያደረገዉ ነዉ። አሁንም በቅዱሱ ኪዳን ላይ በዓመፃና በክህደታቸዉ ከጸኑ «እግዚአብሔር ሆይ ስለ ዓመፃና ክህደታችን ይቅር በለን፣ ስለቅዱሱ ኪዳን ስትል ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ተዋሕዶ የሚመራበትን ሰማያዊ ሥርዓትህን(መንግሥትህን) መልስልን?» እስኪሉ ድረስ ለሌላ ለተለየዉና ለባሰዉ እንዲሁም ለሚቀጣቸዉ ወንበሩ ተላልፎ ሊሰጥና ሊቀጡበት ይችላሉ።

አቶ ኃይለማርያም፤ በማርያም ስም ተጠርተዋልን በማርያም ኃይል ወደ ወንበር እንደመጡ ወይንም በጨለማዉ ገዥ ኃይል እንደመጡ ወደፊት እጅግ በቅርቡ የምንመለከተዉ ይሆናል። ምክንያቱም «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ ላይ በኢትዮጵያ ምድር የተለየ መድረክ ተፈጥሮ ዉይይት በተካሄደበት ወቅት ከሰሜን ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ፣ ከምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከምስራቅ ኢትዮጵያ ከመጡት የተለያዩ ተወካዮች ዉስጥ ወደ ልቡ ተመልሶና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ የኢሕአዴግን ተንኮልና መሰሪ ተግባር የገለጸዉ፣ እንዲሁም ስለ እዉነት የመሰከረዉና ራሱን ለእዉነት አሳልፎ የሰጠዉ ብቸኛ ተወካይ ሰዉ የደቡብ ተወካይ ስለነበረ፤ ምናልባት ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ያንን ሰዉ የሚወክሉት እሳቸዉ ከሆኑ በማርያም ኃይል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ወደ ወንበር እንደመጡ ይታመናል። ያ ሰዉ(ያ የተመረጠዉ የደቡብ ኢትዮጵያ ሰዉ) ሌላ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በጨለማዉ ገዥ አማካይነት እንደወጡ ይገመታል።

ሌላዉ ለማስታወስ የምፈልገዉ «የኢሕአዴግን አቋም እንኳን ምድራዉያን ሰማያዉያንም ማስለወጥ ሆነ ማንበርከክ አይችሉም፤» ባሉት በትዕቢትና እብሪት አቋማቸዉ ከጸኑ ደግሞ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ትዕቢተኞችና እብሪተኞች የደረሰባቸዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሊደርስባቸዉና ከወንበራቸዉ ሊቆረጡ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ «ዘላለማዊ ክብር ለመለስ»ና « እስከ ወዲያኛዉ ይታሰባል» ማለታቸዉ ራሳቸዉን እንደ እግዚአብሔር ወይንም እንደ እግዚአብሔር እንደራሴ

ያስቆጠሩበት  አቋም መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን፤ የእግዚአብሔር እዉነታ ግን «የኃጥአን መታሰቢያ ለዘላለም ይጠፋል» ነዉና የሚለዉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳንና በተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ሁሉ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ መታሰቢያቸዉ ለዘላለም የሚጠፋና የሚደመሰስ መሆኑን እንዲያዉቁት በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ:: በሌላ በኩል ደግሞ «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነዉ» እንደተባለ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽመዉና አስፈጽመዉ የሄዱ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ለዘላለም ይታሰባሉ፣ ይከበራሉ::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: ከላይ የእስልምና እምነት ተወካይ በስተመጨረሻ ላይ «ለወደፊት ደግሞ ብዙ የምንመሰክረዉ አለ» በማለት ሰምና ወርቅ የተላበሰ ትንቢታዊ ንግግር የተናገሩ መስሎኛልና በዚህ ላይ አስተያየት ቢሰጡን?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: እግዚአብሔር ካለ ምክንያት ሁለቱም አባባሎች እንዲቀርቡ አላደረገም:: ሕወሓት(ኢሕአዲግ) የተባለዉ መንግሥት ወደ ወንበር ላይ እንደመጡ ወዲያዉ ነዉ በዉስጣቸዉ የነበረዉን የበቀል ተግባር ሻዕቢያ ከሚባለዉ ቡድን ጋር ተቀናጅተዉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ክርስቲያኖችን ወይንም ዐምሐራዎችን በአራቱም ማእዘን ለመበቀል ተሰልፈዉ በእስልምና እምነት ዉስጥ ያሉትን ወገኖች «እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሐራዎች) ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ እምነታችሁን ያጠፉና የለወጡ ናቸዉ:: ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል» በማለት ሕሊናቸዉን መርዘዉ ክርስቲያኖች(ዐምሐራዎች) እንዲጨፈጨፉ፣ እንዲፈናቀሉ፣ እንዲሰደዱ፣ የተለያየ መከራ እንዲደርስባቸዉ፣ አድሎና በደል እንዲፈጸምባቸዉ፣ ቤተክርስቲያናቸዉ እንዲቃጠል አስደርገዋል::

ታዲያ እግዚአብሔር ለዚህ ድርጊታቸዉ ዋጋ የሚያስከፍልበት የራሱ ጊዜ አለና የሥልጣን ዘመናቸዉን ለማስረዘምና በቀላቸዉን ለማስፈጸም የፈጠሩት የጥላቻ ፍሬ መራራ ቢሆንም፤ ወደ ራሳቸዉ መምጣቱና መጠጣታቸዉ እንደማይቀርና እንደሚታይ ነዉ የሚያሳዉቀን:: መቅጫ ሆነዉ ሊታዘዙባቸዉ ይችላል:: የአገሪቱ መሪ ሆኑ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች  ከዚህች ምድር አልፈዉ ወደሚጠብቃቸዉ ቦታ መሄዳቸዉ ለማይቀረዉና ከተቆረጠባቸዉ ቀን ለአንድ ቀን እንኳ እድሜያቸዉን ማስረዘም የማይችሉ ተራና ደካማ ፍጡር መሆናቸዉን እያወቁ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ ለከፋዉ ቅጣት የሚዳርጋቸዉን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ስራ ሰርተዉና አሰርተዉ መሄዳቸዉ  እጅግ ያሳዝናል፤ ያስተዛዝባል!:: ምክንያቱም በምድር ሆነ በሰማይ የሚጠብቃቸዉ ስቃይና መከራ እጅግ የባሰ ስለሆነ፤ እንደኔ ባይወለዱና ይህን የዓመፃ ተግባር ባይፈጽሙ ይሻላቸዉ ነበር እላለሁ::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: እዚህ ላይ ከተሰብሳቢዎቹ የሃይማኖት ተወካይ ጋር እንደ ሃይማናት አባት ተቆጥረዉ የቀረቡትና የኢሕአዴግን መንግሥት ሲያገኑ የነበሩት የባህላዊ እምነት ተከታዮች እነማን ናቸዉ::

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: እነዚህ የባህል እምነት ተከታዮች የሕወሓት(የኢሕአዴግ) መንግሥት ከግንቦት ፳፥፲፱፻፹፫ (20/9/1983) ዓ.ም ወዲህ የኢትዮጵያን ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማዳከምና ክርስትናን እንደ ምስጥ ዉስጥ ዉስጡን በመቦርቦር ባዶ ለማስቀረት የፈጠራቸዉ በተለያየ ባዕድና ጣዖት አምላኮ የሚመላለሱ ናቸዉ:: የሰዉ ሕሊና እንዲቀበለዉም በተለያየ መገናኛ ብዙኃን ሽፋን እየተሰጣቸዉ በወንዛወንዙና በየዛፉ እንዲሁም በተለያየ ቦታ ባዕድ አምልኮዋቸዉን ሲፈጽሙ እንደ ትክክለኛ አምልኮ በማሳየት ትዉልዱን በማለማመድ ላይ ይገኛሉ:: የሚያስገርመዉና የሚያሳዝነዉ ካድሬ የሆኑ ባለመስቀል ካህናት ጭምር የሃይማኖት ሴሰኞች ሆነዉ ርኩሰቱን ይባርካሉ:: እንደ ትክክለኛ አምልኮ እንዲቆጠርም ትምህርት ይሰጣሉ:: ታዲያ ይህ ድርጊታቸዉ የከፋዉን መቅሰፍት ነዉ የሚያመጣባቸዉ እንጂ ለሥጋቸዉም ለነፍሳቸዉም አይጠቅምም:: ምናልባት የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎች ባለጊዜ በሆኑበት ወቅት የተለየ ሥጋዊ ጥቅም አግኝተዉበት ይሆናል:: የርኩሰት ባለጊዜነት ሲሻር ደግሞ በሥጋቸዉም በነፍሳቸዉም በምድርም በሰማይም ዋጋ የሚከፍሉበት(የሚቀጡበት) ይሆናል::

አሳዛኙና አስገራሚዉ ነገር በተለያየ ክፍልፋይ እምነት ዉስጥ ሆነ በተለያዩ ባህላዊ ባዕድ አምላኮ ዉስጥ የሚመላለሰዉ ሰዉ በእግዚአብሔር በፈጣሪ ስም ነዉ የሚነግደዉ እንጂ «እኔ ዲያብሎስን ወይንም ሰይጣናትን ነዉ የማመሰግነዉ፣ የማመልከዉ » አይልም:: ምክንያቱም በዚያ የክህደት፣ የጥርጥር፣ እንዲሁም የርኩሰት እምነትና አምልኮ ላይ ሰዎች እንዲሳተፉና እንዲያገለግሉ እንዲሁም ሕሊናቸዉ በቀላሉ እንዲቀበልና ጥፋት አድርገዉ እንዳይቆጥሩት ለማድረግ ነዉ:: እዉነታዉ ግን የጨለማዉ ገዥ(ርኩሳን መናፍስት) በመንፈሳቸዉ በእያንዳንዱ የእምነቱ አራማጅ ሕሊና(አእምሮ) ዉስጥ በማደር የእያንዳንዱን አገልጋያቸዉን አንደበት አንደበታቸዉ አድርገዉ በመጠቀም ነዉ ዓመፃዉን፣ ክህደቱን፣ ርኩሰቱን እንደ እምነት በማስመሰል ትዉልዱን ለሞት ሞት የዳረጉት

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ በገጽ194 ላይ:

« __በቅርቡ በዓለም ላይ ሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሃዲያንና የዓመፅ ሰዎች ለጥቂት ወቅት ባለ ጊዜ መሆናቸዉና የእግዚአብሔር ቁጣ ሆነዉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ በዓመፃቸዉ የተቀመጡትን ከወንበራቸዉ ለመቁረጥና ዋጋ ለመክፈል መመጣታቸዉ አይቀርም__:: ይህም የዓመፃ ልጆች በእግዚአብሔርና በእዉነተኛ አገልጋዮቹ እንዲሁም አማኞቹ ላይ የፈጸሙት በደልና ግፍ፣ ክህደትና ዓመፃ በዚህ ምድር ዉስጥ ጭምር ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል እንዲያዉቁና ተራና አቅመ ቢስ መሆናቸዉን ለማሳወቅ ነዉ እንጂ የሚጸና አይደለም:: እነሱም የዓመፃና የግፍ ጽዋቸዉ ሲሞላ እግዚአብሔር ስለተመረጡት አገልጋዮቹና ሕዝቦቹ ሲል በመለኮታዊ ቁጣዉ እንዳልነበሩ ያደረጋቸዋል:: ስለዚህ ማንም ሰዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሆነዉ ከሚመጡት ከተከታዮቹ የዓመፃ ልጆች ጋር ህብረትና አንድነት እንዳይፈጥር ከአደራ ጭምር አሳስባችኋለሁ:: በምድርም በሰማያም ዋጋ ለማግኘት የሚፈልግ ሰዉ ሁል ጊዜ አንድነቱና ህብረቱ ከእዉነት ጋር ብቻ ማድረግ ነዉ የሚጠበቅበት::» የሚል አለ::

**እኝህ የእግዚአብሔር አገልጋይና ባለሟል እግዚአብሔር ለመረጣቸዉ በእስልምና እምነት ዉስጥ ላሉ እህቶቻችን እንዲናገሩ ያደረገዉን እኔም ሆንኩ ሌሎች መልእክቱን ማስተዋል ስለከበደን ቢያብራሩልን?**

*<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: አሁንም የምለዉ እግዚአብሔር ያናገረዉን ማወቅ ሆነ ማስተዋል የሚቻለዉ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ሲገልጽልን ብቻ ነዉ፡፡ እኔም በተረዳዉት መልክ ነዉ የምነግራችሁ እንጂ ከሃዲያን እነዚህ ናቸዉ፣ የዓመፅ ሰዎች የተባሉት እነዚህ ናቸዉ ለማለት አልችልም፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የእግዚአብሔርን መልካም ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ አይደሉም፡፡ ለመቅጫ ነዉ ባለ ጊዜ የሚሆኑት፡፡ ልክ እንደ «ጉዲት» እንደተባለችዉ ዮዲትና እንደ ግራኝ አህመድ ክህደትን እንዳስፋፉት፣ እንደ ደርግ(ኢሠፓ) ዓመፃንና ክህደትን እንዳስፋፉት፣ እንዲሁም እንደ ሕወሓት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋትና በቅዱሱ ኪዳን በተዋሕዶ ሃይማኖት ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን እንዳነገሡት ከሃዲያንና ዓመፀኞች ሰዎች እንደሆኑ ነዉ የምገምተዉ፡፡ በሁለት መልክ ስለተገለጹ ለእግዚአብሔር ቁጣነት አንድነት ፈጥረዉ ቢሰለፉም ዓላማቸዉና ሐሳባቸዉ የተለያየ መሆኑን ነዉ የሚያሳዉቀን፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ ባለጊዜነታቸዉ ለቀናት ወይንም ለወራት እጅግ ቢበዛ ደግሞ ለዓመታት ቢሆን ነዉ እንጂ የሚጸና አይደለም፡፡ ምክንያቱም በቅዱሱ ኪዳን ላይ እጅግ ክህደትና ዓመፃ ስለሚፈጽሙ እድሜ አይኖራቸዉም፡፡ የክህደትና የዓመፃ እንዲሁም የርኩሰት ጽዋቸዉ እንደሞላ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ቁጣ በተለያየ መንገድ ከባለጊዜነታቸዉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይሻራሉ፤ ይጠረጋሉ፡፡ ለዚህም ነዉ ማንም ይሁን ማን ለአጭር ጊዜ ባለ ጊዜ ከሚሆኑት ከቀጣዮቹ ከክህደትና ከዓመፃ ልጆች ጋር አንድነትና ኅብረት እንዳይፈጥ ምክር የተለገሰዉ፡፡»* **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለሚመለከተዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ዘጠኝ

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ ስምንት በገጽ 330 ላይ ከኑሮ ዉድነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ ቀርቧል:: ይኸዉም:

«በኑሮ ዉድነት የተማረሩና ለመኖር የተቸገሩ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ቅሬታቸዉን ለአገሪቱ መሪና ለከፍተኛ ባለሥልጣናት እንዱሁም ለዉጭ መንግስታት አቀረቡ:: ይኸዉም «እኛ ኢትዮጵያዉያን በችግርና በችጋር እንድንኖር የተፈረደብን አስኪመስል ድረስ በየወራቱና በየቀናቱ መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ ዋጋቸዉ እየጨመረ መሄዱና ለተወሰነ ቀን የዋጋ ተመን ቢወጣም ወዲያዉ ተሸሮ፤ በቀል በሚመስል መልኩ ዋጋቸዉ በእጥፍ እጥፍ ጨምሮብናል:: ለድሀ የሚያስብ አካል ካለ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጠን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን::» በማለት በኀዘንና በለቅሶ ብሶታቸዉን አቅርበዋል::

ለጥያቄያቸዉ የአገሪቱ መሪና ከፍተኛ ባለስልጣናት ምላሻቸዉን በሚከተለዉ መልክ ሰተዋል: «እኛ ጥቂቶች አገሪቱንና ሕዝቡን እንደፈለግነዉ ማሽከርከር እንደምንችለዉ ሁሉ በንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቂቶች ነጋዴዎች እንዲሁ ንግዱን እንደፈለጉት ማሽከርከር ችለዋል:: እኛ ኃይላችን ከእነሱ በላይ የሆነ መስሎን የዋጋ ቁጥጥር ለማድረግ ሙከራ ያደረግን ሲሆን፤ ያልጠበቅነዉ መልስ ምት ስለተሰጠንና ጠንከር ያለ ስለሆነብን ለሥልጣናችንና ለሕልዉናችን አደጋ ስለሆነ ወዲያዉ ነዉ እጅ የሰጠነዉና አቅማችን ወደሚችለዉ ሕዝብ ዞር ያልነዉ:: <u>ምክንያቱም እናንተ አቅማችሁንና ልባችሁን ስለምናዉቅ ምረጡን ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ የምትመርጡን፤ ለድጋፍ ዉጡ ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ ስለምትወጡልን፣ እንዲሁም ተቃወሙልን ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ ስለምትቃወሙልን እንደልባችን ስለሆነችሁልን በስልጣናችንና በህልዉናችን ላይ አደጋ የማታመጡ ምስኪኖች በመሆናችሁ ከጥቂት ኃያላን ነገዴዎች ጋር ከመጣላትና ያላሰብነዉ ጣጣ ከማምጣት ሸክም የምታቃልሉልን ሰፊዉ ሕዝብ የዋጋ ንረቱን ቢሸከም ያዋጣናል በሚል እምነት ነዉ:: በመሆኑም እስከአሁን ለምስጋናዉ የዘገየን ቢሆንም በዚሁ አጋጣሚ ስለመልካም አሽካከማችሁ ምስጋናችንን እናቀርባለን::</u> ለወደፊት ደግሞ የአሸላለም ሁኔታዉን በመቀየር ይኸዉም ባለጸጎችን በየክልሉ ስንሸልምና ስናገን እንደነበረ ሁሉ ለወደፊት ደግሞ የዋጋ ንረቱን በብዛት በመሸከም የሚታወቀዉን ሰፊዉ ሕዝብን እንሸልማለን:: ስለዚህ የሚሻላችሁ ያንቺን ሽልማት ለማግኘት የሚመጣባችሁን ሸክም ሁሉ ታግሳችሁ መሸከም ነዉ:: እዚህ ላይ በምስጢር ያዙት እንጂ አንዳንዶቱን ነጋዴዎች በተለያየ መልኩ የምንበቀላቸዉ መሆኑን በዚሁ አጋጠሚ እናሳዉቃችኋለን::» በማለት መልስ ሰተዋቸዋል::

**ከላይ የሚገልጽልን የአገሪቱ መሪ ሆኖ ከስራቸዉ ያሉት ባለሥልጣናት በሕዝብ ላይ ምን ያህል እንደሚያላግጡና ንቀታቸዉን፣ ትዕቢታቸዉን፣ ትምክህታቸዉን ነዉ የሚያሳየን:: አሁን ደግሞ በሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ምትክ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ተተክተዋል:: የተለየ ለዉጥ ይመጣል ብለዉ ያስባሉ?**

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: በአገራችን አንድ የተለመደ አባባል አለ:: ይኸዉም «ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም»:: ይህን አባባል ያቀረብኩት ኢሕአዴግ በጨለማዉ ገዥ መንፈስ ተለክፏል ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር መልእክቱን በተለያየ መንገድ እያቀረባላቸዉ እንዲሁም ተአምሩን እያሳያቸዉ እስከ አሁን ድረስ ሕሊናቸዉ እንደደነደነና በዚያዉ በአቶ መለስ አስተሳሰብ እንደጸኑ ነዉ:: አቶ መለስንም እንደ አምላክና አማልክት ነዉ የሚመለከቷቸዉ:: በእነርሱ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት፤ ቤተክስቲያን፣ ታቦት የሚባል የለም እንጂ እንደ ቅዱስ ተቆጥረዉ ታቦት ቢቀረጽላቸዉና ቤተክርስቲያን በስማቸዉ ቢሰየም ደስታዉን አይችሉትም ነበር:: ፓትርያርኩም በአንድ ላይ ተጠሩ እንጂ «ለአቶ መለስ በቤተክርስቲያን አንድ ነገር መታሰቢያ ይሰራለት» ከማለት ወደ ኋላ አይመለሱም ነበር:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ተአምራዊ አሰራር አንዳቸዉ ለአንዳቸዉ አንዳች ነገር እንዳይሰሩና እንዳይፈይዱ በአንድ ላይ ተጠሩ::

***ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ*** በጥቅምት፮÷፳፻፭ (6/2/2005) ዓ.ም በተወካዮች ምክር ቤት በተደረገዉ ስብሰባ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የአቶ መለስ ዜናዊ ግልባጭ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ መሆናቸዉን አስተዉለናል:: ይህም አቶ መለስ ዜናዊ በራሳቸዉ አምሳያ የመቅረጽ ብቃት እንደነበራቸዉ ልንረዳ ችለናል:: ከዚህ አንጻር አንዳች የተለየ ነገር አንጠብቅም:: ምክንያቱም በበላይ የሚመራቸዉ ሸዋጁ የዲያብሎስ መንፈስ፤ የዲያብሎስ መንፈስ እንደ መንፈስ ቅዱስ አንድ ቢሆንም አገላለጡ ግን እንደ ሰዉየዉ ሕይወትና ብቃት ይለያያል:: የሽንገላ፣ የማስመሰል ንግግራቸዉ ያዉ እንደ አቶ መለስ ዜናዊ ነዉ:: በዚህም ምክንያት ንግግራቸዉና አቀራረባቸዉ ሊለያይ ቢችልም ዓላማቸዉና ግባቸዉ አንድና አንድ ነዉ:: ይኸዉም የጨለማዉ ገዥን ፈቃድ በአራቱም ማዕዘን መፈጸምና ማስፈጸም ነዉ:: ነገር ግን እጅግ በቅርቡ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ሊፈጽሙ ይችላሉ ብለን እንግምታለን:: ምክንያቱም በመጽሐፈ ምሳሌ በምዕራፍ 14 ቁጥር 12 ላይ «ለሰዉ ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነዉ::» ይላል:: ይህን የሚያስተዉሉበት ዓይነ ሕሊናቸዉ ከተከፈተላቸዉ ቅን የመሰለችዉን የሞት መንገድ አብዮታዉ ዲሞክራሲ እምነት ምን እንደሆነች ስለሚያስተዉሉ አንቅረዉ በመትፋት ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔር እምነት ሊሰለፉ ይችላሉና::

የኢሕአዴግ መንግሥትና አባላቱ በሕዝብ ላይ አላጋጭ መሆናቸዉን የሚያሳየን ደግሞ ሕዝቡ በችግርና በድህነት እየማቀቀ «ይህ ችግርና ድህነት የእድገት መገለጫ ነዉ፤ ኢኮኖሚያችን ከአስር አኃዝ በላይ ማደግ ስለቻለ ነዉ ... ወዘተ» እያሉ በመግለጻቸዉ ነዉ:: የሚጠየቁት ሌላ ምላሻቸዉ ሌላ መሆኑን ለማሳየት ከላይ ስለ ኑሮ ዉድነት ሲጠየቁ « **<u>በዚሁ አጋጣሚ ስለመልካም አሸካከማችሁ ምስጋናችንን እናቀርባለን</u>**» ብለዋል:: አሁንም አቶ ኃይለ ማርያም ስለ ስለሃይማኖት ሲጠየቁ መንግሥት የሰራዉን የተንኮልና የመሰሪነት ተግባር ሕሊናቸዉ እያወቀ «መንግሥት በሃይማኖት ዉስጥ ጣልቃ አይገባም:: በዚህም መሰረት ሕዝበ ሙስሊሙ በጠየቀዉ ጥያቄ መሰረት ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሳዊ ምርጫ አድርጎ የሚመሩትን መርጧል:: በዚህ አጋጣሚ ለሕዝበ ሙስሊሙ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ» ብለዋል:: ዓለም እንደሚያዉቀዉ አማኙ ሕዝብ የወከላቸዉን ሰዎች እምነታቸዉ ምንም ይሁን ምን፣ ዓላማቸዉ ምንም ይሁን ምን «እዉነተኛ የሃይማኖት ሰዎች

ከመንግሥት ካድሬነት ነጻ የሆኑና መልካም ስነምግባር ያላቸዉ በነጻነት እንምረጥ» በማለታቸዉ እስር ቤት ታጉረዉና ሌሎቹም ማስፈራሪያ ደርሶባቸዉ እንዲሁም እየተደበደቡና እየተሰደዱ እያለ መንግሥት በበላይነት የእርሱን ስራ አስፈጻሚዎች በአራቱም ማዕዘን ማስመረጡ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በእዉነተኛ አማኙ ላይ ሲያላግጡ «እንኳን መሪዎቻችሁን በነጻና በዲሞክራሲ መንገድ ለመምረጥ በቃችሁ» ብለዋል፡፡ ይህም የሚያሳየን ሌላዉ መለስ ዜናዊ ናቸዉ ማለት ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ ሌላዉ በዚሁ ምዕረፍ በገጽ 331 ላይ በሌላ ጊዜ ደግሞ ነጋዴዎች ባሉበት በማወያየት ነጋዴዎች ሐሳብ እንዲሰጡበት ተደርጋል፡፡ ይኸዉም፡

«እኛ ነጋዴዎች ምን እናድርግ? በዚህ በተጨካከነ ሕይወት እንድንኖር ያደረገን ብልጡና መሰሪዉ መንግሥት ነዉ፡፡ እነሱ ያላቸዉ ሀብትና ንብረት በቂ ሆኖ ሳለ «አልጠገብንም» በማለት የአገሪቱን ሀብትና ንብረት ሲበዘብዙና ሲቀራመቱ እንዲሁም ለግል መጠቀሚያቸዉ ሲያደርጉ፤ የሕዝቡ በድህነት አረንቋ ዉስጥ መሆንና መቸገር አንዳች ስሜት ያማይሰጣቸዉ ጨካኝ በመሆናቸዉ፤ እኛም የእነሱን ፈለግ ተከትለን ነዉ ራሳችንን ብቻ የምናበለጽግበትና ለልጅ ልጆቻችን ብቻ የሚተርፍ እንዲሁም ከሁሉ በላይ ለመሆን ካለን የስግብግብነትና የራስ ወዳድነት ጠባይ የተነሳ ነዉ በአጭር ዓመታት ዉስጥ ከሁሉ በላይ የሆነ ሀብትና ንብረት ለማከማቸትና ምኞታችንን ለማሳካት ስንል ትርፋችንን እጥፍ በእጥፍ የምንጨምረዉ እንጂ እኛ የምንበላዉ፣ የምንጠጣዉ፣ ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ አተን አይደለም፡፡» በማለት ተናግረዋል፡፡

የዉጭ መንግስታት ተወካይ የሕዝቡንም የነጋዴዉንም አስተያየት ካዳመጡ በኋላ «ይህ ዴሞክራሳዊ ጥያቄያችሁ ተገቢ ቢሆንም፤ ይህ ችግር የመጣባችሁ ከልማታዊ መንግስታችሁ ጉን በጋራ ተሰልፋችሁ መስራት ካለመቻላችሁና ነጻ የኢኮኖሚ ግብይት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙ በደንብ ስላልገባችሁ ነዉ፡፡ ይኸዉም ነጻ ግብይት ማለት አቅምና ኃይል ያለዉ ግለሰብ ሆነ ነጋዴ ከፈለገ የዓለምን ሀብት ጠቅልሎ በመያዝ ዓለምን ሆነ የዓለምን ሕዝብ እንደፈለገዉ ማሽከርከር ይችላል፡፡ የግለሰቦች መድህየትና መቸገር ብዙም ቦታ አይሰጠዉም፡፡ የሚችል ይኖራል፤ የማይችል አይኖርም፡፡ ይልቁኑ የዓለም አቀፍ ችግር የሆነዉን የአየር ንብረት ችግርና ኤድስና አባላዘር በሽታ ትኩረት ብትሰጡትና፣ እንዲሁም ወንዶች ከወንዶች እንዲጋቡ ሙሉ ሰብአዊ መብታቸዉ እንዲረጋገጥ ቢደረግ ችግራችሁ ሊቃለልና እርዳታም በደንብ ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ስለዚህ የማይገባ ችግር በማቅረብ የመንግስታችሁን ወርቃማ ጊዜ አታባክኑ፡፡ እናንተ ነጋዴዎች ደግሞ ለዚህ ብልጽግና ያበቃችሁን ወዳደጉት አገራት ደረጃ ለማድረስ ደፋ ቀና የሚለዉን መንግሥታችሁን ማማት አልነበረባችሁም፡፡ እናንተም እንደነሱ ብልጥ ሆናችሁ በሀብት ላይ ሀብት፣ በሕንጻ ላይ ሕንጻ፣ በንብረት ላይ ንብረት መጨመሪ እንጂ ስለ ድሆችና ስለችግረኞች እኛ ስላለን ብዙም ሊያስጨንቃችሁና ሊያሳስባችሁ አይገባም፡፡» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል፡፡

ሕዝቡም « እሺ ወደማን ነዉ አቤት የሚባለዉ!? የመጣነዉ በዉኑ እነዚህ የእኛ ወንድምና እህት ወደሆኑት የአዳም ዘሮች ነዉ? ወይስ በሥጋ የተገለጹ የጨለማዉ ገዥ አገልጋዮች ናቸዉ እንደዚህ የሚያስቡትና የሚላግጡብን? እዉነተኛ ፈራጅ እግዚአብሔር የለም ብለዉ አስበዉ ይሆን?.» በማለት በኀዘንና በምሬት ወደቤታቸዉ ተመልሰዋል::

በማግስቱ ደግሞ ንዴቱ አልበርድ ያላቸዉ ሰዎች ተመልሰዉ ጥያቄቸዉንና ብሶታቸዉን ለማቅረብ ወደሚመለከተዉ አካል ቢሄዱም « ባለጉዳይ የሚስተናገደዉ በሳምንት አንድ ቀን ስለሆነ ማክሰኞ ኑ» ተብለዉ ተመለሱ:: ማክሰኞን ጠብቀዉ ሲሄዱ «የሚያነጋግሯችሁ ስብሰባ ስለገቡ ሳምንት ኑ» ተባሉ:: ሳምንት ጠብቀዉ ሲሄዱ «ለስልጠና ስለሄዱ ከወር በኋላ ኑ» ተባሉ:: ወር ጠብቀዉ ሲሄዱ «ኀዘን ስላጋጠማቸዉ ዛሬ አይገቡም» ተባሉ:: እኔም የጨለማዉ ገዥ በሕዝቡ መጉላላትና በመሪዎቻቸዉ መጨከን እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ እንቆማለን የሚሉት የተባበሩት መንግስታት ተስፋ አስቆራጭ መልስ ተደስቼ እስከአሁን ሕዝቡ በችግርና በረሀብ አለጋ እያስገረፍኩት እገኛለሁ::

**ከዚህ የምንረዳዉ ነጋዴዉ ለወገኑ እንዳያስብና ስግብግብ እንዲሆን የጨለማዉ ገዥ ሥርዓት ተጽህኖ እንዳሳደረበትና በሕዝብ ስም የሚነግዱት በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ ያሉ ባለ ሥልጣናትና ኃላፊዎች የሕዝብ ሀብትና ንብረት ዘራፊ መሆናቸዉን ነዉ:: እንዲሁም የዓለም መንግሥታት የእነርሱን ፈቃድ እስከፈጸመና የዓላማቸዉ ተባባሪ እስከ ሆነ ድረስ ማንኛዉም መንግሥት የፈለገዉን የጭከናና ግፍ ተግባር እንዲሁም አድሎና በደል ቢፈጽም አንዳች ስሜት የሌላቸዉና፤ የሰዉን ሕሊና በሚያደረነዝዙበትና የእግዚአብሔርን ህልዉና በሚያስክዱ፣ በሚያስረሱ ተግባር ላይ ትዉልዱን አሰልፈዉ የራሳቸዉን መሰሪ ተግባር እንደሚፈጽሙና እንደሚያስፈጽሙ ነዉ:: በዚህ ላይ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?**

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በግልጽ እንደሚታወቀዉ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በዓለም ላይ ያሉ መንግሥታት የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ ስለሆኑ ስግብግብነትንና ራስ ወዳድነትን ነዉ ያነገሡት:: እነሱ ጥቅም እስካገኙና ሥልጣናቸዉ ከተጠበቀ ስለ ድሆች ሆነ ስለ ችግረኞች ስሜት የላቸዉም:: ምናልባት ድህነቱና ችግሩ ለሥልጣናቸዉ የሚያሰጋ ሆኖ ካገኙ ብቻ ስለ ሕዝቡ በማሰብ ሳይሆን ለራሳቸዉ ጥቅምና ሥልጣን ሲሉ አንዳንድ መፍትሔዎችን ይፈልጋሉ እንጂ «የአዳምና ሔዋን ዘር ወገኔ ተራበ፣ ተጠማ፣ ተቸገረ፣ ተጎሳቆለ፣ መከራና ፍዳ ደረሰበት፣ ተቸገረ፣ ታሰረ፣ ግፍ ተፈጸመበት፣ አድሎና በደል ደረሰበት፣ ተሰደደ፣ ተገደለ ...ወዘተ» ብለዉ ጥብቅና አይቆሙም:: በዚህም ምክንያት በተለያዩ ክፍለ አህጉር ዉስጥ ባሉ አገሮች ዉስጥ የተለያዩ አምባገነን መሪዎችና በሕዝብ ስም የሚነግዱ አስመሳይ አገልጋዮች በተለያየ የሥልጣን እርከን ላይ ተቀምጠዉ ሕዝቡን በተለያየ መንገድ እያሰቃዩት ያለዉ:: የተባበሩት መንግሥታት፣ የአዉሮፓ ኅብረት፣ የአፍሪካ ሕብረት፣ የአረብ ሊግ፣ ቡድን 20፣ ቡደን 8 ... ወዘተ የሚል ስያሜ ተላብሰዉ «ለዓለም ሕዝብ ሰላም፣ ብልጽግና፣ እኩልነት፣ ነጻነት፣ ዲሞክራሲ ... ወዘተ ለማስጠበቅ ነዉ የተቋቋምነዉ» እያሉና ወርቃማ ቃላት እየተጠቀሙ ተግባራቸዉ ግን ተቃራኒ ነዉ::

ይልቁኑ ከራሳቸዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር በተጨማሪ በእርዳታ ተጽህኖ ሌሎች አገሮችም በዓመፃ፣ በክህደት፣ ርኩሰት ተግባር ላይ እንዲሰለፉ የሚያደርጉ ናቸዉ:: በመሆኑም እኛ የኢትዮጵያ ሆነ የዓለም ሕዝቦች ተስፋ ማድረግ ያለብን የዓለም መንግሥታትን ወይንም ድርጅቶችን ወይንም ቡድኖችን ወይንም ግለሰቦችን ሳይሆን የሁሉ ፈጣሪና አምላክ እግዚአብሔርን ብቻ መሆን አለበት:: እርሱ እንደ ሰዉ የማይሸነግል፣ ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ ፍትሐዊ ፍርድ የሚሰጥ፣ ለችግረኛና ለተገፌ ሰዉ ጥብቅና የሚቆምና እዉነተኛ ፍርድ የሚሰጥ አዛኝ፤ ለፍጥረቱ የሚያስብ ርኅሩኅ ጌታ ነዉ::

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አራት ዉስጥ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ «እንደ ልቤ» የሚላቸዉን የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎቿን፣ ክልል ፕሬዘዳንቶችን የተለያዩ ባለሥልጣናትን እንዲሁም ካድሬዎችን ሲያላግጥባቸዉ «እናንት እንደራሴዎቼ መሪዎች፣ ባለሟሎቼ ባለሥልጣናት፣ ዉዶቼ ካድሬዎች» እያለ ለሃያ ዓመት በቅንነትና በትጋት ስላገለገሉት ምስጋናዉን እያቀረበላቸዉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከቆረጠባቸዉ ቀን አንድ ቀን እንኳ ሊጨምርላቸዉ አለመቻሉ እያስቆጨዉ ይናገራል:: ታዲያ ይህ የሚያሳየን በክፉ ትንቢት ፈጻሚነት ለሃያ ዓመት እንደተፈቀደላቸዉና ከዚያ በኋላ ዋጋ የሚከፍሉበትና ከወንበራቸዉ የሚቆረጡበት መሆኑን ነዉ:: እዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: እግዚአብሔር እንዲህ እንዲላገጥባቸዉ ያደረገዉ እነሱም ለዓመታት ስላላገጡበት ነዉ:: ያ ብቻ አይደለም በቅዱሱ ኪዳን ላይ ስለፈጸሙትና ስላስፈጸሙት ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍላቸዋል:: ይህንንም ቀመን እየተመለከትን ነዉ:: ገና 21ኛ ዓመታቸዉን እንደ ጀመሩ «የዲያብሎስ እንደራሴ» የተባለዉ መሪያቸዉ ባላሰቡትና ባልጠበቁት ጊዜ በምድርም ፍዳዉን ተቀብሎ በስቃይ ሞት ከነዓመፃዉ ተጠርቶ ወደ መረጠዉ የዓመፀኞች ቦታ ሄዷል:: ቀሪዎቹም ፍዳቸዉን እየተቀበሉ ይቀጥላሉ ማለት ነዉ:: እጃቸዉን ለእግዚአብሔር የሰጡና በቅዱሱ ኪዳን ላይ ማመፃቸዉንና ማሳመፃቸዉን አምነዉ በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እዉነት የሚመለሰትን ደግሞ እግዚአብሔር መሐሪ ነዉና መክፈል ያለባቸዉን ዋጋ በምድር አስከፍሏቸዉ ለሰማያዊ መንግሥቱ ሊያበቃቸዉ ይችላል:: ከዚያ ዉጪ በምድርም በሰማይም ስለ ዓመፃቸዉ እንደ ዓመፃቸዉና ክህደታቸዉ እንዲሁም ርኩሰታቸዉ ደረጃ ዋጋ ይከፍሉበታል:: ስለዚህ ሁላችንም «የዓመፃ ልጆች» የተባሉት የክፉ ትንቢት ፈጻሚ ሰዎች ባለጊዜነት ከ21ኛው ዓመታቸዉ ጀምሮ የተሻረ መሆኑን አዉቀን ከእነሱ ጋር በዓመፃቸዉ አንዳች አንድነትና ኅብረት መፍጠር የለብንም:: ባለማወቅ ከእነርሱ ጋር በአንድነት ተሰልፈን እጅን ጓንት ሆነን የምንሰራ ሰዎች ካለን ደግሞ ዛሬ ነገ ሳንል፣ ምክንያቱም በራሳችን ሥልጣንና ፈቃድ በተቆረጠዉ እድሜያችን ላይ አንድ ቀን የመጨመር ሥልጣን ስለሌለንና ዛሬ በሥጋ ሞት እንጠራ ነገ እንጠራ በእርግጠኝነት ስለማናዉቅ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰን ቅዱሱን ኪዳን እንጠብቅ፤ እናስጠብቅ::

__ጠያቂዉ አገልጋይ:__ ሌላዉ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ በገጽ 260 ላይ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዉ መንግሥት ተወካይ:

«ታዲያ አንዳንድ የኛን ታላቅ ተግባር የማይደግፉና «የጽዮን ልጆች ነን» የሚሉ ትምክህተኞች፣ የገዥ መደቦች ርዝራዦችና የነፍጠኛ ስርዐት ናፋቂዎች፤« ስንትና ስንት ቅዱሳን ጻድቃን ከወጡበት ስፍራ፣ ታቦተ ጽዮን በቅርብ ርቀት ሆና እየታዘበችና ስለ ዐመጻ፣ ስለክህደት፣ ስለአምልኮ ምንዝርና ተግባራችሁና ንግግራችሁ ላይ ከምትመሰክርበት ቦታ፤ በቅዱስ ኪዳኑ ላይ ዐይን ያወጣ ዐመጻ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማ ላይ ዐይን ያወጣ ክህደት እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ ሕዝቡ ተስፋዉን ምድራዊ አድርጎ እንዲኖርና እንዲመላለስ አድርጋችኋል። እንዲሁም ሕዝቡን በተለያየ ጥቅማ ጥቅምና ስልጣን ዐይኑን አሳዉራችሁት ለጥፋትና ለዉድቀት እየዳረጋችሁት ነዉ። ቀድሞ ለሃይማኖቱ ይቆረቆር እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕግና ስርዐት ዘብ ይቆም የነበረዉን የቅዱስ ኪዳን ሕዝብ ሳይቀር አሳምጻችሁታል፤ ርኩሰትን አስፈጽማችሁታል።

ስለዚህ እዉነተኛ ንስሐ ካልገባችሁ እናንተም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ፤ እናንተና መሰሎቻችሁ ዐመጻና ክህደት ከፈጸማችሁባትና ካስፈጸማችሁባት፣ ርኩስት ካነገሣችሁባት፣ <u>እንዲሁም ብቸኛይቱን የሕይወት መንገድ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት ቆርጣችሁ ከተነሳችሁበት ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቁጣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትጠረጋላችሁ።</u>» በማለት የሚናገሩ ዐመጸኛና ሁከት ፈጣሪዎች ቢኖሩም፤ እኛ ግን የአገሪቷ ዋና ምሶሶ የሆነዉን የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የያዘዉን አንዳች እንከን የሌለዉን ሕገ መንግስታችንን ይዘን፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገን፣ <u>ብቸኛዉን የሕይወት እምነታችንን አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዘን፣ የጨለማዉን ገዥ ጌታችንን አምነን ማንም ሊነካንና ሊነቀንቀን አይችልም። ይልቁኑ ስንት ምሁራን ከጎናችን ተሰልፈዉና ታላቅ ተግባራችንን እያደነቁና ምስክርነትን እየሰጡ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስርዐታችንን አንቀበልም የሚሉትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደመስሳቸዋለን።</u>» በማለት ተናግረዋል።

የሁሉም «ክልላዊ መንግሥታት» ተወካዮች አገላለጽ ብንመለከት የመጀመሪያዉ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ተከትለዉ እንደ ድምፅ ማጉያ ያስተጋቡት የመጀመሪያዎቹ « የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት(ብአዴን) ተወካይ ነን» የሚሉት ናቸዉ። በመቀጠል ያንኑ ድምፅ ማጉያ ተቀብለዉ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር እንደ ድምፅ ማጉያ ያስተጋቡት «የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት(ኦሕዴድ) ተወካይ ነን» የሚሉ ናቸዉ። ከዚያ ደግሞ እነሱ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር እንደ ድምፅ ማጉያ አስተጋብተዉ፤ ድምፅ ማጉያዉን እንደ ብአዴን ተወካይ ለቀጣይ ተናጋሪ ማስተላለፍ ሳይሆን ቦታዉን ለቀዉ የጋበዙት «የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት(ሕወሓት) ተወካይ ነን» ለሚሉት ነዉ። ሌሎቹ ክልላት ሳይፈለጉ ለማዳመቂያ ብቻ የመናገር እድል እንደተሰጣቸዉ ነዉ የአጻጻፉ አቀራረብ የሚያሳየን። ታዲያ የሕወሓቱ ተወካይ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነዉ የተናገሩትና በመጨረሻም «በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት የማያምኑትን

እንደመስሳቸዋለን» በማለት ነዉ በትዕቢትና በእብሪት የተናገሩት:: **ለእዚህ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?**

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በግልጽ እንደሚታወቀዉ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሥርዓት ፈጥረዉ በበላይ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር በመፈጸምና በማስፈጸም ላይ ያለዉ «ሕወሓት ወይንም ወያኔ» በመባል የሚታወቀዉ ቡድን ነዉ:: ነገር ግን በአገሪቷ በአራቱም ማእዘን ግልጽና ስዉር ዓለማቸዉን ለማሰካት እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ የሚሄዱና እንደ ጠፍ ከብት የሚነዱ የተለያዩ ቡድኖችን አቋቁመዋል:: ሁሉንም በቋንቋ አከላለል ከፋፍለዉ «የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ድርጅት» በማለት የተለያየ ስያሜ በመስጠት ይኸዉ እንደ መሳሪያ ተጠቅመዉባቸዉ የዓመፃ ተግባራቸዉን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ በግልጽ እየተመለከትን ነዉ::

እግዚአብሔር ግን «ምናልባት ነጻ ሕሊናቸዉን ተጠቅመዉ ወደ ልባቸዉ ይመለሱ ይሆናል» በሚል መልእክቱን በተለያየ መንገድ አስተላልፎላቸዉ ነበር:: እነርሱ ግን አሁንም ሕሊናቸዉን በማደንደን በትዕቢትና በእብሪት የሚናገሩ፣ በጦራቸዉ የሚመኩ፣ በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ እንዲሁም በአምልኮ ምንዝርናቸዉ የጸኑ ናቸዉ:: በመሆኑም እግዚአብሔር እንደተናገረዉ ትዕቢታቸዉና እብሪታቸዉ እስከሚጠፋ ድረስ በቁጣዉ ይጠርጋቸዋል፤ ያከስማቸዋል:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከባለጊዜነት ይሽራቸዋል:: ምክንያቱም ቅዱሱን ኪዳን ከማንም በላይ መጠበቅና ማስጠበቅ ሲገባቸዉ በተቃራኒዉ ስለተሰለፉ ነዉ:: ምናልባት ከመሃላቸዉ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር የሚሰጡና በእዉነተኛ ንስሐ የሚመለሱ ካሉ ደግሞ ስለ ፈጸሙት ዓመፃ ዋጋ አስከፍሏቸዉ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሊያደርሳቸዉ ይችላል::» **በማለት የየዋሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ክፍል ስድስት

### ምዕራፍ አንድ

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: አንድ ጉዳት ሆነ ጥቃት የደረሰበት ግለሰብ ሆነ አካል ለፍርድ አካላት ጉዳቱንና ጥቃቱን አቅርቦ ቢያስፍርድ አግባብ ነዉ ወይ?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: በዚህ ምድር የተዘረጋዉ የዲያብሎስ ሥርዓት ነዉ እንጂ እዉነተኛ የእግዚአብሔር ሥርዓት ቢሆን ኖሮ ዳኞች እንደ እግዚአብሔር ሆነዉ ነበር የሚፈርዱት:: የሚፈረድበትም ሰዉ ቅጣቱ ቀኖና ሆኖለት ስለ ኃጢአቱ ንስሐ ባይገባ እንኳ ከዚህ ምድር በሥጋ ሞት ሲጠራ ከመጨረሻዉ ከእግዚአብሔር ፍርድ ባያመልጥም ፍርዱ ግን ይቀልለታል:: በዓለም የሚታየዉ ግን በአብዛኛዉ የዲያብሎስ የጨለማዉ ሥርዓት ስለሆነ ጠበቃዉም ዐቃቤ ሕግሙ ዳኛዉም ለአንድ እዉነት ቆመዉ በበዳይ ላይ ማስፈረድ ለተበዳይ ደግሞ መፍረድ ሲገባ፤ ተቃራኒዉ ይፈጸማል:: የከፋዉ ደግሞ ሕሊናዬን አልሸጥም የሚለዉን በሐሰት ይወነጀላል፤ የግፍ ፍርድ ይፈጸምበታል:: ዳኛዉም፣ ጠበቃዉም፣ ዐቃቤ ሕጉም ለእዉነት ሳይሆን የሚፈረዱትና የሚያስፈርዱት ለጥቅማቸዉ ነዉ:: ይኸዉም ዐቃቤ ሕግና ዳኛ፤ ለሾማቸዉ አካል ብቻ ነዉ የቆሙት እንጂ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ አይደለም:: መንግሥት እርምጃ እንዲወስድበት የሚፈልገዉ ግለሰብ ሆነ አካል ላይ በተቀነባበረ ሐሰት መረጃ ይወነጅላሉ፣ ያስፈርዳሉ፣ ይፈርዳሉ:: ጠበቃዉም ለሚያገኘዉ ገንዘብ ሲል ወንጀል የፈጸመዉ ግለሰብ ሆነ አካል ወንጀል መፈጸሙን ሕሊናዉ እየመሰከረበት ነጻ የሚሆንበትን የሐሰት መረጃ ነዉ የሚያቀርበዉ::

ሕግ አዉጭዉ፣ ሕግ ተርጓሚዉ፣ ሕግ አስፈጻሚዉ ለአንድ እዉነት ብቻ መቆም ሲገባቸዉ፤ ሲፈልጉ በሐሰት ዉንጀላ ላይ በአንድ አዛዥ ይመራሉ፤ ሲፈልጉ ለማስመሰል «እያንዳንዱ አካል ነጻ ነዉ፣ ራሱን ችሎ ነዉ በነጻነት የሚንቀሳቀሰዉ፣ ለእዉነት የቆመ ነዉ፣ ... ወዘተ» እያሉ በተግባር ግን አንድ አካል ነዉ ሁሉን እንደፈለገዉ የሚያደርገዉ:: በእዚህ ምክንያት ግልጽነትና ተጠያቂነት የለም:: ባለ ጠመንጃዉ ነዉ ፈላጭ ቆራጭ:: ለምሳሌ የኢትዮጵያን ሥርዓት ብንመለከት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብና የዓለምን መንግሥት ለመሸንገልና ለማታለል እንዲሁም የዋሃንን በመስመራቸዉ ዉስጥ ለማስገባት «ሕግ አዉጪ፣ ሕግ ተርጓሚዉ፣ ሕግ አስፈጻሚዉ የተለያየና እያንዳንዱ በነጻነት ነዉ የሚሰራዉ» ይባላል:: ያለዉ እዉነታ ግን ሁሉን እንደፈለገ የሚያዘዉ ፈላጭ ቆራጩ የሆነዉ ጦሩን የሚያዘዉ የነበረ አንድ ግለሰብ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነበር:: ሲፈለግ በአንድ ቀን አርቅቆ በአንድ ቀን አጸድቆ ሊበቀላቸዉ በሚፈለግዉ ግለሰብ ሆነ አካል ላይ የበቀልና የግፍ ተግባሩን መፈጸም ይችላል:: ምክንያቱም በእያንዳንዱ አካል ዉስጥ ያስቀመጣቸዉ ሰዎች ከሆዳቸዉና ከጥቅማቸዉ ዉጭ ለሕዝብና ለአገር የማያስቡ እነ ሆዱና ጥቅሙ አምላኩ የሆኑ ሰዎች ስለሆኑ «አድርጉ» የተባሉትን ሁሉ የሚያደርጉ፣ «አታድርጉ» የተባሉትን ሁሉ የሚያደርጉ ናቸዉ እንጂ «ይህ በደል ነዉ፣ ይህ ግፍ ነዉ፣ ይህ አድሎ ነዉ፣ ይህ ቅንነትና እዉነተኛነተ የጎደለዉ ነዉ፣ ይህ በቀል ነዉ፣ ይህ የማስመሰል ተግባር ነዉ ... ወዘተ» የማይሉ ሆዳቸዉ ከሞላና ጥቅማቸዉ ከተጠበቀ

በራሳቸዉ ላይ የፈለገዉ ነገር ቢፈጸምባቸዉ «ችግር የለዉም ዋናዉ የሆዳችንና የጥቅማችን ጉዳይ ብቻ ይጠበቅለን» የሚሉ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ያልታመኑ ናቸዉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሞቱ በኋላም አዛዥ ናዛዥ የሆነዉ ጦሩ ነዉ። ይህን ትዕቢቱንና እብሪቱን ያስመሰከረዉ ከሕገ መንግሥቱ ዉጭ በራሱ ሥልጣን የፈለገዉን ሰዉ መልምሎ እንደ ድምፅ ማጉያ በሚጠቀምበት አካል ወይን ግለሰብ አማካይነት ለአገር ታሪክ የሰራና ጀብዱ የፈጸም ሰዉ ያለ ይመስል ለታማኝ አገልጋያቸዉ ጀነራል በጅነራል ማዕረግ አምነሽንሿቸዋል። አሁንም «ትግል ከጀመርኩ ጀምሮ ያለዉ ዘመኔ ተሰልቶ ጡረታዬ ይከበር፣ እምቢ ከተባለ ደግሞ ልክ አስገባችኋለዉ፣ «እስከ አሁን ዘመን የሚታወቀዉ የጦር ኃይል በበላይ ሲገዛ እንጂ ችሎታ፣ እዉቀት፣ ብቃት የሚባለዉ ለማስመሰያ ብቻ ነዉ» በማለት በዚያዉ ትዕቢትና እብሪት ሕይወት ዉስጥ ነዉ ያሉት። እንግዲህ የትዕቢቱንና የእብሪቱን መጨረሻ ምን እንደሚሆን በቅርቡ የምናየዉ ይሆናል።

ባጠቃላይ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመራ ሕግ አዉጪ ፣ሕግ ተርጓሚ፣ ሕግ አስፈጻሚ አካል ቢኖር ኖር ሦስቱም በነጻነት ለአንድ ለእግዚአብሔር እዉነት ብቻ ነበር የሚቆሙት። አሁን ግን በዓለም የሚታየዉ የተደበላለቅ ፍርድ ነዉ። ዞሮ ዞሮ ተበዳይ ቢፈረድለትም ባይፈረድለትም ለፍርድ የሚያበቃ በደልና ጥቃት ከተፈጸመበት አጥፊዉንና ግፈኛዉን ለእዉነተኛ ፍርድ ማቅረብ መብቱና በዳዩና ግፈኛዉ ዋጋ እንዲከፍል( እንዲቀጣ) ማስደረጉ አግባብነት አለዉ። ያማ ካልሆነ እያንዳንዱ «ከሕግ በላይ ልሁን» እያለ በደልና ግፍ ይፈጽማል፣ ሕገ ወጥነትና ሥርዓት አልበኝነት ይነግሣል። ዋናዉ ግን እዉነተኛን ጉዳት ይዞ መቅረብ ነዉ እንጂ በሐሰት የምናስወነጅል ከሆነ ደግሞ በምድርም በሰማይም የባሰዉ ቅጣት ነዉ የሚጠብቀን። ምክንያቱም እዉነተኛ ዳኛ እግዚአብሔር ጊዜዉን ጠብቆ ፍርዱን ይሰጣልና።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ «ሰባት ጊዜ ሰባት ወይንም አርባዘጠኝ ጊዜም ቢሆን የበደለህን ይቅር በለዉ »ተብሏል። ታዲያ የበደለንን ለፍርድ ማቅረብ የእግዚአብሔርን ቃል መሻር አይሆንብንምን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እያንዳንዱ ቃላት ሆነ ዐረፍተ ነገር እንዲሁም አንቀጽና ምዕራፍ የተጻፈበት፣ የተነገረበት ምክንያት አለዉ። ለወንጀልና ለግፍ ተግባር  እንዲመቸን አድርገን የእግዚአብሔርን ቃል መጠቀም የለብንም። እግዚአብሔርማ ፍርዱ እጅግ ጥብቅ መሆኑን ነዉ የተናገረን። ይኸዉም ወንድሙን በድህነቱ፣ በመሃይመነቱ፣ በችግሩ ምክንያት «አንተ ቡትታም፣ መሃይም፣ ደሀ፣ መናጢ» ብለን ብንሰድበዉ ወደ ፍርድ ቀርበን ለእዚያ የንቀትና የትምክህት ስድባችን ዋጋ መክፈል(መቀጣጥ) እንዳለብን ነዉ የሚያስረዳን። እንዲሁም አንድ በተፈጥሮዉ ይሁን በአደጋ ወይንም ከጊዜ ብዛት በአካሉ ላይ ጉድለት ቢታይበት ወይንም በበሽታ አካሉ ቢጎል በጎደለዉ አካሉ «አንተ ደንቆሮ፣ አንተ እዉር፣ አንተ ቆማጣ ... ወዘተ» ብለን ብንሰድበዉ ምድራዊ ፍርድ ብቻ ሳይሆን የሚጠብቀን የሕያዉነት ፍርድ የሆነዉ ገሃነመ እሳትን

ነዉ። ይህ የሚያሳየን አካል ጉዳተኞችን በጎደላቸዉ አካል ብንሰድባቸዉ እግዚአብሔርን እንደሰደብን እንደሚቆጠርና ፍርዱ ከባድ መሆኑን ነዉ።

ሰዉ ግን የደረሰበትን በደል በይቅርታ ይለፈዉ ወይንም ያስፈርድበት እንደ ግለሰብ ደረጃ ግን ያ ሰዉ ይቅርታ ቢጠይቀዉም፣ ባይጠይቀዉም ከልቡ ይቅር ማለት ይጠበቅበታል። ምክንያቱም ያ በዳይ ሳይቀጣ ይሁን ተቀቶ ወደ ልቡ ቢመለስና ጥፋቱ እንዲጸጸት ቢያደርገዉና ይቅርታ ቢጠይቅ ተበዳይ «በደል ተፈጽሞብኝ እዴት ይቅር እላለሁ» እንዳይል ነዉ እግዚብሔር ለበደል ይቅርታ ገደብ ያላበጀለት። ምክንያቱም እኛ እርሱን ለዘመናት እየበደልነዉ በእዉነተኛ ንስሐ «ይቅር በለን» ስንለዉ ካለገደብ ሁሌ ይቅር ይለናልና፤ እኛም እርሱም የመምስል ባሕርይ የተላበስን ስለሆነ እንደ እርሱ እንድንሆን ፈልጎ ነዉ የይቅርታን ገደብ ያላበጀልን። ነገር ግን እያንዳንዱ በዳይ በምድርም ሆነ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሰ በሰማይም እንደ በደሉ ደረጃ ዋጋ ይከፍልበታል(ይቀጣበታል)። እንደ መጸጸቱ ደረጃ የሚመለከተዉ አካል ምሕረት ካደረገለትም በምድርም ምሕረት ሊያገኝ ይችላል። በእዉነተኛ ንስሐ አምላኩን ይቅርታ ከጠየቀ በሰማይም ሙሉ ምሕረት ይደረግለታል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ስለ ነጻነትና እኩልነት ያሎት አስተያየት ምንድነዉ? ይህን ያነሳሁበት ምክንያት በአገራችን ኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ዉስጥ ያሉ ብዙ ድርጅቶች «ዲሞክራት ነን ፣ ነጻነትና እኩልነት የሰፈነበትን ሥርዓት ነዉ የዘረጋነዉ፣ ነጻና ገለልተኛ ፍትሕ ተቋም ነዉ ያለን፣ መንግሥታችን ተጠያቂነትና ግልጸኝነት ያለዉ ነዉ ፣ ማንም በነጻነት የመናገር፣ ሐሳቡን የመግለጽ፣ የመጻፍ መብት አለዉ» በማለት ሌት ተቀን እየለፈፉ በተግባር የሚታየዉ ደግሞ ፍጹም ተቃራኒ ነዉ። አስመሳዮች፣ ግፈኞች፣ ጨቃኞች፣ አድሎና በደል የሚፈጽሙ፣ ሙሰኞች፣ ሰዎች እዉነቱን በመናገራቸዉና «ሕሊናዬን አልሸጥም» በማለታቸዉ የሚታሰሩበት፣ የሚሰደዱበት፣ የሚገደሉበት፣ የሚወነጀሉበት፣ ባጠቃላይ መከራና ስቃይ የሚደርስባቸዉ ነዉ። ታዲያ የነጻነትና የእኩልነት መገለጫ ይህ ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ስለ ነጻነትና እኩልነት ያለዉን እዉነታን በእግዚአብሔር እዉነት ነዉ የምገልጽላችሁ። በዓለም የሚነገረዉ ነጻነትና እኩልነት ለመሸንገያና የራስን ስዉር ዓለማ ለማስፈጸም የሚጠቀሙበት፤ የሚነገረዉና በሕግ ሆነ በጽሑፍ ያለዉ ሌላ፣ በተግባር የሚፈጸመዉ ደግሞ ሌላ ነዉ። ይህም ሰዎችን ለመሳብና በዓላማቸዉ ዙሪያ ለማሰለፍ ወርቃማ ንግግሮችን ይናገራሉ፣ ወርቃማ ጽሑፎችን ያቀርባሉ። ነገር ግን ለመሸንገያና ለማስመሰያ ስለሆነ ወደ ተግባር ሲመጣ አይፈጸምም። ንግግሩና በሕገ መንግሥቱ የተጻፈዉ ሁሉ የሚጠበቅ የሚመስለዉ የዋህና «በእዉነት አገለግላለሁ፣ ስለ እዉነት እመሰክራለሁ» የሚል ሰዉ ደግሞ፤ ከዓመፃ ሰዎች ስዉር ዓላማ ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ በማንኛዉም መንገድ ጥቃትና በቀል ይፈጸምበታል። እስከ መሞት ሊያደርሰዉ ይችላል። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚታይ እዉነታ ነዉ። ንግግርና ጽሑፍ ከተግባር ጋር አለመገናኘት እንኳን በሥጋዉያን «መንፈሳዉያን» በተባሉትም ጎልቶ ይታያል። ፍርዱ ደግሞ «መንፈሳዉያን» በተባሉት ላይ ይብስባቸዋል። ምክንያቱም በፈጣሪ በእግዚአብሔር ስም ነዉና የሚነገደዉ።

በእግዚአብሔር እዉነት ነጻነት ማለት ለማንም ሰዉ ነጻ የሆነዉ ሐሳብ ማንም ሰዉ በነጻነት ሊያስብ ይችላል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዋጋ የሚያገኘዉ እንደ ቅንና መልካም ሐሳቡ ደረጃ ሲሆን፤ በተቃራኒዉ ዋጋ የሚከፍለዉ እንደ ጠማማና ክፋት ሐሳቡ ነዉ። እንዲሁም እንደ ማንኛዉም ሰዉ ማንም ሰዉ የመናገር ነጻነት አለዉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዋጋ የሚያገኘዉ ቅን ፣ መልካም፣ እዉነት ከተናገረ ነዉ። በተቃራኒ ዋጋ የሚከፍለዉ ዉሸት፣ ስድብ፣ ርኩሰት ከተናገረ ነዉ። እንደ ማንኛዉም ሰዉ ማንም ሰዉ የመስራት ነጻነት አለዉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዋጋ የሚያገኘዉ የሚሰራዉ ስራ ለሰዉ ዘሮች የሚጠቅም፤ ከችግር፣ ከድህነት፣ ከጉስቁልና የሚለይ ሲሆን ነዉ። በተቃራኒዉ ዋጋ የሚከፍለዉ የሰዉ ልጆችን የሚጎዳ፣ ዓመፃን ክህደትን ርኩሰትን የሚያነግሥ ተግባር ከሰራ ነዉ።

በእግዚአብሔር እዉነት እኩልነት ማለት ማንም ሰዉ የሚያገኘዉን እድል ሁሉም በእኩል ካለ አድሎ በእኩልነት ሲጠቀም ነዉ። ማንም ሰዉ የመማር፣ የመስራት፣ የመኖር ነጻነት እንዳለሁ ሁሉ አንዳች ልዩነትና አድሎ ሳይፈጠርበት መማር፣ መስራት፣ መኖር አለበት። ከእግዚአብሔር ዋጋ የሚያገኘዉ የተማረዉን ለመልካም ፍሬ ሲያዉል፤ የሚሰራዉ ለራሱ ሆነ ለትዉልዱ የሚጠቅም ሲሆን፤ መኖሩ በቅንነት፣ በመልካምንት፣ በእዉነተኛነት ሕይወት ሲመራ ነዉ። በተቃራኒዉ ዋጋ የሚከፍለዉ ትምህርቱን ለክህደት፣ ለዓመፃ፣ ለርኩሰት ካዋለዉ፣ ስራዉ ጥፋትና ተንኮል ከሞላዉ፤ መኖሩ ለዓመፃ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት ሕይወት ከሆነ ነዉ። እያንዳንዱ ሰዉ ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሔር የብርሃን ሕግ ፊት እኩል የሆነና እንደ ስራዉና እምነቱ የሚፈረድለት ወይንም የሚፈረድበት ነዉ። ከእግዚአብሔር የሆነዉ የሚነገረዉ ሆነ በጽሑፍ ያለዉ ተግባራዊ የሚሆን እንጂ የማይሸነገልበትና የማያስመስሉበት ነዉ። ባጠቃላይ የእግዚአብሔር እዉነት ስለ ነጻነት ፣ስለ እኩልነት የሚነግረን እያንዳንዱ ሰዉ ከእግዚብሔር ዋጋ የሚያገኘዉ ቅንነት፣ መልካምነት፣ እዉነተኛ ነት ሕይወት ሲይዝ ብቻ እንደሆነና ዋጋ የሚከፍለዉ ደግሞ በተቃራኒ ሕይወት ሲሰለፍ ብቻ እንደሆነ ነዉ። እያንዳንዱ የሕዝብ ሆነ የአማኞች አገልጋይ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ የሚገኝ እንጂ አንደበቱ ሌላ ተግባሩ ሌላ ከሆነ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ለመፈጸምና ለማስፈጸም አይችልምና መወጣት ካልቻለበት አገልግሎት ይነሳል እንጂ፤ በዘር፣ በጎጥ(በብሔር)፣ በወገን፣ በዘመድ አዝማድ፣ በቤተሰባዊ ግንኙነት ከእግዚአብሔር እዉነተኛ ፍርድና ከብርሃን ችሎት አያመልጥም።

በዓለም የሚታየዉ ነጻነትና እኩልነት ደግሞ ሰዎች በኃጢአት ሕይወትና ተግባር እንዲሰለፉ የሚያደርግ፤ ግብረ ሰዶም ጭመር እንደ ነጻነት የሚታይበት፤ ሰዎች በዓመፃ፣ በክህደት፣ ርኩሰት ተግባር ላይ እንዲመላለሱና ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነታ በተቃራኒ እንዲሰለፉ የሚያደርግ ነዉ። ያ ብቻ አይደለም ሰዎች እርስ በእርስ እንዲጣሉ፣ እንዲከፋፈሉ፣ እንዲለያዩ፣ በጥላቻና በበቀል ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ ያደረገ ፍጹም የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ፈቃድ በአራቱም ማእዘን የተፈጸመበት ነዉ። እንዲሁም በዘር፣ በጎጥ (በብሔር)፣ በወገን፣ በዘመድ አዝማድ፣ በቤተሰባዊ ግንኙነት ብዙ አድሎ፣ ግፍ፣ ዓመፃ ተፈጽሞበታል። ምክንያቱም በንግግር ሆነ በጽሑፍ ያለዉና

በተግባር የሚፈጸመዉ ተቃራኒ ነዉና፡፡ » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምእራፍ ሁለት

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: አንድ ድርጅት ሆነ መንግሥት ራሱን ከደካማዎች ወይንም ሁኔታዎች ካለተመቻቸላቸዉ ድርጅቶችና መንግሥታት ጋር በማነጻጸር ራሱን ሊያገንና ከፍ ከፍ ሊያደርግ ይገባዋል ወይ? ይህን ያነሳሁት የሕወሓት(ኢሕአዴግ) መንግሥት «ከዚህ በፊት ያሉ መንግሥታት እንዲህ አልሰሩላችሁም ነበር፤ እኛ ግን እንዲህ ሰራንላችሁ፣ ነጻነት አይሰጧችሁም ነበር፣ እኛ ግን አንበሸበሽናችሁ፤ አድሎና በደል ይፈጽሙባችሁ ነበር፣ እኛ በመልካም እያስተዳደርናችሁ ነዉ፤ እነሱ ኢ-ሰብአዊ ተግባር ይፈጽሙባችሁ ነበር እኛ ግን ሙሉ ሰብአዊ መብት አጎናጽፈናችኋል... ወዘተ» እያሉ ራሳቸዉን መልአክ ሌላዉን ሰይጣን አድርገዉ ስለሚያቀርቡ ነዉ?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: ማንም ሰዉ ካለፉት ሆነ አሁን ካሉት ጋር ራሱን እየገመገመ ለበለጠ ስራ ነዉ መሰለፍ ያለበት እንጂ ከቀድሞ ድክመት ጋር ራሱን እያነጻጸረ ብዙ መስራት ሲችልና ሲጠበቅበት «ከእርሱ ተሽያለሁና እኔ ታላቅ ነኝ» ማለት አይችልም:: እንዲሁም «እርሱ በብረት ነዉ የቀጠቀጠህ፤ እኔ ግን በዱላ ነዉ የመታሁና የተሻልኩ ነኝ» ማለት አይችልም:: «እርሱ ሰዉነት እስከሚሰባበርና ምልክት እስከሚታይ ድረስ ነዉ ያሰቃየኸ፤ እኔ ግን ለመረጃ ሊቀርብ በማይችል መልኩ ነዉ ያሰቃየሁና ኢ- ሰብአዊ ተግባር አልፈጸምኩም» ማለት አይችልም:: «እርሱ ዐይን ያወጣ ግድያ ነዉ የፈጸመብህ፤ እኔ ግን ባስገድልህም ገዳዩን እየፈለኩና እያፈላለኩ ነኝ ስላልኩ ከእርሱ እሻላለሁ» ማለት አይችልም:: «እርሱ ዓላማዉን የሚያሳካለትን ሰዉ የዘር፣ የጎጥ ልዩነት ሳያደርግ ስለመደበ፣ እኔ ደግሞ እንደልቤ የማሽከረክራቸዉንና እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚሄዱልኝን ሰዎች እየመረጥኩ በተለያየ ቦታ ስላስቀመጥኩ የብሔር ብሔረሰብ መብት አስጠብቄያለሁ» ማለት አይችልም:: «እርሱ ሞባይል አላስገባም፤ በኮምፒተር አልተጠቀመም፤ እኔ ግን ይኸዉ ሕዝቡን ባለ ሞባይልና ባለ ኮምፒተር አድርጌያለሁና ትልቅ ሥልጣኔን አምጥቻለሁ» ማለት አይችልም:: «እርሱ የገንዘብ እጥረት የነበረበት ደሀ ስለነበረ የተወሰነ መንገድና ትምህርት ቤት... ወዘተ ነዉ የሰራዉ፤ እኔ ግን ብዙ ብድር ከዉጭ ስላገኘሁና ብዙ ግንባታዎን ስለሰራዉ ታላቅ ታሪክና ተግባር ነዉ የፈጸምኩት» ማለት አይችልም:: ባጠቃላይ ማንም ይሁን ማን በዘመኑ መስራት ያለበትን በመስራቱ እንደተለየ ሊቆጠርና ሊገን አይገባዉም:: ሊመሰገን ሆነ ሊደነቅ የሚችለዉ ሊሰራ የማይችለዉን የተለያየ መስዋዕትነት ከፍሎ የሚሰራ ነዉ እንጂ፤ የተለያየ ዓላማዉን ስላሳካ፣ የተለያየ ርዳት በማግኘቱና ሕዝቡንም አስጨንቆ ገንዘብ በመሰብሰብ የተለያዩ ግንባታዎች ስተለተሰሩ በተለየ ሁኔታ የሚመሰገንበት ሆነ የሚደነቅበት ምክንያት የለም::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** *አሁን ያለዉ የሕወሓት ኢሕአዲግ መንግሥት አስተሳሰብ እንደ ሌሎች የዓለም መንግሥታት የአእምሮ ቀላሎችና የአእምሮ ሕፃናት አስተሳሰብ ነዉ:: በአሁን ዘመን ከዛሬ ሃምሳና መቶ ዓመት በፊት የነበረዉን ሁኔታ የሚገመግሙና ያኔ የነበረዉ አስተሳሰብና ንቃተ ሕሊና በአሁን አስተሳሰብና ንቃተ ሕሊና እየመዘኑና እያነጻጸሩ ራሳቸዉን በባዶ ሕይወት የሚክቡና የሚያመጻድቁ ናቸዉ:: የብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያዉን)፣ እንዲሁም ከፍርድ ተቋማት ጀምሮ ሁሉንም ተቋሞች በቁጥጥራቸዉ ስር ስላዋሉና የራሳቸዉ ፓለቲካ ማራማጃ ስላደረጉት ነዉ እንጂ*

በገለልተኛ አካል ተይዘዉ ቢሆን ስንትና ስንት የግፍ፣ የጭከና፣ የአድሎ፣ የበደል፣ የርኩሰት፣ የዓመፃ፣ የክህደት ተግባራቸዉ ይጋለጥ ነበር። ነገር ግን ሁሉ በእነርሱ ቁጥጥር ዉስጥ በመሆኑ ሕዝቡን በወሬ፣ በቅስቀሳ፣ በስብሰባ፣ በተለያየ ጥቅማጥቅም፣ በቅርበት ስለላ ስላደነዘዙት ነዉ እንጂ ተግባራዉና ድርጊታቸዉ እንዲሁም ዓላማቸዉና ግባቸዉ በእዉነተኛ ሕሊናዉ ለሚመላለስ ሰዉ የሚዘገንን ነዉ። ምክንያቱም አሁን ባለዉ አስተሳሰብና ንቃተ ሕሊና ሲታይ ቀሎ የተገኘ ተግባርና ድርጊት ነዉ። ይሁንና ከባለፉት መንግሥታት ጋር ሲነጻጸር የተወሰኑ የተሻሉና የበለጠ ሊጠናከሩ የሚገባቸዉ ተግባርና ድርጊት የፈጸሙት አሉ። እንደ አጠቃላይ ግን የተማረና ሕሊናዉ የነቃ ትዉልድ የማይፈጽመዉን የከፋ፣ የከረፋ ተግባርና ድርጊት ፈጽመዋል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ በሁሉም መስሪያ ቤትና ድርጅት ለማለት በሚያስችል ደረጃ የተለያዩ ሰራተኞች እርስ በእርስ ይጠላለፋሉ፣ አንዱ የአንዱን ሙያ ይንቃል፣ አንዱ የአንዱን ሙያ ለማጥፋትና ለማዳከም ይሰለፋል፣ በኃላፊነት ላይ የሚቀመጡ ደግሞ እዉቀትና ችሎታ እንዲሁም ቅንነትና እዉነተኛነት እንደመስፈርት ታይቶ ሳይሆን የኢሕአዴግና አጋር ድርጅት አባልና ደጋፊ በመሆን ነዉ። በዚህም ምክንያት ሰራተኛዉ ስነምግባር በጎደለዉ አሰራርና አገራዊና ወገናዊ ፍቅር በሌለዉ ሕይወት እያገለገለ ይገኛል። ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ አሁን ያለዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥርዓት፤ ምንም እንኳ አገራዊና ወገናዊ ፍቅር ያለዉና በቅንነትና በእዉነት የሚያገለግል ትዉልድ መፍጠር ባይችልም፤ አንዳንዶች ስለ ሕሊናቸዉና ስለ አምላካቸዉ ሲሉ በሚችሉት አቅም ሕዝብን እያገለገሉ ያሉ ሰዎች በተለያዩ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አሉ። ነገር ግን ቁጥቸዉ እጅግ አነስተኛ ነዉ። ያ ብቻ አይደለም የኢሕአዴግና አጋር ድርጅት አባል ሆነዉ ሕዝብን በቅንነትና በእዉነት ለማገለግገል የተሰለፉ ከቁጥር የማይገቡ ሰዎችም አሉ። ነገር ግን ዉስጣቸዉ ክፋትና ተንኮል፣ እንዲሁም ዘረኝነትና ጎጠኝነት፣ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት የተላበሱ ሰዎች፤ ለፓለቲካ ዓላማቸዉ ነዉ የሚጠቀሙባቸዉ እንጂ ቦታና ሙል ሥልጣን ሰተዋቸዉ ማገልግል ስለማይችሉ እነሱም በጨለማዉ ሥርዓት ተሳታፊ በመሆን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን ዉስጥ ተሰማርተዋል። ሌላዉ ደግሞ ሥርዓቱ ራስ ወዳድነትና ስግብግነትን እንዲሁም እርስ በእርሰ መጠላለፍና በወሬ አቀባይነት የሚሰራ ተቋም እንዲፈጠር ስላደረገ፤ ሰራተኛዉ ከልቡ አይደለም የሚሰራዉ። አብዛኛዉ ሰራተኛ ከላይ ያሉት መሪዎችና ባለሥልጣናት እንዲሁም ኃላፊዎች ሰርቀዉ ሲከብሩ፣ እንዲሁም በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድነዉ የሕዝብን ሀብትና ንብረት ሲዘርፉ እያየ፤ እሱም ባገኘዉ አጋጣሚ ሰርቆ ለመክበር ነዉ ሌት ተቀን የሚያስበዉ እንጂ ወቶ፣ ወርዶ፣ ሰርቶ፣ ሀብትና ንብረት ለማፍራት አይተጋም።

ሌላዉም ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ በቅንነት፣ በእዉነት ሕዝብን ማገልገል ተስኖት እርስ በእርሱ እየተጠላለፈ፣ በወሬ እየተፈታ፣ ክብረ ሕሊናዉ(ሞራሉ) ተነክቶ ተስፋ ቢስ በሆነ ሕይወትና አሰራር ለገቢዉ ሲል ብቻ ይሰራል እንጂ፤ ችግሮች የሚፈቱበት፣ ሰራተኛዉ ለስራ የሚነሳሳበት፣

አገራዊና ወገናዊ ፍቅር አድሮበት ለአገር እድገትና ለሕዝብ ብልጽግና «በምን መልኩ ልስራ?» በሚል ስሜት አይሰራም።

ፓለቲከኛዉም ድጋፍ ለማግኘትና ለሸንገላ «መልካም አስተዳደር ማስፈን፣ ሙሰኝነትንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ጥገኝነትን ማስወገድ፤ ፍትሐዊ አሰራርን መዘርጋት፤ ነጻነትን ማጎናጸፍ» እያለ ሌት ተቀን ይለፈልፋል እንጂ ተግባራዊነቱ ላይ በተቃራኒ ነዉ የሚሰለፈዉ። ዋናዉ ለፓለቲካዉ ታማኝ ለመሆን የማያደርገዉን ሕሊናዉን ሸጦ የማስመሰልና የሸንገላ ንግግር መናገር እንጂ፤ ሕዝብን ቢያጉላላ፣ ቢያሰቃይ፣ በሐሰት ቢወነጅል፣ ቢሰርቅ አንዳች አይባልም። ነገር ግን ትንሽ ከፓለቲካዉ ካፈነገጠ እንኳን በሰራዉ ወንጀል አይደለም ሌላ የፈጠራ ወንጀል ተዘጋጅቶለት በእስር ሆነ በሌላ መንገድ ፍዳዉን ያያል። በእነዚህ ላይ ብቻ አይደለም ሌሎች የፓለቲካዉ ተቃዋሚ ወይንም ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የታመኑ ሰዎች በሐሰት መረጃና ምስክር፤ እንዲሁም ሲፈለግ በጸረ ሙስና፣ ሲፈለግ በፀረ ሽብርተኛነት ተፈርጀዉ በቀል ይፈጸምባቸዋል። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ነዉ ሰራተኛዉ በትጋትና በቆራጥነት መስራት የተሳነዉና እንዲሁም ቅንነትና እዉነተኛነትን ተላብሶ ለአገርና ለሕዝብ እድገትና ብልጽግና መቆም ተስኖት በደመ ነፍስ የሚሰራዉ። ከዚህ በተጨማሪ በማይገባ ሕይወትና አቋም ዉስጥ የሚመላለሰዉ። ለዚህ የሚሆን «የጨለማዉ ገኘ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ ስምንት በገጽ332-336 ላይ የተገለጸዉን አቀርባለሁ። ይኸዉም፡-

«ስለ አገራቸዉ የግንባታ ጥራት ያሳሰባቸዉ አንዳንድ ሥራ ተቋራጮች፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አማካሪ ድርጅቶች፣ የኪነ ህንጻ ባለሙያተኞች፣ መሀንዲሶች፣ የተለያዩ ባለሙያተኞች፣ ለተለያዩ ግንባታ የሚዉሉ የተለያየ ግብአት (የተፈጥሮና የምርት ዉጤት) አቅራቢዎች፤ በአንድ ላይ በመሰባሰብ፤ « በአገራችን ቀደም ሲሉ የተገነቡ የህንጻ፣ የመንገድ፣ የፋብሪካ ፣ የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ጥራታቸዉን የጠበቁ እስከ አሁን ድረስ የጎላ ጉዳትና መበላሸት የማይታይባቸዉ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያሉ የተለያዩ ግንባታዎች ሁለትና ሶስት አመት እንኳ አገልግሎት ሳይሰጡ የተለያየ ብልሽት የሚያጋጥማቸዉና አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ የሚሆኑ ሁሉ አሉ። የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ በኢትዮጵያዉያን ባለሙያተኞች እየተሰሩና ቁጥጥር እየተደረገባቸዉ ነዉ ይህ ሁሉ ጉድለትና ብልሽት የሚያጋጥማቸዉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን ለራሳችን ንብረት ትኩረትና ጥንቃቄ ካላደረግን ማን ሊያደርግልን ይችላል?» በማለት እርስ በእርስ የተወያዩ ሲሆን፤ ሁሉም ተሰብሳቢዎች በተነሳዉ አሳብ ተመሳሳይ አቋም ያላቸዉ መሆኑን በመግለጽ «ችግሩ ምንድ ነዉ?» በማለት ለዉይይት አቅርበዉታል።

ከተሰብሳቢዎቹ መካከል የግንባታ ግብዐቶችን የሚያቀርቡና የሚያመርቱ አካላት፤ « እንግዲህ ሁላችንም የአገረና የወገን ፍቅር አስገድዶን ነዉ በራሳችን ፈቃድ የተሰባሰብነዉ። ስለዚህ ስለማንም ሳይሆን ለኅሊናችንና ስለ አገራችን ስንል ያለዉን ችግር በግልጽ ልንወያይና የራሳችን ችግር ካለም በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርብናል። ለምሳሌ በኛ በኩል በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከኛ በላይ እንደሆኑት

ሀብታሞች ለመሆንና ለመክበር ስለምንፈልግ ጥራት የጎደለዉና ደረጃዉን ያልጠበቀ ግብአት እናመርታለን፤ እናቀርባለን። በዚህም ምክንያት ወደ ግንባታ ሲለወጡ በሂደት በግንባታዉ ላይ የጥራት መጓደልና መበላሸት ይታያል» በማለት አስተያየት ሰተዋል።

በማስከተል ከስራ ተቋራጮች፤« በእርግጥ በግልጽ እንነጋገር ተብሏልና እኛም ስራ ተቋራጮች በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመክበርና ለመበልጸግ ካለን ፍላጎትና ከኛ በላይ የሆኑት ባለጸጋዎች ላይ ለመድረስ ከዚያም ለመብለጥ ካለን ምኞት የተነሳ ከፍ ያለ ትርፍ ማግኘታችንን እንጂ ግንባታዉ በጥራት ደረጃዉን በጠበቀ መልኩ እንደራሳችን ህንጻ በመመልከት አይደለም የምንሰራዉ። የዱሮዎቹ ተቋራጮች ሆኑ ባለሙያተኞች ከገንዘብ ፍቅር ይልቅ ለስማቸዉ ቅድሚያ ስለሚሰጡ ከራሳቸዉ ጥቅም ይልቅ የአገራቸዉንና የሕዝባቸዉን ጥቅም ነዉ የሚያስቀድሙት የነበረዉ። ለዚያም ይመስለናል በድሮ ስራዎች ላይ ብዙ ብልሽትና ጉድለት የማይታየዉ።

አሁን ያለነዉ ነጋዴዎች እንደአጠቃላይ ሲታይ ራስ ወዳዶች፣ ስግብግቦች ስለሆን በሀብት ላይ ሀብት፣ በሕንጻ ላይ ሕንጻ፣ በንብረት ላይ ንብረት እንዲኖረን ነዉ የምንፈልገዉ እንጂ አገራዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብ የለንም ማለት ይቻላል። ስለዚህ ይህ አስተሳሰባችን በመጀመሪያ ደረጃ ሊታደስ ይገባል። ያኔ ለአገርና ለወገን ማሰብ እንጀምራለን። መስገብገብና ራስ ወዳድነት አይደለም ከገንዘባችን በተጨማሪ ለአገራችንና ለሕዝባችን እንደ ቀደሙት አባትና እናቶቻችን ደማችንን ጭምር መስዋዕት ከማድረግ አንመለስም። አሁን ባለን አስተሳሰብ ግን የዓለም ሕዝብ ሀብቱና ንብረቱ የእኛ ብቻ ቢሆንና እኛን ሌት ተቀን ደጅ ቢጠናን ምርጫችን ነዉ» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል።

አርክቴክቶች፣ መሐንዲሶችና የተለያዩ ባለሙያተኞች፤« ጥንት ኢትዮጵያዉን በራሳቸዉ ልጆች ለዓለም የሚያስደንቅ የጥበብ ስራና ግንባታ አሳይተዋል። ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ደግሞ እነዚያ ጥበበኛ ኢትዮጵያዉያን ጠፍተዉ ኢትዮጵያዉያን ባልሆኑ ባለሙያተኛ ነበር የዲዛይኑና የቁጥጥሩ ስራ ይከናወን የነበረዉ። አሁን ደግሞ ብዙ ባለሙያተኞችን አገሪቷ አፍርታ ሳለ ከዱሮ በበለጠ የተሻለና ጥራቱን የጠበቀ ህንጻ፣ መንገድ የመሳሰሉት ሊኖረን ሲገባ ከዱሮ ያነሰና የሚያስተቸን ሆኗል። ይህም የሙያ ስነምግባር ጠብቀን ስለማንሰራና ከሥራ ተቋራጩ ጋር ተሻርከን እኛም ገቢያችንን ከፍ ለማድረግና በኋላም ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ለመሆን ነዉ የምንሰራዉ እንጂ ለስራዉ ጥራት ትኩረት ስለማንሰጥና በአቋራጭ ለመክበር ስለምንፈልግ ግንባታዉን በጥራት መቆጣጠር አልቻልንም» በማለት አስታየታቸዉን ሰተዋል።

በመቀጠል የኮንስትራክሽን ግንባታና ቁጥጥር አማካሪ ድርጅቶችም፤ « በሥራ ተቋራጭ ሆነ በዕቃ አቅራቢዎችና አምራቾች ዘንድ ችግር ቢኖር እንኳ በኛ በኩል በአግባቡ በመቆጣጠር የግንባታ ጥራቱንና ደረጃዉን ጠብቆ እንዲሰራ ማድረግ ሲጠበቅብን በአግባቡ የስራ ድርሻችንን ስላልተወጣን እኛም ለስራዉ ጥራት መጓደልና መበላሸት አስተዋጽኦ አድርገናል። ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያት እያንዳንዳችን ባለሙያተኞች ከጥናት፣ ከዲዛይን ፣ ከግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ጀምሮ ስራችንን እንደ ትርፍ ስራ (ሁለተኛ ስራ) አድርገን እየተመለከትን ስለምንሰራና በጋራ ተቀናጅተን ጥራቱንና ደረጃዉን

በጠበቀ መልኩ እንዲሰራ ለአንድ ዓላማ መቆም ስላልቻልን ነዉ:: ይባስ ብሎ በሙያችን እየተከፋፈልንና እየተባደን እርስ በእርስ የምንተቻች፤ የምንጠላለፍ፤ አገራዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብ የሌለን ፤ የራሳችንን ሙያ ብቻ ከፍ እያደረግን የሌላዉን የምናጥላላና የምናኳስስ፤ የአንድ አካል የተለያዩ ብልቶች መሆናችንን የዘነጋን ፤ ጆሮ በዐይን ላይ፣ እጅ በእግር ላይ ጥሩ አመለካከት የሌለዉ፤ የአንዱ ዉድቀትና መበላሻት ለሌላዉም እንደሚተርፍ ያላስተዋልን ነን ። ባጠቃላይ ለአንድ ዓላማ መቆም ያልቻልን ፤ ለጥራት ስራ አንዳች የማንቆረቆር፤ ደሞዛችንን በየወሩ ከመዉሰድ ዉጭ አንዳች አገራዊና ወገናዊ ፍቅር ተሰምቶን ለግንባታ ጥራትና እድገት ስሜት አልባ በመሆናችን ምክንያት ነዉ ጥራቱ ሆነ ደረጃዉን ያልጠበቀ ስራ ሊሰራ ያቻለዉ» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል::

በመጨረሻም ሁሉም የራሳቸዉ ጉድለት አምነዉ በቀጣይ ለአንድ ዓላማ በተቀናጀ መልኩ ጥራት ላለዉ ግንባታ በመሰለፍ የበደሉትና አገርና ሕዝብ ለመካስ ቆርጠዉ የተነሱ መሆናቸዉን በመግለጽ ለሚመለከተዉ አካል አቋማቸዉን ለማሳወቅ እየተዘጋጁ ሳላ፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ የመልካም ነገር ተቃራኒ ነኝና አንድ ልብ እንዳይሆኑ በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ከፋፍዬ፤ ዉይይቱንም በካድሬዎቼ አማካይነት ከፖለቲካ ጋር እንዲያያዝ አድርጌ መልካም አሳባቸዉንና እቅዳቸዉን አኮላሽቻለሁ::

አንዳንድ የጤና ባለሙያተኞች በአገር ዉስጥ ስለሚሰጠዉ የጤና አሰጣጥ ድክመትና ስነምግባራዊ ባልሆነ መንገድ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከት ዉይይትና አቋም መዉሰዳቸዉ ታዉቃል:: ይኸዉም በዉይይታቸዉ« እኛ ሀኪሞች፣ ጤና መኮንኖች፣ ነርሶች፣ ጤና ረዳቶች፣ የላብራቶሪ ቴክኒሺያኖች፣ እንዲሁም ተዛማችነት ባለዉ ስራ በጋራ የምንሰራ ሰራተኞች ሕዝቡን ቃል በገባነዉ መሰረት በትህትናና በቅንነት ማገልገል ሲገባን በአገባቡ ማስተናገድና አገልግሎት መስጠት አልቻልንም:: ምክንያቱም እኛ አገልጋይ መሆናችንን በመዘንጋት ገና በሽተኛዉ ሲመጣ የምናመናጭቅና ሌላ ያላሰበዉን በሽታ የምንጨምርበት ሆነን ተገኝተናል:: ከዚህ በተጨማሪ ቀልጠፍ ያለ አገልግሎት መስጠትና ጥንቃቄ የሞላበት ህክምና መስጠት ሲገባን የምናጉላላና ጥንቃቄ የጎደለዉ የቸልተኛነት ስራ በመስራታችን አንዳንዶቹ ለሞትና ለከፋ ጉዳት ዳርገናቸዋል:: ስለዚህ በተለያየ መልክ ሕዝቡ ስለተማረረብን በመልካም ስነምግባር እንደ ወላጆቻችንና ቤተሰቦቻችን በመመልከት ልናስተናግዳቸዉና ልናገለግላቸዉ ይገባል::» በማለት በጋራ ተወያይተዋል::

በማስከተል በግል ህክምና የሚሰሩት ደግሞ « እኛ በግል ህክምና የምንሰራ ባለሙያተኞች ከፍ ያለ ገቢ ለማስገኘትና በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመክበር እንዲሁም በአጭር ጊዜ ዉስጥ የራሳችን የንግድ ሆስፒታል ለመክፈት ስንል ስነምግባር በጎደለዉ መልኩ ምርመራ ሊደረግበት የማይገባዉን የተለያየ ምርመራ ዉጤት እንዲቀርብ በማዘዝ የማያስፈልግ ወጭ በሕዝቡ ላይ ጭነናል:: ሙያችንን ልክ እንደ ንግድ ስራ በመመልከት በአንዴ የምነበለጽግበትን መንገድ ነዉ የምንፈልገዉ እንጂ ወገናችንንና ቤተሰባችንን የምናክም መሆኑን ዘንግተነዋል:: በመሆኑም ከእንግዲህ ታካሚዎችን እንደ አባቶቻችን

እናቶቻችን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በመቁጠር በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል ቃል እንገባለን» በማለት በመንግስትና በግል የህክምና ተቋም የሚሰሩ የተለያዩ የጤና ባለሙያተኞች ስምምነት ያደረጉ ቢሆንም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ የቅንና የእዉነት ተግባር ተቃዋሚ ነኝና የአፍ ዉይይት ብቻ እንዲሆን አድርጌ እስከአሁን ድረስ ተግባራዊ እንዳይሆንና ህመምተኛዉም እንዲማረር አድርጌያለሁ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በየትምህርት ተቋሙ ያሉ መምህራን በትምህርት አሰጣጥና በተማሪዎች ጉዳይ በጋራ ተሰብስበዉ ዉይይት ያደረጉ ሲሆን፤ በዉይይታቸዉም « እኛ መምህራን ከማንኛዉም ሙያ በላይ ትዉልዱን በእዉነተኛ አስተሳሰብና ሕይወት ልንቀርጸዉ የሚገባና አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተሳሰብ እንዲኖረዉ እንዲሁም እግዚአብሔር መፍራት ባለበት ሕይወት እንዲመላለስ ማድረግ ሲገባን የመንግስትን ፖሊሲና ፖለቲካ ተግባር ለማስፈጸም ስንል ኅሊናችን ሳይፈቅድ በዉስጣችን በተሰገሰጉ ካድሬዎች አማካይነት በተቃራኒዉ ተግባር ተሰልፈናል። ይኸዉም ገና ከህጻንነት እድሜ ጀምሮ ትዉልዱ በዘረኝነትና በጎጠኝነት አስተሳሰብ እንዲያድግ አለቆቻችን ባመጡልን በዓለም ላይ ተሰምቶም ታይቶም የማይታወቀዉን «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን ኅሊና ማሸጫ ቋንቋና የአባልነት ማጥመቂያ መንፈስ ኅሊናቸዉ ዉስጥ እየዘራን በዘፈንና በዳንኪራ እያሳበድን ይኸዉ በአገሩ ላይ፣ በሰንደቅ ዓላማ ላይ፣ በአምላኩ ላይ ዐመጻና ክህደት የሚፈጥር ርኩሰትን የሚያነግሥ ትዉልድ አፍርተናል።

አሳዛኙና አስገራሚዉ ደግሞ ተማርን ተመራመርን የተባልን ሰዎች ነን፤ ከታች ከመዋዕለ ህጻናት ጀምር እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያለን መምህራን የመንግስት እንደራሴ ሆነን የመሪያችንን አንደበት አንደበት፣ መንፈሱን መንፈስ አድርገን ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት እንዲመች አድርገን ትዉልዱን እየቀረጽን ያለነዉ። ወላጆቻችን አንዳች ሳይማሩ እናት አገራቸዉን ኢትዮጵያን፣ የተቀደሰዉን ሰንደቅ ዓላማቸዉን፣ ፈጣሪቸዉን አላስካዱም፣ አላጥላሉም፣ ዐመጻም አላስፈጸሙም። እኛ ግን የዐመጻኛዉና የከሃዲዉ መንግስት አገልጋይ ሆነን በየትምህርት ተቋሙ ትዉልዱን ከእዉነት አርቀነዋል። የፈጠረዉን አምላክ አስክደነዉ «የዘር ሐረጎችህ አዳምና ሔዋን አይደሉም። ፈጣሪህም አንዱ እግዚአብሔር አይደለም። ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ አሁን ላለህበት ደረጃ የበቃኸዉ፤ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣችህ ተፈጥሮ ነች፤ እንደፈለክ በዚህ ምድር ላይ ተመላለስ እንጂ «መንግስተ ሰማያት፣ ገነት፣ ሲኦል፣ ገሃነመ እሳት» የሚባሉት የገዥ መደቦች ለመጨቆኛ ያመጡት ነዉ» በማለት ከሰዉነት ባሕርይ አስወጥተነዋል። በዚህም ምክንያት ክብሩ ታላቅ የነበረዉ የመምህርነት ሙያችን ሞገሱ ተገፎ እኛም በተማሪዎቻችን እየተናቅን እንገኛለን።

ስለዚህ ከእንግዲህ መንግሥት ከፈለገ ለእሱ ጨለማ አገዛዝ የሚመች ትዉልድ ካገኝ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ትምህርት ያስተምራቸዉ እንጂ የቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከእንግዲህ አናሳምጽም፤ እግዚአብሔር መፍራት ያለበትን ትምህርት እንዲሁም በሥጋቸዉም በነፍሳቸዉም የሚጠቀሙበትን እዉቀትና ጥበብ ብቻ ነዉ የምናስተምረዉ

እንጂ ዳግም የካድሬነት ተግባር አንፈጽም» በማለት በአንድ አቋም የተስማሙ ቢሆንም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ስለ ድፍረት ዉይይታቸዉና እንደራሴዎቼ የሆኑትን መሪዎች ፣ ባለሟሌ የሆኑትን ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ዉዶቼ የሆኑትን ካድሬዎች ስላጣጣሉብኝና ስለናቁብኝ እንዲሁም የጨለማዉ ተግባሬን አናስፈጽምም በማለታቸዉ ዋንኛ አስተባባሪዎችን ለአለቆቻቸዉ በዉዶቼ አሳሳቢነት ወደ እስርና ስደት ዳርጌያቸዋለሁ።» ይላል ዓለምን እንፈለገዉ እያሽረከረ ያለዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ።» በማለት ቀርቧል

ከላይ እግዚአብሔር እንድናዉቀዉ ያደረገዉ በተለያየ ሙያ ዉስጥ የተሰማራን ሰዎች እየሰራን ያለነዉ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን እንጂ አገራዊና ወገናዊ ስሜት ኖሮን እንዲሁም ቅንነትና እዉነተኛነት ተላብሰን እንዳልሆነ ነዉ። በመሆኑም አሁን ያለነዉ ትዉልዶች ከጨለማዉ ከዲያብሎስ ሥርዓት አስተሳሰብና ሕይወት ራሳችንን ለይተን እግዚአብሔርን በማፍቀርና በመፍራት ሕይወት ዉስጥ በመሆን በቅንነት፣ በእዉነት፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በትጋት፣ ሁሉም «ወገኔ፣ አባቴ፣ እናቴ፣ ወንድሜ፣ እህቴ፣ ልጄ ናቸዉ» በሚል ስሜት ሕዝቡን ልናገለግልና ከችግርና ከጉስቁልና ሕይወት ልንለየዉ ይገባል እንጂ፤ አሁን በሚታየዉ ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ ዉሸት፣ ማጭበርበር፣ መጠላለፍ፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ስንፍና፣ ባጠቃላይ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ፍሬዎች በሆኑት የምንመላለስ ከሆን እንኳን ለሌላዉ ልንተርፍ ይቅርና ለራሳችንም አንሆንም። ቀጣይ ትዉልዱም ለሞት ሞትና ለመቀመቅ ሕይወት ነዉ የምናዳርገዉ። ስለዚህ በሥጋችንም በነፍሳችንም በምንጠቀምበት ሕይወትና ተግባር ላይ እንሰለፍ። » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ሦስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: አንዳንድ አገልጋዮችና አማኞች ወደዘመናዊ ሕክምና ሄዶ መታከምና መድኃኒት መጠቀም በእግዚአብሔር ላይ አለመተማመን መሆኑን የሚናገሩ አሉ:: ለዚህ ያሎት አስተያት ምን ይመስላል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በማንኛችንም መታወቅ ያለበት ሊያድነን የሚችለዉ እምነታችን ነዉ እንጂ ሰዉ ወይንም ሕክምና ወይንም መድኃኒት አይደለም:: እዉቀቱንም፣ መድኃኒቱንም የገለጸዉና የሚገልጸዉ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች አይደሉም:: ሰዎች መሳሪያ ለመሆን በቅተዉ በመገኘታቸዉ እግዚአብሔር ብናምነዉም ባናምነዉ ፍጡሮቹ ነንና በርኅራኄዉ የተለያዩ ሕክምናዎችና መድኃኒቶችን ለትዉልዱ ፈጥሯል:: ታዲያ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ ነዉ ሕክምናዉ ሕክምና መድኃኒቱም መድኃኒት የሚሆነዉና የምንድነዉ እንጂ ስለታካምንና መድኃኒት ስለወሰድን ብቻ አንድንም:: ስለዚህ ትምክታችን ሆነ እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መሆን አለበት እንጂ ፍጡር በሆነዉ ሰዉ ሆነ ሕክምና እንዲሁም መድኃኒት ላይ መሆን የለበትም::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ከቀላል እስከ ከባድ በሽታ፣ ከራስ ምታትና ዉጋት እስከ ራስን መሳት ድረስ የሚያመጡ በሽታዎች ምንጫቸዉ ሁሉ ከቫይረስ እጅግ እጅግ የረቀቁት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ናቸዉ:: ነገር ግን እኛን የሚጎዱንና የሚያሳምሙን እንደ ባሕርያቸዉ ረቂቅነት ሳይሆን በሌላ ረቂቅ አካል ወይንም በዐይናችን በሚታይ አካል ወይንም በአጉሊ መነጽር በሚታ አካል ነዉ:: ለዚህም ነዉ እንደ ቫይረስ ዓይነቶቹን በመሳሪያም መመልከት የማንችለዉ፤ እንዲሁም እንደ ኮሶ፣ ወስፋት የሚሳሰሉትን በሥጋዊ ዐይናችን መመልከት የምንችለዉ፤ እንደ አሜባ፣ ባክቴሪያ የመሳሰሉትን በአጉሊ መነጽር መመልከት የቻልነዉ:: ታዲያ እግዚአብሔር በገለጸዉ እዉቀትና ጥበብ እነዚህ ርኩሳን መናፍስት የተገለጹበት ረቂቅ ሆነ ግዙፍ እንዲሁም በአጉሊ መነጽር የሚታየዉ አካላቸዉ ሊሞት፣ ሊዳከም፣ ኃይሉ ልምሾ ሊሆን ይችላል:: እንደተፈጥሮ ረቂቅ አካልነታቸዉ የሚያጠቁንና ጉዳት የሚያደርሱብን ከሆነ ልንድን ሆነ ልንፈወስ የምንችለዉ በሥጋዊ እዉቀት በተገኘ ሕክምና ሆነ መድኃኒት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በሥጋና ደሙ፣ በጠበል፣ በእምነት ነዉ:: ለዚህም ነዉ ልክፍት፣ አእምሮ ሕመም፣ ራስን መጣል፣ እንዲሁም ኤድስ፣ ካንሰር፣ ... ወዘተ የመሳሰሉት ሕመሞች ዘመናዊዉ ሕክምናና መድኃኒት ሊያድናቸዉና ሊፈዉሳቸዉ ያልቻለዉ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ቤትና በእግዚአብሔር መሳሪያ ርኩሳን መናፍስት እንደ ተፈጥሯቸዉ ረቂቅነት እንዲያዙና እንዲታሰሩ፣ እንዲቀጡና እንዲቃጠሉ፣ እንዲሁም ከበሽተኛዉ እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: በተለያየ መገናኛ (በማስ ሚዲያ)ና በስብሰባ እንዲሁም በተለያዩ ስልጠናዎች እንዲሁም በተለያዩ እምነት ተወካዮች ዘንድ ስለ ኤድስ ይሰበካል:: እንዲሁም ሰዎች የተለያዩ መከላከያዎችን እንደ «ሕይወት ትረስትና ሴንሰሽን» ኮንደም «ተጠቀሙ» እያሉ በቴሌቭዥን፣

በሬዲዮን፣ በማስታወቂያ በመሳሰሉት በየጊዜዉ ይቀርባል:: ስለዚህ ጉዳይ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ሌላዉ ዓለም ስለ ጉዳይ በዓለማዊ መንገድ ለመፍታት ቢሄድ ብዙም አያስደንቅም፤ አያሳዝንም:: ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ በዲያብሎስ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆኑ፣ አሕዛባዊ ሕይወት ስለሚኖሩ፣ ተስፋቸዉ ምድራዊ ብቻ ስለሆነ፣ ለሕያዉነት ዘመን እንደሚኖሩና ሕያዉ ነፍስ እንዳለቸዉ ስለማያዉቁ፣ እንዲሁም ስላላስተዋሉ ነዉ:: የማያስገርመዉና የሚያሳዝነዉ በቅዱስ ኪዳኗ በሀገር እግዚአብሔርና በቅድስት ድንግል ማርያም አስራት አገር፣ በዓለም መንገድ መፍትሔ ለመፈለግ መሄዳቸዉ ነዉ:: በተለይ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ተጠሪዎችና አገልጋዮች እንዲሁም አማኞች የጨለማዉ ገዥ ስብከት መከናወኑ ነዉ::

ይህን ለማለት የቻልኩት እንኳን የረቀቁ ኤድስ በሽታ ቀርቶ ሌሎች በሽታዎች ሁሉ ምንጫቸዉ ርኩሳን መናፍስት መሆናቸዉ እየታወቀ፤ የኤድስም በሽታ በሰዉ ዘሮች ላይ የታዘዘዉና ርኩሳን መናፍስት እንዲሰለጥኑ የተፈቀደላቸዉ እግዚአብሔር አምላክ «የሰዉ ዘሮች እኔን ባያምኑና ባይፈሩ እንኳ ኤድስን ፈርተዉ ከግብረ ሰዶምና ከዝሙት እንዲሁም ከአመንዝራነት ይከልከሉ» በማለት ነዉ:: ይሁንና ደንዳናዎቹ የሰዉ ዘሮች መከላከያ መድኃኒት መፍጠር ሲሳናቸዉ ዝሙቱንና አመንዝራነቱን ለማስቀጠልና ለማስፋፋት እንዲሁም ትዉልዱን ለዝሙትና ለአመንዝራነት ለማደፋፈር «ለአስተማማኝ ሕይወት፤ ሕይወት ትረስት ኤድስን የመከላከል ብቃት አለዉና ተጠቀሙ:: ሴንሴሽን የርካታ ምንጭ ነዉና በእርሱ እየተጠቀማችሁ ዝሙትን ፈጽሙ... ወዘተ» እየተባለ የዲያብሎስ አገልጋይ በሆነዉ መንግሥት ቁጥጥር ዉስጥ ባለዉ በቴሌቭዥንና በሬዲዮን ፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ ... ወዘተ ይተዋወቃል:: እንዲሁም ለዝሙትና ለሴሰኝነት የሚያነሳሳ ዘፈንና ዳንኪራ፣ ፊልም በግልጽ ይቀርብበታል:: ይህ ተግባሩ ደግሞ መንግሥት በግልጽ ፈጹም የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፈጻሚና አስፈጻሚ መሆኑን ይመሰክርበታል:: የዲያብሎስ አገልጋይ መሆኑን ይገልጠዋል::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ረቂቃኑን ርኩሳን መናፍስት በዚህች ምድር ዉስጥ የሚገድባቸዉና የሚከላከላቸዉ አካል የለም:: ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ እኛ ደንዳናነትና ጠማማነት እንዲሁም ስንፍናና ድክመት ሳይመለከት በቸርነቱና በርኅራኄዉ «ይከላከልልናል» በማለት አምነን ስለተጠቀምበት ሊከላከልልን ቻለ እንጂ ርኩሳን መናፍስትን አንዳች ሊከላከል አይችልም:: ምክንያቱም ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) የተገለጹበት አካል በዚህች ምድር ዉስጥ ካሉት ፍጥረታት ረቂቅ ስለሆነ እንኳን ላስቲክ ከዚያ የበለጠ ነገር እንኳ ቢኖር አይከላከላቸዉም:: ስለዚህ ትዉልዱ በዲያብሎስ ስብከት ሳይታለል ራሱን ከዝሙትና ከአመንዝራነት፣ ከሴሰኝነት መጠበቅ አለበት:: «የሃይማኖት ተጠሪና አገልጋይ ነን» የሚሉት እንደ ምድራዉያኑ ባለሥልጣናት ሌት ተቀን ሐሳባቸዉ ገንዘብ ላይ በመሆኑ ለገንዘብ ሲሉ ለመንግሥት ዋና መሳሪያ በመሆን የዲያብሎስን ስብከት አስፋፍተዋል፤ ትዉልዱም ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ላይ እንዲያተኩር አስደርገዋል:: በተለያየ መገናኛ ብዙኃንና በማስታወቂያ ሰሌዳ በግልጽ «ዝሙትን ፈጽሙ፣ አመንዝሩ» እየተባለ በዐይናቸዉ እያዩና በጆሯቸዉ

እየሰሙ አለመቃወማቸዉና አለማዉገዛቸዉ ሳይንስ መንግሥትን «በርታ፣ ቀጥልበት፣ እኛም እናበረታታለን፣ የእርዳታ ገንዘቡን ብቻ አምጣ» እያሉ የዓመፃ ተባባሪና ደጋፊ ሆነዋል።

እዚህ ላይ አንድ ገጠመኜን ብናገር፡ አንድ ወቅት አንድ «የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነኝ» የሚል አስመሳይ አገልጋይ በቦርሳዉ ዉስጥ ኮንደም ይዞ ታይቶ «ይህን ለምን ያዝክ?» ሲባል፤ «አንዳንዴ ለአገልግሎት ስሄድ ለምእመኑ አጠቃቀሙን ለማስተማር ነዉ» የሚል ምላሽ ነዉ የሰጠዉ። እዉነታዉ ግን ብዙ እህቶቻችንን በእግዚአብሔር ቃል እየነገደ የደፈረና በድንገት ሲረገዝበትም ፅንስ በማስወጣት የሚታወቅ ሴሰኛና ዘማዊ ነዉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ናቸዉ ሃይማኖታችንንና ቤተክርስቲያናችንን እያስነቀፉና ሕዝቡንም እያሰናከሉ ያሉት። አንደበት ስላላቸዉ ደግሞ በተለያየ ወንበር ላይ የተቀመጡትን የሃይማኖት አባቶችን ሳይቀር እየሸነገሉና እያወደሱ በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ ተቀምጠዋል።

እዚህ ላይ ሌላ ለመግለጽ የምፈልግዉ «የሃይማኖት ተጠሪ ነን ፣አባት ነን... ወዘተ» እያሉ በሃይማኖት ስም የሚነግዱና ራሳቸዉን ለማስከበርና ለማስመለክ እንዲሁም የተለያየ ሥጋዊ ጥቅም ለማግኘት በስሙ ብቻ የሚመላለሱት አስመሳይ አገልጋዮች በ፳፻፬ (2004) ዓ.ም የኤድስና አባላዘር ቀን በተቀደሰችዉ አገር ኢትዮጵያ በኣል ሲደረግለትና ሲመከርበት «በአገራችን ርኩሰቱ ሲነግሥና ሲበረታታ ምን እንባላለን? ስለዚህ ቢያንስ የግብረ ሰዶምን ተግባር እናዉግዝ» በማለት በጋራ እንደተሰበሰቡ፤ ቀድሞም ቢሆን አገልጋይነታቸዉ ለመንግሥት ነዉ እንጂ ለእግዚአብሔር ስላልሆነ የመንግሥት አካል መቶ አንድ ነገር ትንፍሽ እዳይሉ ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸዉ፤ እንደ ሃይማኖት አባትነታቸዉ ቅርፊት ሥጋን ለባሽ ሳይፈሩ «የእግዚአብሔርን እዉነት እንመሰክራለን» በማለት የዲያብሎስን ስራ ማጋለጥ ሲገባቸዉ፤ መመሪያቸዉ የአሕዛብ መመሪያ ነዉና «ተመሳስለህ ኑሩ፣ ሕሊናህ ባይቀበልም ሕሊናህን ሸጠህ ኑር... ወዘተ» በሚለዉ መመሪያ መሰረት «አይ! መንግሥት በአቋማችን ካልተደሰተማ ከእርሱ ሌላ ማን አለን» በማለት ዝምታን መርጠዉ አፋቸዉን ለጉመዉ ነበር። የሚያስገርመዉ ደግሞ እንደ ድምፅ ማጉያ መንግሥት እንደሚጠቀምባቸዉና እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚወሰዱ መሆኑን እንዲሁም ማፈሪያ ሕይወትና አቋም እንዳለቸዉ የመሰከረባቸዉን ተግባር የፈጸሙት ደግሞ «ጅግ ከሄደ ዉሻ ጮኸ» እንደሚባለዉ፤ የቀድሞ የቀለለ ተግባራቸዉ በተለያየ መንገድ ሲተቹ፤ ብልጡና መሰሪዉ መንግሥት ዓላማዉን ከፈጸመ በኋላ፤ « በሉ እንደ ፈቃዳችን ስለሆናችሁ የምትፈልጉትን ብር የምንሰጥ ሲሆን፤ አሁን ከፈለጋችሁ ስለ ግብረ ሰዶም መቃወም ትችላላችሁ፣ የስብሰባዉን ማዕከል ፈቅደንላችኋልና አሁን መለፈፍ ትችላላችሁ» ሲላቸዉ፤ ለእዉነት የቆሙ ይመስል «በእርዳታ ሽፋን ግብረ ሰዶም እንዲፈቀድ የሚጠየቀዉን እንቃወማለን... ወዘተ» እያሉ አስመሳይነታቸዉን ገልጸዋል።

ታዲያ ማንነታቸዉ አስቀድሞም በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃልና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛሙ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ አምስት በገጽ 311-313 ላይ ማንነታቸዉና ተግባራቸዉ ተገልጿል። ይኸዉም፡

«በማግስቱ ደግሞ አንዳንድ በዝሙት የሚተዳደሩ ሴተኛ አዳሪዎች በሴቶች ጉዳይ ዘርፈ የሴተኛ አዳሪዎች ችግር አስወጋጅ ዲያሬክተር ለሆኑት ጉዳያቸዉን አቅርበዋል። ይኸዉም «እናንተ ለሴቶች ነዉ የቆምነዉ፤ ለእኩልነታችሁና ለዴሞክራሲ መብታችሁ እንታገላለን» ትላላችሁ። ነገር ግን አንድ ቀን የኛ ሕይወት አሳስቧችሁ አያዉቅም። እናንተ ለፖለቲካችሁ ብቻ ሌት ተቀን የምትሯሯጡ ናችሁ እንጂ «እነዚህ እህቶቻችን በምድራዊ ኑሮዋቸዉም በሚያጎሳቁልና በሚያዋርድ ሕይወት ዉስጥ ይኖራሉ። በእግዚአብሔር ዘንድም የኃጢአት ተግባር እየፈጸሙ ነዉ ። ስለዚህ ከዚህ ሕይወት ልናላቅቃቸዉና ራሳቸዉን የሚረዱበትን ስራ ልንፈጥርላቸዉ ይገባል።» ብላችሁ አንድ ቀን እንኳ ለሥጋችን ሆነ ለነፍሳችን አስባችሁልን አታዉቁም።

ይልቁኑ እግዚአብሔርን በሚያስቆጣ ተግባር የተሰለፈዉና ለኛም ሕይወት አንዳች ስሜት የሌለዉ መንግስታችሁ በዝሙት ሕይወታችን እንድንገፋበት የሚያበረታታ ማስታወቂያዎችን በቴሌቭዥንና በሬዲዮን እንዲሁም በሕትመት ዉጤቶች ላይ እያወጣ ሲያስፈልገዉ « ሕይወት የሆነዉን ኮንደም ተጠቀሙ ኤድስ የሚባል ነገር አይደርስባችሁም» ይላል። ሲያስፈልገዉ ደግሞ «የደስታና የእርካታ ምንጭ የሆነዉን ሰንሴሽን ተጠቀሙ።» እያለ በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ዳንኪራ እያጀበ ትዉልዱን ለዝሙት እያነሳሳና እያገፋፋ እንዲሁም እያደፋፈረ ነዉ። ምንም የማያዉቁት ሴቶችና ወንዶች ቢያንስ የእግዚአብሔር ቁጣ የሆነዉን ኤድስ በሽታ እንኳ እንዳይፈሩ « ኮንደም ኤድስን የመከላከል ብቃት አለዉና ዝሙትን አትፍሩ፤ ድፈሩ።» እያለ ሌት ተቀን የሚለፍፍ ነዉ።

የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግም የሃይማኖት አባቶችና የእምነት ተቋማት ይህ በግልጽ የዲያብሎስ ስራ የሆነዉን የርኩሰት ማስታወቂያ ሊያስቆሙና ሊያወግዙ ሲገባ፤ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚ ከሆነዉ መንግስት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በዐመጻዉ ስራ ተሰልፈዋል። እርዳታንና ገንዘብን ለማግኘት ሲሉ በአጭሩ «አታመንዝር፤ አትዘሙት» በሚለዉ የእግዚአብሔር ሕግ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለዉን ችግርና በሽተኞቹንም « ንስሐ ግቡ፤ ቅዱስ ቁርባንን ተቀበሉ፤ ጠበሉንና እምነቱን ተጠቀሙ፤ ራሳችሁን ጠብቁ፤» በማለት መምከርና ማጽናናት ሲገባቸዉ፤ እንዲሁም ሕዝቡንም «በኤድስ የተያዘዉን ሆነ በሌላ በሽታ የተያዘዉን ሰዉ አድሉና መገለል አታድርጉ፤ ወገኖቻችሁ ናቸዉና እርዷቸዉ፤ ተንከባከቧቸዉ፤ አፍቅሯቸዉ።» በማለት ሊያስተምሩ ሲገባ፤ በጨለማዉ ገዥ በሚመራዉ ሥርዓት ዉስጥ በመመላለስ አብረዉ ከመንግስት ጋር በመሰለፍ እንደ ትልቅ ስራ «ኤድስን እንከላከል፣ የአባላዘር በሽታ እንከላከል» እያሉ ወሬ በማራገብ በእግዚአብሔር ቁጣ ላይ ከንቱ

ሥጋዊ መጠበብ የሚያደርጉና በተዝዋዋሪ ዝሙት የሚስፋፋበትን መንገድ የሚደግፉና የሚያበረታቱ እንዲሁም ግብረ ሰዶምነትን ጭምር በይሉኝታና በጥቅም ኅሊናቸዉን አሳዉረዉ ማዉገዝ ያልቻሉ ለስልጣናቸዉና ለሥጋዊ ክብራቸዉ የቆሙ ናቸዉ::

እኛ ግን ከምድሩም ሳይደላን ከሰማዩም ሳንሆን ለሥጋችንና ለነፍሳችን የሚያስብልን ግለሰብና አካል አተን በአየር ላይ ተንሳፈን የቀረን ምስኪኖች ነን:: እናንተ በእዉነት ለሴቶች የምታስቡ ቢሆን ኖሮ የፖለቲካ ወሬያችሁን ትታችሁ ከዚህ ሰቆቃ ሕይወት የምንገላገልበትን ኑሮ ታመቻቹልን ነበር:: መንግስታችሁ ደግሞ «የዴሞክራሲ መብታችሁን ስላጎናጸፍናችሁ ማንኛዉንም መብታችሁን በመጠቀም ማመንዘርና መዘሞት ቀርቶ በግልጽ የሥራ መተዳደሪያና የገቢ ማግኛ ልታደርጉት ትችላላችሁ::» ብሎ የሕግ ሽፋን ስለሰጠን ሳንፈራና ሳንሸማቀቅ በግልጽ እንደ ስራ መስክ ቆጥረነዉ ገላችንን እንሸጣለን:: በሕግ እንኳ ብንገደብ ሌሎች አማራጭ ስራዎችን እንፈልግና ሕይወታችንን እንለዉጥ ነበር:: እናንተም ሆናችሁ መንግስታችሁ ሌት ተቀን የምትሯሯጡት የሰዎችን ኅሊና አደንዝዛችሁ የራሳችሁን መሰሪ ዓለማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ እንጂ የሰዉ ሕይወት አንዳች የሚያሳስባችሁ አይደለም:: ከዚያም አልፎ አንዳንዶች ባለስልጣናትና ካድሬዎች ዉሿቸዉንና አዳራቸዉን ከኛጋ እያደረጉ ዝሙት ስራችንን ያበረታታሉ፤ ይደግፋሉ::» በማለት በምሬት ብሶታቸዉን አቅርበዋል::

ዲያሬክተሯም ሐፍረትና ኀዘን ተሰምቷቸዉ ወደ ልባቸዉ በመመለስ «ለካስ መንግስታችን ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን እኛን ካድሬዎቹን ጭምር አደንዝዞናል:: ከዚህ በኋላ እነዚህን እህቶቻችንን ከዚህ ጎስቋላና መከራ ሕይወት ልናወጣቸዉና የስሜት ጉዳታቸዉንም ልንክሳቸዉ ይገባል:: በየቦታዉ የወደቁ ወገኖቻችን የሆኑትን አባቶቻችንን እናቶቻችንን ወንድምና እህቶቻችንን ልናስባቸዉ ይገባል እንጂ ነጋ ጠባ የፖለቲካ ስራ መስራት የለብንም::» በማለት ለኅሊናቸዉ በመናገር፤« እህቶቼ ንግግራችሁ ዓይኔን ከፍቶልኛል ለወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብኝ አስተምራችሁኛል:: እስከአሁን ድረስ ሴቶች እያልን በስማችሁ በመነገዳችን ይቅርታ አድርጉልኝ:: ከዚህ ሕይወት የምትለዩበትን መንገድ እናመቻቻለን::» በማለት የሚያጽናና መልስ የሰጡ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ለኅሊናቸዉ የነገሩትንም እዛዉ ኅሊናቸዉ ጋር ሆኜ በደንብ አዳምጫለሁና ከዚያ በተጨማሪ መልካም ምላሽ በመስጠታቸዉና ለእንደራሴዎቼ ዘብ ሆነዉ የሚያሳፍርና የሚያዋርድ መልስ ባለመስጠታቸዉ ተናድጄ ስለነበር በታማኝ ካድሬዎቼ አማካይነት ከበላይ ላሉት ባለስልጣናት ሪፓርት አስደርጌ ከወንበራቸዉ እንዲሻሩና ታማኝ ዉዶቼ እንዲመደቡ አስደርጌያለሁ::» በማለት ቀርቧል

ጠያቂዉ አገልጋይ፡ እዚህ ላይ አያይዤ የምጠይቀዉ በአንዳንድ አገረ ስብከት መነኩሴ ለመምሰል ቆብ ይደፉና የተለያየ የኃላፊነትና የአስተዳዳሪነት ወንበር ከያዙ በኋላ በዝሙት ይልከሰከሳሉ:: ምእመኑ ከእዉነተኛ አገልጋዮች ጋር በመሆን ተግባራቸዉን እየገለጸና እጅ ከፍንጅ እየያዛቸዉ ከሥልጣናቸዉ መሻርና መወገዝ እንዲሁም በሕግ ሊጠየቁ ሲገባ ሥልጣናቸዉ ይጸናላቸዋል፤ ወይንም ወደ ሌላ ሀገረ ስብከት እንዲሳወሩ ተደርጎ በኃላፊነት ላይ ተመልሰዉ እንዲያገለግሉ ይደረጋል:: የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ሆኑ ሌሎች ከፍተኛ ኃላፊዎች ይህን ዉሳኔ ለምን ይፈጽማሉ? እንደ ሃይማኖት አባትነታቸዉ እንደነዚህ አሰናካይና አስመሳይ አገልጋዮችን መለየትና ማዉገዝ ሲገባ ሌላ ሹመት የሚሰጧቸዉና መረጃ እየቀረበባቸዉ ስለ እነርሱ ለምን ጥብቅና ይቆሙላቸዋል?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡ በአሁን ሰዓት ከጥቂቶች አባቶችና ወንድሞች በስተቀር ብዙዎች መንፈሳዊዉን ወንበር የሚፈልጉት ለሥጋዊ ጥቅም፣ ለመከበር፣ ለመግነን፣ የራሳቸዉን የሥጋና የደም ስሜትና ዓላማ ለማሳካት ስለሆነ ነዉ:: እነዚህ ዝሙትን ሆነ ስርቆትን የሚፈጽሙ አስመሳይ አገልጋዮች ሊወገዙና በሕግ ሊጠየቁ ያልቻሉት እነሱን እዛ ቦታ ላይ የመደቡ ሰዎች በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ የተገናኙ ይሆናል፤ ወይንም እነርሱም በዚህ በዝሙት፣ በስርቆት ዉስጥ ተሰማርተዉ ይሆናል፤ ወይንም ከእነርሱ ጋር በተለየ ጥቅማጥቅም ተገናኝተዉ ሊሆን ስለሚችል ነዉ:: በዚህም ምክንያት ጥብቅና በመቆም በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት እንዲፈጽሙ የሚያስደርጉት:: እግዚአብሔር ግን ታግሶ ታግሶ እንደነዚህ ዓይነቶቹንና ልክስክሶቹን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ በቁጣዉ ወደ እዉነተኛዉ መቀጫ ቦታ ጠርቷቸዋል:: ሌሎችንም በቁጣዉ እንደሚጠርጋቸዉና እንደሚያጸዳቸዉ ይገመታል::

ጠያቂዉ አገልጋይ፡ ለእኔ የሚገርመኝና ለሕሊናዬ የሚከብደኝ ሰዉ «ጳጳስ፣ መነኩሴ፣ አስተዳዳሪ፣ ቄስ፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ፣ መምህር፣ መርጌታ፣ ዲያቆን... ወዘተ» እየተባለ እንዴት በዝሙት ይልከሰከሳል? እንዴት አድርጎ መለኮት የተዋሐደዉን ቅዱስ ሥጋና ደም ይቀበላል? በምን ክብረ ሕሊናዉ(ሞራሉ) ነዉ ሌላዉን ሊያስተምርና ሊሰብክ የሚችለዉ? እግዚአብሔርስ በቤቱ ሲደፋፈሩትና ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን ሲያቃልሉ እንዴት አይቀስፋቸዉም?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡ ቁጥራቸዉ ትንሽ ቢሆንም እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ ሥልጣነ ክህነታቸዉንና ኃላፊነታቸዉን አክብረዉ እያገለገሉ ያሉ እዉነተኛና ታማኝ ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ መርጌታ፣ መምህራን፣ መዘመምራን፣ ሕጋዊ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ባጠቃላይ በተለያየ ኃላፊነትና አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች እንዳሉ መታወቅ አለበት:: ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ይህ ሰዉ «ጳጳስ፣ መነኩሴ ፣ አስተዳዳሪ፣ ቄስ፣ ሰባኪ፣ ዘመሪ፣ መምህር፣ መርጌታ፣ ዲያቆን... ወዘተ ነዉ» ብለዉ ማንንም አይፈሩም:: ይልቁኑ እንደነዚህ ዓይነቱን ለማሰናከልና ለመጣል እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ለማጣላት ነዉ የሚተጉት:: ምክንያቱም ምእመናንን እያገለገሉ፣ ስለ እግዚአብሔር እየመሰከሩ፣ እዉነትን እየገለጡ

ስለሚያስቸግሯቸዉና እንደ ዋና ጠላት ስለሚመለከቷቸዉ፤ በሚችሉት አቅም ሁሉ የተለያየ ፈተና በማምጣጥ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ለመዳረግ ነዉ ቀን ከሌሊት የሚተጉባቸዉ:: እነዚህ አገልጋዮች በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት ካልተጉና ራሳቸዉን በመግዛት ሕይወታቸዉን በትህትና፣ በፍቅር፣ በቅንነት፣ በእዉነት፣ በመልካምነት ካልመሩ በስተቀር በአንዱ የስሜት ድክመታቸዉ በመግባት ይፈትኗቸዋል፣ በመጨረሻም ይጥሏቸዋል::

ርኩሳን መናፍስት ለዐይን ቅጽበት ያህል እንኳ ከሰዉ ሕሊናና አካል ስለማይለዩ እንኳን ለሰዓታትና ለደቂቃት ኃጢአትን ማሰብ አይደለም ለሰከንድ እንኳ ብናስብ ወዲያዉ ነዉ ያንን ሐሳባችን እዛዉ ሕሊናችን ወይንም ነፍሳችን ጋር ሆነዉ ስለሚያዳምጡን ያንን ያሰብነዉን ኃጢአት እንድንፈጽም የሚገፋፉንና ዉጤቱን እንዳናስተዉል የሚያደርጉን:: ስለዚህ ማንም ይሁን ማን በመጀመሪያ መጠበቅ ያለበት ከሐሳብ ኃጢአት መሆን አለበት:: ያኔ ነዉ ሰይጣናት ቦታ የማያገኙትና እንደ ኳስ እየነጠሩ የሚመለሱት:: እኛም ከእግዚአብሔር ኃይልን እየተጎናጸፍን በጸጋ ላይ ጸጋ የሚጨመርልን፤ እንዲሁም ክብርና ሞገስ አግኝተን ለሰማያዊ መንግሥት የምንበቃዉ::

የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ግን በድፍረት ሆነ በሥጋ ድካም በኃጢአት የወደቁ አገልጋዮች በእዉነተኛ ንስሐ መመለስና ያሰናከሉትንም ምእመን በግልጽ ይቅርታ መጠየቅ ሲገባቸዉ፤ እንደገና የድፍረት ኃጢአት ይፈጽማሉ:: አገልግሎታቸዉንም እንደ ገቢ ማግኛ ስለቆጠሩትና እንደ ማንኛዉም ስራ መስክ ስለሚያዩት ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን በድፍረት ይቀበላሉ፤ ያቀብላሉ:: ታዲያ ይህ ድፍረታቸዉ ለከፋዉ ለመከራ ሥጋና ለመከራ ነፍስ ነዉ የሚዳርጋቸዉ እንጂ ከእዉነተኛዉ ከእግዚአብሔር ፍርድ አያመልጡም:: እግዚአብሔር ደግሞ እንደ ሰዉ ለፍርድ የማይቸኩል ስለሆነ ነዉ ኃጢአታቸዉንና ድፍረታቸዉን እየተመለከተ ዝም የሚለዉ እንጂ ሳይመለከት፣ ሳያዝን፣ ሳይቆጣ ቀርቶ አይደለም:: ነገር ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ የንስሐ እድል ይሰጣቸዉና በዚያ እድል መጠቀም ካልቻሉ አይቀጡ አቀጣጥ ነዉ የሚቀጣቸዉና ፍዳቸዉን በምድርም በሰማይም የሚያሳያቸዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ብዙ ወገኖቻችን በኤድስና አባላዘር በሽታ ተጠቅተዋል፤ ብዙዎችም እንኳን ይሞታሉ «አፈር ይነካቸዋል እንዴ!» የሚባሉ ረግፈዋል:: ያ ደም ግባትና ዉበት በቁማቸዉ እያዩት ጠፍቶና ተበላሽቶ ወደ መቃብር ወርደዋል:: ከእነርሱ አልፎ ችግሩና ጉስቁልናዉ ወደ ልጆቻቸዉና ቤተሰባቸዉ በተለያየ መንገድ ተላልፏል:: በመሆኑም በእርሶ እምነት ለበሽታዉ ሆነ በበሽታ ለተጠቁ ወገኖቻችን ምን መደረግ አለበት ብለዉ ያስባሉ? ይመክራሉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ሥጋ ለባሽ ሁሉ ደካማ ነዉና በተለያየ መንገድ በሰይጣናት ፈተናና ራሱም በሚያመጣዉ ፈተና ሊወድቅ፣ ሊጎሳቆል ይችላል:: ነገር ግን ደካማነቱንና ኃጢአተኛነቱን አምኖ ፈጣሪዉን ይቅርታና ምሕረት እንዲሁም ፈዉስ መጠየቅ ይኖርበታል እንጂ በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት መፈጸም የለበትም:: « ኮንደም ወይንም ሰንሴሽን ኤድስን ይከላከላል» እያለ በዲያብሎስ ስብከት ተታሎ ራሱን ለዝሙትና ለአመንዝረኛነት

ማሰለፍ የለበትም። ይልቁኑ ይህን የዲያብሎስ አገልጋዮች ስብከት ሊቃወመዉና «ከዝሙትና ከአምንዝራነት ራሳችሁን ጠብቁ፤ አንድ ለአንድ ብቻ ተወሰኑ» በማለት ሊመሰክርና ሊያስተምር ይገባል።

በበሽታዉ የተያዙትም አዳኙና ፈዋሹ እግዚአብሔር ስለሆነ እዉነተኛ ንስሐ ገብተዉ ቅዱስ ሥጋዉን ክቡር ደሙን ይቀበሉ፣ ጠበሉን እምነቱን ይጠቀሙ፣ እንዲሁም አስፈላጊዉን ሕክምና አድርገዉ የሚታዘዝላቸዉም መድኃኒት በአግባቡ ይጠቀሙ። በበሽታዉ ያልተያዝንም እግዚአብሔር ከበሽታዉ በቸርነቱና በምሕረቱ ስለጠበቀን ነዉ እንጂ እንደነሱ ታማሚ ልንሆንና በሞት እንደተወሰዱት ወገኖቻችን ልንወሰድ እንችል እንደነበረ አስተዉለን፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ስለጠበቀን እያመሰገን፣ በሕመም የተያዙትን ወገኖቻቸዉንን ግን እንደ ወገንነታቸዉ አስፈላጊዉን እንክብካቤና እርዳታ ልናደርግላቸዉና እንዲሁም ፍቅርና አክብሮት ልናሳያቸዉ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ራሳችንን ከዝሙት፣ ከአመንዝራነት፣ ከሴሰኝነት መጠበቅ ይኖርብናል።

ሌላዉ በአገልጋዮች ሆነ በአማኞች ዘንድ መታወቅ ያለበት ነገር በእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ላይ ማንም ይሁን ማን መደራደርና ማስቀረት አይችልም። ምክንያቱም የሚታየዉ እንደ ሃይማኖት ነዉና። «አታመንዝር፣ አትዘሙት» የሚለዉ የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ስለሆነ እንደ ሁኔታዎችና አስገዳጅነት የሚሻሻልና ሰፊ መንገድ የሚፈለግለት አይደለም። ሕጉንና ትእዛዙን ያፈረሰና የጣሰ በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍልበታል። እንኳን ሕግና ትእዛዝን መጣስ አይደለም እንደ አስፈላጊነቱና አስገዳጅነቱ ማሻሻያና ለዉጥ የሚደረግበትን አግባብነት ያለዉን ሥርዓት በትዕቢትና በንቀት የሚጥስ ሰዉ እንደ ሕግ አፍራሽ ነዉ የሚቆጠረዉና የሚፈረድበት። ነገር ግን ሕሊናቸዉ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመራ ሰዎችና የሚመለከተዉ አካል ሥርዓትን እንደ አስፈላጊነቱ ሊለዉጥና ሊያሻሽል ይችላል።

አንድ ቀላልም ከባድም ምሳሌ ብሰጥ፤ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ሊቀደስ የሚችለዉ አምስት አገልጋዮች ሲሟሉ ነዉ። ነገር ግን በበረኃ ወይንም በዉጭዉ ዓለም አገልጋይ ጠፍቶ ሁለትና ሦስት፣ አራት አገልጋይ ከተገኘ ነፍሳትን ለእግዚአብሔር ልጅነትና እንዲሁም ለቅዱስ ቁርባን ማብቃት ይበልጣልና «አምስት አገልጋይ ካልተሟሏ ክርስትና ማንሳቱም አይስፈልግም፤ ምእመኑም ቅዱስ ቁርባን መቀበል አይገባዉም» በማለት ከነፍስ ድኅነት በላይ ለሥርዓት ቅድሚያ መስጠቱ ለእግዚአብሔ መቅናትና እዉነተኛ አገልጋይነት መሆንን አያሳይም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከማንም በላይ ያለዉን ችግር ያዉቃልና። ምእመኑ ሆነ አዲስ የተወለዱት ፍጥረታቱና ልጆቹ በስሙ መጠመቅና ከእርሱ ልጅነት ማግኘት እንዳለባቸዉ ይታወቃል። ነገር ግን አገልጋይ በመጥፋቱ «አገልጋይ ሳይሟሏ ብትቀድሱና ብታጠምቁ፣ ብታቆርቡ ዓመፃን ፈጽማችኋል» አይልም። ምክንያቱም አገልጋይ ተገኝቶ በተሟላ ሥርዓት ቢቀደስ እንኳን ፈጣሪ ፍጡሮቹ ሰዎች እጅግ ደስ ይላቸዋል። አገልጋይ ካልተገኘ ደግሞ የተሟላ አገልግሎት ባሉት አገልጋዮች ቢፈጸም እግዚአብሔር አይደለም ሰዎችም ጭምር ይደሰቱበታል። ሥርዓትን እንደ ሃይማኖትና ሕግ የሚቆጥሩ አገልጋዮችና

አማኞች፣ አገልጋይ እስካልተሟላ ድረስ በበረኃ ሆነ በዉጭዉ ዓለም ያለዉ አማኝ ልጆቹ ክርስትና ተነሱ አልተነሱ አንዳች ስሜት አይሰጠዉም፤ ሕይወታቸዉን በንስሐ እየመረመሩ ቆረቡ አልቆረቡ አንዳች ስሜት አይኖረዉም፤ የእግዚአብሔር አገልግሎት ተሰጠ አልተሰጠ አንዳች አይቆረቁረዉም፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶች ሰዎች እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን ከተከበሩና ጥቅማ ጥቅም ከተሰጣቸዉ፣ ስለ ነፍስ ጥፋትና ድኅነት አንዳች ስሜት የሌላቸዉና በተቃራኒ ደግሞ የእግዚአብሔር ትእዛዝና ሕግ መጣስ ጥቅም የሚያስገኝላቸዉ ከሆነ ትእዛዙን ሆነ ሕጉን ለመሻርና ለማሻር ወደ ኋላ የማይሉ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ፡፡

ከላይ ያለዉም ምሳሌ ያነሳሁት በቅንነትና በእዉነት ለቤተክርስቲያናቸዉ እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ምግባርና ትዉፊት የሚቆረቆሩ እዉነተኛ አገልጋዮች እንዳሉ ሁሉ፤ ለሆዳቸዉና ለጥቅማቸዉ ያደሩ፣ ነገር ግን እዉነተኛ ለመምሰል የሚንቀሳቀሱና ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር የሚጋጩና የሚላተሙ ስላሉ ነዉ፡፡ ከላይ ያለዉን በእዉነት ካየነዉ ሥርዓቱ ምንም ይሁን መጠበቅ አለበት፡፡ በቅንነት ካየነዉ ደግሞ ሥርዓት የተፈጠረዉ ለሰዉ ልጆች ስለሆነ እንደ አስፈላጊነቱና አስገዳጅነቱ ሊያሻሽሉት ስለሚችሉ ነፍሳት ትልቁን ከእግዚአብሔር ልጅነትን ከሚያጡና ከቅዱስ ቁርባን ከሚለዩ አገልጋዮች እስኪሟሉ ድረስ አንዱ የሌላዉን በመሸፈን በተሟላ መልኩ አገልግሎት ቢሰጡ የተሻለ ነዉ፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ አገልጋይ ሆነ ምእመን እዉነትን ከቅንነት ጋር አጣምሮ ማየትና መጠቀም ነዉ ያለበት እንጂ አንዱን ካጎደለ ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ሊርቅና ሊላተም ይችላል፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከእዚህ ጋር በተያያዘ ከእምነትና ከሥርዓት ጋር ያለኝ ጥያቄ: አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን «በያሬዳዊ ዜማ ባልሆነ ዜማ መዝሙር ቢዘመር ምናለበት? እንደ ፕሮቴስታንት በፒያኖዋ በኦርጋን እንዲሁም በተለያዩ ዘመናዊ መሳሪያ ታጅበን ብንዘምር ምናለበት? ትዉልዱን በዚህ መልኩ ለመሳብና ወደ ቤተክርስቲያን ማቅረብ ይቻላል.. ወዘተ» የሚሉ አሉ፡፡ ይህ በእዉነትና በቅንነት ሲታይ ምን ይመስላል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ማንኛዉንም ነገር በእዉነትና በቅንነት ከተመለከትን መሪያችን መንፈስ ቅዱስ ስለሚሆን የእርሱን ሙሉ እዉነታ ይገልጽልናል፡፡ ከላይ የቀረበዉም ጥያቄ አንዳንዶቹ በየዋህነት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በዓላማ ያቀርቡታል፡፡ በእዉነት ከተመለከትነዉ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልጆች የሆን አገልጋዮች ሆነ ምእመናን እንደ ቤተክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ዜማና ትዉፊት ነዉ መመላለስ ያለብን፡፡ በቅንነት ስንመለከት ደግሞ ቤተክርስቲያን የጎደላት ልታሟላዉና ልታሻሽለዉ የሚገባት ነገር ካለ ያንን ማሟላትና ማሻሻል ይጠበቅባታል፡፡ በዜማ በኩል ስንመለከት እግዚአብሔር ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚሆን የማመስገኛ ዜማ በቅዱስ ያሬድ በኩል ለትዉልዱ ሰቷል፡፡ በመሆኑም ዜማዉ እንኳን ለኢትዮጵያዉያን ቀርቶ የዓለም ሕዝብ በቋንቋዉ ለምስጋና ሊጠቀምበት የሚገባና ከሰማያዉያን መላእክት ጋር የሚያስደምረን ስለሆነ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ የሰጠንን ዜማ በአግባቡ ጠብቀን ልንጠቀምበትና ለቀጣይ ትዉልድ ልናስተላልፍ ይገባል

እንጂ ዓለም ይህን ዜማ ስላላገኘ ወደ ዘፈንና ዳንኪራ የሚወስደዉን ዜማ እኛ ልንጠቀም አይገባም። ሌላዉ ዓለም ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና ስለመጣ የቀደመዉ የማመስገኛ መሳሪያ የሆኑት በገና፣ ከበሮ፣ ጸናጽል ስለሌለዉ በፒያኖ ቢያመስግን «ለምን ተጠቀምክ?» ልንለዉ አንችልም። እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን ከብሉይ ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔርን ስናመልክና ስናመሰግን ስለነበረ ያ የምናመሰግንበት ከበሮ፣ ጸናጽል፣ በገና እስከአሁን ድረስ እየተጠቀምንበት ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ በአገልግሎት ሂደት መቋሚያንም በመጨመሪ ለአገልግሎት እየተጠቀምንበት ነዉ። ወጣት ዘማሪያን ደግሞ መዝሙራቸዉን በክራር ጭምር እያጀቡ ሥርዓቱንና ዜማዉን በጠበቀ መልኩ እያቀረቡ ይገኛል። ታዲያ እኛ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልጆች እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት የተሟላ መሳሪያ ስላለን ሌላ ባዕድ መሳሪያ አያስፈልገንም። ምክንያቱም ዜማ ብቻ ሳይሆን መሳሪያዉ ጭምር አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ተሟልቶልናልና።

እዚህ ላይ በዓላማ የሚንቀሳቀሱ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች « ከያሬዳዊ ዉጭ በሆነ ዜማ ብናመሰግን ምናለበት? እንደ ፕሮቴስታንቱ በዘመናዊ መሳሪያ ብንዘምር ምናለበት? ጠንቋይ ከበሮን ለዲቤ ስለሚጠቀም እኛ ከበሮን አንጠቀምም ማለት አለብን ወይ?... ወዘተ» እያሉ የዋሃንን ለማሳመንና ለስዉር ዓላማቸዉ ማስፈጸሚያ የሚያቀርቡት ሐሳብ እዉነተኛነትና ቅንነት የሌለዉ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት ምግባርና ትዉፊት ለመለወጥ በሂደት ደግሞ እንደ ፕሮቴስታንት የሥጋና የደም ስሜት ማርኪያ እንዲሁም መዝናኛ ሥርዓት ፈጥረዉ ቤተክርስቲያንን ወደ አዳራሽነት ለመለወጥና ለሥጋቸዉ የሚመች እምነትና ሥርዓት ለመዘርጋት ነዉ። ሌላዉ መታወቅ ያለበት የተለያዩ የፕሮቴስታንትና መሰል ድርጅቶች የተመሰረቱት በአታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ በዲያብሎስ ሲሆን፤ ይህ መንፈስ በኢየሱስና በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ሽፋን የተቋቋመ የኢየሱስ ክርስቶስ ዋና ተቃዋሚና ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ» እያለ እያስካደና እያሰደበ ያለ ነዉ። እንዲሁም «አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ አካላት የለም። ራሱ ወልድ ነዉ መልኩን እየለዋወጠ የመጣዉ » በማለት የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በመካድ በፀረ ሥላሴ ሕይወትና እምነት እንዲመላለሱ ያደረገ ነዉ።

ለዚህም ነዉ በዚህ አስተሳሰብ ይመላለሱ የነበሩት አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች፤ « እንደ ቤተክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊትና ዜማ ተመላለሱ» ሲባሉ «አሻፈረኝ» ብለዉ «አማኑኤል ኅብረት ቸርች» የሚል አቋቁመዉ ከፕሮቴስታንት የባሱ ሆነዉ የተገኙትና አንዳንዶቹም ከቤተክርስቲያን ርቀዉ በፕሮቴስታነት እምነት ዉስጥ የገቡትና ቀሪዎቹም ቤተክርስቲያናቸዉን እንዲጠራጠሩ በመደረጉ ከቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ዉጭ በሆነ ሕይወት የሚመላለሱና ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሆነ ስለ ቅድስት ቤተክርስቲያን አንዳች ፍቅር የሌላቸዉና ይልቁኑ ጥፋቷን የሚመኙት ሆነዉ የተገኙት። ይህ ታዲያ በበላይ ሆኖ ይመራቸዉ የነበረዉ መንፈስ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ስለነበረ ነዉ እንደ ማንነታቸዉ መኖር ያቃታቸዉና በዓመፃና በክህደት ሕይወት ዉስጥ ሊመላለሱ የቻሉት።

እንደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ከሆነ ቤተክርስቲያን የጎደላት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት አስተዳደራዊ መዋቅርና እዉነተኛና ታማኝ አገልጋይና አማኝ ነዉ እንጂ እምነቷ ሆነ ሥርዓቷ እንዲሁም ትዉፊቷ ሆነ ዜማዋ እንኳን ለኢትዮጵያዉን ለዓለም የሚተርፍ ነዉ። በመሆኑም አሁን ያለዉ ትዉልድ የአስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ስዉር ሴራ ተረድቶ የቤተክርስቲኑን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊትና ዜማ ጠብቆ ለቀጣይ ትዉልድ ማስተላለፍ፣ ራሱም ሕይወቱን በንስሐ እየመረመረ በቅዱስ ሥጋዉና ደሙ ተወስኖ በመልካም ምግባር፣ በቅን ሐሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት ሊኖር ይገባዋል እንጂ «እንደዘፈን የምዝናናበትና ትዝታ ዉስጥ የሚያስገባኝ እንዲሁም ሞቅ ሲለኝ እንድጨፍር የሚያደርግ እምነትና ሥርዓት ነዉ የሚያስፈልገኝ» ማለት የለበትም። ምክንያቱም ለሥጋ የሚመቸዉ እምነትና ሥርዓት የሞት መንገድ ስለሆነና ለሥጋዉም ሆነ ለነፍሱ አንዳች የማይጠቅመዉ፣ ይልቁኑ ለመከራ ሥጋና ለመከራ ነፍስ የሚዳርገዉ ነዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ሌላዉ ጥያቄ አንዳንድ የእምነት ድርጅቶች «ለማምለኪያ እግዚአብሔር የተለየ ቦታ አያስፈልገዉም። ስለዚህ ቤተክርስቲያን፣ ታቦት የሚባል አያስፈልግም» ይላሉ። ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ በማንኛዉም ቦታ የሚቀርብለትን ጸሎትና ምስጋና የሚሰማ ነዉ። እንዲሁም «ቤቴና ቅጥሬ» ብሎ በተለየ ሁኔታ የሚያየዉና በረከቱንና ጸጋዉን በተለየ ሁኔታ የሚያድለበት ልዩ ስፍራ አለዉ። በአዲስ ዘመን ልዩ ስፍራዉ በረከትና ጸጋ በተለየ ሁኔታ የሚታደልበትና በተለየ መልኩ ምስጋና የሚቀርብበት ቦታ ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። እነሱ «ቤተክርስቲያን አያስፈልግም» ቢሉ የተለያዩ ጉዳዮች የሚፈጸሙበት ቢሆንም «ቸርች» ብለዉ ይሄዱ አይደለም ወይ? «አያስፈልግም» ካሉ ሁሉም በየቤቱ አምልኮቱን አይፈጽምም ነበር? ነገር ግን በበላይ የሚመራቸዉ መንፈስ የቤተክርስቲያን ተቃዋሚ ስለሆነ፤ የሆነዉን ያልሆነዉን በራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት እየፈጠሩ የሕይወትን በር እየተቃወሙና በአንዷ በር ላለመግባት በራሳቸዉ ላይ የሞት አዋጅ እዳወጁ ነዉ የሚሰማኝ። በቅድስት ቤተክርስቲያን ማንኛዉም ሰዉ እስካመነ ድረስ ከእግዚአብሔር በጥምቀት ልጅነትን የሚያገኝበትና ለሕያዉነት ዘመን በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ አድርጎት የሚያኖረዉ ህብስትና ወይን በቅዳሴ ጊዜ ወደ መለኮት ሥጋና ደም የሚለወጥበት ነዉ። መዘምራኑ፣ ካህናቱ፣ ዲያቆናቱ፣ ምእመኑ የእንቅልፍ ድካም ሳያሸንፋቸዉ ከሌሊት ጀምሮ ስብሐተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት የእግዚአብሔር ቤት ነዉ። እያንዳንዱ አገልጋይና ምእመን በሚፈጽመዉ አምልኮ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ የሚያገኝበት እንዲሁም የተለያየ ጸጋ የሚታደልበት የተቀደሰ ስፍራ ነዉ። በመሆኑም እግዚአብሔርን የትም ሆነን ማምልክና ማመስገን ብንችለም በተለየ ሁኔታ የምናመልከዉ ቅዱስ ስፍራ ቤተክርስቲያን ብቻ ነዉ።

ለዚህም ነዉ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልጆች እግዚአብሔር «ቤቴና ቅጥሬ» ያለዉን በአግባቡ አክብረን ወደ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ስንገባ በትህትና ጫማችንን አዉልቀን እንዲሁም ቅጥሬ ካለዉ ከመግቢያዉ በር ጀምሮ በመሳለም

የምንገባዉ፡፡ ይህም ለእኛ ከእምነታችን በተጨማሪ ትሩፋት ተግባራችን ነዉ፡፡ ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰበትን ሥጋዉን የቆረሰበትን መስቀል ቅዱስ ነዉ ብለን የምናሳለም ነን፡፡ ያ ብቻ አይደልም ቅዱሳት መጻሕፍትንና ቅዱሳት ሥዕላትን የምንስም ነን፡፡ ይህ ተግባራችን «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት ምዕራፍ ሁለት በገጽ 65 ላይ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በቃል የተናገረዉን አቀርባለሁ፡፡ ይኸዉም:

«የትኛዉ አገር ነዉ በእኔ፣ በሥለሴ፣ በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች ስም በተሰየመዉ ቤተ ክርስቲያን በእምነቱ፣ በጠበሉ «እግዚአብሔር ያድነኛል» ብሎ በማመን በስጦታዬ የሚጠቀም የዋህ የማይጠራጠር ሕዝብ ያለበት? የትኛዉ አገረ ነዉ በእኔና በቅዱሳኖቼ ስም የተሰየመዉን ቤቴና ቅጥሬን የሚያከብር፣ጫማዉን አዉልቆ ወደ ቤቴ የሚገባና አምልኮቱን የሚፈጽም፣ክቡር መስቀሌን የሚሳለም፣ የቤቴና የቅጥሬን ሕንጻና አጥር ሳይቀር የሚስም እግዚአብሔርን መፍራት ያለበት ሕዝብ ያለዉ?» በማለት ቀርቧል

ይህ የሚያሳየን ተግባራችንና ሥርዓታችን አስመሰገነን፣ አስመሰከረልን እንጂ አላስተቸንም፣ ተቃዉሞም አላስመጣብን፡፡ የእኛ ትልቁ ችግራችን በሕይወቱ የሚሰብከንና እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ የሚያገለግለን ፣ ለነፍሳት የሚያስብና ስለ እዉነት የቆመ ቅንና እዉነተኛ፣ ትሁትና አፍቃሪ ፣ ልባምና የዋህ አግልጋይ ብቻ ነዉ እንጂ እምነታችን፣ ሥርዓታችን፣ ትዉፊታችን ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም የሚተርፍ ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደተገለጸዉ ያለዉ አንድ ሰንበት ብቻ ነዉ፡፡ ይኸዉም በብሉይ ዘመን ቀዳሚት ናት እንደ ሰንበር ትከበር የነበረዉ፡፡ በአዲስ ዘመን ግን በዓለም ላይ ባሉ አብያተክርስቲያናት ከአድቬንትስት እምነት ተከታዮች በስተቀር እሁድን ብቻ ነዉ እንደ ሰንበት የሚያከብሩት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ለምን ከእሁድ በተጨማሪ ቀዳሚትን እንደ ሰንበት ትቆጥራለች? እንዲሁም ቀዳሚት ሰንበት ብትባልም እንደ ሰንበት የማትከበርና እንደ ሌሎች የስራ ቀናት ተቆጥራ ስራ እየተሰራበት ነዉ፡፡ ይህስ ትክክል ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ ደረጃ መታወቅ ያለበት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ እንደተናገረንና እንዳስተማረን ይኸዉም በማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ 2 ቁጥር 27እስከ28 ደረስ « <u>ሰንበት ስለ ሰዉ ተፈጥሮአል እንጂ ሰዉ ስለ ሰንበት አልተፈጠረም፤ እንዲሁም የሰዉ ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነዉ አላቸዉ</u>፡፡» ይላል

እግዚአብሔር አምላክ ሰንበትን ለሰዉ ልጆች የእረፍት ቀን እንድትሆን ያደረገዉ፤ ስለ ነፍሳቸዉ በተለየ ሁኔታ እንዲያስቡና እርሱንም በተለየ ሁኔታ እንዲያመልኩት ለማስቻል ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ከላይ የተገለጸዉን ለመናገር የቻለዉ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት፣ የሕግ አዋቂ ሊቅ የሚባሉ በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የጌታችን ደቀመዛሙርት በእለተ ሰንበት በእርሻ መካከል ሲያልፉ ርቧቸዉ ነበርን ቀጥፈዉ ሲበሉ በተመለከቱበት ወቅት «በሰንበት ያልተፈቀደዉን ስለምን

ያደርጓሉ?» በማለት ሲከሷቸዉ ነዉ፡፡ የሰንበት ጌታ እዛዉ አጠገባቸዉ ነበርና እንኳን ይህ እንደ ኃጢአት የማይታየዉና እንደ ኃጢአተኛ የማያስቆጥረዉ ይቅርና መደረግ የሌለበትን ዳዊት ሲርበዉ በእግዚአብሔር ቤት  ለካህናት ብቻ የተፈቀደዉን የመስዋዕት እንጀራ እንደበላ የተናገራቸዉና ከላይ የተገለጸዉን የተናገራቸዉ፡፡

ያ ብቻ አይደለም በሰንበት መልካም ነገር መስራት እንደሚቻል እዛዉ አጠገባቸዉ እጁ የሰለለች በሽተኛን ፈዉሶ አሳይቷቸዋል፡፡ እነሱ ግን ከእግዚአብሔር በላይ ሆነዉ ስለእግዚአብሔር ጥብቅና የቆሙ በመምሰል «ሰንበትን ሽሯል፣ ኃጢአተኛ ነዉ፣ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ የሙሴን ሕግ አልጠበቀም... ወዘተ» እያሉ ወንጅለዉታል፣ ለመሰቀል ያበቃዉም አንዱ ይህ የእዉነት ምስክትነቱና አገልግሎቱ ነበር፡፡

በአሁን ዘመንም ብዙ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን የሰንበትን ጥቅም አልተረዱትም፣ አላስተዋሉትም ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሰንበትን እንደ ሰንበት ባለማክበራቸዉና እንዲሁም በሰንበት የተከለከለዉንና የተፈቀደዉን በግልጽ ለይተዉ ባለማወቃቸዉ ነዉ፡፡ በእለተ ሰንበት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ዝግ ቢሆኑም የተለየዩ የሥጋ መርሐ ግብር በተለያየ መልኩ ይከናወናል፡፡ ያም ብቻ አይደልም ቃለ እግዚአብሔር በደንብ እንዳይሰበክ «እንዲህ ዝግጅት፣ እንዲህ ስብሰባ፣ እንዲህ ማኅበራዊ ጉዳይ ...ወዘተ ስለላለ፤ ትምህርቱን ሆነ ስብከቱን አጠር አጠር አድርጉት» ይባላል፡፡ ታዲያ ለነፍስ እረፍት የታዘዘዉ ቀን ለነፍስ አገልግሎት ካልዋለ ምኑን ሰንበት ተባለ? ለሥጋ ስራ ከዋለ ምኑን አከበርነዉ? ሌላዉ ደግሞ በዚህ እለት የተለያየ መንፈሳዊና ግዳጅ ተግባር ስለተከናወነ አንዳንዶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ «ሰንበት ተሸረ» ይላሉ፡፡ በሰንበት መንፈሳዊ መርሐግብርና የሰዎችን ችግርና ጉስቁልና ማቅለል እንዴት እንደ ሰንበት መሻር ይቆጠራል? ወይስ እንደ ቀደሞት አስመሳይ አገልጋዮች ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት እነሱ የማያደርጉትን ሌላዉ ግን እንዲያደርግ የሚፈልጉትን ሰዉ እግርና እጁን አጣጥፎ እንዲቀመጥ ለማድረግ ተፈልጎ ነዉ ወይ? ወይስ «እነዚህ ትክክለኛ አገልጋዮች ናቸዉ» እንድንባል ፈልገን ነዉን? እግዚአብሔር ከመስዋዕት በፊት ቅንነትና እዉነተኛነት የተላበስ ሕይወት ነዉ ከእኛ የሚፈልገዉ፡፡ ቅንነትና እዉነተኛነት በሌለዉ ሕይወት ሆነን የምናቀርበዉ መስዋዕት አንዳች ዋጋ የለዉም፡፡ ምናልባት ሰዎች «እንዲህ አደረጉ» ብለዉ ያወሩልን፣ ያመሰግኑን፣ ያገኑን ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ግን የዉስጣችንን ስለሚያዉቅ የራሱን ፍርድ ነዉ የሚሰጠዉ እንጂ በዉጭያችን በምናሳየዉ ማስመሰል ተግባር አይደልም፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ**: እንደተባለዉ ሰንበት አንዲት ናት፡፡ በብሉይ ዘመን ትከበር የነበረችዉ ቀዳሜ ብቻ ናት፡፡ በሐዲስ ዘመን ግን የሰንበት ጌታ የሆነዉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእለት እሁድ ከሙታን ተለይቶ በመነሳት ትንሣኤን ለትዉልዱ ስለባሰረ፣ እንዲሁም የጌታ ቀን ስለተባለች፤ ሰንበት ሳይሻር ልክ በብሉይ ዘመን የነበረዉ የእንስሳ መስዋዕት በክርስቶስ ሥጋና ደም መስዋዕት እንደተተካ ሁሉ ቀዳሚት ሰንበትም በእሁድ ልትተካ ችላለች፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቀዳሚትና እሁድ ሁለቱም ሰንበት ናቸዉ የተባሉበት ምክንያት ያለ ሲሆን፤

ይህም በተለያዩ አባቶች ዘንድ በተከሰተዉ መከፋፈልና ወደ አንድነት ለማምጣት ሲባል የተደረገ ነዉ፡፡ በመሆኑም በቅርቡ በሚመጣዉ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ባለሟሎችና እንደራሴዎች በእዉነተኛዉ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ሲቀመጡና እረኛዉ አንድ መንጋዉ አንድ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚወስነዉ የመጨረሻ ዉሳኔ በእነርሱ በኩል ስለሚገልጽልን እስከዛዉ ድረስ እንደ ቤተክርስቲያኒቱ እምነትን፣ ሥርዓት፣ ትዉፊት፣ አስተምሮ መመላለስ ነዉ ያለብን እንጂ «ይህ ስህተት ነዉ፣ ይህ ይቀየር፣ ይህ ይሻር፣ ይህ ይለወጥ» ማለት የለብንም፡፡ ምክንያቱም እንደ ሥጋና ደም ሐሳባችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ የሆነ ተግባር ልንፈጽም እንችላለንና፡፡ ይህም በምድርም በሰማይም ዋጋ ያስከፍለናል፡፡ በመሆኑም ለጥቂት ወራቶች መታገስ ነዉ የሚጠበቅብን እንጂ ከአስተዳደራዊና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ከሚያመች የአሰራር ማሻሻያ ዉጭ ወደ ሥርዓት ለዉጥ ሆነ ማሻሻል ባንመጣ ለሥጋችንም ለነፍሳችንም የሚበጅ ነዉ፡፡ በመልካሙ ዘመን ሁሉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እየተመረመረ ትክክለኛዉን መስመር ስለሚይዝ ባለንበት ጸንተን መገኘት ነዉ ከእኛ የሚጠበቀዉ፡፡ » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አራት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: አንዳንድ ሰዎች ትዳርን በመጥላት ሕይወት ይመላለሳሉ:: ነገር ግን የሥጋ ስሜታቸዉን ለማርካት በዝሙት ሕይወት ይኖራሉ፤ እንዳንዶች ደግሞ ትዳር ይዘዉ ልጆችን መዉለድ ይጠላሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ማንነታቸዉን ያላስተዋሉ ታላቅ የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆኑትን ሕያዋን ፍጥረትና ልጆችን «ተምች» በማለት ልጆች እንዲኖሯቸዉ የማይፈልጉ አሉ:: ለዚህ ያሎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ትዳር ለማንኛዉም ለአዳምና ሔዋን ዘር የታዘዘና የተፈቀደ እግዚአብሔር ያዘዘዉ ሕይወትና የመጀመሪያዉ የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ነዉ:: ማንም ሰዉ በዚህ ሥርዓት ዓመፃና ክህደት በዝሙት ሆነ በአመንዝራነት ከፈጸመ የሚጠየቅበትና ዋጋም የሚከፍልበት ነዉ:: ስለዚህ እንደ ነብዩ ኤልያስ፣ እንደ ወንጌላዊ ዮሐንስ፣ እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ፣ እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ፣ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እንደ ቅድስት አርሴማ፣ እንደ አቡነ አረጋዊ፣ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ እንደ ታላቁ አባት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ተመርጦና ጸጋዉን አግኝቶ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቻ ሕይወቱን የሚያሰልፍ፣ በቅድስናና ንጽህና የሚኖር ሰዉ ካለ ደግሞ ይህም እግዚአብሔር የፈቀደዉ ነዉ:: ከዚህ ዉጪ ግን ትዳርን በመጥላትና በማቃለል በዝሙት ሕይወት መመላለስ ግን እግዚአብሔርን የማያዉቁና የማያምኑ የአረማዉያንና «እግዚአብሔር የለም» የሚሉ ሰዎች የዓመፃ ሕይወት ነዉ::

ትዳር ይዘዉ የፍትወት ስሜታቸዉን ብቻ ለማርካት የተሰለፉና ከእግዚአብሔር የሚወጡት (የሚሰርጹት) ሕያዋን ነፍሳትን በወላጅነትና በኃላፊነት ለመዉለድና ለማሳደግ እንዲሁም ቁም ነገር ደረጃ ላይ ለማድረስ የማይፈልጉ ሰዎች ደግሞ፤ በዚህች የዐይን ቅጽበት እድሜያቸዉ ከእግዚአብሔር ኃላፊነትን መቀበል አልፈለጉምን እግዚአብሔርም በመንግሥቱ የተለየ ኃላፊነት አይሰጣቸዉም:: እንዲሁም ለራሳቸዉ ስሜት ብቻ ያደሩ ስለሆነ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመመላለስ ስለሚቸገሩ ለእግዚአብሔር መንግሥትም ለመብቃት ይቸገራሉ:: ከዚያ በተጨማሪ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ልጅ ስለሌላቸዉ ባዶነት የሚሰማቸዉና በልጅ አማካይነት የሚገኘዉን ጸጋ ሊያገኙ አይችሉም:: ከዚህ ዉጭ ግን በተለያየ ምክንያት ለምሳሌ መሃን ቢሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ልጅን በተመለከተ አንዳች አያስጠይቃቸዉም፤ ዋጋም አያሳጣቸዉም:: ምክንያቱም ልጅ እንዲኖራቸዉ እግዚአብሔር አልፈቀደምና:: እግዚአብሔር ሲፈልግ እንደ ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐና እንደ ካህኑ ዘካርያስና ቅድስት ኤልሳቤጥ አንድ ልጅ ብቻ ሊሰጥ ይችላል:: ሲፈልግ እንደ ጻድቁ ይስሐቅ ሁለት ልጅ ብቻ ሊሰጥ ይችላል:: እንደ ጻድቁ ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጅ ሊሰጥ ይችላል:: ይህም የሚያሳየን ጭራሹንም ልጅ አለመስጠትና የልጅ ቁጥር መወሰን የእግዚአብሔር ድርሻ ነዉ እንጂ የሰዉ ልጆች አይደለም:: ሰዎች ለመዉለድ ስለፈለጉ ብቻ አይወልዱም፤ እንዲሁም ለመዉለድ ስላልፈለጉ ብቻ አይወልዱም:: ነፍስ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለሆነች እሱ ሲፈቅድ ነዉ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ሰዉ ሆኗ በምድር የምትገለጸዉ:: ለዚህም ነዉ አንዳንድ ሴቶች የወሊድ መከላከያ

እየተጠቀሙ እንኳ እግዚአብሔር ያንን ሰዉኛ መጠበብ ከንቱ አድርጎና ሽሮ እንዲያረግዙ የሚያደርገዉ::

ልጆች(ሕፃናት) ክፋት የሌለባቸዉ፤ ተንኮልና ምቀኝነት የማይታይባቸዉ፤ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የማይፈጽሙ ስለሆነ፤ በሥጋ ከመገለጻቸዉ ዉጭ እንደ ቅዱሳን መላእክት ንጹሃን ናቸዉ:: ይህን ቅድስናቸዉን በወጣትነት ሆነ በጉልምስና እንዲሁም በእርግና እድሜቻዉ ከጠበቁ እንደ ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር መንግሥት ሕያዉ ሆነዉ የሚኖሩ ናቸዉ:: ስለዚህ እነዚህን ሕፃነት «ተምች» ማለት በተዘዋዋሪ መላእክትን እንደ መስደብ ስለሚያስቆጥር ስለ ስድቡ ዋጋ የሚከፍሉበት ይሆናል ማለት ነዉ:: እያንዳንዱም ወላጅ እነዚህ የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች በኃላፊነትና በአደራ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ በአግባቡና በሥርዓቱ ተቆጣጥሮና ተንከባክቦ ማሳደግና ለቁም ነገር ደረጃ ላይ ማድረስ ይጠበቅበታል:: ይህን ካለደረገ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድም ይጠየቅበታል፤ በምድራዊ ዘመኑም ዋጋ ይከፍልበታል:: ይኸዉም ጋጠወጥ፣ ሥርዓትና ምግባር የሌለዉ ልጅ ካሳደጉ በዚህችዉ ምድር በመጀመሪያ ወላጆች ናቸዉ የሚቀጡበትና ከዚያም ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለሰፈር፣ ለአገርና ለዓለም ጥፋቱና ዓመፃዉ የሚተርፈዉ:: በተቃራኒ ደግሞ በሥርዓትን፣ በምግባር፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን በመፍራትና በማምለክ ካሳደጉ የመጀመሪ ተጠቃሚዎች ወላጆች ናቸዉ:: ከዚያም ጥቅሙ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለሰፈር፣ ለመንደር፣ ለአገር፣ ለዓለም ይተርፋል::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ቀደም ብለዉ እንደገለጹልን ጋብቻ ለአዳምና ሔዋን ዘሮች ሁሉ የተፈቀደና ከቅድስና ሆነ ከብቃት እንዲሁም ከአገልግሎት የማይለይ እግዚአብሔር ያዘዘዉና የፈቀደዉ ነዉ:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት አገልግሎት ዉስጥ በትዳር የተወሰኑ፣ ቤተሰብ ያላቸዉ የተለያዩ ሊቃዉንትና መምህራን እንዲሁም ሕጋዊ ካህናት በከፍተኛ ሥልጣንና አመራር ዉስጥ የሉብትም:: ይህን በተመለከተ አስተያየቶትን ቢሰጡን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በዚህች ዓለም ከጥንት ጀምሮ ግለሰቦች ሆኑ ቡድኖች በሥጋዊዉም ሆነ በመንፈሳዊዉ ሕይወት ዉስጥ ለራሳቸዉ የሚሆን ሥርዓትና ሕግ አዘጋጅተዉ እስከ አሁን ድረስ ለራሳቸዉ ብቻ ሲጠቀሙበት በተለያዩ መዋዕለ ዜናና ታሪክ አንብበናል፤ እንዲሁም በዐይናችን ተመልክተናል፤ በጆሮዋችንም አዳምጠናል:: በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የሚከናወነዉ መንፈሳዊ አገልግሎት በሕጋዊ ካህናት መሆኑ ግልጽ ነዉ:: በሂደት ግን በግብፃዉያን መመራትና በእነሱ ሥርዓት መመላለስ ጀመርን:: እስከ አሁንም ድረስ እነሱ ያሳደሩብን ተጽህኖ አለቀቀንም:: በገዳማዊ ሕይወት ዉስጥ ላሉ አገልጋዮችና ምእመናን በእነሱ ሕይወት በምንኩስና ዉስጥ ያለ አባት በበላይ ሆኖ ሊመራቸዉና ሊያስተዳድራቸዉ ይገባል:: በዚሁ መልኩ በዓለም ዉስጥ ያሉ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን በእነሱ ሕይወት ዉስጥ የሚኖር ለመምራትና ለማስተዳደር ብቃቱ ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ ሊመራቸዉና ሊያስተዳድራቸዉ ይገባል እንጂ በምንኩስና ሕይወት ብቻ ያሉትን ወደ ወንበር ማምጣት ከላይ እንደተገለጸዉ ጥቅምንና ሥልጣንን ለተወሰ ግለሰብ ወይንም ቡድን ወይንም አባላት ለማድረግ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር ባዘዘዉና በፈቀደዉ ሕይወት ዉስጥ የሚመላለስንና ለአገልግሎት ብቁ የሆነዉን ሊቃዉንት ሆነ መምህር እንዲሁም

ሕጋዊ ካህን «ለመሪነት ሆነ ለአስተዳዳሪነት አትበቃም፤ በወንበር ላይ መቀመጥም አትችልም» ማለት እነ መልከ ጸዴቅን፣ እነ አብርሃምን፣ እነ ካህኑ ዮቶርን፣ እነ ቅዱስ ጴጥሮስን የመሳሰሉትን ለከፍተኛ ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም መሪነትና አስተዳዳሪነት ያበቃዉን አምላክ «እኛ ካንተ በላይ ነንና እኛ ዉ በራሳችን በፈጠርነዉ ሥርዓት እንጂ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተዘጋጀዉ ሥርዓት አንመራም፤ አንመላለስም፤» ማለታችን እንደሆነ ልናዉቅ ይገባል፡፡ ደግሞ ቤተሰቡን በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር የሚችል ሰዉ ነዉ ሌላዉን ወገኑን በአግባቡ ሊመራና ሊያስተዳድር የሚችለዉ እንጂ፤ በተለያየ ማኅበራዊ ሕይወት ዉስጥ ያልተመላለሰ ሰዉ የሰዎችን ስሜት በቀላሉ ተረድቶና ያለፉበትንና እያለፉበት ያለዉን ሕይወት አስተዉሎና ተገንዝቦ እንዲሁም ሊደረግላቸዉ የሚገባዉን አዉቆ እንደ ደረጃቸዉ ሊያገለግል እንዴት ይችላል?

ለዚህም ነዉ በሰዉ ሥርዓት በመመላለሳችን ምክንያት ምንም እንኳን ንጽህናቸዉንና ክብራቸዉን ጠብቀዉ እግዚአብሔርን በመፍራት ሕይወት በቅንነትና በእዉነት፣ በከተማና በገጠር የሚያገለግሉ መነኮሳት እንዳሉ ሁሉ፤ ለሥልጣንና ለጥቅም ብለዉ ቆብ በመድፋት በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱ አሰናካይና የእዉነት እንቅፋቶች፣ ሌባ፣ ቀማኝ፣ ወንበዴ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ዘማዊ የሆኑ አስመሳይ አገልጋዮች የሆኑ አስመሳይ መነኮሳት በከተማም በገጠርም የሚታዩት፡፡ ታዲያ ለሁሉ መፍትሔ የሚሰጠዉ እግዚአብሔር ነዉና እዉነት ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ስትነግሥና የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባለሟሎችና እንደራሴዎች ለእዉነተኛ አገልግሎት ወደ ወንበር ሲመጡ ያኔ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ የሰዉ ሥርዓት የሆነዉ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ሥርዓት ይተካል፡፡ በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊዉ ሕይወታችን እዉነተኛ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ እዉነተኞች ወደ እዉነተኛ ወንበር ይመጣሉ፡፡ አስመሳዮች ደግሞ ከወንበራቸዉ ይቀረጣሉ፤ እንደ ዓመፃቸዉም ደረጃ በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ይጠረጋሉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ ወላጆች «የሰዉነታችን ቅርጹ ስለሚበላሽና እንዲሁም እስረኛ ስለምንሆን አንወልድም፤ ብንወልድም አናጠባም ... ወዘተ» የሚሉ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «እንደ አቅማችን ነዉ የምንወልደዉ» የሚሉ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግም «አቅም ኖረን አልኖረን በእድላቸዉ ያድጋሉ» በማለት ዝም ብለዉ የሚወልዱ አሉ፡፡ አንዳንዶች «የማንፈልገዉ እርግዝ ነዉ» ብለዉ የሚያስወርዱ አሉ፡፡ አንዳንዶች «መምህር እገሌ እስከ ሰላሳና እርባ ቀን ያለ ጽንስ ልጅ ስለማይሆን ቢወርድ ወይንም ቢጠፋ ችግር የለዉም ብለዉኛልና» ብለዉ በተለያየ መንገድ ፅንሱን የሚያስወግዱ አሉ፡፡ ለዚህ ያሉትን አሰትየየት ቢሰጡን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ ሊኖረን የሚገባዉ ግንዛቤ «እኛ ማነን? ለምን ወደዚህች ምድር መጣን? ቀጣይ ሕይወታን ምንድነዉ? በምድራዊ ቆይታችን ዘመን የስራ ድርሻን ምንድነዉ? እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሕይወት ብንይዝ ነዉ የሚፈልገዉ?... ወዘተ» የሚሉትን በሚገባ ማወቅና ማስተዋል ይገባናል፡፡ ይህች ምድር ለእኛ አልነበረም የተፈጠረችዉ፡፡ አዳምና ሔዋን ወደዚህች ስደት ምድር ከመግባታቸዉ በፊት በድቅድቅ ጨለማ የተሞላች በብዙ

ትእልፊት(በብዙ ቢሊዮን) ርኩሳን መናፍስት( ሰይጣናት) ከዋና መሪያቸዉ ዲያብሎስ ጋር በጎሰቆለ ባሕርይ የሚቀጡበት ነበር፡፡ ይሁንና አዳምና ሔዋን ከዚህች ምድር ጉን በገነት ዉስጥ እያሉ እግዚአብሔር «አትብሉ» ያላቸዉን ያልተፈቀደላቸዉን ፍሬ በመብላታቸዉ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ዓመፃና ክህደት በመፈጸማቸዉ ምክንያት ባደፈና በጎሰቆለ እንዲሁም በጉስቁልና ባሕርይ እንዲቀጡ በዚህ በጎስቋላዉ ሥጋ ተገልጸዉ በግዙፍ ዓለም ዉስጥ እንዲኖሩ፣ ርኩሳን መናፍስት ደግሞ በዚህችዉ ምድር ዉስጥ በረቂቅ ዓለም ዉስጥ እንዲኖሩ አድርጎ ፈረደባቸዉ፡፡ በመሆኑም ምድራዊ ሕይወታችን በእግዚአብሔር የተመረጠና የታዘዘ አልነበረም፡፡ የቀደሙት ወላጆቻን አዳምና ሔዋን ያመጡት ጣጣ ነዉ፡፡ ነገር ግን ርኅሩኅ አምላካችን የእነርሱን ንስሐና እኛም ልጆቻቸዉ ባላወቅነዉና ባልፈጸምነዉ ዓመፃ ምክንያት የእዚህች ምድር ጎስቋላ ሕይወት ተካፋይ እንድንሆን የተፈረደብንን ቅጣት፤ በምሕረቱ ከምድራዊ ዘመን በኋላ ከምንኖረዉ ሕያዉነት ዘመን አንጻር ሲነጻጸር የዐይን ቅጽበት እድሜ በማትሞላዉ ምድራዊ ዘመናችን ቀላል የስራ ድረሻ ተሰቶናል፡፡

የመጀመሪያዉ የስራ ድርሻችን በመጀመሪያዉ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ጋብቻ አማካይነት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የሚሰርጹትን(የሚወጡትን) እርሱን እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሱትን ሕያዋን ነፍሳት በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ካለመኖር ወደመኖር ማምጣት ሲሆን፤ ለዚህም ብቃት ደረጃ ላይ መድረሳችንን የሚያሳዉቀን ለወንዱ የዘር ፍሬ፣ ለሴቷ ድግሞ የወር አበባ ምልክት ሰቶናል፡፡ እነዚህ ምልክቶች በወንዱ ሆነ በሴቷ ሲታይ የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች የሆኑት ሕያዋን ነፍሳትን በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይት በኃላፊነት መረከብ የሚችሉ መሆኑን ነዉ፡፡ ሌላዉ መታወቅ ያለበት እነዚህ ምልክቶች ቢታዩ እንኳ እግዚአብሔር ከእርሱ ባሕርይ የሚወጡት ነፍሳት ሰዉ ሆነዉ እንዲገለጡ እስካልፈቀደ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመደረጉ ብቻ ልጅ መዉለድ አይቻልም፡፡ እርሱ ሲፈቅድ ብቻ ነዉ ያንቺ ነፍስ ሰዉ ሁና በማኅፀን የምትፀነሰዉ፡፡

ነፍስ ሰዉ የምትሆነዉ ደግሞ የወንዱ የዘር አብራክና የሴቷ ፍሬ በሚገናኙበት ቅጽበት ነዉ እንጂ ሠላሳኛ አርባኛ በሚባል ቀን አይደለም፡፡ የቀን ልዩነት የሥጋ እድገት ብቻ ነዉ የሚገለጽበት፡፡ ነፍስ ማስተዋልና እዉቀቷ በመገደቡ ነዉ እንጂ እንደ ማንኛዉም ሰዉ የሚያመዛዝን፣ የሚያገናዝብ፣ የሚያዉቅ ነጻ የሆነች ሕያዉ ፍጥረት ናት፡፡ እግዚአብሔር ከፈቀደላት በአንድ ቀን እድሜዋ በማኅፀን ዉስጥ እያለች የተለያዩ ተአምራትን ልታደርግ ትችላለች፡፡ ምክንያቱም ፍጹም ሰዉ ሆናለችና፡፡ ከእናቷም ከአባቷም ሥጋን ነስታ ተዋሕዳ ተገኝታለችና፡፡ ስለዚህ የአንድ ቀን ፅንስ ሆነ የአርባ ቀን እንዲሁም የሠለሳ ቀን ሆነ የስድስት ወር ... ወዘተ ፅንስ ሆን ብሎ ፅንሱን ያስወረደ ሆነ በመድኃኒት የገደለ፤ ያዉ ልጁን እንደገደለ ነዉ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚቆጠረዉ፡፡ በምድር ላይ በሕይወት እያለ ልጁን ከገደለ እኩል ቅጣት ባይጠብቀዉም፤ የቅጣቱ ደረጃ ቢለያይም እንደ ነፍሰ ገዳይ የሚያስጠይቀዉና የሚያስኮንነዉ ነዉ፡፡

ወላጆች የእግዚአብሔርን ልጆችና ፍጥረታት በኃላፊነት የመረከብና በአግባቡና በእንክብካቤ የማሳደግና የማስተዳደር የዉዴታ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ይህን ኃላፊነት የተሰጣቸዉም በዚህች በዐይን

ቅጽበት ምድራዊ ዘመን ስለሆነ በሥርዓቱና እግዚአብሔን በማክበርና በመፍራት ሊያሳድጓቸዉ እንዲሁም በርኅራኄና በፍቅር ሊንከባከቧቸዉ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ከእግዚአብሔር ልጆቹን በኃላፊነት መረከብ የለባቸዉም። ምክንያቱም በደል፣ ግፍ፣ ስቃይ፣ መከራ፣ ችግር ቢያደርሱባቸዉ ይጠየቁበታልና። ሌላዉ ደግሞ እያንዳንዱ እንደአቅሙ ልጁን ማሳደግና ማኖር አለበት እንጂ ከእርሱ በላይ የሆኑትን እያየ «በድሎትና በቅንጦት እንዲሁም ከፍተኛ ገንዘብ በሚከፈልበት ትምህርት ቤት ልጄን ካላስተማርኩ መዉለድ የለብኝም» ማለት የለበትም። እንዲሁም ስለ ልጁ አንዳች የማያስብና ከእርሱ የሚጠበቅበትን ሁሉ የማያደርግ ወላጅ የግል ስሜቱን ብቻ ለማርካት ሲል የማያሳድገዉንና የማያኖረዉን፣ የማይንከባከበዉን ልጅ መዉለድ የለበትም። ስሜቱን መቆጣጠርና መግታት ይኖርበታል።

ሌላዉ ደግሞ አቅሙ እየፈቀደለት «ቅርጼ ይበላሻል፣ እታሰራለሁ» እያለ የእግዚአብሔርን ልጆች በኃላፊነት ተረክቦ ለመዉለድ እምቢ ማለት የለበትም። ምክንያቱም ሴቷ የመዉለድ ብቃት የሚኖራት ጊዜ እግዚአብሔር በእድሜ ገድቦ ነዉ የሰጣትና። ወር አበባዋ በሚቋረጥበት ጊዜ ልዉለድም ብትል አትችልም። ነገር ግን እስከዚያ ድረስ ግን አቅምና ብቃት እዳላት እግዚአብሔር ስለሚያዉቅ ነዉ የእርሱን ልጆችና ፍጥረታት በኃላፊነት እንድትረከብ ያስቻለዉ። በኃጢአት መኖር ብቻ ነዉ መታሰር እንጂ ልጅ መዉለድ መታሰር አይደለም። በእግዚአብሔ ዘንድ ለሴት ትልቅ ቦታ የተሰጣትና ኃላፊ ሆነ መሪ የመሆን ብቃት ያላት ከባዱንና ትልቁን ስራ ከወንዶች በላይ በመሆን የእግዚአብሔርን ልጆችንና ፍጥታትን በአግባቡ ስለምታሳድግና ስለምትንከባከብ ነዉ። ይህን በማድረጓ ቅርጻ የሚበላሽና ከወንድ የምታንስ ሳይሆን ክብርና ጸጋ የምትላበስ ናት። አሁን ባለነዉ ትዉልድ ግን ማንነታችንን የዘነጋንና ከጸጋ እግዚአብሔር የራቅን ስለሆነ «እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ በዚያም የሕይወታችን ፍጻሜ ይሆናል» እንደሚሉት አሕዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች ሕይወት ስለያዝንና እንደነርሱ መኖር ስለምንፈልግ፤ እንዲሁም ኃላፊነት መሸከም ስለሚከብደን እንደ ዉጭዎቹ ሕይወታችንን በዘፈን፣ በጭፈራ፣ በመዝናናት ማሳለፍ ነዉ የምንፈልገዉ እንጂ ተስፋችንን ሰማያዊ አድርገን ይህችን ምድራዊ ጉስቁልና የሞላባትን አጭሩ ምድራዊ ዘመናችንን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አንመራም፣ አንኖርበትም። ይህ ደግሞ በምድርም በሰማይም ዋጋ የሚያስከፍለን ይሆናል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ አንዳንድ ሴቶች ገላቸዉን በማረቆትን፣ እንዲሁም በተወጣጠረ ሱሬ ቂጣቸዉንና የተለያየ አካላቸዉን በማሳየት የወንዱን ፍትወት ለማነሳሳትና ገላቸዉም በሰዎች እንዲደነቅላቸዉ፣ እንዲገና፣ ከዛም ባለፈ እንዲመለኩ ይፈልጋሉ። የአሁን ትዉልድም እንደ ትክክለኛ ተግባርና የታላቅነት መገለጫ አድርጎ በመቆጠር ይህን ድርጊትና አስተሳሰብ ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ በዚህ አለባበስ ይታያሉ፤ ይህን አስተሳሰብ ያስፋፋሉ። በዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ እግዚአብሔር እንኳን የእርሱን ባሕርይ የተላበሰች ሕያዉ ነፍሳችን የተገለጸችበትን የከበረ ሥጋ ቀርቶ ሌሎች ፍጥረታትን ካለምክንያት አልፈጠራቸዉም። ነገር ግን አግባብነት ካለዉ ሕይወት የሚወጣ መገለጫ ካለ ደግሞ የተከበረዉ ወደ

ርኩሰት፣ ከታላቅነት ወደ ተራነት ሊለወጥ ይችላል፡፡ ይህች ነፍሳችን የተገለጸችበት ሥጋችን በየትኛ ዉም መልክና ደም ግባት እንዲሁም ቁመናና ዉፍረት ትገለጽ የእያንዳንዱ ሰዉ አካል ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ የከበረ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ሕያዉ ነፍሳችን በአካል ደረጃ በአንጎላችን ዉስጥ በግንባራችን ፊት ለፊት ብትገኝም ከእርሷ በወጣ ኃይል ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ድረስ መላ አካላችንን ተዋሕዳ ስለምትገኝ የእርሷ ክብር የሥጋችንም ክብር ነዉና፡፡ የእርሷ ዉርደት የሥጋችንም ዉርደት ነዉ፡፡ የእርሷ ቅድስና የሥጋችንም ቅድስና ነዉ፡፡ ባጠቃላይ በምድራዊ ሕይወት ዘመኗ በዚህ ሥጋ ተገልጻ በምድር እንደምትመላለስ ሁሉ የሥጋዋ ጉዳት የእርሷም ጉዳት ነዉ፡፡ የሥጋዋ ጉስቁልና የእርሷም ጉስቁልና ነዉ፡፡ የሥጋዋ ጥቅም የእርሷም ጥቅም ነዉ፡፡ ሥጋ ጤነኛ ከሆነ ነፍስም ጤነኛ ትሆናለች፤ ሥጋ ከታመመ ነፍስም ትታመማለች፡፡ ሥራ ከረከሰች ነፍስም ትረክሳለች፡፡ ሥጋ ከተቀደሰ ነፍስም ትቀደሳለች፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** ራሱን አራቁቶ የሚሄድ ሰዉ የታላቅነት መገለጫ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ሲርቀዉና ርኩሳን መናፍስት እንደፈለጉ አድርገዉ ሲያሾሩት የሚታይበት መገለጫ ነዉ፡፡ ለእዚህ ነዉ እብዶች ተራቁተዉ ሲሄዱ ምንም የማይመስላቸዉ፡፡ እናቶቻችንና እህቶቻችን የአሜሪካዉያንና የአዉሮፓዉያን አለባበስ እንደታላቅነት ቆጥረዉ በተራቆተና በተጠባባቀ ልብስ ሲገለጹ ለእነሱ ታላቅ የተለዩ ይመስላቸዋል እንጂ የከበረዉን ሥጋ እያራከሱትና የሰይጣናት መሳሪያ በመሆኑ ወንዱን ለዝሙት ስሜት እያነሳሱት ነዉ፡፡ በዚህ ደግሞ በነጻ ፈቃዳቸዉ ስላደረጉት የራሳቸዉን ገላ በማራከሳቸዉም ሆነ ወንዱን ለዝሙት ስሜት በማነሳሳታቸዉ በእግዚአብሔር ዘንድ ይጠየቁበታል፤ በምድርም በሰማያም ዋጋ ይከፍሉበታል፡፡ መራቆት የክብር መገለጫ ሳይሆን የዉርደትና የጉስቁልና መገለጫ ነዉ፡፡ ነገር ግን ነዉሩ እንደክብር እየታየ ስለሆነ፤ ሰዎች ተራቁተዉ ሲሄዱ የሰለጠኑ ይመስላቸዋል እንጂ ራሳቸዉን እያዋረዱ መሆኑን አያስተዉሉትም፡፡ ጠጉራቸዉ ተንጨባረዉ ሲሄዱ እንደ ዉጭዎቹ የሰለጠኑ አድርገዉ ይቆጥሩታል እንጂ የእብደት መገለጫ መሆኑን አያስተዉሉትም፡፡

ሌላዉ አካላቸዉን በተጠባበቀ ሱሬ ሆነ ቀሚስ ወጣጥረዉ ሲሄዱ ያ ገላቸዉ የተለየ ተደርጎ እንዲታይላቸዉና ሰዎችም በአድናቆትና በማግነን እንዲመለከቱላቸዉ በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ገላችንን የምናመልከዉና የምናስመልከዉ ከሆነ እግዚአብሔር ከፈጠረዉ ዓላማ ዉጭ ስላዋልነዉ መጨረሻ ቅርፊት በስባሽ የመሬትና የምስጥ እንዲሁም የትሎች መብል ነዉ የሚሆነዉ እንጂ ጣዖት ሆነ አምላክ አይደለም፡፡ ቂጣችንንም ወጣጥረን የምናሳየዉ ለመቀመጫነት አገልግሎትና እንዲሁም ላደፈና ለጎደፈ ባሕርያችን ማዉጫነት የሚጠቅም ነዉ እንጂ እንደተለየ ተደርጎ የሚቆጠርና የሚገን፣ የሚመለክ አይደለም፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ትክክለኛ ክብር እንዲኖረዉ የከበረዉን ሥጋ በአግባቡ ሊያከብረዉ ያገባል እንጂ ለያገነዉ ሆነ ሊያስመልከዉ አይገባም፡፡

ሌላዉ እህቶቻችንና እናቶቻችን እንዲሁም ልጆቻችን ማወቅ ያለባቸዉ ደረታቸዉንና ጡታቸዉን፣ እንብርታቸዉንና ቂጣቸዉን፣ ታፋና ዳሌያቸዉን ገላልጠዉ፤ እንዲሁም በተወጣጠረ ሱሪ የሰዉነታቸዉን ቅርጽ እያሳዩ ትዉልዱን ለዝሙትና ለፍትወት ማነሳሳታቸዉ፣ ማሰናከያ

ማምጣታቸዉ መሆኑን በሚገባ ሊያዉቁት ይገባል፡፡ ማሰናከል ደግሞ በምድርም በሰማይም ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍል በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 18 ከቁጥር 7እስከ11 የተጻፈዉና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ የተናገረዉን መመልከት ይቻላል፡፡ ይኸዉም

«ወዮ ለዓለም ስለ ማሰናከያ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፣ <u>ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰዉ ወዮለት</u>፡፡ እጅህ ወይም እግርህ ብታሰናክልህ፣ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሁለት እጅ ወይን ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል ይልቅ አንካሳ ወይን ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል፡፡ <u>ዓይንህ ብታሰናክልህ አዉጥተህ ከአንተ ጣላት ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትጣል ይልቅ አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል፡፡</u>

ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ መላእክቶቻቸዉ በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለዉን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለዉና፡፡» ይላል

ታዲያ ከላይ ያለዉ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የሚያሳዉቀን፤ ምን ያህል የእግዚአብሔር ፍርድ ጥብቅ መሆኑንና እንኳን ራሳችን ፈቅደን የዲያብሎስ መሳሪያ በመሆን ሰዉን ማሰናከል ይቅርና ፈተና የሚመጣበት ሰዉ እንኳን በፈተናዉ ከወደቀ የሚገጥመዉን የከፋ ቅጣት፤ እንዲሁም ለተለያየ ፈተና የተዳረገ ሰዉ እንኳ በፈተና ላለመዉደቀ ራሱን በሚገባ መጠበቅ እንደሚኖርበት ነዉ፡፡

እህቶቻችንና እናቶቻችን የዓመፃ ሓሳብና ተግባር ሲመጣባቸዉ በመጀመሪያ ሊያስቧት የሚገባዉ ቀዳሚዋ እናታችን ሔዋንን ነዉ፡፡ ምክንያቱም በዓመፃዋ የተነሳ ላልተገባ ጉስቁልና ሕይወት መዳረጓንና ከአዳም በተለየ ሁኔታ የተከሰተባትንና ለወር አባባና ለምጥ የስቃይ ስሜት መዳረጓን፣ ለልጅ ሎጆቿም መተላለፉን በማስታወስ ራሳችንን ከዓመፃ ሕይወት መለየት አለብን፡፡ በዓመፃ ሕይወት ዉስጥ የምንመላለስ ከሆነ ለከፋ ጉስቁልናና መከራ ሕይወት እንደምንዳረግ አስተዉለን እግዚአብሔርን በማፍቀርና በመፍራት ሕይወት ልንመላለስና ሌላዉንም ላለማሰናከል ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል እንጂ እንደ አሕዛብ አሕዛባዊ አለባበስና ሕይወት ይዘን ከተመላለን እግዚአብሔርን ከማያምሉ አሕዛብ ባላይ የከፋዉ ቅጣት ይጠብቀናል፡፡ ምክንያቱም «እግዚአብሔርን እናምናለን፣ እናመልካለን» በማለት ስለምንመላለስና የድፍረት በደል ስለምንፈጽም ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ በአሁን ሰዓት በተለያየ ቦታ የርኩሰት ፊልም ያታያል፡፡ እጅግ የሚያሳዝነዉና የሚዘገንነዉ ደግሞ፤ የወጭዎቹ ርኩሰት ፊልም መታየቱ አንሶ «አበሾች የሰሩት የዝሙት(ርኩሰት) ፊልም» እየተባለ በአዳባባይ ሲሸጥ ይታያል፡፡ አሁን ያለዉ መንግሥት ደግሞ በዲሞክራሲ ሽፋን ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን አንግሷል፡፡ ይህ ድርጊት በዚህች በተቀደሰች አገር ላይ መከሰቱ የከፋዉን የእግዚአብሔር ቁጣ አይመጣብንም ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ በግልጽ እንደሚታወቀዉ አሁን ያለዉ የኢሕአዴግ መንግሥት የክፉ ትንቢት ፈጻሚ ሆኖ የመጣ በመሆኑ በዚህች አገር የተለያዩ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ቢታይ ብዙም ላይስደንቅ ይችላል፡፡ በወንበሩ ዙሪያ የተሰባሰቡት

በልጅነታቸዉ፣ በወጣትነታዉ፣ በጎልማሳነታቸዉ እድሜ ባሳዩት ትዕቢትና ዓመፃ፣ ክህደትና ምንፍቅና፣ ተንኮል፣ ክፍት፣ ጥላቻና በቀል፣ ክፉ ቅናትና ምቀኝት ... ወዘተ በሆኑ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ፍሬ ምክንያት ስለሆነ፤ ትዉልዱ በተለያየ ሱስ ቢጠመድና ቢደነዝዝ፤ የተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ ቢፈጸም፤ ዝሙት፣ ዘፋኝነት፣ ዳንኪረተኛነት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ጥላቻና በቀል፣ ስካር፣ ሴሰኛ ነት፣ ... ወዘተ ቢነግሡ ስሜት የማይሰጣቸዉና ይልቁኑ «ብሔር ብሔረሰቦች የተጎናጸፋችሁት የዲሞክራሲና ነጻነት መብት ስለሆነ በርቱበት፤ ቀጥሉበት» እያሉ የሚያበረታቱ ፍጹም የዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች ናቸዉ::

የሚያሳዝነዉ ግን እነሱም ባስፈጸሙት ሆነ ትዉልዱ በሚፈጽመዉና በሚያስፈጽመዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር እያንዳንዱ በራሱ ላይ የከፋዉን የእግዚአብሔረ ቁጣ የሆኑት የተለያየ መቅሰፍትና መከራ እየጋበዘ ስለሆነና እግዚአብሔርንም «እስከ አሁን ድረስ የዓመፃና የርኩሰት ትግባራችን እንዴት ጽዋዉ አልሞላም? ስለዚህ ጽዋዉ ቶሎ እንዲሞላ የከፋዉን ርኩሰት ተግባር እንፈጽማለት» እያለ የንስሐ እድል እንኳ እንዳይገኝ ራሱን ለጠረጋና ለጥፋት እያሰለፈ ይገኛል:: የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ጽዋችን ሞልቶ እየፈሰሰ ስለሆነ እጅግ በቅርቡ የሚደርስብንና የሚመጣብን መዓት የምንመለከት ይሆናል:: ወደ ልቡ መመለስ የሚፈልግ ደግሞ በእዉነተኛ ንስሐ እጁን ለእግዚአብሔር ቢሰጥና በእዉነተኛ ሕይወት ቢመላለስ ይበጀዋል::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በዝሙት(በሴተኛ) አዳሪነት ሕይወት ላይ የተሰማሩ ወገኖቻችን ከዚያ ሕይወት ተለይተዉ በሌላ ስራ ለምሳሌ በካፍቴሪያ በመሳሰሉት ስራ ላይ ለምን እንደማይሰማሩም ሲጠየቁ፤ አንዳንዶቹ «250 ብር ተከፍዬ ለቀለብ፣ ለቤት ኪራይ፣ ለልብስ እንዴት ይበቃኛል? ኤድስ ቢኖርብኝም በኮደመ እጠቀማለሁ... ወዘተ» እያሉ የዝሙት ስራ አዋጭ መሆኑን በመናገር በዚያ ሕይወት ይጸኑበታል:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በመጀመሪያ ሊታወቅ የሚገባዉ እህቶቻችንን ለዚህ ሕይወት የዳረገዉ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ያለዉ የጨለማዉ ገዥ ሥርዓት ነዉ:: ምክንያቱም በዲያብሎስ ሥርዓት ዉስጥ የሰዎች ተስፋ ምድር ብቻ ስለሆነችና «እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ ሕይወታችን በዚህ ይደመደማል፤ ይጠናቀቃል» ብለዉ ስለሚያምኑና አስተሳሰባቸዉ፣ አኗኗራቸዉ ይህን የተከተለ ስለሆነ፣ ለምን ወደዚህች ምድር ሊመጡ እንደቻሉና ታላቅ ተስፋቸዉን ለሕያዉነት ሕይወት እንደሚኖሩ አያዉቁም፤ አያስተዉሉም:: ይልቁኑ በመንግሥታቱ እየተበረታቱ «ለአስተማማኝ ሕይወት ኮንደም ተጠቀሙ፣ ለአስደሳች ሕይወት ሰንሰሽን ተጠቀሙ... ወዘተ» እየተባሉ በዚህ በሞት ሕይወት ዉስጥ እንዲኖሩ ተደርጓል::

እዉነተኛ ለሕዝብ የሚያስብ የበጎች እረኛ ቢኖር ኖሮ ስለ በጎቹ ሕይወት ያስባልና ከዚህ ከሞተ ሕይወት የሚለዩበት መንገድ ነበር የሚፈጥረዉ:: ገና ከሕፃንነታቸዉ ጀምሮ እግዚአብሔርን እንዲያዉቁና እንዲያፈቅሩ እንዲሁም እንዲፈሩ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ዝሙትን እንኳን እንደ ስራ መተዳደሪያ ሊቆጥሩት ቀርቶ፤ ዝሙትና አመንዝረኛነት በእግዚአብሔር የተከለከለና በምድርም

በሰማይም የሚያስጠይቅና የሚያስፈርድ መሆኑን በሚገባ ስለሚያዉቁ፣ ተሰፋቸዉን ሰማያዊ አድርገዉ ከትንሽ ስራ ጀምሮ እስከ ትልቅ ስራ ሳይንቁ በመስራት ራሳቸዉንም፣ ቤተሰባቸዉን፣ ከዚያም አልፎ ወገኖቻቸዉን ለመርዳት ይነሱ ነበር። አሁን ግን እንኳን ለሌላዉ ሊተርፉ ይቅርና ለራሳቸዉ መሆን ተስኗቸዉ በተለያየ በሽታ እየተጠቁ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ ቀርተዋል። በጨለማዉ ሥርዓት ዉስጥ ሆነዉ እንኳ ማስተዋሉ ቢኖራቸዉ የራሳቸዉን ገቢ ቢፈልጉ በዝሙት ሕይወት ከመመላለስ ስራን ሳይንቁ በቤት ሰራተኛነት ቢቀጠሩ በአሁን ሰዓት የመንግሥት ሰራተኛ በወር የማያጠራቅመዉን ገንዘብ ማጠራቀም ይችሉ ነበር። ይኸዉም ለቀለባቸዉ፣ ለኪራይ ቤት አንዳች ወጭ ሳይኖርባቸዉ በወር የምትከፈላቸዉን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሊቆጥቡ ይችላሉና። የመንግሥት ሰራተኛ ግን እንኳን ሊቆጥብ ቀርቶ ደሞዙ ከወር ወር አላደርስ እያለዉ በብድር ወይንም የሚበላዉንና የሚያወጣዉን ወጭ በመቀነስ ተሳቆ ነዉና የሚኖረዉ።

ስለ ወገናቸዉ የሚስቡ ሰዎች ግን እህቶቻችንን ከዚህ የሞት ሕይወትና የዓመፃ ተግባር የሚለዩበትን መንገድ ሊፈጥሩ ይገባል። ምክንያቱም የአዳምና ሔዋን ዘር የሆኑ ቤተሰቦቻችን ናቸዉና። በዝሙት ተግባር የተሰማሩትም ይህች የዐይን ቅጽበት ምድራዊ ዘመናቸዉን እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ለመመላለስ በቆራጥነት ሊሰለፉ ይገባል እንጂ ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊ ስቃይ ሕይወት የሚዳርጋቸዉንና የሚያስፈርድባቸዉን የኃጢአት ተግባር መፈጸም የለባቸዉም። » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አምስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: አንዳንድ በመንፈሳዊ ሆነ በሥጋዊ እዉቀት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሊቀ ምሁራንና ምሁራን (ፕሮፌሰርና ዶክተር) እንዲሁም ሊቃዉንት፤ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት በራሳቸዉ እዉቀት ሚዛን ነዉ የሚመዝኑት እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸዉን ባዶ አድርገዉ በእዉነትን በመንፈስ ቅዱስ አይደለም:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለመቀበል ይቸገራሉ:: ከዚያም አልፈዉ የሚቃወሙና የሚተቹ አሉ:: ለእዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በቅድሚያ አንድ መታወቅ ያለበት ዘመናዊዉ ትምህርት የዉጭዎችን ሥርዓት የተከተለ ስለነበረና ስለሆነ ለከፍተኛ እዉቀትና ማዕረግ የደረሱ ምሁራን እጅግ ብዞዎቹ አስተሳሰባቸዉና ተስፋዉ ምድራዊ የሆነ፤ ሃይማኖትን እንደ መጨቆኛ መሳሪያ አድርገዉ የሚመለከቱ፣ የእግዚአብሔርን ህልዉና የሚጠራጠሩና የካዱ፤ በማርክዚዝት፣ ሌኒዝስት፣ በቻርልስ ዳርዊን ፍልስፋና ሕሊናቸዉ የተበከለና የተመረዘ ነዉ:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል ሆነ መልእክት ከቁም ነገር ባይቆጥሩትና በራሳቸዉ እዉቀት መነሻ ቢተቹና ቢቃወሙ ብዙም አያስደንቅም:: ምክንያቱም ለእነርሱ ከእነርሱ በላይ የሆነዉ እግዚአብሔር ሳይሆን እዉቀታቸዉ ስለሆነ እዉቀታቸዉን እንደ አምላክ ቆጥረዉ «እኔ ከማምነዉና ከማዉቀዉ እዉቀት ዉጭ የሆነ አላምንም፤ አልቀበልም» ቢሉ የሚጠበቅ ነዉ:: ስለሆነ አስተሳሰባቸዉና አቋማቸዉ ብዙም አያስገርምም:: ሊያስደንቅና ሊያስገርም የሚችለዉ በመንፈሳዊ እዉቀት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዉ ሊቅና ሊቃዉነት ተብለዉ እዉቀታቸዉ ጣዖት ሆኖባቸዉ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት መቀበል የተሳናቸዉና የሚሳናቸዉ ነዉ:: ምክንያቱም የፈቀደዉ እዉቀት ይኑራቸዉ ከእግዚአብሔር እዉቀትና ጥበብ ጋር ሲነጻጸር፤ በዓለም ዉስጥ ካለ የዉኃ አካል ጋር አንድ ጠብታ ስትነጻጸር ካለዉ ልዩነት መጠን እጅግ እጅግ ያነሰ ስለሆነ፤ ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርገዉና ባዶ ሆነዉ መቅረብ ሲጠበቅባቸዉ ራሳቸዉን እንደ አዋቂና ሊቅ በመቁጠር «ከእኔ አስተሳሰብና እዉቀት ዉጭ የሆነን፣ የእግዚአብሔር መልአክ ቢናገረኝ እንኳ አልቀበልም» ማለት፤ «እኔ ከእግዚአብሔር በላይ ነኝ» ማለት ነዉ:: በዓለማዊ እዉቀት ያሉ ከፍተኛ የእዉቀት ደረጃ ላይ ያሉ ምሁራን የእግዚአብሔርን ቃለ በሚገባ ካወቁና ካስተዋሉ ብዙዎቹ ከማንም በላይ ስለ እዉነት እንደሚቆሙ ይገመታል:: ምክንያቱም ለሕሊናቸዉ ታምነዉ «ለምን በደልና አድሎ ይፈጸማል? ለምን ተግባራዊ የማይሆን የይስሙላ ነጻነት በወረቀት ላይ ይሰፍራል? ከሰፈረ ደግሞ ለምን ተግባራዊ አይሆንም? ለምን ኢ- ሰብአዊ ተግባር ይፈጸማል? ለምን ስለ እዉነት ስለተመሰከረ ሰዎች ይታሰራሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ይገደላሉ? ... ወዘተ» በማለት በጦር መሳሪያ የተደራጀን መንግሥት ሳይፈሩና «ለክብሬ፣ ለጥቅሜ» ቅድሚያ ሳይሉ የሚቃወሙና የሚተቹ ቆራጦች አሉበትን::

የእግዚአብሔርን ቃል አዉቆና አስተዉሎ «ለክብሬ፣ ለጥቅሜ፣ ለሥልጣኔ፣ ለዝናዬ... ወዘተ» የሚል ግን የጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ የአይሁድ ካህናትና የሕግ አዋቂዎችን ሕይወት ስለተላበሰ ለእዉነተኛ አገልግሎት መሰለፉ አጠራጣሪ ነዉ:: ምክንያቱም እዉቀቱ ለመከበሪያና ጥቅም ለማግኘት

ነዉ የተጠቀመበት እንጂ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል አይደለም። ለእዚህም ነዉ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ የተሰለፉ ትልልቅ ቦታ ላይ የደረሱ ስለ ክብራቸዉና ጥቅማቸዉ እንዲሁም ለሥልጣናቸዉና ለዝናቸዉ ሲሉ ከነፈሰዉ ጋር አብረዉ የሚነፍሱትና በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባር ላይ የሚሰለፉትና ተባባሪ የሚሆኑት፡

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ በአሁን ሰዓት በለተያየ ሥልጣን እርከን ላይ ያሉና በተለያየ ቁልፍ ኃላፊነት ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እዉነተኛ ታሪክ የማይናገሩና የሕወሓት ኢሕአዴግ ቡድኖች ወደ ወንበር ከመጡ በኋለ የፈጠሩትን የማስመሰልና የክህደት ታሪክ ነዉ ለትዉልዱ የሚያቀርቡት። በዚህ ላይ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__፡ በግልጽ እንደሚታወቀዉ ኢትዮጵያና የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ሰይጣናት ዋንኛ ጠላት ናቸዉ። በመሆኑም ለዘመናት ዲያብሎስ ኢትዮጵያንና የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ለማስጠፋትና ለማጥፋት የመጨረሻዉን ጥረት አድርጓል። በተለይ ከሃያ ዓመት ወዲህ ጥረቱ ተሳክቶለት ለፍሬ እየበቃለት ነዉ። ነገር ግን ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አገር ስለሆነችና እስካሁን ድረስ በታማኝ አገልጋዮቿና አማኞቿ ቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ተጠብቆ ስላለ የመጨረሻ ዉጤት የሚሆነዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ለማጥፋት የተሰለፉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከምድር ይጠራጋሉ፣ ይጸዳሉ። ያለፈዉና የቅርቡ ዉጤት ምንም የከፋና የሚከፋ ቢሆንም የመጨረሻዉ ዉጤት እጅግ እጅግ የላቀ ስለሚሆን በዚያ እንጽናናለን።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ** አሁን ያለዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የዲያብሎስ እንደራሴና አገልጋይ ስለሆነ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት የተሰለፈ ስለሆነ «እዉነተኛዉን የኢትዮጵያን ታሪክ ላቅርብ» ካለ በተዝዋዋሪ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት ታሪክ ስለሆነ የሚያቀርበዉ፤ ይህን ደግሞ ሕሊናቸዉ ዉስጥ የነገሠዉ የዲያብሎስ መንፈስ ለመመስከር ስለማይፈልግ፣ ያለዉ አማራጭ የዉሸት እዉነት ታሪክ መፍጠርና ማዉራት ነዉ ። ለዚህም ነዉ በጽሑፍ ሆነ በትምህርት እንዲሁም በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ (ማስ ሚዲያ) የፈጠራ ታሪክ የሚወራዉና ትዉልዱ ወደ እዉነተኛ ማንነቱ እንዳይመጣ ሕሊናዉን በተለያየ ወሬ አደንዝዘዉት በሥጋዉም በነፍሱም እየገደሉት ያለዉና ራሳቸዉን ደግሞ የተለየ ቦታ ላይ አስቀምጠዉ በተለየ ግነትና ክብረት የሚታዩት። ነገር ግን ሁሉ በእግዚአብሔር የሚታወቅና ጊዜዉም የተገደበ ስለሆነ እዉነት ባለ ጊዜ ስትሆን በኢትዮጵያ ቀን ያኔ የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ይገለጣል። ሐሰተኞችም ይዋረዳሉ። ከነክህደታቸዉም ወደ መቃብርና ወደ ጨለማዉ ቦታ ይወርዳሉ።

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት «ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት አሳይተናል፣ ወዳደጉት አገራት እየደረስን ነዉ፣ በቅርቡ እንደ ሕንድና ቻይና ከፍተኛ እድገት ደረጃ ላይ እንደርሳለን፣ ለሕዝቡ የሚፈለገዉን እያደረግንለት ነዉ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያን በዓለም

ላይ ሞገስንና ዝናን እያገኙ ነዉ፣ የኢሕአዴግ መንግሥት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን የቆመ ነዉ.... ወዘተ» እያሉ በየቴሌቭዥኑ፣ በየሬድዮኑ፣ በየስብሰባዉ፣ በየጽሑፉ ያቀርባሉ፡፡ በእዉኑ ከፍተኛ ኢኮኖሚ እድገት አሳይተናል ወይ? ወደከፍተኛ እድገት እያመራን ነዉ ወይ? ሕዝቡን ከችግርና ከጉስቁልና እየወጣ ነዉ ወይ? በዓለም ላይ ሞገስና ዝና እያገኘን ነዉ ወይ? ባጠቃላይ ለዓለም የሚታይ ብልጽግናና ክብር ደረጃ ላይ እየደርስን ነዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ በእዉነተኛዉ ሕሊናዉ በሚመለከትና በሚታዘብ ሰዉ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን እንደ አሁን ኢሕአዴግ ዘመን ተዋርደዉና ተንቀዉ፣ ተጠልተዉና ተሰደዉ፣ ጎስቁለዉና ተንከራተዉ፣ መከራና ፍዳ ድርሶባቸዉ አያዉቅም» ብሎ መናገር ማጋነን አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ከአርባ ዓመት በፊት ኢትዮጵያዉያን በዓለም ዘንድ የተለየ ሞገስና ክብር የነበራቸዉ፣ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ጭምር ኩራት የነበሩ፤ በጀግንነታቸዉ፣ በነጻነታቸዉ፣ በሃይማኖታችዉ፣ በባህላቸዉ፣ በጨዋነታቸዉ፣ በአስተዋይነታቸዉ፣ በዉበታቸዉ፣ ባጠቃላይ በመልካም ጎናቸዉ የሚታወቁ፤ ሕዝቡም የአገርና የወገን ፍቅር የነበረዉ ነበር፡፡ ሕሊናዉን የማይሸጥ እንደ ቦይ ዉኃና እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብሎ የማይነዳ፣ ለአገርና ለሕዝብ የሚስብ ትዉልድ ነበር፡፡

አሁንስ? ብንል፤ ወደ ዉጭ የመዉጣት ነጻ እድል አሁን ላለዉ ትዉልድ ቢሰጠዉ፤ እንኳን በጉስቁልናና በችግር ያለዉ ዜጋ አይደለም በጥሩ ገቢ ዉስጥ ያሉ ሰዎች ሳይቀር ከአገራቸዉ ተሰደዉ በዉጭ መኖርን ነዉ የሚመርጡት፡፡ «በአሁን ሰዓት ከመቶ አስር እጅ(አሥር ፐርሰንት) የሚሞላ ኢትዮጵያዊ ስለ አገርና ወገን ፍቅር ብሎ በኢትዮጵያ ምድር የሚቀር ሰዉ ይኖር ይሆን?» ብሎ አንድ ሰዉ ቢጠይቅ፤ «አዎን» ብሎ በድፍረት የሚናገር ባለሥልጣን ይኖር ይሆን? ሕሊናዉን የሸጠ ትዉልድና እዉነቱን ሕሊናዉ እየመሰከረበት ከሕሊናዉ ተቃራኒ ስለሚሰራና ስለሚናገር አሁን ያሉ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች፤ «አስር ፐርሰንት ብቻ አይደለም ከዘጠና ፐርሰንት ባላይ የአገርን የወገን ፍቅር እንዲኖረዉ ስላደረግን ከአገሩ መዉጣት አይፈልግም» ብለዉ ከመመለስ ወደ ኋላ የማይሉ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እዉነታዉ ግን አገራዊና ወገናዊ ፍቅር እንዳይኖረን፣ ሌት ተቀን ስለገንዘብ ብቻ እንድናስብ፣ አምላካችን ገንዘብ እንዲሆን፣ በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተበከለና የተመረዘ ሕሊና እንድንይዝ በመደረጉ፤ ሕዝቡ አገሩን ለቆ በሌላ አገር መኖርን የሚመርጥ ሆኗል፡፡ ይህም የጨለማዉ ገዥ ሥርዓት የፈጠረዉና ሕዝቡ ኢትዮጵያዊነት ስሜት እዳያድርበት፣ እንዲሁም ስለ ወገኑ እንዳያስብና እንዳይቆረቆር በመደረጉ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ይኸዉ በሕጋዊና ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ትዉልዱ ወደ ዉጭ እየጎረፈ ይገኛል፡፡ የተወሰኑትም በኢትዮጵያ ምድር ከመኖር በዉጭ ምድር ብሞት ይሻለኛል እያሉ በየበረኃዉና በየባሕሩ እየተጣሉ የምናየዉና የምንሰማዉ አሳዛኝ ክስተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ብዙ እህቶቻችን ተከብረዉበት ከሚኖሩትበት ከእናት አገራቸዉ ተሰደዉ በግርድና ሕይወት ተሰማርተዉ ያሉትና ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ መስራታቸዉ ሳያንስ፤ ከሚሰሩበት ስደት አገር ተቆርቋሪና ጥብቅና የሚቆምላቸዉ መንግሥትና አካል ጠፍቶ፣ አሰሪዎቻቸዉ ከፎቅ ላይ እየወረወሯቸዉና አካላቸዉ ላይ የተለያየ መከራና ስቃይ እያደረሱባቸዉ የምንመለከተዉና የምንሰማዉ የየእለት ዜና ነዉ፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ ሲባል እንደ አዉሬ የሚታይና የምንበላዉ፣

የምንጠጣዉ፣ የምንጠለልበት የሌለ እስከሚመስል ድረስ ነዉ በዉጭ ዓለም የምናታየዉ:: ታዳይ ይህ ጉስቁልናና ዉርደታችን ነዉ ትልቅ ቦታ ላይ ደርሰናል፣ በልጽገናል፣ ምጣኔ ሀብታችን አድጓል፣ ዝናና ሞገስ አግኝተኛል ... ወዘተ የሚያስብለን?

በእዉነት እንነጋገር ከተባለ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት አንድ ፐርሰንት የማይሞሉትን ሰዎች ሚሊየነር ስላደረገና፤ የተወሰኑ የሥርዓቱ ተጠቃሚ ሌት ተቀን እንደ አምላክ የሚያመሰግኑትና የሚያገኑት ትዉልዶችን ስላዛጋጀ፤ «ሕዝቡ ከችግር ተላቋል፣ ኑሮዉ ተሻሽሏል» ማለት ይቻላልን? እጅግ እጅግ ብዙዉ ሕዝብ በቀን ሦስት ጊዜ ሊመገብ ቀርቶ አንዴና ሁለቴ ለመመገብ አልተቸገረምን? በየመንገዱ፣ በየእምነት ተቋሙ ዙሪያ የወደቁት ኢትዮጵያዉያን አይደሉምን? ማነዉ ዞር ብሎ ያያቸዉ? ወስኪ የሚያንቀረግረዉ ነዉ ወይስ ጮማ የሚቆርጠዉ ወይስ በኮብራና በፎቅ የሚፏለለዉ ነዉ ከድህነት አወጥቶ በብልጽግና ሕይወት ዉስጥ ያስገባቸዉ? ትዉልዱ ተስፋ እንዲቆርጥ፣ እግዚአብሔርንም ሰዉን እንዳይፈራ ተደርጎ በመቀረጹ ምክንያት በየጫት ቤቱ፣ በየሺሻ ቤቱ፣ በየቁማር ቤቱ፣ በተለያዩ አልባሌ ቦታ እንዲዉሉ የተደረገዉ፤ ስለ ሕዝብ የሚያስብ መንግሥት ኖሮ ነዉን? ሌላዉ ደግሞ ስንቱ ባለሀብት ነዉ እየተባለ፤ ስንትና ስንት ቦታ እየተሰጠዉ በነጻነት ሲሰራና ሲያለማ፤ ኢትዮጵያዊዉ ግን በእናት አገሩ ምድሩ ሰርቶ እንዳይበላና እንዳይኖር «ይህ ያንተ አገርና ክልል አይደልም» እየተባለ ከአገሩ ሲሰደድና የትም ሲጣል፤ በበላይ ሆኖ ይህን የሚያስፈጽም መንግሥት ነዉ ለሕዝብ የቆመ መንግሥት? በየመስሪያ ቤቱ ባለጉዳይ ሲጉላላና ሲመናጨቅ ይህ ነዉ የሕዝብ አገልጋይነትን  የሚያስመሰክር? ሕዝቡን «በነጻነት የመኖር፣ የመናገር፣ የመጻፍ መብት ተሰቶሃል» እየተባለ ስለ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ተግባራቸዉ ሲመሰከርባቸዉና «ሕሊናዬን አልሸጥም» ሲል የተለያዩ መበቀያ አዋጆችን በየጊዜዉ እያወጡ ትዉልዱን መበቀላቸዉ ነዉ ለኢትዮጵያዉያን የቆሙ ናቸዉ የሚያስብላቸዉ?

ትዉልዱ ኢትዮጵያዊነቱን ንቆና ትቶ አዉሮፓነትንና አሜሪካዊነትን መርጦ በተራቆተና ለዝሙት በሚያነሳሳ አለባበስ በመገለጹ ነዉ በዓለም ዘንድ ሞገስና ዝና ያሰገኘለት? የዝሙትና የአመንዝራነት ማስታወቂያ እያተበረታታና በዲሞክራሲ ሽፋን የዝሙት ስራንና የዝሙት ቤቶችን እያስፋፋ፣ እንዲሁም የዳንኪራና የዘፈን ቤቶችን እያጠናከረ፣ ከዚያም በላይ ባዕድና ጣዖት አምልኮ እንደ ታላቅ ስራ እየቆጠረና እያበረታታ፣ ባጠቃላይ የዝሙትን መንፈስና የርኩሰትን መንፈስ በአራቱም ማእዘን እያስፋፋ ነዉ «ኢትዮጵያ ከበለጸጉት አገር ጎዳና አሰልፋለሁ» የሚለዉ?  ከሕፃን እስከ አዋቂ ድረስ በዳንኪራና በዘፈን ነፍሳቸዉን ስላሰባደ ነዉ እንደታላቅ ስራ የሚወራለት? ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ነግሦ፣ ፍቅርና መተሳሰብ ጠፍቶ፣ ሰዉ ሁሉ አዉሬ ሆኖ መኖርን እንዲመርጥ በመደረጉ ነዉ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዉያን የቆመ መንግሥት ነዉ የሚያስብለዉ? የአንዲት እናት ልጆች የነበሩ እንዲገነጣጠሉና ከዚያም ጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች የኢትዮጵያን ሀብትና ንብረት እንዲቀራመቱት በመደረጉ ነዉ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ቆመዋል የሚያስብለዉ? ያ ብቻ አይደለም እንዲገነጣጠሉ ያደረጉት እንሶ እንደ ገና አንዳች የተለየ ለዉጥ ላላመጡበት፣ ሕዝቡ እርስ በእርስ እንዲገዳደልና ደሙ በከንቱ እንዲፈስ ማስደረጋቸዉ ነዉ ስለ ኢትዮጵያዉያን ቆመዋል የሚያስብለዉ? እንዲሁም ሕዝቡን «በነጻነት የፈለገዉን መምረጥ ትችላህ»

ብለዉ አለመመረጣቸዉን ሲያረጋግጡ በተለያየ መንገድ ሕዝቡን በመበቀላቸዉና ደሙን በማፍሰሳቸዉ፣ በማሰራቸዉ፣ በማሳደዳቸዉ፣ በመግደላቸዉ፣ የተለያዩ ተጽኖ ማሳደረቸዉ ነዉ ወይ ለሕዝብ የቆሙ ናቸዉ የሚያስብለዉ?

ባጠቃላይ በዚህች በእግዚአብሔር አገር ላይ ዓመፃን፣ ክህደትን ፣ ርኩሰትን በማንገሣቸዉና ሕዝቡን ለችግርና ለመከራ፣ ለእስራትና ለስደት፣ ለእርዛትና ለረኃብ፣ ለሞትና ለጎስቁልና ሕይወት ስላበቁት ነዉ «አበልጽገዉናል፣ አሳድገዉናል፣ ወደታላቅ አገራት ደረጃ ላይ አድርሰዉናል፣ ለዓለም ሞገስና ክብር እንድንሆን አብቅተዉናል፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት የቆሙ ናቸዉ » እየተባለ ሕዝቡ የሚሸነገለዉና ሌት ተቀን በተለያየ ብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያ) የሚለፈፈዉ!?

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: «የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከአሥር አኃዝ ብላይ አደገ፣ እድገታችን በዓለማ አቀፍ ደረጃ በአድናቆት ተነገረለት፣ አድገናል፣ በልጽገናል ... ወዘተ» እየተባለ ነጋ ጠባ የሚወራዉ ሐሰት ነዉ ማለት ነዉ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__: ኢትዮጵያ በጥሩ ጎኗ ስሟ ሲጠራ እንዲሁም እዉነተኛ ማንነቷ ሲታወቅ እንደ ኢትዮጵያዊነታችን ደስ ይለናል እንጂ አይከፋንም:: ነገር ግን ሕዝቡ እየተራበ፣ እየተቸገረ፣ እየተሰቃየ፣ እየታሰረ፣ እየተሰደደ፣ እየተገደለ፣ ባጠቃላይ መከራና ስቃይ እየደረሰበት፣ ተቃራኒዉን መናገርና ሌት ተቀን መለፈፈ በሕዝብ ላይ ማላገጥና መቀለድ ነዉ:: ያለዉ እዉነታ በደንብ ይታወቃል:: ይህንንም እዉነታ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ ሰባት በገጽ 24-29 ላይ ተገልጿል:: ይኸዉም:

«አንዳንድ ምሁራን «የእድገት መለኪያዉ መስፈርት ትክክለኛ የአገርና የሕዝብ እድገትና ብልጽግና አይገልጽም » በማለት ለአገሪቱ ለምጣኔ ሀብት ባለሙያተኞች አስተያየታቸዉን አቅርበዋል:: ይኸዉም «በተለይ እጅግ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዉያን በችግር ዉስጥ እያሉና በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ በብልጽግናዉ ዓለም እየተንዙ እያለ «አገሪቷ ከ10٪ በላይ እድገት አሳይታለች:: በጥቂት ዓመታት ዉስጥ እንደቻይናና ህንድ ትሆናለች» እያሉ ሕዝቡን ማደንዘዛቸዉና ከግምት ዉስጥ የሚያስገባቸዉን ወሬ ነጋ ጠባ ማዉራቱ አግባብነት የለዉም:: እንዲሁም «በአገሪቱ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ተሰርተዋል፤ የተለያዩ መንገዶች፣ የተለያዩ ተቋማት፣ የተለያዩ የልማት አዉታሮች.. ወዘተ ተዘርግተዋል:: ጂዲፒ ከፍ ብላል» እየተባለ ሕዝቡ ግን በችግር፣ በጉስቁልና፣ በልመና፣ በረኃብ፣ በእርዳታ፣ እየተማረረና እያዘነ የሚኖር ከሆነ፤ በጥቂቶች ሰዎች መበልጸግና መግነን እንዲሁም በህንጻ መሰራትና በተቋማት መብዛት እንዴት በለጸግን፣ ኢኮኖሚያችን አደገ ለማለት እንደፍራለን?» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል::

የሚመለከታቸዉም አካል፤ «በእዉነቱ ለአገሪቱ እድገት ተቆርቁራችሁ አስተያየት መስጠታችሁ አግባብ ቢሆንም የእኛ ስሌት በዓለም አቀፍ ስሌት መሰረት ስለሆነ፤ የዓለም አቀፉ ስሌት መድኸየትን

እንደ እድገት የሚቆጥር ቢሆን እንኳ፤ እኛም በዚያዉ መሰረት ነዉ የምናሰላዉ እንጂ እንደ ማንነታችን ወይንም ስሙን እንኳ ብዙ ጊዜ እንዲጠራ ባይፈለግም ሰላይ ስለሌለብኝ ለጊዜዉ ብጠራዉ ችግር የለዉምና ይኸዉም እንደ ኢትዮጵያዊነታችን አይደለም የምናሰላዉ:: ብዙዎቻችን በካፒታሊስት መንፈስ የተጠመቅንና ከኢትዮጵያዊነታችን ይልቅ ለጌቶቻችን «ብሔር ብሔረሰቦች» እያልን ሕሊናችንን መሸጣችንን ብናስመሰክር ነዉ ሞገስና ሥልጣን የምናገኘዉ::ለዚህም ነዉ እየተሰቀኩ «እንደ ኢትዮጵያዊነታችን» ያልኩት ::

ከእናንተ ቀደም ብለዉ የተወሰኑ «አገር ወዳድ ነን» ብለዉ ወደ እኛ በመምጣት የሚያስገርምና የሚያስቅ የብልጽግናና እድገት ትንታኔ አቅርበዉልን ነበረ:: ይኸዉም « እኛ ኢትዮጵያዉያን ድሆችና ጎስቋሎች አይደለንም:: ከማንም የዓለም ሕዝብ በላይ ሀብታሞች ነን:: እናንተ ተስፋችሁ ምድራዊ ስለሆነና ለልመናና ለእርዳታ እንዲያመቻችሁ ልመና ሃፍረት ያልሆነባችሁ ከየመንግሥታቱ «እኛ ለማኞች ድሆች ነን» እያላችሁ የተለያዩ አገራት መንግሥታትን ደጅ የምትጠኑ አሰዳቢዎች ናችሁ:: ሕዝቡን ራስ ወዳድና ስግብግብ አደረጋችሁት እንጂ እዉነተኛ ለአገሩና ለሕዝቡ የሚቆረቆር መንግሥት ቢኖር ለፖለቲካዉ ዓለማ ሲል በህዳሴ ግድብ ስም በተለያየ መንገድ ከሕዝቡ ገንዘብ እንዳሰባሰበ ሁሉ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ «ወገን ለወገኑ ይድረስለት» በማለት ሕዝቡ እርስ በእርስ እንዲተሳሰብ፣ እንዲተዛዘን፣ እንዲረዳዳ፣ እንዲፋቀር፣ አንድ እንዲሆን አድርጎ ቢሆን ኖሮ አንድ ለማኝ ለማየት ብርቅ ይሆንብን ነበር::

ነገር ግን መንግሥታችሁ ነጋ ጠባ «ለብሔር ብሔረሰብ፣ ለሰንሴሽን ኮንደም፣ለዘፈንና ለዳንኪራ.. ወዘተ» ቅስቀሳ የሚያደርግና በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ የሚያሳምጽ፤ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲጨካከን ያደረገ ጨካኝ ነዉ:: «ኢኮኖሚ አደገ» ሊባል የሚችለዉ ደግሞ ሁሉ በልቶ ሲኖርና ራሱን ችሎ መኖር ሲችል ብቻ ነዉ እንጂ ሕንጻና የተለያዩ ተቋማት በመሰራታቸዉ «አደግን፣ተመነደግን፣ ኢኮኖሚዉ ከፍ አለ» ልንል አንችልም:: ከሁሉ በላይ ደግሞ በመንፈስ ደሀ የሆነ መንግሥትና ሕዝብ ነዉ ደሀና ጎስቋላ እንጂ እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ ራሱ ፈቅዶ እየጾመ የሚራብ፣ የጾመዉን ደግሞ የሚበሉትና የሚቀምሱት ለሌላቸዉ ወገኖቹ የሚሰጥ ሰዉና ሕዝብ አይደለም:: ይልቁኑ ይህ አይነቱ ሕዝብ እዉነተኛ ባለጸጋና ባለሀብት ነዉ::

ምን ዋጋ አለዉ የብዙ ሀብትና ንብረት ባለቤት ሆኖ ባዶነት በተሞላ ሕይወት መኖር!? ምን ዋጋ አለዉ ምድራዊ ሕይወትን ብቻ ተስፋ ያደረገ ኑሮ መኖር? ስንቱ ነዉ በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት የሰበሰበዉን ሀብትና ንብረት ሳይበላና ሳይጠቀምበት ለማንም አስረክቦና በትኖ በሥጋ ሞት ወደ ሁለተኛ ዓለም የተጓዘዉ? ስንት ችግረኛንና ድሀን ረግጦና ዞር ብሎ ሳያይ በስግብግብነት ለራሱ ብቻ ያከማቸዉን ሀብትና ንብረት እንኳን ራሱ ሊጠቀምበት ቀርቶና «ለትዉልዴ አስተላልፋለዉ» ብሎ የተጨነቀበትና የተጠበበት ከንቱ መኖ ሆኖ የሚቀርበት አጋጣሚ የለምን? ስለወደፊቱ ማን እንደሚጠቀምበትና እንደሚበላዉ በእርግጠኝነት መናጋር ይቻላልን? አይቻልም:: ታዲያ እያንዳንዱ ባለሀብት ምናለ ምስኪን ወገኑን ቢያስብ? ወገኑን ቢያስብ ኖሮ እዉነተኛ እርካታንና በረከትን ያገኝ

ነበር:: ነገር ግን ባለሺህዉ ባለመቶ ሺህ፣ ባለመቶ ሺህዉ ሚሊየነር፣ ባለ ሚሊየነሩ ቢሊየነር ለመሆን ነዉ ሌት ተቀን የሚሯሯጠዉ እንጂ በየቦታዉ የወደቀዉን የአዳም ዘር ወገኑን ዞር ብሎ የሚያይ ባለሀብት ስለሌላ ይኸዉም እንደምናየዉ በተቅበዘበዘና እርካታ በሌለዉ ሕይወት ሲባዝኑ ነዉ የሚታየዉ::

ምስኪኑ ወገን ደግሞ የሚመለከተዉ በሥጋዊ ዐይን የሚታየዉን ኮልኮሌ ነገሮችን ስለሆነ፤ እርሱም በምኞች ይቃጠላል እንጂ ባለዉ ተመስገን እያለ ረክቶ መኖርን አይመርጥም:: እንዲህ ስንል ደግሞ ሰዉ ኑሮዉን ለማሸነፍ አይዉጣ፣ አይዉረድ፣ አይንቀሳቀስ ለማለት ሳይሆን አቅም ያለዉ ሰዉ የተቸገረዉ ወገኑን «ቤተሰቤ ፣ ዘመዴ፣ ዘሬ፣ ጎጤ» ብሎ ልዩነት ሳይፈጥር እንዲረዳ፣ እንዲያግዝ ለማሳሰብ ነዉ እንጂ በዚህች ስደት አገራችን ምድር ዉስጥ ወተን፣ ወርደን እንድንሰራና እንድንኖር ነዉ የታዘዝነዉ:: በሃይማኖታችንም ቢሆን ስንፍና የተከለከለና እያንዳንዱ ሰዉ ሰርቶ እንዲበላ ነዉ የታዘዘዉ:: ስለዚህ ሁላችንም በትጋትና በንቃት መስራት እንደሚጠበቅብን ይታወቃል::» በማለት ነበር ብሶታቸዉንና ፍልስፍናቸዉን ያቀረቡት::

በወቅቱም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተወካይ የሰጧቸዉ ምላሽ « እናንተ ናቸዉ አገራችንን ደሀ ያደረጋችሁት:: የገዥ መደቦች ናቸዉ ብሔር ብሔረሰቦችን ለመጨቆንና ለማድኸየት «እግዚአብሔር ፣ መንግሥተ ሰማያት፣ ገነት፣ ሲኦል፣ ገሃነመ እሳት .. ወዘተ» እያሉ አገራችን እንደ አሜሪካና ቻይና እንዳትሆን «በእለተ ሰንበት እሁድ ሙሉ ጊዜያችሁን በመንፈሳዊ አምልኮና ተግባር ላይ ብቻ አዉሉ፤ ዓበይት በዐላት በሆኑት ዘመን መለወጫ፣ በመስቀል፣ በልደት፣ በጥምቀት፣ በስቅለት፣ በትንሳኤ..ወዘተ የሥጋ ስራ አትስሩ፤ መንፈሳዊ ተግባር በመፈጸም ነፍሳችሁን አሳርፉ» በማለት ሕዝቡ ከዓመት እስከ ዓመት ሃያ አራት ሰዓት ለሥጋዊ ኑሮዉ እንዳይሯሯጥ ያደረጋችሁት:: እንዲሁም ተስፋችን የሆነችዉን ምድር ህንጻ በህንጻ እንዳትደምቅና በዉስጧም በዘፈንና በዳንኪራ እንዳንዝናና ነፍሳችንን እየጨቆናችሁ ያላችሁት እናንተና መሰሎቻችሁ ናችሁ:: ይብላኝ ለእናንተ እንጂ እናንተ ለነፍስ ህንጻ ስታስቡ እኛ ደግሞ ለሥጋ ህንጻ የሚመች የብልጽግና የብሔር ብሔረሰቦች ጎዳናን የጀመርን ስለሆነ ወደ ኋላ አንመለስም:: ይልቁኑ መጥገብ አይደለም ገና በደንብ ያልቀመሳችሁትን ሕግ መንግሥታችንን ብታታጣጥሙት ኖሮ ረኃባችሁንና ችግራችሁን ማስወገድ ትችሉ ነበር» በማላት ምላሽ የሰጧቸዉ ሲሆን፤

ሰዎቹ ግን የተወካዩ ንግግር አሳዝኗቸዉና አስቆጥቷቸዉ ነበርና ወዲያዉ «እናንተ ሃፍረተ ቢሶች ናችሁ:: ብላችሁ ብላችሁ አሜሪካን፣ አዉሮፓን፣ ኤሽያን፣ ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ጋር ታነጻጽራላችሁን!? የመጨረሻ ጎስቋላና ድሀ አገራትን ከቅድስት ኢትዮጵያ ጋር ለማነጻጸር ሕሊናችሁ እንዴት ደፈረ? ወይስ በማያየዉ ዐይናችሁና ማስተዋል በጎደለዉ አእምሮዋችሁ ተመልክታችሁ ይሆን? ወይስ እንደ ቁስ አካላዊያን ይህ ቅርፊት ዐይናችሁ የሚያየዉ ሰዎች ጎስቋላ ኑሮና ሕይወታቸዉ እንዲቀልላቸዉ የሚያደርገዉን የተለያዩ ህንጻዎች፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት

የሚዉሉ የተለያየ መንቀሳቀሳዎችን፣ የተለያዩ የልማት አዉታሮችን ብቻ ነዉ? ወይስ ዐይናችሁና ሕሊናችሁ ዋናዉንና እዉነተኛዉን ህንጻ ነፍሳችሁን ማየት አልተቻለዉ ይሆን?

እነዚህ በሥጋዊ ዐይናችን የምናያቸዉ ለሥጋችን የሚጠቀሙና ጉስቁልና ሕይወታችንን የሚያቃልሉ ሁሉ ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆኑ ኮልኮሌዎች ናቸዉ እንጂ ለእዉነተኛ ገንዘባችን ለሕያዉ ነፍሳችን ድኅንነትና ብልጽግና የሚሰጡ አይደለም። በዚህም ምክንያት እናንተ እንደ ታላቅ አገር በቆጠራችዋቸዉ አገራት በየዕለቱና በየጊዜዉ በሚሊዮኖችና በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ነፍሳት( ሰዎች) እዉነተኛ ድኅነትና ብልጽግና አተዉ እየተጎሳቆሉና እየሞቱ ይገኛሉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን ምንም እንኳ በአንዳንድ ተጽህኖና በራሳችን ስንፍና ምክንያት በሥጋዊ ብልጽግናችን እነሱ ላይ ባንደርስም በነፍሳቸን ግን እጅግ የበለጸግንና ያልተጎሳቆልን ነን። የሥጋዊ ብልጽግናዉንም ራሳችንን ከስንፍና፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከትዕቢት፣ ከዓመፃ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከስግብግብነት፣ ከጥላቻ፣ ከመከፋፈል፣ ከመለያየት፣ ከዘረኝነት ፣ ከጎጠኝነት ..ወዘተ ከመሳሰሉት ካጸዳንና በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ከተመላለስን በአጭር ጊዜ ዉስጥ እነሱ ከደረሱበት በላይ ልንደርስ እንችላለን።

እነሱ ግን በዓመፃና በክህደት፣ እንዲሁም በርኩሰተ ሕይወት ዉስጥ ሆነዉ ስለሆነ ለዚህ የደረሱት፤ ብልጽግናቸዉና ሥልጣኔያቸዉ አንዳች ዋስትና የለዉም፤ በጥቂት ቀናት ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ( በተለያዩ መቅሰፍቶች) እንዳልነበረ ሊሆን የሚችል ነዉ። ምክንያቱም እጅግ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን አበለጸጉ እንጂ ለሕዝቡ አንዳች ነገር አላመጡለትም። ለዚህም ነዉ ሕዝባቸዉ በአሜሪካ ሆነ በአዉሮፓ እንዲሁም በኤሽያና በመካከለኛዉ ምስራቅ አገራት እየተቃወማቸዉና ብሶቱን በአዳባባይ እያሰማ ያለዉ። ለመንግሥታቱም በግልጽ « እናንተ የምትወክሉት አንድ ፐርሰንት የማይሞሉትን ግለሰቦች ነዉ እንጂ እኛን ዘጠና ዘጠኝ ፐርሰንት የምንሆነዉን አትወክሉምና ከወንበራችሁ ወርዳችሁ እኛን ብዙዎቻችንን ሊወክሉ የሚችሉ በወንበሩ ተቀምጠዉ ያገልግሉን» በማለት ድምጻቸዉን እያሰሙ ያሉት።

ደግሞ በዚህ ምድር ዉስጥ የፈለግነዉ ነገር ሁሉ ተሟልቶልን ነፍሳችን ግን ከእግዚአብሔር መንገድ ከወጣችና ሕያዉ ሆና ለምትኖርበት ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃት ካልቻለች ምን የተለየ ጥቅም እንሰጣታለን? ሥጋዊዉ ፍላጎቷ ብቻ ቢሟላላት ምን ትርጉም አለዉ? ከምድራዊ ሕይወት ዘመን በኋላ ለሕያዉነት ዘመን ከምንኖረዉ ሕይወት አንጻር የዚህች ምድር ኑሮ የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ አይሞላም። ታዲያ በዚህች ምድር ዉስጥ የዓለም ሀብትና ንብረት የኛ ቢሆን እንኳ ነፍሳችን ሕያዉ ሆና ለእግዚአብሔር መንግሥት መታጨት ካልቻለችና ለሕያዉነት ዘመን በሲኦልና በገሃመ እሳት ዉስጥ እንደ ዓመፃዋ ደረጃ ፍዳዋን የምትቀበል ከሆነ የዚህ ምድር ቆይታዋ ምን ይጠቅማታል? የድሎቱና የመንደላቀቁ ሕይወት ለነፍሷ ምን ያደርግላታል? ይልቁና ሰላም፣ እርካታ፣ ፍቅር፣ ደስታ ከማታገኝበት የድሎቱና የመንደላቀቂያዉ ሕይወት ቀርቶባት አምላኳን አምናና እንደ እርሱ ፈቃድ ተመላልሳ በምድራዊ ዘመኗም በእዉነተኛዉ ብልጽግና በበረከት፣

በሰላም፣ በፍቅር፣ በደስታ ሕይወት መመላለስና ከሥጋ ሞት በኋላ ደግሞ በቅዱን መላእክት አኗኗር በፍጹም ቅድስናና ደስታ ሕይወት ሕያዉ ሆኗ በመንግስተ ሰማያት መኖር አይሻላትምን?

እዉነታዉ ይህ ስለሆነ ነዉ እነዚህ በሥጋዊ ዐይናችን ስንመለከት የበለጸጉ የሚመስሉት አገራት በሙሉ ድሆችና ጎስቋሎች ናቸዉ ያልናችሁ፡፡ እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን አምላካችንን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ በተለያየ ስጦታዉ እየተጠቀምን ለሕያዉነት ሕይወት የሚሆነን ቅዱስ ቁርባን ስንቃችንን ይዘን በበረከት፣ በጸጋ፣ በርካታ፣ በኀሊና ሰላም፣ በፍቅር፣ በደስታ እየኖርን ያለነዉና ከዚህች ጎስቋላ ዓለም የምንገላገልበትንና ወደ አምላካችን እቅፍ የምንሄድበትን ቀን እያናፈቅን በታላቅ ተስፋ የምንኖረዉ፡፡

በእርግጥ እናንተ «ተማርን ተመራመርን ዶክተር፣ ፕሮፌሰር ነን፤» ብላችሁ ሕሊናችሁን የምትሸጡ እዉነቱን ሕሊናችሁ እየመሰከረባችሁ ለጊዜያዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ድሎት፣ ምቾት ስትሉ ሕሊናችሁን በማደንደን ጨለማዉን ብርሃን ፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ ዓመፃዉንና ክህደቱን እንደ ታላቅ ስራ፣ ታላቁን ስራ እንደ ዉርደትና ክህደት አድርጋችሁ የምታቀርቡ እነ ሆዱ አምላኩ ናችሁ፡፡ ነዉሩንና ዉርደቱ እንደ ክብርና ታላቅ የምትቆጥሩ፣ በሕዝብ ስምና በኢትዮጵያ ስም የምትነግዱ የዓመፀኛዉና የከሃዲዉ መንግሥት ካድሬ የሆናችሁ ባዶ ቀፎ ሰዎች ናችሁ፡፡ እምነታችሁ የቻርልስ ዳርዊን እምነት የሆነዉ « እኛ የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች አይደለንም፡፡ ዘሮቻችንም አዳምና ሔዋን አይደሉም፡፡ ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት የኒያንደርታንና የክሮማግነን ሰዉነት ደረጃ አልፈን አሁን ላለንበት ሰዉነት ማዕረግ የበቃነዉ» ብላችሁ የምታምኑ፡፡ በራሳችሁ ላይ ማፈሪና ያበደ አእምሮ መያዛችሁን የምትመሰክሩ ናችሁ፡፡ እኛን የሚሳዝነን ግን የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በእናንተ ዓመፀኞችና ከሃዲዎች መመራቷና የእናንተ ርኩሰት ተግባር በተቀሰደሰችሁ አገር ነግሦ ማየታችን ነዉ፡፡ ሕዝቡንም በጨለማዉ ስብከታችሁ በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በሕትመት ዉጤቶች፣ በስብሰባዉ አደንዝዛችሁት ለዲያብሎስ እየገበራችሁት መሆኑን በመመልከታችን ነዉ፡፡

እንግዲህ ወደ ልባችሁ ለመመለስ ፈቃደኞች ከሆናችሁ ዛሬ ነገ ሳትሉ እዉነተኛ ንስሐ በመግባት ራሳችሁን ከጥፋትና ከዉድቀት አድኑ፡፡ እንዲሁም ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብና አመለካከት አርማችሁ እንደ እዉነተኛ ማንነታችሁ እንደ ኢትዮጵያዊነታችሁ ልታስቡ፣ ልትናገሩ፣ ልትሰሩ ይገባል እንጂ በአሕዛብ ሥርዓት እየተመላለሳችሁ ራሳችሁን ደኃና ለማኝ ማድረግ የለባችሁም፡፡ እዉነተኛ ደኃ በመንፈስ ደኃ የሆነ ብቻ ነዉ፡፡ የሕሊና ሰላምና እርካታ የሌለዉ ተስፋ ቢስና በተቅበዘበዘ ሕይወት የሚኖር እርሱ ነዉ የመጨረሻ የዓለም ደኃና ጎስቋላ እንጂ፤ የሕሊናዉ ሰላም የተጠበቀ፣ የሕሊና ርካታ ያለዉ ሰዉ እርሱ እዉነተኛና በደስታ ሕይወትና ኑሮ የሚኖር ነዉ፡፡ በዓለም ሆነ በአገራችን ኢትዮጵያ ብዙዎቹ አምላካቸዉ ሆዳቸዉ፣ ክብራቸዉ ነዉራቸዉ ስለሆነ በዓመፃና በክህደት ሕይወት ዉስጥ ሆነዉ ወደ ሞትና መቀመቅ ዉስጥ እየሄዱ ስለሆነ ልታድኗቸዉና ወደ ሕይወት መንገድ ልታመጧቸዉ ይገባል፡፡ እንዲሁም እዉነተኛ ብልጽግናና እድገት ምን እንደሆነ

**በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታችሁ ልትመሰክሩና ልታስረዷቸዉ ይገባል እንጂ እናንተ በአሕዛብ አስተሳሰብ ልትመሩ አይገባል። እዉነተኛዉ ብልጽግናና ደስታ እንዲሁም ሰላም ለማግኘት ከተፈለገ እግዚአብሔር እንደ እዉነተኛ ፈጣሪነቱና አባትነቱ ተከብሮና ተፈቅሮ ሊመለክ ይገባል።» በማለት ተሰምቶም፣ ታይቶም የማይታወቅ ፍልስፍናና ምክር የሰጡ ቢሆንም፤ እኛ ግን ከእብድ ንግግር ባልተለየ መልኩ ነበር የሰማናቸዉ።**

*የእናንተ አቀራረብ ግን እንደ እኛዉ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ ስለሆነ ለሥጋ የሚመች ማንኛዉንም አስተያየት ለመቀበል ዝግጁዎች ብንሆንም ከፖለቲካችን በተለይ ከብሔር ብሔረሰብ ክፍፍላችን የሚቃረን ወይንም የማይጣጣም አሳብ ከሌላችሁና እንኳን ለአገር የሚበጀዉን አሳብ ቀርቶ «ዝርያችሁ ጦጣዎች ናቸዉ። ሁሉም ነገር የተፈጠረዉ ከቁስ አካል ስለሆነ እግዚአብሔር ሆነ ሰይጣን የሚባል ነገር የለም። «መንግስተ ሰማያት፣ ሲኦል፣ ገሃነመ እሳት» የሚባል ነገር የለም ተረት ተረት ነዉ» እያላችሁ ምሁራዊ ትምህርትና ትንታኔ ስትሰጡን በደንብ ተቀብለናችኋል። በዚህም መሰረት የመጀመሪያዉ የማርክዚስትና ሌኒዚስት ፍልስፍናችሁን አሻሽላችሁ ከሶሻሊዝም ሥርዓት ወደ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስታሸጋግሩንም በደስታ ነዉ የተቀበልናችሁ።» በማለት አሰተያየትና መላሽ ስለሰጡ እኔ የጨለማዉ ገዥ በመጨረሻ ንግግራቸዉ ስለተደሰትኩ ቀደም ሲል ስለ ኢትዮጵያ ቀባጥረዉ በነበረዉ ንግግራቸዉ ላስመታቸዉ አስቤ የነበረዉን ክፉ አሳብ ለጊዜዉ አንስቼላቸዋለሁ። » ይላል የጨለማዉ ገዥ ትዉልዱን በሥጋዊ ዐይን በሚታየዉ ያደነዘዘዉና በብልጭልጭ ዓለም ሕሊናዉን ያሳመጸዉ ዲያብሎስ።» ተብሎ ተገልጿል»* **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ክፍል ሰባት

### ምዕራፍ አንድ

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: ብሔሮትንና ዘሮትን እንዲሁም ነገዶትን ቢገልጹልን?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: እስከአሁን በገለጽኩላችሁ ምላሽ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይነቴና እንደ አዳም ዘርነቴ እንዲሁም እንደ ኢትዮጵያዊነት ነዉ ያቀረብኩት እንጂ ጉሳን ወይንም ነገድን ወክዬ አይደለም:: ኢትዮጵያዊነት እንደ ብሔር የሚቆጠር ከሆነ ብሔሬ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነዉ :: እኔ ግን ኢትዮጵያዉነትን እንደ ሃይማኖት ነዉ የምመለከተዉና የምቀበለዉ:: በኢትዮጵያዊነት ላይ ዓመፃና ክህደት፣ እንዲሁም ርኩሰት ፈጸምኩ ማለት በሃይማኖቴ ላይ ዓመፃ፣ ክህደተ፣ ርኩሰት እንደፈጸምኩ ነዉ የምቆጥረዉ::

ዘሬንና ነገዴን በተመለከተ በነፍሴ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልኩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቄ ከእግዚአብሔር ፍጹም ልጁነትን ያገኘዉ ሲሆን፤ በሥጋዬ ደግሞ ሕያዋን የሆኑት የአዳምና ሔዋን ዘር የሆንኩና የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉሕድ ዘርና እንደማንኛዉ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት አባልና የመልከ ጼዴቅ ወገን የሆንኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ::

***ጠያቂዉ አገልጋይ***: ስለ ቋንቋ ምን የሚሉን አለ?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: በመጀመሪያ ለመግለጽ የምፈልገዉ የቋንቋ መለያየት የመጣዉ በጽድቅ ስራ ሳይሆን በሰዎች ዓመፃ፣ ክህደትና ርኩሰት ተግባር እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነዉ ቋንቋቸዉን የደባለቀዉ:: ታዲያ ከእኛ የሰዉ ዘሮች የሚጠበቀዉ በኃጢአታችን ምክንያት የመጣዉን መለያየትና መከፋፈል በጽድቅ ስራ ወደ አንድነትና ኅብረት ማምጣት ነዉ እንጂ የዓመፃ ዋጋችንን የምናስፋፋ መሆን የለብንም:: ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ በአሁን ሰዓት ብዙ ቋንቋዎች ይነገራሉ:: አሁን ያለዉ መንግሥት ቋንቋን ለመግባቢያነት ሳይሆን የሚጠቀመዉ ለራሱ መሰሪ ተግባርና በቀል ዓላማ ነዉ ያዋለዉ:: ይኸዉም በቋንቋ ልዩነት የተለያዩ ክልሎችን ለወደፊት ደግሞ አገሮችን ለመፍጠር ነዉ «ይህ የዚህ መንግሥት ክልል ነዉ፤ ያ ደግሞ የዚያ መንግሥት ክልል ነዉ» በማለት ኢትዮጵያን በመከፋፈልና በማጥፋት ዘመቻ ላይ የተሰማራዉ:: ለዚህ የዓመፃ ተግባሩ የተጠቀመበት ደግሞ የቋንቋ ልዩነትን ነዉ::

በእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ የቋንቋ ጥቅሙ ከመግባቢያነትና ሕዝቦች እንዲዋሃዱበት፣ አንድ እንዲሆኑበት ከማድረግ አያልፍም:: የኢትዮጵያዉያን ቀደምት ቋንቋቸዉ ግእዝ ሲሆን፤ በሥጋዊዉም በመንፈሳዊዉም በበላይነት አገልግሎት ሲሰጥበት የነበረና በአሁን ሰዓት ግን ከሥጋዊዉ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ የተወገደና አገልግሎት የማይሰጥበት ነዉ:: በመንፈሳዊዉም ቢሆን እንደ ቋንቋ ሳይሆን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ የዋለ ነዉ:: ከዚያ ዉጭ ከግእዝ በኋላ

ለተፈጠረዉ ዐማርኛ ቋንቋ ፊደሉ ከማገልገሉ ዉጪ ብዙም ትኩረት ያልተሰተዉ ቋንቋ ነዉ። ፊደሉም ቢሆን የኢትዮጵያዉያን ቅርስና ማንነት ለማጥፋት የተሰለፈዉ አሁን ያለዉ የዲያብሎስ መንግሥት በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚነገሩ የተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት እንዳይሰጥበት አድርጎ በባዕዳን በላቲን ፊደል የተተካ ነዉ። ይህም ትዉልዱ ማንነቱን እንዲያጣና በሂደት ራሱን ሙሉ በሙሉ ወደ ባዕዳን ለዉጦ ኢትዮጵያዊነቱን እንዲያጠፋ የተደረገ መሰሪ ተግባር ነዉ።

እኛ የአሁን ትዉልዶች ግን ለግእዝ ቋንቋ ሆነ ለፊደሉ ትኩረት ልንሰጥና ቋንቋዉንም ልንማረዉ ይገባል። ምክንያቱም ቀደምት ታሪካችን ሆነ የተለያዩ እዉቀቶች በዚሁ ቋንቋ ነዉና የተጻፉት። በተለይ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ያለን ሰዎች የተሟላ አገልግሎት ለመስጠጥ ቋንቋዉን በሚገባ ማወቅ ይጠበቅብናል። ከግእዝና ከሌሎች ቋንቋዎች ሊፈጠርና የኢትዮጵያዉያን የጋራ የመግባቢያ ቋንቋ ሊሆን የቻለዉ ኢትዮጵያዉኛ (ዐማርኛ) ቋንቋ፤ ምንም እንኳን ቀዳሚ ቋንቋችን ባይሆንም፤ እግዚአብሔር በፈቀደዉ አሁን ያለዉ ትዉልድ የሚዋሃድበትና የሚግባባት እንዲሁም አንድ የሚሆንበት ቋንቋ ሆኖ እንዲገኝ ስላደረገዉ፤ እኛም ተቀብለነዉ የጋራ ቋንቋችን አድርገን እንማርበታለን፣ እንሰራበታለን፣ እናገለግልበታል።

ኢትዮጵያም ለእግዚአብሔር መንግሥትነት የተመረጠችና ለዓለምም አገልጋይነት የተዘጋጀች ስለሆነ፤ ልክ የእንግሊዘኛዉ ሆነ የዐረብኛዉ ቋንቋ በተለያዩ አገራት እንደሚነገርና እንደሚማሩበት እንዲሁም እንደሚሰሩበት ሁሉ፤ የኢትዮጵያዉኛዉ ቋንቋ ዐማርኛም እንዲግባቡት፣ እንዲማሩት፣ በሂደትም እንዲሰሩበት ይደረጋል። ይህም በሣልሳዊ ቴዎድሮስ በኩል «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በግልጽ ተቀምጧል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አገሮት የት ነዉ? ዜግነቶ ምንድነዉ? የትዉልድ ቦታዎና ያደጉት፣ እንዲሁም ክልሎዎ የት እንደነበረና አሁን ደግሞ የትኛዉ ክልላዊ መንግሥት ዉስጥ እንዳሉ ቢገልጹልን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: እኔ አገሬ በምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያ ነዉ። ዜግነቴም የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት የሆነችዉ ኢትዮጵያዊ ነኝ። እጅግ በቅርቡ ዓመፃን፣ ክህደትን ፣ ርኩሰትን፣ ዘረኝነትን ፣ ጎጠኝነትን ያነገሡና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕድ ሃይማኖትን ለማጥፋት ቆርጠዉ የተነሱ የዓመፃ ልጆች በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራቸዉ ሲቆረጡና ከምድረም ሲጠረጉ በሚዘረጋዊ ሰማያዊ ሥርዓት፤ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት የተከፋፈለችዉ ቅድስት ኢትዮጵያ ወደ አንድ ስለምትመጣና የተዘረጋዉ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሥርዓት ሙሉ ሙሉ ስለሚወገድ፤ በዚያን ጊዜ በሚኖረዉ አከላለል መሰረት የትዉልድ ቦታዬ በደቡብ ኢትዮጵያ ወይንም በመሃል ኢትዮጵያ ሊካላል በሚችል በአንድ እገሌ በምትባል ወረዳ ዉስጥ በትንሽዬ ከተማ እገሌ የምትባል ዉስጥ ነዉ። አሁን የመኖረዉ በመሃል ኢትዮጵያ እገሌ በምትባል ከተማ ዉስጥ ነዉ። ክልሌም፣ ክፍለ አገሬም ኢትዮጵያ ብቻ ናት ማለት ነዉ። ሌላ ክልል ወይንም ክፍለ ሀገር የለኝም። እንዲሁም ከኢትዮጵያ መንግሥት ዉጭ ሌላ መንግሥት የለኝም። ሕወሓት

ኢሕአዲግ የተለባለዉ መንግሥት ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን ለማስፋፋት፣ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ፣ እንዲሁም የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት ለማጥፋት የተሰለፈዉ የዓመፃ ቡድን፤ በበላይ በሚመራቸዉ በዲያብሎስን መንፈስ ተመርተዉ «የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት» እያሉ የፈጠሩት የስዉር ዓላማቸዉ ማሳኪያ ስያሜ በእኔ ዘንድ ሆነ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት በሚያምኑ እዉነተኛ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት የሌለዉና የጨለማዉ ገዥ የፈጠረዉ ስለሆነ በኢትዮጵያ ቀን እንደ እንክርዳድነቱ የሚወገድ ይሆናል::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምን ይላሉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት በግልጽ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተጻፉት «ኢትዮጵያዊ በማንነቱ ፍለጋ»፣ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ»፣ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ ምስጢሮችና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለት፣ ቁጥር ሦስት» በሚል ርእስና በተመሳሳይ ሁኔታ በተጻፉ መጻሕፍት ላይ በሚገባ ተገልጧል:: በእኔ በኩል ግን የተወሰነ እዉነታዎችን ማስታወስ እፈልጋለሁ::

ኢትዮጵያ ከሰዉ ፍጥረት ጋር የተገናኘ ታሪክ ያላት፤ የመጀመሪዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን ከገነት ከተሰደዱ በኋላ በሥጋ የተገለጹበት ምድርና ሥጋቸዉም ከዚሁ ከኢትዮጵያ አፈር የተዘጋጀ ነዉ:: ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ የሰዉ ዘሮች ቀደምት አገራቸዉ የሆነችና እግዚአብሔር ለተለየ ዓላማ ያዘጋጃት መሆኑ ግልጽ ነዉ:: ከዚያም በዓለም ላይ የሰዉ ልጆች ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ሲነግስ የእግዚአብሔር ቁጣ በሆነዉ የጥፋት ዉኃ የሰዉ ዘሮች ከምድር ተደምስሰዉ፣ ቅንነትና እዉነተኛነት የተገኘባቸዉ ኖኅና ቤተሰቡ ከመጥፋት ተርፈዉ፣ ትዉልዳቸዉን ማስቀጠል ችለዋል:: የኖኅ ልጆች የሆኑት ሴም፣ ካም፣ ያፌት በሦስት ነገድ ተከፍለዉ ከሦስቱ ነገድ የተዋሐደዉ ኢትዮጲስ የተባለዉ ተወልዶ እንደገና ለኢትዮጵያዉያን መቆርቆር ምክንያት ሆኗል:: በዚህም ምክንያት የእርሱ ዘሮች በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ተሰራጭተዋል:: ይህም የሚያሳየን በአዳምና ሔዋን አገርነቷና የሰዉ ዘሮች የተዋለዱባት በመሆኑ የዓለም ሕዝብ ካስተዋለ ኢትዮጵያዊ ነዉ ማለት ነዉ:: ትዉልዱ «በኖኅ ልጆች ነገድ ልወሰን» ካለም የሦስቱም ነገድ ዉሕድ ዘር የተገለጸዉ በኢትዮጵያዊ ሰዉነት ስለሆነ፤ ሁሉንም የሰዉ ዘር ሆነ ነገድ የሚወክሉት ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ ማለት ነዉ:: በሃይማኖት ደረጃ ካየን ደግሞ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተጠብቀዉ ያሉት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዉያን ስለሆነ ከቅዱሱ ኪዳን አንጻር ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ነዉ:: ይህም የሚያሳየዉ ኢትዮጵያዊነቱን የካደ ሰዉ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ካደ ማለት ነዉ:: እዉነተኞቹ ኢትዮጵያዉያን ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ የነደደ ፍቅር ያላቸዉና ስለ ኢትዮጵያዊነታቸዉ የሚቆረቆሩት፤ እንዲሁም በሚደርስባት ጥፋት ደግሞ የሚብገነገኑት፤ ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፣ እዉነት ፣ ሕይወት ሆኖ ስለተገኘ ነዉ:: ይህን የተለየ ስሜት የፈጠረዉ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ራሱ ሃይማኖት ሆኖ በመገኘቱ ነዉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይና መልእክተኛ**: በእርሶ በኩል በተላላፉት በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ ቅዱሱ ኪዳን፣ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት እየተባለ በተለያየ ቦታ ተገልጿል፡፡ ስለነዚህ ቅዱሳት ኪዳናት ምንነት ቢገልጹልን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ:** ስለ ቅዱሱ ኪዳን ወይንም ስለ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት በዝርዝርና በተሟላ መልኩ በእግዚአብሔር ገላጭነትና አሳሳቢነት በተጻፉት « ኢትዮጵያዊዉ በማንነቱ ፍለጋ» « ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ» «ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ ምሥጢሮች የተገለጡበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት» በሚል ርእስ በተጻፉት መጻሕፍት ላይ በደንብ በጥልቀት ስለተገለጸ እያንዳንዱ ሰዉ ያንን በማንበብ የተሟላ እዉቀት ሊይዝ ይችላል፡፡ እኔ ግን በአጭሩ እነማን እንደሆኑ ብቻ ነዉ የምገልጸዉ፡፡

**የመጀመሪያዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ አዳም ወሔዋን ነዉ፡፡ ይህ ቃል ኪዳን በጋብቻ ሥርዓት ምልክትነት ዘላለማዊነትን ተቀናጅቷል፡፡

**ሁለተኛዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ ኖኅ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ከኖኅና ከሰብአዊ ፍጡሩ ጋር ያደረገዉ ቃል ኪዳን ዘላለማዊ ምልክቱ በቀስተ ደመና ገዝፎ ይታያል፡፡ ይህም በኢትዮጵዉያን በሰንደቅ ዓላማ ተጠብቆ ይገኛል፡፡

**ሦስተኛዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ መልከ ጼዴቅ ነዉ፡፡ ይህም በመሶብ ወርቅና በጽዋ በሚቀርበዉ ኅብስትና የመጠጥ ቁርባን ምልክትነት ይታወቃል፡፡ ኅብስተ አኰቴትና ጽዋዓ በረከት ይባላል፡፡ የመጨረሻዉና አማናዊዉ መልከ ጼዴቅ የሆነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ የምሕረት ጸጋዉን በሥጋዉና በደሙ ቃል ኪዳን ፍጥረቱ ኹሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለዘላዓለም ሰቷል፡፡

**አራተኛዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ አብርሃም ነዉ፡፡ ይህ ቃል ኪዳን የተከናወነዉ ከአብርሃም ጋር ሲሆን በዘላለማዊነት የቀጠለበት ምልክት ግርዛት ነዉ፡፡ በዘመነ ሐዲስም በጥምቀት ተጠብቆ ይገኛል፡፡

**አምስተኛዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ ሙሴ ነዉ፡፡ ይህ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ከእስራኤል ጋር ያደረገዉ ቃል ኪዳን ነዉ፡፡ ምልክቱም አሠሩ ትእዛዛት የተቀረጸባቸዉ ጽላት ነዉ፡፡ በኪዳነ ኦሪት የሚጠበቅ ነዉ፡፡

**ስድስተኛዉ ቅዱሱ ኪዳነ**፤ ኪዳነ ዳዊት ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገዉ ሲሆን እሱም በመለኮታዊ ዘዉድ ዙፋን ምልክትነት ይታወቃል፡፡ «የዳዊት ልጅ» እየተባለ በተጠራዉና «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ሥርወ ለዳዊት!» በማለትም « የዳዊት ዘር ሥር ከኾነዉ ከይሁዳ ነገድ የተወለደ አንበሳ አሸናፊ!» ተብሎ በራእየ ዮሐንስ የአዋጅ ቃል በተነገረለት በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜ አግኝቷል፡፡

**ሰባተኛዉ ቅዱሱ ኪዳን**፤ ኪዳነ ምሕረት ነዉ። ይህ ቃል ኪዳን የተፈጸመዉ ዳግማዊ አዳም ተብሎ ከዳግማዊት ሔዋን ከድንግል ማርያም በተወለደዉና የእግዚአብሔር ልጅ በሆነዉ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ። ኪዳነ ልቡናና ኪዳነ ኦሪት የተባሉት ስድስቱ የብሉይ ቅዱሳት ኪዳናት የታደሱበትና አዲሱ የምሕረት ቃል ኪዳን ለዘላለም ሲታሰብና ሲከበር ይኖራል። ሲታሰብና ሲከበር የሚኖረዉም የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ይሆን ዘንድ በምሥጢረ ቁርባን ሥርዓት ቅዳሴ በሚለዉጠዉ ኅብስትና ወይን ገዝፎ በሚቀርበዉ ቅዱስ መሥዋዕት ነዉ። ይህ ምሥጢረ ቁርባን የመጨረሻዉ ማኅተምና ዘዉድ ነዉ። ሌላ ቃል ኪዳን ከዚህ በኋላ፤ ይህ የመጨረሻ ነዉ።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ሁለት

« <u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚኖረዉ የኢትዮጵያና የዓለም አከላለል እንዴት ነዉ የሚሆነዉ?

<u>መላኩ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚሆነዉ አከላለልና የመንግሥት መዋቅር በግልጽ በሣልሳዊ ቴዎድሮስ በኩል «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል በተጻፈዉ ሦስተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ፤ «<u>19: የአስተዳደር ማዕከላት</u>» በሚለዉ ርእስ ስር ላይ ተገልጿል። በዚያዉ መሰረት የአፍሪካ አህጉር በአራት ክልል የሚከፈል ሲሆን፤ ይኸዉም የመጀመሪያዉ ክልል ምስራቅ አፍሪካ፣ ሁለተኛዉ ክልል ደቡብ አፍሪካ፣ ሦስተኛዉ ክልል ሰሜን አፍሪካ፣ አራተኛዉ ክልል ምዕራብ አፍሪካ ናቸዉ።

በክልል አንድ ምስራቅ አፍሪካ (ኢትዮጵያ) የሚካተቱት ኢትዮጵያ፣ ሱዳን ፣ ኬንያ፣ ሱማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ባህረ ነጋሽ (ኤርትራ)፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛኒያ ናቸዉ። በክልል ሁለት በደቡብ አፍሪካ የሚካተቱ ደቡብ አፍሪካ፣ ናሚቢያ፣ ዚምባብዌ፣ ሞዛንቢክ፣ ማዳጋስካር፣ ሌሴቶ ፣ ማላዊ፣ ቦትስዋን ፣ ሞሪሺየስ፣ ኮምሮስ፣ አንጎላ ናቸዉ። በክልል ሦስት ሰሜን አፍሪካ የሚካተቱ ግብፅ፣ ሊቢያና ቱኒዚያ ናቸዉ። በክልል አራት በምእራብ አፍሪካ የሚካተቱት ሞሮኮ፣ ሞዉሪታንያ፣ አልጄሪያ፣ ሴኔጋል፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ ቢሳዋ፣ ጊኒ፣ ሴራሊዮን፣ ኬፐቬርድ፣ ላይቤሪያ፣ አይቬሪኮስት፣ ቡረኪና ፋሶ፣ ጋና፣ ቶጎ፣ ቤኒን፣ ናይጄሪያ፣ ካሜሩን፣ ጋቦን፣ ናቸዉ። ቀሪዎቹ በማእከላዊ አፍሪካ ያሉት አገራት ቻድ፣ ኮንጎ፣ ሴንትራል አፍሪካ፣ ዲሞክራቲክ ኮንጎ የመሳሰሉት ለአዋሳኝ ክልሎች ባላቸዉ ቀረቤታ ዉስጥ ይካተታሉ።

የአዉሮፓ አገራት እንግሊዝ፣ ጀርመን ፣ ፈረንሳይ፣ ስፔን፣ ዴንማርክ፣ ጣሊያን፣ ፖርቹጋል፣ ሆላንድ፣ ፖላንድ፣ ቼክ ፣ ላቲቪያ፣ ኦስትሪያ፣ ክሮሺያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሩማኒያ፣ ሃንጋሪን የመሳሰሉት ምስራቅና ምእራብ በመባል በሁለት ክልሎች ይካለላሉ።

የስካንደኒቪያ አገሮች ስዊድን፣ ኖርዌይ፣ ፊንላድ፣ ግሪንላንድ፣ አይስላንድ በአንድ ክልል ይካለላሉ። አዉስትራሊያ፣ ኒዉዚላድን ፣ ፓፓዉ ጊኒያ የመሳሰሉት በዙሪያዉ ካሉት ደሴቶች ጋር በአንድ ክልል ይካለላል።

የሰሜን አሜሪካ አገራት ካናዳ፣ ዩኤስኤ፣ ሜክሲኮ በሁለት ክልል ሰሜንና ደቡብ ተብሎ ይካለላል። የላቲን አሜሪካ አገራት ብራዚል፣ አርጀንቲና ፣ ቬንዚዌላ፣ ቺሊ፣ ኮሎምቢያ፣ ኢኳዶር፣ ቦልቪያ፣ ኒኳራጋ፣ ጉያና፣ ፓራጓይ፣ የመሳሰሉት በሁለት ክልል ተከፋፍለዉ ይከለላሉ። በደሴት የተከበቡ ጃማይካ፣ ኩባ፣ ጓቲማላ፣ ኮስታሪካ፣ ሆንዱራስ፣ ኢልሳልቫዶር ፓናማ የመሳሰሉት ደግሞ በአንድ ክልል ይካለላሉ።

የኤሽያ አገራት በሰባት ክልል የሚካለሉ ሲሆን፤ ክልል አንድ ራሽያንና ሞንጎሊያን ይይዛል፡፡ ክልል ሁለት ቻይናንና ሆንግ ኮንግን ይይዛል፡፡ ክልል ሦስት ጃፓን ፣ ኮሪያዎችን፣ ታይዋንን ይይዛል፡፡ ክልል አራት ህንድንና ፓኪስታንን ይይዛል፡፡ ክልል አምስት ቬትናም፣ ታይላድ፣ ካምቦዲያ፣ በረማ፣ ፊሊፒንስ፣ ኔፓል፣ ባንግላዲሽ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ላኦስ የመሳሰሉትን ይይዛል፡፡ ክልል ስድስት ካዛኪስታን፣ ታጀኪስታን፣ ኡዝቤክስታን፣ ተርኪሚስታን፣ አርመኒያ፣ አዘርባጃን ፣ ኪርግስታን፣ ጆርጂያ የመሳሰሉትን ይይዛል፡፡ ክልል ሰባት ኢራንና አፍጋኒስታንን ይይዛል፡፡

የመካከለኛዉ ምስራቅ አገራት ሳኡዲ አረቢያ፣ የመን፣ ኳታር፣ ባህሬን፣ ኩዌት፣ ኤምሬትስ፣ ጆርዳን ፣ ኢራቅ፣ ሊባኖስ የመሳሰሉት በሁለት ክልሎች ይካለላሉ፡፡

ዓለም ሁሉ ቅዱሱን ኪዳን ጠብቃ ለተገኘችዉ ለኢትዮጵያ ተላልፋ ስትሰጥ ቅዱሱን ኪዳን መጠበቅ ሲገባቸዉ ባለመጠበቃቸዉ ምክንያት «አባቷ ቤት ያልገባች በዓመፅ ያለች እስራኤል የኢትዮጵያ ታናሽ ወንድም» ተብላ ባለችበት ሚጢጢ ቦታ በራሷ የዉስጥ አስተዳደር መብት ትተዳደራለች፡፡ መንፈሳዊ አመራሩ ግን ከኢትዮጵያ ባለዉ ማዕከል ይመራል፤ ይደራጃል፡፡

የሁሉም ክፍለ አህጉር ክልልሎች ዋና ማዕከላቸዉ የእግዚአብሔር መንግሥት በሚዘረጋባት ኢትዮጵያ ይሆናል፡፡ ለኢትዮጵያ ሆነ ለዓለም የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆነዉ ለሕዝቡና ለምእመኑ አመራር የሚሰጡትና የሚያስተዳድሩት ርእስ ነገሥታት(ንጉሠ ነገሥት) እና ርእሰ ሊቃና ካህናት እጨጌ(ፓትርያርክ) መቀመጫቸዉ በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ይሆናል፡፡ በሌሎቹ ክልሎች በሚመረጠዉና በሚወሰነዉ ክልል ዋና ከተማ ለእያንዳንዱ ክልል ለርእሰ ነገሥቱ(ንጉሠ ነገሥቱ) እና ለርእሰ ሊቃና ካህናቱ ተጠሪ የሚሆኑ ነገሥታትና ሊቃነ ካህናት ይኖራሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ከእነሱ ስር ደግሞ በየደረጃዉ የተለያዩ ባለሥልጣናትና መንፈሳዊ መሪዎች ከጠቅላይ ምሉክ(ጠቅላይ ሚኒስትር)ና ከሊቀ ካህናት(ሊቀጳጳስ) ጀምሮ የቀበሌና የገጠር አብያተክርስቲያን ተጠሪ ድረስ በተዋረድ ይኖራሉ፡፡

ምናልባት እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ ለሚያስብና የእግዚአብሔርን ስራና ፈቃድ ነጥብ በማትሞላ እዉቀቱና ጥበቡ እንዲሁም ከልምሾነት በማያልፈዉ ኃይሉና ጉልበቱ የሚመካ፤ ከዚህ በተጨማሪ በጦሩ፣ በሥልጣኑ፣ በሀብቱ የሚመካ ሰዉ፤ ባጠቃላይ የቅርፊት ሥጋዊ ስሜት ያየለበት ሰዉ «ይህ ሊሆን አይችልም» ሊል ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነዉና የተናገረዉን ያደርጋል፡፡ የንስሐ እድሜ የተሰጠዉ ሰዉ ይኸንኑ በቅርቡ በዓለም ላይ ተፈጽሞ ያያል፡፡ ለእግዚአብሔር እቅድና ተግባር እንቅፋት የሚሆኑት የዓመፃ ልጆች ደግሞ በእግዚአብሔር ቁጣ ሙሉ በሙሉ ከምድር ስለሚጸዱ(ስለሚጠረጉ) ከነትዕቢታቸዉና ዓመፃቸዉ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ሲኦል ይሄዳሉ፡፡ ቅኖች፣ የዋሃን፣ እዉነተኞች፣ እግዚአብሔር መፍራት በዉስጣቸዉ ያለ ሰዎች ብቻ፤ ምንም ይሁን ምን፣ የምንም ተከታይ ይሁን የምን በእግዚአብሐር ቸርነትና ምሕረት እንዲሁም በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ስለሚደርሱ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሥርዓት የሚቀበሉትና የሚኖሩበት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም እረኛዉ አንድ መንጋዉ አንድ ይሆናልና፡፡

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: ከላይ የገለጹልን በሥጋና ደም ስሜት ለምንመላለስ ሰዎች ተግባራዊ የሚሆን የማይመስልና እንዲሁም እዉቀታቸዉንና ጥበባቸዉን፣ ኃይላቸዉን፣ ሥልጣናቸዉ፣ ሀብታቸዉን፣ ገላቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ ሰዎች እንደ ቅዠት አስተሳሰብና ምኞት አድርገዉ የሚቆጥሩ ሊኖሩ ይችላልና ለዚህ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እርግጥ እንደ ሥጋ ፈቃዱ የሚመላለስና የእግዚአብሔርን ስራና ኃይል ያላስተዋለ ሰዉ፤ የሚሆን ላይመስለዉና እንደ ቅዠት ሐሰብ ሊወስደዉ ይችላል። እኔም ሆንኩ ሌሎች አገልጋዮች በራሳችን ፈቃድና ምኞት ሳይሆን ለአገልግሎት የተጠራነዉ እርሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ነገሥታትን የሚያፈራርቅ፤ የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ በፈለገዉ መንገድ ማከናወን በሚችል አምላክ ስለሆነ፤ እኛ እርሱ «እንዲህ ይደረጋል፤ እንዲህ ይሆናል» ያለዉን አንዳች የማንጠራጠር፤ ለተጠራንበትም ተልኮ በቆራጥነትና በታማኝነት የተሰለፍን፤ ኃይላችን እግዚአብሔር የሆነ፤ ፈቃዱን ለመፈጸምና ለማስፈጸም ብቻ የተዘጋጀን ስለሆነ እኛ እርሱ የተናገረዉን ለዓለም መግለጽ እንጂ እንዴት አደርጎ የተናገረዉን ተግባራዊ እንደሚያደረግ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እኛ አናዉቅም። በእርግጠኝነት የምናዉቀዉ የተናገረዉ ሁሉ አንዳች ሳይቀር ተፈጽሞ እንደምናይና ኢትዮጵያም ኢትዮጵያዉያንን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ጭምር በእግዚአብሔር እንደራሴነቷ እንደምትመራና ልጆቿንም በአራቱም ማዕዘን አሰማርቷ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በአራቱም ማዕዘን እንደሚፈጸም ነዉ።

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: ከዚያ ጋር አይይዤ የምጠይቀዉ ከላይ በዝርዝር እንደገለጹልን በአፍሪካ ከ52 አገራት በላይ የሆኑት በአራት ክልልና መንግሥት ብቻ ተከፍለዉ እንደሚተዳደሩ፤ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካም እያንዳንዳቸዉ በሁለት ክልል ተከፍለዉ በሁለት መንግሥት ብቻ እንደሚታዳደሩ፤ አዉሮፓም በሁለት ክልል ተከፍለዉ በሁለት መንግሥት ብቻ እንደሚተዳደሩ፤ መካከለኛዉ ምስራቅም በሁለት ክልል ተከፍለዉ በሁለት መንግሥት ብቻ እንደሚተዳደሩ፤ ሰፊዉ የእስያ አገራትም በሰባት ክልል ተከፋፍለዉ በሰባት መንግሥታት እንደሚተዳደሩ፤ የስካንደኒቪያ አገራት በአንድ ክልልና መንግሥት እንደሚተዳደሩ፤ አዉስተራሊያና በደሴት የተከበቡ አገራት እያንዳንዳቸዉ በአንድ ክልልና መንግሥት እንደሚተዳደሩ ነዉ። በዓለም ላይ ያለዉ እዉነታ ደግሞ እንኳን በነገድ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት የማይገናኙት አገራት አንድነትን መፍጠር ይቅርና አንድ ቤተሰብ የሆኑት ኢትዮጵያና ኤርትራ በጠላትነት ነዉ የሚተያዩት፤ ደቡብ ሱዳንና ሱዳን በጠላትነት ነዉ የሚተያዩት፤ ሰሜን ኮሪያና ደቡብ ኮሪያ በጠላትነት ነዉ የሚተያዩት፤ ህንድና ፓኪስታን... ወዘተ በጠላትነት ነዉ የሚተያዩት። ታዲያ እነዚህ በቀላሉ ሊዋሐዱና አንድነት ሊፈጥሩ የሚገባቸዉና የሚችሉ አገሮች በአንድነት መኖር ተስኗቸዉ ተገነጣጥለዉ የራሳቸዉን ነጻ መንግሥት መስርተዉ እየኖሩ መሆኑ ይታወቃል። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣም አገሪቷ በክልል ተከፋፍላ የትግሬ መንግሥት፣ የአማራ መንግሥት፣ የኦሮሞ መንግሥት፣ የሱማሌ መንግሥት፣ የአፋር መንግሥት፣ የሐረሪ መንግሥት፣ የጋምቤላ መንግሥት፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ መንግሥት፣ ... ወዘተ መንግሥታት ተፈጥረዋል። ታዲያ ዓለም ሆነች ኢትዮጵያ እንዴት ወደ አንድነትና ብዙ አገራት ተዋሕደዉ በአንድ ክልልና መንግሥት ይተዳደራሉ፣ አንድ ይሆናሉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ ሊታወቅ የሚገባዉ በዓለም ላይ የነገሠዉና እያንዳንዱን አገር በበላይ ሆኖ በአገልጋዮቹ አማካይነት ዓለምን እየገዛና እየመራ ያለዉ የጨለማ ገዥ ዲያብሎስ ነዉ:: ለዚህም ነዉ በአራቱም ማእዘን የእርሱ ፈቃድ እየተፈጸመ ያለዉ:: ለዚህም ምስክሩ በእያንዳንዱ አገር የነገሠዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርና ሕይወት በቂ ማስረጃ ነዉ:: በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ደግሞ በአራቱም ማእዘን የሚነግሠዉ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ:: እንዲሁም በአራቱም ማእዘን የሚፈጸመዉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነዉ:: የሚታየዉ ተግባርና ሕይወት ቅንነት፣ እዉነኛነት ፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነት የሞላበት ነዉ:: ለአስተዳደር ይመች ዘንድ በክልልና አህጉር ይከፋፈላሉ እንጂ እንደ አዳምና ሔዋን ዘርነታቸዉ እንዲሁም እንደ ኖኅ ልጆች ነገድ ወሕድነታቸዉ ነዉ የሚኖሩት እንጂ፤ በኃጢአት ምክንያትና በዲያብሎስ ፈተና የመጣዉ መከፋፈልና መለያየት ይቀራል:: ሁሉም ለአንድ ፈጣሪ ተገዥና ተስፋቸዉንም ሕያዉ ሆነዉ የሚኖርበትን የእግዚአብሔር መንግሥት አደርገዉ በምድራዊ ዘመናቸዉም ከእነሱ የሚጠበቅባቸዉን ሁሉ ፈጽመዉ ይኖራል እንጂ ለክፋትና ለዓመፃ፣ ለክህደትና ለርኩሰት ሕይወት አይነሳሱም::

አሁን እንደሚታየዉ በሁሉም አገራት የዲያብሎስ አገልጋዮች ነግሠዉ ስለሆነ፤ ሕዝቡንም የሚመሩት በጨለማዉ ገዥ መንፈስ በመሆኑ ፍሬያቸዉ ክፋት፣ ተንኮል፣ ጥላቻና በቀል፣ ምቀኝነት፣ ትዕቢት፣ ነፍሰገዳይነት፣ ሌብነት፣ ዘማዊነት፣ ባዕድና ጣዖት አምላኪነት፣ ዘፋኝነትና ዳንኪርተኛነት፣ ዓመፀኛነት፣ ርኩስነት የመሳሰሉት ናቸዉ:: በመሆኑም እንኳን ብሔርን ከብሔር፣ ጎሳን ከጎሳ ማለያየትና መከፋፈል አይደለም አንድ ቤተሰብን የሚለያዩና የሚከፋፍሉ ፍጹም የዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች እንዲሁም ወዶች የሆኑ አገልጋዮቹ ናቸዉ:: ነገር ግን የባለጊዜነት ዘመናቸዉ የተደመደመባቸዉ ስለሆነ ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራቸዉ በምድር ጭምር ዋጋ ከፍለዉበት በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ስለሚጠረጉና ስለሚጸዱ፤ እዉነት ባለ ጊዜ ትሆናለች:: ያኔ የዲያብሎስ ሥርዓት ሙለ በሙሉ ስለሚወገድ የእግዚአብሔር ሥርዓት በአራቱም ማእዘን ይዘረጋል:: ለአስተዳደር አመቺ በሆነ መልኩ አገራቱ ይካለላሉ፤ በዘረኝነትና በጎጠኝነት እንዲሁም በጥላቻና በበቀል የተከለለዉ የጨለማ ገዥ አከላለል ይቀራል:: ለዚህም ነዉ የተለያዩ አገራት እንደ አንድ ቤተሰብ በአንድ ላይ የሚካለሉት::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: እዚህ ላይ ያለኝ ሌላዉ ጥያቄ ብዙ አገራት ባንድላይ ሲካለሉ ከሕዝቡ ብዛት አንጻር ለአስተዳደር አያስቸግርም ወይ? እንዲሁም የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት ያላቸዉን ሰዎች በአንድ ላይ ማካለሉ ችግር አይፈጥርም ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ** : አሁንም መስተዋል ያለበት የዲያብሎስ ሥርዓት ሲወገድና የእግዚአብሔር ሥርዓት ሲዘረጋ የተለያየዉ የሰዉ ዘሮች አስተሳሰብ ወደ አንድ የእግዚአብሔር እዉነታና አስተሳሰብ ነዉ የሚመጣዉ:: በእግዚአብሔር እዉነታ ደግሞ መሪዉ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ነዉ የሚኮነዉ:: በዓለም የተለያየ ቋንቋና ባህል እንዲሁም ሃይማኖት ሊፈጠር የቻለዉ ሰዎች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ

ስለሚመላለሱና ስለሚኖሩ ነዉ እንጂ፤ እንደ ሕያዉ ነፍስ ባሕርያቸዉ ቢመላለሱ ሁሉም የአንዱ የእግዚአብሔር ፍጥረታትና የአዳምና ሔዋን ዘሮች ስለሆኑ ወደ አንድነትና ወደ ቤተሰብነት ነዉ የሚመጡት:: ከእግዚአብሔር ቁጣ በኋላ የሚተርፉት ትዉልዶች የኃጢአት የዓመፃ ዉጤት የሆነዉን መለያየት አስወግደዉ የጽድቅ፣ የቅድስና ፍሬ የሆነዉን ፍቅርና እዉነተኛት፣ እንዲሁም ቅንነትና ትህትናን ይዘዉ ነዉ ወደ አንድነት የሚመጡት::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ለምሳሌ አፍሪካ፤ ከሩሲያ፣ ከዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ፣ ከቻይና፣ ከሕንድ አገርና ሕዝብ ብዛት አንጻር በአራት ክልል አይደለም በአንድ ክልል ብትካለል አያንስም:: ምክንያቱም ከላይ የተገለጹት አገራት ከአፍሪካ ሕዝብ ቁጥር የሚበልጡ ሆኖ ሳለ በአንድ ክልልና መንግሥት ዉስጥ ነዉ የሚተዳደሩት:: ከዚህ አንጻር አገራት በአንድ ላይ መካለላቸዉ ችግር አያመጣም:: በመልካሙ ዘመን ክፍል አኅጉራት የሚካለሉት እንድ አሁን ዘመን አገርን ከአገር፣ ዘርን ከዘር፣ ነገድን ከነገድ፣ ጎሳን ከጎሳ፣ ቋንቋን ከቋንቋ ለመለየት ሳይሆን ለአስተዳደር እንዲመች ብቻ ነዉ:: በሁሉም አገር የሚኖረዉ ሥርዓት ተመሳሳይ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚፈጸምበት፣ ሕዝቡ መልካም አስተዳደር የሚያገኝበት፣ ጉስቁልናና መጉላላት የሚቀርበት፣ እያንዳንዱ እንደቤተሰብ በሰላም፣ በፍቅር፣ በአንድነት ተሳስቦና ተዋዶ የሚኖርበት ነዉ::

ከዚህ በተጨማሪ መታወቅ ያለበት ለመልካሙ ዘመን ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ስንት ሰዉ ነዉ የሚደርሰዉ? የሚለዉ ነዉ:: በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ስንቱ ሰዉ ነዉ ራሱን ከዓመፃ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት ሕይወት ለይቶ በቅንነት፣ በትህትና፣ በየዋህነት፣ እግዚአብሔርን በመፍራት እየተመላለሰ ያለዉ? አሥር ከመቶ (አስር ፐርሰንት) ይሞላል ወይ? በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባርና ሕይወት ዉስጥ ያሉት በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ላለመጠረግ ምን ዋስትና አላቸዉ? ዋስትናቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሰለፍ ነበር:: ነገር ግን እንኳን የዉጭ አገር መሪዎችና ሕዝቦች ይቅርና የቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ መሪዎችና ሕዝቡ እስከ አሁን ድረስ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር አልሰጡም፤ ራሳቸዉን ለእዉነተኛ ንስሐና ለእግዚአብሔር መሉ እዉነት አላበቁም:: ታዲያ አሁን በዓለም ላይ ካለዉ ሰባት ቢሊዮን ሕዝብ አሥር ከመቶ ማለትም ሰባት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ እንኳ ለመትረፉ ምን ዋስትና አለን? አሁን የተለያየ ኃጢአት የነገሠባቸዉና ርኩሰት የሚፈጸምባቸዉ የተለያዩ አገራትና ከተሞች ላለመጥፋታቸዉና ላለመደምሰሳቸዉ ምን ዋስትና አላቸዉ? የትኛዉ ሕይወታችንና ንስሐችን ነዉ ከጥፋትና ከመደምሰስ የሚታደገን? እግዚአብሔር የመጨረሻዉን የተለያዩ ቁጣዎቹን አምጥቶ የዓመፃ ልጆችንና የዓመፃ ሰዎችን ከምድር እስከሚጠርግና እስከሚያጸዳ ድረስ የንስሐ እድል ይሰጣል:: ነገር ግን የመጨረሻዉ ቁጣ ሲመጣ ልክ የኖኅ መርከብን እንደዘጋ የንስሐ እድላቸዉን ይዘጋል፤ መጨረሻቸዉም መጠረግ ብቻ ይሆናል:: ምክንያቱም ሕሊናቸዉን እንደ ኖኅ ዘመን ሰዎች አደንድነዉ በመገኘታቸዉና የእግዚብሔርንም የዓመታት የንስሐ ጥሪና ልመና አልሰማ በማለታቸዉ ነዉ::

በእዚህ አጋጣሚ የዓለም መንግሥታት የሚሰሙኝ ከሆነ መሪዎች ሆናችዉ በዓመፃ፣ በክህድት፣ በርኩሰት ተግባርና ሕይወት የተሰማራችሁ ሕዝቦች! በእዉነተኛ ንስሐ ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት አዋርዱ፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ተሰለፉ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ተቀበሉ እላለሁ:: <u>«እኛ በእዉነተኛ ንስሐ አንመለስም፣ እጃችንን ለእግዚአብሔር አንሰጥም፣ የእርሱን ሙሉ እዉነት ተቀብለን ለፈቃዱ አንሰለፍም» የምትሉ ከሆነ ደግሞ፤ ዓለም በኃጢአት ስለተበላሸች ያበላሻቿት ደግሞ እናንተ ስለሆናችሁ፤ እናንተም አገራችሁም በእግዚአብሔር ቁጣ ትጠፋላችሁ::</u>

ለኢትዮጵያዉያን ደግሞ: እናንተ ኢትዮጵያዉያንና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸማችሁና ያስፈጸማችሁ፤ እንዲሁም ለማስፈጸም እየተዘጋጃችሁ ያላችሁት! እንደ ሻዕቢያ፣ ሕወሓት ኢሕአዴግ እንዲሁም ሌሎች የእነርሱን የዓመፃና የክህደት አቋም በመያዝ ለጥፋት የተሰለፋችሁ የዓመፃ ልጆች! የናቃችኋትና የካዳችኋት እንዲሁም ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ያነገሣችሁባት ኢትዮጵያ ቅዱሱን ኪዳን ጠብቃ የተገኘች አገር በመሆኗ በእግዚአብሔር ዘንደ ሞገስን አግኝታ ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም አስተዳዳሪነትና መሪነት የተመረጠች ስለሆነ እናንተ በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከምድሪቱ ስትጠረጉና ስትጸዱ ትንሣኤዋ ለዓለም ይታያል:: የጨለማ ስራችሁ ለዓለም ይገለጣል:: መታሰቢያችሁ ለዘላለም ይጠፋል:: ከምድሩም ከሰማዩም ሳትሆኑ በሁለቱም ቦታ ፍዳችሁን የምታዩ፣ ስለ ዓመፃ ተግባራችሁ ከማንም በላይ ዋጋ የምትከፍሉበት ይሆናል:: <u>ባለማወቅ፣ በየዋህነትና በቅንነት ከእነዚህ የዓመፃ ልጆች ጋር የተሰለፋችሁና የእነሱን የዓመፃ ዓላማ እያስፈጸማችሁ ያላችሁ ሰዎች! ዛሬ ነገ ሳትሉ ምክንያቱም በራሳችሁ ሥልጣን አንድ ቀን ማደር ሆነ መዋል ስለማትችሉ፤ በእዉነተኛ ንስሐ ራሳችሁን በእግዚአብሐር ፊት ራሳችሁን አዋርዳችሁ ተገኙ፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድና ሙሉ እዉነታ ብቻ ተሰለፉ</u>:: ምክንያቱም በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሳችሁ በስተቀር የዓመፃ ተግባር ተባባሪና አስፈጻሚ ሆናችሁ ስለተገኛችሁ እናንተም ከእግዚአብሔር ቁጣና ጠረጋ አትድኑምና::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ አንቱ የተባሉ ኢትዮጵያዉያን፤ ከኢትዮጵያ አልፈዉ ለዓለም ይተርፋሉ ተብሎ የሚገመቱ ሰዎች እንኳን ለዓለም ሊተርፉ ቀርቶ ለኢትዮጵያዉያን መሆን አቅቷቸዉ «እኔ ብሔሬ እገሌ ነዉ፣ በዚህ ብሔር ላይ ገዥዉ መደብ የተለያየ በደልና አድሎ ገፍ ፈጽሟል...» ወዘተ እያሉ ለአንድ ጎሳቸዉ ብቻ ጥብቅና የሚቆሙና እንደ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ሳይሆን እንደ ክልላዊና ጎጣዊ አስተሳሰብ የሚመላለሱና የሚኖሩ ናቸዉ:: እንዲሁም ከአገሩ አልፎ ለዓለም በማሰብ ለሰዉ ዘር ጥብቅና ይቆማል፣ ያገለግላል ተብሎ ይጠበቅ የነበረዉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም እየተማረ ያለዉና ተምሮ የወጣዉ የተማረ ኃይል፤ እንኳን ስለ ዓለም ሕዝብ ማሰብ ቀርቶ ስለ ቅርብ ወገኖቹና ቤተሰቦቹ ኢትዮጵያዉያን አያስብም:: ይልቁኑ በብሔርና በጎጥ እየተቧደነና እየተደራጀ እርስ በእርሱ የሚጣላ፣ የሚከፋፈል፣ የሚለያይ፣ በጥላቻና በበቀል አስተሳሰብ የሚመላለስ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሳ፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን ለማንገሥ የተሰለፈ ነዉ:: ለእዚህ ያሎት አስተያየት ምንድ ነዉ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት እግዚአብሔር አምላክ፤ «እዉነተኛ እረኞችንና አገልጋዮችን እንዲሁም ሐሰተኞችንና ተኩላዎችን ከፍሬያቸዉ ታዉቃላችሁ» በማለት የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ በግልጽ ስላስተማረንና ስላስጠነቀቀን፤ ከምናየዉና ከምንሰማዉ ፍሬ በአቶ መለስ ዜናዊ ይመራ የነበረዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የማን አገልጋይ እንደነበረና እንደዚህ ዓይነት ፍሬ እንደዘራ ነዉ ከፍሬዉና ከዉጤቱ መረዳትና ማወቅ የምንችለዉ:: የሚታየዉ ፍሬ እንደ ምኞታቸዉና እቅዳቸዉ ዓላማቸዉ ግቡን እንደመታላቸዉ ነዉ በግልጽ የሚያሳዉቀን:: ይኸዉም በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረዉና የሕያዉ ነፍስ ባለቤት የሆነዉ ሰዉ የራሱን እዉነተኛ ማንነት ክዶ «እኔ የዚህ ጎሳ(ብሔር) ተወካይ ነኝ፤ የዚህን ጎሳ(ብሔር) ነጻነት ለማስጠበቅና ለመጠበቅ ነዉ የቆምኩት» እያለ የቅርብ ወገኑን የረሳና እንደ እግዚአብሔር ፍጥረትነቱ፣ እንደ አዳምና ሔዋን ዘርነቱ፣ እንዲሁም እንደ ኖኅ ልጆች ካም ሴም ያፌት ነገድ ዉሕድነቱ እንደ ሆነዉ ኢትዮጵያዊነቱ ማሰብ ተስኖት፤ በጥላቻና በበቀል፣ በመለያየትና በመከፋፈል ሕይወት ዉስጥ መመላለሱና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፍቅሩና ስሜት ከዉስጡ ተመንግሎ መዉጣቱና ዘረኝነትና ጎጠኝነት በሕሊናዉ መንገሡ፤ ዲያብሎስና እንደራሴዎቹ ምን ያህል መራራ ፍሬ በትዉልዱ ላይ እንዳፈሩ ነዉ በግልጽ የሚያሳየን::

የሚያዛዝነዉና የሚያስተዛዝበዉ፤ «የተማርኩ ነኝ፣ አዋቂ ነኝ» ብሎ በዚህ ዓመፃና ክህደት ተግባር ዉስጥ የተሰማራና፣ እንዲሁም በአጼ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን ዉስጥ በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጠና በተለያየ ማኅበራዊ ሕይወት ያሳለፈ ሰዉ በጎጥ ተከፋፍሎና ተቧድኖ እርስ በእርስ ሲበላላና ሲጣላ፣ እንዲሁም የሕወሓት ኢሕአዴግ ምኞትና ግብ ሲያሳካ መታየቱ ነዉ:: ማንም ኢትዮጵያዊ በሰሜን ሆነ በደቡብ፣ በምስራቅ ሆነ በምዕራብ ኢትዮጵያዉ ዉስጥ፣ በማንም ኢትዮጵያዊ ላይ በሚደርሰዉ አድሎና በደለ፣ ግፍና መከራ ጥብቅና ሊቆምና ሊቃወም እንዲሁም እንደ አቅሙና ችሎታዉ አስፈላጊዉን መስዋዕትነት መክፈል ሲገባዉ፤ ራሱን በመንደርና በጎጥ ወስኖ «ለዚህ ጎሳ ነዉ ጥብቅና የምቆመዉና የምታገለዉ» ማለቱ ምን ያህል የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የሚፈልገዉን የጎጠኝነት አስተሳሰብና ሕይወት እንዳሳካ ነዉ የሚያስረዳን:: ምክንያቱም ሕወሓት፤ ትዉልዱ እንደ ኢትዮጵያዊነት እንዳያስብና ከኢትዮጵያዊነትና ከአንድ ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ይልቅ የጎጥና የጎጥ ማስመሰያ ሰንደቅ ዓለማ ፍቅር እንዲያድርበት በማድረግ፣ በመጨረሻም ኢትጵያዊነት ስሜቱ ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ የራሱን ነጻ መንግሥት እንዲያቋቁም ያቀደዉና ለዓመታት የታገለለት ዓላማ መሳካቱን ነዉ የሚያሳየን::

ሕሊናችን በዘረኝነትና በጎጠኝት ስብከት ያልተመረዘን ሰዎች ግን እንኳን ለኢትዮጵያዊዉ የቅርብ ወገናችን አይደለም፣ በዓለም ዉስጥ ስላሉት የአዳምና ሔዋን ዘሮች ወገኖቻችን ልናስብና እንደ እግዚአብሔር ፍጥረትነታችንና እንደ አዳምና ሔዋን ዘርነታችን እንዲሁም ሃይማኖት እንደ ሆነዉ ኢትዮጵያዊነታችን ልናስብና ልንኖር ይገባል:: እንክርዳድ ፍሬ ያፈሩት በቅርቡ ያፈሩትን መራራ ፍሬ ማጨዳቸዉና መራራም ቢሆን ጠጥተዉ ማለፋቸዉ ስለማይቀር፤ የዓመፃ ልጆችን ዓላማ ሳይገባችሁና ሳታስተዉሉ በቀናነት በዚህ በዘረኝነትና በጎጠኝነት አስተሳሰብና ሕይወት ያላችሁ ኢትዮጵያዉያን! ዛሬ ነገ ሳትሉ ከዚህ ከከፋዉና ከከረፋዉ አስተሳሰብና ሕይወት ወታችሁ እንደ ሕያዉ ነፍሳችሁ

አስተሳሰብና ሕይወት ኑሩ። ምክንያቱም በከፋዉና በከረፋዉ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ተግባር ላይ የተሰለፉ የዓመፃ ልጆች በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከምድር ሲጠረጉና ዳግሞ የንስሐ እድል ወደማያገኙበት ሲኦል ሲገቡ የእናንተም እድል ፈንታ እንደነሱ እንዳይሆን በሚል ስጋትና እንዲሁም ራሳችሁን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅታችሁ፣ ምድራዊ በረከትን አግኝታችሁ፣ ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥት እንድትበቁ በማሰብ ጭምር ነዉ።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: ሕሊናቸዉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ለተበከለ ሰዎች የሚያስተላልፉት የተለየ መልእክት አለ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: የእኔ መልእክት ለሁሉም የሰዉ ዘር ነዉ። ይኸዉም ወደ ኋላ ያለዉን ትዉልዳችሁን ቁጠሩ። ኢትዮጵያዉያን ከካም ከሴም ከያፌት ነገድ ዉሕድ ዘር ከተገኘዉ ከኢትዮጲስ ልጅነት አትወጡም። ሌሎቻችሁም ከከኖኅ ልጆች ከወንድማማቾቹ ከካም፣ ከሴም፣ ከያፊት ዘር አትወጡም። ምናልበት «ከዚህ ነገድ ዉስጥ» የለንም የምትሉ ደግሞ ከኖኅ ልጅነት አታልፉም። ከዚያም ከአዳምና ሔዋን ዘርነት አትዘሉም። እንዲሁም ከእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጅነት አትወጡም።

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በድርግ ዘመን ሆነ በሕወሓት ኢሕአዴግ ዘመን በተለያየ የኃላፊነትና ባለሥልጣንነት ደረጃ ዉስጥ ሥልጣና ክህነት ያላቸዉ ሰዎች ጭምር የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ ታይቷል። እንዴት ከእግዚአብሔር ክህነትን ያገኘ ሰዉ ከዲያብሎስ ሥርዓት ጋር አብሮ ተሰልፎ በዓመፃ ተግባር ላይ ይመላለሳል?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እንደ እዉነቱ ከሆነ የሥልጣነ ክህነቱ አሰጣጥ እንኳን በቀደሞ ዘመን አይደለም አሁን እንኳ በአግባቡና በሥርዓቱ አይደለም የሚሰጠዉ። ከድቁና እስከ ቅስና እንዲሁም ከምንኩስና እስከ ጵጵስና የሚሰጠዉ የሥልጣነ ክህነት አሰጣት የግለሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ቀናነት፣ መልካምነት፣ እዉነተኛነት ታይቶ ሳይሆን፤ ወይን እዉቀቱ ስላለዉ ብቻ ይሆናል፣ ወይን በዘመድ አዝማድ ይሆናል፣ ወይን በሥጋና ደም ስሜት ሞቅ ሲላቸዉ ይሆናል፣ ወይን ለስዉር ዓለማ ይሆናል፣ ወይን የራስ ደጋፊን ለማፍራት ይሆናል፣ ወይን በጥቅማጥቅም ይሆንል፣ ወይን በገንዘብ ተገዝቶ ይሆናል። ታዲያ መንፈሳዊነቱ ሳይኖረዉ ሥልጣነ ክህነት ያገኘ ሰዉ እንዴት ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ፣ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ፣ በእዉነት ኖሮና አገልግሎ ሊመላለስ ይቻለዋል? እንዴት ከሥጋና ደም ስሜት ርቆ እግዚአብሐርን በማፍቀርና በመፍራት ሊኖር ይችላል? እንዴት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ሊሚላሰስና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ሊፈጽምና ሊያስፈጽም ይችላል? ከቶ አይችልም። ምክንያቱም ሥልጣነ ክህነቱን የፈለገዉ ለጥቅም፣ ለክበር፣ ለሥልጣን እንጂ ራሱን ዝቅ አድርጎ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያገለግልበትና ከእግዚአብሔርም ሰማያዊ ዋጋ ሊቀበልበት አይደለም። ለእዉነተኛ ሕይወትና አገልግሎት ቢሆን ኖሮማ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት በዚህች በእግዚአብሔር አገር ላይ በግልጽ ሲነግሥ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎችን ባወገዘና ስለ እዉነት በመሰከረ ነበር። ይልቁኑ የዓመፃ ስራቸዉ ተባባሪና

አስፈጻሚ የሆነ፣ እንዲሁም በዓመፃና በክህደት፣ በርኩሰት ተግባር ላይ የተሰማሩትን በሹመት ላይ ሹመት የሚጨምር ነዉ፡፡ በመሆኑም በዲያብሎስ ሥርዓት ዉስጥ ሥልጣነ ክህነት ኖሯቸዉ በተለያየ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ሕይወት የተመላለሱ ሰዎች፤ አንድም መንፈሳዊነቱ ሳይኖራቸዉ ነዉ ክህነቱን የተቀበሉት፤ አንድም የሥልጣነ ክህነቱ ጥቅም ሳይገባቸዉ ነዉ የወሰዱት፤ አንድም ለሥጋ ፈቃዳቸዉ ተሸንፈዉ ነዉ በዓመፃ ተግባር ላይ የተሰማሩት፤ አንድም በፈተና ወድቀዉ ነዉ ለዲያብሎስ ሥርዓት ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ የሆኑት፤ አንድም በሃይማኖታቸዉና በቤተክርስቲያናቸዉ ላይ ጥላቻ አድሮባቸዉ ነዉ፤ አንድም በእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አስመሳይ አገልጋዮች በፈጸሙት የክፋትና የግፍ፣ የበደል፣ የአድሎ ባጠቃላይ  የኃጢአት ተግባር ተሰናክለዉ ዉስጣቸዉ የጥላቻ መንፈስ ነግሦባቸዉ ሊሆን ይችላል፡፡

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ በዓለም ላይ ያሉ መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣናት «በሕዝብ ተመርጠን ነዉ ወደ ወንበር የመጣነዉ» የሚሉት፡፡ እግዚአብሔር የሕዝብን ምርጫ አያከብርም፣ አይቀበልም ወይ?

__መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ__፡ እግዚአብሔር በነጻነት የሚገዛ አምላክና ለእያንዳንዱ ደግሞ እንደ ምርጫዉና እንደ አቋሙ ዋጋ የሚከፍልና የሚያስከፍል ነዉ፡፡ በዓለም ላይ ያለዉ እዉነታ ከብዙ ዘመን ጀምሮ መሪዎች ሆኑ ባልሥልጣናት በሕዝብ ስም የሚነግዱና የሚያስመስሉ ናቸዉ እንጂ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በተላበሰች ሕያዉ ነፍሱ ነጻ ፈቃድ የመምረጥ እድል አልተሰጠዉም፡፡ በተለያየ ሽንገላና እንዲሁም ተጽህኖ፣ ሲከፋም በማስፈራራትና በማስገደድ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ «ሕዝቡ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ በማመዛዘንና በማገናዘብ መረጠኝ» ብሎ ለማዉስወራት የሚያስችል አይደለም፡፡ ነጻ ምርጫ ነዉ የሚካሄድባቸዉ በሚባሉት አገር ጭምር የትዉልዱን አመለካከትና አስተሳሰብ ቁሳዊ በማድረግና ቅርፊት ሥጋዉንና ምድራዊ ሕይወቱን ብቻ ተስፋ አድርጎ እንዲኖር በመቀስቀስና የማይፈጽሙትንና የማያደርጉትን «እናደርጋለን» በማለት ሕዝቡን በሽንገላ አንደበት በመዋሸትና በማታለል ነዉ፡፡

ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ደግሞ «እኛ ተራማጅ አብዮተኛ ነን ፣ በዲሞክራሲ ነዉ የምናምነዉ፣ የሕዝብ ምርጫ እናከብራለን... ወዘተ» እያሉ በደርግ ኢሠፓም፣ በሕወሓት ኢሕአዴግም መንግሥት የተፈጸመዉን ስለተመለከትን ሌላ ምስክር ሳያስፈልገን የሕዝብ ይሁንታ ያገኙ አልነበረም፡፡ በአምባገነንነትና በይስሙሉ ምርጫ በሕዝብ አናት ላይ የተቀመጡና በወንበሩ ላይ ፀረ ሕዝብ ተግባር የፈጸሙ አስመሳዮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ሕዝብ በትክክለኛዉ መንገድ ያልመረጣቸዉ ስለነበረና ስለሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ የቀለሉና የተተፉ ናቸዉ፡፡ ሕዝቡ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ መርጧቸዉ ቢሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ዘንድም ተቀባይነት ይኖራቸዉ ነበር፤ ለሕዝብም መልካም ፍሬ ያፈሩ ነበር፤ ሕዝቡም ከድህነት፣ ከችግር፣ ከመከራ፣ ከጉስቁልና፣ ከመፈናቀል፣ ከስደት፣ ከእስር፣ ከግፍና ስቃይ ሞት ይለይ ነበር፡፡ ኢትዮጵያም ለዓለም ሞገስና ክብር ትሆን ነበር እንጂ ለማኝና ዉርደትና ጉስቁልና የተላበሰች አትሆንም ነበር፡፡

*<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የዲያብሎስ የጨለማ ሥርዓትና የእግዚአብሔር ብርሃናዊ ሥርዓት መገለጫቸዉ ምንድነዉ?*

*<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የአሁን ትዉልዶች በመላዉ ዓለም በአራቱም ማዕዘን በጨለማ በዲያብሎስ ሥርዓት ዉስጥ ስላለን የጨለማዉ ሥርዓት መገለጫዉ ምን እንደሚመስል ማወቅና መለየት አይከብደንም:: አንዳንዶቹን ብጠቅስ ለምሳሌ በእኛ አገር በኢትዮጵያ በሥጋዉያን ወንበር ከላይ ከአገር መሪዉ ጀምሮ እስከ ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ያለዉ አስተዳዳሪ(ኃላፊ) እምነታቸዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ነዉ:: ይህም በግልጽ በእዉነተኛዉ አምላክ የማያምኑ በተዘዋዋሪ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ አማኞች ናቸዉ ማለት ነዉ:: ሌት ተቀን የሚተጉትም የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ:: ለዚህም ነዉ በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ (ማስ ሚዲያ) ላይ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ስራዎችና ፍሬዎች የሚቀርበዉ:: ለምሳሌ ብንወስድ ሰዎች ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ በመኖራቸዉና ሕሊናችንን አንሸጥም በማለታቸዉ የሐሰት ምስክርና መረጃ በማቀናበር ሕዝብ እንዲቃወማቸዉና እንዲጠላቸዉ በተለያየ ሚዲያ ቅስቀሳ ይደረጋል:: ለነፍሳችን ሆነ ለሥጋችን አንዳች ጥቅም የማይሰጡ ሕሊና ማደንዘዣ ትዕይንቶች ይቀርቡበታል:: የሐሰት ዘገባና ሕሊና ማሸጫ ምስክርነቶች ይታይበታል:: እዉነቱና የተሰራዉ ሌላ የሚቀርበዉ ደግሞ ሌላ፤ ሰዎችን ለማታለያና ለመደለያ በማስመስ በተቃራኒ መልኩ ይቀርብበታል:: አንዱን በአንዱ ላይ ለማነሳሳትና ለመከፋፈል እንዲሁም ጥላቻንና በቀልን ለመዝራት ይጠቀሙበታል:: ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ በየጥንቆላዉና በሚጎራዉ እንዲሁም ባዕድና ጣዖት አምልኮ በሚፈጸምበት በየምናምንቴ ቦታ ይቀርብ የነበረዉ ዘፈንና ዳንኪራ እንደ ጥበብና እንደ ትክክለኛ ሙያና ተግባር ተቆጥሮ ይቀርብበታል:: ቅርፊት ሥጋ ለባሹ ሰዉ ይመለክበታል፤ ይገነበታል::*

*በአስተዳደርና ማኅበራዊ ሕይወት ስንመለከት ደግሞ በሕዝቡ ላይ አድሎና በደል ይፈጸማል:: ከዚያም ባለፈ የግፍና የጭከና ተግባር ይፈጸምበታል:: በሕዝብ ስም እየተነገደ በወንበር ላይ የተቀመጡ ሰዎች ራሳቸዉንና ደጋፊዎቻቸዉን በማበልጸግ ሕዝቡን በረኃብና በችግር ይቀጡታል:: ለስደት፣ ለእስር፣ ለሞት ይዳርጉታል፤ ሕይወቱን ያጨልሙበታል:: ከዚህ በተጨማሪ ሕዝቡን እርስ በእርስ እያጣሉና እየከፋፈሉ የሥልጣን እድሜያቸዉን ለማራዘም ከንቱ መጠበብ ያደርጋሉ:: የተለያዩ የክህደትና የምንፍቅና እንዲሁም የርኩሰት እምነት ያስፋፉበታል:: ባጠቃላይ ሕዝቡን በሥጋዉም በነፍሱም ፍዳዉን ያበሉታል:: ራሳቸዉንና መሰሎቻቸዉን ግን ለተንደላቀቀና ለተለየ ክብረት እንዲሁም ግነት ሕይወት ያዘጋጃሉ:: ይህ የጨለማ ሥርዓት የፈጠራቸዉ ሰዎች የሚፈጽሙት ከብዙዉ እጅግ ጥቂቱ ነዉ::*

*የብርሃን ሥርዓት አሁን ያለነዉ ትዉልዶች በየትም ዓለም ስላላየነዉ እንደ ምሳሌ የምናቀርበዉ የለም:: ነገር ግን እንደ መንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የሚሆነዉን ለመግለጽ አንችገርም:: በብርሃናዊ ሥርዓት አንደ ጨለማዉ ሥርዓት ለማስመሰልና ሰዎችን ለመሳብ ተግባራዊ የማይሆን ሕግና ሥርዓት በጽድቅና በቅድስና ሕገ መንግሥት ዉስጥ አይኖርም:: በጽድቅና በቅድስና ሕገ መንግሥት ዉስጥ የሚሰፍረዉ ማንኛዉም ነገር አንዱ ከአንዱ ሳይለይና ሳይበላለጥ በእኩልነት*

ተግባራዊ ይሆንለታል ወይንም ይሆንበታል። በማንም ላይ አድሎና በደል አይፈጸምም። ሁሉ በሕግ ፊት እኩልና ተጠያቂ ይሆናል። በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ዉስጥ የሚከናወን የሕዝብና የምእመናን አገልግሎት ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት ይሆናል። እያንዳንዱ እንደ ሥራዉና ልፋቱ፣ ድካሙና ጥረቱ ዋጋ የሚያገኝ ይሆናል። እንዲሁም እያንዳንዱ ለሚፈጽመዉ የዓመፅ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እንደ ደረጃዉ ፍትሐዊ የሆነ ተመጣጣኝ ዋጋ ይከፍልበታል(ይቀጣበታል)። ማንም ሰዉ ለሕሊናዉና ለአምላኩ በመታመኑ ምክንያት አንዳች ጥቃት ሆነ በደል እንዲሁም በቀል አይፈጸምበትም። እዉነተኞችና ቅኖች ስለእዉነት ራሳቸዉን የሚክዱና ስለ እዉነት የሚመሰክሩ ሰዎች እንደ ብቃታቸዉ ደረጃ በእዉነተኛ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ሕዝቡንና ምእመኑን በእዉነትና በቅንነት ያገለግላሉ። ማንም ሰዉ በቀለሙ፣ በነገዱ፣ በዘሩ፣ በጎጡ አንዳች ልዩነትና አድሎ አይፈጸምበትም፤ ጥቃትም አይደርስበትም። ማንም ሰዉ በእኩልነት ለሥጋዊ ሆነ ለመንፈሳዊ ወንበር የሚያበቃ ሕይወትና ብቃት ከያዘ እንደ ብቃቱ በማንኛዉም ወንበር ላይ ተቀምጦ ሕዝቡንና ምእመኑን ማገልገል ይችላል። በሥጋዊ ወንበርና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ የሚቀመጡት ርእስ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት)ና ርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌ (ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ) ልክ እንደ ንጉሥ ዳዊትና እንደ ነብዩና ካህኑ ሳሙኤል፤ በእግዚአብሔር የሚመረጡና የሚቀቡ ሲሆን፤ ከእነሱ ስር የሚሆኑት ደግሞ ከላይ እስከ ታች ድረስ ያሉት ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ ላይ በመሆን የሚመርጧቸዉና እንደ ሕይወታቸዉና ብቃታቸዉ ደረጃ የሚመደቡ ይሆናል። እያንዳንዱ አስተዳደር ሆነ አከላለል ሕዝቡ የሚጠቀምበት፣ አንዳች የማይጉላላበት፣ መከፋፈልና ልዩነት የማይፈጠርበት፤ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የማይነግሥበት፤ ዘረኝነትና ጎጠኝነት የማይታይበት፣ የግለሰብ መመለክና መግነን የሚቀርበት ነዉ። ባጠቃላይ እግዚአብሔርም በእዉነትና በመንፈስ የሚመለክበት ሥርዓትና የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚፈጸምበት ነዉ።

በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም በአራቱም ማእዘን የሚፈጸመዉ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ የግለሰብ ወይንም የተወሰነ ቡድን ፍላጎትና ዓላማ አይሆንም። እያንዳንዱ ሰዉ በምድርም በረከትን አግኝቶና ተባርኮ ለሰማያዊ ሕያዉ ሕይወት እንዲበቃ የሚያደርገዉ ሥርዓት ነዉ የሚሆነዉ። ስለዚህ እያንዳንዳችን ይህን ብርሃናዊ ሥርዓት ነዉ በጸሎትና በተስፋ መጠባበቅ ያለብን እንጂ ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች የሚያመጡት፣ የሥጋና የደም ስሜታቸዉ የሚንጸባረቅበት፣ የዲያብሎስ ፈቃድ የሚፈጸምበት መሆን የለበትም። በጨለማዉ በዲያብሎስ ሥርዓት እንኑር የምንል ከሆነ ደግሞ በምድርም በሰማይም ፍዳችንን የምናይና የምንቀበል ይሆናል እንጂ ለዲያብሎስ አገልጋዮች ካልሆነ በስተቀር ለሥጋችን አንዳች ጥቅም አናገኝበትም፤ በነፍሳችንም ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልተመላለስንና እንደ ቃሉ ሆነን ካልተገኘን በስተቀር ለሰማያዊ እዉነተኛ ሕይወት አንበቃም።

__ጠያቂዉ አገልጋይ__: በአገራችን ኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ዘንድ «ምሁራን» በተባሉት ዘንድና «መንግሥታት» በተባሉት ዘንድ የሚታወቀዉ፤ እርሶ ቀደም ባሉት ክፍሎች ዉስጥ በዝርዝር ከገለጹልን ከመጀመሪያ ሥነ ፍጥረት ጀምሮ እስከ አሁንና እንዲሁም እስከ ዓለም ፍጻሜና ከዚያ በኋላ ስላለዉ ሕይወት ፍጹም ተቃራኒ ነዉ። ይኸዉም እርሶ ምድር እያሉ የሚጠሯት ይህች ዓለም ከብዙ

ትእልፊት(ቢሊዮን) ዓመታት በፊት እንደተፈጠረችና የሰዉ ዘሮችም ከጦጣ መሰል እንስሳ ከብዙ አእላፋት(በብዙ ሚሊዮን) ዓመታት በፊት እንደተፈጠሩ ነዉ:: ኢትዮጵያዉያኑ «ምሁራን» የተባሉት ሳይቀር መገናኛ ብዙኃን በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ በሆነዉና ፈቃዱ በሚፈጸምበት በመንግሥት ቴለቪዥንና ሬድዮን እንዲሁም የተለያዩ ሕትመቶች ላይ «ይህዉ ከዚህ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የተገኘ የሰዉ አጽም» እያሉና የተለያየ ስም «ሉሲ፣ ድንቅነህ፣ ሰላም... ወዘተ» በማለት ሰይመዉ በግልጽ ይቀርባል፤ እንደ ታላቅ ግኝት ተቆጥሮ በዓለም ጭምር ይዘገባል:: በእዉኑ የዚህች ዓለም ዘመንና የሰዉ ዘሮች ዘመን በቢሊዮንና በሚሊዮን የሚቆጠር ነዉ ወይ?

__*መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*__: አንድ ማወቅ ያለብን መመራመሩ፣ ማጥናቱ ችግር የሌለዉ ሲሆን፤ ያ ምርምርና ጥናት ግን ለሰዉ ልጆች የሚጠቅም፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት መሆን አለበት:: አሁን እያየን ያለነዉ በቅሬተ አፅም ጥናት እየተካሄደ ያለዉ ለሰዉ ልጆች አንዳች ጥቅም የሌለዉ፤ እንዲሁም የእግዚብሔርን ህልዉና የሚያስክድ፣ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰችዉን ሕያዉ ነፍስ ባለቤት የሆነዉን ትልቁ ሰዉ ራሱን እንደ እንስሳ እንዲቆጥር አደርጎ አሁን በዓለም ላይ ገኖ እንዳለዉ እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት ዉስጥ እንዲመላለስና ተስፋዉንም ይህችን ዓለም ብቻ አድርጎ እንዲኖር፣ አስተሳሰቡም «እኔ እንስሳ ነኝና እወለዳለሁ፣ አድጋለሁ፣ እሞታለሁ፣ ሕይወቴ በዚህ ይደመደማል» ብሎ እንዲያስብና ስለ ጽድቅ ሆነ ስለኩነኔ አንዳች እንዳያስብ፣ እንዳይሰጋ የሚያደርግ ነዉ:: እንዲሁም ሰዉ ሕሊናዉን በማደንደን እንደፈለገዉ እንዲኖርና የፈለገዉን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እንዲፈጽም የሚያበረታታ ነዉ:: ምክንያቱም ሰዉ ተስፋዉ ምድር ብቻ ከሆነ ለዚህች ለዐይን ቅጽበት እድሜዉ የሥጋና የደም ስሜቱን ለማሟላትና ለማርካት ከቀላል እስከ ከባድ ወንጀል፣ ከቀላል እስከ ከፍተኛ ርኩሰት፣ ከቀላል እስከ ከፍተኛ ዓመፃ፣ ከቀላል እስከ ከባድ ግፍ፣ ... ወዘተ ለመፈጸም ወደ ኋላ አይመለስም:: ነገር ግን ሕያዉ መሆኑን ቢያዉቅ ግን ነፍስ ከሥጋዉ እንደተለየች ረቂቅ አካል ተላብሳ ለሕያዉነት ዘመን እንደ ኃጢአቷ ደረጃዋ የምትቀበለዉን ቅጣት ስለምታዉቅ በምድራዊ ሕይወት ዘመኗ ከኃጢአት ትጠበቃለች::

አሳዛኙና አስገራሚዉ ደግሞ በዚህ በዓመፃና በክህደት ተግባር ላይ የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት የሆኑ የኢትዮጵያ ሰዎች መሳተፋቸዉና ይህን ዓይን ያወጣ የዉሸት ግኝነት እንደ ትክክል ቆጥረዉ ለዓለም ማስተዋወቃቸዉ፣ እንዲሁም «መንግሥት» ተብየዉም ለእርሱ የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ተግባር ስለሚጠቅመዉ ይህንኑ የሐሰት ግኝት እያገነና ለሕዝቡ ማቅረቡ ነዉ:: የእግዚአብሔር እዉነታ ግን የሰዉ ዘሮች የተገኙት ከዚህችዉ ከኢትዮጵያ መሬት ሲሆን ይኸዉም የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ከገነት እንደተባረሩ ይህች «ዓለም» የምንላት ምድር ለዚህ ለተገለጽንበት ሥጋ መኖሪያ እንድትሆን ተደርጎ ከተፈጠረ በኋላ የገቡባት ነዉ:: ይህ ዘመን ደግሞ በቢሊዮንና በሚሊዮን የሚቆጠር ዘመን ሳይሆን አሥራ ሺህ ዘመን እንኳ አይሞላም:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን መሰረት ይህች ዓለም ሆነ የሰዉ ዘሮች ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ደግሞ 2005 ዓመት ነዉ ያስቆጠረዉ:: ይህም የሚያሳየን የሰዉ ዘሮች ታሪክ እንኳን በሚሊዮን አይደለም አሥር ሺህ ዓመት አልሞላትም::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: ታዲያ በምን መነሻ ነዉ «ከዚህ ሚሊዮን ዓመት በፊት በዚህ አካባቢ ይኖሩ የነበረ ከጦጣነት ወደ ሰዉ ደረጃ እየጠለወጡ የነበረበትን የእድገት ደረጃ የሚያሳይ ቅሬተ አፅም ነዉ » እያሉ የሚያሳዩን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ከላይ እንደገለጽኩት እነዚህ ራሳቸዉን እንደምሁርና ሳይንቲስት የሚያዩና የሚቆጥሩ ሰዎች ለዚህች ምድር(ዓለም) የቢሊዮን እድሜ የሰጧት ስለሆነና ሕይወት ያለዉ ፍጥረት የተገኘዉ «ከረቂቅ ቁሳ አካል ነዉ» ብለዉ ነዉ የሚያምኑት፡፡ እዚህ ላይ እንዴት ሕይወት ያለዉ ፍጥረት ሕይወት ከሌለዉ ነገር እንደሚገኝ እጅግ ግራ የሚያጋባ ነዉ! እነርሱ ግን ሕሊናቸዉ የደነደነ ስለሆነ ያ ሥጋ የተገኘዉ አስቀድሞ ሕይወት ካለዉ ፍጥረት እንጂ ከበድን አለመሆኑን ማስተዋል ተስኗቸዉ፤ «ሕይወት ከሌለዉ ከሥጋ ትል ይገኝ የለም ወይ?» ብለዉ ምላሽ ከመስጠትና ካለ ሃፍረት ከሰዉ በፊት የነበረችዉ ጦጣ ከትል ደረጃ ነዉ በቀስ በቀስ እድገት ለዚያ ደረጃ የበቃችሁ፣ እርሷም በአዝጋሚ ለዉጥ ወደ ሰዉ ተለወጠች» በማለት የሚመሰክሩ ናቸዉ፡፡ ይህን የዓመፃና የክህደት እዉቀታቸዉን ለማሳመን ግምት ነዉ የሚጠቀሙት እንጂ «ይህ ቁስ አካል ወይንም ቅሬተ አጽም የዚህን ያህል እድሜ ያስቆጠረ ነዉ» ብሎ የሚገልጽ መሳሪያ ሆነ ሌላ መረጃ የለም፡፡ አፅሙ የተገኘበት ዓለት ወይንም አፈር በራሳቸዉ የእዉቀት ደረጃ የብዙ ሚሊዮን እድሜ ይሰጡታል፤ ከዚያም ያገኙትን አፅም ከእርሱ ጋር በተያያዘ የራሳቸዉን ስሌት አስልተዉ «ከዚህ ሚሊዮን ዓመት በፊት የነበረ የሰዉ ቅሬተ አፅም» እያሉ ያስተዋዉቃሉ፤ በዚያም ይከብሩበታል፣ ይገኑበታል፣ ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ ያለፈ ተስፋ የላቸዉም፤ ተስፋቸዉ ሁሉ እንደ ግኝታቸዉ ምድርና መሬት ናቸዉ፡፡ ማንነታቸዉን ዘንግተዋል፤ ታላቅ ተስፋቸዉንም አጨለመዋል፡፡

እስቲ ማስተዋሉ ካለን የሰዉ ዘሮች በሚሊዮን የሚቆጠር እድሜ ካላቸዉ በዚህ ሚሊዮን እድሜ ዉስጥ በአሁን ሰዓት ስንት ሕዝብ መኖር ነበረበት? የዛሬ ሃምሳና መቶ ዓመት በፊት የሰዉ ልጆች ቁጥር ስንት ነበር? የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጥር እንደ ምሳሌ ብወስድ አሁን ያለዉ ሕዝብ ወደ ዘጠና ሚሊዮን እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ደግሞ ወደ ሰላሳ ሚሊዮን የሚጠጋ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየን በሃምሳ ዓመት ዉስጥ በሦስት እጥፍ እንዳደገ ነዉ፡፡ ለዚያዉም ትዉልዱ የወሊድ መቆጣጠሪያና የራሱን ሥጋዊ መጠበብ እያደረገ፡፡ ከመቶ ዓመት በፊት ደግሞ ከአሥርና አስራአምስት ሚሊዮን እንደማይበልጥ ይገመታል፡፡ ከአምስት መቶ ዓመት ቢፊት ደግሞ ከአምስት ሚሊዮን እንደማይበልጥ ይገመታል፡፡ ከሺህ ዓመታት በፊት ደግሞ በመቶ ሺህ ቤቶች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ እንዲህ እያለ ወደ ኋላ ስንቆጥር ከዛሬ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በፊት በዓለም ላይ የነበሩት ሰዎች በአሥራ ቤት የማይቆጠሩ መሆኑን በግልጽ እንረዳለን፡፡ ታዲያ የሚሊዮን ዓመት እድሜ ብናስቆጥር ኖሮ የኢትዮጵያ ሕዝብም በብዙ ቢሊዮን የሚቆተር፣ የዓለም ሕዝብ ደግሞ ከቁጥር በላይ የሆነ የትሪሊዮን ትሪሊዮን ብዛት ሊኖረዉ ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም ይኸዉ በአጭር ዓመታት ዉስጥ የሕዝብ ቁጥር ከሦስት እጥፍ በላይ አድጎ ሰባት ቢሊዮን ከደረሰ፤ እንደተፈለገዉ በሚወለድበትና ሥጋዊ መጠበብ በሌለበት በጥንት ዘመን ደግሞ በብዙ እጥፍ ሕዝቡ እየተዋለደና እየበዛ ይህች መሬት ብቻ አይደለም ከመሬት ጥበት የተነሳ የዉኃ አካል ሁሉ ለሰዉ ዘሮች መኖሪያ በሆነ ነበር፡፡ ባጠቃላይ ይህ ዓይነቱ የተሳሳተና የክህደት እዉቀትና ጥናት የመጣዉ የክህደት እምነት

አመንጪ በሆኑት ቻርልስ ዳርዊን፣ ማርክስ፣ ሌኒን በመሳሰሉት ዓመፀኞችና ከሃዲያን ፈሳስፎች አማካይነት ሲሆን፤ አሁን ግን ዓመፀኞችና ከሃዲያን ስለ ዓመፃቸዉና ክህደታቸዉ ዋጋ የሚከፍሉበት ጊዜ ስለደረስን፣ ይኸዉም በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ላይ በክፍል ሁለት በምዕራፍ 3 በገጽ 43 ላይ እግዚአብሔር ቃል በቃል እንደተናገረዉ:

«እናንተ የቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (የኢቮልሺን) አማኞች፤ ሰዉ የተገኘዉ ከተፈጥሮ ነዉ፤ «የቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ አማካይነት ከእንስሳ ነዉ» በማለት ህልዉናዬን በመካድና በማስካድ ላይ ያላችሁ፤ ማፈሪያና ያበደ አእምሮ (ሕሊና) የያዛችሁ፤የእብደታችሁን ዋጋ በዚህች ምድር ላይም እከፍላችኋለሁ። የዘራችሁትን የክህደትና የዓመፃ ፍሬ ታጭዳላችሁ።» ተብሎ እንደተገለጸ፤ እያንዳንዱ ዓመፀኛና ከሃዲ የእብደት ፍሬዉን ያጭዳል፤ መራራ ፍሬ ቢሆንም ቋቅ እያለዉ ይጋተዋል። ባጠቃላይ ስለ ዓመፃና ክህደቱ ዋጋ ይከፍልበታል(ይቀጣበታል)።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠያቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ሦስት

« ጠያቂዉ አገልጋይ: ስለ ዐምሓራነትና «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» በማለት «የአማራ ብሔር፣ የአማራ ክልል፣ የአማራ መንግሥት» በማለት ከሰየሙት ጋር ያለዉ አንድነትና ልዩነት ማብራሪያ ቢሰጡን?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ: ስለ ዐምሓራነት ልክ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነትና መሪነት «ኢትዮጵያዊ በማንነቱ ፍለጋ»፣ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ»፣ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ ምስጢሮችና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለት፣ ቁጥር ሦስት» በሚል ርእስ በተጻፉት መጻሕፍት ዉስጥ በዝርዝር ቀርቧል:: በእኔ በኩል ደግሞ ከላይ የገለጻችሁት አንዳች አንድነት እንደሌላቸዉ ለመግለጽ እወዳለ:: ይኸዉም ዐምሐራ ማለት አንድን ጎሳ ወይንም ብሔርን የሚወክል ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ የሚያምንና አምልኮትን የሚፈጽም፣ እንዲሁም ተገዢነቱ ለአንድ አምላክ ለፈጣሪ ብቻ የሆነ ነጻ ሕዝብ ማለት ነዉ:: ከላይ በተገለጹት መጻሕፍት ዉስጥ በእግዚአብሔር እዉነታ እንደተገለጸዉ አንድ በእግዚአብሔር የማያምን ወይንም በተለያየ ባዕድና ጣዖት አምልኮ ዉስጥ የሚመላለስ ወይንም በተለያየ የክህደት እምነት ዉስጥ ያለ ሰዉ ወደ እዉነተኛ አምልኮ ሲመጣና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ (በሥላሴ) ስም ተጠምቆ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ሲወለድና የልጅነት ማዕረግ ሲያገኝ የሚሰጠዉ ሲያሜና በክርስቶስ ክርስቲያን ወይንም ነጻ ሕዝብ ወይንም ዐምሐራ ሆነ የሚባልበት እንጂ፤ ጎሳን ወይንም ብሔርን አይወክልም:: ይህም የሚያሳየን አንድ ሰዉ ክርስቲያን ነዉ ማለት ዐምሐራ ነዉ ማለት ነዉ::

አሁን የሚታየዉና እየተሰራ ያለዉ ክርስትናን በረቂቅ መንገድ ለማጥፋትና ክህደትና መናፍቅነትን እንዲሁም የተለያዩ ባዕድና ጣዖት እምልኮን ለማስፋፋት የተሰለፈዉና ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋትና ዘረኝነትና ጎጠኝነትን ለማንገሥ ቆርጦ የተነሳዉ የሕወሓት(ኢሕአዴግ) መንግሥት፤ በክርስቲያኑ(በዐምሐራዉ) ላይ በቀል፣ አድሎ፣ በደል ለመፈጸም የፈጠረዉ «አማራ ብሔር፣ አማራ ክልል፣ አማራ መንግሥት»፤ ከዐምሐራነት ጋር አንዳች አንድነት ሆነ ኅብረት የሌለዉና ይልቁኑ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ፤ ለጊዜያዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ዝና ሲሉ ሕሊናቸዉን በሸጡና በዐምሓራዉ ስም በሚነግዱ ሰዎች አማካይነት የበቀል፣ የግፍ፣ የአድሎ ተግባር እየተፈጸመበትና ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት በአገሪቱ በአራቱም ማዕዘን ለማንገሥ የተጠቀሙበት ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፍለዉ የተለያዩ መንግሥታት እንዲፈጠሩ በማድረግ ህልዉናዋን ለማጥፋት ነዉ ለዓመታት ሲጥሩና ሲታገሉ የነበሩት::

እዚህ ላይ «ለአማራ ሕዝብ ነዉ የቆምኩት» የሚለዉ «ብአዴን» የተባላ የዓመፃ ቡድን፤ ማንነቱ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ በገጽ275-278 እንደሚከተለዉ ተገልጻል:

«እኔም የጨለማዉ ገዥ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ለእንደራሴዩ መሪ(ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ) በሕሊናዉ እንዳሳሰብኩት፣ ወዲያዉ ያልተጠበቁ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሻርፕ ያደረጉና ሙሉ በሙሉ ልብስ አድርገዉት የለበሱ እንዲሁም በትረ መስቀላቸዉ ላይ የሚያዉለበልቡ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የአንበሳ ምልክት በመሀሉ ላይ ያለዉን ሰንደቅ ዓላማ በመያዝ ቀደም ካላቱ « እብዶች»(የእግዚብሔር መልእክተኞች) ከተባሉት ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ::

<u>ወዲያዉ ዐይናቸዉ ደም የለበሰዉ የብአዴን ከፍተኛ አመራሮች በጋራ በመጮኽ</u> « ይኸዉ ቀደም ሲል እንደተናገርነዉ የነፍጠኞችን ሥርዓት ለመመለስ የመጡ ትምክህተኞችና አሸባሪዎች መሆናቸዉ በዚህ ይታወቃል:: <u>የያዙት ሆነ የለበሱት ሰንደቅ ዓላማ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የማይወክል፣ ኮኮብ የሌለበት፣ ጥንትዊቷን ኢትዮጵያ የሚገልጽ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የኛ ኅሊና የሚመራበት መንፈስ የሚወደዉና የሚቀበለዉን ኮኮብ ዓርማችንን አስወግደዉ የኛ ሕሊና መንፈስ የማይቀበለዉና የሚጠላዉን የአንበሳ ዓርማ ያለበትን ሰንደቅ ዓለማ ነዉ ያደረጉት</u>::

ስለዚህ እነዚህ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችን አገር ስለማይወክሉና ጥንታዊዋን ኢትዮጵያ ናፋቂዎች ስለሆኑ ከፈለጉ የጥንቶቹ ሰዎች መተዉ ይስሚቸዉ እንጂ እኛ ቦታ ሰተናቸዉ ልናዳምጣቸዉ አይገባም:: አሁን «ብሔራችሁ ምንድነዉ? እኛ ብሔራችን አማራ ነዉ» ብለን ብንጠይቃቸዉ፤ «ኢትዮጵያዊ ነን» የሚሉ ትምክተኞች የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትና ነጻነትን የማይፈልጉ የቀድሞ ሥርዓት ርዝራዦች ናቸዉ:: <u>በመሆኑም ቀጥተኛ እርምጃ ቢወሰድባቸዉ እያልን እንጠይቃለን» በማለት ንዴታቸዉንና ቁጣቸዉን ገልጸዋል</u>::

**አዲስ የመጡትም መልእክተኞችም** « በእርግጥ እናንተ እንደምትፈልጉት የማንንም ጎጥ ሆነ ቋንቋ ወክለን አይደለም በፊታችሁ የቆምነዉ:: በኢትዮጵያዊነታችንም አናፍርም እስከ መጨረሻዉ እቅታ ድረስ እንመሰክራለን:: እንኳን እናንተ የስም ኢትዮጵያዉያን ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተሰለፋችሁ የዓመጻ ልጆች አይደለም፣ «በእግዚአብሔር አምናለዉ የሚልና የኖኅ ልጆች የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዘሮች ነን፤» የሚሉትን የዓለም ሕዝብ ሁሉ የምንወክል ኢትዮጵያዉያን መሆናችንን ልታዉቁ ይገባል::

እናንተ አሁን በእብሪትና በድንፋታ የተናጋራችሁ ሰዎች! ለሥልጣን፣ ለጥቅም፣ ለሆዳችሁ ስትሉ ሕሊናችሁን የሸጣችሁ፤ ከኢትዮጵያዊነታችሁ ይልቅ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሕይወት የነገሠባችሁ፤ እንኳን «የዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆቹ ናቸዉ፣ የአዳም ዘር ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉ» ብላችሁ ልታስቡ ቀርቶ፤ «ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉ» ብላችሁ የማታምኑ፤ አስተሳሰባችሁ ምድራዊ፤ ሆዳችሁና ክብራችሁ አምላካችሁ የሆነ ነዉ::

እኛ ደግሞ ለሆዳችን ያደርን ሳይሆን ተስፋችንን ሰማያዊ አድርገን ስለ እዉነት ብቻ ልንመሰክርና ልናገለግል የመጣን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነን እንጂ በጨለማ ሕይወት በጥላቻ፣ በበቀል በተመረዘ ሕሊና የምንመላለስና እዉነተኛ ማንነታችንን የምንክድ አይደለም:: እናንተ እንኳን

« አማራ ነን» ማለት ቀርቶ «አማራዉያን ነን። ትግራዉያን ነን። ኦሮሚያዉያን ነን። ኤርትራዉያን ነን።.. ወዘተ» በማለት ማንነታችሁን ልትክዱ ትችላላችሁ። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እስከ አሁን ድረስ እርስ በእርስ እያጣላችሁና እያገዳደላችሁ እንዲሁም እየከፋፈላችሁ ብዙ ደም እንዲፈስ፣ በደልና ግፍ እንዲፈጸም ስላደረጋችሁ፤ እዉነተኛ ንስሐ ገብታችሁ ለአምላካችሁ እጃችሁን ካልሰጣችሁ በስተቀር ከመሰሎቻችሁ ጋር ዋጋ ሳትከፍሉበት እንደማታልፉ ልታዉቁ ይገባችኋል።

ሌላዉ ደግሞ ስለ ሰንደቅ ዓላማ የመናገሩ ሞራሉና ብቃቱ የሌላችሁ፤ የዲያብሎን ዓርማ ያገነናችሁ፤ እናንተና መሰሎቻችሁ ታላቅ ክህደትን የፈጽማችሁ፤ ሕዝቡንም በማስፈጸም ላይ ያላችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል። ይህን ሰንደቅ ዓላማ የተረከብነዉ ከፍጡር ሰዉ ሳይሆን እርሱ እግዚአብሔር ለሰዉ ልጆች በኖኅ አማካይነት የሰጠዉ ከቅዱሱ ኪዳን አንዱ ነዉ። ማንም ሊያጠፈዉ የማይችል ሰማይና ምድር የሚመሰክሩት ነዉ። አንበሳዉ ዓርማም ቢሆን ግለሰቦች ለራሳቸዉ አድርገዉ በተሳሳተ መንገድ ቢጠቀሙበትም እዉነቱ ግን አሸናፊዉ አንበሳ «ሞአ አንበሳ » የተባለዉ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጫ መለኮታዊ ዓርማ የምንጠበቅበት ነዉ እንጂ እንደ እናንተ ለዲያቢሎስ ተገዥነታችሁን በግልጽ ለዓለም እንዳስመሰከተራችሁት የዲያብሎ ዓርማ የሆነዉ ኮኮብ አይደለም። ይህን ክህደት እናንተ ብቻ ሳትሆኑ የፈጸማችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚነግዱት የቤተ ክህነት ሰዎች ጭምር ናቸዉ። ለዚህም እዉነተኛ ንስሐ ካልገቡና እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡ ታላቅ ዋጋ በቅርቡ እንደሚከፍሉበት በዚሁ እንናገራለን።

ሌላዉ እንድታዉቁት የምንፈልገዉ ቤተ ሕዝቡን፣ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናዉ ለያይታችሁ ለዲያብሎስና ለእግዚአብሔር እንዲገዛ የዘረጋችሁት የዲያቢሎስ ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እግዚአብሔር በቁጣዉ እንደሚደመስሰዉና፤ ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱና ቤተመንግስቱ በአንድ ላይ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራበት ሰማያዊ ሥርዓት በቅርቡ እንደሚዘረጋ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን። ምናልባት ኃይላችሁንና ጦራችሁን አስባችሁ «ይህማ በምንም ሁኔታ ሊሆን አይችልም » ትሉ ይሆናል። ምክንያቱም ከጸጋ እግዚአብሔር የራቃችሁ፤ በሕሊናችሁ የዲያብሎስ መንፈስ የነገሠባችሁ ስለሆነ በዚህች በጠባቧ አእምሮዋችሁ በማስላት ከንቱ የሆነ ንግግር አድርጋቹት እንደምታስቡ እንገምታለን።

ኢትዮጵያ እንኳን ዜጎቿን «ኢትዮጵያዉያን ነን» የሚሉትን ቀርቶ የዓለምን ሕዝብ ትመራለች ብንላችሁ «ኡኡ» ልትሉ ስለምትችሉ የንስሐ እድሜ ካገኛችሁ ተፈጽም እንደምታዩ እንነግራችኋለን። በዓመጻችሁ ጸንታችሁ ከተጠረጋችሁ ደግሞ ቅኖችና የዋሃን ትዉልዶች እንደሚያዩት በእግዚአብሔር ስም እናረጋግጥላችኋለን። እንደእናንተ የእግዚአብሔርን ኃይል የምንጠራጠር አይምሰላችሁ። እግዚአብሔር፤ ንጉሡ ሰናክሬም የተመካባቸዉንና የተማመነባቸዉን **185000** (አንድመቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ» ሠራዊት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ እንዳልነበሩ አድርጎ እንዳረገፋቸዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አላነበባችሁምን? ሲወራስ አላዳመጣችሁምን?

እግዚአብሔር አሁን በኛ ዘመን ኃጢአት እጅግ በነገሠበት ወቅት ደግሞ **185000** አይደለም **1850000000** (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ) ሠራዊት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ማርገፍ የሚያቅተዉ ይመስላችኋልን? እናንተ ሆናችሁ በዓለም ዉስጥ ያለዉ ትዉልድ ማንም ይሁን ማን በዓመጻዉ ከጸናና እጁን ለእግዚአብሔር አልሰጥ ካለ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዓመጸኛ ትዉልድ ረግፎ እንደ ኖኅና ቤተሰቡ ቅንነት፣ የዋህነት፣ እዉነተኛነት የተላበሱትን ሰዎች ብቻ የማያስቀር ይመስላችኋልን?

ስለዚህ «ሠራዊቴ፣ ደኅንነቴ፣ ጠባቂዬ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ኃያላን መንግሥታት፣ የአዉሮፓ ህብረት፣ የአፍሪካ ህብረት .. ወዘተ» የሚባሉት እንኳን እናንተን ራሳቸዉንም ማዳን እንደማይችሉ በዚሁ ልንነገልጽላችሁ እንወዳለን። ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድኑ የሚችሉት በእዉነተኛ ንስሐ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሲሰጡና በኢትዮጵያ በቅርቡ እግዚአብሔር ለሚዘረጋዉ መንግሥቱ ለሥጋዊዉም ለመንፈሳዊዉም ሥርዓት ተገዥ ሲሆኑ ብቻ ነዉ። በተቀረ ግን የዓመጻ፣ የክህደት፣ የርኵሰት ጽዋቸዉን እያንዳንዱ መንግሥት፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ እየጠጣ ነጻነቱ ተገድቦ ወደሚኖርበትና እንደ ዓመጻዉ ደረጃ ፍዳዉን ወደሚቀበልበት ቦታ መሄድ ነዉ የሚቀረዉ። ይህን ሁሉ የተናገርነዉ መቼስ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ ብለን በማሰብ ሳይሆን የእናንተ ልበደንዳናነት ቢታወቅም ባለማወቅ በቅንነትና በየዋህነት አብሯችሁ የተሰለፉ ሰዎች ካሉ ከዛሬ ጀምሮ ከእናንተ ጋር አንድነትና ኅብረት መፍጠራቸዉን አቁመዉ ከእዉነትና ከአምላካቸዉ ጋር ብቻ አንድነትና ኅብረት እንዲፈጥሩ፣ እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ ለማሳሰብ ነዉ።» በማለት ተገልጿል

ይህም የሚያሳየን በብአዴን ቡድን ዉስጥ የተሰባሰቡት በተለይ በከፍተኛ አመራር ዉስጥ ያሉ ለጥቅምና ለሥልጣን እንዲሁም ለሆዳቸዉ ሲሉ ሕሊናቸዉን የሸጡ ሰዎች ናቸዉ። የኢትዮጵያን እዉነተኛ ሰንደቅ ዓላማ ሲመለከቱ ከማንም በላይ ዐይናቸዉ ደም መልበሱና የእግዚአብሔር መንግሥትን የሚቃወሙ፣ ከእዛም ባለፈ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ላይ ቀጥተኛ እርምጃ እንዲወሰድ (እንዲገደሉ) ጠቅላይ ሚኒስትሩን የወተወቱ ናቸዉ። ስለዚህ እነዚህ የዓመፃ ሰዎች እንኳን ክስርቲያኑን(ዐምሓራዉን) ሊወክሉ ቀርቶ ቤተሰባቸዉን መወከል አይችሉም። ለወደፊትም የበለጠ ማንነታቸዉ የሚታይና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚፈጽሙት ዓመፃና ክህደት የምንመለከተዉ ይሆናል። እንዲሁም የተንኮልና የክፋት ዉትወታቸዉ አይሳካላቸዉም እንጂ የጭከና ምክራቸዉ ምን እንደሚሆን ለወደፊት እንሰማዋለን፤ እናየዋለን።

ሕወሓት የተባለዉ ሌላዉ የዓመፃ ቡደን በዓላማ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ተዋሕዶን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ሲሆን፤ ወደ ልባቸዉ ቢመለሱ ደግሞ በተቃራኒዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማስጠበቅ በቆራጥነት እንደሚነሱ ይገመታል። ኦሕዴድና ደኢሕዴን የተባለሉት ሌሎቹ የዓመፃ ቡድኖች ደግሞ እንደ ቦይ ዉኃ ወደወሰዷቸዉ አቅጣጫ እየሄዱ ለሕወሓትና ብአዴን ኢሕአዴግ መንግሥት ሕሊናቸዉን በመሸጥ እያገለገሉ ያሉ ናቸዉ። ሌሎች አጋር ድርጅቶች የሚባሉ የዓመፃ ቡድኖች ደግሞ «እናንት ብሔር ብሔረሰቦች ለዘመናት ክርስቲያኖች(ዐምሓራዎች) በደልና ግፍ

ሲፈጽሙባችሁ፣ ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ ሃይማኖተችሁን፣ እምነታችሁ ሲለዉጡ፣ አድሎና መድሎ ሲፈጽሙባችሁ ነበር። አሁን የኢሕአዴግ መንግሥት የብሔር ብሔረሰብና የሃይማኖት፣ የእምነት ነጻነት አጎናጽፏችሁ ወደ ንግሥና ወንበር አምጥቷችኋል፣ ስለዚህ ይህን ታላቅ መንግሥት በመደገፍ «አንብቡ» የምትባሉትን ማንበብ፣ «አድርጉ» የምትባሉትን ማድረግ፣ «ደግፉ» የምትባሉትን መደገፍ፣ «ተቃወሙ» የምትባሉትን መቃወም፣ ባጠቃላይ እንደ ልባችን ሁኑ» ተብለዉ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን እንዲሁም ጥላቻና በቀልን እንዲላበሱ ተደርገዉ፣ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባር ላይ እንደሌሎቹ የዓመፃ ቡድኖች የተሰለፉ ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ በተቃዋሚ ሽፋን አንዳንድ ተለጣፊ የዓመፃ ቡድኖች በአራቱም ማዕዘን እንዲቋቋሙ የተደረጉ ሲሆን፣ እነዚህ ተለጣፊ ቡድኖች በሚሰጣቸዉ ጥቂት ጉርሻና ጥቅማጥቅም፣ ሕሊናቸዉ የጨለማዉን ገዥ መንፈስ እንዲነግሥበት አድርገዉ ለጥፋትና ለበቀል እንዲሁም ሌሎች እዉነተኛ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማጥፋትና ለማዳከም የተሰለፉ እነ ሆዱና ጥቅሙ አምላኩ የሆኑ ቡድኖች ናቸዉ።

ኢትዮጵያ ግን በእግዚአብሔር የተመሰረተችና በቅዱሳን ቃል ኪዳን የተጠበቀች፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የእመቤታችን አስራት አገር ስለሆነች እንኳን በአገር ዉስጥ ለጥፋቷ የተሰለፉ አይደለም፣ እርሷን ለማጥፋት የተሰለፉ የዉጭ መንግሥታት በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ፣ ከምድር ይጠረጋሉ። እርሷ ግን በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ትቆያለች። ታዲያ አሁንም ቢሆን «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» እያሉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚላግጡት ሆኑ እርሷን ለማጥፋት የተሰለፉ የተለያዩ ቡድኖችና ድርጅቶች እንዲሁም መንግሥታትና ግለሰቦች ዛሬ ነገ ሳይሉ በእዉነተኛ ንስሐ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ቢሰጡና ወደማንነታቸዉ ወይንም ወደ ኢትዮጵያዊነቷቸዉ ቢመለሱ የሚበጃቸዉ እንደሆነ በዚሁ አጋጣሚ መልእክቴን አቀርባለሁ።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በአሁን ሰዓት እንኳ ያልተማረዉ፣ «ምሁር» የተባለዉ የተማረ ክፍል ሳይቀር «እኔ ብሔሬ ይህ ነዉ፣ ክልሌም ይህ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነዉ፣ ቋንቋዬም ይህ ነዉ፣ ሰንደቅ ዓላማዬም የዚህ ብሔር ሰንደቅ ዓላማ ነዉ... ወዘተ» ይላሉ። እርሶ በዚህ ምልኩ ማንነቶትን ቢገልጹልን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ሕወሐት(ኢሕአዲግ) የተባለዉ የዓመፃ ቡድንና የዲያብሎስ ወኪል ሆኖ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሕዝቡን በቋንቋ ከፋፍሎና ቀድሞ ቀኝ ገዥዎች አፍሪካን ሲቀራመቱ የፈጠሩትን ሴራና በወሰን ማካለል ልዩነት ፈጥረዉ እርስ በእርሱ እስካሁን ድረስ እያገዳደሉት እንዳለዉ፣ እነሱም ትንሿን አገር በዘረኝነትና በጎጠኝነት ስሜት ከፋፍለዉ «ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል ነዉ፣ ያ ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል ነዉ፣» በማለት እንኳን ፊደል የቆጠረ ቀርቶ መሃይም እንኳ የማያደርገዉን ድርጊት ፈጽመዉ ይኸዉ ለሃይ ዓመት በላይ እርስ በእርስ እያጋጩንና እያጣሉን እንዲሁም እየለያዩንና እያገዳደሉን ይገኛሉ። በዚህ መሰሪና በቀል ተግባራቸዉ ከሃያ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ምድር የሌለ አገር ፈጥረዉ «ትግሪያ፣ ኦሮሚያ፣ አማሪያ፣ ሱማሊያ፣ አፋሪያ፣ ሐረሪየ... ወዘተ» በማለትና «የትግሬ ሰንደቅ ዓላማ፣ የኦሮሞ ሰንደቅ

ዓለማ፣ የአማራ ሰንደቅ ዓላማ፣ የሱማሌ ሰንደቅ ዓላማ፣ የአፋር ሰንደቅ ዓላማ፣ የሐረሪ ሰንደቅ ዓለማ፣ የጋምቤላ ሰንደቅ ዓለማ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰንደቅ ዓላማ... ወዘተ» በማለት የኢትዮጵያዊነት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ለመቀነስና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ለማጥፋት ከንቱ የሆነ ሥጋዊ መጠበብን አድርገዋል።

በዚሁ ጥረታቸዉ ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነት እምነት አጥፍተዉና ኢትዮጵያዊነቱን እያንዳንዱ ክዶ፤ «እኔ ብሔሬ ትግሬ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ኦሮሞ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አማራ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አገዉ ነዉ እንጂ ኢትዮጵያዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ሱማሌ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አፋር ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አደሬ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አኘዋክ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ጉሙዝ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ሲዳማ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ወላይታ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ሃዲያ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ባስኬቶ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ አላባ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ጉራጌ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም፣ እኔ ብሔሬ ስልጤ ነዉ እንጂ ኢትዮጵዊነት አይደለም ... ወዘተ» በማለት በኢትጵያዊነቱ በግልጽ ክህደትን እንዲፈጽም አድርገዉታል። እርስ በእርሱ እንዲጠላላና እንዲከፋፈል እንዲሁም ጥላቻና በቀል እንዲሞላ አድርገዋል። ታዲያ ይህን የዘሩትን የዘረኝነትና የጎጠኝነት የዓመፃ ፍሬና በኢትዮጵያዊነት ላይ የፈጸሙት ክህደት ዉጤቱ መራራ ቢሆንም የመጀመሪያዉ መራራ ጽዋ ተጋች እነዚህ ለዓመፃ መሪና ተዋናይ የሆኑ ዓመፀኛና ከሃዲ ሰዎች ናቸዉ።

እስቲ ትዉልዱን አንዳንድ ጥያቄ ልጠይቀዉ እፈልጋለሁ። አሁን ያለንባቸዉ ከተሞች የዛሬ መቶ፣ ሁለት መቶ፣ ሦስት መቶ፣ አራት መቶ፣ አምስት መቶ፣ ስድስት መቶ፣ ሰባት መቶ፣ ስምንት መቶ፣ ዘጠኝ መቶ አንድ፣ ሺህ፣ ሁለት ሺህ፣... ወዘተ ዓመት በፊት ነበሩ ወይ? በዚህች አጭር እድሜያችን እንኳን ያልነበሩ ብዙ ከተሞችና መንደሮች አልተመሰረቱም ወይ? ከዚያ በፊት በደንና በአራዊት እንዲሁም በበረኃነት የተዋጡ አልነበሩም ወይ? እንኳ እኛ ቀርቶ ዘር ማንዘሮቻችን አሁን በምንኖርበት ቦታ ላይ ይኖሩ ነበር ወይ? ሕዝቡ እየበዛ ሲሄድ አይደለም ወይ በእናት አገሩ ምድር ላይ እየሰፋ እየተስፋፋ ከተማና መንደር እየመሰረተ የኖረዉና እርስ በእርሱ በጋብቻና በኑሮ ተዋሕዶ የተገኘዉ? ታዲያ የዲያብሎስ አገልጋዮችና እንደራሴዎች «ይህ ያንተ ክልል ነዉ እንጂ የሌሎች አይደለም፤» እያሉ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን ሲፈጥሩ ስለምን ተቀበልናቸዉ? ስለምንስ ነዉ ኢትዮጵያዊዉ ከእናት አገሩና ምድሩ «ይህ ያንተ አገርና ክልል አይደለም» ተብሎ የሚፈናቀለዉና በደልና አድሎ የሚፈጸምበት? ምንስ በደለና ነዉ ቤተሰቡ መጠለያና መኖሪያ እንዳያገኙ የሚሰደደዉና ግፍና በደል የሚደርስበት? ለመሆኑ እኛስ ማነንና ነዉ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያዉያን በሰጣቸዉ ምድር ላይ አዛዥ ናዛዥ ሆነን የራሳችን መሰሪና የበቀል ተግባር የምንፈጽመዉና የምናስፈጽመዉ!?

ሌላዉ ደግሞ ክርስቲያኑን(ዐምሐራዉን) ለመበቀልና በአራቱም ማዕዘን የስራ እድል እንዳይኖረዉና በአገሩ ላይ አድሎ በደል የሚፈጸምበት ስለ ምንድነዉ? የስራ መስፈርት ትምህርትና እዉቀት መሆኑ እየታወቀና እንዲሁም እያንዳንዱ ተማሪ ተምሮ ባገኘዉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዉጤት ከዚያም ባገኘዉ ሰርተፍኬት፣ ዲፐሎማ፣ ድግሪ መሆኑ እየታወቀ፤ ያንንም ለማግኘት በኢትዮጵያዉኛ ቋንቋዉ(ዐማርኛ) ተምሮ ሳይሆን በባዕዳን ቋንቋ እንግሊዘኛ ተምሮ እንደሆነ በሚገባ እየታወቀ፤ ስለምድነዉ «አንተ ትግሪኛ ቋንቋ፣ ኦሮምኛ ቋንቋ፣ አደሪኛ ቋንቋ፣ ሱማሊኛ ቋንቋ፣ አፋሪኛ ቋንቋ፣ ሲዳምኛ ቋንቋ... ወዘተ ስለማትችል የስራ እድል የለህም» የሚባለዉ? ታዲያ ይህን የከፋና የከረፋ ሥርዓት ያመጡት የማን እንደራሴ መሆናቸዉ ተግባራቸዉና ፍሬያቸዉ የሚመሰክርባቸዉ ሲሆን፤ እዉነት ባለ ጊዜ ስትሆን የሚያፍሩበትና ዋጋም የሚከፍሉበት ይሆናል። ምክንያቱን እንኳን የተማረ ነገሮችን ግራና ቀኝ ማመዛዘን የሚችለዉ ቀርቶ መሃይም እንኳ ይህን የመሰሪነትና የበቀል ተግባር መፈጸም አይጠበቅበትም ነበር።

ሌላዉ እነዚህ የዓመፃ ልጆች ተከትላችሁ ቤተቦቻችሁን የበደላችሁና የጭካኔ ተግባር የፈጸማችሁትን የምጠይቀዉ ጥያቄ አለ። ይኸዉም እናንተ መሪዎች! ባለሥልጣናት! ካድሬዎች! የቋንቋ ክፍፍልና መለያየት አምጥታችሁ «በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ነዉ የምንማረዉ፣ የምንሰራዉ፣ የምንነጋገረዉ» በማለት የቅርብ ወገኖቻችሁን እስከ ስምንተኛ፣ አሥረኛ ክፍል ደርሰዉ እንዲሁም ከኮሌጅና ከዩኒቨርስቲ ተመርቀዉ በኢትዮጵያዉኛዉ (ዐማርኛዉ) ቋንቋ ሌላዉ ይቅርና ከኢትዮጵያዉያን ወገኖቻቸዉ ጋር እንዳይግባቡ ያደረጋችሁት፤ የራሳችሁን ልጆች ሲያስፈልጋችሁ በዉጭ አገር፣ ሲያስፈልጋችሁ በአገር ዉስጥ ባሉ ታዋቂ ትምህርት ቤት፣ ካቃታችሁ ደግሞ እንደ በፊቱ በዐማርኛና በእንግሊዘኛ ትምህርት በሚሰጥበት ትምህርት ቤት እያስተማራችሁ፤ ከዚህ በተጨማሪ እንኳን የራሳቸዉን ብሔራዊ ቋንቋ አይደለም እንግሊዘኛዉን ቋንቋ በደንብ እንዲናገሩበት እያስቻላችሁ፤ «ክልል» ብላችሁ በፈጠራችሁት ዉስጥ ደግሞ ዐማርኛ ቋንቋ እንደ ጠላት ቋንቋ አስቆጥራችሁ እንዳይማሩበት፣ እንዳይናገሩበት፣ እንዳይሰሩበት አድርጋችሁ ወገኖቻችንን ዱዳ ማድረጋችሁ መሰሪነታችሁንና ትዉልዱን መግደላችሁ አይደለምን? ይህስ ከላይ እስከ ታች ያላችሁትን ወንጀለኛ አድርጎ አያስቀራችሁምን? እናንተ ዐማርኛን ቋንቋ በመናገራችሁና በማወቃችሁ ምን ተጎዳችሁ? ይኸዉ ለአገር መሪነትና ባለሥልጣን እንዲሁም በተለያየ የኃላፊነት ወንበር ላይ ተቀመጣችሁ እንጂ የበደለችሁ ወይንም የጎዳችሁ ነገር አለ ወይ? ሌላዉስ ትዉልድ እንደ እናንተ መሪ፣ ባለሥልጣን፣ ኃላፊ መሆን የለበትምን? ወይስ የራሳችሁን ሰዉ ብቻ ዐማርኛን ቋንቋ እንዲናገሩበት፣ እንዲማሩበት ማድረጋችሁና ሌላዉ ሰዉ በጥላቻ እንዳይማርበትና እንዳይነጋገርበት እንዲሁም የስራ ቋንቋ እንዳያደርገዉ ማደረጋችሁ የእናንተ ልጆች ብቻ በመሪነት፣ በባለሥልጣንነት፣ በኃላፊነት ብቻ እንዲቀመጡ ፈልጋችሁ ይሆን? ትዉልዱን ዱዳ በማድረጋችሁ የመጀመሪያ ተጠያቂዎችና በታሪክም ተወቃሽ እንደምትሆኑ ልታዉቁ ይገባል!።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አራት

« <u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የኢትዮጵያ ትንሣኤና መልካሙ ዘመን እንዴት ነዉ የሚመጣዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እያንዳንዳችን በሚገባ ልናዉቀዉና ልናስተዉለዉ የሚገባን እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ መንገድና ጊዜ ማከናወን እንደሚችልና እንደ ፍጡሮቹ የዓመታት፣ የወራት፣ የቀናት ዝግጅት እንደማያስፈልገዉ ነዉ:: ምክንያቱም ሕይወት ያለዉም የሌለዉም ከእርሱ በወጣ ኃይል የተዋቀረ ስለሆነ ሁሉን ያዉቃል፤ ሁሉ በእርሱ እይታና ቁጥጥር ዉስጥ ነዉ:: ልክ እኛ ንፋስ ሥዕላችንን (ቴሌቪዥናችንን) በርቀት መቆጣጠሪያ (በሪሞት ኮንትሮል) ጣቢያዎችን (ቻናሎችን) በርቀት ሆነን እንደምንለዋዉጥና ከፈለግንም ማጥፋት እንዲሁም ድምፁን ከርቀት ሆነን መጨመርና መቀነስ እንደምንችል ሁሉ፤ ይኸዉም የርቀት መቆጣጠሪያዉ (የሪሞት ኮንትሮሉ) ዉስጣዊ አካሉ ከንፋስ ሥዕሉ (ከቴሌቪዥኑ) ዉስጣዊ አካሉ ጋር የሚገናኝበት የተለየ ኃይል ስላለዉ የርቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዉ ንፋስ ሥዕሉን በቀላሉ ማዘዝ ስለሚችል፤ እንደዚሁ ሁሉ ማንኛዉም ፍጥረት በእግዚአብሔር ኃይል ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜና መንገድ ማከናወን ይችላል:: በማንኛዉም ጊዜ ማንኛዉንም ትዕዛዝ በመስጠት የሚፈልገዉን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል::

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሆነ መልካሙ ዘመን የሚመጣዉ እርሱ እግዚአብሔር በወሰነዉ ቀን፣ ከቀናት በኋላ ይሁን ከወራት ወይንም ከዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: እኛ በተነገረን መሰረት በእርግጠኝነት አሁን ባለነዉ ትዉልድ ነዉ በእግዚአብሔር መልእክታት ላይ የተገለጸዉ ሁሉ የሚፈጸመዉ:: ልክ የቀድሞዉ የአገሪቱ የቤተ ምልክናዉ(የቤተ መንግሥት) ተጠሪ የነበሩቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና የቤተ ክህነቱ ተጠሪ የነበሩት ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስ ባልታሰበና ባልተገመተ ጊዜና አጠራር በአንድ ላይ ተጠርተዉ እንደሄዱ ሁሉ፤ የዓመፃ ልጆችም ባላሰቡት ጊዜና አጠራር ከምድር ተጠርገዉና ዋጋ ከፍለዉ እንዲሁ ብን ብለዉ ይጠፋሉ፤ ከምድር ይጸዳሉ:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን መልክእትና የንስሐ ጥሪ «አንቀበልም» ብለዉ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የጸኑት ሰዎች፣ ልክ በኖኅ ዘመን የንስሐ ጥሪና እድል ተሰቷቸዉ በኖኅ ላይ ባላገጡትና የእግዚአብሔርን ጥሪ ከቁም ነገር ባልቆጠሩት ላይ ድንገት ሳያስቡትና ሳይገምቱ የእግዚአብሔር ቁጣ መቶ እንደጠራረጋቸዉ ሁሉ፤ አሁንም የዓመፃ ስራ አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች በየአገሩ ያሉ ዓመፀኛ መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች፣ እንዲሁም በዓመፃ የጸኑ ሕዝቦች ሕሊናቸዉን አደንድነዋልና እንዲሁ ሳያስቡትና ሳይዘጋጁ በእግዚብሔር ቁጣ ይጠረጋሉ፤ ከምድር ይጸዳሉ:: ያ የሚጠረጉበትና የሚጸዱበት መንገድ የሚታወቀዉ በአንዱ አምላክ በፈጣሪ ነዉ::

ከእኛ የሚጠበቀዉ ራሳችንን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅተን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ብቻ ነዉ:: ስራዉን ሁሉ በበላይ የሚያከናዉነዉ እግዚአብሔር ስለሆነ የእርሱን ድንቅ ስራና ተአምር በናፍቆትና በጽናት መጠባበቅ ነዉ:: ወደ መጨረሻዉ ጠረጋና ጽዳት ጊዜ ስለደረስን አንድ የተለየ ክስተት ሲፈጠር የሚመለከታቸዉ ኃይሎች በተጠንቀቅ እንደሚቆሙ፤ እኛም በቅን

ሐሳብ፣ በመልካም ምግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ሆነን በተጠንቀቅ መጠበቅ ነዉ ያለብን። በራሳችን ሥልጣን አንድ ቀን የመቆየትና የመኖር ዋስትና ስለሌለን ዛሬ ነገ ሳንል ሁል ጊዜ ዝግጅዎች ሆነን መገኘት አለብን።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: እንኳን የሌላዉ ዓለም ሕዝብ ይቅርና የኢትዮጵያ እጅግ እጅግ ብዙዉ ሕዝብ ሳይቀር በአሁን ሰዓት በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ ዓለም ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ በመመልከት «የእግዚአብሔር መንግሥት በምንም ሁኔታ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ሊዘረጋ አይችልም» ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ «ቢዘረጋ እንኳን አንቀብልም» የሚሉ አሉ። አንዳንዶች ደግሞ «እግዚአብሔር መንግሥቱን ቢዘረጋም እንቃወማለን» የሚሉ አሉ። አንዳንዶች ደግሞ «በተስፋ እየተጠባበቅን ነዉ ይባስ ዘገየ» የሚሉ አሉ። ለዚህ ምን አይነት አስተያየትና ምክር አሎት?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ለዚህ ጥያቄ ምላሽ እንዲያመቸኝ የኢትዮጵያን ሆነ የዓለምን ሕዝብ በዋናነት በሦስት መልኩ እከፍለዋለሁ። **አንድኛዉ** እግዚአብሔር የለሽ በመሆነዉ ምድራዊ ሥርዓት ሕሊናቸዉ በፓለቲካ የተበከለና የተመረዘ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ ስለሚመላለሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትም ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህንቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድነት ተዋሕዶ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበት የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ሥርዓት፤ ለእነርሱ ተረት ተረትና ቅዠት ነዉ። **ሁለተኛዎቹ** ሰዎች ዓይነት ደግሞ «በፈጣሪ እግዚአብሔር» እናምናለን የሚሉ ነገር ግን እንደ ሥጋና ደም ሰሜታቸዉ የሚመላለሱና ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚሆን ምድራዊ ሥርዓት የሚመሰርቱና የሚፈልጉ ናቸዉ። **ሦስተኞቹ** ደግሞ እግዚአብሔርን በእዉነትና በእምነት የሚያመልኩበት ሰማያዊ ሥርዓት የሚፈልጉ ናቸዉ። በእያንዳንዱ ዓይነት እንዲሁም የተለያየ አቋምና ሕይወት የሚያራምዱ አሉ።

**በመጀመሪያዉ ዓይነቶች** ሕይወት ዉስጥ ያሉ ሰዎች «ፓለቲካና ዲሞክራሲ» በሚል ሽፋን የራሳቸዉን የዉሸት እዉነት ፈጥረዉ የሚመላለሱ፣ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር የሚያጋጩ፣ የራሳቸዉን ስዉር ዓለማ ለማሳካት አንዱን ከአንዱ ጋር ከማለያየት፣ ከመከፋፈል፣ ከማጋጨት፣ ከማጣለት፣ ከማገዳደል ወደ ኋላ የማይመለሱ፤ ተስፋቸዉ ምድር የሆነች፣ ባጠቃላይ እነ ሆዱና ሥልጣኑ እንዲሁም ጥቅሙ አምላኩ የሆኑ ሰዎች የተሰባሰቡበት ነዉ። የተወሰኑት ደግሞ ለሕዝብ ጥቅም እንቆማለን በማለት የተሰለፉ ነገር ግን ሙሉ እዉነታ ያልያዙ የተለያየ አመለካከት የያዙ ሰዎች የተሰባሰቡበት ነዉ።

**በሁለተኛዎቹ ዓይነት** ሕይወት ዉስጥ የሚካተቱት ከሕሊናቸዉ በላይ የሆነ አምላክ መኖሩን አምነዉ የሚመላለሱ፤ ነገር ግን በመሰላቸዉ ሕይወትና እምነት ዉስጥ የሚኖሩ፣ ዋና ተስፋቸዉ በሚታይና በሚጨበጥ ነገር ላይ ያደረጉ፣ መንፈሳዊነቱን ከአንገት በላይ የሚፈልጉ ናቸዉ። ጥቅም የሚያገኙበት ከሆነም መንፈሳዊነቱንም የሚገለገሉበት ናቸዉ። የተወሰነት ደግሞ መንፈሳዊነቱ በበላይ ሆኖ የሥጋና የደም ስሜታቸዉን ለማርኪያ የሚጠቀሙበት ከእግዚአብሔ እዉነታ በተቃራኒ ቢሆን

እንኳ ከመሰለፍ የማይመለሱ፣ ነገር ግን ሕሊናቸዉ እንዳይወቅሳቸዉ በራሳቸዉ የዉሸት እዉነት መንፈሳዊነት ተላብሰዉ ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ የቆሙ ናቸዉ።

**በሦስተኛዉ ዓይነት ሕይወት** ዉስጥ የሚካተቱት ደግሞ መንፈሳዊነቱ ቢልቅና የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ቢፈጸም የሚመርጡ ነገር ግን አስተሳሰባቸዉና አመለካከታቸዉ ካለዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ስለሆነ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብን እያደረጉ የራሳቸዉን የሥጋና የደም ስሜት ፈቃድ ከመንፈሳዊ ፈቃድ ጋር ደበላልቀዉ የሚመላለሱ ናቸዉ። የተወሰኑት ደግሞ መንፈሳዊነቱ መላቁን ብቻ ሳይሆን የሚመኙት እግዚአብሔር የራሱን መንግሥት እንዲያጸናና በአራቱም ማእዘን የእርሱ ፈቃድ ብቻ እንዲፈጸም የሚፈልጉ ከሌሎች ሰዎች ቁጥር አንጻር እጅግ እጅግ ጥቂት የሆኑ ሰዎች ናቸዉ።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት ዉስጥ የሚመላለሱ ሰዎች የእግዚአብሔርን እዉነታ ባይቀበሉና ለተግባራዊነቱ ባይሰለፉ አንዳች አያስደንቅም። ምክንያቱም ተስፋቸዉ ምድር ስለሆነች «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንጨፍር፣ እንዝናና፣ ሥጋችን ይድላዉ፣ ይመቸዉ፣ ሞተን በስብሰን ስለምንቀር እስከምንሞት ድረስ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን እንደልባችን እንመላለስ» የሚሉ ናቸዉ። ምናልባት እግዚአብሔርን የማወቅ እድል ቢገጥማቸዉ ከስም አማኞች በላይ ለእግዚአብሔር ሊታመኑና እንደ ፈቃዱ ሊመላለሱ ይችላል። የተወሰኑት ደግሞ በዚሁ ሥርዓት ዉስጥ ለሰዉ ልጆች ደኅንነት ሆነ መልካምነት ጥብቃና የሚቆሙ ሰዎች ቢሆኑም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉና እዉቀታቸዉ ስለሚመላለሱ ከእግዚአብሔር እዉነታ ጋር ሊጋጩና ለጥፋት ሊሰለፉ ይችላሉ። ነገር ግን ለሕሊናቸዉ ታምነዉ የሚኖሩ ናቸዉ። እነሱም ተስፋቸዉ ምድር ስለሆነ ከዛ ባለፈ አያስቡም፤ ልፋታቸዉም፣ ጥረታቸዉም፣ ትግላቸዉ ለቅርፊት ሥጋና ለምድራዊ ሕይወት ብቻ ነዉ። በመሆኑም እነሱም የእግዚአብሔር እዉነታን ባይቀበሉና ለፈቃዱ ባይሰለፉ አያስደንቅም። ይልቁኑ እነዚህ የእግዚአብሔርን ህልዉና የማወቅ እድሉ ቢያጋጥማቸዉ በቆራጥነት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሰለፉ ይችላሉ።

ሌላዉ መንፈሳዊነቱን ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ማርኪያ የሚጠቀሙ ሰዎች እዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ የጠፋባቸዉና እንዲሁም በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ሆነዉ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚገባ ያላስተዋሉ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱ ናቸዉ። ምናልባት ራሳቸዉን ከትዕቢትና ከዓመፃ ለይተዉ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ለእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ለመሰለፈ ከተዘጋጁ እግዚአብሔር ወደ ሙሉ እዉነት ዉስጥ ሊያስገባቸዉና ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸዉ ይችላል። የስም አማኞች ደግሞ ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ህልዉና ቢያምኑም ቅድሚያ የሚሰጡት ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለመቀበልና ለማመን የሚቸገሩ፣ በራሳቸዉ የዉሸት እዉነት ሕይወት የሚመላለሱ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ከራሳቸዉ ሥጋና ደም እዉቀት አንጻር ስለሚገመግሙ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ሊያጣጥሉና አንቀበለዉም ሊሉ ይችላል። ምናልባት ከስም አማኝነት ወተዉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ማምለክ ከጀመሩ ለሙሉ እዉነት ሊሰለፉ ይችላሉ።

የተወሰኑ ሰዎች ደግሞ መንፈሳዊነቱን እየፈለጉ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ከራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት ጋር እየቀየጡ የሚመላለሱ፤ ከዛም ባለፈ የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነታን «አንቀበልም፣ እንቃወማለን፣ ተመሳስሎ ኑሮን እንደግፋን፣ ከራስ በላይ ነፋስ በሆነ ሕይወት ነዉ የምንመላለሰዉ... ወዘተ» በማለት የሚመላለሱ፣ በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ያሉ ሰዎች ናቸዉ:: እነዚህ ሰዎች በእርግጥ ሊያስገረሙን ይችላል:: ምክንያቱም ለሰማያዊ ሕይወት የሚያበቃዉን ጠባቡን መንገድ እያወቁ፣ የጨለማ መንገዶችን «የሕይወት መንገድ ናቸዉ» ተብሎ እየተኖረባቸዉ እየተመለከቱ፣ ለጊዜያዊ ሥልጣን፣ ጥቅም፣ ክብር፣ ዝና፣ ድጋፍ ... ወዘተ ሲሉ የዓመፃዉን፣ የክህደቱን፣ የርኩሰቱን ሕይወትና እምነት እንደ ሕይወትና እምነት ተቀብለዉ ትዉልዱ በእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ላይና በቅዱሱ ኪዳን ላይ እየፈጸመ ባለዉ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም የአምልኮ ምንዝርና እንዲጸና በማድረጋቸዉ ነዉ:: በእንደዚህ ዓይነት ሕይወትና አቋም የሚመላለሱ ሰዎች ናቸዉ የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቃቀሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና መልእክት የሚያጣጥሉት፣ የሚንቁት፣ ሕሊናቸዉን በማደንደን ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነታ በተቃራኒ ተሰልፈዉ የዲያብሎስን ሥርዓት ለማጽናት በእግዚአብሔር ስም የሚነግዱት::

ይህን ሕይወት የተላበሱ ሰዎች ልክ እንደ ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት አምላካቸዉና ፈጣሪያቸዉ እዛዉ አጠገባቸዉ እያለ፤ «እናመልከዋለን» የሚሉትን አምላክ፤ ንጉሣቸዉ፣ መሪያቸዉ፣ አስተዳደሪያቸዉ፣ የበላያቸዉ ማድረግ ሲገባቸዉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስናቅና ለማዋረድ እንዲሁም በደልና ግፍ ለማስፈጸም ሲሉ «እኛ ንጉሣችን ፍጡሩ ሰዉ የሆነዉና አንቀጥቅጦና ረግጦ የሚገዛን ቄሣር ነዉ እንጂ ክርስቶስ አይደለም» በማለት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ግፍና ስቅላት እንዲፈጸምበት እንዳስደረጉት፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ያገለገሉ እንደነበሩት አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ዓይነት ናቸዉ:: እነዚህ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹህ፣ አንዳች በደልና ኃጢአት እንደሌለበት እያወቁ፣ ጲላጦስም መርምሮ አንዳች በደል እንዳላገኘበት እየመሰከረ፤ እነሱ ግን «ኢየሱስ ከወንበዴዉ በርባን በላይ በደል የፈጸመ ስለሆነ ይሰቀል፤ በርባን ግን ይፈታ» እያሉ ወትዉተዉ እንዳሰቀሉት፣ አሁንም ለጊዜያዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ዝና፣ ድጋፍ ሲሉ ሕሊናቸዉን የሚሸጡ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይፈጸምና የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ እስከመጨረሻዉ ድረስ አለመቀበል ብቻ አይደለም ከዲያብሎስ ሥርዓት ጋር ወግነዉ የእግዚአብሔርን አገልጋዮችና መልእክተኞችን ለማጥፋት ወደ ኋላ የማይመለሱ የዓመፃ ሰዎች ናቸዉ::

ታዲያ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት የራሳቸዉ በድልና ክህደት አንሷቸዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ከእነርሱ አልፎ በልጅ ልጆቻቸዉ ጭምር ላይ እንዲፈጸም በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ **27** ቁጥር **24**እስከ**26** ላይ «ጲላጦስም ሁከት እንዲጀምር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፣ ዉኃ አንሥቶ :- እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰዉ ደም ንጹህ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ:: **ሕዝቡም መልሰዉ:- ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ**:: በዚያን ጊዜ በርባንን ፈታላቸዉ፣ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል ሰጠ::» ተብሎ እንደተገለጸልን፤ ወደ **1900** ዓመት ለሚጠጋ ዘመን ትዉልዳቸዉ መከራንና ስቃይን፣ ስደትን እንዲወርስ አስፈርደዉበታል::

አሁንም የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነትና መንግሥት «እንቀበልም፣ አንፈልግም፣ እንቃወማለን፣ በምድር የዲያብሎስ ሥርዓት እስከ መጨረሻዉ መቀጠል አለበት... ወዘተ» የምንል ሰዎች፤ «እግዚአብሔር ሆይ ይቀር በለን፣ ተሳስተናል፣ ለአንተ መንግሥት ነበር ልንቆምና ልንከራከር የሚገባ የነበረዉ፣ እንዲሁም የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርን ማንንም ሳንፈራና ሳንሸነግል መቃወም ነበረብን፣ አሁን ግን ያንተን ሰማያዉ ሥርዓትህን ዘርጋልን፣ አንተ የመረጥከሃቸዉን አገልጋዮች በእዉነተኛዉ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ አስቀምጥልን... ወዘተ» እስከምንልና እኛችንን ለእግዚአብሔር እስከምሰጥ ድረስ የእግዚአብሔር ቁጣዉ በእያንዳንዱ መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ ግለሰብ ላይ ይነዳል። ያኔ ልክ ስለምንገባ እንኳን በእዉነተኛዉ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ዉስጥ መመላለስ የሚገባንና የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ዉስጥ ያለን አይደለም በሌላ እምነትና ሕይወት ዉስጥ የምንመላለስ ሰዎች፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምንፈልግና የዲያብሎስ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ እንዲወገድ እግዚአብሔርን በተራችን የምንለምነዉ እንሆናለን።

እግዚአብሔር «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ባስተላለፈዉ ሁለተኛዉ መልእክቱ በክፍል አንድ በምዕራፍ ዘጠኝ ከገጽ 118-123 ላይ ስለ ፓለቲካና ስለ ዲሞክራሲ ምንነት እንድናዉቅና ዲያብሎስ በምን መልኩ እየተጠቀመበት እንደሆነ በግልጽ እንድንረዳዉ አቅርቦልናል። ይኸዉም፡-

«እናንተ «ፖለቲካ፣ ዲሞክራሲ» የሚለዉ ልዩ ቋንቋዬ ስያሜ ያልገባችሁና በተደጋጋሚ ማብራሪያ እንድሰጥበት እየጠየቃችሁ የምታስቸግሩኝ ሰዎች፤ አሁን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምላሼንና ማብራራዬን እኔ የጨለማዉ ገዥ እሰጣችኋለሁ። ፖለቲካ የሚለዉ ስያሜ የተፈለሰፈዉ በቀጥታ እዉነታ የሚለዉ የእግዚአብሔር እዉነትን ለመቃወምና ስያሜዉንም ጭምር ለመተካት ታስቦ በእግዚአብሔር ተቃራኒ መንፈስ አሳሳቢነትና መሪነት የተፈጠረ ታላቅ ቃል ነዉ። በዚህም ምክንያት ሰዎች የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት አስተሳሰብን ሕሊናቸዉ በቀላሉ እንዲቀበለዉና ወደ ተግባርም ለመፈጸም እንዲቻል እንደ ዶግማና ቀኖና በርዕዮተ ዓለም መልክ እንዲቀበሉት የተደረገ ነዉ። ልዩ ጥበብና ፍልስፍ እንዲጨመርበትና ወርቃማ ቃላቶች እንዲካተቱበት የተደረገዉ፤ ሰዎች ተታለዉ ለእኔ ለጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች እንዲሆኑ፤ በነጻ ፈቃዳቸዉ እንዲቀበሉት፣ እንዲመሩበት፣ እንዲተዳደሩበት፣ እንዲታገሉበት፣ እንዲጋደሉበት፣ እንዲፋጩበት፣ እንዲገዳደሉበት፣ እንዲጨካከኑበት፣ አንዲከፋፈሉበትና እንዲለያዩበት፣ አንድ እንዳይሆኑበት፣ ባጠቃላይ ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ እንዲመላለሱበት ለማስቻልና በመጨረሻም ለታላቁ ለጨለማዉ መንግሥቴ ለማብቃት ታስቦ ነዉ።

በመሆኑም የምርጦቼ እንደራሴዎቼ መሪዎች ሆነ የባለሚሎቼ ባለሥልጣናት፣ የዉዶቼ ካድሬዎች፣ እንዲሁም ተጠባባቂ እጭዎቼ አስተሳሰብና ዓላማ እግዚአብሔር መፍራት ያለበትንንና ፈቃዱን የሚፈጽሙበትንንና የሚያስፈጽሙበትን ሥርዓት መዘርጋትና ሕዝቡ ምድራዊ በረከት እንዲያገኝ አድርገዉ ለሰማያዊ ሕያዉ ሕይወት ለማብቃት ሳይሆን፤ የእግዚአብሔርን ህልዉና

በመካድ «ሰዉ የተገኘዉ ከተፈጥሮ ነዉ። በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ወደ ሰዉ ተለዉጦ ነዉ። ጽድቅና ኮነኔ የሚባል ነገር የለም። ሰዉ በዚህች ምድር ሞቶ፣ በስብሶ ይቀራል እንጂ ትንሳኤ፣ ገነት፣ መንግሥተ ሰማያት የሚባል ነገር የለም ..ወዘተ።» በማለት በእኔ በጨለማዉ ገዥ ፍልስፍና የሚመሩ ፍጹም ለእኔ ታማኝ ሆነዉ ባሪያዎቼ የሆኑና ሕዝቡም ባሪያዎቼ እንዲሆኑ ሌት ተቀን የሚተጉልኝ የምርጦቼ ምርጥ መሆናቸዉን በዚሁ አጋጣሚ እመሰክርላቸዋለሁ።

ታዲያ በዚህ ፍልስፍናዬ የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶችን፣ እንዲሁም የተለያዩ ርዕዮተ ዓለሞች በየጊዜዉ እንደ ፋብሪካ ምርት እንዲመረቱና ሕዝቡም እንዲከፋፈል፣ እንዲለያይ፣ በጥላቻ እንዲተያይ፣ እንዲጣላ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንዳይሆን አድርጌ ሙሉ በሙሉ በጨለማ ሥርዓቴ እንዲመላለሱ አድርጌያለሁ። ስለዚህ ፖለቲካ የምለዉ ቋንቋዬ እጅግ ፍሬ ያፈረሁበት ለሕዝቡም ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነጻነት ፣አንድነት፣ ክብር፣ ታላቅነት፣ ብልጽግና፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ... ወዘተ ባጠቃላይ ወርቃማ የሆኑ ነገር ግን ወደ ተግባር የማይለወጡ አባባሎችንና ቃላቶችን አጎናጽፌዋለሁ። ስለዚህ እያንዳንዱ አባሌና ተከታዬ እንዲሁም ደጋፊዬ ዉለታዬን አሰቦ በየቦታዉ ሐዉልት አቁሞልኝ ሊያመልከኝ እንደሚገባ በዚሁ ትእዛዝና መመሪያዬን ለእንደራሴዎቼና ለባለሚሎቼ፣ ለዉዶቼ አስተላልፋለሁ።

ታዲያ አደራ የምላችሁ እዉነታ የምትባለዉን ሥርዓት ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ ፣ቤተ መንግሥቱ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመሩበትና ወደ ተግባር ተለዉጦ ሕዝቡ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት፣ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በሚሆኑበት፣ ባጠቃላይ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበትና ምድራዊ በረከት በሚያገኙበት፤ ለሰማይዊ መንግሥት በሚበቁበት ሕይወት እንዲመላለሱ እንዳታደርጉ። ይልቁኑ ዲሞክራሲ መብታቸዉን ተጠቅመዉ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሱበትን፤ እንዲሁም አድሎ፣ በደል፣ ግፍ፣ ጭከና.. ወዘተ የሚፈጸምበትን የበለጠዉን ሥርዓት አዘጋጁላቸዉ።

ሌላዉ ጥያቄያችሁ ስለ ዲሞክራሲ ምንነትና መገለጫዉ ሲሆን፤ ዲሞክራሲ ልክ እንደፖለቲካዉ እዉነታን ለመቃረንና ሰማያዊ ሥርዓትን ለመተካት ያዘጋጀሁት ልዩ ፍልስፍና ቋንቋዬ ነዉ። ይህም መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣኖች እንዲሁም ካድሬዎች እንደ ዶግማና ቀኖና ተመልክተዉት ሕሊናቸዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንዲቀበለዉ በርዕዮተ ዓለም መልኩ ያዘጋጀዉላቸዉ ሲሆን ዉጤቱም ሕዝቡ በሙሉ ነጻነቱ ተጠቅሞ ከፈለገ «እግዚብሔር የለም» ከፈለገ «እግዚአብሔር አለ» ብሎ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ፣ በትዕቢት፣ በዓመፃ ፣ በዝሙት፣ በግብረ ሰዶም፣ በዘፈን ፣ በዳንኪራ፣ በጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ በዘረኝነት፣ በጎጠኝነት፣

በአስማት፣ በጥንቆላ፣ በመተት ..ወዘተ ሕይወት ዉስጥ ምንም ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ እንዲመላለስ በማድረግ ለታላቅ ክብር ለማብቃት በማሰብ ነዉ በበላይ ሆኜ ዲሞክራሲ ሥርዓት የዘረጋዉላችሁ::

ታዲያ ይህን የተጎናጸፋችሁትን ዲሞክራሲ መብታችሁን ለመገደብና ብሎም ለማስቀረት ሰማያዊ ሥርዓት ናፋቂዎችን አንዳች እንዳትቀበሉ፣ እንዳትሰሙ:: እነሱ ከዚህ ከሚጣፍጠዉ ሕይወት ሊለያችሁና እግዚአብሔርን በመፍራትና በማስደሰት እንድትኖሩ አድርገዉ ከስስት፣ ከስግብግብነት፣ ከራስ ወዳድነት ሕይወት ለይተዉ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በመተዛዘን እንድትኖሩና ሕይወታችሁም በቅድስና እንድትመላለስ ሊያደርጉ ስለሆነ አንዳች እንዳትሰሟቸዉ፣ የሚሉትንም እንዳትፈጽሙ:: ይልቁኑ ሌት ተቀን ኮንደሙን በቴሌቭዥንና በሬድዮን፣ በስብሰባ እያስተዋወቃችሁ ዝሙትን አስፋፉ:: ከሕፃን እስከ አዋቂዉ ድረስ ነፍሱን በማሳበድ ሌት ተቀን በዘፈኑና በዳንኪራዉ አስጨፍሩት:: በተለያዩ ትዕይንቶችና ወሬዎች ሕሊናዉን አደንዝዙ:: ብቻ ምን እኔ እነግራችኋለሁ እናንተ ከኔ በላይ ሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ታዉቃላችሁና እንደማሳስባችሁና እንደምመራችሁ ሁሉን አስፈጽሙልኝ:: ለጠቅላላ እዉቀት ስለ ፖለቲካና ዴሞክራሲ የዚህን ያህል ካልኳችሁ ለወደፊቱ በዋናዉ መንግስታችን የበለጠ ማብራሪያ እንደምሰጣችሁ በጨለማዉ ስሜ ቃል እገባላችኋለሁ:: ዋናዉ ለዚያ መንግስት ያብቃችሁ እላለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ተራማጅ ኃይሎች፤ የሶሻሊስት፣ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ የካፒታሊስት፣ የኢምፔሪያሊስት .. ወዘተ እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓቶችን ለመቀበልና አዉሮፓዊ፣ አሜሪካዊ፣ ኤሽያዊ፣ አረባዊ ሥርዓት ለመዘርጋት ወደ ኋላ የማትሉ፤ የራሳችሁን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ለመዘርጋት ፈቃደኛ ያልሆናችሁ፤ ስለተራማጅ አስተሳሰባችሁና እንደማንነታችሁ ለመሆን አለመፈለጋችሁ ያለኝን አድናቆት እኔ የጨለማዉ ገዥ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ለወደፊትም በምንም መልኩ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ ምልክናዉ አንድ ሆነዉ በሚመሩበት የእግዚአብሔር መንግስት ሥርዓት እንዳትዘረጉ:: ከዘረጋችሁ ግን ከእኔ መንግሥት የምትለዩና የፈለጋችሁትን የዓመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር መፈጸም እንደማትችሉ አሁኑን እንድታዉቁ እፈልጋለሁ:: በዚህም ምክንያት ኃጢአትን ማንገስ ስለማትችሉ፣ የእግዚብሔር ባሪያ ሆናችሁ የምትቀሩና የእኔን የጨለማ መንግሥት ማግኘት ተስኗችሁ ወደ ሰማያዊ መንግሥት ልትገቡ እንደምትችሉ አዉቃችሁ ከእኔ እንዳትለዩ እስከመጨረሻዉ አንድነታችሁንና ኅብረታችሁን ለእኔ ብቻ መግለጽ ይጠበቅባችኋል:: ያኔ ከአንዱ ወደ አንዱ ወንበር አሸጋግራችኋለሁ:: ሕሊናችሁን በምታገለባብጡት ብቃት ደረጃ እኔም በዚያኑ ልክ እያገለባበጥኩ ወደፈለጋችሁት ወንበር አደርሳችኋለሁ::

ታዲያ በኔ ታቃራኒ መንፈስ የሚመሩ፤ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት እያሉ ስለ ሰባቱ ቅዱስ ኪዳናት የሚናገሩትን አትስሙ:: የእናንተ የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን 7500 አይደለም 3000 እንኳ አይሆንም:: ምርጥ እንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁና ባለሚሎቼ ባለሥልጣናት እንዲሁም ዉዶቼን ካድሬዎች መጠየቅ ትችላላችሁ:: በአስተያየት የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ አላችሁ ቢባልም

ዋናዉ ታሪካችሁ የጀመረዉ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዘመን ስለሆነ ታሪካችሁ ገና ሃያ ዓመትን አስቆጥሯል።

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ እንደ እናንተዉ ሕያዉ የሆንኩ ፍጥረት ነኝ። እንደእናንተዉ የማልሞት ከመኖር ወደ አለመኖር የማላልፍ፣ እንደ እናንተዉ የሚያስብ ሕሊና ያለኝ ዘመዳችሁ ነኝ። ታዲያ እኔ የሚያስገርሙኝና የሚያስደንቁኝ ጥያቄዎች ሁሉ ጊዜ በሕሊናዬ ይመላለሳሉ።

ለምሳሌ ያህል፣ እኔ ምን አድርጌላችሁ ነዉ ሌት ተቀን እኔ የጨለማዉ ገዥ ደስ በምሰኝበት ሕይወት የምትመላለሱት? ምንስ ዉለታ አድርጌላችሁ ነዉ በቴሌቭዥኑ፣ በሬድዮኑ፣ በሕትመቱ፣ በስብሰባዉ፣ በትምህርቱ፣ በድረ ገጽ ለኔ ፈቃድ የምትተጉትና ሌት ተቀን ፈቃዴን የምትፈጽሙትና የምታስፈጽሙት? ምን እንድከፍላችሁ ነዉ የአምላካችሁ ህልዉና የምትክዱትና «የተገኘነዉ ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ። እንደ እንስሳ ሚች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ነን። ከሞት በኋላ ሕይወት የለም፤ አንዳች አናዉቅም፤ አንጠየቅም።» በማለት ክህደት የምትፈጽሙት? ባጠቃላይ ምን ተስፋ አድርጋችሁ ነዉ የተለያየ ኃጢአት በመፈጸም ሌት ተቀን የምትመላለሱት?

ሌላዉ ግራ የገባኝ ስለምን ይሆን የእኔን የጨለማዉ ገዥ ሥርዓት ለመዘርጋትና የበላይነቴን ለማረጋገጥ በነፍሳችሁ ፈርዳችሁ፤ በሥጋችሁ ጫካና በረኃ ገብታችሁ፤ ገንዘባችሁን፣ እዉቀታችሁን፣ ጉልበታችሁን፣ ባጠቃላይ ሰዉነታችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ የምትታገሉልኝ? ስለምን ይሆን ለነፍሳችሁ ድኅነትና ሕያዉነት በሥጋችሁ ፈርዳችሁ ራሳችሁን በመካድና ስለ እዉነት በመመስከር በቆራጥነት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሕይወታችሁን የማታሰልፉት?

በዚህች ምድር አንድ ቀን ቀርቶ አንድ ሰዓት እንኳ በራሳችሁ የመቆየት ሥልጣንና ዋስትና የሌላችሁ መሆኑ እየታወቀ ስለምን ይሆን በትዕቢትና በእብሪት የምትናገሩት? ስለ ምን ይሆን የምትደነፉት? እግዚአብሔርስ ምን ያላደረገላችሁ ነገር አለና ነዉ «እኛ ምርጫችን የዲያብሎስ እንደራሴዎችንና ስራ አስፈጻሚዎችን ነዉ። ዲያብሎስ ይንገሥብን እንጂ እጃችንን ለእግዚአብሔር አንሰጥም። እንዲነግሥብንም አንፈልግም።» በማለት እኔን የጨለማዉን ገዥ አብልጣችሁ የመረጣችሁኝ?

ምንስ በደላችሁና ነዉ ሌት ተቀን እሱን በሚያስቆጣና በሚያሳዝን ተግባርና ሕይወት የምትመላለሱትና እኔን የጨለማዉን ገዥ ለማስደሰት የምትሯሯጡት? ምን ያልከፈለላችሁ ዋጋ ኖሮ

ነዉ ሁል ጊዜ በመስቀል ላይ ራቁቱን ሰቅላችሁ የእኔን ምስ ዳንኪራዉን፣ ዘፈኑን፣ የተለያዩ አጸያፊ ትዕይንቶችን እያቀረባችሁ የምታላግጡበትና እኔን ደግሞ ዙፋን ላይ አስቀምጣችሁኝ ነፍሴን የምታስደስቷት?

እኔ የተለያየ ፈተና፣ መከራ፣ ችግር፣ ስቃይ፣ በዚህች ምድር እያመጣሁባችሁ፣ ሌት ተቀን ፍዳችሁን እያሳየዋችሁ፣ በኋላም ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ እያዘጋጀዋችሁ፣ እረ ለመሆኑ ምን አድርጌላችሁ ነዉ እንዲህ ሙጭጭ ብላችሁ ከእኔ ከጨለማዉ ገዥ አልላቀቅ ብላችሁ የምታስቸግሩኝ?» ይላል የፖሊቲካና የዴሞክራሲ ጽንስ አሳብ አፍላቂና ሊቀ ምሁር  እንዲሁም አስመሳዩና አታላዩ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ፡፡» ተብሎ ተገልጾልናል፡፡

*ታዲያ ከላይ በተገለጸዉ የእግዚአብሔር መልእክት የምንረዳዉ ዲያብሎስ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ሕይወት አለያይቶ የእዉነትን መንገድ ለማጥፋት የተጠበበትን አካሄድና ትዉልዱም የእርሱን ምኞችና ፍላጎት ለማሳካት ቆርጠዉ መነሳታቸዉን፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር የሆነዉን ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ ላይ ተዋሕዶ ለእግዚአብሔር እዉነት ብቻ የሚቆምበትን ሰማያዊ ሥርዓት አጥብቆ እንደማይፈልግ፤ ከዚህ በተጨማሪ የእርሱ ባሪያ ለመሆን የምንተጋና በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ መሆናችንን ስላረጋጋጠ ምን ያህል እያላገጠብን መሆኑን ነዉ፡፡*

*<u>መልካሙን ዘመን የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለምትጠባበቁትና በእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት ለመመላለስ ራሳችሁን ላዘጋጃችሁት የማስተላልፈዉ መልእክት</u>፤ ምንም እንኳን እንደ ሥጋ ለባሽነታችሁ ቀኑ የዘገየ ቢመስልም፤ በተለያየ ፈተና፣ ችግር፣ መከራ ዉስጥ ብትሆኑም፣ እንዲሁም በዓመፃ ልጆች የተለያየ ግፍ፣ በደል፣ በቀል ቢፈጸምባችሁም፤ አሁን ወደ መጨረሻዉ ሰዓት የደረስን ስለሆነ የወራቶችን እጅግ ቢበዛ የዓመታትን ጊዜ በትዕግስትና በጽናት ልንጠባበቅ ይገባናል፡፡ ለአስራዎቹ ዓመታት ታግሰዉና እስከ አሁን ድረስ ጸንተዉ ያሉ ወገኖቻችንን በማሰብ ልንጽናና ይገባናል እንጂ አንዳች ተስፋ መቁረጥ የለብንም፡፡ እግዚአብሔር በአገልጋዮቹና በመልእክተኞቹ በኩል ያስተላለፈዉ መልእክት አንዱም ሳይቀር ይፈጸማል፡፡ አሁን ባለነዉ ትዉልዶች ዘመን ሁሉ ተፈጽሞ እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሔር በቸርነቱና በምሕረቱ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ያድርሰን እላለሁ፡፡»* **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አምስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በዓለም ላይ ስለ ሐሳዊ መሲህና ስለ 666 ብዙ ይነገራል፣ ይጻፊል። ነገረ ግን ስለ መልካሙ ዘመን «ሺህ ዓመት» ስለተባለዉ ሆነ ስለ ኢትዮጵያ ትንሣኤ (ስለ ኢትዮጵያ ቀን) ብዙም አይነገረም፣ አይጻፍም። ይህ ከምን የመነጨ ይመስሎታል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በዓለም ያለዉ እዉነታ ሰዎች ጆሮዋቸዉን የሚሰጡትና ለማንበብም የሚነሳሱት ለመልካም ነገር ሳይሆን ለመጥፎ ነገር ነዉ። እንዲሁም አንድ ሰዉ ዘመኑን ሁሉ መልካም ተናግሮ አንድ ቀን የተለየ ስሜት ዉስጥ ገብቶ የማይሆን ነገር ቢናገር ያ ለዘመናት የተናገዉ መልካሙ ንግግር ተሰርዞ አንድ ቀን የተናገራት መጥፎ ንግግር ነዉ ለዘመናት ተናግሮት እንደነበረ የሚቆጠረዉ እንጂ «ይህ ሰዉ ለምን እንደዚህ አለ?» ተብሎ አይጠየቅም። የንስሐ እድልም አይሰጠዉም።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** ሐሳዊ መሲህ ወይንም ሐሰተኛ ክርስቶስ ወይንም ሐሰተኛ አምላክ ስለሚባለዉና በዓለም ፍጻሜ ዘመን ለሦስት ዓመት ተኩሉ ለአጭር ዘመን ባለጊዜ ስለሚሆነዉ፤ በተለያየ እምነት ዉስጥ የሚመላለሱ አገልጋዮች ሆኑ አማኞች የሚናገሩና የሚጽፉ፣ ትዉልዱም ጆሮ ሰቶት የሚያዳምጠዉና የሚያነበዉ መሆኑ ይታወቃል። የሚያስገርመዉና የሚያሳዝነዉ ለረጅም ዘመን ባለ ጊዜ የሚሆነዉ እግዚአብሔር የሚነግሥበትን ወይንም በአራቱም ማእዘን ፈቃዱ የሚፈጸምበትም ሺህ ዘመን ስለተባለዉ የሚናገርም፣ የሚያስተምርም፣ የሚጽፍም የለም ማለት ይችላል። ምክንያቱም አንድም ባለመረዳትና ባለማወቅ፣ አንድም «እግዚአብሔር በምድር ሊነግሥ አይችልም» በሚል በተሳሳተ የሥጋና የደም እዉቀታቸዉ በመመላለሳቸዉ ነዉ። በዚህም ምክንያት በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ያሉ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን ስለ ሺዉ ዘመን ብዙ ግንዛቤ የላቸዉም። ነገረ ግን ይህ «ሺህ ዓመት» የተባለዉ፤ ረጅም ዘመንን የሚገልጸዉ እግዚአብሔር ባለጊዜ የሚሆንበትና እዉነተኛ አገልጋዮቹ በእዉነተኛዉ በሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽሙበትና የሚያስፈጽሙበት ዘመን ነዉ። በዚህ ዘመን የዓመፃ ልጆች ባለጊዜነት ሙሉ በሙሉ ይቀርና የእግዚአብሔር ሕዝቦች ባለ ጊዜ ይሆናሉ፤ እዉነት ትነግሣለች፤ ክህደት፣ ዓመፃ፣ ርኩሰት ይቆማል፤ ቅንነት፣ መልካምነት፣ እዉነተኛነት በዓለም ይሰፍናል።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተመረጠችዉ አገርና ሕዝብ ደግሞ ቅዱሱን ኪዳን የጠበቁ እዉነተኛ አገልጋዮችና ሕዝቦች የተገኙበት ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ናቸዉ። የሚያሳዝነዉ ደግሞ እነዚህ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በአሁን ሰዓት ላይ በዲያብሎስ እንደራሴዎችና አገልጋዮች መከራና ስቃይ እየደረሰባቸዉ ያሉ፣ እንዲሁም ግፍና በደል የሚፈጸምባቸዉ ናቸዉ። አንዳንዶቹ በእስር፣ አንዳንዶቹ በመንከራተት፣ አንዳንዶቹ በስደት፣ አንዳንዶቹ በጉስቁልናና በኀዘን ሕይወት ዉስጥ ነዉ ያሉት። «የሃይማኖት አገልጋይ ነን» የሚሉት ሳይቀር ከጨለማዉ ገዥ አገልጋዮች ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት እየፈጸሙና እያስፈጸሙ ነዉ። እንዲሁም የመንግሥት

የተለያዩ ተቋማት ሕዝቡ ሆነ ምእመኑ የኢትዮጵያን ትንሣኤ በተስፋ እንዳይጠባበቁ ቀን ከሌሊት በቴሌቭዥን፣ በሬድዮን፣ በመጽሐፍ፣ በመጽሔት፣ በጋዜጣ ሕሊናዉን እንዲደነዝዝ አድርገዉ የዲያብሎስን ፈቃድ  እንደ ልባቸዉ በአራቱም ማእዘን እየፈጸሙና እያስፈጸሙ ነዉ:: ይህ ብዙ ዓመታትን የሚገልጸዉ «ሺህ ዓመት» የተባለዉ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን ኢትዮጵያ ለዓለም ሁሉ ብርሃን የምትሆንበት፣ በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምታስፈጽምበት፣ እረኛዉ አንድ መንጋዉ አንድ የሚሆንበት፣ የተለያዩና የተከፋፈሉ እንዲሁም በጥልና በጥላቻ የሚፈላለጉ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት እንደ አንድ ቤተሰብ የሚኖሩበት ዘመን ነዉ::

ይህ ዘመን የሚያበቃዉም  በተለያዩ ዓለማት ዉስጥ የሚኖሩት የሰዉ ዘሮች ነፍስ ድምር ቁጥራቸዉ በምድር ዉስጥ ካሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር ጋር በሚቀራረብበት ዘመን ነዉ:: ያኔ ሐሰተኛዉ አምላክ በሰዉ ሥጋ ይገለጻል፣ ዓለምንም ያስታል፣ ለሦስት ዓመት ተኩል ዘመን ብቻ ባለጊዜ ይሆናል:: ከዚያም ዓመፀኞች፣ ከሃዲያን፣ ርኩሰት ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ለወራቶች ያህል በምድርም በእግዚአብሔር መቅሰፍት ይሰቃያሉ፣ ይቀጣሉ፣ በመጨረሻም በመቅሰፍት ሞት ለመጨረሻ ፍርድ ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ በእምነታቸዉ ጸንተዉ የተገኙ እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች በምሕረት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ተጠርተዉ በገነት ዉስጥ ከሚኖሩት ጻድቃን ጋር የመጨረሻዉን የእግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን ፍርድ ተመልክተዉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ወደ ሰማያት ዉስጥ ገብተዉ ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ:: በሲኦል ያሉና በዓለም ፍጻሜ ከምድር በመቅስፍት ሞት የተጠሩት ዓመፀኛ ነፍሳት «ርኩሳን ነፍሳት» ተብለዉ፤ በምድር ዉስጥ ከሚኖሩት በብዙ ትእልፊት ( በብዙ ቢለዮን) ከሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላሉ:: በዚያም እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ ፍዳቸዉን ያያሉ፣ እዉነተኛዉን ቅጣት ይቀበላሉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ሺህ ዓመት የሚለዉ በትክክል ሺህን ቁጠር ነዉ የሚወክለዉ ወይስ ሌላ ትርጉም አለዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጽሐፍ ቅዱስ ያለዉን ይቅርን ማንም በራሱ አመንጭቶ የጻፈዉን እንኳ መረዳት ተስኖን፣ ጸሐፊዉ እንዲያብራራልን እንደምንጠይቅና ምን ለማለት እንደፈለገ ከገለጸልን በኋላ በእርግጠኝነት እንደምናዉቅ ሁሉ፤ እግዚአብሔር «ሺህ ዓመት ማለት ይህ ነዉ» ብሎ ሲገልጽልን ወይንም ሲናገረን ነዉ በእርግጠኝነት የዓመቱን ርዝመት የምንናገረዉ:: ለምሳሌ በዓለም ፍጻሜ ዘመን የሚነሳዉ ሐሳዊ መሲህ ወይንም ሐሰተኛዉ አምላክ ወይንም ሐሰተኛዉ ክርስቶስ የባለጊዜነቱ ዘመን ሦስት ዓመት ተኩል መሆኑን በግልጽ ስለተነገረን ሦስት ዓመት ተኩል ነዉ ብለን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን:: ስለ ሺህ ዓመት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብዙ ቦታ ተገልጿል:: ነገር ግን ብዙ ዘመንን ከመወከል ዉጭ ቁጥሩ አሥር መቶዎችን ወይንም አንድ ሺህ ዓመት ይወክላል አልተባለም:: በመሆኑም በእርግጠኝነት ስለ ሺህ ዓመት መናገር የምንችለዉ ብዙ ዓመታት ወይንም ዘመን መሆኑን ነዉ:: ይኸዉም አምስት ወይንም አርባ ወይንም

ሁለት መቶ ዓመት ብለን ልንገለጸዉ አንችልም። በአሥራዎቹ ወይንም በመቶዎቹ ወይንም በሺዎቹ ዓመት ሊቆጠር ይችላል።

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ይህ ዘመን እንደ ሕዝቡ ቁጥር ብዛት ሊያጥርም ሊረዝምም ይችላል። ምክንያቱም የዓለም ፍጻሜ የሚሆነዉ በተለያየ ዓለማት ዉስጥ የሚኖሩት ማለትም በገነት፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሲኦል፣ በሰማያት፣ በምድር ዉስጥ የሚኖሩት የሰዎች ነፍስ ቁጥር በምድር ዉስጥ ካሉት ጅግ ብዙ ትእልፊት(እጅግ ብዙ ቢሊዮን) ከሆኑት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ቁጥር እኩል በሚሆንት ጊዜ ስለሆነ፤ ቁጥሩ በሚቃረብበት ዘመን የዲያብሎስ ዘመን ሦስት ዓመት ተኩልና እንዲሁም በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ የሚሳተፉና የዲይብሎስ ወይንም የሐሳዊ መሲህ ወይንም የሐሰተኛዉ አምላክ ወይንም የሐሰተኛዉ ክርስቶስ ተከታዮች ለወራቶች በዚህች ምድር ፍዳቸዉን የሚያዩበት ወራት ከቁጥር ዉስጥ ስለሚገባ እስከዛ ዘመን ያለዉ ዘመናት ነዉ ሺህ ዓመት የሚባለዉ። ይህ ዘመን እጅግ በቅርቡ በዓለም ላይ በእያንዳንዱ ዓመፀኛ መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ ግለሰብ ላይ የሚመጣዉ የተለያየ የእግዚአብሔር ቁጣ፤ ብዙ ሰዎችን ከምድር የሚጠርግ ከሆነ ሺህ ዘመን የተባለዉ መልካሙ ዘመን የኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመኑ በጣም ይረዝማል ማለት ነዉ። ብዙ ሰዉ ከቁጣዉ ከተረፈ ደግሞ ዘመኑ ያጥራል ማለት ነዉ። ይህ የሚታወቀዉ በእግዚአብሐር ዘንድ ነዉ። እግዚአብሔር በገለጸልንና በተናገረን መሰረት እኛ በእርግጠኝት ልንናገር የምንችለዉ ይህ ሺህ ዓመት የተባለዉ በአራቱም ማእዘን እዉነት የምትነግሥበትና የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚፈጸምበት ነዉ። ይህንን የእግዚአብሔር ፈቃድ የምትፈጽምና የምታስፈጽም ደግሞ ቅዱሱን ኪዳን የጠበቀችዉ ኢትዮጵያና ቅዱሱን ኪዳን የጠበቁ ሕዝቦቿ ናቸዉ። የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተጠሪ ሆነዉ በእንደራሴነት ሕዝቡንና ምእመኑን የሚያገለግሉት ደግሞ የዚህችዉ የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆኑ ቅዱሱን ኪዳን የጠበቁና ለዚህ አገልግሎት ራሳቸዉን ያበቁ እዉነተኛ አገልጋይ የሆኑት ካህኑ ንጉሠ ነገሥትና ካህኑ እጨጌ ናቸዉ። በእነርሱ ስር ሆነዉ ለአገልግሎት የሚሰማሩትም በእዉነትና በቅንነት የሚኖሩና እንዲሁም የእመቤታችን ምርጥ ባለሟሎችና ልጆች ናቸዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በብዙ የእምነት ድርጅቶች ማለት ይቻላል በተለያየ ጊዜና አሁንም «ዓለም በዚህ ጊዜ ታልፋለች፣ ክርስቶስ ወደ ምድር መቶ ከቅዱሳኑ ጋር ይነግሣል፣ እኛም ከእርሱ ጋር እንነግሣለን... ወዘተ» የሚሉ ሰዎች አሉ። ለዚህ ምን አስተያየት አሎት?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ ብዙ የእምነት ድርጅቶች ማለት ራሱ የብዙ አማልክት አምላኪዎች ማለት እንደሆነ መታወቅ አለበት። ምክንያቱም አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ሁሉ እርሱ የሚመለክበት አንድ እምነት ወይንም ሃይማኖት ብቻ ነዉ ያለዉና። ሰዎች በሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚፈጥሩት እምነት ሆነ ሃይማኖት እዉነተኛ እምነትና ሃይማኖት አይደለም። ለዚህም ነዉ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሥጋና ደም እዉቀታቸዉና ስሜታቸዉ እየተረጎሙ የተሰናከሉትና ያሰናከሉት። እንዲሁም እየተሰናከሉና እያሰናከሉ ያሉት። የዓለም ፍጻሜ ከላይ የተገለጸዉ መልካሙ ዘመን ሺህ ዓመት የተባለዉ የኢትዮጵያ ትንሣኤና እንዲሁም የሐሳዊ መሲህ

ወይንም የዲያብሎስ ዘመን (ሦስት ዓመት ተኩልና ዋጋ የሚከፈልበት ወራቶች) ሳይመጣ አይመጣም:: ምናልባት እጅግ በቅርቡ በዓለም ላይ የሚመጣዉ የእግዚአብሔር ቁጣ የዓለም ህልፈት ሊመስል ይችላል:: ነገር ግን የዓለም ህልፈት ሳይሆን እያንዳንዱ ዓመፃኛ ከምድር የሚጠረግበት፣ የዓመፃ ተግባርም የሚደመሰስበት፣ እንዲሁም መልካሙ ዘመን የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚመጣበት ነዉ:: «ዓለም በዚህ ዓመት፣ በዚህ ወር፣ በዚህ ቀን ታልፋለች» እያሉ የሚያስተምሩ ሆነ የሚናገሩ በዲያብሎስ መንፈስ የተታለሉና ሽዋጁ(አታላዩ) መንፈስ በሕሊናቸዉ የነገሠባቸዉ ናቸዉ:: ስለዚህ እንኳን ፍጡሮቹ ሰዎች ይቅርና ፈጣሪ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ምልክቶቹን ነዉ የተናገረዉ እንጂ «በዚህ ዓመት፣ በዚህ ወራት፣ በዚህ ቀን ዓለም ታልፋለች ብሎ » አልተናገረም::

«ክርስቶስ ወደዚህች ምድር መቶ ከቅዱሳኑ ጋር ይነግሣል» እያሉ የሚያስተምሩት ሆነ የሚናገሩት እንዲሁ መሪያቸዉ የዲያብሎስ መንፈስ የሆነና በሕሊናቸዉ ይህ መንፈስ ነግሦባቸዉ እየተጫወተባቸዉ ያሉ ሰዎች ናቸዉ:: እንዲሁም ክርስቶስን ያላወቁ « ፍጡር ነዉ፣ አማላጅ ነዉ፣ አንድ ኢየሱስ ብቻ ነዉ አብና መንፈስ ቅዱስ የሉም... ወዘተ» የሚሉ የክርስቶስ ተቃዋሚና ተሳዳቢዎች ሰዎች ናቸዉ:: ምክንያቱም ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች ግን እንደ እግዚአብሔርነቱ በሁሉ ቦታ ንጉሥ መሆኑን ስለሚያዉቁ እንደ ፍጡር የሚነግሥ አምላክ አለመሆኑን በሚገባ ያዉቃሉ:: እንኳን ክርስቶስ ይቅርና የእርሱ እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች በዚህች ምድር መኖርን አይፈልጉም:: ምክንያቱም ለመጥራት፣ ለመንጠር፣ ለመንጣት፣ እንዲሁም በአዳምና በሔዋና በቀደም ዓመፃቸዉ ምክንያት ባደፈና በጎደፈ በጎሰቆለ ባሕርይ እንዲሁም በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ለመቀጣት፣ ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ካልሆነ በስተቀር አንዲት ቀን በዚህች ምድር መቆየትን አይመርጡም:: አንዳች መልካም ነገር የሚቀርባቸዉ የሌለና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ቢሄዱ እጅግ የበለጠዉ ነገር ስለሚጠብቃቸዉ ነዉ:: ይህም የሚያሳየን ይህች ምድር የእኛ ምድር እንዳልሆነችና ወደ እዉነተኛዉ መኖሪያችን መሸጋገሪያ ድልድይ ብቻ መሆኗን ነዉ:: ከእኛም የሚጠበቀዉ በዚህች መሸጋገሪያ ድልድይና በዓይን ቅጽበት እድሜያችን ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስና ፈቃዱን ብቻ መፈጸም፣ ማስፈጸም ነዉ::

ክርስቶስ ፈቃደኛ በሆነበት ሰዉ ላይ ሆነ መንግሥት ላይ ነግሦ ሊኖርበት ይችላል:: ይህም ያ ግለሰብ ወይንም መንግሥት የክርስቶስን ፈቃድ ብቻ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል ማለት ነዉ:: በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚሆነዉም ይህ ነዉ:: እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በእዉነተኛ አገልጋዮቹና አማኞቹ ላይ ነግሦ እርሱ ራሱ መሪያቸዉ ሆኖ ፈቃዱን ያስፈጽማል:: በዚህም ምክንያት እዉነት ትነግሣለች ማለት ነዉ እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘዉድ ደፍቶ በዚህች ምድር ላይ አይነግሥም:: መንገሥ ብቻ አይደለም ወደዚህች ምድርም ዳግም ባሕርይዉን ወስኖ አይመጣም:: ለፍርድ የሚመጣዉም ከዚህች ምድር(ዓለም) ዉጭ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በመጽሐፍ ሽፋን ላይ በግልጽ እንደሚታየዉ በማረፊያ ቦታ ላይ ብቻ ነዉ:: በፍርድ ቀን ወደ ማረፊያ ቦታ በእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክትና እንዲሁም በቅዱሳን ነፍሳት ታጅቦ ሲመጣ ልክ እኛ እዚህ

ሆነን ፀሐይን እንደምንመለከት በዚያን ጊዜ በምድር የሚኖሩ ሰዎች እንደፈቃዱ የሚመላለሱ ሁሉ፤ ይህች ምድርና ማረፊያ ቦታ በተነካኩበት ቦታ ላይ በግልጽ እንደ ጨረቃ እየታያቸዉ በምሕረት ሞት ወደማረፊያ ቦታ ይነጠቃሉ:: በዚያም የመጨረሻዉን ፍርድ ተቀብለዉ በገነት ካሉት ነፍሳት ጋር በአንድ ላይ ወደ ሰማያት ዉስጥ ይገባሉ:: በተቃራኒ ደግሞ ሐሳዌ መስህን የተቀበሉና በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱት ሰዎች በመቅሰፍት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይሄዱና የመጨረሻዉን ፍርድ ተቀብለዉ፤ ይከተሉት ከነበረዉ ከዲያብሎስና ከሠራዊቶቹ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ጋር እንዲሁም በሲኦል ዉስጥ ካሉት ርኩሳን ነፍሳት (ዓመፀኛ ሰዎች) ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላሉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ሌላዉ ጥያቄዬ ልክ እንደ ሺህ ዘመንና ሐሳዌ መሲህ የሰዎች መነጋገሪያ የሆነዉ 666 ስለተባለዉ ነዉ:: ስለ 666 የተነገሮትን ወይንም የተገለጸሎትን ቢነግሩን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: «666» የዲያብሎስ ዓርማ ነዉ:: ይህም ዓርማ የተቀበለ ሁሉ ዲያብሎስን ተቀብሏል ማለት ነዉ:: «666» ተብሎ የተገለጸዉ ዲያብሎስ ዓርማ ስዉር ሳይሆን ግልጽ የሚታወቅ መሆኑን ለማሳየት ነዉ እንጂ ራሱ ቁጥሩ ነዉ ማለት አይደለም:: በዓለም ፍጻሜ ዘመን ለዲያብሎስ ዓርማነት የሚያገለግለዉን እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: የአሁን ዘመን እንደ 666 የሚያገለግለዉ የዲያብሎስ ዓርማ ኮኮብ ነዉ:: በዓለም ላይ ያሉ መንግሥታት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጭምር ይህን የአሁን ዘመን የዲያብሎስ ዓርማ የሆነዉን በመንግሥት ሰንደቅ ዓላማ ላይ፣ በድርጅት ሰንደቅ ዓላማ ላይ፣ በታተሙ ወረቀቶች ላይ፣ እንዲሁም በተለያየ መንገድ ላይ በግልጽ በማኖር መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች፣ ብዙ ሕዝቡ ተቀብሎታል:: ይህም የሚያሳየን በዓለም ፍጻሜ ዘመን የሚሆነዉ 666 የዲያብሎስ ዓርማ እንዲሁም በማያስታዉቅ መልኩ፣ ይልቁኑ እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት «ይህ ኮኮብ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትን የሚያሳይ ነዉ» በማለት ሌላዉ ላይ ተጽህኖ ሊፈጥርና ይህንን የዲያብሎስ ዓርማ የሚቃወም ወይንም አልቀበልም የሚል አካል ወይንም ግለሰብ ካለ በወንጀል ሊያስጠይቅ በሚያስችል መልኩ ነዉ በመጨረሻ ዘመን ዲያብሎስ መንግሥታት ሆኑ ሕዝቡ ዓርማዉን እንዲቀበል የሚያስገድደዉና ተጽህኖ የሚፈጥረዉ:: ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠዉ 666 የዲያብሎስ ዓርማ የሆነና የሚሆን ነዉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ከላይ በገለጹልን መሰረት በአሁን ሰዓት ብዙ አገራት፣ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ግለሰቦች «የአሁን ዘመን 666 የዲያብሎስ ዓርማ ነዉ» ያሉትን ኮኮብ ተቀብለዉ እየተጠቀሙበት ነዉ:: ታዲይ እነዚህ አገራት፣ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች ዲያብሎስን ተቀብለዋል ማለት ነዉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ሰይጣን « እኔ ሰይጣን ነኝና ተቀበሉኝ» ብሎ አይደለም፤ ዓለም ወይንም ሕዝቡን የሚያሳስተዉና ከሕይወት የሚያሶጣቸዉ:: እንደ ትዉልዱ መራቀቅ እርሱም እየተራቀቀ ነዉ የሚያሳስተዉና የሚያሰናክለዉ:: ታዲያ አሁንም በዓለም ላይ ዓርማዉ እንዲገንና ተቀባይነት እንዲያገኝ የተለያየ ወርቃማ መገለጫና ትርጉም ተሰቶት ነዉ ጥቅም

ላይ ያዋለዉ፡፡ ከዓለም አገራት ሆነ ሕዝቦች አስገራሚና አሳዛኝ አገርና ሕዝብ ደግሞ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ናቸዉ፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር በአገሪቱ ነግሦ የነበረ ቢሆንም፤ እስከ መስከረም ፪÷፲፱፻፷፯ (2/1/1967) ዓ.ም ድረስ ግን ዲያብሎስን በግልጽ «ይንገሥብኝ» ብላ አልተቀበለችም ነበር፤ ሕዝቡም አልተቀበለዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከመስከረም ፪÷፲፱፻፷፯ 2/1/1967 ዓ.ም ጀምሮ ዲያብሎስ ነግሦባት ዓርማዉም ተቀባይነት አግኝቶ ከፍ ከፍ ብሏል፡፡ ከግንቦት፳÷፲፱፻፹ ፫ (20/9/1983) ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በከፋ መልኩ ዲያብሎስ በአገሪቱ በአራቱም ማእዘን ነግሚል፡፡ ያ ብቻ አይደለም በግልጽ በሰንደቅ ዓለማና ኅትመቶች ላይ ተቀባይነት እንዲያገኝ ተደርጎ የዲያብሎስ ዓርማ ዓርማቸዉ አድርገዉ መጠቀም ችለዋል፡፡

እጅግ አዛዛኙና አሳፋሪዉ ደግሞ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት አባቶችና በተዋረድ እስከ ታች ያሉ አገልጋዮች በአደባባይ «ኮከብ የሌለበት ሰንደቅ ዓላማ የእኛ ሰንደቅ ዓላማ ስላልሆነ እዳትይዙ፣ እንዳታመጡ» በማለት ተናግረዋል፡፡ 666 የሆነዉን የዲያብሎስ ዓርማ በቤተክርስቲያን ሳይቀር ከፍ ከፍ አድርገዉ ሰቅለዋል፡፡ የዲያብሎስን «ዓርማዉ ዓርማችን ነዉ» ብለዉ ተቀብለዋል፡፡ ታዲያ ይህ ክህደት በእያንዳንዱ ላይ የከፋዉን የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደሚያመጣ በእምነት ዉስጥ ላለ ሰዉ ይታወቀዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ዓመፃና ክህደት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ሰዎች ሁሉ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሱና የዘመኑ የዲያብሎስን ዓርማ የሆነዉን ኮከብ ከአገሪቱ ካላስወገዱ በስተቀር ዲያብሎስን በግልጽ ተቀብለዋል፣ በስራዉ ተባብረዋል፡፡ በመሆኑም በራሳቸዉ ላይ የከፋ ቅጣት ማምጣታቸዉ አይቀርምና በእዉነተኛ ንስሐ ራሳቸዉን ከዲያብሎስ አገልጋይት ቢለዩ ይበጃቸዋል፡፡ «ካለ እርሱ አይሆንልንም፣ መንግሥትም አይፈቅድልንም፣ ይበቀለናል » ካሉ ደግሞ በዓለም ፍጻሜ ዘመንም የዲያብሎስን ዓርማ መንግሥታት ሆኑ ግለሰቦች የሚቀበሉት «ሥልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ዝና ይቀርብናል፤ ልንገደል፣ ልንታሰር፣ ልንሰደደ ልንቸገር እንችላለን» ብለዉ ስለሆነ፤ አሁንም ከእነርሱ ያልተለየ ሕይወት እንደያዝን በሚገባ ልናዉቅና ልናስተዉል ይገባል፡፡ የቅዱሱ ኪዳን ዓርማችን የመለኮት ዓርማ የሆነዉ «ሞአ አንበሳ» የተባለዉ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓርማ ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ ልንቀበለዉ ሆነ የእኛ ነዉ የምንለዉ ዓርማ የለም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ሐሳዊ መሲህ ወይንም ሐሰተኛዉ ክርስቶስ ወይንም ሐሰተኛዉ አምላክ ማን እንደሚሆን ፣ የምን ዜጋ እንደሚሆን ይታወቃል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በዓለም ፍጻሜ ዘመን ለሦስት ዓመት ተኩል በዓለም ባለጊዜ የሚሆነዉ ሐሳዊ መሲህ እዉነተኛዉን ክርስቶስን በመምሰል ነዉ ዓለምን የሚያስተዉና የሚያሰናክለዉ፡፡ ልዩነቱ ተግባሩና ሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር ፍጹም ተቃራኒ ነዉ፡፡ ልክ ክርስቶስ በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና እንደተወለደ፤ ሐሳዊ መሲህም በዝሙት ከዲያብሎስ ተወልዶ ሳለ «በድንግልና ተወለድኩ» ይላል፣ በሐሰተኛ ነብያቱ የሐሰት ምስክር ያሰጣል፡፡ ልክ ክርስቶስ እግዚአብሔር ቢሆንም በሰማያት ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ፣ እንዲሁም ከአማናዊ ሕዋ ዉስጥ እንደ አማናዊ ባሕርይዉ ከመኖር ሳይለይ፣ ፍጥረታቱን ከመቆጣጠርና ከመመገብ ሳይለይ፣ ባሕርይዉን ብቻ ወስኖ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

ከሥጋዋ ሥጋና ከነፍሳ ነፍስ ነስቶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ እንደተገለጸ ሁሉ፤ ዲያብሎስም የአዳም ዘር ከሆነችዉና የራሱ መንፈስ ካደረባት ሴት ከሥጋዋ ሥጋና ከነፍሳ ነፍስን ነስቶ ፍጹም ሰዉ ፍጹም ዲያብሎስ ሆኖ ይገለጻል:: እግዚአብሔር ሰዉ በመሆኑና ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔዓለም፣ ወልደ እግዚአብሔር፣ ጌታችን፣ አምላካችን፣ የሚለዉን ስም እንዳገኘ ሁሉ፤ ዲያብሎስም የተለያየ ስም ይይዛል:: ክርስቶስ ሐዋርያትንና ደቀመዛሙርትን መርጦ ለእዉነተኛ ለአገልግሎት እንዳሰማራ ሁሉ፤ ሐሳዌ መሲህም ትዕቢት፣ ክፋት፣ ዓመፃ የተባሉ የፈርያን፣ የይሁዳ፣ የአርዮስ ወንድምና እህቶን መልምሎ ለዓመፃና ለክህደት አገልገሎት ያሰማራቸዋል:: ክርስቶስ በሠላሳ ዓመቱ ማስተማርና የተለያዩ ተአምራት፣ ፈዉስ እንዳደረገ ሁሉ፤ በሥጋ የተገለጸዉ ሐሳዌ መሲህም የክህደት፣ የዓመፃ ትምህርት፣ የግፍ የጭከና ተግባር፣ የርኩሰት ተአምራት ያደርጋል:: ክርስቶስ በሦስት ዓመት ተኩል ዉስጥ የሚያስፈልገዉን ተግባር ፈጽሞ ወደ ቀደመ ክብሩ እንደተመለሰ ሁሉ፤ ሐሳዌ መሲህም በሦስት ዓመት ተኩል ዉስጥ ባለጊዜ ሆኖ በእርሱ በሚያምኑትና በሚቀበሉት ላይ እንደ አምላክ ነገሦ ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን ካነገሠ በኋላ ከባለጊዜነቱ ይሻራል:: በእግዚአብሔር መቅሰፍት ይመታል:: እርሱን ያመኑ፣ የተከተሉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ በመቅሰፍት በምድር ዉስጥ ጭምር ይሰቃያሉ:: በመጨረሻም በመቅሰፍት ሞት ለመጨረሻ ፍርድ ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ:: በተቃራኒ ደግሞ እርሱን ያልተቀበሉና ያልተከተሉ አእምሮ ጽንአን በምሕረት ሞት ወደ ማረፊይ ቦታ ተጠርተዉ የመጨረሻ ፍርድ ተቀብለዉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ::

ሐሳዌ መሲህ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ እንደማይሆን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ምክንያቱም ቅዱሱን ኪዳን ጠብቀዉ ከተገኙት ኢትዮጵያዉያን ዘንድ ሊወለድ አይችልምና:: ትዉልዱና ነገዱ ደግሞ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አምላክነቱ በማይቀበሉትና በካዱት እንዲሁም «ክርስቶስ ገና ከእኛ ይወለዳል» ብለዉ በአጉል ተስፋ በሚጠባበቁት፣ ቅዱሱን ኪዳን መጠበቅ ሲገባቸዉ መጠበቅ ባቃታቸዉ ዘንድ መሆኑ ይታወቃል:: ስለዚህ ማንም ሰዉ «ክርስቶስ ዳግሞ ይወለዳል ወይንም ወደዚህች ምድር ይመጣል» ብሎ እንኳን ማመንና መቀበል አይደለም ማሰብ አይገባዉም:: ምክንያቱም ዲያብሎስ ትንሽ የሐሳብ ክፍተት ካገኘ ያቺኑ ክፍተት እያሰፋ ወደ ዓመፃና ክህደት ሊመራን ይችላልና::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ከዚያ ጋር አንድ የሚመልሱልኝ ጥያቄ አቀርባለሁ:: ይኸዉም አንዳንድ መምህራን እግዚአብሔር በምሕረት ሞት የጠራቸዉ ሰዎች እንደ ጻድቁ ሄኖክ፣ ነቢዩ ኤልያስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ የመሳሰሉት ሰዎች «ተመልሰዉ ወደዚህ ምድር መተዉ ይሞታሉ እንጂ ሳይሞቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» የሚሉ አሉ:: ሰዉ ከሞተ በኃላ ተመልሶ እንደገና ሊወለድ ይችላል ወይ? እንዲሁም በሥጋ ተገልጾ ሊመላለስ ይችላል ወይ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: እግዚአብሔር በተለያየ መልኩ ነፍሳችንን ከሥጋችን ለይቶ ሊጠራን እንደሚችል ቀደም ብዬ ገልጫለሁ:: ሞት የምንለዉ ነፍስ ከሥጋ መለየትና ሌላ ረቂቅ አካል ለብሳ በተዘጋጀላት ቦታ መገለጽ እንጂ ህልዉና የሚታጣበት ወይንም ከመኖር ወደ አለመኖር የሚታለፍበት አይደለም:: ይህ ግንዛቤ እንኳን እግዚአብሔርን በማያመልኩት ዘንድ ቀርቶ እግዚአብሔርንና ትንሣኤን በሚያምኑ ዘንድ በሚገባ የተስተዋለ አይመስለኝም:: ምክንያቱም የተለያዩ

ምእመናን በተለያየ መድረክና ጽሑፍ ሰዉ ከሥጋዉ ሲለይ የሕይወቱ ፍጻሜ አድርገዉ ነዉ የሚያስቡትና የሚገምቱት:: ትንሣኤ የሚባለዉን በጥርጣሬ ነዉ የሚያምኑት እንጂ በእርግጠኛነት «ሕያዋን ነን፣ አንሞትም፣ ወደ ሌላ ዓለም ነዉ የምንሄደዉ» በማለት አይናገሩም፤ ምስክርነትም አይሰጡም:: ለዚህም ነዉ አንድ ቤተሰባቸዉ ወይንም ወገናቸዉ በሥጋ ሞት ሲለያቸዉ ኀዘናቸዉ መሪሪ የሚሆነዉና እስከ መጨረሻ ድረስ እንደተለዩት አድርገዉ የሚቆጥሩት::

በእዉነተኛ አምልኮና በትንሣኤ የሚያምን ሰዉ፣ ስለ ሕያዉነቱ እርግጠኛ የሆነ ሰዉ ሞቱን አንዳች አይፈራም:: ይልቁኑ ከዚህች ኀስቋላ ዓለም እንዲገላገል የሚፈልግና ወደ ፈጣሪዉ ለመሄድ የሚናፍቅ ነዉ:: በዚህም ምክንያት ሞቱን በናፍቆትና በጉጉት ይጠባበቃታል እንጂ ከቤተሰቡ፣ ከወዳጆቹ፣ ዓላማዉ ከሆነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸምና ከማስፈጸም ከመለየቱ ኀዘን ዉጭ አንዳች የተለየ የመረረ ኀዘን አይሰማዉም:: ስለዚህ ሞት የሚያስፈራዉና እንደ ተለየ ነገር ተደርጎ የሚቆጠረዉ ከሥጋ ሞት በኋላ ያለዉን ሕይወት ለማያምን እንጂ፤ በእኛ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ለምናምንና እምነትን ከምግባር ጋር አዋሕደን ለያዝን ኢትዮጵያዉያን ግን ከዚህ ኀስቋላ ዓለም የምንለይበትና ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታችን የምንሄድበት የእግዚአብሔር ታላቅ መሳሪያ ነዉ::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስግባ**: የሞተ ሰዉ ተመልሶ ሰዉ ሆኖ በምድር አይወለድም፣ አያድግም፣ ተመልሶም አይሞትም:: አንድ ሰዉ በተለያየ ጥሪ ወደ ፈጣሪዉና ፈጣሪዉ ወዳዘጋጀለት ቦታ የሄደ ሰዉ ተመልሶ ወደ ኀስቋላዋ ምድር አይመጣም:: ምክንያቱም ጠርቶ፣ ነጥሮ፣ ነቶ፣ እንዲሁም በአዳም ሔዋን የመጀመሪያ ኃጢአት ምክንያት ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጉስቁልና ባሕርይ፣ እንዲሁም በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ተቀቶ ስለሆነ ወደ ተዘጋጀለት ቦታ የሄደዉ፤ ዳግም ወደዚህች ምድር ለመንጣት ሆነ ለመንጠር እንዲሁም ለመጥራትና ለመቀጣት አይመጣም:: ምክንያቱም ድርሻዉንና አገልግሎቱን በሚገባ ፈጽሞ ሄዷልና:: ከዚህ አንጻር ወደ እግዚአብሔር በምሕረት ሞት ተጠርተዉ የሄዱ ጻድቃንና ቅዱሳን ነፍሳቸዉን ብቃት ደረጃ ላይ በማድረሳቸዉ ስለሆነ፤ የሚጠበቅባቸዉን ድርሻና አገልግሎት በሚገባ ፈጽመዋል ማለት ነዉ:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲገቡም በምድር በተገለጹበት ግዙፍ ሥጋ አይደለም:: ከምድራዊ ሕይወት ዉጭ ያለዉ ዓለም ሁሉ ረቂቅ ዓለም ስለሆነ ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ከምድራዊ ሕይወታቸዉ ዘመን በኋላ ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተላብሰዉ ነዉ ወደ ረቂቁ ዓለም ገነት ሆነ መንግሥተ ሰማይ እንዲሁም ሲኦል ሆነ ገሃነመ እሳት ዉስጥ የሚኖሩት:: ግዙፉ ሥጋ ምሳሌያዊ ፍጥረት ነዉና በዚሁ ምድር ዉስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር የሚያልፍ ነዉ:: ነገር ግን በጽድቃቸዉ የተለየ ሞገስና ክብር ያገኙ ቅዱሳን ሰዎች፤ ጻድቅና ቅዱስ መሆናቸዉ እንዲታወቅ ነዉ እግዚአብሔር በምሕረት ሞት የወሰዳቸዉ:: እንኳን ነፍሳቸዉን ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሱት አይደለም፤ በዓለም ፍጻሜ ዘመን በእምነታቸዉና በምግባራቸዉ ጸንተዉ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በምሕረት ሞት ነዉ ወደ ማረፊያ ቦታ ተንጥቀዉ የሚሄዱትና የመጨረሻዉን የእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ፍርድ ተቀብለዉ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚገቡት:: ይህም የሚያሳየን ይህ ሥጋቸዉ እኛ በምናዉቀዉ መልክ ከነፍስ ተለይቶ መቃብር ዉስጥ ሳይገባ እግዚአብሔር በምሕረት ነፍሳቸዉን ከሥጋቸዉ ለይቶ ረቂቅ አካል፣ የማይሞት፣ የማይፈረስ፣ የማይደማ፣ የማይቆስል፣

ቅዱሳን መላእክት እንደ ተገለጹበት ረቂቅ አካል አልብሶ ነዉ እግዚአብሔር ወደ መንግሥቱ የሚያስገባቸዉ::

እግዚአብሔር በተለያየ ዘመን የተለያዩ አገልጋዮችንና መልእክተኞችን አስነስቷል፤ እያስነሳም ነዉ፤ ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያስነሳል:: ጻድቁን ሄኖክ ሆነ ነቢዩን ኤልያስን እንዲሁም ቅዱስ ዮሐንስን... ወዘተ የመሳሰሉትን የበቁ ነፍሳትን ያስነሳ አምላክ፤ አሁንም ሆነ ወደፊትም እንዲሁም በዓለም ፍጻሜ ዘመን ለሦስት ዓመት ተኩል ባለ ጊዜ የሚሆነዉ ዲያብሎስ ወይንም ሐሳዌ መሲህ ወይንም ሐሰተኛዉ አምላክ በምድር እንደ እግዚአብሔር (እንደ ክርስቶስ) በሥጋ ሲገለጽና፤ የተለያዩ የዓመፃ፣ የክህደት፣ እንዲሁም የርኩሰት ተግባር ሲፈጽምና ሲያስፈጽም ለእዉነተኛ ምስክርነት እንደ እነሱ የበቁ ሰዎችን ያስነሳል፤ ቅዱሳንን ይመራቸዉ የነበረዉ መንፈስ ቅዱስ በመጨረሻዉ ዘመንም እዉነተኛ ምስክሮቹን እየመራ ፈቃዱን ያስፈጽማል:: እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ የበቁ ነፍሳት ስላሉት በተለያየ ዘመን ያስነሳል እንጂ ድርሻቸዉንና አገልግሎታቸዉን የጨረሱትን ዳግም መከራና ስቃይ እንዲቀበሉ አያደርግም::

እዚህ ላይ «እነ ኤልያስ፣ እነ ሄኖክ ይመጣሉ አይመጡም» የሚለዉ እዉቀት እንጂ ሃይማኖት እንዳልሆነ ለማሳወቅ እወዳለሁ:: የእግዚአብሔር እዉቀት ብቻ ነዉ ፍጹም እንጂ የሰዉ እዉቀት ዉሱንና የተገደበ ነዉ:: እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነዉ እዉቀት ሆነ ምስጢራት የሚገለጹት:: እነዚህ እዉቀቶች ሆኑ ምስጢራቶች እንደ መጀመሪያ መልእክት ተቀባዩና እንደ ትዉልዱ አቀባበል ደረጃ ነዉ እግዚአብሔር በዘመኑ የሚያጽፈዉና የሚገልጸዉ:: ይህን ለማለት የቻልኩት አንዳንድ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ መምህራን ሆኑ ሊቃዉንት ለእነሱ እዉቀታቸዉና ሊቅነታቸዉ ጣዖት ስለሚሆንባቸዉ ከእነሱ የተለየዉን ወይንም የማያዉቁትን እዉቀት እንደ ሃይማኖት ለዉጥ ወይንም እንደ ክህደት በመቁጠር የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም::

እኛ የቅዱስ ኪዳና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሆነ በሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የተደበቀ እዉነት አለ:: እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ደግሞ በእዉነተኛ አገልጋዮቹና ባለሟሎቹ አማካይነት ለትዉልዱ ይህ እዉነት እንዲገለጽ አድርጓል:: ይኸዉም በእኛ በኢትዮጵያ ዘንድ በቅዱሱ ኪዳናችን ሃይማኖት፣ ዘመን መለወጫችን መስከረም አንድ ነዉ:: ይህም ዘመነ ኩነኔ አልፎ ዘመነ ምሕረት የተጀመረበት በመሆኑ ነዉ:: ዘመነ ምሕረት የተጀመረዉ እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ ከሁለት ባሕርይ በአንድ ባሕርይ ከሁለት አካል በአንድ አካል ተገልጾ በተወለደ ጊዜ ነዉ:: ይህ ጊዜ ደግሞ አንድ ብለን የምሕረት ዘመን ስንቆጥርና ዓመተ ምሕረት ባልንበት መስከረም አንድ ነዉ:: ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያዉያን ይህን ምሕረት የታወጀበትን ዘመንና ቀን ወደፊት በመግፋት እንደ ፈረንጆቹ በታሕሳስ ወር መጨረሻ ላይ ነዉ የምናከብረዉ:: ታዲያ እግዚአብሔር ትዉልዱ ሊቀበለዉ በሚችልበት ዘመን ሙሉዉን እዉነታ ይገልጻልና ይኸዉ በአገልጋዮቹና በባለሟሎቹ አማካይነት ምሕረት የታወጀበት የጌታችን ልደት

መስከረም አንድ መሆኑን ቢገልጽም እስከ አሁን ድረስ በወንበር ላይ በተቀመጡ አባቶች ዘንድ ሆነ በመምህራንና በሊቃዉንት ዘንደ ተቀባይነትን አግኝቶ ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ነገር ግን ቅዱሱን ኪዳን በጠበቁ አገልጋዮችና ምእመናን እንዲሁም መምህራንና ሊቃዉንት ዘንድ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ለወደፊትም በኢትዮጵያ ትንሣኤ እዉነት ሙሉ በሙሉ በምትነግሥበት ጊዜ ደግሞ አስመሳይ አገልጋዮች ሆኑ አስመሳይ ምእመናን የእዉነት እንቅፋቶች በእግዚአብሔር ቁጣ በተለያየ መንገድ ከምድር ስለሚጸዱ ወደ እዉነተኛዉ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችን እምነትና ሥርዓት ስለምንመጣ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ሌላዉ ስለ ሙሉ እዉነት መዳፈን የማቀርበዉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአብርሃምና የኢትዮጵያዊዉ መልከ ጼዴቅ ዘርና የሦስቱ ነገዶች ማለትም የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዉሕድ ዘር መሆኗ እየታወቀ፤ አንድም ሰባኪ ሆነ መምህር እንዲሁም ሊቃዉንት ከአብርሃም ከዳዊት ዘር ብቻ እንደተገኘች አድርጎ ነዉ የሚያስተምረዉና የሚሰብከዉ እንጂ የሦስት ነገድ ዉሕድ ዘር ኢትዮጵያዊ መሆኗን የሚያስተምርና የሚሰብክ የለም፡፡ ይልቁኑ ይህ እዉነት በእግዚአብሔር አገልጋዮችና ባለሟሎች ሲነገረዉና ሲመሰከር የሚያሽሟጥጥና የሚቃወም ነዉ፡፡ ምክንያቱም ከጥንት ጀምሮ እንደ ማንነቱ ወይን እንደ ኢትዮጵያዊነቱ እንዲያድግና ማንነቱንም እንዲያዉቅ ስላልተደረገ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ራሱን አዋቂና ምሁር አድርጎ ስለሚቆጥርና እዉቀቱና አዋቂነቱ እንዲሁም ምሁርነቱ ጣዖት ስለሆነበት፤ የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነታ ሲቀርብለት ይተናነቀዋል፡፡ ማንነቱ ሲገለጥለት ደግሞ የባዕዳን አምላኪና ተከታይ ስለሆነ ራሱን ማዋረድና ማንነቱን መደበቅ እንዲሁም ሌላዉን ከፍ ከፍ በማድረግ የሌለዉን ሰብእና ይላበሰል፡፡ ይህ የሚያሳየን እኛ ኢትዮጵያዉያን በባዕዳን ሆነ በራሳችን ወገኖች በኢትዮጵያዉያን በተቀነባበረ መንገድና ሴራ ወደ ሙሉ እዉነት እንዳንደርስና እንደ ማንነታችን እንዳንኖር መደረጉን ነዉ፡፡ በመሆኑም አሁን ያለዉ ትዉልድ ወደ ማንነቱ መምጣትና እንደ ማንነቱ መኖር ይጠበቅበታል እንጂ እንክርዳድ በተደበላለቀበት ማንነትና ሕይወት መመላለስ የለበትም፡፡

የእኛ ኢትዮጵያዉያን ታሪክ የሚጀምረዉ ከአዳምና ሔዋን መፈጠርና ወደ እዚህች ምድር ካለመኖር ወደ መኖር ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ እንጂ አንዳንዶች እንደሚያስተምሩትና እንደሚናገሩት የዛሬ ሦስት ሺህ ዓመት አይደለም፡፡ የዛሬ ሦስት ሺህ ዓመት ገደማ የመልከጼዴቅ ዘር የሆነችዉ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ(አዜብ)(ሳባ) ከአብርሃም ዘር ከእስራኤላዊዉ ከዳዊት ልጅ ከሰለሞን ዘር ጋር ዉሕደት የፈጠረችበት ነዉ፡፡ በዚያን ወቅትም እርሷ ሆነች ሌሎች ኢትዮጵያዉያን እግዚአብሔርን ያመልኩ እንደነበረ የሚገልጽልን በመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ምዕራፍ10፣ ከቁጥር 23እስከ29 እንደተጻፈው፤ ንጉሥ ሰለሞን በባለጠግነትና በጥበብ ከምድር ነገሥታት ሁሉ በልጦ በነበረበት ዘመን የሳባም(የኢትዮጵያ) ንግሥት የነበረችዉ ማክዳ በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰለሞንን ዝና በሰማች ጊዜ ወደ እርሱ የመጣችዉና፡

*«ንጉሡንም አለቸው -ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝም አላመንሁም ነበር፣ ጥበብህና ስራህ ከሰማሁት ዝናህ ይበልጣል።*

*በፊትህ ሁል ጊዜ የሚቆም፣ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎችህ ምስጉኖች ናቸው። __አንተን የወደደ፣ በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሄር የተባረከ ይሁን፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘላለም ወድዶታልና ስለዚህ ጽድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሳህ__» መ.ነገስት ቀዳማዊ ምዕራፍ 10፣ ከቁጥር 1እስከ9 በማለት ነበር በሕገ ልቦና(በኪዳነ ልቦና) እግዚአብሔርን የምታመልክ እንደነበረች የሚገልጸዉን ምስክርነት የሰጠችዉ።*

*ታሪካችን፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተሰለፉትንና የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን እንደ ምስጥ ዉስጥ ዉስጡን ቦርቡረዉ ባዶ አድርገዉ ለማስቀረትና ለማጥፋት እንዲሁም ለመደምሰስ ቆርጠዉ እንደ ተዘጋጁት የዓመፃ ልጆች እንደሚሉት የመቶ ዓመት ታሪክ አይደለም። እንዲሁም «አዲሲቷ ኢትዮጵያ» እያሉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ እንደሚያላግጡት የዓመፃ ሰዎች ተከታዮች የሃያ ዓመት ታሪክ አይደለም።*

*እጅግ ብዙዉን የራሳችንን እንድናቃልልና እንድንንቅ የተደረገዉን ለጊዜዉ ማንሳቱን ልተወዉና አንዷን ብቻ ልጥቀስ። ለሥጋዊ ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚጠቅመን እዉቀት መማር ደረጃችን ሊለያይ ቢችልም፤ የመማርና የማወቅ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት የዉዴታ ግዴታ አለብን። በዚሁ መሰረት ከጎስቋላዉ ሕይወትና ኑሮ ለመለየትና ኑሮዋችንን ለማቅለል የምንጠቀምበትን እዉቀትና የተለያዩ የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን መማርና ማወቅ የሚያስፈልገን ሲሆን፤ ነገር ግን ወደ ክህደትና ወደ ዓመፃ የሚመራን ትምህርት ደግሞ አንዳች አያስፈልገንም። ነገር ግን እየታየዉ ያለዉ እግዚአብሔር በሚመለክባት አገርና እግዚአብሔር መፍራት ባላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሕዝቦች ዘንድ ግን በነፋስ ሥዕል (በቴሌቪዥን)፣ በነፋስ ድምፅ(በሬድዮ) እንዲሁም በተለያዩ ትምህርት ተቋማት አሁንም የቻርልስ ዳርዊኒ የክህደት ትምህርት የሆነዉ የዝግምተኛ ለዉጥ(የኢቮልሽን) ትምህርት እንደ ትክክለኛ ተቆጥሮ እየተሰጠ ይገኛል። እንዲሁም «ሚሊዮኖች እድሜ ያስቆጠረ አፅም ተገኘ» እየተባለ በአገር ዉስጥና በዉጭ ዓለም እየተጋነነ ይቀርባል። ይህም «መንግሥት» የተባለዉ የዓመፃ ቡድን የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ መሆንን በግልጽ ያሳያል።*

*እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገዉ ትዉልዱ የእዉነት ተቃራኒ በመሆነዉ በዉሽት(በፖለቲካ) ሕሊናዉ እንዲበከልና እንዲመረዝ በመደረጉ ይኸዉ ትዉልዱ የማርክዚስት፣ የሌኒዚስት፣ እንዲሁም የሌሎች የክህደት ፍልስፍና አስተሳሰብ እንዲይዝና ይህንንም የዓመፃ እምነት እንዲያራምድ በመደረጉ ትዉልዱ እንደማንነቱ እንዳይኖርና ሕሊናዉንም እንዲሸጥ ተደርጎ በእዉነተኛ ሕሊና በሚመላሰስ ሰዉ ዘንድ እጅግ የሚያሳፍርና የሚዘገንን ተግባርና ድርጊት እየተፈጸመ ይገኛል። ትዉልዱ ነዉሩን እንደ ታላቅነት፣ ክህደቱን እንደ አዋቂነት፣ ዓመፃዉን እንደ ጀብዱ፣ ርኩሰቱን እንደ መልካም ነገር፣ ጉስቁልናዉን እንደ ክብር ቆጥሮት ይመላለሳል፤ ይኖርበታል።*

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: *እጅግ በቅርቡ በሚመጣዉ በኢትዮጵያ ትንሣኤ በመልካሙ ዘመን በርእስ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) ማዕረግና በርእስ ሊቃና ካህናት(ፓትርያርክ) ማዕረግ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡት ምን ዓይነት ሰዎች ይሆናሉ ብለዉ ይገምታሉ?*

***<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>***: ስለ ተመረጡት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለማንነታቸዉና ስለምንነታቸዉ የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ነዉ፡፡ በአራቱም ማእዘን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ብቁ ሆነዉ ስላገኛቸዉ ነዉ የቀባቸዉ፡፡ በሰዉ መስፈርት ወይንም በቡድንና በድርጅት መስፈርት ያልታጩ ስለሆነ ስለ እነሱ እንዲህ ናቸዉ ብቻ መናገር አይቻልም፡፡ በእግዚአብሔር እዉነታ ግን ለእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ የሚመረጡ ሰዎች ቅን፣ እዉነተኛ፣ ለመልካም ተግባር የተሰለፉ፣ አእምሮ ጽኑአን የሆኑ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የማይመላለሱ፣ የማይፈሩ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚመላለሱ፣ እርሱ የሚያናግራቸዉን ብቻ የሚናገሩ፣ እርሱ የሚያሰራቸዉን ብቻ የሚሰሩ፣ እርሱ የሚፈርደዉን ብቻ የሚያጸኑ፣ እርሱ የሚያሳስበቸዉን ብቻ የሚያስቡ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆኑ ሰዎች ናቸዉ፡፡ ልክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን በሚመርጥት ሰዓት ናትናኤል «ከናዝሬት መልካም ነገር ይወጣልን?» እንዳለ በኢትዮጵያም ትንሣኤ ዘመንም እንዲሁ አገልጋዮች ካልተጠበቀ ቦታና ሕይወት እንዲሁም አገልግሎት ነዉ ለሥጋዊ ሆነ ለመንፈሳዊ ወንበር የሚታጩትና ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚሰለፉት፡፡ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር ምርጫና ዉሳኔ ስለሆነ ማንም ይህን ሊያስቀር አይደለም አንድ ቀን ማዘግየት አይችልም፡፡ የንስሐ እድሜ እግዚአብሔር ይስጠን እንጂ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ሁሉ ተፈጽሞ የምንመለከተዉ ስለሆነ በትዕግስትና በጽናት ያንችን ወራት መጠበቅ ነዉ የሚጠበቅብን፡፡

እዚህ ላይ ሌላ ለመግለጽ የምፈልገዉ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ በርእስ ነገሥትና በርእሰ ሊቃነ ካህናት ማዕረግ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡት አባቶች ምን እንደሚሆኑ እያወቁ፣ ያላቸዉን ሥልጣንና ክብር እየተረዱ፣ ራሳቸዉን ግን «ኃጢአተኛ ነኝ፣ ለምንም ነገር የማልጠቅም ነኝ፣ ወራዳ ነኝ፣ አባራ ነኝ፣ በኃጢአት የጨቀየሁ ነኝ፣ ተራ ነኝ … ወዘተ» እያሉ ነዉ በእግዚአብሔር መልእክታት ላይ ራሳቸዉን ያስተዋወቁት፡፡ ይህ የሚያሳየኝ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉና አዋርደዉ አምላካቸዉን ለማግነንና ለማስገነን የተዘጋጁ፣ የተመለኩትን ሥልጣንና ክብር ከንቱ ለማድረግ ቆርጠዉ የተነሱ መሆኑን ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ እግዚአብሔር የጽድቅ ተግባራቸዉንና ነፍሳችቸዉን ብቃት ደረጃ ላይ ስላደረሱ መርጧቸዉና ቀብቷቸዉ ወደዚያ ወንበር ላይ የሚያመጣቸዉ፡፡ እነሱ ምንም እንኳ «የማንጠቅም፣ ኃጢአተኛ፣ ተራ ሰዎች ነን» ቢሉም እግዚአብሔር ደግሞ «እናንተ ምርጦቼ አገልጋይ» ብሎ ነዉ የመረጣቸዉና በእርሱ ሰንድ ሞገስን አግኝተዉ ባለሟሉና እዉነተኛ እንደራሴዉ ያደረጋቸዉ፡፡

***<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>***: *በአሁን ሰዓት በኦርቶዶክር ተዋሕዶ ሃይማኖት አገልጋዮችና ተከታዮች ዘንድ ሆነ በሌሎች ዘንድ «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል» ስለሚባለዉ የተለያየ ነገር ይነገራል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «እኔ ነኝ ቴዎድሮስ» እስከማለት የደረሱ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «በኢትዮጵያ በምንም መልኩ የዘዉድ ሥርዓት አይመለሰም፤ በአብዮታዉያንና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዳግም*

እንዳይታሰብና እንዳያነሰራራ አከርካሪዉ ተመቷል... ወዘተ» የሚሉ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ «እስላም ይነግሣል» የሚሉ አሉ፡፡ ሰሞኑን ደግሞ «ነቢዩ አልያስ ከሰማይ ወርዷል» በማለት የሚናገሩ ሰዎች ሰምቻለሁ፡፡ ባጠቃላይ የተደበላለቀ ነገር ነዉ የሚነገረዉና የሚደመጠዉ፣ የሚነበበዉ፡፡ ለዚህ ያሎትን አስተያየትና ምክር ቢሰጡን፡?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**፡ ዲያብሎስ ከባለጊዜነቱ የሚሻርበት ሰዓት ሰለደረሰ በአዳምና ሔዋን ዘሮች ነፍስ ላይ ለመጫወት የማያደርገዉና የማይጥረዉ ጥረት የለም፡፡ ለዚህም ነዉ የተደበላለቀ አስተሳሰብና ንግግር እንዲኖር እያደረገ ሕዝቡንና አማኙን እየከፋፈለ ያለዉ፡፡ ያ ብቻ አይደለም ከእግዚአብሔር ቁጣ በኋላ የኢትዮጵያ ትንሣኤ እንደሚመጣና እንዲሁም ከእግዚአብሔር የሆኑትን መልእክት በደንብ ለይቶ ስለሚያዉቅ፤ የብርሃን መልአክ መስሎ ጭምር አማኙን ለማታለልና ለማደናገር እንዲሁም ለመከፋፈልና ለመጣል የመጨረሻዉን የሞት ሽረት ጦርነት እያደረገ መሆኑን ሁሉም ሰዉ ሊያዉቅና ሊያስተዉል ይገባል፡፡ በዚህን ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን «**<u>ብዙ ሐሰተኞች ነብያት ይነሳሉ ብዙዎችንም ያስታሉ</u>** ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡ **<u>እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል</u>**፡፡» ማቴ.24÷11እስከ13 ባለን መሰረት በእምነታችንና በሥርዓታችን ጸንተን መገኘት ነዉ ከእኛ የሚጠበቀዉ፡፡

በአሁን ሰዓት ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትና ሥርዓት መመላለስ፤ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት መገኘት ብቻ ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ ማንም ሰዉ የማንም ግለሰብ ሆነ ቡድን ተከታይ መሆን የለበትም፡፡ ዲያብሎስ እንደ ትዉልዱ ስለተራቀቀ እንደ እያንዳንዱ ሕይወትና አመለካከት እንዲሁም አስተሳሰብ ነዉ የሚቀርበዉና የሚፈትነዉ፡፡ እንኳን በዓለም ያለነዉን አይደለም በገዳምና በዋሻ የዘጉትን ሳይቀር ይፈትናል፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚወጣ የሚገባ ሰዉ ካለ ደግሞ ያሰናክለዋል፡፡ በመሆኑም መስተካከል ያለባቸዉ ነገሮችና አመለካከቶች ቢኖሩ እንኳ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን በእግዚአብሔር ተመርጠዉና ተቀብተዉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ በሚቀመጡት እንደራሴዎች አማካይነት ስለሚስተካከል፤ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ተመርተዉ «ይህ ስህተት ነዉ፣ ይህ እንዲህ ይደረግ፣ ያለበለዚያ ዓመፃ ነዉ.... ወዘተ» እያሉ አገልጋዩንና አማኙት የሚከፋፍሉና የሚለያዩትን ልንሰማና ልንከተል አይገባም፡፡ እያንዳንዱ ራሱን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅቶ በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ ከተወሰነ፤ ሰማይና ምድር ቢደበላለቁ አንዳች የሚሆነዉ ነገር የለም፡፡ ቢሞትም ወደ አምላኩ እቅፍ ነዉ የሚሄደዉ እንጂ አንዳች የሚቀርበት መልካምና የሚያጓጓ ነገር የለም፡፡ እግዚአብሔር ከፈቀደለት ደግሞ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ይደርሳል፡፡

ሌላዉ በአገልጋዮችና በአማኞች ዘንድ ያከፋፈለና ያለያየ ነገር ካለ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ወደ ወንበር ሲመጡ ያኔ ለሁሉ መፍትሔ ይገኝለታል፡፡ እኔም ሆንኩ ሌላ፣ ማንም ይሁን ማን፣ ለምን «ከሰማያዉያን መላእክት ጋር በሰማያት ዉስጥ የማመስገን ብቃት ደረጃ ላይ የደረስኩ ሰዉ ነኝ» አይልም፤ ከእዉነተኞቹ ከእግዚአብሔርን ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

እንደራሴዎችና ባለሟሎች በላይ ሊወስን ሆነ ሊፈርድ አይችልም፡፡ የሁለቱ ዉሳኔና ፍርድ የእግዚአብሔር ዉሳኔና ፍርድ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በምድር ካሉ ሁሉ አልቆ መርጧቸዋልና፤ ቀብቷቸዋልና፡፡ ከእነዚህ እንደራሴዎችና ባለሟሎች ፍርድና ዉሳኔ የሚያፈነግጥና እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ «ይህ ትክክል አይደልም፣ በዚህ ይለወጥ፣ ይተካ» ቢል ማንም ሰዉ ሊሰማዉና ሊቀበለዉ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ያለዉ አምላክ አንድ ነዉና ከእርሱ የሆነ ደግሞ አይከፋፈልም፣ አይለያይም፣ ወደ አንድነት ነዉ የሚመጣዉ፡፡ ባጠቃላይ በአሁን ሰዓት እያንዳንዱ ሰዉ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ በመገኘት በእምነቱና በሥርዓቱ ጸንቶ መገኘት ነዉ የሚጠበቅበት፡፡

ሌላዉ መታወቅ ያለበት እጅግ እጅግ በቅርቡ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚጠብቀን መልካም ነገር ሳይሆን ጥፋትና መደምሰስ ነዉ፡፡ ይኸዉም እያንዳንዱ መንግሥት፣ ድርጅት፣ ቡድን፣ ግለሰብ ስለ ዓመፃዉ፣ ስለ ክህደቱ፣ ስለ ርኩሰቱ ዋጋ የሚከፍልበትና የሚቀጣበት ነዉ፡፡ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ የዓለም ሕዝብ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ሲሰጡና በእዉነተኛ ንስሐ ሲመለሱ ነዉ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚበርደዉና መልካሙ ዘመን የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚመጣዉ፡፡ የቅጣቱና የጥፋቱ ዘመን እንደ መመለሳችን ፍጥነት ሊረዝምም ሊያጥርም ይችላል፡፡ ቶሎ እጃችንን ከሰጠንና እግዚአብሔር የተናገረዉን ተግባራዊ ካደረግን የቁጣዉ ወራት ያጥርልናል፡፡ በዓመፃችንና በትዕቢታችን ከጸናና ደግሞ ከምድር ተጠርገን እስከምናልቅ ድረስ የቁጣዉ ወራት ይረዝማል፡፡ ማሳጠሩም ማስረዘሙም የእኛ የአዳም ዘር ነጻ ምርጫና ዉሳኔ ነዉ፡፡ የነነዌ ሰዎች በሦስት ቀን ዉስጥ ባሳዩት እዉነተኛ ንስሐ የእግዚአብሔርን ቁጣን ማራቅ ችለዋል፡፡ በኖኅ ዘመን የነበሩ በትዕቢትና በዓመፃ የጸኑት ሰዎች ለአርባ ቀን በንፍር ዉኃ ተቀቅለዋል ከምድር እነሱም መታሰቢያቸዉም ለዘላለም ሊጠፉ ችሏል፡፡

ሌላዉ ደግሞ «እኔ ነኝ ቴዎድሮስ» እያሉ ተከታይ የሚያፈሩትን አስመሳዮች አትስሟቸዉ፤ አትከተሏቸዉ፡፡ እንዲሁም «የተለየ ተአምርና ምልክት አሳያለሁና ተከተሉኝ» የሚሉ ካሉም አትስሟቸዉ፤ አትከተሏቸዉ፡፡ በሃይማኖታችሁና በቤተክርስቲያናችሁ ብቻ ጸንታችሁ ተገኙ፡፡ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የሚቀመጡት እንደራሴዎች ርእሰ ነገሥቱ(ሣልሳዊ ቴዎድሮስ)ና ካህኑ እጨጌ(ፓትርያርኩ) የታወቁና፤ እግዚአብሔር ዉጡ ሲላቸዉ ብቻ የሚወጡ ናቸዉ፡፡ «ቴዎድሮስ» ተብለዉ የሚጠበቁት «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ በተከታታይ አምስት መልእክት ያስተላለፉት ናቸዉ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ እሳቸዉም እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸዉ ቦታ ሆነዉ ሁሉን እየተከታተሉና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ርእሰ ሊቃና ካህናት (ፓትርያርክ) የሚሆኑትም እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸዉ ቦታ ሆነዉ ሁሉን እየተከታተሉና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ «እገሌ ነዉ ቴዎድሮስ፣ እገሌ ነዉ ፓትርያርክ... ወዘተ» በሚለዉ ወሬ ሳንደናገርና ሳንታለል የኢትዮጵያን ቀን በተስፋና በጽናተ መጠባበቅ ይኖርብናል፡፡

ሌላዉ ማወቅ ያለብ ቅዱሳን መላእክት ሆኑ ቅዱሳን ጻድቃን ሊራዱን ወደ እዚህች ምድር ይመጣሉ እንጂ በሥጋ ተገልጸዉ ሥጋዊ አናኗር ሆነ ተግባር አይፈጽሙም፡፡ እግዚአብሔር ካዘዛቸዉና ከፈቀደላቸዉ ካሉበት ቦታ በዓይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ መተዉ ሊረዱን፣ ሊያጽናኑን

ይችላሉ:: ልክ አናንያ፣ አዛሪያ፣ ሚሳኤልን ቅዱስ ገብርኤል በሰዉ አምሳል ተገልጾ ከነደ እሳቱ እንዳዳናቸዉ፤ የእግዚአብሔር መልአክ የሰናክሬም ሠራዊት 185000(አንድ ሞቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ) ሠራዊት በቅጽበት ዉስጥ እንዳልነበሩ እንዳደረገ፤ እንዲሁም በታሪክና በትዉፊት እንደሚነገረዉ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤ ጣሊያን ኢትዮጵያን ልትወር በመጣች ጊዜ የቅዱሱን ኪዳን ሕዝብ ለመርዳት በጦርነቱ ቦታ ላይ ተገልጦ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር በመሆን የጣሊያንን ወታደሮችን እንዳልነበሩ እንዳደረጋቸዉ ሁሉ፤ በአሁን ዘመንም በተለያየ መልኩ ተገልጸዉ ሊራዱን ይችላሉ እንጂ ቅዱሳን መላእክት ሆኑ የቀደሙት ነቢያት ሆኑ ሐዋርያት፣ እንዲሁም ሰማዕታትና ጻድቃን በሥጋ ተገልጸዉ በዚህች ምድር ዉስጥ አይኖሩም::

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 7 ከቁጥር 13እስከ 27 የተጻፈዉን ራሱ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ የተናረዉን አቀርባለሁ::

«<u>በጠበበዉ ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደዉ ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ናዉና</u>፣ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸዉ ወደ ሕይወት የሚወስደዉ ደጅ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነዉና፣ <u>የሚያገኙትም ጥቂት ናቸዉ::</u>

<u>የበግ ለምድ ለብሰዉ ከሚመጡባችሁ በዉሥጣቸዉ ግን ነጣቂ ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ:: ከፍሬያቸዉ ታዉቋቸዋላችሁ</u>:: ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል:: መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት ወይን ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለዉም:: <u>መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቍረጣል ወደ እሳትም ይጣላል:: ስለዚህ ከፍሬያቸዉ ታዉቋቸዋለችሁ</u>::

በሰማያት ያለዉን የአባቴን ፈቃድ ያሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም:: <u>በዚያን ቀን ብዙዎች: - ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገረንምን፣ በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል:: የዚያን ጊዜም :- ከቶ አላዉቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ</u>:: » ይላል

ከላይ ከእግዚአብሔር ቃል የምንረዳዉ የሕይወት መንገድ ጠባብ መሆኗንና የሚኖሩባትም ጥቂቶች እንደሆኑ፤ ሐሰተኛ መምህራንና ነቢያትን ከፍሬያቸዉ ማወቅ እንደምንችል፤ እንዲሁም አንድ ሰዉ እንኳን በመመስከሩና በማስተማሩ ብቻ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ ይቅርና ማንም ሰዉ ሊሰራ የማይችለዉን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ትንቢት በመናገሩ፣ አጋንንትን በማዉጣቱ፣ የተለያየ ተአምራት በማድረጉ ብቻ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ እንደማይችል ነዉ:: ምክንያቱም እስከመጨረሻ ድረስ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ የማይገኝ ሰዉና ዉስጡ ትዕቢትና ዓመፃ የሞላዉ ሰዉ በምንም መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ እንደማይችል ነዉ::» **በማለት የዲያብሎስና የሐሰተኛ ነብያት ተቃዋሚ የሆኑት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ክፍል ስምንት

### ምዕራፍ አንድ

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**፤ አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን ያልሆኑ የዉጭ ዜጎች በተለይ ጃማይካዉያን «ኢትዮጵያዉያን ነን» ከሚሉት በላይ የኢትዮጵያ ፍቅር ያላቸዉና ኢትዮጵያን «ቅድስት አገራችን» እያሉ ጭምር ነዉ የሚጠሩት፡፡ የስም ኢትዮጵያዊዉ ደግሞ በስዉር ዓላማ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ ተሰልፏል፡፡ እንዴት በኢትዮጵያ ያልተወለደዉ በኢትዮጵያዊነት ፍቅር ሊነድ ቻለ? በተቃራኒ ደግመ በኢትዮጵያ ዉስጥ የተወለደዉ «ከፈለኩ በኢትዮጵያዊነቴ አምኜ እንደ ኢትዮጵያዊነት ዜግነት እኖራለሁ፤ ካልፈለኩ ደግሞ ፦ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ በሚለዉ ታላቁ ሕገ መንግሥት ተጠቅሜ የራሴን ነጻ መንግሥት በመመስረት የጎጤን(የብሔሬን) ዜግነት ይዤ እኖራለሁ» በማለት ከአንገት በላይ በሆነ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ለመኖር በቃ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**፤ ኢትዮጵያዊዉ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያዊነት ስሜት የሚኖርና ለአገሩ ነጻነትና ክብር ማንኛዉንም መስዋዕትነት የሚከፍል ነበር፡፡ ይሁንና ከዚሁ ኢትዮጵያዊነት ሰዉነት የተገኘዉ የአሁን ትዉልድ ደግሞ ከ20 ዓመት ወዲያ ሕወሓት(ኢሕአዴግ) በተባለዉ ቡድን ሕሊናዉ በጥላቻና በበቀል እንዲበከል በመደረጉና ሆዱ አምላኩ እንዲሆን ስላደረጉት እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ በመመራቱ ምክንያት ነዉ እንደዚህ አሁን እንደሚታየዉ አሳፋሪ አቋምና አስተሳሰብ የያዘዉ፡፡ የእርሱ ሆድ ካልሞላ፣ ጥቅም ካለገኘበት፣ ኢትዮጵያ ብትበታተን አንዳች ስሜት የለዉም፡፡ ሥልጣንና የተለየ ጥቅም ካገኘ ደግሞ ኢትዮጵያ በሚለዉ ስም እየተጠራ የራሱን ስዉር ዓላማ ለማስካት ይተጋል፡፡ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈልገዉ ከግሉ ጥቅም አንጻር ነዉ እንጂ ለእርሱ ኢትዮጵያዊነት ሆነ ሰንደቅ ዓለማ ምንም ያልሆነና ጨርቅ ነዉ፡፡ ታዲያ እንደዚህ አስተሳሰብ ካለዉ መሪ ሆነ ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬ እንኳን ቅድስት አገር ብሎ መጥራት አይደለም «የብሔር ብሔረሰቦች መጨቆኛ አገር» ተብሏ የተፈረጀችና በሂደት ተከፋፍላና ተዳካማ የምትከስምበት ሕገ መንግሥት ነዉ በዳንኪራና በጭፈራ የጸደቀዉ፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** «ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞች ፊተኞች» ይሆናሉ እንደተባለዉ፤ ከማንም በላይ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሊቆረቆሩና ጥብቅና ሊቆሙ ከዛም ባለፈ ራሳቸዉን መስዋዕት ማድረግ ሲጠበቅባቸዉ «የእሳት ልጅ አመድ» እንደሚባለዉ ወያኔ(ሕወሓት)ና ሻዕቢያ በመባል የሚታወቁ ሁለት የዓመፃ ቡድኖች ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት በመነሳታቸዉ ኋለኞች ሆነዉ መቅረት ብቻ አይደለም በራሳቸዉ ላይም ጥፋት የሚያመጡ ናቸዉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ፤ ወደ ራሳቸዉ ማንነት ወደ ኢትዮጵያዊነታቸዉ የመለሳቸዉ በዉጭ ያሉ ወገኖቻችን ደግሞ ከኋለኛነት ወደ ፊተኛነት እየመጡ መሆኑን ነዉ የሚያሳየን፡፡ አሁንም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያላገጡ የዘመኑ ባለ ጊዜ ሰዎች መጨረሻቸዉ ኋለኛ መሆን ነዉ፡፡ በተቃራኒዉ በኢትዮጵያና

በኢትዮጵያዊነታቸዉ ያመኑትና ስለ እናት አገራቸዉ ጥብቅና የቆሙ ደግሞ ከማንም በላይ ፈተኞች ይሆናሉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ እዚህ ላይ አንድ የሚታይ የተሳሳተ አመለካከትና እምነት እንዳለ ይታወቃል:: ይኸዉም የተወሰኑ ጃማይካዉያን አጼ ኃይለ ሥላሴን እንደ አምላክ የሚቆጥሩና አምልኮት የሚፈጽሙ አሉ:: ይህን በምን መልኩ ነዉ የሚመለከቱት?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ ማንም እንደሚያዉቀዉ አጼ ኃይለ ሥላሴ፤ እንደማንኛዉ ሰዉ ከወላጅ አባትና እናታቸዉ የተወለዱ፣ በተለያየ ሕይወት ዉስጥ የኖሩ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በመሆን የመሩ፣ በመጨረሻም በደርግ የተገደሉና እንደ ማንኛዉ ሰዉ በሥጋቸዉ የሞቱና በነፍሳቸዉ ደግም እንደ ማንኛውም ሰዉ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸዉ ቦታ የሄዱ ናቸዉ:: እምነታቸዉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የነበረ፣ በእምነቱ ዉስጥ እዉነተኛዉ ፈጣሪና አምላክ የሆነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ  ብቻ መሆኑ የታወቀ ነዉ:: ከዚህ አንጻር እንኳን መጨረሻቸዉ ምን እንደሆነ በእርግጠኛነት የማናዉቀዉን አጼ ኃይለ ሥላሴን ይቅርና ከእግዚአብሔር ቅድስን ማዕረግ የተሰጣቸዉና በእግዚአብሔር ዘንድ ክብርና ሞገስ ያገኙት ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን እንኳ እንደ ፍጡረነታቸዉ  የሚገባቸዉን ክብርና ምስጋና ነዉ የምናቀርበዉ እንጂ እንደ አምላክ የሚታዩበትና የሚመለኩበት መንገድ የለም::

አጼ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ እስከ አሁን ድረስ ከእግዚአብሔ የቅድስና ማዕረግ ተሰቷቸዉ እንደ ቅዱሳን፣ ጻድቃን በተለየ ሁኔታ እንዲታሰቡ አልተደረገም:: በዚህም ምክንያት እንደ አገር መሪነታቸዉና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደዋሉት ዉለታ ቤተክርስቲያን ታስባቸዋለች እንጂ እንኳን ከአምላክ ጋር ማስተካከል ቀርቶ እንደ ቅዱሳንና ጻድቃን አትመለከታቸዉም:: ነገር ግን ከደርግ መንግሥት ሆነ ከኢሕአዴግ መንግሥት በላይ በመቶ እጥፍ ለቅድስት ቤተክርስቲያንና ለተዋሕዶ ሃይማኖት አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ለአገራቸዉም በሚችሉት አቅም ሰርተዉ አልፈዋል:: በሦስቱም ሥርዓት ማለትም በአጼ ኃይለ ሥላሴ፣ በኮሎኔል መንግሥቱ፣ በአቶ መለስ ዘመን፤  ቅንነትና እዉነተኛነት የተሞላዉ፣ አድሎና በደል የሌለበት፣ ፍትሐዊ ሀብት ክፍፍል በአግባቡ አልተከናወነም:: በሦስቱም ሥርዓት ደረጃዉ ቢለያይም ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ነግሷል:: ሰዉ በተማረና ባወቀ መጠን ቅንነትና እዉነተኛነት እንዲሁም ታማኝነትና ትጋት እየተለባሰ ስራዉን ማከናዉን ሲጠበቅበት በተቃራኒዉ በብልጠት የተሞላ የበቀል፣ የክፋት፣ የተንኮል፣ የስርቆት፣ የግፍ፣ የጭከና፣ የአድሎ፣ የበደል ተግባር ሲፈጸም ነዉ የታየዉና የሚታየዉ:: ከዚህ አንጻር አሁን ያለዉ የሕወሓት(የኢሕአዴግ) መንግሥት ያለፉትን መንግሥታት የመዉቀስ ክብረ ሕሊና(ሞራል) የለዉም:: ምክንያቱም በብልጠት የግፍ፣ የአድሎ፣ የበደል፣ የበቀል፣ የስርቆት፣ የማታላል፣ የማስመሰል ... ተግባር እየፈጸመ ነዉና:: የደርግ(ኢሠፓ) መንግሥት ያለፉትን መንግሥታት የመዉቀስ ክብረ ሕሊና(ሞራል) የለዉም:: ምክንያቱም ዓይን ያወጣ ግፍ፣ በደል፣ አድሎ፣ ስርቆት፣ ማታለል፣ ማስመስል ... ወዘተ ተግባር ፈጽሟልና::

በሦስቱም መንግሥታት ደረጃቸዉ ቢለያይም እያንዳንዳቸዉ የራሳቸዉ ደካማና ጠንካራ ጎን ነበራቸዉ:: በግላቸዉ ሆነ እንደ መሪ የፈጸሙት ስህተትና በደልም አለ:: አጼ ኃይለ ሥላሴ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ ይገኙ አይገኙ፣ እዉነተኛ ንስሐ ይግቡ አይግቡ እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚያምኑ ነበር:: ኮሎኔል መንግሥቱ በግልጽ እግዚአብሔር የለሽ የሶሻሊስት እምነት ተከታይ ናቸዉ:: መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆም እግዚአብሔር ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ:: ምናልባት በኢትዮጵያዊነታቸዉ ስለሚያምኑ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ እዉነትን ይቀበሉ አይቀበሉ፣ በእዉነት ይኑሩ አይኑሩ እግዚአብሔር የሚያዉቀዉና ወደፊት የሚታይ ነዉ:: አቶ መለስ እንደ ኮሎኔል መንግሥቱ ዘመናዊዉን እግዚአብሔር የለሽ እምነት የሆነዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲም ነዉ የሚከተሉት:: ያም ብቻ አይደለም ዋና መስራችና ብዙ ደቀመዛሙርትን ያፈሩ ናቸዉ:: መጨረሻቸዉም በዓመፃና በክህደት ሕይወት ላይ እንዳሉ ነዉ የተለያየ ማስጠንቀቂያ ቢደርሳቸዉም የእግዚአብሔርን ጥሪ ባለመቀበልና በዓመፃቸዉ በመጽናታቸዉ ምክንያት ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ በእግዚአብሔር ቁጣ የተጠሩት::

**ወደ ጥየቄዉ ምላሽ** ስገባ የተወሰኑ ጃማይካዉያን አጼ ኃይለሥላሴን እንደ አምላክ የቆጠሩት ባለማወቅና የሰዉ ዘሮች ዋና ጠላት የሆነዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ ፍቅር ስላላቸዉ የሕይወትን መንገድ እንዳይኖሩበት ለማድረግና እዉነትን ተቀብለዉ በእዉነት እንዳይኖሩ ያመጣባቸዉ ፈተና ነዉ:: ታዲያ እዉነተኛ እረኛና መስካሪ ካገኙ ወደ እዉነተኛ እምነታቸዉ ወደ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ሊመጡና፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ የሚያምኑትና ያመልኩት የነበረዉን እዉነተኛና ብቸኛ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያምኑና ሊያመልኩ እንደሚችሉ ይገመታል:: እግዚአብሔርም አለማወቃቸዉን ተመልክቶ ወደ እዉነት እንደሚመራቸዉ ተስፋ እናደርጋለን:: ምክንያቱም ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነት የተቀበሉ በመሆኑና የኢትዮጵያዊነት ፍቅር ያላቸዉ ስለሆነ ሙሉ እዉነትን ለመቀበልና ለመኖር እንደማይቸገሩ ይታወቃል::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፤ ከቀርብ ዘመን ጀምረዉ ስለነበሩት የኢትዮጵያ መሪዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ስለፈጸሙትና ስላስፈጸሙት የዓመፃ፣ የክህደተ፣ የርኩሰት ተግባር ቢገልጹልን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፤ ከአጼ ዳግማዊ ቴዎድሮስ እስከ አቶ መለስ ያነበሩትን በተወሰነ ደረጃ እገልጻለሁ:: ማንኛዉ መሪ የራሱ ጠንካራና ደካም እንዲሁም የተለየ ተሰጦኦ እንዳለዉ ይታወቃል:: እያንዳንዱም ሰዉ እንደመሆኑ ደረጃዉ ቢለያይም ስህተትና በደል ሊፈጽም ይችላል:: እያንዳንዱ ደረጃዉ ቢለያይም ቀንነትና መልካምነት አለዉ:: አንዳችን ቅንነትና መልካምነት የሌላቸዉ ዲያብሎስና ሰይጣናት ብቻ ናቸዉ:: የሰዉ ዘሮች ከ20 እስከ 99 ፐርሰንት ያህል ቅንነትና መልካምነት አላቸዉ:: የአስቆርቱ ይሁዳ ሳይቀር እጅግ እጅግ ዝቅተኛ ቢሆንም የተወሰነና የተገደበ ቅንነትና መልካምነት ነበረዉ:: ነገር ግን ያንን የተወሰነና የተገደበ ቅንነትና መልካምነት ለዓመፃና ለክህደት ተግባር ነዉ የተጠቀመበት እንጂ ለእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም:: በዚህም ምክንያት ራሱን ከሰይጣናት ደረጃ ሊመድብ ችሏል:: እንኳን ዝቅተኛ ነጥብ የሆነዉን 20 ነጥብ የያዘ አይደለም

እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ የሚጠብቀዉን ዝቅተኛ ነጥብ 60 ነጥብ እንኳ የያዘ ሰዉ፤ ቅንነቱንና መልካምነቱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ካላዋለና ለሥጋና ደም ስሜቱ በማድላት ለዓመፃና ለክህደት እንዲሁም ለርኩሰት ተግባር ካዋለዉ፤ ራሱን ወደ ርኩሳን መናፍስትነት(ሰይጣንነት) ደረጃ ለዉጧልና፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚታየዉ እንደ ዓመፀኞቹና ከሃዲዎቹ ሰይጣናት ነዉ:: በዚህም ምክንያት የሚጠብቀዉ ቅጣትም እነሱ የሚጠብቃቸዉን ነዉ::

ይህን ያነሳሁበት ምክንያት እያንዳንዳቸዉ ማለትም አጼ ኃይለ ሥላሴ ሆኑ በኮሎኔል መንግሥቱ እንዲሁም አቶ መለስ፤ በዘመናቸዉ ደረጃዉ ቢለያይም ለአገራቸዉ እንደ አቅማቸዉ ሰርተዉ አልፈዋል:: በየግል ሕይወታቸዉ እግዚአብሔር የማይወደዉን ተግባር ፈጽመዉ ሊሆን ይችላል:: እኔ አሁን የምገልጽላችሁ «አገሌ ይህን በደልና ስህተት ፈጽሟል፤ ይህን ጥሩና መጥፎ ስራ ሰርቷል» የሚለዉን አይደለም:: ይህ የእያንዳንዱ መዋዕለ ዜና በእዉነተኛ አምላክ ሲመረመር የሚታወቅ ይሆናል:: እኔ የምገልጸዉ በቀረበልኝ ጥያቄ መሰረት በኢትዮጵያና በኢትዮያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ለተፈጸመዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እንደ አጠቃላይ ነዉ:: አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት አልፈጸሙም:: አጼ ኃይለ ሥላሴ ምንም እንኳን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ባይፈጽሙም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ በተወሰነ ደረጃ ዓመፃ ፈጽመዋል፤ አስፈጽመዋል:: ኮሎኔል መንግሥት በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ፈጽመዋል አስፈጽመዋል:: አቶ መለስ ዜናዉ ደግሞ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ፈጽመዋል፤ አስፈጽመዋል::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ በአሁን ሰዓት በየመንገዱ፣ በየቢሮዉ፣ በየሱቁ፣ በየካፍቴሪያዉ፣ በየመስሪያ ቤቱ፣ በየቢሮዉ፣ በየሆቴሉ፣ በየመኪናዉ፣ በየልብሱ፣ በየማስታወቂዉ ቦርድ፣ በየቴቨዥኑ፣ ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ... ወዘተ ባጠቃላይ በሁሉም ቦታ ማለት በሚያስችል ደረጃ የአቶ መለስ ዜናዊ ምስል በብርሃናዊ ሥዕል(በፎቶግራፍ)፣ በባነር፣ በቢልቦርድ በተለያየ መልኩ ይገኛል:: ይህ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ታላቅነታቸዉን ይመሰክራል ወይ? ሕዝቡ መዉደዱን የሚገልጽበት መንገድ ነዉ ወይ? በሕይወተ ሥጋ እያሉ ይህ ልምድ ነበር ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ የሰዉ ታላቅነቱን የሚመሰክረዉ ስራዉና እዉነተኛነቱ ነዉ እንጂ ምስሉ በየቦታዉ ስልተለጠፈና የተለያዩ መታሰቢያ ስያሚ በስሙ ስለተሰጠዉ አይደለም:: በዚህ መሰረት ይህ በየቦታዉ የሚታየዉ ፎቶግራፋቸዉ ታላቅነታቸዉንና በሕዝብ መወደዳቸዉን የሚገልጽ አይደለም:: ያለፈዉ ሥርዓት መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥት በመሪነት ደረጃ ላይ እያሉ እንደ አቶ መለስ በሥጋ ሞት ወደ ሁለተኛዉ ዓለም ቢጠሩ ኖሮ አሁን ከምናየዉ በላይ ምስላቸዉን በየቦታዉ እናይ ነበር:: ይህም የሚያሳየን ባለጊዜ የሆኑ ሰዎች የሞተዉ ሰዉ የፈለገዉን ተግባር ፈጽሞ ቢሞት፤ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ለፓለቲካ ድጋፍና ለራሳቸዉ የግል ጥቅም ብቻ አስበዉ ያንን ሰዉ ያስገንናሉ፣ ያስመሰግናሉ፣ ያስመልካሉ እንጂ፤ ያ ሰዉ

እዉነተኛ ሰዉ ሆኖና ታላቅ ስራ ሰርቶ በመሄዱ እግዚአብሔር እንደ ቅዱሳን እዉቅና የሰጠዉ አይደለም:: ይልቁና ከእርሱ ፈቃድ ዉጭ ተመላልሶ የሄድ ሰዉ ምን ያህል በሕዝብ ቢወደድ እንኳ ስለ ዓመፀኛነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላና መታሰበዉም ለዘላለም የሚጠፋ ነዉ::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ** አቶ መለስ ዜናዊ «ለዚህች አገር ታላቅ ስራ ስርተዋል» ተብሎ ቢታመን እንኳ መታሰቢያ የሚሆን አንድ ተቋም ወይንም አገልግሎት የሚሰጥ በስማቸዉ ሊሰየምና ለማስታወሻነት ፎቶዋቸዉ አግባብነት ባለዉ መልኩ ሊታይ ይገባል እንጂ፤ አሁን ባለሥልጣናቱና ካድሬዎች እንዲሁም ደጋፊዎቻዉ እያደረጉት ያለዉ እሳቸዉን እንደ አምላክ(አማልክት)(ጣዖት) እያስመለኩና ርኩሰትን እያስፈጸሙ ነዉ:: ይህም በግልጽ ዲያብሎስ በብልጠት የሰዎች ሕሊና በሚቀበለዉ መልኩ «እምነት አለኝ» በሚለዉ ሆነ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት በሚያምነዉ ሰዉ እየተመለከ መሆኑን ነዉ:: ይህ ዉጤት ደግሞ አቶ መለስ በሕይወት ሥጋ እያሉ ያፈሩትን ፍሬ ነዉ የሚያሳየን:: ይኸዉም ሰዉን አምላኪና አግናኝ ትዉልድ ፈጥረዉ እንደሄዱ ነዉ የሚያሳየዉ:: ምንም እንኳ በሕይወተ ሥጋ እያሉ እንደ ዶክተር አባ ጳዉሎስ በየቦታዉ ፎቶግራፋቸዉንና ሐዉልታቸዉን አስቁመዉ ራሳቸዉን ባያስመልኩም፤ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በተለይ የሚቀናቀኗቸዉን ባለሥልጣናትና በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡትን ከሥልጣናቸዉ ካስወገዱ በኋላ ግን በዉስጣቸዉ ተሰዉሮ የነበረዉ ዐይን ያወጣ አምባገነንነታቸዉ ጎልቶ በመዉጣቱ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ምስላቸዉ ተሥሎ ከፍ ከፍ ሲሉና ሲገኑ ታይቷል፣ ተሰምቷል:: አገልጋዮቻቸዉ (ባሪያዎቻቸዉ)ና አምላኪዎቻቸዉ ደግሞ በተለመደዉ የሽንገላና የማስመሰል ንግግራቸዉ «መለስ መግነንን ሆነ መወደስን አይፈልግም» እያሉ ሊያታልሉንና ለሽነግሉን ይፈልጋሉ:: ነገር ግን የተዘራዉ ነዉና የሚበቅለዉ ይኸዉ ፍሬያቸዉ አፍርቶ ቀን ከሌሊት ባለሥልጣኑም፣ ካድሬዉም፣ እንዲሁም የሥርዓቱ ደጋፊ አቶ መለስን እንደ አምላክ ቆጥሮ «መለስ» እያለ ሳያገንና ስሙን ሳያነሳ እንዲሁም ዛይዘምርለት ዉሎና አድሮ አያዉቅም:: ይህም የሚያሳየን ልክ ክርስትናን የመሰረተዉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነና በክርስትና በእዉነት የሚያምኑ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አምላክ እንደሚከተሉና እንደሚያመልኩት ሁሉ፤ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት ዋና መስራችና ፈጣሪ የሆነዉን አቶ መለስ ዜናዊን የሚያምኑና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት አራማኝ የሆኑ ሁሉ፤ ምንም እንኳ እምነቱ ትንሣኤ ሆነ ጽድቅና ኩነኔ የለለዉ ቢሆንም፤ በእምነቱ የሚመላለሱት ሁሉ በብልጠት የመለስ ወይንም የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ አምላኪ ናቸዉ ማለት ነዉ:: ይህ የአምልኮ ምንዝራና ደግሞ በራስ ላይ ከባድ የእግዚአብሔር ቁጣን የሚያመጣና በሰማይም በምድርም ዋጋ የሚያስከፍል ይሆናል ማለት ነዉ::

ሌላዉ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የአቶ መለስን ሥዕል በየሱቁ፣ በየሆቴሉ፣ በየቢሮዉ፣ በየቤቱ ፣ በየመኪናዉ፣ በየቦታዉ የለጠፉ ሰዎች ሁሉ የአቶ መለስ ወዳጆችና የሥርዓቱ ደጋፊዎች አይደሉም:: የተወሰኑት «ለመኖር ተመሳሰል» የሚለዉን የአእምሮ ቀላሎችን የአእምሮ ሕፃናት መመሪያ በመያዝ ነዉ ሊለጥፉትና ልብሱንም ሊለብሱ የቻሉት:: ምክንያቱም «የኢሕአዴግ መንግሥት በቀለኛ ነዉና ጊዜና ወቅት ጠብቆ ይበቀለናል፤ የተለያየ ተጽህኖ ያደርስብናል፤ በአንድ ለአምስት አደረጃጀቱ በካድሬዎቹ ስለላ መረብ ዉስጥ ስለወደቅን ለመኖር ስንል ሕሊናችን

ያልተቀበለዉን ድርጊት ፈጽመናል» በሚል በእነ ሆዱና ጥቅሙ አምላኩ በሆኑ ሰዎች መመሪ ነዉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ድጋፊ በመምሰል የተለየ ጥቅም ለማግኘት ነዉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ አምላክ በመቁጠር ነዉ:: አንዳንዱ ደግሞ እንደ ፓለቲካ መሳሪያ በመጠቀም የራሳቸዉን ዓላማ ለማሳካት ነዉ:: ለእዚህ ነዉ አእምሮ ቀላልና አእምሮ ሕፃን የሆኑ ከከፍተኛ ባለሥልጣን እስከ ታች ካድሬዉ ድረስ «ሕዝቡ ለአቶ መለስ ያለዉን ፍቅርና አክብሮ በለቅሶ ጊዜ ሆነ አሁን ሥዕሉን በመለጠፍና ስሙን በማንሳት እለት እለት የሚጠሩት የእርሱን ፓሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ እቅድ፣ ተግባር ስለደገፉና ስለወደዱ ነዉ» በማለት ነጋ ጠባ የሚለፈልፉት:: አንዳንዶች «ይህን ተንኮለኛና መሰሪ እግዚአብሔር ነቀለልን» ያለት ደግሞ፤ «ንግግራችን ድንገት በካድሬዎቹ ከተሰማ በቀል ይፈጸምብናል» በሚል ስጋት ነዉ ለማስመሰልና ራሳቸዉን ለማዳን ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ በማድረግ አብረዉ የሚያሽቃብጡት ። ቤተሰብና እዉነተኛ ወዳጁ ቢያዳንቁትና ፎቶዉን ቢለጥፉ አያስገርምም፤ አያስተዛዝብም:: ምክንያቱም ሁሉም ለወዳጁ የሚያደርገዉ ነዉና:: ሌላዉ ለመኖር ሲል ሕሊናዉ ያልተቀበለዉን የፈጸመ ግን ትዝብት ላይ ነዉ የወደቀዉ::

እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገዉ እግዚአብሔር የተለያየ ክስተቶችን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሳይጠበቅና ሳይገመት ያመጣዉ እንክርዳዱና ገለባዉ ከስንዴዉ እንዲለይና ገለባዉና እንክርዳዱ ማን እንደሆነ እንዲታወቅ፣ እንዲሁም አስመሳዩና ሕሊናዉን የሚሸጠዉ ሰዉ ማንነቱ በግልጽ እንዲለይ ለማድረግ፣ ከዚህ በተጨማሪ አእምሮ ጽንአን እነማን እንደሆኑ ትዉልዱ እንዲያዉቅ ለማስቻል ነዉ:: ለወደፊትም በሚከሰተዉ የተለያየ ፈተናና መከራ ትዉልዱ የሚለይበትና ማንነቱ የሚታወቅበት የሚጠራበትና የሚነጥርበት ይሆናል ማለት ነዉ:: በመጨረሻ ግን በእግዚአብሔር በተለያየ ቁጣ ገለባዉና እንክርዳዱ ከስንዴዉ ይለያል::ስንዴዎች ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ለመልካሙ ዘመን ይደርሳሉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ኢትዮጵዊነት በሥጋና በደም ብቻ ሊገለጽ ይችላል ወይ? ዋና መገለጫ ምንድ ነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሥጋና ደም (የሚታየዉ ሥጋዊ አካልና መልክ)፣ ነፍስ፣ መንፈስ ናቸዉ:: ሥጋና ደም ብቻ መገለጫ ሊሆን አይችልም:: ብዙዎች በሥጋና ደማቸዉ ኢትዮጵያዉያን ቢሆኑም ኢትዮጵያዊነታቸዉን አያዉቁም:: አንዳንዶቹ ደግሞ በነፍሳቸዉና በመንፈሳቸዉ ኢትዮጵያዊነታቸዉን ክደዋል:: አንዳንዶቹ ደግሞ ፀረ ኢትዮጵያዊነት አቋም በመያዝ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ ተነስተዋል:: በቁጥራቸዉ እጅግ እጅግ አነስተኛ የሆኑ ደግሞ በሥጋና ደማቸዉ ኢትዮጵያዉያን ባይሆኑም ወደዉና ፈቅደዉ ኢትዮጵያዊነትን በነፍሳቸዉና በመንፈሳቸዉ እንደ ሃይማኖት ተቀብለዉት ይኖሩበታል::

ከላይ የተገለጹትን ለማብራራት ይህል የሻዕቢያዉ መሪ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂና የሕዉሓት መሪ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዉ በሥጋና በደም ኢትዮጵያዉያን ቢሆኑም ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነታቸዉን አቃለዉና ክደዉ ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አቋም በመያዝ በነፍሳቸዉና በመንፈሳቸዉ ኢትዮጵያዊነታቸዉን የካዱ ከሃዲዎችና አስመሳይ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ፣ ነበሩ::

የተወሰኑ ጃማይካዉያን በሥጋና በደማቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሲሆኑ በነፍሳቸዉና በመንፈሳቸዉ ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነት በመቀበል ላይ ናቸዉ:: የመጀመሪያዊ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ አቡነ ሰላማ በሥጋና ደማቸዉ ኢትዮጵያዊ ባይሆኑም በነፍስና በመንፈሳቸዉ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ናቸዉ:: የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በሥጋቸዉና በደማቸዉ ኢትዮጵያዊ ቢሆኑም ኢትዮጵዊነታቸዉን ያላወቁና በነፍስና በመንፈሳቸዉ አሜሪካዊ የሆኑ ናቸዉ:: በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ ዓለም ያሉ በሥጋቸዉና ደማቸዉ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ነገር ግን በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕሊናቸዉ የተመረዘና የተበከለ «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ነዉ» እያሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳከምና በሂደትም ገዝግዞ ለመጣል ለመደምሰስ የተሰለፉ ሁሉ ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነትን በነፍሳቸዉና በመንፈሳቸዉ የካዱ፣ በኢትዮጵያና ኢትጵያዊነት ላይ ዓመፃና ክህደት የፈጸሙ ናቸዉ:: ስለዚህ የእዉነተኛ ኢትዮጵያዊነት መገለጫ ዋናዉ ሥጋና ደም ሳይሆን በነፍስና በመንፈስ በኢትዮጵያዊነት እምነትና ምግባር እንዲሁም ሕይወትና ሥርዓት መመላለስ ነዉ::

ከዚህ በተለየ ሕይወት በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ብንመላለስ ምንም እንኳን በሥጋና በደማችን ኢትዮጵያዉያን ብንሆንም በነፍሳችንና በመንፈሳችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ ወተናልና ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነትን ስላቃለልንና ስለናቅን እንዲሁም ዓመፃና ክህደት ስለፈጸምን በራሳችን ጊዜ በነፍሳችንና በመንፈሳችን ኢትዮጵያዊነታችን ክደናል ማለት ነዉ:: በመሆኑም እንደ ኢትዮጵያዊነታችን በሥጋችንና በደማችን ብቻ «ኢትዮጵያዉያን ነን» ማለት ሳይሆን የሚጠበቅብን በመልካም ምግባርና ሕይወት በመሆንና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመመላለስ መኖር ይጠበቅብናል:: የሦስቱ ነገድ ማለትም የካም የሴም የያፌት ዉሕድ ዘር ሁሉ በሥጋና በደሙ ኢትዮጵያዉያን ቢሆኑም፤ ዉሕድ ዘር የሆነዉ ብቻ ሳይሆን በተናጠል የአንዱ ነገድ ዘር የሆነ ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን በነፍሱና በመንፈሱ ከተቀበለና በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ምግባር እንዲሁም ሥርዓት ከኖረ እርሱ እዉነተኛ ኢትዮጵያዊ ነዉ ማለት ነዉ:: ያኔ ኢትዮጵያዊነትን እንደ ሃይማኖት ተቀበለዉ ማለት ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከላይ እንደገለጹልን ማንኛዉ የአዳም ዘር በነፍስና በመንፈስ ኢትዮጵያዊ ሊሆን እንደሚችል አዉቀናል:: በሥጋና በደማቸዉ ኢትዮጵያዉያን የሆኑ ሰዎች መለያቸዉ ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በሥጋቸዉና በደማቸዉ ኢትዮጵያዉያን የሆኑት በመልካቸዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ የሆኑና፤ ቀይ ለቀይ ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: እንዲሁም ጥቁር ለጥቁር ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: ጠይም ለጠይም ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: የቀይ ዳማ ከቀይ ዳማ ጋር ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: ቀይና ጥቁር ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: ቀይና ጠይም ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: ቀይና የቀይ ዳማ ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ:: ጥቁርና ጠይም ተጋብተዉ ቀይ፣

ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ፡፡ ጥቁርና የቀይ ዳማ ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ፡፡ ጠይምና የቀይ ዳማ ተጋብተዉ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ሊወልዱ የሚችሉ ናቸዉ፡፡» **በማለት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት የሚያምኑት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሁለት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: ቀድሞና አሁን በመንግሥት ላይ የነበሮት አስተያየትና አመለካከት ልዩነት አለዉ ወይ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ቀድሞ አሁን ያለዉ የኢሕአዲግ መንግሥት የራሱን ስዉር መሰሪ ተግባር ሲፈጽምና ሲያስፈጽም፤ ኑሮዬን ለማሸነፍ ከመዉጣትና ከመዉረድ ዉጭ ብዙም ትኩረት አልሰጥም ነበር:: አሁን ግን እያንዳንዱን እንቅስቃሴና ንግግር በተወሰነ ደረጃ እከታተላለሁ:: ቀድሞ ብዙም የማላዉቃቸዉ የተለያዩ ሰዎች ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ ምን ያህል ሕሊናቸዉን የሸጡ እንደሆነ የሚያሳይ መሆኑንና እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚሄዱ፣ እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብለዉ የሚነዱ መሆኑን ሳስተዉል ችያለሁ:: ከአርባ ዓመት በፊት የነበሩት ወጣቶች ሆኑ ጎልማሶች፤ ሁሉ ተማልቶላቸዉ፣ በእዉቀትም ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሰዉ፣ የሕዝብ መበደል፣ የፍርድ መጓደል፣ አድሎና መድሎ ሲፈጸም ተመልክተዉ «ፍትሐዊ ሥርዓት መኖር አለበት፣ አድሎና መድሎ መቆም አለበት፣ ትክክለኛ ፍርድ መሰጠት አለበት፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል መኖር አለበት፣... ወዘተ» በማለት ራሳቸዉን ክደዉ ስለ እዉነት ሲሟገቱና ለዉጥ ለማምጣት ዋጋ መክፈላቸዉን ስሰማና ሳነብ፤ «ያ ኢትዮጵያዊ ወኔ የት ሄዶ ነዉ እነዚህ ስለ ሆዳቸዉና ስለ ወንበር እንዲሁም ስለ ልዩ ጥቅማ ጥቅም ሲሉ ሕሊናቸዉን የሚሸጡት፣ ዉስጣቸዉ በጥላቻና በበቀል ተሞልቶ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት የሚመላለሱት?» እላለሁ:: እንዲሁም «ይህን ትዉልድ ማን ፈጠራቸዉ?» ብዬ እጠይቃለሁ::

እንዲሁም የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ለመቀነስና የክልል መንግሥታትን በመመስረት ለወደፊት ደግሞ ለነጻ መንግሥትነት ለማብቃትና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሱ የዓመፃ ልጆች ተግባር ቢያናድደኝም፤ ምንም ማድረግ ባለመቻሌም ዉስጤ ቢብገነገንም፤ የጨለማ ስራቸዉ በደንብ በግልጽ የተገለጸልኝ የእግዚአብሔር መልእክታትን በምጽፍበት ወቅት ነዉ:: ሰንደቅ ዓለማ ላይ የተቀመጠዉ ኮኮብ የዲያብሎስ ዓርማ መሆኑን ያስተዋልኩትና ያወኩት የእግዚአብሔር መልእክታትን በምጽፍበት ጊዜ ነዉ:: አሁን ሦስተኛዉን መልእክት በምጽፍበት ጊዜ ደግሞ ኮኮቡ ለአሁን ዘመን በግልጽ የዲያብሎስ መገለጫና መመለኪያ የአሁን ዘመን 666 መሆኑን የተረዳሁት:: እንዲሁም «የክልል መንግሥታት ሰንደቅ ዓለማ» ተብለዉ የተዘጋጀዉም በጨለማዉ ገዥ በዲያብሎስ መንፈስ አሳሳቢነትና በእንደራሴዉ (በአገልጋዩ) የመሪነት ወንበር ባስጨበጠዉ አማካይነት የተዘጋጁ እዉነተኛዉን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ለማስጠፋት የጠፈጠሩ መሆኑን ነዉ በሚገባ ያስተዋልኩት::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ በባህልና በእምነት ሽፋን የሚካሄዱት የተለያዩ ባዕድ አምላኮዎች ተወግዘዋል፤ የዲያብሎስ ዉጤቶች መሆናቸዉ ተመስክሮባቸዋል:: ታዲያ በአሁን ዘመን ያሉ መሪዎችና የእነሱ አገልጋይ የሆኑ ፖለቲከኞች የተለያዩ ባዕድ አምልኮዎችን መፈጸም እንደ ታላቅ ተግባር እየቆጠሩ በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ(በማስ ሚድያ)

ያስተላልፋሉ፡፡ እንዲሁም «የቀድሞ ገዥ መደቦች ክርስቲያኖች ወይንም ዐምሓራዎች ይህን ባህላችንንና እምነተችንን አጥፍተዉብን ነበር፡፡ አሁን ግን የሕወሓት(ኢሕአዲግ) መንግሥት ነጻነታችንን አጎናጽፎን በየወንዛወንዙ፣ በየተራራዉ፣ በየሸለቆዉ፣ በየምናምንቴዉ ቦታ ሳይቀር በነጻነት አምልኳችንን እንፈጽማለን» እያሉ አሁን ያለዉን መንግሥት ያደንቃሉ፣ ያገናሉ፤ የጥንቶቹን ደግሞ ያወግዛሉ፣ ይኮንናሉ፡፡ ለዚህ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: የሕወሓት(የኢሕአዴግ) መንግሥት ማለት የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት ማለት ነዉ ነዉ እንጂ የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለም፡፡ በመሆኑም የሰዉ መንግሥት የሥጋና የደም ስሜትንና የዲያብሎስን ፈቃድ ነዉ የሚፈጽመዉ፣ የሚያስፈጽመዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ሕወሓት(የኢሕአዴግ) ወደ ሥጋዊ ወንበር ላይ ሲመጡ ዉስጣቸዉ ጥላቻና በቀል የሞላዉ ስለነበረ በቀጥታ የፈጸሙትና ያስፈጸሙት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት እንዲሁም በክርስቲያኑ(በዐምሓራዉ) ላይ በቀልና አድሎ በደል መፈጸምና ማስፈጸም ነበር፡፡ ለዚህም የተጠቀሙት መሳሪያ ሕዝቡን «እነዚህ የገዥ መደቦች ወይንም ነፍጠኞች ወይንም ዐምሓራዎች ወይንም ክርስቲያኖች ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ እምነታችሁን፣ ሃይማኖታችሁን የለወጡ ናቸዉ፡፡ ሴቶቹን ጡጣቸዉን እየቆረጡ ወንዶቹን እጃቸዉን እየቆረጡ ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል፡፡ ይህም ድርጊታቸዉ እንዳይረሳ የተለያዩ ሐዉልቶች በመስራት ግፋቸዉንና በደላቸዉን ለልጅ ልጆቻችሁ ማሳወቅ አለባችሁ... ወዘተ» እያሉ በፍቅርና በአንድነት ተዋሕዶ በኖረዉና በኢትዮጵያዊነቱ በሚያምነዉ ምስኪን ሕዝብ ዉስጥ ፍጹም የዲያብሎስ መሳሪያና አገልጋይ ሆነዉ ጥላቻችንና በቀልን ዘሩ፡፡ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን አስፋፉ፤ ርኩሰት የሆነዉን ባዕድ አምላኮ አነገሡ፡፡ ባጠቃላይ ፍጹም የጨለማ ሥርዓት ዘረጉ፡፡

በዚህም ምክንያት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲቃጠሉ አደረጉ፣ ክርስቲያኖች (ዐምሓሮች) እንዲጨፈጨፉ፣ ከመኖሪያ አገራቸዉ እንዲፈናቀሉና አድሎና በደል እንዲፈጸምባቸዉ አደረጉ፡፡ በቀላቸዉን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተጠናከረና በረቀቀ መንገድ ሲፈጽሙ ቆዩ፡፡ ኢ- ክርስቲያናዊ (ፀረ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት» ለማስፋፋትና ክህደትንና ርኩሰትን ለማንገሥ ሲሉ ኢትዮጵያንን በቋንቋ በመከፋፈል ለወደፊት እያንዳንዱ የተከፋፈለ ክልል ነጻ መንግሥት መመስረት የሚችበትን ሕገ መንግሥት በማዘጋጀት እንዲሁም የየራሳቸዉ እምነትና ሃይማኖት ብሔራዊ ሃማኖቶች ሆኖዉ እንዲያገለግሏቸዉ ታሳቢ በማድረግ የዘረኝነትንና የጎጠኝነት ሥርዓት አስፋፉ፡፡

እነዚህ «የዓመፃ ልጆች» ተብለዉ በእግዚአብሔር የተገሰጹና የዓመፃ ስራቸዉ የተመሰረከረባቸዉ ሰዎች፤ በቋንቋ ሽፋን «ብሔራዊ ክልላዉ መንግሥት» ብለዉ ባቋቋሙት መንግሥት ዉስጥ በየወንዛወንዙና በየተራራዉ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች ርኩሰት የተባለዉን ባዕድ አምልኮ በግልጽ እንዲፈጸምና ሕዝቡ የአምልኮ ምንዝርና እንዲፈጸም አድርገዋል፡፡ እንዲሁም ራሳቸዉ አገር እየመሩበትና እያስተዳደሩበት «የነፍጠኛ ወይንም የዐምሓራዎች ቋንቋ ቋንቋችሁንና ባህላችሁን እንዲሁም ሃይማኖታችሁን ያጠፉ ስለሆነ አትማሩበት፣ አትስሩበት፣ አትነጋገሩበት» በማለት

የኢትዮጵያዉን የጋራ ቋንቋቸዉ የሆነዉ ዐማርኛ ቋንቋ እንዲጠሉት በማድረግ ከመማሪያነትና ከሥራ ቋንቋነት አስወግደዉታል። ዋናዉ ዓላማቸዉ በቋንቋ ሽፋን ክርስቲያኖችን (ዐምሐራዎችን) መበቀልና ከመኖሪያ፣ ከስራ ማፈናቀል፤ አድሎና በደል እንዲፈጸምባቸዉ ማድረግ ስለነበረ፤ ስራ መስፈርቱ የትምህርትና የእዉቀት ደረጃ መሆኑ ቀርቶ በክልል ቋንቋ ማወቅና አለማወቅ እንዲሁም የፖለቲካ አገልጋይ በመሆን ሆነ። በዚህ ብዙ ክርስቲያኖችን (ዐምሓራዎን) ከስራ አፈናቀሉ። ቤተሰቦቻቸዉ ለችግርና ለልመና እንዲዳረጉ አደረጉ። ዓላማቸዉ ሁሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ነበርና ቋንቋዉን ማጥፋት ብቻ አይደለም በተለምዶ የዐማርኛ ፊደል የሚባዉን የግእዝ(የኢትዮጵያዉን ፊደል) አጥፍተዉ በባዕዳን በላቲን ፊደል ተኩት። እነሱ ብቻ አይደሉም የተመረጡት ሳይቀር የእነሱ ተባባሪና ስራ አስፈጻሚ ሆነዉ በኢትዮጵያ የሚነገሩ የተለያዩ ቋንቋዎች በራሳቸዉ በኢትዮጵያዉያን ፊደል መጻፍ ሲገባዉ በላቲን ፊደል እየጻፉ የዓመፃዉ ስራ ተቀባይነትና ድጋፍ እንዲያገኝ አስተዋጽኦ አደረጉ።

ቤተክህነቱም በዉስጡ የጨለማዉ ሥረዓት አገልጋዮች ተሰግስገዉበታልና አንድም ሰዉ ስለ ኢትዮጵያዉያን ፊደል መደምሰስ አልተቀረቀረም፤ ተቃዉሙም አላሰማም። «አንተም በፊናህ እንደፈለክ ሁን፤ እኔም በፊናዬ እንደፈለኩ ልሁን» በመባባል በዓመፃቸዉ በመጽናት እስከ አሁን ድረስ በጋራ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን እንዲሁም ብቸኛዋን የሕይወት መንገድ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ተዋሕዶን በማጥፋት ላይ ይገኛሉ። ታዲያ እነዚህ የዓመፃ ልጆች ከክህደትና ከርኩሰት ተግባር ፈጻሚነትና አስፈጻሚነት በእዉነተኛ ንሰሐ ካልተመለሱና ስለ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነትም ካልመሰከሩና እጃቸዉንም ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ካልሰጡ በስተቀር እነሱም ሆኑ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በተሰለፉና በተባበሩ ባዕዳን መንግሥታት ጭምር እግዚአብሔር የቁጣዉን መዓት ማዉረድ ብቻ አይደለም ያዘንብባቸዋል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: እዚህ ላይ ስለፊደል ካነሱ አይቀር አንዳንድ ምሁራን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እንዲሁም በቀናነት ይሁን በዓለማ «አንዳንድ ተመሳሳይ የሆኑ ፊደሎች ይቀነሱ» የሚሉ አሉ። ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ስዎች ስለ ፊደል መቀነስ ሆነ ስለ ቋንቋ መጥፋት ስሜት እንዳይሰጣቸዉ የሆነዉ በመጀመሪያ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ስሜት ከልቦናቸዉ መንግሎ ማዉጣት ስለተቻለ ነዉ። እንኳን ፊደልና ቋንቋን አይደለም «ተምሬያለሁ፣ ምሁር ነኝ» የሚለዉ ሳይቀር ያልተማረዉ መሃይም እንኳ ያላደረገዉንና ያልፈጸመዉን «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ» የሚለዉን ሕገ መንግሥት በፈንጠዝያና በጭፈራ፣ በእልልታ ነዉ ደስታዉን የገለጸዉ። ያ ብቻ አይደለም ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነቱን ክዶ «እኔ ብሔሬ ትግሬ ነዉ አገሬም ትግሪያ ነዉ። እኔ ብሔሬ አማራ ነዉ አገሬም አማሪያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ኦሮሞ ነዉ አገሬም ኦሮሚያ ነዉ። እኔ ብሔሬ አፋር ነዉ አገሬም አፋሪያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ሱማሌ ነዉ አገሬም ሱማሊያ ነዉ። እኔ ብሔረ ሐረሪ ነዉ አገሬም ሐረሪያ ነዉ። እኔ ብሔሬ አኝዋክ ነዉ አገሬም ጋምቤላ ነዉ። እኔ ብሔሬ ጉሙዝ ነዉ አገሬም ቤንሻንጉል ነዉ። እኔ ብሔሬ ሲዳማ

ነዉ አገሬም ሲዳሚያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ሐድያ ነዉ አገሬም ሐዲይያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ወላይታ ነዉ አገሬም ወላይቲይያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ስልጤ ነዉ አገሬም ስልጢያ ነዉ። እኔ ብሔሬ ጉራጌ ነዉ አገሬም ጉራጊያ ነዉ። እኔ ብሔሬ አገዉ ነዉ አገሬም አገዊያ ነዉ። ... ወዘተ » በማለት ኢትዮጵያዊ ብሔሩን ወይንም አገሩን በግልጽ የካደ ምሁር ሆነ ሌላዉ ክፍል «ፊዳላት ይቀነሱ፣ ሙሉ በሙሉ ተደምስሰዉ በባዕዳን በላቲን ወይንም በአረብኛ ይተኩ» ቢል ብዙም አይስደንቅም፤ አያስገርምም። ምክንያቱም በእግዚአብሔር መፈጠሩንና ካለመኖር ወደ መኖር መምጣቱን የካደና ሕያዉ ፍጥረት እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍስ እንዳለዉ እየታወቀ «እኔ እንስሳ ነኝ፤ ዘሮቼም ጦጣ መሰል እንስሳ ናቸዉ፤ በዝግምተኛ ለዉጥ ነዉ ሰዉ የሆንኩት» በማለት በራሱ ላይ ማንነቱን ስለመሰከረ ነዉ። ታዲያ በእንደዚህ እምነትና አስተሳሰብ ያለ ምሁር ሆነ ሌላ አካል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም ራሱን ለማጥፋት ቆርጦ ቢነሳ መሪዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ዉጤቱን መገመት አያስቸግርም።

**ወደ ጥያቄዉ አስተያየት ስገባ** እኛ ኢትዮጵያዉያን እጅግ አሳዛኝ ሰዎች መሆናችንን ለመግለጽ እወዳለሁ። ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን የራሳቸዉን ማንነትና ታሪክ ራሳቸዉ የሚያጠፉ ሕዝቦች ሆኑ አገሮች ያሉ አይመስለኝም። ሌላዉ አገርና ሕዝብ የሌለዉን ማንነትና ታሪክ እየጨማመረ ሲታይ፤ የእኛ አገር መሪዎችና ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎች የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዉያንን ታሪክና ማንነት ለማጥፋት ቆርጠዉ መነሳታቸዉ እጅግ ያሳፍራል፤ ያስገርማል። ምክንያቱም ለዓለም የሚተርፍ እምነት፣ ሥርዓት፣ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ባህል እያለን ዓለምንም ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ማምጣት እያቻልን፤ የራሳችንን እምነት፣ ሥርዓት፣ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ባህል ለማጥፋት ቆርጠን መነሳታችን፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሱ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር የጨለማ ገዥ አገልጋዮች ቅጥረኞች መሆናችንን ነዉ የሚያሳየዉ። ኢትዮጵያዊነቱ ከልቦናዉ ያልተመነገለ እዉነተኛ ኢትዮጵያዊዉማ ለሁሉም ቋንቋዎች እንዲሆን እንደ ቀደምት ወላጆቻችን ባሉት ፊደላት ላይ ተጨማሪ ቅጥያ የሚያስፈልጋቸዉን በተጨማሪ ያዘጋጃል እንጂ ያሉት ይቀነሱ አይልም። ከማንኛዉም ፊደል በላይ የኢትዮጵያዉያን ፊደል ሳይንዛዛና እጥረት ሳያጋጥመዉ ቋንቋዎችን ሁሉ ለመግለጽ የሚችል ነዉ። ቅንነትና እዉነተኛነት ቢኖር ኖሮ አስፈላጊ ምልክቶችንና ቅጥያዎችን በማድረግ ለሁሉም ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ ይቻል ነበር።

«ተመሳሳይ ፊደላት አሉና ይቀነሱ» የሚለዉ አባባል በአብዛኛዉ ካለማወቅ የመጣ ነዉ የሚመስለኝ። ምክንያቱም ዘመናዊ ትምህርት ስንማር በቅድሚያ የራሳችንን በደንብ እንድናዉቅ አልተደረገምና። ይኸዉም የባዕዳን ፊደልና ቋንቋ ስንማር፣ አስፈላጊዉ ጥንቃቄ እንድናደርግ ሲደረግ፣ ለራሳችን ቋንቋና ፊደል ግን አንዳች ትኩረት ሆነ ጥንቃቄ እንዲደረግለት አልተደረገም። ይልቁኑ የእዉነታ ተቃራኒ በሆነዉ በፖለቲካ(በዉሸት) ትዉልዱ ሕሊናዉ እንዲበከልና እንዲመረዝ ስለተደረገ በኢትዮጵያዊዉ ቋንቋና ፊደል ላይ የማጥላላትና የማጥፋት ዘመቻ ነዉ የተደረገዉ። ኢትዮጵያዉኛ ወይንም ዐምሓርኛ ቋንቋ በዋናነት ከግእዝ ቋንቋ የተገኘ ስለሆነ በግእዝ ያለዉ ፊደል ካልተጠበቀ ቃላቱ ትርጉም አልባ ይሆናል።

በእንግሊዘኛዉ ቋንቋ ፊደላቱ ካልተጠበቁና ከተቀነሱ ትርጉም እንደማይኖራቸዉ፤ ለምሳሌ Butter የሚለዉን አንዱ t ን ብናስቀር አነባብ ላይ ለዉጥ ባያመጣም ትርጉም ግን አይኖረዉም፤ ወይንም ሌላ ትርጉም ነዉ የሚሰጠዉ:: እንዲሁም u የሚለዉ በ e ቢተካ የማይገናኝ ትርጉም ነዉ የሚሰጠን:: ወደ ኢትዮጵያዊዉ ቃላትና ፊደል ስንመጣ መምህር የሚለዉና መምሕር፣ እንዲሁም ምሕረት የሚለዉን «ምህረት» ብለን በንጽፍ ፍጹም የማይገናኙ ሆነዉ እናገኛለን:: ምሕረት የሚለዉ ሆነ መምህር የሚለዉ ቃላት የተገኙት ከግእዝ በቀጥታ ሲሆን ዋናዉ ግሳቸዉም መሀረና መሐረ ነዉ:: መሀረ ማለት አስተማረ፣ መራ፣ አለማመደ፣ መከረ፣ ቀጣ ማለት ሲሆን፤ መሐረ ደግሞ ማረ፣ ራራ፣ አዘነ ማለት ነዉ:: ከዋናዉ ግሳቸዉ ባዕድና ምዕላድ ሲሆኑ ደግሞ መምህርና ምሕረት የሚለዉን ቃላት እናገኛለን:: ሌሎች ቀላቶችም የተፈጠሩት ከዚያዉ ከመጀመሪያዉ ከግእዝ ግስ ነዉ:: ይኸዉም በዘመድ ዘር ወይንም ባዕድ ከምላድ ወይንም ቅጽል ወይንም ዉስጠዘ ወይንም ጥሬ ዘር ሆነዉ ነዉ:: በዚሁ መሰረት ከመሐረ መሓሪ እናገኛለን:: ከመሀረ ትምህርት፣ ምሁር የመሳሰሉትን እናገኛለን:: እነዚህ የግእዝ ቃላት ናቸዉ ወደ ዐማርኛ ቃለት የተወሰዱት:: በመሆኑም አነባበባቸዉ ተመሳሳይ ቢሆን እንኳ ምሕረት ለማለት ምህረት ብለን ከጻፍን እንደ እንግሊዘኛዉ ትርጉሙ የማይታወቅ ቃላት ነዉ የሚሆነዉ:: ምክንያቱም መሰረቱን መሐረ ከተመለከትን ከመሀረ ትርጉም ጋር የተለያየና የማይገናኝ በመሆኑ ነዉ:: ይህም የሚያሳየን ፊደል ቢቀነስ የቃላቶቹን ትርጉም ያዛባል:: እንዲሁም አንዱን ፊደል ከእንግሊዘኛዉ ስንቀንስ ትርጉም አልባ እንደሚሆን ሁሉ እኛም ከቃላቶች ዉስጥ አንዱን ፊደል ብንቀንስ ትርጉም አልባ ይሆናል ማለት ነዉ:: ለምሳሌ ምሕረት የሚለዉን ምረት ብንል ስህተት ነዉ ማለት ነዉ::

በእንግሊዘኛዉ ሌላዉ አይደለም በካፒታል ሌተር Ethiopia (ኢትዮጵያ) የሚለዉን capital **E** ን በ small letter ethiopia (ኢትዮያጵያ) ብለን ብንጽፍ እንኳን የቋንቋዉ ባለቤቶች አይደለም፤ ሕይወት የሌለዉ ግዑዙ መቀመሪያ(ኮምፒተር) ቀይ መስመር በማስመር «ተሳስታችኋልና አርሙት ትክክልኛዉ ይህ ነዉ» ብሎ ያርመናል:: ወደ እኛ ስንመጣ ለምሳሌ ጸሎት የሚለዉን ፀሎት ብለን ብንጽፍ ምንም እንኳን ጸሎት ለማለት ፈልገን እንደሆነ ቢታወቅም ቃላቱ በቀጥታ የመጣዉ ከግእዙ ስለሆነ ፀሎት የሚለዉ ትርጉም አልባ ይሆናል:: ይህን ስህተት እንኳን በከፍተኛ በዓለማዉ እዉቀት ዉስጥ ያለዉ ሰዉ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ በመንፈሳዊ እዉቀት ዉስጥ ያሉት ጭምር ይፈጽማሉ:: ምክንያቱም የተለየ ቦታና ጥንቃቄ እንድናደርግ ተደርጎ የተቀረጸነዉ ለባዕዳኑ እዉቀት እንጂ ለራሳችን ባለመሆኑ ነዉ:: እንኳን ሕይወት የሌለዉ ግዑዙ መቀመሪያ(ኮምፒተር) ሊያርመን ቀርቶ የቋንቋዉ ምሁራንም አያርሙንም:: እኛም እንደ ትክክል ቆጥረን ስለምንመለከት ሌላዉ የምናሳዉቅበት እዉቀት የለንም:: ይልቁኑ « ጸ እና ፀ አንድ አይነት እስከሆኑ ድረስ ለምን አንደኛዉ ፊደል አይቀነስም?» የምንል እንሆናለን:: በዚህ ምክንያት ምንጫቸዉ የግእዝ ቃላት የሆኑት ፀሐይ የሚለዉን ጸሐይ ብለን ብንጽፍ ቅር አይለንም፤ አንጸየፈዉም:: ብሔር(አገር) የሚለዉን ብሄር(ትርጉሙ የማይታወቅ) ብለን ብንጽፍ ቅር አይለንም፤ አንጸየፈዉም:: ሠዐለ (ሣለ፣ አስመሰለ፣ ነደፈ) ከሚለዉ ግሥ የተገኘዉን ዘመድ ዘር የሆነዉን ***ሥዕል*** የሚለዉን ቃል «ስእል» ብለን ብንጽፍ ቅር አይለንም! አንጸየፈዉም:: እንዲሁም ሰአለ (ለመነ፣ ፈለገ፣ ሻተ) ከሚለዉ ግስ ቅጽል

ሆኖ የተገኘዉ <u>ሰኣሊ</u>**(የሚለምን፣ለማኝ)** የሚለዉን፤ «**ሠዐሊ**»(የሚሥል፣ ሳይ) ብለን ብንጽፍ ቅር አይለንም፤ አንጸየፈዉም። ምክንያቱም ልዩነቱን በደንብ አላስተዋልነዉምና። እንዲሁም ይህን ስህተታችን ሚያሳዉቀን፣ ለራሱ ማንነትና ቅርስ የሚቆረቆረ ቆራጥ እዉነተኛ ታማኝ ኢትዮጵያዊ የለምና። የባዕዳን ቃላት ሆነ ፊደል አንድ ብንሳሳት ግን የሚተቹን፣ ስህተት ነዉ የሚሉን፣ የሚገምቱን፣ እንደ አላዋቂ መሃይም የሚቆጥሩን ግን እጅግ ብዙ ኢትዮጵያዉያን አሉ።

ሌላዉ እዚህ ላይ ላማስታወስ የምፈልገዉ የኢትዮጵያ ፊደል እንኳ በኢትዮጵያ ዉስጥ ለሚነገሩ ቋንቋች አይደለም ለዓለም የሚሆን ነዉ። ምክንያቱም ሁሉንም ድምጾች ለመግለጽ የሚቻልበትና እንዲሁም ለአጻጻፍ የሚቀል ለምሳሌ በላቲን ፊደል አንዱን ፊደል «ጸ» ለመጻፍ ሦስት ፊደላት (tse) ያስፈልጉታል። እንዲሁም አንዱን ፊደል «ዠ»ን ለመጻፍ (zhe) ብሎ መጻፍ ያስፈልገዋል። እዲሁም በአጠራር ተመሳሳይ የሆኑ ነገር ግን በፊደል ብቻ የሚለያዩት የእንግሊዘኛ ቃላት ፊደላትና ቃላት ብንመለከት (see) (sea) (si)፤ ይህ ሁሉ በኢትዮጵያዉኛ ፊደል በአንድ ፊደል «ሲ» ተብሎ ይጠራል። የኢትዮጵያ ፊደል ለማንኛዉም ቋንቋ ቢዉል የተንዛዘዉን የፊደል ጋጋታ ይቀንሳል እንጂ አቅም የሌለዉ ፊደል አይደለም።

የኢትዮጵያዉያንን ፊደል ለማጣጣልና ለማሳናስ የሚፈልጉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያላግጡ የስም ኢትዮጵያዉያን ደግሞ «በላ» «ሳይገባዉ» «ዋና» ... የሚለዉ ሲላላና ሲጠብቅ የተለያየ ትርጉን አለዉ በማለት ለማናናቅ ይሞክራሉ። የባዕዳንን ሦስት ድምፅ አመሳስለዉ ለመጥራት ግን ምንም አይመስላቸዉም። ቅንነቱ ቢኖር ኖሮ «የሚጠብቀዉ ላይ ጠባቂ መሆኑን ለማሳየት ነቁጥ ወይንም ጭረት ወይም የተሻለ ሌላ ምልክት ይደረግበት፣ እንዲሁም ለአንዳንድ ድምጾች መግለጫ ተጨማሪ ፊደል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በዚያ ግእዝ ፊደል ላይ በተጨማሪ ይግባ» በማለት ቋንቋዉንና ፊደሉን ለሁሉም ቋንቋዎች ምሉዕ ማድረግ ይቻል ነበር። ነገር ግን የዓመፃ ልጆች ዓላማቸዉ የራሳቸዉን ስዉርና ግልጽ ዓላማ መፈጸምና ማስፈጸም ስለሆነ ቋንቋዉንና ፊደሉን ማጥፋትና ማዳከም ነዉ የተያያዙት።

አሁን ያለዉ የሕወሓት(ኢሕአዲግ) መንግሥት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነትን ቅርስ ለማጥፋትና ዘረኝነትና ጎጠኝነት በማንገሥ ኢትዮጵያዉያን እንዳይዋሓዱና አንድ እንዳይሆኑ የሚፈልግ ስለሆነ አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር ፈጽሟል። ይኸዉም «ይህ ፊደል የአበሾ ነዉ እናንተን አይወክልም፤ ይህ የዘመን አቆጣጥር የክርስቲያኖች(የዐምሓራዎች) ነዉ እናንተን አይወክልም፤ ይህ እምነት፣ ባህል፣ ቋንቋ የክርስቲያኖች(የዐምሓራዎች) ነዉ እናንተን አይወክልም... ወዘተ» እያለ «ብሔር ብሔረሰብ» የሚል ስያሜ ለእያንዳንዱ በማዉጣት ዉስጥ ዉስጡን እንደ ምስጥ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እያዳከመና እየገዘገዘ ባዶ ሊያስቀርና በመጨረሻ ትዉልዱ ማንነቱን አቶ ከሰማኒያ በላይ መንግሥታት ተመስርተዉ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ የሚለዉን ሁሉ ለማጠፋት ነዉ የተሰለፈዉ።

አሁን ያለዉ ትዉልድ የራሱን ፊደልና ቃላት ስላልተማረ ልዩነቱን አያዉቅም፤ አያስተዉልም:: እነዚህ ልዩነቶች ለማወቅ ደግሞ በመጀመሪያ የራስን ፊደልና ቃላት በደንብ መታወቅ ይኖርበታል:: ለእዚህ ሁሉ መፍትሔዉ ደግሞ ግእዝ ቋንቋን እንደ ቋንቋ ስንማርና ስናዉቅ ነዉ:: ያኔ ትክክለኛ አጻጻፍ መጻፍና መናገር እንችላለን ማለት ነዉ:: ከዚያ ዉጪ ግን ጽሑፋችን ሆነ አነጋገራችን ከትክክለኛ ትርጉም የወጣና ስህተት ይሆናል:: ለባዕዳን ቋንቋና ፊደል ትኩረት እንደምንሰጥ ለራሳችን ቋንቋና ፊደል አንዳች ትኩረት ስለማንሰጥ የተማረዉም ያልተማረዉም ፊደል እየለወጠና እየቀነሰ ይጽፋል፤ ትርጉም አልባ ቃላትንም እንደትክክለኛ ቆጥሮ ይጠቀምበታል:: ከእዚያም ባለፈ ተቃራኒ ትርጉም ልንጽፍ እንችላለን:: ለምሳሌ <u>በዓል</u> የሚለዉ ከተቀደሰ ክብረ በዓል ጋር የሚሄደዉን ቃል፤ **በኣል** ብለን ብንጽፍ ከጣዖትና ከባዕድ አምልኮ ጋር ነዉ የሚሄደዉ እንጂ ትክክለኛ በዓልን አይገልጽልንም:: ሌላዉ ደግሞ በእንግሊዘኛ የተጻፈዉ «write» (ጻፈ ) የሚለዉ ሲነበብ ዉ ተጎርዶ (ራይት) ተብሎ ነዉ እንጂ እንደ አጻጻፉ «ዉራይት» ተብሎ አይደለም:: እንዲሁም «right» (ቀኝ) የሚለዉ በንባብ ድምጽ ከጻፈ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በፊደል ሆነ በትርጉም የተለያየ ስለሆነ ያንኑ አክብረን እንደ አጻጻፉ ፊደሉና ቃላቱ እንዲሁም አነባበቡ እንጠቀምበታለን እንጂ «w» የማይነበብ ከሆነ ለምን ከቃላቱ ላይ አናወጣዉም? አንልም:: ምክንያቱም ከዉጭ ስለመጣና እነሱም በስምምነት ቃሉን ጠብቀዉ ስለሚጠቀሙበት እኛ ደግሞ ከእነሱ በላይ እንደ ዶግማ ስለምንመለከተዉ እንኳን አስተያየት መስጠት አይደለም ሁለተኛዉ ቋንቋ የሆነበት ሰዉ እንደ ቋንቋዉ ባለቤቶች አነጋገር ዘይቤ ሳይናገር ቢቀር ከፍተኛ በደል እንደፈጸመ ነዉ የምንቆጥረዉና የምንተቸዉ:: እንዲሁም እንደ ሕግ አፍራሽነት ስለመንቆጠር ለፊደሉ ብቻ አይደለም ስለ አነባበቡ ጭምር ከፍተኛ ጥንቃቄ እናደርጋለን::

ሌላዉ ደግሞ በእንግሊዘኛዉ food በእኛ ሲነበብ fud (ፉድ) ተብሎ ነዉ:: ነገር ግን በእንግሊዘኛዉ የተጻፈዉን እንዳለ በመቀበልና አነባበቡን ደግሞ (ፎኦኦድ) ሳንል «ፉድ» ብለን እንጠራለን:: እንደ ቋንቋ ቃላቱን ተቀብለነዉ በዚያ እየተጠቀምን ነዉ እንጂ ፊደሉ እንደ ድምፁ ይለወጥ ብለን ምንጩን እናጥፋና በድምፁ አጠራር እንጥራ አላልንም፤ አንልም:: እንዲሁ የራሳችንን ኢትዮጵያዉኛ(ዐማርኛ) ቋንቋና ቃላትን በትክክለኛዉ መንገድ መጻፍና መጠራት ይኖርብናል፣ ከግእዙ ጋር ያለዉን አንድነት ማስጠበቅ ይኖርብናል እንጂ የሌላዉን ብቻ እያገነንና እየጠበቅን ያራሳችንን የምናጥላላና የምንንቅ ከሆነ በሂደት ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊነታችንን አተን ያልሆነዉን ሆነን ልንገኝ እንችላለን::

ወደ ራሳችን ቃለትና ፊደል ስንመጣ ድኅነትና ድህነት ሲጠሩ ድምፃቸዉ ተመሳሳይ ቢሆንም ትርጉማቸዉ ግን እንደ እንግሊዘኛዉ የማይገናኝ ነዉ:: ይኸዉም ድኅነት ከመዳን ጋር የተገናኘ ሲሆን፤ ድህነት ደግሞ ከችግር የተያያዘ ነዉ:: ይህም የሚያሳየን ፊደላትን ብንቀንስ ቃላትንም ማጥፋት ይኖብናል ማለት ነዉ:: ይህ ደግሞ በቅንና በእዉነተኛ ሕሊና ለሚመላለስ ሰዉ የፊደል መቀነስ ዓላማዉ ሌላ መሆኑን ነዉ የሚያሳዉቀን:: ሌላ ደግሞ «known» የሚለዉን (ክኖዉን) ብለን አናነብም «nown (ኖዉን) ብቻ ብለን አንጽፍም:: ከዚህ በተጨማሪ ለብዙ «people» ብለን

የምንጽፈዉን «peoples» ብለን አንጽፍም፤ ምክንያቱም እንደ ሕግ ተደንግጓልና:: ወደ ኢትዮጵያዊ ቋንቋችን ዐማርኛ ስንመጣ ግን ለምሳሌ መላክ(መልአክ) ለአንድ ብዛት ሲሆን ለብዙ ደግሞ መላእክት ይባላል:: ቀሳዉስት ለብዙ ሲሆን ቀሳዉስቶች ተብሎ እንደገና በስህተት ይባዛል:: ነገር ግን «ለምን መላአክቶች ተብሎ ይጻፋል? ለምን መልአክት ተብሎ በትክክሉ አይጻፍም? ለምን ቀሳዉስት ተብሎ አይጻፍም? ለምን ትርጉም የሌለዉ ቀሳዉስቶች ይባላል? ለምን ቤተክርስቲያኖች ተብሎ ይጻፋል? ለምን አብያተክርስቲያናት አይባልም?... ወዘተ» ተብሎ አስተያየት ሲሰጥ «መላእክቶች ተባለ መላእክት ያዉ አንድ ነዉ፤ ቀሳዉስት ተባለ ቀሳዉስቶች ተባለ ያዉ ነዉ፤ ቤተክርስቲያኖች ተባለ አብያተ ክርስቲያን ያዉ ነዉ፤ ዝም ብላችሁ ወግ አትጠርቁ» የሚል ምላሽ ነዉ የሚሰጠዉ::

አለማወቅ ወይንም ስንፍና ሌላ ጉዳይ ነዉ፤ ምክንያቱም በሚታወቅ ጊዜ ማስተካከል ይቻላል:: እንዲሁም ስንፍና ሲርቅ ትክክለኛዉን ማስቀመጥ ይቻለል:: ነገር ግን እያወቁ የራስን ፊደልና ቋንቋ ማቃለልና ከዛም ባለፈ ማጥላላት እንዲሁም የራስ ፊደል እያለና አስፈላጊ ቅጥያዎችንና ጭረቶችን ጨምሮ ምሉዕ አድርጎ መጠቀም እየተቻለ በባዕዳን ፊደል መጠቀምና የእነሱን ማጋነንና ማድነቅ የሚያሳየን በተዝዋዋሪ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችና ጠላቶች መሳሪያ መሆንና የራስ ማንነትን መካድና የሌላ ጥገኝና ባሪያ መሆንን ነዉ:: በእዉነትና በቅንነት ከተመለከትን በሚጠብቁትና በሚላሉት ፊደላት ላይ የተለየ ምልክት ወይንም ጭረት በማሳየት ልዩነት እንዲኖራቸዉ ከተደረገና ባለዉ ፊደል ላይ ለተጨማሪ ድምፆች ቅጥያ ማድረግ ከተቻለ የኢትዮጵያ(የግእዝ) ፊደል ለማንኛዉም ቋንቋ ሊያገለግል ይችላል:: «አዉቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም» እንደሚባለዉ በጥመት የተሞላ ሕሊና የያዘና ለጥፋት የተሰለፈ ሰዉ አንድ ሲደመር አንድ ሁለት መሆኑ ቢታወቅም፤ ይህን እዉነት ለመቀበል ሕሊናዉ ይተናነቀዋል እንጂ ሙሉ እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም::

እኛ ኢትዮጵያዉያን ስንፍና እንደሌለብን ደግሞ ይኸዉ በራሳችን በኢትዮጵያዉኛ ቋንቋ (በብሔራዊ ቋንቋችን በዐማርኛ) እንደ ቻይና፣ ጃፓን፣ ሩሲያ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳኝ፣ ዐረብ አገራት እንደ መሳሰሉት አገራት መማር ስንችል፤ በባዕዳን ፊደልና ቋንቋ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም ዉስጥ እንማርበታለን፤ እንዲሁም የስራ ቋንቋ እናደርገዋለን:: ችግሩ ለራስ የሚያስብና የሚቆረቆር አካልና ግለሰብ መጥፋቱ ነዉ እንጂ በእግዚአብሔር እዉነታ ስንመለከት እኛ ኢትዮጵያዉያን በእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት የምንመላለስ ስለሆነ ሌላዉን ዓለም ከዲያብሎስ መንግሥት ሥርዓት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት መመለስ ሲገባን፤ በተቃራኒዉ ራሳችንን ወደ ዲያብሎስ መንግሥት ሥርዓት ያስገባንና የዲያብሎስ ስራ ፈጻሚና አስፈጻሚ ሆነን ተገኝተናል:: በዚህም ምክንያት ማንነታችንን አተን በተቅበዘበዝና ትስፋ ቢስ በሆነ ሕይወት በመከራና በስቃይ ሕይወት ዉስጥ እንመላለሳለን:: ስለ ዓመፃችን፣ ስለ ክህደታችንና ስለ ርኩሰታችን ደግሞ ዋጋ እየከፈልን እንገኛለን::

ቀደም ያሉት ኢትዮጵያዉያን በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርት የተማረ ኢትዮጵያዊ ብዙም ስላልነበረ በባዕዳን ፊደልና ቋንቋ ቢማሩ ብዙም ሊያስገርመን አይችልም:: አሁን ግን እንኳን ለኢትዮጵያዉያን ይቅርና ለዓለም የሚተርፉ ብዙ ምሁራንና አዋቂዎች እያሉ በራሳችን ፊደልና

በኢትዮጵያዉኛ(በዐማርኛ) ቋንቋችን አለመማራችን ግን እጅግ ያስገርማል፤ ያሳዝናልም! ለነገሩ እንኳን ይህን የሚያስብ የመንግሥት አካል ሊኖር ቀርቶ ይኸዉ የሕወሓት(ኢሕአዲግ) የተባለዉ ቡድን በክርስቲያኖች(በዐምሓሮች) ላይ ባለዉ ጥላቻና በቀል ምክንያት «ይህ የዚህ ቋንቋ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነዉ» በማለት ዐማርኛን ቋንቋ ከመማሪያነትና ከስራ ቋንቋነት እንዲወገድ አድርጓል፡፡ ይኸም የሚያሳየን ይህ የዓመፃ ቡድን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማስጠበቅ ሳይሆን በተጠና እቅድ በሂደት ከሰማኒያ በላይ መንግሥታት በኢትዮጵያ ዉስጥ እንዲፈጠሩ አድርጎ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ዓላማ ነዉ፡፡ ነገር ግን ይሞክራሉ እንጂ ማንም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፣ ማንነቷን፣ ቅርሷን፣ አንድ የሚያደርጋትን ቋንቋ ሊያጠፋ አይችልም፡፡ ይልቁኑ በዚህ ተግባር የተሰለፉ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ ዓለም ያሉ የዓመፃ ልጆች በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ራሳቸዉ በእግዚአብሔር በተለያየ ቁጣ ይጠፋሉ፡፡ ስለ ዓመፃ ተግባራቸዉም በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍሉበታል፡፡

እዚህ ላይ እግረመንገዴን የማነሳዉ ቀድሞ ዐማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ ያልሆኑ ኢትዮጵያን ወገኖቻችን ወላጆች ነበሩ፡፡ በቋንቋዉ ሐሳባቸዉን ለመግለጽ ተቸግረዉ በልጆቻቸዉ አስተርጓሚነት ይገልጹ ነበር፡፡ አሁን ግን ልጆች ዐማርኛን ቋንቋ እንዲጠሉትና በትምህርት ቤት እንዳይማሩበት በመደረጉ ምክንያት ልጆች በተቃራኒዉ ወላጆቻቸዉን የዐማርኛ አስተርጓሚ እያደረጉ የሚጠቀሙበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ በእንግሊዘኛዉ ለመማር ያልተጸየፈዉ ትዉልድ ዘረኞችና ጎጠኞች በፈጠሩት የጥላቻና የበቀል ተግባር ይኸዉ በብሔራዊ ቋንቋዉ በኢትዮጵያዉኛዉ ቋንቋ ዐማርኛ መነጋገር፣ በመማር፣ መስራት ትቶ በጎጡ ቋንቋ ብቻ ይነጋገራል፣ ይማራል፣ ይሰራል፡፡ ይህን የክፋትና የተንኮል እንዲሁም የበቀል ተግባር ያመጡት ግን የራሳቸዉ ልጆች እንዲነጋገሩበት፣ እንዲማሩበት፣ እንዲሰሩበት በማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያዉኛ ቋንቋ(ዐማርኛ) መናገር፣ መስራት ካልቻለ ለአገር መሪነትና ለከፍተኛ የሥልጣን እርከን አይደለም የአንድ ቀበሌ ኃላፊ እንኳ እንደማይሆኑ በደንብ ያዉቁታልና፡፡ ሌላዉን ግን እንደ ወገን አልቆጠሩትምና ዱዳ አድርገዉ አስቀርተዉታል፡፡ ይህም ምን ያህል መሰሪ መሆናቸዉን ነዉ የሚመሰክርባቸዉ፡፡

አሁን ያለነዉ ትዉልድ ግን ወደራሳችን ማንነት ልንመለስና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ የተነሱትን የአገር ዉስጥ ሆነ የዉጭዉ ዓለም የዓመፃ ልጆች ተግባር ልንቃወምና «እናንተን አንከተልም» በማለት ልናሳፍራቸዉ ይገባል፡፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወተን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን ከተመላለስን ግን ለዲያብሎስ እንደራሴዎች (መሪዎች)፣ ባለሟሎች (ባለሥልጣናት)ና ወዶች(ካድሬዎች) እንደ ልባቸዉ ስለምንሆንና ስለሚጋልቡን የዓመፃ ስራ ፈጻሚና አስፈጻሚ ሆነን ነዉ የምንቀረዉ፡፡ በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያዉያን ለዓለም እንተርፋለን እንጂ ዓለም ለኛ ሊተርፍ አይችልም፡፡ ስለ ቁሳቁሱም ሥልጣኔ ቢሆን ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን እግዚአብሔርን ይዘዉ ስለነበረ የሚንቀሳቀሱት ዓለምን የሚያስንቅ ስራ ሰርተዉ አልፈዋል፡፡ አሁንም እግዚአብሔርን ከያዝን ለዓለም የሚተርፍ ሥልጣኔ ልናሳይ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የማያምኑ አሕዛብ እንኳ ጥረታቸዉንና ትጋታቸዉን እግዚአብሔር ተመልክቶ እዉቀትንና ጥበብን

ካደላቸዉ፤ እኛ እግዚአብሔርን ይዘንና መሪያችን አድርገን ለሕዝብ የሚጠቅም የተለያየ የእዉቀትና የጥበብ ስራ እንዴት አንሰራ!? እጅግ እንሰራለን።

ዓለም ግን በተሰጠዉ እዉቀትና ጥበብ ራሱንና ሌላዉን የሚያጠፋበትን መሳሪያና ስለ ዓመፃዉ ዋጋ የሚከፍልበትን ነዉ የሰራዉ። እኛ ግን ከጉስቁልና ሕይወት የምንገላገልበትንና እግዚአብሔር የሚከብርበትን ስራ ነዉ የምንሰራዉ፤ የምናሰራዉ። በአሁን ትዉልድ ይህ እዉቀትና ጥበብ ለእኛ ኢትዮጵያዉያን ተሰቶ ቢሆን ኖሮ እጅግ የከፋዉን የዓመፃ ስራ ነበር እንሰራ የነበረዉ። ነገር ግን እግዚአብሔር የዉስጣችንን ዓመፃ ያዉቃልና ለሌሎች የፈቀደዉን እዉቀትና ጥበብ ስለ ጠማማነታችንና ስለ ክህደታችን ከእኛ ገድቦታል። እንደዚያም ሆኖ እኛ እስከ አሁን ድረስ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባራችን ጸንተንና በንስሐም ላለመመለስ ሕሊናችንን አደንድነን እንገኛለን። የእግዚአብሔር እዉቀትና ጥበብ ተትረፍርፎ ሊሰጠን የሚችለዉ ከዓመፃችን ሙሉ በሙሉ ተመልሰን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስንመላለስ ብቻ መሆኑን አሁን ያለዉ ትዉልድ ሊያዉቀዉና ሊያስተዉለዉ ይገባል።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ እዚህ ላይ ሌላዉ ለማንሳት የምፈልገዉ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የተሰማሩና እንዲሁም ቅኔዉን ጭምር በደንብ የሚያዉ አገልጋዮች ጭምር የሚጽፉት አጻጻፍ የተለያየ ነዉ። ለምሳሌ ግእዝ ግዕዝ፣ አመጻ ዐመፃ ዓመፃ ዐመጻ፣ሥዕል ስዕል፣ ርኩስ ርኩስ እግዚአብሔር እግዚአብሄር፣ ንጉሥ ንጉስ፣ ባሕርይ ባህሪ ባህርያ ባህሪ፣ ጠጉር ጠጉር ጸጉር፣ መጻሕፍት መጽሐፍት፣ ሕፃን ህጻን ህፃን፣ ማኅበት ማህብር ማሕበር፣ … ወዘተ» ብለዉ በተለያየ ፊደላት ይጽፋሉ። አብዛኛዉ ቃላት ከግእዝ ከወጡ ለምን አንድ ዓይነት አጻጻፍ አይኖርም?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፡ አንድ መታወቅ ያለበት በመንግሥት ይሁን በቤተክህነት በኩል ለግእዝ ቋንቋ ባለቤት የለዉም። ቋንቋን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ በቆራጥነት የተሰለፈ አካል የለም። ምክንያቱም ትኩረትና ቅድሚያ የተሰጠዉና እየተሰጠ ያለዉ ለዘመናዊ ትምህርና ዘረኝነትና ጎጠኝነት የሚያስፋፋ የራስን ታሪክና ቅርስ በሚያጠፋ ተግባር ላይ ነዉ እንጂ ለራስ ቅርስና ታሪክ አይደለም። እንዲሁም በመሪነት ላይ ያሉ አስመሳይ አገልጋዮች፤ ትዉልዱ ወደ ራሱ እዉነተኛ ማንነት ከመጣ ገበናቸዉ ስለሚጋለጥና የጨለማ ተግባር ፈጻሚና አስፈጻሚ መሆናቸዉ ስለሚጋለጥባቸዉ የራሳቸዉን የስዉር ተግባር ነዉ የሚሰሩት።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** አንድ ዓይነት አጻጻፍ የማይታየዉ፤ በመንፈሳዊ ትምህርት ዉስጥ አንደኛ አንድ ዓይነት ወጥ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ የለም። ሁለተኛ ደግሞ ቅኔዉን ሆነ ሌላዉን ትምህርት ሲማሩ ትኩረት የሚሰጡት ለቃላቱ ብቻ ስለሆነ ፊደላቱን በአግባቡ አይጠብቁም። ሦስተኛ ደግሞ በተለያየ መልኩ ቢጻፍ ተቀባይነት ስላለዉ እያወቁም ይሁን ሳያዉቁ እንደፈለጉት ስለሚጽፉ ነዉ። አራተኛ ደግሞ የተሳሳተዉን አጻጻፍ የሚያርምና ስህተት መሆኑን የሚገልጽ አካል ወይንም ተቋም ስለሌለ ነዉ። ባጠቃላይ ለግእዝ ቋንቋ ሆነ ለፊደሉ ትኩረት የሚሰጥ ግለሰብ ሆነ አካል ባለመኖሩ ነዉ ። አሁን ያለነዉ ግን ከግእዙ በቀጥታ የተወሰዱ ቃላት እንደፊደላቸዉ ለኢትዮጵያዉኛ

ዉ (ለዐማርኛዉ) ቋንቋ ቢዉሉ፣ ሌሎች ደግሞ የሚመለከታቸዉ ግለሰቦች ሆኑ አካላት ተቀናጅተዉ ቃላቶችን ሆነ ፊደላት አንድ ዓይነት እንዲሆንና ትዉልዱም በተመሳሳይ መንገድ እንዲጠቀሙበት የሚያስችል አንድ የተለየ ተቋም ቢዘጋጅና ግእዝ ቋንቋና የፊደል አጠቃሙን በሚገባ የሚያሳዉቅና የሚያስጠበቅ ከመንግሥትና ከቤተክህነት በጋራ የተሰየመ አካል ቢዘጋጅ ስለቋንቋዉ ሆነ ስለ ፊደሉ መፍትሔ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአብነት ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚሰጠዉ የትምህርት አሰጣጥ ዘመኑን የዋጀና ወጥነት ያለዉ እንዲሁም ወንጌል የበለጠ የሚስፋፋበትና ትዉልዱም ዘመናዊዉን ትምህርት በተጓዳኝ የሚማርበት መንገድ ቢፈጠር ዘመኑን የሚዋጅ ምሉዕ የሆነ አገልጋይ ማፍራት ይቻላል፡፡

በመጨረሻም ስለ ግእዝ ቋንቋና ቃላት ለመግለጽ የምፈልገዉ አብዛኛዉ የዐማርኛ ቃላት ከግእዝ የወጣ ነዉ፡፡ ይህም በተዝዋዋሪ ግእዝ በዐማርኛ ቋንቋ እየተጠበቀ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ለዚሁ ማሳያ የሚሆን አንድ ምሳሌ አቀርባለሁ፡፡

| | ግስ | ዘመድ ዘር | ባዕድ ዘር | ምዕላድ ዘር | ቅጽል |
|---|---|---|---|---|---|
| ግእዝ | ኀተመ | ኅትም | ማኅተም | ኅትመት | ኀታሚ |
| ዐማርኛ | አተመ | እትም | ማኅተም | ኅትመት | አታሚ |

» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሦስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: አንዳንድ ሰዎች «ሕወሓት(ኢሕአዲግ) ለሕዝቡ ብዙ ልማት ሰርቷል፤ ለዚህም ማሳየዉ የመንገድና የሕንጻ ግንባታ፤ የመብራትና የስልክ ማስገባት፤ የጤና፣ የትምህርት፣ የፋብሪካ ተቋም ማስፋፋት፣ የግድብና የመስኖ ስራ... ወዘተ፤ ዘርፈ ብዙ ተግባር በተጨባጭ ይታያል:: ከዚህ በላይ ምን እንዲሰራ ነዉ የሚፈለገዉ?» የሚሉ አሉ:: ለዚህ ያሉትን አስተያየት ቢገልጹልን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት በየትኛዉ ዘመን ያሉ መንግሥታት ደረጃዉና መጠኑ ቢለያይም ለሥጋችን የሚጠቅም ተግባር ፈጽመዋል፤ አስፈጽመዋል:: እንኳን ኢትዮጵያዉያን መሪዎች ቀርቶ ፋሽስት የኢጣሊያ መንግሥት የነበረዉ ሳይቀር ለሥጋችን የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባሮችን ፈጽመዋል:: አሁን ያለዉ መንግሥትም ከላይ የተገለጹትን ተግባሮች መፈጸሙ በማንም ዘንድ የሚታወቅ ይመስለኛል:: ነገር ግን በተለየ ሁኔታ የምናገነዉና የምናደንቀዉ አይደለም:: ምክንያቱም ማንም መንግሥት እርዳታ ካገኘና ገቢ መሰብሰብ ከቻለ እንዲሁም ሰላም ከሆነ ሊሰራቸዉ የሚችልና ሊሰሩም የሚገባቸዉ ነዉ:: ይልቁኑ በእርዳታ የተገኘዉን ገንዘብና ከሕዝብ በተለያየ መንገድ የተሰበሰበዉ ገንዘብ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲዉል ተደርጎ ቢሆን ኖሮ አሁን ከተሰራዉ ግንባታና ልማት በላይ የበለጠ ይሰራ ነበር:: ነገር ግን ጥቂቶች በዘመድና አዝማድ፣ እንዲሁም በዘርና በጎጥ ተቧድነዉ የሥርዓቱ ደጋፊና አስፈጻሚ፣ አባል በመሆናቸዉ ምክንያት ወደ ልማት ሊለወጥ የሚገባዉም ገንዘብ በተለያየ አቋራጭ መንገድ ለግል መጠቀሚ ስላደረጉትና ከዚያም ዓለፎ አንዳንዶች አገራዊና ወገናዊ ፍቅር የሌላቸዉ ስግብግብና ስስታም ሰዎች፤ የመዘበሩትን ገንዘብ ወደ ዉጭ በማሸሽ ለአገር ግንባታ የሚዉለዉን ገንዘብ ለግላቸዉ አድርገዉታል:: በዚህም አንዳንድ የመንግሥት ቁልፍ ሰዎች ሆኑ ግለሰቦች በአገር ላይ በደል ፈጽመዋል:: በአገር ዉስጥ ያላቸዉን ንብረት ደግሞ በባንክ ብድር በእዳነት እየጠጠቀሙበት ሲሆን፤ አንድ ችግር ቢፈጠር በዉጭ ያስቀመጡትን ገንዘብ ተስፋ በማድረግ ራሳቸዉን ለስደት አዘጋጅተዋል::

እዉነተኞቹ የአገርና የወገን ፍቅር ያላቸዉ አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን ደግሞ በዉጭ ያጠራቀሙትን ገንዘብ በአገራቸዉ ላይ ፈሰስ አድርገዉ የተለያዩ ልማትና ግንባታ እያከናወኑ ራሳቸዉንም ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻቸዉንም እየጠቀሙ ይገኛሉ:: እንዲሁም በአገር ዉስጥም በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችም በንጹህ ላባቸዉና ድካማቸዉ የተለያዩ ልማትና ግንባታ በማከናወን ራሳቸዉንም ወገናቸዉንም እየጠቀሙ ይገኛል:: ከፖለቲከኞች ጋር እጅግ ጓንት ሆነዉ የሚሰሩት ግን በተለያየ መንገድ የሀገሪቱን ሀብትና ንብረት ተቀራምተዉ፣ የሕዝብ ደም እየመጠጡ ራሳቸዉን ግን የተለየ ቦታ በማስቀመጥ አዛዥ ናዛዥ ሆነዋል፤ እንዲሁም ራሳቸዉን እንደ መንግሥት አስቀምጠዋል:: ሥርዓቱንም እስከ መጨረሻዉ ለማስጠበቅ የሚቻለቻዉን ሁሉ ከመንግሥት ጋር በመወገን ይሰራሉ፤ያሰራሉ:: እንደ መንግሥት ማንኛዉንም እርምጃ ለመዉሰድ ወደ ኋላ የማይሉ ናቸዉ:: ከዚህ በተጨማሪ ከመንግሥት ጋር በመሆን፤ አገራዊና ወገናዊ ፍቅር ኖሯቸዉ ለአገራቸዉ ልማትና

ለሕዝቡ መልካም የሚሰሩ ነገር ግን ራሳቸዉን ከፖለቲካዉ ያራቁትንና «እንደ ቦይ ዉኃ ወደሚፈለገዉ አቅጣጫ አንወሰድም፤ እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብለን እንነዳም» የሚሉትን በተለያየ መንገድ ድርጅቶቻቸዉን ያዘጋሉ፤ እርምጃም ያስወስዳሉ። በዚህም ምክንያት እዉነተኞቹና በሀቅ ለመስራት የሚፈልጉ ሰዎች ወይን ይሰደዳሉ፤ ወይን አንገታቸዉን ደፍተዉ በአገራቸዉ ይኖራሉ።

የተለያዩ ልማቶችና ግንባታዎች የሚከናወኑትም አገራዊ ራእይ በያዘ መልኩ ሳይሆን፤ ክልሎች ለወደፊት ነጻ መንግሥታቸዉን ቢያዉጁ ተጠቃሚ በሚሆኑበት መልኩ አድሎና በደል እንዲሁም በቀል በተሞላዉ መንገድ ነዉ። ምክንያቱም ከማንም በላይ ቅድሚያ ተሰቷቸዉ ሊሰሩ የሚገባቸዉ መንገዶች ሆነ ሌሎች ግንባታዎች በዘረኝነትና በጎጠኝነት እንዲሁም «ደጋፊያችን አይደሉም» በሚል የጥላቻ አስተሳሰብ ቅድሚያ ሳይሰጣቸዉ ያልተሰሩ መንገዶችና ግንባታዎች አሉ። እንዲሁም ከዋጋ አንጻር አነስተኛ ወጭ በሚያሶጣ፣ በማኅበራዊ ሆነ በሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ አንዳች ችግር በማያመጡ ቦታዎች ላይ ግንባታ ሆነ ልማት መስራት እየተቻለ፤ «ለወደፊት የምንገነጠል ከሆነ፤ ሊጠቅመን የሚችለዉ ግንባታዉን ሆነ ልማቱን በእኛ ክልል ዉስጥና በአጎራባች ክልል ዉስጥ ከተሰራ ነዉ» በሚል አገራዊና ወገናዊ ባልሆነ አስተሳሰብ ነዉ እየሰሩት ያለዉ። ከዚህ አንጻር ይህ የአሁኑ መንግሥት ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አንዳች ስሜት የሌለዉ ዘረኛና ጎጠኛ መንግሥት መሆኑ ይታወቃል። የሚሰራቸዉ የተለያዩ የልማት ስራዎች «መስራት ስላለብን ነዉ የምንሰራዉ» በማለት ስሜት ሳይሆን «እንዲህ ሰራንላችሁ፣ እኛ ከሌሎች የተለየን ነን፣ እኛን ደግፉ፣ እኛን ምረጡ፣ ሌሎች ግን የተለየ ዓላማ ነዉ ያላቸዉ፣ የብሔር ብሔረስብ እኩልነት የማይምኑ ነፍጠኞችና ትምክተኞች ናቸዉ፤ የክርስቲያን(የዐምሓራዉን) ነፍጠኛ ሥርዓት ለመመለስ የተነሱ የገኘ መደብ ርዝራዦች ናቸዉ፤ ሊደመሰሱ የሚገባ ነዉ... ወዘተ» በማለት ስለሆነ አስተሳሰባቸዉ ሁሉ ቂምና በቀል የሞላዉ ለጨለማዉ ገዥና መንፈስ ፈቃድ የተሰለፉ የዲያብሎስ አገልጋዮች መሆኑን ይመሰክርባቸዋል።

ብዛት ያላቸዉን የከፍተኛ ተቋም ግንባታ ቢከናወንም፤ ዓላማዉ ደረጃዉንና ጥራቱን የጠበቀ የሰዉ ኃይል ለማፍራትና ለስራ ለማብቃት ሳይሆን «ይህን ያህል ሕንጻ በክልላዊ መንግሥታችሁ ሰራንላችሁ» በማለት ለፖለቲካ ፍጆታ እንጂ በአገራዊ ራእይና ለሕዝቡ በማሰብ አይደለም። ለዚህም ነዉ እንደ ዉትድርና ማሰልጠኛ ካምፕ ለተማሪዎች አመቺ ባልሆነበት ቦታ ላይ ጭምር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተገንብቶ ቀድሞ «ልጄ ነጥብ መጣለት» ብሎ የሚደሰት ወላጅ፤ አሁን ደግሞ «የት ይሆን የሚመደበዉ?» በማለት ጭንቀት ዉስጥ ሊገባ የቻለዉ። እልም ያለ ደጋ ዉስጥ ያደገና የኖረን ተማሪ እልም ያለ በረኃ ዉስጥ እንዲማር ማድግ፤ ተማሪዉን አንድም መቅጣት ነዉ ወይንም እንዳይማር ማድረግ ነዉ። በተቃራኒዉ ደግሞ እልም ያለ በረኃ ዉስጥ የኖረና ያደገ ሰዉን እልም ያለ ደጋ ዉስጥ እንዲማር ማድረግ፤ ተማሪዉን አንድም መቅጣት ነዉ ወይንም እንዳይማር ማድረግ ነዉ። ነገር ግን ባደገበትና በኖረበት አየር ጠባይ ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ እንኳ ምደባ ቢደረግ ቅንነት ያለዉ አመዳደብ ይሆን ነበር።

መንግሥት «የዚህን ያህል ተማሪዎች ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም አበቃዉ» ለማለት እንጂ፣ በትክክል ጥራቱንና ደረጃዉን የጠበቀ የትምህርት አሰጣት ስለመሰጠቱ አንደች ስሜት የሌለዉ፣ ይልቁኑ የገቡ ሁሉ ፈተና አለፉ አላለፉ ተመርቀዉ እንዲወጡና «የዚህን ያህል ተማሪዎች አስመረኩ» ብሎ ለማሰራት የሚፈልግ ነዉ። እያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠዉን ትምህርት በአግባቡ አጥንቶና ተፈትኖ ዉጤታማ እንዲሆን ፍላጎት የለዉም። ተመርቆም የወጣዉ ተማሪ ስራን የሚያገኘዉ የድርጅቱ አባልና ካድሬ ከሆነ ነዉ እንጂ በራሳቸዉ ጥረት የሚቀጠሩ ጥቂቶች ናቸዉ። ሌላዉ አስገራሚዉና አሳዛኝ ተግባራቸዉ ደግሞ አንድ ከከፍተኛ ተቋም ተመርቆ፣ ምንም ያልተማረ ሰዉ ሊሰራዉ በሚችል ተግባር ላይ ሲሰለፉ እንደታላቅ ስኬት ተቆጥሮ በየብዙኃን መገናኛ መታየቱና መነገሩ ነዉ። እሱም ስራ ቢሆን የሚገኘዉ በአነስተኛና ጥቃቅን ተደራጅቶ ካለፍላጎቱ በተጽህኖ የፖለቲካ አባልና ደጋፊ ሆኖ ከተገኘ ነዉ።

በሰዉ ችግርና ጉድለት እየገባ «የስራ እድል የምታገኘዉ የእኛ አባልና ደጋፊ ከሆንክ ነዉ» በማለት ትዉልዱ ካለፍላጎቱ ሕሊናዉ የማይቀበለዉንና የማይደግፈዉን የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሥርዓት በግድ እንዲቀበል መደረጉ የሚያሳየን፣ አሁን ያለዉ መንግሥት ምን ያህል ጨካኝ መሆኑን ነዉ። ምክንያቱም ለመኖር ያቃተዉ ሰዉ እንኳን ሰፊ አገራዊ ራእይ ሊኖረዉና ሊይዝ ቀርቶ ከዕለት ኑሮዉ ዉጭ እንዳያስብ በመደረጉ፣ ይኸዉም «ለድጋፍ ሰልፍ ዉጣ» ሲባል ይወጣል፣ «ለተቃዉሞ ሰልፍ ዉጣ» ሲባል ይወጣል። ከዛም ባለፈ በራሱ ላይ የሞት ሆነ የጉዳት ዉሳኔ ተወስኖበት «ለእኔ ተፈረደልኝ» በማለት በመስቀል አደባባይ ይወጣል። ለዚሁ ማሳያ ደግሞ በብዙ አስራ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ «እኛ ኢትዮጵያዉያን አይደለንም» በማለት ሃይማኖት በሆነዉ በኢትዮጵያዊነታቸዉ ላይ ዓመፃና ክህደት የፈጸሙት ኤርትራዉያን ወገኖቻችን በከንቱ ደማቸዉ ከፈሰሰና ከረገፉ በኋላ፣ «ባድሜ ለእኛ ተወሰነልን» በማለት በመስቀል አደባባይ በዘፈንና በዳንኪራ የተገለጸዉ የደስታ ሰልፍ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል። ይህም የሚያሳየዉ መንግሥት በካድሬዎቹና በሰላዮቹ አማካይነት ሕዝብን እያስጨነቀና ተጽህኖ እያደረሰ እንደሚፈልጋቸዉ እንደሚያደርግ ነዉ። ለዚህም ነዉ በአቶ መለስ አስከሬን(ሬሳ) የፓለቲካ ስራ የተሰራዉና «ሕዝቡ ኢሕአዴግን ስለ ወደደና ምርጫ ስላደረገ ነዉ በተለያየ አደባባይና መድረክ ኀዘኑን በዚህ መልክ የገለጸዉ» በማለት ባለሥልጣኖቹ መግለጫ የሰጡትና «ከአቶ መለስ በላይ ለሕዝቡ እንዳርግበታለን» በማለት ያላገጡት። አላስተዋሉትም እንጂ በተዘዋዋሪ «እርሱ በሳማ ገርፏችሁ ከሆነ እኛ ደግሞ በእሾህ ልክ እናጋባችኋለን» ማለታቸዉ ነዉ። ወይንም «ምንም የምታመጡት ነገር የለም እንደፈለግን እናደርጋቸዋለን» በማለት መታበያቸዉን ያሳያል።

ይህ የኢሕአዴግ መንግሥት የተለያየ ግንባታ ያከናወነዉ «እንዲህ ሰራን» ብሎ ለማሰራትና የተለያዩ ብድሮችን ለማግኘት፣ እንዲሁም ከንቱ በሆነ ሥጋዊ መጠበብ የሕዝብ ድጋፍ በማግኘት የሥልጣን እድሜዉን ለማስረዘምና በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ለማበልጸግ ነዉ እንጂ በኢትዮጵያዊነት ስሜት «በአራቱም ማዕዘን ያሉ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ናቸዉና ከጉስቁልና ሕይወት እንዲገላገሉ ማድረግ ያለብንን እናድርግ » በሚል ስሜት አይደለም። ለዚሁ ማሳያ ከብዙ ጥቂቶቹን ብገልጽ ከሰባት ዓመት በፊት በቋንቋ ሽፋንና «ክልልና የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት»

የሚል ሽፋን «ኢትዮጵያን መከፋፈልና ማዳከም ብሎም ማጥፋት» የሚለዉን የጨለማ ገዥ ዓላማ ለማሳካት፤ እያንዳንዱ ክልል የራሱ ከተማ እንዲኖረዉ ሲደረግ «የኦሮሞ ክልል(ኦሮሚያ)» በመባል የሚታወቀዉን ክልል እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚሄዱትንና እንደፈለጉ የሚያሽከረክሯቸዉን አስመሳይ ሰዎችን፣ የተለያየ የይስሙላ ሥልጣን ሰተዉ «አንተ የክልልህ ፕሬዝዳንት(ንጉሥ) ሆነሃል፤ እናንተ ደግሞ የንጉሥ ሹሞች ሆናችኋል:: የአሁኑ የክልል መንግሥታችሁ የወደፊት ነጻ መንግሥታሁ ላይ ሌላ ተጽህኖ እንዳይመጣባችሁ ፊንፊኔ ዋና ከተማችሁ ናት» በማለት፤ ሌላዉን እያጃጃሉ የራሳቸዉን ስዉር ዓላማ ሲያስፈጽሙ ቆይተዉ፤

የሚፈልጉትን ከፈጸሙ በኋላ ደግሞ፤ «ያዉ ሕሊናችሁን መገለባበጥ አትቸገሩምና አሁን ደግሞ :- የራሳችን የክልል መንግሥት ያስገፈልገናልና አዳማ ከተማ የክልላዊ መንግሥታችን ዋና ከተማ ይሁን በሉ:: አዲስ አበባ ያሉት ሰራተኞቻችሁን ደግሞ በአርባ አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ከፊንፊኔ ወደ አዳማ(ናዝሬት) የምትደርሱበት ዘመናዊ ባቡር አሁን ይሰራላችኋል:: ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችም ይጠበቁላችኋል በማለት አሳምኗቸዉ:: «እምቢ የሚሏችሁንና የሚከራከሯችሁን ደግሞ የኦነግ ደጋፊና አባል ናቸዉ በማለት አስመቷቸዉ» ብለዉ ከአዲስ አበባ ካስወጡ በኋላ፤ በ97 ምርጫ በቅንጅት ሲዋረዱና አንድ ሰዉ እንኳ በምርጫ ማሸነፍ ሲሳነዉ:: «ለካስ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ነዉ የሚሸነግለን፣ ልቡ ግን ከተቃዋሚዎች ጋር ነዉ፣ ስለዚህ የመገንጠል ዓላማ ካላቸዉ ቡድኖች ጋር ተደራድረን ማስፈራራትና ቅንጅት የተባለዉን በተለጣፊ ድረጅት ልናጠፋና ልንደመስሰዉ ይገባል፤ ደጋፊዉንም በተለያየ መልኩ ልንበቀላቸዉ ይገባል» በማለት የተለያየ የግፍና የጭከና ተግባረ ፈጽመዋል:: የብዙዎችን ሕይወት አበላሽተዋል:: በአራቱም ማእዘን የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊ በተፈጸመባቸዉ ግፍና በደል በመማረር «ነጻ ምርጫና ድጋፍ መስጠት ይቻላል ተብሎ በግልጽ ስለተነገረ ነዉ ሐሳባችንን በነጻ የገለጽነዉና የምንፈልገዉን የመረጥነዉ እንጂ፤ መንግሥት ሰብአዊነት የማያዉቁ የተለያዩ ልዩ የጥቃት ኃይሎች ማዘጋጀቱንና ማንነታቸዉ እንዳይታወቅ ደግሞ በተለያየ ቀን እንዲፈራረቁ በማድረግ ድብደባና ግርፋት እንዲሁም ግድያ እንደሚያደርሱብን፣ ቂም ተይዞብን የተለያየ ተጽህኖ እንደሚጠብቀን ብናዉቅ ኖሮ በአንደበታችን ሆነ በተግባራችን የምንናገረዉና የምናከናዉነዉ ነገር አይኖርም ነበር» በማለት ሲናገሩና ሲያማርሩ ታይቷል፤ ተደምጧል::

ታዲያ ቀደም ብሎ «የክልላችሁ ዋና ከተማ አዲስ አባባ አይደለም» በማለት ወደ ናዝሬት እንዲገቡ የተደረጉትን ደግሞ፤ «በሉ በለመዳችሁት የመገለባበጥ ጠባይ አሁን ደግሞ :-የእኛ የክልላችን መንግሥት ዋና ከተማ ፊንፊኔ ነዉ መሆን ያለባት እንጂ አዳማ አይደለም ብላችሁ፤ ወደዚሁ አዲስ አበባ መጣችሁ ይህን የቅንጅትን ቡድንና ደጋፊን ማጥፋትና ማዳከም አለባችሁ፤ በእኛ ስር የሚሽከረከር ማንኛዉንም ሥልጣን እንሰጣችኋለን፤ ዋናዉ አድርጉ የምትባሉትን ማድረግ ነዉ፤ ተበቀሉ የምትባሉት በመበቀል ነዉ፤ ስሩ የምትባሉትን መስራት ነዉ» በማለት እንደገና ሕሊናቸዉን እንዲያገለባብጡ አስደርገዉና ቀድሞ ቃል የተገባዉ የመንገድና የባቡር ... ወዘተ ስራዎች ትተዉ ለሥልጣን እድሜዉ ማራዘሚ መጠቀሚያ ማድረጋቸዉ የሚያሳየን ምን ያህል ተንኮለኛና መሰሪ

መሆናቸዉን ነዉ። ንግግሮቻቸዉ ሁሉ ለመደለያና ለራስ ስዉር ዓላማ ማሳኪያ እንጂ ለአገር ልማት የታሰበ አለመሆኑን ያሳያል።

እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገዉ ምርጫ 97 የሕወሓት ኢሕአዲግ መንግሥት ገበናዉ የተጋለጠበትና የተዋረደበት ነበር። ቅንጅትና ኅብረት የተባሉ ሁለት ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ዓላማቸዉና ግባቸዉ ምንም ይሁን ምን በጋራ ተሰልፈዉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነታቸዉ አምነዉ መንግሥት እያሰራ ያለዉን የተንኮልና የበቀል እንዲሁም የጥፋት ተግባር በመግለጻቸዉ፣ ለሕዝቦች እኩልነት መነሳታቸዉ፣ ፍትሐዊ ሥርዓት እንዘረጋና አድሎና በደል እንዳይፈጸም እናደርጋለን በማለታቸዉ፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር እናደርጋለን እንዲሁም እያንዳንዱ ሰዉ እንደ እዉቀቱና ብቃቱ ነዉ በኃላፊነት ሊቀመጥ የሚገባዉ እንጂ በፖለቲካ መስፈርትና ሕሊናን በመሸጥና እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ወሰዱት አቅጣጫ በመሄድ አይሆንም በማለታቸዉ፤ ከዚህ በተጨማሪ «ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመጣፋት እንዲሁም የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ለመቀነስና ለማጠፋት በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተመሰረተዉና የከፋፍለህ ግዛ ኢትዮጵያን አዳክም ብሎም አጥፋ የሚለዉ «የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል ድረስ ነዉ» በማለት የታወጀዉ እንኳን ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ቀርቶ የኢትዮጵያ ዋና ጠላት እንኳ ያስበዋል ትብሎ የማይጠበቅ አንቀጽ በሕገ መንግሥቱ የሰፈረዉ የራሳቸዉን ስዉርና በቀል ተግባር ከፈጸሙ በኋለ አገሪቷ እንድትበታተን ለማድረግ ነዉ» በማለት በማጋለጣቸዉ ... ወዘተ ምክንያት በአራቱም ማዕዘን ያለዉ ሕዝብ የሕወሓት ኢሕአዲግን መንግሥት አንቅሮ እንዲተፋዉና በምራጫም በብዙ ቦታ እንዲሸነፉ አስደርገዋል።

መሰሪዉና ተንኮለኛዉ እንዲሁም በቀለኛዉ መንግሥት ግን ሽንፈቱን በጸጋ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም። ይልቁን «ትንሽ ሕዝቡ ሆነ ዓለም ይታዘበኛል» ሳይል፤ የመሰሪያ ኃይል ባለቤትን አዛዥ ሆኖ ሳለ እንዲሁም እንደፈለገዉ የሚያሽከረክራቸዉና እንደ ድምፅ ማጉያ የሚጠቀምባቸዉ ምርጫ ቦርድ ሆነ ታዛቢዎች የእርሱ ዋና መሳሪያ ሆነዉ እያለ፤ «ተቃዋሚ ድርጅቶች አጭበረበሩኝ እንጂ አላሸነፉኝም፣ ምርጫ ይደገምልኝ?» በማለት ካለ ሃፍረት እንደ ልቡ የሚጋልባቸዉንና በአንደበታቸዉ የሚፈነጭባቸዉን ምርጫ ቦርድን በማዘዝ ምርጫዉን አስደገመ። ከዛም ሕዝቡን በማስፈራራትና በመሸንገል እንዲሁም የተለያዩ የጥላቻ ቅስቀሳ በማድረግ የተዋረዱበትን ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንደገና እንዲመረጡና በክልልና በተወካዮች ምክር ቤት እንዲገቡ አደረገ።

ሌላዉ ደግሞ በአራቱም ማዕዘን ያሉ ሕዝቦች የሚኖሩባትና ሁሉንም ኅብረተሰብና ማኅበረሰብ ልትወክል በምትችለዉ አዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ በቅንጅት በመሸነፋቸዉና ይህም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም፤ ዉጤቱንም በጸጋ ለመቀበል በጥላቻና በበቀል የተሞላዉ ሕሊናቸዉ ቢተናነቀዉም፤ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በቅርበት የተከታተሉትና ሽንፈቱም በከፍተኛ ልዩነት በመሆኑ መሸነፋቸዉን አምነዉ ነበር። ነገር ግን ለእዉነት ሳይሆን ለጥፋት የቆሙ ቅጥረኞችና ዓመፀኞች ስለነበሩ ሕዝቡንም የድርጅቶቹን አባላትንም የራሳቸዉ መሰሪ ምክንያት አዘጋጅተዉ በመግደል፣ በማሰር፣ በማሳደድ፣ በመጨፍጨፍ ተበቅለዉታል። በዚህም ተግባራቸዉ

አሸናፊ በመምሰል አገሪቱን በኃይላቸዉ ሊመሩ ችለዋል፡፡ እኛም እግረመንገዳችንን ስንት አስመሳይ ተቃዋሚ ይመስሉ የነበሩ ሰዎች ለገንዘብና ለጥቅም ሕሊናቸዉን ሲሸጡ ለማየትና ለመታዘብ ችለናል፡፡ እንዲሁም ሰዎች ለራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት እንጂ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ያልካዱ መሆኑን ልናስተዉል ችለናል፡፡ በዚህም ሰዎች ተስፋ ማድረግ ያለባቸዉ አንድ ፈጣሪ እግዚአብሔርን እንጂ ፍጡሮቹን ሥጋ ለባሽ ሰዎችን መሆን እንደሌለበት እግዚአብሔር ለትዉልዱ አስተምሯል፡፡

አዲስ አበባን ካነሳዉ አይቀር ለአዲስ አበባ መቆርቆር ምክንያት የሆኑትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ በአራቱም ማዕዘን ያሉትን በማዋሐድና አንዲት ኢትዮጵያን በማጽናት ታሪክ የሰሩትን ታላቁ መሪ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩትን አጼ ምኒልክን ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡ ከዛሬ 125 ዓመት በፊት በደንና በዱር አራዊት ብቻ ተሞልታ የነበረችዉ አዲስ አበባ እንኳን በሚሊዮን ቀርቶ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያልኖሩባት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከተማዉን በአዲስ አበባ ሲያደርግ በአራቱም ማዕዘን ያሉት ኢትዮጵያዉያን መሬታቸዉ ነዉና ከተማዋን አቀኗት፡፡ አንድ ሕንጻ ያልነበረባት በአሁን ሰዓት እጅግ ብዙ ሕንጻዎች ሊታዩባት ችለዋል፡፡ ዘመናዊ ሥልጣኔንና የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን በመጠቀምና በማምጣት በዋናነት ቀዳሚ ነበሩ፡፡ ያ ብቻ አይደለም በአራቱም ማዕዘን «እኔ ልንገሥ እኔ ልንገሥ፣ ጎጤን በባለይ ልምራ፣ ላስተዳድር፣ ፈላጭ ቆራጭ ልሁን» የሚሉትን ከጎጣዊ አስተሳሰብ አዉጥተዉ አገራዊ ራእይ እንዲይዙና ለእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያ እድገትና ልማት እንዲሁም ብልጽግና በጋራ እንዲሰለፉ ማድረግ ችለዋል፡፡

የሚያሳዝነዉና የሚገርመዉ ዉስጡ በጥላቻና በበቀል የተሞላዉ ወያኔ(ሕወሓት) መንግሥት የመጀመሪያ ዓላማዉ የሻዕቢያ ቅጥረኛ ነበርና ኤርትራን ማስገንጠል፣ በሂደት ደግሞ የራሳቸዉን መንግሥት ካጠናከሩ በኋላ ነጻ መንግሥት መመስረት፤ ይህንንም ለማሳካት ኢትዮጵያን በቋንቋ በመከፋፈል አንዱን በአንዱ ላይ ማነሳሳትን፣ በቀል ማስፈጸም፣ ጥላቻ መፍጠር፣ በመጨረሻም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ነበር፡፡ ለዚህ ዓላማቸዉም እነዚህ የዓመፃ ልጆች ተብለዉ በእግዚአብሔር የተጠሩት ወያኔ(ሕወሓት)፤ በኢትዮጵያዊነታቸዉ ጸንተዉ ለአገራቸዉ የሚችሉትን ሁሉ ሰርተዉ ወደ ሁለተኛዉ ዓለም የሄዱትን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ምኒልክን «እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች፤ ይህ ክርስቲያን (ዐምሓራ)(ነፍጠኛ) ወንዶቹን እጃቸዉን፣ ሴቶቻችሁን ጡታቸዉን በማስቆረጥ በደልና ግፍ ፈጽሞባችኋል፡፡ እንዲሁም እምነታችሁን፣ ባህላችሁን፣ ቋንቋችሁን አጥፍቶባችሁ ይኸዉ ለዘመናት ስትማቅቁ ነበር፤ እኛ ግን ይኸዉ ነጻ አዉጥተናችኋል፤ እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) በክልላችሁ ለምን መጡ? ...እንዲህ እያሏችሁ እየሰደቧችሁ እንዴት ዝም ትላላችሁ? ከስራ አፈናቅሉ፤ በሚኖሩበትም ቦታ በቀል ፈጽሙ፣ አስጨንቁ፣ አሳዱ፣ በቤተክርስቲያናቸዉ ፊትለፊት ወይንም አቅራቢያ መስጊዳችሁን ስሩ፣ ምን ያመጣሉ፣ እኛ ከጎናችሁ አለን እንደፈለጋችሁ አድርጉ፣ » በማለት ምንም ጥላቻና በቀል የሌለዉንና ተዋሕዶ የነበረዉን ሕዝብ እርስ በእርስ በማጣላት አገዳደሉት፤ አፈናቀሉት፤ እንዲበቃቀል አደረጉት፡፡

በዚህም የመጀመሪያ ተጠያቂዎቹ በሽግግሩ መንግሥት ጊዜ ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም ከስራቸዉ ሆነዉ የግፍና የበቀል ተግባር ሲያስፈጽሙ የነበሩ ባለሥልጣናት ሲሆኑ፤

የቅድሞዉ ፕሬዝዳንት የቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር በእግዚአብሔር ቁጣ ተጠርተዉ ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ ለእዉነተኛ ፍርድ ወደ ተዘጋጀላቸዉ ዓለም የሄዱ ሲሆን፤ በሽግግሩ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት በግፍ ስርቆታቸዉና አጭበርባሪነታቸዉ ለተወሰኑ ዓመታት በእስር ፍዳቸዉን የተቀበሉ ሲሆን፤ ሌሎቹ ግፈኛ ባለሥልጣናት ደግሞ በአገር ዉስጥና በስደት ይገኛሉ:: ምናልባት ጥቂት ቅንነትና መልካምነት ተገኝቶባቸዉ በቅርቡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በተነሱትና በሚነሱት መንግሥታት፣ ድርጅቶች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች ላይ ከሚመጣዉ ከእግዚአብሔር ቁጣ ተርፈዉ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ከደረሱ፤ እያንዳንዱ ካለበትና ከተደበቀበት ቦታ ለእዉነተኛ ፍርድ በብርሃን ችሎት ቀርቦ እንደ ዓመፃና ግፍ ፈጻሚነቱና አስፈጻሚነቱ ይጠየቅበታል እንጂ እያንዳንዱ በሕዝብ ላይ ግፍና በደል የፈጸመና ያስፈጸመ ካለ ዋጋ የኢትዮጵያን ትንሣኤ አይመለከትም:: ወደ ልቦናዉ ከተመለሰ ደግሞ በምድር ዋጋ ቢከፍልም፤ ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥት በእዉነተኛ ንስሐ ሊበቃ ይችላል:: በምድርም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍርድና ምሕረት ነዉ የሚጸናዉ እንጂ እንደ ዲያብሎስ እንደራሴዎች የሥጋና የደም ስሜትና በቀል በማንም ላይ አይፈጸምም::

ሌላዉ እዉነታ ይህ መንግሥት(የመንግሥት ተወካዮች) የአዲስ አበባ መኖር ለሥልጣናቸዉ አደጋ ሆኖ ከተገኘ፤ ሕሊናቸዉን በመገለባበጥ በሚታወቁ ታማኝ አገልጋዮቻቸዉን(ባሪያዎቻቸዉን) በመጠቀምና ከላይ ሆኖ እንደልባቸዉ በማሽከርከት አዲስ አበባን ከርእሰ ከተማነት ከማስወገድ ወደ ኋላ የማይሉ ከሕሊናቸዉ ጋር የተጣሉ ናቸዉ:: ሥልጣኑ ከተጠበቀላቸዉና በበላይነት ስሜት የሚንቀሳቀሱና የሚኖሩ ከሆነ ደግሞ እንኳን ለዋና ከተማነት አይደለም የአፍሪካ ኅበረትን መዲና እንድትሆን ሽንጣቸዉን ገትረዉ የሚከራከሩ፣ ለግል ክብርና ጥቅም የቆሙ ምንደኛ ናቸዉ:: እዉነተኞቹ ኢትዮጵያዉያንና ቅጥረኛ ያልሆኑ መሪዎች እንዲሁም ባለሥልጣናት ግን እነሱ ሥልጣን ኖራቸዉ አልኖራቸዉ፣ ጥቅም አገኙ አላገኙ፣ ተሰደዱ አልተሰደዱ፣ ተበደሉ አልተበደሉ፣ ተገፉ አልተገፉ፣ የአገሪቷን መከፋፈልና መዳከም የማይፈልጉ፤ ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነታቸዉን የማይክዱ፤ በኢትዮጵያዊነታቸዉ ላይ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም የአምልኮ ምንዝርና በመፈጸም « እኔ አልተመቸኝም ወይንም ሥልጣን አግኝቼ የበላይ አልሆንኩም ወይንም የተለየ ጥቅም አላገኘሁምና ነጻ መንግሥት መስርቼ መሪና ባለሥልጣን ሆኜ መኖር አለብኝ፤ ኢትዮጵያዊነቴን አልፈልግም፣ እኔ ኤርትራዊ ነኝ፤ እኔ ትግራዊ ነኝ፤ እኔ አማራዊ ነኝ፤ እኔ ኦሮሚያዊ ነኝ፤ እኔ ሱማሊያዊ ነኝ፤ እኔ አፋራዊ ነኝ፤ እኔ ሐረሪያዊ ነኝ፤ እኔ ጉሙዛዊ ነኝ፤ እኔ አኝዋክያዊ ነኝ፤ እኔ ጋምቤላዊ ነን ፤ እኔ ሲዳማዊ ነኝ፤ እኔ ወላይታዊ ነኝ፤ እኔ አድይያዊ ነኝ፤ እኔ ስልጤያዊ ነኝ፤ እኔ ጉራጌያዊ ነኝ፤ እኔ አገዊያዊ ነኝ፤ እኔ ከፊቾዋዊ ነኝ፤ እኔ እገሌያዊ ነኝ... ወዘተ» የማይሉ ናቸዉ:: እዉነተኛ ኢትዮጵያዊ ምንም ይሁን ምን፣ ምንም ይደረግበት ምን፣ ስለ እዉነት ከመመስከርና የዓመፃን፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርን ከመቃወምና ስለ እዉነት ራሱን መስዋዕት ከማድረግና እዉነተኛ ዳኝነት የሁሉ ፈጣሪ እንዲሰጥ ከማድረግ ዉጭ እንኳን ኢትዮጵያን መገነጣጠል ቀርቶ በሕሊናዉ እንኳ አያስበዉም::

አሁን ያለዉ የሕወሓት(ኢሕአዴግ) መንግሥት ግን «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» እንዳለችዉ የእርሱ የሥልጣን በላይነት ከተሻረና የዘረኝነቱና የጎጠኝነቱ ሥርዓት ከተቀየረ ኢትዮጵያ የሚለዉ ስያሜ ከምድረ ገጽ ጠፍቶ ኤርትሪያ፣ ትግሪያ፣ ኦሮሚያ፣ አማሪያ፣ አፋሪያ፣ ሱማሊያ፣ ሐረሪያ፣ ጋምቤሊያ፣ ቤንሻንጉሊያ፣ ሲዳሚያ፣ ወላዩቲያ፣ አዲዩያ፣ አገዊያ... ወዘተ አገሮች እንዲመሰረቱ የሚፈልግ ቅጥረኛ፣ ሌባ፣ ወንበዴ፣ ተኩላ፣ ነፍሰ ገዳይ ነዉ።

ልማቱን የሚፈልገዉ የሥልጣን እድሜዉን ለማስረዘምና የራሱን መሰሪና ስዉር ዓላማ እስከሚያሳካ ድረስ ነዉ። ስለ ሕዝብ መጉላላት አንዳች ስሜት የማይሰጠዉ መሆኑን ከሚያሳዩት አንዱን ለመጥቀስ፣ ስንትና ስንት መንገዶች በትእልፊት(በቢልዮን) የሚቆጠር ገንዘብ ወጭ ተደርጎ በተለያዩ ቦታ እየተሰራ በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብቻ አይደለም የአፍሪካ ኅብረት መዲና በሆነችዉ በአዲስ አበባ በመገቢያና በመዉጫ እንዲሁም በተለያዩ አደባባዮችና መንገዶች ለቀናተ አይደለም ለወራትና ለዓመታት ተበላሽተዉ ሕዝቡ በትራንስፖርት እየተማረረና ወደ ስራ ገበታም በሰዓቱ ባለመድረስ ስራዎች እየተበደሉ፣ ሕዝቡ እየተጉላላ መሆነ እየታወቀ ለፖለቲካ ፍጆታ እስካልጠቀመ ድረስ አንዳች የሕዝብን ችግር ለማሶገድ ተነሳሽነቱ የላቸዉም።

ማንም ሰዉ የአገሩን ልማትና ዕድገት የማይጠላ ነገር ግን ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ቅድሚያ እንዲሰጠ የሚፈልግ። «በመጀመሪያ በሕይወት ልቆይና ከዚያ በኋላ ለእኔም ሆነ ለትዉልዱ የሚሆን ቅርስ ሆነ ልማት ልስራ» የሚል ነዉ። ነገረ ግን የኢሕአዲግ መንግሥት ሕዝቡ በአሁን ሰዓት በተያየ ችግርና የሕሊና እስረኛነት እየማቀቀ «አይዞህ አሁን ድህነት ካንተ ይወገዳል፣ ደህና ሰንብት ብለነዋል፤ ሻማም ለልደት እንጂ ለመብራትነት አገልግሎት አይዉልም፤ በቀን ሦስት ጊዜ በልተህ ታድራለህ፤» እያለ እያላገጠና እያስላገጠ፤ «አሁን አንተ ብትሞትም ለፖለቲካ ዓላማችን ሕዝቡን በዙሪያችን እያሰለፍን ነዉና ገንዘብ አምጣ፤ የአንድ ወር ደሞዝህን ለግስ፤ እምቢ ካልክ ደግሞ በፀረ ልማትና በአሸባሪነት ትፈረጃለህ፤ እነ እገሌ በሚሊዮኖች ገንዘብ እየለገሱ አይደለም ወይ? አንተ ምን ትሰራለህ» እያሉ ምስኪኑን ደሀና የወር ደሞዝተኛ እንኳን ከወር ሊተርፈዉ አይደለም በተለያየ ብድር ተደጉሞ ያለዉን ሰራተኛ፤ በካድሬዎቻቸዉ ቀስቃሽነትና ተጽህኖ እንዲሁም በሥርዓቱ ተጠቃሚ በመሆኑት በጣት በሚቆጠሩ ባለሀብት ቀስቃሽነት ልጁን ማስተማርና ማብላት ያቃተዉን ትዉልድ አስጨንቀዉና በተለያየ መንገድ ገንዙብን ቀምተዋል። ለስዉር ፖለቲካ ዓላም አዉለዉታል። አሁን ደግሞ ዋናዉ ቀያሹ መሀንዲሳቸዉ በሥጋ ሞት ባይለያቸዉ ደግሞ ለሥልጣን እድሜቸዉ ማራዘሚያ የተሻለ ሐሳብ ቢፈጠር በዚያ ዙሪያ ደግሞ ትዉልዱን ሕሊናዉን እያሸጡ ይጠቀሙበት ነበር። ነገር ግን አሁንም መሪያቸዉ ያ የአቶ መለስ መንፈስ ስለሆነ በዚያ መንፈስ እየተመሩ ሕዝቡን እያስጨነቁትና እያማረሩት ይገኛል።

ባጠቃላይ መንግሥት የሚሰራቸዉ የተለያዩ የልማት ሥራዎች ለፖለቲካ መጠቀሚያና ለራስ ስዉር ዓላማ ማሳኪያ እንጂ ችግረኞች እንዲረዱና ከጉስቁልና ሕይወት እንዲገላገሉ፣ አገሪቷ ከድህነት እንድትወጣና ከራሷ አልፋ ለሌላዉ እንድትተርፍ በማሰብ አይደለም። ለዚህም ነዉ ሕዝቡ በችግርና በኑሮ ዉድነት እየተማረረና መፍትሔ እንዲደረግለት እየጠየቀ «ይህ ሁሉ ችግርና መከራ የመጣብህ

ኢኮኖሚያችን ከፍተኛ እድገት እያሳየና ከሕንድና ከቻይና ጋር እየተቀራረብ ስለሆነ ነዉ» እያሉ በሕዝብ የሚያላግጡትና ለጌቶቻቸዉ የተለያዩ መንግሥታት ደግሞ «ከ10 ፐርሰንት በላይ ኢኮኖሚያችን አድጓል፣ የብልጽግና ጎዳና ይዘናል፣ የምትሉንን እንዳርጋለን፤ በሌላ አገራት ገብታችሁ ተበቀሉልን ብትሉም እንፈጽመዋለን ወደ ኋላ አንልም፤ ለዚህም በምስራቅ አፍሪካ፤ የናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ መሆናችን ብቻ በቂ ምስክሩ ነዉ፤ ስለዚህ የተለመደዉ ድጋፋችሁና ብራችሁ አይለየን?» እያሉ በመሸንገል፤ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ በታመኑ ሰዎች ላይ ደግሞ ኢ- ሰብአዊ ተግባር ይፈጽማሉ፤ ያስራሉ፣ ይገላሉ፣ ያሳድዳሉ፣ በሐሰት ይወነጅላሉ፣ የግፍ ብቀላ ተግባራቸዉን በአራቱም ማዕዘን ያከናዉናሉ።

እዚህ ላይ አንድ ለማስታወስ የምፈልግዉ በመንግሥት ዙሪያ የተሰባሰቡ ሕሊናቸዉን እንደፈለጉ መገለባበጥ የሚችሉ እነ ሆዱ አምላኩ ካድሬዎች፤ ጥቁሩን ነጭ፣ ነጩን ጥቁር፣ ጨለማዉን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማዉን ቢሉ ብዙም አያስደንቅም። ምክንያም ተስፋቸዉና ምኞታቸዉ ሁሉ በምድር የሚያገኙት የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችና ወንበር በመሆኑ፤ ያንን ላለማጣት ከሕሊናቸዉ ተቃራኒ ሊቆሙ ይችላሉና። የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ግን በራሳቸዉ ተምረዉ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱና ትዉልዱንም በእዉቀታቸዉ ሊያገለግሉ የሚችሉ አንዳንድ «ምሁራን» የተባሉ ከሕሊናቸዉ ተቃራኒ የሚኖሩ ሰዎች ናቸዉ። ምክንያቱም ያለፈዉን ታሪክ፣ የአሁኑን ታሪክ ማመዛዘንና ማገናዘብ በቀላሉ የሚችሉ ሆኖ ሳለ፤ ከዛሬ ኀምሳ ዓመት በፊት የከፍተኛ ተቋም ትምህርት በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘን እንደሌለ፣ እንዲሁም ዘመናዊ ትምህርት ገና እየተስፋፋና ወላጆች ልጆቻቸዉን እንዲያስተምሩ ቅስቀሳና ድጋፉ እየተደረገ እንደነበረ እየታወቀ፤ «ከዚህ በፊት የነበሩ ገዥ መደቦች የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አላስፋፉም፤ የተስፋፈዉም እነሱ ባሉበት ከተማ ነዉ እንጂ በሌላ ቦታ አይደለም፤ አሁን ግን የኢሕአዴግ መንግሥት በብሔር ብሔረሰቦች ክልል ሁሉ አስፋፍቷል» በማለት እንኳን ዶክተር፣ ፕሮፌሰር የተባለ ቀርቶ አንድ ማመዛዘና ማገናዘብ የማይችል መሃይም እንኳ የማይናገረዉን ንግግር በየመድረኩና በብዙኃን መገናኛ (በማስ ሚዲያ) ሲናገሩ ታይቷል፣ ተደምጧል።

አሳፋሪ አስተሳሰባቸዉን የሚገልጽባቸዉ ደግሞ ከዛሬ አስር ዓመት በፊት አሁን ያለዉ መንግሥት በአሁን ሰዓት በተለያየ ቦታ የተከፈቱትን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አላስገነባም፤ አልከፈተም። «ታዲያ ከዚህ በፊት አላደረገም? »ተብሎ ሊወቀስና ሊኮነን ነዉ? አሁን ደግሞ መስራት በቻለበት ወቅት መስራት በመቻሉ በተለየ ሁኔታ ሊመሰገንና ሊደነቅ ይገባዋል? ለመሆኑ የዛሬ አምሳና አርባ ዓመት የተማሪዎች ቁጥር ስንት ነበር? አሁን ያሉት ከፍተኛ ተቋማት የግማሽ ግማሽ ተከፍቶ ቢሆን ኖሮ በፈተና መዉደቅ ሳይኖር ሁሉም ተማሪዎች የመግባት እድል ቢሰጣቸዉ ብዙዎቹ ተቋማት ካለተማሪ ብቻቸዉን አይቀሩም ነበርን? «የዛሬ አስራ አምስት ዓመት በፊት መስሪያ ቤቶች በኮምፒተር የተደገፈ ስራ አይሰሩም፣ ኋላ ቀር ነበር» ብሎ መኮነንና አሁን የኮምፒተር ቴክኖሎጅ በመግባቱና እንኳን መስሪያ ቤት ቀርቶ በግለሰብ እጅ በተገኘበት ወቅት ጋር ከሚሰራዉ የተቀላጠፈ ስራ ጋር ማነጻጸር ይቻላልን? ለመሆኑ እንኳን በኢትዮጵያ በዓለም ላይ እንኳ በቅርቡ አይደለም ወይ ኮምፒተር አገልግሎት ላይ የዋለዉ? «ከዛሬ ሃያ ዓመት ቢፊት በገዥ መደቦች ምክንያት ብሔር

ብሔረሰቡ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ እንዳይሆን ተደርጎ ነበር፤ አሁን በኢሕአዴግ ዘመን ይኸዉ ተንቀሳቃሽ ስልክ በገጠር ሁሉ ገብቶ አገልግሎት እየሰጠ ነዉ» ብሎ ያለፈዉን እየኮነኑ የአሁኑን ማግነን ይገባ ነበር ወይ? ቀድሞ በእጅ ይጻፍ የነበረዉ የመጻፊያ መሳሪያ ባለመኖሩ ምክንያት መሆኑ እየታወቀ እንዲሁም ኮምፒተር ባልኖረበት ዘመን በእጅ መጻፊያ መሳሪያ በመጠቀመ ስለተጻፈ፤ የዱሮዉን መኮነን የአሁኑን ደግሞ ልዩ ማድረግና ማግነን ይገባል ወይ?

ነገሮችን ማመዛዝና ማገናዘብ ካልቻልንና ለሕሊናችን መታመን ካቃተን መማራችን ምን ትርጉም አለዉ? ሊያስወቅስ የሚችለዉ ማንም ይሁን ማን በዘመኑ መስራት እየቻለ ያልሰራዉ ካለና በክፋትና በተንኮል እንዲሁም በበቀል ለትዉልድ የሚጠቅመዉን የሚያጠፋ መንግሥት ሆነ ቡድን እንዲሁም ግለሰብ ነዉ:: ሊመሰገን የሚገባዉ ደግሞ መስራት የሚገባዉን በሚገባ መስረት የቻለና ለትዉልድ መልካም ቅርስና ሕይወት የተወ ሰዉ ነዉ:: ሊደነቅ የሚገባዉ ደግሞ ሊሰራ የማይችል ነገር ግን የራስን ትጋትና ጥረት እንዲሁም መስዋዕትነት ከፍሎ ለትዉልድ መልካም የሆነዉን ስራ የሰራ ነዉ:: ከዚያ ዉጭ በዘመኑ እያንዳንዱ እንደ አቅሙ በሰራዉ ስራ ሊኮነንና መስራት የሚገባዉን ስራ ስለሰራ ሊደነቅና ሊገን አይገባዉም:: ምክንያቱም ማንም ይሁን ማን ወንበር ላይ እስካለ ድረስ መስራት ያለበትን ሁሉ መስራት ይጠበቅበታል::

የትምህርት ጥራትን በተመለከተም የራሳቸዉ መሃይምነትና ባዶነት ጭንቀት ስለፈጠረባቸዉ እዉቀትንና ሙያን ማራከስ ነዉ የያዙት:: ይኸዉም ማንም ይህም ማን በድካሙና በልፋቱ ደረጃ ነጥብ ሊሰጠዉ ሲገባ፤ አሹፎ እየተማረና እንዲሁም ትምህርቱን ንቆ የካድሬነት ተግባር በመፈጸሙ «ማንኛዉንም ተማሪ 10 ይሁን 20 ወይንም ሰላሳ ነጥብ ቢገኝ ቢያንስ ሲ(c) ሰተህ ማሳለፍ አለብህ፤ ካድሬዎቻንን ብትጥል ደግሞ ወዮልህ! ቃላችንን ተላልፈህ አንድ ተማሪ ብትጥል ማስተማር ያልቻለና ብቃት የሌለዉ መምህር ነዉ ብለን እርምጃ እንወስድብሃለን» እያሉ የከፍተኛ ተቋም መምህራንን እያስፈራሩና ተጽህኖ እያሳደሩ የማጥናትና የመማር ትርጉምን አጥፍተዉ እንኳን በትጋትን በጥራት በመስራት እናት አገሩን የሚያገለግል ትዉልድ ሊፈጥሩ ቀርቶ እራሱን የሚረዳ ትዉልድ መፍጠር አቅቷቸዋል:: እንዴት ትምህርቱን በሚገባ አጥንቶና ተምሮ ጥሩ ዉጤት ማምጣት ያልቻለ ተማሪ በኃላፊነት ላይ ተቀምጦ በትጋትና በእዉቀት ስራዉን ይሰራል? ጊዜዉንና ሕይወቱን በመሰዋት ያልተማረና በአግባቡ ተፈትኖ ዉጤት ያላመጣ ተማሪ «ይህን ያህል ሰዉ አስመረቅን» ለማለትና ካድሬዎቹን ደግሞ «እናንተ ለፓለቲካችን ቁርጠኛ አገልጋዮች ብቻ ሁኑ እንጂ ስለ መመረቃችሁና በኋላም በልዩ ቦታ ስለመመደባችሁ ሐሳብ አይግባችሁ፤ እኛ ከዛም ባለፈ ነዉ የምናስብላችሁ» በማለት ፍትሐዊ ያልሆነ ነጥብ አሰጣጥና ስራ ምደባ የሚያደርግ መንግሥት እንዴት ሕዝብን ይወክላል? ተምሮ ጥሩ ዉጤት ያመጣ ተማሪ ስለ ድካሙና ትጋቱ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ዋጋ እንዲያገኝ ካልተደረገ ጉብዝናና ትጋት ምን ጥቅም ይኖረዋል? በጎበዞችና በትጉሆች አእምሮ ተጠቅመንባቸዉ ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ እንዲያገለግሉ ካለደርግን፤ ካድሬዉን ብቻ በቁልፍ ቦታ ሰግስገን ካስቀመጥን፣ ላልተጋበትና ላላፋበት ዋጋ ዝም ብለን ከከፈልነዉ፣ እንዴት ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ በቅንነት፣ በእዉነት፣ በትጋት፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በታማኝነት ያገለግላል?

ስንትና ስንት ዓመት ተምሮ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያላለፈ ሰዉ የሚሰራዉን የተለያየ ስራ ባለድግሪዉ እንዲሰራ በማድረጋችን እንዴት እንደ ስኬት ተቆጥሮ በየሚዲያዉ ይቀርባል? ምንም እንኳ የስራ አማራጭ በማጣታቸዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ከተራ ስራ ጀምሮ ለመስራት የተሰለፉ ተመራቂ ተማሪዎች አቋማቸዉ የሚደነቅ ቢሆንም፤ መንግሥት ግን እንደ ትምህርት ደረጃቸዉና እዉቀታቸዉ የተለያየ የስራ መስክ ሊከፍትላቸዉና እነሱም እንዲፈጥሩ ማድረግ ሲገባ፤ ባለ ሁለት ድግሪ ባለቤት የሆነዉን ኮብል ስቶን በማሰራቱ እንደ ትልቅ ስኬት ማየትንና መቁጠር አልነበረበትም:: ዉጤቱ መንግሥት ሙያንና እዉቀትን ማራከስና «መሃይምም ቢሆን የፓለቲካ ዓላማዬን ካሳካልኝ የተለያየ ሹመትና ሥልጣን እሰጠዋለዉ» ያለዉን የመሃይምነት አስተሳሰብና የእዉቀትንና ብቃትን ንቀት ተግባራዊ ማድረጉን ነዉ የሚያሳየን::

እንዲሁም የራሳቸዉ የሕሊና ባዶነት የሚቀይርላቸዉ እየመሰላቸዉ ካድሬዎቻቸዉን የቀናት ወይንም የሳምንታት ቢበዛ የወራት የተለየ ሥልጠናና የተለየ ተልኮ ትምህርት እያሰጡ በስንት ድካምና ትጋት የሚገኘዉን የመጀመሪያ ዲግሪ ሆነ ሁለተኛ ድግሪ በገንዘብ ኃይል እየገዙ ይቀበላሉ:: ለማስመሰያም ጋዎኑን እየለበሱ ፎቶ ግራፍ በመነሳት ካለ ሃፍረት (እኛ ባለድግሪና ባለሁለት ድግሪ ነን» እያሉ ይናገራሉ:: የሾሟቸዉም መሪዎችና ባለሥልጣናት ካለ ሃፍረት «እኛ በተለያየ ኃላፊነትና ሥልጣን ቦታ ላይ የሳቀመጥናቸዉ የተማሩ ምሁራን ናቸዉ» ብለዉ ይናገራሉ::

መሪዎቹና ባለሥልጣናቱ እንዲሁም ካድሬዎቹና «ምሁር፣ አማካሪ ነን» ተብዬዎቹም በሕዝቡ ላይ አላጋጭና በዉሸት እዉቀት እንዳሉ የሚገልጸዉ፤ ሕዝቡ በችግርና በኑሮ ዉድነት እየማቀቀ እያለ፣ በየመንገዱና በየእምነት ተቋማቱ ወድቆ መከራ እያየ፣ በቤት እጦትና በኪራይ እየተማረረ ብሶቱንና ችግሩን ሲያቀርብ፤ ለ5 ፐርሰንት ሰዎች እንኳ ያልሆነና ያልበጀ መንግሥት «ብዙ ባለአእላፍ ብር(ባለሚየነር) ሀብታም ገበሬና ሰራተኛ ፈጥረናል፥ ይህ ችግር የተከሰተባችሁ ደግሞ ከፍተኛ እድገትና ብልጽና ደረጃ ላይ ስለደረስንና የእድገታችንም መጠን ከ10 ፐረሰንት በላይ ስለሆነ እንደ ቻይና ሕንድ እንደመሳሰሉት አገሮች እድገት ስላሳን ነዉ.... ወዘተ» እያሉ የሚያላግጡና የሰዉ ችግርና ጉስቁል የማይገባቸዉ፣ የራሳቸዉ በዉስኪና በቢራ መራጨት፣ በቪላና በፎቅ መኖር፣ በኮብራ መኪና መሽርከር፣ ሥጋና ጮማ መቁረጥ፣ እንደፈለጉት መዝናና ብቻ የሚታያቸዉ፤ ለማስመሰልና ለመሸንገል ብቻ የሚያወሩ አስመሳይና ባዶ ቀፎ የሆኑ ናቸዉ::

ሌላዉ ለሥልጣናቸዉ እንጂ ስለ ኢትዮጵያዉያን ምስኪን ሕዝብ ደንታ ቢስ መሆናቸዉ ከሚያሳዩን አንድ ሁለቱን ተግባራቸዉን ብንመለከት፤ ከዛሬ አስራ አምስትና አስር ዓመት በፊት ከፍተኛ ገቢ ላለዉ ሆነ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ላለዉ ሕዝብ አነስተኛ እድል ቢሆንም የመኖሪያ ቦታ የማግኘት እድል እጣ ላይ መሳተፍ እድል ነበራቸዉ:: ከአስር ሁለት ዓመት ወዲህ ግን የራሳቸዉን ሰዉ በዘመድ አዝመድ፣ በጎጥ፣ በዘር፣ በትዉዉቅ፣ በጉቦ፣ በአቋራጭ መንገድ፣ በአጉል ብልጣብልጥነት ካደረጁና ካበለጸጉ በኋላ፤ ኢትዮጵያዉያን እንደ ኢትዮጵያዊነታቸዉ በእናት አገራቸዉ ላይ የቦታና የቤት ባለቤት እንዳይሆኑ እንኳን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸዉ አይደለም መካከለኛ ገቢ ያላቸዉ ሰራተኞች እንኳ የቤትና የቦታ ባለቤት እንዳይሆኑ ፍትሐዊነት በሌለዉና አድሎ መመሪያ(ፖሊስ)

ምክንያት ለመኖሪያ የሚሆኑ ቦታዎች ሁሉ የሚሰጡት ሀብት ላላቸዉ ብቻ ነዉ። እነሱን ብቻ በሀብት ላይ ሀብት፣ በንብረት ላይ ንብረት፣ በገንዘብ ላይ ገንዘብ እንዲጨምሩና ምስኪኑ ሕዝብ ደግሞ በኑሮ ዉድነት እየተማረረ እንኳን የቦታና የቤት ባለቤት ሊሆን ቀርቶ ደሞዙ ከወር እስከ ወር አላደርስ ብሎት በሰቀቀን ነዉ የሚኖረዉ። እድሜ ልኩን አገርና ሕዝብን በቅንነትና በትጋት አገልግሎ እንኳ በቤት ኪራይ ነዉ የሚንገላታዉ። ባለጊዜ ነኝ የሚለዉ ግን በዓመታት አይደለም በወራትና በቀናት ከመንግሥት ባለሥልጣናትና ከመሪዎች ቤተሰብ ጋር ተቀናጅቶ ሚሊየነር ነዉ የሚሆነዉ። ለዚሁም ምስክር ቁልፍ ቦታ ላይ የተቀመጡ ባለሥልጣናት በሲሚንቶ ሆነ በብረት እንዲሁም በሌሎች ላይ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚጨምር ለራሳቸዉ ሰዎች አስቀድመዉ በመግለጽ ምርቱን በከፍተኛ መጠን እንዲይዙ አድርገዉ በመንገር፣ ዋጋዉ እንደጨመረ ወዲያዉ በገዙበት እጥፍ ለሕዝቡ ይሸጣሉ። በዚህም መንግሥት  ብዙዎችን ሚሊየነር አድርገናል እያለ የሕዝብን ደም መጣጮችን ያገናል። ለፓለቲካዉ ታማኝ ያልሆነ ባለሀብት ካለ ደግሞ ንብረቱን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ይዘርፋል፤ በተለያየ ተጽህኖ አዳክሞ ከገቢያ ያስወጣል። ሌት ተቀን ገንዘብ ላይ ነዉና ሐሳባቸዉ ኢትዮጵያዉያንን ከእናት አገራቸዉ ላይ እያፈናቀሉና እያሳደዱ እንዲሁም «ይህ አገር ያንተ አገር አይደለም ወደ ጎሳህ(ብሔርህ) ክልል ሂድ» እያሉ ስነቱን መንገድ ላይ እያጣሉ፤ የተወሰነ ገንዘብ ይዞለት የመጣዉን የዉጭ ዜጋ ሆነ ኢትዮጵያዊነቱን የካደን ሰዉ ቦታዎችን እያንበሸበሸ ይሰጣቸዋል። ታዲያ ይህ መንግሥት ለ5 ፐርስነት ለማይሞሉ የቆመ፣ ለአገልጋዮቹና ለደጋፊዎቹ የቆመ ነዉ እንጂ 95 ፐርሰንት በሆኑት ሕዝብ ስም እየነገደ ያለ፤ አገራዊና ሕዝባዊ ፍቅር የሌለዉ ኢትዮጵያዉያንን ለመቅጣትና ኢትዮጵያዊነትን ስሜት ለማጥፋት የመጣ የክፉ ትንቢት ፈጻሚ ነዉ።

አሁን ደግሞ ለሕዝብ በማሰብ ሳይሆን «ለሥልጣናችንና ለመንግሥታችን ህልዉና አደጋ ነዉ» በሚል፤ በፊት ልቅ ያደረጉትን ሙስና ለመቆጣጠር ሙከራ ያደርጋሉ። ይህም ቢሆን ለፓለቲካ ታማኝ የሆነዉን የማይመለከት ሲሆን፤ ለዘብተኛዉንና ሌላዉን ኅበረተሰብ ብቻ ላይ ያተኮረ ነዉ። ዋና ሙስና ፈጻሚ የሆኑት ከላይ እስከ ታች ያሉት ግን አንዳች ምርመራ የማይደረግባቸዉ ነዉ። በፌደራል ሆነ በክልል ስንቱ ፕሮጀክት «ይህን ያህል አስብልኝ» እያሉ ሊሰራበት በማይገባ ገንዘብ መጠን ለሚፈልጉት ሰዉ እየሰጡና ሌሎች ደግሞ አየር በአየር እንዲሰሩ የዘርና የጎጥ ሥልጣን እየሰጡ ስንትና ስንት የሙስና ስራ እንዳሰሩ እየታወቀ፤ የራሳቸዉን ሰዉ በመሆናቸዉ ማንም ምንም አይላቸዉም። የእነሱን ፈለግ ተከትሎ የሄደዉን ነገር ግን የፓለቲካ ደጋፊ ያልሆነዉን ግን ይበቀሉታል።

ሌላዉ ኢሕአዴግ «መስራት የሚገባቸዉን ነዉ የሰሩት» ብንል እንኳ፤ የሚታየዉ ልማት ሆነ ግንባታ ከጉስቁልና ሕይወት የምንገላገልበተ፣ ለሥጋችን ብቻ የሚጠቅም እንጂ ለዋናዉ ገንዘባችን ለሕያዉ ነፍሳችን ግን አንዳች ነገር አልሰሩልንም። ይልቁንም በግልጽ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት እንድንፈጽም አድርገዉ ለሞት ሞት ዳርገዉናል። በዚህም ምክንያት ነፍሳችንን ሙሉ በሙሉ ገለዋል ማለት እንችላለን። ምን ዋጋ አለዉ ለሥጋችን የሚያስፈልገን ሁሉ ተዘጋጅቶ በነፍሳችን ግን ከእግዚአብሔር እዉነታ ወተን እንደ ሥጋ ፈቃዳችን ከተመላለስንና ለእግዚአብሔር ሕያዉ መንግሥት መብቃት ካልቻልን!? ምክንያቱም በዚህ ሥጋ አካላችን በምድር ልንቆይ

የምንችለዉ ቢበዛ ለሰማኒያና ለመቶ ዓመት ነዉ። በነፍሳችን ግን ለሕያዉነት ዘመን የማንኖርበት ዘመን የሌለ ነዉ። ታዲያ 100 ሲካፈል ለትየለሌ(ኢንፊኒቲ)(∞) ዉጤቱ አልቦ(ዜሮ) ስለሆነ፤ ለሥጋ ብቻ መሮጡ አንዳች ጥቅም የለዉም ማለት ነዉ። ነገር ግን ነፍሳችንን በአግባቡ ጠብቀዉ ለሥጋችን ደግሞ የሚያስፈልገንን አድርገዉ ቢሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ስም ልናመሰግናቸዉና ልንመርቃቸዉ እንችል ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ አገራዊ ራእይ ይዘዉ «ለወገኖቻችን ኢትዮጵያዉያን በሙሉ እዉነተኛ አገልግሎት እንፈጽማለን፤ አድሎና በደል አንፈጽምም፤ ሁሉም በኢትዮጵያዊ ዘግነቱ ሆነ በአገሩ(በብሔሩ) እንዲኮራና እንዳያፍርበት እናደርጋለን፤ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን እናወግዛለን፤ እናጠፋለን፤ እንዲሁም እግዚአብሔርን አንግሠን መሪያችን፣ አስተዳዳሪያች፣ መጋቢያችን እንዲሆን እናደርጋለን፤ የዲያብሎሰ ዓርማ የሆነዉን ኮከብ (666) አንቀበልም፤ አናገንም፤ አናነግሥም፤ እዉነተኛዉን ሰንደቅ ዓለማ አረንጓዴ ብጫ ቀይ ብቻ ከፍ ከፍ እናደርጋለን፤ ዓርማችንም «አሸናፊዉ የይሁዳ አንበሳ» የተባለዉ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና አገራችን፣ እናታችን እመ አምላክ ድንግል ማርያም ብቻ ናቸዉ፤ አንዲት ኢትዮጵያን አንዲት ሰንደቅ ዓላማዋን እናስጠብቃለን። ባለ ብዙ ቋንቋና ባለ ብዙ መልክ የሆነዉን አንድ ሕዝብ በቅንነት፣ በእዉነት፣ በፍቅር፣ በትህትና፣ በትዕግስት፣ በጽናት፣ እናገለግላለን ... ወዘተ» ቢሉና ስላለፈዉም የዓመፃ ስራቸዉ እዉነተኛ ንስሐ ቢገቡ፤ እጃቸዉንም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ቢሰጡ ኖሩ ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊዉ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚበቁ እንነግራቸዉ ነበር።

ባጠቃላይ ለነፍሳችንና ለሥጋችን የሚጠቅም ስራ በአንድ ላይ ሰርተዉ ቢሆን ኖሮ ባለታሪክ፣ ባለ ራእይ፣ ባለ ገድል ያደርጋቸዉ ነበር። የታየዉ ግን ሥጋን ከነፍስ እየለዩ ነፍሳችንን መግደላቸዉና ከእግዚአብሔር የምንገናኝበትንም የእዉነት መንፈስ ከእኛ አርቀዉ ፍጹም የዲያብሎስ ተገዥ አድርገዉናል፤ ፈቃዱንም ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን የእርሱ አገልጋይ እንድንሆን አድርገዋል። የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት እንዲሁም የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ከልቦናችን ዉስጥ መንግለዉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት አሰልፈዉናል። በዉስጣችን ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን አንግሠዋል። የአንዲት ሰንደቅ ዓላማን ፍቅር አጥፍተዉ የጎጥ ሰንደቅ ዓላማ በመፍጠር የአሁን ዘመን የዲብሎስን ዓርማ የሆነዉን (666) ኮከቡን እንድንቀበል አድርገዋል።

እዚህ ላይ በመጨረሻ የምለዉ ደግሞ፤ የፋሽስት ኢጣሊያ መሪ ሞሶሎኒና ግራዚያን የሥልጣንና የአገዛዝ ዘመናቸዉን ለማስረዘም ሲሉ የተለያዩ መንገዶችንና የልማት አዉታሮችን እንዲሁም አንዳንድ የሚጠቅሙ ተግባሮችን በማሰራታቸዉ ልናገናቸዉና ባለ ራእዩ መሪ፣ ታላቁ መሪ ፣ ጀግናዉ መሪ፣ ሰማዕቱ መሪ፣ በታሪክ አጋጣሚ የተከሰተ ልዩ መሪ፣ የአፍሪካ ዕንቁ፣ ታላቁ አባታች፣ ለሕዝብ ተወልዶ ኖሮ ለሕዝብ እንደሻማ የቀለጠ መሪ ... ወዘተ እንላቸዋለን?። ፈጽሞ አንላቸዉም። ምክንያቱም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ያጠፉ፣ የአገርና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ከትዉልዱ ልቦና መንግሎ ለማስወጣት የተጉ፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በመፍጠር አንዱን በአንዱ ላይ በማነሳሳት ክፋትና ተንኮል፣ ጥላቻና በቀል ያስፈጸሙ፣ በተለያየ መልኩ ግድያ፣ ግፍ፣ አድሎ፣ በደል

የፈጸሙና ያስፈጸሙ፤ ያ ብቻ አይደለም ነጻነትን በመደፍጠጥ ነፍሳትን(ሕሊናን) የገደሉ፣ እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ናቸዉ። በመሆኑም በወቅቱ መስራት ያለባቸዉንን በመስራታቸዉና የሥልጣን ዘመናቸዉን ለማስረዘም የተለያዩ መልካም ተግባር በመስራታቸዉ ታሪክ በበጎ መልኩ አይዘክራቸዉም፤ መታሰቢያም አያደርግላቸዉም። ይልቁኑ በእግዚአብሔር እዉነት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር በመፈጸማቸዉና በማስፈጸማቸዉ ኃጥአን ናቸዉና የኃጥአን መታሰቢያ ደግሞ ለዘላለም የሚጠፋ ነዉና መታሰቢያቸዉ ሁሉ የሚደመሰስ ነዉ።

አሁንም የስም ኢትዮጵያዉን ሆነዉ ከላይ ፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ከፈጸመዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ግፍ፣ በደል፣ ጭከና በላይ የፈጸሙ የዓመፃ ልጆች፤ መስራት ያለባቸዉን ስለሰሩና እንዲሁም የሥልጣን ዘመናቸዉን ለማስረዘም ሲሉ መልካም ተግባር ስለሰሩ የሚገኑና የሚታሰቡ አይደለም። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ የተነሱ፣ የአገርና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ከትዉልዱ ልቦና መንግለዉ ለማስወጣት የመጨረሻ ትግል ያደረጉ፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በማሰፋፋት ግፍ፣ ግድያ፣ ጭከኛ፣ የበቀል ተግባር የፈጸሙና ያስፈጸሙ፣ ነፍሳትን(ሕሊናን) የገደሉና ያሳበዱ፣ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ፣ ባጠቃላይ የዲያብሎስ እንደራሴ በመሆን ቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሱ የዓመፃ ሰዎች ስለሆኑ መታሰቢያቸዉ ለዘላለም የሚጠፋና የሚደመሰስ ነዉ። » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አራት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በአሁን ሰዓት የሕወሓት(ወያኔ) ዓላማ ምን እንደነበረ በግልጽ እስከ 1981 ዓ.ም ድረስ የድርጅቱ መሪ የነበሩትና አሁንም በከፍተኛ የሥልጣንና ኃላፊነት ያሉት የድርጅቱ መስራች እየተናገሩ ነዉ:: ይኸዉም «እኛ የታገልነዉና ታጋዮቻችንም ደማቸዉን ያፈሰሱት፣ ሥጋቸዉን የከሰከሱት፣ እንዲሁም የተለያየ መስዋዕትነት የከፈሉት፣ ሥልጣንን ከኦርቶዶክስ ሃይማኖትና ከዐማራዉ ለማስወገድና የዐማራዉን ሥርዓትንም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ ነዉ» በማለት ሳያፍሩና ሳይፈሩ በመገናኛ ብዙኃን(በማስ ሚዲያ) ተናግረዋል:: በዚህ ላይ ምን አስተያየት አሎት?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: ይህን አባባል አሁን ብቻ አይደለም ከ1967 ዓ.ም ጀምረዉ ሲናገሩት የነበረና የቆሙለት ዓላማና ግብ መሆኑን ቀደም ብለዉ በሁሉም የድርጅቱ አባላት ሲነገር የነበረና ይታገሉለት የነበረዉ ለዚሁ መሆኑ ይታወቃል:: የአሁኑ ልዩነቱ ወደ መጨረሻዉ ሰዓት ስለደረስን ማለትም ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራቸዉ ዋጋ ወደሚከፍሉበት ጊዜ ላይ ስደረስን፤ ዋናዉ የዚህ የዓመፃ አስተሳሰብና ተግባር ይመራ የነበረዉ የድርጅቱ መሪ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ተጠርጎ እያዩ፣ ያንን ባለ ማስተዋል የራሳቸዉን ጥፋት ለማፋጠን በመፈለግ «እግዚአብሔር ሆይ እንዴት ትዕቢታችንና እብሪታችን እስከ አሁን ድረስ ጽዋዉን አልሞላም?» በማለት እግዚአብሔር የመጨረሻ ቁጣዉን እንዲያመጣባቸዉ በመጎትጎታቸዉ ነዉ::

እጅግ አሳዛኙ ደግሞ «ነጻ አዉጪ ህ ነን» ብለዉ በስሙ የሚነግዱበት የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ እጅግ ብዙዎቹ ለዚህ ሊያጠፉት ቆርጠዉ የተነሱት የቅዱሱ ኪዳን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችና ዐምሓራዎች(ነጻ ሕዝቦች)(በአንድ አምላክ የሚያምኑና ተገዢነታቸዉም ለአንዱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ የሆነ)(ክርስቲያኖች) ናቸዉ:: ሕዝቡ እነዚህ የዲያብሎስ ተጠሪዎችና ስራ አስፈጻሚዎችን መቀበሉና ከዓመፃ ስራቸዉ ጋር ተባባሪ መሆኑ እጅግ ያስገርማል፣ ያስተዛዝባል:: አላስተዋሉትም እንጂ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዲሁም ስ ቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ሃይማኖት ከማንም በላይ ሊቆሙለትና ሊጋደሉለት የሚገባቸዉ እነሱ ነበሩ:: ነገር ግን በተቃራኒ ለማጥፋት መሰለፋቸዉ እጅግ አስገራሚና ጉደኛ ሰዎች መሆናችን ነዉ የሚያሳየን:: ኢትዮጵያንም

አሁን ባለዉ በቋንቋ ክፍፍል አድርገዉ የከፋፈሉትም የመጀመሪያዉን የጥፋት ዓለማቸዉን ከግብ ለማድረስ መሆኑ ግልጽ ነዉ::

«የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ በገጽ 58-64 ላይ በግልጽ የሕወሓት(ወያኔ) በሚል ስያሜ የሚታወቀዉ የዓመፃ ቡድን ዉስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች ማንነታቸዉ፣ ተግባራቸዉ፣ ዓላማና ግባቸዉ ምን እንደሆነና መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆን፣ እስከመጨረሻ የሚያሳዩት ማንነትና አቋም ምን እንደሚመስል... ወዘተ በግልጽ እግዚአብሔር  አሳዉቆናል:: ይኸዉም:

«ቀጣይ ተናጋሪ የነበሩት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ ሲሆኑ እሳቸዉም «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! ዉድ ታጋዮቻችን መስዋዕትነትን ከፍለዉ ደማቸዉን አፍሰዉ በገዥ መደቦች በጭቆና ዉስጥ የነበሩት ወገኖቻችን ኤርትራዉያን ነጻነታቸዉን ተጎናጽፈዉ ነጻ መንግሥታቸዉን መስርተዉ በዐይኖት እንዳዩ ሁሉ አሁንም ከሰማኒያ መንግሥት በላይ እጩዎች ማየቶት የእድለኞች እድለኛ ያሰኞታልና እንኳን ደስ ያሎት:: ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግሥታቸዉን መስርተዉ እኛም በአንድነት እየተጋበዝን በራሳቸዉ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሲናገሩ፣ ሲማሩ፣ ሲዳኙ፣ ሲሰሩ፣ ባጠቃላይ እቅዶትና ምኞቶት ተሳክቶሎት ይህች የገዥ መደቦች የሌሎችን እምነትና ባህል ጨፍልቀዉ የራሳቸዉ ሃይማኖትና ባህል አስፋፍተዉ የብሔር ብሔረሰቦች መጨቆኛ አገር የነበረችዉ «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር ጠፍታ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግሥት መስርተዉ ሲኖሩ ለማየት ያብቃዎት:: ያብቃን::

እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች ደግሞ ከጎሊናችሁ ሊጠፋ የማይገባዉን የነፍጠኞች ግፍንና ጭካኔን ላስታዉሳችሁ እፈልጋለሁ:: ይኸዉም እነዚያ የገዥ መደቦች የሴቶቻችሁን ጡት እየቆረጡ፤ የወንዶቹንም ብልት እየሰለቡ ለዘመናት ሲያሳቃያችሁና ሲጨቁኗችሁ ነበር:: ከሃይማኖታችሁ፣ ከባህላችሁ፣ እንዲሁም ከቋንቋችሁ ዉጭ ስማችሁን እንኳ ሳይቀር እየለወጡ ዮሐንስ፣ ኃይለማርያም፣ ወልደገብርኤል፣ ጳዉሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ኢያሱ ..ወዘተ እያሉ ማንነታችሁን በመለወጥ በደል አድርሰዉባችኋል::

አሁን ግን እድሜ ለመንግሥታችን የብሔር ብሔረሰብ ማንነታችሁን የሚገልጽ ስያሜ ለልጆቻችሁ በማዉጣት እናንተም በፍርድ ቤት ስማችሁን በማስለወጥ ላይ ትገኛላችሁ:: በሃያ ዓመት ዉስጥ ለእኩልነታችሁ፣ ለብልጽግናችሁ፣ ለማንነታችሁ ማረጋገጫ፣ ለዲሞክራሲ መብታችሁና ለነጻነታችሁ መረጋገጥ የልጆቻችሁ ስም ብቻ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል:: በእኛ ክልላዊ

መንግሥታችን ወደጥንት ማንነታችን ለመመለስና ስም አወጣጣችንን ለማስተካከል የገዥ መደቦች የጫኑብን የሃይማኖት ተጽህኖ ከእናንተ ዘመናትን ያስቆጠረ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የትምክህተኞችና የነፍጠኞች መሸሸጊያ የሆነችዉን ቤተክርስቲያንን ስንቆጣጠር ያኔ የፈለግነዉን መስራትና መለወጥ እንችላለን:: ምንም እንኳን እላይ ያሉትን እንደፈለግነዉ ማሽከርከር ብንችልም፤ ሕዝቡ ገና ንቃተ ሕሊናዉ ስላልዳበረና «ሃይማኖትና እግዚአብሔር» የሚባለዉን ገዥ መደቦች ለመጨቆኛ የፈጠሩት መሆኑን ስላላወቀ፣ እንደ ፍላጎታችንና እቅዳችን በፍጥነት ልናከናዉንና ያሰብነዉ በቀላሉ መፈጸም አልቻልንም::

እኛ ጥቅም እስካገኘንበት ድረስ ማንኛዉም ሃይማኖት በአገሪቱ እንዲንሰራፋ እንፈልጋለን:: የዉጪ ፖሊሲያችን ማንኛዉንም ዓላማ የያዘ ሰዉ ብር ይዞ ይምጣ እንጂ ካለምንም ገደብ የፈለገዉን እንዲያከናዉን ሙሉ ነጻነትና ዴሞክራሲ የሚያጎናጽፍ ነዉ:: ያኔ ሕዝቡ በተለያየ ተጽህኖ ዉስጥ ስለሚወድቅ አሁን ያለዉን የግትርነት አቋሙን አስተካክሎ እኛ በምንፈልገዉ ርዕዮተዓለም እንደሚመላለስ ተስፋ እናደርጋለን:: ለዚህም ማሳያ በብሔራዊ ክልላዊ መንግስታችን ዋና ከተማ በመቀሌ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ሲከበር አብዛኛዉ ሕዝብ የብሔር ብሔረሰቡን የዳንኪራና የዘፈን ትዕይንት ሰማያዊ ትዕንት አድሮጎ ነዉ የቆጠረዉና የተያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓለማን ሰማያዊ ሰንደቅ ዓለማ አድርጎ በመመልከት በታላቅ ሐሴትና ፈንጠዚያ ነዉ በዐሉን ያደመቀዉና ያገነነዉ:: በዚህም ምክንያት ጌታችን መሪያችን ገዥያችን የተለያዩ ምሶቹ የሆኑት ዘፈንና ዳንኪራ ስለቀረበለትና ዓርማዉን ኮኮብ ስላገነንለት እንዲሁም ሕዝቡን ከጎናችን አሰልፈን ታላቅ ተግባራችንን ስለፈጸምንና ስላስፈጸምን ታላቅ ዋጋ እንደምናገኝ እናምናለን::

ታዲያ አንዳንድ የኛን ታላቅ ተግባር የማይደግፉና «የጽዮን ልጆች ነን» የሚሉ ትምክህተኞች፣ የገዥ መደቦች ርዝራዦችና የነፍጠኛ ስርዐት ናፋቂዎች፤« ስንትና ስንት ቅዱሳን ጻድቃን ከወጡበት ስፍራ፣ ታቦተ ጽዮን በቅርብ ርቀት ሆና እየታዘበችና ስለ ዐመጻ፣ ስለክህደት፣ ስለአምልኮ ምንዝርና ተግባራችሁና ንግግራችሁ ላይ ከምትመሰክርበት ቦታ፤ በቅዱስ ኪዳኑ ላይ ዐይን ያወጣ ዐመጻ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማ ላይ ዐይን ያወጣ ክህደት እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ ሕዝቡ ተስፋዉን ምድራዊ አድርጎ እንዲኖርና እንዲመላለስ አድርጋችኋል:: እንዲሁም ሕዝቡን በተለያየ ጥቅማ ጥቅምና ስልጣን ዐይኑን አሳዉራችሁት ለጥፋትና ለዉድቀት እየዳረጋችሁት ነዉ:: ቀድሞ ለሃይማኖቱ ይቆረቆር እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕግና

ስርዐት ዘብ ይቆም የነበረዉን የቅዱስ ኪዳን ሕዝብ ሳይቀር አሳምጻችሁታል፤ ርኩሰትን አስፈጽማችሁታል።

<u>ስለዚህ እዉነተኛ ንስሐ ካልገባችሁ እናንተም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ፤ እናንተና መሰሎቻችሁ ዐመጻና ክህደት ከፈጸማችሁባትና ካስፈጸማችሁባት፣ ርኩስት ካነገሣችሁባት፣ እንዲሁም ብቸኛይቱን የሕይወት መንገድ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት ቆርጣችሁ ከተነሳችሁበት ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቁጣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትጠረጋላችሁ።</u>» በማለት የሚናገሩ ዐመጸኛና ሁከት ፈጣሪዎች ቢኖሩም፤ እኛ ግን የአገሪቷ ዋና ምሶሶ የሆነዉን የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የያዘዉን አንዳች እንከን የሌለዉን ሕገ መንግስታችንን ይዘን፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገን፣ <u>ብቸኛዉን የሕይወት እምነታችንን አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዘን፣ የጨለማዉን ገዥ ጌታችንን አምነን ማንም ሊነካንና ሊነቀንቀን አይችልም።</u> ይልቁኑ ስንት ምሁራን ከጎናችን ተሰልፈዉና ታላቅ ተግባራችንን እያደነቁና ምስክርነትን እየሰጡ፤ <u>አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥርዓታችንን አንቀበልም የሚሉትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደመስሳቸዋለን።</u>

<u>የገዥ መደቦች የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የባህል ነጻነትን ገድበዉ በራሳቸዉ ሃይማኖትና ባህል እንዲሁም ቋንቋ ስር እንድንኖር በመደረጉ በስቃይና በመከራ ሕይወት ለዘመናት ኖረናል። አሁን ግን እድሜ ለመንግሥታችንና ለተስፋችን ሕወሐት(ወያኔ) የሃይማኖትና የባህል ነጻነት ተሰቶን የፈለግነዉን ሃይማኖት እንድንከተልና ባህላችንንና ቋንቋችንን ልናሳድግ ችለናል።</u>

በዚህ አጋጣሚ አንድ ቅሬታችንን መግለጽ እንወዳለን። ይኸዉም ከክልላችን ወተዉ በራሳቸዉ አፍ መፍቻ ቋንቋ መነጋገር፣ መምራት፣ ማስተዳደር ሲገባቸዉ እኛ እንዳንነጋገርበት፣ እንዳንማርበት፣ እንዳንሰራበት በተደረገዉ አማርኛ ቋንቋ በመጠቀም እየተነጋገሩበት፣ እየተማሩበት፣ እየሰሩበት ስለሆነ፤ ይህም በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ላይ ተጽህኖ እያመጣብን ስለሆነ ቋንቋዉን ቢችሉ እንኳ በአስተርጓሚ ቢናገሩና ቢሰሩ ይሻላል እንጂ ለብሔር ብሔረሰቦች አርአያ መሆን ሲገባ እኛዉ ራሳችን <u>ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዉን እንዲጠቀሙ እያደረግን ለወደፊት ነጻ መንግስታቸዉ ዉስጥ ቋንቋዉ የመናገር እድል እንዲኖረዉ እያደረግን ስለሆነ ጥንቃቄ ሊደረግበት እንዲሚገባ በዚሁ አሳስባለሁ።</u> ሌላዉ ደግሞ አንዳንዶች «ነጻ መንግስትነታችን እንደ ኤርትራ ቶሎ መታወጅ ይኖርበታል» እያሉ ያቻኩሉናል። እዚህ ላይ ኤርትራ ቶሎ መገንጠሏና ከመንግሥታችን ጋር ቅራኔ በመፍጠሯ ተጎዳች

እንጂ አልተጠቀመችም:: <u>ስለዚህ ቀስ ብሎ መገንጠል ጥቅም አለዉ እንጂ ጉዳት እንደሌለዉ በዚህ አጋጣሚ እንድታዉቁት እፈልጋለሁ:: » በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል</u>::» ተብሎ ተገልጿል::

ከላይ በግልጽ እንደተገለጸዉ ሕወሓት(ወያኔ) የተባለዉ የዓመፃ ቡድን ዉስጥ የተሰባሰቡ በእግዚአብሔር «የዓመፃ ልጆች» የተባሉ ምን ያህል የከፋ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር በመሪነትና በዋናነት እየፈጸሙና እያስፈጸሙ መሆኑን ነዉ:: እንዲሁም የጽዮን(የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም) ልጆች ግን፣ የዓመፃ ስራቸዉን ከመቃወም አልፈዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ከፈጸሙባትና ካስፈጸሙባት ከቅዱስ ክዳኗ ኢትዮጵያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡና እንደሚጠረጉ ነዉ የተናገሯቸዉ:: ይህን ያናገራቸዉ ደግሞ የሥጋና የደም ስሜታቸዉ ሳይሆን የወደፊቱን ሁሉ የሚያዉቀዉ መንፈስ ቅዱስ ነዉ:: ታዲያ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት በመፈጸማቸዉና በማስፈጸማቸዉ ዛሬ ነገ ሳይሉ በእዉነተኛ ንስሐ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድና ስለ ዓመፃ ተግባራቸዉም በግልጽ ይቅርታ መጠየቅና ለእዉነት መሰለፍ ሲገባቸዉ በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት እየጨመሩ ይገኛሉ:: ይህ ድርጊታቸዉ ደግሞ የንስሐ እድላቸዉን የሚዘጋባቸዉና ለመጨረሻዉ ለእግዚአብሔር ቁጣ ራሳቸዉን እየዳረጉ መሆኑን ነዉ የሚያሳየዉ::

አሁንም እንደ ወገንነታችን የመጨረሻ ምክርና ጥሪ የምናቀርብላቸዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሳይነድባችሁ በፊት ዛሬ ነገ ሳትሉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራችሁን አምናችሁ በእዉነተኛ ንስሐ በእግዚአብሔር ፊት ዉደቁ:: እግዚአብሔርን እጅግ ስላስቆጣችሁ እጅግ የከፋዉን ቁጣ ያመጣባችኋል:: እናንተም ሆናችሁ፤ የቅዱሱ ኪዳን ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ሃይማኖትና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተሰለፉ የዓመፃ ቡድኖችና የእነሱ ግብረአበሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድባችኋል:: ከምድሩም ከሰማዩም ሳትሆኑ ለከፋዉ ቅጣት ራሳችሁን ትዳርጋላችሁ:: የመጠረጊያ ዘመኑም አሁን ባላችሁበትና ባለጊዜ በሆናችሁበት ዘመን ዉስጥ ስለሆነ በብልጣብልጥነትና በአቋራጭ መንገድ ራሳችንን እናድናለን ብላችሁ አታስቡ:: በምድርም በሰማይም ሊያድናችሁ የሚችለዉ እዉነተኛ ንስሐና በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጸመዉ አምልኮ ብቻ ነዉ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ወደ ወንበር ከወጣ ዘመን ጀምሮ «የብሔር ብሔረሰብ ተዋጽኦ መጠበቅ አለበት፣ የፆታ ተዋጽኦ መጠበቅ አለበት» በማለት ለብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሰጠ ይናገራል፡፡ ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: አንድ መታወቅ ያለበት የሕወሓት ኢሕአዲግ መንግሥት በኢትዮጵያ ዉስጥ ላሉት የኅበረተሰብ ክፈሎች አስቦ አይደለም ሥልጣንን ለማከፋፈል የተነሳዉ፡፡ ዋናዉ ስዉሩ ዓላማዉ ክርስቲያኖንችን(ነጻ ሕዝቦችን)(ዐምሓራዎችን) መበቀልና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትን በማዳከም ክህደትና ምንፍቅና እንዲሁም ርኩሰት ለማንገሥ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም «አንዲት ሰንደቅ ዓላማ» የሚለዉን ስሜት ማዳከምና ብሎም ማጥፋት፤ ዘረኝነትንና ጎጠኝነት ማንገሥ ነዉ፡፡ በመጨረሻ ራሱንም በደንብ ካደራጀና የሚፈልግበት ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ እንደ ሻዕቢያ ነጻ መንግሥት አቋቁሞ ኢትዮጵያ ተገነጣጥላ ማንነቷ እንዲጠፋ ነዉ፡፡ ይህንን በበላይ የሚመራዉ ራቂቁ መንፈስ ዲያብሎስ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት የዲያብሎስ አገልጋዮች ከሆኑ ሰዎች ብዙ የምንጠብቀዉ የለም፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** አሁን ያለዉ መንግሥት የሕዝቦችን እኩልነት አለመቀበሉን የሚያሳየን ልዩነት እየፈጠረ አንዱን በአንዱ ላይ ማነሳሳቱና ጥላቻና በቀል ማስፈጸሙ ነዉ፡፡ ያ ብቻ አይደለም እስከ አሁን ድረስ በኢትጵያዉ ዉስጥ ያሉ ያተለያዩ ኅብረተስብ ክፍሎች መሆናቸዉን አለማመኑን የሚያስመሰክርበትን «ብሔር ብሔርሰቦቹ ሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝቦች» ሆኑ እያሉ ነገ ጠባ የሚለፍፉት አስቀድሞዉኑ በዉስጣቸዉ «እኩል አይደሉም፤ ኢትዮጵያዉያን አይደሉም» ብለዉ ያምኑ እንደነበረ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ አሁን ያለዉ መንግሥት የመጨረሻ መሰሪ መንግሥት መሆኑን ይመሰክርበታል፡፡ «ብሔር ብሔረስብ» እያለ በአራቱም ማእዘን ባሉ በኢትዮጵያዉያን ስም የሚነግደዉ የራሱን መሰሪ ዓላማ ለማሳካት ነዉ እንጂ ዋናዉን ሥልጣን ተቆጣጥረዉ አገሪቷንና ሕዝቡን እንደ ፈለጋቸዉ የሚያደርጉት ጥቂት የዓመፃ ቡድኖች ናቸዉ፡፡ እነርሱም በዘር፣ በጎጥ፣ በዘመድ አዝማድ ተባድነዉ እንደ ቦይ ዉኃ ወደፈለጉት አቅጣጫ የሚወስዱትን ሰዉ እየመለመሉ የተለያየ ቦታ በመስጠት እንደ ድምፅ ማጉያ የራሳቸዉን ድምጽ እንዲያስተጋቡላቸዉ ነዉ የሚጠቀሙባቸዉ እንጂ ለሕሊናቸዉ ታምኖዉ የሚያምኑበትንና የሚቀበሉትን አይደለም የሚፈጽሙት፡፡ ሲያስፈለጋቸዉ ከላይ ይሾሙትና የሚሰራዉንና የሚያነበዉን ከስር ሆነዉ የሚያዘጋጁት እነዚህ የዓመፃ ቡድኖች ናቸዉ፡፡ «የብሔር ብሔረሰብ ተዋጽኦ» እያሉ የሚያወሩት ለማስመሰልና ለሽንገላ ነዉ እንጂ በወሰኛ ወንበር ላይ የሚያስቀምጡት ሰዉ ሲያስፈልጋቸዉ ጉሳዉን(ብሔሩን) የማወክል ነገር ግን የሚወክል እንዲመስል ስሙን ጭምር በመለወጥ ነዉ፡፡ እንደ ልባቸዉ የሚጋልቡት የጎሳዉ ተወካይ ካለ ደግሞ በእነርሱ አስተሳሰብ ቀርጸዉ ለራሳቸዉ ዓላማ ይጠቀሙበታል እንጂ ለጉሳዉ(ለብሔሩ) አንዳች ስሜት የላቸዉም፡፡ የእነርሱ ዓላማ ካልተሳካ ደግሞ እያንዳንዱ ጉሳ(ብሔር) እርስ በእርስ እንዲጨፋጨፍ ከማድረግ የማመለሱ ዉስጣቸዉ በቀልና ጥላቻ የሞላዉ ፍጹም የዲያብሎስን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ ናቸዉ፡፡

አሁን ያለዉ ትዉልድ ግን አስተሳሰቡ የሚሰፋበትን ንቃተ ሕሊናዉ የሚዳብርበት ዘመን ላይ ስለሆነ፤ የሁሉም ሕዝብ እኩልነትን የሚያምንና ሁሉም የአዳምና ሔዋን ዘር ነዉ፤ የኖኅ ልጆች የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገዶች ናቸዉ:: እንዲሁም የሦስቱ ነገድ ዉሕድ ዘር ኢትዮጵያዊ ነዉ በማለት፤ ኢትዮጵያዉያንን ሁሉ እንደ አባቱና እናቱ፣ እንደ ወንድምና እህቱ፣ እንደልጆቹ መመልከት ነዉ የሚጠበቅበት:: ይህ ከሆነ ደግሞ ማንም ይሁን ማን ልክ በአንድ ተወዳዳሪ ቡድን ዉስጥ የዘር፣ የቋንቋ፣ የነገድ፣ የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ብቃቱን እስካሟላና ለዉድድር ብቁ እስከሆነ ድረስ በዚያ ቡድን ዉስጥ እንደሚካተት ሁሉ፤ በሰሜንም በደቡብም በምስራቅም በምዕራብም ያለዉ ኢትዮጵያዊ ማንም ይሁን ማን ለዚያ የኃላፊነት ሆነ የሥልጣን ቦታ ብቃት ቃለዉ ማስቀመጥና እንደ ኃላፊነቱና ሥልጣኑ በአራቱም ማእዘን ያሉትን ኢትዮጵያዉን እንደ ራሱ ሆኖ ማገልገል ይጠበቅበታል እንጂ «ለዘሬ፣ ለጎጤ፣ ለነገዴ፣ ለክልሌ ... ወዘተ» የሚል ከሆነ እንኳን ለአገር ቀርቶ ለቤተሰቡ የሚጠቅም አይሆንም:: ምክንያቱም በበላይ የሚመራዉ ሸዋጁ(አታላዩ) መንፈስ ስለሆነ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለዉምና:: እዉነተኛ ሰዉ እንኳን የቅርብ ወገኑን ኢትዮጵያዉያንን ቀርቶ የሩቆቹ ወገኖቹን የዓለም ሕዝብን ሁሉ እንደ ራሱ መመልከት ይጠበቅበታል:: ያኔ ነዉ ቅንነት፣ እዉነተኛ ነት፣ መልካምነት ተላብሶ በምድርም ተባርኮ በሰማይም በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ ሕያዉ ሆነ ለመኖር የሚችለዉ:: አሁን በተጨባጭ የምናየዉ ግን ለሥልጣን፣ ለገንዘብ፣ ለክብር፣ ለዝና፣ ባጠቃላይ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም ሕሊናዉን የሸጠ ትዉልድ ነዉ ከኢሕአዴግ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በተለያየ የሥልጣንና የኃላፊነት ወንበር ላይ ተቀምጦ በሕዝብ ላይ የሚያላግጠዉና በሕዝብ ስም የሚነግደዉ፤ እንዲሁም የሕዝብ ደም የሚመጠዉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት በየክልሉ ሰራተኞች የስራ ቦታ ላይ እንዲቀጠሩ የሚያደርገዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋን መሰረት አድርጎ ነዉ:: የክልሉን ቋንቋ የማይችል የስራ እድል የለዉም:: ለእዚህ ያሎት አስተያየ ምን ይመስላል?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ከእዚህ በፊት እንደገለጽኩት የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ወደ ወንበር ላይ ሲቀመጡ ዉስጣቸው ጥላቻና በቀል የሞላዉ በበላይ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመሩ ስለሆኑ በክርስቲያኑ(በዐምሓራዉ) ላይ በቀል ለመፈጸም የተነሰ ስለነበረ ተሰምቶም ተደርጎም በማይታወቅ መልኩ «ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል(አገር) ነዉ:: ያ ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል(አገር) ነዉ)» በማለት ክፍፍል የፈጠረዉ:: በዚያም ሳይረካ የስራ መስፈርት እዉቀትና የትምህርት ደረጃ መሆኑ እየታወቀ ለዚያዉም ለዚያ እዉቀት ደረጃና የትምህርት ደረጃ የሚደረሰዉ በኢትዮጵያዉኛ(ዐማርኛ) ቋንቋ ሳይሆን በባዕዳን(በእንግሊዘኛ) ቋንቋ መሆኑ እየታወቀና ለስራም መስፈርቱ ያ የእዉቀትና የልምድ ደረጃ መሆን ብቻ ሲገባዉ፤ እነርሱ ግን ስዉሩ ዓለማቸዉ ክርስቲያኑንን(ዐምሓራዉን) መበቀልና የስራ ድርሻ እንዳይኖረዉ በማድረክ ለማዳከም፣ ከየክፍል ሀገሩ እንዲፈናቀልና እንዲሰደድ ለማድረግ ስለነበረ፤ ይኸዉ እንደምናዉቀዉ «የዚህን ቋንቋ አትችልምና የስራ ድራሻ የለህም» እየተባለ ከየመስራቤቱና ከእናት አገሩ እንዲፈናቀልና ወደማያዉቀዉ አካባቢ እንዲሰደድና እንዲንከራተት ተደርጓል:: በአንዳንድ «ክልል» በተባሉት መስሪያ ቤቶች እየሰራ ያለዉም የክልሉን ቋንቋ የሚናገር በቂ ባለሙያተኛ ስለሌለ ነዉ እንጂ እንደ ሕወሓት ኢሕዴግ እቅድ የክልሉን

ቋንቋ የሚናገር ባለሙያተኛ ከተገኘ ያ ስንት ዘመን የተማረበትና ልምድ ያካበተበት እዉቀት መና ቀርቶ «የዚህን ጎሳ(ብሔር) ቋንቋ መናገር አትችልምና የስራ እድል የለህም» ተብሎ የሚባረርና ከሚኖርበት ቦታ የሚፈናቀል ነዉ። ይህም የሚያሳየን ሕወሓት ኢሕአዴግ የተባለዉ ቡድን ፍጹም የዲያብሎስ እንደራሴ ሆኖ የበቀልና የግፍ ተግባር እየፈጸመ ያለ በእርግጥ እግዚአብሔር እንደተናገረዉ የዓመፃ ልጆች ናቸዉ። ታዲያ ይህ የጭከናና የበቀል ተግባራዉ በሰማይ ብቻ ሳይሆን በእዚህ ምድር ዉስጥ ጭምር በመቶ እጥፍ ዋጋ የሚያስከፍላቸዉ ይሆናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በሁለቱም ቦታ ነዉ እዉነተኛ ፍርዱን የሚሰጠዉ። በመሆኑም እነዚህ የዓመፃ ልጆች ከጥፋት ለመዳን ከፈለጉ በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር መስጠትና ግፍና በደል የፈጸሙበትን ሕዝብ በግልጽ ይቅርታን መጠየቅ አለባቸዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ እዚህ ጋር አያይዤ የምጠይቀዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት « ይህ የዚህ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነዉ፣ ያ ደግሞ የዚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነዉ» እያለ የመሰረተዉ መንግሥታት ትክክል አይደለም እያሉን ነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ ለመሆኑ የዛሬ መቶ ዓመት፣ ሁለት መቶ ዓመት፣ አምስት መቶ ዓመት፣ አንድ ሺህ ዓመት፣ ሁለት ሺህ ዓመት፣ ሦስት ሺህ ዓመት፣ አምስት ሺህ ዓመት ... ወዘተ አሁን ያሉ ከተማዎች ሆኑ አሁን ሰዉ ያለባቸዉ ቦታዎች ላይ ሰዉ የሚባል ይኖር ነበር ወይ? ማን ነበር ያንጊዜ? በደንና በአራዊት የተሞላ አልነበረምን? በአዲስ አባባ ከዛሬ መቶ ሃያ አምስት ዓመት በፊት ማን ይኖርባት ነበር? በደንና በአራዊት የተሞላች አልነበረም? ሌሎቹን አካባቢዎች መቼ ነዉ የተቆረቆሩት? ቀድሞ ሰዉ ይኖርባቸዉ ነበር? በረኃና ዱር እነዲሁም በደንና በአራዊት የተሞሉ እልነበረም? ታዲያ «ይህ የእኔ ክልል ነዉ፣ ይህ የዘሮቼ ግዛት ነዉ፣ ይህ የጎሳዬ ክልል ነዉ» ብሎ ደፍሮ ለመናገር የሚችል ሰዉ አለ?

እዉነታዉ ግን ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዉያን ሁሉ ስለሆነች በአራቱም ማእዘን ያለ ቦታ የሁሉም ኢትዮጵያዉያን ነዉ እንጂ የአንድ ጎሳ(ብሔር) ወይንም የአንድ ዘር ወይንም የአንድ ነገድ አይደለም። ይህ «ክልል(አገር)» ተብሎ ክፍፍል የመጣዉ ለበቀልና ለስዉር ዓለማቸዉ ማሳኪያ ብቻ ነዉ። ሰሜንም ደቡብም ምስራቅም ምዕራብም ሁሉም የኢትዮጵያዉያን መኖሪያ የሆነ ነዉ እንጂ የማንም ጎሳ(ብሔር) አይደለም። ልክ አዲስ አበባን በአራቱም ማእዘን ያሉ ሕዝቦች ከተማቸዉና መኖሪያቸዉ አድርገዉ እንደሚጠቀሙባትና ሁሉንም በእኩልነት የምታስተናግድ እንደሆነች ሁሉ፤ በአራቱም ማእዘን ያሉ ቦታዎች ሁሉም ኢትዮጵያዉን በእኩልነትና በነጻነት የሚኖሩበት ይሆናል። የዘረኞችና የጎጠኞች ተግባር ከንቱ ይሆናል። የዘሩትን የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፍሬ መራራ ቢሆንም የመጀመሪያ ጨላጭ እነሱ ይሆናሉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰዉ በምድርም በሰማይም እንደ ስራዉና እምነቱ ነዉ የሚፈርድለትና የሚፈርድበት።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ባለጊዜ ከሆኑ በኋላ የተለያዩ የስም መንግሥታትና ንጉሦች(ፕሬዝደንት) ተፈጥረዉ፣ ዋናዉ አሽከርካሪና አዛዥ ናዛዥ የሆነዉ

ሕወሓት(ወያኔ) የሆነዉ ቡድን በፈጠራቸዉ የክልል መንግሥታት ዉስጥና በአገልጋዮቹ (ባሮቹ) አማካይነት «እናንተ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) የራሳችሁን ስም ብቻ ሳይሆን ሕይወት የሌላቸዉን የቦታዎች ስም ሳይቀር ቀይረዉባችኋል፡፡ ይኸዉም «አዳማ» የሚለዉን ናዝሬት፣ «ቢሾፍቱ» የነበረዉን ደብረዘይት፣ እንዲሁም በደልና ግፍ ያደረሱባችሁ ክርስቲያን(ዐምሓራ) በሆኑት በገላዉዴዎስ፣ በኃይለ ማርያም፣ በመኮንን ስም ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ አዳራሽ ሰይመዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ስያሜ ማጥፋትና መደምሰስ አለባችሁ» በማለት ኢ-ክርስቲያናዊ ዓለማ በመያዝ ፀረ ክርስትና ተግባር ፈጽመዋል፣ አስፈጽመዋል፡፡ ለእዚህ ያሉት አስተያየት ምንድነዉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፡ በተደጋጋሚ እንደተገለጸዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የኢየሱስ ክርስቶስ ተቃራኒ በሆነዉ በዲያብሎስ መንፈስ በበላይነት የሚመራና የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ ናቸዉ፡፡ በመሪነት ያሉት ዋና የዲያብሎስ እንደራሴ ሲሆኑ፣ ከስር ያሉት ባለሥልጣን ደግሞ ባለሚሎቹ፣ ካድሬዎቹ ደግሞ ዉዶቹ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ፀረ ክርስትና አቋምና ሕይወት ስለያዙ የቀደሙት አባቶችና እናቶች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሰብ፤ ባደገበት፣ የተለያየ ትምህርት በሰጠበት፣ ተአምራትና ፈዉስ ባደረገባት፣ በተወለደበት፣ ባጠቃላይ ከእርሱ ሕይወትና ተግባር ጋር በተገናኘ ሁኔታ የተለያየ ቦታዎችን ስያሜ ሰተዋል፡፡ ዲያብሎስ ደግሞ ቅናተኛና ምቀኛ ስለሆነ እንደ ልቡ በሆኑለት አገልጋዮቹ(ባሪያዎቹ) አማካይነት ስያሜዉን ሊያስጠፋ ችሏል፡፡ የቀደሙት አባቶችና እናቶች ብዙ የቦታ ስያሜ ቀይረዋል፡፡ ለምሳሌ ደብረ ማርቆስ ከአሥራ ዘጠነኛዉ ክፍል ዘመን በፊት የነበራት ስም መንቆረር ነበር፡፡ ነገር ግን ቀድሞ ከነበረዉ የተሻለና የበለጠ ስያሜ ስለሰጧት ያንን እንጠብቃለን፣ እናስጠብቃለን፡፡ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመሩ ደግሞ ፀረ ክርስቲያን ናቸዉና ይህን ስያሜዉን አይፈልጉትም፤ ወደ ጥንት ስሙ ይቀየር ሊሉ ይችላሉ፡፡ ሌላዉ እነዚህ የዓመፃ ልጆች በሕሊናቸዉ የነገሠዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ሕዝበ ክርስቲያኑ ለልጆቹ ከክርስትና ጋር የተያያዘ ስም እንዳያወጣ ጭምር ነዉ ሕሊናዉን የበከሉትና ጥላቻ እንዲያድርበት ያደረጉት፡፡ በዚህም ምክንያት በአሁን ሰዓት ትዉልዱ ጎጡን(ብሔሩን) የሚገልጽበትን ስያሜ ነዉ ለልጁ የሚያወጣዉ እንጂ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ባገኘበት ወይንም የእግዚአብሔር ወገን መሆኑን የሚገልጽበትን አይደለም፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳየን አገሪቷን በአራቱም ማእዘን በበላይ ሆኖ የሚያስተዳድራት ዲያብሎስ መሆኑን ነዉ፡፡ ምክንያቱም በአራቱም ማእዘን የእርሱን አገልጋዮች ነዉ በወንበር ላይ ያስቀመጠዉ፡፡

የዲያብሎስ መንፈስ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ እንዲሁም ለቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት መልካም የሰሩትን የሚጠላና ዋንኛ ደመኛ ጠላቶቹ ስለሆኑ በዘመናቸዉ የተለያየ ስራ ሰርተዉ ያለፉትን «ክርስቲያኖች(ዐምሓራ) ናቸዉ» በማስባልና ጥላቻ በመፍጠር መታሰቢያቸዉን ሊያስጠፋ ችሏል፡፡ ነገር ግን ለዘላለም የሚጠፋዉና የሚደመሰሰዉ የዓመፃ ሰዎች መታሰቢያ ነዉ እንጂ መልካም የሰሩ ሰዎች አይደለም፡፡ ሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ከሕሊናዉ ተቃራኒ እንደሚያስብ እንድ ምሳሌ ባቀርብ ከምንም ጋር የማይገናኘዉን ዉስጣቸዉ ብቻ በክርስቲያን(በዐምሓራ) ላይ ጥላቻና በቀል ስለሞላዉ ብቻ ብዙ ዩንቨርስቲዎች የተለያየ ስም እንደተሰጣቸዉ እየታወቀ፤ አለማያ(ዓለም

ማያ) ተብሎ የተሰየመዉን «ዐምሓሮች(ክርስቲያኖች) ያወጡት ስያሜ ስለሆነ «ሐሮማያ» መባል አለበት ብለዉ የቀድሞ ስያሜዉን አጥፍተዋል። ያላወቁትና ያላስተዋሉት ነገር ቢኖር እጅግ በቅርቡ በሚመጣዉ በመልካሙ ዘመን (በኢትዮጵያ ቀን) የዓመፃ ልጆች መታሰቢያ ለዘላለም ሲጠፋ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ እንዲሁም ለቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ታሪክ የሰሩ ሰዎች መታሰቢያቸዉ ለዘላለም ይኖራል።

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ወደ ወንበር ላይ ከመጣ በኋላ በአራቱም ማእዘን «እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) እምነታችሁን፣ ሃይማኖታችሁም፣ ባህላችሁን፣ ቋንቋችሁን ለዉጠዋልና ወደ ራሳችሁ ማንነት ተመለሱ» በማለት ጥላቻንና በቀልን አሳድረዉባቸዉ ይኸዉም የተለያዩ ጎሳዎች(ብሔሮች) «የእኛ ዘመን መለወጫ እንደ ክርስቲያኖቹ አይደለም፤ የእኛ አምላክ የክርስቲያኖቹ ሆነ የእስላሞቹ አምላክ አይደለም፤ የራሳችን የኦሮሞ ጥቁር አምላክ አለን፤ እምነታችንም ዋቄፈታ ነዉ፣ እመቤታችንንና እናታችን አቴቴ ናት እንጂ የሀበሾቹ ነጭ አምላክና ነጭ እናት አይደለም፤ እንዲሁም ለእመቤታችንና ለአቴታችን በጨሌ አማካይነት ቅቤ እየቀባን ምስጋናችንንና አምልኮታችንን እናቀርባልን፤ ለራሳችን አምላክ በየወንዛወንዙና በየተራራዉ እንዲሁም በየአድባሩ ምስጋና እናቀርባለን፤ የእኛ በዓል የክርስቲያኖቹ በዓል ሳይሆን ፍቼ፣ ጨንበላላ፣ እሬቻ፣ አቴቴ... ወዘተ ነዉ» እያሉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት እንዲሁም በባዕድ አምልኮ በተበከለ ሕሊና የተለያዩ አምላኮችና አምልኮዎች ተፈጥረዉ እየተመለከትን ነዉ። ለእዚህ ያሉት አስተያየት ምን ይመስላል?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: አስቀድሜ ለማሳወቅ የምፈልገዉ ማንኛዉ ሰዉ በተሰጠዉ ነጻ ሕሊና አመዛዝኖና አገናዝቦ የሚያዋጣዉን የሕይወት መስመር ሊያዝ ይችላል። አሁን የምናየዉ ግን መንግሥት ብዙኃን መገናኛን (ማስ ሚዲያን) ለፓለቲካዉ ዓላማ ማስፈጸሚያ በመጠቀሙና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ክህደቱን እንደ እምነት፣ ርኩሰቱን እንደ ቅድስና፣ ዓመፃዉን እንደ መልካም ነገር እያቀረቡ የትዉልዱን ሕሊና ለሚፈልገዉ ዓለማ ላይ አዉሎታል። በዚህም ምክንያት ትዉልዱ ክህደቱን እንደ እምነት፣ ርኩሰቱን እንደ ታላቅ ስራ፣ ዓመፃዉን እንደ መልካም ተግባር ቆጥሮ እየኖረበት ነዉ።

እኔ ደግሞ እግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት የጠራኝ ስለሆነ እያስመሰልኩና እየሸነገልኩ እንዲሁም ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ እያደረኩ አልኖርም፣ አልመሰክርም። እንክርዳዱን እንክርዳድ፣ ስዴዉን ስንዴ ነዉ የምለዉ እንጂ፤ ቅርፊት ሥጋ ለባሽን ፈርቼ ክህደቱን እምነት፣ የርኩሰቱን ተግባር ቅድስና ተግባር፣ የዓመፃዉን ተግባር መልካም ተግባር አልልም። የተጠራዉበት ዋና ተግባሬ የዲያብሎስን ስራ መግለጽና የእግዚአብሔርን እዉነት መመስከር ብቻ ነዉ። ሌላ ሙያና ተግባር የለኝም። በዚህ የሚመጣብኝን ፈተና ሆነ መከራ በጸጋና በአኮቴት የምቀበለዉ ነኝ። ለዐይን ቅጽበት ለማትሞላ ለአጭሯ ምድራዊ ዘመኔ ስል ሕሊናዬን አልሸጥም፤ ከዓመፃ ልጆች ጋር አንዳች አንድነትና ኅብረት አልፈጥርም። በጨለማዉ ገዥ መንፈስ ተመርተዉ የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን ፈቃዳቸዉን አልፈጽምም፣ አላስፈጽምም። ለተለየ አገልግሎት የጠራኝ አምላክ ካልፈቀደላቸዉ በርስተቀር እነርሱ ሆኑ ሰይጣናት እንኳን ጉዳት ሊያደርሱብኝ ይቅርና አንዲቷን ጠጉሬን የመንካት

ሥልጣንና አቅም የላቸዉም:: ከተፈቀደላቸዉ ደግሞ በዚህ ቅርፊት ሥጋዬ አምላኬን አክብሬ ለሰማያዊ መንግሥትና የድል አክሊል እበቃለሁ እንጂ ከዓለም አንዳች የሚቀርብኝ ነገር የለም:: በመሆኑም አሁንም የምገልጸዉና የምመሰክረዉ በግልጽ ነዉ::

ቀደም ሲል በግልጽ እንደተገለጸዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የጨለማዉን ገዥ ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ቆርጦ የተነሳና የጨለማ ፍሬም ከሚገባዉ በላይ ለጨለማዉ ገዥ ለዲያብሎስ ያፈራ ነዉ:: እንደሚታወቀዉ በዓለም ላይ እንደ እምነት ሁለት ዋንኛ ሃይማኖቶች አሉ:: እነሱም ክርስትናና እስልምና ናቸዉ:: ሁለቱም በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ አምላክ የሚያምኑ ናቸዉ:: ዋንኛ ልዩነታቸዉ ክርስቲያኖች ይህ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ በሥጋ ማርያም መገለጹን የሚያምኑ ሲሆን፤ በእስልምና እምነት ዉስጥ ያሉ ደግሞ «የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ በሥጋ ሊገጥ አይችልም» በማለት በሥጋ ማርያም የተገለጸዉ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ አገልጋይና መልእክተኛ የሆነ እንደ ነብያችን መሀመድ ነብይ ነዉ» ብለዉ ነዉ የሚያምኑት:: እዉነተኛ ክርስቲያኖች ደግሞ «በሥጋ ማርያም የተገለጸዉ ኢየሱስ ክርስቶስ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆን አምላክ አልፋና ዖሜጋ የሁሉ ፈጣሪና አምላክ ነዉ:: ከእርሱ በላይ ማንም የሌለ፤ የሁሉ አዛዥና አስገኝ ነዉ እንጂ፣ የሁሉ ፈጣሪ አገልጋይና መልእክተኛ ነብይ አይደለም» ብለዉ ነዉ የሚያምኑት:: እንዲሁም እርሱ እግዚአብሔር ወልድ የገለጻቸዉ በሥልጣን፣ በህልዉን፣ በክብር፣ በፍርድ፣ በመለኮት፣ ባጠቃላይ በባሕርይ አንድ የሆኑ በአካል፣ በስም፣ በግብር ብቻ የሚለያዩ እርሱን የማይቀድሙና የማይበልጡ እርሱም የማይቀድማቸዉና የማይበልጣቸዉ «እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ» በመባል የሚታወቁ እንዳሉና አንድ አምላክ አንድ ፈጣሪ መሆናቸዉን ገልጾልናል:: በዚሁ መሰረት እግዚአብሔርን በአንድነትና በሦስትነት እያመለክነዉ እንገኛለን::

ታዲያ ወገኖቻችን የሆኑት የእስልምና እምነት ተከታዮች ከቅርብ ወላጆቻቸዉ በወረሱት እምነት ዉስጥ እምነቱ በሚያዛቸዉ ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ መልካም ተግባር፣ መልካም ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱ አማኞች አሉበት:: እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ከተገለጸ በኋላ በዮሐ. ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 16 እንደተገለጸዉ «ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፣ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛዉም አንድ::» በማለት በሰጠዉ ተስፋና ቃል ኪዳን መሰረት በቅንነትና በመልካም ሕይወት የሚመላለሱት ድምፁን ይሰማሉና በቅርቡ ወደ እዉነተኛ በረት ዉስጥ ገብተዉ አንድ መንጋ ይሆናሉ በአንድም እረኛ ይጠበቃሉ:: ቅንነትና መልካም ሕይወት የሌላቸዉን በዓመፃና በክህደት የሚመላለሱትና ለጥፋት የተሰለፉትን ደግሞ ከዓመፃ ልጆች ጋር በተለያየ መንገድ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጠረጋሉ፤ ይጸዳሉ::

በሕወሓት ኢሕአዴግ ዘመን የተስፋፉትና አሁን ላሉበት ደረጃ የደረሱ በእምነት ሽፋን በየወንዛወንዙና በየተራራዉ እንዲሁም በተለያየ ምናምንቴ ቦታ ላይ የሚፈጸሙ ባዕድ አምልኮዎች ሁሉም ርኩሰት ናቸዉ:: በመሆኑም የአምልኮ ምንዝርና የፈጸሙ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል:: ስለ ዓመፃና ርኩሰት ተግባራቸዉ ዋጋ ይከፍሉበታል:: የሚገርመዉና የማሳዝነዉ

አንዳንዶቹ ሕሊናቸዉ እንዳይወቅሳቸዉና የሌሎችንም ሕሊናቸዉን ለማደንደንና ለመሳብ እንዲሁም ለማታለል «እኛ የምናመልከዉ ፈጣሪን ነዉ፣ ምስጋናም የምናቀርበዉ ለእርሱ ነዉ» በማለት ራሳቸዉን እያሞኙና እያጃጃሉ ይገኛሉ፡፡ ዲያብሎስ እኮ እንኳን በምድር በግዛቱ አይደለም በሰማይ እንኳ «እኔ ፈጣሪ ነኝ፣ እኔን አምልኩ፣ አመስግኑ» በማለት ነዉ ስንቱን መናፍስት ጉድ የሰራዉና ያመኑበትንና ተጠራጣሪዎቹን ከሰማያት ዉስጥ ወደ እዚህች ምድር እንዲገቡና ፍዳና መከራ እንዲቀበሉ ያስደረገዉ፡፡ በዚህች ምድርም «እኔ ዲያብሎስ ነኝ፣ እኔን አምልኩ፣ አመስግኑ» አይልም፡፡ ከበፊቱ በተራቀቀ መንገድ ነዉ ራሱን እንደ ፈጣሪና አምላክ መስሎ እየተመለከና እየተመሰገነ ያለዉ፡፡

ከሁሉ ከሁሉ የሚያስገርመዉና የሚያሳዝነዉ የክህነት ልብስና መስቀል ይዘዉ በዚህ ርኩሰት በሆነዉ ባዕድ አምልኮ ላይ እየተገኙ ቡረኬ የሚሰጡና የሚሰብኩ የኢሕአዴግ ካድሬ፣ የሃይማኖት ሴሰኛ የሆኑ፣ አምልኮ ምንዝርና የፈጸሙ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ፡፡ እጅግ የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ የኢሕአዴግ ቀኝ እጅ የነበሩት ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስ እንደነዚህ የሃይማኖት ሴሰኞችና አምላኮ ምንዝርናን የሚፈጽሙትን አስመሳይ ካህናትን ታላቅ ተግባር እንደፈጸሙ በመቁጠር በሹመት ላይ ሹመት እየጨመሩ ርኩሰትን ማበረታታቸዉ ነዉ፡፡ እዉነተኛ የሃይማኖት ተጠሪ ቢኖር ኖር እንኳን በሹመት ላይ ሹመት ሊጨምር ቀርቶ ወዲያዉ ነበር ሥልጣነ ክህነቱን ሽሮ በዚያዉ በዲያብሎስ አገልጋይነቱ፣ በካድሬነቱ እንዲኖር ያስደርግ የነበረዉ፡፡ ነገር ግን የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ የቀደሙት መምህራንና ሊቃዉንት እንዲሁም የጻድቃንን ተግባርና ሕይወት ይዞ የሚያገለግል እዉነተኛ ቆራጥ የሃይማኖት አባት በመጥፋቱ እንደነ ሆዱና ጥቅሙ አምላኩ «ተመሳስለህ ኑር ፣ ሕሊናህ ባይቀበለዉም ለመኖር ስትል ተቀበል» በሚለዉ የአእምሮ ሕፃናትና የአእምሮ ቀላሎች መመሪያ መሰረት እጅግ ብዙዎቹ በማስመሰል አገልግሎት ዉስጥ ይገኛሉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ወደ ወንበር ከመጣ በኋላ በዲሞክራሲ ሽፋን በአብያተክርስቲያናት ፊት ለፊት ወይንም አጠገብ መስጊዶች(መስኪድ) እንዲሰሩ አድርጓል፡፡ እንዲሁም የሰማዕታት ሐዉልትና የብሔርብሔረስብ ሐዉልት አቁሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ፕሮቴስታንትና መሰል ድርጅቶች በየሰፈሩና መንደሩ እንዲስፋፉ አደርጓል፡፡ ይህ ተግባሩ ፍጹም ፀረ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ፀረ ክርስቲያን መሆኑንን አይመሰክርበትም ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በሚገባ መታወቅ ያለበት ለ7504 ዓመት ያህል የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጋር በመሆን እዉነትን ሲያጠፋና ትዉልዱን በሞት ሕይወት አስኪዶ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ሲዳርግ ነዉ የኖረዉ፡፡ ዓለማዉን የሚያስፈጽመዉም ለእርሱ እንደልቡ የሆኑትን ሰዎች በመምረጥና ወደ ወንበር ላይ በማምጣት ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ሕወሓት ኢሕአዴግ የተባለዉ ቡድን ለእርሱ እንደልቡ ሆነዉ ስላገኛቸዉ ይኸዉም በሕሊናቸዉ ነግሦ ፈቃዱን በአራቱም ማእዘን ሲያስፈጽም እየተመለከትን ነዉ፡፡ እነዚህ የዲያብሎስ አገልጋዮችና ባለሚሎች ወደ ወንበር ሲመጡ የሚመሩበት ሕሊና በሰይጣናት መንፈስ የሚመራ ስለነበረ ሰይጣናት ደግሞ ዋና ጠላታቸዉ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና አማኞች ስለሆኑ

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይና  በአማኙ  ላይ የብቀላና የግፍ ተግባር ፈጽመዋል፣ አስፈጽመዋል፡፡ ያም አልበቃ ብሏቸዉ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት ተዋሕዶ የኖረዉን ሕዝብ በሃይማኖት በመከፋፈልና አንዱን በአንዱ ላይ ጥላቻ በመፍጠርና በማነሳሳት ተግባር ላይ ተሰልፈዋል፡፡

በየአብያተክርስቲያኑ ፊት ለፊትና አጠገብ መስጊድ ማሰራታቸዉ የእስልምና እምነት ተከታዩን በክርስትና እምነት ተከታይ ላይ ለማነሳሳትና ለማስፈራራት እንዲሁም ተጽህኖ ለመፍጠር የተጠቀሙበት መሰሪ ተግባር ነዉ፡፡ በቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ያቆሙት ሐዉልትም «እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) ግፍ ፈጽመዉባችኋል፣ ይህ ከሕሊናችሁ እንዳይጠፋ፣ መዘከሪያ ነዉ፡፡ በመሆኑም ያንን የነፍጠኛ ሥርዓት ለመመለስ በሚንቀሳቀሱ ሰዎች ላይ ማንኛዉን እርምጃ ከመዉሰድ እንዳትመለሱ፣ ጊዜዉ የእናንት በመሆኑ ማንም ምንም ሊያደርጋችሁ እንደማይችል በዚያዉ በሚያመልኩበት ቦታ ላይ ይኸዉ የፈለጋችሁትን ማድረግ እንድትችሉ እኛ የኢሕአዴግና አጋር ድርጅቶች ሙሉ ዋስትና ሰተናችኋል፡፡» በማለት ዐይን ያወጣ የእብሪትና የትዕቢት፣ የንቀትና የጥላቻ፣ እንዲሁም የበቀል ተግባር መሆኑ ነዉ በግልጽ የሚያሳየን ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ በአሁን ሰዓት አንዳንድ ሰዎችና «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች፣ ባለሥልጣነት፣ካድሬዎች እንዲሁም የሥርዓቱ ደጋፊዎች»ነን የሚሉ ሰዎች «ኢሕአዴግ ከሌለ አገሪቷ ትበታተናለች፤ ሕዝቡም እርስ በእርስ ይጫራሳል» የሚሉ አሉ፡፡  እንዲሁም «የተደራጀና ብቃት ያለዉ ተቃዋሚ ድርጅት ስለሌለ ሥልጣኑን የሚረከብና የሚመራ አካል የለም» የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡ ለእዚህ ያሎት አስተያየት ቢሰጡን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡  በእርግጥ ሕወሓት(ኢሕአዴግ) የተባለዉ ቡድን እርሱ በሥልጣን ላይ ከሌለ አገሪቱ እንድትበታተንና ሕዝቡም እርስ በእርስ እንዲጫረስ አድርጎ ነዉ ኢትዮጵያን የቀረጻትና ሕዝቡም ጥላቻና በቀል እንዲያድርበትና ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ የሚለዉን ከደሙ ጋር የተዋሐደዉን ስሜት ከልቦናዉ መንግሎና ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በልቡ ስላነገሠ የተባለዉ ሲጋት ቢባል ብዙም አያስገርምም፡፡ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» እንዳለች፤ እነዚህ  በሕወሓት (ኢሕአዴግ) ቡድን ዉስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች አገሪቷን በቋንቋ ከፋፍለዉና ክልል መንግሥታት የፈጠሩት እንዲሁም «እነዚህ ክርስቲያኖች(ዐምሐራዎች) ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ ሃይማኖታችሁን፣ እምነታችሁን... ወዘተ የለወጡና በደልና ግፍ የፈጸሙባችሁ ናቸዉ፡፡ አሁን ያንን የነፍጠኛና የገዢ መደብ ሥርዓት ለመመለስ የሚሯሯጡ የሥርዓቱ አቀንቃኝ ተቃዋሚ ድርጅቶች ስላሉ ልትደመስሷቸዉ ይገባል» እያሉ በየስብሰባዉ፣ በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያ) ቅስቀሳ ያደረጉትና እያደረጉም ያሉት፤ «እኛን ከሥልጣናችን የሚጋፋና የሚቀናቀን ካለ እናጠፋዋለን፣ እንደመስሰዋለን» በማለት ታብየዉና በኃይላቸዉ ተመክተዉ የሚናገሩትና የሚሰሩት ለዚሁ ለጥፋት ዓለማቸዉ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ከአገሪቷና ከሕዝቡ በላይ ለራሳቸዉ ሥልጣንና ጥቅም የቆሙ መሆናቸዉንና ይህ ሥልጣናቸዉና ጥቅማቸዉ የሚቀር ከሆነ አንዳች ኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌላቸዉና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ የተነሱ ቅጥረኞች ስለሆኑ የአገሪቷ መበታተን ሆነ የሕዝቡ እርስ በእርስ መጫረስ አንዳች ስሜት አይሰጣቸዉም፡፡ ሰማኒያ መንግሥታት

ተመስርተዉ ሕዝቡ እርስ በእርስ እየተጣላ ቢኖርና አገሪቷም ከነስሟ ብትደመሰስ፤ ዓይነ ሕሊናቸዉ በሥልጣንና በጥቅም የታወረ ስለሆነ ደንታም የላቸዉም፡፡ ለዚህ ነዉ ከአገሪቱ መሪ ጀምሮ እታች ድረስ ባሉ ባለሥልጣናት «በሬሳቻችን ላይ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰዉ ሕገ መንግሥቱን ሊያሻሽልና ሊለዉጥ አይችልም» በማለት በትዕቢትና በእብሪት፣ በትምክህት የሚናገሩት፡፡

ማን መሆናቸዉን አላወቁም፣ አላስተዋሉም እንጂ እንኳን እነሱ በባሕርይዉ የማይለዋወጥና ሁሉን በፈለገዉ መንገድ ማከናወን የሚቻለዉ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንኳ ዉሳኔዉን ያሻሽላል፣ ይለዉጣል፣ እንደ ሕዝቡ ጥያቄና ፈቃድ ባይሆንም ፈቃዳቸዉን እንዲፈጽሙ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ነገር ግን እንደ ምርጫቸዉ ነዉ ዋጋ የሚከፍላቸዉና የሚያስከፍላቸዉ እንጂ እንምኞታቸዉ አይደለም፡፡ ለእዚህም ነዉ ሰዎችን በኃጢአታቸዉ ሊያጠፋቸዉ ከወሰነ በኋላ ንስሐ ሲገቡ ይቅር የሚላቸዉና ዉሳኔዉን በምሕረት የሚለዉጠዉ፡፡ እንዲሁም እርሱ ራሱ በሕዝቡ ላይ ለመንገሥ ወስኖ ሕዝቡ «እኛ ያንተን ንግሥና አንፈልግም የሰዉ ንጉሥ አድርግልን» ብለዉ ሲጠይቁት፤ «ከእኔ ሌላ ንጉሥ ከፈለጋችሁ እንደ ምርጫችሁ ፍዳችሁን የሚያሳይ፣ መከራና ስቃይ የሚያደርስባችሁን መሸም ትችላላችሁ» በማለት ምርጫቸዉን ያከብርላቸዋል፡፡ የዘመኑ መሪዎችና ባለሥልጣናት ግን የጨለማዉ ገዥ እንደራሴና ባለሟል እንዲሁም ዉዶች ስለሆኑ ትዕቢታቸዉና እብሪታቸዉ ከእርሱ በልጦ በራሳቸዉ ላይ በሚሟረት፤ «ከእኛ በላይ ለሕዝብ አስባለሁ፣ የሚበጀዉን አደርጋለሁ» የሚል አካል ካለ በሬሳችን ላይ ካልሆነ በስተቀር አይችልም ስላሉ፤ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ደግሞ፤ እግዚአብሔርን «አንተ ንገሥብን፣ ያንተን ሥርዓት ዘርጋልን፣ ያንተን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ እንደራሴዎችህንና ባለሟሎችህን እንዲሁም አገልጋዮችህን በእዉነተኛ ወንበር ላይ አስቀምጥልን?» ብለዉ ስለጠየቁና እየጠየቁም ስለሆነ፤ እንደ ሕዝቡ ጥያቄና ፍላጎት እግዚአብሔር በአራቱም ማእዘን የሚነግሥበት ወራት ደርሷልና ትዕቢተኞቹንና እብሪተኞቹን እንዳልነበሩ ያደርጋቸዋል ማለት ነዉ፡፡

እነዚህ «የዓመፃ ልጆች» የተባሉ የዲያብሎስ እንደራሴዎች መሪዎች፣ ባለሟሎች ባለሥልጣናት፣ እንዲሁም ዉዶች ካድሬዎች፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የዘሩት መራራ ፍሬ የመጀመሪያ መራራዉን ጽዋ የሚጠጡት እነሱ ሲሆኑ፤ ከዚያም ሕዝቡ እንደ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተባባሪነቱ ደረጃ ይጠጣል ማለት ነዉ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍርዱ እዉነተኛ ና ፍትሐዊ ስለሆነ ማንም ሰዉ እንደ ሥራዉ ዋጋ ይቀበላል ወይንም ይከፍላል፡፡ በእርግጥ የሕወሓት(ኢሕአዲግ) ባለጊዜነት ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት በኋላ የተሻረና የተደመደመበት ቢሆንም፤ ከእንግዲህ የሚቀረዉ እያንዳንዱ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚ ሁሉ፤ የዘራዉን ፍሬ ማጨድና ስለ ዓመፃዉ ዋጋ ከፍሎ ማለፍ ብቻ ነዉ፡፡ ይህም ለኢትዮጵያ ትንሣኤ የሽግግር ዘመን ላይ ነን ማለት ነዉ፡፡ እነሱ ሌት ተቀን ሐሳባቸዉና ተግባራቸዉ የሥልጣን እድሜያቸዉን ማስረዘምና የአገሪቷን ሀብት መቦጥቦጥና ለራስ ማከማቸት ስለሆነ፤ እንዲሁም «በሬሳችን ላይ ካልሆነ በስተቀር ማንም በዚህች አገር ላይ ከእኛ ዉጪ ሊመራና ሊያስተዳድር አይችልም» ስላሉ፤ የኢትዮጵያ እዉነተኛዉ መሪና አስተዳዳሪ እግዚአብሔር በተለያየ ቁጣዉ እንደ ትዕቢታቸዉና እብሪታቸዉ ዋጋ አስከፍሏቸዉ ከወንበሩ ይቆርጣቸዋል፤ ተራነታቸዉን ያሳያቸዋል፤ ልክ ያስገባቸዋል፤ በዓመፃቸዉና

በትዕቢታቸዉ እስከ መጨረሻ ከጸኑ ደግሞ በመጨረሻዉ ቁጣ ከምድር ያጸዳቸዋል፤ ይጠርጋቸዋል። ከዚያም የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለዓለም ገልጦ በአራቱም ማእዘን እርሱ ይነግሣል፤ ፈቃዱም በአራቱም ማእዘን በእዉነተኛ አገልጋዮቹ አማካይነት ይፈጸማል።

ሌላዉ «ከኢሕአዲግ የተሻለ  አገርን ሊመራ የሚችል ድርጅት የለም» የሚለዉ አባባል ያሚያሳየን ነገር  ቢኖር፣ አሁን ያለዉ መንግሥት ምን ያህል ሕዝቡን ማደንዘዝ እንደቻለና እዉነተኛ ና ቅኖች ሰዎችን አጥፍቶና አሳዶ እንዲሁም አንገት አስደፍቶ ያለ መሆኑን ነዉ። እነሱ እንኳ ከጫካና ከበረኃ ወተዉ አገር መምራትና ማስተዳደር ከቻሉ፤ ስንት በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ትምህርት የላቀ ደረጃ ላይ የደረሱ ዕንቁ የሆነ ልጆች ያሏት አገር እንዴት ሰዉ እንደሌላት ተቆጥሮ «በክፋት፣ በትንኮል፣ በበቀል፣ በጥላቻ፣ በዓመፃ፣ በትዕቢት፣ በክህደት፣ ባጠቃላይ ሰዎችን በሚያረክስ ሕይወት የሚመላለሱ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ይህችን አገር ሊመራና ሊያስተዳድር የሚችል የለም» ይባላል!?  እግዚአብሔር ያዘጋጃቸዉ የራሱ ምርጦች ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም የሚተርፉ አሉት። አሁን ግን የነገሠዉ ዲያብሎስ ስለሆነ ቦታ አላገኙም፤ እነሱም የዲያብሎስ አገልጋይ ለመሆን ስለማይፈልጉ ወደ ወንበር አልመጡም። የዲያብሎስ ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእግዚአብሔር ቁጣ ካልተደመሰሰ በስተቀር ወደ ወንበር ለመምጣት አይፈልጉም። ምክንያቱም አንዳች የሥልጣን ሆነ የተለየ ክብርና ጥቅም የማይፈልጉ ስለሆነና ሕዝቡን በእዉነትና በቅንነት፣ በታማኝነት ብቻ በማገልግል በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ስለሆነ ፍላጎታቸዉ፤ ከዲያብሎስ ስራ ፈጻሚና አስፈጻሚዎች ጋር አንዳች አንድነት ሆነ ኅበረት የላቸዉም። ራሳቸዉን ለዓለም ስላልገለጡ፣ ሕዝቡም የሚመለከተዉ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱትንና የሚናገሩትን እንዲሁም የሚሰሩትን ሰዎች እንጂ፤ እግዚአብሔር ያዘጋጀዉን ስላለወቀና ስላላስተዋለ፤ የዲያብሎስ አገልጋዮችን እንደ አገልጋይ ቆጥሮ ተቀብሏቸዋል። ነገር ግን እዉነት ስትገለጽ የማን እንደራሴና አገልጋይ መሆናቸዉን ስለሚያዉቅና ስለሚያስተዉል አንቅሮ ነዉ የሚታፈታቸዉና ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰለፈዉ።

በመጨረሻ የምለዉ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ የዓለም ሕዝቦች እግዚአብሔር በአራቱም ማእዘን የሚነግሥበት፣ ፈቃዱ የሚፈጸምበት ወራት ስለደረሰ፣ ራሳችሁን ለእዉነተኛ ንስሐ እያበቃችሁና ለሕሊናችሁና ለአምላካችሁ ታምናችሁ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ተመላለሱ። ከዓመፃ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት ሕይወት ራሳችሁን ለዩ። የዓመፃ ልጆች ከምድሪቱ በእግዚአብሔር ቁጣ በተለያየ መንገድ ስለሚጠረጉ አንዳች ከእነሱ ጋር አንድነትና ኅብረት እንዳትፈጥሩ። እግዚአብሔር በቸርነቱና በምሕረቱ ለኢትዮጵያ ትንሣኤና በዓለም ለሚዘረጋዉ ሰማያዊ ሥርዓት ለመልካሙ ዘመን ያብቃን።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አምስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: አንዳንድ የሕወሓት ኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ለሃያ ዓመት በክርስቲያኑ(በዐምሓራዉ) ላይ የፈጸሙት ግፍና በደል እንዲሁም በቀል እስከአሁን ሳያረካቸዉ ቀርቶ፤ አሁንም «የክርስቲያኑን(ዐምሓራዉን) ሥርዓት ዳግም እንዳያንሰራራ አድርገን አከርካሪዉን መስበር አለብን» እያሉ በትዕቢትና በእብሪት ይናገራሉ፣ ይደነፋሉ:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል::

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: እግዚአብሔር እንደ ሰዉ ለሚፈጸምበት ዓመፃና ክህደት ወዲያ ምላሽ አይሰጥም:: ምናልባት ወደ ልባቸዉ ይመለሱ ይሆናል እያለ የንስሐ እድሜ ይሰጣል:: ነገር ግን እስከ መጨረሻዉ በትዕቢታቸዉ የሚጸኑ ከሆነ በምድርም አይቀጡ አቀጣጥ ከቷቸዉ ነዉ ወደ ሁለተኛዉና ዳግም የንስሐ እድል ወደ ሌለዉ ለሕያውነት ዘመን ስለ ትዕቢትና እብሪት ተግባራቸዉና ሕይወታቸዉ ወደሚቀጡበት የጨለማ ቦታ የሚጠራቸዉ:: በመሆኑም አሁን እየተመሩበት ያለዉ ሕሊና በጥላቻና በበቀል የተሞላዉ በዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ አሁንም የቀድሞዉን የእብሪትና የትዕቢት ንግግር ቢናገሩ ብዙም አያስደንቅም:: ሊያስደንቅና ሊያስገርም የሚችለዉ በተቃራኒዉ «ዉስጣችን በጥላቻና በበቀል ተሞልተን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ስንፈጽምና ስናስፈጽም ነበር:: እንዲሁም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በቀልና በደል፣ ግፍ ስናስፈጽምና ስንፈጽም ነበር» ቢሉ ነበር:: ነገር ግን አሁን እየታየዉ ያለዉ ራሳቸዉን ለከፋ ቅጣትና ጠረጋ እያዘጋጁና «የእግዚአብሔር ቁጣ ዘገየብን፣ ትዕቢታችን አልበርድ አለ» እያሉ የእግዚአብሔርን የከፋ ቅጣት እየናፈቁ መሆኑን ነዉ የሚሰማኝ::

**ጠያቂዉ አገልጋይ**: ሕወሓት ኢሕአዴግን የመሰረቱት አራት ድርጅቶች መሆናቸዉ ይታወቃል:: ታዲያ «ሕወሓት ኢሕአዴግ» ብለዉ ከመጥረት «ኢሕአዴግ» ብቻ ብለዉ ለምን አይጠሩም?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በግልጽ እንደሚታወቀዉ ኢሕአዴግን የፈጠረዉ ሕወሓት የተባለ የዓመፃ ቡድን ነዉ:: በአራቱም ማእዘን ያሉትን ሕዝቦች በቋንቋ ከፋፍሎ ዓለማዉን ለማሳካት ሲልና ሌሎቹ የጎሳቸዉ(የብሔራቸዉን) ቋንቋ ብዙ ተናጋሪ ስላለዉ በቀላሉ እያንዳንዱን ጎሳ ለዓለማዉ ለማሰለፍና ፈቃዱን ለመፈጸም ይቻለዉ ዘንድ ነዉ እነሱን በዙሪያዉ ያሰባሰባቸዉና፤ እንደ ፈለገዉ ሊጋልባቸዉና ሊያሽከረክራቸዉ የሚችለዉን «የጎሳዉ(የብሔሩ) ተወካይ ነን» የሚሉትን ለይስሙላ ወደ ወንበር ያመጣቸዉና የጨለማዉን ተግባር ሲያስፈጽማቸዉ የነበረዉና ያለዉ:: እያንዳንዱ የፈጠራቸዉ አገልጋዮቹ በነጻ ሕሊናቸዉ ያመኑበትን መፈጸም እንዳይችሉ በተለያየ ወንጀልና ጥቅማጥቅም አስሮ ስለያዛቸዉ እንደ ድምፅ ማጉያ አስተጋቡ የተባሉትን ነዉ የሚያስተጋቡት:: ጦሩ፣ ደኅንነቱ፣ ቁልፍ ሥልጣን ቦታ፣ የተለያዩ ሀብትና ንብረት በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ሲፈልጉ «ንጉሥ(ፕሬዝዳንት) ነህ፣ ሲፈልጉ ጠቅላይ ሚኒስትር ነህ፣ ሲፈልጉ ሚኒስትር ነህ፣ ሲፈልጉ አጋር ድርጅት ነህ፣ ... ወዘተ» እያሉ ለሥልጣንና ለጥቅም እንዲሁም ለክብርና ለዝና ዓይነ ሕሊናዉን ያሳወረዉን በወንበር ላይ እያስቀመጡ አገሪቷን እንደፈለጉ

የሚያደርጉት እነዚህ ከሻዕቢያ ጋር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ታጥቀዉ የተነሱ የጥፋት ኃይሎች «ሕወሓት(ወያኔ)» ብለዉ ራሳቸዉን የሰየሙት ስለሆኑ ነዉ፤ ፈላጭ ጎራጭ መሆናቸዉን እንዲሁም ስለ ዓመፃዉ፣ ስለክህደቱ፣ ስለርኩሰቱ ተግባር ዋንኛ ተጠያቂዎች መሆናቸዉን ለማጉላት ፈልጌ ነዉ ሕወሓት ኢሕአዴግ በማለት የምጠራቸዉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: እዚህ ላይ ሌሎቹ ቡድኖች(ድርጅቶች)ና አጋር ቡድኖች(ድርጅቶች) እንዲሁም ተለጣፊ ቡድኖች(ድርጅቶች) ስለ ዓመፃ፣ ስለ ክህደት፣ ስለ ርኩሰት ተግባራቸዉ አይጠየቁም እያሉኝ ነዉ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: አይደለም:: እግዚአብሔር እያንዳንዱን እንደ ዓመፃዉ ደረጃ ነዉ ዋጋ የሚያስከፍለዉ:: ማንም ከእግዚአብሔር ፍርድና ቁጣ አያመልጥም:: በዓለማ የሚንቀሳቀሰዉ ዋና ፈጻሚዉና አስፈጻሚዉ ሆነ ሕሊናዉን ሸጦ በዓመፃ ፈጻሚነትና አስፈጻሚነት ላይ የተሰማረዉ ሁሉ እንደ ዓመፃ፣ ክህደቱ፣ ርኩሰቱ ተግባር ይጠየቃል:: በምድርም በሰማይም ዋጋ ይከፍልበታል:: ምን ያህል በጦራቸዉና በስለላ መዋቅራቸዉ ቢመኩ እንዲሁም በሥልጣናቸዉና በሀብታቸዉ ቢታበዩ እጅግ እጅግ በቅርቡ ከወንበራቸዉ ሙሉ በሙሉ ከመቆረጥና በእግዚአብሔር ቁጣ ከመጠረግ አይተርፉም:: ምናልባት እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ የተወሰነ ቅንነትና የዋህነት የተገኘባቸዉ ሰዎች ካሉ ለምስክርነት ከጠረጋዉ ተርፈዉ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሊደርሱ ይችላሉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በአሁን ሰዓት እንደሚታወቀዉ የኢትዮጵያ «ሰንደቅ ዓላማ» ተብሎ እየተዉለበለበ ያለዉ የኮኮብ ዓርማ ያለበትና እንዲሁም የተለያዩ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት «ሰንደቅ ዓላማ » ተብሎ ነዉ:: ቀደም ሲል የሚታወቀዉ ሰነደቅ ዓለም አረንጓዴ ቢጫ ቀይና ዓርማዉ ደግሞ የመጾር መስቀል የያዘ አንበሳ ነበር:: ለምን የቀደመዉ ሰንደቅ ዓላማችን ሊለወጥና ዓርማችን ሊቀር ቻለ?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በተለያየ ቦታ ላይ እንደተገለጸዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ወደ ወንበር የመጡት የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ሆነዉ ነዉ እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም አይደለም:: ለክፉ ትንቢት ፈጻሚነት የተመረጡትም በነጻ ሕሊናቸዉ ተመርተዉ ባሳዩት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የትዕቢት፣ የክፋት፣ የተንኮል የጥላቻና በቀል አስተሳሰባቸዉና ተግባራቸዉ እንጂ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዉ አይደለም:: ታዲያ እንኳን ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ይቅርና መልካም ትንቢት ፈጻሚዎች ጭምር ዘመናቸዉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀና የተገደበ ነዉ:: አሁን የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ዘመናቸዉ የተደመደመ ስለሆነ የጨለማ ስራቸዉ የሚጋለጥበትና የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚ መሆናቸዉ የሚመሰከርበት ዘመን ላይ ስለሆን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉን አሳዉቃችኋለሁ::

መደቡ አረንጋዴ ቢጫ ቀይ የሆነዉ ሰንደቅ ዓላማችን ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት አንዱ የሆነ በአባታችን ጻድቁ ኖኅ አማካይነት ከእግዚአብሔር ያገኘነዉ ነዉ:: በዚህ ቃል ኪዳን ላይ ዓመፃና

ክህደት መፈጸም ማለት በግልጽ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፃና ክህደት መፈጸም ማለት ነዉ። ዉጤቱ ደግሞ ዉድቀትና ጥፋት እንዲሁም መደምሰስ ነዉ። በሕወሓት መንግሥት ዉስጥ የተሰባሰቡት ዉስጣቸዉ ጥላቻና በቀል የሞላባቸዉና መሪያቸዉ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ወደ ወንበር ሲመጡ ተግባራቸዉ ሁሉ ቅዱሳት ኪዳናትን ማጥፋትና የዲያብሎስን ፈቃድ መፈጸምና ማስፈጸም ነበር።

በዚሁ መሰረት የመጀመሪያ ተግባር አድርገዉ የተነሱት የኢትዮጵያዊነትንና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅርና የተለየ ስሜት ማጥፋት ነበር። እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትና በክርስቲያኑ(በዐምሓራዉ) ላይ ጥላቻና በቀል ማስፈጸም ነበር። ለዚሁ ተግባራቸዉ ይረዳቸዉ ዘንድ የመጀመሪያ ተግባራቸዉ ያደረጉት አገሪቷን በቋንቋና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን እንዲሁም አማኙ ተጽህኖና በቀል ሊፈጸምበት በሚያስችል አከላለል መከፋፈል ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዳይፈጠርና እንዲዳከም ክልላዊና ጎጣዊ ስሜት እንዲነግሥ ብሎም በሂደት እንደ ባሕረ ነጋሽ(ኤርትራ) የመገንጠል ሐሳብ እንዲፈጠርና እንዲጠናከር የተለያዩ መንግሥታትን ፈጠሩ። ታዲያ በእያንዳንዱ በፈጠሩት መንግሥታት ከላይና ከታች ሆነዉ የጥላቻና የበቀል ተግባር ሲፈጽሙ ሲያስፈጽሙ የነበሩት በዋናነት ሻዕቢያና ሕወሓት(ወያኔ) በተባለዉ ቡድን ዉስጥ የነበሩና እነርሱ የፈጠሯቸዉና ድጋፍ ያደርጉላቸዉ የነበሩ የተለያዩ ቡድኖች ብአዴን፣ ኦህዴድ፣ ደኢሕድን፣ አጋር ድርጅት የተባሉ የጎሳ(የብሔር) ቡድኖች እንዲሁም ኦነግ፣ ኦብነግ፣... ወዘተ የመሳሰሉ ቡድኖች ናቸዉ። የሻዕቢያ፣ የሕወሓት፣ የብአዴን ፣ የኦሕዴድ፣ የደኢሕዴን፣ የአጋር ድርጅቶ የተባሉ ፍሬያቸዉ የታየ ሲሆን፤ የሚቀረዉ ደግሞ የኦነግ ፣ የኦብነግ የመሳሰሉት ፍሬ ነዉ። የእነርሱን ፍሬ እጅግ በቅርቡ እንደምንመለከተዉ ይገመታል። ምክንያቱም እያንዳንዱ የዘራዉንና ያፈራዉን በምድርም በሰማይም ማጨዱ አይቀርምና።

በመጀመሪያ ዓላማቸዉ መሰረት የተለያዩ መንግሥታትን ፈጠሩ፤ የመጀመሪያ መንግሥታቸዉ የትግራይ(የትግሬ መንግሥት)፣ ሁለተኛዉ መንግሥታቸዉ የአፋር መንግሥት፣ ሦስተኛዉ መንግሥታቸዉ የአማራ መንግሥት፣ አራተኛዉ መንገሥታቸዉ የኦሮሚያ(የኦሮሞ) መንግሥት፣ አምስተኛዉ መንግሥታቸዉ የሱማሌ መንግሥት፣ ስድስተኛዉ መንግሥታቸዉ የሐረሪ(አደሬ) መንግሥት፣ ሰባተኛ መንግሥታቸዉ የጋምቤላ መንግሥት፣ ስምንተኛ መንግሥታቸዉ የቤንሻንጉል ጉሙዝ መንግሥት፣ ዘጠነኛዉ መንግሥታቸዉ «ለጊዜዉ ለአስተዳደር ይቸግረናል» በሚል አስተሰሳብ ከ56 ጎሳዎች(ብሔሮች) ያለበትን በደፈናዉ የደቡብ መንግሥት በማለትና አዲስ አበባንና ድሬደዋን ምንም አማራጭ ስላጡና ለአንድ ጎሳ(ብሔር) ስያሜ መስጠት ስለተቸገሩ በልዩ ከተማ አስተዳደር እንዲካለሉ አደረጉ።

ከዚያ ቀጣዩ ተግባራቸዉ የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ማጥፋት ነበርና የትግራይ(የትግሬ) ሰንደቅ ዓላማ፣ የኦሮሚያ(የአሮሞ) ሰንደቅ ዓላማ፣ የአማራ ሰንደቅ ዓላማ፣ የአፋር ሰንደቅ ዓላማ፣ የሱማሌ ሰንደቅ ዓላማ፣ የሐረሪ(አደሬ) ሰንደቅ ዓላማ፣ የጋምቤላ ሰንደቅ ዓላማ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዥ ሰንደቅ ዓላማ፣ የደቡብ ሰንደቅ ዓላማ፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋን ስለተቸገሩ

ስያሜ ሳይሰጡት አልፈዋል:: በዚህ ዓመፃና ክህደት ተግባር ሳያበቁ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ላይ ጥላቻና በቀል ስለነበራቸዉ ልክ ያማረ ጋቢና ነጠላ ፈርስ ወይን ዐይነምድር ወይንም ፋንዲያ እመሃሉ ላይ ቢቀመጥና ቢገኝ ምንም እንኳን ጋቢነቱን ወይንም ነጠላነቱን ባያጠፋዉም ያ ቆሻሻ እስከሚታጠብ ድረስ አገልግሎቱንና ተወዳጅነቱ እንደሚያስቀር ሁሉ፤ እነሱም እንደተበላሸዉ ጋቢና ነጠላ ያደረጉት ሲሆን፤ በእግዚአብሔር እዉነታ ደግሞ የአሁን ዘመን የዲያብሎስ ዋና ዓርማ የሆነዉ 666(ኮኮቡን) ነዉ በሰንደቅ ዓላማችን ላያ አስደርገዉ ዲያብሎስን እያስመለኩና እያስገነኑ ያለዉ:: ታዲያ ይህ ዓመፃና ክህደታቸዉ ምን ዓይነት ጥፋትና መደምሰስ እንደሚያመጣባቸዉ በቅርቡ የምንመለከተዉ ይሆናል:: ምክንያቱም ዲያብሎስ በበላይ ሆኖ ዓመፃን፣ ክህደትን፣ ርኩሰት ያስፈጸማል እንጂ የእግዚአብሔርን ቁጣ መከላከል ሆነ ማስቆም ስለማይቻለዉ፤ ምንም እንኳን ቢያምልኩትም፣ ቢያስመልኩትም፣ ቢያገኑትም፣ ቢያስገንኑትም አንዳች አይታደጋቸዉም::

ወደ አንበሳዉ ዓርማ ስመለስ በዚህ ዓርማ ላይ ዓመፃና ክህደት በግልጽ የተፈጸመዉ ከደርግ ዘመን ጀምሮ ነዉ:: አሁንም ብዙዎች በተሳሳተ አስተሳሰብና እምነት ከነገሥታት ጋር የሚያገናኙትና የሚያያይዙት ሲሆን፤ እዉነታዉ ግን «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» (አሸናፊዉ አንበሳ የይሁዳ ነገድ) ለተባለዉ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ስምና መለኮታዊ ዓርማችን ነዉ:: በዚህ ዓርማ ላይ ዓመፃና ክህደት መፈጸም ማለት በእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ዓመፃና ክህደት መፈጸም ማለት ነዉ:: ታዲያ የዓመፃና የክደህት ዉጤቱ ምን እንደ ሆነ በዘመነ ደርግ በደንብ የተመለከትነዉ ሲሆን፤ አሁንም በሕወሓት እያየን ሲሆን ነዉ:: ወደፊትም፤ ስላቃለልነዉና ከዓርማነት አስወግደን የዲያብሎን ዓርማ ኮኮብ ስላደረግን ምን እንደሚመጣብን በቅርቡ የምንመለከተዉ ይሆናል:: ሌላዉ እግዚአብሔር እዉነታዎችን የሚገልጽበትና ወደ ምሉዕነት የሚያመጣን ጊዜና ዘመን ስላለ በዚሁ መሰረት ከመለኮታዉ አንበሳ ዓርማችን በተጨማሪ «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» (ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚብሔር ትዘረጋለች) የተባለችዉ ኢትዮጵያ ተብላ እኛን ኢትዮጵያዉያን ያሰኘችን ድንግል ማርያም እጆቿን ዘርግታ የሚያሳየን በተጨማሪ ከአንበሳዉ ዓርማችን ጋር እንዲታይ አድርጓል:: ምክንያቱም በብቃቷ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን ስለቻለች፤ ለአዳምና ሔዋን ዘሮች በሙሉ በአዳምና ሔዋን ምትክ የአደራ እናትነት ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰቷታልና:: በመሆኑም ከመለኮታዊ ዓርማችን ጋር እሷም እጇን ወደ ሰማይ የዘረጋችበት ዓርማ በተጨማሪ ተደርጎበታል

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በአሁን ሰዓት የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች፣ ደጋፊዎች፤ «መንግሥታችን ነጻነትና ዲሞክራሲ ስለሰጠ ይኸዉ ከ75 በላይ የፓለቲካ ድርጅቶች ተመስርተዉ እየተንቀሳቀሱ ነዉ፤ ሐሳባቸዉን በነጻት የመግለጽ፣ መርሐግብራቸዉን ማቅረብ ችለዋል፤ ከዚህ በላይ ነጻነትና ዲሞክራሲ ምን ያስፈልጋል... ወዘተ » እያሉ ሌት ተቀን ያወራሉ:: ለእዚህ ምን አስተያየት አሎት?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ነጻነትና ዲሞክራሲ ማለት አንዱን ከአንዱ ማለያየት፣ መከፋፈል፣ ማጣላት፣ ወደ አንድነትና ኅብረት እንዳይመጡ የሚያደርግ፣ በተለያየ መልኩ አደራጅቶና አቧድኖ እርስ በእርስ እያጣሉ የራስን ሥልጣን እድሜ ማረዘም ከሆነ፤ ይህ ስያሜና

እምነት ለጨለማዉ ገዥ አገልግሎት የሚያሰልፍና ፈቃዱንም ለመፈጸምና ለማስፈጸም እየተጠቀሙበት መሆኑን ነዉ የሚያሳየን:: 75 የተለያዩ ተቃዋሚ እርስ በእርስ አንድነትና ኅብረት የሌላቸዉ ድርጅቶች ወይንም ቡድኖች ማዘጋጀት ማለት፤ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት ምን ያህል ኢትዮጵያዉያንን ለመከፋፈልና ለማጠፋፋት እንዲሁም ለማጣላት መሰለፋቸዉን ነዉ የሚያሳየዉ እንጂ እንደ ታላቅ ተግባር የሚታይ አይደለም:: ከእግዚአብሔር ቢሆኑ ኖሮ እንኳን መከፋፈልና ማለያየት፣ ማጣላት አይደለም የተከፋፈሉና የተለያዩ አካላት ቢኖሩ እንኳ ወደ እግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ያመጡና አንድ ያደርጉ ነበር:: ነገር ግን በበላይ በዲያብሎስና በሠራዊቱ መንፈስ የሚመሩ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ተቃራኒ ተግባር ይፈጽማሉ ያስፈጽማሉ::

የሚያሳዝነዉና የሚገርመዉ ድግሞ እነዚህ ከ75 ባላይ የፓለቲካ ድርጅቶች መስርተዉ በተለያየና በተከፋፈለ እንዲሁም በጥላቻና በበቀል በተሞላ ሕሊና ዉስጥ ሆነዉ «ለሕዝብ ጥቅም የቆምን ነን፤ ነጻነትን፣ ዲሞክራሲን፣ እኩልነት ... ወዘተ ለማስፈን ነዉ የምንሰራዉ የምንቀሳቀሰዉ » ማለታቸዉ ናቸዉ:: በእዉኑ ለሕዝብ መቆም ማለት መከፋፈልና መጣላት እንዲሁም መጠላለፍ፣ እንዱን ለማጥፋት ጉድጓድ መቆፈር፣ ወጥመድ ማጥመድ ነዉን? ለመሆኑ በስሙ የሚነገድበት ሕዝብ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጅ አይደለምን? የሰዉ ዘሮች ሊመሩበት ፈቃደኛ ከሆኑ በአንዱ እግዚብሔር በመንፈስ ቅዱስ ብቻ መመራት አልነበረባቸዉምን? መንፈስ ቅዱስ የሚያድለዉ ጸጋዉ ቢለያይም ለአንድ ዓላማና ግብ አይደለም ወይ የሚያሰልፈዉ? እንዴት ከእግዚአብሔር የሆነ ከ75 በላይ ሊከፋፈል ይቅርና ሁሉት እንኳን ይሆናል? በእርግጥ በሕዝብ ስም በመነገድ ሥልጣን ይያዝበታል፣ ገንዘብ ይገኝበታል፣ ይከበርበታል፣ የራስ ስዉር ዓላማ ይፈጸምበታል፣ ዝና ይገኝበታል:: መንግሥታትም የጨለማ ስራቸዉ እንዳይጋለጥና በብርሃን እንዳይተካ እዉነትን በተለያየ መንገድ እያጠፏት መሆኑ ግልጽ ነዉ:: ለዚህም ነዉ አሁን ያለዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባሩ እንዳይታወቅ፤ በቋንቋ፣ በአመለካከት፣ በርእዮተ ዓለም፣ በዘር፣ በጎጥ፣በሃይማኖት... ወዘተ እየከፋፈለና እያባደነ፤ እርሱ ግን እዉነትን እንደ ምስጥ ዉስጥ ዉስጡን እየቦረቦረ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋትና የራሱን ስዉር ዓለማ ለማሳካት ተግቶ የሚሰራዉ::

በእግዚአብሔር እዉነት ስንመለከት የተለያዩ ሓሳቦችና አመለካከት ሊኖር ይችላል:: የአንዱ ሐሳብ ከአንዱ የተሻለና የበለጠ ሊሆን ይችላል:: አንዱ ቅንነት አንዱ በጠማማነት ሊመላለስ ይችላል፤ አንዱ ለአገርን ለሕዝብ በማሰብ ለአገርና ለሕዝብ የሚበጀዉን አቋም ሊይዝ ይችላል፤ ሌላዉ ደግሞ በተቃራኒ የራሱን ስዉር ዓለማ ለማሳካት በሕዝብ ስም ሊነግድ ይችላል:: ነገር ግን በቅን ልቦና የሚመላለስ ሰዉ ከእርሱ የተሻለና የሚበልጥ ሐሳብ ሲመጣ በቅንነት ይቀበለዋል፣ ለዚያ ለበለጠዉ ሐሳብ ተግባራዊነት ይሰለፋል እንጂ፤ «ከእኔ አስተሳሰብና አመለካከት ዉጭ የሆነ አልቀበልም» አይልም:: በዚህም ምክንያት በትክክል ለሕዝብና ለአገር የሚበጅ ሓሳብና አመለካከት ያላቸዉ ሰዎች በአንድነት እየተመካከሩና እየተደጋገፉ አብረዉ ይሰራሉ፣ ይሰለፋሉ እንጂ የግላቸዉን ሐሳብና ዓላማ ለማሳካት አይሄዱም:: በጊዜዉ ደግሞ የተሻለና የበለጠ ሐሳብና ተግባር ከተባለዉ ሌላ የበለጠ ሓሳብና ተግባር ሊመጣ ይችላል:: ያኔም በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ተመርምሮ በትክክል የበለጠና የተሻለ

ከሆነ ያንን ሐሳብና ተግባር መጠቀም ነዉ የሚያስፈልገዉ እንጂ እንደ ሶፍት ዌር «አንዴ በዚህ ነዉና የምጠቀመዉና ሕሊናዬ የተሞላዉ፤ እስከ መጨረሻዉ በዚህ ሐሳብና ተግባር ነዉ የምጸናዉ እንጂ የተሻለና የበለጠ ቢሆንም አልፈልገዉ፣ አልጠቀምም» ማለት የለብንም:: ምክንያቱም በየጊዜዉ እግዚአብሔር ለፍጥረተ ዓለሙ የተለያየ እዉቀትና ጥበብ እየገለጠ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች እንዲፈጠሩ ያደረገዉ፤ ሰዎች ከጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲለዩ ፈቅዶና ፈልጎ ነዉ:: በመሆኑም የሰዉ ልጆች ከችግርና ከጉስቁልና ሕይወት የሚለዩበትን መንገድ በየጊዜዉ እየተሻሻለና እየተሟላ መሄድ ነዉ ያለበት እንጂ፤ ሰዎች በችግራቸዉና በጉስቁልናቸዉ እንዲጸኑ ማድረግ አንድም ካለማወቅ፣ አንድም ከሕሊና ጥመት፣ አንድም የራስን ስዉር ዓላማ ከማሳካት፣ አንድም ለሰዎች ደንታቢስ ከመሆነ የተነሳ ሊሆን ይችላል::

በዓለም የሚታየዉም እዉነታ ሰዎች ለፓለቲካ ዓላማቸዉ ሲሉ ሕዝብና አገር የሚጎዳበትን ተግባር ሲፈጽሙና የክፋት፣ የተንኮል፣ የበቀል፣ የጥላቻ፣… ወዘተ ሐሳብ ሲያመነጩ ይታያል:: በእርግጠኝነት ለመናገር ሰዎች ለቅን ሐሳብ፣ ለመልካም ተግባር፣ ለእዉነተኛ ሕይወት ራሳቸዉን ቢያዘጋጁ በአንድ እዉነት ዉስጥ እንደ አንድ ልብ መካሪ አንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነዉ መኖር ይችላሉ:: ምክንያቱም መሪዉ አንድ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ለአንድ ዓላማና ግብ ነዉ የሚያሰልፋቸዉ እንጂ ለተለያየ ዓላማና ግብ አያሰልፋቸዉም:: በዓለም የሚታየዉ ግን በሥጋዊዉም በመንፈሳዊዉም ሕይወት መሪዎች ሆኑ ሕዝቡና አማኞች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ ስለሚመላለሱ፤ የሚቆሙት ለእግዚአብሔር እዉነት ሳይሆን ለራሳቸዉ የዉሸት እዉነትና ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ማርኪያ ነዉ :: በዚህም ምክንያት በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ጸንተዉ ይገኛሉ:: አሁን ግን የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ዘመን የተደመደመበት ስለሆነና የዲያብሎስ እንደራሴዎቹም በእግዚአብሔር ቁጣ እንደተመቱ ሁሉ፤ በስራቸዉ ሆነዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የነበሩትም «እረኛ ሲመታ በጎች እንደሚበተኑ» ሁሉ፤ እነዚያ የዲያብሎስ አገልጋይ የነበሩ አስመሳይ የሕዝብና የምእመናን እረኞች ስለተመቱ በስራቸዉ የነበሩና የእነርሱን የዓመፃ ተግባር ሲያስፈጽሙ የነበሩ ሁሉ ይበተናሉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ ለሕዝብና ለአገር የሚያስቡ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከልቦናቸዉ ተመንግሎ ያልወጣባቸዉ ሰዎች በአንድነት ተሰባስበዉ ለአንድ እግዚአብሔር እዉነት በመሰለፍ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም በአራቱም ማእዘን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይሰለፋሉ፤ ፈቃዱንም እየፈጸሙ ያስፈጽማሉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: የኢትዮጵያ ታሪክ ዘመን ሦስት ሺህ ነዉ ብለዉ የሚናገሩ አሉ:: እንዳንዶች ደግሞ «ነፍጠኞች ወይንም ዐማሮች ወይንም ክርስቲያኖች፣ የተለያዩ ክልሎችንና ብሔር ብሔረሰቦችን ወረዉ ነዉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የፈጠሩት እንጂ ኢትዮጵያ ታሪኳ ወደ አንድ መቶ ዓመት ገደማ ነዉ ይላሉ:: በዚህም ምክንያት ታላቁን መሪ ዳግማዊ አጼ ምኒልክን «ወራሪዉና ግፈኛዉ ምኒልክ የፈጠራትን ኢትዮጵያ እንደ ቀድሞ በክልላትና በብሔር ብሔረሰብ ተከፋፍላ መተዳዳደር አለባት፤ ብሔር ብሔረሰቦች ፍላጎቱ ካላቸዉ «ኢትዮጵያዊ ነን» ብለዉ በመዋሐድ መኖር ይችላሉ:: ካልፈለጉ ደግሞ ተገንጥለዉ እንደ ቀድሞ ነጻ መንግሥታቸዉ፣ እንደ ኤርትራ መስርተዉ መኖር ይችለሉ:: ለዚህም ዋስትና እንዲሆናቸዉ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል

የሚለዉን አዋጅ በሕገ መንግሥቱ ተረጋግጦላቸዋል... ወዘተ»የሚሉ አሉ:: አዲሱ ትዉልድ ደግሞ «የአዲስቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ገና የሃያ ዓመት ታሪክ ነዉ፣ ከዚያ በፊት ነጻነት የሌለበት፣ በዐምሓሮች(በክርስቲያኖች) ግፍንና በደል የተፈጸመበት፣ ብሔር ብሔረሰቦች እንደ ዜጋ የማይታዩበት፣ እኩልት ነጻነት ዲሞክራሲ ያልሰፈነበት ስለበረ እንደ ኢትዮጵያ አገር መቆጠር የለበትም፤ እኩልነት፣ ነጻነት ፣ ዲሞክራሲ ያሰፈነባት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የተፈጠረችሁ ከግንቦት፳፥፲፱፻፹፫ (20/9/1983) ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ፤ ታሪኳ ከኢሕአዴግ ዘመን መጀመር አለበት» የሚሉ ዘመናዊ ፓለቲከኞችና ካድሬዎች አሉ:: ለነዚህ ምን ምላሽና አስተያየት አሎት?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ከሁሉ ከሁሉ የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ከማንም በላይ ከምስራቅ ኢትዮጵያ፣ ከምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ ካሉ ኅብረተሰብ በላይ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ጥብቅና ሊቆሙና ታሪኳን፣ ቅርሷን፣ ማንነቷን ለቀጣይ ትዉልድ ማስተላለፍ የሚገባቸዉ ከሰሜን የወጡ «የእሳት ልጅ አመድ» እንደሚባለዉ የሆኑት ሕወሓት(ወያኔ) እና ሻዕቢያ የተባሉ የዓመፃ ቡድኖች ተነስተዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵዊነትን ለማጥፋት ቆርጠዉ መነሳታቸዉና የ7504 ዓመት ታሪኳን ደምስሳዉ 125 ዓመት ታሪክ ለመፍጠር መነሳታቸዉ ነዉ::

በዘመነ መሳፍንት በሥልጣን ጥማት የተከፋፈሉ የአካባቢ ነገሥታትን ድል አድርገዉ ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ ወደ አንድነት ለማምጣት የጀመሩትን የአጼ ቴዎድሮስን ተጋድሎ አጼ ዮሐንስ የቀጠሉትና ለእናት አገራቸዉና ለቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸዉ በወራሪዎች የተሰዉትን ፈለግ ተከትለዉ፤ በየጎጡ ራሳቸዉን ለማንገሥና የራሳቸዉን የግል ፍላጎት ብቻ ለማሟላት ይታገሉ የነበሩ የተለያዩ የአካባቢ ነገሥታትን ወደ አንድነት ያመጡትና አሁን ላለንበት የዉሕደት ሕይወትና ቤተሰባዉ አንድነት መሰረት የጣሉትን ታላቅ መሪን ዳግማዊ አጼ ምኒልክን «በወራሪነት፣ በግፈኝነት... ወዘተ» መፈረጃ ምን ያህል ዉስጣቸዉ ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መሆኑን ነዉ የሚያሳየን:: ለዚህም ነዉ በሃያ ዓመት ዉስጥ በክርስቲያኖች(በዐምሓራዎች) ላይ የፈጸሙትና ያስፈጸሙት የበቀልና ግፍ ተግባር አላረካ ብሏቸዉ፤ አሁን ድረስ «አከርካሪያቸዉ እንዳያንሰራራ መሰበር አለበት፣ ሊደመሰሱ ይገባል» እያሉ በትዕቢትና እብሪት የሚናገሩትና የሚደነፉት:: ሌላዉ የዉስጣቸዉ ጥላቻንና በቀልን የሚመሰክርባቸዉ፤ ለአዲስ አበባ መቆርቆር ምክንያት የሆኑት አጼ ምኒልክና እትጌ ጣይቱ በአዲስ አበባ በ125ኛዉ በዓል መታሰቢ ሊታሰቡ ሲገባ፤ ቀን ከሌሊት በተለያየ መገናኛ ብዙኃን ስሙ ሲጠራ የምንሰማዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳዉና በቅዱሱ ኪዳን ላይ ዋና መሪ ሆኖ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸመዉና ያስፈጸመዉ አቶ መለስ ዜናዊ ነዉ::

እግዚአብሔር፤ ሕወሓት ኢሕአዴግን ባለጊዜ ያደረጋቸዉ የሚፈጽሙት ተግባር ስለለ ነዉ እንጂ እንደነሱ የክፋትና የተንኮል እንዲሁም የጥፋትና በቀል ተግባር ቢሆን ኖሮ የአንድ ዓመት እድሜ አይሰጣዉም ነበር:: አሁን ግን የተፈቀደላቸዉ የሃያ ዓመት እድሜ ስለተጠናቀቀ፤ የሚቀራቸዉ የዘሩትን የዘረኝነት፣ የጎጠኝነት፣ የክፋት፣ የጥላቻ፣ የበቀል፣ የጥፋት ዘራቸዉን

ማጨድና ያፈሩት ፍሬ እጅግ መራራ ቢሆንም ቋቅ እያላቸዉ የሚጠጡት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገለጸዉ ከሥጋ ሞት በኋላ ብቻ ሳይሆን በዚህች የዐይን ቅጽበት ምድራዊ ዘመናችን ጭምር ነዉ፡፡ በክርስቲያኑ(በዐምሐራዉ) ላይ በደልና ግፍ ያስፈጸሙት የከፋ ተግባራቸዉ ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍላቸዉ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲነድባቸዉ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡ እኛ እንደወገንነታችን አሁንም የመጨረሻዉ ቁጣ መቶ ሳይጠርጋቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደዉ ስለ ሰሩትና ስላሰሩት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የግፍና የጭከና ተግባር በግልጽ ይቅርታን መጠየቅና ወንበሩን እግዚአብሔር ለመረጣቸዉ ቢለሚሎቹ ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር መልቀቅ ብቻ ነዉ፡፡ «አይሆንም የሚሉና ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነታችን ዉጭ አንወጣም፣ በዚህም የማያምኑትን እንደመስሳቸዋለን» የሚሉ ከሆነ ደግሞ ለአንዴን ለመጨረሻ ጊዜ ከወንበራቸዉ ተቆርጠዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ካነገሡባት ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠረጋሉ፡፡

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስገባ** የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረዉ ከሰዉ ፍጥረት ጀምሮ ነዉ፡፡ ይኸዉም አዳምና ሔዋና ከገነት እንደተባረሩ የተገለጡበት የመጀመሪያ ምድር የኢትዮጵያ ምድር ነዉ፡፡ «ዔድን ገነት» የተባለችዉ የግዮን(የዓባይ) ወንዝ የሚነሳባት፣ በተለያዩ ወንዞችና ፈሳሾች የተከበበች አገር ኢትዮጵያ ናት፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዉያን ታሪክ የሚጀምረዉ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ነዉ፡፡ በዓለም ዉስጥ ያሉት ሕዝቦች አላስተዋሉም እንጂ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ፡፡ ምክንያቱም የአዳምና ሔዋን ዘሮች የሆኑ የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገዶች እንዲሁም የሦስቱ ነገድ ዉሕድ ዘር የሆነዉ የኢትዮጲስ ልጆች የመልከ ጼዴቅ ልጆች ናቸዉ፡፡

ነገር ግን እንኳን ሌላዉ የዓለም ሕዝብ ይቅርና የቅርቦቹ ኢትዮጵያዉያን የነበሩት የባሕረ ነጋሽ(የኤርትራ) ተወላጆች «እኛ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ዜጎች አይለንም» በማለት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ በግልጽ ዓመፃ ፈጽመዋል፤ ሃይማኖት በሆነዉ ኢትዮጵያዊነት ላይም ክህደት ፈጽመዋል፡፡ ይህ ዓመፃና ክህደት ደግሞ ምን ዓይነት ዋጋ እንደሚያስከፈል እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡ እንደ ወገንነታችንና ቤተሰብነታችን የምንመክራቸዉ ዛሬ ነገ ሳይሉ፣ ቀኑ ሳይመሽባቸዉና ሳይጨልምባቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ ከእናት አገራቸዉ ከድንግል ማርያም ከኢትዮጵያ እቅፍ እንዲገቡ ነዉ፡፡

እነርሱ ብቻ አይደለም በቀኝ ገዥዎች ከፋፋይ ሴራ ኢትዮጵያዊነታቸዉን የካዱት በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ ወገኖቻችን ከእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያ ጋር ቢዋሓዱ ከጥፋትና ከመደምሰስ ይተርፋሉ፡፡ ሌላዉ ዓለምም ቢሆን ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነት ቢቀብልና እንደ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት ቢመላለስ ራሱን ከጥፋትና ከመደምሰስ ሊያድን እንደሚችል ወገናዊ ምክራችንንና ጥሪያችንን በዚሁ አጋጣሚ እናቀርባለን፡፡

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ ከ ፳፻፩(2001) ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ዉስጥ በመስከረም ወር የሰንደቅ ዓላማ ቀን እየተከበረ ይገኛል፡፡ ዘንድሮ ደግሞ የቀድም ጠቅላይ ሚኒስትርን በተለየ ሁኔታ ለማሰብና

«ታላቁ ፣ ጀግናዉ፣ አባታችን፣ መሪያችን፣ ሰንደቅ ዓላማን ከፍ ከፍ ያደረገዉን፣ የሕዳሴዉ ቀያሽና መሐንዲስ የሆነዉን፣ ሰማዕቱን፣ ታጋዩን፣ ባጠቃላይ ሁለመናችን የሆነዉን መለስ ዜናዊ የሚታሰብበትና የጀመረዉን ሕዳሴ ከግብ እንደምናደርስ ቃል የምንገባለት ነዉ» በማለት ነበር ሲያከበሩት የነበረዉ ። በእዉኑ አቶ መለስ ዜናዊ የሰንደቅ ዓላማና የአገር ፍቅር አላቸዉ ወይ? ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓለማ ጋር የተለያዩ የክልል መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማዎች እንዲሁ ከፍ ብለዉ አብረዉ ሲከበሩ ነበር። ከአንድ ሰንደቅ ዓላማ ዉጭ «የዐምሓራ ሰንደቅ ዓላማ፣ የትግሬ ሰንደቅ ዓለማ፣ የኦሮሞ ሰንደቅ ዓለማ፣ የአፋር ሰንደቅ ዓላማ፣ የሱማሌ ሰንደቅ ዓላማ፣ የሐረሪ(አደሬ) ሰንደቅ ዓላማ፣ የጋምቤላ ሰንደቅ ዓላማ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰንደቅ ዓላማ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓላማ፣ ለወደፊት ደግሞ የተለያዩ የክልል መንግሥታት ሲመሰረቱ የእገሌ ሰንደቅ ዓላማ» እየተባለ እስከ አሁን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ተደርጎም ተሰምቶም የማይታወቅ ተግባር በእዉኑ የሰንደቅ ዓላማን ፍቅር ያሳያል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በአራቱም በአገሪቱ ማእዘን አይደለም በሌላዉ ዓለም ጭምርና በግለሰብ ደረጃም ከፍ ተደርጎ እንዳይዉለበለብ በአዋጅ ተደንግጓል። በአቶ መለስ ዜናዊ ሐሳብ አፍላቂነትና አመንጪነት፣ በአእምሮ ቀላሎችና በአእምሮ ሕፃናት አጽዳቂነት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን የሚያዉለበልብ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ እንዲፈረድበት ተደርጓል። የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት እያዉለበለበ ያለዉ የአሁን ዘመን የዲያብሎስ ዓርማ የሆነዉን 666 ወይም ኮኮቡን ነዉ። ሌሎች «ሰንደቅ ዓላማ» ተብለዉ ለተለያዩ ጎሳዎች(ብሔሮች) የተፈጠረዉ በጨለማዉ ገዥ በዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች መሪዎችና ባልሥልጣናት ነዉ። ያዉ እንደ ዲያብሎስ ዓርማ 666(ኮኮብ) የሚቆጠሩ ናቸዉ። ይህ የሚያሳየን ደግሞ አቶ መለስ ሆኑ በእርሷቸዉ ስር ሆነዉ አረንጓዴ ብጫን ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን ከምድሪቱ በአዋጅ ማስወገዳቸዉ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ሰንደቅ ዓላማ አቋም እንዳለቸዉ የሚመሰክርባቸዉ ነዉ እንጂ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እንዳላቸዉ የሚገልጽ አይደለም። እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ «ጨርቅ ነዉ» እያሉ ሲያጣጣሉና ሲያጥላሉት አልነበረም ወይ? አሁንም አምነዉበት ሳይሆን እያከበሩት ያለዉ ያዉ ለፖለቲካ ጥቅም ብቻ ነዉ። ምክንያቱም ትዉልዱ አገራዊና የሰንደቅ ዓለማ ፍቅር እንዳይኖረዉ ስላደረጉት፤ ለራሳቸዉ ህልዉና አስጊ ሆኖ ስለታያቸዉና አንዳንድ የአገርና የሰነደቅ ዓላማ ፍቅር ያላቸዉን በስራቸዉ አስገብተዉ ለመጠቀም ስለፈለጉ ነዉ እንጂ፤ ሰንደቅ ዓላማ ሙሉ በሙሉ በመወገዱ የተለየ ጥቅም የሚያገኙበት ከሆነ እንደ ኤርትራ ከማስወገድ ወደ ኋላ አይሉም። ይኸዉ የክልል ሰንደቅ ዓላማ ብለዉ የፈጠሩት እኮ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማን ለማስወገድ ነዉ። እርሱም ተሳክቶላቸዉ አስወግደዉታል።

የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ እንዲሁም ምን ያህል መሰሪ መሆናቸዉን የሚያሳየዉ ተግባራቸዉ አንዱ፤ የዲያብሎስ ዓርማ የሆነዉ ኮኮብ ተቀባይነት እንዲያገኝና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለማሶወገድ የተጠቀሙት፣ ልክ የይሁዳ መሰሪነት በዮሐንስ ወንጌል በምእራፍ 12 ከቁጥር 3እስከ6 ላይ እንደተገለጸዉ፤ ይኸዉም ለደሀ ተቆርቋሪና ሓሳቢ በመምሰል የፈጠረዉ ወርቃማ አባባልና አስተሳሰብ ነዉ። «ማርያምም ዋጋዉ እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶዶ ሽቱ ንጥር ወስዳ

የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ:: ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠዉ ያለዉ የስምዖን ልጅ የአስቆርቱ ይሁዳ:- ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነዉ?አለ:: ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነዉ እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸዉ አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በዉስጡ ከሚገባዉ ይወስድ ስለ ነበረ ነዉ::» ይላል

አሁንም የዘመኑ ይሁዳዎች በወርቃማ ቃላት ታጅበዉ ነዉ «ኮከቡ የብሔር ብሔረስብ እኩልነት የሚግልጽ ነዉ» በማለት የዲያብሎስ ዓርማ ከፍ ከፍ እንዲልና እንዲዉለበለብ እንዲሁም በኅትመት ዉጤቶች ላይ ሁሉ በግልጽ እንዲገን ያስደረጉት:: የመጨረሻ መሰሪ አስተሳሰባቸዉ ደግሞ «ለምን ይህን የዲያብሎስ ዓርማ ይደረጋል?» ብሎ የሚጠይቅና እንዲሁም «የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነዉን ብቻ ነዉ የማዉለበልብ» ብሎ ቢነሳ፤ «ይህ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት የማያምን ነዉ፣ ነፍጠኛ ነዉ፣ ትምክተኛ ነዉ፣ ዐምሓራ(ክርስቲያን) ነዉ ... ወዘተ» እያሉ ከፈለጉ በመሱና፣ ከፈለጉ በሁከት ፈጣሪነት ፣ ከፈለጉ በሽብርተኛነት ፈርጀዉ ከፈለጉ ማስገደል፣ ከፈለጉ እንድሜ ልክ እስራት ማስፈረድ፣ ከፈለጉ የፈለጉትን ዓመት እንዲታሰር ያስደርጓሉ:: አሁን ያለዉ ትዉልድ ግን እያከበሩት ያለዉ የዲይብሎስን ዓርማ የዘመኑ 666 መሆኑን ሊያዉቅ ይገባል:: በዓለም ፍጻሜም ዲይብሎስ እንደአሁኖቹ ዓይነት አገልጋዮች መልምሎ ነዉ በወርቃማ አባባል ወይንም ተጽህኖ ሊፈጥር በሚችል አባባል ታጅቦ የመጨረሻዉን ዓርማ 666ትን በዓለም ላይ የሚያገነዉና ራሱን የሚያስመልከዉ:: አሁን ግን የቅዱሱ ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ የሆነዉን እንዳይዉለበለብ ተደርጓል:: የተለያዩ የክልል መንግሥታትን ፈጥረዉ የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎችን የፈጠሩትም የአንዲት ሰንደቅ ዓላማና የአንዲት አገር የኢትዮጵያን ፍቅር ለማጥፋት ነዉ:: ነገር ግን «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በገጽ 56 ላይ ማንታቸዉና ምን እንደሚጠብቃቸዉ እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገረዉ ተጽፏል:: ይኸዉም:

«ለመሆኑ ምን የሀገር ፍቅር አላችሁና ነዉ ስለ ሰንደቅ አላማ የምታወሩት? ሰንደቅ አላማ «ጨርቅ ነዉ » ብላችሁ እንዳላጥላላችሁ፣ የእዉነተኛዋን የኢትዮጵያ መለያ ሰንደቅ አላማ ፍቅር ለመቀነስ ይህችን ሀገር በቋንቋ:በጎሳ ከፋፍላችሁ «የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ሰንደቅ አላማ ፣የዚህ ጎሳ ክልል ሰንደቅ አላማ » በማለት ማንም ኢትዮጵያዊ ያላደረገዉን የተንኮልና የክፋት ተግባር ፈጽማችኋል::ከዚህ አልፎ ደግሞ እዉነተኛዉን ሰንደቅ አላማ ከፍ ከፍ ያደረገ በወንጀል እንዲቀጣ፣ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ ከሆነና ሕሊናቸዉን ከሸጡ ከአእምሮ ህጻናትና ከአእምሮ ቀላሎች ከግብረ አበሮቻችሁ ጋር በመሆን አጽድቃችኋል::ዲያብሎስ ያዘጋጀላችሁን የኮኮብ አርማ በእዉነተኛዉ ሰንደቅ አላማ ላይ በማድረግ የአንዲት ሰንደቅ አላማና የአንዲት ሀገር ፍቅር ለመቀነስ፤ ኢትዮጵያዊ ወኔን ለመስለብ፤ ከንቱ የሆነ መጠበብ ተጠባችኋል::ነገር ግን ክፉ ተግባራችሁና ሐሳባችሁ ከንቱ ሆኖ ይቀራል:: እዉነተኛዋና ብቸኛዋ ሰንደቅ አላማ ከፍ ከፍ ይላል::» ይላል::

በመሆኑም እነርሱ ያዘጋጁት የተለያዩ የጎሳ(የብሔር) ሰንደቅ ዓላማቸዉ የሬሳቸዉ መጠቅለያ የሚሆን ሲሆን፤ እዉነተኛዋና ብቸኛዋ ሰንደቅ ዓላማ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በዓለም ላይ ከፍ ብላ ትዉለበለባለች።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በአሁን ሰዓት ማንኛዉም ዝቅጅት ይዘጋጅ፣ ማንኛዉም መርሐግብር ይቅረብ ሁሉን «ከባለ ራእዩ መሪያችን መለስ ዜናዊ… ወዘተ»እየተባለ ነዉ የሚከናወነዉ። ነገ ጠባ «ታጋይ መለስ፣ ሰማዕት መለስ፣ ጀግና መለስ፣ ባለራእዩ መለስ፣ ለሰዉ ተፈጥሮ ለሰዉ ኖሮ የሞተ መለስ፣ ዘላለማዊዉ መለስ፣ የሕዳሴ መሐንዲስና ቀያሽ መለስ፣ ድህነት ያጠፉ መለስ፣ ባለ ልማቱ መለስ… ወዘተ» እየተባለ በብዙኃን መገናኛ ሲቀርብ ይታያል፤ ይደመጣል። ይህ መቼ የሚቆም ይመስሎታል? ይህ ድርጊትስ ምን ያሳየናል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: አሁን ያለዉ ሥርዓት እስካለ ድረስ ይህ አምልኮና ምስጋና እንዲሁም መለማመንና ማግነን መቼም አይቆምም። ምክንያቱም አሁን ያሉትን ባለሥልጣናትና ካድሬዎች እንዲሁም የሥርዓቱን ደጋፊና አገልጋይ የፈጠረዉ አቶ መለስ ነዉ። ስለዚህ አቶ መለስ ማለት ለእነሱ አምላክ ስለሆነ ነጋ ጠባ ቢያነሱት፣ ቢያመሰግኑት፣ ቢያገኑት፣ ቢዘክሩት፣ ቢለማመኑት፣ ባጠቃላይ ቢያመልኩት ብዙ አያስገርምም። ሕሊናቸዉ እንደ ሶፍር ዌር ተደርጎ ስለተቀረጸ ከአቶ መለስ ዉጭ ሊያስቡና ሊሰሩ አይችሉም። እርሱ በሥጋ እያለ የፈጠራቸዉ አንድም እንደ ድምፅ ማጉያ የእርሱን ሁሉ እንዲያስተጋቡ፣ አንድም እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ እንዲሄዱ፣ አንድም እንደ ጠፍ ከብት ዝም ብለዉ እንዲነዱ አደርጎ ስለፈጠራቸው፤ ራሳቸዉ የሚፈጥሩት፣ የሚያስቡት፣ የሚናገሩት የለም። አቶ መለስ የፈጠረዉን፣ ያሰበዉን፣ የተናገረዉን ነዉ የሚያስቡት፣ የሚሰሩት፣ የሚናገሩት። ለዚህም ነዉ ነጋ ጠባ «መለስ መለስ» የሚሉት። አሁን ግን ባለጊዜነታቸዉ ወደ መጨረሻዉ መሻሪያ ወራት ላይ ስለደረሰ፤ ከእንግዲህ የአንድ ግለሰብ ዓለማ ሳይሆን የሚፈጸመዉ የአንዱ የእግዚአብሔር ዓላማ ብቻ ነዉ በአራቱም ማእዘን የሚፈጸመዉ። ግለሰብ ወይንም ቡድን የሚመለክበትና የሚገነበት እንዲሁም የሚመሰገንበት የዓመፃ ዘመን ያበቃለት ስለሆነ፤ እስከዛዉ ድረስ በዚህ አምልኮ ምንዝርናና ዓመፃ ዉስጥ ከመሳተፍና ተባባሪ ከመሆን ራስን ለይቶ በእዉነትኛ ሕሊና መኖር ነዉ ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቁጣ ቀን ከጥፋትና ከመደምሰስ፤ መለስ ሆነ ሌላ ኃይል አይታደጋቸዉምና። እዚህ ላይ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አራት በምዕራፍ ሦስት ከገጽ 386-395 ድረስ የተገለጸዉን አቀርባለሁ፡

«ለእንደራሴዎቼ አንድ እዉነት ሳልነግራቸዉ ብቀር ለወደፊት ይጸጽተኛልና - እናንተ እንደራሴዎቼ! እስከዛሬ ድረስ በታማኝነት ስላገለገላችሁኝ በታላቁ ስሜ ሉሲፈር ወይንም የጨለማዉ ባለስልጣን ወይንም ዓለም በሚያዉቀኝ ዲያቢሎስ ስሜ በቅድሚያ አመሰግናችኋለሁ። በመቀጠል ደግሞ <u>የሥልጣን እድሜያችሁን በብልጣብልጥነትና በሥጋዊ ጥበብ የምታስረዝሙ መስሏችሁ ሌት ተቀን መትጋታችሁ የሚደነቅ ቢሆንም ከተቆረጠላችሁ ቀን አንዲት ቀን ማስረዘም የማትችሉ</u>

መሆኑን ሳዉቅ ስለ አቅመቢስነቴ እጅግ ባዝንም ባለተረኛ ስለሚተካ በዚያ እጽናናለሁ:: እናንት ለሃያ ዓመታት እኔን የጨለማዉ ገዥን በቅንነትና በታማኝነት፣ ትጋት በተሞላ አገልገሎታችሁ አስደስታችሁኝ የአንድ ቀን ዋስትና መስጠት አለመቻሌና እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ ማከናወን መቻሉና እርሱ ሳይፈቅድ ደግሞ ምርጥ ባለሟሎቹ ላይ አንዳች ሊደረግባቸዉ አለመቻሉ እጅጉን ያስቆጨኛል፤ ያንገበግበኛል::

እንደኔ ቢሆን ምንም እንኳን የአንደኝነት ማእረግ ባልሰጣችሁም ከኢራቁና ከሊቢያዉ መሪ ልዩ ባለሟሎቼ ከነበሩት በማስከተል እናንተ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የክልልሎች መሪዎች ከዋናዉ ከርዕሰ ክልላት መሪያችሁ ጭምር የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ዋስትና እሰጣችሁ ነበር:: ምን ያደርጋል ታዲያ! እንኳን ለእናንተ ዋስትና ልሰጥ ቀርቶ ለራሴ አንዳች ዋስትና የሌለኝ ተራ ደካማ ፍጡር በመሆኑ ኀዘኔ እጅግ የከፋ ነዉ:: ስምህ ያጽናናህ እንድትሉኝ እፈልጋለሁ:: እናንተንም ርኩስ የሆነዉ ስሜ ያጽናናችሁ::

ታዲያ ይህን አባባሌን እንዳታጣጥሉት:: እግዚአብሔር እንኳን እናንተን ቀርቶ ማንም አይነካቸዉም አይነቀንቃቸዉም የተባሉትን ነገሥታት፣ ፕሬዘዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ባለስልጣናት፣ ባጠቃላይ ኃያላን የተበሉትን እንኳ እንዳልነበሩ አድርጓቸዉ መታሰቢያቸዉን ሳይቀር ከምድር ደምስሷል:: እናንተ ዋና ዐመጸኞችንና ከሃዲዎችን እንዴት አብልጦ አይደመስሳችሁ! እጅግ ይደመስሳችኋል::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ ስለዓመጻና ክህደት ተግባረችሁ እንድትጸጸቱ፣ ንስሐ እንድትገቡ ልመክራችሁ ፈልጌ አለመሆኑን በክፋትና በተንኮል፣ በበቀለኝነት የተሞላዉ ልቦናችሁ እንደሚነግራችሁ ምንም አልጠራጠርም:: ስለዚህ የዘራችሁትን የዓመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያችሁን ማጨዳችሁ ስለማይቀር፤ ልክ እንደ አጥፍቶ ጠፊዎቼ የመጨረሻዉን ኒሻን ተሸላሚ እንድትሆኑ፤ እናንተም መጥፋታችሁ ስለማይቀር ኢትዮጵያ የተባለች አገርና ሕዝቧን እንድታጠፉልኝ የመጨረሻ ታላቁን ምክሬን እለግሳችኋለሁ::

ጊዜ ያለ መስሏችሁ «ቀስ በቀስ ኀሊናን እያደነዘዝንና እየመረዝን በወርቃማ ቃላቶች እየታጀብን በሕገ መንግስትህ ተመርተን የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል በሚለዉ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ መሰረት ተግባራዊ እናደርጋለን፤ እጅግ ጠግበን እስከምናስታዉክ ድረስ ትንሽ ታገሰን » እንዳትሉኝ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ:: እኔ ተረብሻለዉ፤ ኃይለኛ ጭንቀት ላይ ነኝ ያለሁት:: በአራቱም ማእዘን ያሉ የዓለም መንግስታት፣ የተለያዩ ቡድኖችና ግለሰቦች የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋቸዉን

እየተጎነጩ በማለፍና ፍዳቸዉን በመቀበል ላይ ናቸዉ:: <u>በተለይ አንተ አእምሮህ አንዳንዴ ከኔ ላቅ እያለ የምታስቀናኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ላንተ ምክር ባያስፈልግም የልቤን ታዉቃለህና የምታደርገዉን በፍጥነት አድርግ</u>::

ስለ እንደራሴዎቹ ተግባርና ማንነት ኃያላኑን መንግስታቴን ትቼ፤ ሌት ተቀን ለኔ ታማኝነታቸዉን በማረጋገጥ የኃያልነት ማዕረግ እንድሰጣቸዉ በልዩ አምልኮ ደጅ ስለሚጠኑኝ የዚህችዉ የአዲሲቷ የኢትዮጵያ እንደራሴዎቼን ምሳሌ በማቅረብ ታላቅነቴን ለማሳወቅ እፈልጋለሁ:: እነዚህ የቀድሞ የጫካና የዋሻ ምልምሎቼ ለማርክዚስት ሌኒዚስት ፍልስፍናና የሶሻሊስት ስርዐቴን በሚገባ ካስጠናዋቸዉና ዉሳጣቸዉ ያለዉን የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት፣ የጥላቻና የበቀል ስሜታቸዉን በደንብ ካጠናከርኩ በኋላ፤ የመጀመሪያ የእጩ መኮንንነት ማዕረግ በመስጠት እንደመመሪያ በያዝኩት «በፊት ለፊት ወርቃማ ቃላቶችንና አባባሎችን ማስቀደም» በሚለዉ መርህ እነዚሁ እጩ መኮንኖቼ የዐመጻዉና የክህደቱ ጽዋ የሞላባቸዉ የቀድሞዉ መኮንኖቼ ከወንበራቸዉ ሲሰናበቱ አዲሶቹ እጮዎቼ በወርቃማ አባባሎቼ በሆኑት ነጻነት ፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ በኔዉ ስያሜ ዴሞክራሲ ታጅበዉ በግንቦት ፲፱፻ወ፫(1983) ዓ.ም.ወደ ተከበረዉ ወንበሬ መጡ::

በበላይ መሪያቸዉ እኔ አታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ ነበርኩና የዉስጣቸዉን ጥላቻና በቀል በደንብ አዉቅ ነበርና ይህች እንድትጠፋ እፈልግ የነበረችዉን «ሀገረ እግዚአብሔር» የምትባለዉን ኢትዮጵያን፤ «ብሔር ብሔረሰቦች» በሚለዉ ተወዳዳሪና ተቀራራቢ በሌለዉ ወርቃማ ቃሌ በመጠቀም አገራዊና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እንዲቀንስ በማድረግ የተለያዩ መንግስታት እንዲመሰረቱ አስደረኩ:: እዚህ ላይ አስደረኩ ስል አስገድጄ ሳይሆን ያቀረብኩላቸዉን አሳብ ቀደም ሲል በጫካዉ ዉይይታችን ተግባራዊ ለማድረግ በደስታ የተቀበሉት ስለነበረ፤ በወንበር ሲቀመጡ ወዲያዉ ተግባራዊ ለማድረግ አልተቸገሩም::

እዚህ ላይ የመንግስታቱን ስያሜ በተመለከተ «በሂደት ሳናስፎግር እንዳንተ እቅድ መሰረት ስያሜዎቹን መሉ በመሉ ተግባራዊ እንዳርጋለን፤ ለጊዜዉ ኢትዮጵያ የሚለዉን ስያሜ ሊቀናቀንና ሊተካ የሚችለዉን «ኦሮሚያ» በማለት እንሰይማለን ፤ ሌሎቹንም በሂደት ትግሪያ፣ አማሪያ፣ ሱማሊያ፣ አፋሪያ፣ ሐረሪያ፣ ጋምቤሊያ፣ ቤንሻንጉሊያ፣ ሃዲይያ፣ ወላይትዪያ፣ ጉራጊያ፣ ስልጢይያ፣ ሲዳማዪያ.. ወዘተ በማለት እናስተካክላለን፤ ለጊዜዉ ግን በምትፈልገዉ በብሔር ብሔረሰቦች ስም

የተለያዩ መንግስታትን እናቋቁማለን፤ ለዚህም እኛ የጫካ ታማኝ እጭዎችህ በርኩስ ስምህ እንምልልሃለን።» በማለት ምህላ ስለፈጸሙልኝ መንግስታቸዉን ሙሉ እዉቅና ሰጥቻለሁ።

<u>እንደእቅዴና ምኞቴ ኢትዮጵያ የሚለዉ ስያሜና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ቶሎ ባይጠፉም፤ በልዩ የጥላቻና የበቀል ስብከቴ አገልግሎት ላይ በተሰማሩት እጨዎቼና ካድሬዎቻቸዉ አማካይነት ልቤን ሙሉ በሙሉ ባያረካም የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዉልኛል፤ ክርስቲያኖችም ተጨፍጭፋዋል፤ የቀሩትም ከትዉልድ ቄያቸዉ ተፈናቅለዋል፤ መከራና ችግር ደርሶባቸዋል፤ ሌሎቹም ተሳቀዉ በጭንቀትና በስጋት እንዲኖሩ ተደርገዋል። ለወደፊት ደግሞ እንደራሴዎቼ ከዚህ በላይ ፍሬ ያፈሩልኛል ብዬ ተስፋ በማድረግ ይኸዉ ለሃያ አመት የማማከር አግልግሎት በመስጠት ላይ እገኛለሁ</u>።

በዚሁ አጋጣሚ በጥላቻና በበቀል ቅስቀሳ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋችሁ የምትፈልጉትን የስልጣን እርከንና ብልጽግና ሳይሳካላችሁ ቀርቶ የተወሰናችሁ ታስራችሁ ሌሎቻችሁ ልታጠፏት ከነበረችሁ ቅድስት ምድራችሁ ኢትዮጵያ ተሰዳችሁ በጨለማዉ ግዛቴ በስደት ዓለም ያላችሁና በአገር ዉስጥ ምኞታችሁ ተፈጽሞላችሁ በድሆች አናት ላይ ያላችሁ ዉድ ባለሚሎቼ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። እስከ ሕይወታችሁ ፍጻሜ ድረስ ለኔ ያላችሁን ታማኝነት እንድትገልጹልኝ እያሳሰብኳችሁ፤ በዋናዉ እንደራሴና በአጫፋሪዎቹ ቅሬታ ያላችሁ ግን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ቅሬታችሁን ለኔና ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እግልጻለሁ። በቅሬታችሁ ግምገማ ዉጤት እንደራሴዎቼ የእናንተን ያህል ዓላማዬን ለማሳካት ሳይጥሩ ቀርተዉ ከሆነ በአንድ ዓመት ዉስጥ ወደ ወንበሬ አመጣችኋለሁ። አይዟችሁ እኔ እስካለዉ ድረስ የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት፣ የግፍ፣ የበቀልና የጥላቻ ዉለታችሁን አልረሳም። ለዚህም በታላቁ ስሜ ዲያብሎስ እምልላችኋለሁ።

እናንተ ኢትዮጵያዉያን! ዉድ እንደራሴዎቼ ያመጡትን የዘረኝነትና የኀጠኝነት ስርዐት «አሜን» ብላችሁ በመቀበላችሁና የአዳም ዘር መሆናችሁን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉህድ የሆነዉ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሕዝብ መሆናችሁን፣ አባታችሁ አንዱ እግዚአብሔር መሆኑን ክዳችሁ ይህች ምድር መኖሪያችሁ ሳትሆን በአዳምና ሔዋን ዐመጻ ምክንያት በሥጋ ተገልጻችሁ እየተቀጣችሁ፣ እየጠራችሁ መሆኑን በመዘንጋትና ሰማያዊ ተስፋችሁን በማጨለም እዉነተኛ ገንዘባችሁ የሆነች ነፍሳችሁን በዓመጻ ተግባር ላይ በማሰለፋችሁ፣ እንዲሁም በእንደራሴዎቼ አማካይነት ተግባራዊ ያደረኩትን የብሔር ብሔረሰቦች የኀጠኝነት ክፍልፋይ አገዛዜን መቀበል ብቻ

አይደለም «እኔ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ነኝና ይህ ክልሌ ነዉ፤ ያንተ ክልል አይደለም፤» በማለት የከፋ የከረፋዉን ስብከቴን ተግባራዊ በማድረጋችሁና ባጠቃላይ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተባባሪ ለመሆን ሙሉ ፈቃደኞች በመሆናችሁ ከፍ ያለዉን ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: መቼም እንደምታጨበጭቡልኝና እንደራሴዎቼና አጫፋሪዎቻቸዉ ደግሞ የብሔር ብሔረሰብ ዘፈንና ጭፈራ እንደምታቀርቡልኝ ሙሉ በሙል እተማመናለሁ::

በተለይ «የሃይማኖት አባት ነን፣ ባለመስቀል ነን» ብላችሁ በዚሁ በከፋና በከረፋዉ ስርዐቴ ተሳታፊና አስፈጻሚ የሆናችሁ የተለየ ምስጋና ሊቸራችሁ ይገባል:: ምክንያቱም ሌላዉን እንኳ እንደ ኳስ ብጠልዘዉ፣ ባንከባለዉ፣ ብወረዉረዉ፣ ብረግጠዉ፣ ባጠቃላይ እንደልቤ ባደርገዉ ብዙም አይደንቀኝም:: ምክንያቱም ሆዱ አምላኩ የሆነዉን በሆዱ እገባበታለሁ፤ ስልጣኑን፣ ክብሩን የሚያመልከዉን በስልጣንና በክብሩ እገባበታለሁ፤ ገላዉን የሚያመልከዉን ገላዉን አስመልክለታለሁ፤ ምስጋናን የሚፈልግ ከንቱ ዉዳሴ አስቀርብለታለሁ፤ ብልጽግናን የሚፈልገዉን በገንዘብ እጥለዋለዉና ነዉ:: እናንተ ግን በአፋችሁ ሁል ጊዜ « እነዚህን ናቁ፣ ተስፋችሁን ገነት መንግስተ ሰማያት አድርጉ ስለምትሉና እናንተ በተግባር የምትፈጽሙ እየመሰለኝ በቁጥጥሬ ስር ማዋል ያዳግተኛል እያልኩ እጨነቅ ነበርና ነዉ:: አንዳንዶቻችሁማ ከሥጋዉያኑ ብሳችሁ ሳገኛችሁ፤ - እነዚህ ለካስ የሥጋዉ መንገድ ጠፍቶባቸዉ ነዉ ለዘመናት በስቃይ ሕይወት ዉስጥ ሲዳክሩ የነበሩት እላለሁ::

አንዳንዶቻችሁ ግን እኔን በማስቀናት ላይ በመሆናችሁ እርማት ማድረግ ይጠበቅባችኋል:: ይኸዉም እናንተ በቁማችሁ ሐዉልት እያስቆማችሁ መከበርና መግነን ፣ መመለክ ከፈለጋችሁ እኔ በጣዖታት ላይ አድሬ የምመለከዉን ማን ያስታዉሰኛል በሚል ስጋት ሲሆን፤ በየቤተክርስቲያኑ ተሰቅሎ ምእመናን ስለሚለማመኑበት ሥዕል (ባነር) ግን እግዚአብሔርና ቅዱሳን አስተያየታቸዉን ቢሰጡ የተሻለ ነዉ እያልኩ አንድ ምስክርነት ለመስጠጥ ግን እፈልጋለሁ:: ይህም እኔ የማዉቀዉ ስዕላት ሰዎች በምድራዊ ቆይታቸዉ የቅድስናና የጽድቅ ስራ ሰርተዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ ሲሄዱና ቅድስናቸዉ በእግዚአብሔር ሲረጋገጥ ነበር ለጻድቃኑ ሥዕላቸዉ ተዘጋጅቶ በአብያተ ክርስቲያን ዉስጥ ይሰቀል የነበረዉ::

ይሁንና ጽድቁና ቅድስናዉ ያልተረጋገጠለት ሰዉ በሕይወት እያለ «ቅዱስ፣ ብጹዕ ነኝ» ስለሚል፤ እንኳን ስዕል ቀርቶ ታቦት ቢቀረጽላቸዉ እግዚአብሔር ስለሚቆጣና እዉነተኛ ቅዱሳኑም ስለሚያዝኑ እኔ ደስ ይለኛል:: ሌላዉ ደግሞ አድኋዊ አሰራራችሁን ትታችሁ በአዲስ አበባ የተጀመረዉ የጣዖት ማቆምና ሥዕላትን መስቀል በየክልላቶቼ መንግስታት ዉስጥ በሚገኙ አብያተ

ክርስቲያናት ጭምር እንድታቀሙ አሳስባለሁ:: እናንተ በሐዉልት ማቆምና ስዕላትን በመስቀል ዋና አስተባባሪዎችና ጣዖት አስመራቂዎቼ፤ «አይሮፕላን ይገዛል» የምትሉትን የማስመሰል አሳባችሁን ትታችሁ ለኔ በሚጠቅመዉ በቀድሞ ተግባራችሁ እንድትቀጥሉ እናንተንም በጥብቅ አሳስባለሁ:: እምቢ ካላችሁ ደግሞ ከመሪያችሁ ጋር ያስተሳሰራችሁትን ህትብት እቆርጥባችኋለሁ::

ዱሮ ዱሮ እነዚህ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት እንደራሴዎቼና ባለሟሎቼ አንዳንዴ በንግግራቸዉ የሚያሰሙት ወርቃማ ንግግሮች ተግባራዊ ያደርጉት ይሆን እያልኩ እሰጋ ነበር:: አሁን ግን ብዙ ጊዜ ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ አለመገናኘቱንና ዉጫቸዉና ዉስጣቸዉ አንድ አለመሆኑን ስረዳ፤ ሺህ ወርቃማ ንግግሮች እንኳን ኢትዮጵያዉያን ቀርቶ ዓለም የሚቀበለዉን ወሬ ቢያወሩ ከቁም ነገር የማልቆጥረዉና አንዳችም ስጋት የማይታይብኝ ሆኗል:: ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ተገዢዎቼ ሆነዋልና ይልቁኑ ተደማጭነትና ተቀባይነት እንዲኖራቸዉ ከልባቸዉ ያልሆነዉን መልካም ንግግሮችን አሳስባቸዋለሁ:: ወደ ተግባር ሲመጣ ደግሞ ተቃራኒዉን አስፈጽማቸዋለሁ:: እነሱን ብቻ ሳይሆን በእነሱ መንፈስ የሚመሩትን እስከ ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማኅበርና ቤተ ክርስቲያን ድረስ ተግባራዊ አስደርጋለሁ:: «አሻፈረኝ ኅሊናዬን አልሸጥም» የሚለዉን ከስራ በማፈናቀልና ወደ ማይፈልገዉ ቦታ በማዟዟር እበቀላለሁ፤ ሲብስ ደግሞ በእስራትና በግድያ እርምጃ ለማስወሰድ ማንኛዉንም ጥረት አደርጋለሁ::

እንዲገባችሁና በፍርሐት እንድትዋጡ በምሳሌ ጭምር ላስረዳችሁ እችላለሁ:: እንደራሴዎቼ ሆኑ ባለሟሎቼ ኅሊናቸዉን ለመገለባበጠ የማይቸገሩ በመሆናቸዉ አስቀድሜ ምስጋና አቀርብላቸዋለሁ:: ምሳሌ አንድ: የሥጋዊዉ መሪ ስለ ኢትዮጵያዊነት ሆነ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ደንታ የሌለዉ ይልቁንም ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማን ለማጥፋት ቀን ከሌሊት የሚተጋ ዉስጡ ጥላቻና በቀል የሞላበት መሆኑን እሱም እኔም በደንብ እናዉቃለን:: ከእርሱም በላይ እኔ አዉቃለሁ፤ ይኸዉም አንዳንድ ንግግሮቹንና ተግባሮቹን እርሱ ስለሚዘነጋ እኔ ደግሞ አንዱንም ስለማልረሳ ነዉ:: ገና ከወጣትነቱ ጀምሮ አሳቦቹ ሁሉ ለኔ የሚመቹ በማርክስና በሌኒን ፍልስፍና የተሞሉ «እግዚአብሔር የለም» በሚል፤ በከሃዲዎች ርዕዮተ ዓለም የሚመራ ስለነበረ፤ከሁሉ ይልቅ እንደልቤ መሆን በመቻሉ ለባለወንበርነት አጨሁት::

ከዚያም ያ ያፈጀዉን ተሐድሶ ያልተደረገበት የሶሻሊስት ስርዐትና መሪዎቹ ከወንበራቸዉ ሲገነደሱ እሱን በወንበር ላይ ቀብቼ አስቀመጥኩ:: ታዲያ አንዳንዴ በአስተሳሰቡ ከኔ ላቅ ይላልና ህዝቡ በሶሻሊስት ሥርዓት መንገሽገሹን ተረድቶ ኅሊናዉን ወዲያዊ ገልበጥ አድርጎ ያላሰብኩትን

የካፒታሊስት ስርዐት ዘረጋልኝ:: ታድያ ጭንቅላቱ እንዳልኳችሁ ከሁሉ የመጠቀ ነዉና የትግል ጓዶቹ ቅር እንዳይላቸዉ ያቀበልኩትን ልዩ ቃሌን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ስያሜ በማዉጣት ዓርማቸዉና መመሪያቸዉ እንዲሆን አስደረኩ:: በዚህም ብልጠቱ በሂደት የሚቀናቀኑትን ሁሉ ደምስሶ እንዲገንና አምባ ገነን እንዲሆን ሙሉ ስልጣንን አጎናጸፍኩት::

ታዲያ ከመጀመሪያዉ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የሰንደቅ ዓላማን ፍቅር ለመቀነስ ታጥቆ የተነሳ ታጋዬ ነበርና፤ ኢትዮጵያን በተለያየ መንግስታት ከፋፈለልኝ፤ ሰሜን ክፍል የነበረችዉንም «ኤርትራዊያን ናቸዉ እንጂ ኢትዮጵያዉያን አይደሉም» ብሎ አዋጅ አስነገረልኝ:: ሰንደቅ ዓላማዉንም ከፋፍሎ «የትግሬ ሰንደቅአላማ፣ የኦሮሞ ሰንደቅአላማ፣ የአማራ ሰንደቅአላማ፣ የሱማሌ ሰንደቅአላማ፣ የአፋር ሰንደቅአላማ፣ የሐረር ሰንደቅአላማ፣ የጋንቤላ ሰንደቅአላማ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰንደቅአላማ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ አላማ» በማለት ሁሉም የጎጡን ሰንደቅዓላማ ከፍ ከፍ እንዲያደረግና « አይ ይህን ሽወዳ አንቀበልም፤ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ ነዉ ከፍ የምናደርገዉ» ብለዉ ያስቸገሩትን ደግሞ <u>ወርቃማ ዓርማዬን ኮኮብ በመሃሉ ጉብ አደረገዉና አንጀቴ እስከሚርስ ድረስ በመላዉ ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ እንዲል አስደረገ</u>::

በእሱ መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እቅዱንና ንግግሩን ተግባራዊ አደረጉ:: እንኳን ኮኮብ ዓርማዬን ቀርቶ ስዉሩ ምስጢራዊ ቁጥሬን «666 ይደረግበት» ቢባል፤ ይህ ሕሊናዉን የሸጠ ትዉልድ በፈንጠዝያ ነዉ የሚቀበለዉ:: ለዚህም ምስክር እንዲሆን ሕገ መንግስቴ በሚጸድቅበት ወቅት «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድርሰ ነዉ» ተብሎ በእንደራሴዎቼ ሲበሰር በአዳራሽ ዉስጥ የተዘለለዉ ዝላይና ጭፈራ፣ እልልታና ሆሆታ መጥቀስ ይቻላል:: ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ ትዉልዱ ለኔ ጨለማ ፈቃድ ምን ያህል ታማኝና ዝግጁ መሆኑን በሚገባ ያስረዳል:: ለኔ ኮኮቡ በቂዬ ስለሆነ <u>ከፈለጉ «የቅድስና መገለጫ ነዉ» ይበሉት፤ ሲፈልጉ «የብሔር ብሔረሰቦች መገላጫ ነዉ» ይበሉት፤ ዞሮ ዘሮ መመለኬንና ከፍ ከፍ ማለቴን ነዉ የምፈልገዉ::</u>

ስለሰንደቅ ዓላማ አንዳች ፍቅር የሌለዉና ገና በትግል ዉስጥ እያሉ ኮኮብ ዓርማዬን ዓርማቸዉ አድርገዉ ሲታገሉ የነበረ፤ እዉነተኛዉን ሰንድቅዓላማ <u>«ጨርቅነዉ» ብሎ እንዳላጥላላ</u>፤ አሁን ደግሞ ኅሊናዉን እንደ አክሮባት ገለባብጦ የኢትዮጵያ ወዳጅ ለመምሰልና የሰንደቅዓላማ ፍቅረ እንዳለዉ ለማስመሰል <u>«የሰንደቅ ዓላማ ቀን» ብሎ ያስከብራል:: በምስጢር ስለምንተዋወቅ «ልዩ እንደራሴ እደግ ተመንደግ» ብዬ እመርቀዋለሁ</u>:: ምክንያቱም ዋና ዓላማዬ እዉነተኛዉን ስንደቅ ዓላማና እዉነተኛዉን የመለኮት ዓርማ ከአገሪቱ ማስወገድና ክህደት ማስፈጸም ነዉና ፍላጎቴ::

ይኸዉ ተሳክቶልኝ ከምድሪቱ በአዋጅ ማስወገድና እዉነተኛዉን ሰንደቅ ዓለማ የሚያዉለበልብም በወንጀል እንዲቀጣ ብቻ አይደለም ዓርማዪ ከፍ ብሎ ከክልሎቼ ሰንደቅዓላማ ጋር ቀን ተይዞለት እንዲዉለበለብ ተደርጎልኛል፡፡

<u>ለዚህ አስተዋጽኦ ላደረጋችሁ የተወካዮች ምክርቤት አባላት፣ የፌደሬሽን ምክርቤት አባላት፣ የክልል መንግስታት ምክርቤት አባላት፣ ከታች እስከላይ ያላችሁ ከድሬዎቼና ደጋፊዎቼ፤ ከእግሬ ስር በመርገጥ በከበረዉ ዲያብሎስ ስሜ አመሰግናችኋለሁ፡፡</u> ለወደፊትም ቀራጡ መሪ «ኮኮብ ብቻ አይበቃም የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትና ነጻነት የሚገልጽ  ምስጢራዊ ቁጥር አለ ይደረግበት» ቢላችሁ፤ መቼም ከሱ በላይ ኅሊናችሁን ማገለባበጥ የምትችሉ ብልሆች መሆናችሁን ስለማዉቅ እናንተን መምከር ሆነ ማሰልጠን አያስፈልገኝምና እንደሚላችሁ ሁኑለት፡፡

ምክንያቱም በኢኮኖሚዉ በኩል «ወገኔ፣ ፈቃዴን የሚፈጽሙ» በማለት ስለሆነ ብልጽግናን የሚያድለዉ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ በአስተሳሰብ ከእሱ የተለዩትን የሚመሩትን ድርጅት ለማጥፋት ወደ ኋላ የማይልና ከባሰም ለማሳሰር፣ ለማሳደድ፣ ለማስገደል አንዳች ርኅራኄ የሌለዉ መሆኑን እናንተም ሳታዉቁ ትቀራላችሁ ብዬ አልገምትም፡፡

እስቲ የትኛዉ ባለሃብት ነዉ ወቶ፣ ወርዶ፣ ላቡን አፍሶ፣ በድካሙ የበለጸገ? ሚሊየነርና ቢሊየነር የሆነ? እንዳትዋሹ  በደንብ እንተዋወቃለን፡፡ ይኸዉም በአቋራጭ መንገድ፣ በስርቆት፣ በብልጣብልጥነት፣ በክህደት፣ በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ በመቧደን መሆኑን እንዳልደብቅላችሁ ዓለም ያዉቀዋል፡፡ በንጹህ ስራ ቢሆን፤ ይህ መንግስቴ ካለዉ የጭከናና የአድሎ ፖሊሲ፤ እንኳን ሚሊየነርና ቢሊየነር ልትሆኑ ቀርቶ አንዲት ያማረ መኖሪያ ቤትና መንቀሳቀሻ መኪና አይኖራችሁም ነበር፡፡ ታዲያ እናንተ ባለስልጣናትና ባለሃብቶች፤ ለእንደራሴ መንግስቴ ታማኝ ብትሆኑና ኅሊናችሁን በመሸጥ « አድርጉ፣ በሉ» የሚላችሁን ብታደርጉ፣ ብትሉ ከኔ ልዩ ሽልማት የሚሰጣችሁ አይመስላችሁ፡፡ እኔ ካለምንም ጥቅም እንደቦይ ዉኃ የሚነዳልኝን ነዉ ሞገስና ክብር የምሆነዉ እንጂ፤  ከጥቅሙ ጋር የሚገለባበጥ ሌላ የተሻለ ጥቅም የሚያገኝበት አጋጣሚ ካገኘ ወዲያዉ ሊክደኝ እንደሚችል እገምታለሁና አላምነዉም፡፡ ዞሮ ዞሮ ከትቢያ አንስቶ ለዚህ ያበቃችሁን መንግስቴንና እኔን ከእግሬ ስር በመዉደቅ ልታመሰግኑንና ልትሰግዱልን ይገባችኋል፡፡

እንቢ  ካላችሁ ደግሞ ለእናንተ እንዲመች አድርጌ ያስቀረጽኩትን  ፓሊሲ ይኸዉም በሀብት ላይ ሀብት፤  በቦታ ላይ ቦታ፤  በስልጣን ላይ ስልጣን፤  በኃላፊነት ላይ ኃላፊነት እንዲጨመርላችሁና ምስኪኑ ወገናችሁ ለመኖር እስኪያቅተዉ ድረስ እንዲንገዳገድ፣ እናንተም በአናቱ ላይ እንድትረማመዱ

ያስደረኩትን፤ ደሀዉ እንዲያዝንና እንዲንከራተት፣ በየጥጋጥጉ እንዲወድቅ፣ ባለ ደሞዝተኛም የቤትና የቦታ ባለቤት እንዳይሆን፣ ቦታዎችሁ ሁሉ በሊዝ አቅም ላለዉና ለባለጊዜ እንዲቸበቸብ ያደረኩትን ለዉጥና ማሻሻያ አድርጌ፡-

«ሁለት ልብስ ያሉት አንዱን ለሌለዉ» እንደተባለዉ፤ ይህን ጥቅስ በመጥቀሴ ቅር እንዳትሰኙ፤ ካለቦታዉ መጠቃቀስ የለመድኩት ከእንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁና ከካድሬዎቻቸዉ ስለሆን በዚሁ አጋጣሚ ስለእግዚአብሔር ቃል መጠቃቀሴ ይቅርታ እያልኩ፤ እኔ ግን የራሴን «ሁለት ቤት ያለዉ አንዱን ለሌለዉ ያድል፤ እኔ ብቻ ልበልጽግ የሚለዉ ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ ይበልጽግ፤ በአቋርጭና በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድኖ የሕዝብን ሀብት መመዝበር ይቁም፤ ማጭበርበርና መስረቅ ይቁም፤ ባጠቃላይ በኢትዮጵያዉያን ስም በልመና ሆነ በብድር መልክ መቶ የተወሰነ ግለሰቦችና ቡድኖች በበለጸጉበት ሀብት ንብረት ሕዝቡን ይካሱ፤ አገራቸዉንና ሕዝባቸዉን በታማኝነት ያገልግሉ፤ ከሕዝብ በተለያየ መንገድ የሚሰበሰበዉ ገንዘብ ለትክክለኛ ዓላማ ይዋል ..ወዘተ» የሚለዉን ፓሊስ ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማልመለስ አዉቃችሁ፤ እስከመጨረሻዉ ድረስ ታማኜ እንድትሆኑና የሕዝቡን ሀብትና ንብረት ብቻችሁን ተቀራምታችሁ፣ ጠግባችሁ እስከምትፈነዱ ድረስ ሕዝቡን እንድታጎሳቁሉና እንድታደኸዩ ምክሬን እለግሳችኋለሁ፡፡ ከፈለኩ በደርግ ጊዜ ያስወሰድኩትን እርምጃ በእናንተ ላይም የማሶሰድ ስልጣንና ብቃት እንዳለኝም ልታዉቁ ይገባችኋል፡፡» ተብሎ ቀርቧል

<u>ከላይ በተገለጸዉ መሰረት እግዚአብሔር የአቶ መለስ ዜናዊ ተግባርና የተፈቀደለት ሃያ ዓመት መሆኑናን ከተቆረጠበት ቀን አንድ ቀን በራሱ ሥልጣን መጨመር እንደማይችል ነዉ የሚያሳዉቀን፡፡ እንዲሁም በሥጋዉያን ሆነ በመንፈሳዉያን ያለዉን እዉነት ምን እንደሚመስል ነዉ የሚያስረዳን፡፡</u>

ሌላዉ ደግሞ በዚሁ ክፍል በምዕራፍ አራት በገጽ 401-407 ላይ ሌላ የእግዚአብሔር እዉነታ ቀርቦልናል፡፡ ይኸዉም፡፡፡

«እናንተ የአዳም ዘር ከእግዚአብሔር ጸጋ ለመለየት ሌት ተቀን የምትተጉ ሰዎች፤ ልክ እንደኔ የጨለማዉ ገዥ ዉሎዋችሁንና ዙፋናችሁን በተዝዋዋሪ በሚሸተዉ፣ በሚጠነባዉ፣ በሚገማዉ በዐይነ ምድሩ፣ በሽንቱ ፣ በቆሻሻ ላይ ለማድረግ እየታገላችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል፡፡ በዚህም ምክንያት ምርጫቹ ከተቀደሰ ስፍራ ይልቅ የርኩሰት ቦታ ነዉ፡፡ <u>ለመሪነት ሆነ ለአገልጋይነት የምትመርጡት የሚያጎሳቁላችሁን፣ የሚቀጠቅጧችሁን፣ የሚያስጨንቃችሁን፣ ፍዳና መከራ</u>

የሚያሳያችሁን፣ ተቧድኖ ራሱን ብቻ የሚያበለጽገዉን፣ እናንተን ግን በድህነት፣ በረሀብ፣ በችግር የሚቀጣችሁን ሰዉ ነዉ።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት ደግሞ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። ይኸዉም በምርጫ 2002 በአራቱም ማዕዘን ያላችሁ የኔን የጨለማዉ ገዥ እንደራሴ መሪና ባለሚሎቼን ባለስልጣናትን እንዲሁም ዉዶቼን ካድሬዎቼን ከመቶ ከ ዘጠና ዘጠኝ እጅ በላይ በሆነ ብዛት መርጣችኋል። ይህም የሚያሳየዉ ምርጫችሁ እኔን የጨለማዉ ገዥን መሆኑንና « እኛ የምንፈልገዉ መሪ ሆነ ባለስልጣን እንዲሁም ኃላፊ ዉስጡ ተንኮል፣ ክፋት፣ ዓመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ጥላቻ፣ በቀል የሞላዉ፤ ኅሊናዉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተበከለና የተመረዘ ጨካኝ፤ አስመሳይና ሸንጋይ፤ ኅሊናዉን የሚገለባብጥ ሰዉን ነዉ» በማለት ስለመረጣችሁ ምርጫዬ ምርጫችሁ በመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ።

ታዲያ በራሳችሁ ምርጫ « እንዲህ ሆነን ፣ እንዲህ ተቸገርን፣ ፍዳችንንና መከራችንን አየን፣ ተሰቃየን.. ወዘተ» በማለት አምላካችሁን እንዳታማርሩ። ምክንያቱም በነጻ ኅሊናችሁ ተመርታችሁ ነዉና የመረጣችሁት ምርጫችሁን ያከብራል። ነገር ግን የምርጫችሁን ፍሬ ነዉ የሚሰጣችሁ እንጂ የእርሱን ፍሬ አይሰጣችሁም።

በተቃራኒዉ ደግሞ « እግዚአብሔር ሆይ! ምርጫችን አንተን ነዉ፤ አንተ ንገሥብን ፤ አንተ አስተዳድረን።» ካላችሁ ደግሞ እንደምርጫችሁ የራሱን መንግስት አቋቁሞላችሁ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ መንግስቱን በአንድላይ በመንፈስ ቅዱስ እንዲመራ አድርጎ ምድራዊ በረከትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ እርካታን የምታገኙ፤ ከሥጋችሁ ስትለዩ ደግሞ ለሕያዉነት ዘመን በሰማያዊ መንግስቱ በቅዱሳን መላእክት አኗኗር እንድትኖሩ ያደርጋችኋል። ይሁንና እናንተም እንደ እኔ ጨለማዉ ገዥና እንደ ጭፍሮቼ ሰይጣናት ክብር የማይወድላችሁ ስለሆነ ምርጫችሁ ከእግዚአብሔር ጸጋ መለየትንና መራቅን ፣ በጉስቁልና ሕይወት መመላለስን፣ በመከራና በፍዳ ኑሮ መኖርን ስለሆነ ይኸዉ ፍዳችሁንና መከራችሁን ትቀበላላችሁ። በዚህ ሳያበቃ ነፍሳችሁ ደግሞ ዳግም የንስሐ እድል በማታገኙበት በሲዖል ነጻነቷን ተገድቦ ትኖራለች። በመጨረሻም በፍርድ ቀን «ምርጫህ ምራጫችን ነዉ።» ካላችሁኝ ከግብር አባታችሁና ጌታችሁ ጋር በገሃነመ እሳት ዉስጥ ተከባብረን እንኖራለን።

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ በእንደራሴዎቼና በባለሥልጣኖቼ፣ እንዲሁም በካድሬዎቼ ስብከት ተታላችሁና ኅሊናችሁ ተበክሎ የአህዛብያዉያን አምልኮ የሆነዉ ባህላዊ ( ባዕድ) አምልኮና ጣዖት አምልኮ « እምናታችን ነዉ» ብላችሁ በዐመጻና በክህደት እንዲሁም በአምልኮ ምንዝርና ሕይወት

ተመላልሳችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት መዉረስ ቀርቶ፤ በሰማያዊ አባታችሁና አምላካችሁ ክርስቶስ ስም ክርስቲያን የሚለዉን ስያሜ ይዘዉ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የፕሮቴስታን «እምነት» ተከታዮችን እንኳ በተለያየ ምልክ መጫወቻ አድርጌያቸዉ ከእግዚአብሔር መንግስት ለይቻቸዋለሁ::

ይኸዉም በአታላዩ(በሸዋጁ) ርኩስ መንፈሴ መሪነት ባዘጋጀዉላቸዉ የእምነት መመሪያ (ዶክትሪን) ነዉ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን « አማላጅ ነዉ:: ፍጠር ነዉ :: ነብይ ነዉ:: ተራ ሰዉ ነዉ :: አብና መንፈስ ቅዱስ  የሚባሉ የሉም አንድ ኢየሱስ ብቻ ነዉ::» እያስባልኩ ወደ ክህደትና ሞት መንገድ የመራዋቸዉ:: እኔን የሚገርመኝ እስከ ዛሬ ድረስ ለዉድቀትና ለጥፋት የተጠበብኩባቸዉን አለማወቃቸዉ ብቻ ሳይሆን በከፋፍለህ አዳክም መመሪያዬ መሰረት አንድ እንዳይሆኑ «አንዱ አማላጅ፣ አንዱ ፍጡር፣ አንዱ ኢየሱስ ብቻ» በሚል «የእምነት» ድርጅት እንዲያቋቁሙ በማድረግ ከአስራ ሺህ ድርጅቶች በላይ አቋቁሜ በእምነት አንድ አለመሆናቸዉን እያወቁ «ልሳን » የሚባለዉን ዘመናዊ የዛርና የሟርት ትዕይንት «መንፈስ ወረደልን» በሚል ስሜት እንዲመለከቱ አድርጌ  በሁሉም ድርጅቶቼ እንዲከሰት እያደረኩ፤ አንድ ሰዉ እንኳ «ተቃራኒ እምነት እያለን እንዴት ተመሳሳይ ልሳን ምልክት በሁላችን ላይ ይታያል? የሆነ የተታለልነዉና የሳትነዉ እዉነት  አለ» ብሎ የሚጠይቅና እዉነትን የሚፈልግ የለም::

ሁሉም ለቅርፊት ሥጋዉ በሚመች ሕይወትና ሥርዓት መመላለስ ስለሆነ ምርጫዉ፤ በአንደበቱ « እግዚአብሔር ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወንጌል» እያለ በሞት መንገድ ዉስጥ እንዲመላለሱ በማድረጌ አንደኛዉን የሚሊኒየም ግቤን አሳክቻለሁ:: ታዲያ ብዙ ተከታይ እንዲያገኙ እኔን «ዲያብሎስ» እያሉ እንዲያጥላሉኝና እንዲረግሙኝ ሙሉ ነጻነትንና ፈቃድ ሰጥቻቸዋለሁ:: ልክ እንደዘመኑ አንዳንድ «ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ነን» በማለት የመንግስት መሳሪያ የሆኑና ተቃዋሚ ላማስመሰልና ደጋፊ ለማግኘት ሲሉ አንዳንዴ መንግስትን ሲቃወሙና ሲኮንኑ መንግስት የራሱ ተለጣፊ መሆናቸዉን ስለሚያዉቅ አንዳች እንደማይላቸዉና ቂም ይዞባቸዉ እንደማይበቀላቸዉ ሁሉ፤ እኔም የጨላማዉ ገዥ እነዚህ በእግዚአብሔር ሆነ በኢየሱስ ስም የሚነገዱ አገልጋዮቼ በኔ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆኑ ቢሰድቡኝ ሆነ ቢረግሙኝ አንዳች የማይሰማኝ ሲሆን፤ ዋናዉ ፍላጎቴ በእዉነተኛዉ አምልኮና እምነት ዉስጥ ያሉ ምእመናን « እግዚአብሔር የሚሰበክበትና ዲያብሎስ የሚረገምበት አዳራሽ ነዉ» በማለት ወደ እኔ ጨለማዉ ገዥ የእምነት ድርጅቴ  ዉስጥ እንዲመጡ ነዉ::

ኀሊናቸዉን በራሳቸዉ ጊዜ አደነደኑት እንጂ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ቢሆን ኖር እንኳን አስራ ሺህ ቤት ድርጅት ሊቋቋም ቀርቶ ሁለት የተለያዩ ተቋም አይሆኑም ነበር:: ነገር ግን

ምርጫቸዉን እኔን ስላደረጉና ሁሉም ድርጅቶች በበላይ የምመራቸዉና የማሳስባቸዉ እኔ ስለሆንኩ እያንዳንዱን የድርጅቴን አባል እንደ ኳስ ልጫወትበትና ከእዉነት ላርቀዉ ችያለሁ፡፡

የሚያሳዝነዉና የሚገረመዉ ደግሞ ከእዉነተኛነት፣ ከቅንነት ፣ ከየዋህነት፣ ከልባምነት ሕይወት መራቃቸዉና፤ በደመ ነፍስ በመመላለስ በክህደት፣ በዐመጻ መኖራቸዉ ሳያንሳቸዉ፤ እኔ እንኳ የማልዳፈረዉን በትዕቢትና እብሪት በሞላዉ ንግግር ቅዱሳን መላእክትን፣ ነብያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የአደራ እናታቸዉን ለሰዉ ዘሮች ደኅንነት ሁል ጊዜ ኀዘንተኛ መሆንን የመረጠችሁንና ለሰዉ ዘር በሙሉ ጥብቅና የምትቆመዉን ድንግል ማርያምን ያዋርዳሉ፤ ያቃልላሉ፤ ይሰድባሉ፡፡ በዚህ ብቻ ሳያቆሙ እለት እለት እዉነተኛዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ ፤ ፍጡር ነዉ » እያሉ ይሰድባሉ፤ ያዋርዳሉ፡፡ ታዲያ ይህን ድርጊታችሁን ማቅረቤ ማንነታችሁን ለመግለጽና ወደ እዉነተኛ የሕይወት መንገድ ዉስጥ በንስሐ እንድትመለሱ ፈልጌ ሳይሆን ከእኔ በላይ የሆነዉን ድፍረታሁንና ጀግንነታችሁን ለማድነቅ ፈለጌ መሆኑን እናንተም የምትረዱት ይመስለኛል፡፡

እናንተ ኢትዮጵያዉያንና የዓለም ሕዝቦች፤ እንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁ፣ ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ ዉዶቼ ካድሬዎች፣ እንዲሁም ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ ባለዛሮች.. ወዘተ ያመጡላችሁን የባህልና የክህደት፣ የርኩሰት አምልኮና ሥርዓት ርግፍ አድራጋችሁ በመተዉ፤ በእዉነተኛ ንስሐ የቀደሙ ወላጆቻችሁ ያመጡላችሁን በብሉይ ዘመን በእዉነትና በመንፈስ የሚከናወነዉን ኪዳነ ልቦና፣ በኋላም በሙሴ አማካይነት የመጣዉን ኪዳነ ኦሪት፣ በመጨረሻም የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉህድ ዘር ከሆነችዉ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰዉ የሆነዉ አምላክ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በመሰረተዉ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ተመርታችሁ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቅ ከእግዚአብሔር እዉነተኛ ልጅነትን ብታገኙ፣ ሕያዉ ሆናችሁ በመንግስተ ሰማያት እንድትኖሩ የሚያስደርገዉንና ኃጢአታችሁን ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚደመስስላችሁን ቅዱስ ሥጋዉንና ክቡር ደሙን ብትቀበሉ፤ በእዉነተኛነት፣ በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በልባምነት ሕይወት ብትመላለሱ፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ደስ የማይለኝ ስለሆነ ከኔ ጋር ያላችሁን ወዳጅነት ሆነ አንድነት ወዲያዉ እንድታቋርጡ የማደርግ መሆኑን በጥብቅ አሳዉቃችኋለሁ፡፡ ስለዚህ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወታችሁ እስከመጨረሻ እንድትጸኑ አሳስባችኋለሁ፡፡

ሌላዉ አደራ የምለዉ ሰባቱ ቅዱስ ኪዳናት የተባሉትን መመሪያችሁ አድርጋችሁ ብትኖሩ፤ በምድራዊ ሕይወት ዘመናችሁ በረከት፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ እርካታ፣ አንድነት፣ ቅድስና በተሞላዉ ኑሮና ሕይወት እንድትመላለሱና ከሥጋ ሞት በኋላ ደግሞ በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆናችሁ በቅዱሳን መላእክት ሕይወት አይነት አኗኗር በቅድስናና በደስታ ሕይወት ብቻ እንድትኖሩ ስለሚያደርግ፤ ይህ ድርጊታችሁ ደግሞ በኔ ላይ ክህደትና ዐመጻ እንደፈጸማችሁ ስለሚያስቆጥር የክህደትና የሽብርተኛነት አዋጅ አስወጥቼ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ሆነ ለማጥቃት እንዳልችል ልምሾ ብታደርጉኝም፤ እንዲሁም ሌት ተቀን እረፍት ነስታችሁኝ በመከራ፣ በስቃይ፣ በምሬት ሕይወት ዉስጥ እንድኖር ብታስገድዱኝም፤ እናንተን እስከ መጨረሻዉ እቅታ ድረስ ልበቀላችሁ ወደ ኋላ የማልል መሆኔን  በተለመደዉ ጉራ፣ እብሪትና በዶነት በተሞላዉ አንደበቴ አስጠነቅቃችኋለሁ::

መቼስ እኔ የማዝንለት ግለሰብ ሆነ ቡድን፣ መንግስት፣  የእምነት ተቋም የሌለ ቢሆንም፤ «ግድ እዘንላቸዉ» ብባል የሚያሳዝኑኝ ሙስሊም ወገኖቻችሁ ናቸዉ:: ዉዱ ባለዉለታዬ የሆነዉ፤ ፍጹም እግዚአብሔር የሆነዉን አምላክ በድፍረት «ኢየሱስ (ኢሳ) እንደ እኔ ነብይ ነዉ እንጂ አምላክ አይደለም::» በማለት ትዉልዱ በክህደት እምነት እንዲመላለሱ በማድረጉ ምክንያትና በእምነቱ ዉስጥም « ሰዉ ሰዉን ገሎ፣ ግፍና ጭከናን ፈጽሞ ገነት ይገባል» የሚል  አሰተምሮ ስላለዉ በአራቱም ማዕዘን ፈቃዴን ለማስፈጽም እጅግ ስላመቻቸልኝ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስሜ ባለበት ቦታ አመሰግነዋለሁ::

ታዲያ አሳዛኞቹ ደግሞ በእምነቱ ዉስጥ ባለዉ አንዳንድ እዉነት ማስመሰያ አስተምሮ አምላካቸዉን በመፍራት በጾሙ፣ በጸሎቱ፣ በስግደቱ፣ በምጽዋዕቱ.. ወዘተ የሚመላለሱ፤ ከአህዛብ የራቁትነት አለባበስ  ራሳቸዉን ለይተዉ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት የጨዋ አለባበስ የሚለብሱ፤ ከዳንኪራዉ፣ ከዘፈኑ ራሳቸዉን የለዩ፤ ከሱስና ከስካር የራቁ፤ የአሜሪካንና የአዉሮፓን የአህዛብ ባህል የማይከተሉ፤ ሌሎች ወገኖቻቸዉን የሚወዱና የሚያከብሩ፤ ባጠቃላይ እኔ የጨለማዉ ገዥ ደስ በማይለኝ ሕይወት የሚኖሩት በእምነቱ ዉስጥ የሚመላለሱት ሰዎች ናቸዉ::

ዞሮ ዞሮ የሕይወት መንገድን ስለሳቱልኝ ፍርዱ ቢቀልልላቸዉም እንደ እግዚአብሔር ቃል « በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ (በሥላሴ) ስም  ተጠምቆ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ያላገኘና መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ያልተቀበለ የእግዚአብሔር መንግስት አይወርሱም::» በሚለዉ የፍርድ ቃል እጽናናለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ተገልጾ የተናገረዉ ስለሆነና « ቃሌ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል» በማለት ቃሉ ምን ያህል ጥብቅ መሆኑን

ለአዳም ዘር ስለገለጸ ለኔም ሆነ ለእናንተ አንዳች አድሎ እንደማያደርግ የታወቀ ነዉና። ስለዚህ ከተፈረደባችሁ አይቀር እኔ ደስ በምሰኝበት የኃጢአት ተግባርና ሕይወት ብትመላለሱ የተሻለ መሆኑን እመክራችኋለሁ።

በዚሁ አጋጣሚ አንድ ሥጋቴን እገልጽላችኋለሁ፤ ይኸዉም የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ለማጥፋትና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመደምሰስ የተሰለፋችሁ የጥፋት ሰዎችና የዐመጻ ልጆች የሆናችሁ ዉዶቼ፤ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋችሁ ሲሞላ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታችሁ የሚሆነዉ በዚህች ምድርም መዋረድ፣ መከራና ስቃይን መቀበል፣ በመጨረሻም መጠረግና በቀጥታ ካለምንም ጥያቄ ወደ ጨለማዉ ቦታ ሲኦል መግባት መሆኑን አዉቃችሁ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ የሚል ነዉ።

ታዲያ አንዳንዶች የእኔን አሰራር ያልተረዱ ባለሟሎቼና ዉዶቼ  ያልገለጽኩላቸዉን ምስጢር አሁን ብገልጽላቸዉ ምን እንደሚሉ ባላዉቅም፤ የጥፋት ሰዎችና የዓመጻ ልጆች ለእኔ ዉዶቼ የሆናችሁ ግን ትምህርት እንዲወስዱ ቀኝ ገዢዎች ከእናት አገራቸዉ ለይተዉ «ሱማሊያ» የሚል ስያሜ አዘጋጅተዉ የዓመጻና የክህደት ተግባር ሲያስፈጽሟቸዉ የደረሰባቸዉንና እየደረሰ ያለባቸዉን ችግርና መከራ ዓለም ስለሚያዉቀዉ ብዙ አልናገርም። በተዝዋዋሪ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተሰለፉት የኢራቁና የሊብያዉ መሪ ምን አይነት እድል እንደገጠማቸዉ ዓለም ስለሚያዉቅ ስለዚህም አልናገርም።

ስለ ሁለተኛዉ ዓለም ጦርነትም ማስታወስ አልፈልግም። እኔ የምናገረዉ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ የተቀደሰችዉን አገር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት የተሰለፉ መንግስታት፣ ቡድኖች(ድርጅቶች)፣ ግለሰቦች ካለፉት መማር አልቻሉምና በእግዚአብሔር ቁጣ እንዳልነበሩ ቢሆኑና ቢጠረጉ እኔ አንዳች እንደማልጠየቅ እየገለጽኩ፤ በመጨረሻ ግን «እናንተ ዉዶቼንና ባለሟሎቼ እናንተን የማጣ ከሆነ አዘንተኛ እንደምሆን አዉቃችሁ አሁን ባለቀለት ሰዓት ቢሆንም «ምናለ ብታጽናኑኝና ብታስደስቱኝ? » በማለት የመሰናበቻ ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ።

ምክንያቱም ለወደፊት ፈቃዴን የሚፈጽም የሚያስፈጽም እንደራሴና ባለሟል አጣለሁ የሚል ስጋት ስላለብኝ ነዉ። መቸስ ተማሪ አጥንቶ አጥንቶ ጥሩ ዉጤት እንደሚጠብቅ ሁሉ እኔም በኃጢአት አሰልጥኜ አሰልጥኜ ጥሩ ዉጤት እንደምጠብቅ እንኳን እናንተ ምርጦቼ የጥፋትና የዐመጻ ልጆች ቀርቶ ጠላቶቼ የሆኑት «የእግዚአብሔር ባለሟልና ልጆች» የሚባሉት ከአምላካቸዉ ጋር

አንድነትና ህብረት ፈጥረዉ ከኔ ፈቃድ የወጡና ያፈነገጡት ሰዎች ጭምር ያዉቃሉ፡፡» **ይላል የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዉያንን መጥፋት የሚፈልገዉ የጨለማዉ ገዥዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡ » ይላል**

**<u>ከላይ በተገለጸዉ መሰረት እግዚአብሔር ሊያሳዉቀን የፈለገዉ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ያለዉን እዉነታ ነዉ፡፡</u>**

እንዲሁም በዚሁ ክፍል በምዕራፍ ሰባት በገጽ427-431 ላይ ዲያብሎስ ከላይ እስከ ታች ላሉ አገልጋዮቹ የሚያስተላልፈዉና ማንነታቸዉን የገለጸበት መልእክት አለ፡፡

«እናንተ የመንግስት ፍርድ ተቋማት፣ ምስጋና በጨለማዉ ስሜ ልቸራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይኸዉም ለፍትሕና ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለነጻነት ለቆመዉ መንግስቴ አጋር ሆናችሁ እዉነተኛ ዉንና ኅሊዬን አልሸጥም የሚለዉን፣ ስለእዉነት የሚመሰክረዉን ሰዉ የመወንጀያ መረጃ አቀነባብራችሁ ካለጥፋቱና ወንጀሉ በተቀነባበረ ሴራ ለእስርና ለሞት ፍርድ ስላበቃችሁ፣ እንዲሁም ግፈኛዉን፣ ሌባ ቀማኛዉን፣ ወንበዴዉን፣ ወንጀለኛዉን ጥሩ በተቀነባበረ መረጃ ነጻ አዉጥታችሁ በመፍረዳችሁ ምክንያት ነዉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተበድለዉ «ደሀ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ» የሚል መንግስት አለና «ፍርድ እናገኛለን» ብለዉ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተበዳዮችን፣ ለኅሊናቸዉ ሳይሆን ለገንዘብና ለጥቅማቸዉ በቆሙ ዳኞች፣ ጠበቆች፣ አቃብያን በሐሰት መረጃና ተበዳይም የሚፈለገዉን ሊያቀርብ እንዳይችል ተደርጎ፣ ይልቁኑም «ጉዳዬን ወደ ፍርድ ቤት ባላመጣሁ» ብሎ እስኪመረር ድረስ «ይፈረድልኛል» ብሎ እዉነተኛ ፍርድ የሚጠባበቀዉን ሰዉ ፍዳዉን ስለምታሳዩልኝ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት እለት እለት በሀብት የምትበለጽጉበትን መንገድ አመቻችላችኋለሁ፡፡ ዋናዉ እናንተ መቆም ያለባችሁ ለኅሊናችሁ ሳይሆን ለጨለማዉ ስርዐቴና ገንዘብ ለምታገኙበት ጉዳይ ብቻ መሆን አለበት፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ የገረመኝና እጅግ ያስደነቀኝ ይህ አይነቱ የፍርድ አሳራርና አወሳሰን የሚፈጸመዉ ምንም ባልተማሩ ወገኖች ሳይሆን «ተማርን፣ ከደሀዉ ቤተሰብ ነዉ የወጣነዉ» በሚሉ ግለሰቦች መፈጸሙ ነዉ፡፡ የጥንት ዳኛች ሆኑ ጠበቃዎች ካለምንም ሰርተፍኬት፣ ዲፕሎማ፣ ድግሪ ሳይዙ እዉነተኛዉን ፍርድ እግዚአብሔር እንዲፈርድ ኅሊናቸዉን አሳልፈዉ ስለሚሰጡ በዳኞች ላይ አድሮ እግዚአብሔር ነበር የሚፈርደዉ እንጂ ስለ ደሞዝና ስለጥቅም ሲሉ የበደለዉን ነጻ ፣ የተበደለዉን እንዳልተበደለ አድርገዉ አይፈርዱም ነበር፡፡ ያንን ዘመን ያሳለፈልኝ ይመስገን እንዳልል

በተዝዋዋሪ እግዚአብሔርን ማመስገን ይሆንብኛልና እኔዉ ራሴን በራሴ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ይህን የከፋና የከረፋ ስርዐት ያመጣችሁልኝን ሁሉ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ፡፡

የፍርድ ቤትን ጉዳይን ከሌሎቹ መስሪያ ቤቶች በተለየ ሁኔታ አንስቼ ምስጋናዬን የቸርኳችሁ፣ ሌሎቹ መስሪያ ቤቶች ሳያስደስቱኝ ቀርቶ ሳይሆን ጠበቃ፣ አቃቤሕግ፣ ዳኛ ለእዉነት ብቻ ቆመዉ በበደለኛዉ ላይ ማስፈረድ፤ ለተበዳዩ ደግሞ እንዲፈረድለት ካላደረጉ፣ በፍርዱ አድሎ የሌለዉ፤ በዘመድ አዝማድ፣ በትዉዉቅ፣ በገንዘብ፣ በጥቅም የማይፈርደዉ እዉነተኛ ፈረጃ ዳኛ እግዚአብሔር፤ ስለተገፉ፣ ስለተበደሉ፣ ስላዘኑ፣ ስለተከዙ፣ ስለተመረሩ ሰዎች ሲል በስርዐቱ ላይ የማያዳግም ፍርዱን አምጥቶ የንግሥናዬ ዘመን እንዳያጥር ካለኝ ስጋት አንጻር ብቻ መሆኑን ላሳዉቃችሁ እወዳለሁ፡፡

እናንተ በየመስሪያ ቤቱ ሕዝቡን የምታጉላሉና ፍዳዉን የምታሳዩልኝ ወኪል አገልጋዮቼ «ለምን የተለየ ምስጋና አልተቸረንም?» ብላችሁ አንዳች ቅሬታ እንዳይገባችሁ፡፡ ስርዐቱ እስካለ ድረስ እናንተም ትኖራላችሁና አንዳች የተለየ ምስጋና ከኔ እንዳትጠብቁ፡፡ ምክንያቱም በኋላ ተገልብጣችሁ ሕዝቡን በቅንነትና በእዉነት ብታገለግሉ ምን ዋስትና አለኝ? በቅንነትና በእዉነት ላለማገልገል ዋስትና የሚሰጠኝ ግለሰብ ካለ የተለየ ምስጋና በጨለማዉ ስሜ ላቀርብለት እችላለዉ፡፡ ዋናዉ ደግም እምነታችሁ ስለሆነ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በጭከና፣ በጠማማነት፣ ባጠቃላይ ቅንነትና እዉነተኛነት በሌለዉ አገልግሎት ዉስጥ የምትመላለሱ ሰራተኞች ሁሉ በጨለማዉ ስሜ እንደተመሰገናችሁ ልታዉቁ ይገባል፡፡

ታዲያ ፍርድ ቤትን ካነሳዉ አይቀር ዉዶቼ ካድሬዎች የተሰገሰጉበትን ክፍለከተማ የመሳሰሉ መስሪያ ቤቶቼን ሳላመሰግናቸዉ ባልፍ ኅሊናዬ ስለሚወቅሰኝ በእናንተ የተመሰገንኩ ልሁን እላለሁ፡፡ ምክንያቱም ሳይማር ያስተማራችሁን ሕዝብ ብቻ አይደለም የተማረዉንም ጭምር በካድሬነት መታወቂያችሁ ተመክታችሁ ፍዳቸዉን በማሳየት ስለምታጉላሉትና በአግባቡ እንኳ ጉዳያቸዉን ሰምታችሁ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆናችሁ ብቻ አይደለም ከፍ ዝቅ እያደረጋችሁ የምታዋርዱና የምትሳደቡ በመሆናችሁ ጭመር ነዉ፡፡ እንዲሁም ራሳችሁን  አድራጊ፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ አድርጋችሁ በመቁጠር ለፈለጋችሁት የፈለጋችሁትን ስታደርጉ፤ ላልፈለጋችሁት ደግሞ አንድ አመት አይደለም ከአስር አመት በላይ እንዲመላለስ፣ እንዲጉላላ የምታደርጉ ጨካኞች ስለሆናችሁ በዚህም ልትመሰገኑ ይገባችኋል፡፡

እነዚህ አገልጋዮቼ እንኳን ተራዉን ሕዝብ አይደለም በሕዝብ ስም የሚነግዱትን ለአፋቸዉ ይምስል «መልካም አስተዳደር » እያሉ የሚያለግጡትንና ሕዝቡን የሚሸነግሉትን እንደራሴዎቹ

መሪዎችና ባለሚሎች ባለስልጣናት መልካቸዉን ለዉጠዉ ለመስተናገድ ቢመጡ ያዉ ሕዝቡ ላይ የሚደረሰዉ መጉላላትና እንግለት በእነሱ ላይም ከማድረስ ወደ ኋላ የማይሉ፤ ከእነሱ በተቀበሉት የዐመጸ አገልጋይነት ምስክር ወረቀት በመመካት ታላቅነታቸዉንና ጀግንነታቸዉን ስለሚያስዩ፣ በዚህ አቋማቸዉ ከጸኑ ደግሞ ለወደፊቱ የመሪነቱንና የባለስልጣንነቱን ወንበር እንደሚረከቡ ተስፋ አድርጋለሁ።

ግምት ዉስጥ የጣላቸዉን ሳልጠቁም ብገልጥ «አድሎ ተደረገብን» የሚሉ ወገኖቻችሁ አገልጋዮቼ አሉና፤ የተለየ ተግባራችሁን ለዓለም ማሳወቅ እፈልጋለሁ። ይኸዉም በዘመድ አዝማድ፣ በበላይ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም በገንዘብ ኃይል የሚቀርቧችሁን ሁሉ እንኳን መመሪያዉ ፈቅዶላቸዉ አይደለም ሳይፈቅድላቸዉም የሚመቻቸዉን መመሪያ ራሳችሁ በመፍጠር ጉዳያቸዉን ሳይመላለሱና ሳይጉላሉ ትፈጽሙላችዋላችሁ።

በተቃራኒዉ ደግሞ ለምስኪኖች እንኳን ጉዳያቸዉን መፈጸም አይደለም በትህትና እንኳ ለማነጋገር ፈቃደኞች አይደላችሁም። ሊፈጸምላቸዉ የሚችለዉን ጉዳይ እንከንና ጉድለት እየፈለጋችሁ በራሳችሁ (መስሪያ ቤቱ) በፈጠረዉ ስህተትና ጉድለተ ባለጉዳዩን ለዓመታት እንዲቀጣ፣ እንዲጉላላ ታደርጋላችሁ። የሚገርመዉና ትዝብት ላይ የጣላችሁ ደግሞ በግርግዳ ላይ « ሕዝብን በቅንነትና በግልጸኝነት ለማገልገል ካለአድሎና ካለ ሙስና ለማገልገል በቁርጠኝነት ተነስተነናል» ብላችሁ ትለጥፋላችሁ። በእርግጥ ይህን በቃላት ማታለልና በተግባር ተቃራኒዉን መፈጸም ከኔ ከግብር አባታችሁ ከጨለማዉ ገዥ የተማራችሁት ቢሆንም፤ እኔ ግን ለሁሉም ሰዉ ጥሩ ተግባር እንዲፈጸም አልፈልግም። እናንተ ግን ሰዉን እየመረጣችሁ ለፈለጋችሁት ብቻ መልካም መልካም መስተንግዶ ታደርጋላችሁ።

እዚህ ላይ ለማስጠንቀቅ የምፈልገዉ በቅንነትና በእዉነተኛነት ሕዝብን ለማገልገል የተሰለፋችሁ የኔ የጨለማዉን መንፈስ አሰራር የምትቃወሙ ሰራተኞች፣ በአጠቃላይ ስርዐቱን በበላይ ሆኜ የምመራዉ እኔ ስለሆንኩ አገልጋዮቼንም አታልዬ(ሸዉጄ) ፈቃዴን የማስፈጽም ስለሆነ፤ ከስራ የመባረር ሆነ በሌላ የመጠቃት እድል እንዳያጋጥማችሁ በኔዉ መንፈስ ብትመሩ የሚሻላችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እንግራችኋለሁ።

እናንተ ምርጦቼ ሕዝብን የምታጉላሉልኝ ግን ከፍ ከፍ አደርጋችኋለሁ። ታዲያ አንዳንድ ሰዎች የሚሉትን አትስሙ። ይኸዉም «እነዚህ ደሞዝ የሚከፈላቸዉ የሚያጉላሉን ሰዎች ገንዘቡ መቼስ ከሰማይ እንደማይዘንብ ይታወቃል፤ ከኛዉ በተለያየ መልኩ ከሚሰበሰበዉ ነዉ የሚከፈላቸዉ፤

እንኳን ለእነሱ አይደለም አገሪቷን ለሚመሩና ለባለስልጣኖቹ ሳይቀር የሚከፈለዉ ከኛዉ ከተሰበሰበዉ ገንዘብ ነዉ:: ታዲያ እኛ ሕዝቦች እንደዚህ ለሚያጉላሉንና ለሚያሰቃዩን ሰራተኞች «አንከፍልም» ብንል፤ ደጅ መጥናትና መጉላላት ምን እንደሆነ ያዉቁ ነበር:: አሁን ግን የሚያገኙት ገንዘብ ስላሰከራቸዉ የሰዉ ድካምንና እንግልትን ሊያዉቁ አይደለም ሊሰሙ ፈቃደኞ አይደሉም» በማለት የሚናገሩትን አንዳች እንዳትሰሙ:: ይልቁኑ «ቀድሞ በአለንጋ ነበር የምናሰቃያችሁ አሁን ደግሞ በጉጠት ነዉ ፍዳችሁን የምናሳያችሁ » በማለት ዲያብሎሳዊ ስርዐቴን ለማስጠበቅ እስከ ደም መስዋዕትነት እንድትከፍሉ አሳስባችኋለሁ:: <u>ለዓለማዊ ማሳካትም ቴሌቭዥኑን፣ ሬድዮኑን፣ የተለያዩ ሕትመቶችን፣ ስብሰባዎችን፣ እድሮችንና ሰንበቴዎችን ሳይቀር በመጠቀም ትዉልዱን በወሬ፣ በማስመስልና በሽንገላ ቃላት ልታደነዝዙት ይገባል::</u>

<u>ምክንያቱም የማመዛዘንና የመገምገም ጊዜ ካገኙ ምርጡ እንደራሴዬ የሆነዉ መሪያችሁን « ታላቁ፣ አንገት ያለዉ፣ አስተዋዩ መንግሥታችን» እያላችሁ የምታገኑትን የመንፈስ አባታችሁን ሊቃወሙና ሊተቹ ይችላሉ:: ለዚሁ ማስረጃ እንዲሆናችሁ ሳይቸግራችሁ የምርጫ ነጻነት ሰታችሁ በዘጠና ሰባት ዓመት ምህረት ያ ሁሉ መሪያችሁን ለመደገፍ የወጣዉ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ተቃዋሚዎቻችሁን የመረጠዉና እናንተንም ከነመሪያችሁ ስጋትና ጭንቀት ዉስጥ የጣላችሁ መሰሪ የሆነዉን ተግባራችሁን ሕዝቡ እንዲያዉቅ ስለተደረገ ነዉ::</u>

ይሁንና እግዚአብሔር ሕዝቡ ሰዉን ተስፋ እንያደርግና በእሱ ብቻ እንዲተማመኑ እንዲሁም እሱን ብቻ ተሰፋ እንዲያደረጉ ለማስተማርና ተስፋ የተደረገባቸዉ ሰዎች በህብረት የተነሱት ያዉ የሥጋና ደም ስሜታቸዉን ለመፈጸም እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ባለመሆኑ ያ ሁሉ ስጋታችሁና ጭንቀታችሁ ተወግዶላችሁ ካለምን ተቀናቃኝ ይኸዉ በወንበሮቻችሁ ላይ ቂብ ብላችሁ ተቀምጣችኋል::

መንግስታችሁም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥሩ ትምህርት በመዉሰዱ እነዚያ ያስጨነቁትንና ለዓለም ገበናዉን ያጋለጡበትን በእስር፣ በማሳደድ፣ በማስደብደብ፣ በማስገደል፣ አካለ ስንኩል በማድረግ፣ ሀብትን ንብረታቸዉን በመቀማት፣ ኅሊናን በማሸጥ .. ወዘተ ፍዳቸዉን አሳይቶልኛል:: እኔም ይህን ቆራጥነቱንና ጀግንነቱን እንዲሁም ጭካኔዉንና በቀለኝነቱን ስላወኩ ነዉ ለመሪነት ያጨዉትና ለወንበር ያበቃሁት::

<u>ታዲያ እዚህ ላይ ላልነግራችሁ ብፈልግም እንደበፊቱ በእሳት ሰንሰለት ተጠፍሬያለዉና የዐመጻ ጽዋችሁ ከሞላ ግን እኔም ልታደጋችሁ እንደማልችል፤ እናንተም ራሳችሁን ማዳንና ከወንበራችሁ</u>

ላለመቆረጥ እንደማትችሉ ሳዉቅ ሆዴን ባር ባር ይለዋል:: ምክንያቱም ምስኪኑ ወገናችሁ ሲራብ፣ ሲቸገር፣ ሲጠማ፣ ሲታረዝ፣ በየመንገዱ እንደ ቆሻሻ ሲጣል፣ መከራና ስቃይ ሲደርስበት፣ ባጠቃላይ ሲጎሳቆልና ሲማረር፣ ሲያነባ ዝም ብላችኋልና፤ እንዲሁም የራሳችሁን በቢራ በመራጨት፣ በዘፈኑና በዳንኪራዉ በመመላለስ፣ « ማን ይነካኛል » ብሎ በመታበይ ሕይወት ዉስጥ እየተመላለሳችሁ በመሆኑና ተንኮላችሁና ጭከናችሁ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ በላይ ሆኖ ስለተገኘ፤ ከእናንተ በላይ ተንኮለኛና ጨካኝ እንደሚታዘዝባችሁ እገምታለሁ:: ዞሮ ዞሮ በሥጋ ብትለዩኝ እንኳ የኔን የጨለማ መንግስት በነፍሳችሁ እንደማታጡና በዚያም አሁን ያለዉ ሹመታችሁ እንደሚጠብቃችሁ አሳዉቃችኋለሁ:: በዚህም እንድትጽናኑና እስከመጨረሻዉ ድረስ እንድትታመኑልኝ እመክራችኋለሁ::» **ይላል በተለያየ ስልት የአዳምን ዘር እያሰቃየ ያለዉ አላጋጩ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ::»**

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት እግዚአብሔር እንድናዉቀዉ ያደረገዉ በዲያብሎስ ሥርዓት ዉስጥ በተለያየ የኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች ዉስጣቸዉ ምን እንደሆነና አሁን በተለየ ሁኔታ እየተተገበረ ያለዉ ለመለስ የሚፈጸወመዉ የተለያየ አምልኮና ማግነን እንዲሁም ምስጋና ዲያብሎስ ለዉድ ባለሟሎቹና ለዉድ ካድሬዎቹ ያዘዘዉና ያሳሰበዉ ነዉ::

ጠያቂዉ አገልጋይ: ሌላዉ የምጠይቀዉ የሕዳሴዉ ግድብ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስና እንዲሁም ሥርዓቱ እስከሚያበቃ ድረስ « አባይን የደፈረ፣ የሕዳሴዉ መሐንዲስ፣ ድህነትን ያጠፋ፣ ጀግና መለስ... ወዘተ» እየተባለ ነጋ ጠባ ይለፈፋል:: እንዲሁም እያንዳንዱ ሰራተኛ የአንድ ወር ደሞዙን እንዲያወጣ ተደርጓል:: አሁንም እየተደረገ ነዉ:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምንድነዉ?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ: እዚህ ላይ ሁላችንም ማወቅ ያለብን ለእናት አገራችን ኢትዮጵያ ዕድገት፣ ብልጽግና፣ ክብር፣ እንዲሁም ሕዝቡ ከችግርና ከጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ለሚለይበት ተግባር በቅንነት፣ በእዉነት፣ በትጋት፣ በመስዋዕትነት ልንቆምና የሚጠበቅብንን ሁሉ ልናደርግ ይገባል:: ያ ሲሆን ነዉ ራሳችንን ልንችልና ለሌላዉም ልንተርፍ የምንችለዉ:: ታዲያ ተግባራችን ሁሉ «ልናደርግ የሚገባንን ነዉ ያደረግነዉ፤ ሌላዉም ሊያደርግ የሚገባዉን ማድረግ ይገዋል» በሚል ስሜት መሆን አለበት እንጂ፤ አሁን እንደሚታየዉ ለፖለቲካ ዓላማና የራስን ስዉር ተግባር ለመፈጸም፣ ሕዝብን ለማስጨነቅና ለማማረር እንዲሁም «በሕዳሴዉ ግድብ ላይ ያልተሳተፈ፣ ገንዘብ ያላወጣ፣ ፀረ ልማት ነዉ፤ አሸባሪ ሁከት ፈጣሪ ነዉ፤ ኢትዮጵያዊ አይደለም... ወዘተ» በማለት የሕዝቡን ነጻነትና ኢትዮጵያዊነት በመግፈፍ አይደለም::

በግልጽ እንደሚታወቀዉና አቶ መለስ እንዳሉት፤ «ይህን ግድብ እንኳን ወደ ሥልጣን ወንበር ስንመጣ አይደለም የዛሬ አስርና አምስት ዓመት እንኳ በሐሳባችን ዉስጥ የለም ነዉ» ያሉት፤ ይህም የሚያሳየን ቀደም ሲል በሐሳባቸዉ ዉስጥ ስለ አባይ መገደብ አንድም ነገር እንደሌለ ነዉ:: አንድ ግንባታ ሊሰራ በሚችልበት ወቅት የሚታሰብና በደትግበራ የሚሄድ ነዉ እንጂ አንድ ግለሰብ ወይንም ቡድን የተለየ ሆኖ የሚፈጥረዉና እንደልዩ ሰዉ ተደርጎ የሚገነበት፣ የሚመለክበት ምክንያት እንደሌለ ነዉ:: አሁን የሚታየዉ ግን ለፓለቲካ ፍጆታ ስለሆነ ፓለቲካዉን የሚቃወሙ ሆነ የሥርዓቱ ደጋፊ ያልሆነዉን ሰዉ ለመለያየት፣ እንዲሁም በሕዳሴዉ ግድብ ሽፋን ሕዝቡን ከጎናቸዉ አስልፈዉ ወርቃማ ቃላቶችንንና ንግግሮችን በመጠቀም ለዓመፃ ተግባራቸዉ ለማሰለፍ ነዉ:: ሌላዉ አዛዛኙ ተግባራቸዉ ድግሞ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በፍላጎቱ ለግንባታዉ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ሲገባዉ፤ በየመስሪያ ቤቱ፣ በየድርጅቱ፣ ባጠቃላይ በሁሉም ተቋማት ዉስጥ በጥቂት ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ቅስቀሳና ንግግር «ሰራተኛዉ የአንድ ወር ደሞዙን ለሕዳሴዉ ግድብ ለግሷል» በማለት ካለአቅሙ እያንዳንዱ ሰራተኛ የአንድ ወር ደሞዙን ወስደዉበታል:: ይህን ደግሞ ዓለም ያዉቀዋል:: እጅግ ብዙ ሰራተኛ በወር ደሞዙ ቤተሰቡን ማስተዳደርና ልጆቹን ማሳደግ፣ ማስተማር አቅቶት በችግርና በሰቆቃ ዉስጥ ነዉ:: ባለ ጊዜ የሆኑት ሦስቴ ይደለም አሥሬ በቀን መብላትና ልጆቻቸዉንም በዉጭ አገር ማስተማር የሚችሉ ሰዎች «አንተ ሙት፣ ልጆችህም ይቸገሩ፣ በመከራ ሕይወት ዉስጥ ተመላለስ፣ እኛ ግን ለስማችን መጠሪያና :- እንዲህ ሰሩ እንድንባል፣ እንዲሁም :-ሕዝቡ የሥርዓቱ ደጋፊና አባል ነዉ፣ ይህም ማስረጃዉ :-ሁሉም ሰዉ ለሕዳሴዉ ግድብ የአንድ ወር ደሞዙን ለግሷል እያልን ለዓለም እንድንገልጽ» በማለት በጭከናና መሰሪነት አስተሳሰብ ሕዝቡን ያማርሩታል:: ለመኖር አቅቶት እየተንገዳገድ በመዉደቅ ላይ እያለ፣ እንደ ሥርዓቱ አባልና ደጋፊ እጅና ጓንት ሆነዉ እንደሚሰሩት እጅግ እጅግ ጥቂት ሰዎች በኮብራና በሮቅ እንደሚንፋለሉት፣ ጮማ እንደሚቆርጡት፣ በቢራና በዉስኪ እንደሚራጩት፣ በዳንኪና በዘፈን እንደሚዝናኑት ሰዎች በመቁጠር፤ እጅግ እጅግ ብዙን ሕዝብ በተለያየ ተጽህኖ አስጨንቀዉት ይገኛል::

አንድ የራሴን ምሳሌ ባቀርብ እኔ በወር ከ5000 እስከ 8000 ሺህ ብር የተጣረ ክፍያ አገኛለሁ:: ነገር ግን ቤተሰቤን አስተዳድሬ፣ ልጆቼን አስተምሬ፣ በወር ዉስጥ አምስት መቶ ብር መቆጠብ አልቻልኩም:: የቤት ኪራይና የትራንስፓርት ወጭ ቢኖብኝ ደግሞ እኔም ለመኖር እቸገራለሁ ማለት ነዉ:: ምክንያቱም የኑሮ ዉድነትና የዋጋ ግሽበቱ ብሩን ዋጋ አሳጥቶታልና:: እኔ እንኳ የአንድ ወር ደሞዜን ባወጣ አኗኗሬን በመቀነስ በማገኘዉ ልኖር እችላለሁ:: ነገር ግን በአሁን ሰዓት አንድና ሁለት

ሺህ ብር እንዲሁም በመቶ ቤት የሚከፈለዉ ሰራተኛ በምን መልኩ ነዉ ከቤተሰብ ቀለብ፣ ከልጆች ማስተማር፣ ከቤት ኪራይ፣ እንዲሁም ወሳኝ ከሆኑ የተለያዩ ወጭዎች አትርፎ ለሕዳሴዉ ግድብ ሊያወጣ የሚችለዉ? ያ ብቻ አይደለም መኖር አቅቶት በእየተሳቀቀና የተለያየ ብድር ዉስጥ እየገባ «የአንድ ወር ደሞዙን ለገሰ» ተብሎ ስለምን ይሆን ካለአቅሙ እላይ ባሉ አካላት የሚወሰንበት? ይህም በሰራተኛዉ ላይ ያላቸዉን ንቀትና ጭካኔ ነዉ የሚያሳየዉ።

በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ዕድገትና ብልጽግና በማሰብ አቅሙ ኖሯቸዉ ሆነ ካለምንም ተጽህኖ ወጭያቸዉን ገድበዉ በራሳቸዉ ነጻ ፈቃድ ለሕዳሴዉ ግድብ አስተዋጽኦ ያደረጉትንና እያደረጉ ያሉትን እንዲሁም በግንባታ ላይ የተሰማሩ ከላይ እስከ ታች ያሉ ሰዎችን፤ «ገንዘባችሁንና ጉልበታችሁን እግዚአብሔር ይባርክላችሁ፤ ጤናና የንስሐ እድሜ ይስጣችሁ» በማለት እንመርቃቸዋን። ለፖለቲካ ዓላማ የሚጠቀሙበት እነ ሆዱና ሥልጣኑ አምላኩ የሆኑ ሰዎች ደግሞ፤ እያሰራችሁት ያላችሁት በእዉነተኛ ሕሊና ለአገር ግንባታና ዕድገት እንዲሁም ብልጽግና ስላልሆነ ከዓመፃ ተግባራችሁ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሳችሁና ለሕዝቡም ካለዘናችሁ በስተቀር ለፍሬዉ አትበቁም እንላቸዋለን።» **በማለት የድሆችና የችግረኞችም አምላክ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ክፍል ዘጠኝ

## ምዕራፍ አንድ

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: በቅርቡ ከዚህች ምድር በሥጋ ሞት በተለዩት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት በአቶ መለስ ዜናዊ ሞት ምን ተሰማዎ? ምንስ ታዘቡ?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ***: በመጀመሪያ በእግዚአብሔር እዉነታና በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ስለ ሞት የምለዉ አለ:: በአሕዛብ ወይንም በአረማዉያን ወይንም «እግዚአብሔር የለም፤ ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ነን፤ እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ ሕይወታችን በዚህ ይደመደማል» በሚሉ ከሃድያንና ዓማፅያን ዘንድ ሞት እጅግ አስፈሪና አስጨናቂ የማይፈለግ ነዉ:: ለዚህም ነዉ ከወገናቸዉ ወይንም ከቤተሰባቸዉ ወይንም ከሚያዉቁት ሰዉ አንዱ ሲሞት ጠጉራቸዉን የሚነጩትና ፊታቸዉን የሚያበላሹት:: እንዲሁም ጨለማ ጥቁር ልብስ ለብሰዉ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉት:: ከዚህ በተጨማሪ እድሜያቸዉን ሁሉ ስለግለሰቡ በማዘን፣ ተስፋ ቢስ ሆነዉ የሚኖሩት:: ምክንያቱም በትንሣኤ ስለማያምኑና የሕይወታቸዉ ፍጻሜ አድረገዉ ስለሚያምኑ ነዉ::

እኛ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት የምናምን ግን ሞት ከዚህ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ፣ እንዲሁም ጎስቋላ ሕይወትና ኑሮ ከሚፈራረቅብን የመከራና የፈተና ዓለም የምንገላገልበትና አንዳች ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ ሆነ ጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ወደ ማይከሰትበት ቦታ እንዲሁም በእዉነተኛ ደስታና ቅድስና ሕይወት ወደምንኖርበት ገነት ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ወደ ሰማያት(መንግሥተ ሰማያት) የምንገባበት፣ ከዚህች ምድር የምንገላገልበት ልዩ የእግዚአብሔር መሳሪያ ነዉ:: በዚህም ምክንያት አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉና እንደ እግዚብሔር ፈቃድ የሚመላለሱ ሰዎች፤ ነፍሳቸዉ በምድር ከተገለጸችበት ሥጋ የምትለይበትን የእረፍት ጊዜ በዘልማድ «ሞት» የሚባለዉን በናፍቆትና በጉጉት ይጠብቁታል እንጂ አንዳች ፍራቻ ሆነ ጭንቀት የለባቸዉም::

ትንሣኤን በትክክል በእምነት የሚያምኑ አማኞች ከምድር በሕይወተ ሥጋ የሚለያቸዉ ቤተሰባቸዉ ሆነ ወገናቸዉ ወይንም የሚያዉቁት ሰዉ ነፍስ ከሥጋዉ ተለይታ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ስፍራ ስትሄድ የሚያዝኑትና የሚያለቅሱት፤ «የሕይወቱ ፍጻሜ ተደመደመ፣ ሞተ» ብለዉ ሳይሆን «ከእኛ በሥጋ ተለየን፣ አጎደለብን» በማለት ነዉ እንጂ፤ እንደ አረማዉያኑና እግዚአብሔር የለም ሥርዓት አራማጆች «የሕይወቱ ፍጻሜ ሆነ» በማለት አይደለም:: ኀዘናቸዉ ሆነ ለቅሷቸዉ ገደብና ሥርዓት ያለዉ ነዉ:: እንደ አረማዉያን ደረታቸዉን አይደቁም፣ ጠጉራጨዉን አይነጩም፣ ፊታቸዉንም አያበላሹም:: አለባበሳቸዉም፣ የብርሃን ጸጋ ተጎናጽፋ ወደ ፈጣሪዋና እርሱ ወዳዘጋጀላት መኖሪያ ቦታ እንደሄደችዉ ነፍስ፤ ነጭ ልብስ ለብሰዉ ነዉ በአካለ ሥጋ የተለያቸዉን ሰዉ የሚሸኙት እንጂ ወደ ጨለማዉ ቦታ ጨለማ አካል ለብሳ ወደ ሲኦል እንደተጓዘችዉ ነፍስ ጨለማ ጥቁር ልብስ ለብሰዉ አይደለም::

ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ከመግባቴ በፊት በቅድሚያ ለማሳወቅ የምፈልገዉ፤ በኢትዮጵያዊ ባህል ማንንም ሰዉ እንደ ስራ ድርሻዉና እንደ እድሜዉ ታላቅነት አንቱ የምል ሲሆን፤ እንደ ቀረቤታዬና ግንኙነቴ አንተ አንቺ የምላቸዉ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፤ እግዚአብሔር የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉን የመሰከረባቸዉንና የሚመሰክርባቸዉን በንቀትና በጥላቻ ሳይሆን፤ እንደ ዓመፀኛነታቸዉ በአንተታ ልጠራቸዉ እንደምችል አስቀድሜ አሳዉቃለሁ።

ሌላዉ  እያንዳንዱ እንደ ግለሰብ የራሱ የተወሰነና የተገደበ ቀናነት፣ መልካምነት ሊኖረዉ ይችላል። ይህ በተወሰነ ደረጃ ለግል ሕይወቱ ሊጠቅመዉ ይችላል። በእግዚብሔር ወንበር ላይ ሲቀመጡ ደግሞ በዲያብሎስ መንፈስ እየተመሩ ለግፍ፣ ለአድሎ፣ ለበቀል ከተሰለፉ ያ ቅን፣ መልካም፣ ደግ፣ የሚመስለዉ አቋምና ጠባይ ለማስመሰልና ተቀባይነት ሆነ ተወዳጅነት ለማግኘት የተደረገ መሆኑን ነዉ የሚመሰክርባቸዉ። ወዳለፉት ሁለት መሪዎች ስንመጣ ኮሎኔል መንግሥቱ ሆኑ አቶ መለስ ወደ ሥልጣን ወንበር ላይ ከመምጣታቸዉ በፊት ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለመልካም አስተዳደር፣ የተገፉትንና የተበደሉትን ለመታደግ፣ ፍትሐዊ ፍረድ እንዲኖርና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር የሚፈልጉ፣ በሚያያቸዉና በሚያነቧቸዉ አንዳንድ የግፍና አድሎ ተግባር የሚቢገነገኑ፣ ይህን ዓይነት ሥርዓት እንዲወገድ የሚፈልጉና ለዚያም ዓላማ በሥጋና ደም አስተሳሰባቸዉ ቆርጠዉ መነሳታቸዉን መገመት አይከብድም። በዘመናቸዉም እንደ አቅማቸዉ መጠኑ ቢለያይም ለዚህች አገር ለሥጋዊ ኑሮ የሚጠቅም የተለያዩ የልማት ስራዎች በመሪነት አከናዉነዋል። በተወሰነ ደረጃ የሕዝቡ ኑሮ የሚሻሻልበትን መንገድ ፈጥረዋል። በተቃራኒዉ ደግሞ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እጅግ ዓመፃ ፈጽመዋል፤አስፈጽመዋል።

ይህን የዉስጣቸዉን ፍላጎትና ዓላማ ለማሳካት የሄዱበት መንገድና የወሰዱት አቋም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ እንጂ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድና መሪነት ስላልሆነ፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ በሆነ ሕይወትና ተግባር ተሰልፈዉ ነበር። በዚህም ምክንያት ሕሊናቸዉ(ነፍሳቸዉ) በእግዚአብሔር ቃል፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በእዉነተኛ ንስሐ፣ በእዉነተኛ አምልኮ ስላልተመራች በትዕቢትና በዓመፃ ሕይወት ዉስጥ ፈቃዳቸዉን ለመፈጸም በመነሳታቸዉ ምክንያት ርኩሳን መናፍስት(ዲያብሎስ) እነዚህን በዓመፃና በትዕቢት ሕይወት ያሉትን ለእሱ የሚመቹ እንደ ልባቸዉ የሚሆኑለት ሆኖ በማግኘቱ፤ ለአስራ ሰባትና ለሃያ ዓመታት በበላይ እየተቆጣጠሯቸዉና እያሳሰቧቸዉ የተለያየ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ሲፈጽሙ ሲያስፈጽሙ ነበር።

እኔ በግሌ በሁለቱም ግለሰቦች(መሪዎች) አንዳች በደል ሆነ አድሎ፣ ግፍ እንዲሁም የተለያየ ተጽህኖ አልደረሰብኝም። በእነሱ ላይም አንዳች ጥላቻ ሆነ በቀል የለኝም። እነሱን ግን የምቃወመዉና የዓመፃ ስራቸዉን የምመሰክረዉ በእግዚአብሔር እዉነትና በቅዱሱ ኪዳን ላይ በፈጸሙት የዓመፃ፣ የክህደት፣ እንዲሁም የአምልኮ ምንዝርና ተግባራቸዉ ነዉ። ለምሳሌ የዓመፃ ተግባራቸዉ ሁለቱም በአብዮተኛነት ተሰልፈዉ እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት ሶሻሊስትና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥርዓት ዘርግተዉ በእምነት ላይ ግልጽ ዓመፃና ክህደት ስለፈጸሙና ስላስፈጸሙ ነዉ። እንዲሁም ሕዝቡ በተለያየ መልኩ ለግድያ፣ ለእስራት፣ ለስደት ስለተዳረገና በደጎንነቶች አማካይነት የሕዝቡ ነጻነት

ስለተገፈፈ ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ በአቶ መለስ ዘመን በባህል ሽፋን ርኩሰት የሆነዉ ባዕድና ጣዖት አምልኮ በየአደባባዩና በየወንዛወንዙ በግልጽ እንዲፈጸም በመደረጉና ሃይማኖት የሆነዉን ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋትና እንዲሁም የሰንደቅ ዓላማን ፍቅር ለመቀነስ በሂደትም ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት፤ ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፍለዉና የተለያዩ «ሰንደቅ ዓላማዎችን» ፈጥረዉ የኢትዮጵያን የብዙ ሺህ ዓመት ታሪክ አጥፍተዉና ደምስሰዉ ሻዕቢያ ከተባለ ቡድን ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ ሕዝቡን በተለያየ መልክ ስለተበቀሉና የራሳቸዉን መሰሪና በቀል ተግባር ስለፈጸሙ ነዉ::

በግሌ በደርግ(ኢሠፓ) ጊዜ ተምሬ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም በቅቼ፤ በሕወሓት(ኢሕአዴግ) ዘመን ደግሞ ትምህርቴን ጨርሼ ወደተለያየ ስራ ገበታ ተሰማርቼ፣ ከዚያም የትምህርት ደረጃዬን አሻሽዬ፣ ትዳር መስርቼ፣ የልጆች አባት ሆኜ፣ የመንግሥት አድሏዊና ጭከና ፓሊሲ ቢኖርም በእግዚአብሔር የቸርነት ስራ በድካም፣ በእርዳታ፣ በብድር፣ በአቋራጭ መንገድ፣ በዓመፃ ገንዘብ ለሰዉ ያላለቀና ጅምር ተራ ቤት ቢመስለዉም ለእኛ ግን ከበቂያችን በላይ የሆነ ማረፊያ ቤት ሰርቼ፣ በጥሩ ስራና ደሞዝ እየሰራዉ እገኛለሁ::

እዚህ ላይ ለመግለጽ የምፈልገዉ የተወሰኑ አንድ እጅ (ፐርሰንት) የማይሞሉ ራስ ወዳዶችና ስግብግቦች እንዲፈጠሩና እጅግ እጅግ ብዙዉ ሕዝብ በችግርና በድህነት አረንቋ ዉስጥ እንዲኖሩ በተፈረደበት የጭከና ዘመን ዉስጥ፤ በንጹህ ላባቸዉና ድካማቸዉ መኖሪያ ቤትና መንቀሳቀሻ መኪና ያላቸዉ ሰዎች ካሉ የሚደንቅና እንደ ተአምር ሊታይ የሚችል ነዉ:: ምክንያቱም የኑሮዉ ወድነት እንኳን ገንዘብ ከቀለብ፣ ልጅን ከማሳደግና ከማስተማር አልፎ ተቀማጭ ገንዘብ ሊኖርና ለቤት መስሪያና ለመኪና መግዣ ለማትረፍ ቀርቶ በአግባቡ ለመኖር በሚያስቸግርበት የስግብግቦችና የራስ ወዳዶች እንዲሁም የአስመሳይና የጨቃኝ ገገርዎች ዘመን ነዉና::

ሌላዉ መንግሥት መስራት ያለበትን በመስራቱና እኔም ማድረግ ያለብኝን በማድረጌ መንግሥትን ሆነ ራሴን እንዲሁም ሌሎች አካላትን አንዳች አላገንም፤ አላስመልክም፤ አላመልክም:: እንዲሁም በእግዚአብሔር ቦታና ወንበር ላይ ሆነዉ መመስገን ከፈለጉ ደግሞ አላመሰግናቸዉም:: ነገር ግን ስለ ሰሩት መልካም ስራ እግዚአብሔር ይስጣችሁ፤ በሕይወት ያሉትም እግዚአብሔር ከትዕቢትና ከእብሪት እንዲሁም ከዓመፃ ሕይወት ለይቷቸዉ ለንስሐ ያብቃችዉ፤ በሥጋ የተለዩትንም እግዚአብሔር በምሕረት ይጎብኛችዉ ከማለት ዉጭ፤ የማመሰግነዉ፣ የማገነዉ፣ እንዲሁም የማመልከዉ ሁሉን ማድረግ የሚችዉን እግዚአብሔርን ነዉ::

ከዚህ በተጨማሪ «እንዲህ ተደርጎልኛል፣ ዉለታ አለብኝ» ብዬ የእግዚአብሔርን እዉነት አልደብቅም:: ማንም ይሁን ማን በቅዱሱ ኪዳን ላይ የፈጸመዉን ዓመፃ ከመግለጽ ወደ ኋላ አልልም:: ስለ እያንዳንዱ የግል ሕይወት እያንዳንዱ ይጠየቅበታል እንጂ ስለ ግል ሕይወታቸዉ የእነሱን ሆነ የሌላዉን እንዲህ የምለዉ ነገር የለም:: ቢበዛ ስለ ኃጠአት ተግባራችን፣ ንግግራችን፣ እንዲሁም ሐሳባችን ጭምር ንስሐ እንግባ፤ በእዉነተኛ ሕይወት ወደ ቅዱስ ቁርባን እንቅረብ ከማለት በስተቀር:: በተለያዩ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተፈጸመ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ግን

የመግለጽና ትዉልዱም ከዓመፃ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት ተግባር እንዲለይና አንዳች ከዓመፃ ልጆች ጋር በዓመፃቸዉ አንድነትና ኅብረት እንዳይፈጥር የመመስከር ግዴታ ስላለብኝ፤ እንደ ጥሪዬ እስከ ምድራዊ ሕይወት ዘመኔ መጨረሻ ድረስ ስለ እዉነት ከመመስከርና የዓመፃን ስራ ከማጋለጥ ወደ ኋላ አልልም።

**ወደ ጥያቄዉ መልስ ስመጣ** የጠቅላይ ሚኒስትሩ በጠና መታመምና ሞት ባለሥልጣኖቻቸዉ ከደበቁ በኋላ ነሐሴ፲፭፥፳፻፬ (15/2004) ዓ.ም መሞታቸዉ በግልጽ ተነገረ። ምናልባት በእሳቸዉ ዘመን በደል፣ ግፍ፣ አድሎ የተፈጸመበትና እጅግ ያዘነባቸዉ ሰዉ ካልሆነ በስተቀር፤ አንድ ሰዉ «ሞተ» ሲባል የሚደሰት ሰዉ ያለ አይመስለኝም። እኔም በመጀመሪያ እንደ ማንኛዉም ሰዉ፣ ሰዉ ከዚህች ምድር በሥጋ ሲለይ  እንደሚታዘነዉ አዝኛለሁ፤ ነገር ግን የማን እንደራሴ ሆነዉ ሲያገለግሉ እንደነበረ እግዚአብሔር ስላሳወቀኝ እንባዬ ሊመጣ አልቻለም። ትልቁ ያዘንኩት በተለያየ ጊዜ እግዚአብሔር መንገዳቸዉን እንዲያስተካክሉ፣ ሕይወታችዉንም በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመሩ በአገልጋዮቹና በእንደራሴዎቹ እንዲሁም በመልእክተኞቹ አማካይነት ቢገለጽላቸዉም፤ ፈቃደኛ ሆነዉ ሳይገኙ በመቅረት ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ ከዓመፃ፣ ከክህደተ፣ ከርኩሰት ሕይወታቸዉ ጋር ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ በመሄዳቸዉ ነዉ። ምክንያቱም ዳግም የንስሐ እድል አይሰጣቸዉምና። እንደ አገር መሪነታቸዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽመዉና አስፈጽመዉ መገኘት ሲጠበቅባቸዉ እንደ ሌሎቹ አገራት መሪዎች ለሰዎች ነፍስ ደኅንነት አንዳች ጥቅም የማይሰጠዉን፣ ሰዎች ከምድራዊ ጉስቁልና ሕይወት ብቻ የሚገላገሉበትና ኑሮ እንዲቀልላቸዉ የሚያደርገዉን ተግባር ብቻ ነዉ ፈጽመዉ የሄዱት። እርሱንም ቢሆን እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ አድሎና በደል እንዲሁም በቀልና ጭከና በተደባለቀበት ሕይወት ዉስጥ በመሆን ነዉ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የነበሩት።

ኢትዮጵያዉያንን ሙሉ በሙሉ በነፍሳቸዉ እንዲያምጹና በዳንኪራና በዘፈን እንዲያብዱ አድርገዉ ነዉ ያለፉት። ከዚህ በተጨማሪ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እጅግ ዓመፃ ፈጽመዉና አስፈጽመዉ ነዉ ወደ ማይቀርበት ቦታ የሄዱት። ለዚህም ነዉ የከፋዉ የእግዚአብሔር ቅጣት ስለሚጠብቃቸዉ የንስሐ እድል በተለያየ ጊዜ ተሰቷቸዉ፤ ራሳቸዉ ለራሳቸዉ እድሜ እየሰጡ በምድር የሚቆዩ መስሏቸዉ «የንስሐ እድሉን አልጠቀምም» በማለትና ራሳቸዉንም በማስታበይ በንስሐ ሳይታጠቡ፣ በእግዚአብሔር እጅ ከተያዙም በኋላ ከሕዝቡ ጋር ሳይገናኙ፣ በሕመም ስቃይ ዉስጥ ሆነዉ ሞታቸዉን እየተመኙ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ በመሄዳቸዉ ነዉ እጅግ የሚሳዝነዉ እንጂ፤ ከዚህች ምድርማ ሁላችንም በተለያየ መንገድ በሥጋ ሞት ተጠርተን ወደ ሁለተኛዉ መኖሪያ ወይንም መቀጫ ቦታ መሄዳችን አይቀርም።

እኔ እንኳ የማዉቀዉና ያነበብኩት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አገልጋይነትና ጠባቂነት የእግዚአብሔር እንደራሴ «ሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁት ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) በሰኔ፲፱፥፳፻ (19/10/2000) ዓ.ም፣ በሚያዚያ፲፱፥፳፻፩ (19/08/2001) ዓ.ም፣በየካቲት፩፥፳፻፪ (01/06/2002) ዓ.ም የእግዚአብሔር መልእክት የሆነዉ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ የተጻዉንና ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ በደብዳቤ በግልጽ አሳዉቀዋቸዋል። እንዲሁም ወንበሩንም

ለእግዚአብሔር አገልጋዮች በክብር እንዲያስረክቡ የጊዜ ገደብ ሰተዋቸዉም ነበር፡፡ ነገር ግን ለመስማት ሆነ ትእዛዙን ለመፈጸም ቀርቶ ለማነጋገር ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡

እንዲሁም በእኔ በኩል በየካቲት፳፯÷፳፻፬ (27/6/2004) ዓ.ም በግልጽ በእግዚአብሔር ቁጣ እሳቸዉም ሆኑ የዓለም መንግሥታት በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ ከመቆረጣቸዉ በፊት ወንበሩን እግዚአብሔር ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ለእንደራሴዎቹ እንዲያስረክቡና የእግዚአብሔርንም መልእክት ለዓለም መንግሥታት ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ እንዲያቀርቡ የእግዚአብሔር መልእክታት ጭምር አባሪ ተደርጎላቸዉ በ-እጦማር (በኢሜል አድራሻ) ተልኮላቸዉ ነበር፡፡ ይህን መልእክት ከነአባሪዉ የተለያዩ የመንግሥት ሆነ የግል መገናኛ ብዙሃን(ማስ ሚዲያ)፣ የተለያዩ ቡድኖችና ድርጅቶች፣ እንዲሁም ብዙ ግለሰቦች በግልባጭ እንዲደርሳቸዉ በ-ኢሜል አድራቸዉ ተልኮላቸዉ ነበር፡፡ ነገር ግን እሳቸዉም ሆኑ ሌሎች ከቁም ነገር አልቆጠሩትም፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነዉ አልተገኙም፡፡ እያንዳንዱ ዋጋ ለመክፈል ሕሊናዉን አደንድኖ ጊዜዉን እየጠበቀ ያለ ይመስላል፡፡ አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ በድጋሜ «እባካችሁ ለዓለማዊ ትምህርት ለሥጋችሁ ብቻ የሚጠቅመዉን ብዙ ዓመታት ጊዜያችሁን ሰዉታችሁ እንደምትማሩና እንደምታጠኑ ሁሉ፤ ለሕያዉ ነፍሳችሁ ሆነ ለሥጋችሁ የሚጠቅመዉን የእግዚአብሔር መልእክታትና ቃሎች የተወሰነ ጊዜ ሰታችሁ ብታነቡና እግዚአብሔር የሚላችሁን ብትፈጽሙ ምን አለ?» በማለት ለትዉልዱ ማሳሰቢያዬን አቀርባለሁ፡፡

**ወደ መጀመሪያዉ ትዝብቴ ስመጣ** ስለ ጠቅላይ ሚንስትሩ ሞት ቤተሰቦቻቸዉና የትግልና የስራ አጋሮቻቸዉ በተለየ ሁኔታ ቢያዝኑ አንዳች አይስገርምም፡፡ ምክንያቱም ቤተሰብና እንዲሁም ዓላማቸዉ ምንም ይሁን ምን ያንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አብረዉ ተሰልፈዋልና፤ በድንገት በሥጋ ሞት ሲለያቸዉ ያስደነግጣል፤ ያሳዝናል፡፡ እንዲሁም በሥርዓቱ የተለየ ጥቅምና ሥልጣን፣ ክብር ያገኙ ሰዎች ተስፋቸዉ እርሱን አድርገዉ ስለሚኖሩ ተስፋ የሚያደርጉት ሰዉ ሲለያቸዉ ተስፋቸዉ የሚጨልም አድርገዉ ስለሚያስቡ ለጥቅማቸዉ ሲሉ ያዝናሉ፡፡ ከዚያ ዉጪ ግን በዚያ አጋጣሚ የተለየ ጥቅም ሆነ ሥልጣን ለማግኘት ሲሉ የማስመሰል ኀዘን የሚያሳዩም ነበሩ፡፡ እኔ ያስገረመኝ ግን በአስራና በመቶ ቤት ብር ደሞዝ ራሱን ሆነ ቤተሰቡን በሚገባ ያስተዳድር የነበረ ሰዉ መኖር አቅቶት ለልመና እየተዳረገና የመከራና ስቃይ ኑሮ እየኖረ፣ እንዲሁም በአስራና በመቶ ቤት ብር ስንዴና ጤፍ ይገዛና እንደልቡ ሳይሰቀቅ ይኖር የነበረዉ ሕዝብ፣ በሺህ ቤት እየገዛና መግዛት ያልቻለዉም ያገኘዉን እየበላ መኖሩ እየታወቀ፤ እንዲሁም ስንት ሰዎች «ሕሊናችንን አንሸጥም፣ እንደ ቦይ ዉኃ አንነዳም፣ ያመንበትን ነዉ የምንናገረዉ፣ የምንጽፈዉ፣ የምንሰራዉ» በማለታቸዉ በሐሰት ተወንጅለዉ በእስር እንደሚማቅቁ እየታወቀ፤ ስንት ንጹሀን ዜጎች በተለያየ ጊዜና መንገድ ደማቸዉ በከንቱ እንዲፈስ መደረገ እየታወቀ፤ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ብቻ ራሳቸዉን እንዲያበለጽጉና በደሀ እናት ላይ እንዲረማመዱ እየተደረገ፤ አገርን ያህል ያስገነጠለና ወደብ አልባ ያደረገ መሆኑ እየታወቀ፣ ጠባዩና ሕይወቱ በትዕቢትና በእብሪት እንደተሞላ እየታወቀ፣ የጋጠወጥና የሥርዓት አለብኛ ሰዉ ስድብ የሚሳደብ እንደሆነ እየታወቀ፤ «ድህነትን ያጣፋ መሪ፣ ነጻነትን ያጎናጸፈ መሪ ፣ ኑሮን ያሻሻለ መሪ፣ ቅንና ርኅሩኅ መሪ፣ ትሁትና ታጋሽ መሪ፣ ፍትሐዊ ሀበት ክፍፍል ያደረገ መሪ፣ ፍትሐዊ

የፍርድ ሥርዓት የዘረጋ መሪ፣ ድንበርን ያስጠበቀ መሪ፣ ታላቅ ባለ ራእይና አባት መሪ፣ ታላቅ መሪ፣... ወዘተ» እየተባለ በተለያየ መከራና ችግር ዉስጥ ያሉ ሰዎች ሕሊናቸዉን እንዲሸጡ እየተደረገና አንዳንዶቹም በራሰቸዉ ፈቃድ ሕሊናቸዉን ሸጠዉ በየመድረኩ ይህን የሐሰት ምስክርነት ሲሰጡ መመልከቴ ነዉ::

**ሌላዉ ትዝብቴ ስመጣ** ባልሥጣኖቹ ሆኑ ካድሬዎቻቸዉ፤ ሬሳን(አስከሬንን) ለፖለቲካና ለራሳቸዉ መሰሪ ተግባር ማዋላቸዉ ምን ያህል ሐሳባቸዉና ተግባራቸዉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ የሆነ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚያስቡና እርሱንም ወደ ተግባር የሚለዉጡ አእምሮ ቀላልና አእምሮ ሕፃን መሆናቸዉን መመልከቴ ነዉ:: እንዲሁም ትዕይንቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ምን ያህል አስተሳሰባቸዉ የላሸቀና እንደ ቦይ ዉኃ የሚነዱላቸዉና የሚያመልኳቸዉን ባለሥልጣናትና ካድሬዎች እንዲሁም ደጋፊዎች መመልመላቸዉን ነዉ የሚያሳየዉ:: ለዚህም ማሳያዉ ከዋናዉ ከተማ ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ገበሬ ማኅበር ድረስ በአራቱም ማእዘን ካድሬዎቻቸዉን በማዘዝ ሕዝቡን አደባባይ እያስወጡ ደረታቸዉን እያስደቁ፣ ፎቶ ግራፍ እያስያዙ በግልጽ ሕሊናቸዉን እንዲሸጡ በማድረጋቸዉ ነዉ:: ከዚህም በተጨማሪ የዲያብሎስን መንፈስና ዓርማ እንዲቀበሉ ማድረጋቸዉና ርኩሰትን ማጽፈጸማቸዉ ነዉ::

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ነፍስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይሆን ፍጹም የዲያብሎን ፈቃድ ስትፈጽምና ስታስፈጽም ኖራ ነዉ ባላሰበችዉና ባልጠበቀችዉ ጊዜና መንገድ በእግዚአብሔር ቁጣ የተጠራችዉ:: በምድራዊ ዘመኗ መሪያዋ አታላዬ(ሸዋጁ) መንፈስ ዲያብሎስ በመሆኑ የሳቸዉን ምስል በልብስ ላይ እያደረጉና በሥዕል መልክ እያያዙ፣ እያቆሙ፣ እየለጠፉ እሳቸዉን ማድነቅና ማግነን ከዚያም ባለፈ «ያንተን ፈቃድ እስከመጨረሻ ድረስ አጠናክረን እንሰራለን፤ መንፈስህ አይለየን ከእኛ ጋር ይሁን» ማለት፤ በተዝዋዋሪ «የዲያብሎስ መንፈስ አይለየን» ማለታቸዉ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል:: በመፈክርና በጽሑፍ መግለጽ ሆነ የዲያብሎስን ዓርማ የሆነዉ ኮከቡን ዓለም በተለያየ መልክ እንደተቀበለዉ አሁንም የዲያብሎስን መንፈስ ትዉልዱ በፈቃደኛነት በግልጽ መቀበሉን ድርጊቱ ይመሰክርበታል:: በዚህም ምክንያት የአሁን ዘመን የዲብያብሎስን ዓርማ(666) በተለያየ መልኩ የተቀበሉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቀን በእግዚአብሔር ቁጣ የሚጠረጉ ይሆናሉ ማለት ነዉ:: ምክንያቱም ዲያብሎስ በግልጽ «እኔ ነኝ፣ ይህ የእኔ ዓርማ ነዉ፣ ይህ የእኔን ፈቃድ ሲፈጽምና ሲያስፈጽም የኖረ ነዉ፤...ወዘተ» በማለት ራሱንና አገልጋዩን በእግዚአብሔር መንፈስ ካልታሰረና ካልተቃጠለ በስተቀር አይጋልጥምና::

**የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ የተመለከትኩትና ያመሰገንኩት** ደግሞ: ያ እንኳን ሊገቡበት ቀርቶ በአካባቢዉ ማለፍ ሆነ መቆም የተከለከለዉ፣ እንዲሁም በስህተት ቆሞ የተገኘ ሰዉን አንዳች ስነ ምግባር ሆነ ሰብአዊነት በሌላቸዉ ጨካኝ፣ ጋጠወጥ፣ ሥርዓት አልበኛ፣ ዉስጣቸዉ ጥላቻና በቀል በሞላባቸዉ ጠባቂዎች ማስፈራትና ስድብ እንዲሁም ድብደባ የሚፈጸምበት፤ ሰዎች ሥጋ ለባሽ መሆናቸዉን ረስተዉ ራሳቸዉን እንደ እግዚአብሔር የሚያስመልኩበትና ቦታዉንም እንደተለየ ተደርጎ እንዲቆጠር በማድረግ የሚያስመልኩት ቤተ መንግሥት፤ በደስታ ሳይሆን በቁጣዉ( በኀዘን)

ማንም ሰዉ እንዲገባበት፣ እንዲወጣበት በማስደረጉ ነዉ፡፡ እንዲሁም እነዚያ ራሳቸዉን የተለየ አድረገዉ ይቆጥሩ የነበሩና ከዛም ባለፈ ራሳቸዉን ያመልኩና ያስመልኩ የነበሩ ሰዎች ማንም ሰዉ ሊገባበት የሚችል እንደማንኛዉ ቦታ መሆኑን እንዲያዉቁ በማስደረጉ ነዉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕይወተ ሥጋ እያሉ እሳቸዉ ወደ ቦሌ አየር ማረፊያ ሲሄዱና ሲመጡ ሽብር እንደተፈጠረ መኪኖች ሁሉ አስባልቱን ባስቸኳይ እንዲለቁና ወደተለያየ አቅጣጫ እንዲገቡ ወከባ እንዳልተደረገና፤ ሰዉም ፊቱን አዙሮ እንዲቆምና አንዳች እንቅስቃሴ እንዳያደርግ እንዳልተደረገ ሁሉ፤ ሕይወት(ነፍስ) የተለየዉ በድን(አስከሬን) ግን ከሕፃን እስከ አዋቂዉ፣ ከታላላቅ እስከ ታናናሽ፣ ከባለሥልጣን እስከ ተራ ሰዉ ድረስ እንዲያጅበዉ በመደረጉ፤ ያ ይፈራና ይመለክ የነበረዉ የአንድ ግለሰብ ማንነት እንዲህ መሆኑ ዓለም እንዲያዉቀዉ በመደረጉ የእግዚአብሔርን ስራና ፍርድ አደንቂያለሁ፡፡ አንዳንዴ እግዚአብሔርን፤ «እንኳን እለተ ሞታችንን ያላሳወከን፡፡ ብናዉቅ ኖራማ እምነት የሚባል ነገር ከዓለም ሙሉ በሙሉ ይጠፋ ነበር፡፡ ምክንያቱም በክፋትና በተንኮል እንዲሁም በትዕቢትና በእብሪት ሕይወታችን እስከ ምንሞት አንድ ቀን እስከሚቀረን ድረስ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ስንፈጽም ቆይተን በመጨረሻ ቀን «ማረን፣ ይቅር በለን፣ በድለናል» በማለት አንተን ጭምር ለማታለል እንጥር ነበርና፡፡ እንዲሁም «ሞት የሚባል እንኳን ፈጠርክ፡፡ ምክንያቱም በነጻ ሕሊናችን ተመርተም አንተን ማምለካችንና መፍራታችን በምን ይታወቅ ነበር?» እላለሁ፡፡

ሌላዉ ይህ የአቶ መለስ በሥጋ ሞት መጠራት ኢትዮጵያዉያን አንዳች ሁከት ፈጣሪዎችና አሸባሪዎች አለመሆናቸዉ ለመንግሥትና ለዓለም ሕዝብ የገለጡበትና ያስመሰከሩበት አጋጣሚ እንደፈጠረ አምናለሁ፡፡ ይኸዉም ቀደም ብሎ በግልጽ መሞታቸዉ ሳይነገር ሆነ «ሞተ» ተብሎ ሲነገር ሕዝቡ አንዳች አለመረበሹና ለሁከት ሆነ ለጥል አለመነሳሳቱ ምን ያህል ተስፋዉ በእግዚአብሔር እንጂ በሰዉ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመንግሥት በኩል በደል ሆነ ግፍ እንዲሁም አድሎ የተፈጠረባቸዉ ሰዎች ለሌላ ዓላማ አልተነሱም፡፡ ሁከትና ሽብር ፈጣሪ ኢትዮጵያዊ ቢኖር ኖሮ በአስከሬኑ ላይ ሆነ በባለሥልጣናቱ ላይ እንዲሁም በካድሬና በደጋፊዎቹ ላይ የተለያየ አደጋ ይፈጥር ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳች ነገር በለቅሶዉ ቦታ ሆነ በተለያዩ ለፖለቲካ ፍጆታ በዋሉ የኀዘን ሰልፎችና መድርኮች ላይ አንዳች የተፈጠረ ነገር የለም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ከዚህ በፊት በዋናነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራዉ ራሱ መንግሥት ሊበቀላቸዉ የሚፈልገዉን ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሁም ድርጅቶችን ሆን ብሎ ለመበቀል ራሱ አቀነባብሮ የተለያዩ ቦታዎች ፍንዳታ ሊፈጠሩ እንደተዘጋጁ በማስመሰልና እንዲሁም አንዳንድ ጋዜጠኞችን፣ የተቃዋሚ ፓለቲካ ድርጅት መሪና አባል የሆኑትን ለእስር፣ ለእንግልት፣ ለስደት፣ ለግድያ ለመሳሰሉት የዳረገዉ በሐሰት መረጃና ሆዳቸዉ አምላካቸዉ በሆኑ ዐቃቢ ሕግና ዳኞች ሎሌነት አማካይነት በግፍ ሕጋዊ ሽፋን መሆኑ ይህ የሰሞኑ የኢትዮጵያዉያን ጨዋነት ያስመሰክራል፡፡ ራሱ መንግሥት አንዱን በአንዱ ላይ ለማነሳሳትና ለመከፋፈል የሚፈጥረዉ ሁከትና ሽብር መሆኑን በግልጽ ታዉቃል፡፡ እንዲሁም ለአሜሪካንና ለአዉሮፓ መሳሪያ በመሆን በማገልገል ላይ ያለ መሆኑን አሳብቆበታል፡፡ በዚህም ምክንያት

ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በተለያዩ አገራትና ቡድኖች እንድትጠላና ለበቀልና ለጦርነት እንዲነሳሱባት የሚያደርግ የእብሪትና የትዕቢት ተግባር እንደፈጸሙ ይታወቃል፡፡

**የሚገርመዉ ደግሞ** ሕዝቡ በኑሮ ዉድነት እየተሰቃየና መኖር እያቃተዉ በየመንገዱ፣ በየእምነት ተቋሙ ወድቆ እያለ እንዲሁም አድሎ በደል፣ ግፍ እየተፈጸመበትና ለእስራት፣ ለስደት፣ ለሞት እየተዳረገ፤ ስንቱ በማንነቱ ከእናት አገሩ እየተፈናቀለና «ክልል፣ አገርህ አይደለም» እየተባለ፤ ለተለያየ ስቃይና መከራ ሕይወት እየተዳረገ፤ ከዚህ በፊት ለዘመናት ማንም መሪ ያላደረገዉን ሻዕቢያ ከሚባለዉ የዓመፃ ቡድን መሪ ጋር እጅን ጓንት ሆኖ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት በቋንቋ ሽፋን ዘረኝነትንና ጎጠኝነት፣ ጥላችንና በቀልን ያነገሠና የራሳቸዉን መሰሪ ዓላማ ለመሳካም የዲያብሎስ ቋንቋ የሆነዉም በመጠቀም «ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸዉን እድል በራሳቸዉ የመወሰንና እስከ መገንጠል ድረስ የማወጅ መብት አላቸዉ» በማለት አገር የምትበታተንበትንና የምትገነጣጠልበት መንገድ የከፈተና የጠረገ መሪ መሆኑ እየታወቀ፤ «ታላቁ መሪ፣ የዋህ ደግ ርኅሩኅ ይቅር ባይ የደሀ አባት የሆነ መሪ፣ በመወያየት የሚያምንና ለሕዝቡ እንደ ሻማ ቀልጦ ያበራ፣ ድህነትን ያጠፋ፣ የአፍሪካ መሪና ዕንቁ፣ ለሕዝብ የኖረና የሞተ፣ አገር ወዳድና ድንበር አስከባሪ ፣ አንድነትን ፈጣሪ፣ ታላቅ ሐዋሪያ፣ ታላቅ ባለ ራእይ መሪ፣ ... ወዘተ» እየተባለ የፈጠራና ፍጹም ተቃራኒ ሰብእና መስጠትና ሕዝቡን ለብዙ ቀናት በቴሌቭዥን፣ በሬድዮን፣ እንዲሁም በጽሑፍ፣ በማስታወቂያ፣ በሥዕል፣ በሻማ ማብራት፣ በድጋፍ ሰልፍ፣ በመፈክር ... ማደንዘዙ ተግባር ላይ መሰማራቸዉ፤ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ምን ዓይነት ሰዎች መሆናቻዉን የሚገልጣቸዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን እዉነት ስትገለጥና ባለጊዜ ስትሆን የሐሰት ሰብእና እንደ ጨዉ ክምር የማይሆን መስሏቸዉ ይሆን? ወይስ ሕዝቡ መለስን ካመለከልንና ካገነነልን እግዚአብሔር ገበናችንን አይገልጥም፤ ቁጣዉንም አይመጣብንም ብለዉ ይሆን!? ወይስ በብልጣብልጥነትና ሕሊናን በማሸጥ የሥልጣን እድሜያቸዉን የሚያስረዝሙ መስሏቸዉ ይሆን? ይህ ለአስራ ቀናትና ለወራት አንድ ግለሰብ እንዲገንና እንዲመለክ የተደረገዉና ባለሥልጣናቱ ሆኑ ካድሬዎቹ እንዲሁም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት ደጋፊዎች፣ የሰዉ አምላኪና አግናኝ እንዲሆኑ በራሳቸዉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተፈጠሩ መሆኑን ይኸዉ ፍሬያቸዉ ይመሰክርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ያለዉ እዉነታ ምን እንደሆነ እየታወቀ በተለያየ መድረክ እጅግ ዉሱን የሆኑ ግለሰቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደወከሉ ተቆጥሮ ሕሊና ማሸጫ ንግግር በየመድረኩና በየሚዲያዉ ሲናገሩ ታይቷል፤ ተደምጧል፡፡

እዚህ ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በግለሰቡ የተሰናከላችሁና የተታለላችሁ ሰዎች አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ ይኸዉም ጌታን አሳልፎ የሰጠዉ ይሁዳ በብሉይ ዘመን ካሉት ሆነ በሐዲስ ዘመን ካሉት ሰዎች ይልቅ ተንኮልና ክፋት የሞላበት ሰዉ ነዉ፡፡ እንደማንኛዉም ሰዉ የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ነጻ ሕሊና ያለዉ ሰዉ ቢሆንም ሕሊናዉን ለመልካም ሳይሆን ለጥፋትና ለራሱ መሰሪ ዓላማ ነዉ ያሰለፈዉ፡፡ ለምሳሌ አእምሮዉ አዋቂና ብልጥ መሆኑን ከሚያሳዩን ተግባሮች አንዱን ብጠቅስ በዮሐንስ ወንጌል በምእራፍ 12 ከቁጥር 3እስከ6 ላይ«ማርያምም ዋጋዉ እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶዶ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ፡፡ ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠዉ ያለዉ የስምዖን ልጅ የአስቆርቱ ይሁዳ፡-

ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነዉ?አለ፡፡ ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነዉ እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸዉ አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በዉስጡ ከሚገባዉ ይወስድ ስለ ነበረ ነዉ፡፡»

ይህ የሚያሳን ከሽያጭ ከሚገኘዉ ገንዘብ ለራሱ ሊሰርቅ አስቦ የተጠቀመበት ንግግርና ያቀረበዉ ሐሳብ ግን ለድሆች ተቆርቋሪ በመምሰል፣ እግዚአብሔርም ሰዉም ሊቀበለዉና ሊደግፈዉ የሚችል መልካም ሐሳብ ነበር፡፡ በቅንነት ሲታይ መልካም ያሰበ የሚመስል፤ በእዉነት ሲመረመር ደግሞ የራሱን የስርቆት ዓለማ ለማሳካት የተጠቀመበት ልዩ የጥበብ ንግግር ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት የዉጭን ንግግር ሳይሆን የዉስጥን ሐሳብ የሚያዉቀዉ አምላክ አጠገባቸዉ ነበርና ሐሳቡን አልተቀበለዉም፡፡ ይልቁኑ የተደረገዉ ትክክለኛ ስራ እንደሆነ ነዉ አሳፍሮ የመለሰዉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምድቡ ከሰይጣናት ብቻ ሳይሆን የሰይጣነት መሪ ከሆነዉ ዲያብሎስ ጋር መሆኑን በዮሐ. ወንጌል ምዕራፍ 6፡ ቁርጥ 70 ላይ «፡- እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነዉ ብሎ መለሰላቸዉ፡፡» ይላል፡፡ ይህም የሚያሳየን እኛ የአሁን ትዉልዶች ብንሆን ኖሮ የሰዉን የዉስጥ ሐሳብና ዓላማ ስለማናዉቅ እንደ ይሁዳ መልካም ሐሳብ እያቀረበ የራሱን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚመላለሰዉን ሰዉ የምናደንቅና የምናገን ነበር የምንሆነዉ እንጂ ዋና የዲያብሎስ አገልጋይና እንደራሴ መሆኑን አናስተዉልም፤ አናዉቅም ነበር፡፡

እኛ ሰዎች ግን በአንደበቱ የሚሸነግለንን ሰዉ እናምናለን፤ ለራሱ መሰሪ ዓላማና ተግባር ሲያስልፈን እያደነቅነዉ እንደ ቦይ ዉኃ ወደፈለገዉ አቅጣጫ እንኄድለታለን፡፡ በመጨረሻም የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ፈጻሚና አስፈጻሚ እንሆናለን፡፡ ራሳችንን ለመከራ ሥጋና ለመከራ ነፍስ አሳልፈን እንሰጣለን፡፡ ለዚህ ለዓመፃ ሕይወት እንዳንዳረግ ነበር እግዚአብሔር ሰዉ ሆኖ በተገለጠበት ዘመን ከሐሰተኛ መምህራንና ሰባኪዎች እንድንጠበቅ የመከረንና ያስጠነቀቀን፡፡ እንዲሁም ማንነታቸዉን ከፍሬያቸዉና ከተግባራቸዉ ማወቅ እንደምንችል በግልጽ የነገረን፡፡ ይሁንና በሥጋና በደም ስሜታችን እየተመራን የዲያብሎስን ፈቃድ ስንፈጽምና ስናስፈጽም እንገኛለን፡፡ ስለ ይሁዳ ያነሳሁት ካለ ምክንያት አይደለም፡፡ አንዳንድ የማልጠብቃቸዉ እንዲሁም ትልቅ ቦታ የሰጠዋቸዉ ሰዎች ሳይቀር የአቶ መለስ አምላኪና አግናኝ ሆነዉ ስላገኘዋቸዉና የተለያየ የሥጋና የደም ስሜታቸዉን ምስክርነት ሲሰጡ በመመልከቴና በመስማቴ ነዉ፡፡ ንግግሮችን ሆነ ተግባሮችን በቅንነትና በእዉነት በጣም ካልታየ ልንሰናከልና ልንሳሳት እንችላለን፡፡ የይሁዳን ሐሳብ በቅንነት ብቻ የሚመለከት ሰዉ ይሰናከልበታል፤ ስለ ተንኮልና ክፋት ሐሳቡም አድናቂዉና አግናኙ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት፣ እንደ ይሁዳ፤ ሰዎች ሊቀበሉት በሚችል አቀራረብ «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ፤ ኢትዮጵያዊነት ማንም ፈልጎ ሊቀበለዉና ካልፈለገ ደግሞ አሽቀንጥሮ መተዉ ይችላል እንጂ እንዳለፉት ገዥ መደቦች ወይንም ክርስቲያኖች ወይንም ዐምሐራዎች በግድ ኢትዮጵያዊነትን እንዲቀበል አይገደድም፤ ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸዉ ቋንቋ መናገር፣ መማር፣ መስራት ይችላሉ፤ ማንኛዉም ሰዉ የፈለገዉን

እምነት ሆነ አምልኮ መከተልና ያንንም ማስፋፋት ይችላል፤ መንግሥታዊ ሃይማኖት የለም፤ መንግሥት በሃይማኖት ዉስጥ ጣልቃ አይገባም፤ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል ናቸዉና ማንም ሰዉ የማንንም ሃይማኖትን መተቸት ሆነ መንቀፍ የለበትም፤ ከፈለገ ጣዖት ዛፍ ያምልክ መብቱ ነዉና፤ ማንም አካል ሆነ ግለሰብ ይህን አምልኮ መቃወምና ማዉገዝ የለበትም፤ ምክንያቱም እንደማንኛዉም እምነት እምነት ነዉና፣ በሕግ ፊት እኩል መብትና ነጻነት አለዉ:: ...» ወዘተ የሚለዉን አባባል በዋንኛነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕሊና የፈለቁ ሐሳቦች ሲሆኑ፤ ዋናዉ ዓላማቸዉም ከመሰሎቻቸዉ ጋር ሆነዉ በዚህ የተንኮልና የበቀል ጥበብ አስተሳሰብ ዘረኝነትንና ጎጠኝነት በማንገሥ ኢትዮጵያዊነትን ፍቅር በመቀነስ በሂደት እያንዳንዱ ክልል ልክ እንደ ኤርትራ የራሱን ነጻ መንግሥትና የራሱን ነጻ ሰንደቅ ዓላማ በማቋቋምና በማዉለብለብ ኢትዮጵያ የሚለዉን ስምና አረንጓ ብጫ ቀይ የሚለዉን ሰንደቅ ዓለማ ከምድረ ገጽ ለማጥፋ ነበር:: በነበር ቀረ እንጂ:: ምክንያቱም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሱና የሚነሱ የአገር ልጆች ቀርቶ ባዕዳን ጭምር በኢትዮጵያ ቀን በእግዚአብሔር ቁጣ ተጠርገዉ ወደ ሲኦል ይሄዳሉና:: በዚህ የኢትዮጵያዊዉ ይሁዳ የጥላቻና የበቀል አስተሳሰብ ምክንያት ክርስቲያኖችን (ዐምሐራዎችን) ከስራቸዉ እንዲፈናቀሉና በአገራቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ በነጻነትና በእኩልነት እንዳይኖሩ ተደርጓል:: የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግሞ ለሃያ ዓመት ሙሉ የበቀል ተግባራቸዉን ፈጽመዉ እንኳ አሁንም ያልረኩና «እንደመስሳቸዋለን» በማለት የእብሪትና የትዕቢት ንግግር በግልጽ በሚዲያ የሚናገሩ የዓመፃ ልጆች ናቸዉ::

ከእንግዲህ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናት ከመሪያቸዉ ሞት መማር ካልቻሉ ሊማሩ የሚችሉት የእግዚአብሔር ቁጣ ወደ እነሱ ሲመጣ ነዉና ቁጣዉን እንደሚቋቋሙትና ከጠረጋዉ እንደሚተርፉ እጅግ በቅርቡ የምንመለከተዉ ይሆናል:: አሁንም ታዲያ ወደልባቸዉ ተመልሰዉ በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ቢሰጡና ራሳቸዉን ቢያዋርዱ እንዲሁም ወንበሩን ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ለእዉነተኛ እንደራሴዎቹና አገልጋዮቹ ቢለቁ ይሻላቸዋል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርግ የወሰነዉን ማንም ሊያስቀረዉ አይደለም ለአንድ ቀን ማዘግየት አይችልምና:: እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ማንም ሊደራደር ሆነ ቅድመ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ አይችልም:: ምክንያቱም ሊደረግ የሚችለዉና የሚገባዉ የመጨረሻዉ መልካም ነገር ነዉ በእርሱ ፈቃድ የሚከናወነዉና:: እንዲሁም የሰዉ ፈቃድና ሐሳብ ለራስ ሥጋና ደም ስሜት ነዉ ቅድሚያ የሚሰጠዉ እንጂ ከእግዚአብሔር ፍጹም ለሆነና የመጨረሻ መልካም ለሆነ አይደለምና::

ሌላዉ የታዘብኩት «ለእዉነት አገልግሎትና ምስክርነት ነዉ የቆምነዉ» የሚሉ ለብርሃን አገልግሎት የተሰለፉ ሰዎች ከዲያብሎስ ጨለማ አገልጋዮች ትጋትና ቆራጥነት ጋር ሳነጻጽራቸዉ እጅግ አንሰዉብኝ ማየቴ ነዉ:: ምናልባት እነዚህ የዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች እንዲሁም ዉዶች ሥጋዊዉን ሆነ መንፈሳዊዉም ወንበር በተለያየ መልኩ ስለተቆጣጠሩትና በኃይላቸዉ ተመክተዉ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን አፍነዉና አስጨንቀዉ ስለያዙ ይሆናል:: ለዚህ መስክሩ ሕዝቡን ከክልል እስከ ዞን እንዲሁም ወረዳና ቀበሌ ድረስ እንደተቆጣጠሩትና ተጽህኖ እንዳሳረፉበት በሚገባ የሚያስረዳዉ በሬሳ(በአስከሬን) የፓለቲካ ስራቸዉን ለማስፈጸም የካድሬዎቻቸዉ ትጋት

የታየዉ ሕዝቡን ከየመስሪ ቤቱ፣ ከሚኖርበት፣ ከተለያየ አገልግሎት ከሚሰጥበት በኀዘን ሽፋን የዲያብሎስ እንደራሴ ሆኖ የጨለማ አገልጋይ የነበረዉን መሪ እንደ ታላቅ ጀግናና ታላቅ አባት ተቆጥሮ ማግነንና የብልጠት አምልኮ እንዲፈጸምለት በማድረጋቸዉ ነዉ።

እንዲሁም አምላክን ያህል ራቁቱን በመስቀል ላይ ሰቅለዉ በዘፈኑና በዳንኪራዉ ሃያ አራት ሰዓት ነፍሳትን በተለያዩ ብዙኃን መገናኛ እንዳላሰበዱና በእግዚአብሔር ላይ እንዳላላገጡ ሁሉ፤ የጨለማ ስራ ፈጻሚና አስፈጻሚዉ መሪያቸዉ ሲለያቸዉ በመገናኛ ብዙኃን ብቻ አይደለም የተለያዩ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ሁሉ ዘፈንና ዳንኪራ አስቁመዋል። በአስረሽ ምቺዉ ቦታ ሁሉ ተገድቧል። ይህም የሚያሳየዉ ዘፈኑና ዳንኪራዉ ትክክለኛ ስራ አለመሆኑን ሕሊናቸዉ እየመሰከረባቸዉ፤ ለዓመታት ሕሊናቸዉን በማደንደን በዓመፃ ተግባር እንደተሰማሩ ነዉ። ምክንያቱም ትክክለኛ ተግባር ቢሆን ሰዉ ሞተ አልሞተ አይቀርም ነበርና። ለምሳሌ ለእግዚአብሔር የሚቀርበዉ ምስጋና ሆነ ሽብሸባ ሰዉ ሞተ አልሞተ ሁሌም ይቀርባል። ምክንያቱም ትክክለኛ ተግባር ነዉና። አሁን የታየዉ ግን ያ እንደትልቅ መቀስቀሻና ጥበብ ይቆጠር የነበረዉ ዘፈንና ዳንኪራ እንዲሁም በቴሌቭዥንና በሬዲዮን ይታላለፉ የነበሩት የተለየዩ ማደንዘዣ መርሐግብሮችና እንደ ፎክስ ሙቪስ የመሳሰሉት ትዕይንቶች እንዲቆሙ ተደርጎ የኀዘን እንጉርጉሮና ለጨለማዉ ገዥ አገልጋይ ምስጋና፣ ሙገሳ፣ ማግነን፣ አምልኮት ነበር ይቀርብ የነበረዉ። ታዲያ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተሰማራን ሰዎች እንዴት ከዓመፃ ልጆች በላይ በአገልግሎታችን አንተጋም? ቆራጦች ስለምን አንሆንም?። እነሱ ለዚያዉም ምድርን ተስፋ አድረገዉ ነዉ የሚኖሩትና ለአጭሯ ዘመናቸዉ የሞት ሽረት ትግል የሚያደርጉት። እኛ ግን ተስፋችን ሰማያዊ፣ ለሕያዉነት ሕይወት ተስፋ ነዉ የተሰለፍነዉ። ታዲያ በእጥፍ እጥፍ ከእነሱ በላይ መትጋት አይጠበቅብንም ነበር? ተመሳስሎና አስመስሎ ኑሮ ከእኛ ይጠበቃልን? ፈጽሞ አይጠበቅም ነበር።

ይህ ዘመኑን ሁሉ የዲያብሎስ አገልጋይ የነበረዉ ሰዉ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቤተክርስቲያንን ለማዳከም ብሎም ለማጥፋት የተሰለፈ «የትምክተኞችና የነፍጠኞች መሸሸጊያ ናት፤ የገዥ መደቦች መጨቆኛ መሳሪያ ናት» እያለ እንዳላጥላላና ጥቃትና በቀል እንዲፈጸምባት እንዳላደረገ፤ አንድ ቀን እንኳ የራሱን አገልግሎት ያልሰጠ፤ ያ ብቻ አይደለም አንድ እንኳ ተሳልሞ ፈጣሪዉን ያላመሰገነ፤ ፀረ ክርስቲያን የሆነ፤ የቀደሙ አባቶቻችንና እናቶቻችን፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተለያየ መልኩ ለማሰብ ቦታዎችን ሳይቀር እርሱ ባደገበት፣ ባስተማረበት፣ የተለያዩ ተአምራትና ፈዉስ ባደረገበት ቦታ ስም «ናዝሬት፣ ደብረ ዘይት» እያሉ የሰየሙትን ስም ሳይቀር «ይህ የነፍጠኞች ወይንም የዐምሐራዎች ወይንም የክርስቲያን ስያሜ ነዉ» እያለ ጥላቻንና በቀልን እየዘራ እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚነዱትን አእምሮ ቀላሎችንና አእምሮ ሕፃናትን እንዲሁም ዉስጣቸዉ ክፋትና ዓመፃ የሞላባቸዉን ሰዎች በማስበሰብና የእርሱን ፈቃድ እንዲፈጽሙ በማድረግ የእግዚአብሔር እዉነታን ከመታሰቢያነት ያጠፋ፤ ከዚህ በተጨማሪ ለአገራቸዉ የራሳቸዉን አስተዋጽኦ አድርገዉ ያለፉ ኢትዮጵያዉያን ክርስቲያኖች (ዐምሐራዎች) «ክርስትናን ያስፋፉና ሃይማኖታችሁን ያስለወጡ፣ ቋንቋና ባህላችሁን ያጠፉ ናቸዉ።» በማለት በትምህርት ቤት፣ በሆስፒታል፣ በአዳራሽ መታሰቢያ የተደረገላቸዉ አጼ ገላዉዲዎስ

ኃይለማርያም ማሞ፣ ራስ መኮንን የመሳሰሉትን ስያሜ ከአገሪቱ እንዲጠፋ ያደረገ፤ በተቃራኒዉ በአገራቸዉ ላይ ዓመፃና ክህደት የፈጸሙ ርኩሰት ያነገሡ ሰዎች እንዲታሰቡ ያደረገ፤

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቤተክርስቲያንን «የሃይማናት እኩልነት» በሚል ፈሊጥ በተለያየ መልኩ እያዳከማትና እየከፋፈላት የራሱን ካድሬዎች በተለያየ ወንበርና ኃላፊነት እያስቀመጠ የፖለቲካ መድረክ እያደረጋትና የክህደትና የመናፍቅነት እምነት እያስፋፋ የነበረ መሪ፤ ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር የለሽ የክህደት እምነት የሆነዉን አብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነትን የመሰረተና የመራ፤ ያ ብቻ አይደለም እንኳን ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ማመን ቀርቶ በእግዚአብሔር ህልዉና የማያምን የማርክዚስት ሌኒዚዝት እምነት አራማጅ የሆነ ሰዉ፣ ከዛም ባለፈ «ዐምሐሮች(ክርስቲኖች) እምነታችሁን፣ ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን በመለወጥ ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል፤ አሁንም የነፍጠኛ ዉን ሥርዓት ለመመለስ የተሰለፉ ሰዎች ስላሉ እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጸመባችሁን ግፍና በደል በማሰብ አስፈላጊዉን እንድትፈጽሙ» በማለት ሕዝቡን ለበቀልና ለጥላቻ አሰልፎ ብዙ የግፍና የጭከና እንዲሁም አድሎ ተግባር በክርስቲያኖች(በዐምሐራዎች) ላይ እንዲፈጸም በበላይ ሆኖ የመራ ዓመፀኛ ሰዉን፤ ለቤተክርስቲያን ታላቅ ስራ እንደሰራ ተደርጎ «የእግዚአብሔር አገልጋይ» ተብሎ በጸሎት በቤተክርስቲያን ሲታሰብና ሥዕሉ እንደ ጻድቅና ቅዱስ ተቆጥሮ በካደዉ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ላይ ተለጥፎ ሲታይና ሌላም መታሰቢያ እንዲደረግለት ቅስቀሳ በተለያዩ አስመሳይ አገልጋዮች ሲደረግ በማየቴና ለአገሪቷ ሆነ ለቤተክርስቲያን ብዙ የሰሩት የቀደሙት ነገሥታቶች ደግሞ ከአንድ ጳጳስ በስተቀር ማንም በጸሎት ስማቸዉን ሲያነሳ ያልተሰማ፤ ይልቁኑ በአገርና በቤተክርስቲያን ላይ በደልና ግፍ እንደፈጸሙ ሕዝቡንም እንደጨቆኑ ሳያፍሩ የሚመሰክሩና የሕወሓትን ወይንም የወያኔን (የኢሕአዴግን) መንግሥት ደግሞ እያዳናቁና እያገነኑ የሚናገሩ ሰዎችና አስመሳይ አገልጋዮች መታየታቸዉ፤ ምን ያህል ትዉልዱ በዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች እንዲሁም ዉዶች ተጽህኖ ስር መዉደቁን ነዉ::

ሌላዉ ደግሞ ባለሥልጣናቱና ካድሬዎቹ፣ እንዲሁም ደጋፊዎቹ በቀብሩ ሰዓት እንኳ የፓለቲካ ስራና የጥላቻና የዘረኝነት እንዲሁም የጎጠኝነት ተግባራቸዉን ያሳዩበት፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት መማር ያልቻሉ፣ ለበለጠዉ ዓመፃ ተግባር መሰለፋቸዉን በግልጽ የመሰከሩበት፣ ይኸዉም«የጠቅላይ ሚኒስትሩ የዓመፃ(የትግል) መንፈሳቸዉ በተዝዋዋሪ ደግሞ የዲያብሎስ መንፈስ ሳይለያቸዉ የተያያዘዉን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ተግባር እንደ መልካም ራእይ ቆጥረው የበለጠ እንደሚያቀጣጥሉት ተናግረዋል:: ከዚህ በተጨማሪም በሬሳዉ(በአስከሬኑ) ለአስራ ሁለት ቀን በላይ ለፖለቲካ ድጋፍና ቅስቀሳ እንዲሁም ሕሊና ማሸጫ እንደተጠቀሙበት ሁሉ፤ በአጽሙ ደግሞ በሂደት ሙዝየም አዘጋጅተዉ እንደሚጠቀሙበት በግልጽ ተናግረዋል:: በእርግጥ ከተቀደሰዉ ቦታ ወቶ ሲያገለግለዉ ወደ ነበረዉ ወደ ጨለማዉ ገኸ ወደሚያዘጋጅላቸዉ ቦታ አጽሙን ለማፍለስ መወሰናቸዉ በአንድ በኩል «የመንፈስ ቅዱስ ስራ» ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አሳድሮብኛል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር አገልጋይና የዲያብሎስ አገልጋይ አንዳች አንድነትና ኅብረት የላቸዉምና:: የሚገርመዉ ግን ልክ እግዚአብሔር የቅዱሳን የጻድቃን አጽማቸዉ ፈልሶ እርሱ በፈቀደዉ ቦታ እንዲያርፉና በስማቸዉ መታሰቢያ ቤተክርስቲያን እንዲሰራ አድርጎ ለዘላለም

እንዲታሰቡ እንደሚያደርግ ሁሉ፤ ዲያብሎስም ከማን አንሼ በሚል ስሜት እንደራሴዎቹንና ባለሟሎቹን፤ የዓመፃ ስራቸዉ እንደመልካም እንዲቆጠርና ትዉልዱ የእነሱን ፈለግ ተከትሎ እንዲኖርና እንዲሰራ በተለያየ መልኩ እንዲታሰቡ ማድረጉ ነዉ።

**ሌላዉ አስገራሚ ምስክርነት** ደግሞ ትዉልዱ ለሕሊናዉና ለአምላኩ እንዳይታመን አድርጎ ሕሊናዉን እንዲሸጥ ያደረገ መሪ፤ እንዲሁም የሰዉ አግናኝና አምላኪ የፈጠረ መሪ ሆኖ ሳለ፤ እነ ሆዱ አምላኩና ከሕሊናቸዉ ተቃራኒ የሚኖሩ ሰዎች «መለስ እንዲህ ሰራ ተብሎ እንዲነገርለት የማይፈልግ ነዉ፤ መግነንን የማይፈልግ ነዉ» እያሉ ምስክርነት መስጠታቸዉ ነዉ። ምክንያቱም ማንም የሚታወቀዉ በፍሬ ነዉና ይኸዉ የመለስ ፍሬ ለአስራ ቀናትና ለወራቶች «የጤናዬ ጌታ፣ የዉኃ ጌታ፣ የኑሮዬ ጌታ... ወዘተ» እያለ የሚያመልክ፣ ያሚያገን፣ የሚያመሰግን፣ ተስፋዉን በሥጋ ለባሽ በፍጡር የሚደርግ ትዉልድ በየመድረኩ ታይቷል፤ ተሰምቷል። ይህ ደግሞ በግልጽ የሚያሳየን ትዉልዱ ተስፋዉን ምድር ብቻ እንዲያደርግ መደረጉና ታላቅ ተስፋዉን እንዳያዉቅና እንዳያስተዉል ተደርጎ ለዲያብሎስ እንደተገበረ ነዉ። ያ ባይሆንማ ኀዘኑ ሆነ ለቅሶዉ እንደ ትንሣኤ አማኞች አግባብ ባለዉ መልክና በእዉነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት ይገለጽና ይከናወን ነበር። የታየዉ ግን የአረማዉያን(የአሕዛብ) የኀዘን አገላለጽና ለቅሶ ነዉ። በዚህች «ሀገረ እግዚአብሔር» በተባለች አገር እንደዚህ አይነቱ ቅጥ ያጣና በእግዚአብሔር የማያምኑ አሕዛብና አረማዉያን የሚፈጽሙት ተግባር መታየቱ ምን ያህል ኢትዮጵያዉያን ማንነታቸዉን እንዳጡና የአረማዉያን ሕይወት እንደተንጸባረቀባቸዉ፣ ሥርዓቱም ሙሉ በሙሉ በጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ቁጥጥር ዉስጥ መሆኑን ነዉ የሚያሳየዉ። የእኛ ባልሥልጣኖች ፍጹም የዲያብሎስ ተጠሪ መሆናቸዉን ያስመሰከረባቸዉ ደግሞ፤ ከሌላ አገር የመጡ ባለሥልጣናት ሆኑ መሪዎች የሚያምኑትን አምላክ ስም እየጠሩ ኀዘናቸዉን ሲገልጹ፤ ከእኛ ግን አንድም ባለሥልጣን የፈጣሪ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ኀዘኑን አልገለጸም። በነዚህ ከሃዲያን፣ እግዚአብሔርን በማያዉቁ ሰዎች መመራታችን አያሳዝንም!

ሌላዉ የድፍረት ድርጊት ደግሞ ሕሊናዉን የሸጠዉ ትዉልድ ጨለማዉን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ ጥቁሩን ነጭ ነጩን ጥቁር ማለቱ አንሶት በእግዚአብሔር ላይ ማላገጡና መዳፈሩ ነዉ። ይኸዉም መልካም ይሁን መጥፎ ሐሳብ እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጃቸዉን በአንድ ላይ አያይዘዉ የተነሱትን ፎቶ፣ ልክ ጸሎት ወደ ፈጣሪ የሚያቀርቡ አስመስሎ «እግዚአብሔር ሆይ ኢትዮጵያን በዘር በብሔር ብሔረሰብ በፍቅር በአንድነተ እንዳይለያዩ እንድትጠብቅ አድራ» ብሎ እንደጸለየ በማስመሰል በተለያየ ቦታ ፎቶዉና ጽሁፉን በመለጠፉ ነዉ። እንዲሁም ኢትዮጵያዉያን በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቋንቋ እንዲለያዩና ዉስጣቸዉ በጥላቻና በበቀል፣ በመለያየትና በመከፋፈል እንዲኖሩ ማድረጉ እየታወቀ፤ ከሻዕቢያ መሪ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ኢትዮጵያና ኢትዮጵዊነት ለማጥፋት እንደተጋ በደንብ እየታወቀ፤ አሁን ደግሞ አእምሮ ቀላሎችና አእምሮ ሕፃናት እንዲሁም በአስመሳይ አገልጋዮቹ «እግዚአብሔር ሆይ ኢትዮጵያዉን በሃይማኖት፣ በዘር፣ በብሔር ብሔረሰብ የፍቅር ልዩነት እንዳይፈጥሩ አዳራ ብያለሁ» በማለት በየቦታዉና በየመኪናዉ ላይ መለጠፋቸዉ ምን ያህል በእግዚአብሔር ላይ አላጋጭ ትዉልድ መፈጠሩን ነዉ የሚያሳየን።

እግዚአብሔርን የማያዉቅ መሪ፣ ኢትዮጵያን በቋንቋና በዘር የከፋፈለ ዘረኛ መሪ ፣ አንዲት ኢትዮጵያንና አንዲት ሰንደቅ ዓለማን ለማጥፋትና ኢትዮጵያዉያን በፍቅር በአንድነት እንዳይኖሩ ያደረገ መሰሪና ተንኮለኛ መሪ፣ አሁን ነፍሱ በእግዚአብሔር እጅ ከተያዘች በኋላ ጻላይ፣ ቆራቢ፣ ለማስመሰል የሚጣረዉ ከንቱ ጥረት፤ የእርሱ አድናቂና አምላኪ ሰዎች ምን ያህል ሕሊናቸዉን እየሸጡና የተለመደዉን የማስመሰልና የሸንገላ ተግባራቸዉን እንደቀጠሉ የሚያሳይ ነዉ:: እንዲሁም ምንም ከማለትና ከመስራት ወደ ኋላ የማይመለሱ፣ ንስሐን ያቃለሉ፣ ሕሊናቸዉን ያደነደኑ መሆናቸዉን ነዉ የሚገልጸዉ:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ላይ ማላገጣ ፍጹም ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ሰይጣናት እኩልና በላይ የሚያስቆጥር ነዉና::

**ሌላዉ የእግዚአብሔር ድንቅ ምስክርነትን ያየሁት** በቀብራቸዉ እለት በእለቱ በየአብያተ ክርስቲያኑ የተነበበዉ የዕለቱ ወንጌል የሉቃስ ወንጌል ምእራፍ12 ከቁጥር16እስከ21 ድረስ ያለዉ ነዉ:: ይኸዉም:

«ምሳሌም ነገራቸዉ እንዲህም ሲል - አንድ ባለጠጋ ሰዉ እርሻ እጅግ ፍሬያማ ሆነችለት:: እርሱም :- ፍሬዬን የማከማችበት ስፍረ አጥቻለሁና ምን ላድርግ ብሎ በልቡ አሰበ:: እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጎተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፣ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም - አንቺ ነፍሴ፣ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፣ ብዪ፣ ጠጪ፣ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ:: እግዚአብሔር ግን:- <u>አንተ ሰነፍ</u>፣ በዚች ሌሊት ነፍስህን ካንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸዉ ለማን ይሆናል? አለዉ:: ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነዉ::»ይላል

ይህ ደግሞ በጠቅላይ ሚስትሩና በመሰሎቻቸዉ ሕይወት ላይ የሚመሰክር ነዉ:: ይኸዉም ለምድራዊ ሥጋዊ ኑሮ ብቻ ሲወጡ፣ ሲወርዱ፣ ሲደክሙ፣ ሲጠበቡ ምንም እንኳን እንደሚፈልጉትና እንደሚመኙት ፍሬ ባያገኙም፤ ዞሮ ዞሮ የተለየ ተግባርና ስኬት እንዳደረጉ በማሰብ የሚናገሩና አንዳንዴም በትዕቢትና በእብሪት ቢደነፉም፤ በዚህ ተግባራቸዉና ንግግራቸዉ አባሎቻቸዉና ደጋፊዎቻቸዉ «ጎበዝ፣ የጀግኖች ጀግና፣ ታላቅ» ቢሏቸዉም፤ ለራሳቸዉ ሆነ ለሌሎች ሕያዉ ነፍስ አንዳች የሰሩት የለምና፤ ተሳክቶላቸዉ ድህነትና ቢያጠፉና ሀብት በሀብት ቢያደርጉን እንኳ «ሥጋዬ ጥገቢ» እንላለን እንጂ ለሕያዉ ነፍሳችን አንዳች የሰሩት ነገር የለምና፤ ይልቁኑ በነፍሳችን አሳምፀዉናል፣ አስክደዉናል፣ አስረክሰዉናል፣ አሳብደዉናልና፣ የነፍሳችን ዋና ጠላት ነበሩ:: በእግዚአብሔር ዘንድም «ሰነፍ» የሚል ስያሜ ተሰቷቸዉ ነዉ ነፍሳቸዉ ከሥጋቸዉ ተለይታ ወደተዘጋጀላት ቦታ የሄደችዉ::

ሌላዉ ደግሞ ዞሮ ዞሮ በእግዚአብሔር እጅ መያዝ አይቀርምና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእግዚአብሔር በቁጣዉ በስቃይ ሞት ከተጠሩ በኋላ፤ ለቤተክርስቲያንና ለአገር ትልቅ ስራ እንደሰራ ተቆጥሮ «ጀግና፣ ሰማዕት፣ ጻድቅ፣ ሐዋሪያ» ተብሎ በእግዚአብሔር ቤት በዋና መድረክ ላይ እንዲቀበርና እንዲታሰብ ተደርጓል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ለእናት አገራቸዉና ለቤተክርስቲያናቸዉ

ታላቅ ስራ የሰሩት የትም ተጥለዉ መታሰቢያቸዉ ተደምስሷል። እንደ በደለኛ፣ ግፍ እንደ ፈጸሙ፣ አገርንና ሃይማኖትን እንደካዱ ተቆጥረዉ የትም ተጥለዋል። ይህም የሚያሳየን ዓለም ለዲያብሎስ በትጋትና በቆራጥነት የሚያገለግሉትን እንጂ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉትንና ስለ እዉነት የሚመሰክሩትን ሰዎች አንዳች ቦታ እንደማትሰጣቸዉና መታሰቢያቸዉን እንምታጠፉ ነዉ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን እዉነት ባለ ጊዜ ስለምትሆን የዓመፀኞች መታሰቢያ ለዘላለም የሚጠፋና የእዉነተኞች መታሰቢያ ደግሞ ለዘላለም የሚታሰብ ይሆናል።

**ሌላዉ አሳዛኝና አስገራሚዉ ደግሞ** በእግዚአብሔር እዉነት ላይ እጅግ ዓመፃ የፈጸመዉ መሪ እንደ ቅዱሳንና ጻድቃን ሥዕሉ በትልቁ ተስሎ በሥላሴ ቤተክርስቲያን ላይ ተለጥፎ መታየቱና ይህን ርኩሰት ተግባር የሚከለክል የሃይማኖት አባት መጥፋቱ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ በተቀደሰዉ ስፍራ የዓመፃ ስራ አስፈጻሚ ሬሳ መቀበሩ አንሶ እንደገና በሬሳዉ ምክንያት የተለያዩ የዲያብሎስ ዓርማዎች የሆኑት «በክልላዊ ሰንደቅ ዓላማ» ሽፋን ስም በቦታዉ እንዲዉለበለቡ በመደረጉና ጌታችን «ርኩሰቱን በተቀደሰዉ ስፍራ ላይ ስትመለከቱ አንባቢዉ ያስተዉል» እንዳለዉ የጥፋት ዘመን መድረሱን ነዉ። እዉነተኛ ታሪክ ያጠፋና ያበላሸ መሪ «ታሪክ ሰሪዉ መሪ» እየተባለ ቅኔ ሲቀኙለትን፣ ግጥም ሲደረድሩለት፣ እንዲሁም ምስጋና ሲያቀርቡለት፤ ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ ዘመን ለሰዉ ዘሮች እረፍት እንድትሆን የነፍስ ተግባር እንዲፈጸምባት ያደረገዉን ያቺኑ የብሉይ ዘመን ሰንበትን በማጽናት በትንሣኤዉ ዕለት የገለጻትን የሐዲስ ዘመን ሰንበት እሁድን የባለሥልጣናቱንና የካድሬዎቹን ሕሊና በክሎ የገብያ ቀን እንድትሆነ የፈቀደና እንደ ቀደሞዎቹ መሪዎች የተለያዩ የነፍስ ስራና የነፍስ ግብይት እንዳይካሄድባት የተለያየ የሥጋ ስራና ትዕይንት እንዲፈጸምባት የፈቀደ መሪ፤ ትንሣኤ ሙታንን የማያምን መሪ፣ እንደ አማኝ ተቆጥሮ በመላዉ አብያተክርስቲያናት ጸሎት ሲደረግለትና ያቃለለዉንና የናቀዉን ክርስትና እንደ ጠበቀዉ ተቆጥሮ ፀረ ማርያሙ «የማርያም አገልጋይ (ገብረ ማርያም)» እየተባለ ስሙ ሲጠራ መሰማቱ ምን ያህል እጁን በቤተክርስቲን ዉስጥ ጭመር አስረዝሞ እንደነበረ ነዉ የሚያሳየዉ።

ይህ ፀረ ክርስቲያን የሆነ መሪ፣ ባለሥልጣኑም ሆነ ካድሬዉ በግልጽ እንደመሰከረዉ የሁሉ ነገር አመንጪ ፣ቀያሽ፣ መሐንዲስ፣ እንደ ክርስቲያን ተቆጥሮ ለአርባኛዉ ቀን መታሰቢያ የየአብያተክርስቲያኑ አስተዳዳሪዎችና የተለያዩ ኃላፊዎች በቤተክርስቲያንና በቤተክህነት አዳራሽ እንዲገኙ ተደርጎ የተለየ ጸሎት መደረጉና እንዲሁም በየክብረበዓሉና መድረኩ «ተወዳጁና ታላቁ የኢትዮጵያና የአፍሪካ መሪ» እየተባለ በቁልፍ የሃይማኖት አባቶች ሲገን መታየቱና መደመጡ የሚያሳየን ብዙዎቹ የሃይማኖት አባቶችና አማኞች «ተመሳስለህና ሕሊናህን ሸጠህ ኑር፤ አገልግል፤» የሚለዉን የእግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማጆች ሰላባ መሆናቸዉንና የእዉነተኞቹ የነቢያት፣ የመምህራን፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታትና የጻድቃን ፈለግ ያልተከተሉ፤ ለሥጋዊ ጥቅምና ክብር የቆሙ አስመሳይ አገልጋዮች መሆናቸዉን ነዉ።

መንፈስ ቅዱስ ጸፍቶ ባለሥልጣናቱንና ካድሬዎችን ያናገረዉ ደግሞ፤ የሁሉ አድራጊ ፈላጭ ቆራጭ ወሳኚ መሪ የኢሕአዴግ ሞተር የነበረዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆኑን አንዳች ሳያፍሩና

ሰይሸማቀቁ በተለያየ መገናኛ ብዙኃን መግለጻቸዉና እንደ ቦይ ዉኃ ወደፈለገዉ አቅጣጫ እንደሚወስዳቸዉና እንደ ጠፍ ከብት ወደ ሚነዳቸዉ እንደሚሄዱ መግለጻቸዉ ነዉ:: እርሱ በሥጋ ሞት ከተጠራ በኃላ ደግሞ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ በሕሊናቸዉ ማሰብና ሕሊናቸዉ የሚያሰራቸዉን መስራት ሲጠበቅባቸዉ፤ አሁንም በሙቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መንፈስ እንደሚመሩና እርሱ የጀመረዉን ራእይ እስከ መጨረሻ እንደሚያስፈጽሙና መለስ ዜናዊን ሊተካ የሚችል ብቃት ያለዉ ሰዉ በመሃከላቸዉ እንደሌለ በመግለጻቸዉ ነዉ:: በተዝዋዋሪ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሪነት ዘመኑ የዲያብሎስ እንደራሴ ሆኖ ሲያገለግል ስለነበረና እንዲሁም የሚመራበት መንፈስ የመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ስለነበረ «አሁንም የዲያብሎስ እንደራሴ ሆነን እናገለግላለን፣ የምንመራበትም መንፈስ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ መንፈስ ነዉ» ማለታቸዉ ነዉ::

**ሕሊናዉን የሸጠዉን ትዉልድ፣ ባለሥልጣናትን፣ እንዲሁም ካድሬዎችን የታዘብኩት ደግሞ**፤ አቶ መለስንና ግብረ አበሮቹን፣ እግዚአብሔር «በዓለም ላይ እስከ አሁን ያልታየና ያልታዩ፣ የራሱንና የራሳቸዉን አገርና ታሪክ እንዲሁም ሃይማኖት ለማጥፋት ቆርጦና ቆርጠዉ የተነሳ የተነሱ የዓመፃ ልጆች» እያለ ሲወቅሳቸዉና ሲገስጻቸዉ፤ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሰዉ ትዉልድና ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎቹ ሕሊናቸዉ አንዳች ሳይከብዳቸዉ፤ አቶ መለስ ዜናዊን «በታሪክ ሂደት ዉስጥ በልዩ ክስተት የተገኘና ታላቅ ታሪክ የሰራ መሪ፣ እስከ አሁን ድረስ እንደ እሱ ዓይነት መሪ በኢትዮጵያ ምድር ያልተፈጠረ... ወዘተ» እያሉ ሲያገኑና ሲያስመልኩት በመመልከቴ ነዉ:: እንዲሁም እግዚአብሔር እንኳ ለእያንዳንዱ ነጻ ሕሊና የሰጠዉና የተሻለዉንና መልካሙን እንዲሰራ ሙሉ ነጻነት የሰጠዉ ሲሆን፤ አቶ መለስ ግን አገርንና ትዉልድን ለመግደል ከስሩ ያሉትን ሁሉ በእርሱ መልክ ፈጥሮ ከእርሱ ዉጭ እንዳያስቡና ከፈጣሪም በላይ አድርገዉ እንዲቆጥሩት አድርጎ ስለሆነ ሕይወት እንደሌለዉ ፍጡር የቀረጻቸዉ፤ በሥጋ ሞት ከተጠራ በኋላ እንኳ የተሻለና የበለጠ መልካም ሐሳብና ተግባር የሚፈጥር ባለሥልጣን ጠፍቶ «አቶ መለስ ያሰቡትንና ያቀዱትን ብቻ ነዉ ተግባራዊ የምናደርገዉ እንጂ ሌላ የምንፈጥረዉ ነገር የለም::» እያሉ በተለያየ መድረክና መገናኛ ብዙኃን ካለ ሃፍረት ሲናገሩ ስመለከትና ሳዳምጥ፤ ቀሪዎቹ ባለሥልጣናት ራሳቸዉን ከሰዉነት ማዕረግ ያወረዱና ድርጅታቸዉንና አገሪቷን አንድ ሰዉ ብቻ ይመራትና ያስተዳድረት እንደነበረ ነዉ ያስተዋልኩት:: ምክንያቱም ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የሚታመኑ እንቁዎች በተለያየ መንገድ ተወግደዋል፣ ወይንም ተሰደዋል፣ ወይንም አንገታቸዉን ደፍተዉ እንዲኖሩ ተደርጓል፣ ወይን በእስር እየማቀቁ ይገኛሉ:: ባጠቃላይ ለሕዝቡና ለአገሪቱ እንዳያገለግሉ በመደረጉ ምክንያት ሕሊናዉን የሚሸጥና ሆዱን፣ ጥቅሙን፣ ክብሩን፣ ዝናዉን የሚያመልክ ሰዉ ብቻ ነዉ ከስሩ አድርጎ እንደፈለገ ሲጋልባቸዉና ሲያሽከረክራቸዉ የነበረዉና፤ አሁንም ያ ጥቅም ከተጠበቀለት በኢትዮጵያና በሕዝብ ስም እየነገደ ሕሊናዉን እያገለባበጠ መኖርን የሚፈልግ ባለሥልጣንና ካድሬ ብቻ እንደቀረ ነዉ የሚያሳየዉ::

በመጨረሻ ሕሊናዉን የሸጠዉን ትዉልድ ከላይ እስከ ታች ድረስ ያለዉን የምጠይቀዉ ጥያቄ አለ:: ይኸዉም «ጀግና አይሞትም» እያላችሁ የምትለፈልፉት ለመሆኑ «ጅግና» የሚል ስያሜ ሊሰጣቸዉ የሚገባቸዉ እነማን እንደሆኑ አዉቃችኋላን? አስተዉላችኋልን? ወይስ እናንተ «ጀግና»

የሚል ስያሜ የምትሰጡት ዘመኑን ሁሉ የዲያብሎስ አገልጋይ ሆኖ ዓመፃን፣ ክህደትንና ርኩሰትን ያነገሠን፣ ትዕቢተኛንና እብሪተኛ ሰዉን ነዉ? ወይስ ዉስጡ ጥላቻና በቀል ሞልቶት ዘረኝነትንና ጎጠኝትን አንግሦ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ቅጥረኛን ነዉ? ወይስ አንዳች እግዚአብሔር መፍራት የሌለበት እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚንቀሳቀስና ለጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ዋና መሪና ተሰላፊ ሆኖ በእግዚአብሔር የተቀደሱ በዓላት ቀን ሳይቀር መድረኮችንና ብዙኃን መገናኛ(ማስ ሚዲያዎችን) በእግዚአብሔር ቦታ ዲያብሎስ በዳንኪራና በዘፈን እንዲነግሥ ያደረገ መንግሥትን ነዉ? ለነገሩ ሕሊናዉ በሶሻሊስትና በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት የተበከለና የተመረዘ «ከፍጡሩ ፈጣሪያችን ጓድ አመራር ጋር ወደፊት» እያለ ግልሰብን ያገነነና ያመለከ ትዉልድ፤ «ከአፍሪካ ሰማይ አንድ ኮኮብ ጠፋ» እያለ የዓመፃ ልጆችን ቢያገንና ቢያስመልክ ብዙም አያስደንቅም::

በእግዚአብሔር እዉነት «ጅግና አይሞትም» የሚባለዉ በእዉነት እየኖረ፤ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ እየመሰከረ፤ በቅንነትና በእዉነት እያገለገለ፣ ከሥጋዉ ተለይቶ በረቂቅ አካል ወደ እግዚአብሔር እቅፍ የሄደዉ ነዉ እንጂ፤ «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንደለቅ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን እንመላለስ፤ እንደ እንስሳ እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን» የሚል የአረማዉያንና የአሕዛብን ሕይወት የያዘ እንዲሁም እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓት አራማኝ አይደለም:: በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ተመላልሶ ከሥጋዉ በተለያየ መንገድ የተለየ ሰዉ በዮሐንስ ወንጌል በምእራፍ6:ቁጥር 70 እንደተገለጸዉ ለዲያብሎስ ፈቃድ በዋና መሪነት የተሰለፈ እንደ ይሁዳ በክፋትና በተንኮል ሕይወት የሚመላለስና በሽንገላ አንደበት የተሞላ ሰዉ ምድቡ ከሰይጣናት ጋር ብቻ ሳይሆን ከትዕቢተኛዉን ከዓመፀኛ የሰይጣናት (የርኩሳን መናፍስት) መሪዎች ከሆነዉ ከዲያብሎስ ጋር ነዉ::

ለሃያ ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፍሎና መበቀል የሚፈልገዉን የተበቀለዉ አንሶ ያም ስላላረካዉ፤ «መከፋፈላችን ወይንም መለያየታችን ወይንም ብዙኃነታችን በማይቀለበስበትና ወደ አንድነት የማይመጣበት ደረጃ ላይ ስላልደረስን አጥብቀን መስራት ይኖርብናል፤( በእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሕሊና ዉስጥ ጥላቻና በቀል መዝራትና እንደ አንድ ወገንና ቤተሰብ እንዳይተያዩ ማድረግ አለብን)» እያለ የተናገረና አባላቱንና ደጋፊዉን በዚህ በጨለማ አቋምና አስተሳሰብ ያሰለፈ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለዓለም ታላቅ ሰዉ ለመምሰል «ለቤት ቀጋ ለዉጭ አልጋ» እንዲሉ፤ «ምስራቅ አፍሪካ ብሎም አፍሪካ ወደ ዉሕደት ልታመራ ይገባል» በማለት የሸነገል አስመሳይ፤ አንደበቱና ልቡ አንድ ያልሆነ፤ ፀረ አንድነትና ፀረ ዉሕደት ያራምድ የነበረ መሪ፤ እንዴት «የአፍሪካ አባት፣ ዕንቁ ፣ ታላቅ... ወዘተ» ይባላል? ትዉልዱስ አንደበቱና ዉስጡ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ አስመሳይና ባዶ ቀፎ የሆነዉንና የሥልጣኑን ዘመን ሁሉ ለጨለማዉ ገዥ ለዲያብሎስ እንደራሴ ሆኖ ሲያገለግል የነበረዉን ዓመፀኛ፤ «ታላቁ አባታችን፣ ታላቁ መሪያችን፣ ታላቁ ተስፋችን፣ ጌታችን...» እያለ እንዴት ይጠራል?

እዚህ ላይ አንድ የፖለቲከኞችንና የደጋፊዎቻቸዉን አእምሮ ቀላልነትና አእምሮ ሕፃንነት ለመግለጽ እወዳለሁ:: ይኸዉም ከላይ እንደገለጽኩት ለፖለቲካ ፍጆታ እንዲዉል በሬሳ(በአስከሬን) በነገዳቸዉ ምን ያህል ከእዉነተኛ ሕሊናቸዉ ተቃራኒ የሆኑ መሆኑን ነዉ የሚያሳየን:: ትንሽ እንኳ ለሕሊናቸዉ የማይኖሩ፣ ሃፍተቢሶች መሆናቸዉ ሌላዉ ምስክር ጥቅምት 4/ 2005 ዓ.ም የኢትዮጵያና

የሱዳን ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድኖች ተጫዉተዉ ኢትዮጵያ በማሸነፏና ሰንደቅ ዓላማዋ ከፍ በማለቱ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከደሙ ጋር የተዋሐደዉ ኢትዮጵያዊ ደስ ያለዉና የእናት አገሩን ሽንፈትና ዉድቀት የማይፈልገዉ ኢትዮጵያዊ በድሉ ሲደሰት፤ አእምሮ ቀላሎቹና አእምሮ ሕፃናቱ ባለሥልጣናትና ካድሬ፣ እንዲሁም የጨለማዉ ሥርዓት ደጋፊዎች፤ ይህን አሸናፊነት እንኳ ከሟቹ ሰዉ ከአቶ መለስ ጋር አያይዘዉታል:: ለእግር ኳስ የተለየ ነገር እንዳደረገ ቆጥረዉ «መታሰቢያዉ ይሁን» ሲሉ ምን ያህል ሕሊናቸዉ ማመዛዘንና ማገናዘብ የተሳነዉ መሆኑን መስክሮባቸዋል:: እግዚአብሔር ከሦስት አስራ ዓመታት በኋላ የአሸናፊነት እድል የሰጠዉ ሕዝቡ ለአገሩ ልዩ ፍቅር ያለዉና በጥሩና በአሸናፊነት አገሩ እንድትጠራ ስለሚፈልግ ፍላጎቱን ለሟሟላትና ከሁሉ በላይ ግንም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰቱ የፈጸሙና ያስፈጸሙት እንደ አቶ መለስ ዜናዊ ያሉ ዓመፀኞች ከኢትዮጵያ ሆነ ከዓለም በእግዚአብሔር ቁጣ ሲጸዱና ሲጠረጉ እዉነተኛዉ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ለኢትዮጵያዉያን ሆነ ለዓለም እንደሚገለጽ ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ ሩጫዉን «የመለስ ሩጫ»፣ የፕሪሜር ሊግ የእግር ኳስ ግጥሚያዉን «የመለስ ጨማዋ»፣ ኅዳር 29/2005 ዓ.ም የሚያከብሩትን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነት ለማንገሥ፣ በአራቱም ማእዘን ያሉ ኢትዮጵያዉያንን ለመበታተንና ለመከፋፈል፣ ሕወሓት ኢሕአዴግ የተባለዉ የዓመፃ መንግሥት «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል» የሚለዉን ሕገ መንግሥት ያጸደቀበትና በፈንጠዝያና በዳንኪራ፣ በዘፈን ደስታቸዉን የገለጹበትን ዕለት ደግሞ «የመለስ መታሰቢያ» በማለት ለማክበር በታለቅ ዝግጅት ላይ ናቸዉ:: ይህ የሚያሳየን ደግሞ በእዉነትም አቶ መለስ አምላካቸዉና አማልእክታቸዉ እንደነበረ ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ቀድም ብለዉ በገለጹት ላይ «እዚህ ላይ ለመግለጽ የምፈልገዉ የተወሰኑ አንድ እጅ (ፐርሰንት) የማይሞሉ ራስ ወዳዶችና ስግብግቦች እንዲፈጠሩና እጅግ እጅግ ብዙዉ ሕዝብ በችግርና በድህነት አረንቋ ዉስጥ እንዲኖሩ በተፈረደበት የጭከና ዘመን **ዉስጥ፤ <u>በንጹህ ላባቸዉና ድካማቸዉ መኖሪያ ቤትና መንቀሳቀሻ መኪና ያላቸዉ ሰዎች ካሉ የሚደንቅና እንደ ተአምር ሊታይ የሚችል ነዉ::</u>** ምክንያቱም የኑሮዉ ወድነት እንኳን ገንዘብ ከቀለብ፣ ልጅን ከማሳደግና ከማስተማር አልፎ ተቀማጭ ገንዘብ ሊኖርና ለቤት መስሪያና ለመኪና መግዣ ለማትረፍ ቀርቶ በአግባቡ ለመኖር በሚያስቸግርበት የስግብግቦችና የራስ ወዳዶች እንዲሁም የአስመሳይና የጨቃኝ ገዢዎች ዘመን ነዉና::» በማለት የተናገሩት፤ አሁን ከሚታየዉ እዉነታ ጋር ይጋጫል:: ይኸዉም አንድ መኖሪያ ቤት አይደለም ሁለት ሦስት ከዛም ባለፈ ለወደፊት ስለሚወልዷቸዉ ልጆች ጭምር ቤት የሚሰሩና እንዲሁም ዓይነት በዓይት መኪና የሚቀያይሩ አንድ ብቻ አይደለም አስርና ከዛም ባለይ ያላቸዉ ሰዎች አሉ:: ታዲያ ይህ እንደ ተአምር ሊታይ ይችላል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u> : እዚህ ላይ ሁላችንም ማወቅ ያለብን የለፋ፣ የወጣ፣ የወረደ፣ የደከመ ሰዉ፣ እንደ ድካሙና ልፋቱ እንዲሁም እንደ ጥረቱ ሊያገኝ ይገባዋል:: በዚህም ምክንያት በሀብት ላይ ሀብት፣ በንብረት ላይ ንብረት ሊኖረዉ ይችላል:: የማይሰራ፣ ሰነፍ ደግሞ እንኳን ለሌላዉ ሊተርፍ አይደለም ራሱንም ማኖር አይቻለዉም:: እኔ ለማለት የፈለኩት በንጹህ ላቡና በድካሙ ሀብት ንብረት ስለሚያፈረዉ አይደለም:: እነዚህን ሕዝቡም ከሁለ በላይ ደግሞ

እግዚብሔር ያዉቃቸዋል፡፡ ነገር ግን እጅግ እጅግ ጥቂት ስለሆኑ «እገሌ እገሌ» ተብለዉ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ እጅግ ብዙዎቹ ግን አንድም በአቋራጭ መንገድ ይኸዉም ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ጋር ተሻርከዉ ሊያገኙ ከሚገባቸዉ በላይ በእጥፍና ከዛም በላይ የሕዝብን ገንዘብ ለራሳቸዉ በማድረግ፣ ወይንም ሌሎች እንዳይወዳደሩና እንዳይሰሩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ተሻርከዉ ገቢያዉን ብቻቸዉን በመቆጣጠር፣ ወይንም ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ተሻርከዉ በጋራ በመስራት፣ ወይንም ዋጋ ከመጨመራቸዉ በፊት እላይ ካሉ ዘመድ አዝማድ እንዲሁም ጎጥ ተወካይ ባለሥልጣናት ዘንድ መረጃ አግኝተዉ እቃን በማከማቸትና ዋጋዉ በሚጨምርበት ሰዓት ከተገቢዉ በላይ በማትረፍ፣ ወይንም የፓለቲካ ደጋፊና አጋር በመሆኑ የተለየ ስራ ተመቻችቶላቸዉ የተለየ ጥቅም በማግኘት፣ ወይንም ካገኙት ትርፍ ለመንግሥት(ለሕዝብ) መክፈል የሚገባዉን ባለመክፈል ለግላቸዉ በመጠቀም፣ ወይንም ግልጽ ስርቆትና ዝርፊያ በማካሄድ፣ ወይንም በተመደቡበት ኃላፊነት በታማኝነት  ባለመስራት፣ ባጠቃለይ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም በማግኘት ነዉ፡፡

አንድ ነጋዴ ስለ ድካሙና ልፋቱ አንድ መቶ ሺህ ብር ማትረፍ የሚገባዉን ሁለት መቶ ሺህ ብር ቢያተርፍ ያ ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ ሊያገኝ ከሚገባዉ በላይ ሳይደክምና ሳይለፋ አገልግሎት ሳይሰጥ የሚከፈለዉ ክፍያ ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ አንድ ግለሰብ ከሌላ ግለሰብ ሆነ ከመንግሥት ባለሥልጣን ጋር ተሻርኮ በስዉር የሚሰራዉ ስራ ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ ግልጽ ባልሆነ ጨረታ ጥቂቶች ተባድነዉና አፍነዉ  የሚያገኙት አላስፈላጊ ትርፍ ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ በማጭበርበርና በማታለል የተገኘ ሀብት ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ በቁማር የተገኘ ገንዘብ ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ የድሆችን ጉልበት በመበዝበዝ የተገኘ ሀብት ንጹህ ሀብት አይደለም፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱ ባለ ሀብት መነሻዉና የሀብቱ ምንጭ ቢመረመርና ቢፈተሽ ከጀርባዉ አላግባብ የሆነ ገንዘብ ያገኘበት መንገድ አለ፡፡ ይህን ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ዓለም ያዉቀዋል፡፡ ምክንያቱም የዲያብሎስ የስግብግብነትና የስስት፣ የራስ ወዳድነት ሥርዓት የፈጠረዉ፤ ጥቂቶች በብልጣብልጥነትና በአቋራጭ መንገድ የከበሩበት ነዉ፡፡ እጅግ እጅግ እጅግ ብዙዉ ሕዝብ በድህነትና በችግር ሕይወት የሚኖርበት፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል የሌለበትና ጥቂቶች በሀብታቸዉ የበላይነታቸዉን አስጠብቀዉ በጨለማ ሥርዓት ዉስጥ ነግሠዉ የሚኖሩበት ነዉ፡፡

ሌላዉ ሁላችንም ልናዉቅ የሚገባን እነዚህ የምናያቸዉ ትላልቅ ሕንጻዎች፣ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎችኝ ፣ ሆቴሎች፣ የተለያዩ ተቋሞች … ወዘተ በባለሀብቱ ብቻ የተሰሩ ሳይሆን፤ በአብዛኛዉ በሕዝብ(በመንግሥት) ነዉ፡፡ ይኸዉም ከባንክ ብድር ወስደዉ የሰሩት ነዉ እንጂ ፈሰስ ያደረጉበት ገንዘብ የአብዛኛዎቹ ከ30 ፐርሰንት የማይበልጥ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየን እነሱ በኃላፊነትና በተጠሪነት ንብረቱን ይቆጣጠራሉ፣ ስራዉንም ይመራሉ እንጂ ንብረትነቱ የእነርሱ ብቻ ሳይሆን የሌላዉም ሕዝብ ሀብትና ንብረት  ጭምር ነዉ፡፡ ከሌሎች በበለጠ ስለደከሙበትና ስለለፉበት የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ እንጂ ሌላዉም ሕዝብ እንደ ድካሙና ልፋቱ ይጠቀምበታል፡፡ በቅርብ በባለቤትነት ስሜት ያስተዳድሩታል እንጂ ንብረትነቱ የሕዝብ ነዉ እንጂ የአንድ ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ ወይንም ቡድን ወይንም ድርጅት አይደለም፡፡ » **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሁለት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: ፈቃዶት ከሆነ ስለ አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ስለ ኮሎኔሌ መንግሥቱ፣ ስለ አቶ መለስ ዘመንና እንዲሁም በአሁን ሰዓት የኢትዮጵያ መንግሥት ተጠሪ ስለሆኑት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ስለ ሰብእናቸዉን የሚያዉቁትን ያህል ቢነግሩን?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ** : በእዉነቱ ስለ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሆነ ስለ ኮሎኔል መንግሥቱ ከመጻሕፍት ወይንም በወሬ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር በመመልከት ሆነ በመስማት አንዳች ነገር አላዉቅም:: ምክንያቱም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሕፃን የነበርኩ ሲሆን፤ በኮሎኔል መንግሥቱ ጊዜም ሕፃንና ልጅ የነበርኩ ከትምህርት ዉጭ አንዳች የማላስብ ነበረ:: ለብላቴ ዘመቻ የክፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች በተሰበሰቡበት ወቅት እንኳ ስለ ፖለቲካ ሆነ ስለአገር የተለየ ስሜት ስላልነበረኝ በስብሰባዉ አዳራሽ አልተገኘሁም:: በተማሪዎች ጥያቄ «ስልጠና እንግባ» የተባለዉ ተግባራዊ ሲሆንም፤ ጓደኞቼ ፈቃደኛ ሆነዉ ለስልጠና ሲዘጋጁ ተመልክቼ እኔም ፈቃደኛ ሆኜ ለስልጠና ተዘጋጅቼ ነበረ:: ምንም እንኳን ወንድሞቼ አቋሜን የደገፉ ቢሆንም አባቴ ያልደገፉትና ምክር የሰጡኝ ስለሆነ የአባቴን ቃል አክብሬ ከስልጠና ቀረሁ:: ሕወሓት(ኢሕአዴግ) አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ የተለያዩ ቡድኖችንና ድርጅቶችን አስባስቦ የሽግግር መንግሥት በሚመሰርበት ወቅት በቅንነት ሓሳብ ሁሉንም ጋብዞ ለአንድ አገርና ሕዝቡ ተፋቅረዉ እንዲያገለግሉ ዉስጤ የፈለገና አንዳንድ ድርጅቶችና ቡድኖች በወቅቱ ምክንያቱን ባላዉቅም እንዲካተቱ ባለማድረጉ ቅር የተሰኘሁበትም ጊዜ ነበር:: ከብዙ ዓመታት በኋላ ግን የማይታረቅ ሐሳብና አቋም ስላላቸዉ መሆኑን ላስተዉል ችያለሁ:: ከዚያም በምክንያት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ገባዉ:: የሃይማኖትና የአገር ፍቀር በዉስጤ መቀጣጠል ሲጀምር የኢሕአዴግ መንግሥት የዲያብሎስ እንደራሴ መሆኑን አስተዋልኩ:: በመጨረሻም የኢትዮጵያን ትንሣኤ መጠባበቅ ጀመርኩ::

በመሆኑም የወጣትነትና የጎልማስነት ዘመን ያሳለፍኩት በሕወሓት(ኢሕአዴግ) ዘመን ስለሆነ ስለ አቶ መለስ በተወሰነ ደረጃ መናገር እችላለሁ:: በኮሎኔል መንግሥቱ ዘመን ግን ወገን በወገኑ ላይ እንኳን ሊያደርግበት ይቅርና ሊያስበዉ የማይገባ እጅግ ዘግናኝና የጭካኔ ተግባር እንደተፈጸመና እሳቸዉም በዋና መሪነት እንዳስፈጸሙ ከሰዎች ሰምቻለሁ፤ ከመጻሕፍት አንብቤያለሁ:: አቶ መለስ የተገነዘብኳቸዉ ሕሊናቸዉን እንደፈለጉት ማድረግ የሚችሉ፣ የቡድኖች ሆነ የመንግሥታትን ፍላጎት የሚገባቸዉና እንደ ፍላጎታቸዉ መሆን የሚችሉ፣ ተለዋዋጭ አቋም ለማሳየት የማይቸገሩ፣ ለመበቀል ከፈለጉ ደግሞ በሕጋዊ ሽፋን የሚበቀሉ፣ ከስራቸዉ ያሉትን በራሳቸዉ አስተሳሰብ ለመቅረጽ የሚተጉ፣ ከእርሷቸዉ አቋም ዉጪ ያሉትን አንዳች ቦታ የማይሰጡና ለሥልጣናቸዉ አደገኛ ሆነዉ ከተጠረጠሩ በማንኛዉም መንገድ ከአጠገባቸዉ ለማስወገድ ወደ ኋላ የማይሉ፣ ያመኑበትን በማንኛዉም መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ቆራጥ የሆኑ፣ የተወሰነና የተገደበ ቅንነትና ትህትና ሊኖራቸዉ ቢችልም ዉስጣቸዉ ግን በቀልና ጥላቻ፣ ተንኮልና መሰሪነት የሞላባቸዉ፣ እንዲሁም በትዕቢትና በእብሪት የተሞላ ሕይወት የተላበሱ፣ አእምሯቸዉንና አንደበታቸዉን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አላዋሉትም እንጂ ንቁና የሰላ አንደበት ያላቸዉ ናቸዉ:: ባጠቃላይ ለጨለማዉ

ገኘ እንደ ልቡ የሆኑ ናቸዉ። አንዳንዴ ለዓላማቸዉ የሚያሳዩትን ቆራጥነትና ትጋት እንዲሁም ንቁና የሰላ አንደበታቸዉን ስለመለከት «ምናለ በንስሐና በእዉነተኛ ሕይወት እንዲሁም በጽኑ አቋም ሆነዉ በእግዚአብሔር አገልግሎት ቢሰለፉ ብዙ መልካም ፍሬ ሊያፈሩ ይችሉ ነበር» እያልኩ በእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ እንዲሰለፉ የምመኛቸዉ ጊዜ ነበር።

ስለ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም አሁን መናገር የምንችለበት ደረጃ ላይ ባንሆንም እግዚአብሔር የሚያናግረኝን ግን እነግራችኋለሁ። ወደ አገሪ መሪነት ከመጡ ገና የወራት እድሜ ያስቆጠሩ ስለሆነ ስለሚያፈሩት ፍሬ እንዲህ ነዉ ብሎ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ስለሳቸዉ ሰብእና በቅርበት የማላዉቅ ሲሆን፤ ከተለያዩ ጽሑፎችና አሰተያየቶች እንደተረዳዉት ቅንነትና መልካምነት ያላቸዉ ትሁትና ከሙስና የጸዱ መሆናቸዉን ነዉ። አሁን በተቀመጡበት ወንበር ላይ ሆነዉ የሚናገሩት ንግግር የሥጋና የደም ስሜታቸዉን ሊሆን ይችላል። ዉስጣቸዉ ደግሞ የእግዚአብሔርን እዉነትን የሚፈልግ ይሆናል። በሥጋና በደም ስሜት የሚነግሠዉ ደግሞ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ስለሆነ መልካምና እዉነተኛ ፍሬ ማፍራት አይቻልም። ምክንያቱም በበላይ የሚመራዉና የሚቆጣጠረዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ስለሆነ። አንድ በእርግጠኝነት መናገር የምፈልገዉ እኝህ መሪ «የማርያም ኃይል» የሚል ነዉ የስማቸዉ ስያሜ፤ በመሆኑም በማርያም ኃይል ከሆነ ወደወንበር የመጡት የዉስጣቸዉን እግዚአብሔርና እመቤታችን ስለሚያዉቁ ወደ ልባቸዉ ሊመለሱና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ሊሰለፉ እንዲሁም የዲያብሎስን ስራ ሊያጋልጡ ይችላሉ። ምክንያቱም በመርዝ የተቀመመዉ የአቶ መለስ ስብከት ስቧቸዉ ይሆናል ከዓመፃ ልጆች ጋር አብረዉ የተሰለፉት። ወደ ልባቸዉ ሲመለሱ አቶ መለስ የማን እንደራሴና ስራ አስፈጻሚ እንደነበሩ ስለሚያስተዉሉ አሁን እንደ አማልክት የሚመለከቷቸዉንና የሚቆጥሯቸዉን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አንቅረዉ ሊተፏቸዉና የሕወሓት ኢሕአዴግ የበቀልና የተንኮል አገዛዝን ሊያጋልጡና ሊያወግዙ ይችላሉ። እንዲሁም ለዓመፃ ልጆች «በእዉነተኛ ንስሐ ተመለሱ፣ ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር  ተሰለፉ፣ ወንበሩንም እግዚአብሔር ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ልቀቁ» ሊሉ ይችላሉ።

ከላይ የገለጽኩትን ለማለት የቻልኩት «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ ላይ የተቀመጠዉ በኢትዮጵያ ምድር በተዘጋጀዉና የተለያዩ አካላት ከአገር ወስጥም ከዉጭም በተሰባሰቡበት መድረክ ላይ ከሁሉም ክልሎችና የፓለቲካ ድርጅቶች በብቸኝነት ካለምንም ፍርሃትና ይሉኝታ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ ስለ እዉነት የመሰከረዉና የአቶ መለስ የበቀልና የተንኮል ተግባርን ያጋለጠዉ ተወካይ የደቡብ ኢትዮጵያ ተወካይ ስለሆነ፤ ያ ሰዉ ደግሞ እሳቸዉ ሊሆኑ ይችላሉ። ለማስታወስ ያህል በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ በገጽ263-266 ላይ

«በማስከተልም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ ፡- የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር(አቶ መለስ ዜናዊ)! እኛ እንኳን ደስ ያሎት ለማለት ይከብደናል። ምክንያቱም «ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለዴሞክራሲ የቆምን ነን» እያላችሁ፤ ይኸዉ  ዱሮ በአንድነት

ተጨፍልቀን እንድንኖር የተደረገብን ግፍና በደል በእናንተ ዘመን እንደገና መደገሙና ከአምሳ በላይ ብሔር ብሔረሰቦችን በአንድላይ ጨፍልቃችሁ በነፍጠኞች ቋንቋ እንድንነጋገር፣ እንድንግባባ፣ እንድንማርበት፣ እንድንሰራበት በመደረጉ ነዉ:: ከኛ መሀል እንኳ አንዳንድ ብሔሮችን እየመረጣችሁ በራሳቸዉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲናገሩ፣ እንዲማሩበት፣ እንዲሰሩበት ታደርጋላችሁ፤ ብዙዎቻችንን ግን በመጨፍለቅ ታስተዳድሩናላችሁ::

«ኢትዮጵያዉያን ናችሁ፤ በአንድ ላይ ኑሩ::» የሚሉን ከሆነና «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር መኖሯን ከልቦት ካመኑና «ኢትዮጵያዉያን» የሚባሉ ዜጎች መኖራቸዉን ካስተዋሉ፤ ይህን የተንኮልና የመሰሪነት እንዲሁም የበቀለኝነት አገዛዞትን ይተዉና በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ሳንከፋፈልና ሳንጠላላ እንዲሁም ሳንለያይ እንደ ኢትዮጵያዊነታችንና እንደ አዳም ዘርነታችን በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት እንድንኖር አድርጉ እንጂ በአንዱ ጎሳ ላይ አንዱን ጎሰ፤ በአንዱ ብሔር ላይ አንዱን ብሔር እያነሳሳችሁ በቋንቋ ሽፋን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ልክ እንደ ኤርትራ ለመገንጠልና ኢትዮጵያዊነት ዜግነትን ለማስካድ የምታደርጉትን የወደፊት ምኞታችሁንና እቅዳችሁን ለማስካትና የትግራይ አገርና ትግራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የኦሮሚያን አገርና ኦሮሚያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የአማሪያን አገርና አማራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሱማሊያን2 አገርንና ሱማሌያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ አፋሪያን አገርንና አፋራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሐረሪያን አገርና ሐረሪያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ጋምቤሊያን አገርና ጋምቤሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ቤንሻንጉሊያን አገርና ቤንሻንጉሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሲዳሚያን አገርና ሲዳማዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሃዲዩያን አገርና ሃዲያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ወላይቲያን አገርና ወላይታዉያን ዜጎችን ለመፍጠር.. ወዘተ ዜጎችን ፈጥረዉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለማጥፋት መነሳሳቶትን ያቁሙ:: በአሁን ሰዓት የክፋትና የተንኮል ተግባራችሁን ሕዝቡ በደንብ አዉቋል:: ዝም ያላችሁም በጦራችሁና በደጎንነታችሁ ኃይል ተመክታችሁ ስላስፈራራችሁት ነዉ እንጂ ከተፋችሁ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል:: በፊትም ተንኮላችሁ ስላልገባዉ ነዉ እርሱ በእርሱ የተጣላዉና የተገዳደለዉ፣ የተከፋፈለዉ::

ከጎኖትም የተሰለፉት እንሆዱ አምላካቸዉና የሥልጣን ጥመኞች ለጥቅም፣ ለክብር፣ ለዝና ሲሉ ሕሊናቸዉን የሚሸጡት ናቸዉ:: «በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳንባ ነዉ የሚተነፍሱ::» የሚባሉት ናቸዉ አብሮዎት ከልብ የሚያገለግሎት እንጂ ሕዝቡ ማንነታችሁን ስላወቀ ሁሉን ነገር ትቶ ለአምላኩ እጁን ከሰጠ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል:: አብሮት ያሉት የሚያጫፍሮትም ጊዜ እስከሚካዳዎት ነዉ እንጂ ወደ ልባቸዉ ሲመለሱና የማን እንደራሴ መሆኖትን ሲያስተዉሉ አንቅረዉ ነዉ የሚተፎት:: ስለዚህ እርሶም ቢሆን ወደልቦት ተመልሰዉ እጆትን ለፈጣሪ ቢሰጡና ወንበሩንም በእግዚአብሔር ለተመረጡትና ለተቀቡት ለእዉነተኛ እንደራሴዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ቢለቁ ያተርፋሉ እንጂ አይጎዱም:: እንቢ ብለዉ እንደፈርኦን ሕሊናዎን ካደነደኑ ደግሞ ደንዳናዎች የገጠማቸንዉን ጽዋ እንደሚጎነጩ አንዳች አይጠራጠሩ::

ከዛሬ ቀን ጀምሮ ስለኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት ለማዉራት ብቃቱና ሞራሉ ስለሌሎት ከእርሶና ከቢጤዎቾ ጋር ምንም አንድነትና ኅብረት ፈጥረን የዓመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር አንሰራም፤ ተባባሪም አንሆንም፡፡ እናንተ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፓሊሲ አራማጆች፤ በብሔር ብሔረሰቦች ስም የምትነግዱ፤ ሕሊናችሁን የምትገለባብጡና የምትሸጡ አስመሳይ አገልጋዮች፤ የዲያብሎስ ሥርዓት ፈጻሚና አስፈጻሚ ሆናችሁ ሕዝቡን መከራዉንና ፍዳዉን የምታሳዩ፤ እርስ በእርስ እያጣላችሁና እየከፋፈላችሁ የራሳችሁን መሰሪ ተግባር የምትፈጽሙ፤ ስለ ክፋትና ጭከና ተግባራችሁ ዋጋ እንደምትከፍሉበት ልታዉቁ ይገባል፡፡

ሕሊናችሁ በክህደት ፍልስፍና የተሞላ፤ የማርክስ፣ የኤንግልስ፣ የሌኒን፣ የቻርልስ ዳርዊን የመሳሰሉት የክህደት እምነቶችን አምጥታችሁ « ዘሮቻችሁ  አዳምና  ሔዋን ሳይሆኑ ጦጣ መሰል እንስሳዎች ናቸዉ፡፡ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ ሰዉ የሆናችሁት፡፡ አምላክ የሚባል ያመጡት እናንተን ለመጨቆኛ መሳሪያ እንዲሆናቸዉ የገዥ መደቦች ናቸዉ፡፡» በማለት የምትናገሩና የምታስተምሩ አንዳች ሃፍረት የማይታይባችሁ ከሃዲዎች ናችሁ፡፡ እዉነተኛ ማንነታችንን ያስካዳችሁና አሁን ደግሞ በቋንቋ ለያይታችሁን እርስ በእርስ በጥላቻና በቂም በቀል እንድንመላለስ ያደረጋችሁ ዓመጸኞች ናችሁ፡፡ አሁን ግን ልታፍሩ ይገባችኋል፡፡

እኛ የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆቹ የሆን ዘሮቻችንም ጦጣዎች መሰል እንስሳት ሳይሆኑ የከበሩ ሕያዋን ፍጥረቶች አዳምና ሔዋን ናቸዉ፡፡ ነገዳችንም የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዉህድ ዘር የሆነዉ ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ ብሔራችንም ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነዉ፡፡ እናንተ ግን እዉነተኛ ማንነታቸንን እያጠፋችሁ «የማንነታችሁ መለያ የሆነዉ ቋንቋችሁ ነዉ» በማለት የራሳችሁን መሰሪ ፍላጎት ማሟያ አደረጋችሁን፡፡ ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠችና አገራት እየተዋሀዱ ባለበት ዘመን እናንተ ትንሺን አገር በጎጥ ከፋፍላችሁ፣ ምንም እንደማናዉቅ ሰዎች አድርጋችሁ በመቁጠር « ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ፡፡ ያ ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ፡፡ ብሔር ብሔረሰቦች ዙፋን ላይ ስላስቀመጥናችሁ ለሥልጣናችሁና ለክብራችሁ ዙፋኑን ላለመልቀቅ እስከ መጨረሻዉ ድረስ የሞት ሽረት ማድረግ አለባችሁ፡፡» በማለት እንኳን የተማረ ፊደል የቆጠረ አይደለም ሀ ሁ ን እንኳ የማያዉቅ መሃይም ይህን አስተሳሰብ ፈጥሮ ኢትዮጵያዉያንን አያጻጅልም ነበር፡፡ እናንተ ግን ተማርን የምትሉ ይህን ለመፍጠርና ወደ ተግባር ለመለወጥ ኅሊናችሁ ፈቃደኛ ሆነ፡፡ ወደተግባርም ለወጠዉ፡፡ ይህም አስገራሚ ፍጡሮች መሆናችሁን ነዉ የሚያሳየዉ፡፡» በማለት በምሬት እየተናገሩ እያለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕግስታቸዉ አልቆ ወዲያዉ ወደ ልዩ እስርቤት ተይዘዉ እንዲሄዱ ትእዛዝ ለሚመለከተዉ አካል በመስጠታቸዉ፤ ተወካይ ተናጋሪዉ ለሰዉ ርኅራኄ በሌላቸዉ ልዩ ኃይሎች እየተዳፉና እየተቀጠቀጡ ተወሰዱ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩም(አቶ መለስ ዜናዊ) ከተቀመጡበት በቁጣና በንዴት ተነስተዉ «የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮችና የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ተወካዮች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ተወካይ በስተቀር ሁላችሁም አርቆ አሳቢና አስተዋይ መሆናችሁን

ንግግራችሁ ይገልጻል:: ለዚህም በታላቁ መሪያችንና ገዥያችን ስም አመሰግናችኋለሁ:: እስከዛሬ ድረስ ጨርቁን ሰንደቅ ዓላማና አዲሲቷን ኢትዮጵያ በትዕግስት የጠበኩት በቅድሚያ መስተካከል ያለባቸዉ ነገሮች እንዲስተካከሉ በማሰብ ስለነበረ አሁን በምንፈልገዉ የኢኮኖሚ፣ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ ደረጃ ስለደረስን ከሚከጥለዉ ዓመት ጀምሮ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ነጻ መንግስትን መስርቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚለዉን ስም ከምድረ ገጽ ማጥፋት ይችላል::

እኔ ተልእኮዬንና ሩጫዬን ጨርሻለሁ:: እናንተ አጉል ተስፈኞች «የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይመጣል::» በማለት የምትጠባበቁ ከዛሬ ጀምሮ ተስፋችሁን ሙሉ በሙሉ ልትቆርጡ ይገባል:: ከፈለጋችሁ ወደ አዉሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤሽያና አረብ አገራት መሰደድ ትችላላችሁ:: ከሚቀጥለዉ ዓመት ፳፻፭(2005) ጀምሮ «ኢትዮጵያ » የሚባል ስም በብሔር ብሔረሰቦች አገራት አይጠራም» በማለት ንግግራቸዉን የቋጩ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥና የእሳቸዉ ደጋፊዎች በንግግራቸዉና በዉሳኔያቸዉ ደስታችንንና ጭፈራችንን በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ዳንኪራ ሳናጣጥም እንዲሁም አንዳንዶች የስብሰባዉ ተሳታፊዎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ከመደሰታቸዉ የተነሳ ራሳቸዉን እስከሚስቱ ሲዘሉና ሲፈነድቁ እንዳለ፤... » በማለት ቀርቧል::

**ይህም የሚያሳየን** በመጀመሪያ ላይ ባለማወቅና ባለማስተዋል በተግባራቸዉ አብረዉ መሰለፋቸዉንና ወደ ልባቸዉ ሲመለሱ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት የተንኮል፣ የመሰሪነት ፣ የበቀል አገዛዝ መሆኑንና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተሰለፉ መሆናቸዉን በሚረዱበትና በሚያስተዉሉበት ወቅት የዓመፃ ስራቸዉን እንደሚቃወሙና እንደሚመሰክሩባቸዉ ነዉ::

**ያ የደቡብ ተወካይ እሳቸዉ ይሁኑ ሌላ ሰዉ በእርግጠኝነት የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ነዉ::** በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተመረጡ ከሆነ ደግሞ ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይሰለፋሉ:: እዚህ ላይ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ሁሉ ማወቅ ያለባቸዉ፤ ይህችን ዓለምንና ሕዝቧን በበላይ በእናትነት ርኅራኄዋና ፍቅሯ እንድታስተዳድር የተደረገችዉ እመቤታችን ናት:: ምክንያቱም በገነት ዉስጥ አዳምና ሔዋን ለሁሉም ነፍሳት(የሰዉ ዘሮች) በአባትነትና በእናትነት እንዲያስተዳድሩ ሙሉ ሥልጣን ተሰቷቸዉ፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ ባለመገኘታቸዉ ምክንያት ሥልጣናቸዉ ተሽሮ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆና የተገኘችዉና ለእግዚአብሔር እናትነት የበቃችዉ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያ ሥልጣን ስለተሰጠ ነዉ:: በመሆኑም በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ እዉነተኞችና ቅኖች እንዲሁም የእርሷ ባለሟሎችና ወዳጆች ብቻ ናቸዉ በእዉነተኛዉ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙትና የሚያስፈጽሙት:: ምንም እንኳን በአሁን ሰዓት አቶ ኃይለማሪያም በስሟ ብቻ የሚጠሩ የካዷትና እግዚአብሔርም በአንድነትና በሦስትነት እንደሚመለክ የማያምኑንና ሥላሴን የካዱ ቢሆንም፤ የወደፊቱን ግን እግዚአብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: አሁንም ቢሆን የልባቸዉን እግዚአብሔር ነዉና የሚያዉቀዉ ወደ እናትነት ፍቅሯና ወደ ሙሉ እዉነት ሊመጡ ይችላሉ:: እንኳ በእግዚአብሔር ወልድ(በእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ) የሚያምነዉ አይደለም የማያምነዉ ሰዉ እንኳ ተመርጧል:: ምክንያቱም ቅንነትና እዉነተኛነት የተላበሱ ሰዎች፤

እዉነት ባለጊዜ ስትሆን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ወደ ሙሉ እዉነት ለመምጣት ለፈጣሪ አምላክ አያስቸግሩትምና፡፡

እንግዲህ ወደ ወንበር የወጡት በእርሷ ኃይል ይሁን በጨለማዉ ገዥ ኃይል በእጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ለመስጠት የምፈልገዉ ማሳሰቢያና ፈቃደኛ ለሆናችሁ ሰዎች የማቀርበዉ ጥያቄ፤ የእርሳቸዉን አድራሻ የምታዉቁ ሰዎች ወይንም አካላት ያለፉትን ሆነ የአሁኑን የእግዚአብሔርን መልእክት እንዲደርሳቸዉ ብታደርጉ፡፡ የእርሳቸዉን አድራሻ ማግኘት ባትችሉ እንኳ በቤተሰባቸዉ ወይንም በቅርብ ወዳጆቻቸዉና ጋደኞቻቸዉ አማካይነት እንዲደርሳቸዉ ብታደርጉ፡፡ ምክንያቱም ለራሳቸዉ ሆነ ለመንግሥታቸዉ የሚበጀዉን ሊያደርጉ ይችላሉና፡፡ ማን ያዉቃል! እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ በቁጣዉ ገስጿቸዉ ለታላቅ አገልግሎት ቢያበቃቸዉ? ማን ያዉቃል! ሌሎችም ባለማወቅና ባለማስተዋል እንዲሁም በቅንነት አብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነትን የተቀበሉና በዚሁ እምነት የተለከፉ ሰዎች፣ ከአምላክ ፌዉስን አግኝተዉ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ቢመሰክሩ? ማን ያዉቃል! ከማንም በላይ ስለ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋድሎ ቢያደርጉ? ማነዉ የእያንዳንዱን ልቦና የሚያዉቅ? እግዚአብሔር አይደለምን? እግዚአብሔርና እመቤታችን ድንግል ማርያም የመረጡትን ማነዉ «አልቀበልም» ሊል የሚችል? ማንስ ምንስ ሥልጣን አለዉና ነዉ ከእግዚአብሔርና ከእመቤታችን የሆኑትን «አልቀበልም» ሊል የሚችለዉ!

ጠያቂዉ አገልጋይ፡ ሁሉም ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ከላይ ከአገር መሪዉ እስከታች ድረስ ያሉ ባለሥልጣናት ወደ ወንበር ሲወጡ ራሳቸዉን የተለየ አደርገዉ ይቆጥራሉ፡፡ በሰዎች እንዲገኑና እንዲመለኩ ይፈልጋሉ፡፡ ራሳቸዉንም እንደ አድራጊ ፈላጭ ቆራጭ አድርገዉ ይቆጥራሉ፡፡ ከዚያ ከፍታ ቦታ ላይ ሲወርዱ ደግሞ እንደ ዉርደትና ክብር ማጣት አይተዉ፤ ያንን ወንበር ላለማጣት ሕሊናን ከመሸጥ ጀምሮ የግፍና የጭከና ተግባር ከመፈጸም ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ይህ ለምን ይመስሎታል?

መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡ እኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማወቅ ያለን አሁን በዓለም ላይ ባላዉ ሥርዓት ላይ ነግሦ ያለዉና በበላይ ሆኖ የእያንዳንዱን አገር መሪና ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎችን የሚመራዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ እንደ ልቡ ሆነዉለት ስላገኛቸዉ ነዉ እንጂ፤ እግዚአብሔር የእርሱ አገልጋይ ባሪያ እንዲሆኑ ወስኖባቸዉ አይደለም፡፡ ለዚህም ነዉ የዉስጥ ሰላምና ርካታ ስለሌላቸዉ ወደ ወንበር ሲወጡ ያን እርካታና ሰላም የሚያገኙ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን በባሰ ሁኔታ ባዶነት ስለሚሰማቸዉ፤ ይኸዉም የሚዋሐዳቸዉ የዲይብሎስ መንፈስ፤ ዓላማዉንና ፈቃዱን ለማስፈጸም በሕሊናቸዉ ስለሚነግሥ ራሳቸዉን የተለየ አደርገዉ በመቁጠር በሰዎች እንዲገኑና እዲመለኩ እንዲሁም እንዲታጀቡ ይፈልጋሉ፡፡ ራሳቸዉንም ከፍታ ወንበር ላይ ስለሚያስቀምጡና ተስፋቸዉ ምድር ብቻ ስለሆነች፤ ከዚያ ወንበር ከወረዱ ሰማይና ምድር የሚደበላለቅባቸዉ ስለሚመስላቸዉ፤ በማንኛዉም መንገድ በዚያ ወንበርና በዚያ ዙሪያ መቀመጥ ነዉ የሚፈልጉት፡፡

በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሕሊና ቢኖራቸዉ ኖሮ ከፍ ወዳለዉ ወንበር በወጡ ቁጥር የበለጠ የሕዝብና የምእመናን አገልጋይ ወይንም ባሪያ መሆናቸዉን ተገንዝበዉ ሕዝቡንና ምእመኑን ራሳቸዉን ዝቅ አድረገዉ በትህትና ያገለግላሉ እንጂ መግነንና መመስገንን እንዲሁም መመለክን አይፈልጉም ነበር:: ምክንያቱም የሕሊናቸዉ ሰላምና ርካታ በመንፈስ ቅዱስ የተጠበቀ ስለሆነ ከሰዉ በመመስገን ወይንም በመታጀብ ወይንም በመግነን የሚፈልጉት ርካታ ሆነ ሰላም የለምና:: ማንም ከሚያገኘዉ በላይ የሕሊና ርካታ ስለሚኖራቸዉ፤ ሁል ጊዜ ከፍ ያለዉን እርካታና ደስታ ለማግኘት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ የሚተጉት እንጂ እንደ አሕዛብ እንደተለየ ተደርገዉ እንዲቆጠሩና እንዲገኑ፣ እንዲመለኩ አይፈልጉም:: የአሕዛብ ነገሥታትና ባለሥልጣናት ናቸዉ ራሳቸዉን ከሰዉ በላይ አድርገዉ የሚቆጥሩትና እንደ አማልክት እንዲታዩ የሚፈልጉት:: የእግዚአብሔር አገልጋዮች ደግሞ ማንነታቸዉ እንዳይታወቅ ራሳቸዉን ሰዉረዉ ነዉ የሚኖሩትና እግዚአብሔር በሕዝብ ፊት ቢገልጻቸዉ እንኳ ራሳቸዉን እንደ ተራ በመቁጠር ከሕዝቡ ጋር እንደ ሕዝብ ሆነዉ ይኖራሉ እንጂ ራሳቸዉን በከፍታ ወንበር ላይ አያስቀምጡም:: ሹመቱንና የተለየ መገለጫዉን የሚቀበሉት አግባብ ያለዉን ሥርዓትና ትዉፊት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ነዉ እንጂ እንጂ አንዳች የተለየ ሹመት ሆነ መገለጫ አይፈልጉም::

ወደዘመኑ የኢትዮጵያ መሪዎችና ባለሥልጣናት ስንመጣ፤ እነርሱ በለመዱት ማስመሰልና ሽንገላ ቋንቋ «እኛ አብዮተኛ ነን፣ እኛ ተረማጅ ነን ፣... ወዘተ» እያሉ ንጉሥ የሚለዉን ስያሜ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርና ፕሬዝዳንት እየለወጡ ይጠቀሙበታል፤ ንግሥት የሚለዉን ወደ ቀዳማዊት እመቤት እየለወጡ ይጠቀሙበታል፤ «እኛ ጓድ ነን» ይላሉ እንጂ የተከበሩና ክቡር እየተባሉ ይጠረቡታል:: ነገር ግን ራሳቸዉን የተለየ አድርገዉ የቀረቡ ይመስል የቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችንን ይቃወማሉ፣ ይተቻሉ፣ ያጥላላሉ:: ይህ ደግሞ የራሳቸዉን ገበናና ባዶነት የሚገልጽ ነዉ:: አንዳንዶቹማ የተወሰነዉ ማዕረግ አልበቃ ብሏቸዉ አንድ ሉክ የሚሞላ የሥልጣን ማዕረግ ተሸክመዉ አንዱም ሳይቀነስባቸዉ እንዲጠሩ የሚፈልጉ ባዶነት የሚሰማቸዉ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ከዚህ ጋር በተያያዘ የምጠይቀዉ በቅርቡ በአቶ መለስ ዜናዉ ምትክ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር መሾሙ ይታወቃል:: ነገር ግን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በወቅቱ የሚገባቸዉ ቦታና መኖሪያ እንዲሁም ክብር አልተሰጣቸዉም:: እንዲሁም የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስተር ባለቤት ከቤተመንግሥት መዉጣት ሞት መስሎ ስለታያቸዉ ለመዉጣት ሲያንገራግሩ ነበር:: ለዚህ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ቀደም ብዬ እንገለጽኩት የቀድመዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ወይዘሮ አዜብ መስፍን ሆኑ ሌሎች ባለሥልጣናት አሕዛባዊ በሆነ ሕይወትና ኑሮ ስለሚመላለሱ፤ እንዲሁም ተስፋችዉ ምድር ስለሆነች ለእነርሱ ሥልጣኑና የሚሰጣቸዉ የክብር ስም የተለየ አድርገዉ ስለሚቆጥሩት፣ ካሉበት ደረጃና ስያሜ መዉረድ እንደ ሞት ሊታያቸዉና ሰማይን ምድር እንደሚደበላለቀባቸዉ አድርገዉ ሊቆጥሩት ይችላሉ:: ወይዘሮ አዜብ ቢያንስ ከማንም በላይ

ከባለቤታቸዉ ሞት ሊማሩ ይገባ ነበር:: ምክንያቱም ባለቤታቸዉ አቶ መለስ ዜናዊ በእግዚአብሔር ቁጣ ለምስልና ለድምፅ በማይሆን መልኩ መሞታቸዉንና በእግዚአብሔር ጭብጥ ዉስጥ መሆናቸዉን ተመልክተዉ ሳለ፤ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸዉን በማዋረድ ሌሎቹንም ባለሥልጣናት «ያለፈዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ዘመናችን ይብቃን፤ በጭብጡ ዉስጥ ለሆነዉ ለእግዚአብሔር እጃችንን እንስጥ፤ የትዕቢትና የእብሪት ሕይወትና ተግባር ለመለስ እንኳ አልበጀዉም፤... ወዘተ» በማለት ራሳቸዉን ለእዉነተኛ ንስሐ ማብቃትና ለቅን ሐሳብ፣ ለመልካም ተግባር፣ ለእዉነተኛ ሕይወት ማሰለፍ ሲጠበቅባቸዉ፤ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት የበለጠዉን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም ቆረጠዉ ተነስተዋል:: አሁንም በዉስጣቸዉ የነገሠዉ የጥላቻና የበቀል መንፈስ አልራቀላቸዉም:: ከባለቤታቸዉ ሞት ምንም ትምህርት አልወሰዱም፤ በእልኸኝነት ቆመዋል:: አቶ መለስ የሚጠየቁበት ነፍስ ከሥጋቸዉ እስከተለየች ድረስ ስለፈጸሙትና ስላስፈጸሙት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርና ንግግር እንዲሁም ሐሳብ ጭምር ነዉ እንጂ ከዚያ ወዲህ ስለተፈጸመዉና ስለሚፈጸመዉ አንዳች አይጠየቁበትም:: ወ/ሮ አዜብና ሌሎቹ ባለሥልጣናት ግን እስከ አሁን ያለዉን ወደፊትም ነፍስ ከሥጋቸዉ እስከምትለይ ድረስ የሚፈጽሙት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርና ንግግር እንዲሁም ሐሳብ ያስጠይቃቸዋል፤ ዋጋም በምድርም በሰማይም ያስከፍላቸዋል::

አቶ መለስ ምናልባት የተገደበዉና የተወሰነዉ ቅንነታቸዉና መልካምነታቸዉ ይሆናል ለክብር መቀበር ያበቃቸዉ:: ሌሎቹ ግን ዉስጣቸዉ ጥላቻና በቀል ሞልቶ በዓመፃቸዉ የጸኑት እንኳን በክብር ለመቀበር አይደለም በክብር ለመሞት ላይበቁ ይችላሉ:: ምክንያቱም ያመልኩትና እንደተለየ አድርገዉ ይቆጥሩት የነበረዉ «ታላቁ መሪያችን» የሚሉት ሰዉ፤ ተራ ሰዉ፣ በእግዚአብሔር ጭብጥ ዉስጥ ያለ፣ እግዚአብሔርም የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜና መንገድ ማከናወን እንደሚችል እያዩ፤ አሁንም በእግዚአብሔር ቦታ ላይ አስቀምጠዉ እያመለኩትና እያስመለኩት እንዲሁም ትዉልዱን እያደነዘዙበትና እየነገዱበት በመሆኑ ለከፋዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሊዳረጉና ከምድርም ሊጠረጉ ይችላሉ::» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል::**

## ምዕራፍ ሦስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዶክተር አባ ጳዉሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጬጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት ሞት ምን ተሰማዎ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: በመጀመሪያ እኛ በቅዱሱ ኪዳን በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት የምናምንና እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ የምናመልክ አገልጋዮች ሆን ምእመን በተለያየ አገልግሎት ላይ ተሰልፎ በሥጋ የተለየን አገልጋይ ሆነ ምእመን ከዚህች ከኀስቋላ ዓለም ተገላገለ፣ ዐረፈ ነዉ የምንለዉ እንጂ ሞተ አንልም:: ምክንያቱም ረቀቅ አካል ተላብሶ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታ ነዉና የሚሄደዉ:: ነገር ግን በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት ሆኖ ነፍስ ከሥጋዉ የተለየች ሰዉ ግን እንደ ርኩሳን መናፍስት በረቂቅ አካል ሆኖ ወደከፋዉ የቅጣት ቦታ ስለሚሄድ የሞት ሞት ስለሚያጋጥመዉ በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቱን ሰዉ ሞተ እንላለን::

ይህ የተንዛዛ ስም አጠራር ብዙዉን ጊዜ የሚወዱት አምባገነን መሪዎች ሲሆኑ፤ ዓለም ከአምባገነን መሪዎች ለመገላገል ትግል ዉስጥ ባለችበት ወቅት በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት ሲሚሚቱለት መመልከቱ እጅግ ያሳዝናል፣ ይዘገንናል:: ምንም እንኳ በተለያየ ምክንያት የሚሰጥ የማዕረግ ስም እንደ አስፈላጊነቱ ቢጠራ ችግር ባይኖረዉም በእኛ ቤተክርስቲያን የሚታየዉ ግን አንዴ ሙሉ ስሙ በመድረክ ከተጠራ በኋላ ቀጣይ ተናጋሪዉም መርሐግብሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ያንኑ እንደ አቡነ ዘበሰማያት ከመደጋገም አጠር አድርገዉ «በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዉሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ» ብቻ ተብሎ ቢጠሩ መልካም ነበር:: እንኳን ቀጣይ ያሉት ተናጋሪዎች ቀርቶ የመጀመሪያዉ ተናጋሪ በድጋሜ ስማቸዉን የሚጠራበት አጋጣሚ ካለ ያ የተንዛዛ ማዕረግ አንዱንም ሳይቀንስ ነዉ በመደጋጋም የሚጠራዉ:: ይህም የሆነበት አንዱ ምክንያት እሳቸዉን በመፍራትና እንዲሁም «እንዳዋረድኳቸዉ በመቁጠር ከሹመቴ ወይንም ከአገልግሎቴ ያወርዱኛል» በሚል ስጋትና፤ ሌላዉ ደግሞ በእሳቸዉ ዘንድ ለመወደድና የተለየ ቦታ ለማግኘት ሲሉ ነዉ በአንድ መድረክ ላይ በተደጋጋሚ ይህን አሰልቺ መጠሪያ የሚጠሩት:: ይህ የሚያሳየን ደግሞ ፓትርያርኩ እንዲህ ተደጋግሞ ሲጠራ ደስ የሚላቸዉና የሚፈልጉት መሆኑን ነዉ :: ምክንያቱም የማይፈልጉትና የማይወዱት ቢሆን ኖሮ በመድረክ «አስፈላጊ ሆነ ከተገኘ አንዴ ይህን ስም ከጠራችሁ ደጋግማችሁ በእዚህ ስም አትጥሩኝ፤ እኔ አገልጋያችሁ ስለሆንኩ አጭሩን መለያ ስሜን ብቻ ጥሩ» በማለት ሌሎቹን ይህን አጠራር እንዳይከተሉ ሊመክሩና ሊያሳስቡ ይችሉ ነበር:: ያኔ ሁሉም ከፍርሃት ርቆ አግባብነት ያለዉን የማዕረግ ሥልጣናቸዉን በመጥራትና በመጻፍ የተንዛዘዉንና ጊዜና ወረቀት የሚፈጀዉ ማዕረግ መፍትሔ ያገኝ ነበር:: ያለዉ እዉነታ ግን መግነንና መመለክን እንዲሁም መመስገን ስለሚፈልጉ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያለ ቅኔ የሚያቀርብላቸዉንና ከሰማያዊ መላእክት እኩል ቆጥሮና ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ «ቅዱስ አባታችን» እያለ የሚሸነግላቸዉን ሰዉ

በሹመት ላይ ሹመት፣ በክብር ላይ ክብር በመስጠት ሕይወቱንና ተግባሩን ሳያጠኑና ሳይመክሩ በተለያየ የኃላፊነት ቦታ ላይ በማስቀመጥ በቤተክርስቲያን ላይ የተለያየ በደልና አድሎ እንዲሁም የዓመፃና የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እንዲፈጸም አስደርገዋል።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ** እንኳን በግሌ አንዳች በደል ሆነ ተጽህኖ ያልፈጠሩብኝ በእዉነተኛ ዉ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ አባት አይደለም፤ «እስከ አሁን በደልና አድሎ ፈጠረብኝ» የምለዉ ሰዉ ባይኖርም፤ ቢኖር እንኳ «ሞተ» ሲባል ያሳዝናል። ነገር ግን የእርሳቸዉ ጋሻ ጃግሬ ሆነዉ እየሸነገሏቸዉ እንደፈለጉ የሚያሽከረክሯቸዉ የሴት ወይዘሮና አንዳንድ ቆብ ደፊዎች እንዲሁም በማፊያነት ተግባራቸዉ በቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ቁልፍ ቦታ ላይ የተቀመጡ ሌቦች፣ ቀማኞች፣ ሴሰኞች፣ አመንዝሪዎች፣ ዘማዉያንና ወንበዴዎች፣ ባጠቃላይ በተለያየ የከፋ ኃጢአት የተዘፈቁ የእዉነትና የቤተክረስቲያን ፀሮች፣ አሰናካይና እንቅፋት የሆኑ አስመሳይ አገልጋዮች በሚፈጽሙት የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር የተማረሩና የሚያነቡ ሰዎች የእርሳቸዉን በእግዚአብሔር ቁጣ ሞት መጠራት ለቤተክርስቲያን ትንሣኤ መንገድ እንደከፈተ አድርገዉ በመቁጥር በአኮቴት ነዉ የተቀበሉት።

ሌላዉ ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት ጋር በአንድ ወቅት መጠራታቸዉ የሚያሳየን በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የማስቀመጥ ሆነ የማንሳት ሥልጣኑ የአንዱ ፈጣሪ የእግዚአብሔረ ብቻ መሆኑንና ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ በምድር በሚቆይበት ዘመን እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትንና ለሰማያዊ መንግሥት የሚያበቃ ተግባር ፈጽሞ መገኘት ነዉ። ትዉልዱ ግን ይህን ያስተዋለ አይመስለኝም። ምክንያቱም የሁለቱም ሞት በአጋጣሚ የተከሰተ አድርጎ በመገመት ቀሪዎቹ በወንበር ላይ ለመዉጣትና ለማስወጣት ተነሳሱ እንጂ አንድም ሰዉ እጁን ለእግዚአብሔር በመስጠት በእዉነተኛ ንስሐ አልተመለሰም። ወንበሩንም እግዚአብሔር ለእንደራሴነት ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ባለሟሎቹ ለማስረከብ ፈቃደኛ አልሆነም። በዚህም ምክንያት እጃቸዉን እስከሚሰጡና ወንበሩን ለእዉነተኛ አገልጋዮች እስከሚለቁ ድረስ የእግዚአብሔር ቁጣ ይበረታባቸዋል እንጂ በቅርቡ በኢትዮጵያ ምድር የሚቋቋመዉን የእግዚአብሔር መንግሥት(ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተመንግሥቱ በአንድ ላይ ተዋሕዶ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበት ሰማያዊ ሥርዓት) ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ አይደለም ለአንድ ቀን ሊያዘገየዉ አይችልም። እያንዳንዱ ዓመፀኛ አይቀጡ አቀጣጥ እየተቀጣ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ዓለም ይሄዳል እንጂ እግዚአብሔር የሚያመጣዉን የኢትዮጵያ ትንሣኤ ማንም ፍጡር አያስቀርም።

እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገዉ ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስ፤ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት የመገናኛ ብዙኃን(ማስ ሚዲያ) ሰፊ ሽፋንና ቅስቀሳ ቢያገኙ ኖሮ፣ በሕይወተ ሥጋ እያሉ «ታላቅ አባት፣ ብቸኛ ታሪክ ሰሪ፣ ቅዱስ አባት፣... ወዘተ ናቸዉ » የሚል ስያሜ በመስጠት በየአብያተክርስቲያኑ እንደ ቅዱሳንና ጻድቃን ሥዕላቸዉ እንዲሰቀል ያደረጉና ሐዉልታቸዉን በአብያተክርስቲያኑ ዉስጥ ለማቆም ቆርጠዉ የተሰለፉና ያቆሙ አስመሳይ አገልጋዮችና አስመሳይ አማኞች፤ «በታሪክ አጋጣሚ የተከሰቱ ልዩ ታሪክ ሰሪ፣ የአፍሪካዉያንና የሰዉ ዘሮች ልዩ ዕንቁ፣

ቅድስናቸዉ ከቅዱሳን መላእክት የሚበልጥ እንጂ የማይተናነስ ፣ በአገር አቀፍ ሆነ በዓለም አቀፍ ታላቅነታቸዉና ቅድስናቸዉ የተመሰከረላቸዉ፣ ቤተክርስቲንን ለታላቅ ማዕረግ ያበቁ፣ ሕያዉ ተግባር የፈጸሙ... ወዘተ» በማለት እንደ አቶ መለስ አጽም፤ «በሙዝየም አስቀምጠን ለዘላለም እንዘክረዋለን፣ እናመሰግነዋለን» በማለት ብቻ ሳይወሰኑ «ቅድስናቸዉ የተረጋገጠ ስለሆነ ታቦት ተቀርጾላቸዉ ቤተክርስቲያን ሊሰየምላቸዉ ይገባል» በማለት ጭምር የሚያገኗቸዉና የሚመልኳቸዉ እነ ሆዱ አምላኩና እንደ ጥቅሙና ክብሩ ከሕሊናቸዉ በላይ የሆኑ፣ ለሕሊቸዉና ለአምላካቸዉ ያልታመኑ ግብረ አበሮቻቸዉን፣ የጥቅም ተጋሪዎቻቸዉን፣ ብዙ አስመሳዮችን በየመድረኩና በየአደባባዩ ምስክርነትን ሲሰጡ  እንመለከት ነበር:: ይሁንና መግነኑን በምድር በሕይወተ ሥጋ እያሉ ስለጨረሱት፤ በምድር መግነንን ያልጨረሱት የአቶ መለስ ሞት በአናታቸዉ ላይ መቶ ብዙ ሽፋን ሳይገኙ ቀርቷል:: ምክንያቱም ሥጋዉያን ብዙኃን መገናኛን(ማስ ሚዲያን) የሚጠቀሙበት ለፖለቲካ ፍጆታ የሚጠቅም ከሆነ ነዉ እንጂ አንዳች ጥቅም ካለተገኘበት ምን ያህል ለአገር ታሪክ የሰራና ኢትዮጵያን ያስጠራ ታላቅ ሰዉ ቢሆን እንኳ፣ አንዳች እንዲነገርለት የማይፈልጉ፤ ዉስጣቸዉ በጥላቻና በበቀል የተሞላ ፍጹም የጨለማዉ ገዥ አገልጋዮች ናቸዉና::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ስለፓትርያርክ አባ ቴዎፍሎስ፣ ስለፓትርያርክ አባ ተክለሃይማኖት፣ ስለፓትርያርክ አባ መርቆርዮስ፣ ስለ ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስ የሚያዉቁትን ያህል ቢገልጹልን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በፓትርያርክ አባ ቴዎፍሎስ ጊዜ ሕፃን ስለነበርኩ ከሚነገረዉና ከሚጻፈዉ ዉጭ ምንም የማዉቀዉ ነገር የለም:: በፓትርያርክ አባ ተክለሃይማኖት ጊዜም ልጅ ስለነበርኩ ብዙም የማዉቀዉ ነገር የለም:: ነገር ግን በልጅነት እድሜዬ ፓትርያርክ ይመርቀዋል ተብሎ በማይጠበቅበት አነስተኛ የገጠር ከተማ ከሌሎች ጳጳሳት ጋር በመሆን መተዉ ቤተክርስቲያን ሲመርቁ ተመልክቻለሁ:: ኑሮዋቸዉም የብሕትዉና ሕይወት እንደነበረ ሰምቻለሁ:: ስለፓትርያርክ አባ መርቆርዮስም እንዲሁ ምንም የማዉቀዉ ነገር የሌለ ሲሆን ስለእሳቸዉ መስማት የጀመርኩት በስደት ወደ አሜሪካ ከሄዱ በኋላ ነዉ:: በዚያን ጊዜም «በእርግጥ በፈቃዳቸዉ «መስራት አልችልም» ካሉ እዚሁ አገራቸዉ በአንድ ገዳም ወይንም ቤተክርስቲያን ተወስነዉ በጸሎት፣ በጾም ቢተጉ መልካም ነበር» ብያለሁ:: ወደ ዉጭ ከወጡ በኋላ «በግዳጅና በተጽህኖ ነዉ የለቀኩት» በማለት ለሲኖዶስ ለሁለት መከፈልና ለመወጋገዝ ምክንያት በመሆናቸዉም አዝኛለሁ:: ተገደዉና ተጽህኖ ተደርጎባቸዉ ቢሆን እንኳ እንደ ሃይማኖት አባትነታቸዉ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፍርድ እንዲሰጥ ወደ እርሱ ማመልከትና እዚሁ አገራቸዉ እዉነትን ይዘዉ መጽናት ነበረባቸዉ እንጂ እንደ ፓለቲከኞች በመሰደድ የራስን ቡድን ማቋቋም አልነበረባቸዉም:: ምክንያቱም ሁሉ ያልፋል፤ የማያልፈዉ የእግዚአብሔር እዉነት ብቻ ነዉ:: ያ እዉነት ደግሞ ባለጊዜ በሚሆንበት ወቅት እዉነተኞች በእዉነተኛ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ሕዝቡንና ምእመኑን በእዉነትና በቅንነት ያገለግላሉና:: እዉነተኛ የክርስቶስ እንደራሴ ምንም ዓይነት ፈተናና መከራ ይምጣበት እንደ ክርስቶስ ስለ ምእመኑ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል፣ መስዋዕት ይሆናል እንጂ ከዓመፃ ልጆች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ አይሰራም፤ እንዲሁም በጎቹን ትቶ ራሱን ነጻ በማዉጣት ስደትን አይመርጥም::

አሁንም እግዚአብሔር የንስሐ እድሜ ሰጧቸዉ በሕይወተ ሥጋ አሉና ስለ ቤተክርስቲያን አንድነትና ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸምና መሳካት ሲሉ በስራቸዉ ካሉት አባቶች ጋር በመሆን በአንድነት እግዚአብሔር የመረጠዉንና የቀባዉን የሃይማኖትና የኢየሱስ ክርስቶስ ተጠሪ እጨጌን(ፓትርያርክ) ለመቀበል የራሳቸዉን መልካም አስተዋጽኦ ቢያደርጉ ለታላቅ ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ ዋጋ እንደሚበቁ እገምታለሁ፡፡ ነገር ግን ባላቸዉ አቋም ከጸኑ እግዚአብሔር የመረጠዉንና የቀባዉን በወርንበር ላይ ከማስቀመጥ ማንም የሚከለክለዉ ስለሌለ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀሎ ከመገኘትና በምድርም በሰማይም ዋጋ ከመክፈል ዉጭ ማንም ሰዉ ቢሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀረት አይቻለዉም፡፡

ሌላ እዚህ ላይ ለማሳወቅና ለማሳሰብ የምፈልገዉ በሥጋዊ ወንበር ላይ የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ የኢትዮጵያንና የዓለምን ሕዝብ ለማገልገል እንደሚቀመጡት ካህን ወ ርእሰ ነገሥት(ካህኑ ንጉሠ ነገሥት)፤ በመንፈሳዊ ወንበር ላይም የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ የኢትዮጵያንና የዓለምን ሕዝብ ለማገልገል የሚቀመጡት እጨጌ(ፓትርያርክ) እግዚአብሔርና እመቤታችን፤ እንደ ካህኑና ርእሰ ነገሥቱ መርጠዉና ቀብተዉ አዘጋጅተዋል፡፡ በመሆኑም በሥጋና ደም ስሜት ተመርቶና የሥጋና የደም ፍላጎትን የሚያሟላ አባት በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ማስቀመጥ፤ አንድም ለዉርደት ነዉ፤ አንድም ራስን ለጥፋት ማዘጋጀት እንደሆነ እያንዳንዱ አገልጋይና ምእመን እንዲያዉቅ እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህ ከሥጋና ደም ስሜት ምርጫ ራስን ለይቶ እግዚአብሔር የመረጠዉን ወደ መንፈሳዊ ወንበር እንዲያመጣ እርሱን እግዚአብሔርን በእዉነተኛ ሕይወት ሆኖ መጠየቅ ነዉ ከእያንዳንዱ የሚጠበቀዉ፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስራና ፈቃድ ማንም ይሁን ማን ማስቀረት አይደለም አንድ ቀን ሊያዘገየዉ አይችልም፡፡ ይህንንም እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡

ፓትርያርክ አባ ጳዉሎስን በተመለከት በወጣትነትና በጎልማሳነት እድሜ ዉስጥ ስለነበርኩ በተወሰነ ደረጃ ስለ እሳቸዉ መናገር እችላለሁ፡፡ ገና መንፈሳዊ ሕይወት በጀምርኩበት ዘመን ስለሆነ ወደ ወንበር የመጡት፤ ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች ከጊዜዉ ፓለቲካ ጋር በማገናኘት ለሳቸዉ ጥሩ አመለካከት ባይኖራቸዉም፤ እኔ ግን ከሚያስተምሩት ትምህርት አንጻር «እንዴት እንደዚህ የመሰለ ትምህርት የሚሰጡ አባትን ይቃወማሉ፣ ይጠላሉ?» በማለት ለዉስጤ እናገር ነበር፡፡ በሂደት ግን ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ የማይገናኝ፤ ለንግግራቸዉም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርጉትና ሰዉን የሚስብ ንግግር የሚያቀርቡት በተማሩት ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርት ፈሊጠኛነትን በመጠቀምና የሰዉ ሕሊናን ለመሳብ እንዲሁም ተቀባይነት ለማግኘነት ሲሉ መሆኑን ላስተዉል ችያለሁ፡፡ ከዓመት ዓመት ከመሻሻል ይልቅ በዙሪያቸዉ ማፊያ የሆኑ ሌባ ቀማኞችን እንዲሁም አስመሳዮችንና ዘማዉያንን የሚያሰባስቡ፣ በእያንዳንዱ ተግባር አምባገነነ የሆኑ፣ በባዕድና በምንፍቅና እምነት ዉስጥ ያሉትን አስመሳይ አገልጋዮችን ለራሳቸዉ ስዉር ዓላማ የሚጠቀሙ፣ በመጨረሻም ዓለማዉያን እንኳ ያላደረጉትን ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ቦታ ላይ አስቀምጠዉ በሥዕላቸዉና በሐዉልታቸዉ ያስገነኑና ያስመለኩ አባት ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ ባለቀ ሰዓት እንኳ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ ለእዉነተኛ

አገልግሎት ሳይበቁ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዉ በዓመፃ ላይ ዓመፃ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በአምልኮ ምንዝርና ላይ አምልኮ ምንዝርና ፈጽመዉና አስፈጽመዉ ወደ ማይቀርበት ቦታ ሄደዋል፡፡» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ አራት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ፤ የዓለም መንግሥታት ከኢትዮጵያ ጭምር መሪዎቹ የዲያብሎስ እንደራሴ፣ ባለስልጣኖቹ ባለሟል፣ ካድሬዎቹ ዉዶች ተብለዉ ተጠርተዋል። ይህን ስያሜ እንዴት እንደተሰጣቸዉ ቢገልጹልን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ለእነዚህ ሰዎች ይህን ስያሜ የሰጣቸዉ እኔ ወይንም ሌላ ግለሰብ አይደለም። እንደዚህ ሲባል ሰምቼ ሆነ አንድብቤ አላዉቅም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን መልእክት በምጽፍበት ወቅት እግዚአብሔር የሰጣቸዉ ስም ነዉ። ምክንያቱም በአራቱም ማእዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምና ማስፈጸም ሲገባቸዉ፤ ሕዝቡን እንደ አገልጋይነታቸዉና እረኝነታቸዉ በቅንነት፣ በእዉነት ካለ አድሎና በደል ማገልገልና መጠበቅ ሲገባቸዉ፤ ኃጢአትን በአራቱም ማእዘን ያነገሡና ሕዝቡንም እየበደሉና ግፍና መከራ እያደረሱበት ስለሆነና ራሳቸዉን ግን ለተለየ ክብረትና ግነት እንዲሁም ብልጽግና እያበቁ ስለተገኙ፤ እንዲሁም የዓመፃ፣ የክህደት ጽዋቸዉ በመሙላቱና እነሱም በእዉነተኛ ንስሐ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ነዉ ይህ ስም ሊሰጣቸዉ የቻለዉ።

እንኳን እነሱ ተራዉ ሕዝብ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልተመላለሰና አምላኩን በእዉነትና በመንፈስ ካላመለከ፣ እንዲሁም በኃጢአት ሲወድቅ እዉነተኛ ንስሐ ካልገባ፣ ልክ ሰይጣናት በረቂቅነታቸዉ ምክንያት ርኩሳን መናፍስት እንደሚባሉ ሁሉ፤ ይህች ዓመፀኛ ነፍስ በምድር ከተገለጸችበት ሥጋ በተለያየ መንገድ ስትለይ «ርኩሳን ነፍሳት» ተብላ ነዉ በሲኦል ዉስጥ እንደ ዓመፃዋ ደረጃ የምትቀጣዉ። እኛ ሰዎች ከሰይጣናት የምንለየዉ በምድር ዉስጥ በግዙፉ ሥጋ ተገልጸን በተለያየ መልክና አካል በመገለጻችን፣ እንዲሁም ነፍሳችን እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ ብቃት ስላላትና በኃጢአት ስትወድቅም በእዉነተኛ ንስሐ የመመለስና ራሷን ለእግዚአብሔር መንግሥት ለማብቃት ስለምትችል ነዉ እንጂ፤ እኛም ሆን ሰይጣናት በዓመፃችን ምክንያት ነዉ ወደዚህች ምድር ዉስጥ ልንመጣ የቻልነዉ። እኛ በአዳምማ ሔዋን ዓመፃና ክህደት ምክንያት፣ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ደግሞ እያንዳንዳቸዉ በሰማያት ዉስጥ በፈጸሙት ዓመፃና ክህደት ምክንያት ነዉ በዚህች ምድር ዉስጥ እየተቀጡ ያለዉ።

ከሰይጣናት በላይ እየተቀጣን የምንገኘዉ ደግሞ እኛ የሰዉ ዘሮች ነን። ምክንያቱም ሰይጣናት በሰማያት ዉስጥ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ጥርጥር በመፈጸማቸዉ ምክንያት ወደዚህች ምድር የተጣሉት፤ እግዚአብሔር በግልጽ በሚገባቸዉ መልክ ተገልጾ ሳያዩትና ድምፁንም ሳይሰሙ ነዉ። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠሩ ሕያዉ ፍጥረታት በመሆናቸዉ ሕሊናቸዉ የሚመሰክርባቸዉን እዉነት መቀበል ሲገባቸዉ፤ በተቃራኒ አቋም ተሰልፈዉ ያልተገባ ሐሳብ በማሰባቸዉና ያንንም በተግባር በማሳየታቸዉ ምክንያት ጸጋቸዉ ተገፎ በጉስቁልና ሕይወት ብቻ እንዲኖሩ ወደዚህች ምድር ተፈርዶባቸዉ የተጣሉት። እግዚአብሔርን ባለመመልከታቸዉና ድምፁንም

ባለመስማታቸዉ ምክንያት ፍርዱ ቀሎላቸዉ በዚህ ምድር ቆይታቸዉ ለመኖር መዉጣት፣ መዉረድ፣ መብላት፣ መጠጣት የለባቸዉም:: እንዲሁም መጠለያና ጥገኛ የሚሆኑባቸዉ ፍጥረታት አያስፈልጋቸዉም:: ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ ሌላ መሳሪያ ሆነ ቁሳቁስ አያስፈልጋቸዉም:: ያደፉና የጎደፉ ባሕርያት የሆኑት ዐይነ ምድር፣ ሽንት፣ ላበት፣ ንፍጥ፣ አክታ የለባቸዉም:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጸጋ የተለዩና በጉስቁልና ሕይወት ዉስጥ እንዲኖሩ ስለተፈረደባቸዉ በነዚህ ቆሻሻ ነገሮች ዉስጥ ያድራሉ፤ መኖሪያቸዉም ያደርጉታል:: በምድራዊ ሕይወታቸዉ ሞት የሚባል አያጋጥማቸዉም:: እነሱ ጉስቁልና ባሕርይ የሆኑት እርካታን አለማግኘት፣ መቅበዝበዝ፣ የሕሊና ሰላም ማጣት፣ መጨነቅ፣ መስጋት፣ መቃጠል፣ በእነዚህ ሕይወት ምክንያት መሰቃየት ነዉ የሚታይባቸዉ::

በእኛ ሰዎች ደግሞ በሥጋ በዚህች ምድር ዉስጥ እንድንገለጽ የተፈረደብን፤ አዳምና ሔዋን የተባሉት ሁለቱ የገነት ነፍሳት በረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) በገነት ዉስጥ የሚያስፈልጋቸዉ ረቂቃን ፍጥረታት ተፈጥረዉላቸዉ፣ እግዚአብሔርን በሚገባቸዉ መልክ ተገልጾ ተናግሯቸዉ፣ ድምፁንም ሰምተዉ፣ ሕሊናቸዉን በማደንደን «አትብሉ» የተባሉትን በድፍረት ስለበሉ ነዉ:: በዚህም ምክንያት ከጉስቁልና ባሕርይ በተጨማሪ በጎደፈና ባደፈ ባሕርይና እንዲሁም በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ እንዲቀጡ ይህን ሟች፣ በስባሽ፣ ጉዳት የሚደርስበትን ሥጋ ለብሰዉ በምድር እንዲገለጹበት አደረገ:: ለዚህም ነዉ በእኛ በሰዉ ዘሮች ላይ ያደፉና የጎደፉ እንዲሁም ጉስቁልና ባሕርይ ሊታይብን የቻለዉ:: ለመኖር ግድ መዉጣት መዉረድ እንዲሁም መብላትና መጠጣት አስፈለገን:: እንዲሁም ጥገኛ የምንሆንባቸዉ እንስሳት፣ እፀዋት፣ አዝርዕትና ሌሎች ምሳሌዊ የሆኑ ፍጠረታት አስፈላጊያችን ሆኑ:: መጠለያ ሆነ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ተጨማሪ ነገሮች አስፈለጉን:: እንዲሁም ከዚህ ምድር ወደ ሁለተኛዉ መኖሪያ ቦታ በሥጋ ሞት መጠራት ግድ ሆነብን:: በዚህች ምድር ቀና ካላሰብን፣ መልካም ካልሰራን፣ ለሕሊናቸን ካልተገዛን፣ እንደ ሰይጣናት ሕሊናችን ሰላም ያጣና እርካታ የሌለን እንዲሁም የተቅበዘበዝንና የተጨነቅን እንሆናለን:: ባጠቃላይ ከሰይጣናት በላይ በመከራ ሕይወት ዉስጥ የምንኖረዉ እኛ የሰዉ ዘሮች ነን:: በተቃራኒ ደግሞ በዚህ እጅግ እጅግ አጭር በሆነች ዘመን ዉስጥ አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ካደረግንና እንደ ፈቃዱ ከተመላለስን ደግሞ የቀደመ የገነት ሕይወትና አካል እንዲሁም ከፍርድ ቀን በኋላ የቅዱሳን መላእክት አካልና ሕይወት እናገኛለን:: በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነን እንኖራለን::

ስለዚህ ይህች ምድር እዉነተኛ ሕይወት ያለባትና የሚታይባት ሳይሆን የምንጠራባት፣ የምንነጥርባት፣ የምንነጣባት፣ እንዲሁም የምንቀጣበት፣ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታችን ገነትና መንግሥተ ሰማያት የምንሸጋገርባት ናት:: በመሆኑም ተስፋችን አድርገን የምንኖርባት አይደለችም:: በዚህች አጭር ዘመናችን ለእግዚአብሔር ታማኝና ተገዥ ካልሆንና እንደ ሰይጣናት በዓመፃችና በክህደታችን ጸንተን በኃጢአት ሕይወት ከተመላለስን፤ እንደ ሰይጣናት የባሰ ቅጣት በሁለተኛ መቀጫ ቦታ ሲኦልና ገሃነመ እሳት ነዉ የሚጠብቀን:: በሲኦል እስከ ፍርድ ቀን በድቅድቅ ጨለማ በስጋትና በጭንቀት የምንሰቃይ ሲሆን፤ ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ እሳቱ በማይጠፋ ረቂቃን የማይሞቱ ትሎች በሞሉበት በገሃነመ እሳት እንደ ዓመፃችን ደረጃ ፍዳችንን እንቀበላለን:: ልክ በደጋና በበረሃ ያሉ ሰዎች

ሁለቱም ምሳሌያዊ ፍጥረት በሆነዉ ግዙፉ ሥጋ የተገለጹና አንድ አይነት ነፍስ ያላቸዉ ቢሆንም፤ ደገኛዉ በበረሃ ከሚኖረዉ ቆለኛ ሰዉ በባሰ መልኩ በበረሃ ያለዉን ሙቀት መቋቋም እንደሚያቅተዉና ጭንቀቱና ስቃዩ እንደሚብስበት፤ እንዲሁም በረሃ የለመደ እጅግ ቅዝቃዜ ወዳለበት አገር እንዲኖር ቢደረግ ከደገኛዉ ሰዉ በባሰ መልኩ ቅዝቃዜዉን መቋቋም እንደሚያቅተዉና ጭንቀቱና ስቃዩ እንደሚብስበት ሁሉ፤ በሲኦል ሆነ በገሃነመ እሳት ዉስጥ መቀጫዉ አንድ ዓይነት ቢሆንም እያንዳንዷ ዓመፀኛ ነፍስ በምድር በፈጸመችዉ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ደረጃ መጠን ነዉ የሚደርስባት ስቃይ የሚለያየዉ:: እጅግ ዓመፃን የፈጸመች ነፍስ እጅግ ልትቋቋመዉ የማትችለዉ ስቃይ ነዉ የሚደርስባት:: እንዲሁም እጅግ አነስተኛ ዓመፃ የፈጸመች ነፍስ እጅግ አነስተኛ የምትቋቋመዉ ስቃይ ነዉ የሚደርስባት::

በመሆኑም ከእኛ የሚጠበቀዉ በዚህች እጅግ አጭር ምድራዊ ዘመናችን ከማንኛዉም የዓመፃ ፣ የክህደትና የርኩሰት ተግባር መለየትና ሕይወታንን በእዉነተኛ ንስሐ እየመረመርን በቅዱስ ቁርባን ተወስነን፤ ቅን በማሰብ፣ መልካም በመስራት፣ በእዉነተኛ ሕይወት መመላለስ ነዉ:: ለዚህ ሕይወት ደግሞ ሙሉ ነጻነት ተሰቶናል:: ማንም ሊከለክለን ሆነ ሊለየን አይችልም:: ኃጢአት እንድንፈጽ የሚያስገድደን አካል ቢኖር እንኳ «አንፈጽምም» በማለት ለሕሊናችንና ለአምላካችን መታመን እንችላለን:: ለታላቅ ክብርና ለሰማያዊ አክሊል የሚያበቃን መከራ ከመጣብን ደግሞ በትዕግስትና በጽናት እንዲሁም በአኰቴት መቀበል ይኖርብናል እንጂ ለሚያልፍ ነገር የማታልፈዉን ነፍሳችንን አሳልፈን መስጠት የለብንም::

ባጠቃላይ መሪዎች ሆኑ ባለሥልጣናት እንዲሁም ካድሬዎችና ሕዝቡ አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ካላደረጉና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልተመላለሱ፤ ደረጃቸዉ እንደ ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) የሆነ፣ ከሰይጣናት የሚለዩት በሥጋ በመገለጻቸዉ ነዉ እንጂ በዓመፃና ክህደት ተግባራቸዉ አንድ የሆኑ ናቸዉ:: ነገር ግን በመሪነት ላይ ያሉ ከተራዉ ሕዝብ የበለጠ የሚጠየቁና ፍርዱም እጅግ የሚብስባቸዉ ነዉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአገልጋይነትና ለእረኝነት ወደ ወንበር ያመጣቸዉ የእግዚአብሔርን ፍጥረትና ልጆች የሆኑትን በአግባቡ እንዲጠብቁና እንዲያገለግሉ  እንዲሁም ለእርሱ ፈቃድ እንዲያስልፉ ስለሆነ፤ ያንን ድርሻቸዉንና ጥሪያቸዉን በአግባቡ ካልተወጡ ስለ ራሳቸዉ ነፍስ ብቻ ሳይሆን ስለ ሕዝቡ ነፍስ ጭምር ስለሚጠየቁ ነዉ ፍርዱ እጅግ የሚብስባቸዉ:: እንደተራነታቸዉ ተጠርተዉ ቢሆን ፍርዱ እንደ ግለስብ ነዉ የሚጠየቁት እንጂ ስለ ሌላ ግለሰብ አይጠየቁበትም ነበር:: በዚህም ፍርዱም ይቀልላቸዉ ነበር:: ነገር ግን ትዉልዱ በወንበር ምኞት ስለተቃጠለና የራሱን የሥጋና የደም ስሜት ዓላማ ለማስፈጸምና ለመፈጸም ይኸዉ ሌት ተቀን ለሥልጣን ይሯሯጣል እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ዓይነት ጥያቄ እንደሚቀርብለትና ስለ ዓመፃ ተግባሩና ሕይወቱ ምን ዓይነት ዋጋ እንደሚከፍል አላስተዋለም!

እንግዲህ ማንኛችንም ብንሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ካልሆነ በስተቀር፤ ለምድራዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ ጥቅማጥቅም ብለን ወደ ወንበር መዉጣት የለብንም:: ምክንያቱም እዉነተኛ ፍሬ ካላፈራን  በምድርም ያፈራነዉን መራራ ፍሬ ጠጥተን እንደምናልፍና

በሰማይም የባሰዉን መራራ ፍሬ እንደምንጠጣ ልናዉቅ ይገባል። ለዚህም ነዉ ነቢያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ለተጠሩበት ጥሪና ለተቀመጡበት ወንበር ታማኝ ሆነዉ፤ «ተመሳስሎ ኑሮ» የሚለዉን ፈሊጥ ሳይከተሉ፤ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ፣ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዉ በመመስከራቸዉና በእዉነት በማገልገላቸዉ ምክንያት ነዉ መሪዎች(ነገሥታት) ሆኑ አስመሳይ አገልጋዮች(አስመሳይ ካህናት) የተለያየ መከራና ስቃይ ያደረሱባቸዉ። ነገር ግን ፍሬያቸዉ ጣፋጭ ነዉና በሰማይ እጅግ ጣፋጭ ሕይወት ነዉ የገጠማቸዉ። እነዚያ ገዳዮችና አሳዳጆች ደግሞ እጅግ መራራ ሕይወት ነዉ የጠበቃቸዉ። ስለዚህ እያንዳንዳችን ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖረን እድሜ አንጻር የዓይን ጥቅሻ እድሜ በማትሞላዉ ምድራዊ ዘመናችን በእዉነት አገልግለን፣ ስለ እዉነት መስክረን፣ በእዉነት ኖረን፣ ከዚህች ምድር ማለፍ ነዉ የሚጠበቅብን እንጂ፤ ለጊዚያዊ ሥልጣን፣ ጥቅም፣ ክብር፣ ዝና ብለን ሕሊናችንን መሸጥና ከዓመፃ ልጆች ጋር መሰለፍ የለብንም።

እዚህ ላይ አሁን በመጨረሻ በጸሎቴ ላይ የጨመርኩት፤ «እግዚአብሔር ሆይ! ወደፊት አንተ በምታስቀምጠኝ ወንበር ላይ ምን እንደምሰራ ታዉቃለህ። እኔ የአንተን ፈቃድ ብቻ ፈጽሜና አስፈጽሜ ወደ ሰማያዊ መንግሥትህ እንድመጣ ነዉ ጸሎቴና ፍላጎቴ። ነገር ግን በአንተ ቦታ ሆኜ ራሴን የማስመልክና የማገን ከሆነ አንተ ታዉቃለህና ወደዚያ ወንበርም አታዉጣኝ። ካወጣኸኝ ደግሞ ከወደድከኝ ይህን የዓመፃ ተግባር ከመፈጸሜ በፊት አስቀድመህ ገለኸኝ ለሰማያዊ መንግሥትህ አብቃኝ። ካልወደድከኝ ደግሞ ይህን የዓመፃ ተግባር ከመፈጸሜ በፊት አስቀድመህ ገለኸኝ በገሃነመ እሳት ፍረድብኝ። ምክንያቱም ፍርዱ ይቀልልኛል» በማለት ነዉ። «የኢትዮጵያና ዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አራት መጨረሻ ላይ እንደተገለጸዉ፤ ከእግዚአብሔር እንደተነገረኝ ለወደፊት ምን እንደምሆን ባዉቅም፤ ራሴን በአክሊል ዉስጥ ያለ ኩስ መስዬ ነዉ ለዓለም ያስተዋወኩት። ይህም አንዳች መግነንን ሆነ መመስገንን ስለማልፈልግና እስከ ምድራዊ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ <u>ብቻ</u> ለመፈጸምና ለማስፈጽም የቆምኩ መሆኑን ሁሉም ሰዉ እንዲያዉቀዉ ፈልጌ ነዉ።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አምስት

« <u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>፡ በመጀመሪያዉ ሆነ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ በዋና መሪ ደረጃ ካሉ ሰዎች በስተቀር በግልጽ ማንነታቸዉ ተገልጾ አልተገሰጹም፤ ስማቸዉም አልተገለጸም፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ የዓመፃ ሰዎች፤ ማስተዋልና መረዳት የሚችለዉ ሰዉ እንዲያዉቃቸዉ ተግባራቸዉ ተገልጿል፡፡ ለምሳሌ ከተገለጸዉ አገላለጽ በግልጽ ማንነታቸዉን ለመለየት የማልቸገረዉን ባቀርብ፤ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምእራፍ ሦስት በገጽ295-296 የተገለጸዉ፡

«የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ያቃጠላቸዉ የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች ለአገሪቱ መሪና ለከፍተኛ ባለሥልጣናት ቅሬታቸዉን አሰሙ፡፡ ይኸዉም «እኛ የብሔር ብሔረሰቦች ወያኔ(ኢሕአዴግ) አባታችንና መንግሥታችን ስንት መስዋዕትነት ከፍሎ ነጻነታችንን አጎናጽፎን ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብታችንን ጠብቆ፤ የተዋደቀለትንና የተጋደለለትን ሰንደቅ ዓላማችንን የተለየ የክብር ቦታ አለመሰጠቱ ቅር አሰኝቶናል፡፡ ምክንያቱም ለወደፊቱ ራሳችንን ችለን ነጻ መንግሥታት እንደምንሆን እየታወቀ በታላላቅ ሆቴሎችና መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ ከሌሎች አገራት መንግስታት እኩል ከፍ ብሎ አለመዉለብለቡና ለወደፊት ከነአካቴዉ ከሚቀረዉና ከሚሻረዉ የፌደራሉ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ እኩል እንኳ አለመቆጠሩ አሳዝኖናል፡፡ በተለይ የጨለማዉ ገዥ ዓርማ ኮኮብ የተደረበት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማዎች እንደ ሌሎቹ ክልላዊ መንግሥታት እኩል መቆጠራቸዉና ከፌደራሉ መንግስት እኩል መዉለብለብ አለመቻላቸዉ ዋናዉን የኮከቡ ባለቤት እንደመናቅ ሊታይ ስለሚችል ቢታሰብበት» በማለት ቅሬታቸዉንና አስተያየታቸዉን አቅርበዋል፡፡

<u>የአገሪቱ መሪም(አቶ መለስ ዜናዊ)፤ ጨለማዉን ነጭ፣ ነጩን ጨለማ ለማለት ወደ ኋላ የማይመለሰዉን ታማኙን አገልጋያቸዉንና አፈቀላጤያቸዉን ምላሽ እንዲሰጡ የጋበዙ ሲሆኑ</u>፤ ተጋባዡም «እናንተ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ተወካዮች፤ ለወደፊቱ ነጻ መንግሥታችሁ ከአሁኑ በመቆርቆር ለክልላዊ መንግሥታችሁ ሰንደቅ ዓላማ ያላችሁ የነደደ ፍቅር እጅጉን አኩርቶናል፡፡ እንኳን በፌደራሉ መንግሥት ቀርቶ በተባበሩት መንግሥታት መሰብሰቢያ አዳራሽ «ለወደፊቱ ነጻ የሚሆኑ የመንግሥታቱንም ቁጥር ከፍ የሚያደርጉ የክልላት መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ» ተብሎ ከፍ ብሎ ቢዉለበለብ ደስታዉን አንችለዉም፡፡

በፌደራሉ ብሔራዊ መንግሥት ግን ይኸዉ «የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓላማ ቀን» ተብሎ በያመቱ እየተከበረና የክልላት መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ ከፌደራሉ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ እኩል ሲዉለበለብ እየታየ ስለሆነ በዚህ አንዳች ቅሬታ የሚገባችሁ አይመስለኝም፡፡ የፌደራሉ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ የነፍጠኞችና የትምክህተኞች ስላልሆነ ዋናዉ የጨለማዉ ገዥ አርማ ኮኮብ ስለተደረገበት ከክልላት ሰንደቅ ዓላማ ጋር አብሮ በመዉለብለቡ እንዲሁ ቅር እንማደትሰኙበት

እናምናለን። ለወደፊት ነጻ መንግሥታችሁን ስትመሰርቱ ከናካቴዉ ስለምታስወግዱት የምትጠሉትም ከሆነ ለትንሽ ጊዜ መታገስ ይጠበቅባችኋል።

ለሌሎች የክልላት መንግሥታት የግብር አባታችን ዓርማ የሆነዉ ኮኮብ ሰንደቅ ዓላማ ላይ እንዲታይ ያላደረግነዉ አድሎ ለመፍጠር ሳይሆን ዋናዉ መሪያችን «ሌሎቹም ሰንደቅ ዓላማዎች በእኔ በጨለማዉ ገዥ መሪነት የተዘጋጁ ስለሆነ ማዕረጋቸዉ እንደ ኮኮቡ ስለሚቆጠር ልዩነት የለዉም» ስላለን ነዉ። <u>በዚሁ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚኒስትራችንን(አቶ መለስ) ሆነ ሌሎቻችሁ ባለሥልጣናትን «እንደበትህ እንደበታችን ነዉ።» ብላችሁ ሙሉ ዉክልና ስለሰጣችሁኝና የኢህአዴግ መንግስትን አቋም እንድገልጽ ስላደረጋችሁ በጨለማዉ ገዥ ስም አመሰግናችኋለሁ። አደራ የምለዉ የጦር አዛዥነትን ዉክልና እንዳትሰጡኝ ነዉ። ምክንያቱም ሕሊናዬ በቀልና ጥላቻ የሞላዉ ስለሆነ ለማንም ምሕረት የማላደረግና ሳላዉቅ በደጋፊዎቻችን ላይ ጭምር እርምጃ ልወስድ እችላለዉ የሚል ስጋት ስላለኝ ነዉ።</u> » እንዳሉ  ሳቅና ሞቅ ያለ ጭብጨባ ቀርቦላቸዋል።» በማለት ቀርቧል።

ከላይ እንደተገለጸዉ ጨለማዉን ወይን ጨለማ ነዉ ወይንም ተቃራኒዉን ብርሃን ነዉ ማለት ሲጠበቅባቸዉ፤ ለሚጠየቁት ጥያቄ የማይገናኝ መልስ በመስጠትና ከሕሊናቸዉ ተቃርነዉ ሁል ጊዜ የሚታዩት አቶ በረከት ስምዖን መሆናቸዉ እየታወቀ ስለ ምን «<u>የአገሪቱ መሪም፤ ጨለማዉን ነጭ፣ ነጩን ጨለማ ለማለት ወደ ኋላ የማይመለሰዉን  ታማኙን አገልጋያቸዉንና አፈቀላጤያቸዉን ምላሽ እንዲሰጡ የጋበዙ ሲሆኑ</u>» በማለት ሊገለጹ ቻሉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰዉ ዉጫዊዉን ብቻ አይደለም ዉስጣዊ ማንነቱን ያዉቃል። በዚህ ምክንያት በሁለተኛዉ መልእክቱ የመንግሥታት ሆነ የድርጅቶች እንዲሁም የቡድኖች ሆነ የግለሰቦች ዉስጣዊ ማንነታቸዉን ነዉ የተገለጸዉ። ዉጫዊዉማ በማስመሰልና በሽንገላ ሕይወት የተሞላ ስለሆነ፤ ሰዉ በዉጭ በሚሰማዉና በሚያየዉ ስለሚታለል እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ዉስጣዊ ዓመፃ ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ተግባርን ነዉ ለትዉልዱ የገለጸዉና ትዉልዱም አቋሙንና አስተሳሰቡን እንዲያስተካክል በዚህ መልኩ እንዲገለጽ ያደረገዉ። እግዚአብሔር በመልእክታቱ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ መሪነት ላይ ያሉትን በግልጽ ማንነታቸዉን ያሳወቀዉ ደግሞ የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆነዉ ፈቃዱን መፈጸምና ማስፈጸም ሲገባቸዉ በተቃራኒ አቋም ተሰልፈዉ በተለያየ ወርቃማ የማስመሰያ ንግግር ታጅበዉ የዲያብሎስን ፈቃድ በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በግልጽ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር በመፈጸማቸዉና በማስፈጸማቸዉ እንዲሁም የዓመፃ ጽዋቸዉ ሞልቶ ስለፈሰሰና ስለተተፉ፣ ሥልጣናቸዉም ስለተሻረና ወደ እዉነተኛ ሕሊናቸዉ እንደማይመለሱ ስለተረጋገጠ ነዉ።

በእነርሱ ስር ያሉት ግን እነሱን ተከትለዉ ስለሆነ በዓመፃ የተሰለፉትና፤ ፈቃደኞች ሆነዉ በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እርሱ ቢመለሱና ለእዉነተኛ ሕሊናቸዉ ቢገዙ በምሕረት ስለሚጎበኛቸዉ እስከ መጨረሻ ይታገሳቸዋል። ነገር ግን የተሰጣቸዉን የንስሐ እድሜ ካልተጠቀሙበት በቁጣዉ እነሱንም ይጠርጋቸዋል። በእዉነተኛ ንስሐ ከተመለሱ ስለሚቀበላቸዉና ከእርሱ ወገኖች ስለሚደምራቸዉ ነዉ

በግልጽ ስማቸዉ ሆነ ሥልጣናቸዉ እንዲገለጽ ያላደረገዉ:: እስከ አሁን ድረስ ታግሏቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ስላልተመለሱ አሁን ግን እነሱም እንደተተፉ ነዉ የሚሰማኝ::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስመጣ**: የመንግሥት ኮምንኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት በሚኒስትር ማእረግ ኃላፊ የሆነዉ አቶ በረከት ስምዖን የተገለጸበት ማንነት ይኸዉም ጨለማዉን ጨለማ ወይንም በተቃራኒዉ ብርሃን ማለት ሲጠበቅበት፤ የማይሆነዉንና አብሮ የማይሄደዉን ምላሽ «ነጭ» በማለት የሚመልስ፣ እንዲሁም ብርሃኑን ብርሃን ወይንም በተቃራኒዉ ጨለማ ማለት ሲገባዉ የማይሆነዉንና አብሮ የማይሄደዉን «ጥቁር» በማለት ምላሽ የሚሰጥ ለሕሊናዉ ተቃራኒ የሆኑ የዓመፃ ልጅ መሆኑን ነዉ የሚያሳየን:: ከላይ ያለዉን ለማብራራት በምሳሌ ባቀርብ አንድ ግለሰብ ወይንም አንድ አካል፤ አንድ ሰዉ በረኃብና በጥም ጣር ዉስጥ መሆኑን ቢገልጽ፤ አቶ በረከት መመለስ የሚገባዉ « አዎ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ መፍትሔ ይፈለግለታል» ወይንም በተቃራኒዉ «አልተራበም፣ አልተጠማማ» ማለት ሲገባዉ፤ የእርሱ መልስ ግን ከጥያቄዉ ጋር የማይሄድ፣ «ሰዉየዉ ለቢራ መጠጫ ገንዘብ አቷል» በማለት ነዉ ምላሽ የሚሰጠዉ:: በተዝዋዋሪ ደግሞ «ሰዉየዉ ጠግቧል፣ ረክቷል፣ ረኃብና ጥም የለበተም፣ የጥጋብ ጥያቄ ነዉ የሚያቀርበዉ» በማለት በዚያ ረኃብተኛና የተጠማ ሰዉ ላይ በማላገጥ ነዉ ምላሹን የሚሰጠዉ ማለት ነዉ::

<u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: ከዚህ ጋር የተያያዘ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሦስት በምእራፍ አንድ በገጽ 59 ላይ:

«<u>**አንተ ዘመናዊዉ ጠንቋይ**</u>፤ የሰዎችን ስሜቱና ተግባር እየተከተልክ በቃሌ የምትነግድ <u>**ሐሰተኛ ሰባኪ**</u>፤ ስንቱን የዋሃን በጎቼን አሳሳትክ፤ አሰናከልክ፤ ስንቱን እረኛ ነኝ ብሎ በእዉነተኛ ወንበር የተቀመጠዉን አሳሳትክ!? እኔ ሳላናግርህ «እግዚአብሔር የሚያናግረኝን ቃል አንድ ሳላስቀር እናገራችኋለሁ» እያልክ በስሜ የምትነግድ **ዓመፅና ትዕቢት የሞላብህ**፤ <u>**በየትኛዉ ቅድስና ሕይወትህ ነዉ እኔ አንተን የማናግር?**</u> ቀደም ሲል የምእመንን ልቦና ተረድተህ **«የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች»** ብለህ አባቶችህን እንዳላዋረድክ አሁን ደግሞ ገበናህ ሲጋለጥ <u>**የአባቶችህን ሐዉልት በክብር አስመርቀህ አስመለክ:: ያዉ ሁለታችሁም በዓመፃ መንፈስ የምትመሩ ስለሆነ**</u> በስተመጨረሻ ለጥፋት ኅብረትና አንድነት ብትፈጥሩ ምንም አያስገርምም! በበላይ የሚመራችሁ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ኅብረትና አንድነት ፈጥሮ ለዓመፃ ስራ ቢሰለፍም ከእኔ የሆነዉን መቋቋም ሆነ ማሸነፍ ስለማይችል <u>**እናንተም ከቤቴ ትጠረጋላችሁ፤ትዋረዳላችሁ**</u>::» በማለት ተገልጿል::

«ዘመናዊ ጠንቋይ» የተባለዉ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም «ሰባኪ ከዛም ባለፈ መጋቤ ሐዲስ ነኝ» ብሎ ራሱን ያገነነዉ በጋሻዉ ደሳለኝ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል:: ታዲያ በእግዚአብሔር መልእክት ላይ ማንነቱና ስሙ ቢገለጽ ኖሮ ሰዎች ማንነቱን አዉቀዉ ይጠነቀቁ አልነበረምን?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: እግዚአብሔር እኛ እንደምናስበዉ አይደለም የሚያስበዉ:: ለእያንዳንዱ ንግግሩ ሆነ ተግባሩ ምክንያት አለዉ:: ማንነቱ በግልጽ ተገልጾ ቢሆን ኖሮ

በወቅቱ ብዙ ሰዎች ሊሰናከሉ እንደሚችሉ ይገመታል። ምክንያቱም ብዙዎች ባለማወቅ እዉነተኛ ሰባኪና መምህር አድርገዉ ቆጥረዉት ነበርና። አሁን ድረስ ከእርሱ በእዉቀትም ሆነ በስብከት እጅግ የሚበልጡት አንዳንድ «አገልጋዮች» ጭምር እርሱን የሚያገኑና የሚያስመልኩ ደቀመዝሙሩ የሆኑ አሉ። እንዲሁም አንዳንድ የሰዉ አምላኪ ምእመናንም ደግሞ እንደተገፋ ቆጥረዉና እንደ እዉነተኛ አገልጋይ ተመልክተዉ ስብከቱን ሆነ ንግግሩን የሚከታተሉ አሉ።

የራሴን ምሳሌ ባቀርብ በመጀመሪያ ራሱን ባስተዋወቀበት «የመስቀሉ ቁማርተኞች» በማለት በጻፈዉ መጽሐፍ ስለ እዉነተኛነቱ አጠራጥሮኝ ነበር። ምክንያቱም በሥጋና ደም ስሜት በመጻፉና ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም አንዳች ምስክርነት ያልሰጠ በመሆኑ ነዉ። ከዓመታት በኋላ «የመማጸኛ ከተማ» በሚል ርእስ ያወጣዉ ስብከቱ ጆሮዬን እንድሰጥ አደረገዉ። የቤተክርስቲያን ሰዉ ባይሆን ኖሮ ስለ እመቤታችን እንዲህ በግልጽ አይመሰክርም በማለት ስብከቶቹን በቅንነት ተቀበልኳቸዉ። ከዚያም ሌሎች ስብከቶቹን በካሴት አዳመጥኩ፤ እንደ «መሃሉ አይነገርም» አይነት ስብከቶቹ ይስቡኝ ጀመር። ከዚያም አጠቃላይ በካሴት ሆነ በመድረክ ለሚሰብካቸዉ ስብከቶች ቦታ ሰጠሁኝ። እንደ እሱ አይነት አሰባበክ ሌሎች ሲሰብኩ፤ «እግዚአብሔር ሌላ በጋሻዉን አስነሳ» እያልኩ እንደ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ አድርጌ እቆጥረዉና እመሰክርለት ጀመርኩ። በሌላ ዝግጅት ምክንያት ሐምሌ፲፱÷፳፻፪ (19/11/2002)ዓ.ም ሃዋሳ ገብርኤል ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ ተገኝቼ ነበር። በዚያን ወቅት የሃዋሳ አገረ ስብከት ጳጳስ የነበሩት «መጋቤ ሐዲስ» በማለት ማዕረግ ሲሰጡት በወቅቱ ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ ሆነ እዉቀቱ አንዳች ግንዛቤ አልነበረኝምና እግዚአብሔርን በማመስገን በእንባ ጭመር «የተገፋን ሰዉ እግዚአብሔር አሰበዉ» በማለት ዉስጤ ደስ ብሎት ነበር የተቀበልኩት። ምክንያቱም «በፓትርያርኩና በመሰሎቻቸዉ ያልተፈለገዉና ያልተወደደዉ እዉነተኛና ቆራጥ ሰባኪ ስለሆነ ነዉ» በሚል አስተሳሰብ ዉስጥ ስለነበርኩ ነዉ።

ታህሳስ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ላይ በሚሊኒየም አዳራሽ ተገኝቼ ስብከቱን ሰምቼ ነበር። ከአንድ ንግግሩና ራሱን ካመጻደቀበትና ካስታበየበት በስተቀር ሌላዉ ስብከቱ እዉነተኛ አገልጋይ የሚያስመስለዉ ነበር። እጅግ ለበዛዉ መልካም ስብከቱ ትኩረት በመስጠት እጅግ ጥቂቱን እንክርዳድ ንግግሩን በቅንነት በማየት ቦታ አልሰጠሁትም ነበር። በዚህ አስተሳሰብ ዉስጥ እያለሁ አንድ ወንድም፤ በአሁን ሰዓት በዚሁ «ዘመናዊ ጠንቋይ» በተባለዉ በጋሻዉ ደሳለኝ ከሳሽነትና በግብረ አበሮቹ መስካሪነት በእስር ላይ የሚገኝ፤ በካሴት እርሱንና ሌሎች መሰሎቹን የሚነካና የሚተች መልእክት አስተላለፈ። እኔም በጊዜዉ «ቅናት ነዉ» በማለት ትችቱን አልተቀበልኩትም፤ ይልቁኑ ተቃወምኩት።

ታዲያ እግዚአብሔር እንደ ሰዉ ያልሆነ የዉስጥን ቅንነት እንጂ ዉጭን የማይመለከት እንደ ሰዉ ዉጭን አይቶ የማይፈርድ፤ ምክንያቱም በዚያ አቋሜ ስለ በጋሻዉ ምንነት በደንብ የሚያዉቁ ግለሰቦች ሆኑ ቡድኖች እንዲሁም ማኅበሮች ዉጫዊዉን አቋሜን ቢመለከቱ ኖሮ የእርሱ ደጋፊና አድናቂ አድርገዉ ይቆጥሩኝ ነበርና። ከዚህ በኋላ ነዉ እግዚአብሔር አቋሜና አስተሳሰቤ የተሳሳተ መሆኑን ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ በወቅቱም እንግዳ በሆነብኝ ድምጽ እኔ « ሞገስ ያለዉ፣ አንደበተ

ርቱዕ፣ ታላቅ ሰባኪ ነዉ» ስል፤ እግዚአብሔር ደግሞ «እርሱ ጠንቋይ ነዉ» ያለኝ:: ዘመናዊ ጠንቋይ በእግዚአብሔር ቃል የሚያስመስልና የሚነግድ መሆኑን በሂደት ነዉ ያስተዋልኩትና የተረዳሁት:: ከዚያ ድምፅ በኋላ በጥርጣሬ እመለከተዉ ጀምርኩ:: አንድ ቀን በዐዉደ ምሕረት ላይ በግልጽ የመንፈስ ቅዱስ ስራን ሲቋወምና ሲኮንን ስመለከት «እዉነት ነዉ በሽዋጁ መንፈስ የሚመራ አስመሳይ ነዉ» አልኩኝ:: ከዚያም እግር ጥሎኝ የፓትርያርኩ ሐዉልት በቦሌ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ሲመረቅ በአስመራቂነት ዋና የመድረክ መሪና አዳናቂ ሆኖ ተመለከትኩት:: የሰዉ ዕይታና የእግዚአብሔር ዕይታ የማይገናኝ መሆኑን በሚገባ አስተዋልኩ:: በሂደት ደግሞ ዛሩ እንደተነሳበት ሽማጊሌዎችንና ልጆችን ሲሳደብ እንዲሁም በእግዚአብሔር አገልግሎት ዉስጥ የተሰማሩትን ሲራገምና ሲኮንን፣ ሲቃወም፣ ሲያጥላላና የጥቃት ዘመቻ ሲመራ አዳመጥኩ፤ ተመለከትኩ:: ስብከቶቹ ሁሉ የሰዎችን ስሜትና ወሬ እየተከተለ መሆኑን አስተዋልኩ:: በትክክል እግዚአብሔር የተናገረኝ ሰዉ ዓይነት መሆኑን ተረዳዉ፤ አወኩ::

ትዉልዱ የሚመለከተዉ ዉጭዉን እንጂ ዉስጥን ስላልሆነ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገርና ለማስመሰል ያህል የማያምንበትን ጭምር ሲመሰክር እዉነተኛ አድርጎ ይቆጥራል:: በጋሻዉ በጎርናና ድምፁ ነዉ ሰዎችን ለመሳብ የቻለዉና ከእርሱ እጅግ የሚልቁ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያዉቁና የሚሰብኩትን ሳይቀር ደቀ መዝሙሩና አድናቂዎቹ ያደረጋቸዉ:: በዓለም ፍጻሜ ዘመን የሚነሳዉ ሐሳዌ መሲህ ወይንም ሐሳዌ ክርስቶስ ወይንም ሐሳዌ አምላክ ለሦስት ዓመት ተኩል ባለ ጊዜ በሚሆንበት ዘመን በጎርናና ድምፅ ብቻ ሳይሆን በድንቃድንቅ ተአምራትና ኃይል ነዉ የሚገለጸዉ:: በመጀመሪያም እንደ በጋሻዉ ደሳለኝ የተገፉ እዉነተኛ አገልጋይና የእግዚአብሔር ሰዉ መስሎ ነዉ በትዉልዱ ዉስጥ የሚኖረዉና ጊዜዉ ሲደርስ ራሱን እንደ አምላክ በመቁጠር ለዓለም ራሱን የሚያስተዋዉቀዉ:: ትዉልዱ እንዲቀበለዉ የተለያዩ ተአምራትና ምልክት ያደርጋል:: ትዕቢት፣ ክፋት፣ ዓመፃ የተባሉት የፈርኦን፣ የይሁዳና የአርዮስ ወንድምና እህቶች ዋና ስራ አስፈጻሚዎቹና አገልጋዮቹ፣ መስካሪዎቹ ይሆናሉ:: አእምሮ ቀላሎችና አእምሮ ሕፃናት ተአምሩንና ምልክቱን አይተዉ ተከታዮቹ ይሆናሉ:: አእምሮ አዋቂዎች «በሥጋዊ ጥቅማችን ላይ ጉዳት ያደርስብናል፣ ኃይል አለዉ፣ ለመኖር እንቸገራለን» በማለት ለጊዜያዊ ሥልጣን፣ ክብር፣ ጥቅምና ዝና ሲሉ ይቀበሉታል:: አእምሮ ጽንአን ግን ምንም እንኳን የሚያደርገዉን ተአምርና ምልክት ቢመለከቱም በኃይሉም ቢፈተኑም «እኛ አምላካችን ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነዉ፤ እሱን ነዉ የምናመልከዉ፣ ለእርሱ ብቻ ነዉ የምንገዛዉ» በማለት በእምነታቸዉ ይጸናሉ፤ እስከ ሰማዕትነት ይደርሳሉ እንጂ አይቀበሉትም፤ አያምኑበትም::

በዚያን ወቅት የሚኖረዉ ትዉልድ ዓርማዉን(666) የሚቀበለዉ ልክ እንደ አሁን ዘመን በሕግና በአዋጅ መልክ በሰንደቅ ዓለማ ላይ የኮኮብ ዓርማ እንዲደረግ እንደተደረገና ያንን ያላደረገ በወንጀል እንደሚጠየቅ ሁሉ፤ ያኔም በዚሁ መልክ እንደ አሁኑ ዘመን ዓለም እንደተቀበለዉና በሰንደቅ ዓላማዉ ላይ እንዳደረገዉ የዲያብሎስ ዓርማ ኮኮብ(666)፤ በማስመሰልና በወርቃማ ቃላቶች ታጅቦ እያንዳንዱ እንዲቀበለዉ ያስደርጋል:: «አልቀበልም» የሚለም ደግሞ የተለያየ ቅጣትና ተጽህኖ ይደርስበታል:: ከዚህ በተጨማሪ ልክ እንደ ኮኮቡ በወርቃማ ቃላት ታጅቦ የሚዘጋጀዉን የዲያብሎስን

ዓርማ ያልተቀበለና እንደ ማኅተብ ያላጠለቀ ሰዉ በማኅበረዊ ኑሮ፣ በእቃ ግዢ፣ በንብረት ማፍራት፣ በተለያየ ለሥጋዊ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ እንዳይሳተፍ ተጽህኖ ይደረግበታል። እዉነተኞቹ አገልጋዮችና አማኞች ግን ቅድሚያ ለነፍሳቸዉ ነጻነትን በመስጠት ነዉ ይህን ፈተናና መከራ በታላቅ መስዋዕትነት አልፈዉ ለታላቁ ሰማያዊ መንግሥት የሚበቁት።

ታዲያ አሁን በንግግር የሚታለልና የሰዉ አግናኝና አምላኪ በሆነዉ ትዉልድ ዘመን ይህ ሐሳዊ መሲህ ቢነሳ ኖሮ ዓለም ሁሉ እንደሚቀበለዉ ምንም ጥርጥር የለዉም። ምክንያቱም እንኳን ተአምርና ምልክት ታይቶ አይደለም በማስመሰል ንግግርና በተለየ ስጦታ ሰዉን የሚከተልና የሚያደንቅ ከዛም ባለፈ የሚያመልክ ትዉልድ ነዉና ያለዉ። ለዚህ ምስክሩ እጅግ ብዙዎቻችን የምንሰማዉና የምንቀበለዉ እንዲሁም ለተግባራዊነቱ የምንሰለፈዉ የእግዚአብሔርን ቃልና ሕሊናችን የሚመሰክርብንን ሰምተን ሳይሆን፤ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ በተለየ ስጦታ በሥጋና ደም ስሜት ሰዎች ተመርተዉ የሚናገሩንን ነዉ።

እግዚአብሔር ታዲያ የሰዎችን አቋምና አስተሳሰብ ስለሚያዉቅ፤ የአስመሳይ አገልጋዮች ማንነት በደንብ እስከሚታወቅ ድረስና ባለማወቅ እዉነተኛ መስሏቸዉ የተቀበሉት የዋሃን እንዳይሰናከሉ በማሰብ ነዉ ዓመፀኞችን በተግባራቸዉ እንዲገለጹና መንፈስ ቅዱስ የገለጸለት ሰዉ ብቻ በሚገባ እንዲያዉቃቸዉ በዚያ መልኩ ያጻፈዉ። አሁንም ድረስ ማንነቱ በግልጽ እየታወቀና ፍሬዉ እየታየ፣ ትዕቢተኛነቱና ዓመፀኛነቱ እንዲሁም እብሪቱና ተሳዳቢነቱ እየታየ፣ ዲያብሎስ ሕሊናዉን ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠረዉ ዛሩ እንደተነሳበት ሰዉ እንደሚራገም፣ እንደሚሳደብ፣ የትዕቢትና የዓመፃ ንግግር እንደሚያደርግ በደንብ ታዉቆ ጭምር፤ ይኸዉም ከእርሱ በእዉቀትም ሆነ በማስተማር እጅግ የሚበልጡት «አገልጋይ ነን» የሚሉና «ዘማሪ ነን» የሚሉ ጭምር አግናኙ፣ አድናቂዉና ደቀመዛሙርቱ፣ ከዛም ባለፈ አምላኪዉ ናቸዉ።

ለዚህ ትንሽ የዓመፅ ልጅ መስካሪዎች፤ ስለ ኢየሱስ ጥብቅና እንደቆሙ አድርገዉ የሚቆጥሩ መሆኑን እየተመለከትንና እየሰማን እንደሆነ ሁሉ፤ በመጨረሻዉ ዘመን ለሚነሳዉ ለዋናዉ የዓመፅ ልጅ ለሐሳዊ መሲህ «እዉነተኛ ክርስቶስ ነዉ፣ አምላክ ነዉ» እያሉ ምስክርነትን የሚሰጡት ሐሰተኛ መምህራንና ሐሰተኛ ነቢያት መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ አድርገዉ፣ እንደ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ መስለዉ፣ አንደበታቸዉን አሳምረዉ፣ ተመሳስለዉ፣ እንዲሁም በምልክትና በተአምራት በኃይል ታጅበዉ ነዉ። የትንሹ ዓመፅ ልጅ የበጋሻዉ ደስለኝ ተከታዮችና ስለ «አገልጋይነቱ» መስካሪዎ የሆኑ «ሰባኪያንና ዘማርያን ነን» የሚሉ፤ ተአምራትና ምልክት የማድረግ ብቃትና ተቃዋሚዎቻቸዉን የመግደል ሆነ የመበቀል ኃይል ቢኖናጸፉ ኖሮ፤ ብቸኛ የሕይወት መንገድ የሆነችዉን የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቅድስት ቤተክርስቲያን ላይ በፈነጨባትና በዋኙባት ነበር። እንዲሁም እንደ ፕሮቴስታንቱ የዳንኪራና የዘፈን፣ የመዝናኛ ቤት ባደረጓት ነበር። ያ ብቻ አይደለም የዲያብሎስ መንፈስ እዲነገሥ አድርገዉ ዓመፃና ርኩሰት እንዲፈጸምባት ባደረጉ ነበር። ነገር ግን የየዋሁ ምእመን አምላክ እንክርዳድ ተግባራቸዉንና ሕይወታቸዉ እንዲጋለጥ፣ ማንነታቸዉ እንዲታወቅ አስደረገ።

በኋላ ያጋጠመኝ አስገራሚ ነገር ደግሞ ይህ «ሐሰተኛ ሰባኪ» ተብሎ በእግዚአብሔር የተመሰከረበት በጋሻዉ፤ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ ተጽፎ በወረቀት ተጠርዞ የተሰራጨዉ የእግዚአብሔር መልእክት «እርሱ ነዉ የጻፈዉ» ብለዉ የሚያምኑና የሚያሶሩ ምእመናን ሁሉ ነበሩ:: በመጨረሻ ላይ እግዚአብሔር እንደተናገረዉ ፓትርያርኩን ሆነ እሱን ዓመፀኛነታቸዉን መስክሮባቸዉ «ትጠረጋላችሁ፤ ትዋረዳላችሁ » እንዳላቸዉ ሁሉ፤ ፓትርያርኩ ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቁ በቁጣዉ ሊጠሩ ችለዋል:: እሱም ገበናዉ ተጋልጦ ተዋርዷ:: ለእዉነተኛ ንስሐ ሳይበቃ በትዕቢትና ዓመፃዉ ሕይወት እንዳለ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠረግ አይጠረግ ወይንም በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሶ ራሱን ከትዕቢትና ከዓመፃ ለይቶ በእዉነተኛ ሕይወት ይኑር አይኑር አንድዬ መድኃኔዓለም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ የሚያዉቀዉ:: እኔ እንደ ወንድምነቴ ለእርሱም ሆነ በማወቅም ይን ባለማወቅ የእርሱ ተከታይና አምላኪ የሆኑ ሰዎች የምመኝላቸዉና የምጸልይላቸዉ ወደ እዉነተኛ ሕሊናቸዉ እንዲመለሱና ራሳቸዉን ከትዕቢትና ከዓመፃ ለይተዉ እግዚአብሔርንም በሥጋና ደም ስሜት ሳይሆን በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልኩትና በመጨረሻም ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥት እንዲበቁ ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ ቀደም ብለዉ እንደገለጹልን በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ የዓመፃ ልጆች ስማቸዉ በግልጽ ያልተገለጸዉ፤ «በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱ ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር ስለሚደመሩና ለእግዚአብሔር መንግሥት ሊበቁ ስለሚችሉ ነዉ» በማለት ነዉ:: ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መፈጸማቸዉ የተመሰከረላቸዉ ግለሰቦች ሆኑ የተለያዩ አካላት ስማቸዉ አልተገለጸም:: ለምሳሌ «ኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀምሪያዉ በእግዚአብሔር መልእክት በክፍል አራት በገጽ 76 ላይና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚብሔር መልእክት ላይ በክፍል ሁለት በምዕራፍ አንድ ዉስጥ «ኢትዮጵያዊዉ በማንነቱ ፍለጋ»፣ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ»፣ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ የሕይወት ምስጢራትን ጥያቄዎች የተመለሱበት ቁጥር አንድ ቁጥር ሁለት ቁጥር ሦስት»፣ እና «የምስራች» በሚል ርእስ የተጻፉ መጻሕፍት በክቡር ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ መጻፋቸዉ ይታወቃል:: ነገር ግን ስማቸዉ አልተገለጸም:: አንድ ሰዉ የሰራዉ መልካም ስራ ተገልጾ ማንነቱ ያልተገለጸዉ ለምንድ ነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: የእግዚአብሔር እዉነተኛ አገልጋዮች የራሳቸዉን ዝናና ክብር የማያስቀድሙ፣ የተለየ ምስጋና የማይፈልጉ፣ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸምና በመልእክቱ የታዘዘዉ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈልጉ ናቸዉ እንጂ፤ ስንትና ስንት ስራ እየሰሩ «የማንጠቅም አገልጋዮች ነን» በማለት ነዉ ራሳቸዉን እንኳ የሚጠሩት:: ዓላማቸዉና ግባቸዉ ሁሉ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ ማግነን፣ በእዉነት በመንፈስ ማስመለክ ፣ራሳቸዉን በመካድ ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መመስከር ነዉ:: መግነንን፣ መመስገንን ፣ መመለክን ስለማይፈልጉ ይመስለኛል መንፈስ ቅዱስ ስማቸዉ እንዳይገለጽ ያደረገዉ:: ምክንያቱም ትዉልዱ እንደሆነ ከቀድሞዎቹ መማር ተስኖት፤ ዛሬ ቅዱስ ባለዉ አንደበቱ ነገ ደግሞ ርኩስ የሚል ነዉ፤ ዛሬ ታላቅ ባለዉ አንደበቱ ነገ ደግሞ ታናሽ ወራዳ ነዉ የሚል ነዉ፤ ዛሬ

ይንገሥብኝ ባለ አንደበቱ ነገ ይሰቀል የሚል ነዉ፤ ዛሬ ጻድቅ ነዉ ባለ አንደበቱ ነገ ዋና ኃጢአተኛ ነዉ የሚለዉ፤ ዛሬ ምን ልታዘዝ ባለ አንደበቱ ነገ የት አዉቅኃለሁ ወግድ ከኔ የሚለዉ:: ታዲያ ይህን በመሰለ ትዉልድ ምን መታወቅ ያስፈልጋል:: ለሥጋም ለነፍስም የሚጠቅመዉ በእግዚአብሔር ዘንድ ስንታወቅ ነዉ:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር የታወቀ በእዉነተኛ አገልጋዮቹና አማኞቹ ዘንድ ይታወቃል:: እንዲሁም ምድራዊ ክብርና ወንበር ሳይሆን ሰማያዊ የክብር ዙፋንና የድል አክሊል ነዉ የሚጠብቀዉ:: ለእዚህ ነዉ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ምስክሮች ምድራዊን ሥልጣን ሆነ ክብር እንዲሁም ጥቅምና ዝናን ከቁም ነገር የማይቆጥሩትና የማይፈልጉት:: ተስፋቸዉ ታላቅ ስለሆነና በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆነዉ ስለሚኖሩ ነዉ የሚመጣባቸዉን ፈተናና መከራ በቆራጥነት፣ በትጋት፣ በትዕግስትና በጽናት፣ በተጋድሎ የሚያሳልፉት::

እዚህ ላይ አንድ የእግዚአብሔር እዉነታን ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: ሰዎች ስንባል የሚያመሰግነንና የሚክበንን ነዉ የሚንፈልገዉና የምንወደዉ እንጂ፤ ድክመታችንና ጉድለታችንን የሚነግረንን እንደ ጠላት ነዉ የምንመለከተዉና ከቻልንም በተግባር ወይንም በንግግር ወይንም በጽሑፍ ለመበቀል  የምንነሳሳዉ:: ማስተዋሉ ካለን ያ በእዉነትና በቅንነት የሚናገረን ሰዉ በሁሉ ዘንድ ለመወደድ ሲል እንደ ስሜታችንና ፍላጎታችን ሊናገረንና ሊሸነግለን ይችላል:: ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት ሰዉ ለግል ጥቅም የቆመ ነዉ እንጂ እዉነተኛ የሕዝብና የምእመን እረኛ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም እዉነቱን እዉነት፣ ሐሰቱን ሐሰት፣ እምነቱን እምነት፣ ክህደቱን ክህደት ማለት ካልቻለና «ሁሉም ትክክል ነዉ» እያለ ሁሉንም በመሸንገል የሥልጣን እድሜዉን ለማስረዘምና የራሱን ዓላማ ብቻ ለመፈጸም የተነሳና የሚነሳ ከሆነ እርሱ የእግዚአብሔር እንደራሴና አገልጋይ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም እግዚአብሔርና ዲያብሎስ ፍጹም ተቃራኒ እስከሆኑ ድረስ ከዲያብሎስ የሆነ ስራ ከዲያብሎስ መሆኑ ሊመሰከርበት ይገባል እንጂ እንደ እግዚአብሔር ስራ መቆጠር የለበትም:: እያንዳንዱ ግለሰብ ግን ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሆነ ከዲያብሎስ የሆነዉን የመቀበልም ያለመቀበልም ሙሉ ነጻነት አለዉ:: በእዉነትኛ አገልግሎት ላይ የተሰለፈ ግን ማንም ይሁን ማን ስለ እዉነት ብቻ ነዉ ማገልገል ያለበት እንጂ እዚያም እዚህም የሚያጣቅስ ከሆነ እርሱ አስመሳይ አገልጋይ ተኩላ ነዉ እንጂ እዉነተኛ የበጎች እረኛ አይደለም::

ይህን ያነሳሁት ካለ ምክንያት አይደለም:: እጅግ የተከበሩ ንቡረ እድ ኤርምያስ የጻፏቸዉ መጻሕፍት በሥጋና ደም ስሜት ተመርተዉ የተጻፈ አይደለም:: እዉነተኛነትና ቅንነት በተሞላዉ ሕሊና በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ የጻፉት ነዉ:: ከራሴ ምሳሌ ብወስድ በቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ ከሚነገረዉ ተነስቼ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ለቅድስት ቤተክርስቲያን ትልቅ ስራ እንደሰሩ፣ ብዙ አብያተክርስቲያናትን እንዳሳነጹ፣ ከግብፅ ጥገኝነት ራሷን እንድትችል እንዳደረጉ፣ ለአገርም ከፍተኛ ስራ እንደሰሩና በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ቦታ የያዙና አገሪቷንም ትልቅ ቦታ እንዳደረሱ የሚነገረዉን ብቻ ሰምቼ፤ እኔም ትልቅ ቦታ ላይ በማስቀመጥና እንደ ጻድቅ በመመልከት እርሷቸዉን የሚተች ሆነ የሚቃወም ግለሰብ ላይ ጥሩ አመለካከት አልነበረኝም:: ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ሆነ ጽድቃቸዉ እንደተመሰከረላቸዉ ቅዱሳንና ጻድቃን ስላልተመለከትኳቸዉ፤ «ኢትዮጵያ የዓለሙ

መፋረጃ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ መጽሐፍ ላይ የሰሩት መልካም ተግባር ብቻ ሳይሆን ድክመትና ስህተት እንደሰሩም የተገለጸዉን በማንበቤ ምክንያት አስተሳሰቤ ሚዛናዊ እንዲሆን አድርጎታል እንጂ፤ «እንዴት በቤተክርስቲያን ትልቅ ቦታ የተሰጣቸዉ ንጉሥ እንዲህ ይተቻሉ፣ ድክመታቸዉ ይገለጻል?» አላልኩም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቻ ነዉ ፍጹም እንጂ ሥጋ ለባሽ ሰዉ በመዉደቅ በመነሳት ነዉ ምድራዊ ዘመኑን ፈጽሞ ወደማያልፈዉ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሄደዉ::

ታዲያ እኝህ የቅዱሱ ኪዳኗ የመንግሥተ እግዚአብሔር የኢትዮጵያ አገልጋይ የሆኑት ንቡረ እድ ኤርምያስ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ድክመትና የስህተት ተግባር በቅንነትና በእዉነት በመግለጻቸዉ ምክንያት፤ አጼ ኃይለ ሥላሴን ከመዉደድና ከማክበር ባለፈ በሚያመልኳቸዉ ሰዎች ዘንድ ተቃዉሞና ጥላቻ ነዉ የገጠማቸዉ:: ንቡረ እድ ኤርምያስ በቅንነትና በእዉነት የገለጹት ድክመትና ጉድለት አጼ ኃይለሥላሴን ብቻ ሳይሆን፤ ለአገራቸዉና ለቤተክርስቲያናቸዉ የተለያየ ስራ ሰርተዉ ያለፉትን ፓትርያርክ አባ ቴዎፍሎስና አለቃ አያሌዉንም የመሳሰሉትን ጭምር ነዉ:: ታዲያ ጉድለታቸዉንና ድክመታቸዉን በመግለጻቸዉ ምክንያት እነሱን ከመዉደድና ከማክበር ባለፈ እያመለካቸዉ ባለ ሰዉ ተቃዉሞና ጥላቻ ነዉ የደረሰባቸዉ:: እኝህ ክቡር ካህን ግን እንኳን ጽድቃቸዉ ገና ያልተረጋገጠላቸዉን ቀርቶ፤ ጽድቁ የተረጋገጠለት ጻድቁ አብርሃምን እንኳ በእዉነትና በቅንነት የሃይማኖትና የምግባር ምሳሌነቱን ገልጸዉ፤ ነገር ግን የመጀመሪያዉ ቅዱሱ ኪዳን ለሆነዉ የአዳምና ሔዋን ጋብቻ ሥርዓት አርአያ መሆን እንማይችልና «የአብርሃምና የሳራ ጋብቻ ይሁንላችሁ» መባሉ አግባብ እንዳልሆነና ሊባሉ የሚገባቸዉ ይህን ቅዱስ ኪዳን በአግባቡ የጠበቁት «የይስሐቅና የርብቃ፣ የዘካርያስና የኤልሳቤጥ፣ የኢያቄምና የሐና፣ የጸጋ ዘአብና የእግዚእ ሐሪያ ... ወዘተ» በማለት ገልጸዋል:: አሁንም ታዲያ የሰዉ አምላኪና አግናኝ ሰዉ «ጽድቁ በእግዚአብሔር የተመሰከረለት ጻድቁ አብርሃም እንዴት እንዲህ ይባላል?» በማለት ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር ሊጣላና ሊላተም ይችላል::

እኛ እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ የምናመልክና የሰዉ አምላኪ ያልሆን ሰዎች! እንኳን ስለ ሌሎች ግለሰቦች ጽድቃቸዉ በእግዚአብሔር ገና ያልተረጋገጠዉን ቀርቶ፤ ምክንያቱም የቅድስና ማዕረግ ላይ ቢደርሱ ኖሮ እንደ ቀደሙት ጻድቃን ለመታሰቢያ ታቦት ይቀረጽላቸዉ፣ በስማቸዉም ቤተክርስቲያን ይሰየምላቸዉ ነበርና፤ ነገር ግን ለዚህ ብቃት ስላልደረሱ፣ ስለ መጽደቅ አለመጽቃቸዉ እንኳ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉና፤ ከእኛ የሚጠበቀዉ ራሳችንን የተለየ ቦታ ያስቀመጥን ሰዎች እንኳ፣ በቅንነትና በእዉነት ድክመታችንን ስህተታችንን የሚገልጽልን ሰዉ እርሱ እዉነተኛ እረኛ ስለሆነ ሰምተነዉ ከድክመታችንና ከስህተታችን ልንስተካከልና ልንታረም ይገባል እንጂ፤ እንደ አሕዛብ የሰዎች ወይንም የራሳችን አምላኪ ሆነን «እንዴት ይተቹብናል? እንዴት እኛስ እንደፈራለን?» ማለት የለብንም:: «እረ ለመሆኑ እኛ ማነን ?» ብለን መጠየቅ ይኖርብናል:: ያኔ ነዉ ወደ ሙሉ እዉነት የምንደርሰዉና ሙሉ በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የምንሆነዉ እንጂ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነተ በራሳችን የዉሸት እዉነት ለመገደብ ከተነሳንና ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር የምንላተምና የምንቃወም ከሆነ ወደ ሙሉ እዉነተ ሳንደርሱ እንደ ሥጋና ደም

ስሜታችን ተመላልሰን የሰዉ አምላኪዎች ወደሚሄዱበት ቦታ ነዉ የምንሄደዉ እንጂ እዉነተኛዉን አምላክ በእዉነትና በመንፈስ አምልከዉ ወደሚሄዱበት እዉነተኛ መኖሪያ ቦታ አይደለም::

ሌላዉ የታዘብኩት በሕዋ ሰሌዳ(በድረ ገጽ) በተለየዩ ብሎጎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም የተለያዩ ጽሑፍ የሚያቀርቡ አሉ:: ታዲያ «የሚጠቅሙ ሌሎች ብሎጎች» እያሉ የተለያዩ ብሎጎችን ከእንሱ ብሎግ ጋር ሲገልጹና ሲያስተዋዉቁ እኔ እስከአሁን የማዉቃቸዉ የተለያዩ ብሎጎች አንድም የሳቸዉን የሕዋ ሰሌዳ(ድረ ገጽ) (www.ethkogserv.org) የሚለዉን ያሳወቀ ሆነ «ቢነበቡ ጠቃሚ የሆኑ ብሎጎች ናቸዉ» ብሎ ከሌሎቹ ዝርዝሮች ዉስጥ የደመረ የለም:: ምክንያቱን በእርግጠኝነት እንዲህ ነዉ ለማለት ባልችልም የራሴ ግምት ግን፡

**አንድ ያለማወቅ ሊሆን ይችላል**:: ይኸዉም ለምሳሌ እኔ በእግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት ከመጠራቴ በፊት (ከ2003 ዓ.ም በፊት) ስለ እርሳቸዉ ሆነ ስለጻፏቸዉ መጻሕፍት አንድም የማወቀዉ ነገር አልነበረም:: ምናልባት ከዚያ በፊት ሰዉ እንኳ «እከሌ የጻፉት መጽሐፍ ነዉ አንብብ » ቢለኝ እንደ አሁን ትኩረት ሰጥቸዉ የማነበዉ አይመስለኝም:: ምክንያቱም ዉሸት በሆነዉ (በፓለቲካ) ሕሊናዬ የተበከለ ስለነበር፤ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከሃይማኖት ጋር ተዋሕዶ ሲቀርብ «አይ ይህ ፓለቲካዊ ይዘት ያለዉ ነዉ» በሚል የተሳሳተ አመለካከትና አስተሳሰብ ብዙ ቦታ ላልሰጠዉ እችል ነበር:: ምክንያቱም ከልጅነቴ ጀምሮ የተመለከትኩትና የምሰማዉ እንዲሁም የተማርኩት ቤተክህነቱ «እኛ የነፍስ እረኛ ነን መንፈሳዊ ሕይወት ከፈለክ እኛ ስንናገርህ ስማን፤ በሥጋዊ ሕይወትህ ደግሞ የመንግሥት ነህና እነሱ ሲናገሩህ ስማ፤ ሁለት ጌታ ነዉ ያለህ አንዱ የነፍስ አንዱ የሥጋ... » በማለት ተከፋፍለዉና ተለያይተዉ ስለሆነ፤ መንግሥት ደግሞ «እኛ የሥጋህ ጌታ ነንና እንደ እኛ አመለካከትና አስተሳሰብ ልትሆን ይገባል:: የምትገዛበትና የምትተዳደርበት ሕገ መንግሥትና አዋጅ ስላለ ምንም ይሁን ከዚህ ዘነፍ ብትል ከእስር እስከ ሞት ድረስ ያደርስሃል:: ያ ገዥ መደቦች ለመጨቆኛና የበላይ ለመሆን የፈጠሩት ሃይማኖት እኛ ባናምነዉም፣ ባንፈልገዉም አንተ እፈልገዋለሁ ካልክ የእኛን የሥጋ መንግሥት አንዳች ሳትቃወምና ሳትተች እንዲሁም የእኛ ባሪያ (አገልጋይ) መሆንህን መስክረህ እንደፈለክ ልትሆን ትችላለህ... ወዘተ» ተብሎ ስለሆነ የተማርኩትና የሰማዉት፣ ያነበብኩት፣ እንዲሁም ተግባራዊ የሆነዉ፤ ሁለቱን ለማጣመር የፈለገና «ነፍስም ሥጋም የአንድ ጌታ ናቸዉ፤ ሁለቱም ተዋሕደዉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሰለፍ አለባቸዉ» የሚለዉን ሰዉ ለመቀበል እንዳልችል ይኸዉ ዉሸት(ፖለቲካ) ሕሊናዬን ስለበከለዉና ተጽህኖ ስላሳደረብኝ ነዉ::

ከእግዚአብሔር ጥሪ በኋላ ግን በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በዓለም ላይ የነገሡት የዓለም መንግሥታት ሁሉ ዉሸት በሆነዉ ፓለቲካ የዲያብሎስን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ በበላይ ዲይብሎስ የሚመራቸዉ መሆኑን እግዚአብሔር ስላሳወቀኝ፤ ራሴን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማሰለፍና ነፍስና ሥጋ ተዋሕደዉ ለእግዚአብሔር መገዛት እንዳለባቸዉ፣ ከነፍስ የተለየ ሥጋ በድን ነዉ እንጂ እዉነተኛ ሕይወት ያለዉ ፍጥረት አለመሆኑን በማስተዋሌ፤ ለሕዝቡ ማሰብና ማዘን ጀምርኩ:: ምክንያቱም «የሕዝብ አገልጋይ ነን» ብለዉ በወንበር የተቀመጡት የጨለማዉ ገዥ የዳያብሎስ(የሰይጣናት) አገልጋይ ናቸዉና:: ሌት ተቀን የተሰለፉት የጨለማዉ ገዥን ፈቃድ

ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ። በዚህ ምክንያት ትዉልዱ ተስፋዉን ምድር አድርጎ እዉነተኛ መኖሪያዉን ገነትና መንግሥተ ሰማያትን እንዲያቃልልና እንዲክድ ተደርጓል። ለዐይን ቅጽበት ለሆነዉ ምድራዊ ዘመኑ ሲል ለሕያዉነት ዘመን (የማይኖርበት ዘመን ለማይኖር) የሚኖርበትን ሕይወት እንዳይፈልግና በምድም በሰማይም ፍዳዉን እንዲቀበል ተደረጓል።

**ሁለተኛዉ ግምቱ ደግሞ**: አገልጋዮች ሆኑ ምእምናን « ኑሮ በመመሳሰል፣ ከራስ በላይ ንፋስ ... ወዘተ» የሚለዉ የዉሸቱ(የፓለቲካዉ) ስብከት ተጽህኖ ስላሳረፈባቸዉ «ይህ ብሎግ እንደ ጠቃሚ አድርጌ ባሳዉቅ መንግሥት ይበቀለኛል፣ አገልግሎት እንዳልሰጥ ያደርገኛል» በሚል ፍርሃትና ስጋት ነዉ።

**ሦስተኛዉ ግምቱ ደግሞ**: እዉቀታቸዉና ሊቅነታቸዉ ጣዖት የሆነባቸዉ ሰዎች እነርሱ ከሚያዉቁት እዉቀት ዉጭ እዉቀት እንዲሁም ምስጢር ስላለበት፤ «ከእኛ እዉቀትና አስተሳሰብ ዉጭ የሆነዉን አንቀበልም» በሚል የጸሐፍት ፈሪሳዉያን እንዲሁም የአይሁድ ካህናትና ሕግ አዋቂዎችን ሕይወት በመያዛቸዉ ነዉ።

**አራተኛዉ ግምቱ** ደግሞ: የእርሷቸዉን ትምህርት ከተቀበሉና በእርሳቸዉ በኩል እግዚአብሔር የገለጸዉን እዉቀትና ምስጢር ካስተዋሉ፤ እነሱ የሚሰሩትና ሕይወታቸዉ በተቃራኒ ዉስጥ ስለሆነ ባዶነት ስለሚሰማቸዉና ሕሊናቸዉን ስለሚወቅሳቸዉ ሙሉ የእግዚአብሔር እዉነትንና እዉቀትን ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ነዉ።

**አምስተኛ ግምቱ** ደግሞ: ሰዎች ሰዎችን ከማክበርና ከማፍቀር ባለፈ በአምላክና በቅዱሳን ደረጃ ባልተናነሰ መልኩ የሚመለከቷቸዉ በመሆኑ፤ መሪዎችን፣ አገልጋዮችን፣ ሕዝብን ፣ ምእመናን ጉድለታቸዉና ድክመታቸዉን ካለፍርሃትና ይሉኝታ በመመስከራቸዉ ምክንያት አምላካቸዉና አማልክታቸዉ እንደተተቹባቸዉ በመቁጠር ከጥላቻ ስሜት በመነሳት ነዉ።

**ስድስተኛ ግምቱ**: በአንደበት መናገር እንጂ ያ የሚነገረዉን በተግባር ባለመፈጸምና ባለማመን ሕይወት የሚመላለሱ አገልጋዮችና አማኞች በእርሳቸዉ በኩል የተገለጸዉ እግዚአብሔር እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ተግባራዊ የሚያደርገዉን እዉነትና ሥርዓት «እግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም፤ የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜና መልኩ ማከናወን ይችላል» የሚለዉን ከልብ ካለማመን የተነሳ ነዉ።

**ሰባተኛ ግምቱ**: የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ሥርዓት ደጋፊና አቀንቃኝ የሆኑ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች እነርሱ ከሚመሩበት አስተሳሰብና አመለካከት የተለየ በመሆኑና «እንክርዳዱን እንክርዳድ፣ ስንዴዉን ስንዴ» ብለዉ በግልጽ ስላስቀመጡ፤ ይህ ደግሞ እነርሱ ከሚመሩበት ርዕዮተ ዓለም ሆነ አስተሳሰብ እንዲሁም አቋም ጋር አብሮ ስለማይሄድና ይልቁኑ ገበናቸዉን የሚገልጽና ባዶነት እንዲሰማቸዉ የሚያደርግ ስለሆነ ነዉ።

ባጠቃላይ ለሥጋና ደም ስሜት ማርኪያና ለዲያብሎስ ፈቃድ መፈጸሚያና ማስፈጸሚያ የማይሆን፣ ለምድራዊ በረከትና ለሰማያዊ ሕያዉ ሕይወት የሚያበቃ ንጹህ ስንዴ እንክርዳድ ያልተደባለቀበት ስለሆነ፤ በትዉልዱ ሆነ በተለያየ አገልግሎት ላይ በተሰማሩት መንግሥታዊ ሆነ መንፈሳዊ ተቋማት ተቀባይነትን ሊያገኝ አልቻለም። አሁን ያለነዉ ትዉልድ ግን እግዚአብሔርን የምንል ከሆነ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ልንሰማና ልንቀበል ይገባል። ምክንያቱም ብንቀበልና የተባልነዉን ተግባራዊ ብናደርግ የመጀመሪያ ተጠቃሚዎች እኛዉ ነን። ከዚያም ለሌላዉ ወገናችን እንተርፋለን፣ ብዙም ፍሬ አፍርተን ለታላቁ ለሰማያዊ ክብርና መንግሥት እንበቃለን።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ በግልጽ እንደገለጹት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደተጻፉ ነዉ። ታዲያ የእርሷቸዉ መጻሕፍት ኬትኛዉ ወገን ነዉ የሚመደበዉ። ምክንያቱም የተለያዩ ቅዱሳት መጽሐፍት በአንድ ላይ ተጠርዘዉ በቀኖና መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ ለዓለም ተሰራጭቷል። ሌሎች የጸሎት፣ የምስጋና፣ የድርስት መጻሕፍት አሉና። እንዲሁም የተአምራት፣ የገድል፣ የመዋዕለ ዜና የተለያዩ እዉቀቶች መጻሕፍት አሉ። ከእነዚህ ዉስጥ በየትኛዉ ዉስጥ ነዉ ሊመደብ የሚችለዉ።

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>፡ በመጀመሪያ ለማሳወቅ የምፈልገዉ እጅግ በተከበሩ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ የተጻፉት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መሆኑን የገለጽኩት እኔ አይደለሁም። እኔ ስለሳቸዉ ማንነት ሆነ ስለጻፉት መጻሕፍት በጥቅምት፳፻፫ (2003) ዓ.ም ባነበብኩ ወቅት ነዉ በመጽሐፋቸዉ ብቻ ያወኳቸዉ እንጂ እስከ አሁን ድረስም ምን ዓይነት ሰዉ እንደሆኑ አላዉቃቸዉም። እርሳቸዉም ምን ዓይነት ሰዉ መሆኔን የሚያዉቁኝ አይመስለኝም። ምክንያቱም አንድም ቀን ተያይተንና ተገናኝተን አናዉቅማና። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ነዉ በኅዳር ወር፳፻፫ (2003) ዓ.ም ላይ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በተገለጸዉ መልክ እንዲገለጽ ያደረገዉ። ምንም እንኳን በጥቅምት ወር መጻሕፍታቸዉን ሳነብ የመንፈስ ቅዱስ ስራ መሆኑን ባዉቅም፤ በራሴ የሥጋና የደም ፈቃድና ሥልጣን በእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ መመስከር ስለሌለብኝ እስከ ኅዳር ወር 2003 ዓ.ም ድረስ በእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ አላስገባዉትም ነበር። ነገር ግን በኅዳር ወር ላይ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በተገለጸዉ መልክ እንዳስገባዉ ማሳሰቢያ የሰጠኝ መልእክቱን ያጻፈኝ እግዚአብሔር ነዉ። ይህ የሚያሳየዉ በእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ የተመሰከረለትና የተገሰጸዉ ሁሉ በእግዚአብሔር ነዉ የተመሰከረለት ወይንም የተገሰጸዉ እንጂ በእኔ በደካማዉና በኃጢአተኛዉ ሰዉ አይደለም። እኔ እንኳን የሌላዉን ሰዉ የራሴን ማንነት በደንብ የማላወቅ ሰዉ ነኝ። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያስመሰክረኝን አሁንም ወደፊትም እመሰክራለሁ። በአሁን ሰዓት የእርሳቸዉን መጻሕፍት «ከዚህ ነዉ ከዚያ ነዉ የሚመደበዉ» የሚለዉን ለመግለጽ አልፈልግም። ምክንያቱም ሰዎች እንዳይሰናከሉ በማሰብ። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነትና ትእዛዝ ስለመጻፉ አሁንም ለወደፊትም እመሰክራለሁ። በመልካሙ ዘመን በኢትዮጵያ ትንሣኤ ግን በሚመደብበት ደረጃ ላይ ሆኖ የቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኑ ሌሎች የሚጠቀሙበት ይሆናል።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ስድስት

« **ጠያቂዉ አገልጋይ**: ከአንድ ቦታ በስተቀር ለዚያዉም ከቋንቋ ጋር በተያያዘ ለዚያዉም ከማዳመጥ በስተቀር «እንዲህ ነዉ፣ እንዲያ ነዉ» ያላሉት የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት(ንጉሥ) በእግዚአብሔር መልክታት ዉስጥ እንደ ፕሬዝደንትነታቸዉ(ንጉሥነታቸዉ) አልተገለጹም። ይህ ለምን ይመስሎታል?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**: «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» የሚሉት በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ(አቶ መለስ ዜናዊ) አእምሮዋቸዉን ለመልካምና ለእግዚአብሔር ፈቃድ አዉለዉት ቢሆን ኖሮ ብሩህ ነበር። ነገር ግን ለአገልግሎት የተጠቀሙት ለጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ነዉ። ታዲያ እጅግ ዉሱን የሆኑት ሰዎች የራሳቸዉን የዘረኝነትና የጎጠኝነት ስሜት እንዲኖራቸዉና ዉስጣቸዉ ጥላቻና በቀል እንዲያድርባቸዉ በማድረግ ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፍለዉ ለሥልጣን ሕሊናዉን የሚሸጠዉንና ኮልኮሌ በሆኑት በተለያዩ ቁሳቁሶችና ጥቅማጥቅሞች የሚደለለዉን እየመረጡ «አሁን ፕሬዝዳንት(ንጉሥ) ሆነሃል፤ ይህ ያንተ ክልልና መንግሥት ነዉ» እያሉ ስዉር መሰሪ ዓላማቸዉንና በቀላቸዉን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ እንደነበረ ይታወቃል። በዚያዉ አስተሳሰባቸዉ የተለየ ሥልጣንና ዝናን እንዲሁም ክብርን የሚፈልጉ ለወንበር አንዳች የማያስጉ፣ እንሚፈልጉ ሊያሽከረክሯቸዉና የዘረኝነትና የጎጠኝነት አስተሳሰባቸዉን ተቀብለዉ በዚያዉ ሥርዓት ለመመላለስ ፈቃደኛ መሆናቸዉን ያረጋገጡላቸዉ ወደ ምልክት ብቻ እንጂ አንዳች ኃይል ሆነ አቅም ወደሌለዉ ወንበር ላይ ያመጧቸዋል። አድራጊዉ ፈጣሪዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ከስራቸዉ የተሰለፉ በበቀልና በጥላቻ የተሞሉ የእሳቸዉ ምልምል የሆኑት ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ናቸዉ አገሪቷን እንደፈለጉ ሲያሽከረክሩ የነበሩት። ፕሬዝዳንቱ(ንጉሡ) ከስም ዉጪ አንዳች የተለየ ተግባር የሌላቸዉ በመሆኑም ነዉ በእግዚአብሔር መልእክት ዉስጥ ቦታ ያላገኙት። የሕወሓት(ኢሕአዴግ) መንግሥት አንደኛዉ መሰሪነቱና ተንኮለኛነቱ የሚገለጽበት፤ ቀለም የሌለዉን ወፍራም ብእር(እስክሪብቶ) ይሰጥህና እንኳን ለደብተር አይደለም ለአንድ ሉክ የማያበቃ ተግባር በባዶ ያስፈጽምሐል። «አሁን ርእሰ ብሔር ወይንም ርእሰ ፕሬዝዳንት ወይንም ንጉሠ ነገሥት ሆነሃል» እያለ በባዶ ሥልጣን አስቀምጦህ የራሱን ስዉር ዓለማ በመስራት እንደ ምስጥ ዉስጥ ዉስጡን እየቦረቦረ ባዶ አድርጎ ያስቀራሃል፤ ማንነትህንም ያስጠፋል።

እኝህን አዛዉንት ፕሬዝዳንት የሕይወት መዋዕለ ዜናቸዉን በሚገልጸዉ «ዱሮና ዘንድሮ» በሚል መጽሐፍ ላይ በተገለጸዉ መሰረት ያለፈዉን ሕይወታቸዉን የተረዳዉት በወጣትነት ዘመናቸዉ ለአገራቸዉና ለወገናቸዉ ፍቅር እንዳላቸዉና የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንጂ ዘረኝነትና ጎጠኝነተ ያልነገሠባቸዉ፤ እንዲሁም ስል እዉነት የሚቆረቆሩ ሆነዉ ነዉ ያገኘሁት። በደርግ ጊዜ ደግሞ «ተመሳስለህና ሕሊናህን ሽጠህ ኑር» የሚለዉ የእግዚአብሔር የለሽ አማኞች እምነት ተከታይ ሆነዉ ከበፊቱ ጽኑ አቋም ወርደዉ ነዉ ያገኘዋቸዉ። በሕወሓት(ኢሕአዴግ) ዘመን ደግሞ ከበፊት አቋማቸዉ ወርደዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለማጥፋት ቆርጦ በተነሳዉ ዘረኛና ጎጠኛ መንግሥት

ፓለቲካ ሕሊናቸዉ ተበክሎና ተመርዞ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ ሥርዓት ተባባሪና አራማጅ ሆነዉ ነዉ ያገኘዋቸዉ።

ታዲያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የሚታመኑትን ሰዎች አንዳች አይፈልጉምና እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚሄዱትንና አርቅቀዉ የሚሰጧቸዉን እንደ ድምፅ ማጉያ የሚያስተጋቡትንና እንዲሁም በኮልኮሌ ቁሳቁሶች፣ በመኪና፣ በወንበር፣ በቤት፣ በገንዘብ በመሳሰሉት ጥቅማጥቅሞች ሕሊናቸዉን የሚሸጡት ሰዎችን ነዉና በዙሪያቸዉ ያሰባሰቡት፤ ይኸዉ እሳቸዉ በሥጋ ሞት ከተጠሩ በኋላ በራሱ ሕሊና ፈጥሮ የሚሰራ ባለሥልጣን ሆነ ካድሬ ጠፍቶ «መለስ ባዘጋጀልን ራእይና መንፈስ ነዉ የምንመራዉ» በማለት በየእለቱ በተለያየ መገናኛ ብዙኃን(ማስ ሚዲያ) ሲለፍፉ ይደመጣል። ስንት ምሁራን የአገርና የወገን ፍቅር ያላቸዉ፣ ለሕዝቡ ብዙ መስራት የሚችሉ፣ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የታመኑ፣ የሚያስጠጋቸዉና የሚጠቀምባቸዉ አካል ተፍቶ አንገታቸዉን ደፍተዉ ዝም ብለዉ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ አገር ይኖራሉ። በዚህ ምክንያት ሰዎች አንድ ጥሩ የመናገር ችሎታ የነበረዉን መሪ በየቀኑ እንደ አምላክ ሲያወድሱትን ሲያገኑት ይታያል፤ ይደመጣል። ከእርሱ በመቶና በሺህ እጥፍ የሚያስንቁ ዕንቁዎች የሆኑ እዉነተኛ ኢትዮጵያዉያን ደግሞ ተረስተዉና መንገድ ተዘግቶባቸዉ ይገኛል።

እኝም አዛዉንት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ስሜታቸዉ ከዉስጣቸዉ ተመንግሎ በመዉጣቱና የወንበርና የክብር ፍቅር ከሕሊናቸዉና ከአምላካቸዉ በልጦባቸዉ በመገኘቱ ምክንያት፤ ከእነዚህ ከዓመፃ ልጆች ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ ለመስራት ፈቃደኛ ሆነዉ በመገኘታቸዉ ነዉ ወደ እዚያ ወንበር ላይ ሊመጡ የቻሉት እንጂ በአገሪቷ ላይ አንዳች የመወሰን ሆነ የማድረግ ብቃት የላቸዉም። አድርጉ የተባሉትን መፈጸም ብቻ ነዉ ተግባራቸዉ። የሚያሳዝነዉ ግን ከሳቸዉ ቀደም ብለዉ የነበሩት ፕሬዝደንት(ንጉሥ) ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባለፉት ሥርዓቶች ዉስጥ በተለየ አገልግሎት ዉስጥ ሳያልፉና የነበረዉንም ሁኔታ በቅርበት ሳይመለከቱ፣ በሕዉሓት(ኢሕአዴግ) መንግሥት ታቅፈዉ በመጀመሪ እዉነተኛ አገልጋዮች የሆኑ መስሏቸዉ የእነሱ ስራ አስፈጻሚና ፈጻሚ ሆነዉ ሲያገለግሉ ቆይተዉ፣ በኋላ ወደ ልባቸዉ ሲመለሱና አስመሳይና ተንኮለኛ መሆናቸዉን ሲመለከቱና ሲያስተዉሉ «እኔ የስም ፕሬዝዳንት(ንጉሥ)(ርእሰ ብሔር) መሆን አልፈልግም፤ የስም የስምማ ወላጆቼ ንጉሥ ብለዉኛል» በማለት ለሕሊናቸዉ ታምነዉ፣ የሚያገኙትን ጥቅምና ክብር ንቀዉ ፣ ከእነሱ በግልጽ ራሳቸዉን በመለየት ሕሊናቸዉ የሚያምነዉን እየተናገሩና እየፈጸሙ ይገኛሉ። እዉነትን ፍለጋ ላይ ስለሆኑ በመጨረሻ ሙሉን እዉነት አግኝተዉ ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታማኝ ሆነዉ እንደሚኖሩና እንደሚያገለግሉ እንገምታለን። ምክንያቱም አስተሳሰባቸዉ ሆነ አቋማቸዉ እንዲሁም ሕይወታቸዉ ምንም ይሁን ምን በሃያ ዓመት ዉስጥ ማንም ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ያላደረገዉን ዉሳኔ ነዉ ያደረጉትና አሁንም በሚያምኑበት መንገድ የመንግሥትን መሰሪነትና ተንኮል፣ ግፍና ጭካኔ ካለአንዳች ፍርሃት እየገለጹ ያሉት። ርእሰ ፕሬዝዳንት(ርእሰ ነገሥት)(ርእሰ ብሔር) ግርማ ወልደጊዮርጊስ ግን ባለፉት ሥርዓቶች ዉስጥ በተለያየ ኃላፊነት ያገለገሉና የአጼ ኃይለ ሥላሴን ሆነ የኮሎኔል መንግሥቱን ሥርዓት በሚገባ አዉቀዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ከተነሱትና እንዲሁም ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ካነገሡት የዓመፃ ልጆች

ጋር በጋራ መሰለፋቸዉና ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ተግባር መፈጸማቸዉ እንዲሁም የዓመፃ ተባባሪና ስራ አስፈጻሚ ሆነዉ በመገኘታቸዉ ነዉ የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ፡፡

በዚህ አጋጣሚ አንዳንድ የሕወሓት(የኢሕአዴግ) መንግሥት መሰሪ ተግባራቸዉን እገልጽላችኋለሁ፡፡ በሕገ መንግሥቱ ላይ የተጻፈዉና በተግባር የሚፈጸመዉ ፍጹም ተቃራኒ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ድጋፍ ለማግኘትና ለማስመሰል ያህል ነዉ በወረቀት ላይ ያሰፈሩት እንጂ በሕገ መንግሥቱ ተመርቶ የተለያዩ ክንዉኖች ሲፈጸሙ መንግሥት በተለያየ መንገድ ይበቀላቸዋል፤ ፍዳና መከራ ያደርስባቸዋል፡፡ አንዳንድ ምሳሌዎች ባቀርብ በሕገ መንግሥቱ «ማንም ሰዉ የመጻፍ፣ የመናገር ነጻነት... ወዘተ» አለዉ ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት መንግሥትን የሚደግፍና የሚያገን ከሆነ አንዳች ተጽህኖ ሆነ ገደብ አይደረግበትም፡፡ ነገር ግን ጽሑፉ ሆነ ንግግሩ የመንግሥትን መሰሪና ተንኮል እንዲሁም በቀልና ግፍ ተግባር የሚገልጽ ከሆነና ይህም በመንግሥት ሥልጣን ላይ ተጽህኖ ሊፈጥር የሚችል ከሆነ ወዲያዉ ነዉ ተናጋሪዉ ሆነ ጸሐፊዉ በተለያየ መንገድ በቀል የሚፈጸምበትና ለስደት፣ ለእስር፣ ለድብደባ፣ ለግድያ፣ ለተለያዩ መከራዎች የሚዳረገዉ፡፡ ታዲያ መሰሪነታቸዉ ደግሞ ይህም የጭከናና የግፍ ተግባር የሚፈጽሙት በሕግ ሽፋን የተለያዩ የሐሰት ሰነዶችንና ምስክሮችን በማዘጋጀት እንዲሁም በባለሥልጣናት ቀጥተኛ ትእዛዝ ነዉ፡፡ እንዲሁም የሕትመት ዉጤቶችን በተመለከተ ገበናቸዉን የሚያጋልጥ መጽሔት ሆነ ጋዜጣ ወይንም ሌላ ሰነድ አሳታሚዎችን «እንዳታሳትሙ» ብለዉ በማዘዝ ሲያግዱ፤ የአገር ዉስጥ ሆነ የዉጪ አካላት ለምን እንደከለከሉ ሲጠይቃቸዉ፤ ምንም እንደማያዉቁና ማንንም እንዳለገዱ ነዉ የሚናገሩት፡፡ ይህም ሕዝቡንና የሚጠይቃቸዉን አካል ለመሸንገልና ለማታለል ነዉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ቀጣፊዎች እንኳን አገር መምራት አይደለም ቤተሰባቸዉን እንኳ በአግባቡ መምራት የማይችሉ ከሕሊናቸዉ ተቃራኒ በሆነ ሕይወት የሚኖሩ ናቸዉ፡፡

ሌላዉ ምሳሌ ደግሞ በሕገ መንግሥቱ የሃይማኖት ነጻነት እንዳለና ሁሉም የመረጠዉንና ያመነበትን ማከናወን እንደሚችልና መንግሥትም በሃይማኖት ዉስጥ ጣልቃ እንደማይገባ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን ያለዉ እዉነታ ፍጹም ተቃራኒ ነዉ፡፡ ይኸዉም መንግሥት በእያንዳንዱ ሃይማኖት ዉስጥ ረጅም እጁን በማስገባት እንደፈለገ ነዉ የሚያሽከረክረዉ፡፡ አማኙ ሃይማኖቱን የሚወክል ያሚያምንበትን አገልጋይ ለመምረጥ ሲፈልግ እድሉን አይሰጡትም፡፡ ምክንያቱም በእርሱ ዘንድ የማይፈለጉ እንደ ቦይ ዉኃ ወደሚፈልገዉ አቅጣጫ መምራት የማይችለዉ አካል እዉቅና አይሰጡትም፡፡ ቀደም ሲል የሥልጣን እድሜያቸዉን ለማስረዘምና ስዉር የበቀል ተግባራቸዉን ለመፈጸም ሲሉ «እነዚህ ነፍጠኞች ወይንም ክርስቲያኖች ወይንም ዐምሓራዎች ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ ሃይማኖታችሁን ለዉጠዉባችኋል፤ አጥፍተዉባቸዋል፤ ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል ... ወዘተ» በማለት ለበቀልና ለጥላቻ ማነሳሳተቸዉና በቀላቸዉንም መፈጸማቸዉና ማስፈጸማቸዉ በደንብ ይታወቃል፡፡

አሁን ደግሞ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ዘንድ የሚደገፉና በጣም የሚፈለጉ የሃይማኖቱ ሰዎችን የሐሰት ስም በመስጠትና «አሸባሪ፣ ሁከት ፈጣሪ» በማለት በመወንጀል ለእስርና

ለግድያ ይዳርጓቸዋል:: እንዲሁም በአራቱም ማእዘን ባለሥልጣናቱንና ካድሬዎቹን በማዘዝ አማኙን ለመንግሥት የድጋፍ፣ ለማይፈልጋቸዉ አካላት ደግሞ የተቃዉሞ ሰልፍ እንዲወጡ ያስደርጋሉ:: ብዙኃን መገናኛዉ(ማስ ሚዲያዉ) በእርነሱ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ጨለማዉን ብርሃን ፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ እዉነተኛዉን ሐሰተኛ፣ ሐሰተኛዉን እዉነተኛ ያስብላል::

ሌላዉ ምሳሌ በሕገ መንግሥቱ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ ታዉጇል:: ነገር ግን ልክ ኤርትራን እንዳስገነጠሉ የራሳቸዉን መሰሪ ተግባር ለመፈጸምና ሥልጣናቸዉ ካልተደላደለና ለሥልጣናቸዉ አስጊ ነገር ከተፈጠረ አገሪቷ ብትንትኗ እንድትወጣና እንድትዳከም በማድረግ የራሳቸዉን ነጻ መንግሥት እንደ ኤርትራ ለመመስራት ነዉ እንጂ፤ የእነሱ ሥልጣን ከተደላደለና የሚፈልጉትን ጥቅም ካገኙና ስዉር ዓላማቸዉ ከተሳካላቸዉ፤ ሕዝቡ «እኔን የሚወክል አካል ነዉ የምፈልገዉ እንጂ የእናንተን ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚን አይደለም» በማለት ቢቃወማቸዉ፤ ዘረኝነትንና ጎጠኝነት ራሳቸዉ መፍጠራቸዉን ይክዱና ሌላዉን «ጠባብ፣ ዘረኛ፣ አሸባሪ» በማለት እርምጃ ይወስዱበታል፤ ፍዳዉን ያሳዩታል:: እንዲሁም ሕዝቡ «በምፈልጋቸዉ አካላት ነዉ መመራትና መተዳደር ያለብኝ፤ ከፈለጉ መልአክ ከፈለጉ ሰይጣን ቢሆን ምንም አያገባችሁም» ሲላቸዉ፤ «አይ እናንተ የምትፈልጋቸዉ ሰዎች ሰይጣናት ናቸዉ፤ እኛ ግን መልአክ ነንና ለእናንተ የምንጠቅመዉ እኛ ነን እንጂ እነሱ አይደሉም» ብለዉ ሕዝቡን በጦር ኃይላቸዉና በደኅንነታቸዉ እንዲሁም በካድሬዎቻቸዉ ተጽህኖ ዉስጥ እንዲገባ አድርገዉ በማይፈልጋቸዉ አካላትና በግለሰቦች እንዲመራና እንዲተዳደር ይደረጋል::

በፊት የመንግሥት ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ከዋናዉ መሪያቸዉ ጋር በመሆን « ክርስቲያኖች ወይንም ዐምሓሮች በኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች ላይ ጭቆናና ግፍ ፈጽመዋል» እያሉ በመጻሕፍት፣ በንግግር የሚገልጡትን ሰዎች፤ «ለእኛ የሚመቹ ዐምሓራን(ክርስቲያንን) የሚያስፈራሩና ለጥላቻና ለበቀል የሚያነሳሱ የቁርጥ ቀን ልጆች አገኘን» እያሉ ሲያበረታቷቸዉና ሲደግፏቸዉ እንዳልነበረ፤ እንዲሁም « እነዚህ ቆራጥና ጀግና ሰዎች፤ እነዚህ ዐምሓሮች(ክርስቲያኖች) አምላክ ነዉ ብለዉ የሚያመልኩትን ኢየሱስን እያጥላሉና እንደ ተራ ሰዉ አድርገዉ በመጻሕፍት አጋለጡልን፣ አጥላሉን» በማለት የዓመፃና የክህደት ተባባሪና መሪ መሆናቸዉ በደንብ እየታወቀ፤ አሁን ደግሞ «:- በቆፈርከዉ ጉድጓድ ትገባበታለህ፣ ባጠመድከዉ ወጥመድ ትጠመድበታለህ የሚለዉ አባባል በእኛ ላይ ሊሰራ ነዉ እንዴ! በማለት ለራሳቸዉ ሥልጣን አስጊ ሆነዉ ስለታያቸዉ የተለያየ ስያሜ በመስጠት ለተለያየ ችግርና መከራ ይዳርጓዋል::ነገር ግን «እኛ ለመንግሥታችሁ እንቆማለን ተለጣፊ እንሆናል» ቢሉ ደግሞ የጥላቻና የበቀል ተግባር እንዲፈጽሙ የሚያበረታቱና የሚደግፉ ናቸዉ::

ያም ብቻ አይደለም እነዚህ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች አሁንም «ግራኝ አሕመድ በክርስቲያኖች(በዐምሓሮች) ላይ የፈጸመዉ ግፍና በቀል እንዲሁም አብያተክርስቲያን ማቃጠሉ እንደትክክለኛ ተግባር መጻፋችሁና ማስተማራችሁ የሚደነቅ ነዉ፣ አሁንም እነዚህን ርዝራዦች ከማስፋራራትን ከማስጨነቅ ወደ ኋላ እንዳትሉ» በማለት ከመምከርና ከመደገፍ ወደ ኋላ የማይሉ፤

ሕሊናቸዉ በጥላቻና በበቀል የተሞላ፤ ለሥልጣናቸዉ እንጂ ለሕዝቡ አንዳች ስሜት የሌላቸዉ፤ ሕሊናቸዉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተመረዘና የተበከሉ ናቸዉ። ዞሮ ዞሮ ሰዉ የዘራዉን ማጨዱ አይቀርምና የዘሩትን የጥላቻና በቀል ዉጤት መራራ ቢሆንም ራሳቸዉ ይጠጡታል። በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቡበታል፤ ባጠመዱት የዘረኝነትና የጎጠኝነት ወጥመድ ራሳቸዉ ይጠመዱበታል።

ሌላዉ አሳፋሪና መራሩ፣ መሰሪ ተግባራቸዉ ደግሞ፤ «ሕሊናዬን አልሸጥም፤ እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ አልሄድም፤ ለሕሊናዬና ለአምላኬ ታምኜ ነዉ የምሰራዉ፤ የምኖረዉ፤» የሚለዉን ሰዉና መሰሪ ተግባራቸዉን የሚያጋልጠዉን ሰዉ፤ አንድ ቀን እንኳ መሳሪያ ተኩሶ የማያዉቀዉን ሰዉ፤ የጦር መሳሪያ እንዲይዝ አድርገዉ ፎቶ ግራፍ በማንሳትና በቤቱም መሳሪያ እንዳከማቸ አድርገዉ በማቀናበር እንዲሁም ባዘጋጁት የሐሰት ሰነድ ላይ በድብደባና በግዴታ እንዲፈርምበት አድርገዉ በደኅንነታቸዉ አማካይነት የሚፈጽሙት ኢ- ሰብአዊ ተግባርና በሕጋዊ ሽፋን ለማስፈረድ ደግሞ የተቀነባበረዉን የሐሰት መረጃቸዉን ለፍርድ ቤት በማቅረብ በወኪሎቻቸዉ አማካይነት ከእስራት እስከ ሞት ድረስ ማስፈረዳቸዉ ነዉ።

ከዚህ ጋር ተያያዝነት ያለዉና ዘግናኝና ጭከና ተግባራቸዉ ደግሞ፤ ክፋትና ክርፋት የሆነዉን ተግባራቸዉን የሚገልጸዉንና ሕሊናዬን አልሸጥም በሚለዉ ሰዉ የሚፈርዱት የእስርና የግድያ ዉሳኔ አላረካ ብሏቸዉ፤ ቤሰቦቻቸዉና ሕፃናት ልጆቻቸዉን ሳይቀር ለመበቀል ወተዉ ወርደዉ ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ይዘርፋሉ፤ ያዘርፋሉ፤ ያግዳሉ። በእነሱ ቤት ሌሎች ለሕሊናቸዉና ለአምላካቸዉ ታምነዉ የሚኖሩትንና ስለ እዉነት የሚመሰክሩትን ለማስፈራራትና አንገታቸዉን ለማስደፋት እንዲሁም ሕሊናቸዉን እንዲሸጡና እንዲሰደዱ ለማድረግ ነዉ። እዉነታዉ ግን ስለ እዉነት የሚመሰክሩ ሰዎች የበለጠ ቆራጥና ራሳቸዉንም ለበለጠ መስዋዕትነት የሚያዘጋጅ ይሆናሉ እንጂ እነሱ በክፋት እንደተጠበቡት በፍርሃትና በስጋት ከምስክርነታቸዉ አይለዩም። ለነገሩ እነዚህ ክፋትና ተንኮል እንዲሁም በቀል የሞላባቸዉ መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎችና ደጋፊዎቻቸዉ እንኳን ለሕሊናዉና ለአምላኩ የታመነዉን ሰዉ ይቅርና የራሳቸዉን አገልጋይና አባል የፈለገዉን ስርቆት ሆነ በደል ሲፈጽም ለእነሱ አገልጋይና ታማኝ እስከ ሆነ ድረስ ዝም ይሉታል። ነገር ግን «ወደ ሕሊናዬ ልመስል፤ ወይንም እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ አልወሰድም» ካለ፤ ያደረገዉም ያላደረገዉም ወንጀል ተቀነባብሮ እንደ ሌሎቹ ይፈረድበታል፤ ይበቀሉታል። በዚህም ምክንያት ሌላዉም የእነሱ ባሪያና አንደበት ሆኖ እስከ መጨራሻዉ ድረስ ሕሊናዉን እንደሸጠ ይኖራል። ያላስተዋሉት ነገር የዓመፃቸዉና የክፋታቸዉ ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ስለሆነ እጅግ የከፋዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ነዉ የሚመጣባቸዉና በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሱና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ካልተሰለፉ በስተቀር እግዚአብሔር በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ አይቀጡ አቀጣጥ ነዉ የሚቀጣዉ።

የጭከናና አረመኔነታቸዉ ተግባር ከሚገልጽልን አንዱን ብጠቅስ፡ በነጻ ሕሊናዉ በተፈቀደለት ሕግ መሰረት ሐሳቡን በነጻ በመግለጹና ያመነበትን በመናገሩ ምክንያት በሐሰት ተወንጅሎ ወደ እስር ከገባ በኋላ፤ «የሁከትና የሽብር ተግባር ፈጽሜያለዉ፤ በሀገር ላይ ክህደትና ዓመፅ ፈጽሜያለሁ፣

ሁለተኛ አይለመደኝም፤ ይቅርታ ይደረግልኝ» በል ያኔ ነጻ ትወጣለህ። ያለበለዚያ በእድሜ ልክ እስራት ወይንም በሞት ፍርድ ፍዳህን ታያለህ» በማለት ሕሊናዉን በማስገዳድና የተለያየ ስቃይና መከራ በማድረስ፣ ሰዉ ያላደረገዉንና ያልፈጸመዉን ተግባር «አድርጌያለሁና ይቅርታ ይደረግልኝ» እንዲል እያስደረጉ ነጻ የሚለቁና ከዚያም ያ ሰዉ ወይ እንዲሰደድ ወይ አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር ወይ የእነሱ ተለጣፊ አገልጋይ እንዲሆን ያደርጉታል።

«በነጻነት መደራጀት፣ መቃወም ትችላላችሁ» እያሉ የሕዝቡን ማንነት ለመለያ እየተጠቀሙበት የእዉነተኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትንና ደጋፊዎችን ወቅትና ጊዜ እየጠበቁ እታች ባሉ ካድሬዎቻቸዉና አገልጋዮቻቸዉ አማካይነት እየተከታተሉ የተለያየ ፈተናና መከራ፣ ስቃይ ያደርሱባቸዋል። ከፈለጉ ግድያ፣ ከፈለጉ እስራት፣ ከፈለጉ ድብደባ፣ ከፈለጉ ንብረት መዝረፍ፣ ከፈለጉ ከስራ ማፈናቀል፣ ከፈለጉ በቤተባቸዉ ላይ የተለያየ ጥቃት መፈጸም፣ ባጠቃላይ ከሕግ በላይ ሆነ የፈለጉትን ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ። የሚያሳዝነዉ ደግሞ ነጋ ጠባ «ዲሞክራሲ፣ ነጻነት ፣ እኩልነት፣ ሰብአዊነት፣ ፍትሕ፣ መልካም አስተዳደር ... ወዘተ ለማስፈን ነዉ የታገልነዉና እየሰራን ያለነዉ» እያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሆነ የዓለም ሕዝብ ይሸነግላሉ፤ ያስመስላሉ። ይህ የሚያሳየዉ የሚናገሩት ሌላ የሚሰሩተ ሌላ መሆኑንና የመጨረሻ መሰሪ መሆናቸዉን ነዉ።

ሲፈልጉ ደግሞ ማንኛዉንም ለመበቀል ሆነ ለማጥቃት የሚፈልጉትን ሰዉ ባወጡት የአሸባሪነትና የሙስና ሕግ መወንጀል ይችላሉ። ምክንያቱም እነሱ እንደ ወንጀል ያስጠይቃል ብለዉ በሁለቱም አዋጆች በወጡት የወንጀል ዓይነት ዉስጥ ከከፍተኛ ባለሥልጣናት እስከ ገጠር ቀበሌ ሊቀመንበር ድረስ እንዲሁም ከከፍተኛ የመንግሥት መስሪያ ቤት ኃላፊ እስከ ተራ ሰራተኛ ድረስ አንዱን ወይንም ከዚያ በላይ የሆነዉን በሙስና ወንጅል ከሚያስጠይቁ ያልፈጸም ሰዉ የለምና። ይህም ማለት በአዋጁ ላይ በተገለጸዉ መሰረት ተግባራዊ ይሁን ከተባለ ከአገሪቱ መሪ ጀምሮ እስከ ገጠር ድረስ ያለዉ ባለሥልጣንና ኃለፊ እንዲሁም የእያንዳንዱ መሰሪያ ቤት ኃላፊ እስከ ተራ ሰራተኛዉ ድረስ ከአንድ እስከ ሃያ አምስት ዓመት እንዲሁም እስከ እድሜ ልክ እስራት የሚያስፈርድ ወንጀል ሰርተዋልና፤ በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ዉስጥ ከላይ እስከ ታች ያሉ የመንግሥት ሆነ የግል ሰራተኞች ወንጀል ሰርተዋልና፤ እንደነሱ መሰሪነትና በቀለኝነት ቢሆን ኖሮ ሁላችንም መታሰር ነበረን።

ያለዉ እዉነታ ግን አዋጁ የሚሰረዉ እንደ ቦይ ዉኃ ወደሚፈለገዉ አቅጣጫ በቀላሉ አልሄድም የሚለዉን ሰዉ ለማጥቃትና ለመበቀል፣ ግለሰቦችና ቡድኖች ሊበቀሉት የሚፈልጉትን ግለሰብ ወይንም ድርጅት በሕግ አስታኮ ለመበቀልና ለማዳከም፤ እንዲሁም በሰሩት የዓመፃና በደል ተግባር በመጸጸት ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ለሕሊናቸዉ ለማደር የሚፈለጉትን በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩ ባለሥልጣናትንና ራሳቸዉን ከፖለቲካዉ ለማግለል የሚፈልሁትን፣ ባጠቃላይ «ለመንግሥት ሥልጣንና ስዉር ዓለማ እንቅፋት ሆነዋል፣ ገበናችንን አጋልጠዋል፣ ባዶናታችንን ገልጠዋል፣ እንደምንፈልገዉ ልንጋልባቸዉና ልናሽከረክራቸዉ አልቻልንም... ወዘተ» በማለት የማይፈልጉትን ግለሰብ፣ ቡድን፣ ድርጅት፣... ወዘተ ለመበቀል ነዉ እንጂ ለአገርና ለሕዝብ በማሰብ

አይደለም። እነዚህንና ሌሎች ድርጊቶቻቸዉን በዚህች በትንሿ እድሜያችን ተመልክተናል፤ ሰምተናል፤ አንብበናል።

ሌላዉ የግፍና የጭከና ተግባራቸዉ ደግሞ «ሕሊናዬን አልሸጥም ሕገ መንግሥቱን አክብሬ ያመንኩበትን እናገራለሁ» ባሉት ላይ ራሳቸዉ የሚፈጽሙት ግፍና ድብደባ አንሶ፤ በእስር ቤት ዉስጥ ባሉ ወንጀለኛ እስረኞች ያስደበድቧቸዋል። እንዲሁም አንድ ለአምስት አደራጅተዉ የሰዎችን ነጻነት ከመገፈፋቸዉና ስዉር የፓለቲካ ተግባራቸዉ ከመፈጸማቸዉ በተጨማሪ፤ ምንም ማድረግ የማይችለዉን እስረኛ በሌላ እስረኛ ያሰልሉ። ታዲይ እነዚህ የዓመፃ ሰዎች ከሰይጣናት እጅግ ቢብሱ እንጂ አያንሱም። ምክንያቱም ሰይጣናት አንዳች ተስፋ የሌላቸዉ ስለሆነ ተስፋ በመቁጠር በሰዉ ልጆች ላይ በሚችሉት አቅም ሁሉ ፈተናና ጥቃት ይፈጽማሉ። እነዚህ የሕዉሓት ኢሕአዴግ አገልጋዮች ግን በወገናቸዉ ላይ የግፍና የጭከና ተግባር ይፈጽማሉ፣ ያስጽማሉ። እንዲሁም ለሕያዉነት ሕይወት የመዳን እድል እያላቸዉ፤ «እኛ እንስሳ ነን እንወለዳለን፣ እናድጋለን፣ እንሞታለን፣ ሕይወታችን በዚህ ይደመደማል። ስለዚህ በዚህች ምድር ዉስጥ የፈለግነዉን ግፍና በደል፣ ተንኮልና ዓመፃ፣ ርኩሰትና ክህደት ፈጽመን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን ነዉ የምንኖረዉ» በማለት ራሳቸዉን እጅግ ለከፋዉ ቅጣት ያዘጋጃሉ።

አሁን ያለዉ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላና እስከ ቅርብ ጊዜ  ድረስ የሥልጣን እድሜያቸዉን ለማስረዘምና የዉስጣቸዉን ስዉር ዓላማ ለማሳካት እንዲሁም በዉስጣቸዉ በታጨቀዉ የጥላቻና የበቀለኝነት አስተሳሰብ ምክንያት ተፋቅሮና ተዋሕዶ የሚኖረዉን ሕዝብ «እናንተ ሙስሊሞች እነዚህ የገዥ መደብ የሆኑት ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) (ነፍጠኞች) በአገራችሁ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንድትኖሩ አድርገዋል፤ ሃይማኖታችሁን በእኩልነትና በነጻነት እንዳታመልኩ አድርገዋል። የተለያየ ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል። አሁን ግን የኢሕአዲግ መንግሥት በእኩልነትና በነጻነት እንድታመልኩ አድርጓል። ራሳችሁን በራሳችሁ እንድታስተዳድሩ ተደርጓል። የመረጣችሁት የሃይማኖት አባት እንዲመሯችሁና እንዲያስተዳድራችሁ ተደርጓል። ስለዚህ ኢሕአዴግን ምረጡ፤ እጅና ጓንት ሆናችሁ አብራችሁን ስሩ... ወዘተ» እያለ የማስመሰልና የተንኮል ስብከቱን እየሰበኩ፣ የራሳቸዉን ካድሬዎች እያስመረጡ፣ የዓመፃ ተግባር ማሰራታቸዉ እየታወቀ፤ አሁን ደግሞ የእምነቱ ተከታዮች «በመሪነት ያሉ ሰዎች ሌቦች፣ ቀማኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ወንበዴ፣ ካድሬዎች ናቸዉ። የመንግሥት ስራ አስፈጻሚ ናቸዉ እንጂ እኛን የእምነቱን ተከታይ አይወክሉንም፤ ከእምነታችን፣ ከዲናችን(ከአስተምሯችን) ዉጭ ያሉና የመንግሥትን ስዉር ዓላማ ለማሰካት የተሰለፉ ስለሆነ አንፈልጋቸዉም። ነጻነትና እኩልነት ተሰጢችኋል ከተባለ እኛን የሚወክል ምግባር ያለዉ የሃይማኖት ሰዉ እንምረጥ» በማለት ጥያቄቸዉን ሲያቀርቡ፤ መሰሪዉና ተንኮለኛዉ መንግሥት ግን «እኛ የምንፈልገዉ እንደ ቦይ ዉኃ ወደተፈለገዉ አቅጣጫ የሚሄደዉንና አንብብ የምንለዉን የሚያነብ፣ ለድጋፍ ሰልፍ አስወጣ ስንል የሚያስወጣዉን፣ ለተቃዉሞ ሰልፍ አስወጣ ስንለዉ የሚያወጣዉን፣ በቀልና በደል ፈጽም ስንለዉ በቀልና በደል የሚፈጽመዉን ነዉ እንጂ፤ እንደ እናንተ ዓይነቱማ አይፈለግም። ስለድፍረት አስተሳሰባችሁ በአገር ክህደትና በአሸባሪነት ትወነጀላላችሁ» ብሎ ለእርሱ አካሄድ አልመች ያሉትን በእስር የሚያጉር፣ ክፋትና ተንኮል የሞላዉ መንግሥት ነዉ። እንዲሁም

በሕጋዊ ሽፋን አማኙን ለምርጫ አስወጥቶ እንደ ፓለቲካዉ የራሱን ሰዎች የሚያስመርጥ ጨካኝ ነዉ፡፡

እነዚህ በወንበሩ ዙሪያ የተሰለፉ ከላይ እስከ ታች ያሉት ሰዎች፤ ለሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ የሚጠቀሙባቸዉ ሆነዉ ካገኙ ደግም ፊተዋቸዉ «እነዚህ የሚቀናቀኑን አካላት የቀድሞዉን የክርስቲያን መንግሥት ለመመለስ የተነሱ ናቸዉና ተቃወሙልን፤ አጥፉልን፤ እንደ በፊቱ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲን የሚያጥላላና የሚቃወም ጽሑፍ ጻፉ፤ አማኞቹን በተለያየ መንገድ ተጽህኖ አድርሱባቸዉ፤ ከዚህ በፊት በተለያየ ጽሑፋችሁ ፡- ግራኝ አህመድ ቤተክርስቲንን ማቃጠሉና ክርስቲያኖችን መጨፍጨፉ ትክክል ነዉ፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያኖትም መስጂድ አቃጥለዋልና እንዲሁም እስላሞችን ጨፍጭፈዋልና እያላቸዉ የጻፋቹትን በአድናቆት የምንመለከተዉና የምናበረታተዉ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያኖች(ዐምሓራዎች) ላይ ተጽህኖ ፈጠራችሁ፣ አስፈራራችሁ ማለት ለእኛ የሥልጣና እድሜ አራዘማችሁ ማለት ነዉ፡፡ ነገር ግን እናንተ አሁን ደግሞ ለእኛ ለሥልጣናችን አስጊ ስለሆነችሁና ገበናችንን እያጋለጣችሁ ስለሆነ «የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ» የተባለዉ እንዳይፈጸምብን ስንል ነዉ እናንተን ያሰርነዉ እንጂ፤ ለእኛ ሥልጣን አንዳች አስጊ ካልሆናችሁ በኅብረት ሆነን የዐምሓራዎችን ወይንም የነፍጠኞችን ወይንም የክርስቲያኖችን ሥርዓት በማጥላላትና የተለያዩ በቀል ተግባር በጋራ መፈጸምና ማስፈጸም እንችላለን፡፡ እንዲሁም «የብሔር ብሔረሰብ መብታችሁና ነጻነታችሁ እስከ መገንጠል ድረስ» በሚለዉ ሕገ መንግሥታችን የታወጀና የጸደቀ ስለሆነ የራሳችንን ዓላማ ካሳካን በኋላ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነጻ መንግሥታቸዉን ሲመሰርቱ ከፈለጋችሁ ያኔ እምነታችሁን ብሔራዊ ሃይማኖት ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ አሁን ግን የምንፈልግበት ደረጃ ላይ ስላልሆን ፡- ሃይማኖታችንን የሚወክሉ እዉነተኛ ሰዎች ይምሩን፤ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ይቁም ማለታችሁን አቁሙ፡፡ አይ በአቋማችን ነዉ የምንጸናዉ የምትሉ ከሆነ በአገር ክህደትና ሽብርተኛናት በእስር ትበሰብሳላችሁ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ትገደላላችሁ... ወዘተ» የሚሉና «እኔ ከሌለዉ ይህች አገር ትጥፋ፤ ሕዝቡም እርስ በእርሱ ይተላለቅ፤ ይባላ የሚሉ ፀረ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ፡፡

ሲያሰኛቸዉ ደግሞ፤ «የእኛን ጨካኝነትና በቀለኝነት ለማስተዋል ከፈለጋችሁ፤ የመጀመሪያዉ የኦሮሚያ ንጉሥ(ፕሬዝዳንት) የነበረዉ ሀሰን አሊን ለጨለማዉ ጌታችን መስዋዕት ሰዉተን ደም ቀብተነዉና በዋቄፈታ እምነት አጥምቀነዉ በክርስቲያኖች(በዐምሓሮዎች) ላይ የምንፈልገዉን የግፍና የበቀል ተግባር ካስፈጸምን በኋላ፤ እንደ ሸንኮራ መጠነዉ እንደጨረስን ጣዕሙ ስላለቀ ወዲያ ነበር ከሥልጣን የሻርነዉ፡፡ ሌላዉ ደግሞ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ንጉሥ(ፕሬዝዳንት) የነበረዉ ያረጋል አይሸሹምን ከሌሎቹ ፕሬዝዳንት(ነገሥታት)ና ባለሥልጣናት የተለየነ ተግባር ፈጽሞ ይመስላችኋል ወይ በሙስና ሽፋን በእስር እያማቀቅን ያለነዉ? አይደለም፡፡ እንደፈለግነዉ በሕሊናዉ ለመጋለብና ለመፈንጨት ሙሉ በሙሉ ሕሊናዉን ክፍት ስላላደረገልን ነዉ፡፡ እኳን እሱን ስዬ አብርሃምን እንኳ ያቺ የቀድሞ የአንድነት መሪ የነበረችዉ ብርቱካን ሚደቅሳ «ከወንጀሉ ነጻ ነዉ» ብላ ብትፈርድም እንድሜ ለበቀለኛዉ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በአንድ ምሽት አዋጅ አርቅቆና በአንድ ቀን እንደ ልቡ በሚጋልባቸዉና በሚፈነጭባቸዉ አገልጋዮቹ(ባሪያዎቹ) አማካይነት አጸድቆ በእስር

ፍዳዉን አብልቶልናል:: እሱን ብቻ አይደለም «ነጻ ነዉ ብላ» የፈረደችለትን ብርቱካንን ጭምር ወቅትና ጊዜ ጠብቆ በእስር ተበቅሏታል:: ዳግም ስለ እዉነት እንዳትመሰክርም ሕሊናዋን አቁስሎና አድምቶ የትግል ወኔዋን አኮላሽቶ ከአገር አሳዷታል:: እኛ እስከዚህን ከዚህም በላይ ነዉ ጠላታችንን የምንበቀለዉ:: ሌሎቹ ነገሥታት(ፕሬዝዳንቶች)ና ባለሥልጣናት እንዲሁም በተለያየ ኃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች በሙስና ሳይዘፈቁ ቀርተዉ ይመስላችኋልን ዝም ያልናቸዉ? አይደለም:: ነገር ግን በሕሊናቸዉ እንደፈለግን ስለምንጋልብና ስለምንፈነጭባቸዉ እንዲሁም አብዮታዊ ዲሞክራሲን ለማስፈጸም ቆራጦች ስለሆኑና አድርጉ፣ ተናገሩ፣ ፈጽሙ፣ የምንላቸዉን ሁሉ ስለሚያደርጉና ስለሚፈጽሙ፣ ስለሚያፈትሙ፣ ባጠቃላይ እንደልባችን ስለሆኑ ነዉ ስኳሩን መላስ ብቻ አይደለም እየቃሙት  ዝም የምንለዉ:: «ወደ ልባችን እንመለሳለን፣ ለሕሊናችን እናድራለን» ቢሉ ደግሞ ያደረጉትንም፣ ያላደረጉትንም አቀነባብረን ለእስርና ከባሰም ለሞት እንዳርጋቸዋለን:: እነሱም ብልጥ ናቸዉና ቀን ከሌሊት «አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ ብሔር ብሔረሰብ» እያሉ ታላቅ ምስክርነትን ስለሚሰጡና ሕሊናቸዉን ስለሚሸጡልን፣ እንዲሁም ስለሚገለባብጡልን አንዳች የበቀል ተግባር አንፈጽምባቸዉም፤ አናስፈጽምባቸዉም» የሚሉ፤ በሰዉ ሕሊና(ነፍስ) ላይ የሚጨክኑ ግፈኞችና መሰሪዎች ናቸዉ::

ሲፈልጉ ደግሞ፤« እናንተ ብሔር ብሔረሰቦችና ሙስሊሞች፤ እኛ በቋንቋ የከፋፈልናችሁና ክልላዊ መንግሥት የመሰረትንላችሁ ዋንኛዉ ምክንያት፤ ክርስቲያኑንን(ዐምሓራዉን)ና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለመበቀልና ለማዳከም ብሎም ከክልላዊ መንግሥታችሁ ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ነዉ:: ለዚህም ነዉ ለወደፊት ሃይማኖታዊ መንግሥት ጭምር ለመዘርጋት በሚያመቻችሁ መልክ ክልሎችን ያዋቀርነዉና ኢትዮጵያ የሚለዉን ስያሜ ለማስወገድ «ኦሮሚያ» የሚል ክልል የፈጠርነዉና በሂደትም ከፈለጉ በዋቄፈታ እምነት ወይንም በእስላማዊ እምነት እንዲተዳደሩ፤ በከተማዉ ዉስጥ ከእነርሱ የሚበልጡ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መኖራቸዉን ብናዉቅም ዓላማችንንና ግባችን ከላይ ለተገለጸዉ ስለሆነ «ሐረሪ» ክልል ብለን የመሰረትነዉ ለወደፊት እስላማዊ መንግሥት እንዲያቋቁሙ፤ «አፋርና ሱማሌ» ክልል ብለን የፈጠርነዉም ከላይ የተገለጸዉ ዓላማና ግባችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ፤ «ጋምቤላና ቤንሻንጉል ጉሙዝ» ክልል ብለን የፈጠርነዉም ከላይ የተገለጸዉ የበቀልና የማጥፋት ዓላማችን እንዲሳኩ፤ «ትግራይና አማራ» ክልል ብለን የመሰረትነዉም እዉነተኛና ብቸኛ እምነታችን የሆነዉን አብዮታዊ ዲሞክራሲን ለማስፋፋትና ብሎም የክልሉ እምነትና መንግሥት እንዲሆን፤ «ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች» ክልል ያለነዉም ለጊዜዉ ስለተቸገርን ነዉ እንጂ ለወደፊት እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ የራሱን ነጻ ሃይማኖታዊ መንግሥት መስርቶ ከላይ የተገለጸዉን ዓላማችንና ግባችንን እንዲያሳካ፤ «አዲስ አበባና ድሬደዋ» ከተማ አስተዳደር ብለን የሰየምነዉም ለጊዜ ዓላማችን የምናስፈጽምባቸዉ ከተሞች ስለሆኑ ለወደፊት አሸናፊዉ መንግሥት ስለሚጠቀልላቸዉ በዚያን ጊዜ ዓላማንና ግባችን እንደሚሳካልን እርግጠኞች ስለሆን ነዉ» በማለት ዉስጣቸው የታጨቀዉን ስዉር ዓለማና ግብ ከመግለጽ ወደኋላ የማይመለሱ ትዕቢተኞችና እብሪተኞች ናቸዉ::

ሌላዉ እጅግ ብዙዉን ምሳሌ ልተወዉና ዓለም የሚያዉቀዉን በክርስቲያኖች(በዐምሐራዎች) ላይ ካለቸዉ ጥላቻና በቀል የተነሰ እንኳን «ኢትዮጵያዊ ነኝ» የሚል አይደለም፤ ባዕዳን እንኳን

ያስቡታል፣ ይፈጽሙታል የማይባለዉን፤ እንደ ሸንኮራ አገዳ እየመጠጡ በሚያስወግዷቸዉና እንደ ፈረስ እየጋለቡ በሚጠቀሙባቸዉ አገልጋዮቻቸዉ(ባሪያዎቻቸዉ) አማካይነት ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ስንቱን ክርስቲያን(ዐምሐራን) ካስጨፈጨፉና ካፈናቀሉ፣ እንዲሁም በቋንቋ አትችሉም ሽፋን ከተለያየ የስራ ገባታ እንዲባረሩ ያደረጉት አንሶዋቸዉ፤ እንደ ዜጋ እንኳ እንዳይኖሩ «ይህ ክርስቲያኖች(ዐምሐሮች) የበዙበት ከተማ ነዉና እነሱን ለማዳከምና ብሎም ለማክሰም «ጎባ» የሚባለዉ የባሌ ዋና ከተማ ተሸሮ ሌላ አዲስ «ሮቤ» የሚባል ከተማ በቅርብ ርቀት እንዲመሰረት አስደርገዋል። እንዲሁም ልጆቻቸዉ በማታዉ መርሐ ግብር የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ «የሚሰራዉ የመዳወላቡ መካነ አእምሮ(ዩኒቨርስቲ) እነሱ ከሚኖሩበት ራቅ ያለ ይሁን» በማለት፤ ዉስጣቸዉ ክፋትና ተንኮል፣ ጥላቻና በቀል እንዲይዙ ባደረጓቸዉ ባለሥልጣናት አማካይነት የዓመፃና የክፋት ተግባር በማስፈጸም በሮቤና በጎባ መካከል ማሰራት እየተቻለ በጎባ የሚኖሩት ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከሮቤ አልፎ እንዲሰራ አስደርገዋል።

ሌላዉ ደግሞ «ልዩነታችን ወይንም መከፋፈላችን ወይንም ብዙኃነታችን አንዳች እንዳይቀለበስና ወደ አንድነት እንዳይመጣ፤ እናንተ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎች እንዲሁም ደጋፊዎቻችን አጥብቃችሁ መስራት ያለባችሁ ለምሳሌ ያ የነፍጠኞችና የትምክህተኞ ሰንደቅ ዓላማ የሆነዉ ፦ የኖኅ ቀስተደመና ከእግዚአብሔር የተሰጠን ኪዳን ነዉ የሚሉት አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነዉን እኛ የቁርጥ ቀን ልጆችና በእሳት ተፈትንና ለዚህ አገልግሎትና ብቃት ላይ የደረስን ሕወሓት ኢሕአዴጎች ከሰንደቅ ዓላማነት እንዳስወገድነዉና ይልቁኑ የጌታችን የመሪያችንን ዓርማ ኮኮብ አድርገን እንዲበላሽ እንዳደረግነዉ ሁሉ፤ እናንተ ደግሞ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታችሁ ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር በልቦናችሁ በማንገሥና የጥንቲቷ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ከልቦናች መንግላችሁ በማዉጣት የጌታችንና የመሪያችንን ዓርማ ኮኮብ ከፍ በማድረግ የብሔር ብሔረሰባችሁን ሰንደቅ ዓላማ ጭመር በልብስ መልክ አሰፍታችሁ መልበስ ይጠበቅባችኋል። እንዲሁም የነፍጠኞች ወይንም የክርስቲያኖች ወይንም የዐምሓሮችን ቋንቋ ብታዉቁ እንኳ፤ በታላቁ እምነታችን አብዮታዊ ዲሞክራሲ የማያምኑ ከሆነ እነሱ ቢያነጋግሯችሁ እንኳ እናንተ በብሔር ብሔረሰብ ቋንቋችሁ መልሱላቸዉ እንጂ በበከተዉ ዐምሓርኛ ቋንቋ አታነጋግሯቸዉ። ያ ብቻ አይደለም እናንተ ብሔረሰቦች በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቦታ፣ በማኅበራዊ ኖሮዋችሁ ሁሉ ከራሳችሁ ብሔር ብሔረሰብ ጋር ብቻ ጋደኝነትና ጉርብትና በመፍጠር እየተቧደናችሁ ኑሩ እንጂ አንድ ላይ መዋሐዱ ለወደፊት ነጻ መንግሥቶቻችሁ ላይ ተጽህኖ የሚፈጥርና ድንገት ልትዋሐዱ፣ ከዛም ባለፈ ዐማርኛን ቋንቋ ቋንቋችሁ አድርጋችሁ ልትጠቀሙ ስለምትችሉ፤ ይህ ደግሞ እኛ መስዋዕነትን ከፍለን፣ ደማችንን አፍስሰን፣ አጥንታችንን ከስክሰን ያመጣነዉን እኩልነት፣ ነጻነት፣ ዲሞክራሲ፣ የብሔር ብሔረስብ መብትና ነጻነት እስከመገንጠል የሚለዉን ታላቁና ገናናዉ ሕገመንግሥታችንን አደጋ ዉስጥ የሚከተዉ ይሆናል። በመሆኑም ጓደኝነትና ጉርብትና ብቻ አይደለም ጋብቻችሁን ጭምር የአፍ ምፍቻ ቋንቋችሁን እንደ ዋና መስፈርት አድርጋችሁ ከብሔር ብሔረሳችሁ ዉጭ እንዳትጋቡ።

ሌላዉ ደግሞ የክርስቲያን (የዐምሓራ) እምነት እምነታችን ነዉ ብላችሁ እንዳትቀበሉ። እናንት እምነታችሁን በብሔር ብሔረሰብ እምነት አድርጋችሁ አምልኮታችሁን ከፈለጋችሁ በወንዝ፣

ከፈለጋችሁ በተራራ፣ ከፈለጋችሁ በአድባሩ፣ ከፈለጋችሁ በጥንቆላዉና በሚርት ቦታ ላይ ማድረግ ይኖርባችኋል እንጂ፤ የብሔር ብሔረሰብ ሃይማኖታችሁ ያልሆነዉን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የነፍጠኞችና የትምክህተኞች ምሽግ የሆነችዉ ቤተክርስቲያን፤ ቤተክርስቲያን አድርጋችሁ እንዳትቀበሉ:: ይልቁኑ አገልጋዮቻቸዉንና አማኞቻቸዉን ለማጥላላትን ለማራከስ፤ እነሱ ቁሶቻቸዉ ጥምጥም እያደረጉ የሃይማኖት አባቶች ነን እንደሚሉና ቡራኬ እንደሚሰጡ ሁሉ፤ እናንተም አናታችሁ ላይ ጥምጣም እያደረጋችሁ እንደ ብሔር ብሔረሰባችሁ ቡራኬ መስጠት ነዉ እንጂ አንዳች እነሱን እንዳታቀርቡ:: ያ ብቻ አይደለም እነሱ ለበዓል በነጭ ልብስ ደምቀዉ በዓላቸዉን እንደሚያከብሩ፤ እናንተም የዚያ ተቃራኒ ነጭ ባልሆነ ልብስ ከፈለጋችሁ የብሔራዊ ክልላችሁን ሰንደቅ ዓላማ፣ ካልሆነም ደግሞ ከእነርሱ የምትለዩበትን የብሔር ብሔረሰብ ልብስ መልበስ አለባችሁ እንጂ እነሱ የሚለብሱትን ለበሳችሁ ማለት በተዝዋዋሪ አንድነትን ፈጠራችሁ ማለት ነዉና ይህ ደግም ለወደፊት ነጻ መንግሥታችሁና ለብሔር ብሔረሰብ መብታችዉና እኩልነታችሁ እንዲሁም ነጻነታችሁ አደጋ ላይ ይወድቃል:: እኛ ሕወሓት ብአዴን ኢሕአዴጎች እናንተ ያንን የክርስቲያኖች(የዐምሓራዎችን) ነጭ ልብስ ለብሳችሁ ከምንመለከት ራቁታችሁን ሆናችን ብንመለከት ነዉ የምንመርጠዉ:: ምክንያቱም :-እነዚህ ሰዎች ከእኛ አቋምና አመለካከት ወጡ እንዴ? በማለት ልክ ንጹሁን ኮከብ የሌለበትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ስንመለከት ዓይናችን ደም እንደሚለብስና ደማችን እንደሚፈላ ሁሉ፤ በዚህ አለባበስ ስትገለጹ እንዲሁም ዓይናችን ደም ይለብሳል፣ ደማችንም ይፈላብናል:: ሌላዉ ቢቀር በደም ብዛት እንዳንጠፋ ለህልዉናችን ስትሉ ይህን ነጭ ልብስ እንዳትለብሱ አደራ እንላለን::

ልዩነታችንና መከፋፈላችን በማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ለመድረስና የአንድነት ተስፋ ሙሉ በሙሉ ለማክሰምና ለማጥፋት፤ በልብሳችሁ ሆነ በባርኔጣችሁ(ኮፍያችሁ) እንዲሁም በክልላዊ ብሔራዊ መንግሥታችሁ ሰንደቅ ዓለማ ላይ፣ ከሆነላችሁ የወደፊት ነጻ መንግሥታችሁን እንደ ኤርትሪያ፤ ትግሪያ፣ ኦሮሚያ፣ አማሪያ፣ ሱማሊያ፣ አፋሪያ፣ ሐረሪያ፣ ጋምቤሊያ፣ ጉሙዚያ፣ ሲዳሚያ፣ ወላይቲያ፣ ሃዲዩያ፣ አገዊያ፣ ሲልጢዩያ... ወዘተ በማለት ጽሑፍ ልታደርጉበት ይገባል እንጂ በምንም ዓይነት ሁኔታ ኢትዮጵያ ብላችሁ መጻፍና እንዲነበብ ማድረግ የለባችሁም:: እኛ ሰንደቅ ዓለማዉ አረንጋዴ ቢጫ ቀይ እንኳን በእጅ ተይዞ አይደለም በወረቀት ላይ ጭምር እንዳይታይ ነዉ በአዋጅ የደነገግነዉና ማተሚያ ቤቶችም ይህን አዋጅ በመፍራት ደፍረዉ በኅትመት ላይ የማያወጡት:: እኛ እስከዚህ ድረስ ነዉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለማጥፋት ቆርጠን የተነሳነዉና በሰንደቅ ዓላማ ላይም የግፍ የዓመፃ የክህደት ተግባር የፈጸምነዉና ታላቁ የጨለማ ገዥ ደስ የሚሰኝበትን ኮከብና የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓለማ ያገነንለትና ከፍ ከፍ እንዲል፣ እንዲዉለበለብ ያስደረግነዉ:: ስለዚህ እናንተም እንደኛ የመጨረሻ ቆራጦችና ጀግኖች መሆን ይጠበቅባችኋል:: ያኔ ነዉ በታላቁ በጨለማዉ ጌታችን ዘንድ ሞገስ የምታገኙትና ከአንዱ ወደ አንዱ ወንበር የምትሸጋገሩት:: በተቃራኒዉ ደግሞ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነታችን ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ከፈጸማችሁ፤ ወይ እስር፣ ወይ ስቃይ፣ ወይ ስደት፣ ወይን ችግር፣ ወይን ሞት ነዉ የሚጠብቃችሁ:: የመቅሰፍት በሽታ ግን አይዛችሁም::

ሌላዉ እዚህ ላይ ኢትዮጵያ በሚለዉ ስም ላይ የፈጸምነዉን ግፍ እንነግራችኋለን፤ ይኸዉም ሕይወት ያለዉን ፍጥረት ብቻ አይደለም በብሔር ብሔረሰብ የከፋፈልነዉ፤ ሕይወት የሌላቸዉን ፍጥረታትን ጭምር ነዉ:: ይኸዉም መኪኖችን ብትመለከቱ እያንዳንዳቸዉ «አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ሱማሌ፣ አፋር፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣... ወዘተ» የሚል ስያሜ አልብሰናቸዋል:: ለወደፊትም ሰያሜ ያልተሰጣቸዉ መኪኖች ቅር እንዳይላቸዉ በሰማኒያ ብሔር ብሔረሰብ ስም እንሰይማቸዋለን:: እኛ ሕወሓት ብአዴን ኢሕአዴጎች የዚህን ያህል ነዉ ኢትዮጵያ በሚለዉ ስያሜ ላይ በቀል እየፈጸምን ያለነዉና ጥላቻችንን እየገለጽን የምንገኘዉ::

ያ ብቻ አይደለም ልዩነታችንና መከፋፈላችን የበለጠ እንዲጠናቀርና እንዲጎለብት ጌታችንና መሪያችን ያወጣልን ታላቁ መጠሪያችን «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን በዓለም ላይ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቀዉን ረቂቁን ልዩ ስም፤ ልክ ክርስቲያኖቹ (ዐምሓራዎቹ) ነጋ ጠባ አቡነ ዘበሰማያት እያሉ ሁል ጊዜ እንደሚደጋግሙ፤ እናንተም በቴሌቪዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በስብሰባዉ፣ በዉይይቱ፣ በንግግሩ፣ በበዓላቱ፣ በእድሩ፣ በቅሬዉ፣ ባጠቃላይ በማንኛዉም ጊዜ ብሔር ብሔረሰብ ማለት ይገባችኋል እንጂ፤ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትሉ ከሆነ፤ «እኔ ትግሬ ነኝ፣ እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ፣ እኔ ሱማሌ ነኝ፣ እኔ አፋር ነኝ፣ እኔ ሐረሪ ነኝ፣ እኔ ጋምቤላ ነኝ፣ እኔ ጉሙዝ ነኝ፣ እኔ ሲዳማ ነኝ፣ እኔ ወላይታ ነኝ፣ እኔ ሃዲያ ነኝ፣ እኔ ስልጤ ነኝ፣ እኔ አገዉ ነኝ፣ እኔ እገሌ ነኝ... ወዘተ» የሚለዉ ልዩ መለያችንና አጠራራችን አደጋ ዉስጥ ስለሚገባና ኢትዮጵያዊነት ስሜት ስለሚያቆጠቁጥ ብሎም አንድነትና ዉሕደት ሊመጣ ስለሚችል ልዩነታችን ሊቀለበስ ይችላል:: በመሆኑም ልዩነታችንና መከፋፈላችን ሊቀለበስ እንዳይችል የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ይገባናል::» በማለት ሁል ጊዜ ቅስቀሳ በመሪዎችና በባለሥልጣናት እንዲሁም በካድሬዎች መደረጉ የሚያሳየን በራሳቸዉ ከንቱ በሆነ ሥጋዊ መጠበብ የሥልጣን ዘመናቸዉን የሚያስረዝሙ መስሏቸዉ ነዉ:: ያላወቁትና ያላስተዋሉት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ከፈቀደላቸዉ የባለጊዜበት ዘመን አንድ ቀን በራሳቸዉ ሥልጣንና ኃይል መጨመር እንደማይችሉ ነዉ::

ሌላዉ የዉስጣቸዉ የታጨቀዉ የከረፋ ሐሳባቸዉና ምኞታቸዉ ደግሞ፤ «እናንተ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በግልጽ ሊታዉቁት የሚገባችሁ እኛ ሕወሓት ብአዴን ኢሕአዴጎች እናንተን የአሁን የስም ኢትዮጵያዉያን የወደፊት ደግሞ ከሰማኒያ በላይ ነጻ ዜጎችን በሦስት ደረጃ ከፋፍለናችኋል፤ እንዲሁም የብቃት ደረጃ ሰተናችኋል:: ይኸዉም:

ሀ. ሕዝቦች የምትባሉ፤ እናንተ ብሔረሰብ የሚለዉ ደረጃ ላይ ያልደረሳችሁ ናችሁ:: በመሆኑም በአሁን ሰዓት ከእኛ አስተሳሰብና አመለካከት ወታችሁ :- የራሳችን ዞንና ክልልላዊ መንግሥት ይኑረን፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋችን እንማር፣ እንስራ፣ እንዳኝ፣ ብትሉ በሁከት ፈጣሪነትና በአሸባሪነት ካለምንም ምሕረት ዋጋ የምትከፍሉ(የምትቀጡ) ናችሁ:: እኛ በሌሎች ብሔረሰቦች ይህን መብትና ነጻነት የፈቀድነዉ ዐምሓሮችን(ክርስቲያኖችን) ለመበቀል ፈልገን ነዉ::

ለ. ብሔረሰቦች የምትባሉ ደግሞ፤ ብቃታችሁ ከሕዝቦች በላይ ስለሆነ የራሳችሁ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ያላችሁና በራሳችሁ ብሔረሰብ ቋንቋ መማር፣ መስራት፣ መዳኘት የምትችሉ፤ ክርስቲያኖችን(ዐምሓሮችን) ደህን አድርጋችሁ የተበቀላችሁልን ምርጦቻችን ናችሁ:: እናንተም ብትሆኑ እኛ ሳናዛችሁና በሉ፣ አደርጉ ሳንላችሁ :- የራሳችን ነጻ መንግሥት እንመስርት፣ እንገንጠል ብትሉ ካለምንም ምሕረት  በአሸባሪነት ወይንም በሙስና ተወንጅላችሁ ፍዳችሁን ነዉ የምታዩት::

ሐ. ብሔር የምትባሉ፤ እናንተ ከወርቅም አልፋችሁ ዕንቁ ደረጃ ላይ ያላችሁ ስለሆነ በእርግጥ እናንተን እንዲህ ማለት ቢከብደንም የምንለግሳችሁ ምክር አለ:: ይኸዉም :- ጠግበናል እስከምናስታዉክ ድረስ ነዉ ወይ ነጻ መንግሥታችንን የማንመሰርተዉ? ኤርትራ እንኳ ይኸዉ ሃያ ዓመት በላይ ነጻ ሪፓብሊክ መንግሥት መስራታ በነጻነት፣ በዲሞክራሲ፣ በእኩልነት እየተዳደረች ያለችዉና ታላቋ አገር እየተባለች የምትጠራዉ:: ለምን እኛስ ታላቋ አገርና ዜጎች ተብለን እንድንጠራ «የብሔር ብሔረሰቦና ሕዝቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል» በሚለዉ አዋጃችን ተጠቅምን ነጻ አገራችንና መንግሥታችን የማንመሰርተዉ? ለምትሉት ታላቅ ጥያቄ ያለን ምላሽ፤ በእርግጥ ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን ሆኖ ይህን ጥያቄ ማቅረቡ ሞኝነት ሞሆኑን ሳንገልጽ ብናልፍ ለወደፊት ይጸጽተናል:: ስለዚህ አሁን ይህን ጥያቄ ባናነሳ ይመረጣል:: ነገር ግን ታላቁ ጅግናዉና ባላራእዩ መሪያችን ጓድ መለስ ዜናዊ በ2004 ዓ.ም ላይ «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ  ሁለተኛዉ መልእክት ላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ በገጽ 266 ላይ እንደገለጸልን፡

« እኔ ተልእኮዬንና ሩጫዬን ጨርሻለሁ:: እናንተ አጉል ተስፈኞች «የኢትዮጵያ ትንሣኤ ይመጣል::» በማለት የምትጠባበቁ ከዛሬ ጀምሮ ተስፋችሁን ሙሉ በሙሉ ልትቆርጡ ይገባል:: ከፈለጋችሁ ወደ አዉሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤሽያና አረብ አገራት መሰደድ ትችላላችሁ:: ከሚቀጥለዉ ዓመት ጀምሮ «ኢትዮጵያ » የሚባል ስም በብሔር ብሔረሰቦች አገራት አይጠራም» እንዳሉና እሳቸዉም ተልኳቸዉንና ሩጫቸዉን ጨርሰዉ ወደ ታላቁ የጨለማዉ ገዥ ግዛት ስለሄዱ፤ እኛም የበላነዉ ሳያስታዉከን በቃን ብለን ነጻ አገራችንና መንግሥታችንን እሱ ባዘዘን መሰረት በዚህ በ፳፻፭ (2005) ዓ.ም ተግባራዊ ብናደርግ ሳይሻለን እንደማይቀር ለመጠቆም እንወዳለን::» በማለት በትዕቢትና በንቀት እንዲሁም በእብሪት ከመናገር ወደ ኋላ የማይሉ ናቸዉ::

ከዚህ በተጨማሪ «እናንተ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ምንም እንኳን በብሔር ብሔረሰባችሁ ዘመን አቆጣጠር ብትመሩና በዓሉንም ብታከብሩ ደስታዉን ባንችልም፤ የእኛ አቋምና አስተሳሰብ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነታችንና ለፓለቲካን የሚጠቅመን ከሆነ የክርስቲያኖችን (የዐምሓሮችን) ዘመን አቆጣጠር እንጠቀማለን፡፡ በመሆኑም ለጊዜዉ ቢሆንም በራሳችሁ ብሔር ብሔረሰብ ዘመን አቆጣጠር በዓላችሁን ብታከብሩም፤ የመስሪያ ቤት አሰራሩን ግን በአበሾቹ አቆጣጠር ተገልገሉ:: ለወደፊት ነጻ መንግሥታችሁን ስትመሰርቱ ከፈለጋችሁ :- እኛ አዉሮፓዊ ነንና እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር ነዉ የምንቆጥዉ እንደምትሉ ያኔ የአበሾቹን አቆጣጠር አስወግዳችሁ እንደ አዉሮፓዉያን አቆጣጠር መጠቀም ትችላላችሁ:: ከፈለጋችሁ ደግሞ እንደ ብሔር ብሔረሰብ ዘመን አቆጣጠራችሁ መጠቀም ትችላላችሁ:: ከፈለጋችሁ ደግሞ እንደ ታላቁ ነብያችሁ መሀመድ ልደት በሂጅራ አቆጣጠር

*መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ከፈለጋችሁ ደግም ለብሔር ብሔረሰብ መብትና ነጻነት እኩልነት ለታገለዉና ላላችሁበት የብልጽግና ጎዳናና እንዲሁም ታላቅነት ባበቃችሁ በታላቁ ጀግናዉና ስማዕቱ መሪያችን መለስ ዜናዉ ልደት ተከትላችሁ መቁጠርና ለዘላላም ይህን ታላቅ አባታችንና ጌታችንን ልታስቡት ትችላላችሁ፡፡*

*አሁን እያደረጋችሁት ያለዉ ታላቅ ተግባር እጅግ የሚያስመሰግኛችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን፡፡ ይኸዉም ፡-በመቶ ብር ኖት ላይ የታላቁ አባታችንና መሪያችን ምስል ይዉጣ፣ ያኔ ብሩ በረከት ይኖረዋል፤ እንዲሁም መንገዶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት፣ ባጠቃላይ ግንባታዎች ላይ ልክ እንደ ፕሪሜሪ ሊግ መለስ ጨዋታ፣ መለስ ሩጫ... ወዘተ እንደተሰየመ፤ ግንባታዎች ሁሉ ኮንደሚኒየም ሳይቀር መለስ ኮንደምኒየም ይባል ብላችሁ ጥያቄ ማቅረባችሁና እንዲሁም ከዋናዊ ፌደራል ሪፓብሊክ መንግሥት ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ክልልና ገጠር ገበሬ ማኅበር ድረስ የታላቁ አባታችሁና መሪያችሁ መለስ ዜናዉ ፎቶ ግራፍ በቢል ቦርድ፣ በባነር፣ በፎቶግራፍ፣ በወረቀት በየመስሪያቤቱና በየመንገዱ በእስር ቤት ሳይቀር በመለጠፋችሁና ከፍ ከፍ በማደረጋችሁ፣ ቀን ከሌሊት እንደ አምላክና አማልክት ቆጥራችሁት ናፍቆታችሁን በምስሉ በመወጣታችሁና እንዲሁም ከሥጋዉ ለይቶ የወሰደባችሁን ለመበቀል በቁጭት ተነስታችሁ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በስብሰባ፣ በጽሑፍ፣ በእድር ሳይቀር በጸሎት እየተለማመናችሁና ለታላቁ ለጨለማዉ ገዥም ዓይናችሁን ጨፍናችሁና አንገታችሁን አቀርቅራችሁ ምስጋና በማቅረባችሁ ነዉ፡፡ እንዲሁም በየዕለቱ ዝማሬና ምስጋና ስለምታቀርቡለት ነዉ፡፡ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር እንኳ የጌታችንና የመሪያችንን መለስ ዜናዊ ያህል እንኳ አልገነነም፣ አልተመሰገነም፣ በየዕለቱ በተለያዩ በብዙኃን መገናኘ ስሙ አልተጠራም፡፡ ታዲያ አደራ የምንላችሁ አንዳንድ ሚርተኞች የሚናገሩትን እንዳትሰሙ፡፡ ይኸዉም «የዓመፀኞች መታሰቢያ ለዘላለም ይጠፋል፤ በቅዱስ ኪዳኑ ላይ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ከምድር በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠረጋሉ፤ መታሰቢያቸዉም ለዘላለም ይደመሰሳል፤ ቅዱስ ኪዳኑን የጠበቁና ያስጠበቁ ደግሞ ለዘላለም ይታሰባሉ» የሚሉትን ነዉ፡፡*

*ለወደፊት ደግሞ ዋናዉ ታሪካችሁ ከተጀመረበት በአበሾቹ አቆጣጠር ከግንቦት፳÷፲፱፻፹፫* **(20/9/1983)** *ዓ.ም ጀምራችሁ የዘመን አቆጣጠራችሁን ልታስተካክሉ ትችላላችሁ፡፡ የመለስ ፍቅር ከጸናባችሁ ደግሞ ወደ ኋላ ሄዳችሁ ለእናንተ ብርሃን ለመሆን ከተወለደበት ቀን ልትጀምሩ ትችላላችሁ፡፡ ነጻ መንግሥታችሁንና እናት አገራችሁን ስትመሰርቱና ሪፓብሊክ ብላችሁ ስትሰይሙ እንደ ፍላጎታችሁና ምኞቻችሁ ልታደርጉት የምትችሉት ነዉ፡፡ አሁን ግን በእኛ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምንት መሰረት አድርጉ ስትባሉ ማድረግ ፈጽሙ ስትባሉ በመፈጸም ነዉ የሚጠበቅባችሁ እንጂ ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ ፡-የምታመነዉ ለሕሊናዬና ለአምላኬ ነዉ ብትሉ፤ አንዳንድ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት ተቃዋሚዎች ፡-በተንኮል ሀሳቡና በበቀል ተግባሩ እድሜዉ አጠር ቢሉም፤ እኛ በአብዮታዊ ድሞክራሲ እምነት በምናምን ግን እድሜዉ በብልሀት ሐሳቡና በቀና ተግባሩ አጠረ እንጂ፤ እድሜ ለታላቁ መሪያቸን ለአቶ መለስ ዜናዊ እናንተንና መሰሎቻችሁንን የምንበቀልበት እጅግ እጅግ የተትረፈረፈ የበቀል አዋጅ አለን፡፡ ስንፈልግ ስኳር ቃሙ፣ ስኳር ላሱ ብልን፤ እድሜ በሕሊናቸዉ ለምንፈነጭባቸዉና በሰዉነታቸዉ ለምንጋልብባቸዉ ዐቃቤ ሕግና ዳኞች እንዲሁም*

የሐሰት መረጃ አቀነባባሪ ልዩ ኃይሎች፤ ለፈለግነዉ ዓመት እንድትቀጡና መከራችሁን እንድታዩ ልናስደርግ እንችላለን፡፡ ከፈለግን ደግሞ ማንንም ሰዉ ልንበቀልበት በምንችለዉ የአሸባሪነት አዋጃችን እስከ ሞትና ንብረት መዝረፍ ጭምር ልናስፈርድባቸዉ እንችላለን፡፡ ስንቶቹን ጋዜጠኛና የተቃዋሚ ድርጅት አባላትን በነፍስ በሥጋቸዉ እንዴት አድርገን እንደተጫወትንባቸዉና እንደምንጫወትባቸዉ አታስተዉሉምን? እኛ ለሚቃወመንና ሕሊናዬን አልሸጥም ለሚለን እስከዚህ ድረስ ጨካኝና አረመኔ ነን፡፡ ስለዚህ እንኳን በተግባርና በንግግር አይደለም በሐሳብ ከእኛ አስተሳሰብና አቋም ብትወጡና ምንም እንኳ አንዳንድ ጨለምተኞች ፡- ተግባራዊ የማይሆኑ፣ ነገር ግን ለማስመሰል በወረቀት ላይ የተጻፉ ቢሉም፤ እኛ ግን በተግባር የዋሉና የተፈጸሙ በማለት ታላቅ ምስክርነት የሰጠንባቸዉ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነታችንና የብሔር ብሔረሰብ እኩልነት፣ ነጻነት ፣ ዲሞክራሲ፣ ፍትሐዊነት፣ መልካም አስተዳደር፣ ፍትሐዊ ሀብት ክፍፍል፣ ባጠቃላይ ሕግ መንግሥቱ ላይ የሰፈረዉን ሕግ እንደጣሳችሁ ተቆጥሮ ከእስራት እስከ እድሜ ልክና ሞት ድረስ እናስፈርድባችኋለን» በማለት በሕዝብ ላይ ከማላገጥና ከመሸንገል እንዲሁም ከማስፈራራት ወደ ኋላ የማይመለሱ፣ ሕሊናቸውን የሸጡ፣ አእምሮ ሕፃንና አእምሮ ቀላል የሆኑ ናቸዉ፡፡

አሁን ደግሞ «ለሥልጣናችንና ለህልዉናችን እድሜ ማራዘሚያ የሚሆነዉን የመጨረሻ ኪኒን የሆነዉን መፈክር ማለትም ፡- መከፋፈላችን ወይንም መለያየታችን ወይንም ብዙኃነታችን(ብዙም) ሆነን፤ እንዲሁም ነፍጠኞችን ወይንም ዐምሓሮችን ወይንም ክርስቲያኖች ለታወቀዉ ዓላማችን ለማሰለፍ ድግሞ ማስመሰያ ቃላችን የሆነዉን(አንድም) ሆነን፤ በታላቁ መሪያችንና አባታችን እንዲሁም ጌታችንና አምላካችን (በመለስ ራእይ) እየተመራንና በታላቁ አዋጃችን የብሔር ብሔረሰብ መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል የያዘዉና ብሔር ብሔረሰቦችን ከፈለጉ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ካልፍለጉ በብሔራቸዉ ዜግነት እንዲኖሩ በሚያደርገዉና የብሔር ብሔረሰቦች መጨቆኛ አገር የሆነችም ለዘመናት ልንበቀላት ፈለገን ከግንቦት፳÷፲፱፻፹፫ (20/9/1983) ዓ.ም ተሳክቶልን እየፈነጨንባት ያላችዉ ደመኛ ጠላታችን ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሕጋዊ ዋስትና በሰጠናችሁ (በሕግመንግስታችን) ዋስትና፤ ሕዳሴያችንን እናሳካለን በማለት ነጋ ጠባ መልፍለፍ አለባችሁ» በማለት ትእዛዝ የሚሰጡ ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚያራምዱ የጨለማ ገዥ መልእክተኞች ናችዉ፡፡

ስፈልጉ ደግሞ «እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች የመጨረሻ አቋማችንን በሚገባ እናሳዉቃችኋለን፡፡ ይኸዉም እናንተ የምትኖሩት እኛ እስካለን ብቻ ስለሆነ በምንም ሁኔታ ወደ አንድነት የመምጣት ሐሳብ እንዳይኖራችሁ፡፡ እናንተ ወደ አንድነት መጣችሁ ማለት እኛ ሕወሓት ብአዴን ኢሕዴጎች የሥልጣንና የህልዉናችን ዘመን ተደመደመ ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህን ዓይነት ሐሳብ ብታመጡና ብታራምዱ እኛ የምንመራበት መንፈስ የተባበሩት መንግሥታት መንፈስ የሆነና አቋማችንም እንደ ታላቋ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ቻይናና፣ ሩሳያ ነዉ፡፡ ይኸዉም ለሥልጣናችንና ለጥቅማችን የማታስፈልጉን ከሆነ እንደ ሶሪያ ሕዝቦች እርስ በእርስ ብትባሉና ብትገዳደሉ አንዳች ስሜት አይኖረንም፡፡ አገሪቷም ብትንትኗ ቢወጣ ግድ አይለንም፡፡ ነገር ግን እንደ ብሔር ብሔረሰብነታችን እንኖራለን ካላችሁና በዐምሓሮች(በክርስቲያኖች) ላይ ያላችሁን ጥላቻና በቀል ካጸናችሁ፤

ለሥልጣናችንና ለህልዉናችን አዳጋ የሚሆኑትን ኃይሎች በተባበረ ኃይል ልክ እንደ ቀድሞዉ ለቢያ መሪ መሀመድ ጋዳፊ የገቡበት ገብተን እንደመስሳቸዋለን ፣ እናጠፋቸዋለን» በማለት ለሕዝቡ አንዳች ስሜት የሌላቸዉ ቀን ከሌሊት ስለ ሥልጣናቸዉና ጥቅማቸዉ ብቻ የሚያስቡና የሚሯሯጡ መሆናቸዉን የሚገልጹ ናቸዉ። ለዚህም ነዉ የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስርት አቶ መለስ ዜናዊ «እኛ ከሌለን ይህች አገር ብትንትኗ ትወጣለች» በማለት ራሳቸዉን ፈጣሪና አደራጊ አድርገዉ በመታበይ ሲናገሩ የተመለከትነዉና የሰማነዉ።

ሲፈልጉም «በፊት ፐሬዝዳንት(ንጉሥ) አሊ አብዶን የአዲስ አበባ መሪ አድርገን በነፍስ ወከፍ የመስጂድ ቦታ እንዲያድላችሁ ያደረግነዉና በአስፋልት ዳር ያለዉን ቦታ መርጦ እንዲሰጣችሁ ያስደረግነዉ እኮ በጋራ ሆነን ክርስቲያኖችን(ዐምሓሮችን) ለማዳከምና የተለያየ ተጽህኖ በመፍጠር ለማክሰም ነበር። እናንተ ግን ይህ ዉለታችንን ዘንግቷችሁ :- መጅሊሶቻችን ካድሬዎች ናቸዉ ብላችሁ ተቃዉሞ አመጣችሁ። እኛ እኮ ገና ብዙ እቅድ ነበረን። ይኸዉም ከእናንተ መካከል የኢትዮጵያ ርእሰ ብሔር(ርእሰ ፕሬዝዳንት)(ንጉሠ ነገሥት) ለማድረግ። ነገር ግን እናንተ በራሳችሁ ጊዜ እየተቃወማችሁ ስላስቸገራችሁን ለጊዜዉ ከሌላኛዉ ምርጫችን እናንተን ለማስቀናት እነዚያ ክርስቲያኖች(ዐምሓሮች) እርር ድብን እንዲሉ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ከፕሮቴስታንት እምነት መርጠኝ እንዲሾም አድርገናል። ስለዚህ በቀጣይ የእንናተን ሰዉ ንጉሠ ነገሥት አድርግን እንድንሾም ዝም ብላችሁ እንደምንላችሁ ሁኑ፤ አድርጉ የምትባሉትን ማድረግ ነዉ እንጂ :-የራስ ነጻነት፣ ራስን የሚወክል የሃይማኖት አባት፣ ... ወዘተ የሚባለዉ አባባል ከንግግር ዉጭ ተግባራዊ እንዲሆን ስለማንፈልግ፤ ይህን የሁከትና የሽብር አቋማችሁንና አስተሳሰባችሁን ብታቆሙ ይበጃችኋል። እኛ እንኳን ለእናንተ በሥልጣናችን ላይ ችግር የሚፈጥር የጥንት አባላችን እንኳ ቢሆን ድባቅ እንመታዋለን፣ እንደመስሰዋለን እንጂ ለማንም ወደ ኋላ የማንል የጅግኖች ጀግና መሆናችንን እንድታዉቁ እንፈልጋለን » የሚሉ የዓመፃ ልጆች ናቸዉ።

ባጠቃላይ የነዚህ የሕወሓት ብአዴን መንግሥት መሰሪነት በማወቅ የሚደረግ ጥፋትና በቀል ስለሆነ በምድርም በሰማይም ፍርዱ ይብስባቸዋል። ምክንያቱም በሕገ መንግሥቱ ሆነ በአዋጅ «እኔን የሚቃወም ሆነ በንግግር ወይንም በጽሑፍ የሚተች ሰዉ ካለ በወንጀል ይጠየቃል» ቢሉ ኖሮ ሰዉ ሁሉ እንዳለፈዉ ሥርዓት ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይጠባበቅ ነበር። አሁን ግን ትዉልዱ «ነጻነት ተሰቶሃል፣ መናገርና መጻፍ እንዲሁም መቃወም ትችላለህ» ሲባል፤ እዉነት እየመሰለዉ እዉነተኛ ተቃዉሞ ሲያቀርብና ስዉር ገበናቸዉንና እዉነትን ሲያወጣ በተለያየ መንገድ በቀልና ግፍ ይፈጸምበታል። መንግሥት አንድፊቱኑን ነጻነትን ቢገድብ ምንም እንኳን ከእዉነተኛዉ ፈጣሪ ፍርድ ባያመልጥም ፍርዱ ግን ይቀልለት ነበር። ነገር ግን ራሱን አድራጊ ፈጣሪ አድርጎ በመቁጠር ሕገ መንግሥቱን ሆነ የተለያዩ አዋጆችን እንደፈለገዉ በመተርጎምና በመጠቀም እንዲሁም በመሻር «ሕሊናዬን አልሸጥም፣ ለአምላኬ ነዉ የምታመነዉ» የሚለዉን ትዉልድ በተለያየ መንገድ በቀልና ግፍ እየፈጸመበት ይገኛል። ታዲያ የበቀሉና የግፉ ጽዋዉ ሞልቶ እየፈሰሰ ስለሆነ እጅግ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የከፋዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል። በምድርም በሰማይም እንደ ዓመፃቸዉና

ግፋቸዉ ደረጃ ዋጋ ይከፍሉበታል፡፡» **በማለት የምስኪኖችና የእዉነተኞች አምላክ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል፡፡**

## ምዕራፍ ሰባት

« ***ጠያቂዉ አገልጋይ***: በአሁን ሰዓት በተለያየ ሕዋ ሰሌዳ(ድረ ገጽ) ላይ በተለያየ ብሎግ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ስም ስለ ሃይማኖትና ስለቤተክርስቲያን የተለያየ መልእክት ይተላለፋል:: አንዳንዶቹ ደግሞ የቤተክርስቲያናችንን አባቶች በሥዕል እያሳዩና እንዲሁም የተለያዩ የቅዱሳን ሥዕል እያቀረቡ መልእክታቸዉ ግን ፍጹም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቤተ ክርስቲያንን የማይወክል፣ የዋህ ምእመናንን ጥርጥር ዉስጥ የሚጥል መልእክት ነዉ የሚተላለፍበት:: ለእነዚህ ጉዳዮች ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?

***መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ*** : በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት «ሰይጣን ሰይጣን ነኝ፣ ግብሬ መጥፎ ነዉ፤» ብሎ ማንንም እንደማይፈትንና እንደማያሳስት ይታወቃል:: የብርሃን መልአክ መስሎ፣ ወርቃማ ቃላት እየተጠቀመ ነዉ ትዉልዱን በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወደሞትና ወደ መቀመቅ እየወሰደ ያለዉና የሚወስደዉ:: እኔም የአንዳንዶቹን መልእክታት በተወሰነ ደረጃ ያነበብኩ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ከሃዲያንና መናፍቃን ባላጥላሉትና ባልደፈሩበት መልክ ነዉ ሃይማኖታችንና ቤተክርስቲያናችንን እያጥላሉ ያሉት:: እኔም ይህን ድርጊታቸዉን ተመልክቼ ምናልባት ባለማወቅና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀንተዉ ይሆን እንዴ? በማለት ቀደም ሲል በተናጠል በአድራሻቸዉ የእግዚአብሔር መልእክትና በእኔ ለሚመለከተዉ አካል የተጻፉ ደብዳቤዎች የላኩላቸዉ ሲሆን፤ ሰኔ፲፭÷፳፻፬ (15/10/2004) ዓ.ም ደግሞ ወደ 25 ለሚጠጉ ብሎጎች ለመፈራረጃ ጭምር በአንድ ላይ በእ-ጦማር(በኢሜል) አድራሻቸዉ የምክርና የማስጠንቀቂያ መልእክት ጽፌላቸዉ ነበር:: ምንም እንኳን አንዳንዶቹ እዉነተኛ ሙሉ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ሲሆን፤ አንዳንዶቹም ደግሞ አገልግሎታችዉ ምሉዕ ባይሆንም በሃይማኖታቸዉና በቤተክርስቲያናቸዉ ላይ የማጥላላት ተግባር አልፈጸሙም፤ ይልቁኑ ዘብ በመቆም ስለ እዉነተኛነቷና የሚፈጸምባትን ደባ እያጋለጡ ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ «ተመሳስለህ ኑር» የሚለዉ የአሕዛብ መመሪያ ተጽህኖ አሳድሮባቸዉ በልባምነት የሚያገለግሉ አሉ::

እነ «አባ ሰላማና ዐዉደ ምሕረት» የመሳሰሉት ብሎጎች ደግሞ መልእክቱም ደርሷቸዉ፣ ወደፊት ምን እንደሚሆን ሁሉ ተገልጾላቸዉ፣ በእግዚአብሔር መልእክት ላይ እንደተገለጸዉ የእግዚአብሔርን ቁጣ እያዩ አሁንም ሃይማኖታችንና ቤተክርስቲያናችንን እያጥላሉ ይገኛሉ:: የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት ትዉልዱ እንዲጠራጠርና እንደ ፕሮቴስታንቱ ከእርሱ በላይ ሌላ አምላክ ሾመዉበት ወደ አማላጅነት እየለወጡት፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ተመልታ በሉቃስ ወንጌል በምእራፍ 1 ቁር 48 ላይ «እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትዉልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» ያለችዉንና ከእግዚአብሔር የሆኑትም እያመሰገኗት ያሉ፤ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን የበቃችሁን የአደራ እናታችንን፣ የመዳኛ ምክንያታችንን፣ ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች የሆነችዉን፣ በሰማያት ክብራና ተመስግና መኖር ስትችል እርሷ ግን ለአዳራ ልጆቿ ስትል ኀዘንን የመረጠች፣ በምልጃዋ የእግዚአብሔርን ቁጣ የምታበርድልን፣ ጻድቃንና ቅዱሳን አመስግነዉ አመስግነዉ ያረኩ፣ ምሳሌ መስለዉ መስለዉ የሚያረካቸዉ ምስሌ ያጡ፣ ንጽህይተ ንጹሁን ቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ

ድንግል ማርያምን እያቃለሉና «ምንም አታዉቅም» እያሉ፤ እየሰደቡ፣ እንዲሁም ቅዱሳንና ለእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያና ለቅድስት ቤተክርስቲያን ታላቅ ስራ የሰሩትን የቀደሙ አባቶችን እያቃለሉና እያዋረዱ መልእክት ያስተላልፋሉ።

ይህም የፈርኦንና የይሁዳ እንዲሁም የአርዮስ ወንድምና እህት መሆናቸዉን አስመስክረዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መልእክታት በተለያዩ አገልጋዮች የተጻፉትን ተልኮላቸዉ፣ እንዲሁም የምክርና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ደርሷቸዉ፣ ንቀዉ በመተዉና ሕሊናቸዉም በማደንደን፤ በሃይማኖታችንና በቤተክርስቲያናን ስም በመነገድ፣ ምእመኑንና አገልጋዩን እያሳሳቱና እያጠራጠሩ በመሆኑና፤ ቤተክርስቲያንን ወደ ፕሮቴስታንት አዳራሽ ለመለወጥና እንደነሱ የዘፈንና የዳንኪራ መዝሙር እያቀረቡ ነፍሳትን ለዲያብሎስ ሊገብሩ ቆርጠዉ የተነሱ በመሆናቸዉ በምድርም በሰማያም ዋጋ የሚያስከፍላቸዉን የዓመፃ ተግባር እየሰሩ መሆኑን ነዉ ድርጊታቸዉ የሚመሰክርባቸዉ።

እንደ ፕሮቴስታንቱ የራሳቸዉ ድርጅት መስርተዉ ክህደትና ዓመፃ ቢፈጽሙ ፍርዱ ይቀልላቸዉ ነበር። ምክንያቱም የሚፈልግ ወደነሱ ሊሄድ ይችላል። የማይፈልግ ደግሞ በተዋሕዶ ሃይማኖቱ ጸንቶ ይገኛል። እነሱ ግን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችን ወደ ክህደትና ጥርጥር እያስገቡትና የመናፍቃን ዋና መሳሪያ በመሆን ላይ እያገለገሉ ይገኛሉ። እነዚህ በተሃድሶ መናፍቃን ስም ሃይማኖታችንና ቤተክርስቲያናችንን ለማጥፋትና ለማበላሸት የመናፍቃን ቅጥረኞች ሆነዉ በማገልገል ላይ ያሉ፤ የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊት ለቀጣይ ትዉልድ ለማስተላለፍ ገንዘባቸዉን፣ እዉቀታቸዉን፣ ጉልበታቸዉን፣ ጊዜያቸዉን ሰዉተዉ እያገለገሉ ያሉትንና በቤተክርስቲያን ዉስጥ እዉነተኛ አገልግሎት እንዲፈጸም በቤተክህነትም መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተዉ የሚሰሩትን አገልጋዮችን ጭምር «ለምን ከፓለቲከኞች ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ አይሰሩም፣ እንዲሁም ለምን ተሃድሶ መናፍቃንን ይቃወማሉ፣ ይለያሉ ... ወዘተ» በማለት ስማቸዉን እያጠፉና የዲያብሎስ አገልጋይ በሆነዉ መንግሥት ጥቃት እንዲፈጸምባቸዉ የተለያየ የማጥላላትና የማነሳሳት እንዲሁም የመከፋፈል ተግባር እየፈጸሙ ይገኛሉ።

እነዚህ አስመሳይ አገልጋዮችና በተዋሕዶ ስም የመነግዱ ረኃብተኛ ተኩላዎች፤ በእነርሱ ቅስቀሳ ምክንያት ለሚመጣ ጥቃት ሆነ ጥፋት እንደሚጠየቁ ማስጠንቀቂ ቢደርሳቸዉም ንቀዉታል። ከእግዚአብሔር ቁጣ ድነዉ ለመልካሙ ዘመን ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ቢድርሱ እንኳ የትም አገር ይኑሩ የት፣ ከፈለጉ አሜሪካ ወይንም አዉሮፓ ወይንም ኤሽያ ወይን መካከለኛዉ ምስራቅ ወይንም ሌሎች አፍሪካ አገር ዉስጥ ይደበቁ እንደ ናዚ አባላቶች ካሉበት ተይዘዉ በኢትዮጵያ በሚዘጋጀዉ የብርሃን ችሎት ለፍርድ ይቀርባሉ። እንደ ዓመፃና ግፍ አስፈጻሚነታቸዉ ይጠየቁበታል። ፍትሐዊ ፍርድ ይቀበላሉ። ለዚያ እድል የማይበቁት ደግሞ እጅግ በቅርቡ በዓለም ላይ በሚመጣዉ በእግዚአብሔር ቁጣ መጠረጋቸዉ አይቀርም። ምናልባት ትንሽ መልካም ስራ ተግኝቶባቸዉ ከእግዚአብሔር ቁጣ ተርፈዉ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚደርሱ ቢኖሩ እንኳ ያለዋጋ የኢትዮጵያን ትንሣኤ አያዩም። ስለዚህ የሚበጃቸዉ አሁንም በጽሑፍ ሆነ በንግግር እንዲሁም በመጻሕፍትና በተለያዩ ድረ ገጽ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም እየፈጸሙ ያሉትን የዓመፃ ተግባር

በግልጽ በማመን በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ ቀደም ሲል ያስተላለፉት የዓመፃና የክደህት መልእክት ስህተት መሆኑን በድረ ገጻቸዉ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚያም ለአንዲት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን መቆማቸዉን መግለጽ አለባቸዉ፡፡ «አይሆንልንም» ካሉ ደግሞ በተዋሕዶና በቤተክርስቲያን ስም መነገዱን አቁመዉ እንደ ማንኛዉም ፕሮቴስታን «እምነት» በራሳቸዉን ስም የዓመፃና የክህደት እምነታቸዉን መግለጽ ይችላሉ፡፡ ከዚያ ዉጭ አሁን በያዙት የዓመፃ አገልግሎት ከቀጠሉ ግን ከላይ የተገለጸዉ ተግባራዊ ይሆንባቸዋል ማለት ነዉ፡፡

የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ደግሞ በእግዚአብሔር ቁጣ በሥጋ ሞት የተጠሩት እጨጌ አባ ጳዉሎስ እንደነዚህ ዓይነቶቹን አቅፈዉና ድጋፍ እየሰጡ እንዲሁም በተለያየ ወንበር ላይና አገልግሎት ላይ በማስቀመጥና በማሰለፍ የቤተ ክርስቲያኗን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊትና አስተምሮ በማስለወጥ ተግባር ላይ ተሰላፊ ነበሩ፡፡ የእርሳቸዉ ምልምሎችና ስራ አስፈጻሚዎች ምግባር በሌለዉ ሕይወትና ትምህርት በተለያየ ኃላፊነት ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ምእመናንን የሚያስናክሉና ተስፋ የሚያስቆርጥ እንዲሁም የሚያሳዝን ተግባር የሚፈጽሙና፤ የሚያስፈጽሙ ናቸዉ፡፡ እንደበታቸዉ ግን ሽንገላ የበዛበት፣ በእግዚአብሔር ቃል የሚነግዱ፣ ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ፣ ለማያዉቃቸዉ ሰዉ መልአክ ጻድቅ የሚመስሉ፣ ነገር ግን በተለያየ ርኩሰት ተግባር የተሰለፉ ሌባ፣ ቀማኛ፣ ወንበዴ፣ ነፍሰ ገዳይ የሆኑ፤ በዝሙትና በአመንዝራ ሕይወት ዉስጥ የሚልከሰከሱ፤ እጅግ የባሰ ፍርድ የሚጠብቃቸዉ ናቸዉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ለሃይማኖትና ለቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ በመመሰል ስብከቱን መናፍቅ መናፍቅ ያሸተቱ፤ መዝሙሩን ዘፈንና ዳንኪራ ያስመሰሉ፤ ባጠቃላይ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሳይሆን እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚያገለግሉና የሚያስገለግሉ ናቸዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ መናፍቅ መናፍቅ የሸተተ ስብከትና፣ ዘፈንና ዳንኪራ የመሰለ መዝሙር ምን ዓይነት ነዉ? መገለጫዎቹና መለያዋቹ ምንድ ናቸዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ መናፍቅ ማለት በጥርጥርና በክህደት እምነት ዉስጥ ያለና ከእዉነተኛ እምነት የወጣ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ፍጹም እግዚአብሔር የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ» እያሉ የሚያምኑ ሰዎች ለምሳሌ የተለያዩ የፕሮቴስታንት ክፍልፋይ ድርጅቶችና መሰሎቻቸዉ የአምላክን አልፋና ያሜጋነት ተጠራጥረዋልና ይልቁኑ «መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያችን ነዉ» እያሉ እንደ ቃሉ ሆነዉ ባለመገኘት እርሱን ተማላጁንና ፈራጁን፣ ሁሉ የእርሱ በእርሱ የሆነዉን ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ ወደ ፈጣሪ የሚያቀርብ ነዉ...» ወዘተ እያሉ እለት እለት ያላግጡበታል፤ ይሰድቡታል፡፡ በዚህም ምክንያት «መናፍቅ» የሚለዉ ስያሜ ሊሰጣቸዉ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ኢየሱስ ክርስቶስን ባለማወቅ «ነብይ ነዉ፤ የፈጣሪ ተላላኪ አገልጋይ ነዉ» የሚሉ በእስልምና እምነት ዉስጥ ያሉ ሰዎች ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊድኑ ባይችሉም፤ ከመናፍቃን ይልቅ ፍርዱ ይቀልላቸዋል፡፡ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ስም አልነገዱምና፡፡ ነገር ግን በዓለም ላይ ክርስትና እየተሰበከ «ምንድ ነዉ ክርስትና» በማለት ሊጠይቁና በእዉነትና በመንፈስ መርምረዉ ፍጹም ወደ ሆነዉ እዉነትና እምነት ባለመምጣታቸዉ ምክንያት

በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል፤ እንደ ክህደታቸዉና ዓመፃቸዉ ደረጃም ዋጋ ይከፍሉበታል፡ መናፍቃን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በግልጽ እግዚአብሔርነቱን እያነበቡና እንዲሁም «አምላክ እንደሆነ እናምናለን» እያሉ ለአታላዩ መንፈስ ለዲያብሎስ ተገዥ በመሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ሽፋን የጨለማዉን ጌታ ዲያብሎስን፤ በየሱስ ስም እያመለኩትና እያስመለኩት በመሆኑ እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ የከፋዉ ፍርድ ነዉ የሚጠብቃቸዉ።

ታዲያ ያ በፕሮቴስታንትና በመሰሎቻቸዉ ስም ይንቀሳቀስ የነበረዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ አሁን ደግሞ ራሱን በመለወጥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን ተቆርቋር በመምሰል በእምነት ሽፋን ነዉ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዉስጥ የተገለጠዉ። የመጀመሪያ መገለጫ ልክ እንደ መናፍቃኑ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን በአማላጅነት ደረጃ መጥራትና የቤተክርስቲያኗን አጠራር የሆነዉን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወይንም መድኃኔ ዓለም ወይንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወይንም አማኑኤል ወይንም እግዚአብሔር ወልድ ወይንም እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ወይንም እግዚአብሔር ወይንም አምላካችን ወይንም ፈጣሪያችን ወይንም ጌታችን ባጠቃላይ እንደ እግዚአብሔርነቱ፣ እንደ አምላክነቱ፣ እንደ ሁሉን ፈጣሪነቱ የሚጠራበትን የተለያየ ስም በማቃለልና በማስካድ እንዲሁም «የማንቆርቆሪያ ማንጠልጠያ በዝቶበታል» በማለት እግዚአብሔርነቱን በመጠራጠርና አልፋና ዖሜጋነቱን በመካድ ልክ እንደ መናፍቃን «ኢየሱስ» እያሉ ከስም አጠራሩ ጀምሮ ማቃለልና የመናፍቃኑን አጠራር ምእመኑን ማለማመድ ነዉ። እንዲሁም ለሁለት ሺህ ዘመን ያህል እንደ ፈጣሪና አምላክነቱ ብቻ ስሙ ቀንና ሌሊት የሚጠራዉንና የሚመሰገነዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ እንደማይጠራና እንደሚጠላ በማስመሰል መስበክና መናፍቃን (ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ እያሉ እለት እለት የሚሰድቡትና የሚያላግጡበት) ግን ስሙን እንደሚጠሩ አድርጎ የመናፍቃንን እምነት እንደ ትክክልኛና ታላቅ አድርጎ ምስክርነትን መስጠት ነዉ። ከዚያም ምእመኑ ለሃይማኖትና ለቤተክርስቲን ያለዉን ፍቅርና መቆርቆር በሂደት መገዝገዝና «አንድ ኢየሱስን ነዉ የምንሰብከዉ» በማለት ከመናፍቃን ጋር ዉሕደትና አገልግሎትን መፍጠር ነዉ የመጨረሻ ግባቸዉና እቅዳቸዉ።

ይህንንም ለማሳካት ምእመኑ በቤተክርስቲያኒቱ እምነት፣ ሥርዓት፣ አስተምሮ፣ ትዉፊት እንዲጠራጠርና በሂደትም በማንነቱ ላይ ጥላቻ ያሳድሩበታል። በዚህም ምክንያት የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሚዋሓደዉ ወደ መናፍቅነት ለመለወጥ ሕሊናዉ አይከብደዉም። ወይንም ከጸሎትና ከጾም ራሱን ለይቶ እንደ አረማዉያን መደዴ ኑሮ ለመኖር አይቸገርም። ብዙ ሰዎች በቅድስት ቤተክርስቲያን ታይተዉና ከዚያም ባለፈ በአገለግሎት ላይ ተሰማርተዉ በስተመጨረሻ የጨለማዉ ጌታ የሱስ ወደሚመለክበትና ወደሚመሰገንበት የፕሮቴስታንትና መሰል ድርጅቶች ዉስጥ የገቡትና የዓመፃና የክህደት ምስክርነት ሲሰጡ የታየዉና የተደመጠዉ በዚህ የጥፋት ተልኮና አገልግሎት ምክንያት ነዉ። እንዲሁም አንዳንዶች በእነርሱ ስብከት ሕሊናቸዉ የተመረዘና የተበከለ በመሆኑ ከቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ዉጭ በሆነ በአሕዛብ ሕይወት ይመላለሳሉ።

አሁንም በቤተክርስቲያናችን ዉስጥ በዚህ በሸዋጁ መንፈስ እየተመሩ አገልግሎት የሚፈጽሙ ብዙ ሰዎች አሉ። እንደበታቸዉና ዉስጣቸዉ አንድ ያልሆነ፤ ለማስመሰል ያህል ብቻ «ቤተክርስቲያናችን፣ ሃይማኖታችን፣ እመቤታችን፣ ቅዱሳን» የሚሉ፤ ነገር ግን ዉስጣቸዉ የፕሮቴስታንቱን የጨለማዉ ገዥ የሰ-ስን ለማንገሥ የሚፈልጉና እዉነተኛዉን አምላክ ኢየሱስን ደግሞ ከምእመናን ልቦና መንግሎ ለማዉጣት ሌት ተቀን የሚተጉ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ። መዝሙሩንም አብዛኛዉ ምእመን «የቱ ነዉ ያሬዳዊ ዜማ የሆነዉ፣ ያልሆነዉ የትኛዉ ነዉ?» የሚለዉን ስለማይለዩ፤ እንደ ዓለማዊ ዘፈን ዓይነት መዝሙር መሳይ ዘፈን በየመድረኩ ያቀርባሉ። ግጥሙም በሥጋና ደም ስሜት የተደረሰ የቤተክርስቲያኒቱን አስተምሮ ያልጠበቀ ነዉ። አዘማመሩም እንደ ፕሮቴስታንቶች እንጣጥ እንጣጥ በማለትና ሕሊናን በመናፍቃን ጨለማ መንፈስ ዉስጥ እንዲመሰጥ እየተደረገ፤ ቢቻላቸዉ ደግሞ የምእመኑን እጅ ወደላይ በማስወጣት እንዲያወዛዉዙ በማድረግና በማስነባት ቢያዘምሩ ዉስጣቸዉ የሚፈልግ ነዉ። ባጠቃላይ በመንፈስ ቅዱስ ሲመረመር ከእዉነተኛዉ እምነትና ሥርዓት ያፈነገጠ፤ በትዕቢትና በዓመፃ ሕይወት አገልግሎት የሚፈጸምበት ነዉ። አሰገራሚዎቹ «ሰባኪና ዘማሪ ነን» የሚሉት ደግሞ የቤተክርስቲያን እዉቀት እያላቸዉ፤ ዲያቆን ፣ ቀሲስ ... ወዘተ ተብለዉ የዘፈንና የዳንኪራ መዝሙር መዘመራቸዉና መድረሳቸዉ ነዉ።

ሌላዉ አሳዛኙ ነገር ድግሞ፤ «የሃይማኖት አባት ነን» የሚሉ የተለያዩ አገልጋዮች የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት፣ አስተምሮ እንዲሁም ትዉፊትና ዜማ በሚገባ እያወቁ የዋህ ምእመን ከእነዚህ የዓመፃ ልጆች ጋር ሲሰለፉ ዝም ማለታቸዉና እዉነታዉን አለማሳወቃቸዉ ነዉ። ምክንያቱም ምእመኑ የዋህና እግዚአብሔር መፍራት ያለበት ስለሆነ በቤተክርስቲያን መድረክ ላይ የሚከናወነዉን ስብከት ሆነ መዝሙር እንዲሁም የተለያዩ አገልግሎቶች ፍጹም ትክክል የሆኑ አድርጎ ነዉ የሚቆጥረዉና «አድርግ» የሚባለዉን ለመፈጸም ቆርጦ የሚነሳዉ። እዉነተኛ ቆራጥ የሃይማኖት አባት ቢጠፋ እንኳ የየዋሁ ምእመን አምላክ እዉነተኛና ቆራጥ የሆኑ ለምእምን ነፍስ የሚገዳቸዉ ለሃይማኖታቸዉና ለቤተክርስቲያናቸዉ የሚቆረቆሩና በእዉነት፣ በቅንነት፣ በትጋት፣ በትህትና፣ በፍቅር የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ስለ ቅዱሱ ኪዳን ሲል በእዉነተኛ ወንበር ላይ ማስቀመጡ አይቀርም። ከእኛ ከምእመናንና ከአገልጋዮች የሚጠበቀዉ የተለያዩ ማዕበሎችና ድርጊቶች ሳያናዉጡን በቤተክርስቲያናችን እምነት፣ ሥርዓት፣ ትዉፊት፣ ዜማ ብቻ ጸንቶ መገኘት ነዉ። በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን የዘልማድ ሕይወትና አገልግሎት መፍትሄ ያገኛል። አገልግሎቱም በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ይሆናል። ለምእመናን ነፍስ የሚራሩና የሚያዝኑ፣ በትህትናና በፍቅር የሚገለግሉ፣ እዉነትኛ አገልጋዮች በእዉነተኛ ወንበር ላይ ከላይ እስከ ታች ስለሚቀመጡ እዉነተኛ አገልግሎት ብቻ በአራቱም ማእዘን ይሰጣል። እንክርዳድ የተደባለቀበት አገልግሎት ሆነ ትምህርት በንጹህ ስንዴ ብቻ ይተካል።

__ጠያቂዉ አገልጋይ__፡ በአሁን ሰዓት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ቤተክርስቲያን ስም «እኔ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ነኝ፤ እኔ ወደ ሰማይ ዐርጌ የነበርኩት ነቢዩ ኤልያስ ነኝ... ወዘተ» እያሉ የራሳቸዉን የሐሰት መስካሪና ተከታይ አዘጋጅተዉ ምእምኑን እያደናገሩትና

እያስናከሉት እንዲሁም ከሕይወት መንገድ እያወጡ ያሉ አስመሳይና ሐሳዉያን መስካሪዎች አሉ:: ስለዚህ ጉዳይ ምን የሚሉን አለ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ቀደም ብዬ በተለያ ቦታ ላይ እንደገለጽኩት ሰይጣናት እንደ ዘመኑ ተራቀዋል:: ፍጹም የሃይማኖት ሰዉ፣ የቤተክርስቲያን ሰዉ፣ እዉነተኛ አገልጋይ መስለዉ ነዉ ትዉልዱን ለማሳናከልና ለማሳሳት የሞት ሽረት ጦርነት እያደረጉ ያሉት:: ለምሳሌ በፕሮቴስታንት የተለያዩ ክፍልፋይ «እምነት» ዉስጥ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ «የሱስ» የሚል ስም ይዞ እየተመለከ መሆኑን ማነዉ ያወቀዉና ያስተዋለዉ!? የእምነቱ ተከታይ ሆኑ በሌላ እምነት ዉስጥ ያሉ ሰዎች አላወቁም፤ አላስተዋሉም:: ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ይዘዉ ስለሚሰብኩና የኢየሱስን ስም፣ የእግዚአብሔርን ስም ስለሚጠሩ ነዉ:: አሁን ደግሞ ዲያብሎስ ፍጹም ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ለቅድስት ቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ በመምሰልና የእግዚአብሔርንና የእመቤታችንን ስም እያስጠራ ነዉ ምእመኑን ለማሰናከልና ለማሳሳት ታጥቆ የተነሳዉ:: በተሃድሶ መናፍቃን ሽፋን እየተንቀሳቀሱ ያሉት አስመሳይ አገልጋዮች የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ አገልጋይ መሆናቸዉን ማነዉ ያወቀና ያስተዋለ? ከጥቂቶች በስተቀር ብዙዉ ሰዉ አላወቀም፤ አሳስተዋለም:: ምክንያቱም ለኢየሱስ የቆሙ አድርጎ ነዉ ትዉልዱ የተመለከታቸዉ እንጂ በኢየሱስ ስም የዲያብሎስን ፈቃድ እየፈጸሙ መሆኑን አላወቀም አላስተዋለም::

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስገባ በአሁን ሰዓት እጅግ ዘግናኝ ተግባር፣ ንግግር፣ ጽሑፍ በያቅጣቸዉ እየታየ፣ እየተሰማ፣ እየተነበበ ነዉ:: ምክንያቱም ዲያብሎስ ሆነ ሰይጣናት በቅርቡ የሚመጣዉን መልካም ዘመን የኢትዮጵያን ትንሣኤ በደንብ ያዉቃሉ:: በዚያን ጊዜ ባለጊዜ እንደማይሆኑና እዉነት ብቻ በአራቱም ማእዘን እንደምትነግሥ ያዉቃሉ:: እግዚአብሔር ለባለሟሎቹና ለእንደራሴዎቹ የገለጸዉን፣ የተናገረዉን በደንብ ያዉቃሉ:: ያ ብቻ አይደለም የተቀቡትንና የተመረጡትን ጭምር በደንብ ያዉቃሉ:: ነገር ግን ይህን እዉቀታቸዉን ለማንም የመግለጽ ሆነ የማሳወቅ ሥልጣን ሆነ ፈቃድ የላቸዉም:: ፈቃዳቸዉ ሆነ ኃይላቸዉ በእግዚአብሔር ተገድቧል:: ያላቸዉ ብቸኛ አማራጭ ለዓለም ብርሃንነት ከተመረጠችዉ ሃይማኖትና አገር ማለትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ከኢትዮጵያዊ ዜጋ ለራሳቸዉ የሚመች፤ እንደልባቸዉ ሊሆንላቸዉና አንደበቱን አንደበት፣ እዉቀቱን እዉቀት፣ ሕይወቱን ሕይወት አድርገዉ ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ሰዉ በማዘጋጀት፤ እንዲሁም እነሱን አንዳች እንዳያዉቃቸዉና እንዳይስተዉላቸዉ ፍጹም የሃይማኖት ሰዉ እንዲመስል በማድረግ ነዉ ለዚህ ለጥፋት ለዓመፃ ሕይወትና ተግባር ያሰለፋቸዉ::

እግዚአብሔር አምላክ ይህ እንደሚከሰት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በደንብ ገልጾልናል:: እንዲሁም «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፈርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሁለት በምዕራፍ አራት ከገጽ52-54 ላይ ስለ ልዩ አገልጋዮቹና መልእክተኞቹ መገለጫና እንዲሁም ለዓለም ፍጻሜ የሚቀረዉን ምልክት ብግልጽ ተናግሯል:: ይኸዉም:

«እናንተ ሰዎች ከኔ ዘንድ የሚላኩ ልዩ መልእክተኞቼ የምትለዩበት መንገዶች የሚከተሉት ናቸዉ:

1. የራሱን ክብር የማይፈልግና እኔን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነዉ::

2. ራሱን ከኔ ጋር ማስተካከል ቀርቶ ራሱን በፊቴ የሚያዋርድና ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ፤ ምክንያቱም የእኔን ከሕሊና በላይ የሆነዉን ባሕርዬንና የራሱን ተራነት በሚገባ ያስተዉላልና ነዉ::

3. ስለ እዉነት የሚመሰክር፣ በእዉነት የሚኖር፣ ስለ እዉነት ራሱን የካደ፣ ስለ እዉነት ማንኛዉም ዓይነት መከራና ችግር ቢመጣበት ሁሉን በጽናት የሚታገስ፣እስከ መሰዋዕትነት የሚደርስ ነዉ::

4. « እንዲህ ይሆናል» ብሎ ከተናገረ ያለዉ የሚሆንለት የሚፈጸምለት ነዉ::

5. በኔ ዘንድ ምሕረትን ሆነ መዓትን ቢጠይቅ እንደ ነቢዩ ኤልያስ የሚከናወንለት ነዉ::

6. በሰማያዉያን ሰራዊት ስለሚጠበቅ ማንም ፍጡር በራሱ ሥልጣንና ኃይል ሊጎዳዉ ሆነ ሊያጠቃዉ የማይችል ነዉ::

7. እኔን እንደ እግዚአብሔርነቴ ብቻ የሚያመልከኝ «አማለጅ ነዉ፣ ነብይ ነዉ ፣ፍጡር ነዉ» የማይለኝ በእግዚአብሔርነቴ ምንም ጥርጣሬ በዉስጡ የሌለ ነዉ::

8. በእኔ ስም፣ በሥላሴ ስም ፣በእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ስም፣ በቅዱሳን መላእክት ስም፣ በጻድቃን በሰማዕታት በነቢያት በሐዋርያት ስም፣ እንደ ተሰጠዉ ጸጋ የመፈወስና ተአምራትን የማድረግ ሥልጣን ያለዉ ነዉ::

9. የእናቴ የአደራ እናታችሁ የእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ያለዉ ነዉ::

10. ለምርጥ ባለሟሎቼና ወዳጆቼ ለቅዱሳን መላእክትና ለቅዱሳን ሰዎች ልዩ አክብሮት ያለዉ ነዉ::

ዕለተ ምጽአቴን በተመለከተ ማንም ሰዉ እንዳያሳስታችሁ፤ ቀኒቷና ሰዓቷ በእኔ ዘንድ ብቻ የምትታወቀዉ ያችም ዕለት የእናንተ የሰዉ ዘሮች በገነት፣ በሲኦል፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሰማያትና በዚህች ምድር ዉስጥ ያላችሁት ነፍሳት ቁጥር በዚህች ምድር ዉስጥ (በዓለም ዉስጥ) ካሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር ጋር እኩል ሲሆን ነዉ:: ያን ጊዜ በዚህች ምድር ዉስጥ የሚታዩትም የማይታዩትም ምሳሌያዊ ፍጥረታት ሁሉ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፤ በዚያን ዘመን የሚኖሩ ከሕፃን እስከ አዋቂ በማኅጸን ዉስጥ ካሉት ጭምር ከዚህ ክብር ከጎደለዉ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ ከተላበሰዉ ቅርፊት ሥጋቸዉ በመቅሰፍት ሞትና በምሕረት ሞት ተለይተዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ በመልበስ ከዚህ

ዓለም ዉጭ ወዳለችዉ ማረፊያ ቦታ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ በዚህች ምድር ዉስጥ (በዓለም ዉስጥ) ያሉት ርኩሳን መናፍስትም ማረፊያ ቦታ ላይ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ በዚህች ዓለም ዉሰጥ በገነት ዉስጥ ያሉት ጻድቃን የመጨረሻዉን የእኔን ፍርድ ለመታዘብ በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ ከዚህ ዓለም ዉጭ ባለችዉ ሲኦል ዉሰጥ የሚገኙ ኃጢአን ሰዎች የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ለመቀበል በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ በሰማያት የሚገኙ እጅግ ብዙ በጣም እጅግ ብዙ ከሰዉ አእምሮ ቁጥር በላይ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት እኔን አምላካዉን ፈጣሪያቸዉን አጅበዉ ፍርዴን ለማየት በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ በዚያን ጊዜ ዓለምም ሲኦልም ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፤ አምስተኛዉ ቦታ ምሳሌያዊ ባሕርይ የሆነዉ ገሃነመ እሳት ካለመኖር ወደ መኖር ይመጣል፤ በማረፊያ ቦታ የሚገኙት ርኩሳን መናፍስትና ኃጢአተኛ ሰዎች (ኃጢአተኛ ነፍሳት) የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ተቀብለዉ ወደ ገሃነመ እሳት፣ እሳቱ ወደ ማይጠፋ ትሉ ወደ ማያንቀላፋ የመቀጫ ቦታ ይገባሉ:: የተፈረደላቸዉ ጻድቃን ደግሞ እንደ ቅዱሳን መላእክት ሆነዉ ወደ ሰማያት ዉስጥ ይገባሉ:: <u>ስለዚህ ክርስቶስ፣ ኢየሱስ፣ አምላክ ፣ እግዚአብሔር በዚህ መንደር፣ በዚህ ከተማ፣ በዚህ ሀገር ተገለጠ፣ ይታያል ቢሏችሁ ማንንም እንዳትቀበሉ፤ እንዳታምኑ፤ እነደዚያ የሚላችሁ እርሱ ሐሰተኛ የሆነ ከዲያብሎስ ነዉ::እኔ ለሁሉም ሕያዉ ፍጥረት የምታየዉ በመጨረሻዉ ፍርድ ቀን በዕለተ መጽአት በማረፊያ ቦታ ላይ ብቻ ነዉ::</u>

<u>ከእንግዲህ ለዓለም ፍጻሜ የሚቀሯችሁ ሦስት ዋንኛ ትንቢቶች የሚከተሉት ናቸዉ:</u>

1.ዓለም ብትመከር፣ ብትገሰጽ፣ እጇን እንድትሰጥ ብትጠየቅ፣አሻፈረኝ ዲያብሎስ ይበልጥብኛል ብላለች:: እናንተ የአዳምና የሔዋን ዘሮች ወደ እኔ በንስሐ አልመለስም ብላችኋል፤ ከእኔ የሆነዉን እዉነት አልቀበልም ብላችኋል፤ <u>እያንዳንዱ አገር የዘራዉን ያጭዳል፤ የዓመጻዉን ፍዳ ይቀበላል::</u> ይህም የመጨረሻ ፍርዴ ሩቅ አይምሰላችሁ፤ በደጃችሁ ቆሟል:: እኔን ከመፍራትና ከማወቅ ስለራቃችሁ ማስተዋሉን አላገኛችሁም እንጂ ደጃችሁን አልፌ ከቤታችሁ ነኝ::

2. የዓመጻ ስራና የዓመጻ ልጆችን ከዚህች ምድር ካጸዳዉ በኋላ በኔ የተመረጠዉ የእናቴ የአደራ እናታችዉ የእመቤታችሁ ምርጥ ባለሟል ለሆነዉ <u>ለኢትዮጵያዊዉ ሰዉ ይህችን የተቀደሰች አገርና ዓለምን በእጁ አሳልፌ እሰጠዋለሁ:: ፈቃዴን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል:: ፈቃዴ ሲፈጸም ይህችን አገርና ዓለምን በምሕረት እጎበኛለሁ፤ መልካም ዘመንን አመጣለሁ::</u>

3.በመልካሙ ዘመን መጨረሻ አንድ ቀን <u>አሁን የሚደረገዉን ማጥሪያና ማበጠሪያ ኃይሌን እንዲሁም መልካሙን ዘመን የሚዘነጋ ትዉልድ በዓለም ይወለዳል::</u> በዚያን ጊዜ ዋናዉ የዓመጻ ልጅ (ሐሰተኛዉ መሲህ) (ሐሰተኛዉ ክርስቶስ) (ሐሰተኛዉ አምላክ) ይነሳል፤ በኃይልና በድንቃድንቅ ተአምራት ለዓለም ይገለጣል:: <u>ለሦስት ዓመት ተኩል(ለአርባ ሁለት ወራት) ብቻ ባለ ጊዜ ሆኖ በእኔ የሚያምኑትን ይፈታተናል፣ ያጠቃል፣ ያሰናክላል::</u> ትዕቢት የተባሉት የፈርኦን ወንድምና እህቶች፣ ክፋት የተባሉት የይሁዳ ወንድምና እህቶች፣ ዓመጻ የተባሉት የአርዮስ ወንድምና እህቶች የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች በዋናነት ተከታዮቹና አጫፋሪዎቹ ይሆናሉ:: ቁጣዉን በመፍራት አእምሮ

ሕፃናትና አእምሮ ቀላሎች ይከተሉታል፡፡ አእምሮ አዋቂዎች ይሰናከሉበታል፡፡ ቁጣዉንና ድንቃድንቅ ተአምራቱን በመመልከት አእምሮ ጽኑአን ይፈተኑበታል፡፡

<u>በሦስት አመት ተኩል ዉስጥ በእምነቱ የጸና እርሱ ለሰማያዊ መንግስት የተመረጠ ሰዉ ነዉ፡፡ የዋናዉ የዓመጸና ዓመጻ ልጆች ባለ ጊዜነት ስሽር ዓለም እንዳልነበረች ትሆናለች፡፡ የዓመጻ ልጆች በመቅሰፍትና በስቃይ ሞት፣ የተመረጡ ሰዎች ደግሞ በምሕረት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ፡፡</u> በዚህች ምድር ዉስጥ ሆነ በዓለም ዉስጥ በዓይን የሚታዩት፣ የማይታዩት ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፡፡ <u>የዓለም ፍጻሜ በዚህ መልክ ይጠናቀቃል</u>፡፡» ይላል አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሔር፤ የቅዱስ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሩፋኤል፣ ዑራኤል፣ ፋኑኤል፣ ራጉኤል አምላክ፡፡ »ይላል

በመሆኑም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ተገልጻ ወደዚህ ምድር አትመጣም፡፡ ለወዳጆቿና ለባለሟሎቿ በሚገባቸዉ መልክ ልትገለጽና በረድኤት ልትቀርባቸዉ ትችላላች እንጂ እንደ ሰዉ በምድር ላይ አትመላለስም፤ አትኖርም፡፡ ጻድቁ ነቢዩ ኤልያስም ለወዳጆቹና ለባለሟሎቹ በሚገባቸዉ መልክ ሊገለጽላቸዉና በረድኤት ሊቀርባቸዉ ይችላል እንጂ እንደ ሰዉ በምድር ላይ አይመላለስም፤ አይኖርም፡፡ እግዚአብሔር፤ እንደ ኤልያስ ለአምላኩ የሚቀና ቆራጥ እዉነተኛ ታማኝ የሆነ አገልጋይ ወይንም መልእክተኛ ያስነሳል እንጂ ድርሻዉን በሚገባ ተወቶ የሄደዉን ቅዱሱን ነቢይ በዚህች ምድር እንዲወርድና እንዲወለድ፣ እንዲያገለግል አያደርግም፡፡ «በዓለም ፍጻሜ ዘመን ሐሳዊ መሲህ ሲነሳ ኤልያስ ይመጣል» የተባለዉም ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ለመንገድ ጠራጊነትና ለምስክርነት መጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እንደተወለደና ምስክርነትን እንደሰጠ ሁሉ፤ በዓለም ፍጻሜ ዘመን ለሦስት ዓመት ተኩል ባለ ጊዜ በሚሆነዉ በሐሳዊ መሲህ ዘመንም ቅዱስ ነቢዩ ኤልያስ ይመራበት በነበረበት መንፈስ የሚመራ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ለአምላኩ ቀናዒ የሆነ እዉነተኛ አገልጋይ እግዚአብሔር ያስነሳል እንጂ ነቢዩ አልያስ ዳግሞ ሰዉ ሆኖ በምድር እንደ ሰዉ ምስክርነትን አይሰጥም፡፡

ሌላዉ መታወቅ ያለበት የእግዚአብሔር ምርጥ ባለማሎች ምድራዉያን ሰዎች ሆኑ ሰማያዉያን ቅዱሳን መላእክት ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ነዉ ምስክርነትን የሚሰጡት እንጂ «እኔ ቅዱስ ነኝ፤ እኔ ታላቅ ነኝ... ወዘተ» እያሉ ራሳቸዉን አያመጻድቁም፤ አያስታብዩም፡፡ ለዚህ ምስክሩ በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ19 ከቁጥር 9 እስከ 10 ላይ የተጻፈዉ የእግዚአብሔር ቃል ይገልጽልናል፡፡ ይኸዉም፡

« እርሱም፡- ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸዉ ብለህ ጻፍ አለኝ፡፡ ደግሞም ፡- ይህ የእግዚአብሔር እዉነተኛ ቃል ነዉ አለኝ፡፡ <u>ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ፡፡ እርሱም ፡- እንዳታደርገዉ ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካለቸዉ ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ</u> የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነዉና አለኝ፡፡» ይላል

ታዲያ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት የጸጋ ስግደት የሚገባቸዉ እንኳ እንዲሰገድላቸዉ ሆነ የተለየ ክብር እንዲሰጣቸዉ ሳይፈልጉ ለእርሱ ለእግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሰገድለት ነዉ

ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ የሰጡትና እንዲሁም አምላካቸዉን ለማስመለክና ለማስገነን ለራሳቸዉ «ባሪያ» የሚል ስያሜ የሰጡት። እኛ ምድራዉያንማ እንዴት እንዲሰገድልን፣ የተለየ ክብር እንዲሰጠን፣ የተለየ ግነትና ምስጋና እንዲቀርብልን፣ ሰዉ እንዲያመልከንና የእኛ ተከታይ እንዲሆን እንፈልጋለን? እንግዲህ እንዲሰገድለት፣ እንዲገን፣ እንዲመለክ፣ ሰዎች እንዲከተሉት የሚፈልግና ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱን ሰዉ ማጋለጥና ሰዎች እንዳይከተሉት እንዲሁም በሕግ እንዲጠየቅ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በዚህ አጋጣሚ ለእዉነተኛ አገልጋዮች የማስተላልፈዉ መልእክት የዋሁ ምእምን በእነዚህ የበግ ለምድ ለብሰዉ በመጡት ተኲላዎች እንዳይበላና የሰዉ ተከታይና አምላኪ እንዳይሆን፤ በተዋሕዶ እምነቱና በቅድስት ቤተክርስቲያን ብቻ እንዲጸና፣ እንዲሁም ራሱን በንስሐ እየመረመረ በቅዱስ ቁርባን እንዲወሰን ማድረግ ይኖርባችኋል እንጂ፤ እናንተም «ተመሳልሎ ኑሮ፤ ከራስ በላይ ንፋስ» በማለት ምእመኑ በተኲላ ሲበላና ሲሰናከል እንዲሁም የሰዉ ተከታይና አምላኪ ሲሆን፣ ከሕይወት መንገድ ወቶ በዓመፃ ሕይወት ሲመላለስ ዝም የምትሉ ከሆነ፤ ስለ እያንዳንዱ ነፍስ ትጠየቁበታለችሁ። ምክንያቱም ነፍሳትን መጠበቅ ካልቻላችሁ፤ አስቀድሞዉኑ «አገልጋይ ነን» ማለት አለነበረባችሁም፣ እንዲሁም የተቀመጣችሁበትን ወንበርና የተለያየ የአገልግሎት ድርሻ ለእዉነተኛ አገልጋዮች መልቀቅ ነበረባችሁ።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ ስምንት

« **<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አራት ጸሐፊዉ ይጸልይ የነበረዉ ጸሎት በሚል የተገለጸዉ ዉስጥ እግዚአብሔርን «አባ(አባባ)»፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን «እማ» እያሉ ጠርተዋል፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ሆነ እመቤታችንን መዳፈር አይሆንም ወይ?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: እንኳን እግዚአብሔርንና ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች የሆነችዉን እመ አምላክን ቀርቶ፤ አንድ መጨረሻዉ ምን እንደሚሆን የማይታወቀዉን ምድራዊ ሹመኛ እንኳ በሚጠራበት የተለያየ ማዕረግ ስም ነዉ የምንጠራዉ እንጂ በስሙ አይደለም፡፡ ነገር ግን ንጉሥ ሆነ ጀነራል፣ ሳይንቲስት ሆነ ሊቀ ምሁር፤ ልጆቻቸዉ ሲጠሯዉ በአባትነት፣ በእናትነት ስማቸዉ «አባዬ፣ እማዬ» እያሉ ነዉ እንጂ ያ በዓለም የተሰጣቸዉን የሥልጣንና የማዕረግ ስም እየጠሩ አይደለም፡፡ እንኳን ልጆቻቸዉ የቅርብ ቤተሰባቸዉና ጋደኞቻቸዉ ሳይቀር ያንን ማዕረግ ከማግኘታቸዉ በፊት ባላቸዉ ስም ነዉ በግለሰብ ደረጃ የሚጠሯዉ፡፡ ነገር ግን ምን ያህል ቀረቤታ ቢኖራቸዉ በመድረክ ሆነ በአደባባይ በሚያቀርቡት ንግግር ሆነ ጽሑፍ ላይ በዓለም ያገኙትን ሥልጣንና ማዕረግ ገልጸዉ ነዉ የሚያቀርቡትና የሚጽፉት እንጂ እንደ ቀሎ ጋደኝነታቸዉና ልጅነታቸዉ አይደለም የሚጠሯቸዉና የሚገልጿቸዉ፡፡

እኔም በእግዚአብሔር መልእክታት ዉስጥ አንድም ቦታ «አባ፣ ወይንም እማ» ብዬ አልጻፍኩም፡፡ ልክ የአንድ ባለሥልጣን ሆነ የአንድ ምሁር የተሰጠዉን ሥልጣንና ማዕረግ በሙሉ እንደምንጠራ፤ እኔም እግዚአብሔርን በሥጋ ከተገለጸ በኋላ ባገኘዉ የተለያየ ስም «ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ፈጣሪያችን ክርስቶስ፣ አምላካችን ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔዓለም፣ አባታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» እያልኩ ነዉ በመልእክታቱ ዉስጥ ስሙን የገለጽኩት፡፡ እመቤታችን ድንግል ማርያምንም «እመ ብርሃን፣ ወላዲተ አምላክ፣ ቅድስተ ቅዱሳን ንጽህይተ ንጹሃን፣ ድንግል ማርያም፣ የመዳኛችን ምክንያት፣ አምባ መጠጊያችን፣... ወዘተ» እያልኩ ነዉ የገለጽኩትና የጻፍኩት እንጂ እንደ መናፍቃን እንኳ የእግዚአብሔርን ስም ልክ እንደ ቀሎ ጋደኛዬ «ኢየሱስ ብቻ» እያልኩ አልጠራሁም፡፡ እንዲሁም ስንት የክብር ስሟን አስቀርቼ «ማርያም ብቻ» አላልኩም፡፡

ነገር ግን በግል ጸሎቴ ማለትም እግዚአብሔርና እመቤታችን ብቻ በሚሰሙኝ፤ አዳምና ሔዋን በገነት ዉስጥ ባይበድሉና ወደ ምድር ባይገቡ ኖሮ በገነት ዉስጥ በእነሱ ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት ካለመኖር ወደመኖር ለሚመጡት ልጆቻቸዉ ሁሉ ወላጆች ስለሚሆኑ፤ ሁሉም ልጆቻቸዉ «አባ እና እማ(አባዬ እማዬ)» እያሉ ይጠሯቸዉ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ መገኘት ባለመቻላቸዉ ምክንያት ያ ጸጋቸዉና ኃላፊነታቸዉ ስለተገፈፈ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ዳግማዊ አዳም ሆኖ የሁላችንም አባት ስለሆነ፤ እንዲሁም የአዳምና ሔዋን የመጀመሪያ የገነት ሕይወት ቅድስና ብቃት ያገኘችዉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ በመሆኗ ዳግማዊት ሔዋን ሆና

ለሁላችንም እናት ስለሆነች፤ ለግሌ እንደ ልጅነቴ አባ እና እማ ብላቸዉ ደስ ይላቸዋል እንጂ እንደተዳፈርኳቸዉ አይቆጥሩብኝም:: ዋናዉ እንደ ልጅነቴ ሆኜ መገኘት ብቻ ነዉ የሚጠበቅብኝ:: እግዚአብሔር ራሱ «ወልድ» ተብሎ ዉሉድ አስብሎናልና፤ በሐዲስ ዘመን እግዚአብሔር የሚፈልገዉ ግንኙነት እንደ አባትና ልጅ እንዲሆን ነዉ እንጂ እንደብሉይ ዘመን እንደ ጌታና ባሪያ አይነት ግንኙነት እንዲኖረን አይደለም:: ራሱ ሰዉ ሆኖ፣ እንደኛ ተመላልሶ፣ ፍቅሩንም የተለያየ ጸዋትዎ መከራ በመቀበል ገልጾ፣ ራሱን ሰዉቶ፣ ቅዱስ ሥጋዉን ክቡር ደሙን ስለሰጠንና ወደ ራሱ ስላቀረበን፤ የጠበቀ ቀረቤታና ግንኙነት እንዲኖረንና እንደ ቃሉ ሆነን እንድንገኝ ነዉ እግዚአብሔር የሚፈልገዉ:: በመድረክ ሆነ በአደባባይ የሚቀርበዉ አጣራር ሆነ አገላለጽ የቤተክርስቲያኒቱን አስተምሮና ቋንቋ የተከተለ መሆን አለበት:: ምክንያቱም እንኳን በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ አይደለም በዓለማዊ እንኳ ወጥ የሆነ አሰራርና አሰያየም ነዉ ያለዉ እንጂ አንዱ እንደፈለገዉ አይሰራም፣ አይጠራም፤ ሌላዉም እንደመሰለዉ አይሰራም፣ አይጠራም:: ማንም ግን በግል ሕይወቱ አግባብ ባለዉ ሕግና ሥርዓት ዉስጥ እንደፈለገዉ መስራት ሆነ መጥራት ይችላል:: ለዚህም ነዉ በግል ጸሎቴ «እመቤትዬ» እያልኩ ማፍቀሬንና መዉደዴን ለግሌ ብቻ የምገልጸዉ:: በአደባባይ ግን አልልም፤ ምክንያቱም የአደባባይ ስሟ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት መሰረት እምቤታችን፣ እምቤቴ ማርያም፣ ወላዲተ አምላክ፣ እመ እምላክ ፣ ድንግል ማርያም፣ ቅድስት ድንግል ማርያም ... ወዘተ የሚለዉ ነዉ:: ሌላዉ ትዉልዱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ወይንም እግዚአብሔርነት እንዲጠራጠር እየተደረገ ስለሆነ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ መጥራት አግባብነት ይኖረዋል:: ምክንያቱም አንዳንድ አስመሳይ አገልጋዮች፣ «ዘመናዊ ጠንቋይ» የተባሉት፣ እንዲሁም የዘመናዊዉ ጠንቋይ ደቀመዛሙርትና ተከታዮች፤ «ኢየሱስን እግዚአብሔር አትበሉ» እያሉ፤ አማኙ በእግዚአብሔርነቱ እንዲጠራጠሩ እያደረጉ ነዉና::

በዚህ አጋጣሚ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ በሕሊናቸዉ የነገሠባቸዉ የተለያዩ የፕሮቴስታንት «እምነት» ድርጅቶች «አገልጋይ÷ ዘማሪ ነን» የሚሉ፤ በእዉነተኛዉ አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሲያላግጡበትና ሲያሾፉበት የሚታየዉንና የሚሰማዉን የዓመፃ ተግባራቸዉን እገልጽላችኋለሁ:: ይኸዉም በየአዳራሹ ሆነ በመሰባሰቢያቸዉ ቦታ ላይ እየተመለከ ያለዉ የጨለማዉ ጌታ ዲያብሎስን «የሱሴ ÷ጌትዬ» እያሉ በየአዳራሹና በየካሴቱ ሲያወዱሱትና ሰያገኑት በመታየቱና በመደመጡ ምክንያት ነዉ:: ከማንም በላይ ደግሞ በምድርም በሰማይም የእግዚአብሔር ፍርድና ቁጣ በእነሱ ላይ ይብሳል:: ምክንያቱም በኢየሱስ ስም ነዉ እየነገዱ ያለዉና፤ እንዲሁም በእዉነተኛ አምልኮ ዉስጥ የነበረዉን ምእመን እያሰናከሉትና ከእዉነተኛ በረት ዉስጥ እያወጡት ስለሆነ ነዉ::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በመጀመሪያዉ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በክፍል አንድ በምዕራፍ ስድስት በገጽ 28 ላይ «የእግዚአብሔር አብ ቸርነት፤ የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅርና ምሕረት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነትና ጸጋ ፤የእመቤታችን፣ የአደራ እናታችን፣ የቅድስተ ቅዱሳን፣ የአዛኙቱ፣ የእመ አምላክ፣ <u>የምስጋና ጸጋ የበዛላቸዉ የአባ ሕርያቆስ የአባ ኤፍሬም የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እመቤት፣</u> የነቢያት ትንቢት፣ የሐዋርያት ስብከት፣ የሰማዕታት አክሊል፣ የጻድቃን እመቤት፣ የኃጢአን ተስፋ፣

ኢትዮጵያ አስራት ሀገሯ የሆች፣ <u>ምሳሌ ተመስሎላት ተመስሎላት ተመስግና ተመስግና የማትጠገብ፣</u> የሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነች፣ ለሰዉ ዘሮች መዳን በምልጃና በኀዘን በአምላክ ፊት የቆመች፣ ክብሯ እጅግ የበዛ፣ እኛ ሰዎች ሳይገባን እማማ እናታችን እንድንላት የተፈቀደልን፣ በኀዘናችን በችግራችን በመገፋታችን ቶሎ የምትደርስልንና የምታጽናናን፣ ብቻ <u>ሁለመናችን የሆነች የሕይወታችን ምስጢር ቁልፍ፣ እዉነተኛ ወዳጆቿን ለታላቅ ክብርና ጸጋ የምታበቃ፣ እንኳን እርሷን የናቀና ያቃለለ ቀርቶ ያላፈቀራት፣ ያልተማጸናት፣ ያላመሰገናት የእግዚአብሔርን መንግሥት የማያይ፤</u> <u>በአምላኳና በልጇ በተሰጣት ሥልጣን ሁሉን ማድረግ የምትችል፤ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የሆነች፤</u> እኔን ዉዳቂዉን ኃጢአተኛ ሰዉ  ለዚህ ያበቃችኝ የድንግል ማርያም ፍቅርና ምልጃ፤ የቅዱሳን መላእክት ጥበቃና ምልጃ፤ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የነቢያት፣ የሐዋርያት በረከትና ምልጃ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ ይላል ሳይገባዉ ለዚህ መልዕክት አስተላላፊነት የተመረጠ ተራና ወራዳ  ኃጢአተኛ ሰዉ።» ተብሎ ተጽፏል።

እዚህ ላይ ያለኝ ጥያቄ እመቤታችን ድንግል ማርያም እንዴት እንዲህ ልትባል ቻለች? እንዴት እንዲህ እንድትገንና እንድትመሰገነት ተደረገ? እንዴት «እንኳን እርሷን የናቀና ያቃለለ ቀርቶቸ ያላመሰገነ፣ ያልተማጸነ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ ቀርቶ አያይም ተባለ? ቅዱስ ያሬድ ለቤተክርስቲያናችን በምስጋና በኩል ታላቅ አገልገሎትን ያደረገ አባት ነዉ። ታዲያ የምስጋና ጸጋ የበዛላቸዉ አባቶች ተብሎ ከተገለጹት ጋር ስሙ ለምን አልተጠቀሰም?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እዚህ ላይ በድጋሜ ለማሳወቅ የምፈልገዉ፤ ጽሑፉን የጻፍኩት እኔ ብሆንም ያጻፈኝ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነዉ። ይኸዉም ነፍሴ ብቻ በምትሰማዉ ድምፅ ብቻ ተመርቼ ነዉ እንጂ፤ በዚህ መልኩ የመጻፍ፣ የእዉቀት ሆነ የቃለት እዉቀት አልነበረኝም። በምጽፍበት ወቅት ወደ ሕሊናዬ የሚመጣዉን እንዳለ እጽፋለሁ እንጂ የራሴ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ እያደረኩ የምጨምረዉና የምቀንሰዉ ነገር አልነበረም። የምስጋና ጸጋ ከበዛላቸዉ ቅዱሳንና ጻድቃን አባቶች አንዱ ቅዱስ ያሬድ ነዉ። በቤተክርስቲያን ለምስጋና የምንጠቀምባቸዉ የጸሎት ሆነ የምስጋና እዉቀቶችን ለትዉልዱ ያዘጋጀ እንዲሁም ሰማያዊ ዜማን ለመንፈሳዊ አገልግሎት በእርሱ በኩል እግዚአብሔር የገለጸ ታላቅ ባለዉለተኛ ቅዱስ አባት ነዉ። ይህን ደግሞ እንኳ ኢትዮጵያዉያን ቀርቶ ዓለም ያዉቀዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንደ ቅዱስ ያሬድ የተለያዩ የምስጋናና የጸሎት ከዚያም በተጨማሪ የተለያዩ መንፈሳዊ እዉቀቶችን ለትዉልዱ ያዘጋጀዉ ታላቁ አባት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በኢትዮጵያዉያን ዘንድ ሆነ በዓለም ብዙ እዉቅና ስላልተሰጠዉና ስላልታወቀ እግዚአብሔር፤ ትዉልዱ እንደነ ቅዱስ ያሬድና እንደ ሌሎቹ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ሐዋርያት፣ ነቢያት እንዲታሰብና እንዲታወቅ ፈልጎ እንዳጻፈ ነዉ የማምነዉ። ይህን ከጻፍኩ በኋላ በግሌ በምጸልያቸዉ ጸሎቶች ዉስጥ የምስጋና ጸጋ የበዛላቸዉን ስማቸዉን ስጠራ የቅዱስ ያሬድንም ስም እያካተትኩ ነዉ የምጸልየዉ።

እግዚአብሔር በትዉልዱ እመቤታችን እንድትመሰገንና እንድትገን ያደረገዉ ዋናዉ ምክንያት ለሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት ሆና ስለተገኘችና ለአዳኙ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት

ለመሆን በቅታ በመገኘቷና ከእርሷ የተነሳዉ ሥጋና ደም መለኮት ተዋሕዶት ለዓለም መስዋዕት ሆኖ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሰዉ ልጆች እየበሉትና እየጠጡት ከእርሱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚሆኑበትና በኃጢአትም ሲወድቁ ከሰማያዊ መዝገብ (ከእግዚአብሔር ባሕርይ) ላይ ኃጢአታቸዉን የሚያስደመስስ ስለሆነ ነዉ:: ለዚህ ምርጫና ብቃት የደረሰችዉ አዳምና ሔዋን እዉነተኛ ንስሐ በገቡ ጊዜ እግዚአብሔር በዚያን ወቅት በምድር ዉስጥ ካላቱ ርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል እስከሚሆን ድረስ ቀደም ሲል በገነት ዉስጥ በአዳምና ሔዋን ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት ካለመኖር ወደ መኖር እንዲመጡ በሐሳቡ(በእቅዱ) ዉስጥ ያሉትን ለቅጽበት ያህል ካለመኖር ወደ መኖር ባመጣቸዉ ጊዜና በዚያች ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ በነጻ ሕሊናቸዉና ፈቃዳቸዉ ተጠቅመዉ ፈጣሪያቸዉን በእዉነትና በመንፈስ የአፈላለጋቸዉን እምነትና ብቃት በሚመለከትበት ወቅት፤ የእመቤታችን ነፍስ የብቃት ደረጃ መቶ ከመቶ ዉጤት አግኝታ በእግዚአብሔር በመወደዷና በመመረጧ ነዉ::

በሥጋም በምድር ላይ ስተገለጸ ያንኑ ብቋቷን በማሳየቷ  እርሱ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ የሆነዉ አልፋና ያሜጋ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰዉ ሆኖ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይና ከሁለት አካል በአንድ አካል ተገልጾ፣ የተለያዩ ተአምራትና ፈዉስ አድርጎ፣ ትዉልዱ ምን ማድረግ እንዳለበትና እንደሌለበት አስተምሮ፣ በመጨረሻ የተለያዩ መከራዎችን ተቀብሎ፣ ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፣ በሥጋዉ ሞቶ፣ እንደገና በመዋሐድ ትንሣኤን አሳይቶ፣ መኖሪያችንም ሰማያት መሆኑን ወደ ሰማይ በማረግ አሳይቶን የማዳን ስራዉን አጠናቋል:: ታዲያ በዚህ የማዳን ተግባሩ ብቸኛዋና የመጀመሪያዋ ተሳታፊ እመቤታችን ስለሆነች ነዉ እንድትመሰገንና እንድትገን ፈቃዱ የሆነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ በገነት ዉስጥ አዳምና ሔዋን ካለመኖር ወደ መኖር ነፍሳት በእነሱ ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት እንዲመጡና ለሁሉም ልጆች ኃላፊዎች፣ ተጠሪዎች እንዲሆኑ የሰጠዉን ሥልጣን፤ እነሱ በእግዚአብሔር ቃል ሆነዉ  ስላልተገኙ ያ ሥልጣን፤ እንደ እግዚአብሔር ቃልና ፍላጎት ሆና ለተገኘችዉ ለእመ አምላክ ድንግል ማርያም ነዉ የተሰጠዉና ለሰዉ ልጆች ሁሉ የአደራ እናት ለመሆን የቻለችዉ::

ለዚህም ነዉ የሰዉ ዘሮች ከሞት መንገድ ወደ ሕይወት እንዲመጡ ተስፋ ሳትቆርጥ ወደ ሰማያት ዉስጥ ከገባች ጀምሮ በተገለጸችበት ብርሃናዊ ባሕርይ ትዉልዱን ስትመራና ልጇንና አምላኳን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁል ጊዜ በምሕረት እንዲጎበኘን በምልጃዋ በፊቱ የምትቆምልንና የእግዚአብሔርን ቁጣ በማብረድ ከምድር ሙሉ በሙሉ ከመደምሰስ እየጠበቀችን ያለዉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅሩና ምሕረቱ ወሰንና ገደብ የሌለዉ የትየለሌ እንደሆነ ሁሉ ፍርዱና ዉሳኔዉ እንዲሁም እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ስለሆነ እርሱን መምሰል የተላበሰች ነፍስ እርሱ የማይወደዉንና የሚጠላዉን ተግባር ሆነ ንግግር እንዲሁም ሐሳብ ስትፈጽም እጅግ ስለሚያስቆጣዉ ትዉልዱን ያጠፋዉ ነበር:: ነገር ግን ይኸዉ ለዘመናት በዋናነት በእመቤታችን ድንግል ማርያም ከዚያም በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ነፍሳት አማላጅነት ታግሶን እስከ አሁን ሳንጠፋ ቆይተናል:: አሁን ግን ዓመፃችን፣ ክህደታችን፣ ርኩሰታችን እጅግ ስለ ከፋ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ባለሟሎችና ወዳጆች እንዲሁም ቅንነተ፣ እዉነተኛነት፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ፍቅር የሚታይባቸዉን

ሰዎች በምድር እንዲቀሩና ሌሎች እግዚአብሔርን በመካድና በንስሐ አልመለስም በማለት የጸኑ ዓመፀኞች ግን ከምድሪቱ እንዲጸዱ እግዚአብሔር ወስኗል፡፡

እመቤታችን ለሰዉ ዘሮች ያላትን ጥብቅናና በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን ሥልጣንና ጸጋ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ስለሚያዉቅ ነዉ ቀን ከሌሊት ትዉልዱን ከእርሷ ለማራቅና እርሷን ከማፍቀርና ከማመስገን ለመለየት የሞት ሽረት የሚያደርገዉ፡፡ ምክንያቱም በተሰጣት ጸጋና በተገለጸችበት ብርሃናዊ ባሕርይ የእያንዳንዱን የአዳምና ሔዋን ዘሮች እንደ መንፈስ ቅዱስ ተግባራቸዉን፣ ንግግራቸዉን፣ ሐሳባቸዉን ጭምር ታዉቃለች፡፡ በዚህም ምክንያት ወዳጆቿ እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ሕይወት እንዲይዙ ሁል ጊዜ የራሷን ጥረት ታደርጋለች፡፡ ጸጋም እንዲላበሱ ታደርጋለች፡፡ በመጨረሻም ለታላቅ ሰማያዊ ክብር ታበቃቸዋለች፡፡ ታዲያ ዲያብሎስ በዚህ ተግባሯ እንዴት አይበሳጭባት!? እንዴት እርሷን ለማስካድና ከትዉልዱ ለመለየት የሞት ሽረት ትግል አያደርግ!? እጅግ ይበሳጫል፤ ያደርጋል፡፡ በማንኛዉም መንገድ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ በመግባትና እንደ ልቡ የሆኑትን ሰዎች በማሰማራት ፍላጎቱን ያስፈጽማል፡፡ ለዚህም ነዉ ሥጋዉያኑ በክህደት እምነት ሥርዓት ዉስጥ እንዲመላለሱ በማድረግ በሞት ሕይወት እንዲኖሩ አድርጎ ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ የሚያዘጋጃቸዉ፡፡ በመንፈሳዊ መንገድ ዉስጥ ያሉትን ደግሞ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶችን እያዘጋጀ ፈጣሪ እግዚአብሔር አልፋና ያሜጋ የሆነዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ከእርሱ በላይ ሌላ አምላክ እንዳለ አደርጎ በማቅረብ «አማላጅ ነዉ፤ ነብይ ነዉ፤ ፍጡር ነዉ፤ ሐሳች ነዉ ... ወዘተ » እያስባለ በክህደትና በምንፍቅና ሕይወት እንዲመሩ በማድረግ ትዉልዱን ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት በእምነት ሽፋን እየማገደ ያለዉ፡፡ ዲያብሎስ ከነ ሠራዊቱ ሰይጣናት ጋር ሆኖ ትዉልዱን ከእመቤታችን ድንግል ማርያም «ለየ፣ አስቃለለ፣ አሰደበ፣ አስካደ» ማለት በእርግጠኛነት ከእግዚአብሔር እንደለየ ያዉቃል፡፡ ምክንያቱም ከእርሷ የተለየዉ ትዉልድ ነዉ ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ፣ ነብይ ነዉ፣ ፍጡር ነዉ» እያለና እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሽፋን በተሐድሶ ስም እየተንቀሳቀሱ «ማርያም ምንም የምታዉቀዉ ነገር የለም፤ መመስገን ሆነ መግነን የለባትም» እያስባለ በኢየሱስ ስም ሽፋን ትዉልዱን ለሞትና ለመቀመቅ እንዲሁም ለቅጣትና ለፍዳ እያዘጋጀዉ ያለዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፡ እዚህ ላይ ግልጽ ያልሆነልኝ አንድ ጥያቄ አለኝ፡፡ ይኸዉም እግዚአብሔር ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ከሥጋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ የሚለዉ አባባል እንዴት ነፍስ ይነሳል?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፡ በእርግጥ የእግዚአብሔርን አሰራር በሥጋና ደም እዉቀትና አስተሳሰብ አንረዳም፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በገለጸልን መጠን እንረዳለን፣ እናስተዉላለን፡፡ በዚህ መሰረት እግዚአብሔር ሥጋንና ደምን ከሰማይ ይዞ አልመጣም፡፡ የአዳም ዘር ከሆነችዉና ፍጹም ሰዉ ከሆነችዉ ከእመቤታችን ንጽህይተ ንጹሃን ቅድስተ ቅዱሳን ከሆነችዉ ከድንግል ማርያም ነዉ ያንን ሥጋና ደም ያገኘዉ፡፡ ያ የተነሳዉ ሥጋና ደም ደግሞ በድን አይደለም፤ ሕይወት ያለዉ ነዉ፡፡ ሕይወትን የሚያገኘዉ ደግሞ ከነፍስ ነዉ፡፡ ነፍስ ከእርሷ በሚወጣ ኃይል

ሕይወትን ለሥጋ እየሰጠች ተዋሕዳዉ ስለምትገኝ እግዚአብሔር ሥጋዋን ሲዋሐድ ሥጋንና ነፍስን እንደነሳ በዚህ ይታወቃል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን እመቤታችን «ጥንተ አብሶ አለባት» የሚሉ አሉ። ለዚህ ሐሳብ ያሎት ምላሽ ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር እናትነት እንዴት ተመረጠች ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። እመ አምላክ የተመረጠችዉ ገና ሳትወለድ በፊት አዳምና ሔዋን በኃጢአት በወደቁና እዉነተኛ ንስሐ በገቡ ጊዜ ነዉ። ያኔም የተመረጠችዉ በነፍሷ ባሳየችዉ የቅድስና ብቃት እንጂ በአጋጣሚ አይደለም። እንደ ማንኛዉ ሰዉ፣ ሰዉ ሆኗ በምድር ስትገለጽም ያንን ቅድስናና ብቃቷን ጠብቃ በመገኘቷ ነዉ እግዚአብሔር ከእርሷ ሊወለድና ልጇ ለመሆን የበቃዉና የድኅነት አገልግሎቱን የፈጸመዉ። እዉነታዉ ይህ ሆኖ ሳለ፤ ጥንት አብሶ «አለባት፣ የለባትም» ብሎ  መከራከርና መለያየት ይገባ ነበርን? እዉነተኛ ሕሊናስ እንዴት ደፍሮ «አለባት» ይላል? ማንነቷንና ክብሯን፣ ቅድስናዋንና ብቃቷን አገልጋዮች ሆኑ ምእመናን እንዴት ማስተዋል ተሳናቸዉ? ስለምንስ ነዉ የሥጋና የደም እዉቀታቸዉንና ስሜታቸዉን በእግዚአብሔር እዉነት ዉስጥ የሚደባልቁትና የዓለሙን ፍልስፍና ከመንፈሳዊነት ዉስጥ የሚቀይጡት? እንግዲህ የእመቤታችንን ቅድስናና ክብር ያቃለለ አይደለም እርሷን ያላመሰገነ፣ ያላገነነ፣ ያልተማጸነ የእግዚአብሔርን መንግሥት መዉረስ እንደማይችልና የእያንዳንዉ ሰዉ የሕይወቱ ምስጢር ቁልፍ እርሷ መሆኗን አስተዉሎና ተገንዝቦ ስለ ድፍረትና ስለ ዓመፃ ንግግሩ ሆነ ጽሑፉ እንዲሁም ሐሳቡ እርሷን እመ አምላክን ይቅርታ ቢጠይቅና ወደ ፍቅሯ ቢመለስ ለሥጋዉ ለነፍሱም የሚበጀዉ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ አሳስባለሁ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ቀደም ብለዉ በተለያየ ቦታ ላይ እንደገለጹልን እኛ ሕያዋን ፍጥረታት ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ባሕርይ የወጣች(የሰረጸች) ስለሆነ ለእግዚአብሔር እንደ ልጆቹ እንደምንቆጠር ነዉ የገለጹልን። ታዲያ የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና የእኛ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን ልዩነቱና አንድነቱ ምንድ ነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>:  ልጅ የሚለዉን ቃል በእኛ እዉቀትና አስተሳሰብ ካየነዉ ከወላጅ በኋላ የሚገኝ መጀመሪያ ያልሆነ ነዉ። የእኛ የሰዉ ዘሮች ነፍሳችን የእግዚአብሔር ልጅ ያሰኛት ከነበረ ካለ ሕያዉ ሆኖ ከሚኖር ከአልፋና ዖሜጋ ከፈጣሪ ከአምላክ ባሕርይ የተገኘችና ካለመኖር ወደ መኖር የመጣች፤ ቀድሞ ያልነበረች በመሆኗ ፍጡር የሆነች ናት። የእግዚአብሔር የልጅነት ማዕረግ የነበራት ደግሞ በገነት ዉስጥ ነበር። ነገር ግን አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ነፍሳት በገነት ዉስጥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተላለፉ ጊዜ ያንን ልጅነታቸዉን አተዉ ዓመፀኛ ተብለዋል። እስከ ሐዲስ(ምሕረት) ዘመንም እነሱ ብቻ አይደለም የልጅ ልጆቻቸዉ ጭምር የልጅነት ማዕረጋቸዉ ተገፎ ነበር። እግዚአብሔርን ያስደሰቱ የእግዚአብሔር ባለሟሎች እነ ነቢዩ ሙሴ፣ ጻድቁ አብርሃም፣ ንጉሥ ዳዊት፣ ነቢዩ ሳሙኤል፣ ነቢዩ ኢሳይያስ፣ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ነቢዩ ኤልያስ

የመሳሰሉት እንኳ «የእግዚአብሔር ባሪያ» የሚል ማዕረግ ነዉ የተሰጣቸዉ እንጂ ልጅነታቸዉ አልተመለሰላቸዉም ነበር።

ለአዳምና ለዘሮቹ የልጅነት ስማቸዉና ማዕረጋቸዉ የተመለሰላቸዉ እርሱ አልፋና ዖሜጋ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ የሆነዉ እግዚአብሔር በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 1 በቁጥር 32 እንደ ተገለጠዉ «:-የልዑል ልጅም ይባላል» ተብሎ ራሱ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ በመወለዱና ሰዉ ሆኖ በምድር ላይ በመመላለስ ለአዳምና ለዘሮቹ መስዋዕት በመሆኑ ራሱ ዋጋ ከፍሎላቸዉና «ልጅ» ተብሎ የልጅነት ስማቸዉና ማዕረጋቸዉን ከመለሰላቸዉ በኋላ ነዉ። በአዲስ ዘመን ማንኛዉም በእግዚአብሔር አምኖ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቀና መለኮት በተዋሐደዉን በቅዱስ ሥጋና በክቡር ደም የታተመ ሰዉ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ የመጠራት ፈቃድ ተሰቶቷል። እስከ ምድራዊ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ልጅነቱን አስጠብቆ ከኖሩ በገነት ሆነ በመንግሥተ ሰማያት ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ሕያዉ ሆኖ መኖር ይችላል።

እግዚአብሔር በብሉይ ዘመን በወልድ ወይንም በኢየሱስ ወይንም በክርስቶስ ወይንም በመድኃኔዓለም ወይንም በአማኑኤል ወይንም በሥላሴ በሚለዉ ስሙ አይታወቅም ነበር። ነገር ግን በእነዚህ ስሞች እንደሚገለጽ አስቀድሞ በነቢያቱ አናግሯል፤ አጽፏል። ለዚህም ነዉ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ፍጹም ሰዉ ፍጹም አምላክ ሆኖ ከሁለት ባሕርይ በአንድ ባሕርይ ከሁለት አካል በአንድ አካል በምድር ተገልጦ በተመላለሰበት ወቅት እነዚህን ስሞች ሊይዝ የቻለዉና፤ የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን በግልጽ ለዓለም ያሳወቀዉ። ከዚያ በፊት የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም በግልጥ በዓለም አይታወቅም ነበር።

የእኛ የሰዉ ዘሮች የእግዚአብሔር ልጅነት ከኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት ጋር ያለዉ ልዩነት፤ እኛ ያልኖረበት ጊዜ ከሌለ የማይኖትበት ጊዜ ከማይኖር ከፈጣሪ እግዚአብሔር ከሕያዉነት ዘመን በኋላ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣን፣ ቀድሞ ያልነበርን ፍጥረታት ስንሆን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅነቱ ደግሞ ከነበረ ካለ ሕያዉ ሆኖ ከሚኖር አልፋና ዖሜጋ የዐይን ቅጽበት እንኳ መቀዳደም በሌለበት ሁኔታ አብሮ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ሕያዉ ሆኖ የሚኖር፣ እንደ እኛ ካልመኖር ወደ መኖር ያልመጣና ያልተፈጠረ፣ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ ነዉ። ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ መድኃኔዓለም፣ አማኑኤል የሚሉትን ስም የያዘዉ በሥጋ ማርያም በምድር ላይ ከተገለጠ በኋላ ነዉ እንጂ የቀድሞ ስሙ አልፋና ዖሜጋ፣ አዶናይ፣ አልሻዳይ፣ ያሕዌህ፣ ፈጣሪ፣ አምላክ፣ የሠራዊት ጌታ ነበር። በመሆኑም ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበረ ያለ ሕያዉ ሆኖ የሚኖር የእኛ አምላክና ፈጣሪ ነዉ እንጂ፤ እንደ እኛ በእግዚአብሔር የተፈጠረና ካለመኖር ወደ መኖር የመጣ አይደለም። ከእኛ ጋር አንድነት ያለዉ፤ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ልጅነታችንን ስለመለሰልንና የእግዚአብሔር ልጆች ስላስባለን የእርሱን ስም ልንይዝ ችለናል። ክርስቶስ በሚለዉ ስሙ ክርስቲያኖች ተብለናል። ወልድ በሚለዉ ስሙ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለናል።

ጠያቂዉ አገልጋይ እግዚአብሔር እንዴት የተለያየ ስም ሊይዝ ቻለ?

**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ፡** የነበረ ያለ ሕያዉ ሆኖ የሚኖረዉ የሁሉ አስገኝና ፈጣሪ ስም ፍጥረታት ከመፈጠራቸዉ በፊት የነበረ ያለ ሕያዉ ሆኖ የሚኖር ፊተኛዉና መጨረሻ ሲሆን፤ ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ ደግሞ ፈጣሪ ተባለ። ምድርንና ሰዎችን ከፈጠረ በኋላ ደግሞ አዶናይ፣ አልሻዳይ፣ ያሕዌህ፣ የሠራዊት ጌታ፣ እግዚአብሔር ተባለ። በሥጋ ማርያም ከተገለጸ በኋላ ወልደ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ልጅ) እና ወልደ ማርያም(የማርያም ልጅ) ተባለ። እንዲሁም አንድነቱና ሦስትነቱ በግልጽ ስለተገለጸ ሥላሴ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፣ አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ መድኃኔ ዓለም፣ ፊተኛዉና መጨረሻዉ፣ አልፋና ያሜጋ፣ ቃል፣ አምላካችን፣ ጌታችን፣ አባታችን ተባለ። አሁንም የጻድቁም የኃጥኡም የቅዱሱም የዓመፀኛ ፈጣሪ ስለሆነ አምላክ ተብሎ ስሙ ይጠራል። ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ልጅነታቸዉን በአግባቡ ያላስጠበቁት ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናትን)ና ርኩሳን ነፍሳት(ዓመፀኛ ሰዎች) በገሃነመ እሳት ተፈርዶባቸዉ ስለሚኖሩ ሙታን ናቸዉና፤ የሕያዋን አምላክና አባት ብቻ ተብሎ ለሕያዉነት ዘመን ይጠራል።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

ምዕራፍ ዘጠኝ

« <u>**ጠያቂዉ አገልጋይ**</u>: በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ አንዳንድ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ቤት የመነገጃና የመሸቀጫ ቦታ አድርገዉታል:: ይኸዉም መዝሙር መዘመሩ፣ ማስተማሩና መስበኩ መልካም ሆኖ ሳላ አንዳንዶቹ ግን መዝሙሩን ሆነ ስብከቱን ለገቢ ማስገኛ ብቻ አድርገዉ ወራሃዊና ዓመታዊ በዓላትን እየጠበቁ በየመድረኩ በመዘመር፤ «ይህ መዝሙር ርኩስ መንፈስ የሚያርቅ ነዉ፣ በሥጋችሁና በነፍሳችሁ የምትጠቀሙበት ስለሆነ ከእኔ ግዙ... ወዘተ» እያሉ የምስጋናዉንና የስብከቱን መድረክና ድምፅ ማጉያዉን በመጠቀም የማስታወቂያ ስራ በመስራት የተቀደሰዉን ስፍራ ከነፍስ ግብይት ይልቅ የሥጋ ግብይት የሚያደርጉ «ዘማሪያንና ሰባኪያን ነን» ስለሚሉት ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን? እንዲሁም ወርሃዊና ዓመታዊ በዓል እየጠበቁ የቤተክርስቲኒቱም እምነትን፣ ሥርዓት፣ ትዉፊት፣ ዜማ... ወዘተ ያልጠበቀ ስብከትና መዝሙር፤ ሌት ተቀን ስለገንዘብ ብቻ በሚያስቡ ሰዎች ምክንያት ረብሻ በሚመስል መልኩ በሞንታርቦ አካባቢዉንና ምእመኑን እየረበሹ መንፈሳዊዉን ቦታ የመነገጃና መሸቀጫ ቦታ አድርገዉታል:: ለዚህስ ምን አስተያየ አሎት?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በአሁን ሰዓት ትዉልዱ ተስፋዉን ምድርን አድርጎ ስለሚመላለስ ሥጋዊዉንም ሆነ መንፈሳዊዉን መድረክና ወንበር የሚጠቀምበት ሕዝብንና ምእመናን ለማገልገል ሳይሆን፤ ኑሮን ለመደጎምና ለግል ብልጽግና ነዉ:: በተለይ በመንፈሳዊ መድረክና ወንበር ለሥጋቸዉ አገልግሎት የሚጠቀሙ «አገልጋይ ነን» የሚሉ ሰዎች ፍርዱ እጅግ ይብስባቸዋል:: ምክንያቱም ቃሉን እያወቁ ነዉ በድፍረት የእግዚአብሔርን ቤት የመሸቀጫና የመነገጃ ቦታና መድረክ ያደረጉት:: ማንም ሰዉ ቢሆን ከደከመና ከለፋ ተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት የሚገባዉ ቢሆንም፤ አሁን እየታየ ያለዉ ግን ጥቂት ግለሰቦች በአቋራጭ መንገድ ለመክበርና ራሳቸዉን ብቻ ለማበልጸግ መሰለፋቸዉን ነዉ:: በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብዙ የማስተማር ሆነ የመስበክ እዉቀቱም ጸጋዉም ያላቸዉ መምህራንና ሊቃዉንት እንዲሁም ካህናት አሉ:: እንዲሁም የመዘመር እዉቀቱና ጸጋዉ ያላቸዉ መዘምራንና ካህናት ከልዩ ጣዕመ ዜማ ጋር ተዋሕደዉ አሉ:: ነገር ግን ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለምእመናን አገልግሎት ነዉ የተሰለፉት እንጂ በእዉቀታቸዉና በድምፃቸዉ በመጠቀም ቃሉንና ምስጋናዉን ለግል ጥቅማቸዉ አልሸጡትም፤ አልነገዱም::

ለኑሮ ድጎማ ቢያስፈልግ እንኳ እነዚህ ለብዙ ዓመታት የቤተክርስቲያን ትምህርት ተምረዉ እንኳን ሊበለጽጉበት ቀርቶ ኑሮን ለማሸነፍና ቤተሰባቸዉን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል የአገልግሎት ክፍያ ለማይከፈላቸዉ ለተረሱትና ለተገፉት መምህራን፣ ሊቃዉንት፣ መዘምራን፣ ካህናት፣ ዲያቆናት ነበር ሊደጎሙና ሊረዱ የሚገባዉ:: ያለዉ እዉነታ ግን አብዛኛዉ የእግዚአብሔርን ቃልና ምስጋና የሚነገደዉ የቤተክርስቲያን በቂ ትምህርትና እዉቀት በሌላቸዉና ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ እንደ አለማዉያኑ ባለፎቅን ባለኮብራ ለመሆን ሌት ተቀን በሚሯሯጡት አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ነዉ:: ለዚህም ነዉ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊት ባልጠበቀ መልኩ የተለያዩ «ስብከቶችና መዝሙሮች» በካሴትን በሲዲ እየወጡ

ምእመኑን የሚያደናግሩትና መናፍቅ መናፍቅ የሸተቱ «ስብከቶች»ና ዘፈንና ዳንኪራ የመሰሉ «መዝሙሮች» የሚደመጡት።

በዓለም ዘንድ በትልቅ ደረጃ የሚታዩትንና የተለየ ደሞዝና ክብር ያላቸዉን «ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ ሳይንትስት» የሚባሉትን የሚያስንቁ በመንፈሳዊ እዉቀት እጅግ የመጠቁት የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት መምህራንና ሊቃዉንት፤ እንኳን በዶክተርና በፕሮፌሰር ደረጃ ሊታዩ ቀርቶ የአንድ ሰርተፍኬትና ዲፕሎማ ምሩቅ የሚያገኘዉን ክብርን ደሞዝ አለማግኘታቸዉ ሲታይና እንዲሁም በቤተክርስቲያኒቱ ስም የእግዚአብሔርን ቃልና ምስጋና እየሸጡ፣ ለተንደላቀቀና ለተለየ ክብረት የተሰለፉ ሰዎችን ስንመለከት፤ ምን ያህ እኛ በሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጥን ሰዎች ኢ- ፍትሐዊ ተግባር እየፈጸምንና እያስፈጸምን መሆናችንን ነዉ። እነዚህ ብልጣብልጥ «ሰባኪ»ና «ዘማሪ» ነን ባዮችና አሳታሚዎች ኪሳቸዉ ስትጎልና አንድ ያቀዱትን የሥጋ ዓላማ ለማሳካት ሲሉ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያልታየና ያልተመረመረ እንዲሁም እምነቱንና ሥርዓቱን፣ ትወፊቱን ያልጠበቀ ስብከትና መዝሙር መሳይ በካሴትን በሲዲ እያወጡ ፍላጎታቸዉንና ዓላማቸዉን ያሳካሉ። እዉነተኞቹ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ለመረዳት፣ ገዳማትንና አብነት ትምህርት ቤቶችን ለመደጎም፣ እንዲሁም መንፈሳዊ አገልግሎት ለማስፋፋት፣ ባጠቃላይ በሥጋም በነፍስም የሚጠቀሙበትንና የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊትና ዜማ በጠበቀ መልኩ የተለያዩ መንፈሳዊ ካሴቶችና ሲዲዎችን ለአገልጋዩና ለምእመኑ ያቀርባሉ። በቤተክርስቲያን መድረክና በዙሪያ የሚደረገዉ የሞንታርቦ ረብሻና ንግድ የሚያሳየዉ ለቤተክርስቲያንና ለምእመናን የሚቆረቆርና የሚያስብ እረኛ እንደሌለ ነዉ። ምክንያቱም በሕግ ሥርዓት ሊያሲዙና እንደ አስፈላጊነቱም ሊያስቀጡ ሲችሉ፤ ማንም እንደፈለገዉ በእግዚአብሔር ቤት እንዲፈነጭ በመፍቀዳቸዉ ነዉ። ምናልባት ተቃዉሞና ጥላቻ እንዳይደርስባቸዉ ፈርተዉ ከሆነ፤ የቀደሙትን እዉነተኛ አገልጋዮች ሕይወት ማስታወስ ይገባቸዋል። ይኸዉም ተቃዉሞና ጥላቻ ብቻ አይደለም ድብደባ፣ ስቅላት፣ ግድያ፣ ስድብ ሌላም ደርሶባቸዋል። ነገር ግን በእዉነት አገለገሉ፣ መሰከሩ እንጂ ለራሳቸዉ ስምና ክብር፣ ሥልጣንና ጥቅም ቅድሚያ አልሰጡም።

እዚህ ላይ መልካም አርአያቸዉና ተግባራቸዉ ሊመሰከርላቸዉ የሚገቡ ሰዎችና ማኅበሮች አሉ። ምንም እንኳን በግለሰብ ደረጃ በማኅበሩ ስም የሚነግዱና እንደ ማኅበሩ ዓላማና ሕይወት የማይኖሩ ሰዎች ቢኖሩበትም፤ እንዲሁም በአገልግሎት ላይ ሆነ በምእመንነት ደረጃ ላይ እያሉ በተለያየ ኃጢአት ተግባር እየተሰለፉ ምእመናንን የሚያሰናክሉና የሚያሳዝኑ፣ የማኅበሩ ስም ለራሳቸዉ መከበሪያና የበላይነት ስሜት ለመፍጠር የሚጠቀሙ፣... ወዘተ ጥቂት ግለሰቦች ቢኖሩም፤ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ግለሰብ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት በእዉቀታቸዉና በነባራዊዉ ሁኔታ በመገምገም ከእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ጋር የሚላተሙና የእግዚአብሔርንም መልእክት ከቁም ነገር የማይቆጥሩ፣ የሚያጣጥሉ ቢኖሩም፤ እንደ ማኅበር ደግሞ በቤተመንግሥት፣ በቤተክህነት፣ በቤተሕዝቡ ዉስጥ ባሉ የዓመፃ ልጆች ተጽህኖና እንዲሁም እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ በሚያገለግሉ ሰዎች ምክንያት አንዳንድ የፈጸሚቸዉ እንክርዳድ ተግባር ቢኖርም፤ እንደ አጠቃላይ ግን በዚህ አስቸጋሪና ፈታኝ ዘመን በተለያየ አቅጣጫ የሚመጣባቸዉን የተለያዩ ፈተናዎች

ተቋቋመዉ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ አገር ለኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ለቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም ትዉፊትና ቅርስ መጠበቅ ከማንም በላይ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ እዉቀታቸዉን፣ ሙያቸዉን፣ ገንዘባቸዉን፣ ጊዜያአቸዉን ሰዉተዉ በትጋትና በቆራጥነት እያገለገሉ ያሉት የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ናቸዉ። ይህም የሚታየዉ መልካም ስራቸዉና ፍሬያቸዉ በሁሉም ቦታ ይገልጻቸዋል።

በተቃራኒ አቋም የተሰለፉ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት፣ ትዉፊትና ማንነት ለሥጋና ደም ስሜት በሚመች መልኩ ለመለወጥና መድረኮችን እንደ ፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅቶች የመዝናኛና የጊዜ ማሳለፊያ እንዲሁም የዳንኪራና የጭፈራ ለማድረግ ቆርጠዉ የተነሱ ተሐድሶ መናፍቃን የተባሉ የዓመፃ ቡድኖች፤ ከአንዳንድ የመንግሥትና የቤተክህነት ሰዎች ጋር እንዲሁም ከተወሰኑ ምእመን ጋር በመሆን የዓመፃ ሰዎችን በማስተባበር ማኅበሩን ለማጥቃትና ለማጥፋት የማይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማያወሩት የፈጠራ ወሬ የለም። ምክንያቱም ይህ ማኅበር እነዚህ የዓመፃ ቡድኖች በቤትክርስቲያኒቱ ዉስጥ እንደፈለጉት ለመፈንጨትና ለመዋኘት እንዳይችሉ ያደረገና የዓመፃ ስራቸዉንም በማጋለጥ ስዉር ዓላማቸዉን ያከሸፈ ነዉ። በዚህም ተሓድሶ መናፍቃን፤ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ በሕሊናቸዉ የነገሠ ስለሆነ ይህንን ማኅበር በቻሉት መንገድ ሁሉ ከመንግሥትና ከቤተክህነት እንዲሁም ከሕዝብ ጋር በማጣላት ለመበቀል ሌት ተቀን ይጥራሉ። ነገር ግን ማኅበሩን የመሰረተዉ ሰዉ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ እስከ መጨረሻ ድረስ በአገልግሎት ያጸናቸዋል፤ ይጠብቃቸዋል። ከፍተዉ ሊያጠቋቸዉ የሚመጡትን ደግሞ በቁጣዉ ይጠርጋቸዋል።

በግልጽ በመታወቅ ያለበት በማኅበረ ቅዱሳን ዉስጥ እጅግ ብዙ አገልጋዮችና ምእመናን ጊዜያቸዉን፣ ጉልበታቸዉን፣ ገንዘባቸዉን፣ እዉቀታቸዉን በመሰዋት በአገር ዉስጥና በዉጭዉ ዓለም በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት በትጋት የተሰማሩ ያሉበት፤ ለተለያዩ አብያተክርስቲያናትና ገዳማት እንዲሁም ለአብነት ትምህርት ቤቶች የገንዘብ፣ የሙያ፣ የእዉቀት፣ የጉልበት ድጋፍ የሚያደርጉ፤ በትርፍ ሰዓታቸዉ ኑሮዋቸዉን መደጎምና ተጨማሪ ገቢ ማግኘትና እንዲሁም የትምህርት ደረጃቸዉን ጭምር ማሻሻል ሲችሉ፤ ራሳቸዉንና ጊዜያቸዉን ለመንፈሳዊ አገልግሎት በመሰዋት ቀን ከሌሊት የሚተጉ አገልጋዮችና ምእመናን የተሰባሰቡበት፤ ያ ብቻ አይደልም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ያሉ አካላት አንዳች ድጋፍና እርዳታ ሳያደርጉላቸዉና እንዲሁም በተለያየ መንገድ እየተፈታተኗቸዉና እያጠቋቸዉ ፈተናዉን በትዕግስትና በጽናት በመቋቋም ምእመናንን በማስተባበርና ራሳቸዉንም ለአገልግሎት በማሰለፍ ትዉልዱ በዓለም ተዉጦ እንዳይቀር የአገርና የወገን እንዲሁም የቤተክርስቲያን ፍቅር እንዲያድርበትና ሃይማኖቱንም በሚገባ አዉቆ በመልካም ስነምግባር እንዲመላለስ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዉስጥ ለተማሪዎች ከፍተኛ አገልግሎት እየፈጸሙ ያሉ ናቸዉ።

ታዲያ አንዳንዶች እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመሩና ራሳቸዉን አዋቂና ፍጹም አድርገዉ የሚቆጥሩ አገልጋዮችና ምእመናን እንዲሁም ሥጋዉያን ተሰናክለዉባቸዋል። ማኅበሩ ሆነ

በዉስጡ የተሰባሰቡት አገልጋዮችና ምእመናን ዓለማቸዉና ግባቸዉ ቅድስት ቤተክርስቲያንን በቅንነትና በእዉነት ማገልገል እንዲሁም አገልጋዩ ሆነ ምእመኑ ከዘልማድ አገልጋሎትና ሕይወት ተለይቶ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ እንዲያገለግልና እምነቱንም በሚገባ አዉቆ እንደ እምነቱ ሥርዓት እንዲመላለስ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋሕዶ ሃይማኖት አንዳች ሳትበረዝና ሳትከለስ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሰረታት ተጠብቃ እንድትቆይና የቤተክርስቲያኒቱም ቅርስና ትዉፊት በሚገባ ተጠብቆ ለቀጣይ ትዉልድ እንዲተላለፍ ነዉ እንጂ አንዳች ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ወንበር የማይፈልጉና ምኞትም የሌላቸዉ ናቸዉ፡፡

እያንዳንዱ ሰዉ በዚህች ምድራዊ ሕይወት ዘመኑ እዉነትን ከቅንነት ጋር ካላዋሓዳት በስተቀር ሊሰናከልና ሊወድቅ ይችላል፡፡ ይኸዉም በእዉነት ሽፋን ቅንነት የጎደለዉ ፍርድ ከፈረድን እንጠየቅበታለን፡፡ እንዲሁም በቅንነት ሽፋን በእዉነት ካልፈረድን እንጠየቅበታለን፡፡ ስለዚህ አንድን ጉዳይ በሥጋና ደም ስሜት ባልሆነ በመንፈስ ቅዱስ በእዉነት ልንመረምርና ከዚያም በቅንነት እዉነተኛ ፍርድ ልንሰጥ ይገባል እንጂ፤ እንደ ግል ፍላጎታችንንና ጥቅማችን አይተን እዉነተኛነትና ቅንነት የሌለዉን ፍርድ ከሰጠን በምድርም በሰማይም የሚያስጠይቀን ይሆናል፡፡ ለዚህ ሐሳብ ማብራሪያ እንዲሆነኝ እንደ ምሳሌ አቀርባለሁ፡፡ ይኸዉም፡

በትራፊክ ሥርዓትና ሕግ በሁለት አቅጣጫ ወይንም ከላይና ከታች ለሚሄዱ መኪኖች መለያ ድፍን መስመር በሚደረግበት ቦታ በአንዱ አቅጣጫ የሚሄድ መኪና ወደሌላኛዉ አቅጣጫ በሚሄደዉ ወሰን ዉስጥ ነጠብጣብ መስመር ከተደረገበት ቦታ በስተቀር መግባት አይችልም፡፡ ይሁንና በዓለም ላይ በእያንዳንዱ የሕይወት ጉዞዋችን ላይ ያልታሰቡ ክስተቶች ይፈጠራሉና በግጭትም ይሁን በብልሽት ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄደዉ መንገድ ቢዘጋ ከኋላ የሚመጣዉ መኪና የድፍን መስመሩን ሥርዓት በመጣስ ከተቃራኒ መስመር የሚመጣዉን መኪና ሁኔታ አይቶ ነጻ ሲሆንለት ድፍን መስመሩን በማለፍ ሥርዓቱት ጥሶ ያ የተዘጋበትን መንገድ በማለፍ ወደ ራሱ መስመር ሊገባ ይችላል፡፡ ለዚህ መስመር መጣስ ምክንያት የሆነዉ ሌሎች መኪኖዎች መስመሩን በተለያየ መንገድ ስለዘጉት ነዉ እንጂ ያንን የትራፊክ ሥርዓትን ሕግ በድፍረት በመጣስ አይደለም፡፡ ሥርዓት ደግሞ ሰዉ የፈጠረዉና እንደ አስፈላጊነቱና አስገዳጅነቱ በፈጠረዉ ሰዉ ሊሻሻልና ሊስተካከል የሚችል ነዉ፡፡

ታዲያ አንድ ትራፊክ አስከባሪ በእዉነት ከተመለከተ ያ ከፊት ለፊቱ በግጭት ይሁን በብልሽት መንገዱ ስለተዘጋበት የድፍን መስመር አለማለፍ ሥርዓትና ሕግ ጥሶ በሌላኛዉ መስመር ዉስጥ መግባቱ ሥርዓትና ሕግ ስለጣሰ የሚያስጠይቀዉና እንደ ሕጉ ሊቀጣ ይገባዋል፡፡ ነገር ግን የፈጸመዉ ድርጊት በቅንነት ከታየ ደግሞ በወቅቱ የተከሰተዉ አስገዳጅ ሁኔታ ነዉ ያንን መስመር እንዲጥስና ወደ ትክክለኛዉ መስርመር ተመልሶ ጉዞዉን እንዲቀጥል ያደረገዉ፡፡ ታዲያ ሕሊናዉን በቅንነትና በእዉነት የሚመራ ሰዉ ራሱ የተከሰተዉን ሁኔታ መርምሮና ገምግሞ መፍረድ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን እዉነቱን ብቻ በመያዝ ቅንነት በጎደለዉ ሕሊና በዚያ አሽከርካሪ ላይ ቅጣት የሚፈጽም ትራፊክ ካለ ደግሞ ከእርሱ በላይ በፍርድ ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰዉ በእዉነትና በቅንነት የመጨረሻዉን ፍርድ ሊፈርድ ይገባል እንጂ፤ ሁለቱንም አጣምሮ የልያዘ ሰዉ በምንም ሁኔታ በፍርድ ወንበር ላይ

መቀመጥ አይገባዉም:: እንኳን በፍርድ ወንበር ቀርቶ በተለያየ አገልግሎት ዉስጥ የተሰለፍን ሰዎች ማንኛዉንም አገልግሎት በእዉነትና በቅንነት በማየት ልናገለግልና ልንፈርድ ይገባል እንጂ፤ የሕዝብና የምእመናን አገልጋይ ሆነን ሳለ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን የምናገለግል ሆነ የምንፈርድ ከሆነ በሰዉም በእግዚአብሔርም ልንጠየቅ እንችላለን::

አንድ ሌላ ምሳሌ ብንመለከት: አንድ በአገልግሎት ወይንም በኃላፊነት ወይንም በሌላ የስራ ድርሻ የተመደበ ሰዉ ቤተሰቡ ወይንም ራሱ ከባድ ችግር ገጥሞት ያልተፈቀደለትን የአዳራ ገንዘብ በመስረቅ ለችግሩ ቢያዉል እንደ ሰዉ ሰዉኛ በቅንነት ሲታይ ያጋጠመዉ ችግር አስገድዶት ሊሆን ይችላል በአገልግሎቱ ሆነ በኃላፊነቱ ታማኝ ባለመሆን ያልተፈቀደለትን ገንዘብ በመስረቅ ለችግሩ ያዋለሁ:: ነገር ግን በእዉነት ሲታይ ደግሞ «አትስረቅ» የተባለዉን ምድራዊ ሕግን ሆነ ሰማያዊ ሕግን ጥሷል:: በመሆኑም የእግዚአብሔር ሕግ እንደ ሁኔታዎችና አስገዳጅ ነገር የማይሻሻልና የማይሻር ስለሆነ በእዉነትና በቅንነት ያለ ሰዉ በስርቆቱ ሊጠይቀዉና ሊፈርድበት ይችላል:: ነገር ግን ፍርዱ እንደ ስርቆቱ ክብደትና ቅለት ከሌላዉ ሰራቂ ሊቀልለትና ሊለያይ ይችላል:: ባጠቃላይ ከእያንዳንዱ ሰዉ ደረጃዉ ቢለያይ እንኳ እዉነተኛና ቅን መሆን ይጠበቅበታል:: እንደ እዉነተኛነቱና ቅንነቱ ብቃት ደረጃ መጠን ወንበር ላይ ሊቀመጥ ይገባዋል እንጂ እዉነተኛነትና ቅንነት የሌለዉ ሰዉ ምን ያህል እዉቀት ቢኖረዉ ሕዝቡን ሆነ ምእመኑን በሚገባ ሊያገለግልና እዉነተኛ ፍርድ ሊሰጥ አይችልም::

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ማንም ሰዉ ሊሽራቸዉ የማይችሉት የእግዚአብሔር ትእዛዝና ሕግ የትኞቹ ናቸዉ? እነሱስ ከባድና ሸክም ናቸዉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ሊሻሩ ሆነ ሊሻሻሉ የማይችሉት በአዲስ ዘመንም እግዚአብሔር ያጸናቸዉ ትእዛዝትና ሕግጋት በኦሪት ዘጸአት ከምዕራፍ 20 ከቁጥር 1እስከ7 ላይ በግልጽ ተቀምጠዋል:: ይኸዉም:

«እግዚአብሔር ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ :-ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁ እግዚአብሔር አምላክ እኔ ነኝ:: <u>ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ</u>::

በላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድርም ካለው፣ ከምድርም በታች፣ በውሃ ካለው ነገር፣ የማናቸውንም ምሳሌ፣ <u>የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው አታምልካቸውምም፤</u> በሚጠሉኝ እስከ ሦስትና እስከ አራትኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁኝ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረት የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክ ቀናተኛ አምላክ ነኝ::

<u>የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ</u>፣ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና::

**<u>የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ</u>**፣ ስድስት ቀን ስራ፣ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፣ ሰባተኛዉ ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው አንተ፣ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ ከብትህም፣ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ስራ አትሥሩ፣ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጠሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፣ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበት ቀን ባርኮታል፣ ቀድሶታልም።

**<u>አባትህንና እናትህን አክብር</u>**፣ እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።

**<u>አትግደል</u>**።

**<u>አታመንዝር</u>**።

**<u>አትስረቅ።</u>**

**<u>በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር</u>**።

**<u>የባልነጀራህን ቤት አትመኝ</u>**፣ የባልንጀራህን ሚስት፣ ሎሌውንም፣ ገረዱንም፣ በሬውንም፣ አህያውንም፣ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛውንም አትመኝ።» ይላል

ታዲያ የትኛዉ ሕግ ነዉ ከባድና ሸክም የሆነዉ? እስት አንድ በአንድ እንየዉ፡

ከእግዚአብሔር ሌላ አምላክ አለማድረግ ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? በአንድ አምላክ አምኖና እንደ ቃሉ ሆኖ በመገኘት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? ከእግዚአብሔር ዉጭና በእግዚአብሔር ስም ሽፋን ርኩሰት በሆነዉ በባዕድና በጣዖት አምላኮ ዉጭ ሕይወት መመላለስ ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? በርኩሰት ተግባር የሚያድሩብንን ርኩሳን መናፍስትን በእኛ ላይ እንዳያድሩ ማድረግ ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? የእግዚእብሔርን ስም በከንቱ አለመጥራት ነዉ ወይ ከባድና ሸክሙ? ለራሻችን ጥቅም የሚሆነዉን በሰንበትና በዓበይት በዓላት በጌታ ልደት፣ በመስቀል፣ ጥምቀት፣ በስቅለት፣ ትንሣኤ፣ በመሳሰሉት ከሥጋ ስራ ማረፍና ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ፣ ቃለ እግዚአብሔር መማር፣ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ነዉ ወይ ሸክሙና ከባዱ? እናትና አባትን ባጠቃላይ ሰዉን ማክበር ነዉ ከባዱና ሸክሙ? ወላጅን በመስደባችን ምክንያት ከሚፈረድብን ከገሃነመ እሳት ፍርድ ራሳችንን ማዳን ነዉ ወይ ከባድና ሸክሙ? ከፈጸምነዉ በምድራዊ ፍርድ ጭምር በሚያስጠይቀን፤ ሰዉን አለመግደል ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? ከፈጸምነዉ ለተለያየ በሽታና መከራ የሚዳርገንን፤ አለማመንዝር ነዉ ወይ ከባድና ሸክሙ? በሐሰት አለመመስከር ነዉ ወይ ከባድና ሸክሙ? ከፈጸምነዉ ሰላምና ርካታን ከእኛ የሚያርቀዉን፤ በሰዉ ላይ ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ክፋት፣ ቅናት፣ ጥላቻ፣ በቀል፣ ግፍ፣ አድሎ የመሳሰሉትን አለማድረግ ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ? ባጠቃላይ እንደ ሰይጣናት አለመሆንና እግዚአብሔርን መምሰል ነዉ ወይ ከባዱና ሸክሙ?

እስቲ በቅንነትና በእዉነት የታዘዝነዉንና እንድንጠብቅ የተሰጠንን የእግዚአብሔርን ሕግ እንመርምረዉ? ትእዛዙን ብንጠብቅ ጥቅሙ ለእኛ እንጂ ለእግዚአብሔር ምን የሚጨምርለት ሆነ የሚቀንስበት ነገር አለ? በእኛ ሕይወት ከመደሰትና ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ በቅተን እንደ ልጅነታችን እርሱ አባት ሆኖን ሕያዉ ሆነን አብረነዉ ከመኖር ዉጭ ለእርሱ የምንሰጠዉ ምን ነገር አለ? ይህች እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ነፍሳችን ነገሮችን በሚገባ አመዛዝናና አገናዝባ የእግዚአብሔር እዉነት ላይ እንድትደርስ ነበር ወደዚህች ምድር በሥጋ ተገልጻ የመጣችዉ፡ ነገር ግን ክብሯንና ብቃቷን አቃላና ንቃ በነጻ ሕሊናዋ በመመራት ከሰይጣናት በላይ በዓመፃና በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት ተመላለሰች። በዚህም ምክንያት ራሷን ለከፋዉ ለሕያዉነት ዘመን ቅጣት ዳረገች።

እግዚአብሔር አምላክ በአዲስ ዘመንም ቢሆን የተለያዩ ሸክሞችን አቃሎልን ቀላል ሸክምና ልዝብ ቀንበር ነዉ ያደረገለን። ለዚህም ነዉ «እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ወደ እኔ ኑ እኔም ከሸክም አሳርፋችኋለዉ ሸክሜ ቀሊለ ቀንበረም ልዝብ ነዉ» በማለት የተናገረን። ይኸዉም የኦሪትን የእንስሳ መስዋዕት አስቀርቶልን ራሱን በመሰዋት ለሕያዉነት ሕይወት የሚሆነንን ቅዱስ ሥጋዉን ክቡር ደሙን የሰጠን። ማንም ሰዉ ሕይወቱን በንስሐ እየመረመረ እንዲቀበለዉና ኃጢአቱ ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ማስፋቅ እንዲቻለዉ አስደረገ። የኦሪትን የፍርድ አፈጻጸም አሻሽሎ ይኸዉም «የገደለ ይገደል፣ ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይዉጣ፣ ያመነዘረች ተወግራ ትገደል፣ ጠላትህን ጥላ፣… ወዘተ» የሚለዉን በፍርድ ሸንጎ እንዲታይና ቅንነትና እዉነተኛነት በተላበሰ መልኩ እዉነተኛ ፍርድ እንዲሰጥ ያደረገዉ። ያ ብቻ አይደለም ጠላታችንንም እንድንወድ ያዘዘዉ። ባጠቃላይ የድኅነት መንገድ በማቅለል ለሰማያዊ መንግሥቱ እንድንበቃ የልጅነትን ማእረግ የምናገኝበትን እንዲሁም በኃጢአት ስንወድቅ በእዉነተኛ ንስሐ እድል እንድንጠቀም ሰማያዊ ሥርዓት የዘረጋልን።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በመንፈሳዊ መርሐግብርና በእርዳታ ማሰባሰብ ሽፋን በተለያየ ቦታ የመግቢያ ትኬት እየተዘጋጀ ይሸጣል። ለዚህስ ያሎት አስተያየት ምን ይመስላል?

<u>**መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ**</u>: በመጀመሪያ ነገሮችን ሁሉ በቅንነትና በእዉነት መመልከት አለብን። አንዱን ይዘን አንዱን የምንተዉ ከሆነ የተሟላ ፍሬ ማፍራት አንችልም። ይልቁና ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒ ልንሰለፍ እንችላለን። አንኳን አንዱን ማለትም ቅንነትን ወይንም እዉነትን ትተን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናሳካ ቀርቶ፤ ቅንነትን ሆነ እዉነትን በሙሉ ይዘን ካልተመራን ሙሉ ፍሬ ልናፈራና እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ብቻ ልናከናዉን አንችልም። በዓለም የሚታየዉ እዉነታ ደግሞ ሰዎች ከእዉነት ሆነ ከቅንነት እጅግ እግጅ ጥቂቷን ይዘዉ የራሳቸዉን የሥጋና የደም ስሜት ነዉ የሚፈጽሙት።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ** ስገባ፤ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስም ብዙ መንፈሳዊ መርሐግብሮች እንደተከናወኑ ይታወቃል። ነገር ግን «ምንድነዉ የተፈጸመባቸዉ? ምን ዉጤት አመጡ? ይዘታቸዉ እንዴት ነበር?» ለሚለዉ ምላሽ ያፈሩት ፍሬ ነዉ የሚገልጸዉ። አንዳንድ ምሳሌዎችን ብንመለከት

በሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ስም ብዙ መንፈሳዊ መርሐግብሮች በተለያዩ አዳራሽ ዉስጥ ይፈጸሙ ነበር፡፡ ብዙዎች ደግሞ ፍሬያቸዉ የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት፣ ዜማና ቋንቋ ወደ ፕሮቴስታንቲዚም መለወጥ ነበር፡፡ የዋሃን አገልጋዮችና ምእመናን የዚህን የዓመፃ ተግባርና ዓላማ ያላስተዋሉ፤ እዉነተኛ ወንጌል የሚሰበክ እየመሰላቸዉ ይሳተፉና ያገለግሉ ነበር፡፡ እዉነታዉ ደግሞ በዓላማ የሚንቀሳቀሱ የተወሰኑ አስመሳይ አገልጋዮችና ምእመናን ነበሩ፡፡ ዓላማቸዉና ግባቸዉ እንደ ፕሮቴስታን «እምነት» የመዝናኛና የዘፈን እንዲሁም የዳንኪራ አዳራሽ መስርተዉ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ሥርዓት፣ ትዉፊትና ዜማ እንዲሁም ቋንቋ ማጥፋት ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ዓላማቸዉ ሳይሳካላቸዉ በአጭሩ ተቀጭቶ ነበር፡፡ ይሁንና አሁን ያ እርሾ በቤተክርስቲያን ዉስጥ አለ፡፡ «ኦርቶ ጴንጤ» ወይንም «ተሐድሶ መናፍቃን» በመባል የሚታወቁት በቡድንና በግል ያንን ስዉር ዓላማቸዉን ለማሳካት የተለያዩ የሃይማኖት አባቶችን በመያዝ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የተለያዩ አጋጣሚዎችን እየተጠቁ የዓመፃ ተግባራቸዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም እስከአሁን ድረስ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በግልጽ በሕዋ ሰሌዳቸዉ(በድረ ገጽ) አቋማቸዉን ማንንም ሳይፈሩና ሳያፍሩ ይገልጻሉ፡፡ ተግባራቸዉም ትክክል መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ ያንን ዓላማ እንዳያሳኩ እንቅፋት የሆነባቸዉን እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ዓይነቱን ለማጥፋት የተለያየ ሙከራና ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ሌላዉ እንደምሳሌ የማቀርበዉ በ፳፻፪ (2002)ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ሁለት መንፈሳዊ መርሐግብር ተከናዉነዋል፡፡ የመጀመሪያዉ ደጆችሽ አይዘጉ በሚል ማኅበር ሲሆን፤ ዋናዉ ዓላማዉ የቤተክርስቲያኒቱን ችግሮች ለመቅረፍ ገቢ ማሰባሰብ ነበር፡፡ የተገኘዉንም ገንዘብ በጅማ ሀገረ ስብከት ዉስጥ ላሉ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ አዉለዉታል፡፡ ይህ ፍሬያቸዉ የሃይማኖታቸዉና የቤተክርስቲያናቸዉ ፍቅር አስገድዷቸዉና መንፈሳዊ ቅናት አድሮባቸዉ የቤተክስቲያኒቱን ችግር ለመቅረፍ መነሳታቸዉን ነዉ የሚያሳየዉ፡፡ ጌታችንም «እዉነተኞቹንና ሐሰተኞቹን ከፍሬያቸዉ ታዉቀላችሁ» ባለን መሰረት እስከ አሁን ድረስ መልካም ፍሬያቸዉ ነዉ የሚታየዉ፡፡ ሌሎችም በግልና በማኅበር ሆነዉ በተለያዩ የአገሪቱ አቅጣጫ የተዘጉ አብያተክርስቲያናትን ያስከፈቱ፣ የተለያየ እገዛና እርዳታ ያደረጉ፣ ምእመኑም ከሁሉ በላይ ደግሞ እግዚአብሔር የሚያቃቸዉ አሉ፡፡ እነዚህ ዓይነቶቹ በአንድ ላይ በመዋሐድ ለአንድ ዓላማና ግብ ሊሰለፉ ይገባቸዋል፡፡ የሚመለከታቸዉ አካላት ሆኑ እያንዳንዳችን ድጋፍ ልናደርግላቸዉና ልናበረታታቸዉ ይገባል፡፡ ምክንያቱም አንዳች የግል ጥቅም ሳይፈልጉ ነዉ ጊዜያቸዉን፣ እዉቀታቸዉን፣ ጉልበታቸዉን፣ ገንዘባቸዉን ሰዉተዉ በዚህ በተቀደሰ አገልግሎት ላይ የተሰለፉት፡፡ ታዲያ ከላይ በገለጽኩት መርሐግብር ላይ ሕዝቡ ለመግቢያ ትኬት ገንዘቡን ያወጣዉ የእግዚአብሔርን ቃል በክፍያ ለመማር ፈልጎ ሳይሆን፤ ለቤተክርስቲያን የራሱን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነዉ፡፡ እንኳን ለነፍስና ለሥጋ ለሚጠቅም አይደለም፤ ለሥጋም ሆነ ለነፍሳችን አንዳች በማይጠቅሙን የተለያዩ መርሐግብሮች ላይ ገንዘባችንን አዉጥተን ቀኑን ሙሉ ተሰልፈን እንዉል አይደለም ወይ? ለሥጋም ለነፍስም በሚጠቅመን ላይ ደግሞ የበለጠዉን ገንዘብ ብናወጣ ሆነ ጊዜያችንን ብንሰዋ የሚያንስ ነዉ እንጂ የሚበዛብን አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በዚያዉ ዓመተ ምሕረት በታሕሳስ ወር በሚሊኒየም አዳራሽ «ለወንጌል ማስፋፊያ» በሚል ሽፋን «ቅድስት ማርያም» የሚባል ማኅበር መንፈሳዊ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ

ነበር። በኋላ የታየዉ ፍሬያቸዉ ማንነታቸዉን የሚገልጽ ሆኗል። ይኸዉም በዚያዉ ዓመተ ምሕረት ለአባ ጳዎሎስ ሐዉልት ማስመረቂያና መድረክ ማድመቂያ ሥነ ሥርዓት ለወንጌል ተብሎ በተሰበሰበዉ ብር ከመቶ ሺህ ብር በላይ ወጭ ተደርጎ በበጋሻዉ ደሳለኝ የመድረክ መሪነት ጣዖቱ እንዲመረቅ አስደርገዋል። ያም ብቻ አይደለም ገንዘቡን በተለያየ አገር እየተንቀሳቀሱበት የራሳቸዉን የዓመፃ ተግባር ፈጽመዉበታል፤ አስፈጽመዉበታል። እንዲሁም ለግለሰቦች ለኪሳቸዉ መደጎሚያ አድርገዉታል። ይህም የሚያሳየን ፍሬያቸዉ እንክርዳድ መሆኑንና ለእዉነተኛ ወንጌል አገልግሎት ላይ እንዳላዋሉት ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ የእነርሱን ዓለማ በስዉር ለማሳካት እንደ ይሁዳ ወርቃማ ቃላት በመጠቀም ይኸዉም ይሁዳ ለድሆና ለችግረኛ ተቆርቋሪ በመምሰል «ይህ ሽቶ ተሽጦ ለድሆች ልምን አይሰጥም? ለምን ይባክናል?» እንዳለዉ በተለያዩ አዳራሽ ዉስጥ ዓላማቸዉን ለማስፈጸም ሙከራ አድርገዋል። አሁንም አጋጣሚዉን ካገኙ ከማድረግ የማይመለሱ ናቸዉ።

ከላይ በጥቂት ምሳሌዎች እንደተመለከትነዉ በተለያየ ቦታ ቅንነትና እዉነትን ተላብሰዉ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚተጉ እንዳሉ ሁሉ፤ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሽፋን የራሳቸዉን የዓመፃ ዓላማ ለማስፈጸም የሚተጉ የዓመፃ ልጆችም አሉ። ለዚህ መፍትሔዉ ለእያንዳንዱ መርሐግብር ኃላፊነት የሚወስድና ለትክክለኛ ተግባር መሰለፉን የሚያረጋግጥ አካል በዋናዉ ቤተክህነት ስር መኖር ይኖርበታል። ከቤተክርስቲያኒቱ እምነት፣ ሥርዓት፣ አስተምሮ፣ ትዉፊት ዉጭ የሆነ ተግባር እንዳይፈጸምና ግለሰቦች ለሥጋና ደም ስሜታቸዉ ማርኪያና መጠቀሚያ እንዳያዉሉት የሚቆጣጠር፤ ለእዉነተኛ ተግባር ደግሞ አስፈላጊዉን ድጋፍና እርዳታ የሚያደርግ መሆን ይጠበቅበታል።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: «በመንፈሳዊ አገልግሎት» ዉስጥ የተሰማሩ ሰዎች ሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት በፈጠረዉ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሥርዓትና ፓለቲካ ሕሊናቸዉ ተበክሎና ተመርዞ «እኔ በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ካልተሰበከልኝ ክርስትና ባፍንጫዬ ይዉጣ፤ በፈረንጆቹ ላቲን ፊደል ካልተጻፈ በስተቀር በዐማርኛ ፊደል የተጻፈዉን አላነብም... ወዘተ» የሚሉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት በዚህ አመለካከትና አስተሳሰብ የመረዛቸዉና የበከላቸዉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት ያለ ሰዎች አሉ። በዚህ ላይ ያሉትን አስተያየት ቢሰጡን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በመጀመሪያ ትዉልዱ ማወቅ ያለበት ክርስትና ምን ማለት እንደሆነ ነዉ። ያኔ ምን ዓይነት ሕይወትና አስተሳሰብ መያዝ እንዳለበት እያንዳንዱ ያዉቃል፣ ያስተዉላል። ክርስትና ማለት እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ነዉ። ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ክርስቶስ ተብሎ ነዉ እኛን ክርስቲያን ያሰኘን። ክርስቶስ ደግሞ የሰዉ ዘሮችን ሁሉ በፍቅር የሚመለከትና አንድ ቤተሰብ አድርጎ የሚቆጥር፤ እያንዳንዱ ሰዉ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት እንዲመላለስ የሚፈልግ፤ እንዲሁም እያንዳንዱ እንደ ተሰጠዉ ስጦታ ስለ እዉነት እንዲመሰክርና በእዉነት እንዲኖር፣ በዚህ ሕይወቱና አስተሳሰብ እንዲሁም ምስክርነቱ ምክንያት ማንኛዉም ፈተናና መከራ ቢመጣበት ስለ እዉነት ራሱን ክዶ እንዲመሰክርና መስዋዕትነት እንዲከፍል፣ በመጨረሻም የማያልፈዉን የድል አክሊል ተቀናጅቶ በሰማይዊ መንግሥት ዉስጥ እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆኖ እንዲኖር ነዉ።

**ወደ ጥያቄዉ ምላሽ ስንገባ** ክርስትና እንኳን በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት ሊመላለሱበት ቀርቶ ስለ እዉነት በመመስከሩና በመኖሩ ምክንያት እያንዳንዱ ሰዉ ከቤተሰቡ፣ ከሚስቱ፣ ከልጆቹ፣ ከወንድሞቹ፣ ከእህቶቹ፣ ከዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከስራዉ፣ ከሥልጣኑ፣ ከሚያገኘዉ ጥቅም ... ወዘተ የሚያስለየዉ ቢሆን እንኳ፤ «ቤተሰቤ፣ ልጆቼ፣ ዘመዶቼ፣ ወገኖቼ፣ ዘሮቼ፣ ጎጦቼ... ወዘተ» ሳይል መለየት ጭምር ይጠበቅበታል እንጂ፤ ስለ እነርሱ ሲል ከእዉነት መለየት የለበትም:: ይህም ብቻ አይደለም የተለያየ በደልና አድሎ እንዲሁም መከራና ግፍ ቢደርስበት እዉነትን ይዞ እስከ መጨረሻዉ መገኘት አለበት እንጂ፤ ከምድራዊ ሕይወቱ ዘመን በኋላ ከመያገኘዉ የሕያዉነት ዘመን ሕይወት አንጻር የዐይን ቅጽበት እድሜ ለማይሞላዉ ምድራዊ ዘመኑ ሲል በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት መመላለስ የለበትም::

«በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ካልተሰበከልኝ፣ በላቲን ፊደል ካልተጻፈልኝ ክርስትና በአፍንጫዬ ይዉጣ» የሚል ሰዉ በእርግጠኝነት ክርስትና ምን እንደሆነ ያልገባዉና እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚመላለስ ነዉ:: ለእንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ለያዘና በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት ዉስጥ ያለ ሰዉ እንኳን በአፍ መፍቻ ቋንቋዉ ተሰብኮለትና በላቲን ፊደል ተጽፎለት አይደለም «ዝሙት ብትፈጽም ችግሩ የለዉም፣ ብዙ ብታገባ ችግር የለዉም፣ እንደፈለገዉ ብትበላ፣ ብትጠጣ፣ ብትኖር ችግር የለዉም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ትወርሳለህ» ቢባል እንኳ ለቅን ሐሳብ፣ ለመልካም ተግባር ራሱን ማሰለፍ አይችልም:: ምክንያቱም በሕሊናዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለነገሠ እዉነትን ለማጥፋት ነዉ የሚሰለፈዉ እንጂ በምንም ሁኔታ በዚህ አስተሳሰብ ዉስጥ ያለ ሰዉ ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማሰለፍና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም አይቻለዉም::

በቅንነትና በእዉነት ስለ ቋንቋ አጠቃቀም ብንነጋገር ደግሞ፤ ቋንቋ ሰዎች የሚግባቡበት ስለሆነ አንድሰዉ ቢቻለዉ ሁሉንም ቋንቋ ቢያዉቅ ይመረጣል:: ምክንያቱም ለሁሉም እንደሚሰሙበት ቋንቋ በመናገር ስለ እዉነት ሊያስተምርበትና ሊመሰክርበት እንዲሁም የተለያየ አገልግሎት ሊሰጥበት ይችላልና:: የቋንቋ ጥቅሙን ለዚህ ነዉ እንጂ ሰዎች ራሳቸዉን የተለየ የሚያድርጉበትና የሚያመጻድቁበት አይደለም:: ለዚህም ነዉ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ ብዙ ቋንቋ የማወቅ ጸጋ የተሰጣቸዉና በየቦታዉና በያገሩ ሲሄዱ ሕዝቡ ሊሰማቸዉ በሚችለዉ ቋንቋ ያስተማሩት:: ምክንያቱም አንደ ሰዉ በማይሰማዉ ቋንቋ ትምህርት ቢሰጠዉ ድምፅ ከመስማት ዉጭ አንዳች የሚያዉቀዉና የሚያስተዉለዉ ነገር የለም:: በመሆኑም በኢትዮጵያ ዉስጥ በገጠርም ይሁን በከተማ እንዲሁም በበረኃ ከተወለዱበት ቋንቋ (ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ) ዉጭ የማይሰሙ ወገኖቻችን አሉና በሚሰሙት ቋንቋ ማስተማሩ ተገቢና ትክክል ነዉ:: በዘረኝነትና በጎጠኝነት አስተሳሰብ ያሉ ቢኖሩ እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙና ሲያስተዉሉ ኢትዮጵያዊ ወገናቸዉ ብቻ አይደለም የዓለም ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጥረታትና ልጆች የሆኑ የአንድ የአዳም ሔዋን ዘሮች የአንዱ ኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገዶች ወንድማማችን እህትማማች መሆናቸዉን እንዲሁም አንድ ቤተሰብ እንደሆኑ ያስተዉላሉ፤ ይረዳሉ:: ከእዚህ በተጨማሪ ለምን ወደዚህች ምድር እንደመጡ፣ እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸዉ፣ ታላቅ ተስፋቸዉ ምን እንደሆነ፣ ምንስ ማድግ እንደሚጠበቅባቸዉ፣ ምን እንደተከለከሉ፣ ምን እንደተፈቀደላቸዉ በሚገባ ያዉቃሉ፤ ያስተዉላሉ::

ያኔ ተስፋ ባለዉ ሕይወትና በእዉነተኛ ሕይወት ይመላለሳሉ:: በዘረኞችና በጎጠኞች የተበከለዉና የተመረዘዉ ሕሊናቸዉ ይጸዳል:: የዘረኞችና የጎጠኞች የጨለማ ተግባርንና የማን አገልጋይ እንደነበሩ ያስተዉላሉ::

በሌላ በኩል ኢትጵያዉኛ ቋንቋ (ዐማርኛ ቋንቋ) እየሰማና ማንበና መጻፍ እየቻለ «እኔ በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ካልተማርኩና የክርስቲያኖች(የዐምሓሮች) ፊደል ባልሆነዉ በላቲን ፊደሌ ካልተጻፈልኝ ክርስትና ባፍንጫዬ ይዉጣ» የሚል ሰዉ፤ ፍልጎቱ ቢሟላ እንኳ ክርስትና በሚያዘዉ ሕይወት መኖር ስለማይቻለዉ፤ ምክንያቱም ሕሊናዉ ሙሉ በሙሉ በዘረኞችና በጎጠኞች ስብከት ስለተበከለና ስለተመረዘ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰዉ መጸለይ ነዉ የሚገባዉ እንጂ፤ የሥጋና የደም ስሜቱን ለማርካት ተብሎ የሚፈጸም ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ ዘረኝነትና ጎጠኝነት ያስፋፋል እንጂ እዉነትን አይመጣም:: «እኔ በኢትዮጵያዉኛ ፊደል መጻፍ ሆነ መማር መስራት አልፈልግም፤ የባዕዳን ፊደል ይሻለኛል» የሚል ትዉልድ በኢትዮጵያ ምድር መፈጠሩ የሚያሳየን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የጨለማዉ ገዥ እንደራሴ በመሆን በክፉ ትንቢት ፈጻሚነት ወደ ወንበር የመጣዉ የሕወሓት ኢሕአዴግ መንግሥት እንደፍላጎቱና ምኞቱ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከትዉልዱ ልቦና መንግሎ ማዉጣቱና ጎጠኝነትን ማንገሡን፣ በሂደትም ኢትዮጵያዊነትን ሙሉ በሙሉ የመደምሰስ ምኞቱና ፍላጎቱ እንደተሳካለት ነዉ:: ከእዉነተኛ አገልጋይና አማኝ የሚጠበቀዉ ግን እንኳን ኢትዮጵያዉያን አይደለም ዓለም ልክ እንደ እንግሊዘኛዉና አረብኛዉ በኢትዮጵያዉኛዉ (ዐማርኛ) ቋንቋ በአንድ ላይ የሚዋሐዱበትና የግእዝ ፊደሉም ለዓለም እንዲተርፍ ማድረግ ነዉ:: ምክንያቱም ከአንድ ፊደል በላይ ሁለትና ሦስት ፊደል የሚያስፈልገዉ የሌላዉ ቋንቋ ቃላት በኢትዮጵያዉኛዉ(በግእዝ) ፊደል ቢጻፍ አንድ ፊደል ነዉና የሚያስፈልገዉ:: ይህም ጊዜን፣ ሀብትን የሚቆጥብና ሽክምን የሚያቃልል ነዉ:: ሌላዉና ዋንኛዉ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥትነትና ለዓለም እንደራሴነት የተመረጠችዉ ኢትዮጵያ ስለሆች ዓለም ወደ እርሷ ነዉ መምጣት ያለበት እንጂ እርሷ ወደ ዓለም የምትሄድበት ምክንያት የለም::

እዚህ ላይ አንድ ለማንሳት የምፈልገዉ አለ:: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩላችሁ ማኅበረ ቅዱሳን ብዙ የሚያስመሰግኑት ተግባር እንደፈጸመ ሁሉ ዘረኞችንና ጎጠኞችን ተከትለዉ እንክርዳድ ተግባር ፈጽመዋል:: ይኸዉም በኢትዮጵያዉ ዉስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች ዐማርኛ ቋንቋ ለማይሰሙ ወገኖቻችን ስብከት፣ መዝሙር ማዘጋጀቱና በሚሰሙት ቋንቋ ማስተማሩ መልካም ሆኖ ሳለ፤ ለተማረዉ ክፍል የግእዝን ፊደል ሀ ሁን ለሚያዉቅ ትዉልድ ኢትዮጵያዉኛ ባልሆነ በላቲን ፊደል መጽሐፍ እየጻፉ በማሰራጨታቸዉና ትዉልዱ የራሱ የሆነዉን ቅርስንና የማንነቱ መገለጫዉን ፊደል እንዲያጠፋና እንዲያጥላላ በተዝዋዋሪ ለመንግሥት ድጋፍ ማድረጋቸዉ ነዉ:: ቀደም ሲል «ፊደል መቀነስ የለበትም» ብለዉ እንዳልተከራከሩና በጽናት እንዳልቆሙ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ ለተለያዩ ድምፆች የግእዝ ፊደል ላይ ተጨማሪ ጭረቶች ሆነ ምልክቶች በማድረግ የግእዝን ፊደል ለሁሉም ቋንቋ እንዲያገለግል ማድረግ ሲጠበቅባቸዉ፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም ተዋሕዶ ሃይማኖት ለማደከምና ብሎም ለማክሰም በመጨረሻም ለማጥፋት ከተሰለፉ የዓመፃ ልጆች ከተሰባሰቡበት የሕወሓት ኢሕአዲግ ቡድን ጋር ፊደልን በተመለከተ አንድነት ፈጥረዉና በጥፋት

ዓላማዉ ከጎኑ ሆነዉ ይኸዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚነገረዉን ቋንቋ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ በባዕድ ፊደል በላቲን እየጻፉና እያጻፉ ይገኛሉ፡፡

ለእዉነተኛ አገልግሎት እስከተሰለፉ ድረስ ስለ እዉነት መቆም ይጠበቅባቸዉ ነበር እንጂ እንደ ሥጋዉያንና እንደ ዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚዎች ከንቱ ሥጋዊ መጠብብ ማድረግ አልነበረባቸዉም፡፡ «በግእዝ ፊደላችን ነዉ የምንጠቀመዉ» በማለት በጽናት መቆምና በዚህም ምክንያት የሚመጣባቸዉ ፈተና ቢኖር እንኳ ሌሎችን ፈተናዎች በድል እዲወጡ ያደረገ የኢትዮጵያ አምላክ በዚህም የሚመጣባቸዉን ፈተና ድል እንዲያደርጉ ይረዳቸዉ ነበር፡፡ ይሁንና «ተመሳሰለህ ኑር፣ ሕሊናህ ባይቀበለዉም ለመኖርና ለመስራት ስትል ሕሊናህል ሸጥ» የሚለዉን የአእምሮ ሕፃናትና የአእምሮ ቀላሎች አስተሳሰብ አሸንፏቸዉ ይህን እንክርዳድ ተግባር ሊፈጽሙ ችለዋል፡፡ ነገር ግን የሰሩት ታላላቅ ስራና ለቤተክርስቲያናቸዉ የከፈሉት መስዋዕትነት እጅግ ብዙ በመሆኑና የዲያብሎስ ሥርዓት ተጽህኖ ስለፈጠረባቸዉ እንዲሁም በሌላ አመለካከት እንዳይታዩ ስጋት ስላደረባቸዉ በመሆኑ በእግዚአብሔር ሆነ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኩል አልተወቀሱም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ እንደ ሰዉ ዉጭዉን ብቻ ሳይሆን ዉስጡን በደንብ ያዉቃሉና ነዉ፡፡

ነገር ግን «ልጆቼ ይህን ከንቱ ሥጋዊ መጠበባችሁን ተዉኑ ለሕናችሁና ለአምላካችሁ ብቻ ታምናችሁ እርሱ በሚያሳስባችሁን በሚመራችሁ ተግባር ላይ ብቻ ተሰለፉ፤ እነዚያ «በኃይላቸዉ ተመክተዉ እንዲህ እናደርጋችኋለን፣ እናስደርጋችኋለን» እያሉ የሚፎክሩትን አትፍሩ፡፡ ተለምነዉ፣ ተመክረዉ ፣ ተገስጸዉ እንኳ «አንመለሰም፣ በዓመፃችን እስከ መጨረሻዉ እንጸናለን፣ ማንም ምንም ሊምደርገን አይችለም፣ በመቃብራችን ላይ ካልሆነ በስተቀር ማንም አቋማችንን አያስለዉጠንም... ወዘተ» እያሉ ሕሊናቸዉን ስላደነደኑና ስለታበዩ ልጄንም እጅግ ስላስቆጡ በቅርቡ እንደ እንፉሎት ተነዉ፣ እንደ አቧራ በነዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደማያገኙበት መቀጫ ቦታ ይገባሉ፡፡ እናንተ ግን በእነሱ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር አትሰለፉ፡፡ የእነሱን የክፋት፣ የተንኮል፣ የበቀል ዓላማ አስፈጻሚና ፈጻሚ አትሁኑ፡፡ ከእነሱ ጋር በዓመፃቸዉ አንዳች አንድነትና ኅበረት አይኑራችሁ» በማለት እመቤታችን ለጥቂቶቹ ብትመክራቸዉም፣ ብታስጠነቅቃቸዉም፤

እነሱ ግን «እኛ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ በመመልከት ነዉ እያገለገልን ያለነዉ እንጂ እንደ ቆራጦቹ ኢያሱና ካሌብ፤ «እንደ ሰዉ ሰዉኛ ካየን ሰዎቹ የሚያስፈሩና ጨካኝ የሚመስሉ በቀላሉ ድል የማይደረጉ ናቸዉ፡፡ እግዚአብሔር ግን በቃሉ የታመነ ነዉና ወደ ከነዓን ያስገባናል፡፡ ስለዚህ እናንት ሕዝቦች በአምላካችሁ ተማመኑ እንጂ ልባችሁ ወደ ግብፅ ባርነት አይመለስ፡፡» በማለት ከአሥሩ ነገድ ተወካዮች በተለየ አቋም ተሰልፈዉ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸዉን መተማመን በግልጽ ለሕዝቡ እንደመሰከሩት ቆራጥ ልብ ስለሌለንና፤ በድምፅ ብልጫ ስለምናምን አሥሩ ነገድ «እነዚያ የከነዓን ሰዎች አስፈሪና ጨካኝ ናቸዉና ሙሴና እግዚአብሔር በግብፅ እንዳንኖር ሊያስጠፉን ነዉ ወደዚያ እንድንገባ ያሚያድርጉት» በማለት የኢያሱና የካብን አቋምና በእግዚአብሔር መተማመን በመቃወም በድምፅ ብላጫ ስላሸነፉ እኛም በድምፅ ብላጫ በመሸነፋችን፤ እንዲሁም ፊደል የቆጠርን ስለሆነ በዓይናችን ከምናየዉና በጆሯዋችን ከምንሰማዉ ነባራዊ ሁኔታ ዉጭ በሆነ አቋም ለመሰለፍ

ጽናትና ቆራጥነት ስለሚጎለን፣ በተማርነዉና ባወቅነዉ ብቻ እናገለግላለን እንጂ፣ የአስተሳሰብና የአቋም ማስተካከያ አናደርግም:: ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስና በተለያዩ ገድላትና ተአምራት ላይ እግዚአብሔር ከሕሊና በላይ የሆነ ተግባር እንደሚፈጽም ቢገለጽም፣ እኛም ይህን ለመመስከር ባንቸገርም፣ ተግባራዊነቱ ላይ ለማመን ግን ሃምሳ ሃምሳ(ፊፍቲይ ፊፍቲይ) ስለሆነ እምነታችን፣ ወደ ሙሉ እዉነታና አቋም እስከምንመጣ ድረስ ትንሽ ታገሸን፣ :-ይህ በሚታይና በሚጨበጥ ነዉ መታመን ያለበት የሚለዉ የዘመኑ ትምህርት ተጽህኖ ስላደረብንና እኛም ከዚህ አስተሳሰብ በቀላሉ ለመላቀቅ ስለተቸገርን ጊዜ ይሰጠን:: እስከዛዉ ባለዉ ነባራዊ ሁኔታ እናገልግል» በማለት እስከ አሁን ድረስ ከእንክርዳድ ተግባራቸዉ አልተለዩም:: እዉነት ባለ ጊዜ ስትሆን ግን የእነሱ ሆነ የሌሎች እንክርዳድ ተግባር ከስዴዉ ተለይቶ ኢትዮጵያ ሆነች ዓለም በንጹህ ስንዴ ብቻ የምትገለገል ይሆናል:: እስከዚያ ድረስ ግን እያንዳንዱ በእዉነተኛ ተግባር ብቻ ነዉ መጽናት ያለበት:: ምክንያቱም ቀሎ ከተገኘና የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት በመቃወም እንደ አሥሩ ነገድ እንደ ሥጋና ደም ሐሳቡ ከተመላለሰ፣ ስለ ዓመፃዉም ዋጋ ይከፍላል፣ እንዲሁም ከነዓን ሳይገባ(ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሳይደርስ) በመንገድ ላይ ሊቀር ይችላልና ::

ሌላዉ መታወቅ ያለበት ደግሞ የሚሰራ ሰዉ ነዉ እንጂ የማይሰራ ሰዉ አይሳሳትም:: በዚህም ምክንያት አንዳንድ ግለሰቦች ሆናችዉ ቡድኖች ምናልባት ማኅበረ ቅዱሳን ለሃይማኖታቸዉና ለቤተክርስቲያናቸዉ ካላቸዉ ቅናዓት የተነሳ፣ ካለስማችሁ የተለየ ስም ተሰቷችሁ እንደሆነ፣ ከዛም ባለፈ ተወግዛችዉ ከሆነ ከክፋት ወይንም ከጥላቻ ወይንም ከበቀል አለመሆኑን አስተዉላችሁ በዉስጣችሁ አንዳች ቅሬታና ጥላቻ ሳያድርባችሁ ለአንዲት ሃይማኖትና ለአንዲት ቤተክርስቲያን ልትቆሙና ልትሰለፉ ይገባችኋል:: ምናልባት የሥጋና የድም ስሜት አካሄድ ሄዳችዉ ሊሆን ይችላል፣ ወይንም ትክክለኛ አቋምና ሕይወት አልያዛችሁ ይሆናል፣ ወይንም በሌሎች አማካይነት ሕሊናችሁ ተመርዞና ተበክሎ በተቃራኒ አቋም ተገኝታችሁ ይሆናል፣ ወይንም እግዚአብሔር ለበጎ ሊያደርገዉ ፈቅዶ ሊሆን ይችላል እንጂ፣ ማኅበሩ በበላይ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ካለምክንያት አልተከሰሳችሁም፣ አልተወገዛችሁም:: አሁን ግን በጸሎት ሆነ በሌላዉም ከጎናቸዉ ልትቆሙ ይገባል እንጂ፣ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችሁ ልትመለከቷቸዉ አይገባም:: ለቤተክርስቲያን በጽናትና በቆራጥነት ባይሰለፉ ኖሮ፣ እስከ አሁን ድረስ የተለያዩ መናፍቃንና የእነርሱን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ቆርጠዉ የተነሱ ተሐድሶዎች በቤተክርስቲያን ዉስጥ ይፈነጩ ነበር:: ቤተክርስቲያንም ወደ አዳራሽነት ተለዉጣ የዘፈንና የዳንኪራ እንዲሁም የመዝናኛ መድረክ ትሆን ነበር:: ማኅበረ ቅዱሳንና  እነሱን መሰል አገልጋዮች እያሉም ነዉ ተሐድሶዎችና አስመሳይ አገልጋዮች በቀድሞዉ ፓትርያርክና በመሰሎቻቸዉ ድጋፍና ጥብቅና በቤተክርስቲያን ዉስጥ ሲፈነጩ የነበሩትና ያሉት:: አሁን ግን እንክርዳዱና አስመሳዩ እንደ እንደ እንክርዳድነቱና ገለባነቱ የሚለይበትና የሚበጠርበት ወቅት ላይ ስላለን እያንዳንዱ እንደ ቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ምግባር እንዲሁም ሥርዓትና ትዉፊት ነዉ ጸንቶ መገኘት ያለበት::

ሌላዉ እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገዉ፣ ዳግም በዚያ ምክር ቤት የመናገር እድል እንደማይገጥማቸዉ በእርግጠኝነት የሚያዉቀዉ የኢትዮጵያ አምላክ፣ በሚያዚያ፳፻፬ (2004) ዓ.ም

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ መለስ ዜናዉን ጸፍቶ ከልቦናቸዉ ሞልቶ ሊፈስ የነበረዉን ንግግር እንዲናገሩ አስደርጓል። ይኸዉም በንግግራቸዉ ከአክራሪነት ጋር በተያዘ ወገኖቻችን ከሆኑት በእስልምና እምነት ዉስጥ በአክራሪነት(በአሸባሪነት) የሚፈርጇቸዉ ሰዎች እንዳሉ ከገለጹ በኋላ፤ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዉስጥ ደግሞ ማኅበረ ቅዱሳንን በዚሁ መልክ ፈርጀዉታል። ይህን ያቀረቡት ደግሞ ለባለሥልጣኖቻቸዉና ካድሬዎቻቸዉ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ በሙሉ ነዉ። ይህ የመጨረሻ መሰናበቻ ንግግራቸዉም በቀጣይ በየስብሰባዉ ላይ የሕወሓት ብአዴን ኢሕአዴግ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ማኅበሩን በማጥላላትና የተለያየ ተጽህን እንዲደርስበት እንዲሁም የቅርብ ክትትል እንዲደረግበት ተደርጓል። ያም ብቻ አይደለም ሕዝበ ሙስሊሙ «ይወክሉኛል፣ እዉነተኛ አገልጋዮች እንዲመረጡ ያስደርጉልኛል» ብሎ የመረጣቸዉን ወገኖች የሕወሓት ብአዴን ኢሕአዴግ መንግሥት «አሸባሪ፣ ሁከት ፈጣሪ ናቸዉ» ብሎ ወደ እስር እንዳስገባቸዉ ሁሉ፤ ማኅበረ ቅዱሳንንም «ለሥልጣኔ ያሰጋኛል» ብሎ በሚያስቡበት ወቅትም «አሸባሪ፣ሁከት ፈጣሪ» ብለዉ ተወካዮቹን ከማሰር ወደ ኋላ የማይመለሱ ቀን ከሌሊት ለሥልጣናቸዉ ብቻ የሚያስብ፣ በበላይ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመሩ የእዉነት ተቃዋሚ ናቸዉ።

የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ግን ኢሕአዴግና ማኅበረ ቅዱሳን የሚመራበት መንፈስ ፍጹም ተቃራኒ መሆኑ እየታወቀና፤ እንዲሁም ባለማወቅና በቅንነት አንዳንዶች የማኅበሩ አባል ሆነዉ የኢሕአዴግ አባልም በመሆን እጅና ጓንት ሆነዉ ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎች፤ በዚህን ወቅት ይህን የኢሕአዴግን አመለካከትና አቋም እንደሰሙ ድርጅቱ የዲያብሎስ ድርጅት መሆኑን አስተዉለዉና አዉቀዉ ከድርጅቱ አባልነት መዉጣትን በመንፈስ ቅዱስ ብቻ በሚመራዉ ማኅበር ብቻ የሚጠበቅባቸዉን መፈጸም ሲገባቸዉ፤ ለዲያብሎስ ድርጅት ጥብቅና በመቆም «ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህን የተናገሩት በእኩልነት ስለሚያምኑ ከእስልምናዉ ሃይማኖት አክራሪ(አሸባሪ) ብለዉ የጠሯቸዉ ሰዎች ስላሉ፤ ያንን ለማመጣጠን (ባላንስ) ለማድረግ ሲሉ ማኅበረ ቅዱሳንን እንዲሁ በአክራሪነት(በአሸባሪነት) ሊጠሩት የቻሉት እንጂ ማኅበሩ አሸባሪ ነዉ ለማለት ፈልገዉ አይደለም» በማለት ድርጅታቸዉ በጥሩ አመለካከት እንዲታይላቸዉ ጥረዋል። ለወደፊት ደግሞ ይህ ጥብቅና የቆሙለት ድርጅት ምን እንደሚሰራ የምንመለከተዉ ስለሆነ፤ በዚህ የዲያብሎስ ድርጅት ዉስጥ ያሉ የማኅበሩ አባላት ዛሬ ነገ ሳይሉ ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ከድርጅቱ ቢወጡና ለአንድ አምላካቸዉና እምነታቸዉ ቢታመኑ ያተርፉሉ እንጂ አይጎዱም። ምክንያቱም ድርጅቱ የዓመፃ ልጆች የተሰባሰቡበት ስለሆነ፤ እጅግ እጅግ በቅርቡ ጊዜ ዉስጥ ስለ ዓመፃቸዉ ዋጋ ይከፍሉበታልና። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቁጣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይጠረጋሉና።» **በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ለጠየቃቸዉ አካል ምላሻቸዉን ሰተዋል።**

## ምዕራፍ አሥር

« <u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ ሰዎች «ፓትርያርክ፣ ጳጳስ፣ መነኩሴ፣ ቄስ፣ ዲያቆን፣ መርጌታ፣ ዘማሪ፣ ሊቅ፣ መምህር፣ ንጉሥ(ፕሬዝዳንት)፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ባለሥልጣን... ወዘተ የሆነና ቅዱስ ቁርባን የተቀበለ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ» ይላሉ:: ለዚህ ምን አስተያየት አሎት?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ቅዱስ ቁርባን ለታላላቅ ወይንም ለታናናሽ ሰዎች ተብሎ አልተለየም፤ አልተከፈለም:: ማንኛዉም ሰዉ ከሕፃን እስከ አዋዊ፣ ካልተማረ እስከ ተማረ፣ ከተራ እስከ ዋና መሪ ድረስ ሊቀበለዉ የሚችልና እስከ ምድራዊ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ቃል ሆኖ ከተገኘ ለእግዚአብሔር መንግሥት ይበቃል፤ የማያልፈዉን የእግዚአብሔር መንግሥትን ይወርሳል:: ከላይ የተገለጹትና ሌሎች የአገልግሎት ስያሜዎች እንዲሁም ጥሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በአግባቡ በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል፣ ለመምራትና ለማስተዳደር ነዉ እንጂ፤ ስማቸዉና ሥልጣናቸዉ ብቻ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያበቃ አይደለም:: በመንፈሳዊ ወንበር ሆነ በሥጋዊ ወንበር ላይ እንደ ኃላፊነታቸዉ ደረጃ ሆነዉ ካልተገኙና እግዚአብሔር የሚፈልገዉን ፍሬ ማፍራት ካልቻሉ፣ እንዲሁም አገልግሎታቸዉን እንድ ስራ መስክ ብቻ ቆጥረዉና መንፈሳዊ ለመምሰል ብቻ ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ፤ ቅዱስ ቁርባኑ ፍዳ ነዉ የሚሆንባቸዉ እንጂ ሕይወት አይሆናቸዉም፤ ይልቁኑ ከተራዉ ምእመን ይልቅ ፍዳቸዉን የሚያስብስባቸዉ ይሆናል:: በተቃራኒዉ ደግሞ እንደ ኃላፊነታቸዉ ደረጃ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ ከተገኙና እግዚአብሔር የሚፈልገዉን መልካም ፍሬ ማፍራት ከቻሉ እንደ አገልግሎታቸዉና ፍሬያቸዉ ደረጀ በእግዚአብሔር መንግሥትም የበለጠዉን ክብርና ሞገስ ያገኛሉ::

ብዙዎቻችን ንስሐንና ቅዱስ ቁርባንን እንለያያቸዋለን:: ነገር ግን የማይለያዩና በዓመፃ በኃጢአት ሕይወት ዉስጥ ለነበረ ሰዉ ከቅዱስ ቁርባን በፊት እዉነተኛ ንስሐ ይቀድማል:: እያንዳንዱ ዓመፀኛ ወይንም ኃጢአተኛ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስለ ፈጸመዉ ዓመፃዉ ንስሐ ሊገባና ሊጸጸት ይገባዋል:: እንዲሁም ዳግም ያንን የዓመፃ ተግባር ላለመፈጸም ለአምላኩ ቃል ኪዳን ሊገባና ያሳሳተዉና ያሰናከለዉ ሰዉ ካለም ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባዋል:: ይህን ሳያደርግ ለይስሙላ ቅዱስ ቁርባን በድፍረት ቢቀበል ስለማቃለሉ የባሰዉን ፍርድ ነዉ የሚቀበለዉ:: በአሁን ሰዓት በግልጽ እንደሚታወቀዉ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ በተለያየ ደረጃ የተቀመጡ ሰዎች፤ አንዳንዶቹ ሕይወታቸዉና ተግባራቸዉ ዓመፃ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሞላዉ፤ ነገር ግን «አገልጋይ» ተብለዉ በተለያየ የሥልጣን ደረጃ ላይ የተቀመጡ፤ የእዉነትና የቤተክርስቲያን እንቅፋቶችና ምእመናንን የሚያሰናክሉ፣ አንደበታቸዉ ሌላ ሕይወታቸዉ ሌላ የሆነ፣ እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጡና የከፋዉን ቅጣት በራሳቸዉ ላይ እየጠሩ ያሉ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ:: ነገር ግን አገልግሎቱን እንደ ገቢ ማግኛ፣ እንደ ስራ መስክ ብቻ ስለቆጠሩት ቅዱስ ቁርባኑን በድፍረት ይቀበላሉ፤ ያቀብላሉ:: እነዚህ አስመሳይ አገልጋዮች በምድርም በሰማይም ፍርዱ እጅግ ይብስባቸዋል:: እንደ ዓመፃቸዉ ደረጃ

የማይቋቋሙት ቅጣት ነዉ የሚጠብቃቸዉ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስምና በቃሉ ነዉ የነገዱትና።

በአሁን ሰዓት በሥጋዊ ወንበር ላይ ከዋና መሪ እስከ ታች ድረስ ያሉት ሰዎች፤ ሁሉም ማለት ይቻላል የክህደትና የዓመፃ እምነት በሆነዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚያምኑና ለተግባራዊነቱ ቆርጠዉ የተነሱ ስልሆነ እንደ ኃላፊነትና ዓመፃ ደረጃቸዉ ነዉ የሚጠየቁትና የሚፈረድባቸዉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ስምና በቃሉ ስላልነገዱ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ከተቀመጡት ዓመፀኛ ሰዎች ይልቅ ፍርዱ ይቀልላቸዋል። ሌላዉ ደግሞ ማንም ሰዉ ቢሆን ሕሊናዉ እያወቀ ስለ ሰራዉ የዓመፃ ወይንም የኃጢአት ተግባር ንስሐ ካልገባና ካልተጸጸተ በስተቀር፤ በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ በተለያየ በሽታ ሕሊናዉን ካጣ በኋላ «ያድነዉ ወይንም ይግደለዉ» በሚል አጉል አስተሳሰብና እምነት ቅዱስ ቁርባን ቢቀበል፤ ምንም እንኳን ሕሊናዉ ሳያዉቅ በሰዎች አማካይነት የሚቀበል ከሆነ እንደ ድፍረት ተቆጥሮበት ፍዳ ባያመጣበትም ሕይወት ግን አይሆነዉም፤ እንዲሁም እዉነተኛ ንስሐ ስላልገባ ኃጢአቱን ከሰማያዊ መዝገብ (ከእግዚአብሔር ባሕርይ) ላይ አይደመስስለትም። ሕሊናዉ እያወቀ እዉነተኛ ንስሐ ሳይገባና ሳይጸጸት በድፍረት ቅዱስ ቁርባኑን ከተቀበላ ግን ከኃጢአቱ በተጨማሪ ስለ ድፍረቱና ስለማቃለሉ ፍዳዉን ይቀበላል። በሌላ በኩል ደግሞ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በተለያየ የዓመፃ ወይንም ኃጢአት ሕይወት የተመላለሰ ሰዉ፤ ወደ ልቡ ተመልሶ ስለ ኃጢአቱ እዉነተኛ ንስሐ ከገባና ከተጸጸተ ቅዱስ ቁርባኑ ኃጢአቱን ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ይደመስስለታል፤ በፍርድ ቀንም ንስሐ ለገባባት ኃጢአት አይጠየቅበትም። እንዲሁም በበሽታ ተይዞ ከሆነም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በቅዱስ ቁርባኑ ሊፈወስና ሊድን ይችላል። ከዚህ ዉጭ በአጉል ብልጣብልጥነትና በአቋራጭ መንገድ እግዚአብሔርን አታሎ ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃት አይቻልም። እዉነተኛ ንስሐና ጸጸት ናት ኃጢአትን የምታስደመስስና ነጻ የምታስወጣዉ።

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: አንዳንድ ሰዎች ሰዎችን «ጌታዬ» ብለዉ ይጠራሉ። ተጠሪዎችም «አቤት» ብለዉ ጌትነታቸዉን ይቀበላሉ። ይህ የአንዱን ጌታ ስም እንደመዉሰድ አይቆጠርም ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በአገራችን ሆነ በዉጭዉ ዓለም የአክብሮት አጠራሮች አሉ። አንዳንዶች ደግሞ እንደ አምላክ እንዲፈሩና እንዲመለኩ የሚፈልጉ አሉ። አንዳንድ ሰዎች፤ ሰዎችን «ጌታዬ» ብለዉ የሚጠሩት ከአክብሮት የተነሳ ነዉ። አንዳንዶች ደግሞ ከፍርሃትና እንዲሁም ከሽንገላ የተነሳ ነዉ። ሁላችንም ማወቅ ያለብን የሁላችን ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ። ጌታችን ብለን ልንጠራዉ የሚገባ እርሱ ሰዉ ሆኖ የተገለጸዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ሊሆን ይገባል። ባለማወቅ «ጌታይ» ብሎ የሚጠራን ሰዉ እንኳ ቢኖር እንኳ እንደ እድሜያችን «አይ ጌታህ አምላክህ ብቻ ነዉ! እኔ አባትህ ወይንም ወንድምህ ወይንም ልጅህ ነኝ» ማለት ይገባናል እንጂ የእግዚአብሔርን ስም ለሰዉ ልንሰጥ ሆነ ለንቀበል አይገባም። እንኳን «ጌታ» የሚለዉን አይደለም፤ «መምህር፣ ሊቃዉንት፣ አባት» ተብላችሁ አትጠሩ አልተባለምን! ምክንያቱም በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጥነዉ የሕዝብና የምእመናን አገልጋይ ነን እንጂ ጌታና ሊቅ አይደለንም። የሚሰጠን ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ የክብር ማዕረግ ራሳችንን በሕዝብና በምእመናን ፊት

ዝቅ አድርገን እንድናገለግል እንጂ፤ ራሳችንን እንድናስታብይና እንድናስመልክ እንዲሁም እንድናገን አይደለም፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ ሰዉ በሕይወት *ሥጋ* እያለ «ቅዱስ» የሚል ስያሜ ሊሰጠዉ ይገባል ወይ? እንዲሁም ቅዱስ የሚያስብል ሕይወት የያዙ ሰዎች በዚህ ምድር ዉስጥ አሉ ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ እግዚአብሔር የእያንዳንዳችን ነፍስ ከባሕርይዉ ያወጣ(ያሰረጸ) ስለሆነ እንደሱ ቅዱስ እንድንሆንለት ነዉ የሚፈልገዉ፡፡ ለምሳሌ ሕፃናት ምንም ክፋትና ተንኮል የለላቸዉ፣ በነፍሳቸዉ ቅዱሳን መላእክት የሚመስሉ ስለሆነ ቅዱስና ቅድስት ናቸዉ፡፡ ነገር ግን ይህን ቅድስናቸዉን ከዚህች ምድር በሥጋ ሞት እስከሚለዩ ድረስ ከጠበቁ ብቻ ነዉ ቅዱስ ወይንም ቅድስት ሊባሉ የሚችሉት፡፡ እስከዛ ድረስ ግን እኛ ሰዎች የቅድስና ማዕረግ ልንሰጣቸዉ አንችልም፡፡ እርሱ የዉስጥንም የዉጭንም የሚያዉቅ አምላክ ብቻ ነዉ ይህን ቅድስና ሊያረገግጥ የሚችለዉ፡፡ እንደ ግምት እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ በዋሻ ሆነ በገዳም እንዲሁም በበረኃ ሆነ በገጠርና በከተማ ቅድስና የተላበሱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እስከ ዕለተ ሞታቸዉ ድረስ በቅድስናቸዉ ጸንተዉ ከተገኙ ብቻና ያንንም እግዚአብሔር በእዉነተኛ ባለሚሉቹና አገልጋዮቹ ዘንድ ቅድስናቸዉን ሲመሰክርላቸዉ ነዉ እንደ ቅዱስ ሆነ ጻድቅ ልንቆጥራቸዉ የምንችለዉ፡፡ በዓለም የሚታየዉ በተለይ በአስመሳዮችና በሸንጋዮች ዘንድ ቅዱስና ቅድስት የሚለዉ ስያሜ መጫወቻና ማላገጫ ሆኗል፡፡ ለመሸንገልና የራሳቸዉን ስዉር ዓላማ ለማሳካት ዓመፀኛዉን፣ ከሃዲዉን፣ ርኩሱን ሰዉ «ቅዱስ» «ቅድስት» እያሉ ይጠሩታል፡፡ ሲፈልጉም ራሳቸዉን ቅዱስ ያስብላሉ፡፡

እንደ እኔ ሰዉ በሕይወተ *ሥጋ* እያለ ቅድስና ደረጃ ላይ ቢደርስ እንኳ «ቅዱስ» ተብሎ ባይጠራ እመርጣለሁ፡፡ ምክንያቱም በዚህች አአጭሩ እድሜያችን እንኳ የእግዚአብሔርንና የቅዱሳን መላእክት እንዲሁም የቅዱሳን ነፍሳት ቅጽል ስም የሆነዉን «ቅዱስ» የሚለዉን ስያሜ ይዘዉና «ቅዱስ አባታችን፥ ቅዱስነታቸዉ፥ ቅዱስነቶዎ... ወዘተ» እየተባለ ሐሳባቸዉ፣ ተግባራቸዉ፣ ንግግራቸዉ፣ ባጠቃላይ ሕይወታቸዉ ግን እንኳን «ቅዱስ» ሊያስብል ቀርቶ ለአንድ ተራ ግለሰብ የማይሰራዉን የማይገባ ተግባር ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ ተመልክተና ሰምተናል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ቅዱስ የሚለዉን ስም ለመነገጃነትና ራሳቸዉን ለማግነን እንዲሁም ለማስመለክ እንደተጠቀሙበት ነዉ፡፡ እንኳን ቅዱስ ቀርቶ ብፁዕ መባል የማይገባቸዉ ሰዎች ናቸዉ በአብዛኛዉ በእዉነተኛ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒ የተሰለፉትና የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስን ፈቃድ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የሚታየዉና የሚሰማዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>፤ አንዳንድ ሰዎች ለመልካምም ይሁን ለመጥፎ፣ ለቅድስና ይሁን ለርኩሰት ተግባር የእግዚአብሔርን ወይንም የእመቤታችንን ወይንም የቅዱሳንን ስም በከንቱ ያነሳሉ፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ወይንም እመቤታችንን ወይንም ቅዱሳንን መዉደድ ያመለክታል ወይ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>፤ እግዚአብሔርን መዉደድ የሚገለጸዉ ትእዛዙን በመጠበቅና እንደፈቃዱ በመመላለስ ነዉ እንጂ ስሙን በከንቱ በማንሳት አይደልም፡፡ ይልቁና

የእግዚአብሔር ስም በከንቱ የሚያነሣ ሰዉ ከአስርቱ ትእዛዝ አንዱን ሽሯል ማለት ነዉ:: ምክንያቱም «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራዉን ከበደል አያነጻዉምና::» ይላል ዘጸአት20÷7:: ይህም የሚያሳየን አሁን በትዉልዱ የሚታየዉ ለመልካምም ይህን ለመጥፎ፣ ለተቀደሰ ይሁን ለርኩሰት ተግባር «እግዚአብሔርን፣ ማርያምን፣ ሚካኤልን፣ ጊዮርጊስ... ወዘተ» እያሉ ማሏ የሚፈጸመዉ እግዚአብሔርን ሆነ እመቤታችንን ወይንም ቅዱሳንን በመዉደድ ሳይሆን ራስን በአግባቡ ባለመግዛትና አእምሮ ሕፃንነትና አእምሮ ቀላልነት ሲያጠቃን ነዉ:: እግዚአብሔር ሆነ እመቤታችን እንዲሁም ቅዱሳን ስማቸዉ ሊነሳ የሚገባዉ በምስጋና ወይንም ከሕይወታችን ጋር በተገናኘ ጉዳይ ነዉ መሆን ያለበት እንጂ ለዓመፃዉ፣ ለክህደቱ፣ ለርኩሰት ተግባር ስማቸዉን በከንቱ የምንጠራ ከሆነ እንደ በደል እንደሚቆጠርብን ልናዉቅ ይገባል::

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: አንዳንድ አገልጋዮችና አማኞች «ያ ሰዉ፣ ያንቺ ሴት ቡዳ ናቸዉ፤ ይበሉሃል... ወዘተ» ይላሉ:: ሰዉ ሰዉን እንዴት አድርጎ ሊበላ ይችላል?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: ሁላችንም ማወቅ ያለብን ሰዉ በተፈጥሮዎ ሰዉ ነዉ እንጂ አጋንንት ወይንም ሰይጣን ወይንም ርኩሳን መናፍስት ሊሆን አይችልም:: ነገር ግን የእነርሱ ማደሪያና መሳሪያ ሊሆን ይችላል:: ይህም ወዶና ፈቅዶ ካቀረባቸዉና እንዲሁም በወላጆቻቸዉ አማካይነት ወላጆች ሲሞቱ በእነርሱ ላይ ያደሩት ርኩሳን መናፍስት በእርሱ(በእርሷ) ላይ የሚያድሩት፤ ልጆች እግዚአብሔር በሰጣቸዉ መንፈሳዊ መሳሪያ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ በቅዱስ ቁርባን እነዚያን ርኩሳን መናፍስት ማራቅና ኃይላቸዉን ልምሾ ማድረግ ከዛም ባለፈ መቅጣትና ማቃጠል ካልቻሉ፣ ማደሪያቸዉ ከሆኑ፣ እነሱም እንደወላጆቻቸዉ የርኩሳን መናፍስት መሳሪያ በመሆን ሌላ ሰዉን ሊፈትኑና ሊያጠቁ ይችላሉ:: ስለዚህ «ቡዳ» የሚል ስያሜ ሊሰጠዉ የሚገባዉ ለርኩሳን መናፍስት(ለሰይጣናት) ነዉ እንጂ ለግለሰቡ አይደለም:: ሰይጣን ግለሰቡን እንደመሳሪያ ነዉ የሚጠቀመዉ እንጂ ያ ግለሰብ የተለያ ኃይል ኖሮት ሰዉን «ሊበላ» አይችልም:: ይኸዉም በግለሰቡ ዓይን ላይ አድሮ በመመልከት ፈተናና ጥቃት የሚያመጣዉ ሰይጣን ስለሆነ ነዉ:: በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ የሰይጣን መሳሪያ ወይንም አገልጋይ እንዳይሆን እንዲሁም በሰይጣናት እንዳይጠቃ ሕይወቱን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መምራትና የተሰጡትን መንፈሳዊ መሳሪያ መጠቀም ይኖርበታል

**<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>**: በሕሊናዎ ሁልጊዜ በተለየ ሁኔታ የሚታሰብና ሊገልጹት የሚፈልጉት ሐሳብ ካለ ቢገልጹልን?

**<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>**: በሕሊናዬ ሁሌ በተለየ ሁኔታ የተቀረጸና አንዳንዴም የሚያስለቅሰኝ፤ እግዚአብሔር አምላክ በአምላካዊ ሥልጣኑ ሁሉን ማድረግ ሲችል፤ ከፈለገም እያንዳንዱን ሰዉ «እኔን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍስና የምታመዛዝንና የምታገናዝብ ነጻ ሕሊና ሰጥቸዋለሁ::» በማለት እያንዳንዱ ሰዉ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ በሚፈጽመዉ ቅን ሐሳብና መልካም ተግባር እንዲሁም እዉነተኛ ሕይወት «ይህ የተወሰነ ቅንነትና መልካምነት ተገኝቶበታልና

ወደ ገነትና መንግሥተ ሰማያት ይግባ፤ ይህ ደግሞ ቅንነትና መልካምነት አልትገኘበትም እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ  የኖር ዓመፀኛ ሰዉ ነዉ ወደ ሲኦልና ገሃነመ እሳት ይግባ» ብሎ መፍረድና መወሰን ሲችል፤ ለሰዉ ሕሊና የሚከብድና ላስተዋለዉም እጅግ የሚዘገንነዉን፣ ምክንያቱም ዓለማትን በቅጽበት ዉስጥ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት የሚችል፣ ከፈለገም በቅጽበት ዉስጥ ዓለማትን ከመኖር ወደ አለመኖር ማሰለፍ የሚችል፣ የፈለገዉን በፈለገዉ መንገድና ጊዜ ማከናወንና መፈጸም የሚችል፣ ባጠቃላይ ምንም የሚሳነዉ ነገር የሌለ አምላክ፤ መለኮታዉ ባሕርይዉን ዝቅ አድርጎ፣ ደከማዉንና ጎስቋላዉን ሥጋ ተዋሕዶ፣ የሰዎችን ጎስቋላ ሕይወት ኖሮ፣ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በምድር መመላለሱና ሰዎች ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን ማስተማሩና የተለያየ ፈዉስ ማድረጉ አንሶት፣ የተለያየ ፈተናና መከራ ደርሶበት፣ በመጨረሻም ለሰዉ ልጆች ፍቅሩን በመስቀል ላይ እንደ ወንጀለኛና ኃጢአተኛ ተቆጥሮ፣ የሰማይና የምድር የሁሉ ፈጣሪ አምላክ ራቁቱን በመሰቀል ተሰቅሎ፣ ከሕሊና በላይ የሆነዉን ፍቅሩና ቸርነቱን ለሰዉ ዘሮች ሁሉ የገለጸበትን ታላቅ ስራ ባስታወስኩ ጊዜ ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በሕይወት ዘመኖ ለሕሊናዎ በተለየ ሁኔታ እርካታ የሰጠት ነገር ካለ ቢገልጹልን?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: በሕይወት ዘመን የተለየ የሕሊና እርካታ የሰጠኝ፤ እግዚአብሔር ሳይገባኝና ሳልመኘዉ ሊታወቀኝ በመቻሉና እኔም በእርሱ ዘንድ በተለየ ሁኔታ የታወኩ በመሆኔ ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ለትዉልዱ የሚያስተላልፉት የተለየ መልእክት ካለ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: ለትዉልዱ የማስተላልፈዉ መልእክት በእዚህች ምድር(ዓለም) ዉስጥ ትረጉምና ጣዕም ያለዉ ሕይወት ለመኖር እያንዳንዱ በመጀመሪያ ማን መሆኑንና ታላቅ ተስፋዉን ሊያስተዉል ይገባል፡፡ ይኸዉም የእግዚአብሔር ሕያዉ ፍጥረት፣ የማይሞት፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የማይልፍ፣ የሥጋ ሞቱ፤ ሕያዉ ነፍሱ ከሥጋ የምትለይበትና እንደ መናፍስት ረቂቅ አካል የምትለብስበት፣ በረቂቅነት የምትገለጥበት መሳሪያ መሆኑን ማስተዋልና፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከተመላለሰ በእግዚአብሔር መንግሥት ዉስጥ እንደ ቅዱሳን መላእክት ሕያዉ ሆኖ እንደሚኖር ማመንና ማወቅ ይኖርበታል፡፡ በምድራዊ ቆይታዉም በአዳምና ሔዋን በገነት በተፈጸመ ዓመፃ ምክንያት ለዳፈና ለጎደፈ፣ ለጎሰቆለ ባሕርይና ለጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ መዳረጉን በማስተዋል «ለነገ(ለወደፊቱ) አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል» ያለዉን የጌታ ቃል አስተዉሎ፤ ምድራዊ ሕይወታችን እዉነተኛ ሕይወት ያልሆነና ወደ እዉነተኛ ሕይወት መሸጋገሪያ ድልድይ መሆኑን ተገንዝቦ፤ በአጭር ዘመኑ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖረዉ ዘመን አንጻር የዐይን ቅጽበት እድሜ በማትሞላዉ እጅግ እጅግ አጭር ዘመኑ ማድረግ ያለበትን እያደረገ፤ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት መመላለስ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ለሕያዉነት ዘመኑ የሚጠቅመዉን ነገረ መስቀሉን ማስተዋል፣ እግዚአብሔርን ማፍቀርና መፍራት በልቦናዉ ዉስጥ ማሳደር አለበት፡፡ ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊ ጸጋና ክብር ለመብቃት፤ በምድራዊ ዘመኑ ሁሉ የሕይወት

ምስጢር ቁልፉ የሆነችዉን፣ የገነት አዳምና ሔዋንን ቦታ ተክታ ያለችዉን፣ የአደራ እናቱን ድንግል ማርያምን ማፍቀርና መያዝ ይኖርበታል፡፡ ያኔ ከእዉነተኛዉ አምላክ ከፈጣሪ ዘንድ ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ ምስጢር እንዲያዉቅና እንዲያስተዉል ታስደርገዋለች፡፡ ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ታበቃዋለች፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: ለትዉልዱ የሚመኙት ምንድነዉ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እኔ ለትዉልዱ የምጸልየዉና የምመኘዉ በመጀመሪያ ሁሉም የሰዉ ዘር በእግዚአብሔር እዉነት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖር፣ በምድራዊ ሕይወቱ ዘመንም እያንዳንዱ ሰዉ እንደ አቅሙ የራሱ ማረፊያና መጠለያ ቤት እንዲኖረዉ፣ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ራሱ ፈቅዶ በጾም ከመራብና ከመጠማት ዉጭ በማጣትና በችግር እንዳይራብና እንዳይጠማ፤ እያንዳንዱ ሰዉ በነጻ ሕሊናዉ ለሕሊናዉና ለአምላኩ ታምኖ እንዲኖር፤ ማንም ማንንም በጉልበቱ፣ በኃይሉ፣ በሥልጣኑ፣ በሀብቱ፣ በዘሩ፣ በወገኑ ... ወዘተ ተመክቶ በማንም ላይ ጥቃት፣ በደል፣ አድሎ፣ ግፍ፣ በቀል እንዳይፈጽምበት፤ በዓለም፤ ጦርነት ፣ ጥል፣ ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነት፣ መከፋፈል፣ መለያየት ጠፍቶ፤ ሁሉም እንደ አዳምና ሔዋን ዘርነቱ አንድ ቤተሰብ ሆኖ ተሳስቦና ተፋቅሮ በአንድነት እንዲኖር ነዉ፡፡

<u>ጠያቂዉ አገልጋይ</u>: በተለየ ሁኔታ የሚያሳዝኖትና የሚያስገርሞት ነገር ካለ?

<u>መላሹ የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ</u>: እኔ በተለየ ሁኔታ የሚያሳዝነኝና የሚያስገርመኝ፤ በዚህ ምድር ዉስጥ ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይና በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ ዉስጥ እያለን፤ ከዚህ ሕይወት ለመገላገልና በመልካም ሕይወት ዉስጥ ለመኖር መትጋት ሲገባን፤ በባሰ ሁኔታ ራሳችንን ለጉስቁልናና ለመከራ፣ ለስቃይ አሳልፈን መስጠታችን ነዉ፡፡ ያደፈና የጎሰቆለዉ ባሕርይና ጎስቋላ ሕይወታችንና ኑሮዋችን አንሶን በትዕቢትና በእብሪት ሕይወት በመመላለስ ከእግዚአብሔርን እዉነት በተቃራኒ መሰለፋችን ነዉ፡፡ እንዲሁም ይህ ምድራዊ ሕይወታችንን ሕይወት ነዉ ብለን ከሰይጣናት በባሰ ሁኔታ በዓመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ መኖራችንና ከሰይጣናትም ብሰን በወገናችን ላይ የጭከናና የግፍ ተግባር መፈጸማችንና ማስፈጸማችን ነዉ፡፡ ሌላዉ የሚደንቀኝ ደግሞ እኛ በቤታችን ወይንም በጎረቤታችን የማይሆን ተግባር ሲሰራ በእኛ መሰፈርት ተግባሩ ወይንም ንግግሩ ያናድደናል፣ ያስቆጣናል፣ ትዕግስት አተንም ወደ መቅጣት ልንሄድ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ደግሞ በዓለም ዉስጥ ትእልፊት(በቢሊዮን) በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ በተግባርና በንግግር ብቻ አይደለም በሐሳብ የሚፈጸመዉን ክፋት፣ ተንኮል፣ ጥላቻና በቀል፣ ግፍ፣ ግድያ፣ ጭከና ርኩሰት... ወዘተ፣ ባጠቃላይ እጅግ የሚያስቆጣዉን ተግባርና ሕይወት እያወቀና እየተመለከተ ለዘመናት በትዕግስት ዝም ማለቱና፤ ለሚያስተዉል ሰዉ ደግሞ ትምህርታዊ ቅጣት ብቻ መስጠቱ ነዉ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም በዓለም ላይ በግልጽ ተክዶና «እግዚአብሔር የለም»

ተብሎ የምንበላዉን፣ የምንጠጣዉን፣ የምንተነፍሰዉን፣ ባጠቃላይ በምድር ሊያቆየን የሚችለዉን ሁሉ በፍቅሩና በቸርነቱ መስጠቱ ነዉ።

**ቅኔ**

**ቅቡዕ ዓመፂ ገብረ ማርያም ብሔር**

**ምድረ እብን ሐነጸ ሕይወተ ገነት ፀር**

**ግጥም**

**ተንሢኢ ኢትዮጵያ ኖላዊ ኄር፤**

**አቅርቢ ጸሎትኪ በቅድመ እግዚአብሔር፤**

**ያብጽሀነ አምላክ በመንግሥቱ ወለኵሎም ብሔር።**

**ኢትዮጵያ ሆይ! ተነሱ በዓለም ያሉ ልጆችሽ፤**

**ጸንተዉ ያሉ በቅዱሱ ኪዳንሽ፤**

**ቆርጠዉ ተነስተዋል በቅንነት ሊያገለግሉሽ፤**

**በትጋትና በወኔ ከጠላት ሊታደጉሽ፤**

**በአምላክ ኃይል ተማምነዋል ለማዕርግ ሊያደርሱሽ።**

**ኢትዮጵያ አገሬ ኑሪልኝ ለክብሬ፤**

**ባንቺ ላይ ነዉ መከበሬ፤**

**መመኪያዬና ኩራቴ ነሽ ለኔ፤**

**የካም፣ የሴም ፣የያፌት ነገድ ዉሕድ ዘሬ፤**

**የጥንት የአዳምና ሔዋን ፍሬ፤**

የሰዉ ዘሮች መገኛና መዳኛ ምድሬ::

ታዲያ ምን ያደርጋል ክብርሽ ተዳፍኖና ተገፎ ዛሬ፤

ለወደፊትም እንዳትኖሪ ተፈተንሽ በጎጠኝነት ወሬ፤

በአራቱም ማዕዘን ሞሉብሽ የዲያብሎስ ካድሬ፤

አስተሳሰባቸዉና ተግባራቸዉ የመሰለ አዉሬ፤

በተለያየ ቦታ ተሰገሰጉ ሳይቀራቸዉ ከቅሬ፤

ልጆችህ ግን ተነሱ የዓመፃን ስራ ሊያጠፉ ከተደበቀበት ጎሬ::

ምንም እንኳ መፈናፈኛ ቢያሳጡሽ በክፋትን በበቀል ወኔ፤

እዉነተኛና ጀግና ልጆችሽ ተነሱ በቆራጥ ወኔ፤

ሁሉም የሰዉ ዘር ቤተሰቤ ናቸዉ በማለት ወገኔ:: »

በማለት የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ አንድ ጉባኤ ቃና ቅኔና አንድ ግጥም በማቅረብ የመጨረሻ ምላሻቸዉን ለጠየቃቸዉ አካል ሰተዋል::

ኅዳር፲፪፥፳፻፭(12/03/2005) ዓ.ም

# ክፍል አሥር

## ምዕራፍ አንድ

*ቀን 27/06/2004 ዓ.ም*

**ለተከበሩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለአቶ መለስ ዜናዊ**

በመጀመሪያ የንስሐ እድሜዉን ሰቶን እኔን መልእክት እንዳደርስ እርሶም እንዲደርሶት ፈቃዱ የሆነዉ እግዚአብሔር አምላክ ፈጣሪያችንን እያመሰገንኩ ወደ ዋናዉ ጉዳይ እገባለሁ።

ከየካቲት 22 እስከ 30 /2004 ዓ.ም ድረስ የሕዳሴዉን ግድብ በተመለከተ ጥያቄና አስተያየት እንድንሰጥ በተከፈተልን ልዩ መገናኛ መስመር ይኸዉ እኔም እድሉን በመጠቀም ስለሕዳሴዉ ሆነ ስለ ወሳኝ ጉዳዮአስተያየቴንና ጥያቄዬን እንደሚከተለዉ አቀርባለሁ።

በመጀመሪያ ስለ ኢትዮጵያ ልማትና እድገት፣ ብልጽግና እንዲሁም ስለ ሕዝቡ መልካም ኑሮና ሕይወት የማያስብና የግሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የማይነሳሳ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም፤ ምናልባት ኢትዮጵያዊነቱን እንዲጠላና በዉስጡ ጥላቻ እንዲፈጠርበት ካልተደረገ በስተቀር። ነገር ግን ለፖለቲካ መጠቀሚያ፣ ለራስ ስዉር ዓላማ ማሳኪያ፣ እንዲሁም ለጎሊና ማሸጫ ለሚሆን ቅስቀሳ ደግሞ « ከነፈሰዉ ጋር አንነፍስም ፣ እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ አንነዳም ፣ ኅሊናችንን አንሸጥም፣ ጥሩንባ አንነፋም ፣ ቅድሚ የሚሰጠዉ ስራ ሆነ ድርጊት በመጀመሪያ ትኩረትና ቅድሚያ ይሰጠዉ፤» የሚሉ ለኅሊናቸዉና ለአምላካቸዉ የታመኑ ኢትዮጵያዉያን እንዳሉም ሊታወቅ ይገባል። እነዚህ ሰዎች ለእናት አገራቸዉ እንኳን ገንዘባቸዉንና እዉቀታቸዉን ብቻ አይደለም ሕይወታቸዉን አሳልፈዉ የሚሰጡ እንደ ቀደሙት ቆራጥና ጀግና አባቶቻቸዉና እናቶቻቸዉ ለጊዜያዊ ስልጣን ሆነ ጥቅማጥቅም እንዲሁም ክብርና ዝና ሲሉ ኅሊናቸዉን የማይገለባብጡና የማይሸጡ ራሳቸዉን የካዱና ስለ እዉነትም የሚመሰክሩ፤ በዚህም ምክንያት የሚመጣባቸዉን ማንኛዉንም ፈተናና መከራ በትዕግስትና በጽናት የሚወጡ ኢትዮጵያዉን ናቸዉ።

ስለ ሕዳሴዉ ግድብ ይህን ካልኩ ወደ ሁለተኛውና ለእርሶም ሆነ ለዓለም ሕዝብ ወሳኝ ወደ ሆነዉ ጉዳይ እገባለሁ። እግዚአብሔር እያንዳንዱ የአዳም ዘር በምሳሌዉ ሕያዊ ባሕርይ እንዲኖረዉና እርሱን የመምስል ጸጋ ስለ ሰጠዉ ከእያንዳንዱ ሰዉ መልካም ፍሬን ይፈልጋል። በተለይ ብዙ ጸጋ ከተሰጣቸዉ ኢትዮጵያዉያን ብዙ መልካም ፍሬ የሚፈልግ ሲሆን ነገር ግን እንኳን ብዙ ፍሬ ሊያገኝበት ቀርቶ መልካም ፍሬ የሚመስለዉን ለማጥፋት ነዉ ትዉልዱ ቆርጦ የተነሳዉና በዐመጻና በክህደት ሕይወት የጸናዉ። እርሶና መሰሎቾት ደግሞ በዋናነት ለጥፋቱ መሪና ተዋናይ ናችሁ። ለዚህም ዋጋ እንደምትከፍሉበት ማወቅ ይኖርባችኋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍርዱ አንዳች አድሎ የሌለዉና ለእያንዳንዱ ዐመፀኛና ከሃዲ እንደ ስራዉ በምድርም በሰማይም ዋጋ እንዲከፍልበት ያስደርገዋልና ነዉ። ምናልባት ዐመፀኛና ከሃዲ የሚለዉ ትርጉም በእናንት ሐሳብና ተግባር በተቃራኒ የተሰለፈ ሰዉ እንዳይመስላችሁ። በእግዚአብሔር እዉነትና በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያመፀ፣ የካደና የአምልኮ ምንዝርና የፈጸመ ሰዉ ነዉ።

እናንተም« የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» የምትሉት ሆነ « የዓለም መንግስታት መሪዎች ነን» የሚሉት ሰዎች፤ ሁላችሁም በአራቱም ማእዘን የዲያብሎስን ፈቃድ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ በመሆኑ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራችሁ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ትቀረጣላችሁ። ስለ ዐመፃችሁም ከእግዚአብሔር የከፋዉን ዋጋ በዚህች ምድር

ዉስጥ እያላችሁም ትቀበላላችሁ:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጥሪ በተለያየ ጊዜ በእዉነተኛ ባላሚሎቹና እንደራሴዎቹ ቀርቦላችሁ ንቃችሁ በመተዋችሁና የእግዚአብሔርንም ድምጽ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆናችሁ ነዉ:: እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገራችሁንና የመጨረሻዉ የፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔዉ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጋችሁ በእኔ በተራዉና በደካማዉ፣ በመሃይሙና በኃጢአተኛዉ በኩል በመስከረም 2003 ዓ.ም «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚል ርእስ ባስተላለፈዉ መልእክት በክፍል ሁለት በምእራፍ ሁለት በገጽ 32 በአንቀጽ 4 ላይ ለዓለም መንግስታት የተናገረዉ ቃል «**ታድያ ይህን ሁሉ ስታደርጉ ዝም ብዬ የማያችሁ አይመስላችሁ፤ እናንተ ለረጅም ጊዜ እንኖራለን፣ የራሳችንን ሐሳብ እናጸናለን፣ ለትውልዳችን እናስተላልፋለን ትላላችሁ:: ነገር ግን ይህ ሐሳባችሁ ይሻራል፤ ይቆረጣል፤ ፍሬ ሊያፈራ ለሚችል ይሰጣል::**፤» በማለት ነዉ::

ለእናንተ «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» ለምትሉት ደግሞ በክፍል ሦስት በገጽ 56 በአንቀጽ 2 « **በቃ የእናንተም የዐመፃና የርኩሰት ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነዉ:: የዘራችሁትን የክፋት፣ የተንኮል፣ የዘረኝነት ፣ የጥላቻ፣ የመለያየት፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያችሁን ታጭዳላችሁ:: ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ:: በቅንነትና በእዉነት ለሚመላለሱ፣ የኔን ፈቃድ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለድንግል ማርያም ምርጥ ባለሚሎች ሥጋዊዉንም መንፈሳዊዉንም ወንበር አሳልፌ እሰጣለሁ:: የጽድቅ ፍሬ ያፈሩበታል:: በርኃብ፣ በችግር፣ በልመና፣ በጦርነት ፣ በጉስቁልና በዓለም ዘንድ እንድትታወቅ ያደረጋችኋትን « ሀገረ እግዚአብሔር » የተባለች ምስጢር አገሬ የቅድስት ድንግል ማርያም አስራት አገር የቀደመ ክብሯ ይመለሳል:: ከራሷ አልፋ ለዓለም ብርሃን ትሆናለች:: ልጆቿን በአራቱም ማእዘን ትሾማለች:: በጎቹን በመልካም ሕይወት እንዲኖሩ ታደርጋለች::**» በማለት ነዉ የተናገረዉ::

ታዲያ ይህን የተናገረዉን የሚያስቀር ኃይል በዓለም ላይ ያለ ይመስሎታልን? ምናልባት ነጥብ በማትሞሏ እዉቀቱና ጥበቡ እንዲሁም ከልምሾነት በማያልፈዉ ኃይሉ የሚመካ፣ የቅርፊት ሥጋዉ ስሜት ያየለበት ሰዉ « ይህማ በምንም አይነት ሊሆን አይችልም» ሊል ይችል ይሆናል:: ነገር ግን በእግዚአብሔር እዉነታ እግዚአብሔር የተናገረዉን የተባበሩት መንግስታት ሆነ የአዉሮፓ ሕብረት እንዲሁም የአፍሪካ ሕብረት በአንድላይ ቢሰለፉ ሊያስቀሩት አይደለም ለአንድ ቀን የማዘግየት አቅምና ኃይል የላቸዉም:: ምክንያቱም እንኳን በግዙፍ አካል የተገለጹት ሰዎች ቀርቶ በረቂቅ አካል የተገለጹት ሰይጣናት አንድነትና ሕብረት ፈጥረዉ የእግዚአብሔርን ስራ ለማስቀረትና ለማዘግየት ቢሞክሩ አይቀጡ አቀጣት ተቀተዉና ዋጋ ከፍለዉበት ያልፋሉ ፍዳቸዉን ይቀበላሉ እንጂ፤ በየትኛ ዉም ቦታ ማንኛዉም ፍጡር እግዚአብሔርን ማሸነፍ ቀርቶ ሊገዳደረዉ የሚችል የለም:: ስለዚህ የዓለም መንግስታት ሆኑ «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» የምትሉትና በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የምታላግጡት ሁሉ! የሚያዋጣችሁ ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር እጃችሁን ለእግዚአብሔር መስጠትና ወንበሩንም በእርሱ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ንጉሠ ነገሥትና ለካህኑ እጨጌ አሳልፋችሁ በመስጠት በእዉነትኛ ንስሐ በእግዚአብሔር ስርዐት ዉስጥ መመላለስ ብቻ ነዉ::

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! ስለዚህ ለልማቱም ሆነ ለጥፋቱ እንዲሁም ለዐመፃና ለክህደት ተግባር ከዓለም መንግስታት ጋር አንድነት ፈጥረዉ እንደተሰለፉ ሁሉ አሁን ደግሞ ፈቃዶት ከሆነ ነፍሳትን ለማዳን (የዓለም ሕዝብን ከጥፋትና ከጠፈጋዉ ለመታደግ) ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ የሆኑት 76 ገጽ የመጀመሪዉን የእግዚአብሔር መልእክት፣ 463 ገጽ ሁለተኛዉን መልእክት እንዲሁም የመጀመሪያዉንና ሁለተኛዉን ደብዳቤ ለዓለም መንግስታት ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ እንዲያቀርቡ በትህትና እጠይቃለሁ፤ አሳስቦታለሁ ይላል ታናሹ ወንድሞት ::

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም
እግዚአብሔር ቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያን ይባርክ ተዋህዶ ሃይማኖታችንን ይጠብቅ
ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ

<u>ግልባጭ</u>

ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ኢትዮጵያዊዉ እጨጌ

ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ኢትዮጵያዊዉንጉሠ ነገሥት

<u>ኢትዮጵያ</u>

በመጀመሪያዉ፣ በሁለተኛዉ፣ በሦስተኛዉ ዙር በኢሜል አድራሻችሁ የተላከላችሁ ሁሉ

<u>ባላችሁበት</u>

በአንድነትና በሦስትነት ለሚመለከዉ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

## ምዕራፍ ሁለት

**To**www.ethkogserv.org<ekogyesus@aol.com>;<info@ethkogserv.org>;
www.danielkibrete.org<dkibret@gmail.com>; www.adebabay.com<ephremeshete@gmail.com>;
www.eotc-mkidusan.org<mk.mainoffice@gmail.com>; <hamermk08@gmail.com>;
<simeatsidk@gmail.com>; www.dejeselam.org<dejeselam@gmail.com>;
www.abaselama.org<abaselama.eotc@gmail.com>;
www.melakuezezew.info<melakuezezew@gmail.com>;
www.akotetzetewahed.org<akotet2003@gmail.com>; www.spiritualhardtalk-ethiopiantestimonymiracle<feweslamnute@gmail.com>;
www.andadirgen.blogspot.in<enasetewel@facebook.com>;
www.gebrhere.com<gebrher33@gmail.com>; www.kofeda.org<info@kofeda.org>;
wwwkbmz.org<contact@kbmz.org>; www.ahatitewahedo.com<qedamawi@live.com>;
www.kesisyaredgebremedhinblogspot.com<kerlosrd1@gmail.com>;
www.aleqayalewtamiry.org<feedback@aleqayalewtamiru.org>;
www.awdemihret.blogspot.com<awdemihret@live.com>;
www.dejebirhan.blogspot.com<dejebirhan@verytrue.co.uk>;
www.betepawlos.com<betepawlos@hotmail.com>;www.betefikir.blogspot.com<betefikir@gmail.com>; www.bisrat-views.blogspot.com<man.bisrat@yahoo.com>;
www.trinityuniversitycollege.net<info@trinityuniversitycollege.net>;www.tewahedo.org<orthodox@tewahed.org>;www.zeorthodox.org<kesisolomon@zeorthodox.org>

*ቀን ሰኔ፲፭፥፳፻፬(15/10/2004) ዓ.ም*

**ለሚመለከተዉ ሁሉ**

የተከበራችሁ አባቶቼና እናቶቼ፣ እንዲሁም ወንድምና እህቶቼ፤ በቸሩ ፈጣሪ አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስና በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የእግዚአብሔር ሰላምታዬን እያቀረብኩ ወደ ዋና ፍሬ ጉዳይ እገባለሁ::

እንደሚታወቀዉ ከዛሬ ስድስት ወር ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተለያየ ጊዜ በኢ-ጦማር(በኢሜል) አድራሻችሁ በእኔ በደካማዉና በኃጢአተኛዉ እንዲሁም በተራዉና በመሃይሙ በኩል፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ትንሣኤ በሥጋዊ ወንበር ላይ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አገልጋይነትና ጠባቂነት የእግዚአብሔርና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደራሴ ሆነዉ ርእሰ ነገሥት (በንጉሠ ነገሥትነት) ማዕረግ በሚያገለግሉት በአንደኛዉ እንደራሴ በኩል የተላለፈዉን የእግዚአብሔር መልእክታትን ማስተላለፌ ይታወቃል:: በአግባቡ ተነበዉ ይሁን አልተነበቡ እግዚአብሔርና እናንተ ናችሁ የምታዉቁት:: ለማስተዋስ ያህል በእኔ በኩል የተጻፉት መልእክታት«**የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!**» እና «**የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር**» በሚል ርእስ ሲሆን በአንደኛዉ እንደራሴ በኩል የተላለፈዉ ደግሞ «**ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን**» በሚል ነዉ::

በቅድሚያ በድጋሜ በማንነቴ እንዳትሰናከሉ አንዳንድ ነገሮችን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ እኔ ለእናንተ ልጽፍ የቻልኩት ከእናንተ የተለየ ሰዉ እንዲሁም ንጹህና ቅዱስ ሆኜ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥሪ ምክንያት ነዉ፡፡ እንደማንኛዉም ሰዉ በዓለም ዉስጥ ኑሮዬን ለማሸነፍና በኃላፊነት የተረከብኩትን ቤተሰብ በአግባቡ ለማስተዳደር የምወጣ የምወርድ ሰዉ ነኝ፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነትና ሥርዓት የምመላለስም ነኝ፡፡ ነገር ግን በገዳማትና በዋሻ ዉስጥ ሕይወታቸዉን ሰዉተዉ ሙሉ በሙሉ በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ እንደተሰለፉት፣ ሥጋቸዉን እየቀጡ ነፍሳቸዉን እያበለጸጉ እንዳሉት ጻድቃን አይደለሁም፡፡ እንዲሁም መንፈሳዊ ትምህርት ተምረዉ በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ እንደተሰማሩት አገልጋዮችም አይደለሁም፡፡ አንድ ተራ ምእመን ነኝ፡፡ በሕፃንነት ዕድሜዬ በቃሌ የተማርኳቸዉ ዉዳሴ ማርያም፣ መልክዐ ማርያምና መልክዐ ኢየሱስ ተረስተዉኝ አሁን በመጽሐፍ ብቻ በመድገም(በመጸለይ) ላይ ያለሁ መሃይም ሰዉ ነኝ፡፡ ያማረኝን እየበላሁ፣ እየጠጣሁ፣ እየለበስኩ ቤተሰብ መስርቼ የልጆች አባት የሆንኩ አንድ ምስኪን ሰዉ ነኝ፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር የአኗኗሬን ሕይወት፣ የእዉቀቴን ደረጃ፣ የማንነቴን ሁኔታ እንደ መስፈርት ሳይመለከት በጽድቃቸዉ፣ በአገልግሎታቸዉ፣ በእዉቀታቸዉ፣ በችሎታቸዉ፣ እንዲሁም በማንነታቸዉ የሚመጻደቁትን ለማሰፈርና የእርሱ ምርጫና የዓለም ምርጫ የማይገናኝ መሆኑን ለዓለም ለመግለጽ ሲል ከአገልግሎት አገልግሎት ዉስጥ የሌለሁበትን ፣ ከቅድስና ቅድስ ከሌለኝ፣ ከእዉቀት እዉቀት ከሌለኝ፣ ከተለየ ማንነት የተለየ ማንነት ከሌለኝ እኔን ተራና መሃይም እንዲሁም ኃጢአተኛዉን ሰዉ እንደ ሰዉ ቆጥሮኝ ለአግልግሎት ጠራኝ፡፡ ለዚህም ነዉ ባዶነት ሊሰማኝና ኀዘንተኛ ልሆን የቻልኩት፡፡ ምክንያቱም ስንት ጻድቃንና ቅዱሳን በየገዳማቱ፣ በየዋሻዉ፣ በየበረሃዉ፣ እንዲሁም በገጠርና በከተማ እያሉ እኔ ከተሜዉን ለተለየ አገልግሎት በመጠራቴና እንዲሁም አስቤዉ፣ ተመኝቼዉ፣ ፈልጌዉ የማለዉቀዉን የአገልግሎት ድርሻ ሊሰጠኝ በመወሰኑ ነዉ፡፡

የመጀመሪያዉን የእግዚአብሔር መልእክት መስከረም ፳፻፫(2003)ዓ.ም ጽፌ እንደጨረስኩ «ተገናኛ ቸዉ» ከተባልኩት ለሚመለከተዉ አካል መልእክቱኝ እንደሰጠዉ በመስከረም ፳፱፥ ፳፻፫ዓ.ም በቀጣይ ምን እንደምሆን በግልጽ ተነግሮኛል፡፡ ያ የተነገረኝን ደግሞ ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ አይደለም ለአንድ ቀን ሊያዘገየዉ እንማይችል በእርግጠኝነት አዉቃለሁ፤ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን ያ «እንዲህ ትሆናለህ» የተባልኩት ደስታን ሳይሆን ኀዘን ነዉ የጨመረብኝ፡፡ ምክንያቱም ተራነቴንና ማንነቴን በሚገባ ስለማዉቅና ሳይገባኝ ለዚያ ጥሪ ስለታጨሁ ነዉ፡፡ የእርሱ የባለቤቱ ጥሪ ስለሆነ ብቻ በጸጋ የተቀበልኩት ሲሆን ዋና ተግባሬም የሚሆነዉ የተመለኩትን ሥልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ የግል ብልጽግና፣ ገላ የመሳሰሉትን ከንቱ ማድረገና ተራ መሆናቸዉንም በማሳየት ያን ምስኪን አባትና አምላክ ማስገነንና ማስመለክ፤ እንዲሁም ያቺን ምስኪን እናት ማስገነንና ማስመስገን ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ ገና ወደታጨሁበት ጥሪ ሳልመጣ ምን እንደምሆን ባዉቅም ራሴን በዶሮ ኩስ መስዬ ለዓለም ያስተዋወኩት፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ ይኸዉም ያ ኃያልና ገናና፣ ረቂቁ አምላክ ከሕሊናችን በላይ የሆነዉንና ለዓይን ቅጽበት እንኳ ከሕይወታችን(ከነፍሳችን) የማይለየዉን እዉነተኛ ፈጣሪና አባት የሆነዉን እግዚአብሔርን ያገኘሁት በብልጣብልጥነት፣ በማስመሰል፣ ራስን በመካብና በማመጻደቅ ሳይሆን፤ ራስን ባዶ በማድርግ፣ በመሃይምነትና በጅልነት ሕይወት ነዉ፡፡ ይህንንም ለማስተዋል በመጀመሪያዉ መልእክት በክፍል አራት «ጸሐፊዉ ይጸልየዉ የነበረዉ ጸሎት» ተብሎ የተጻፈዉን መመልከት ይቻላል፡፡ የራሴን ማንነት በመካድ ለሰዉ ሕሊና ለመጥራት እንኳ በሚከብደዉ ጥሪና ስያሜ ነበር ራሴን በመጥራት ጸሎቴን ለዓመታት አቀርብ የነበረዉ፡፡ ታዲያ

ይህን ደግሞ ራሴ የፈጠርኩት ሳይሆን ቅዱሳንና ጻድቃን አባቶቼን ተከትዬ ነዉ:: ለምሳሌ ብንወስድ ታላቁ ንጉሥና ነብይ የነበረዉ ዳዊት በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ ሰዉ መሆኑን ቢያዉቅም፣ የተሰጠዉን ጸጋ ቢረዳም ራሱን ግን «የሞተ ዉሻ ነኝ፣ ትል ነኝ» ያለዉ፤ ታላቁ አባት አብርሃም ራሱን «አፈርና አመድ ነኝ» ያለዉ፤ ታላቁ ነብይ ኢሳይያስ ራሱን «ጭቃ ነኝ» ያለዉ፤ ታላቁ ጻድቅ ኢዮብ « ኃጢአተኛ ነኝ» ያለዉ፤ ያ «ዘሮቼ፣ ዘመዶቼ ናቸዉ፤ ባለስልጣን፣ ባለ ጊዜ ሊኀዱኝ የሚችሉ ናቸዉ... ወዘተ» በማለት አንዳች ፍርሃትና ይሉኝታ ሳይዘዉ ዓመፀኞችንና ከሃዲያንን « እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጠዉ ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ በልባችሁም -አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና:: አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጧል <u>እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል</u>» በማለት የመሰከረዉና እራሱን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ ያደረሰዉ ታላቁ ነብይና ሐዋሪያ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ «ለጫማ ማሰሪያ ፈቺነትና ተሸካሚነት የማይገባኝ ነኝ» ያለዉ፤ ታላቁ ሐዋሪያ ጳዉሎስ « እኔ የዓለም ጥራጊ ጉድፍ ጭንጋፍ ነኝ» ያለዉ፤ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ «ኃጢአቴ ከዓለም ኃጢአት ይበልጣል» ነዉ ያለዉ፤ አሁን ደግም ለሥጋዊዉ ሆነ ለመንፈሳዊዉ ወንበር የታጨት ለዓለም ሕዝብ ለእዉነተኛ አገልጋይነትና ጠባቂነት የተቀቡትና የተመረጡት አባቶች የተጠሩበትን የርእሰ ነገሥት ሥልጣንና የርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌነት ሥልጣን ከቁም ነገር ሳይቆጥሩት ራሳቸዉን « ኃጢአተኛ፣ አቧራ፣ ወራዳ፣ ምስኪን፣ ደኃ ነኝ» በማለት ነዉ ለዓለም በመልእክታቶቻቸዉ ራሳቸዉን ያስተዋወቁት:: ባጠቃላይ ነብያት ሆኑ ሐዋርያት እንዲሁም ሰማዕታት ሆኑ ጻድቃን የተሰጣቸዉን ጸጋና ቅድስና ከቁም ነገር ሳይቆጥሩት አምላካቸዉን ከፍ ከፍ ለማድርግና ለማስገነን እንዲሁም ለማስመስገንና በእዉነትና በመንፈስ ለማስመለክ ሲሉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዋል፤ አዋርደዋል:: ከዚያ ባለፈም ራሳቸዉን ለመከራና ለስቃይ ሕይወት ለመስዋዕትነት አሳልፈዉ ሰተዋል::

እኔ ደግሞ ከእነሱ እጅግ ያነስኩ ስለሆነ «ከሞተ ዉሻ፣ ከፋንዲያ፣ ከኩስ እኩል ልቆጠር አይገባኝም» ብል ሲያንሰኝ ነዉ እንጂ አይበዛብኝም:: እንዲሁም በዘወትር ጸሎቴ « እናንተ ቅዱሳን መላእክት፣ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፤ እኔን ዉዳቂ ባሪያችሁን ባርኩኝ የማስበዉን አላዉቅምና እናንተ አእምሮ ሆናችሁ አሳስቡኝ፤ የምሰራዉን አላዉቅምና ቀኝ እጅ ሆናችሁ የምታሰሩኝ እናንተ ሁኑ፤ የምናገረዉን አላዉቅምና አንደበት ሆናችሁ የምታናግሩኝ እናንተ ሁኑ፤ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር የሚያሰራችሁን ነዉና የምትሰሩት፣ የሚያናግራችሁን ነዉና የምትናገሩት፣ የሚያሳስባችሁን ነዉና የምታስቡት፤» በማለት ነዉ የመሃይምነት ጸሎቴን የማቀርበዉ:: እንኳን የእግዚአብሔር ባሪያ ብዬ ራሴን ለመጥራት ቀርቶ ለቅዱሳን እንኳ ባሪያቸዉ መሆን የማይገባኝ ስለሆነ ነዉ «ዉዳቂ ባሪያችሁ» በማለት ራሴን ዝቅ አድርጌ ከታመኑለት አምላክ ሁል ጊዜ በምልጃቸዉ እንዳይለዩኝና ሌት ተቀን የሚፈታተኑኝን ሰይጣናት ድል እንዲያደርጉልኝ የምማጸናቸዉ:: ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር ምርጥ ባሎሚሎቹና ልጆቹ መሆናቸዉን እያወቁ ነገር ግን ፈጣሪ አምላካቸዉን ለማስገነንና በእዉነትም ለማስመለክ ሲሉ ራሳቸዉን «የእግዚአብሔር ባሪያ ነን» ብለዉ ከጠሩ እኔ ኃጢአተኛዉና ሥጋ ለባሽ ደካማዉ እንዴት «የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ» ብዬ ለመጥራት ይቻለኛል?! አይቻለኝም:: ይሁንና እግዚአብሔር አፍቃሪና ርኅሩኅ አምላክ ስለሆነ የሞኝነቴንና የማይምነቴን ጸሎት ቦታ ሰቶት «አዋቂ፣ ምሁር፣ ሊቅ ነን» እንደሚሉት ሳይንቀዉና ሳያጣጥለዉ «አንተ ለቅዱሳኖቼና ለጻድቃን ባሪያ መባል አይገባኝም በማለት ዉዳቂ ባሪያችሁ ነኝ» ብትልም፤ «እኔ ለእኔም አግልጋይ አደርግሃለሁ» በማለት ለአገልግሎቱ ጠራኝ::

ያ ሁሉን በአምላካዊ ስልጣኑ ማድረግ የሚችል አምላክ የማይገባዉን የእኛን ጎስቋል ሥጋ በመልበስ በከብቶች በረት ዉስጥ ሲወለድ አልተጸየፈዉም:: እንዲሁም የተለያየ ስድብና መከራ ሲደርስበት አልተማረረም:: ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን በማፍሰስ ሥጋዉን በመቁረስ ፍቅሩን በመስቀል ላይ ሲገልጽ አንዳች ቅር አልተሰኘም:: ስለዚህ ይህን አምላክ ለማግነንና ለማስመለክ ራስን በከፋ በከረፋዉ ስያሜ ብንገልጽ ሲያንሰን ነዉ እንጂ አይበዛብንም:: ነገር ግን በሥጋና ደም ስሜት ብቻ የምንቀሳቀስና በእዉቀታችን ብቻ የምናገለግል ከሆነ እንኳን በዚህ መልክ ራሳችንን መግለጽ አይደለም «ለምን ተሰደብኩ፣ ተተቸሁ?» ብለን ለጥልና ለበቀል እንዲሁም ለጥላቻ እንደምንመላለስ ይታወቃል:: መንፈሳዊነት የሌላቸዉ ሰዎች ደግሞ አምላካችንን ከፍ ከፍ ለማድረግ ራሳችንን ዝቅ ዝቅ በማድርግ በዚህ መልኩ ራሳችንን ብንሰይም « ጤነኞች አይደሉም አማኑኤል ሆስፒታል አስገቧቸዉ» እንደሚሉ ይታወቃል:: ምክንያቱም ነብያት ፣ሐዋርያት፣ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣ ባጠቃላይ እዉነተኛ አገልጋዮችና ምስክሮች «ወፈፌ፣ እብድ፣ ቀባጣሪ፣ ቅዠታም... ወዘተ» እያተባሉ ሲሰደቡ ነበርና:: እንኳን እነሱ ራሱ ባለቤቱ በሥጋ ማርያም የተገለጸዉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባዉና ለሕሊናችን በሚከብድና በሚዘገንን መልኩ « እብድ ነዉ፤ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል፤ ሐሳች ነዉ፤ ኃጢአተኛ ነዉ ... ወዘተ» ተብሏል::

ስለዚህ እኔም አንዳች የተለየ ክብር፣ ምስጋና፣ ዝና፣ የግል ብልጽግና የመሳሰሉትን የማልፈልግ መሆኔን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ለነዚህም ስል ሕሊናዬን የማልሸጥ፣ የማልሸነግል፣ በይሉኝታ የማልጠፈር፣ እንዲሁም ቅርፊት ሥጋን ለባሽ ፈርቼ ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ከመመስከር ወደ ኋላ የማልል መሆኔን አሳዉቃለሁ:: እግዚአብሔር እኔ አጎደልኩበት እንጂ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ኑሮዬና ሕይወቴ አንዳች ያጎደለብኝ ነገር የለም:: እንዲሁም ለወደፊት ያለዉን ብሩ ተስፋ ነግሮኛል:: ታዲያ የምመላለሰዉ እንደ ሥጋና ደም ሐሳብ ቢሆን ኖሮ አጉል ብልጣ ብልጥ ሆኜ የተለያየ ፈተናና መከራ እንዳይደርስብኝ የእግዚአብሔርን መልእክት አፍኜና ድምፄን አጥፍቼ መኖር እችል ነበር:: ነገር ግን በእንደዚህ ሕይወት የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን አይቻልምና ስለ ነፍሳት መጥፋትና ስለ እዉነት መዳፈን ልንቆረቆርና ልናዝን እንዲሁም ነፍሳትን ለማዳንና እዉነትን ለመመስከር በቆራጥነት ልንሰለፍ ይገባልና ነዉ እኔም «በእኔ ላይ ችግር ከመጣ አንዳች መተዳደሪያ የሌላቸዉ ቤተሰቦቼ ችግር ላይ ይወድቃሉ፣ ኀዘን ይመጣብኛል፣ ስሜቴም እጅግ ይጎዳል» ሳልል፤ ሁሉን በጸጋ ለመቀበል ተዘጋጅቼ ነዉ በራሴ ላይ ሆነ በማፈቅራቸዉና በምሰፈስፍላቸዉ ቤተሰቦቼ ላይ ፈርጄ የእግዚአብሔርን መልእክት እርሱ በሚመራኝና በሚያሳስበኝ መንገድ ለአዳም ዘር ለማዳረስ ወስኜ መልእክቱን በማስተላለፍ ላይ የምገኘዉ::

ምክንያቱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ « ከእኔ ይልቅ ቤተሰቡን፣ አባትና እናቱን፣ ልጆቹን፣ ሚስቱን፣ ዘመዶቹን፣ ጓደኛዉን፣ስራዉን፣ ስልጣኑን፣ ክብሩን፣ ጥቅሙን፣ ባጠቃላይ የኔናቸዉ፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸዉን ከወደደና ከኔ ፈቃድ ከወጣ ለኔ ሊሆን ደቀ መዝሙሬ፣ አገልጋዬ ሊሆን አይችልም» ብሏልና፤ ከማንኛዉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም ይኖርብናል እንጂ ለቤተሰቤ፣ ለክብሬ፣ ለጥቅሜ፣ የምንል ከሆነ እንኳን የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ቀርቶ ምእመን እንኳ መሆን እንደማንችል በግልጽ ተናግሮናል:: ለዚህም ነዉ የሕይወት መንገድ ጠባብ የሆነችዉና «የሚድኑትም ጥቂቶች ናቸዉ» ሊባል የቻለዉ:: ለዚሁ ማስረጃ በአሁን ሰዓት በዓለም ላይ ካለዉ ስድስትና ሰባት ትእልፊት(ቢሊዮን) ሕዝብ ማነዉ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔርነቱ አምኖበት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት በሚፈጥርበት በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ ተወስኖ ሕይወቱን በንስሐ እየመረመረ በመልካም ምግባርና ሕይወት እየኖረ ያለዉ?! ወይስ እግዚአብሔር ፍርዱ

ከብዙኃኑ ጋር ይሆናል እንጂ ከቁጥር ከማይገቡ እጅግ ጥቂት ሰዎች ጋር አይሆንም በማለት እንደ ሥጋዉያኑ እናስብ ይሆን? ወይስ ሕያዉ ቃሉን አጥፎ በአስተያየተ ለመንግሥቱ ያበቃናል እያል ራሳችንን እያጽናናንና እያሞኘን ይሆን? ያለዉ እዉነታ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የአዳም ዘር የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ሕሊና ስለሰጠዉ በነጻ ፈቃዱ የፈለገዉን ሕይወት መምረጥ የሚችል ቢሆንም ለሰማያዊ መንግሥቱ ግን በነጻ ምርጫዉ ለሕያዉነት ሕይወት የሚያበቃዉን እምነትና ምግባር ከያዘ ብቻ ነዉ ሊበቃ የሚችለዉ:: ከአንድ አእላፍ(ሚሊዮን) ሰዉ ዉስጥ እንደ ፈቃዱ የሚመላለስ አንድ ሰዉ ካገኘ ከእርሱ ጋር ነዉ አንድነት የሚፈጥረዉ እንጂ እንደ ሰይጣናት በዓመፃቸዉና በክህደታቸዉ ከጸኑት 999999(ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ) ሰዉ ጋር በእዉነተኛ ንስሐ እስካልተመለሱ ድረስ አንዳች አንድነት የለዉም:: ለሰማያዊ መንግሥቱም አያበቃቸዉም:: ከሰይጣናት የሚለዩት በግዙፉ ሥጋ ተገልጸዉ ስለሚመላለሱና የመዳን እድል ተሰጧቸዉ «አንፈልግም» በማለት ነገረ መስቀሉን በማቃለላቸዉ በፍርድ ቀን ከሰይጣናት በላይ የባሰ ቅጣት ስለሚጠብቃቸዉ ብቻ ነዉ:: ደረጃቸዉም ከርኩሳኑ መናፍስ አይለይም:: በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሱና እዉነትን ካልተቀበሉ በስተቀር «ርኩሳን ነፍሳት» የሚል ነዉ መጠሪያቸዉ::

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ በአሁን ሰዓት በአንዳንድ ሕዋ ሰሌዳ(ድረ ገጾቻችሁ) እንኳን መንፈሳዊ አገልጋይና ምእመን ቀርቶ ዓለማዉያን እንኳ የማይጽፉትንና የማያደርጉትን በመመልከቴና በማንበቤ ነዉ:: የዛሬ ሠላሳ ሰባት ዓመት ገደማ ራሱን በርእዮተ ዓለም አራማጅ መስሎ በኢትዮጵያዉያን ሕሊና የነገሠዉ ዲያብሎስ (ሰይጣናት) አሁን ደግሞ ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተቆርቋሪ በመምሰል ነዉ በትዉልዱ ሕሊና የነገሠዉና ከእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድና መስመር እያወጣ ለሞት ሞት በማዘጋጀት ላይ የሚገኘዉ:: ያኔ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ አድርጎ እርስ በእርስ እንዳጨራረሰና ደም እንዳስፈሰሰ ሁሉ አሁንም ጥላቻችንና በቀልን እየዘራ ደም ለማፋሰስና ለጥፋት እያሰለፈ ይገኛል:: ለዚህ ጥፋት የእሱ መሳሪያ በመሆን እያገለገልን ያለነዉ ደግሞ እኛ የስም አገልጋይና ምእመን የተባልን ነን እንጂ እዉነተኛ አገልጋዮችና ምእመናን ስለ እዉነት ከመመስከርና ለእዉነት ከመቆም እንዲሁም ከመጸለይና ከማንባት አልተለዩም::

እዉነትን የምንፈልግና ስለ እግዚብሔር መንግሥት የምንቀና፣ የምንመሰክር ሰዎች! እንግዲህ በሥጋና ደም ስሜት ተመርተን የምንሰራዉን፣ የምንናገረዉን፣ እንዲሁም የምንጽፈዉን እርግፍ አድርገን ትተን ሕሊናችን በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዲመራ እናድርግ:: ያኔ ምን መስራት፣ መጻፍ፣ እንዲሁም መናገርና ማሰብ እንዳለብን በሕሊናችን ሰሌዳ ላይ ያኖርልናል:: ነገር ግን በራሳችን እዉቀትና ሐሳብ ከተጓዝን እኛም ተሰናክለን ሌላዉንም በማሰናከላችን እጅግ የከፋዉን ቅጣት በምድርም በሰማይም መቀበላችን እንደማይቀር የታወቀ ነዉ:: እግዚአብሔር የንስሐ እድሜ በመስጠቱና በመታገሱ ምንም እንደማይመለከት አድርገን የምንቆጥር ሰዎች ካለን ደግሞ ታግሶ ታግሶ አይቀጡ አቀጣጥ ቀቶን ዳግም የንስሐ እድል ወደ ሌለበት ሲኦል እንደሚያስገባን ልናዉቅ ይገባል::

እግዚአብሔር እንደ እኛ ሰዎች የቁጥር ብዛትን ሳይሆን የሚመለከተዉ በእዉነትና በቅንነት እንዲሁም በትህትናና በፍቅር፣ በቆራጥነት የሚመላለሰዉን ሰዉ ነዉ::ለዚህም ነዉ በአባታችን ጻድቁ ኖኅ ዘመን በዓለም ላይ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ:: ነገር ግን እነዚያ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጡና እንደማንኛዉ ሕያዉ ፍጥረት የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ሕሊና ቢኖራቸዉም ሕሊናቸዉን አሳልፈዉ የሰጡት ለመንፈስ ቅዱስ (እግዚአብሔር) ሳይሆን ለተቃራኒዉ መንፈስ ለርኩስ መንፈስ(ለሰይጣናት) ነበርና የዓመፅ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉ እጅግ ስለበዛ ሙሉ ነጻነታቸዉ ወደሚገደብበት ሲኦል በዉኃ ጥፋት መቅሰፍት ነዉ የተጠሩት:: በተቃራኒዉ

ደግሞ ማንም ሳይስገድዳቸዉ ነጻ የሕሊና ፈቃዳቸዉን በመጠቀም በእዉነት፣ በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በጽናት፣ በትዕግስት ሕይወት የተመላለሱት ጻድቁ ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ተርፈዉ ዘራቸዉን ማስቀጠል የቻሉት:: አሁንም ታዲያ ያኔ የነበረዉ አምላክ ነዉ ያለዉና የዓመፃ ጽዋችን ሞልቶ እየፈሰሰ ስለሆነ የዓመፃ ዋጋችንን በምድርም ተቀብለን ሙሉ ነጻነታችን ወደሚገደብበት ቦታ በእግዚአብሔር ቁጣ ተጠርተን መሄዳችን አይቀርም::የሚያሳዝነዉ ደግሞ በእኛ ላይ ፍርዱ እጅግ ይብሳል:: ምክንያቱም ስለ ነገረ መስቀሉ እየሰማንና እንዲሁም እንመሰክራለን እያልን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ተግባር ስለምንፈጽም ነዉ::

እግዚአብሔር በፍርዱ አንዳች አድሎ አያደርግም፤ ፍትሐዊ ፍርድ ነዉ የሚፈርደዉ:: በዚህ ምድር ዉስጥ በጉስቁልና ባሕርይ እንዲቀጡ የተፈረደባቸዉ እልፈ አእላፋት (በብዙ ቢሊዮን) የሚቆጠሩ ሰይጣናት በአንድ ጊዜ ጥፋታቸዉ ነዉ ለዚህ ሕይወት የተዳረጉት:: እንዲሁም ከመጸጸትና ንስሐ ከመግባት ይልቅ በዓመፃ ላይ ዓመፃ በመፈጸም በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን በመፈተን በኋላም እኛ ዘሮቻቸዉን በመፈታተን ላይ በመሰማራታቸዉ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ነጻነታቸዉ ተገድቦ በአንድ ቦታ የሚቀጡበት የገሃነመ እሳት ፍርድ ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: በሌላ በኩል ደግሞ አዳምና ሔዋን በአንድ ጊዜ ስህተታቸዉ፣ ያደፈና የጎደፈ፣ ጉስቍልና ባሕርይ ከማይከሰትበትና እንዲሁም ጉስቁልና ኑሮና ሕይወት አንዳች ከማይታይባት ገነት ተባረዉ በዚህች ለሰይጣናት መቀጫ በተዘጋጀች ምድር ዉስጥ እንዲገቡና ከላይ የተገለጹት በሃያ አራት ሰዓት ዉስጥ ከእኛ ሕይወት ለማይለዩት ላደፉና ለጎሰቆሉ ባሕርያትና ኑሮ የተዳረግነዉ:: ታዲያ እነሱ እንደ ሰይጣናት በዓመፃ ላይ ዓመፃ ከመጨመር ይልቅ ራሳቸዉን ለእዉነተኛ ንስሐ በማብቃታቸዉና እኛም ዘሮቻቸዉ ባልፈጸምነዉ ዓመፃ ምክንያት በእነሱ ላይ የጸናዉ ፍርድ በእኛ በዘሮቻቸዉ ላይ ጭምር በመጽናቱ ምክንያት እርሱ ርኅሩኅ አባታችንና ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ከእመቤታችን ከአደራ እናታችን ቅድስተ ቅዱሳን ንጽህይተ ንጹሃን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ከሕሊናችን በላይ የሆነዉን ፍቅር አሳይቶንና የተለያዩ መከራዎችን ተቀብሎ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚከተለዉና ነጻነታችን ሙሉ በሙሉ ተገድቦ እንደ ዓመፃችን ከምንቀጣበት ከሲኦል ፍርድ ነጻ አዉጥቶን ወደ ቀደመ ግዛታችን ገነት በኋላም ጥንት ለተፈጠርንበት ዓላማ እልፍ አእላፋት ወትእልፊት (የትሪሊዮን ትሪሊዮን) ቅዱሳን መላእክት በሚኖሩበት ሰማያት ዉስጥ እንድንገባና ሕያዉ ሆነን እንድንኖር እድሉን የሰጠን::

የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ደግሞ ይህን እድል መጠቀም አንፈልግም ብለን ከሥጋ ሞት በኋላ ከምንኖረዉ ዘመን አንጻር የዓይን ቅጽበት እድሜ በማትሞላዉ ዘመን ትልቋ እስር ቤት በሆነችዉ በምንጠራበት፣ በምንኑጥርበት፣ በምንነጣበትና በምንቀጣበት ምድር ዉስጥ እንኳ በአግባቡ መኖር ተስኖን እርስ በእርስ እየተጣላንና እየተጠላለፍን እንኖራለን፤ ሕይወት በሆነዉ በእግዚአብሔር ቃል  ሆነን ከመገኘት ይልቅ ለራሳችን ሞት በሆነ የሥጋና ደም ሕይወት እንመላለሳለን:: የራሳችን የዓመፃና የክህደት ሕይወት አልበቃ ብሎን ደግሞ የዋሃን ምስኪን የሆኑትን ምእመናንን እናሰናክላለን:: ታዲያ በዚህ ስራችን በትልቋ እስር ቤት ምድር ዉስጥ ሆነ ሙሉ በሙሉ ነጻነታችን በሚገደብበት በሲኦል እንዲሁም የመጨረሻ ዋጋ በመንከፍልበትና እንደ ዓመፃችንና ክህደታችን እንዲሁም ርኩሰት ተግባራችንና ንግግራችን፣ ጽሑፋችን፣ ሐሳባችን ጭመር ፍዳችንን በምንቀበልበት ገሃነመ እሳት እንደምንቀጣ፤ ልክ እንደምንገባ፣ እንደምንብገነገን፣ እንደምንሰቃይ ሁላችንም ልናስተዉል ይገባል::

የዚህች ምድራዊ ዘመን እድሜያችን እጅግ እጅግ አነስተኛ ዘመን ስለሆነ የተለያዩ ፈተናና መከራ ቢያጋጥሙን እንኳ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚገጥመን መልካም ሕይወት አንጻር አንዲት መርፌ

ለቅጽበት የወጋችን ያህል እንኳ ሊሰማን አይገባም:: ምናልባት እንደ ሥጋ ለባሽነታችን ልናዝን፣ ስሜታችን ሊጎዳ ቢችልም፤ ማየት ያለብን እንደ ቅዱሳን መላእክት ንጹህ የሆኑት ሕፃናት እንኳ ሳይቀር በዚያ ክፉ ጠላት ዲያብሎስ(ሰይጣናት) እየተፈተኑ ያለቅሳሉ፤ ይታመማሉ:: በዚህም ወላጆች ሲረበሹና ሲታወኩ ጠላት ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ይደሰታል:: ታዲያ እኛ አዋቂዎች ከተግባር፣ ከንግግር፣ ከሐሳብ ኃጢአት የማንለይ ሰዎችማ ሌት ተቀን ፈቃዳቸዉን ለምንፈጽምላቸዉ ሰይጣናት ብንፈተንና ብንቀጠቀጥ አያንስንምን?! እጅግ ያንሰናል፤ ምክንያቱም ሌት ተቀን ለሚቀጠቅጠን ለጠላታችን ፈቃድ ነዉና የምንሰራዉና ፈቃዱን የምንፈጽመዉ:: ለሕሊናችን ግን መልካም እንደሰራን ነዉ የምናሳምነዉ:: እግዚአብሔር ደግሞ በዚህች የቅጽበት እድሜያችን ነጻ ፈቃድ ሰለሰጠን ይኸዉም በእዉነትና በመንፈስ እንድናመልከዉና እንደ ቃሉ ሆነን እንድንገኝ በመጨረሻም መንግሥቱን ሊያወርሰን፤ በተቃራኒዉ የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ፈቃደኞች ካልሆን ደግሞ በነጻ ፈቃዳችን ተመርተን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን ተመላልሰን ፈቃዱን ከምንፈጽምለት ዲያብሎስ ጋር በመጀመሪያ በሲኦል በመጨረሻም በገሃነመ እሳት እንድንኖር ነዉ:: እግዚአብሔር፤ በዚህች የዓይን ቅጽበት እድሜያችን በምድርም ሆነ በሰማይ ዋጋ እንደምንከፍልበት ወይንም እንደምንቀበልበት አዉቀን በፈለግነዉ የሕይወት አቅጣጫ እንድንጓዝ ሙሉ ነጻነትን ሰቶናል::

ደግሞ የዚህች ምድር ሕይወት እዉነተኛ ሕይወት እንዳልሆነ በሚገባ ልናስተዉል ይገባል:: ምክንያቱም ለጊዜዉ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕሪያችንንና ጎስቋላ ኑሮና ሕይወታችንን ማስታወሱን ልተወዉና የአዳም ዘር ሁሉ ከሕፃናት እስከ አ ዋዎች፣ ከቅዱሳን እስከ ዓመፀኞች፣ ከታላላቆች እስከ ታናናሾች፣ ከብርቱዎች እስከ ደካሞች፣ ከእዉነተኞች እስከ ሐሰተኞች፣ ከባለጠጎች እስከ ድሆች ድረስ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ከነፍሳቸዉ(ከሕይወታቸዉ) እግዚአብሔር ለዓይን ቅጽበት እንኳ እንደማይለይና የሰራነዉን፣ የተናገርነዉን፣ ያሰብነዉን ሳይቀር በባሕርይዉ መዝገብ ላይ እንደሚያሰፍረዉ ሁሉ፤ በዚህ ምድር ዉስጥ ያሉት በብዙ ትእልፊት (ቢሊዮን) የሚቆጠሩት ረቂቃን ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ከእያንዳንዱ ሰዉ ለመፈታተንና ለማቆሳቆል ለዓይን ቅጽበት እንኳ እንደማይለዩ እንድታስተዉሉና ዋንኛ ጠላቶቻችሁ እነሱ እንደሆኑ እንድትረዱ እንዲሁም ማንነታቸዉን በግልጽ እንድታዉቁ ያህል ብቻ መገለጫዎቻቸዉን እንደሚከተለዉ አቀርበላሁ:: ይህች ምድር የእነርሱ የመጀመሪያ መኖሪያቸዉ ስለሆነች እኛ ከገነት ተሰደን የመጣንባት በመሆኑ በረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጸዉ ስለሚኖሩ ወደ ማንኛዉም አካላችን ሊገቡና ሊወጡ ይችላሉ:: ሊጎዱና ሊያድሩ የሚችሉት እኛ ፈቃዳቸዉን ከፈጸምንና የእነርሱ ባሪያ ከሆን ብቻ ነዉ:: በተቀረ እግዚአብሔር ሳይፈቅድላቸዉ በእዉነተኞቹ አገልጋዮችና ምእመን ላይ ሊያድሩ ሆነ ሊጎዱ አይችሉም:: ሁሉንም ግን መፈታተን ይችላሉ:: በፈተናቸዉ መዉደቅ አለመዉቀድ ደግሞ የእያንዳንዱ ሰዉ ነጻ ፈቃድ ነዉ:: ይኸዉም እግዚአብሔርን መምሰል ጸጋ የተሰጣትና እንደ ቅዱሳን መላእክት ሕያዉ የሆነች ነፍስ የማመዛዘንና የማገናዘብ ብቃት ያላት ስለሆነ ራሷን ለእግዚአብሔር ወይንም ለሰይጣናት ፈቃድ ማስለፍ ትችላለች:: ነገር ግን ዋጋ የምታገኘዉ ወይን የምትከፍለዉ እንደ ምርጫዋና ስራዋ ነዉ እንጂ እንደምኞቷና ፍላጎቷ አይደለም::

ታዲያ እነዚህ ረቂቅ ሰይጣናት ሰዉ ሳይለዩና ሳይመርጡ በአዳም ዘር ሁሉ አካል ዉስጥ ከአየር፣ ከመብል፣ ከመጠጥ፣ ከሽታ፣ እንዲሁም ብቻቸዉን ይገባሉ፤ ይወጣሉ:: ከግንባራችን ፊት ለፊት አንጎላችን ዉስጥ በአካል ደረጃ ያለችሁንና ከእርሷ በሚወጣ ኃይል ለተገለጽንበት ሥጋ ሕይወትን እየሰጠች ተዋሕዳ ያለችዉን ሕያዉ ነፍስ ለመፈታተን ወደ ሕሊናችን የሚገቡት ሰይጣናት ከሕሊናችን በተለያየ ምክንያት ሲወጡ በአፋችን በኩል በማስፋሸክ ነዉ፤ በአፍንጫችን በኩል ደግሞ በማስነጠስ ነዉ፤በቆዳችን በኩል ደግሞ በማሳከክ ነዉ፤ በመገጣጠሚያችን ደግሞ በማንጠራራት ነዉ፤

በመተንፈሻ አካላችን ዉስጥ የሚገቡት ደግሞ በአፋችን በኩል በማሳል ይወጣሉ፤ በሆዳችን ዉስጥ የሚገቡት ደግሞ በግሳትና በፈስ መልክ ይወጣሉ:: ታዲያ ይህ ምድራዊ ሕይወታችን ሕይወት ሆነና ነዉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዉጭ በመመላለስ ሌት ተቀን ሰይጣናትን ለማስደሰትና ፈቃዳቸዉን ለመፈጸም የምንተጋዉ?!

እነዚህን ጨካኞች የአዳም ዘር ጠላቶችን ሰይጣናትን ለማስደሰት ነዉ በእግዚአብሔር ስምና ቃል የምንነግደዉ?! እንደዉ ሌላዉን ልተወዉና ደካማነታችንና ተራነታችንን የሚገልጹትን ፈተናዎች በአጭሩ ልግለጽ:: ይኸዉም ነፍሳችን በባሕርይዋ የማታንቀላፋ ሕያዉ ፍጥረት ናት:: ነገር ግን ይህን ደካማ ሥጋ ለብሰን ስለተገለጽን ሰይጣናት ራሳቸዉን ከጉስቁልናና ስቃይ ለማሳረፍ በምሽት ሆነ በቀንም በእንቅልፍ ያሸንፉናል፤ በተቃራኒዉ ደግሞ እኛን ለመረበሽና እረፍት ለመንሳት እንቅልፍ እንዳይወስደን በማድረግ ያዉኩናል:: ታዲያ በራሳችን ስልጣን እንቅልፍ እንዳይወስደንና እንዲወስደን ማድረግ ይቻለናልን? አይቻለንም:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቸርነትና ጠብቆት ስላልተለየን ነዉ ይህንን ጎስቋላ ምድራዊ ዘመናችንን በእንቅልፍ (በእረፍት) ጭምር እንድናሳልፈዉ ፈቃዱ ስለሆነ ብቻ በሰይጣናት ርኩስ መንፈስ ኃይል ተሸንፈን እንድናቀላፋ የፈቀደዉና ማለዳ ላይ ደግሞ ኃይልን አጎናጽፎን እንድንነቃ በማድረግ ምድራዊ ዘመናችንን እንድንገፋ ያደረገዉና በዚህ አጋጣሚ ሰይጣናትን ከጉስቁልና ስቃያቸዉ እንዲያርፉ ፈቃዱ የሆነዉ:: ምክንያቱም እነሱም እንደኛዉ ሕያዉ ፍጥረታቱ ናቸዉና:: ታዲያ እግዚአብሔር፤ ሰይጣናት እኛን ለማወክ እንቅልፍ በሚነሱን ጊዜ ደግሞ ሙሉ ፍቃድ ሰቷቸዉ ለቀናት አይደለም ለአንድ ቀን እንቅልፍ ብናጣ ደግሞ የነፍሳችን ኃይል ምን ያህል እንደሚደክምና የሕሊና እረፍት እንደምናጣ በሚገባ ይታወቃል:: እንዲሁም ሙሉ የማሸነፍ ኃይል ቢሰጣቸዉ ደግሞ ቀንም ሌሊትም በእንቅልፍ ይጥሉን ፣ያፈዙን ነበር:: ነገር ግን የእነሱ ሆነ የእኛ ኃይል የተገደበ ነዉ:: ስለዚህ አቅማችንንና ተራነታችንን እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የምንመላለስ ከሆነ ደግሞ ታላቅነታችንንና ከሕሊናችን በላይ የሆነ ሕይወት እንደሚጠብቀን ልናስተዉል ይገባል::

ከላይ አድራሻችሁ በቀጥታ የተገለጸዉ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት፣ ስለ ክርስትና እንመሰክራለን፣ እንቆረቆራለን በማለት የተለያዩ ጽሑፎችና መልእክታትን በሕዋ ሰሌዳ(በድረ ገጻችሁ) ታቀርባላችሁ:: የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ደግሞ አንዳንዶቻችሁ ከሃዲያንና መናፍቃን እንኳ የማይሉትንና የማይጽፉትን ሃይማኖቷንና ቅድስ ቤተክርስቲያንን የሚያጥላላ ጽሑፍ ነዉ የምታወጡት:: ብቸኛ የሕይወት መንገድ የሆነችዉን የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ምእመናን ሆኑ አገልጋዮች እንዲጠራጠሯት በማድረግ ነዉ በጽሑፎቻችሁ ትችት የምታቀርቡት:: አንድፌቱኑ ከሃዲና መናፍቅ ሆናችሁ ብታድርጉት ከእግዚአብሔር እዉነተኛ ፍርድ ባታመልጡም ፍርዱ ግን ይቀልላችሁ ነበር:: ምክንያቱም ለሃይማኖቱ ቀናዒ የሆነዉን ምእመን ለማሰናከል በቤተክርስቲያኗ ስም አልነገዳችሁበትምና:: አሁን የሚታየዉ ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስምና በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም ነዉ የምትነግዱትና የዋሃን ምእመናንን እያሳሳታችሁና እያሰናከላችሁ ያላችሁት::

ስለዚህ እዉነተኞች ለሃይማኖታችንንና ለቅድስት ቤተክርስቲያናችን ተቆርቋሪ ከሆን በመጀመሪያ ደረጃ የራሳችንን ሕይወት መርምረን ለንስሐና ለቅዱስ ቁርባን እናብቃ:: ከዚያ ያ መለኮት የተዋሐደዉ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሚያደርገን በእዉነትና በመንፈስ እናገለግላለን፤ እናመልካለን:: ከዚህ ዉጭ በሆነ ሕይወት ግን እንደ አስተሳሰባችንና አቋማችን ደረጃ ሰይጣናት፤ ሕሊናችን በሚቀበለዉ መልክ በሕሊናችን እየነገሡ ፈቃዳቸዉን ያስፈጽሙናል እንጂ ከእግዚአብሔር

የሆነዉን አዉቀንና አስተዉለን አንፈጽምም። እንኳን በመንፈሳዊዉ ዓለም ቀርቶ በዓለማዊዉ እንኳ ሰዎች ሕሊናቸዉን አሳምነዉ ነዉ የራሳቸዉን የዉሸት እዉነት ፈጥረዉ ለግፍ፣ ለጭከና፣ ለበቀል፣ ለርኩሰት፣ ለዓመፃ፣ ለክህደት፣ ባጠቃላይ ለተለያየ ኃጢአት ተግባርና ንግግር እንዲሁም ጽሑፍና ሐሳብ ራሳቸዉን የሚያስልፉት።

በአሁን ሰዓት በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት «የሕዝብና የምእመናን አገልጋይ ነን» የሚሉት ሰዎች በራሳቸዉ የዉሸት እዉነት ሕሊናቸዉን አሳምነዉ በእግዚአብሔር እዉነትና በቅዱሱ ኪዳን ላይ ዓመፅ፣ ክህደት፣ የአምልኮ ምንዝርና በመፈጸም በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛ ሉ። ለዚህም ነዉ ሕዝቡ ሆነ ምእመናን እርስ በእርስ በመከፋፈልና በመጠላላት ሲመላለሱ እንደ ታላቅ ስኬት የሚቆጥሩትና በመከፋፈልና በማጣላት ሂደት ዉስጥ ተሰላፊ የሚሆኑት። ምክንያቱም ሕዝቡ ሆነ ምእመኑ ከእዉነት ጋር ቆመዉ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንደ ቃል ተናጋሪ ከሆኑ የጨለማዉ ስራቸዉ ስለሚገለጽባቸዉና ቦታዉን ብርሃን ስለሚተካዉ ለጨለማ ስራቸዉ ሽፋን መስጠት ሆነ ማስተባበል ስለማይቻላቸዉ ነዉ። ለዚህም ነዉ መንግሥታት ሆኑ የሃይማኖት መሪ ነን የሚሉት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ የዲያብሎስን ፈቃድ ስለሚፈጽሙ አንዱን በአንዱ ላይ እያነሳሱና እየከፋፈሉ የሥልጣን እድሜያቸዉን ለማስረዘም ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ የሚያደርጉት። ያላስተዋሉት ነገር ቢኖር ቀናቸዉ ሲደርስ እንኳን ከንቱ የሆነዉ ሥጋዊ መጠበባቸዉ አይደለም መከላከያቸዉና ኃይላቸዉ አንዳች አይታደጋቸዉም፤ የቀናት እድሜ እንኳ አይጨምሩላቸዉም። በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሱና እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡ በስተቀር ዋጋ ከፍለዉበት አይቀጡ አቀጣጥ ተቀተዉ ሙሉ ነጻነታቸዉ ተግድቦ እንደ ዓመፃ ደረጃቸዉ ወደሚቀጡበት ሲኦል ነዉ የሚገቡት። እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ እዉነተኞችና ቅኖች አገልጋዮች ቢኖሩም፤ ዞሮ ዞሮ ከዓመፅ ተባባሪነት ራሳቸዉን እስካላገለሉና የዓመፅና የክህደት፣ እንዲሁም የርኩሰት ተግባር ፈጻሚዎችን እስካልተቃወሙና ድርጊቱንም እስካላወገዙ ድረስ እንደ ዓለማዉያኑ «ተመሳስለህ ኑር» የሚለዉን የዲያብሎስ ሽንገላ ተቀብለዋልና የእዉነት መስካሪዎች የነብያት፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን መንገድን አለመከተላቸዉ ሕይወታቸዉና አቋማቸዉ ይመሰክርባቸዋል። የሥጋ ፈቃዳቸዉ አሸንፏቸዉ ለጊዚያዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ብልጽግና፣ ዝና ሲሉ ሕሊናቸዉን ሸጠዋልና በእዉነተኛ ንስሐ ካልታደሱ በስተቀር በእግዚአብሔር ዘንድ ቀለዉ የተገኙ ናቸዉ።

አሁን በኢትዮጵያ ያለዉ መንግሥት ክፉ ትንቢት ለመፈጸም ወደ ወንበር የመጣ ነዉ እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም አይደለም። የክፉ ትንቢት ለመፈጸም በወንበሩ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሰዎች ደግሞ የተመረጡት በነጻ ሕሊናቸዉ ገና በልጅነት፣ በወጣትነትና በጎልማሳነት ዘመናቸዉ ባሳዩት የትዕቢት፣ የክፋት፣ የዓመፅ፣ የክህደተ፣ የርኩሰት፣ የጭከና፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት፣ ባጠቃላይ የጨለማ ጸጋ ብቃት አማካይነትና እንዲሁም አእምሮ ቀላልና አእምሮ ሕፃን ሆነዉ በመገኘታቸዉ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር ወስኖባቸዉ አይደለም። በዚህም ምክንያት ዲያብሎስ ለዓለማዊ መንግሥቱ አጭቷቸዉና ቀብቷቸዉ ይኸዉ በአራቱም ማእዘን እንደሌሎች መንግሥታት ፈቃዱን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙለት ይታያል። ታዲያ አሁን ዘመናቸዉ ወደ መደምደሙ ደረጃ ላይ የደረሰ ስለሆነ የዘሩትን ፍሬ መራራ ቢሆንም ከነግብረ አበሮቻቸዉ ጭምር አጭደዉና ጠጥተዉ ማለፋቸዉ አይቀርም። ከነዚህ ከምድር ከሚጸዱ የዓመፅ ልጆች ጋር አንዳች አንድነትና ኅብረት ባይኖራች ለራሳችሁ የሚበጅ ነዉ። «አይ እኛ አንድነታችንና ኅብረታችን፣ ታማኝነታችን ከእነሱ ጋር ነዉ» የምትሉ ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔር በነጻነት የሚገዛና ለእያንዳንዱ እንደምርጫዉና ፍላጎት ዋጋ

የሚከፍልና የሚያስከፍል እዉነተኛ ፈራጅ አምላክ ነዉና የምርጫችሁን እንደምታገኙ አንዳች ጥርጥር የለዉም::

እግዚአብሔርን ያሉትና የሚሉ ደግሞ ገና በልጅነታቸዉ፣ በወጣትነታቸዉ፣ በጉልምስናቸዉ በራሳቸዉ ነጻ ፍቃድ ሕሊናቸዉን በቅንነት፣ በእዉነተኛነተ፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በቆራጥነት፣ በርኅራኄ፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በእዉነተኛ ንስሐ በመምራታቸዉ ምክንያት እጅግ በቅርቡ በኢትዮጵያ በሚዘረጋዉ ሰማያዊ ሥርዓት ዉስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚበቁ የኢትዮጵያን ትንሣኤ የሚመለከቱ ናቸዉ:: ታዲያ ምርጫችንን መልካሙን ዘመን ለማየትና በምድርም ተባርከን በእዉነተኛዉ የእግዚአብሔር መንግሥት ለሕያዉነት ዘመን ለመብቃት ከፈለግን ደግሞ እንደምርጫችንና ፍላጎታችን እግዚአብሔር ስለሚያበቃን አንድነታችንንና ኅብረታችንን ከእርሱና ከእርሱ ፈቃድ ጋር ብቻ እናድርግ:: በአሁን ሰዓት በሥጋዊዉና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት መሪዎችና ግብረ አበሮቻቸዉ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በአግባቡ መጠበቅ ባለመቻላቸዉና የዓመፅ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎች ሆነዉ ስለተገኙ በእግዚአብሔር እንደተተፉና የሚቀራቸዉም እንደ ንጉሥ ሳኦልና ግበረ አበሮቹ እንዲሁም እንደ ካህኑ ዔሊና ልጆቹ ዋጋ መክፈልና ቦታዉን ደግሞ እግዚአብሔር ለእዉነተኛ አገልግሎትና ጥበቃ ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ለእንደራሴዎቹ እንደ ዳዊት ለካህኑ ለርእሰ ነገሥትና እንደ ሳሙኤል ለርእሰ ሊቃነ ካህናት ለእጨጌዉ ለተመረጡት ወንበሩን መልቀቅ ብቻ ነዉ:: እነዚህ እንደራሴዎች በዋሻ ወይንም በገዳም ወይንም በስዉር ቦታ ተሰዉረዉ ያሉ እንዳይመስሏችሁ:: እያንዳንዱን የዓለምን ሆነ የኢትዮጵያን እንቅስቃሴ የሚከታተሉ፤ እየተሰራ፣ እየተነገረ፣ እየተጻፈ ያለዉን የሚመለከቱና የሚያዳምጡ ናቸዉ:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም ለማስፈጸም የተዘጋጁ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ አድሮ እዉነተኛ ፍርድ የሚሰጥባቸዉ የተመረጡ ባለሟሎቹ ናቸዉ እንጂ የሥጋና የደም ሐሳባችንን ሆነ ተግባራችንን እንደ ዲያብሎስ እንደራሴዎች የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ አይደሉም::

በመሆኑም ስለ እዉነት የምንመሰክርና ለአንዲት ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ምስክርነት ከቆምን እንደ ሥጋና ደም ስሜታችን እንዲሁም እንደ ሥጋዊና መንፈሳዊ እዉቀታችን ብቻ መመራት አቁመን ሕሊናችን መንፈስ ቅዱስ እንዲመራዉ ፈቅደንለት በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እናገልግል:: እዚህ ላይ አንዳንድ እዉነታዎችን ለመግለጽ እወዳለሁ፤ በእግዚአብሔር ለእንደራሴነት የተመረጡትና የተቀቡት ሆኑ ሌሎች በእነሱ ስር ሆነዉ ለእዉነተኛ አገልግሎት የሚሰለፉ ሁሉ ዋና ተግባራቸዉ ለአዳምና ሔዋን ዘሮች በሙሉ የተሰጠዉን ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናትን መጠበቅና ማስጠበቅ እንዲሁም ኢትዮጵያን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እንደ እግዚአብሔር መንግሥትነቷ ማጽናት ነዉ:: እነዚህ ቅዱሳት ኪዳናት ከተጠበቁ በምድራዊ ሕይወታችን ዘመን የሚያጋጥሙን ችግሮችና ፈተናዎች መፍትሔ ይገኝላቸዋል:: «አይ እነዚህ ኪዳናትን አንጠብቅም» ብለን በዓመፃችን ከጸናን ደግሞ የዓመፃ ልጆች ነንና ከሌሎች ከዓመፃ ልጆች ጋር በእግዚአብሔር ቁጣ ስለምንጠረግ የኢትዮጵያን ትንሣኤ አንመለከትም::

ሌላዉ ደግሞ ሕይወታችንን በትዕቢትና በዓመፅ የምንመራ ከሆነ በየትኛዉም አገልግሎት ዉስጥ እንሰለፍ ምድባችን ከረቂቃኑ ከትዕቢተኞቹና ከዓመፀኞቹ ሰይጣናት ጋርና እንዲሁም ከሥጋ ለባሾቹ ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ ጨካኝና ግፈኛ መሪዎች... ወዘተ ጋር ነዉ:: ምክንያቱም በእነሱ ወንበር ላይ የመቀመጥ አጋጣሚ ብናገኝ ከእነሱ ባልተለየ መልኩ ቢበዛ ሥጋዊ መጠበብና ብልጣብልጥነት የሚታይበትን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰትና የጭከና ተግባር መፈጸማችን አይቀርምና:: ምናልባት ጥሩ የመናገር አንደበት ሊኖረን ይችላል ወይንም ጥሩ ድምፅ ሊኖረን ይችላላ

ወይንም የተለየ እዉቀትና ችሎታ ሊኖረን ይችላል፤ ነገር ግን ራሳችንን ከትዕቢትና ከዓመፃ ለይተን እንደ እግዚአብሔር ቃል ካልኖር ለሰማያዊ ሕይወት አንዳች አያበቃንም።ነገር ግን ለምድራዊ ሕይወታችን ለገቢ ማግኛና ለዝና እንዲሁም ለተለየ ወንበር ልንበቃበት እንችላለን። ይህ ግን ለቅርፊት ሥጋችን ቢጠቀመን እንጂ ለሕያዉ ነፍሳችን አንዳች ጥቅም የለዉም። በምድራዊ ዘመናችን በስራችን፣ በኑሯችን ከሰይጣናት የባሱ ሰዎች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። ምክንያቱም ሰይጣናትን በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በምጽዋት፣ በእግዚአብሔር ቃል፣ በንስሐ በሥጋና ደሙ ልናሸንፋቸዉና ልናርቃቸዉ እንችላለንና። ልበ ደንዳና የሆኑ ሰዎችን ግን እግዚአብሔር በአምላካዊ ስልጣኑ የደነደነዉን ልቦና አፈራርሶ የተሰበረ ለንስሐ የሚበቃ ልቦና ካልሰጣቸዉ በስተቀር በመከራና በስቃይ ዉስጥ እያሉ እንኳ ከትዕቢታቸዉና ከዓመፃቸዉ የማይለዩ፤ ትህትናና ፍቅር እንዲሁም ርኅራኄና ትዕግስት የማይታይባቸዉ ለዲያብሎስ እንደ ልቡ የሆኑለት በሕሊናቸዉ ነግሦ ፈቃዱን የሚያስፈጽማቸዉ ነዉ። ትዕቢተኛና ዓመፀኛ ሰዉ በምንም መልኩ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሊበቃ እንደማይችል በሚገባ ልናዉቅና ልናስተዉል ይገባል።

በመጨረሻ ለማለት የምፈልገዉ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም የከሃዲያንና የመናፍቃንን እንዲሁም የመንግሥትን የዓመፃና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ዓላማ ለማስፈጸምና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋ የተሰለፋችሁ ሁሉ! ዛሬ ነገ ሳትሉ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሳችሁ ከእዉነት ጋር ብቻ ተሰለፉ። እንደ ቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት እንዲሁም እንደማንነቷ ብቻ ተመላለሱ። በራሳችሁ ሥጋና ደም ስሜት ተመርታችሁ «ይህ ይለወጥ፤ ይህ ክህደት ነዉ፤ ይህ እንዲህ ነዉ» በማለት ቤተክርስቲያንና ሃማኖቷን ማጥላላታችሁን አቁሙ። ቤተክርስቲያን እዉነተኛ አገልጋይና ምእመን ነዉ ያጣችሁ እንጂ ከባዕዳን ሆነ ከከሃዲያን እንዲሁም ከመናፍቃን አንዳች የምትፈልገዉ ነገር የለም። ለዓለም የተትረፈረፈ መንፈሳዉ ጸጋና በረከት ሥርዓትና ሕይወት የሞላባት በቅዱሳን የምትጠበቅ በየገዳማቱ፣ በየዋሻዉ፣ በበረሃም፣ በከተማም፣ በገጠርም ሆነዉ የሚጸልዩና ስለ እዉነት የሚያነቡ ጻድቃን ያሉባት ስለሆነች ለሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ተግባር ባትፈጽሙና ለምድራዊ ሆነ ለሰማያዊ ፍርድ የሚመሰክርባችሁን ጽሑፍ ባትጽፉ ይበጃችኋል። ምክንያቱም እንኳን የምትሰሩት፣ የምትናገሩት፣ የምትጽፉት፣ የምታስቡት ሳይቀር በሰማያዊ በእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ ሰፍሮ ሰማያዊ ዋጋ ያስከፍላችኋልና። በተቃራኒዉ እዉነትና መልካም ከሆነ ደግሞ ዋጋ ታገኙበታላችሁ። በምድርም ቢሆን ስለ ሐሳባችሁ ዋጋ ለማስከፈል ወይንም ለመክፈል ብቃት ያለዉ ሰዉ ባይኖርም ከልባችሁ ሞልቶ ሲፈስ በተግባር፣ በንግግር፣ በጽሑፍ መግለጻችሁ አይቀርምና በእናንተ መዘዝ ለሚመጣ ጥፋትና ጥቃት ሁሉ እንደምትጠየቁበት ልታዉቁ ይገባችኋል።

በተረፈ እግዚአብሔር ሁላችንንንም ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅቶን ከመጪዉ የጥፋትና የጠረጋ ዘመን ጠብቆን ለኢትዮጵያ ትንሣኤና ለሰማያዊዉ መንግሥቱ ያብቃን ይላል ታናሹ ልጃችሁና ወንድማችሁ። በጸሎታችሁም አስቡኝ። ፈቃዳችሁ ከሆነ ደግሞ እናንተ ብትቀበሉትም ባትቀበሉትም ምእመናን ለእዉነተኛ ንስሐ እንዲበቁና በእምነታችዉ ጸንተዉ የኢትዮጵያን ትንሣኤ እንዲጠባበቁ በሕዋ ሰሌዳችሁ (በድረ ገጾቻችሁ) አንዳች ሳትቀንሱና ሳትጨምሩ አቅርቡልኝ። ማንኛዉ ሰዉ በአድራሻዬ አስተያየቱን ሊሰጠኝ ይችላል። teklekidan979@yahoo.com

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም

እግዚአብሔር ቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያን ይባርክ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ይጠብቅ
ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ

**<u>ግልባጭ</u>**

ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ለኢትዮጵያዊዉ ካህኑ እጨጌ

ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ለኢትዮጵያዊዉ ካህኑ ርእሰ ነገሥት

<u>ኢትዮጵያ</u>

በአንድነትና በሦስትነት ለሚመለከዉ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

## ምዕራፍ ሦስት

***ቀን ነሐሴ ፲፭÷፳፻፬ (15/12/2004) ዓ.ም***

### ይድረስ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ በሙሉ

በመጀመሪያ በአምላካችን በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ስም የከበረ ሰላምታዬን እያቀረብኩላችሁ ወደ ፍሬ ጉዳዬ እገባለሁ::ከታሕሳስ ፲፮÷፳፻፬ (16/04/2004) ዓ.ም. ጀምሮ የእግዚአብሔርን መልእክቶች በተለያየ ጊዜ ሳስተላልፍላችሁ መቆየቴና ከሰኔ ፳፭÷፳፻፬ (25/10/2004)ዓ.ም ጀምሮ ማቆሜ ይታወቃል::

ምንም እንኳን ትዉልዱ የእግዚአብሔርን መልእክት በመናቁና በማዳፈኑ በትዉልዱ ተስፋ ብቆርጥም አንድ ሁለት ነፍስ ማዳን እንደ ትልቅ ስኬት መቆጠሩን ስላስተዋልኩና አሁንም የወገኖቼ ኢትዮጵያዉያንና የአዳምና ሔዋን ዘር የሆኑት የዓለም ሕዝብ ጥፋት አላስቻለኝምና ተስፋ ባለመቁረጥ መልእክቴን አስተላልፋለሁ::

እኛ የእግዚአብሔር መልእክቶችን ባንቀበላቸዉ ምናለ ለሌላዉ ወገናችን ቢቀበለዉም ባይቀበለዉ ብናስተላልፍ?! ስንቱን የዓለምን ነገር እናራግብ የለም ወይ? ወይስ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ለማስተላለፍ ሕሊናችን ተናንቆን ይሆን? እኛ እዉቀታችን÷ ጥበባችን÷ ችሎታችን÷ ኃይላችን÷ ስልጣናችን÷ ሀብታችን ጣዖት ሆኖብን እግዚአብሔርን፤ ከእርሱ እዉቀት አንጻር ነጥብ በማትሞላዉ በራሳችን እዉቀት ገድበንና አንዳች ዋስትና በሌላቸዉ ነገሮች ተመክተን ራሳችንን ከማስታበይና ከማመጻደቅ መላቀቅ ካልቻልን፤ ምናለ ለወላጆቻንና ለቤተሰባችን እንዲሁም ለወገኖቻችን መልእክቶቹን አስተላልፈን ወደምንፈልገዉና ወደ ማይቀርልን ጥሪ ብንሄድ?

እኔ የሚያሳስበኝና የሚያሳዝነኝ ከዚህ ምድር በእግዚአብሔር ቁጣ መጠረጋችን አይደለም፤ ምክንያቱም ማንም በዚህች ምድር ዉስጥ ሕያዉ ሆኖ የሚኖር የለምና::ይልቁኑ አካሄዳቸዉን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉና ሕይወታቸዉን በንስሐ እየመረመሩ የሚኖሩ ሰዎች ከዚህች ጎስቋላ ምድር ተለይተዉ የሚሄዱበትን ጊዜ በናፍቆትና በጉጉት ይጠባበቁታል:: ምክንያቱም ለመጥራት÷ ለመንጠር÷ ለመንጣት÷ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ካልሆነ በስተቀር አንዳች የሚያጓጓ ነገር የለባትምና፤ እንዲሁም ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይ ረቂቅ አካል ተላብሰዉ በምድር የሚከሰቱት ያደፈ÷ የጎደፈ÷ የጎሰቆለ ባሕርይና ጎስቋላ ሕይወትና ኑሮ በማይታይባት ገነት ዉስጥ በእዉነተኛ ደስታና ቅድስና ስለሚኖሩና ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ በቅዱሳን መላእክት ሥርዓት በመንግሥተ ሰማያት ዉስጥ ሕያዉ ሆነዉ ስለሚኖሩ ነዉ:: እኔ የሚያሳስበኝና የሚያሳዝነኝ ግን ከዚህ ከምናመልከዉና ከምናስመልከዉ ቅርፊት ከሆነዉ ሥጋችን ስንለይ እግዚአብሔርን መምሰል የተላበሰች ሕያዉ ነፍሳችን ምርጫዋን ባለማስተካከሏ ምክንያት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) እንደ ሰይጣናት ተላብሳ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በድቅድቅ ጨለማ በሲኦል እንደ ዓመፃዋና ክህደቷ እንዲሁም ርኩሰት ደረጃዋ ፍዳዋን ስለምትቀበልና ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ለሕያዉነት ዘመን በማይጠፋዉ በረቂቁ እሳትና በማይሞቱት በረቂቃኑ ትሎች ዉስጥ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ፍዳዋን ስለምትቀበል፤ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖረን ዘመን አንጻር የዓይን ቅጽበት የማትሞላ ምድራዊ ዘመናችንን በሚገባ መኖር ተስኖን ለከፋዉ ቅጣት ራሳችንን ማዘጋጀታችን ነዉ::

እንግዲህ የእግዚአብሔርን መልእክቶች ራሴን ዝቅ አድርጌና ተንበርክኬ ከማቅረብ እንዲሁም ራሴን ከማዋረድ ሌላ በምን መልኩ ላቅርብ? እናንተስ በኔ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ? «ትዉልዱ የእግዚአብሔርን መልእክትና ቃለ ለመስማት ፈቃደኛ አይደለምና በእግዚአብሔር ቁጣ

የዓለም መንግሥታት፥ ባለስልጣናት፥ ካድሬዎች፥ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች እንዲሁም ሕዝቡ ይጠረጉ» ብላችሁ ትወስኑ ይሆን? እኔ ግን ይህን ለማለት አቅም አጣሁ፤ ለዚህም ነዉ እስቲ በእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ኖኅ ዘመን እንደነበሩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ከምድሪቱ ከመጠረጋቸዉና እንደ ሎጥ ዘመን በእሳት ዲን ከመደምሰሳቸዉ በፊት «በቃህ» እስከምባል ድረስ የማዳን ሙከራ ላድርግ በማለት ነዉ በድጋሜ የእግዚአብሔርን መልእክቶች ያቀረብኩላችሁ። ምን ዋጋ አለዉ! ከየሀገሪቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች በእግዚአብሔር ቁጣ ከተጠረጉና ከዓለም በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች ከተደመሰሱ በኋላ ብንጫጫ?! ምክንያቱም አሁንም በነጻ ሕሊናቸዉና ፈቃዳቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሆኑ ሌላዉ የዓለም ሕዝብ በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱና ራሳቸዉን በእግዚአብሔር ፊት ቢያዋርዱ እንዲሁም እዉነትን ቢቀበሉ እንደ ነነዌ ሰዎች በምሕረትና በይቅርታ እግዚአብሔር ይጎበኛቸዉ ነበርና።

በብሉይ ዘመን የእስራኤል ንጉሥ የነበረዉ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ብዙ ተግባሮችን ፈጽሟል። ነገር ግን ከዚህ ምድር በሥጋ ሞት መለየት ግድ ነዉና እግዚአብሔር በሥጋ ሞት ሊጠራዉ በወደደ ጊዜ በነብዩ ኢሳይያስ አማካይነት በሞት እንደሚጠራና ቤቱን እንዲያስተካክል መልእክት በተነገረዉ ጊዜ ምርር ብሎ በማልቀሱና በማዘኑ ምክንያት ርኅሩኅ ፈጣሪ አምላክ ወዲያዉ ነበር የሞት ዉሳኔዉን ሽሮ አስራ አምስት ዓመት እንደተጨመረለት በነብዩ ኢሳይያስ አማካይነት ያሳወቀዉ። ታዲያ ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር እንኳን በእዉነተኛ ንስሐ ለሚመለሱት ይቅርታን ማድረግ ቀርቶ የተቀረጠብን ዉሳኔ ካለ እንኳ በምሕረቱና በቸርነቱ እንደሚያሻሽልልንና እንደሚምረን ልናስተዉል ይገባል። እኛ ግን ንስሐ የመግባትና የመጸጸት ምልክት አናሳይም። በመሆኑም የዓመፃ፥ የክህደት፥ የርኩሰት ተግባራችን እጅግ ስለከፋ እጅግ የከፋዉ ጥፋት በላያችን ላይ እጅግ በቅርቡ(ቀኒቷና ጊዜዋ በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የምትታወቅ) ማምጣታችን አይቀርም። የሚሳዝነዉ ደግሞ ነፍስ ከሥጋችን ከተለየች በኋላ ዳግም የንስሐ እድልና አምላኳን በእዉነትና በመንፈስ የማምለክ ብቃት የላትም። እንደ ዓመፃ ደረጃዋ እንደ ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ፍዳዋን ትቀበላለች።

ስለ እምነት አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር የሚደሰትበት እምነት ለምሳሌ እልም ባለዉ ጠራራ ፀሐይ « እግዚአብሔር ዛሬ ኃይለኛ ዶፍ ዝናብ አዘንቦ ይህችን ከተማ ያጥለቀልቃል» በማለት እግዚአብሔር በመልእክተኞቹ ቢያናግር፤ በየዋህነትና በልባምነት፥ በቅንነትና በእዉነት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ መርምሮ «እግዚአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለም፤ እንኳን በሰዓታት ዉስጥ ቀርቶ በዓይን ቅጽበት ዉስጥ የፈለገዉን በፈለገዉ መንገድ ማድረግ ይችላል።» ብሎ በሚያምንና በሚቀበል ሕሊና እምነት ነዉ እንጂ በራሱ መጠበብና እዉቀት ገምግሞ የእግዚአብሔርን ስራ የሚገድበዉንና የሚያጣጥለዉን አይደለም። የእግዚአብሔር ድንቅ ተአምርና ስራ በግልጽ ሲታይ ከትዕቢት(ከፈርዖን ወንድምና እህቶች)፥ ከክፋት(ከይሁዳ ወንድምና እህቶች)፥ እንዲሁም ከዓመፃ(ከአርዮስ ወንድምና እህቶች) በስተቀር እንኳን እምነት አለኝ የሚለዉ አስመሳይ አማኝና አገልጋይ ቀርቶ እምነት የሌላቸዉ አረማዉያን ሆኑ በክህደትና በምንፍቅና እምነት ዉስጥ ያሉት ሰዎች ያምናሉ። ይህ እምነት ግን እግዚአብሔርን የሚያስደስተዉ አይደለም። ምክንያቱም ተመልሰዉ ወደ ክህደት፥ ዓመፃ፥ ርኩሰት ተግባራቸዉ ሊመለሱ ይችላሉና። እነ ትዕቢት፥ እነ ክፋት፥ እነ ዓመፃ ደግሞ ሕሊናቸዉን አሳልፈዉ የሰጡት ዲያብሎስ(ሰይጣናት) በሕይወታቸዉ ስለነገሡባቸዉ በየትኛ ዉም እምነት ዉስጥ ሆነ አገልግሎት ዉስጥ ይሰለፉ ሕሊናቸዉ እንደደነደነ ይጸናሉ እንጂ የንስሐ ሕሊና የላቸዉም። ደረጃቸዉም እንደ ርኩሳን መናፍስት(ሰይጣናት) ነዉ። መጨረሻቸዉም እንደ ፈርኦን እንደ ይሁዳ እንደ አርዮስ በእግዚአብሔር ቁጣ በተለያየ መንገድ ይጠረጋሉ፤ ፍዳቸዉንም በምድርም በሰማይም ይቀበላሉ። ሰይጣናት የእግዚአብሔርን ሕልዉና ከእኛ በላይ ያምናሉ። ምክንያቱም ከሰማያት ዉስጥ በግልጽ በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾ ጸጋቸዉን ገፎና አዋርዶ ወደዚህች ምድር እንደጣላቸዉ በሚገባ ያዉቃሉና። ነገር ግን ሕሊናቸዉን ያደነደኑ ስለሆነ እግዚአብሔር የማይወደዉን ተግባር ሆነ ሐሳብ ከመስራትና ከማሰብ አልተመለሱም፤ በዓመፃቸዉና

በክህደታቸዉ እንደ ጸኑ ነዉ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነት ለመቀበል ያልፈለግን ሰዎች እንደተሰናከልንብት ልናዉቅ ይገባል። እንዲሁም ልንወድቅበትና ዓመፃችንም ከከፋ ልንደመሰስበት(ልንጠረግበት) እንደምንችል ልናስተዉል ይገባል።

እዚህ ላይ እዉቀታቸዉና ሊቅነታቸዉ ጣዖት ለሆነባቸዉ ሰዎች የምለዉ አለ። ይኸዉም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በምድር በተመላለሰበትና በሚያስተምርበት ዘመን ብዙ የአይሁድ ምሁራን ጸሐፍት ፈሪሳዉያን ካህናት ነበሩ። ከእነርሱ ዉስጥ እዉቀቱን የማያመልክ ግን አንድ ምሁር ነዉ የተገኘዉ። ይህ የኦሪት ምሁር ኒቆዲሞስ የራሱን እዉቀት ከእግዚአብሔር እዉቀት ጋር ሲያነጻጽረዉ ነጥብ የማትሞላ መሆኑን በመረዳት ራሱን ሳያመጻድቅና ሳያስታብይ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሱ አስተሳሰብና እዉቀት ሳይገድብ ሙሉ እዉነትና እዉቀት ወደሚገኝበት እግዚአብሔር በመቅረብ በቅንነት፣ በእዉነት ፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በትህትና በትጋት ሕይወት በመመላለስ እንዲሁም የክርስቶስን ትምህርት፣ ተአምራት፣ ፈዉስ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ በመመርመር ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ያን ትምህርት እንደማይሰጥ እንዲሁም ተአምራትና ፈዉስ እንደማያደርግ በሚገባ አስተዉሎ የእግዚአብሔርን እዉነታ ሊቀበልና ሊያምን ችሏል። ከእርሱ እዉቀት በላይ የሆኑ ትምህርቶች ሲሰጠዉም ለጊዜዉ ማስተዋል ቢያቅተዉ እንኳ እግዚአብሔር የተለያዩ እዉቀቶችንና ምስጢራትን በተለያየ ጊዜ እንደ ትዉልዱ አቀባበል ሊገልጽ እንደሚችል አምኖ እግዚአብሔር፤ የሚያስተዉልበትን ጸጋ እንዲሰጠዉ ጠየቀ እንጂ « ከኔ እዉቀትና ከመምህራኖቼ አይሁድ ሊቃዉንትና መምህራን እዉቀት የተለየ እዉቀትና ምስጢራት ነዉ የሚገልጸዉ» በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ሆነ ምስጢራት «አልቀበለዉም» አላለም። ብዙዎቹ መምህራንና ሊቃዉንት ግን እዉቀታቸዉ ጣዖት ስለሆነባቸዉ በክርስቶስ ተሰናክለዉበታል። ወድቀዉበታል። በእግዚአብሔር ቁጣም ተደምስሰዉበታል። በመጨረሻም ለሲኦልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ ራሳቸዉን አሳልፈዉ ሰተዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትዉልዱ በሲኦልና በገሃነመ እሳት ዉስጥ ያለዉን ቅጣትና በገነትና በመንግሥተ ሰማያት ዉስጥ ያለዉን ሕይወት አስተዉሎ ምርጫዉን እንዲያስተካል በማሰብ በሉቃስ ወንጌል በምእራፍ፲፮ (16) ፥ከቁጥር ፲፱-፴፩ (19-31) ያለዉን እዉነት ገልጾልናል። «ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰዉ ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸዉ በደስታ ይኖር ነበረ። አልዓዛር የሚባል አንድ ድሀ በቁስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ ከባለ ጠጋዉም ማዕድ ከሚወድቀዉ ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር ዉሾች እንኳ መጥተዉ ቁስሎቹን ይልሱ ነበር። ድሀዉም ሞተ፥ መላእክት ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ባለ ጠጋዉ ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ -አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በዉኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን ልጄ ሆይ አንተ በሕይወት ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል አለ። እርሱም- እንኪያስ፥ አባት ሆይ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደዉ እለምንሃለሁ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸዉ አለ። አብርሃም ግን ሙሴና ነብያት አሉላቸዉ እነርሱን ይስሙ አለዉ። እርሱም - አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸዉ ንስሐ ይገባሉ አለ። ሙሴንና ነብያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሳ አያምኑም አለዉ።»

ከላይ የተገለጸዉ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያሚያሳየን በምድራዊ ሕይወት ዘመኑ ዓመፃ፥ ክህደት፥ ርኩሰት የፈጸመና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይመላለስ እንደ አሕዛብ « እንብላ፥ እንጠጣ፥ እንጨፍር፥ በድሎትና በቅንጦት እንኑር፥ ሌላዉ ቢራብ ቢቸገር ቢገፋ በደል ቢፈጸምበት የራሱ ጉዳይ» የሚል ራስ ወዳድና ስግብግብ ከሥጋ ሞት በኋላ የሚገጥመዉ እንደ ዓመፃዉ ደረጃ

የስቃይና የመከራ ሕይወት እንደሆነና በተቃራኒ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለሱና ሁሉን በትግዕስትና በጽናት የሚወጡና ስለ እዉነት መስክረዉ በእዉነት ኖረዉ ከዚህ ዓለም በሥጋ ሲለዩ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ሰላምና ፍቅር እንዲሁም ደስታና ቅድስና ብቻ ወደሚገኝበት ልዩ ቦታ እንደሚሄዱ ነዉ። ሌላዉ ደግሞ ትዉልዱ የእግዚአብሔርን መልእክተኞችንና አገልጋዮችን የማይቀበልና የማይሰማ ከሆነ ከሞቱትና በሲኦል ስቃይ እየተቀበሉ ካሉ ርኩሳን ነፍሳት (የተኮነኑ ሰዎች) ሆነ በገነት ዉስጥ ያሉ ቅዱሳን ነፍሳት (የጸደቁ ሰዎች) ተመልሰዉ ወደዚህች ምድር ቢመጡና በዛ ያለዉን ሕይወት ቢገልጹለት፣ ንስሐ እንዲገባ እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲመላለስ ቢነገረዉ እንኳ እንደማይቀበል ነዉ። ምክንያቱም ሕሊናዉን ያደነደነና ራሱን በአምላክ ቦታ ያስቀመጠ እንዲሁም «ከኔ እዉቀትና አስተሳሰብ ዉጭ የሆነዉን አልቀበልም እንደ ደምና ሥጋ ሐሳቤ ነዉ የምኖረዉ፥ የምመላለሰዉ» የሚል ሰዉና ዉስጡ ትዕቢት፥ ክፋትና ተንኮል እንዲሁም ዓመፃ የሞላበት ሰዉ እግዚአብሔር ተገልጾ ቢናገረዉ እንኳ አይቀበልም፤ አያምንም። በቅንና በእዉነተኛ ሕይወት የሚመላለስና ያመነበትን በቆራጥነትና በትጋት የሚወጣ ሰዉ ካለ ደግሞ በተሳሳተ መንገድ ዉስጥ እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ በድንቅ አጠራር ጠርቶት ለራሱ አገልግሎት ያሰልፈዋል።

ከዚህ ጋር ለማንሳት የምፈልገዉ ሌላዉ የእግዚአብሔር ቃል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በምድር ላይ በሚስተምርበት ወቅት በሉቃስ ወንጌል በምእራፍ፲፮(16) ከቁጥር ፲፫-፲፭(13-15) ላይ የተናገረዉን ነዉ። « ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለዉ ባሪያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛ ዉንም ይወዳል፥ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛዉንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።

ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳዉያን ይህን ሰምተዉ ያፌዙበት ነበር። እንዲህም አላቸዉ - ራሳችሁን በሰዉ ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያዉቃል፤በሰዉ ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነዉና።»

ከላይ የተገለጸዉ የክርስቶስ ቃል የሚገልጽልን በክፋት፥ በተንኮል፥ በዓመፃ፥ በክህደት፥ በቅናት፥በርኩሰት፥በምቀኝነት ሕይወት እየተመላለሰ በየትኛዉም አገልግሎት ዉስጥ ይሁን፥ በየትኛ ዉም እዉቀት ዉስጥ ይገኝ፥ በየተኛዉም የክብር ወንበር ላይ ይቀመጥ፥ በየትኛዉም የፈሊጥ አነጋገር ይናገር፥ በየትኛዉም ሰዉ ይደገፍ፥ በየትኛዉም ስልጣንና ኃይል ይገለጽ፥ ዉስጡን እግዚአብሔር በደንብ ያዉቀዋልና ይህ አይነቱ ሰዉ ታላቅ፥ ክቡር፥ ቅዱስ ሰዉ ሳይሆን «ርኩስ» ሰዉ ነዉ። በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሶ ስለ ዓመፃና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ተግባሩ ምስክርነት ካልሰጠ በስተቀር ከሥጋዉ በተለያየ መንገድ በሞት ሲለይ የሚጠራበት ስያሜ እንደ ርኩሳን መናፍስት «ርኩሳን ነፍሳት» ተብሎ ነዉ እንጂ ግለሰቦች ወይንም ቡድናት ወይንም ድርጅቶች ወይንም መንግሥት ባወጣለት ስም አይደለም የሚጠራዉ። መታሰቢያቸዉም ለዘለዓለም የሚደመሰስ(የሚጠፋ) ነዉ። ለዚህም ነዉ በእኛ በሰዎች ዘንድ ታላቅና የከበሩ የሚመስሉ ዓመፀኛ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ዓመፃ ደረጃቸዉ «ርኩሳን» የሚባሉት። በተቃራኒ ደግሞ በእኛ በሰዎች በኩል የተናቁ ቦታ ያልተሰጣቸዉ ወይንም በገፊኞችና በጨካኞች እንዲሁም በአስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች «ዓመፀኛና ከሃዲ» ተብለዉ የተለያየ ስም የተሰጣቸዉ ነብያት፥ መምህራን፥ ሐዋርያት፥ ሰማዕታት፥ ፃድቃን፥ «ቅዱሳን ነፍሳት» ተብለዉ በእግዚአብሔር የሚጠሩትና መታሰቢያቸዉም በእዉነተኛ በእግዚአብሔር ሰዎች ለዘለዓለም የሚታሰበዉ።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዉያን አባቶቼ፥ እናቶቼ፥ ወንድሞቼና እህቶቼ በቅርቡ ከሚመጣዉ ጥፋትና ጠረጋ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ይመጣል። በቅርቦቹ ሆነ በሩቆቹ ወላጆቻችን ሲነገር የነበረዉ «የሣልሳዊ ቴዎድሮስ» ዘመን አሁን ባለነዉ ትዉልዶች ጊዜ ዉስጥ እጅግ በቅርቡ ይመጣል። ኢትዮጵያ ለዓለም ብርሃን የምትሆንበት ዘመን፥ እግዚአብሔርም በአራቱም ማዕዘን የሚነግሥበትና የሚመለክበት ዘመን፥ እዉነት የምትነግሥበትና ሐሳት የምትደመሰስበት ዘመን፥

በኢትዮጵያ ላይ ዓመፃ ክህደት ርኩሰት ያነገሡ ዓመፀኞች መንግሥታት፥ ድርጅቶች፥ ቡድኖች፥ ግለሰቦች ከወንበራቸዉ በእግዚአብሔር ቁጣ ተቆራርጠዉና ተጠርገዉ ወደ ሲኦል የሚሄዱበት ዘመን፥ የሕዝብ ደም መጣጮችና አስመሳይ አገልጋዮች በምድራዊ ሕይወታቸዉ ጭምር ዋጋ የሚከፍሉበት ዘመን፥ ቅኖች የዋሃን እዉነተኞች ባጠቃላይ እግዚአብሔር መፍራት በዉስጣቸዉ ያለ ምዕመናንና ሕዝቦች በአራቱም ማዕዘን የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚፈጸምበትን መልካም ሥርዓት የሚመለከቱበት ዘመን፥ ባጠቃላይ በዓለም ላይ የተዘረጋዉ የዲያብሎስ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚዘረጋበት ዘመን፥ ክፋት ተንኮል መሰሪነት ትዕቢት ዓመፃ ክህደት ርኩሰት የሚጠፉበትና ፍቅር፥ ሰላም፥ አንድነት፥ ትህትና፥ መተሳሰብ፥ ጤና፥ ደስታ፥ እዉነተኛ ብልጽግና የሚሰፈንበት ዘመን፤ አዎን በቅርቡ ይመጣል። መሰረቱም በኢትዮጵያ ከዚያም በዓለም ይጣላል።

ታዲያ ለዚህ ዘመን ለመድረስና ይህን መልካም ዘመን ለማምጣት ከእኛ የሚጠበቀዉ እዉነተኛ ንስሐ መግባትና ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለፈጣሪያችን ማስረከብ፥ እዉነትን መቀበል፥ በጸሎትና በጾም እንዲሁም በእዉነተኛ አገልግሎትና ምስክርነት መጽናት ነዉ እንጂ፤ እንደ ዓለማዉያኑ፥ እንደ ትዕቢተኞቹና እብሪተኞቹ የዓለም መንግሥታት ጦር፥ ሰይፍ፥ ፈንጅ፥ ቦንብ፥ ኒዩክለር..ወዘተ እና የድጋፍ ሰልፍ፥ የተቃዉሞ ሰልፍ አያስፈልገንም። እግዚአብሔር ከንቱ ሥጋዊ መጠበብን የማይፈልግና የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ በፈለገዉ መልኩ ሊያከናዉን የሚችል ኃያልና ገናና አምላክ ነዉ። ስለዚህ አሁንም «አዲሲቷን ኢትዮጵያ እናስተዳድራለን» በማለት በዓመፃና በክህደት የጸኑት ወገኖቻችን የሆኑት ከሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀምሮ እስከ ቀበሌ ሹም ድረስ ያሉ ባለስልጣናት በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራቸዉ ከመቆረጣቸዉና ከመዋረዳቸዉ በፊት ራሳቸዉን በእዉነተኛ ንስሐ አዋርደዉ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ቢሰጡና ወንበሩንም እግዚአብሔር ለቀባቸዉና ለመረጣቸዉ ባለሚሎቹ በክብር ቢያስረክ የሚበጃቸዉ መሆኑን እየገለጽኩላቸዉ፤ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ በመከራና በዉርደት ይችን ዓለም ለመሰናበትና በነፍሳቸዉ ዋጋ ወደሚከፍሉበት ሁለተኛዉ ዓለም ለመጓዝ ከሆነ ፍላጎታቸዉ የሚመጣባቸዉን የከፋ የእግዚአብሔርን ቅጣት በጸጋ መቀበል ይጠበቅባቸዋል። የእነሱ ተባባሪ የሆናችሁና እጅና ጓንት ሆናችሁ ስትሰሩ የነበራችሁ ደግሞ ዛሬ ነገ ሳትሉ ምክንያቱም በዚህች ምድር በራሳችሁ ስልጣን አንድ ቀን የመቆየት አቅምና ፈቃድ ስለሌላችሁ በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሳችሁ የበደላችኋትን እናት ሀገራችሁንና ሕዝቦቿን በመካስ በቅንነት፥ በታማኝነት፥ በእዉነተኛነት አገልግሉ። በተቀረ እናንተም ከእግዚአብሔር ቁጣ እንደማታመልጡ ልታዉቁ ይገባችኋል።

ስለ ዓለም ሕዝብ መጥፋትና መደምሰስ የሚያሳስባችሁ ሰዎች ካላችሁ፤ የእግዚአብሔርን መልእክቶች ለመንግሥታቱ አቅርባችሁ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱና እጃቸዉንም ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ፥ ወንበራቸዉንም ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ንጉሠ ነገሥት (ሣልሳዊ ቴዎድሮስ) እና ለርእሰ ሊቃነ ካህናት እጨጌዉ አሳልፈዉ እንዲሰጡ ግለጹላቸዉ። « አይ እኛ እግዚአብሔርንም አናዉቅም መልእክቱንም አንቀበልም» ካሏችሁ ደግሞ እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበራችሁና ከመንግሥታችሁ ትቆረጣላችሁ፤ ኢትዮጵያም ሆነች ዓለም ለእግዚአብሔር እዉነተኛ እንደራሴዎች ለርእሰ ነገሥቱና ለእጨጌዉ ተላልፋ ትሰጣለች፤ እናተም ከነትዕቢታችሁና ዓመፃችሁ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ዓለም ወደ ሲኦል ትገባላችሁ» በሏቸዉ።

ከዚህ በፊት የተላለፈላችሁን የእግዚአብሔር መልእክቶች ከቁም ነገር ሳትቆጥሩት ያላነበባችሁት ካላችሁ በድጋሜ በእኔ በኩል የተላለፈዉን «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» እና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ የተላለፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት እንዲሁም በሚያዚያ ፳፻፬ (2004) ዓ.ም. በሶፍት ኮፒ አግኝቼ «በሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በኩል «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን መልእክት አንድ፥ ሁለት፥ ሦስት፥ አምስት» በሚል የተላለፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት ጊዜ ሰታችሁት በማስተዋልና በረጋ መንፈስ ዉስጥ ሆናችሁ አንብቡት።

ከዚህ በተጨማሪ በግልባጭ እንድታዉቁት የተደረገዉን የካቲት፳፯÷ ፳፻፬(27/06/2004) ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተጻፈ የአስተያየትና ምክር ደብዳቤ 3ገጽ  እንዲሁም ሰኔ ፲፭÷፳፻፬ (15/10/2004) ዓ.ም «መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ነን የተሰማራነዉ» በማለት በተለያየ ሕዋ ሰሌዳ (ድረ ገጽ) የተለያዩ መልእክቶች ለሚያስተላልፉ አባቶች÷ እናቶች÷ ወንድሞችና እህቶች የተጻፈላቸዉን የምክርና የማስጠንቀቂያ ድብዳቤ 14 ገጽ እንድታነቡት አያይዤላችኋለሁ።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዉያን አባቶቼ እናቶቼ እህቶቼና ወንድሞቼ፤ እኔ ታናሽ ወንድማችሁና ልጃችሁ ከዚህችዉ ከእናት አገራችሁ ኢትዮጵያ የተገኘዉ የቅዱሷ ኪዳን ኢትዮጵያ ዜጋ ነኝ። በእግዚአብሔር መልእክቶች ዉስጥ የቀረበዉ ከመምህራን ወይንም ከመጽሐፍት ተምሬ ጥናት አድርጌ ሳይሆን እግዚአብሔር በሕሊናዬ በግንባሬ ፊት ለፊት በአንጎሌ ዉስጥ  ባለችዉ ነፍሴ ብቻ ቃል በቃል በምትሰማዉ ድምጽ እግዚአብሔር የገለጸልኝን÷ የተናገረኝም÷ ያስተማረኝንና ያሳሰበኝን ብቻ ነዉ። እንደማንኛችሁም ፍጡር የሆንኩ ÷ ማንኛዉም ሰዉ የሚሰማዉ ስሜት የሚሰማኝ÷ የተለያየ ሕይወት ያሳለፍኩ÷ በኃጢአትም እየወደኩ እየተነሳሁ ያለሁ አንድ ተራ ሰዉ ነኝ። እንኳን ስለ ቀድሞዉ የሰማያት÷ የገነት÷ እንዲሁም የምድር ነገርና ስለ ወደፊት÷ ስለ ፍርድ ቀን ÷ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ስለሚኖረዉ ሕይወት ለመግለጽ ቀርቶ ከደቂቃ በኋላ ስለሚሆነዉ መግለጽ የማልችል ፍጡር ነኝ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሳይገባኝ ለዓለም መገለጽ የሚገባዉን አሳዉቆኝ በመልእክቱ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ  ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በሚልና «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ ሁሉን በግልጽ እንዳቀርብ አድርጓል።ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ ምስጢር ግልጽ ባለ ቋንቋ ቀርቧል።

ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ በሚመጣዉ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሚገባ ለመጠበቅና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ኢትዮጵያና ዓለም ተላልፋ የተሰጠችሁ ኢትዮጵያዊዉ ርእሰ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) አሁን እያለ ስላለሁ ክስተትና በቀጣይም ስለሚሆነዉ እንዲሁም የኢትዮጵያ ትንሳኤ በምን መልኩ እንደሚመጣ እግዚአብሔር የገለጸላቸዉንና የተናገራቸዉን ግልጽ ባለ ቋንቋ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል የአራት ጊዜ መልእክቶች ቀርቦላችኋል። ስለዚህ ለምድራዊ እዉቀት የዓመታት ጊዜ ሰታችሁ እንደምትማሩና እምደምታጠኑ ለሥጋችሁ ሆነ ለነፍሳችሁ የሚጠቅመዉን የእግዚአብሔርን መልእክቶች በተረጋጋ መንፈስ በተለይ ከእንቅልፋችሁ ከነቃችሁ በኋላ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ አንብቡት። ለማስተዋል ከተቸገራችሁ አንድ አምላክ አንድ ፈጣሪ ነዉና ያለዉ «አንተ እዉነተኛ አምላክና ፈጣሪ ማስተዋሉን ስጠኝ » በማለት ጠይቁት። እንኳን ተጠይቆ ሳይጠየቅም በቸርነቱና በፍቅሩ እዉቀትንና ማስተዋልን የሚሰጥ አምላክ ነዉ።

በተለይ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆናችሁ ወገኖቼ! «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በተጻፈዉ በሁለተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት በክፍል ሁለት በምእራፍ አንድ ላይ እናቶቻችሁ÷ እህቶቻችሁ÷ ባልተቤቶቻችሁ÷ ልጆቻችሁ ከእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ካሉ ምእመናን ይልቅ  ተመርጠዉ የእግዚአብሔር እዉነትና ምስጢር እንዲያዉቁ እግዚአብሔር አድርጓል። ይህም የሚያሳየዉ አስመሳይ አገልጋዮችንና አማኞችን ለማሳፈርና እግዚአብሔር የስም አማኞችንና አገልጋዮችን ሳይሆን የሚመርጠዉ እምነታቸዉን በምግባር የሚገልጹትን ሰዎች መሆኑን ነዉ። ፍርዱም እርሱን አዉቀዉ ባግባቡ የማያመልኩት ላይ እንደሚብስና ባለማወቅ በካዱት ላይ ደግሞ ፍርዱ እንደሚቀልላቸዉ ነዉ። በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ እናንተም ባለማወቅ ኢትዮጵያዊዉ ሃይማኖታችሁን ትታችሁ ከቅርብ ዘመን ወላጆቻችሁ በወረሳችሁት ሃይማኖት ዉስጥ ትገኛላችሁ። ወደ ጥንት ወላጆቻችሁ ቆጠራ ብትገቡ የእናንተ ሃይማኖት ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጀመሪያ በሕገ ልቦና(በኪዳነ ልቦና) በአዳምና ሔዋን እንዲሁም በአበዉ ይመለክ የነበረዉ÷ ከዚያም በሙሴ አማካይነት በተገለጸዉ በሕገ ኦሪት(በኪዳነ ኦሪት) ÷ በመጨረሻም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሲገለጽ በመሰረተዉ በሕገ ወንጌል (በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ) የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ነዉ እንጂ ከክርስቶስ መወለድ ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ  በፍጡሩ ሰዉ

የተመሰረተዉና በተለያየ መንገድ በዓለም የተሰፋፋዉ «እምነት» አይደለም:: ስለዚህ የእግዚአብሔርን መልእክት በሚገባ ካነበባችሁ «አሳህ» በማለት የምታመልኩት ማን እንደሆነ በሚገባ እንደምትረዱ ተስፋ አድርጋለሁ:: ታዲያ አሁንም ልትቀኑና በጽናት ልትቆሙለት የሚገባችሁ የሁሉ ፈጣሪ ለሆነዉ አምላክ እንጂ ግለሰቦች ለፈጠሩት መሆን የለበትም::

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዉያን! እግዚአብሔር የቀደሙትን ቅንና እዉነተኛ የሆኑትን ወላጆቻችንን አስቦና በአሁን ትዉልድ ዘመንም እርሱ ደስ በሚሰኝበት ሕይወት የሚመላለሱትን አስቦ ስለ ቅዱሱ ኪዳኑ ሲል የራሱን መንግሥት በቅድስት አገራችን ኢትዮጵያ በቀርቡ ይዘረጋልናል:: የዓመፃ ልጆችም በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰዉ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡና ሥጋዊዉንም ሆነ መንፈሳዊዉን ወንበር እርሱ ለመረጣቸዉና ለቀባቸዉ ካለቀቁ በቀር በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከምድር ያጸዳቸዋል፤ ከወንበራቸዉም በምድር ጭምር ፍዳቸዉን እንዲቀበሉ እያደረገና በእርሱ ጭብጥ ዉስጥ እንዲሁም ተራ መሆናቸዉን ዓለም እንዲያዉቅ እያደረገ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ይጠራቸዋል:: ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀዉ በቅንነት፥ በእዉነት፥ በመልካም ተግባርና በእዉነተኛ አገልግሎትና ምስክርነት መመላለስ ብቻ ነዉ::

ከሥጋዊ መሪ ከርእስ ነገሥት(ንጉሠ ነገሥት) በባዕዳን አጠራር ደግሞ ከፕሬዘዳንት(ከጠቅላይ ሚኒስትር) እስከ ቀበሌ ተጠሪ(ተሿሚ) ድረስ እንዲሁም ከመንፈሳዊ መሪ ከርእሰ ሊቃነ ካህናት(እጨጌ) በባዕዳን አጠራር ደግሞ ከርእሰ ሊቃና ጳጳሳት (ፓትርያርክ) ጀምሮ እስከ ገጠር አብያተ ክርስቲያን ተጠሪ(ኃላፊ) ጭምር እግዚአብሔር ያዘጋጀ ስለሆነ ከዲያብሎስ ሥርዓት መሪዎችና አራማጆች ጋር አንዳች አንድነትና ሕብረት መፍጠር የለብንም:: እነዚህ የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች በሕሊናቸዉ የነገሠዉ የዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነ ሌት ተቀን ለእርሱ ፈቃድ የተሰለፉ ናቸዉ እንጂ ለእግዚአብሔር እዉነት ቦታ የላቸዉም:: በእግዚአብሔር መልእክቶችና በኔ የተለያዩ ደብዳቤዎች ዉስጥ እንደተገለጸዉ የባለጊዜነት ዘመናቸዉ በአራት ነጥብ የተደመደመበትና የሚቀራቸዉም የዘሩትን የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የጥላቻና የበቀል ፣ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፣ የክፋትና የተንኮል ፍሬያቸዉም እንደ ኮሶ የሚመር ቢሆንም ጠጥተዉ ማለፍ ብቻ ነዉ:: እግዚአብሔር በዚህ ምድር ዉስጥ ጭምር ፍርዱ ምን ያህል ፍትሐዊና እጅግ ጥብቅ መሆኑን ያሳያቸዋል:: ስለዚህ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀዉ ራሳችንን ለእዉነተኛ ንስሐና እምነት ማብቃትና ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመራበት የኢትዮጵያዉያን ሥርዓትና የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንን መጠበቅ ነዉ:: በተረፈ ታናሽ ልጃችሁና ወንድማችሁ ስለሆንኩ በጸሎታችሁ አስቡኝ ይላል ተክለኪዳን::

<u>ማስታወሻ</u>

የእያንዳንዳችሁን አድራሻ ያገኘሁት ከማንም ሳይሆን ከመጻሕፍት፥ ከመጽሔት፥ ከጋዜጣ፥ ከማስታወቂያ ሰሌዳ፥ ከፌስ ቡክ፥ ከድረ ገጽ ከመሳሰለት መሆኑን ለማሳወቅ እወዳለሁ

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም
እግዚአብሔር ቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያን ይባርክ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ይጠብቅ
ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ

ነሐሴ፩/፳፻፬ ዓ.ም.

ግልባጭ

ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ካህኑ እጨጌ
ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ርእሰ ነገሥት
ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን የእግዚአብሔር መልእክት ለተላከላችሁ በሙሉ

ኢትዮጵያ

በአንድነትና በሦስትነት ለሚመለከዉ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ